Isenberg
19
7/6
ah
7.11.'02

From the Library of
Professor William Henry Green
Bequeathed by him to
the Library of
Princeton Theological Seminary

PJ9272
.I78

W. Henry Green
Princeton N.J.

April 21. 1854

Digitized by the Internet Archive
in 2019 with funding from
Princeton Theological Seminary Library

https://archive.org/details/regnideiinterris00isen

REGNI DEI IN TERRIS

HISTORIA

AMHARICÈ.

DUABUS PARTIBUS.

I.

ILLA QUÆ POPULO DEI ACCIDERUNT, INDE ADAMI LAPSU AD HIEROSOLYMITARUM DELETIONEM, BREVITER ENARRAT.

II.

ECCLESIÆ CHRISTIANÆ HISTORIAM, À S. JOANNIS MORTE AD TEMPORA NOSTRA, SYSTEMATICE EXPONIT.

AUCTORE

CAROLO GULIELMO ISENBERG,

EVANGELII MISSIONARIO IN AFRICAM ORIENTALEM.

LONDINI:

IMPENSIS ECCLESIÆ ANGLICÆ SOCIETATIS AD RELIGIONEM CHRISTIANAM IN AFRICA ET ORIENTE EXPANDENDAM INSTITUTÆ

IMPRESSIT RICARDUS WATTS.

MDCCCXLI.

በአብ ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ስም ፡ አንድ ፡
አምላክ ፡፡ አሜን ፡፡

የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡
ታሪክ ፡

ከዓለም ፡ ፍጥረት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘመናችን ፡ ድረስ ፡፡

ተጻፈች ፡

በቻርልስ ፡ ዊልየም ፡ ኢዘንበርግ ፡
በወንጌል ፡ መለክተኛ ፡
ለሐበሻ ፡፡

በሎንደን ፡ ባለች ፡ በእንግልጣር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
በሚስዮን ፡ ጉባኤ ፡ ፈቃድ ፡ ታተመች ፡ በሪቸርድ ፡
ወትስ ፡ ማኅተምያ ፡ በክርስቶስ ፡
ልደት ፡ አመት ፡ ፲፰፻፵፩፡፡

ነገርን ፡ ሁሉን ፡ ምርምሩ ፡ መልካሙንም ፡ ጠብቁ ፡፡

፩፡ ተሳሎንቄ ፡ ፭፡ ፳፩፡፡

አስቀድሞ ፡ የተጻፈ ፡ እኛን ፡ ለማስተማር ፡ ተጽፎዋል ፡፡

ሮሜ ፡ ፲፭፡ ፬፡፡

መቅድም ።

ለሐበሻ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ።

ጸጋ ፡ ይሁንላችሁ ፡ ሰላምም ፡ ካባታችን ፡ ከእግዚአ
ብሔር ፡ ከጌታም ፡ ከየሱስ ፡ ክርስቶስ ።

በክርስቶስ ፡ የሱስ ፡ የተወደጃችሁ ፡ ወንድሞቻችን ፡ ሆይ ።

የተዋረደ ፡ የየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ባሮች ፡ የወንጌል ፡ መለ
ክተኞች ፡ ከእንግሊዝ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጉባኤ ፡ ተልከው ፡
ወደ ፡ አገራችሁ ፡ ደረሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ በምህረቱ ፡ የሰጣ
ቸውን ፡ የሰማይን ፡ መዝገብ ፡ ከላንተ ፡ ጋራ ፡ ይከፋፈሉ ፡
ዘንድ ፡ የተባረከውንም ፡ የጌታችንን ፡ ስም ፡ በደህንነታች
ሁ ፡ ያመሰግኑት ፡ ዘንድ ። ይህም ፡ የሰማይ ፡ መዝገብ ፡ ወር
ቅና ፡ ብር ፡ አይደለም ፡ ከወርቅና ፡ ከብር ፡ ካለም ፡ ከብትም ፡
ሁሉ ፡ የተሻለ ፡ ነገር ፡ ነው ፡ እንጂ ። የሥጋ ፡ መድኃኒትም ፡
አይደለም ፡ ነፍሱንና ፡ ሥጋውን ፡ ለዘላለም ፡ የሚፈውስ ፡
አብነት ፡ እንጂ ። የዓለምም ፡ ብልሃት ፡ አይደለም ፡ ሰው
ን ፡ ለዚህ ፡ ዓለምና ፡ ለሚመጣው ፡ ዓለም ፡ ጠቢብ ፡ የም
ታደርገው ፡ ብልሃት ፡ እንጂ ። የሰማይም ፡ መዝገብ ፡ እር
ሱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ነው ፡ ኃጢአተኞችን ፡ በእግዚ
አብሔር ፡ መንገድ ፡ የሚያስተምር ፡ ጽድቅንም ፡ ሸተው ፡
የሚርቡትንና ፡ የሚጸሙትን ፡ በየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጽድ
ቅ ፡ የሚያጸግብ ። የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ የቤተ ፡ ክርስቲ
ያን ፡ መሠረት ፡ ነው ፡ ከሁሉም ፡ የሚበልጥ ፡ ባለጠግነት
ዋና ፡ መዝገብዋ ። እርሱንም ፡ ይዘው ፡ የወንጌል ፡ መለክ
ተኞች ፡ መጡ ፡ ለሚወዱትም ፡ ሁሉ ፡ ይሰጡታል ፡ ያስተም
ሩበትማል ። በርሱም ፡ ነው ፡ አንድነትን ፡ የምናደርግበት ፡
ጌታችንን ፡ ከሚወዱ ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ። እርሱ ፡ እውነትና ፡ ደህ
ንነት ፡ ነውና ፡ አያልፍምም ፡ አይለወጥምም ። የሰው ፡ ቃ
ል ፡ ሁሉ ፡ እስትንፋስ ፡ ነውና ፡ ይጠፋል ፡ በርሱም ፡ የተመ
ሠረተ ፡ የሰው ፡ ልማድና ፡ የሰው ፡ ሥርዓት ፡ ትቢያ ፡ ነው
ና ፡ ገለባም ፡ የፍርድ ፡ እሳት ፡ ሲቃጠል ፡ ጊዜ ፡ ይነደልና ፡
አመድ ፡ ይሆናል ። ሰማይና ፡ ምድር ፡ እንኳ ፡ ያልፋሉ ፡ ቃ

ሌ ፡ ግን ፡ አያልፍም ፡ ይላል ፡ የዘላለም ፡ ቃል ፡ የሱስ ፡ ክ
ርስቶስ ፡፡

ይህች ፡ መጽሐፍ ፡ ከዚህ ፡ የሥንሰጣችሁ ፡ የእግዚአብ
ሔርን ፡ መንግሥት ፡ ታሪክ ፡ ትናገራለች ፡ በሁለት ፡ ክፍል
ም ፡ ተከፈለች ፡፡ መጀመርያ ፡ ክፍልም ፡ በእግዚአብሔር ፡
ቃል ፡ ከተገኘ ፡ ታሪክ ፡ ሁለተኛ ፡ ክፍልም ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲ
ያን ፡ ታሪክ ፡ ታላቅ ፡ ነገርን ፡ ይናገራል ፡፡ የእግዚአብሔርን ፡
ስራ ፡ በወገኑ ፡ ዘንድ ፡ ለማምሰገን ፡ የሰውንም ፡ በጎና ፡ ክ
ፉ ፡ ስራ ፡ ለትምህርታችን ፡ ለመግለጽ ፡ ብለን ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ አረፍትና ፡ ኃይል ፡ በሰጠነ ፡ መጠን ፡ ጻፍነው ፡፡ በቀደ
ም ፡ የተጻፈም ፡ እኛን ፡ ለማስተማር ፡ ተጻፈ ፡ ስለዚህም ፡ የ
ሆነውን ፡ ነገር ፡ በዚች ፡ መጽሐፍ ፡ እናስታውቃችኋለን ፡ አላ
ንት ፡ መርምራችሁ ፡ የሚጠቅማችሁትን ፡ ነገር ፡ ትማሩበ
ት ፡ ዘንድ ፡፡ ይህም ፡ ነው ፡ መስጠታችን ፡ ከእግዚአብሔር ፡
ቃል ፡ ጋራ ፡፡ በፍቅር ፡ ተሰጠ ፡ በፍቅርም ፡ ተቀበሉት ፡ የሱ
ስ ፡ ክርስቶስንም ፡ አመስግኑበት ፡፡ ጳውሎስም ፡ እንደ ፡ ጸ
ለየ ፡ እኛም ፡ ለላንት ፡ እንጸልያለን ፡ እንደዪህ ፡ ብለን ፡

“ ስለዚህም ፡ ጕልበታችነን ፡ እንምበረከካለን ፡ ወደ ፡ ጌ
“ ታችን ፡ ወደ ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አባት ፡ በርሱ ፡ ወደ
“ ምትጸራ ፡ በሰማይና ፡ በምድር ፡ ያለች ፡ አባትነት ፡ ሁ
“ ሉ ፡፡ ይሰጣችሁ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ክብሩ ፡ ባለጠግነት ፡
“ በመንፈሱ ፡ ትበርታችሁ ፡ ዘንድ ፡ በውሥጡ ፡ ሰውነ
“ ታችሁ ፡፡ ክርስቶስ ፡ እንዲያድር ፡ በልባችሁ ፡ በሃይ
“ ማኖች ፡፡ ሥርን ፡ ይዛችሁ ፡ ተመሠርታችሁም ፡ በፍ
“ ቅር ፡፡ ከቅዲሳን ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ፡ ትችሉ ፡ ዘንድ ፡ ለመድ
“ ረስ ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ ርዝመት ፡ ስፋትም ፡ ጥልቅም ፡
“ ቁመትም ፡፡ ከውቀትም ፡ ሁሉ ፡ የምትበልጠውን ፡ የ
“ ክርስቶስን ፡ ፍቅር ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔ
“ ር ፡ ምላት ፡ ሁሉ ፡ እስክትመላባችሁ ፡ ድረስ ፡፡ ለርሱ
“ ም ፡ ከምንለምነው ፡ ከምናስታውለው ፡ ሁሉ ፡ እጅ
“ ግ ፡ አብልጦ ፡ ለማድረግ ፡ ለሚችል ፡ በውሥጣችን ፡
“ እንደምትሰራ ፡ እንደ ፡ ኃይሉ ፡፡ ለርሱ ፡ ምስጋና ፡ ይሁ
“ ን ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በክርስቶስ ፡ የሱስ ፡ እስከ ፡
“ ልጅ ፡ ልጅ ፡ ሁሉ ፡ ድረስ ፡ ለዘላለም ፡፡ አሜን ፡፡”

የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡

ታሪክ ፡

መጀመርያ ፡ ክፍል ፡፡

የእግዚአብሔር ፡ ወገን ፡ ታሪክ ፡

በብሉይ ፡ ኪዳን ፡፡

ከአደም ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ የሩሳሌም ፡ መፍረስ ፡

ድረስ ፡፡

መዝሙር ፡ ፸፰፡ ፪፡—፯።

አፌን ፡ በምሳሌ ፡ እከፍታለሁ ።
ቀድሞም ፡ የሆነውን ፡ እናገራለሁ ፡
የሰማነውን ፡ ያወቅነውንም ፡ ሁሉ ፡
አባቶቻችንም ፡ የነገሩነውን ፡
ከልጆቻቸው ፡ እንደንሰውረው ፡
ለሌላ ፡ ትውልድ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ምስጋና ፡ እንነገ
ር ፡ ዘንድ ፡ እንጂ ፡
ኃይሉንም ፡ ያደረገውንም ፡ ተአምራት ።
ምስክርን ፡ ለያዕቆብ ፡ አቆመ ፡
ለእሥራኤልም ፡ ሕጉን ፡ ሰራ ፡
ላባቶቻችን ፡ ያዘዘውን ፡ ለልጆቻቸው ፡ ይነግሩት ፡ ዘ
ንድ ፡
ሌላ ፡ ትውልድም ፡ ታውቅ ፡ ዘንድ ፡ የሚወለዱ ፡ ልጆ
ቻቸው ፡
ተነሥተውም ፡ ለልጆቻው ፡ ይነገሩ ፡ ዘንድ ።
መታመናቸውን ፡ በእግዚአብሔር ፡ እንዲያደርጉ ፡
የእግዚአብሔርንም ፡ ስራ ፡ እንዳይረሱ ፡
ትእዛዙንም ፡ እንዲጠብቁ ፡
እንደባቶቻቸውም ፡ እንዳይሆኑ ።

በአብና ፡ በልጅ ፡ በመንፈስ ፡ ቀዱስም ፡ ስም ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡፡ አሜን ፡፡

እግዚአብሔር ፡ ሰውን ፡ በፈጠረ ፡ ጊዜ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መልክ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ምሳሌ ፡ ፈጠረው ፡፡ ማለቱ ፡ በውነተኛ ፡ ጽድቅና ፡ በቅድስና ፡፡ ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፡ ምዕራፍ ፡ ፩፡ ቍጥር ፡ ፳፯፡ ፳፰፡፡ ኤፌሶን ፡ ፬፡ ፳፫፡ ፳፬፡፡ እግዚአብሔርም ፡ ለሰው ፡ መግዛት ፡ ሰጠ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ተስፋም ፡ ሰጠው ፡ በዚህ ፡ ምድር ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፈቃድ ፡ ቢፈጽም ፡ በደህንነት ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ለዘላለም ፡ ብሎ ፡ ትእዛዙን ፡ ግን ፡ ቢያፈርሰ ፡ ሞት ፡ ይሞት ፡ ዘንድ ፡ ለዘላለም ፡፡ እውነተኛ ፡ ደህንነታችንና ፡ ሕይወታችን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ አንድነታችን ፡ ነውና ፡ ሌላ ፡ የለም ፡፡ ከእግዚአብሔር ፡ መለየት ፡ ግን ፡ ጥፋታችን ፡ ነው ፡፡ ደሮ ፡ ግን ፡ አባታችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ አንድነት ፡ አልኖረም ፡፡ በሰይጣን ፡ ተንኰልና ፡ ስሕተት ፡ የእግዚአበሔርን ፡ ፈቃድ ፡ አፈረሰ ፡ በጥፋቱም ፡ ፍርድ ፡ በታች ፡ ወደቀ ፡፡ እርሱ ፡ ግን ፡ የሰው ፡ ሁሉ ፡ አባት ፡ ሁንዋልና ፡ ልጆቹም ፡ ሁሉ ፡ በሥር ፡ በርሱ ፡ ኑረዋልና ፡ እርሱ ፡ ኀጢአት ፡ ሲያድርግ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በርሱ ፡ በኀጢአት ፡ ወደቀ ፡፡ እንደሁም ፡ የርሱ ፡ ኀጢአት ፡ የኛ ፡ የሁላችን ፡ ኀጢአት ፡ ሁና ፡ ይቈጠራል ፡ በኀጢአቱም ፡ መክንያት ፡ የሥጋ ፡ ሞት ፡ የዘላለምም ፡ ጥፋት ፡ ገብቶብናል ፡፡ እንደህ ፡ ይላልና ፡ እግዚአብሔር ፡ በቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ አፍ ፡ በመልእክቱ ፡ ወደ ፡ ሮሜ ፡ ሰዎች ፡ በ፭፡ ምዕራፍ ፡ በ፲፪፡ ቍጥር ፡፡ ባንድ ፡ ሰው ፡ ኀጢአት ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ እንደ ፡ ገባች ፡ በኀጢአትም ፡ ሞት ፡ ገባ ፡፡ እንደሁም ፡ ሞት ፡ አለፈ ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡፡ ሁሉ ፡ በድለዋልና ፡፡ እግዚአብሔር ፡ በቅን ፡ ይፈርደልና ፡፡ እርሱም ፡ ጨለማ ፡ የሌለበት ፡ ብርሃን ፡ ነው ፡፡ ኀጢአት ፡ ግን ፡ ጨለማ ፡ ነው ፡፡ ለኀጢአተኛ ፡ ሰውም ፡ አንድነት ፡ የለውም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ከርሱ ፡ ተለየ ፡ እንጂ ፡፡ እግዚአብሔር ፡ የሚወደውን ፡ ነገር ፡ ሰው ፡ ይጸላል ፡፡ እግዚአብሔርም ፡

የሚጸላውን ፡ ነገር ፡ ሰው ፡ ይወደል ፡ ይሻውማል ፡ ያድርገ
ውማል ። ደሮ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ የኃጢአተኛውን ፡ ጥፋ
ት ፡ አይወድም ። እንዴህ ፡ ይላልና ፡ በሕዝቅኤል ፡ አፎ ፡ በት
ንቢቱ ፡ መጽሐፎ ፡ ምዕራፎ ፡ ፴፫ ፡ ቍጥር ፡ ፲፩ ። እንዴህ ፡ ሲ
ል ። እንዴህ ፡ ንገራቸው ። በሕይወቴ ፡ እምላለሁ ፡ ይላል ፡
እግዚአብሔር ። እኔ ፡ የኃጢአተኛውን ፡ ሞት ፡ አልወድ
ም ፡ ኃጥእ ፡ ከክፉ ፡ ባሕርዩ ፡ ሊመለስ ፡ እንጅ ፡ ሊድን
ም ። ስለዚህ ፡ ሁሉን ፡ የሚችል ፡ እግዚአብሔር ፡ በቅድስ
ና ፡ በጽድቅም ፡ የሚኖርም ፡ ዙፋኑም ፡ ከሰማያት ፡ ሰማ
ይ ፡ በላይ ፡ ያለው ፡ ስለ ፡ መድኃኒታችን ፡ ተማከረ ፡ ዓ
ለም ፡ ሳይፈጠር ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡
የሚሆነውን ፡ ቃሉን ፡ እርሱም ፡ የዘላለም ፡ አባት ፡
አንደኛውን ፡ ልጁን ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ መስደድ ፡ ፈቀደ ። ሰ
ው ፡ ሁሉ ፡ በኃጢአት ፡ ኑርዋልና ፡ ኢያንደንዱ ፡ ለራሱ ፡
መድኃኒት ፡ ፈለገ ፡ እርሱ ፡ በርሳቸውም ፡ ማደደን ፡ ሳናቸ
ው ። እንዴት ፡ ይችላል ፡ ወንድም ፡ ወንድሙን ፡ ማደን ፡
ከእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ። መልአክም ፡ አልቻለውም ፡ ያ
ድነን ፡ ዘንድ ። ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ኢየራሱ ፡ ለፈጣሪ ፡ መታ
ዘዝ ፡ ተግብትዋልና ፡ በሌላ ፡ ፍጥረትም ፡ ፈንታ ፡ መታዘዝ ፡
አይችለውም ። የእግዚአብሔርንም ፡ ፍርድ ፡ መታገሥ ፡
ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ አይችልም ፡ ለዘላለም ፡ ኑርዋልና ። ሰው
ም ፡ ያልፈጸመውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ በሰው ፡
ፈንታ ፡ መፎጸም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ተቻለው ። እር
ሱ ፡ ከሕጉ ፡ በታች ፡ አይደለምና ፡ በላይው ፡ እንጅ ። መድ
ኃኒታችነን ፡ ግን ፡ ያበጅልን ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ መኻከለኛ ፡
ተፈለገ ፡ አምላክና ፡ ሰው ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ የሆነ ፡ በሰው ፡
ሁሉ ፡ ፈንታ ፡ የኃጢአትን ፡ ደመወዜ ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ እ
ግዚአብሔርም ፡ የሰጠውን ፡ ሕግ ፡ በጣም ፡ ይፈጽም ፡ ዘ
ንድ ፡ እንዴሁም ፡ ኃጢአታችነን ፡ ያስቀርልን ፡ ዘንድ ።
በእግዚአብሔርም ፡ ፊት ፡ ያጸድቀን ፡ ዘንድ ። መንፈሱን
ም ፡ ይሰድልን ፡ ዘንድ ፡ በልባችን ፡ ኑሮ ፡ ልባችነን ፡ አካሔ
ዳችነንም ፡ የሚቀድስ ፡ እንዴሁም ፡ ከኃጢአት ፡ ወደ ፡ ጽ
ድቅ ፡ ወደ ፡ ቅድስናም ፡ ከሞትም ፡ ወደ ፡ ሕይወት ፡ ከሰይ

ጣን ፡ ኃይልም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከገሃናምም ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ የሚወስድን ፡፡

ምንድር ፡ አደረገ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህችን ፡ ፈቃዱን ፡ ለመፈጸም ፡፡ ወላጆቻችን ፡ በኃጢአት ፡ ከወደቁ ፡ በኋላ ፡ አዲስ ፡ ኪዳን ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ አቆመ ፡፡ ሰይጣን ፡ በርሱ ፡ የነበረበቱን ፡ እባብን ፡ ረገመ ፡፡ ይህም ፡ መርገም ፡ ለሰው ፡ በረከት ፡ ሆነ ፡፡ ተስፋ ፡ ሰጥትዋቸዋልና ፡ እናታችንን ፡ ሄዋን ፡ ከኃጢአት ፡ ሊመልስ ፡ ከሰው ፡ ወገንም ፡ ክፍልን ፡ ለርሱ ፡ ሊመርጽ ፡ ከሰውም ፡ መካከል ፡ መድኃኒት ፡ ሊያስነሣ ፡ የሰይጣን ፡ ኃይል ፡ የሚያፈርስ ፡ ከርሱ ፡ መከራ ፡ ተቀብሎ ፡፡ ይህች ፡ ተስፋ ፡ ትገኛለች ፡ በኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፡ ም ፡ ፫፤ ቍ ፡ ፲፭፤ ሄዋም ፡ ወለደች ፡ ይህችም ፡ ተስፋ ፡ የተፈጸመች ፡ መሰላት ፡፡ ወንድ ፡ ልጅ ፡ አገኘሁ ፡ እርሱም ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ አለች ፡፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሳተች ፡፡ የተወለደ ፡ ልጅዋ ፡ ቃይል ፡ የሰይጣን ፡ ወገን ፡ ሁንዋልና ፡ በርሱ ፡ የኃጢአት ፡ ኃይል ፡ የበዛበት ፡ በሰው ፡ መካከል ፡፡ በቃይል ፡ ወንድም ፡ በሃቤል ፡ ያች ፡ ተስፋ ፡ ተከፍላ ፡ ተፈጸመች ፡፡ ሃቤል ፡ በሃይማኖት ፡ ተጸድቅዋልና ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ደስ ፡ ያሰየውን ፡ ምሥዋዕት ፡ አቅርብዋልና ፡፡ ስለዚህም ፡ ቃይል ፡ ተቈጥቶ ፡ ገደለው ፡፡ ያች ፡ ጸላትነት ፡ በሰው ፡ ሁለት ፡ ወገን ፡ መካከል ፡ የሴት ፡ ዘርና ፡ የባብ ፡ ዘር ፡ በተባሉ ፡ መካከል ፡ ያለች ፡ በዚህ ፡ ጀምሬ ፡ ተገለጠች ፡፡ ሰይጣንም ፡ አሁን ፡ ያሸነፈ ፡ መሰለው ፡ ቃይል ፡ ነፍሱን ፡ ለርሱ ፡ ለማገልገል ፡ ሲሰጥ ፡ ሃቤልንም ፡ ሲገድል ፡፡ ደር ፡ እግዚአብሔር ፡ ተስፋውን ፡ ጠብቆት ፡ ለአደም ፡ ሌላውን ፡ ልጅ ፡ ሰጠ ፡ በሃቤል ፡ ፈንታ ፡፡ እርሱም ፡ ሴት ፡ ተባለ ፡፡ በርሱ ፡ ወገንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ የፈሩ ፡ ሰዎች ፡ ተገኙበት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ የተባሉ ፡ የቃይል ፡ ወገን ፡ በኃጢአት ፡ ደኖሩ ፡ የነበሩ ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ ሲባሉ ፡፡ ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፡ ም ፡ ፯፤

የቃይል ፡ ልጆች ፡ ያለምን ፡ ብልሃት ፡ ብቻ ፡ መርጸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ረሱ ፡፡ በሴት ፡ ወገን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ተጸሬ ፡፡ ሄኖክም ፡ በሰባተኛ ፡ ትውልድ ፡ የተወለደ ፡ ከ

እግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ተመላለሰ ፡ በሃይማኖት ፡፡ ስለ ፡ ሃይ
ማኖቱም ፡ እግዚአብሔር ፡ ሞትን ፡ ሳያይ ፡ አስፈለሰው ፡፡
የሰው ፡ ኃጢአት ፡ ግን ፡ በዛ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡፡ የሰው ፡ ል
ጆች ፡ የተባሉ ፡ የቃይል ፡ ዘመድ ፡ ዐመፃቸውን ፡ በእግዚአ
ብሔር ፡ ላይ ፡ አበዙ ፡ ከሴት ፡ ወገንም ፡ የእግዚአብሔር ፡
ልጆች ፡ ከተባሉ ፡ ጋራ ፡ ተደባለቁ ፡ በሴት ፡ ወገንም ፡ የኃጢ
አት ፡ ኃይል ፡ በዛ ፡ ባለማመን ፡ ባለመታዘዝም ፡፡ የእግዚ
አብሔርም ፡ ፍርሃት ፡ እውነተኛ ፡ ሃይማኖትም ፡ ከፍቅር ፡
ጋራ ፡ አለቁ ፡፡ ማሰባቸውም ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ ብቻ ፡ ሁ
ኖ ፡ መንግሥተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ረሱ ፡፡ ያባቶች ፡ አለቆ
ች ፡ ሁሉ ፡ ከሴት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ኖህ ፡ ድረስ ፡ ሰበኩ ፡ አ
ስተማሩም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ስም ፡፡ ደር ፡ ሰው ፡ አልሰ
ማም ፡፡ ከኃጢአቱም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አልተመለሰ
ም ፡፡ እግዚአብሔርም ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ ለሕዝብም ፡ ሁሉ ፡
ጊዜውን ፡ ቍረጠ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ለመስማት ፡
ለመታዘዝም ፡ ንስሓም ፡ ለመግባት ፡ ለማመንም ፡ ለመዳ
ንም ፡፡ ይህም ፡ ጊዜ ፡ በከንቱ ፡ ቢያልፍ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰ
ውን ፡ በቅን ፡ ፍርድ ፡ ለጥፋት ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጣል ፡፡ ስለዚ
ህ ፡ ይላል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሰውን ፡ ሁሉን ፡ የእግዚአብ
ሔርን ፡ ቃል ፡ የሚሰማውን ፡፡ ዛሬ ፡ አላንተ ፡ ድምጹን ፡ ስ
ትሰሙ ፡ ልባችሁን ፡ አታጽኑ ፡፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ ዕብራው
ያን ፡ ፫፡ ፯፡፡ እግዚአብሔር ፡ የሰው ፡ ክፋት ፡ እንደ ፡ በዛ ፡
ባየ ፡ ጊዜ ፡ አዘነ ፡ በልቡ ፡፡ እርሱ ፡ የኃጥኡን ፡ ሞት ፡ አይወ
ድምና ፡፡ ስለዚህም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ፈተናቸው ፡ ጊ
ዜም ፡ አደረገላቸው ፡ ፻፳፡ ዓመት ፡፡ እንደሁም ፡ ታገሠ ፡ ም
ናልባት ፡ ሰው ፡ ባይመለስ ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡፡ ደር ፡ ሰው ፡
አልሰማም ፡፡ ምድር ፡ ሁሉ ፡ ረከሰች ፡ በሰው ፡ ኃጢአት ፡፡
ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ የድምሳሴ ፡ ውኃ ፡ አስመጣ ፡ በ
ምድር ፡ ላይ ፡ ሥጋ ፡ የለበሰ ፡ ሁሉ ፡ የጠፋበት ፡ ከሰው ፡ ጀ
ምር ፡ እስከ ፡ እንስሳ ፡ ድረስ ፡ እስከ ፡ ሰማይም ፡ ዎፍ ፡ ድ
ረስ ፡ በምድር ፡ ላይም ፡ እስከ ፡ ሚንቀሳቀስ ፡ ሁሉ ፡ ድረ
ስ ፡፡ ደር ፡ ኖህ ፡ ባለምዋልነት ፡ አገኘ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘ
ንድ ፡ በሃይማኖት ፡፡ ለኖህ ፡ አዘነ ፡ እግዚአብሔር ፡ በኖህ ፡

መክንያትም ፡ ለዘመዷ ፡ አዘነ ፡ ስምንት ፡ ነፍስ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ። በኖህ ፡ መክንያትም ፡ ለሌላ ፡ ፍጥረት ፡ አዘነ ፡ የሰው ፡ ወገን ፡ ሁሉ ፡ እንዲደጠፋ ፡ ስለ ፡ ሰውም ፡ የተፈጠረች ፡ ምድር ፡ በርስዋም ፡ ከሚያሸከረክር ፡ ጋራ ፡ ሰይጣንም ፡ እንዲያሸንፍ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃልም ፡ ከንቱ ፡ እንዲይሆን ። ስለዚህም ፡ ኖህን ፡ አዘዘ ፡ መርከብ ፡ ሊሰራ ፡ ቁመቱን ፡ ወርደንም ፡ ርዝመቱንም ፡ ያመለከተለት ። ኖህ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደዘዘው ፡ አደረገ ፡ መርከብንም ፡ ሰራ ፡ ወደርሱም ፡ ገባ ፡ ከ፯ ወገኖቹ ፡ ጋራ ፡ ከቀረውም ፡ ፍጥረት ፡ ጋራ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደዘዘው ።

መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ይላል ። ኖህ ፡ በሃይማኖት ፡ ወደ ፡ መርከብ ፡ ገባ ። መልእክት ፡ ወደ ፡ ዕብራውያን ፡ ምዕራፍ ፡ ፲፩ ቍጥር ፡ ፯። በኦሪትም ፡ ይላል ። ኖህ ፡ ባለሞዋልነት ፡ አገኘ ፡ ከእግዚአብሔር ። ደግሞ ። ኖህ ፡ አደረገ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደዘዘው ፡ ይላል ። ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፡ ፯ ፭። በዚህ ፡ ይታያል ፡ ሃይማኖትና ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነገር ፡ መታዘዝ ፡ አንድ ፡ እንዲሆን ።

የጥፋት ፡ ውኃ ፡ አለፈ ። ምድርም ፡ በርሱ ፡ ታደሰች ። እግዚአብሔርም ፡ ኪዳኑን ፡ አቆመ ፡ ከኖህ ፡ ጋራ ፡ ከሰው ፡ ወገንም ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ፡ ከምድርም ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ምድርን ፡ እንዲያጠፋ ፡ በውኃ ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ኃጢአት ። ለዚችም ፡ ኪዳን ፡ ምልክት ፡ አደረገ ፡ ቀስቱን ፡ አኑሮ ፡ በደመና ።

ኖህም ፡ ላደስ ፡ ትውልድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ማመን ፡ አስተማረ ። ሴምም ፡ ያፌትም ፡ ልጆቹ ፡ አመኑ ። እግዚአብሔርም ፡ የጸጋውን ፡ የመድኃኒቱንም ፡ ተስፋ ፡ አስደረገ ፡ ለልጆቻቸው ። ካም ፡ ግን ፡ ከከናዐን ፡ ከልጁ ፡ ጋራ ፡ አላመነም ፡ የኃጢአት ፡ ባሮች ፡ ነበሩ ፡ እንጅ ። ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ በኖህ ፡ አፍ ፡ ሴምንና ፡ ያፌትን ፡ ሲባርክ ፡ ካምንና ፡ ልጁን ፡ ረገመ ። እርሳቸውንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያልታዘዙትን ፡ የሰው ፡ ባሮች ፡ አደረጋቸው ።

የጥፋት ፡ ውኃ ፡ ምሳሌ ፡ ሆነ ፡ በክርስቶስ ፡ ስለ ፡ ተሰራች ፡ መድኃኒት ፡ ስለ ፡ ክርስቲያንም ፡ ጥምቀት ፡ ጴጥሮስ ፡

እንደ.ል ፡ በ፩፡ መልአክቱ ፡ በ፫፡ ምዕራፍ ፡ በ፳፡ ፬፡ ቍጥር ።

ያቾ ፡ ከጥፋት ፡ ውኃ ፡ በመርከብ ፡ የዳኑት ፡ ትውልድ ፡ ኃጢአት ፡ ቶሎ ፡ መላባት ። ሴምም ፡ ሳይሞት ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ጣዖታትን ፡ ማምለክ ፡ ለመዱ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ረስተውት ። ስለዚህም ፡ የመድኃኒት ፡ ተስፋ ፡ ሁለተኛ ፡ እንዳይጠፋ ፡ እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ ሰውን ፡ መረጸ ፡ እርሱም ፡ አብርሃም ። ለርሱም ፡ ተገለጸ ፡ ለርሱም ፡ ለዘሩም ፡ የመድኃኒትን ፡ ተስፋ ፡ ሰጠ ። አብርሃም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ታዝዞ ፡ ከዘመዱም ፡ ካገሩም ፡ ሒደ ፡ ተሰናበተ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ወደሳየው ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ከናዓን ፡ ገባ ። እግዚአብሔርም ፡ መሐላውን ፡ ማለለት ፡ እንዲህ ፡ ሲል ። ላንተና ፡ ለዘርህ ፡ ይህችን ፡ ምድሪቱን ፡ አንተ ፡ አሁን ፡ እንግዳ ፡ የምትሆንባትን ፡ ለዘላለም ፡ ርስት ፡ እሰጥሃለሁ ። የሚባርክህ ፡ ቡሩክ ፡ ይሆናል ። የሚረግምህ ፡ ግን ፡ ርጉም ፡ ይሆናል ። ዘርህ ፡ ይበዛል ፡ እንደ ፡ ሰማይ ፡ ከዋክብት ፡ እንደ ፡ ባሕርም ፡ አሻዋ ። የጸላቶቹን ፡ ደጆች ፡ ይወርሳል ፡ አሕዛብም ፡ ሁሉ ፡ ይባረኩበታል ። ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፡ ም ፡ ፲፪፡ ቍ ፡ ፩፡ ፪፡ ፫። ም ፡ ፲፭፡ ቍ ፡ ፬፡ ፭፡ ፲፰። አብርሃምም ፡ በእግዚአብሔር ፡ አመነ ፡ ይህችም ፡ ሃይማኖት ፡ ጽድቅ ፡ ሁና ፡ ተቈጠረችለት ፡ ም ፡ ፲፭፡ ቍ ፡ ፮። ሮሜ ፡ ም ፬፡ ቍ ፡ ፫። ሃይማኖቱ ፡ እጅግ ፡ ተፈተነች ። ፳፭፡ ዓመት ፡ እግዚአብሔር ፡ ዘገየ ፡ ተስፋውን ፡ ሳይፈጽም ። ዕድሜው ፡ ፻፡ ዓመት ፡ የሳራም ፡ ዕድሜ ፡ ፺፡ ሳይሆን ፡ ይስሐቅ ፡ የተስፋ ፡ ልጅ ፡ አልተወለደምና ። ያችም ፡ ተስፋ ፡ ፩፡ ዓመት ፡ አስቀድሞ ፡ ተጸንታ ፡ ታተመች ፡ እግዚአብሔር ፡ ግዝረትን ፡ ባደረገለት ፡ ጊዜ ። ግዝረትም ፡ መጀመርያ ፡ ምልክት ፡ ሆነ ፡ ለአብርሃም ፡ ለወገኑም ፡ እርሱና ፡ እርሳቸው ፡ የተለዩበት ፡ ከሌሎች ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ። እርሳቸው ፡ በዚህ ፡ አብርሃም ፡ ስለ ፡ ሃይማኖቱ ፡ በተቀበለው ፡ ምልክት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሕዝብ ፡ ሁነው ፡ ተገለጹበት ።

ይስሐቅም ፡ ባደገ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያብርሃምን ፡ ሃይማኖት ፡ እጅግ ፡ ብርቱ ፡ አድርጎ ፡ ፈተነው ፡ ይህነን ፡ አንደኛውን ፡ ልጁን ፡ የተወደደውንም ፡ መሥዋዕት ፡ ሁኖ ፡ ሊያ

ቀርበው ፡ ባዘዘው ፡ ጊዜ ፡፡ አብርሃምም ፡ አመነ ፡ ታዘዘም ፡ ወደ ፡ ሞርያ ፡ አገርም ፡ ወደንድ ፡ ተራራም ፡ ወሰደው ፡ ከ ዚያ ፡ ያርደው ፡ ዘንድ ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ያብርሃምን ፡ ሃይማኖትና ፡ መታዘዙን ፡ አይቶ ፡ አለው ፡፡ እጅህን ፡ አትዘ ርጋ ፡ በብላቴናው ፡ ላይ ፡፡ አንዳችም ፡ አታድርግበት ፡፡ አሁን ም ፡ አውቅያለሁና ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንድትፈራ ፡ ላንዲ ም ፡ ልጅህ ፡ አራራህም ፡ ስለኔ ፡፡ የእግዚአብሔርም ፡ መ ልአክ ፡ አብርሃምን ፡ ጸራው ፡ ሁለተኛ ፡ ከሰማይ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ በራሴ ፡ ማልሁ ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡፡ ይህነን ፡ ነ ገር ፡ አድርገሃልና ፡፡ ስለኔም ፡ ላንድ ፡ ልጅህ ፡ አራራህም ና ፡፡ እባርክሃለሁ ፡ ዘርህንም ፡ አበዛለሁ ፡ እንደ ፡ ሰማይ ፡ ኰከብ ፡ እንደ ፡ ባሕርም ፡ አሸዋ ፡፡ ዘርህም ፡ ይወርሳል ፡ የ ጸላቶቹን ፡ ደጆች ፡፡ በዘርህም ፡ ይባረካሉ ፡ የምድር ፡ አሕ ዛብ ፡ ሁሉ ፡፡ ቃሌን ፡ ሰምተሃልና ፡፡ ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፡ ፳፪፡ ፲፪፡ ፲፰፡፡ አብርሃምም ፡ የምእምናን ፡ ሁሉ ፡ አባት ፡ ይባላ ል ፡፡ ሮሚ ፡ ፬፡ ፲፩፡ ፲፪፡፡ አሁን ፡ ለርሱ ፡ የተሰጠች ፡ ተስፋ ፡ ለልጁ ፡ ለይስሐቅ ፡ ለይስሐቅ ፡ ልጅም ፡ ለያዕቆብ ፡ ተደግ ማ ፡ ተጸናች ፡፡ ስለዚህም ፡ እግዚአብሔር ፡ የአብርሃም ፡ አ ምላክ ፡ የይስሐቅም ፡ አምላክ ፡ የያዕቆብም ፡ አምላክ ፡ ይባላል ፡፡ ኦሪት ፡ ዘጻአት ፡ ፫፡ ፲፭፡፡

ያች ፡ ጸላትነት ፡ ግን ፡ በገነት ፡ የጀመረች ፡ በሰውና ፡ በባ ብ ፡ መኻከል ፡ ከርስዋም ፡ የተነሣ ፡ መከራ ፡ አልቀረም ፡፡ ከአደም ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ዓለም ፡ ድረስ ፡ መንግ ሥት ፡ እግዚአብሔር ፡ ወትሮ ፡ ትጋደላለች ፡፡ የእግዚአብ ሔርም ፡ መንገድ ፡ በመከራ ፡ ወደ ፡ ደስታ ፡ በመጋደልም ፡ ድል ፡ ወደ ፡ ማንሣት ፡ ይወስደል ፡፡ ያዕቆብም ፡ እጅግ ፡ መ ከራ ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ምሥር ፡ ወረደ ፡ ከቤቱ ፡ ሁ ሉ ፡ ጋራ ፡ ከዮሴፍም ፡ ከልጁ ፡ ጋራ ፡ ተገናኘ ፡ ከዚያም ፡ ሞተ ፡፡ ሳይሞትም ፡ ልጆቹን ፡ ሁሉን ፡ ሰበሰበ ፡ በእግዚአ ብሔርም ፡ መንፈስ ፡ ትንቢት ፡ ነገራቸው ፡ ለ፲፪፡ ወገኖች ፡ ኢየራሳቸው ፡፡ ላራተኛ ፡ ልጁ ፡ ለይሁደ ፡ የተመረጸች ፡ በረ ከት ፡ ደረሰችለት ፡፡ እንዲህ ፡ ብልዋልና ፡ የትንቢት ፡ መንፈ ስ ፡ ለሞት ፡ በቀረበ ፡ በባቱ ፡ በያዕቆብ ፡ አፍ ፡፡ ይሁደ ፡ ላ

ንቱ ፡ ይገዛሉ ፡ ወንድሞችህ ፡፡ እጅህም ፡ በጸላቶችህ ፡ አን
ገት ፡ ላይ ፡ ነው ፡፡ ያባትህም ፡ ልጆች ፡ ይሰግዱልሃል ፡፡ ያን
በሳ ፡ ግልገል ፡ ይሁዳ ፡ ነው ፡፡ ለመርኮ ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ወጣ
ህ ፡፡ ተኛ ፡ አንቀላፋም ፡ እንደንበሳም ፡ ግልገል ፡፡ ማንስ ፡
ይችላል ፡ ያስነሣው ፡ ዘንድ ፡፡ በትርም ፡ ከይሁደ ፡ አይጠ
ፋም ፡ ንጉሥም ፡ ከጭኑ ፡ ሁሉ ፡ ለርሱ ፡ የሆነው ፡ እ
ስኪመጣ ፡ ድረስ ፡፡ እርሱንም ፡ አሕዛብ ፡ ተስፋ ፡ ያድር
ጉታል ፡፡ ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፡ ፵፱፡ ፳፡ ፱፡ ፲፡፡

በዚህች ፡ ትንቢት ፡ የመድኃኒት ፡ ተስፋ ፡ ለአደም ፡ ለኖህ
ም ፡ ለአብርሃምም ፡ ከተሰጠች ፡ ተስፋ ፡ ትበራለች ፡፡ መድ
ኃኒት ፡ ከይሁዳ ፡ ወገን ፡ መምጣት ፡ እንደለች ፡ ብልዋል ፡፡
ዘመኑም ፡ ይገለጻል ፡ እንዴህ ፡ ሲል ፡፡ በትር ፡ ከይሁደ ፡ አ
ይጠፋም ፡ ንጉሥም ፡ ከጭኑ ፡ ሁሉ ፡ ለርሱ ፡ የሆነው ፡ እስ
ኪመጣ ፡ ድረስ ፡፡ ከዚህ ፡ በትር ፡ የተባለ ፡ የመንግሥት ፡
ምልክት ፡ ነው ፡፡ ሁሉ ፡ ለርሱ ፡ የሆነው ፡ ሲል ፡ ክርስ
ቶስ ፡ ማለት ፡ ነው ፡፡ እርሱ ፡ ነውና ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ የተፈ
ጠረበት ፡ የሚድንበትም ፡፡ የዚህች ፡ ትንቢት ፡ ትርጓሜ ፡
ይህ ፡ ነው ፡፡ የእሥራኤል ፡ ልጆች ፡ መንግሥት ፡ ለይሁዳ ፡
ወገን ፡ ነው ፡፡ በርሱም ፡ መካከል ፡ ንጉሥ ፡ ይኖራል ፡ ያለ
ም ፡ መድኅን ፡ እርሱም ፡ ክርስቶስ ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡፡

የያዕቆብ ፡ ልጆችም ፡ በመስር ፡ በዙ ፡፡ ዮሴፍም ፡ ከሞ
ተ ፡ በኋላ ፡ ያችም ፡ ትውልድ ፡ ሁሉ ፡ በርሱ ፡ ዘመን ፡ የነ
በረች ፡ ሌላ ፡ ንጉሥ ፡ ተነሣ ፡ ዮሴፍን ፡ የማያውቅ ፡ እርሱ
ም ፡ የእሥራኤልን ፡ ልጆች ፡ ጸላ ፡፡ እርሳቸውም ፡ ባገሬ ፡
በመስር ፡ እንደይበዙ ፡ ፈራ ፡፡ ስለዚህም ፡ እጅግ ፡ አስደከ
ማቸው ፡ በስራ ፡ አስጨነቃቸውም ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡
ሕዝቡን ፡ ጠበቀ ፡ በፈርዖን ፡ ክፋት ፡ እንደይጠፉ ፡፡ በሚያ
ስጨንቅዋቸው ፡ መጠን ፡ በዙ ፡ እንጅ ፡፡ ፈርዖንም ፡ የምስ
ር ፡ ንጉሥ ፡ — ፈርዖንም ፡ ንጉሥ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ — ያደረገ
ባቸው ፡ ድካም ፡ እንደይጠቅምለት ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ አዋላጆች
ን ፡ አዘዘ ፡ የእሥራኤል ፡ ሴቶች ፡ ሲወልዱ ፡ ወንዶች ፡ ልጆ
ቻቸውን ፡ ሊሠጥሙ ፡ ሴቶች ፡ ልጆቻቸውን ፡ ብቻ ፡ ሊያድ
ኑ ፡፡ እለዚያ ፡ አዋላጆች ፡ ግን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ፈርተው ፡

ንጉሥ ፡ እንደዘዛቸው ፡ አላደረጉም ። ስለዚህም ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ባረካቸው ።

የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ከሌዊ ፡ ወገን ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ስሙ ፡
አምራም ፡ የተባለ ፡ ወንድ ፡ ልጅን ፡ ወለደ ። ምሽቱም ፡ ል
ጅዋ ፡ መልካም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ ሰወረችው ፡ ፫፡
ወር ። ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ ታናሽ ፡ ሣፅን ፡ አደረገችለት ።
ወደ ፡ ሣፅኑም ፡ አግብታው ፡ በወንዝ ፡ አኖረቸው ። ሴት ፡
ልጅዋም ፡ ከርሑቅ ፡ ጠበቀቸው ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ የፈ
ርዖን ፡ ልጅ ፡ መጣች ፡ በወንዝ ፡ ልታፀብ ። ሣፅኑንም ፡ ካ
ሽከራ ፡ ጋራ ፡ አገኘታ ፡ አዘነችለት ። ከዕብራውያንም ፡ ወ
ገን ፡ እንደሆነ ፡ ስታውቅ ፡ የዕብራውያንን ፡ ሴት ፡ አስጸራ
ች ፡ እርስዋም ፡ የሕፃን ፡ እናት ፡ ዮኬቤድ ። እርስዋንም ፡
በደመወዜ ፡ ልታጥባው ፡ ልታሳድገውም ፡ አዘዘቻት ። እግ
ዚአብሔር ፡ ያች ፡ ሴት ፡ እናት ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ ላሽከራ ፡
ከውቀትዋ ፡ ሰውሮላታልና ። ጊዜም ፡ ሲደርስ ፡ ዮኬቤድ ፡
ልጅዋን ፡ ለፈርዖን ፡ ልጅ ፡ መለሰችላት ። የፈርዖን ፡ ልጅ
ም ፡ ስሙን ፡ ሙሴ ፡ ብላ ፡ ጸራችው ፡ ማለቱ ፡ ከውኃ ፡ የ
ወጣ ። እኔ ፡ ከውኃ ፡ አውጥቼዋለሁና ፡ አለች ። ልጅዋም ፡
ሁኖ ፡ ቍጠረቸው ።

መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ይላል ፡ በመልእክት ፡ ወደ ፡ ዕብራ
ውያን ፡ ም ፡ ፲፩፡ ቍ ፡ ፳፬። በሃይማኖት ፡ ሙሴ ፡ ባደገ ፡ ጊ
ዜ ፡ ካደ ፡ የፈርዖን ፡ የልጁ ፡ ልጅ ፡ እንደደባል ። መከራ
ም ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ወገን ፡ ጋራ ፡ ወደ
ደ ፡ በኃጢአት ፡ ጥቂት ፡ ዘመን ፡ ደስ ፡ ኪለው ፡ ይልቅ ። የ
ክርስቶስንም ፡ ስድብ ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡ ባለጠግነት ፡
አደረገው ፡ ከምሥር ፡ ከብት ፡ ይልቅ ። የዋጋውን ፡ መልካ
ምነት ፡ ተስፋ ፡ ያድርግ ፡ ነበረና ።

እግዚአብሔርም ፡ ሙሴን ፡ ጸራው ፡ ሕዝቡን ፡ ከምሥር ፡
ባርነት ፡ ያውጣ ፡ ዘንድ ። የእግዚአብሔር ፡ ኃይልም ፡ በሙ
ሴ ፡ ድካም ፡ ታላቅ ፡ ሆነች ። እርሱ ፡ ሲጠራጠር ፡ ሃይማኖ
ቱን ፡ አጽንቶታልና ። እርሱም ፡ ሲደክም ፡ እጁን ፡ አብር
ቶታልና ፡ በኃይልና ፡ በተአምራት ። የርሱም ፡ መላስ ፡ ሲከ
ብድለት ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃሉን ፡ ባፉ ፡ አኖረው ፡ ወንድ

ሙንም ፡ ሐሮን ፡ ሰጠው ፡ ለነጋሪ ፡፡ እንደሁም ፡ ሙሴ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልክተኛ ፡ ሆነ ፡ ለእሥራኤልና ፡ ለፈርዖን ፡ ሐሮን ፡ ለሙሴ ፡ ነቢይ ፡ ሲሆን ፡፡ ወደ ፡ ፈርዖን ፡ ግን ፡ ሲገባ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ በዕብራውያን ፡ አምላክ ፡ ስም ፡ ሲያዘው ፡ የእሥራኤልን ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ በረኻ ፡ እንዲሰደቸው ፡ ብሎ ፡ የፈርዖን ፡ ልብ ፡ ጸና ፡ በትዕቢት ፡ ባለማመንም ፡ እምቢ ፡ ለማለት ፡ እግዚአብሔር ፡ በታላቅ ፡ ተአምራት ፡ በብርቱም ፡ መቅሠፍቱ ፡ እስኪያገደው ፡ ድረስ ፡፡

የዚያን ፡ ጊዜም ፡ እግዚአብሔር ፡ ፋሲካውን ፡ ሰራ ፡ ለወገኑ ፡፡ በሙሴ ፡ አፍ ፡ የእሥራኤልን ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ አዘዛቸው ፡ በየቤታቸው ፡ ሁሉ ፡ ፩፤ በግ ፡ ሊያርዱ ፡ በደሙም ፡ የቤታቸውን ፡ ደጅ ፡ በመቃኑና ፡ በመድረኩ ፡ ሊያመልክቱ ፡፡ እግዚአብሔር ፡ በዚያች ፡ ሌሊት ፡ መልአኩን ፡ ሰድዋልና ፡ የምሥርን ፡ በኵርነት ፡ ሁሉ ፡ ደገድል ፡ ዘንድ ፡ በሰውም ፡ በንስሳም ፡፡ በእሥራኤል ፡ ቤቶች ፡ ብቻ ፡ አለፈ ፡ ለርሳቸውም ፡ አዘነ ፡ ደህችን ፡ ምልክት ፡ አይቶ ፡፡ የፋሲካ ፡ ማለት ፡ "ማለፊያ ፡" ነው ፡ እግዚአብሔር ፡ አልፏልና ፡ በእሥራኤል ፡ ቤቶች ፡፡ አስቀድሞ ፡ ግን ፡ የተጻፈ ፡ ለትምህርት ፡ ተጽፎልናል ፡፡ የፋሲካውንም ፡ ትምህርት ፡ ጳውሎስ ፡ አወጣልና ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ ፋሲካችን ፡ ክርስቶስ ፡ ስለኛ ፡ ታርድዋል ፡ ፩፤ ቆሮንቶስ ፡ ፭፤ ፯፡፡ በመልእክቱም ፡ ወደ ፡ ዕብራውያን ፡ ደላል ፡፡ ያለ ፡ ደም ፡ ሰርየት ፡ የለም ፡፡ ም ፡ ፱፤ ቍ ፡ ፳፪፡፡ ያች ፡ ፋሲካ ፡ ምሳሌ ፡ ሁንዋልና ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡፡ ያ ፡ በግ ፡ በሪሱ ፡ ቤዛ ፡ ደሆን ፡ ዘንድ ፡ አልቻለውምና ፡ በሰው ፡ ፈንታ ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ብልዋልና ፡፡ ኃጢአት ፡ የምታድርግ ፡ ነፍስ ፡ ሁሉ ፡ ትሞታለች ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጥር ፡ ፈቅድዋልና ፡ ልጁን ፡ በሁላችን ፡ ፈንታ ፡ በውነት ፡ ቤዛ ፡ ያድርገው ፡ ዘንድ ፡ በኦሪት ፡ የክርስቶስን ፡ ተስፋ ፡ አርሶ ፡ ቤዛ ፡ እንዲሆን ፡ በሕዝቡ ፡ ልብ ፡ አጸና ፡ እጅግ ፡ ምሳሌ ፡ አድርጎ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡፡ እንደሁም ፡ ነበረ ፡ ደህ ፡ በፋሲካ ፡ የታረደ ፡ በግ ፡፡ ለክርስቶስ ፡ ጊዜ ፡ ነበረለት ፡ በኛ ፡ ፈንታ ፡ ሊሞት ፡፡ በሞቱ

ም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቍጣ ፡ ሊያሳልፍብን ፡፡ አሁንም ፡ ልቡን ፡ የሚያመልክት ፡ በውነተኛ ፡ ሃይማኖት ፡ ደሙን ፡ በፊንታችን ፡ በፈሰሰው ፡ በክርስቶስ ፡ ይድናል ፡፡ የእግዚአብሔርም ፡ ቍጣ ፡ ያልፍበታል ፡፡ ይህች ፡ ትምህርት ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ላይሁድ ፡ ተሰጠች ፡ በምሳሌ ፡ የርሳቸውን ፡ ሃይማኖት ፡ በሚመጣ ፡ ክርስቶስ ፡ ያጸና ፡ ዘንድ ፡፡

እግዚአብሔርም ፡ በፋሲካ ፡ ሌሊት ፡ የምሥርን ፡ ብኵርነት ፡ ሁሉ ፡ ሲገድል ፡ በቀደም ፡ እምቢ ፡ ያሉ ፡ የምሥር ፡ ሰዎች ፡ በእሥራኤል ፡ ልጆች ፡ በመውጣታቸው ፡ አሁን ፡ በግድ ፡ አወጥዋቸው ፡፡ በወጡም ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ በፊታቸው ፡ ሒደ ፡ መራቸው ፡ በቀን ፡ በደመና ፡ ዓምድ ፡ ሲታደላቸው ፡ በሌሊትም ፡ በሳት ፡ ዓምድ ፡፡ ሙሴንም ፡ አዘዘው ፡ እንደይወስደቸው ፡ ባሕዛብ ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ ኤርትራ ፡ ባሕር ፡ አጠገብ ፡ እንጂ ፡፡

የፈርዖንም ፡ ልብ ፡ የእሥራኤል ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ ሔዱ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ተለወጠ ፡ በመንገደቸውም ፡ ሊወስደቸው ፡ አሰበ ፡፡ ሠራዊቱንም ፡ ይዞ ፡ ተከተላቸው ፡ እስከ ፡ ባሕር ፡ ደርቻ ፡ ድረስ ፡፡ የእሥራኤልም ፡ ልጆች ፡ ጸላቶቻቸውን ፡ በማየት ፡ ፈርተው ፡ እግዚአብሔር ፡ ሙሴን ፡ አዘዘ ፡ በትሩን ፡ በባሕር ፡ ላይ ፡ ሊዘርጋ ፡ ብሎ ፡፡ ሙሴም ፡ እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብርቱ ፡ ንፋስ ፡ አስመጣ ፡ ባሕርን ፡ የከፈለ ፡ በቀኝና ፡ በግራ ፡ መንገድ ፡ እስኪሆንላቸው ፡ ድረስ ፡ በባሕር ፡፡ የእሥራኤልም ፡ ልጆች ፡ በርሱ ፡ ወደ ፡ ማደ ፡ ተሻገሩ ፡ በደርቅ ፡ አግራቸው ፡ ውኃ ፡ ሲቆም ፡ እንደ ፡ መንደቅ ፡ በ፪ ፡ አጠገባቸው ፡፡ ፈርዖንም ፡ ሊከተላቸው ፡ በፈለገ ፡ ጊዜ ፡ እርሱም ፡ ከሠራዊቱ ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ፡ ሲገቡ ፡ እግዚአብሔር ፡ ውኃውን ፡ አስመለሰ ፡ የምስርም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ተሠጠሙ ፡፡ ይህ ፡ ደግሞ ፡ ምሳሌ ፡ ሆነ ፡ ለመድኃኒታችን ፡፡ እሥራኤል ፡ በፋሲካ ፡ እንደ ፡ ዳነ ፡ ካጥፊው ፡ ከፈርዖንም ፡ እጅ ፡ እንዲሁም ፡ እኛ ፡ ደግሞ ፡ ዳነ ፡ በክርስቶስ ፡ ሞት ፡ ከሰይጣን ፡ እጅ ፡፡ እሥራኤልም ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡ ከምስር ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ከናዐን ፡ ይሔድ ፡ ዘንድ ፡ እንዲሁም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ እግዚአብሔር ፡

መድረስ ፡ የሚወድ ፡ ከኀጢአት ፡ ባርነት ፡ ይሰናበት ፡ የሰ
ማዩንም ፡ ነገር ፡ ይሻ ፡፡ በኀጢአት ፡ ግን ፡ የሚኖር ፡ ለኀጢ
አትም ፡ የሚያገለግል ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ አደል ፡፡ ክርስቶስ ፡
ከኀጢአትና ፡ ከሰይጣን ፡ ከዘላለምም ፡ ፍርድ ፡ አድነኝ ፡
ብሎ ፡፡ እውነተኛ ፡ እሥራኤል ፡ በውነት ፡ ክርስቲያን ፡ የ
ተባለ ፡ ከምስር ፡ ባርነት ፡ ማለት ፡ ከኀጢአት ፡ ባርነት ፡ በ
እግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ ወጥቶ ፡ የሰማይን ፡ መንገድ ፡ ይሔ
ዳል ፡ የሰማይንም ፡ ስራ ፡ ይሰራል ፡፡ ደሮ ፡ ይህ ፡ አይሆን
ም ፡ ሰው ፡ የኤርትራን ፡ ባሕር ፡ ባያልፍ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ
ን ፡ ባይቀበል ፡ እርሱን ፡ ለመቀበል ፡ ተስፋና ፡ ማኅተም ፡
የሚቀበል ፡ በጥምቀት ፡፡ ውኃ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ምሳ
ሌ ፡ ነውና ፡፡ ውኃ ፡ የሥጋውን ፡ ዕድፍ ፡ እንዲወስድ ፡ ሥጋ
ውንም ፡ እንዲያነጻ ፡ በማፀብ ፡ እንዲሁም ፡ መንፈስ ፡ ቅ
ዱስ ፡ ብንታፀብበት ፡ ማለት ፡ በጸሎት ፡ በሃይማኖትም ፡ ተ
ቀብለን ፡ አንድነት ፡ ብናደርግበት ፡ ከኀጢአት ፡ ሁሉ ፡ ከት
ዕቢት ፡ ከስስትም ፡ ከዝሙትም ፡ ከሐሜትም ፡ ከብትን
ም ፡ ከመውደድ ፡ ከጸላትነትም ፡ ከሌላ ፡ ኀጢአትም ፡ ሁ
ሉ ፡ ያነጻናል ፡፡ እግዚአብሔርም ፡ የሚወደውን ፡ ነገር ፡ ሁ
ሉን ፡ ወደ ፡ ልባችን ፡ ይሰጣል ፡፡ ኃይልንም ፡ ይሰጠናል ፡ የ
እግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ለመፈጸም ፡ ወደ ፡ ሰማያዊ ፡
ከናዐን ፡ የሚወስደውንም ፡ መንገድ ፡ ለመሔድ ፡፡

የእሥራኤልም ፡ ልጆች ፡ ከምስር ፡ ከወጡ ፡ በኋላ ፡ በሁ
ለተኛ ፡ ወር ፡ ወደ ፡ ደብሬ ፡ ሲና ፡ ደረሱ ፡፡ ከዚያም ፡ እግዚ
አብሔር ፡ በሙሴ ፡ አፍ ፡ ተናገራቸው ፡ ነፍሱንም ፡ ገለጸላ
ቸው ፡ እንደ ፡ ዘላለም ፡ አምላክ ፡ ያለም ፡ ሁሉ ፡ ፈጣሪ ፡
ሁኖ ፡፡ ያባቶችም ፡ አምላክ ፡ በፍቅሩ ፡ የፈቀደ ፡ እርሳቸው
ን ፡ ከምስር ፡ ባርነት ፡ ያወጣቸው ፡ ዘንድ ፡ ከጸላቶቻቸውም ፡
እጅ ፡ ያድናቸው ፡ ዘንድ ፡፡ የሰማይንም ፡ እንጀራ ፡ የደንጊያ
ውንም ፡ ውኃ ፡ ምግብና ፡ መጠጥ ፡ ሁኖ ፡ የሰጣቸው ፡ ወደ ፡
በጎ ፡ አገርም ፡ ወተትና ፡ ማር ፡ ወደ ፡ ሚፈስበት ፡ ይወስዳቸ
ው ፡ ዘንድ ፡ ተስፋ ፡ ያስደረገላቸው ፡፡ አሁንም ፡ ገለጸላቸ
ው ፡ እርሳቸው ፡ የወደዱት ፡ እንደሆን ፡ እርሱ ፡ ንጉሣቸው
ና ፡ አምላካቸው ፡ እንዲሆንላቸው ፡ እርሳቸውም ፡ ለርሱ ፡

ለሕዝብ ፡ እንዲሆኑለት ፡፡ የእሥራኤል ፡ ሽማግሎች ፡ ሁሉ ፡ ይህነን ፡ መላሽ ፡ ሰጡ ፡፡ እግዚአብሔር ፡ የሚለውን ፡ ነገር ፡ ሁሉን ፡ እናድርጋለን ፡ ብለው ፡፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በሶስተኛ ፡ ቀን ፡ ፶፡ ቀን ፡ ሁኖ ፡ ከምሥር ፡ ከወጡ ፡ በኋላ ፡ ዓለምም ፡ ከተፈጠረ ፡ በኋላ ፡ በ፴፻፲፫፡ ዓመት ፡ ፲፬፻፩፡ ዓመትም ፡ ክርስቶስ ፡ ሳይወለድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕጉን ፡ ሰጣቸው ፡ በሲና ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ሁኖ ፡ በሳት ፡ ነበልባል ፡ በደመናም ፡ ጢስ ፡ በመላእክትም ፡ በመለከታቸው ፡ ድምጽ ፡ በመብረቅም ፡ በነጐድጓድም ፡፡

የእግዚአብሔርም ፡ ሕግ ፡ በ፲፡ ትእዛዛት ፡ የሰጠው ፡ ይህ ፡ ነው ፡፡

እግዚአብሔር ፡ ይህነን ፡ ነገር ፡ ሁሉን ፡ አለ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡

እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክህ ፡ ነኝና ፡
ከምስር ፡ ምድር ፡ ያወጣሁህ ፡ ከባርነት ፡ ቤት ፡፡

፩፡ ትእዛዝ ፡፡

ሌሎች ፡ አማልክት ፡ አይሁኑልህ ፡ በፊቴ ፡፡

፪፡ ትእዛዝ ፡፡

ሥእልን ፡ ሁሉ ፡ ምሳሌንም ፡ ከቶ ፡ አትስራልህ ፡፡ በላይ ፡ በሰማይ ፡ ካለው ፡፡ በታችም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ካለው ፡፡ በውኃም ፡ ከምድር ፡ በታች ፡ ካለው ፡፡ አትስገድላቸው ፡ አታመልካቸውም ፡፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክህ ፡ ቀናተኛ ፡ አምላክ ፡ ነኝና ፡ ያባቶችን ፡ ኃጢአት ፡ የምመረምር ፡ በልጆች ፡ እስከ ፡ ሶስት ፡ እስካራትም ፡ ትውልድ ፡ ድረስ ፡ በሚጸሉኝ ፡፡ ምህረትንም ፡ አድርጋለሁ ፡ ለብዙ ፡ ሽህ ፡ ለሚወዱኝ ፡ ትእዛዛቴንም ፡ ለሚጠብቁ ፡፡

፫፡ ትእዛዝ ፡፡

የእግዚአብሔርን ፡ ያምላክህን ፡ ስም ፡ ከንቱ ፡ አታድርገው ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ስሙን ፡ ከንቱ ፡ ያደረገውን ፡ ሳይቀሥፈው ፡ አይተወውምና ፡፡

፬ ፡ ትእዛዝ ፡፡

የሰንበትን ፡ ቀን ፡ አስብ ፡ ትቀድሰው ፡ ዘንድ ፡፡ ስድስት ፡ ቀን ፡ ስራ ፡ ተግባርህንም ፡ ሁሉን ፡ አድርግ ፡፡ ሰበተኛ ፡ ቀን ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ያምላክህ ፡ ሰንበት ፡ ነውና ፡ በርሱ ፡ ስራን ፡ ሁሉን ፡ አትስራ ፡፡ አንተ ፡፡ ወንድ ፡ ልጅህም ፡፡ ሴት ፡ ልጅህም ፡፡ ሎሌህም ፡፡ ገረድህም ፡፡ ከብትህም ፡፡ ባገርህም ፡ የሚቀመጥ ፡ እንግዳ ፡፡ እግዚአብሔር ፡ በስድስት ፡ ቀን ፡ ፈጥርዋልና ፡ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ ባሕርንም ፡ ያለባቸውንም ፡ ሁሉ ፡ በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ አርፎዋልና ፡፡ ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሰንበትን ፡ ቀን ፡ ባረከው ፡ ቀደሰውም ፡፡

፭ ፡ ትእዛዝ ፡፡

አባትህንና ፡ እናትህን ፡ አክብር ፡፡ ዕድሜህ ፡ ይረዝም ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክህ ፡ በሚሰጥህ ፡ ምድር ፡፡

፮ ፡ ትእዛዝ ፡፡

አትግደል ፡፡

፯ ፡ ትእዛዝ ፡፡

አታመንዝር ፡፡

፰ ፡ ትእዛዝ ፡፡

አትስረቅ ፡፡

፱ ፡ ትእዛዝ ፡፡

ባሰት ፡ አትምሰክር ፡ በባልንጀራህ ፡ ላይ ፡፡

፲ ፡ ትእዛዝ ፡፡

የባልንጀራህን ፡ ቤት ፡ አትመኝ ፡፡ የባልንጀራህንም ፡ ምሽት ፡ አትመኝ ፡፡ ባርያውንም ፡፡ ባርያዪቱንም ፡፡ በሬውንም ፡፡ አህያውንም ፡፡ ማናቸውንም ፡ ከባልንጀራህ ፡ ገንዘብ ፡፡

ይህች ፡ ባሥር ፡ ትእዛዛት ፡ ያለች ፡ ሕግ ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ ተሰጠች ፡ የሰውን ፡ ፍቃድ ፡ የሰውንም ፡ መሻት ፡ የሰውንም ፡ ዕውቀት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ መገዛት ፡ ትወስድ ፡ ዘንድ ፡፡ ጳውሎስ ፡ ይላል ፡፡ ሕግ ፡ መንፈሳዊት ፡ ናት ፡ ሮሜ ፡ ፯ ፡ ቍ ፡ ፲፬ ፡፡ ይህ ፡ ይገለጻል ፡ ባሥረኛ ፡ ትእዛዝ ፡ 'አትመኝ' ፡ የሚል ፡፡ እንደህ ፡ ሲል ፡ ክፉ ፡ መመኘትንና ፡ ክፉ ፡

ማሰብን ፡ ኃጢአት ፡ ሁኖ ፡ ይገልጻል ። አሁን ፡ ሰው ፡ ባንድ ፡ ትእዛዝ ፡ ቢበድል ፡ በማሰብ ፡ ኃጢአት ፡ ሁኖ ፡ ይቈጠርበታል ። ባንድም ፡ ትእዛዝ ፡ የበደለ ፡ በሁሉም ፡ በደለ ። እግዚአብሔር ፡ በትእዛዝ ፡ ሁሉ ፡ የሚፈልገው ፡ ነገር ፡ አንድ ፡ ነውና ፡ እርሱም ፡ ፍቅር ፡ ነው ። እግዚአብሔርን ፡ መውደድ ፡ በሁሉ ፡ ላይ ፡ በኃይልም ፡ ሁሉ ፡ ባልንጀራችነንም ፡ መውደድ ፡ እንደ ፡ ነፍሳችን ። እንደሁም ፡ ፩፤ ትእዛዝ ፡ በጣም ፡ የፈጸመ ፡ ሰው ፡ ቢገኝ ፡ እርሱ ፡ የቀረትን ፡ ፱፤ ደግሞ ፡ ይፈጽማል ። ፱፤ ትእዛዛትንም ፡ ፈጽሞ ፡ ፩፤ ያስቀረ ፡ አይገኝም ። ሰው ፡ አይደል ። እኔ ፡ ባልንጀራዬን ፡ አልገደልሁምና ፡ ስድስተኛውን ፡ ትእዛዝ ፡ ፈጸምሁት ። ዮሐንስ ፡ ይላልና ። ወንድሙን ፡ የሚጸላ ፡ ሰው ፡ ገደይ ፡ ነው ። ፩፤ መልእክቱ ፡ ም ፡ ፫፤ ቁ ፡ ፲፭። ሰውም ፡ አይደል ። እኔ ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ የለኝምና ፡ ፩፤ ትእዛዙን ፡ ፈጸምሁት ። ሰው ፡ ከሁሉ ፡ ይልቅ ፡ የሚወደው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አምላኩ ፡ ነውና ፡ የሚገዛለት ። ጳውሎስ ፡ በቈሎሳይስ ፡ መልእክት ፡ ስስት ፡ ለጣዖታት ፡ ማምለክ ፡ ሁኖ ፡ ይቈጥራል ። በፊልጵስዮስም ፡ መልእክት ፡ ስለ ፡ ክፉ ፡ ሰዎች ፡ ሲናገር ፡ "ሆዳቸው ፡ አምላካቸው ፡ ነው ፡" ይላል ። ራሱን ፡ ማክበር ፡ ከሁሉ ፡ ይልቅ ፡ የሚወድ ፡ ራሱን ፡ አምላኩን ፡ ያድርጋል ።

የሕግም ፡ መንፈሳዊ ፡ ባሕርይ ፡ እንደሁ ፡ ነው ። ትእዛዝ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ኃጢአት ፡ ሲከለክል ፡ በዚህ ፡ ኃጢአት ፡ የሚጸላውን ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ ይፈልጋል ። በጎ ፡ ማድረግም ፡ ሲፈልግ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የሚጸላውን ፡ ኃጢአት ፡ ይከለክላል ። ይህ ፡ ነገርም ፡ እንደሁ ፡ ነው ። በመጀመርያ ፡ ትእዛዝ ፡ የጣዖታትን ፡ ማምላክ ፡ ሁሉ ፡ ይከለክላል ፡ እግዚአብሔርን ፡ ግን ፡ ብቻውን ፡ እንድናከብር ፡ በምናድርገውም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የርሱን ፡ ክብር ፡ እንድንፈልግ ፡ ያዝናል ። መጽዋዕትን ፡ የሚሰጥ ፡ ወይስ ፡ ጸሎትን ፡ የሚያድርግ ፡ ወይስ ፡ ሌላውን ፡ የሚገባውን ፡ ነገር ፡ የሚያድርግ ፡ ራሱን ፡ ለማክበር ፡ ስሙንም ፡ ታላቅ ፡ ለማድረግ ፡ በጎነቱ ፡ ኃጢአት ፡ ይሆንበታል ። የሰውንም ፡ ትምርት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይልቅ ፡ የሚቀበል ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ቃል ፡

አልፎ ፡ የሰውን ፡ ትምርት ፡ ወይስ ፡ የሰውን ፡ ልማድ ፡ የ ሚከተል ፡ ጣዖታትን ፡ ያመልካል ፡፡ የኃጢአትም ፡ ባርያ ፡ ሁሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በመታዘዝ ፡ ፈንታ ፡ የራሱን ፡ ፈቃ ድ ፡ የሚሻ ፡ ሰውም ፡ ሁሉ ፡ እንኳ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የ ማያገለግል ፡ ሁለግዜ ፡ በኃይሉም ፡ ሁሉ ፡ ጣዖታትን ፡ ያገ ለግላል ፡፡ በእግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ደስ ፡ የማይል ፡ እግዚአ ብሔርም ፡ ስለሚወድ ፡ ነገር ፡ የሚያዝን ፡ ጣዖታትን ፡ እ ንደሚያመልክ ፡ ሰው ፡ ይቈጠራል ፡፡ በሕማምና ፡ በመከ ራ ፡ በጭንቀትም ፡ በሞትም ፡ ጊዜ ፡ ወይስ ፡ በሌላ ፡ ጊዜ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ የማያመን ፡ በፍጥረት ፡ እንጂ ፡ ለ ሥጋውም ፡ ለነፍሱም ፡ ደህንነት ፡ ፍጥረትን ፡ ተስፋ ፡ የሚ ያድርግ ፡ መጀመርያውን ፡ ትእዛዝ ፡ ያፈርሳል ፡ እርሱም ፡ ጣዖታትን ፡ ያገለግላል ፡፡ እንዲህም ፡ ነው ፡ የትእዛዝ ፡ ሁ ሉ ፡ ትምህርት ፡፡

በ፪፡ ትእዛዝ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፈልጋል ፡ ሥእልንና ፡ ም ሳሌውን ፡ እንደናደርግልን ፡ እንደናመልካቸውም ፡ እንደ ንሰግድላቸውም ፡፡ ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ ከመጀመርያ ፡ ትእዛ ዝ ፡ ይለያል ፡፡ መጀመርያ ፡ ትእዛዝ ፡ ለብቻው ፡ ነው ፡ ይህ ም ፡ ለብቻው ፡፡ መጀመርያ ፡ ትእዛዝ ፡ ሌሎች ፡ አማልክ ትን ፡ ስለ ፡ ማምለክ ፡ ይናገራል ፡ ይህ ፡ ፪፡ ግን ፡ ሥእልን ፡ ስለ ፡ ማክበር ፡፡ የማን ፡ ሥእል ፡፡ እንዴት ፡ ይላል ፡ ትእዛ ዝ ፡፡ 'ወይስ ፡ በላይ ፡ በሰማይ ፡ ካለ' ፡፡ በሰማይ ፡ ያለ ፡ እ ርሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነው ፡ መላእክትም ፡ ብፁዓንም ፡ ሰ ዎች ፡ ፀሓይም ፡ ጨረቃም ፡ ከዋክብትም ፡፡ 'ወይስ ፡ በታ ች ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ካለ ፡' ይላል ፡፡ በምድር ፡ ላይም ፡ ያ ለ ፡ እርሱም ፡ ሰው ፡ እንስሳም ፡ አታክልትም ፡ ደንጊያም ፡፡ 'ወይስ ፡ በውኃ ፡ ካለ ፡፡' እርሱም ፡ ዓሣ ፡ የባሕርም ፡ እን ስሳ ፡ ነው ፡፡ 'ከምድር ፡ በታች ፡ ካለ ፡' ሲል ፡ ማለቱ ፡ በገሃ ነም ፡ ካለ ፡ ነው ፡፡ እርሱም ፡ ሰይጣን ፡ ከመላእክቱ ፡ ከክ ፉኣንም ፡ ከሞቱ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡፡ ደግሞ ፡ ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ ከ ቶ ፡ ሥእልን ፡ ማድረግ ፡ አይከለክልም ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ሰውን ፡ እንዲህ ፡ ፈጥሮታልና ፡ በማየትና ፡ በመስማት ፡ ወ ደ ፡ ዕውቀቱ ፡ የሚገባውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ምሳሌ ፡ እንዲሆ

ገለት ፡ ወይስ ፡ በማሰብ ፡ ወይስ ፡ በመንገር ፡ ወይስ ፡ በጁ ፡ መስራት ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ እርሱ ፡ በዚህ ፡ ትእዛዝ ፡ ይከለክል ናል ፡ ሥእልን ፡ ከማድረግ ፡ ለማምለክና ፡ ለመስገድ ፡፡ ስ ለዚህ ፡ ትእዛዝ ፡ አይገባም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥእል ፡ ቢሆን ፡ ሰው ፡ የሚስመው ፡ ወይስ ፡ የሚሰግድለት ፡፡ የእ ግዚአብሔርም ፡ ነገር ፡ ብርቱ ፡ ነው ፡፡ እንዴት ፡ ይላልና ፡ በ ዚህ ፡ ትእዛዝ ፡ "እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክህ ፡ ቀናተኛ ፡ አምላክ ፡ ነኝና ፡ ያባቶችን ፡ ዓመፃ ፡ የምመረምር ፡ በልጆ ች ፡ እስከ ፡ ሶስተኛ ፡ እስከ ፡ አራተኛም ፡ ትውልድ ፡ ድረስ ፡ በሚጸሉኝ ፡፡ ምህረትንም ፡ አድርጋለሁ ፡ ለብዙ ፡ ሺህ ፡ ለ ሚወዱኝ ፡ ትእዛዛቴንም ፡ ለሚጠብቁ ፡፡" ሥእልን ፡ ማክበ ር ፡ እንኪያስ ፡ ቢከለክል ፡ ምንድር ፡ ይፈልጋል ፡ በዚህ ፡ ት እዛዝ ፡፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ይልዋል ፡ በዮሐንስ ፡ ወንጌል ፡ ም ፡ ፬፡ ቍ ፡ ፳፬፡፡ እግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ነው ፡፡ የሚሰ ግዱለትም ፡ በመንፈስና ፡ በውነት ፡ ይገባል ፡ ይሰግዱለት ፡ ዘንድ ፡፡

በ፫፡ ትእዛዝ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይከለክልናል ፡ ስሙን ፡ ከንቱ ፡ እንደናደርግ ፡፡ ሰው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ ከ ንቱ ፡ ያድርጋል ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ ያለ ፡ ማሰብ ፡ ያለ ፡ ፈርሃትም ፡ ቢናገረው ፡፡ ይህ ፡ እንዴት ፡ ይደረጋል ፡፡ እ ጅግ ፡ ጊዜ ፡ ይገኛል ፡ በመጫወት ፡ በሰላምታም ፡ 'እግዚ አብሔር ፡ ይመስግን' ፡ ሲል ፡ እግዚአብሔርን ፡ በውነት ፡ ሳያመሰግን ፡፡ ወይስ ፡ 'በእግዚአብሔር' ፡ ሲል ፡ ያለ ፡ እ ግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡፡ ወይስ ፡ በመለመን ፡ ልማኝ ፡ 'ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡' 'ስለ ፡ ክርስቶስም ፡' ብሎ ፡ ሲለም ን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታላቅነት ፡ ሳያስብ ፡፡ ወይስ ፡ በመ ማል ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ዝምብሎ ፡ ነገር ፡ ወይስ ፡ ስለ ፡ አሰት ፡ እንኳ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቢምል ፡፡ ወይስ ፡ የእግዚአብሔ ርን ፡ ነገር ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ባለማሰብ ፡ ባለማወቅም ፡ ያለ ፡ ፈርሃትም ፡ የሚደግም ፡፡ ወይስ ፡ ያለ ፡ ማሰብ ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ፈርሃት ፡ ያለ ፡ እውቀትም ፡ የሚጸልይ ፡፡ ወይስ ፡ እንዲያው ፡ ክርስቲያን ፡ የተባለ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በ ውነት ፡ ክርስቲያን ፡ ካልሆነ ፡፡ ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ ደግሞ ፡ እጅ

ግ ፡ ያስፈራል ፡፡ “እግዚአብሔር ፡ ስሙን ፡ ከንቱ ፡ የሚያደ
ርገውን ፡ ሳይቀሥፈው ፡ አይተወውምና” ፡ ይላል ፡፡ ደር ፡ ምን
ድር ፡ ይፈልጋል ፡ እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ ትእዛዝ ፡፡ ምላ
ሽ ፡፡ የእግዚአብሔር ፡ ወገን ፡ የተባለ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በውነ
ት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ወገን ፡ ሊሆን ፡ ማለት ፡ እውነተኛ ፡
ክርስቲያን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ በችሎቱ ፡ ሁሉ ፡ የ
ሚያከብር ፡ ሁለግዜ ፡ በማሰብ ፡ በመናገርም ፡ በማድረግ
ም ፡፡ ሁለግዜ ፡ እውነት ፡ የሚናገር ፡ በመኳንንትም ፡ ት
እዛዝ ፡ ወይስ ፡ በግድ ፡ መሐላ ፡ ቢሆን ፡ በውነት ፡ ብቻ ፡ እ
ግዚአሔርን ፡ የሚያስመሰክርለት ፡፡

አራተኛ ፡ ትእዛዝ ፡ ላይሁድ ፡ እንደ ፡ ተሰጠ ፡ እንዲህ ፡
ለኛ ፡ አልተሰጠም ፡፡ ጳውሎስ ፡ ይላልና ፡፡ “አሁን ፡ ማንም ፡
አይፈረድባችሁ ፡ በመብልና ፡ በመጠጥ ፡፡ ብዓልም ፡ በመ
ጠበቅ ፡፡ ጨረቃውንም ፡ በመቍጠር ፡ በሰንበትም ፡፡” ቆላሳ
ይስ ፡ ም ፡ ፪፡ ቍ ፡ ፲፯፡፡ ይህ ፡ ደግሞ ፡ በዚህ ፡ ይገለጻል ፡፡ በ
ዚህ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰባተኛ ፡ ቀን ፡ ተቀደሰ ፡፡ የሱስ ፡ ክርስቶ
ስ ፡ ግን ፡ በመጀመርያ ፡ ቀን ፡ በእሁድ ፡ ከሙታን ፡ ተነሣ ፡
መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ በ፶፡ ቀን ፡ በእሁድ ፡ በሐዋርያት ፡ ላይ ፡
ፈሰሰ ፡፡ ይህነን ፡ አስበው ፡ ከኦሪት ፡ ሥርዓትም ፡ ተፈትተ
ው ፡ ሐዋርያት ፡ በየሳምንት ፡ በመጀመርያ ፡ ቀን ፡ ተሰበሰ
ቡ ፡ ካብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ጋራ ፡፡ ፩፡ ቆሮንቶስ ፡ ፲፯፡ ፪፡፡ ይ
ህም ፡ ቀን ፡ ስለዚህ ፡ ‘የጌታ ፡ ቀን ፡’ ተባለ ፡፡ የዮሐንስ ፡ ራ
እይ ፡ ም ፡ ፩፡ ቍ ፡ ፲፡፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡
ተሰበሰቡ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ለመስማት ፡ ቍርባን
ንም ፡ ለመቀበል ፡፡ በጸሎትም ፡ በትምርትም ፡ አንድነታ
ቸውን ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡ ለማጽናት ፡፡ ሌላ ፡ ሥርዓት ፡
ግን ፡ አላደረጉም ፡ ጉባኤን ፡ ከመሰብሰብ ፡ በቀር ፡፡ ይህነን
ም ፡ ቀን ፡ ከሌላ ፡ ቀን ፡ መለየት ፡ አልታዘዘም ፡ ከቆንስ
ታንጢኖስ ፡ ዘመን ፡ በፊት ፡፡ ቆንስታንጢኖስ ፡ ፫፻፳፩፡ ዓመ
ት ፡ ክርስቶስ ፡ ከተወለደ ፡ በኋላ ፡ አዝዋልና ፡ በእሁድ ፡ ቀ
ን ፡ ታላቅ ፡ ስራ ፡ ሁሉ ፡ ሊቀር ፡ ብሎ ፡፡ የሰንበትም ፡ ምሥ
ጢር ፡ ይህ ፡ ነው ፡፡ እግዚአብሔር ፡ በ፮፡ ቀን ፡ ዓለምን ፡ ከ
ፈጠረ ፡ በኋላ ፡ ሰባተኛውን ፡ ቀን ፡ ለዕረፍት ፡ ለእግዚአብ

ሔርም ፡ ምስጋና ፡ ቀደሰው ፡፡ እንዲህም ፡ አድርጎ ፡ ወደደ ፡ ሰ
ው ፡ በ፯፤ ቀን ፡ ስለ ፡ ሥጋ ፡ መሻት ፡ ስለዚህ ፡ ዓለምም ፡ ነገ
ር ፡ ከደከመ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ዕረፍት ፡ እንዲሆንለ
ት ፡ በሥጋ ፡ የነፍሱን ፡ ደህንነት ፡ ይሰራ ፡ ዘንድ ፡ ከኃጢአት
ም ፡ ሁሉ ፡ ያርፋ ፡ ዘንድ ፡፡ ደሮ ፡ የሰንበት ፡ ነገር ፡ ምሳሌ ፡
ሆነ ፡ ስለ ፡ መንፈሳዊ ፡ ሰንበት ፡ ክርስቶስ ፡ ስላበጀልና ፡ በ
ሞቱ ፡ በትንሣኤውም ፡፡ እውነተኛ ፡ ዕረፍት ፡ አይገኝም ፡
በወንጌል ፡ ብቻ ፡ እንጅ ፡ የኃጢአትን ፡ ሰርየት ፡ የእግዚአ
ብሔርንም ፡ ፍቅር ፡ የልብንም ፡ ሰላም ፡ ለሚያምን ፡ ሁ
ሉ ፡ የሚሰጥ ፡፡ ይህችን ፡ ዕረፍት ፡ ያበጀልን ፡ ዘንድ ፡ የሱ
ስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለኛ ፡ ደከመ ፡ መከራም ፡ ጭንቀትም ፡ ተ
ቀበለ ፡ የኃጢአታችነን ፡ ክብድ ፡ ሁሉ ፡ ሲሸከም ፡ ሕግንም ፡
ሁሉን ፡ ሲፈጽም ፡ በመስቀልም ፡ ሲሞት ፡፡ እርሱ ፡ በመስ
ቀል ፡ ሁኖ ፡ "ተፈጸመ ፡" ብሎ ፡ በታላቅ ፡ ድምጽ ፡ በጮኸ ፡
ጊዜ ፡ የስራ ፡ የድካምም ፡ ቀን ፡ ሁሉ ፡ ተጨረሰ ፡ ለሚያምና
ት ፡፡ እውነተኛ ፡ እሥራኤልም ፡ እርሱም ፡ የክርስቶስ ፡ ወ
ገን ፡ በክርስቶስ ፡ የሚድኑ ፡ ከኃጢአታቸው ፡ እውነተኛው
ን ፡ ዮሱዓ ፡ ተከትለው ፡ ወደ ፡ ዕረፍት ፡ ምድር ፡ ወደ ፡ ሰ
ማያዊ ፡ ከናዐን ፡ ይገባሉ ፡፡ የሙሴ ፡ ወገን ፡ ግን ፡ እርሳቸው
ም ፡ በተግባር ፡ መጸደቅና ፡ መደን ፡ የሚፈልጉ ፡ በከንቱ ፡ ሲደ
ክሙ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ በእኩል ፡ መንገድ ፡ ይሞታሉ ፡፡ ጳ
ውሎስ ፡ ይህችን ፡ ትምርት ፡ ያወጣል ፡ በመልእክቱ ፡ ወደ ፡
ዕብራውያን ፡ ም ፡ ፬፤ የኦሪት ፡ ሰንበት ፡ ከስራ ፡ ቀን ፡ በኋ
ላ ፡ ከድካምም ፡ በኋላ ፡ ይከተላል ፡ ወንጌል ፡ ከኦሪት ፡ በ
ኋላ ፡ እንደ ፡ ተከተለ ፡፡ ደሮ የወንጌል ፡ ሰንበት ፡ መጀመ
ርያ ፡ ቀን ፡ ነው ፡ ሰውንም ፡ ያሳርፋል ፡ የእግዚአብሔርን ፡
ተግባር ፡ በደስታ ፡ ያድርግ ፡ ዘንድ ፡፡ እንዲህ ፡ የላልና ፡ ደዊ
ት ፡፡ "ልቤን ፡ ባሰፋህ ፡ ጊዜ ፡ የትእዛዛትህን ፡ መንገድ ፡ እሮ
ጣለሁ ፡" መዝሙር ፡ ፻፲፱፡ ፴፪፤ ሰውም ፡ ሳያርፍ ፡ ከኃጢ
አቱ ፡ ከኦሪትም ፡ ድካም ፡ በጎ ፡ ስራ ፡ አይችልም ፡፡ ሰው ፡
ግን ፡ ቢያውቅ ፡ በወንጌል ፡ ባይጠራጠርም ፡ ሲል ፡፡ "ኃጢአ
ቴ ፡ ሁሉ ፡ ቀረልኝ ፡ ኦሪትም ፡ የሚፈልግ ፡ ሁሉ ፡ ተፈጸመ ፡
ክርስቶስ ፡ በፈንታዬ ፡ ፈጽሞታልና ፡፡" እርሱ ፡ በልቡ ፡ ያርፋ

ል ፡ ክርስቶስ ፡ በቀደሰው ፡ በመንፈሳዊ ፡ ሰንበት ። የኃጢአ
ትም ፡ መርገም ፡ የእግዚአብሔርም ፡ ቍጣ ፡ በልቡ ፡ ይከ
ብድ ፡ የነበረ ፡ ይሔደል ፡ ልቡም ፡ ይቀላል ። ልቡም ፡ ሲቀ
ል ፡ እርሱ ፡ ደስ ፡ ይላል ፡ በእግዚአብሔር ፡ በደስታውም ፡
በምስጋናም ፡ ያለ ፡ ፍርሃት ፡ ያለ ፡ ኀዘንም ፡ የእግዚአብሔ
ርን ፡ ፈቃድ ፡ ይፈጽም ፡ ዘንድ ፡ ይመርጻል ። ይህ ፡ የወንጌ
ል ፡ መንፈሳዊ ፡ ሰንበት ፡ ነው ። የሚያምን ፡ ሁሉ ፡ ያርፍ
በታል ። ይህነን ፡ ዕረፍት ፡ ግን ፡ ያልቀመሰ ፡ በክርስቶስ ፡ አ
መናለሁ ፡ ቢል ፡ አሰተኛ ፡ ነው ፡ አፉ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ ልቡ ፡ አ
ያምንም ። እንዴት ፡ ይላልና ፡ ክርስቶስ ። "ወደኔ ፡ ኑ ፡ እላ
ንት ፡ ደካሞች ፡ ሸክማችሁም ፡ የከበደ ። እኔም ፡ አሳር
ፋችኋለሁ ።" አሁንም ፡ ወደ ፡ ክርስቶስ ፡ መምጣት ፡ ማለ
ት ፡ 'ማመን ፡' ነው ። በውነት ፡ የሚያምን ፡ ክርስቶስ ፡ በር
ሱ ፡ ፈንታ ፡ እንደ ፡ ደከመ ፡ የርሱ ፡ ሰንበት ፡ ጀመረ ። ወይ
ስ ፡ የክርስቶስ ፡ ነገር ፡ "እኔ ፡ አሳርፋችኋለሁ ፡" ሲል ፡ በውኑ ፡
ከንቱ ፡ ነውን ። ደግሞ ፡ የክርስቶስን ፡ ነገር ፡ ከንቱ ፡ ሁኖ ፡ የ
ሚቈጥር ፡ ስሙ ፡ ክርስቲያን ፡ አይሁን ። በክርስቶስ ፡ ግን ፡
የሚያምን ፡ ከኃጢአቱም ፡ የሚያርፍ ፡ እርሱ ፡ የክርስቶ
ስን ፡ ትእዛዝ ፡ ደግሞ ፡ ይፈጽማል ፡ ሲል ። "ቀምበሬን ፡ ተ
ሸከሙ ፡ በላያችሁ ፡ ከኔም ፡ ተማሩ ፡ እኔ ፡ ደዋህ ፡ ነኝና ፡
ልቤም ፡ ትሑት ፡ ነው ። ዕረፍትም ፡ ታገኛላችሁ ፡ ለነፍሳች
ሁ ። ቀምበሬ ፡ መልካም ፡ ነውና ፡ ሸክሜም ፡ ቀሊል ፡ ነ
ው ።" ማቴዎስ ፡ ም ፡ ፲፩፡ ቍ ፡ ፳፰፡ ፳፱፡ ፴፡፡ የዚህች ፡ የወ
ንጌል ፡ የረፍቱ ፡ ምሳሌ ፡ እርሱ ፡ ሰንበትና ፡ እሁድ ፡ ነው ።
ደግሞ ፡ እንዴት ፡ ይቀደሳል ። በሀኬት ፡ አይደለም ፡ ወይስ ፡
ክፉ ፡ በማድረግ ፡ ወይስ ፡ በመጫወት ። ከሀኬት ፡ በጎ ፡ ስ
ራ ፡ ይሻላል ። በጎ ፡ ስራም ፡ ይፈልጋል ። መቀደስም ፡ ማለ
ት ፡ ካልተቀደሰ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ መለየት ፡ ለእግዚአብሔርም ፡
ማገልገል ። እሁድም ፡ ይቀደሳል ፡ ስለ ፡ ሥጋ ፡ መሻት ፡ ያ
ለ ፡ ተግባር ፡ ቢቀር ፡ ብንጸሊም ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ብናመ
ሰግን ፡ ከሕዝቡ ፡ ጋራ ፡ በቤቱ ። በርሱም ፡ ቃሉን ፡ ብንሰማ ፡
ብናስተምርበትም ። ድናቍርትንም ፡ ብናስተምሕር ። ኃጢ
አተኞችንም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለመመለስ ፡ ብንደክ

ም ። የሚያዝኑትንም ፡ ብናጽና ። ለድኆችም ፡ በጎ ፡ ብናድ
ርግ ። ባልቴቶችንም ፡ አባትና ፡ እናት ፡ የሌላቸውንም ፡ ል
ጆች ፡ በችሎታችን ፡ መጠን ፡ ብንረዳ ። የታሠሩትንም ፡ ስ
ለ ፡ ጽድቅም ፡ መከራ ፡ የተቀበሉትን ፡ በመከራቸው ፡ ብን
ጐብኝ ። በሁሉም ፡ ብንጋደል ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥ
ት ፡ በልባችንና ፡ በዙርያችን ፡ እንዲዘረጋ ። ይህነንም ፡ ሁ
ሉን ፡ ብናድርግ ፡ የጌታው ፡ ስም ፡ ለመመስገን ፡ የጌታውን ፡
ቀን ፡ በውነት ፡ እንቀድሳለን ። እንዲሁም ፡ ብንቀድሰው ፡
በየእሁድ ፡ የዘላለም ፡ ሰንበት ፡ ይጀምርልናል ፡ ከቶ ፡ የ
ማይጨረስ ፡ በዘላለም ፡ ሕይወት ፡ የሚፈጸም ፡ እንጅ ፡
እግዚአብሔር ፡ ሁሉ ፡ ሲሆን ፡ በሁሉም ።

እለዚህ ፡ ፬፡ ትእዛዛት ፡ ለብቻቸው ፡ ተጻፉ ፡ ባንድ ፡ በደ
ንጊያ ፡ ጽላ ፡ ነገራቸውም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ስለ ፡ መው
ደድ ፡ ነው ። አንድ ፡ ትእዛዝም ፡ ሁናው ፡ ይቈጠራሉ ፡ እ
ርሱም ፡ ይህ ፡ ነው ። "እግዚአብሔርን ፡ ትወድ ፡ ዘንድ ፡ ከ
ፈጹም ፡ ልብህ ፡ ከፈጹምም ፡ ነፍስህ ፡ ከፈጹምም ፡ አሳ
ብህ ፡ ከፈጹምም ፡ ኀይልህ ።" ኦሪት ፡ ዘደግም ፡ ም ፡ ፮፡ ቍ ፡
፭። የሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ይላል ። "ይህች ፡ ናት ፡ መጀመር
ያዪቱ ፡ ትእዛዝ ፡ የምትበልጥ ።"

የቀሩ ፡ ፮፡ ትእዛዛት ፡ ደግሞ ፡ ለብቻቸው ፡ በሁለተኛ ፡ ደ
ንጊያ ፡ ጽላ ፡ ተጻፉ ፡ ነገራቸውም ፡ ባልንጀራውን ፡ ስ
ለ ፡ መውደድ ፡ ነው ። እርሳቸውም ፡ አንድ ፡ ትእዛዝ ፡
ሁነው ፡ ይቈጠራሉ ፡ እንዲህ ፡ የሚል ። "ባልንጀራህን ፡ ው
ደድ ፡ እንደ ፡ ነፍስህ ።" ኦሪት ፡ ዘሌዋውያን ፡ ም ፡ ፲፱፡ ቍ ፡
፲፰። ክርስቶስም ፡ ይላል ። "ሁለተኛዪቱ ፡ ትእዛዝም ፡ የ
ምትመስላት ፡ ናት ፡ ባልእንጀራህን ፡ ውደድ ፡ እንደ ፡ ነፍ
ስህ ።" ማቴዎስ ፡ ፳፪፡ ፴፱።

በ፭፡ ትእዛዝ ፡ እግዚአብሔር ፡ አባትንና ፡ እናትን ፡ እ
ንድናከብር ፡ ያዝናል ። አባትና ፡ እናት ፡ እለዚያ ፡ ና
ቸው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሥርዓት ፡ በኀይሉም ፡ ሕይወታች
ን ፡ መኖርያውንም ፡ ልብስንም ፡ ምግብንም ፡ ሌላም ፡
መሻታችን ፡ እንደሌ ፡ የሰጡን ፡ የሚጠብቁንም ፡ የሚወዱ
ንም ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ በታች ፡ የሚገዙ ፡ በላያችን ።

ያባቶችም ፡ ሁሉ ፡ አባት ፡ የባትና ፡ የናትን ፡ ሥርዓት ፡ በ
ሰማይና ፡ በምድር ፡ የሰራው ፡ የሚጠብቀውም ፡ እርሱ ፡
እግዚአብሔር ፡ ነው ፡፡ ጳውሎስ ፡ እንዲል ፡ ኤፌሶን ፡ ፫፡
፲፭፡፡ ላባትና ፡ ለናት ፡ የሚገባ ፡ ክብር ፡ ይህ ፡ ነው ፡፡ እርሳ
ቸውን ፡ በእግዚአብሔር ፡ በላያችን ፡ የተሾሙትን ፡ እንደ
ንቍጥራቸው ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ምሳሌ ፡ በመግዛታቸው ፡
እንደለ ፡ ልናውቅ ፡፡ ስለዚህም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡
ጋራ ፡ በማይጸላ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለርሳቸው ፡ ልንታዘዝ ፡፡ ፈቃ
ደችነንም ፡ በፈቃደቸው ፡ በታች ፡ ልናድርግ ፡፡ ስለ ፡ በጎነታ
ቸውም ፡ ስለ ፡ ቸርነታቸውም ፡ ልናመሰግናቸው ፡፡ በኃይላ
ችንም ፡ ሁለግዜ ፡ ልናገለግላቸው ፡፡ በበጎም ፡ በክፉም ፡ ቀ
ን ፡ ልናስብላቸው ፡ ልንረደቸውም ፡፡ ይህም ፡ ትእዛዝ ፡ አ
ባትና ፡ እናት ፡ ሲል ፡ እግዚአብሔር ፡ በላያችን ፡ የሾመው ፡
ሰው ፡ ሁሉ ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡ ወላጆች ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡፡
እለዚያም ፡ በየቤት ፡ ሥርዓት ፡ ከወላጆች ፡ በቀር ፡ መም
ህራንና ፡ ጌቶች ፡፡ በያገርም ፡ ሹማምት ፡ በየምድርም ፡ በ
የሕዝብም ፡ መኳንንትና ፡ ነገሥታት ፡ ናቸው ፡፡ ለለዚህም ፡
ሁሉ ፡ በየስፍራቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ሾማቸውበት ፡
ማክበራቸው ፡ ይገባል ፡ ስለ ፡ ራሳቸውም ፡ አይደለም ፡ ስ
ለ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንጅ ፡፡ ክፎችም ፡ ቢሆኑ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ይፈርድባቸዋል ፡ እኛም ፡ አይደለነም ፡ በታቻቸው ፡
ሁነናለና ፡፡ በጎችም ፡ ቢሆኑ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ዋጋ ፡ አይ
ቀርላቸውም ፡ የኛ ፡ ምስጋና ፡ ግን ፡ ጥቂት ፡ ይጠቅምላቸዋ
ል ፡፡ እግዚአብሔርንም ፡ የሚፈራ ፡ የሚወድም ፡ ሰው ፡
በእግዚአብሔር ፡ ፈንታ ፡ የተሾመውን ፡ ሰውን ፡ ሁሉን ፡
በእግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ያከብራል ፡፡ እ
ግዚአብሔርን ፡ ግን ፡ የማያከብር ፡ የእግዚአብሔርንም ፡
ሹም ፡ እንዲገባው ፡ አያከብርም ፡፡ እግዚአብሔርን ፡ ግ
ን ፡ የማያከብር ፡ ሥርዓቱንም ፡ የማይጠብቅ ፡ እግዚአብሔ
ር ፡ እጅግ ፡ ይቀሥፈዋል ፡፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፡ ሳሎሞን ፡፡
አባቱን ፡ የሚንቀውን ፡ እናቱንም ፡ የሚረግመውን ፡ ዓይ
ን ፡ ሁሉን ፡ ቍራ ፡ ያወጣዋል ፡ የንስርም ፡ ግልገሎች ፡ ይ
በሉታል ፡፡ ምሳሌ ፡ ፴፡ ፲፯፡፡ እንዲትስ ፡ ይገባል ፡ በሌላ ፡ ሰ

ው ፡ ላይ ፡ ለተሾመ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ያድርግ ፡ ዘንድ ፡ የእግዚ
አብሔርን ፡ ፈቃድ ፡ እንደ ፡ ፈጽም ፡ በታቹም ፡ ያሉትን ፡ መ
ታዘዛቸውን ፡ ፍቅራቸውንም ፡ ክብራቸውንም ፡ እንደ ፡ ያገ
ኝ ፡፡ ምላሽ ፡፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ያድርግ ፡፡
እግዚአብሔርን ፡ ከሁሉ ፡ ይልቅ ፡ ባልንጀራውንም ፡ ማለ
ት ፡ ሰውን ፡ ሁሉን ፡ (የአደም ፡ ልጆች ፡ ሁነው ፡ ወንድሞች ፡
ሁነዋልና ፡) እንደ ፡ ነፍሱ ፡ ይወድ ፡ ዘንድ ፡፡ ጳውሎስ ፡ ይላል ፡፡
ከትእዛዛት ፡ ሁሉ ፡ ይህች ፡ መጀመርያዪቱ ፡ ናት ፡ ከተስ
ፋ ፡ ጋራ ፡ የምትባል ፡፡ ደህና ፡ ልትሆን ፡ ዕድሜህም ፡ ሊረ
ዝም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡፡ ኤፌሶን ፡ ፯፡ ቍ ፡ ፪፡ ፫፡፡ እንደዚህ ፡ ሰ
ው ፡ ሁሉ ፡ ከሌላ ፡ በላይና ፡ ከሌላ ፡ በታች ፡ ያለ ፡ የእግዚ
አብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ቢከተል ፡ ይባረካል ፡ የእግዚአብሔ
ር ፡ በረከት ፡ አይቀርም ፡፡

ስድስተኛ ፡ ትእዛዝ ፡፡ "አትግደል ፡" ይላል ፡፡ እግዚ
አብሔርም ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡ ሰውን ፡ መግደል ፡ ይከለክላ
ል ፡፡ እንደዚህ ፡ ይላልና ፡፡ "የሰውን ፡ ደም ፡ የሚያፈስ ፡ የርሱ
ም ፡ ደም ፡ በሰው ፡ ይፈሰሳል ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ሰውን ፡ እ
ንደ ፡ ምሳሌው ፡ ፈጥርዋልና ፡፡" እግዚአብሔር ፡ ሰውን ፡ በ
ምሳሌው ፡ ሲፈጥረው ፡ የምድር ፡ ሁሉ ፡ ጌታ ፡ ሁኖ ፡ አደረገ
ው ፡ በምድር ፡ ፍጥረትም ፡ የለም ፡ በሰው ፡ ላይ ፡ የሚሆ
ን ፡፡ የሰው ፡ ፈራጅ ፡ እንኪያስ ፡ ፈጣርዩ ፡ ነው ፡ አርሱም ፡
እግዚአብሔር ፡፡ በሰውም ፡ መኻከል ፡ እግዚአብሔር ፡ ላ
ንደንድ ፡ ሰው ፡ ሥልጣን ፡ ሰጠው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈን
ታ ፡ ወንድሞቹን ፡ ሊጠብቅ ፡ ክፉ ፡ እንደይደርስባቸው ፡ የ
እግዚአብሔርም ፡ ሥርዓት ፡ እንደይፈርስ ፡፡ ያለዚህም ፡
ሰው ፡ ከቶ ፡ አይገዛም ፡ በሰው ፡ ላይ ፡፡ ጳውሎስ ፡ ይላል
ና ፡፡ ሹመት ፡ አይሆንም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ በቀር ፡፡
ሮሜ ፡ ፲፫፡ ፩፡፡ አሁንም ፡ ሰውን ፡ የሚገድል ፡ የእግዚአብ
ሔርን ፡ ምሳሌ ፡ ያጠፋል ፡፡ የርሱም ፡ ደም ፡ እግዚአብሔ
ር ፡ ሥልጣን ፡ በሰጠው ፡ በመኰንን ፡ እጅ ፡ ይፈሳል ፡፡ ደ
ግሞ ፡ ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ ደምን ፡ በከንቱ ፡ ማፍሰስ ፡ ይከለክላ
ል ፡፡ ስለዚህ ፡ ይገባል ፡ ደም ፡ ሁሉ ፡ በሌላ ፡ እንደይፈስ ፡
በመኰንን ፡ እጅ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡፡ እርሱም ፡ በፍርዱ ፡ እጅ

ግ ፡ ሊመረምር ፡ ንጹሕ ፡ ደም ፡ እንዲያፈስ ። በቅንም ፡ ሲ
ፈርድ ፡ ምህረት ፡ እንዲደቀር ። እግዚአብሔርም ፡ የሰው
ን ፡ ደም ፡ ማፍሰስ ፡ ሲከለክል ፡ ጸላትነትን ፡ ሁሉን ፡ ይከ
ለክላል ። ዮሐንስ ፡ ይላልና ። ወንድሙን ፡ የሚጸላ ፡ ነፍ
ስ ፡ ገደይ ፡ ነው ። ፩፡ መልእክቱ ፡ ፫፡ ፲፭፡፡ ይህ ፡ የመግደል ፡
ሁሉ ፡ ሥር ፡ ነውና ፡ እርሱም ፡ አለመውደድ ። አሁንስ ፡
ይህነን ፡ ነገር ፡ ሁሉን ፡ ሲከለክል ፡ ምንድር ፡ ይፈልጋል ።
ሰውን ፡ ሁሉን ፡ ከለልባችን ፡ ልንወድ ፡ የሥጋውንም ፡ የነ
ፍሱንም ፡ ደህንነት ፡ ልንጠብቅ ፡ ደስ ፡ ከሚሉም ፡ ጋራ ፡
ደስ ፡ ልንል ፡ ከሚያለቅሱም ፡ ጋራ ፡ ልናልቅስ ። እንደ ፡ ቾ
ሎታችንም ፡ ባልንጀራችነን ፡ ልንረደው ፡ በሥጋውም ፡ በ
ነፍሱም ፡ ጉደይ ፡ ሁሉ ።

በ፯፡ ትእዛዝ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምንዝርን ፡ ይከለክላ
ል ። ደሮ ፡ "አታምንዝር ፡" ሲል ፡ የዝሙት ፡ ዘመድ ፡ ሁ
ሉ ፡ ወደ ፡ ዝሙትም ፡ የሚወስድ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ማለቱ ፡
ነው ። የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ይላልና ። ሰማችሁ ፡ እንደ ፡ ተባ
ለ ፡ ለቀደሙት ፡ አታምንዝር ። እኔ ፡ ግን ፡ እላችኋለሁ ።
ወደ ፡ ሴት ፡ ያየ ፡ ሁሉ ፡ የተመኛትም ፡ ፈጽሞ ፡ አመነዘረ
ባት ፡ በልቡ ። የቀኝ ፡ ዓይንህም ፡ ብታሰነክልህ ፡ አውጥተ
ህ ፡ ጣላት ፡ ካንተ ። ይሻልሃልና ፡ አንድ ፡ ብልትህ ፡ ቢጠፋ ፡
አካልህ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ገሃናም ፡ እንደይገባ ። የቀኝ ፡ እጅህ
ም ፡ ብታሰነክልህ ፡ ቍርጥህ ፡ ካንተ ፡ ጣላት ። ይሻልሃልና ፡
አንድ ፡ ብልትህ ፡ ቢጠፋ ፡ አካልህ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ገሃናም ፡
እንደይገባ ። ተባለም ። ምሽቱን ፡ የፈታ ፡ የፍችዋን ፡ መጻ
ፍ ፡ ይስጣት ። እኔ ፡ ግን ፡ እላችኋለሁ ። ምሽቱን ፡ የፈታ ፡
ያለ ፡ ዝሙት ፡ መክንያት ፡ እርሱ ፡ አመንዝሬ ፡ አደረጋ
ት ። የተፈታችውንም ፡ ያገባ ፡ አመነዘረ ። ማቴዎስ ፡ ፭፡
፳፯፡ እስከ ፡ ፴፪፡ ድረስ ። በዚህም ፡ ስፍራ ፡ የሱስ ፡ ክርስ
ቶስ ፡ 'ብልቱን ፡ መቍረጥ ፡' ሲል ፡ በምሳሌ ፡ ይናገራል ። ማ
ለቱም ፡ ይህ ፡ ነው ። ዝሙትን ፡ ብትወድ ፡ እንደ ፡ ዓይን
ህ ፡ እንደ ፡ እጅህም ፡ የኃጢአትን ፡ ፍትወት ፡ አውጣ ።
ፍትወትን ፡ ደስታውንም ፡ ሁሉን ፡ በዚህ ፡ ዓለመ ፡ ከመቅ
መስ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ መታዘዝ ፡ ይሻላልና ።

ዝሙትም ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እጅግ ፡ ያስቈጣል ።
ስለዚህ ፡ የቀደመኞችን ፡ ምድር ፡ አጠፋት ፡ በውኃ ። ስለዚህ
ም ፡ ሳደምንና ፡ ገሞራን ፡ በሳት ፡ አጠፋቸው ። ስለዚህም ፡
የከናዐን ፡ አሕዛብ ፡ አጠፋቸው ፡ ምድራቸውንም ፡ ለእሥ
ራኤል ፡ ሰጠ ። ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፡ ፯፡ ፪። ፱፡ ፳፪። ም ፡ ፲፱።
ዘሌዋውያን ፡ ም ፡ ፲፰። ደሮ ፡ ሰው ፡ ቢሆን ፡ ነፍሱን ፡ ጀን
ደረባ ፡ የሚያደርግ ፡ ይህነን ፡ ትእዛዝ ፡ ሊፈጽም ፡ ብሎ ፡
እርሱ ፡ ይስቷል ። የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ይላልና ። ከልብ ፡ ይ
ወጣል ፡ ኃጢአት ፡ ሁሉ ። ማርቆስ ፡ ፯፡ ፳፩። የሥጋውን
ም ፡ ብልት ፡ የሚቈርጥ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፍጥረት ፡ ያ
ጠፋል ፡ ኃጢአቱ ፡ ሳይቀር ። ከሰውም ፡ መኻከል ፡ ሸሸ
ቶ ፡ ወደ ፡ በረኻ ፡ የሚሔድ ፡ በዝሙት ፡ እንዳይወድቅ ፡
ብሎ ፡ ይስታል ። የኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ ምንጭ ፡ ከሚሆን ፡ ከ
ልቡ ፡ መሸሸት ፡ አይችልምና ። ፍትወትንም ፡ እንኳ ፡ ቢ
ያስተኛ ፡ አይገድለውም ፡ አያሸንፈውምም ። አሁንም ፡
ምንድር ፡ ይፈልጋል ፡ እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ ትእዛዝ ።
እግዚአብሔር ፡ የሰራውን ፡ የመጋባትን ፡ ሥርዓት ፡ ልናከ
በር ፡ በሁሉ ። ይህነንም ፡ ሥርዓት ፡ ላናፈርስ ፡ ከርሱም ፡
ላንወጣ ። አንድ ፡ ወንድና ፡ አንዲት ፡ ሴት ፡ በዚህ ፡ ሥር
ዓት ፡ አንድነት ፡ ያደረጉ ፡ ይህችን ፡ አንድነት ፡ በኃይላቸው ፡
ሊጠብቁ ፡ በርስዋም ፡ ሊጸኑ ። አንድ ፡ ሥጋም ፡ ሁነው ፡ የ
ክርስቶስ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ጋራ ፡ ያለቸው ፡ አንድነት ፡
ምሳሌ ፡ ሊሆኑ ። እንደሁም ፡ ልጆችን ፡ ሊወልዱ ፡ ሊያሳ
ድጓቸውም ፡ በተግሣጽና ፡ በምክር ፡ ለእግዚአብሔር ።
እግዚአብሔር ፡ መጋባትን ፡ አድርጓታልና ። ኦሪት ፡ ዘፍጥረ
ት ፡ ፩፡ ፳፯። ፪፡ ፲፰። ቀደሳትም ። ኤፌሶን ፡ ፭፡ ፳፪፡ እስከ ፡
፴፫። ፩፡ ጢሞቴዎስ ፡ ፪፡ ፲፭። አሁንም ፡ እግዚአብሔር ፡
መጋባትን ፡ ካደረገ ፡ ስለ ፡ ምስጋናው ፡ እንዴት ፡ ይላል ፡ ጳ
ውሎስ ፡ ፩፡ ቆሮንቶስ ፡ ም ፡ ፯። ለሰው ፡ ምሽት ፡ ባያገባ ፡
ይሻለዋል ። ደግሞም ። ድንግልን ፡ ለመጋባት ፡ አሳልፎ ፡
የሚሰጥ ፡ መልካም ፡ ያድርጋል ። ድንግሉንም ፡ ለመጋባ
ት ፡ አሳልፎ ፡ የማይሰጥ ፡ ከመልካም ፡ የተሻለውን ፡ ያድ
ርጋል ። መላሽ ። ጳውሎስ ፡ እንደሁ ፡ ይላል ፡ ስለዚያ ፡ ዘ

መን ። ሃይማኖት ፡ ባሕዛብ ፡ መኻከል ፡ ሲጀመር ፡ መጋባ
ት ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አስቸገረ ። ይህም ፡ ችጋር ፡ እንዲደሆን ፡
ሃይማኖትም ፡ እንዲደከለክለ ፡ ብሎ ፡ ስለዚህ ፡ ይላል ።
ይህ ፡ የሚሻል ፡ ይመስለኛል ፡ ስለ ፡ ዘመን ፡ ጭንቀት ። በ
ሰው ፡ ያምርበታል ፡ እንዲህ ፡ ቢሆን ። ፩፡ ቆሮንቶስ ፡ ፯፡
፳፯፡፡ የእግዚአብሔር ፡ ነገር ፡ እርሱ ፡ በርሱ ፡ አይጸላምና ፡
ሁሉም ፡ አንድ ፡ ነው ። ጳውሎስም ፡ ከዚህ ፡ ስላለመጋባት ፡
ከመጋባት ፡ እንዲሻል ፡ ሲል ፡ ይህ ፡ ከሌላ ፡ መንገሩ ፡ ጋራ ፡
አይጸላም ፡ ሲል ። "መጋባት ፡ የከበረች ፡ ናት ።" ያነንም ፡
ነገሩን ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ አይነግርም ። እንደ ፡
አሳቡ ፡ እንደ ፡ ምክሩም ፡ እንጂ ። ፩፡ ቆሮንቶስ ፡ ፯፡ ፯፡ ፳፯፡
፴፡፡ መጋባት ፡ ግን ፡ የሚከለክሉትን ፡ ሰዎች ፡ መናፈቃን ፡ ይ
ለቸዋል ። እንዲህ ፡ ይላልና ፡ ፩፡ ጢሞቴዎስ ፡ ፬፡፡ መንፈስ ፡
ስለዚህ ፡ በግልጥ ፡ ይላል ። በኋለኛው ፡ ዘመን ፡ ሰዎች ፡ ከ
ሃይማኖት ፡ ይርቃሉ ። የሚያስቱትንም ፡ መናፍስት ፡ ይከ
ተላሉ ፡ የሰይጣናትንም ፡ ትምርት ። በማስመሳል ፡ ባሰት
ም ፡ ነገር ። ሕሊናቸውም ፡ በጋለ ፡ ብረት ፡ የተቃጠለች ፡ ና
ት ። መጋባትን ፡ ይከለክላሉ ። እግዚአብሔርም ፡ የፈጠ
ራትን ፡ መብል ፡ ያርማሉ ፡ ምስጋና ፡ ይሰጡ ፡ ዘንድ ፡ እው
ነትን ፡ የሚያውቁ ፡ ቢቀበልዋት ። የእግዚአብሔር ፡ ፍጥረ
ት ፡ ሁሉ ፡ ንጹሕ ፡ ነውና ፡ ከርሱም ፡ አንዳች ፡ ርኵስ ፡ የለ
ም ፡ በምስጋና ፡ ቢቀበሉት ። ነገር ፡ ግን ፡ ይቀደሳል ፡ በእግ
ዚአብሔር ፡ ነገር ፡ በጸሎትም ። መጋባትንም ፡ የሚንቅ ፡
ሰው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሥርዓት ፡ ይንቃል ። በዚህም ፡
መጽደቅ ፡ የሚፈልግ ፡ ሃይማኖትን ፡ አያውቅም ። ሰው ፡
በሃይማኖት ፡ ብቻ ፡ ይጸድቃልና ። አለመጋባት ፡ ግን ፡ ስለ ፡
ዘመን ፡ ጭንቀት ፡ ብቻ ፡ ባይሆን ፡ ለጽድቅ ፡ እንጂ ፡ በሰው ፡
ትእዛዝም ፡ ከንቱ ፡ ነው ። ከሌላ ፡ ይልቅም ፡ ከክህነት ፡ ከ
ትምህርትም ፡ መጽሬት ፡ ጋራ ፡ ይጸላል ። ጳጳሳትና ፡ ዲያቆ
ናት ፡ ከርሳቸውም ፡ ጋራ ፡ ቀሳውስት ፡ ሁሉ ፡ ታዘዋልና ፡ ባ
ለ ፡ አንዲት ፡ ምሽት ፡ እንዲሆኑ ፡ በጎ ፡ ልጆችም ፡ እንዲሆ
ኑላቸው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ ለሰው ፡ ደህንነትም ፡ የ
ሚያሳድጉቸው ። ፩፡ ጢሞቴዎስ ፡ ፫፡ ፪፡ ፲፪፡፡ ቲቶስ ፡ ፩፡ ፯፡፡

በ፰፤ ትእዛዝ ፡ እግዚአብሔር ፡ ‘መስረቅን ፡’ ይከለክላል ፡፡
መስረቅም ፡ ሲል ፡ የባልንጀራችንን ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ በግ
ፌ ፡ ወይስ ፡ በግድ ፡ ወይስ ፡ በትንኰል ፡ መውሰድ ፡ ማለ
ት ፡ ነው ፡፡ ይህ ፡ ይደረጋል ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚገባውን ፡
ነገር ፡ ባንሰጥ ፡ ለኛም ፡ ከባልንጀራችን ፡ የማይገባነውን ፡
ነገር ፡ ብንወስድ ፡፡ ክፉ ፡ መስፈርያ ፡ ክፉ ፡ ሚዛንም ፡ ክ
ፉ ፡ መሸመትና ፡ መለወጥም ፡ በገቢያ ፡፡ ከዋጋውም ፡ ከ
ደመወዜም ፡ መቍረጥ ፡ በመግዛትም ፡ በስራም ፡፡ ግፍም ፡
ሁሉ ፡ መስረቅ ፡ ነው ፡፡ ሰውም ፡ ሁሉ ፡ እንኳ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ በጎ ፡ ስራ ፡ ለመስራት ፡ የሰጠውን ፡ ጊዜውንና ፡ ኃይ
ሉን ፡ በከንቱ ፡ በመጫወት ፡ በሀኬትም ፡ የሚያሳልፍ ፡ በእ
ግዚአብሔር ፡ ስርቅ ፡ ያድርጋል ፡፡ በበጎ ፡ ፈንታ ፡ ክፉ ፡ የሚ
ያድርግ ፡ ኃይሉንም ፡ ገንዘቡንም ፡ ጊዜውንም ፡ ደህንነቱን
ም ፡ ለኃጢአት ፡ ማገልገል ፡ የሚሰጥ ፡ ነፍሱን ፡ ከክርስቶስ ፡
ሰርቅዋት ፡ ለሰይጣን ፡ ይሰጣታል ፡፡ አሁንም ፡ ምንድር ፡ ይ
ፈልጋል ፡ እግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ ትእዛዝ ፡ እናድርግ ፡ ዘን
ድ ፡፡ የባልንጀራችንን ፡ ገንዘብ ፡ ልንጠብቅ ፡ እንደ ፡ ችሎታች
ንም ፡ ልንረደው ፡ ገንዘቡ ፡ እንዳይጠፋ ፡ እንዳይጐደም ፡ ል
ናበዛው ፡ እንጀ ፡ ለሁሉም ፡ የሚገባውን ፡ ነገር ፡ ልንሰ
ጥ ፡፡ ቅንን ፡ ልናድርግ ፡ በመሸመትም ፡ በመልወጥም ፡ በ
መግዛትም ፡፡ በጀችንም ፡ ልንሰራ ፡ የኛን ፡ እንጀራ ፡ እንበ
ላ ፡ ዘንድ ፡ ለነደያንም ፡ መስጠት ፡ እንችል ፡ ዘንድ ፡፡ ራሳ
ችንንም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሎላልት ፡ ሁነን ፡ ልንቈጥር ፡
የርሱንም ፡ ጸጋ ፡ ልንፈልግ ፡ እርሱ ፡ በሰጠነ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡
የታመነ ፡ ሎላልቱ ፡ ሁነን ፡ እንድንገኝ ፡፡

በ፱፤ ትእዛዝ ፡ ያሰትን ፡ ምስክር ፡ በባልንጀራችን ፡ ላይ ፡
ይከለክላል ፡፡ ያሰት ፡ ምስክር ፡ እንደንናገር ፡ እንደንቀበል
ም ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡፡ እንዲሁም ፡ አ ሰትን ፡ መ ንገር ፡ ሁሉ
ን ፡ ይከለክላል ፡፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚፈራ ፡ ሰው ፡ ወ
ትሮ ፡ እርሱን ፡ ያስባል ፡ ሁሉን ፡ እንዲያይ ፡ የተሰወረው
ንም ፡ ነገር ፡ ሁሉን ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ እንደ ያወጣ ፡፡ ስለዚ
ህም ፡ ልቡን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ተከፍቶ ፡ በፊቱም ፡ ተመ

ላልሆ ፡ በማሰቡ ፡ በመናገሩም ፡ እውነተኛ ፡ ሊሆን ፡ ይጋደ
ላል ፡፡ እርሱም ፡ እግዚአብሔር ፡ ሁሉን ፡ እንደ ፡ ያውቅ ፡ አ
ስቦ ፡ በባልንጀራው ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ያው ፡ አይፈርድም ፡፡ ባ
ልንጀራውም ፡ ክፉ ፡ እንደ ፡ ያድርግ ፡ ቢያይ ፡ በፍቅር ፡ ደገ
ሥጸዋል ፡ ቢሆንም ፡ ለብቻው ፡፡ ባልንጀራውም ፡ ይህነን ፡
የፍቅርን ፡ ምክር ፡ ቢሰማ ፡ ቢመለስም ፡ የወንድሙን ፡ ነ
ፍስ ፡ አገኛ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ባይሰማም ፡ ይጸልያል ፡ ስ
ለ ፡ ወንድሙ ፡፡ መፍረድ ፡ ግን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይተዋ
ል ፡፡ ለምስክር ፡ ግን ፡ የተጸራ ፡ እንደሆን ፡ እውነትን ፡ ይነ
ግራል ፡ ከውነትም ፡ አይወጣም ፡፡ እውነትንም ፡ ሊጠብ
ቅ ፡ ብሎ ፡ በፊት ፡ መልካም ፡ ይመረምራል ፡፡ ያሰት ፡ ም
ስክርስ ፡ በፍርድ ፡ ብቻ ፡ አይደረግም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ መ
ናገር ፡ እንጅ ፡፡ እጅግም ፡ ክፉ ፡ ነው ፡ ፍቅርን ፡ ያጠፋ
ል ፡፡ ክብርን ፡ ያስነውራል ፡ በሚናገረውም ፡ በራሱ ፡ ይጐ
ዳል ፡፡ ክርስቶስ ፡ ይላል ፡፡ በምትፈርዱበት ፡ ፍርድ ፡ ይ
ፈረድባችኋል ፡፡ በምትሰፍሩበትም ፡ መስፈርያ ፡ ይሰፈ
ርላችኋል ፡፡

በ፲፡ ትእዛዝ ፡ የባልንጀራውን ፡ ገንዘብ ፡ መመኘት ፡
የከለከላል ፡፡ ደር ፡ ገንዘቡን ፡ መመኘት ፡ ሲል ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ የሚጸላውን ፡ ነገር ፡ መመኘትን ፡ ሁሉን ፡ ይከለክላ
ል ፡፡ በዚህችም ፡ ትእዛዝ ፡ ሕግ ፡ መንፈሳዊ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡
ይገለጻል ፡፡ የጅን ፡ ስራ ፡ የመላስንም ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ አይከ
ለክልም ፡ የልብንም ፡ አሳብ ፡ እንጅ ፡፡ በዚህም ፡ ትእዛ
ዝ ፡ ይከለክላል ፡ ከቶ ፡ አሳብ ፡ በልባችን ፡ እንደ ፡ ይነሣ ፡ በ
እግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡፡ በዚህም ፡ ይገለጻ
ል ፡ ቅዱስ ፡ ያዕቆብ ፡ የሚል ፡ እውነት ፡ እንደ ፡ ሆን ፡፡ ሕግ
ን ፡ ሁሉን ፡ ጠብቆ ፡ ባንዲት ፡ የሚወድቅ ፡ በሁሉም ፡ የተ
ላለፈ ፡ ሆነ ፡፡ የያዕቆብ ፡ መልእክት ፡ ፪፡ ፲፡፡ አሁንም ፡ ሰ
ው ፡ ሁሉ ፡ ይህነን ፡ አስቦ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚለምን ፡
መንፈሱን ፡ እንደ ፡ ሰጠው ፡ ልቡን ፡ ያበራ ፡ ዘንድ ፡ መንፈ
ስ ፡ ቅዱስም ፡ ቢያበራው ፡ ልቡንም ፡ ቢያስታውቀው ፡ ከዚ
ህ ፡ ሕግ ፡ ይማራል ፡ ልቡ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ መላ ፡ በኃጢአት ፡፡

መልካም፡ብንመረምር፡የእግዚአብሔርን፡ሕግና፡ልባችን
ን፡እለዚህ፡ሁለት፡እንደይገጠሙ፡እናገኛለን። እኛም፡እ
ግዚአብሔር፡ካዘዘው፡ሁሉ፡ምንምን፡እንደልፈጸምን፡
ከቶ፡በሁሉም፡እንደ፡በደልን፡እንማራለን። በሕግ፡የኃጢ
አት፡ዕውቀት፡ይመጣልና፡ጳውሎስ፡እንዲል። ሮሜ፡
፫፤ ፳። አሁንም፡እግዚአብሔር፡ተስፋ፡አስደረገ፡ለሰው፡
ሁሉ፡ትእዛዙን፡የሚጠብቅ፡የሥጋና፡የነፍስ፡ደህንነት፡
ይሰጠው፡ዘንድ፡ለዘላለም። ኦሪት፡ዘሌዋውያን፡፲፰፤
፭። ሕጌንና፡ትእዛዛቴን፡ጠብቁ፡እርሳቸወን፡የሚያድር
ግ፡ሰው፡ሁሉ፡ይድንባቸዋልና። እኔ፡እግዚአብሔር፡ነ
ኝና። ይህቺ፡ሕግ፡ግን፡እንዲያው፡አልተሰጠችም፡ሰ
ው፡ሁሉ፡እንኳ፡ባይድንበት። እግዚአብሔር፡በሰው፡
ሲፈርድ፡ስለ፡ኃጢአቱ፡ቅንና፡ጻድቅ፡ሁኖ፡ሊገለጽ፡እን
ጂ። ኃጢአቱንም፡የማያውቅ፡ሰው፡ሁሉ፡ከኃጢአቱም፡
የሚያድነውን፡አይሻም። የኃጢአት፡ታላቅነት፡ግን፡ከመ
ርገሙ፡ይገለጻል። እግዚአብሔር፡ይላል። የዚህች፡ሕ
ግ፡ቃል፡ሁሉ፡የማይፈጽም፡እንደርሱም፡የማያደርግ፡
ርጉም፡ነው። ኦሪት፡ዘደግም፡፳፯፤ ፳፮። ገላትያን፡፫፤ ፲።
ይህ፡መርገም፡ግን፡ምንድር፡ነው። ከእግዚአብሔር፡
ከደህንነትም፡ሁሉ፡መለየት። ሥቃይና፡ጭንቀት፡መከ
ራም፡ለዘላለም፡በገሃነም፡እሳት። ይህ፡ሁሉ፡በመጽ
ሐፍ፡ቅዱስ፡ሞት፡ይባላል። ጳውሎስ፡ይላልና፡"የኃጢ
አት፡ደመወዙ፡ሞት፡ነው።" ሮሜ፡፮፤ ፳፫። የዮሐንስ፡ራ
እይ፡፳፩፤ ፰። እግዚአብሔርም፡ሕጉን፡እንደህ፡ሰራልን፡
ለመድኃኒት፡ልንናፈቅ። ከልባችንም፡ልንጠይቅ። እኔ፡
ጐስቋላ፡ሰው፡ማነው፡የሚያድነኝ፡ከዚህ፡ከሞት፡ሥ
ጋ። ጳውሎስ፡እንዲል፡ሮሜ፡፯፤ ፳፬። ለምእምናንም፡
በውነት፡ለሚያምኑ፡እግዚአብሔር፡ሕጉን፡ሰጠ፡እርሳ
ቸው፡ያመሰግኑት፡ዘንድ፡በክርስቶስ፡ከሕግ፡መርገም፡
ሁሉ፡አድንዋቸዋልና። ጸጋውንም፡ሰጥትዋቸዋልና፡ይወ
ዱ፡ዘንድ፡የእግዚአብሔርን፡ፈቃድና፡ትእዛዝ፡በሁሉ፡
ለመከተል። ለርሳቸውም፡እንዲይህ፡ይገባል፡ከኃጢአት፡

ሁሉ ፡ ኃሯ ፡ ይጋደሉ ፡ ዘንድ ፡፡ ካለምም ፡ ከኃጢአትም ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ይሞቱ ፡ ዘንድ ፡ ላይደክሙም ፡ ይሕጉን ፡ ፈጻሚ ፡ እስኪያገኙ ፡ ድረስ ፡ በሚመጣ ፡ ዓለም ፡፡

ከዚህችም ፡ ሕግ ፡ ሌላ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለእሥራኤል ፡ ልጆች ፡ ፪ ሌሎች ፡ ሕጋጋት ፡ ሰጠ ፡ በሙሴ ፡ እጅ ፡፡ አንዲት ፡ ሕግ ፡ ለካህናት ፡ ለመቀደስም ፡ ነበረች ፡፡ አንዲትም ፡ ለእሥራኤል ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ያገራቸውን ፡ ሥርዓት ፡ የሰራባት ፡፡ ስለለዚህ ፡ ፪ ሕጋጋት ፡ በዚህ ፡ ጥቂት ፡ መናገር ፡ ይበቃል ፡፡

ስለ ፡ ክህነት ፡ ሕግ ፡፡ እግዚአብሔር ፡ እሥራኤልን ፡ ለመንግሥቱ ፡ መረጸ ፡ እርሳቸው ፡ ሕዝቡ ፡ ይሆኑለት ፡ ዘንድ ፡፡ እርሱም ፡ ንጉሥ ፡ ይሆንላቸው ፡ ዘንድ ፡፡ ስለዚህም ፡ በመኻከላቸው ፡ መኖርያውን ፡ አስደረገለት ፡፡ ሙሴንም ፡ የመኖርያውን ፡ ምሳሌ ፡ አሳየ ፡ በሲና ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ሲሆን ፡፡ ፲ ቃላት ፡ በ፪ ደንጊያ ፡ ጽላት ፡ ተጽፈው ፡ ሙሴን ፡ አዘዘ ፡ ታቦት ፡ የተባለ ፡ ሣጥን ፡ ሊያስደርግ ፡ ከንጨት ፡፡ ርዝመቱ ፡ ፪ ክንድ ፡ ተስንዝር ፡ ወርዱም ፡ ፩ ክንድ ፡ ተስንዝር ፡ ቁመቱም ፡ ፩ ክንድ ፡ ተስንዝር ፡ ሊሆን ፡ ጌጹም ፡ እጅግ ፡ ያመረ ፡፡ በርሱም ፡ የ፲ ትእዛዛት ፡ ሕግ ፡ ሊያገባ ፡፡ መክደኛውንም ፡ ሊሰራለት ፡ የጸጋ ፡ ዙፋን ፡ የተባለ ፡፡ እርሱም ፡ ፪ ኪሩቤል ፡ ነበሩ ፡ አያንዳንዱ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡፡ ይህም ፡ የእግዚአብሔር ፡ የታየ ፡ መቀመጫ ፡ ሆነ ፡፡ ለርሱም ፡ በ፫ ክፍል ፡ የተከፈለ ፡ ድንኳን ፡ ተሰራ ፡ ፩ ለታቦት ፡፡ ይህችም ፡ ክፍል ፡ የቅዱሳን ፡ ቅድስት ፡ ተባለች ፡፡ እግዚአብሔር ፡ በርስዋ ፡ ታደትዋልና ፡፡ በርሱም ፡ ሰው ፡ አልገባም ፡ የካህናት ፡ አለቃ ፡ እንጂ ፡ ባያመት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ የሕዝብን ፡ ኃጢአት ፡ ለማስታረቅ ፡፡ ከዚያም ፡ እግዚአብሔር ፡ ታየ ፡ በክብር ፡ በጸጋ ፡ ዙፋን ፡ ላይ ፡ በኪሩቤልም ፡ ላይ ፡ ሲኖር ፡ የሕዝቡን ፡ ጸሎት ፡ ሲሰማ ፡ ፈቃዱንም ፡ ሲያስታውቃቸው ፡፡

የድንኳን ፡ ፪ ክፍል ፡ በመኻከል ፡ ነበረ ፡ ከቅዱሳን ፡ ቅዱስም ፡ በመጋረጃ ፡ ተለየ ፡፡ እርሱም ፡ እንደያው ፡ መቅደ

ስ ፡ ተባለ ፡፡ ይህም ፡ የካህናት ፡ ቦታ ፡ ነበረ ፡ ከዚያ ፡ ለእግ
ዚአብሔር ፡ ያገለገሉ ፡ ሁለግዜ ፡፡ በርሱም ፡ ጢስ ፡ ያደረጉ
በት ፡ መሠውያ ፡ ተገኘ ፡ የማሳዮትም ፡ እንጀራ ፡ ተብሎ ፡
የተቀመጠበት ፡ ሳድቃ ፡ የወርቅም ፡ መቅረዝ ፡፡ ይህ ፡ ስፍ
ራ ፡ ደግሞ ፡ ተለየ ፡ ከ፫፤ ስፍራ ፡ በመጋረጀ ፡፡
ሶስተኛም ፡ ስፍራ ፡ ለሕዝብ ፡ ነበረ ፡ የእሥራኤል ፡ ልጆ
ች ፡ ሁሉ ፡ የቆሙበት ፡ ምሥዋዕትን ፡ ሊያድርጉ ፡ ሊጸልዩ
ም ፡ ሊያመሰግኑም ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ቃል ፡ ሊሰ
ሙ ፡፡ በዚህም ፡ ስፍራ ፡ መሠውያ ፡ ነበረ ፡ ካህናት ፡ ምሥ
ዋዕትን ፡ ሁሉን ፡ ያረዱበት ፡ ያነደዱበትም ፡፡
በዚህም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ድንኳን ፡ ያገለገሉ ፡ ካህናት ፡
ከሌዊ ፡ ወገን ፡ ነበሩ ፡፡ እግዚአብሔር ፡ የሌዊን ፡ ወገን ፡ መ
ርጾታልና ፡ ከእሥራኤል ፡ ሁሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በመቅ
ደሱ ፡ ለማገልገል ፡ ወንድሞቻቸውንም ፡ ለማስተማር ፡፡ የ
ሌዊ ፡ ልጆችም ፡ ፫፤ ነበሩ ፡ እርሳቸውም ፡ ጌርሶም ፡ ካሃት
ም ፡ ምራሪም ፡፡ ከለዚህ ፡ ፫ም ፡ እግዚአብሔር ፡ የካሃት
ን ፡ ወገን ፡ መረጸ ፡ ከርሳቸውም ፡ የሐሮን ፡ ልጆች ፡ ለክህነ
ት ፡፡ ከርሳቸውም ፡ የኤልዓዛር ፡ ይሐሮን ፡ የብክር ፡ ልጁ ፡
ልጆች ፡ መረጸ ፡ ከርሳቸው ፡ መካከል ፡ የካህናትን ፡ አለቃ ፡
ይወስድ ፡ ዘንድ ፡፡ እግዚአብሔርም ፡ ስለ ፡ ልብሳቸው ፡
ስለ ፡ ማገልገላቸውም ፡ ሁሉ ፡ ሥርዓትን ፡ አደረገ ፡፡ የልብ
ሳቸው ፡ መክንያት ፡ ቅድስና ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነበረ ፡፡
ስለዚህም ፡ ሳያገለግሉ ፡ ተቀደሱ ፡ በተመረጸ ፡ ቅቤ ፡ ምሥ
ዋዕት ፡ ከሠው ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ ኃጢአታቸው ፡፡ ድንኳንም ፡
ሁሉ ፡ በርሱም ፡ የነበረ ፡ ሁሉ ፡ ተቀባ ፡ ተቀደሰም ፡፡
የካህናትም ፡ ተግባር ፡ መሥዋት ፡ ነበረ ፡ ስለ ፡ ራሳቸ
ውና ፡ ስለ ፡ ሕዝብ ፡ መጸለይም ፡ መባረክም ፡፡ የምሥዋ
ዕትም ፡ ወገን ፡ አያሌ ፡ ነበረ ፡፡ ምሥዋዕት ፡ ሁሉ ፡ ግን ፡
ደም ፡ ከማፍሰስ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፡፡ ላምን ፡ ወይስ ፡ በግን ፡ ወ
ይስ ፡ ፍዬልን ፡ ወይስ ፡ ርግብን ፡ ያቀረበ ፡ ለመሥዋዕት ፡ እ
ጁን ፡ አኖረው ፡ በምሥዋዕቱ ፡ ራስ ፡ ላይ ፡ ኃጢአቱም ፡ እስ
ታወቀ ፡ ቦርዮትንም ፡ ለመነ ፡፡ ይህነንም ፡ አድርጎ ፡ ካህን ፡
ያነን ፡ ምሥዋዕት ፡ አረደ ፡ በመሠውያ ፡ ላይ ፡ አነደደው

ም ፡፡ በያመትም ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ ታላቅ ፡ ባል ፡ ሆኖ ፡ "የማስ ታረቅ ፡ ቀን ፡" የተባለ ፡ የካህናት ፡ አለቃ ፡ ምሥዋዕት ፡ ከ ሠዋ ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ ሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ኀጢአት ፡ ስለ ፡ ራሱም ፡ ኀጢአት ፡ ከምሥዋዕት ፡ ደም ፡ ወስደ ፡ ወደ ፡ ቅዱሳን ፡ ቅ ዱስ ፡ ገባ ፡ ከዚያም ፡ በተቀደሰ ፡ ዕጣን ፡ ጢስ ፡ መላ ፡ በእ ግዚአብሔር ፡ ፊት ፡፡ እርሱም ፡ የምሥዋዕትን ፡ ደም ፡ በ ጸቱ ፡ ወስደ ፡ ፯ ፡ ጊዜ ፡ ረጨው ፡ ወደ ፡ ጸጋ ፡ ዙፋን ፡ ፊት ፡፡ እንደሁም ፡ እግዚአብሔርን ፡ አስታረቀ ፡፡ የዚህ ፡ ሁሉ ፡ ታ ሪክ ፡ ይገኛል ፡ በኦሪት ፡ ዛሌዋውያን ፡ ትምህርቱንም ፡ የጳ ውሎስ ፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ ዕብራውያን ፡ ይናገራል ፡፡ ሁሉ ፡ ምሳሌ ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ መንግሥቱም ፡፡

የእግዚአብሔር ፡ መኖርያ ፡ ክርሰቶስ ፡ ነውና ፡፡ ጳውሎ ስ ፡ ክርስቶስን ፡ የጸጋ ፡ ዙፋን ፡ ይለዋል ፡፡ ክርስቶስ ፡ በ ሰውነቱ ፡ በታቦት ፡ ተመሰለ ፡ በላየው ፡ እግዚአብሔር ፡ አድርዋልና ፡ ይህ ፡ መለኮቱ ፡ ነው ፡፡ የቅዱሳን ፡ ቅድስት ፡ የሰማይ ፡ ምሳሌ ፡ ነበር ፡ ጳውሎስ ፡ እንደ ፡ ል ፡፡ ዕብራው ያን ፡ ፱ ፡ ፳፬ ፡፡ መኻከለኛ ፡ ቦታ ፡ እንደ ፡ ያው ፡ መቅደስ ፡ የ ተባለ ፡ የምእምናን ፡ ጉባኤ ፡ የውነተኛ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ ያን ፡ ምሳሌ ፡ ነበረ ፡፡ እርሳቸው ፡ በመጋረጃ ፡ በኀጢአት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተለዩ ፡ ሰውም ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ እግዚአብ ሔር ፡ መድረስ ፡ አልተቻለውም ፡፡ ደሮ ፡ በኦሪት ፡ በያመት ፡ የካህናት ፡ አለቃ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ ጢስና ፡ ደም ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ኀጢአቱን ፡ የሕዝብንም ፡ ኀጢአት ፡ ለመሻር ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ለማስታረቅ ፡ እን ደሁ ፡ ክርስቶስ ፡ ደግሞ ፡ እውነተኛ ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ሆነ ፡ በመልከ ፡ ጼዴቅ ፡ ሥርዓት ፡ እንጂ ፡ ማለቱ ፡ ክህነቱ ፡ ለዘ ላለም ፡ የሚኖር ፡፡ እርሱም ፡ ለክህነቱ ፡ ተቀባ ፡ በመንፈ ስ ፡ ቅዱስ ፡ ያ ፡ በተቀደሰ ፡ ቅቤ ፡ እንደ ፡ ተቀባ ፡፡ እርሱም ፡ የብዙ ፡ ወንድማማች ፡ ብክር ፡ ሆነ ፡ በሰውነቱ ፡ ያ ፡ ከሐሮ ን ፡ ከብክር ፡ ልጁ ፡ ከኤልዓዛር ፡ እንደ ፡ ተወለደ ፡፡ ያም ፡ አ ንድ ፡ ጊዜ ፡ በያመት ፡ ምሥዋዕትን ፡ አቀረበ ፡ ለእግዚአብሔ ር ፡፡ ክርስቶስ ፡ ራሱን ፡ ምሥዋዕት ፡ አድርጎ ፡ ስለኛ ፡ አን ድ ፡ ጊዜ ፡ ሠዋው ፡ ባንድ ፡ ምሥዋዕትም ፡ ለዘላለም ፡ ፈጸ

ማቸው ፡ በርሱ ፡ የተቀደሱትን ፡ ሁሉ ፡፡ ደር ፡ ያች ፡ ሕግ ፡ አልተፈጸመችም ፡፡ ያም ፡ አለቃ ፡ ኀጢአተኛ ፡ ሲሆን ፡ ስለ ርሱ ፡ ኀጢአት ፡ ምሥዋዕት ፡ አደረገ ፡፡ ብዙ ፡ ጊዜም ፡ ምሥዋዕትና ፡ መግባት ፡ ይሻ ፡ ነበረ ፡፡ ክርስቶስ ፡ ግን ፡ ፈጹም ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ሁኖ ፡ ያለ ፡ ኀጢአትም ፡ ስለ ፡ ነፍሱ ፡ ምሥዋዕት ፡ አልፈለገም ፡፡ የርሱም ፡ ምሥዋዕት ፡ ስለኛ ፡ ፈጹም ፡ ሁንዋልና ፡ መድገም ፡ አልሻውም ፡ ለዘላለም ፡ በቃ ፡ እንጂ ፡፡ እርሱም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሲገባ ፡ ምሥዋዕቱንም ፡ ሲያቅርብ ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በሰው ፡ መኻከል ፡ የነበረ ፡ መጋረጀ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የለየነ ፡ ኀጢአታችን ፡ ተሻረ ፡፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኀጢአታችነን ፡ በተሸከመ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጁን ፡ ኀጢአት ፡ ሁኖ ፡ ቈጠረው ፡ እርሱም ፡ ተሰቅሎ ፡ ሲሞት ፡ በኛና ፡ በእግዚአብሔር ፡ መኻከል ፡ የነበረ ፡ መጋረጀ ፡ ተቀደደ ፡ ያ ፡ በመቅደስ ፡ የነበረ ፡ መጋረጀ ፡ እንደ ፡ ተቀደደ ፡፡ ዕብራውያን ፡ ፲፤ ፳፡፡ ፪፤ ቆርንቶስ ፡ ፭፤ ፳፩፡፡ የሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ አሁን ፡ ባንደ ፡ ፈጽምት ፡ ምሥዋዕቱ ፡ ያነን ፡ ታላቅ ፡ ክብርን ፡ አገኘልነ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ካህናት ፡ እንድንሆን ፡ ብናምን ፡ ብቻ ፡፡ እንደዚህ ፡ ይላልና ፡ በዮሐንስ ፡ ራእይ ፡፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ካህናትን ፡ ነገሥታትንም ፡ ያደረገነ ፡ ላባቱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡፡ ም ፡ ፩፤ ቍ ፡ ፯፡፡ ጴጥሮስም ፡ ይላል ፡፡ እላንተ ፡ የሕይወት ፡ ደንጎች ፡ ሁናችሁ ፡ የተቀደሳችሁም ፡ ካህናት ፡ ታቅርቡ ፡ ዘንድ ፡ መንፈሳዊት ፡ ምሥዋዕት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የተቀበለች ፡ በየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡፡

የድንኳኑም ፡ ሶስተኛ ፡ ክፍል ፡ የለዚያ ፡ ምሳሌ ፡ ነው ፡ በክርስቶስ ፡ የተጠመቁ ፡ የሃይምኖትንም ፡ ነገር ፡ የሚያውቁ ፡ ከለልባቸው ፡ ግን ፡ አልተመለሱም ፡ ከኀጢአታቸው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡፡ በስም ፡ ብቻ ፡ ክርስቲያን ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ወደ ፡ መቅደስም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ አይገቡም ፡፡ ደር ፡ በወንጌል ፡ ቢማሩ ፡ የሚሰሙትንም ፡ ነገር ፡ በልባቸው ፡ ቢቀበሉት ፡ እርሳቸውም ፡ ወደ ፡ ክርስቶስ ፡ ክህነት ፡ ይደርሳሉ ፡፡

ሶስተኛ ፡ ሕግ ፡ ለእሥራኤል ፡ ሁሉ ፡ ተሰጠ ፡፡ በርሱም ፡

የቤትና ፡ ያገር ፡ ሥርዓት ፡ ተሰራ ፡፡ የርሱም ፡ ትእዛዛት ፡ ሁሉ ፡ ንጉሣቸው ፡ ለነበረ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ደረሱ ፡፡ ሁሉም ፡ ቅድስና ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ፈለገ ፡፡ ስለዚህም ፡ የእሥራኤል ፡ ሕዝብ ፡ ተለዮች ፡ ከሌሎች ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡፡ መለየታቸውም ፡ በግዝረታቸው ፡ በበዓላቸውም ፡ በልማዳቸውም ፡ በመግዛታቸውም ፡ በሃይማኖታቸውም ፡ ሆነ ፡፡ በመብልና ፡ በመጠጥ ፡ መለየት ፡ ነበረላቸው ፡ ንጹሕና ፡ ርኵስ ፡ ፍጥረት ፡ ሲጠብቁ ፡፡ ለዚህም ፡ ታላቅ ፡ መክንያት ፡ ነበረ ፡፡ የእሥራኤል ፡ ወገን ፡ ካልተለየ ፡ ከቀረት ፡ አሕዛብ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ባልጠቀመላቸው ፡፡ እርሳቸውም ፡ ቢደበለቁ ፡ ከቀረት ፡ አሕዛብ ፡ ጋራ ፡ የርሳቸውን ፡ ኃጢአትና ፡ ጨለማቸውን ፡ ቢቀበሉ ፡ ሃይማኖትም ፡ ሁሉ ፡ ቢጠፋ ፡፡ አንድ ፡ ትእዛዝም ፡ ይህ ፡ ነበር ፡ ብኵርነትን ፡ ሁሉን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይቀድሱ ፡ ዘንድ ፡፡ የሰውም ፡ ብኵርነት ፡ በየራሱ ፡ ተለውጦ ፡ የሌዊ ፡ ወገን ፡ በሌላ ፡ ብኵርነት ፡ ሁሉ ፡ ፈንታ ፡ ሆነ ፡፡ ይህ ፡ ምሥጢር ፡ ታላቅ ፡ ነው ፡ ትምርቱም ፡ ለአይምና ፡ ለክርስቶስ ፡ ይደርሳል ፡ ሁለታቸው ፡ በየሥርዓታቸው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ብኵራን ፡ የሆኑ ፡፡ ሮሜ ፡ ፫፡፡ ፩፡ ቆሮንቶስ ፡ ፲፫፡፡

እለዚህን ፡ ሕጋጋት ፡ እግዚአብሔር ፡ በሲና ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ለእሥኤል ፡ ሰጠ ፡ ከተስፋም ፡ ከቅያሜም ፡ ጋራ ፡ ተናገራቸው ፡፡ መታዘዝን ፡ ደህንነት ፡ ተከተለ ፡ ካለመታዘዝ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ መከራ ፡ መጣ ፡፡ የእሥራኤል ፡ ወገን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ተባረከች ፡ ሙሴ ፡ እንደለ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ ምስጉን ፡ ነህ ፡ እሥራኤል ፡ ሆይ ፡፡ ማን ፡ ይመስልሃል ፡፡ አንች ፡ ሕዝብ ፡ ሆይ ፡ በእግዚአብሔር ፡ የምትድኚ ፡፡ እርሱም ፡ የረዴትህ ፡ ጋሻ ፡ የድልህም ፡ ሰይፍ ፡ ነው ፡፡ ለጸላቶችህ ፡ በጅ ፡ አይልም ፡ አንተ ፡ ግን ፡ ባምባቸው ፡ ላይ ፡ ትረግጻለህ ፡፡ ኦሪት ፡ ዘዳግም ፡ ፴፫፡ ፳፱፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ የእሥራኤል ፡ ወገን ፡ የሰው ፡ ሁሉ ፡ ምሳሌ ፡ ሆኑ ፡፡ ኤርምያስ ፡ እንዲል ፡፡ የሰው ፡ ልብ ፡ ይደፍራል ፡ ተስፋም ፡ የሌለው ፡ ነው ፡፡ ማን ፡ ይችላል ፡ ያጥልቀው ፡ ዘንድ ፡፡ ም ፡ ፲፯፡ ቍ ፡ ፱፡፡ እንዲሁም ፡ ነበሩ ፡ የእሥራኤል ፡ ልጆች ፡ በሙ

ሴ ፡ ዘመን ፡፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ደፈረ ፡ ተስፋም ፡ አስደረጉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ለመከተል ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ታመኑ ፡፡ ደሮ ፡ ልባቸው ፡ ቃሊል ፡ ሁኖ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ ቶሎ ፡ ረሱ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ባለመታዘዝ ፡ አስቆጡ ፡፡ ፲፡ ትእዛዛት ፡ ከተቀበሉ ፡ በኋላ ፡ ሙሴ ፡ ገና ፡ በተራራ ፡ ላይ ፡ ሲሆን ፡ እርሳቸው ፡ ሐሮንን ፡ አገዱ ፡ አንዲን ፡ የበሬን ፡ ምሳሌ ፡ በወርቅ ፡ ሊሰራላቸው ፡ የሚሰግዱለት ፡ በዓልም ፡ ያደረጉለት ፡፡ እግዚአብሔርም ፡ በዚህ ፡ ተቈጥቶ ፡ ሕዝብን ፡ ሁሉን ፡ ማጥፋት ፡ ፈለገ ፡፡ ሙሴ ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቍጣ ፡ በልመናው ፡ በጸሎቱም ፡ አስረጋ ፡ እንደህ ፡ ሲል ፡፡ አቤቱ ፡ ደቀር ፡ በላቸው ፡፡ ባይሆን ፡ ፈቅኝ ፡ እኔን ፡ ደግሞ ፡ ከሕይወትህ ፡ መጽሐፍ ፡፡ እግዚአብሔርም ፡ ደቀር ፡ አላቸው ፡፡ ደሮ ፡ ፳፫፡ ሰዎች ፡ ሞቱ ፡ ከሕዝብ ፡ ጣዖትን ፡ ያመለኩ ፡፡ እግዚአብሔርም ፡ መልአኩን ፡ ሰደደላቸው ፡ በፊታቸው ፡ የሔደ ፡ የመራቸውም ፡ ወደ ፡ ከናዐን ፡ አገር ፡፡ ይህነን ፡ መልአክ ፡ እግዚአብሔር ፡ የፊቴን ፡ መልአክ ፡ አለው ፡፡ የእግዚአብሔርም ፡ ስም ፡ የሚኖርበት ፡፡ ደግሞም ፡ እንደ ፡ ያው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ተባለ ፡፡ እርሱም ፡ ነው ፡ በመልክያስ ፡ በነቢይ ፡ ተስፋ ፡ ስለ ፡ ተደረገ ፡ እንደህ ፡ ሲል ፡፡ እነሆ ፡ እኔ ፡ መልአኬን ፡ እሰድልሁ ፡ በፊትህ ፡ መንገድህን ፡ የሚያሰናደልህ ፡፡ ተቸኩሎም ፡ ወደ ፡ መቅደሱ ፡ ይመጣል ፡ የምትፈልጉት ፡ እግዚአብሔር ፡ የምትሹትም ፡ የቃል ፡ ኪደንም ፡ መልአክ ፡፡ እርሱም ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፡ ሌላ ፡ የለም ፡፡ ኦሪት ፡ ዘጸአት ፡ ፴፪፡ ፴፬፡፡ ፴፫፡ ፲፬፡፡ ደሳደያስ ፡ ፷፫፡ ፱፡፡ መልክያስ ፡ ፫፡ ፩፡፡ ማርቆስ ፡ ፩፡ ፩፡፡

የእግዚአብሔርም ፡ ምህረት ፡ በእሥራኤል ፡ ወገን ፡ ታላቅ ፡ ሆነ ፡ በምድረ ፡ በደ ፡፡ ደሮ ፡ ኃጢአታቸው ፡ ደግሞ ፡ በዛ ፡፡ ስላለመታዘዛቸውም ፡ ፵፡ አመት ፡ ዞሩ ፡ በምድረ ፡ በደ ፡፡ ከምሥርም ፡ ከወጡ ፡ ሰዎች ፡ ማንም ፡ አልገባም ፡ ወደ ፡ ከናዐን ፡ አገር ፡ ከካሌብ ፡ ከዮፈኔ ፡ ልጅ ፡ ከዮሱዓም ፡ ከነዌ ፡ ልጅ ፡ በቀር ፡፡

ዮሱዓም ፡ ወሰዳቸው ፡ ወደ ፡ ከናዐን ፡፡ እግዚአብሔር

ም ፡ ጸላቶቻቸውን ፡ በጃቸው ፡ ሰጣቸው ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ የእሥራኤል ፡ ልጆች ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ አልፈጸሙም ፡ ወደጅነት ፡ አደረጉ ፡ እንጅ ፡ ከጸላቶቻቸው ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ ጸላቶች ፡ ከከናዐን ፡ አሕዛብ ፡ ጋራ ፡፡ ስለ ዚህም ፡ አላሸነፏቸውም ፡፡ ካሕዛብም ፡ ጋራ ፡ በጥቂት ፡ በጥቂት ፡ ተደባለቁ ፡ የርሳቸውንም ፡ ልማድ ፡ ለመዱ ፡ የርሳቸውንም ፡ ጣዖታት ፡ አመለኩ ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ነገር ፡ ረሱ ፡፡ ስለዚህም ፡ እግዚአብሔር ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፡ በጸላቶቻቸው ፡ እጅ ፡ ላሞራውያን ፡ ለሚድያናውያንም ፡ ላሞናውያንም ፡ ለፍልስጥኤማውያንም ፡ ለፊኒቃውያንም ፡ ደገዙ ፡ ዘንድ ፡፡ ከጸላቶቻቸውም ፡ እጅ ፡ መከራ ፡ በተቀበሉ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በተመለሱ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ረዳት ፡ ሰደደላቸው ፡፡ ያስጠልዋቸውንም ፡ ሰዎች ፡ አስነሣላቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ላባቶቻቸው ፡ የማለውን ፡ መሐላውን ፡ አልረሳምና ፡፡

ከዮሱዒም ፡ በኋላ ፡ በእሥራኤል ፡ ላይ ፡ የገዙ ፡ ካሕዛብም ፡ የረዳቸው ፡ መኳንንት ፡ እለዚህ ፡ ናቸው ፡፡ ኦትኒኤል ፡ ኤሁድም ፡ ሰምጋርም ፡ ባራቅም ፡ ድቦራም ፡ ጌዴዎንም ፡ አቢሜሌክም ፡ ቶላም ፡ ያዒርም ፡ ዬፍታም ፡ ሳምሶንም ፡ ኤሊም ፡ ሳሙኤልም ፡፡

ሳሙኤልም ፡ ነቢይ ፡ ነበረ ፡፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ነገር ፡ ከጨለማ ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ አወጣው ፡ በቅንም ፡ ፈረደ ፡ በእሥራኤል ፡ በጸሎቱም ፡ አዳናቸው ፡ ከፍልስጥኤማውያን ፡ እጅ ፡፡ ሳሙኤልም ፡ ባረጀ ፡ ጊዜ ፡ ልጆቹም ፡ በርሱ ፡ ፈንታ ፡ እሥራኤልን ፡ በገዙ ፡ በግፍም ፡ በፈረዱ ፡ ጊዜ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የእሥራኤል ፡ ሕዝብ ፡ ንጉሥን ፡ ፈለጉ ፡ ላሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ነገሥታት ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ ብለው ፡፡ እግዚአብሔርም ፡ መሻታቸውን ፡ ሰምቶ ፡ ንጉሥን ፡ ሰጣቸው ፡ እርሱም ፡ ሳውል ፡ የቂስን ፡ ልጅ ፡ ከብንያሚን ፡ ወገን ፡ ሳሙኤል ፡ ያነገሠው ፡ በእሥራኤል ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡፡

ሳውልም ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ተከተለ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ራሱን ፡ አከብሮ ፡ የራሱንም ፡ ፈቃድ ፡ ተከትሎ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ናቀ ፡፡ ስለዚ

ህም ፡ እግዚአብሔር ፡ ጣለው ፡ ከፊቱ ፡፡ በርሱም ፡ ስፍራ ፡ ዳዊትን ፡ መረጸ ፡ የደሳይ ፡ ልጅ ፡ ከቤተልሔም ፡ ከይሁዳ ፡ ወገን ፡፡ ጳውሎስ ፡ ይህነን ፡ ታሪክ ፡ እንደህ ፡ ብሎ ፡ ይነግራል ፡፡ ንጉሥ ፡ ለመኑ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ሰጣቸው ፡ ሳውልን ፡ የቂስን ፡ ልጅ ፡ ከብንያሚን ፡ ወገን ፡ የሚሆንን ፡ ሰው ፡ አርባ ፡ አመት ፡፡ ሻረውም ፡፡ ደግሞ ፡ ንጉሥን ፡ አስነሣላቸው ፡ ዳዊትን ፡ የመሰከረለትን ፡ ያለውንም ፡፡ አገኘሁ ፡ ዳዊትን ፡ የደሳይን ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ልቤ ፡ ያለውን ፡ ሰው ፡ ፈቃዴን ፡ ሁሉን ፡ የሚያድርግ ፡፡ ግብረ ፡ ሐዋርያት ፡ ፲፫፤ ፳፩፤ ፳፪፡፡ ይህ ፡ ሆነ ፡ በሳውል ፡ መንግሥት ፡ በ፴፪፤ አመት ፡ ዳዊት ፡ ያባቱን ፡ ከብት ፡ ሲጠብቅ ፡፡ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ዳዊት ፡ የፍልስጥኤማውያንን ፡ ኃያል ፡ ጎልያት ፡ የተባለውን ፡ ገደለ ፡ የዕብራውያንም ፡ ሴቶች ፡ ዘፍነው ፡ አሉ ፡፡ ሳውል ፡ ፲፻፤ ሰው ፡ ገደለ ፡ ዳዊት ፡ ግን ፡ ፻፻፤ ገደለ ፡፡ በሕዝቡም ፡ ፊት ፡ ከበረ ፡፡ ስለዚህም ፡ ሳውል ፡ ተቀናበት ፡ ሊገድለውም ፡ ፈለገ ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ዳዊትን ፡ አልሰጠም ፡ በሳውል ፡ እጅ ፡፡ ዳዊት ፡ ሸሸ ፡ ከሳውል ፡ ፊት ፡ እጁንም ፡ አላነሣም ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀብቶ ፡ ባነገሠው ፡ ላይ ፡፡ ደር ፡ ፵፤ አመት ፡ ዞረ ፡ በእሥራኤልም ፡ በፍልስጥኤማውያንም ፡ አገር ፡ በመከራ ፡ ሳውል ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡፡ ሳውል ፡ ግን ፡ በፍልስጥኤማውያን ፡ እጅ ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ የይሁዳ ፡ ወገን ፡ ሁሉ ፡ ያንድ ፡ ልብ ፡ ሁነው ፡ ወደ ፡ ዳዊት ፡ መጡ ፡ አነገሡትም ፡ በኬብሮን ፡፡ ከዚያ ፡ ወዲያም ፡ ዳዊት ፡ የሩሳሌምን ፡ ወሰደ ፡ ከየቡሳውያን ፡ እጅ ፡ እርስዋንም ፡ ከተማውን ፡ አደረጋት ፡ ለመንግሥቱ ፡፡

ዳዊት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ወደደ ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ፈቃድ ፡ ተከተለ ፡ የእግዚአብሔርም ፡ ጸላቶች ፡ ጸላቶቹ ፡ ሁነው ፡ ቊጠራቸው ፡፡ ስለዚህ ፡ አዘመተ ፡ በከናዐን ፡ አገር ፡ በዙርያዋም ፡ በነበረ ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡፡ እግዚአብሔርም ፡ በጁ ፡ ሰጣቸው ፡፡ የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ አደረበት ፡ ልቡንም ፡ አጸና ፡ ለበጎ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡፡ በርሱ ፡ ነው ፡ ሥርዓትን ፡ ያደረገ ፡ ለቤተ ፡ መቅደስ ፡ ለካህናትም ፡ ለሌዋውያንም ፡ ላዝማሮችም ፡፡ የእግዚአብሔርም ፡ መ

ንፈስ ፡ በልቡ ፡ ሰጠው ፡ መዝሙራትን ፡ ሊያድርግ ፡ በመቅደስ ፡ ለመዘመር ፡ በጊዜ ፡ ሁሉ ፡ ለእግዚአብሔር ። ዳዊትም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤትን ፡ ሊሰራ ፡ ፈለገ ፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ከለከለው ፡ ተስፋ ፡ ሲያስደርግለት ፡ ልጁ ፡ ቤትን ፡ እንዲሰራ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከወገኑም ፡ ያ ፡ እንዲመጣ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ የሰውም ፡ ሁሉ ፡ መድኀኒት ፡ የሚሆን ፡ የመንግሥቱም ፡ ዙፋን ፡ ለዘላለም ፡ የሚኖር ። ፪ ፡ ሳሙኤል ፡ ፯ ፡ ቍ ፡ ፲፪ ፲፫ ፲፬ ።

ዳሮ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ንጹሕ ፡ የሚሆን ፡ ሰው ፡ የለም ። ሁላቸው ፡ ኃጢአተኞች ፡ ናቸው ፡ ሁላቸውም ፡ በደለኞች ፡ አንድ ፡ ሳይቀር ። ዳዊትመ ፡ ይህን ፡ ዐውቆ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ኃጢአቱን ፡ ሁልጊዜ ፡ አስታወቀ ፡ ከመዝሙራቱ ፡ እንደ ገለጸ ። እርሱም ፡ ለራሱ ፡ በታላቅ ፡ ኃጢአት ፡ ወደቀ ፡ የኡርያስን ፡ ምሽት ፡ ባትሴባን ፡ ባሳታት ፡ ጊዜ ፡ ባልዋንም ፡ ባስገደለ ፡ ጊዜ ። እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ በኃጢአቱ ፡ እንዲኖር ፡ እንዲጠፋም ፡ አልተወውም ። ስለዚህም ፡ ልቡን ፡ መለሰ ፡ በውነት ፡ ንስሓ ፡ ወደ ፡ መግባት ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ መዝሙር ፡ ፶፩ ፡ አደረገ ። ዳዊት ፡ ምሳሌ ፡ ሆነ ፡ ለምእምናን ፡ ሁሉ ። እርሱም ፡ እንደ ፡ ሁላችን ፡ ኃጢአተኛ ፡ ሁኖ ፡ እኛ ፡ ሁላችን ፡ ከኃጢአታችን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልንመለስ ፡ እርሱ ፡ እንደ ፡ ተመለሰ ። በእግዚአብሔርም ፡ ልናምን ፡ ልንታመነውም ፡ እርሱም ፡ እንደመነ ፡ እንደ ፡ ታመነም ። እግዚአብሔርንም ፡ በፍጹም ፡ ልባችን ፡ ልንወድ ፡ ዳዊት ፡ እንደ ፡ ወደደ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አምላኩን ።

ዳዊትም ፡ እጅግ ፡ መከራ ፡ አገኘ ፡ በቤቱ ፡ በዘመዱም ። አንድ ፡ ከልጆቹ ፡ ስሙም ፡ አምኖን ፡ ትእማርን ፡ እቱን ፡ አስነወራት ። ስለዚህ ፡ ሁለተኛ ፡ ልጁ ፡ አቤሴሎም ፡ አምኖንን ፡ ወንድሙን ፡ ገደለ ። አቤሴሎምም ፡ በኋላ ፡ ዐመፀ ፡ ጾርም ፡ አደረገ ፡ ባባቱ ፡ በዳዊት ፡ ላይ ። በዚህም ፡ ጾር ፡ ዳዊት ፡ ለልጁ ፡ ሊያዝን ፡ ፈለገ ፡ ዳሮ ፡ ዮአብ ፡ የጭፍራው ፡ ሁሉ ፡ አለቃ ፡ የቱም ፡ ልጅ ፡ አቤሴሎምን ፡ በዛፍ ፡ ጫፍ ፡ ተሰቅሎ ፡ አይቶት ፡ ገደለው ። ዳዊትስ ፡ በዚህ ፡ ወደ ፡ መንግሥቱ ፡ ተመለሰ ፡ ዳሮ ፡ ለልጁ ፡ እጅግ ፡ ብርቱ ፡ አ

ዘን ፡ አዘነ ፡፡ ፵፤ አመትም ፡ ከነገሠ ፡ በኋላ ፡ መንግሥቱ
ን ፡ ለልጁ ፡ ለሰሎሞን ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠው ፡ እርሱም ፡ በረ
ፋት ፡ ወደባቶቹ ፡ ተሰብስቦ ፡ ሞተ ፡፡

ሳ ሎ ሞ ን ም ፡ በመንግሥቱ ፡ መጀመርያ ፡ እግዚአብሔ
ር ፡ ታየለት ፡ እንደዚህም ፡ ሲል ፡ ጠየቀው ፡፡ ምንድር ፡ ትፈ
ልጋለህ ፡ ከኔ ፡ ልሰጥህ ፡፡ ባለጠግነትን ፡ ብትወድ ፡ ረጅም ፡
ዕድሜንም ፡ እሰጥሃለሁ ፡፡ ወይስ ፡ ጥበብን ፡ ብልህ ፡ ልብ
ንም ፡ ብትወድ ፡ እሰጥሃለሁ ፡፡ ሳሎሞንም ፡ እንዲህ ፡ ብ
ሎ ፡ መለሰ ፡፡ አንተ ፡ ላባቴ ፡ ለደዊት ፡ ለባርያህ ፡ ታላቅ ፡
ምህረትን ፡ አደረግህ ፡፡ እርሱ ፡ በፊትህ ፡ ተመላልሶ ፡ በው
ነትና ፡ በጽድቅ ፡ በቅን ፡ ልቡም ፡ ቸርነትህንም ፡ ጠበቅህለ
ት ፡ ልጅንመ ፡ ሰጠህው ፡ በዙፋኑ ፡ ላይ ፡ ይቀመጥ ፡ ዘንድ ፡
አሁን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡፡ አሁንም ፡ አቤቱ ፡ አምላኬ ፡ ሆይ ፡ ባ
ርያህን ፡ አነገሥህ ፡ ባባቴ ፡ በደዊት ፡ ስፍራ ፡፡ እኔም ፡ ታና
ሽ ፡ ዐሽክር ፡ ነኝ ፡ መውጣቴንም ፡ መግባቴንም ፡ የማለ
ውቅ ፡፡ ባርያህም ፡ አንተ ፡ በመረጽህው ፡ በታላቅ ፡ ሕዝብ ፡
መኻከል ፡ ነው ፡ ቊጥር ፡ የሌለው ፡ ስለ ፡ ብዛቱ ፡፡ ስለዚህ
ም ፡ ለባርያህ ፡ የሚታዘዘውን ፡ ልብ ፡ ስጠው ፡ በሕዝብህ ፡
ይፈርድ ፡ ዘንድ ፡ በጎንና ፡ ክፉን ፡ ነገር ፡ ሁሉን ፡ ያስታውል ፡
ዘንድ ፡፡ ማን ፡ ይችላልና ፡ በዚህ ፡ ታላቅ ፡ ሕዝብ ፡ ይፈር
ድ ፡ ዘንድ ፡፡ ይህ ፡ የሳሎሞን ፡ ጸሎት ፡ እግዚአብሔርን ፡
እጅግ ፡ ደስ ፡ አሳየው ፡፡ እግዚአብሔርም ፡ አለው ፡፡ ይህነ
ን ፡ ነገር ፡ ለምንኻልና ፡ ረጅም ፡ ዕድሜንም ፡ ባለጠግነትን
ም ፡ የጸላቶችህንም ፡ ነፍስ ፡ አለመንህምና ፡ አእምሮን ፡
እንጅ ፡ ለመፍረድ ፡፡ ስለዚህ ፡ እነሆ ፡ እንደ ፡ መንገርህ ፡
አደረግሁ ፡፡ እነሆ ፡ ጠቢብንና ፡ ብልህን ፡ ልብ ፡ ሰጠሁህ ፡፡
አንተንም ፡ የሚመስል ፡ በቀድም ፡ አልነበረም ፡ ካንተም ፡
በኋላ ፡ አይነሣም ፡፡ ደግሞ ፡ ያለመንህውን ፡ ነገር ፡ ሰጠሁ
ህ ፡ እርሱም ፡ ባለጠግነትና ፡ ክብር ፡፡ እንደንተ ፡ የሚሆን ፡
አይገኝም ፡ በነገሥታት ፡ መኻከል ፡ በዘመንህ ፡፡ በመንገ
ዴም ፡ በትመላለስ ፡ ሕጋጋቴንና ፡ ትእዛዛቴንም ፡ ብትጠብ
ቅ ፡ አባትህ ፡ ደዊት ፡ እንደ ፡ ተመላለሰ ፡ ሕይወትህንም ፡
እስረዝማታለሁ ፡፡ ፩፤ መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ፫፡፡

እግዚአብሔርም ፡ የሳሎሞንን ፡ ልመና ፡ ሰምቶ ፡ ተስፋውን ፡ ጠበቀለት ፡፡ ጥበብና ፡ ብልሃት ፡ ሰጠው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ይሰራ ፡ ዘንድ ፡ በየሩሳሌም ፡፡ ያችም ፡ በተፈጸመች ፡ ጊዜ ፡ ቀደሳት ፡፡ እግዚአብሔርም ፡ ታየ ፡ ለርሱ ፡ ለሕዝብም ፡ሁሉ ፡ በምስጋናው ፡፡ ምስጋናውም ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ መላ ፡፡ የሳሎሞንም ፡ ወሬ ፡ ወደ ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ደረሰ ፡ ካገር ፡ ሁሉም ፡ እጅ ፡ መንሽ ፡ ሰደዱለት ፡፡ ንግሥት ፡ አዜብም ፡ ወሬውን ፡ በሰማች ፡ ጊዜ ፡ ከሩቅ ፡ መጣች ፡ ትየው ፡ ዘንድ ፡ ጥበቡንም ፡ ትሰማ ፡ ዘንድ ፡፡ ደሩ ፡ የሰሎሞን ፡ ልብ ፡ አልጸናም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ያባቱ ፡ የደዊት ፡ ልብ ፡ እንደ ፡ ጸና ፡፡ ስለዚህም ፡ ወደጅነት ፡ አደረገ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከጸላቸው ፡ ጣዖታትንም ፡ ካመለኩ ፡ አሕዛብ ፡ ጋራ ፡ ከርሳቸውም ፡ ሴቶችን ፡ ምሽቶቹን ፡ አድርግዋቸው ፡ አጋባ ፡፡ የምሽቶቹም ፡ ቍጥር ፡ ፯፻፤ የቁባቶቹም ፡ ቍጥር ፡ ፫፻፤ ነበር ፡፡ ምሽቶቹም ፡ ልቡን ፡ አሳቱ ፡ ሊመለስ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፍርሃት ፡ ጣዖታትንም ፡ ለማምለክ ፡፡ ለጣዖታትም ፡ መስጊደች ፡ አሰራ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ከርሱ ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ተቀበለ ፡ ቸርነቱ ፡ አላመሰገነም ፡ አስቈጣው ፡ እንጂ ፡፡ ስለዚህም ፡ እግዚአብሔር ፡ ተቃየመው ፡ በነቢይ ፡ በአሂያ ፡ አፍ ፡ የእሥራኤል ፡ ፲፤ ወገን ፡ እንደ ፡ ያምፁ ፡ ይሁደና ፡ ብንያሚን ፡ ብቻ ፡ እንዲቀሩ ፡ ለልጁ ፡ ለሮብዓም ፡፡ እንዲሁም ፡ ሆነ ፡፡

ሰሎሞን ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ እሥራኤል ፡ ሁሉ ፡ ተሰበሰቡ ፡ ልጁን ፡ ሮብዓምን ፡ ያነግሡት ፡ ዘንድ ፡፡ የእሥራኤልም ፡ ፲፤ ወገኖች ፡ የዮርብዓም ፡ የኔባጥ ፡ ልጅን ፡ ምክር ፡ ሰምተው ፡ ለመኑት ፡ ግብራቸውን ፡ አባቱ ፡ ሳሎሞን ፡ ያደረገባቸውን ፡ ያስቀልላቸው ፡ ዘንድ ፡፡ ሮብዓምም ፡ የጠቢባንን ፡ የሽማግሎቹን ፡ ምክር ፡ ከሰማ ፡ የሕዝብን ፡ ልመና ፡ ቢፈጽም ፡ ነበረ ፡፡ ደሮ ፡ የሰነፎችን ፡ መካሮች ፡ ምክር ፡ ሰምቶ ፡ የሕዝቡን ፡ ግብር ፡ በማቅለል ፡ ፈንታ ፡ ሊያስከብድባቸው ፡ ተቃየማቸው ፡፡ በዚህም ፡ ተቈጥተው ፡ ፲፤ ወገን ፡ ዐመፁ ፡ ዮርብዓምንም ፡ ለንጉሣቸው ፡ መረጹት ፡ ተከተሉትም ፡፡

አሁንም ፡ የእሥራኤል ፡ መንግሥት ፡ በ፪፡ ክፍል ፡ ተከ
ፈለች ፡፡ አንድ ፡ ክፍል ፡ ይሁዳና ፡ ብንያሚን ፡ ከሌዊያውያ
ን ፡ ጋራ ፡ የነበረ ፡ የይሁደ ፡ መንግሥት ፡ ተባሉ ፡፡ ሁለተ
ኛም ፡ ክፍል ፡ እርሱም ፡ የቀረ ፡ ፲፡ ወገኖች ፡ የእሥራኤ
ል ፡ መንግሥት ፡ ተባለች ፡፡ በመኻከላቸውም ፡ ከሮብዓ
ም ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ መጨረሻቸው ፡ ድረስ ፡ ሁልጊዜ ፡ ጸላ
ትነት ፡ ነበረ ፡፡ በሁለታቸውም ፡ ሃይማኖት ፡ አነሰ ፡፡

ዮርብዓምም ፡ ለእሥራኤል ፡ ሕዝብ ፡ ፪፡ የወርቅ ፡ በሮ
ች ፡ አሰራላቸው ፡ ያመልኩዋቸው ፡ ዘንድ ፡፡ እርሱ ፡ ሕዝ
ቡ ፡ ሁልጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማምለክ ፡ ወደ ፡ የሩሳሌ
ም ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ እንደይሔዱ ፡ ከርሱም ፡ እንደ
ያመፁ ፡ ከይሁደ ፡ መንግሥትም ፡ ጋራ ፡ እንደይታረቁ ፡ ፈር
ትዋልና ፡፡ በዚህ ፡ ነገርም ፡ የእሥራኤልን ፡ መንግሥት ፡ ሁ
ሉ ፡ አሳተ ፡፡ ከእግዚአብሔርም ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ጣዖታት ፡
መለሳቸው ፡፡ ስለዚህም ፡ እግዚአብሔር ፡ ለቤቱ ፡ መንግሥ
ት ፡ መኖርያ ፡ አልሰጠም ፡፡ የዮሮብዓም ፡ ልጅ ፡ ናደብ ፡ የ
ተባለ ፡ ፪፡ አመት ፡ ብቻ ፡ ከነገሠ ፡ በኋላ ፡ በዓሣ ፡ የአሒያ ፡
ልጅ ፡ ከይሳኮር ፡ ወገን ፡ ሸፈጥን ፡ አደረገበት ፡ ገደለውም ፡
የዮርብዓምንም ፡ ዘመድ ፡ ሁሉን ፡ ገደለ ፡ አንድ ፡ ሳይቀር ፡፡
እርሱም ፡ ነገሠ ፡ ፳፬፡ አመት ፡፡ ኃጢአቱንም ፡ አብዝትዋ
ልና ፡ የእሥራኤል ፡ ምንግሥት ፡ በዘመዱ ፡ ደግሞ ፡ አልኖ
ረም ፡፡ ልጁም ፡ ኤላ ፡ ፪፡ አመት ፡ ከነገሠ ፡ በኋላ ፡ በሎሌ
ው ፡ በዘምሪ ፡ እጅ ፡ ተገድልዋል ፡፡ ዘምሪም ፡ በነገሠ ፡
ጊዜ ፡ የበዓሣን ፡ ዘመድ ፡ ሁሉን ፡ አጠፈ ፡፡ እርሱ ፡ ግን ፡ የ
ሸፈጡን ፡ ደመወዜ ፡ ቶሎ ፡ ተቀበለ ፡፡ ወታደሮች ፡ ሌላው
ን ፡ ንጉሥ ፡ መርጸዋልና ፡ እርሱም ፡ የሠራዊት ፡ አለቃ ፡ ስ
ሙም ፡ ዖምሪ ፡፡ ዘምሪም ፡ ነፍሱን ፡ አቃጠለ ፡ በሳት ፡፡ ዖ
ምሪም ፡ ከተቀደሙት ፡ ነገሥታት ፡ ከፋ ፡ ጣዖታትን ፡ በማ
ምለክ ፡ በቤላ ፡ ኃጢአትም ፡፡ እርሱም ፡ ሣምሪን ፡ ከተማ
ውን ፡ ሰራ ፡ ፲፪፡ አመትም ፡ ከነገሠ ፡ በኋላ ፡ ሞተ ፡፡ ልጁ
ም ፡ አሐብ ፡ ንጉሥ ፡ ሆነ ፡ በስፍራው ፡፡

አሐብም ፡ ከሁሉ ፡ ከፋ ፡፡ በዮርብዓምም ፡ ጣዖት ፡ በ
በሬ ፡ ፈንታ ፡ እርሱ ፡ ብዔልን ፡ የሲደና ፡ ጣዖት ፡ ላምላኩ ፡

ለእሥራኤልም ፡ አምላክ ፡ መረጸ ፡ አመለከውም ፡፡ በዘ
መኑም ፡ ኤልያስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነቢይ ፡ ተነሣ ፡ በእ
ግዚአብሔርም ፡ ኃይል ፡ በጣዖታት ፡ ማምለክ ፡ ላይ ፡ ቀወ
መ ፡፡ የአሐብ ፡ ምሽት ፡ ኢዛቤል ፡ ነበረች ፡ የሲደና ፡ ንጉ
ሥ ፡ ልጅ ፡፡ እርስዋም ፡ ባልዋን ፡ አሳተች ፡ ለኃጢአት ፡ ሁ
ሉ ፡፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ነቢያት ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ በእ
ሥራኤል ፡ የነበረትን ፡ ገደለች ፡፡ የንጉሥ ፡ ሎሌ ፡ ዖብድ
ዩ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የፈሪ ፡ ፻፤ ከእግዚአብሔር ፡ ነቢያት ፡
ሰውሮ ፡ በዋሾች ፡ ሸሸጋቸው ፡ እንጅ ፡ የቀረት ፡ ሁሉ ፡
ሞቱ ፡፡

ኤልያስም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ ሰማይን ፡ ዘጋ ፡ ፫፤
አመትና ፡ ፮፤ ወር ፡ እንደይዘንም ፡ ለመቅሠፍት ፡ ስለ ፡ ሕ
ዝብና ፡ ስለ ፡ ንጉሥ ፡ ኃጢአት ፡፡ አሁንም ፡ በኤልያስ ፡ ቃ
ል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኃይልም ፡ ዝናም ፡ ባለቀ ፡ ጊዜ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ መገበው ፡፡ በልጀቹ ፡ እንኳ ፡ ብርቱ ፡ ያለ ፡ ቍ
ራ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ በጽዋትና ፡
በማታ ፡ እንጀራና ፡ ሥጋ ፡ አመጣለት ፡፡ ወንዝም ፡ አልደረ
ቀም ፡ አንድ ፡ አመት ፡ የሚያህል ፡፡ ይዚያን ፡ ጊዜም ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ሰራጵታ ፡ በሲደና ፡ አጠገብ ፡ ወደለች ፡
ሰደደው ፡ ወደ ፡ ባልቴቲቱ ፡፡ ወደ ፡ ቤትዋ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡
እርስዋ ፡ ጥቂት ፡ እንጨት ፡ በሜደ ፡ ለቀመች ፡፡ ኤልያስ
ም ፡ ውኃና ፡ እንጀራ ፡ ፈለገ ፡፡ እርስዋም ፡ ውኃውን ፡ ስታ
መጣለት ፡ አለቸው ፡፡ ጥቂት ፡ ደቄት ፡ በቃ ፡ ጥቂት ፡ ቅቤ
ም ፡ በተርሙዝ ፡ ብቻ ፡ ቀረልኝ ፡፡ ጥቂት ፡ እንጨትም ፡ ለ
ቀምሁ ፡ ላሰናድውልን ፡ ለኔ ፡ ለልጀም ፡ በልተን ፡ እንሞት ፡
ዘንድ ፡፡ ኤልያስ ፡ ግን ፡ አላት ፡፡ በእግዚአብሔር ፡ ባምላክ
ሽ ፡ ሕይወት ፡፡ አትፍሪ ፡ ሒድሽ ፡ እንደልሁሽ ፡ አድርጊ ፡ እ
ንጅ ፡፡ ለኔ ፡ በፊት ፡ ጥቂት ፡ አጋገሪ ፡ በኋላም ፡ ላንችና ፡ ለ
ልጅሽ ፡፡ እንደዪህ ፡ ይላልና ፡ እግዚአብሔር ፡ የእሥራኤል ፡
አምላክ ፡፡ በቃ ፡ ያለ ፡ ደቄት ፡ አያልቅም ፡ ቅቤም ፡ በተር
ሙዝ ፡ አይጐድልም ፡ እግዚአብሔር ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ እስ
ኪያዘንም ፡ ድረስ ፡፡ እርስዋም ፡ እንደዪህ ፡ አደረገች ፡፡ ኤል
ያስም ፡ እንደላት ፡ ሆነላት ፡፡ ልጅዋም ፡ በኋላ ፡ በሞት ፡ ጊ

ዜ ፡ ኤልያስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ አስነሣው ፡፡ ከዚ
ያ ፡ ወዲያም ፡ ኤልያስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ወደ ፡
አሐብ ፡ ሔደ ፡ አሐብንም ፡ አዘዘ ፡ የእሥራኤልን ፡ ሕዝብ ፡
ሁሉ ፡ በቀርሜሎስ ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ ያከማቻቸው ፡ ዘንድ ፡፡
ከዚያ ፡ ሊገለጽ ፡ ነበረና ፡ እውነተኛ ፡ አምላክ ፡ ማነው ፡ ወ
ይስ ፡ ብዔል ፡ ወይስ ፡ እግዚአብሔር ፡፡ አሐብም ፡ እንደ ፡
ኤልያስ ፡ ፈቃድ ፡ አደረገ ፡፡ የእሥራኤልም ፡ ወገን ፡ ሁሉ ፡
በቀርሜሎስ ፡ ላይ ፡ ተከማቹ ፡ ከ፬፻፶፡ ከብዔል ፡ ካህናት ፡
ከ፬፻ም ፡ ካስተርቴ ፡ ካህናት ፡ ጋራ ፡፡ ሁላቸውም ፡ ባንድ ፡
በተሰበሰቡ ፡ ጊዜ ፡ ኤልያስ ፡ ሕዝብን ፡ ሁሉን ፡ ተናገረ ፡ እ
ንደዚህ ፡ ሲል ፡፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ድረስ ፡ ትዘነብላላችሁ ፡ ወደ ፡
ሁለት ፡ ወገን ፡፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ቢሆን ፡ እርሱ
ን ፡ ተከተሉት ፡፡ ብዔል ፡ ግን ፡ አምላክ ፡ ቢሆን ፡ እርሱን ፡
ተከተሉት ፡፡ ሁላቸውም ፡ ዝም ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ ኤልያስ ፡ እ
ንደዚህ ፡ ሲል ፡ ጨመረ ፡፡ እኔ ፡ ለብቻዬ ፡ ቀረሁ ፡ የእግዚአብ
ሔር ፡ ነቢይ ፡ ሁኜ ፡፡ የብዔል ፡ ነቢያት ፡ ግን ፡ ፬፻፶፡ ነፍስ ፡ና
ቸው ፡፡ አሁንም ፡ ፪፡ በሮች ፡ ስጡን ፡፡ እርሳቸውም ፡ አንድ ፡
በሬን ፡ ይምረጹ ፡ ይክፈሉትም ፡ በንጨት ፡ ላይም ፡ ያኑሩ
ት ፡ እሳትን ፡ ሳያድርጉበት ፡፡ እኔም ፡ ሁለተኛውን ፡ በሬን ፡
ይዤ ፡ በንጨት ፡ ላይ ፡ አኖረዋለሁ ፡ እሳትንም ፡ አልጨም
ርለትም ፡፡ እላንትም ፡ ያምላካችሁን ፡ ስም ፡ ጽሩ ፡ እኔም ፡
የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ እጸራለሁ ፡፡ ሰምቶም ፡ በሳት ፡
የሚመልስ ፡ አምላክ ፡ እርሱ ፡ አምላክ ፡ ይሁን ፡፡ ሕዝብ
ም ፡ ሁሉ ፡ "እንደዚህ ፡ መልካም ፡ ነው ፡" አሉ ፡፡ ኤልያስ
ም ፡ የብዔልን ፡ ነቢያት ፡ አላቸው ፡፡ እላንት ፡ በርያችሁን ፡
በፊት ፡ ምረጹ ፡ ያምላካችሁንም ፡ ስም ፡ ጽሩ ፡፡ እላንት ፡
ብዙ ፡ ናችሁና ፡፡ እርሳቸውም ፡ እንደዚህ ፡ አድርገው ፡ ባም
ላካቸው ፡ ስም ፡ ጸለዩው ፡ ከጥዋት ፡ ጀምረው ፡ እስከ ፡ ቀ
ትር ፡ ድረስ ፡ ደከሙ ፡፡ ብዔል ፡ ግን ፡ አልሰማም ፡፡ በቀትር
ም ፡ ጊዜ ፡ ኤልያስ ፡ ሲላገጽባቸው ፡ እንደዚህ ፡ አላቸው ፡፡ በ
ታላቅ ፡ ድምጽ ፡ ጽሩ ፡፡ ብዔል ፡ አምላክ ፡ ነውና ፡ ታላቅ ፡
ጌታም ፡ ብዙ ፡ ተግባር ፡ አለው ፡፡ ወይስ ፡ ቅኔ ፡ ያድርጋል ፡
ወይስ ፡ መናልባት ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ ወጣ ፡ ወይስ ፡ መናልባት ፡

ይተኛል ፡ ልታነቁት ፡፡ እርሱም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ እርሳቸ
ው ፡ በታላቅ ፡ ድምጽ ፡ ጮሁ ፡ ዘፈኑም ፡ በቀሪም ፡ በብረት
ም ፡ ሥጋቸውን ፡ ቍረጡ ፡ ደም ፡ የሰከፈስ ፡ ድረስ ፡፡ ደክ
መውም ፡ ትንቢትን ፡ አደረጉ ፡፡ ደር ፡ ግን ፡ ሁሉ ፡ በከንቱ ፡
ሆነ ፡ ድምጽም ፡ ወይስ ፡ ምላሽ ፡ ወይስ ፡ መሰመት ፡ አልተ
ገኘም ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ኤልያስ ፡ ሕዝብን ፡ ሁሉን ፡ እ
ንዲህ ፡ ሲል ፡ ተናገረ ፡፡ ኑ ፡ ሁላችሁ ፡ ወደኔ ፡፡ ሁላቸውም ፡
ሲቀርቡ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ የፈረሰውን ፡ መሠውያ ፡ አ
በጀ ፡፡ በዙርያውም ፡ እንደ ፡ ምድር ፡ ተልም ፡ መስኖ ፡ አስ
ቈፈረ ፡፡ እንጨትም ፡ ደረደረ ፡ በላየውም ፡ በሬውን ፡ ከፈ
ሎ ፡ ከፍሎ ፡ አኖረው ፡ በዚያም ፡ ላይ ፡ ውኃውን ፡ አፈሰሰ ፡
መስኖ ፡ ሁሉ ፡ እስኪመላ ፡ ድረስ ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ኤል
ያስ ፡ ወደ ፡ መሠውያ ፡ ቀርቦ ፡ እንዲህም ፡ ብሎ ፡ ጸለየ ፡፡ እ
ግዚአብሔር ፡ ሆይ ፡ የአብርሃም ፡ የይስሐቅም ፡ የያዕቆብም ፡
አምላክ ፡፡ ዛሬ ፡ አስታውቅ ፡ አንተ ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ሆን
ህ ፡ በእሥራኤል ፡ እኔም ፡ ባርያህ ፡ እንደ ፡ ሆንሁ ፡ ይህነን
ም ፡ ነገር ፡ ሁሉን ፡ እንደ ፡ ትእዛዝህ ፡ እንደደረግሁ ፡፡ ስማ
ኝ ፡ አቤቱ ፡ ስማኝ ፡ ይህች ፡ ሕዝብ ፡ ታውቅ ፡ ዘንድ ፡ አንተ ፡
እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ሆንህ ፡ በኋላም ፡ ልባቸ
ውን ፡ ልትመልስ ፡፡ ይህነንም ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔ
ር ፡ እሳት ፡ ወደቀ ፡ ምሥዋዕትንም ፡ እንጨትንም ፡ ደንጊ
ያውንም ፡ መሬትንም ፡ ሁሉን ፡ በላ ፡ በመስኖም ፡ የነበረ
ውን ፡ ውኃ ፡ ሁሉ ፡ ጠጠ ፡፡ ሕዝብም ፡ ሁሉ ፡ ይህነን ፡ ባዩ ፡
ጊዜ ፡ በፊታቸው ፡ ወድቀው ፡ አሉ ፡፡ እግዚአብሔር ፡ አም
ላክ ፡ ነው ፡፡ እግዚአብሔር ፡ አምላክ ፡ ነው ፡፡ ከዚህም ፡
በኋላ ፡ ኤልያስ ፡ የብዒልን ፡ የአስተርቴንም ፡ ነቢያት ፡ ሁ
ሉ ፡ ይዞ ፡ አረዳቸው ፡፡ ወደ ፡ ተራራ ፡ ራስ ፡ ላይም ፡ ሒዶ ፡
ጸለየ ፡ በጸሎቱም ፡ ኃይል ፡ ሰማይ ፡ ተከፈተ ፡ ብርቱ ፡ ዝና
ምም ፡ ዘነመ ፡፡ አሁንም ፡ የአሐብና ፡ የኢዛቤል ፡ ልብ ፡ ካ
ልበረታ ፡ በኃጢአት ፡ እርሳቸው ፡ ከሕዝባቸው ፡ ጋራ ፡ በተ
መለሱ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡፡ ደር ፡ ይህ ፡ ታላቅ ፡ ተአምሬ
ት ፡ ወደ ፡ ልባቸው ፡ አልገባም ፡፡ ኢዛቤልም ፡ የኤልያስን ፡
ሞት ፡ ፈለገች ፡ እርሱ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በደ ፡ ሸሸ ፡፡ ከ

ዚያም ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ታየለት ፡ ለመንገድ
ም ፡ አጸናው ፡ ፵፤ ቀንና ፡ ፵፤ ሌሊት ፡ ይሔድ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡
ኮሬብ ፡ ተራራ ፡ እስኪደርስ ፡ ድረስ ። ከዚያም ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ታየለት ፡ ፈቃደ፡ንም ፡ አስታወቀው ። ኤልያስም ፡
ተመለሰ ፡ ወደ ፡ እሥራኤል ፡ አገር ፡ ኤልሣውንም ፡ በእግ
ዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ቀብቶ ፡ ነቢይን ፡ አደረገው ። የአሐ
ብም ፡ ልጅ ፡ አሐዝያስ ፡ የእሥራኤል ፡ ንጉሥ ፡ ታሞ ፡ ወ
ታደር ፡ ሊያዙት ፡ በሰደደበት ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ንጉሥም ፡ በግ
ድ ፡ ሊያምጡት ፡ እርሱ ፡ እሳትን ፡ ከሰማይ ፡ አውርደ ፡ ገ
ደላቸው ። የኤልያስም ፡ ጊዜ ፡ ሲደርስ ፡ እግዚአብሔር ፡ በ
ሳት ፡ ፈረስና ፡ ሠረገላ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ወሰደው ፡ ሳይሞት ።
ሲወጣም ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ልብሱን ፡ ለኤልሣ ፡ አውርደ ፡
ሰደደው ፡ ምልክት ፡ ይሆንለት ፡ ዘንድ ፡ መንፈሱ ፡ በ፪፤ ዕፅ
ፍ ፡ በኤልሳ ፡ ላይ ፡ እንዲቀመጥ ።

አሐዝያስም ፡ ያሐብ ፡ ልጅ ፡ በሕማሙ ፡ ሞተ ፡ ኤልያ
ስ ፡ እንደ ፡ ተነበየለት ፡ ዮራምም ፡ ወንድሙ ፡ ነገሠ ፡ በ
ስፍራው ። እርሱም ፡ እንደ ፡ አባቱ ፡ እንደ ፡ እናቱም ፡ የ
ከፋ ፡ አልነበረም ። የብዔልን ፡ ዐምድ ፡ ሽርታልና ፡ ደር ፡
የዮርብዓምን ፡ ኃጢአት ፡ ተከተለ ። በዘመኑም ፡ ኤልሣ ፡
ብዙ ፡ ተአምራትን ፡ አደረገ ። እሥራኤል ፡ ግን ፡ ወደ ፡ እ
ግዚአብሔር ፡ አልተመለሰም ። በኃጢአታቸውም ፡ መክን
ያት ፡ የሶርያ ፡ ነገሥታት ፡ መጥተውባቸው ፡ አስጨነቅዋቸ
ው ። እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ገና ፡ በጣም ፡ አልጣላቸውም ፡
ሶስት ፡ ጊዜም ፡ ድል ፡ አስነሣቸው ፡ እርሳቸው ፡ ጥቂት ፡ በ
ነበሩ ፡ ጊዜ ፡ በብዙ ፡ አሕዛብ ፡ ላይ ። ኤልሣም ፡ ሃዛኤልን
ም ፡ ቀብቶት ፡ አነገሠው ፡ በሶርያ ፡ ላይ ፡ ኢዩንም ፡ በእሥ
ራኤል ፡ ላይ ።

ኢዩም ፡ የአሐብን ፡ ወገን ፡ ሁሉን ፡ ገደለ ፡ ኢዛቤልንም ፡
የአሐብን ፡ ምሽት ። እንደ ፡ ኤልያስም ፡ ትንቢት ፡ ውሾ
ች ፡ በሉ ፡ የኢዛቤልን ፡ ሥጋ ፡ ለአሐብ ፡ በግፍ ፡ ባስገዛች ፡
በናቡት ፡ እርሻ ፡ ናቡትን ፡ ከገደለች ፡ በኋላ ። እንደዚህ ፡ እ
ግዚአብሔር ፡ የኃጢአትን ፡ ዋጋ ፡ ይከፍላል ። ኢዩም ፡ የ
ብዔልን ፡ ካህናትና ፡ ነቢያትንም ፡ ሁሉ ፡ ገደለ ፡ የብዔል

ንም ፡ መስጊዶች ፡ አፈረሰ ። ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ የእ
ሥራኤልን ፡ መንግሥት ፡ ሰጠው ፡ ለርሱ ፡ ለልጆቹም ፡ ላሬ
ት ፡ ትውልድ ። ደር ፡ ኢዩ ፡ ከለልቡ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አ
ልፈራም ፡ የዮርብዓምን ፡ ኃጢአት ፡ ተከተለ ፡ እንጂ ። እ
ንዲሁም ፡ ልጁ ፡ ዮአኃዝ ፡ የዮአኃዝም ፡ ልጅ ፡ ይሆአሽ ፡
የይሆአሽም ፡ ልጅ ፡ ዮርብዓም ፡ የርሱም ፡ ልጅ ፡ ዘካርያ
ስ ። እለዚህ ፡ ፬፤ የኢዩ ፡ ትውልድ ፡ ነበረ ፡ በእሥራኤል ፡
መንግሥት ፡ የነገሡ ። ሁላቸውም ፡ የዮርብዓምን ፡ የናባ
ጥ ፡ ልጅ ፡ መንገዱን ፡ ተከተሉ ። የእሥራኤልንም ፡ ክፋ
ትና ፡ ጥፋት ፡ አበዙ ። ዘካርያስም ፡ የዮርብዓም ፡ ልጅ ፡
ሞተ ፡ በሣሉም ፡ በሎሌው ፡ እጅ ። የሣሉም ፡ መንግሥ
ት ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ወር ፡ ብቻ ፡ ኖረች ። መናሄም ፡ የጋዲ ፡ ል
ጅ ፡ ገድሎታልና ፡ በርሱ ፡ ስፍራ ፡ ነገሠ ፡ ፲፤ አመት ። ከርሱ
ም ፡ በኋላ ፡ ፈቅህያ ፡ ልጁ ፡ ፪፤ አመት ፡ ነገሠ ። ፈቅህያን ፡
ግን ፡ ፈቃህ ፡ ገደለ ፡ በስፍራውም ፡ ነገሠ ፡ ፳፤ አመት ። በፈ
ቃህም ፡ ዘመን ፡ ተግለትፈላስር ፡ የአሡርያ ፡ ንጉሥ ፡ አን
ደኑን ፡ ታላቅ ፡ ክፍል ፡ ከእሥራኤል ፡ መንግሥት ፡ አፈለሰ ፡
ወደ ፡ አሡርያም ፡ ወሰዳቸው ። ፈቃህም ፡ ሞተ ፡ በሆሼ
ዕ ፡ በኤላ ፡ ልጅ ፡ እጅ ። ሆሼዕም ፡ በስፍራው ፡ ነገሠ ።
እርሱም ፡ ኋለኛ ፡ ንጉሥ ፡ ነበረ ፡ በእሥራኤል ፡ ላይ ፡ የነገ
ሠ ። የእሥራኤል ፡ ኃጢአት ፡ መልትዋልና ፡ እግዚአብሔ
ር ፡ ባሡርያውያን ፡ እጅ ፡ ሰጣቸው ። ያሡርያም ፡ ንጉሥ ፡
ሰልመናስር ፡ መጣባቸው ፡ ሁላቸውንም ፡ የ፲፤ ወገኖችን ፡
ሰዎች ፡ ከከናዐን ፡ አገር ፡ አውጥቶ ፡ ወደ ፡ አሡርያ ፡ ወሰ
ደቸው ። እንዲህም ፡ ተጨረሰች ፡ የእሥራኤል ፡ የ፲፤ ወገ
ን ፡ መንግሥት ፡ ባመፃ ፡ ትጀምር ፡ የነበረች ፡ በእግዚአብ
ሔርም ፡ ፊንታ ፡ ጣዖታትን ፡ ያመለከች ።

በይሁዳ ፡ መንግሥትም ፡ ጥቂት ፡ ተሻለች ። በመካ
ከልዋም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ነበረ ፡ የእግዚአብሔር
ም ፡ የካህናት ፡ ወገን ፡ የእግዚአብሔርም ፡ ሥርዓት ፡ የጣ
ዖታትን ፡ ማምለክ ፡ ጥቂት ፡ የከለከለ ። ነገሥታታቸው
ም ፡ ከሮብዓም ፡ ጀምረው ፡ እስከ ፡ ባቢሎን ፡ ምርኮ ፡ ድረ
ስ ፡ እለዚህ ፡ ነበሩ ። ሮብዓም ፡ አቢያምም ፡ አሣም ፡ ዮ

ሣፍጥም ፡ ዮራምም ፡ አኃዝያስም ፡ ኢዮአስም ፡ አሜስያ
ስም ፡ ዓዛርያስም ፡ ስሙ ፡ ዖዝያ ፡ የተባለ ፡ ዮአታምም ፡
አሐዝም ፡ ሕዝቅያስም ፡ ምናሴም ፡ አሞንም ፡ ዮስያስ
ም ፡ ይሆአሐዝም ፡ ወንድሙም ፡ ዮአቂም ፡ የርሱም ፡ ል
ጅ ፡ ዮአኪን ፡ ያጉቱም ፡ ልጅ ፡ ሴድቅያስ ፡ ሁላቸውም ፡
፲፱፡ ነገሥታት ፡ በ፫፻፺፯፡ አመት ፡ የነገሡ ፡፡ እለዚህ ፡ ፪፡ መ
ንግሥቶች ፡ የይሁደ ፡ መንግሥትና ፡ የእሥራኤል ፡ መንግ
ሥት ፡ ከተከፈሉ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ባቢሎን ፡ ምርኮ ፡ ድረ
ስ ፡፡ ከለዚህም ፡ ፲፱፡ አሣ ፡ ዮሣፍጥም ፡ ሕዝቅያስም ፡
ዮስያስም ፡ በጎች ፡ ነበሩ ፡፡ የቀሩም ፡ ልባቸው ፡ በጣም ፡
አልቀናም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡፡ የሳሎሞንም ፡ ኃጢ
አት ፡ በመንግሥታቸው ፡ እጅግ ፡ ጉደ ፡፡ ልጆቻቸው ፡ ያባታ
ቸውን ፡ የጣዖታትን ፡ ማምለኩ ፡ ተከተሉ ፡፡ ይህም ፡ ክፉ
ት ፡ ከቶ ፡ በጣም ፡ አልቀረም ፡፡ ዮሣፍጥ ፡ እጅግ ፡ ደከ
መ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሥርዓት ፡ በመንግሥቱ ፡ ይመል
ስ ፡ ዘንድ ፡ ዮራም ፡ ግን ፡ ልጁ ፡ አባቱ ፡ የሰራውን ፡ አፈረ
ሰ ፡፡ ጣዖታትንም ፡ ማምለክ ፡ ከሁሉ ፡ ይልቅ ፡ ያበዛ ፡ አ
ሐዝ ፡ ነው ፡ የዮአታም ፡ ልጅ ፡ የሕዝቂያስም ፡ አባት ፡፡ እ
ርሱም ፡ ወደጅነት ፡ አደረገ ፡ ከአሡርያ ፡ ሕዝብ ፡ ከተግለ
ት ፡ ፈላስር ፡ ከንጉሣቸው ፡ ጋራ ፡ በሶርያውያን ፡ ላይ ፡፡ የ
ሶርያውያንም ፡ የጸላቶቹን ፡ ጣዖታት ፡ አመለከ ፡፡ ሕዝቅ
ያስ ፡ ልጁ ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መቅደስ ፡ ከፈተ ፡ በ
እግዚአብሔርም ፡ ትእዛዛት ፡ ተመላለሰ ፡ እጅግም ፡ አደ
ረገ ፡ የጣዖታትን ፡ ማምለክ ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ አልተቻለው
ምም ፡፡ እርሱም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ታምኖ ፡ በአሡርያ ፡ ን
ጉሥ ፡ ዐመፀ ፡፡ ስለዚህም ፡ ያሡርያ ፡ ንጉሥ ፡ መጣበት ፡
እግዚአብሔርንም ፡ ሰድቦት ፡ የይሁደን ፡ መንግሥት ፡ ሁ
ሉ ፡ እገሉብጣለሁ ፡ አለ ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ በደሳይያ
ስ ፡ በነቢይ ፡ አፍ ፡ የሕዝቅያስን ፡ ልብ ፡ አጽንቶ ፡ መልአ
ኩን ፡ ሰደደ ፡ ያሡርያውያንን ፡ ሠራዊት ፡ ሁሉ ፡ እርሳቸ
ውም ፡ ፻፹፭፲፻፡ ሰዎች ፡ በሌሊት ፡ የገደላቸው ፡፡ ንጉሣቸው
ም ፡ ወደገረ ፡ ወደ ፡ አሡርያ ፡ ከተመለሰ ፡ በኋላ ፡ ልጆቹ ፡
ገደሉት ፡፡ የሕዝቅያስ ፡ ልጅም ፡ ምናሴ ፡ እጅግ ፡ ክፉ ፡ ነበ

ር ፡፡ እጅግ ፡ ንጹሕ ፡ ደምም ፡ አፈሰሰ ፡ በየሩሳሌም ፡፡ ደኅ
ደያስንም ፡ ነቢይን ፡ በመጋዝ ፡ ቈርጦት ፡ እንደ ፡ ገደለው ፡
ይላሉ ፡ አይሁድ ፡፡ ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ የባቢሎንን ፡
ንጉሥ ፡ ሰይደበት ፡ በሰንሰለት ፡ ያሠረው ፡፡ ወደ ፡ ባቢሎን
ም ፡ የወሰደው ፡፡ ከዚያም ፡ በግዞት ፡ ሲሆን ፡ በኃጢአቱ ፡
መክንያት ፡ አዘነ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ተመለሰ ፡፡ ል
ጁም ፡ አሞን ፡ ያባቱን ፡ ኃጢአት ፡ ተከተሉ ፡ ያባቱን ፡ መ
መለስ ፡ አልተከተለም ፡፡ ስለዚህም ፡ ስለ ፡ ክፋቱ ፡ ሎሌል
ቱ ፡ ገደሉት ፡፡ ልጁ ፡ ግን ፡ ዮስያስ ፡ እጅግ ፡ ተጋደለ ፡ ሃ
ይማኖትንና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፍርሃት ፡ ለመመለስ ፡፡
አገርንም ፡ አነጻ ፡ ከጣዖታት ፡፡ እንዲህም ፡ አድርጎ ፡ የእግ
ዚአብሔርን ፡ ቍጣ ፡ በይሁደ ፡ ላይ ፡ ለዘመኑ ፡ ከለከለ ፡፡
ደሮ ፡ እርሱ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ጥፋት ፡ በይሁደ ፡ አገር ፡ ገባ ፡
አልጨረሰምም ፡ ነቡከድናጸር ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡፡ እር
ሱ ፡ የሩሳሌምን ፡ አፈረሰ ፡ የይሁደንም ፡ ምድር ፡ አጠፋ ፡
መቅደስንም ፡ አፈርሶት ፡ እቃውን ፡ ሁሉን ፡ ወደ ፡ ባቢሎ
ን ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ወሰደ ፡ የይሁደ ፡ ወገንም ፡ ሁሉ ፡ ከርሱ ፡
ጋራ ፡ መርኮ ፡ ወሰደቸው ፡፡

የባቢሎንም ፡ ምርኮ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መቅሠፍት ፡
ነበረ ፡ በይሁደ ፡ ኃጢአት ፡፡ እግዚአብሔር ፡ በሙሴ ፡ አፍ ፡
እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ነግሮዋቸዋልና ፡፡ እርሳቸው ፡ በእግዚአብ
ሔር ፡ መንገድ ፡ የሚመላለሱ ፡ እንደሆኑ ፡ እርሱ ፡ ሊጠ
ብቃቸው ፡ እንደለው ፡፡ እርሳቸው ፡ ግን ፡ መንገደን ፡ ቢ
ተው ፡ እርሱም ፡ ከፊቱ ፡ ቢጣላቸው ፡፡ እግዚአብሔር
ም ፡ አልደከመም ፡ ሕዝቡን ፡ በመምከሪቸው ፡ በመግ
ሠጻቸውም ፡ በማስተማሪቸውም ፡ በነቢያቱ ፡ አፍ ፡ እ
ርሱ ፡ በሰደደላቸው ፡ በኃይሉ ፡ በመንፈሱም ፡ መልተው ፡፡
ኤልያ ፡ ነቢያትም ፡ የተመረጹ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፡፡ ለእግ
ዚአብሔር ፡ ሊመሰክሩ ፡ የሕዝብንም ፡ የንጉሥንም ፡ ኃ
ጢአት ፡ ሊጻዮፉ ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ማክበርና ፡ እው
ነተኛውን ፡ ሃይማኖት ፡ ሊጠብቁ ፡ የምእምናንም ፡ ልብ ፡
በመድኃኒት ፡ ተስፋ ፡ ሊያጸኑ ፡፡ እግዚአብሔርም ፡ ለሕ
ዝብና ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ ገለጻቸው ፡ እንደ ፡ መለክተኞቹ ፡

ምስክራቸውንም ፡ አጸና ፡ በተአምራትና ፡ በትንቢት ፡ መንፈስ ፡ የሚመጣውን ፡ ነገር ፡ ተስፈውንና ፡ ቅያሜን ፡ የተናገሩበት ፡፡ የትንቢታቸውም ፡ ሁሉ ፡ ፍጻሜ ፡ ክርስቶስ ፡ ነበረ ፡ የክርስቶስም ፡ መንግሥት ፡፡ የተጻፈውም ፡ ትንቢታቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የቀደሰው ፡ የጠበቀውም ፡ ከሰውም ፡ ነገር ፡ ልይቶት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነገር ፡ ሁኖ ፡ የገለጸው ፡ ፲፯ ፡ መጻሕፍት ፡ ናቸው ፡ እሌህ ፡ ፲፯ ነቢያት ፡ የጻፏቸው ፡፡ ኢሳይያስ ፡ ኤርምያስም ፡ ሕዝቅኤልም ፡ ደንኤልም ፡ ሆሴዕም ፡ ዮኤልም ፡ ዓሞጽም ፡ ኦብድያም ፡ ዮናስም ፡ ሚክያስም ፡ ናሆምም ፡ እንባቆምም ፡ ሶፎንያስም ፡ ሐጌም ፡ ዘካርያስም ፡ መልክያስም ፡፡ ጴጥሮስም ፡ እንደህ ፡ ይላል ፡ ስለ ፡ ነቢያት ፡፡ ስለዚህ ፡ መድኃኒት ፡ ነቢያት ፡ ፈለጉ ፡፡ በዚችም ፡ ለላንት ፡ በሆነቸው ፡ ጸጋ ፡ ትንቢት ፡ ተናገሩ ፡፡ ስለ ፡ ዘመኑም ፡ መረመሩ ፡ የተናገሩባቸውም ፡ የክርስቶስ ፡ መንፈስ ፡ ተቀደመ ፡ በክርስቶስ ፡ ሕማማት ፡ መሰከረ ፡ ከዚያ ፡ በኋላም ፡ ስለ ፡ ሚመጣው ፡ ክብሩ ፡፡ ይኸት ፡ የነበሩትንም ፡ ገለጠላቸው ፡፡ ለራሳቸው ፡ ያገለገሉት ፡ አልነበሩምና ፡ ለኛ ፡ እንጂ ፡፡ ያነን ፡ ስለርሱ ፡ ያስተማሯችሁን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡፡ ከሰማይ ፡ የተላከው ፡ መላእክት ፡ የወደዱ ፡ ያዩት ፡ ዘንድ ፡፡ የጴጥሮስ ፡ ፩ ፡ መልእክት ፡ ም ፡ ፩ ፡ ቍ ፡ ፲ ፡ ፲፩ ፡ ፲፪ ፡፡

የባቢሎንም ፡ ምርኮ ፡ ፸ ፡ አመት ፡ ኖረ ፡ በኋላም ፡ እግዚአብሔር ፡ ምህረቱን ፡ ለሕዝቡ ፡ አሳያቸው ፡፡ የባቢሎን ፡ የካለደውያን ፡ መንግሥት ፡ በአሡርያ ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ ትነሣ ፡ የነበረች ፡ አሁን ፡ በፋርስ ፡ ኃይል ፡ ፈረሰች ፡፡ ቂሮስም ፡ የፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ በባቢሎን ፡ ገብቶ ፡ የካልደውያን ፡ መንግሥት ፡ አፈረሰ ፡ እግዚአብሔር ፡ በይሳይያስ ፡ በሌሎችም ፡ በነቢያቱ ፡ አፍ ፡ ቀድሞ ፡ እንደ ፡ ተናገረ ፡፡ ቂሮስም ፡ የይሳይያስን ፡ ትንቢት ፡ ስለርሱ ፡ ሲያይ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አመነ ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ፈቃድ ፡ ሊፈጽም ፡ ብሎ ፡ አይሁድን ፡ ወደገሬቸው ፡ ሊመለሱ ፡ ከዚያም ፡ መቅደሳቸውን ፡ ሊሰሩ ፡ አዘዛቸው ፡፡

የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ካይሁድ ፡ ፩ ፡ ክፍል ፡ ከካህኑ ፡ ከዕዝ

ራ ፡ ትእዛዝ ፡ በታች ፡ ወደ ፡ የሩሳሌም ፡ ተመለሱ ፡፡ ከዕዝ
ራ ፡ ጋራም ፡ ዜሩባቤልና ፡ ዮሱዓ ፡ ተመለሱ ፡፡ የቀሩ ፡ ግን ፡
በባቢሎንና ፡ በፋርስ ፡ አገር ፡ ተቀመጡ ፡ እስከ ፡ አርተክሰ
ርክሲስና ፡ እስከ ፡ ደሪዮስ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡፡ የዚያን ፡ ጊ
ዜም ፡ ነህምያ ፡ ወሰዳቸው ፡ ወደ ፡ የሩሳሌም ፡፡ በዚያ ፡ ዘ
መንም ፡ ከተማና ፡ መቅደስ ፡ ተሰሩ ፡፡ የእግዚአብሔርም ፡
ነቢያት ፡ ሐጌ ፡ ዘካርያስም ፡ መልክያስም ፡ ተነበዩ ፡፡
እርሳቸውም ፡ ኋለኞች ፡ ነቢያት ፡ ነበሩ ፡ በብሉይ ፡ ሥርዓ
ት ፡፡ ከርሳቸውም ፡ በኋላ ፡ ነቢይ ፡ አልተነሣም ፡ ክርስቶ
ስ ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡፡

በዚያ ፡ ዘመንም ፡ አይሁድ ፡ ከ ፋርስ ፡ ነገሥታት ፡ በ
ታች ፡ ነበሩ ፡፡ የፋርስ ፡ መንግሥት ፡ ግን ፡ በመቄዶንያ ፡ መ
ንግሥት ፡ ስትወድቅ ፡ ታላቅ ፡ እስክንድርም ፡ ሲነግሥ ፡ ከ
እስክንድር ፡ በታች ፡ ሆኑ ፡፡ እስክንድርም ፡ ሲሞት ፡ መኳ
ንንቱ ፡ ተከፋፈሉ ፡ በመንግሥቱ ፡ አንዱም ፡ አንቲጎኖስ ፡
ሶርያን ፡ አንዱም ፡ጵቶልሜዎስ ፡ ምሥርን ፡ ወሰደ ፡ ለመግ
ዛቱ ፡፡ የይሁዳም ፡ አገር ፡ በመኻከላቸው ፡ ተቀምጣ ፡ ሁለ
ግዜ ፡ ጸብ ፡ አደረጉ ፡ ስለርስዋ ፡፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ለምሥር ፡
ንጉሥ ፡ ተገዛች ፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ለሶርያ ፡ ንጉሥ ፡፡ አንቲ
ዎኻስም ፡ የተባለ ፡ የሶርያ ፡ ንጉሥ ፡ ከሰሌውቆስ ፡ ዘመ
ድ ፡ እጅግ ፡ ክፉ ፡ አደረገ ፡ በይሁዳ ፡፡ እርሱም ፡ በመቅደስ ፡
ለጣዖታት ፡ ሰገደ ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ሥርዓት ፡ በጣ
ም ፡ ማፍረስ ፡ ይሻ ፡ ነበረ ፡፡ አይሁድንም ፡ ከመገዘር ፡ ከ
ለከላቸው ፡፡ ለጣዖታትም ፡ ያልሰገዱትን ፡ ገደለ ፡፡ በዚያ ፡
ዘመንም ፡ካይሁድ ፡ እጅግ ፡ ሞቱ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖታቸው ፡፡
ብዙም ፡ ዐመፁ ፡ ከሃይማኖት ፡ ካዱም ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜ
ም ፡ እግዚአብሔር ፡ ፩ ፡ ሰውን ፡ አስነሣ ፡ ወንድሞቹን ፡ ያ
ደናቸው ፡ እርሱም ፡ ካህን ፡ ማታቲያስ ፡ የተባለ ፡፡ እርሱ
ም ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ተሸሸገ ፡ ኖረ ፡ ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ ከሃ
ይማኖታቸው ፡ ያልወደቁ ፡ ወደርሱ ፡ መጡ ፡ እርሱም ፡ ረዳ
ቸው ፡፡ እርሱም ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ልጆቹ ፡ ይሁዳ ፡ መቃቤ
ዎስ ፡ ዮናታንም ፡ ሲሞንም ፡ ተጋደሉ ፡ ጾርም ፡ አደረጉ ፡
ስለ ፡ መቅደሳቸው ፡ ስለ ፡ ሃይማኖታቸውም ፡ እግዚአብሔ

ር ፡ እስኪያድናቸው ፡ ድረስ ፡ ከአንቲዎኮስ ፡ እጅ ፡ መንግሥታቸውንም ፡ እስኪሰጣቸው ፡ ድረስ ፡ በይሁዳ ፡ አገር ፡ ላይ ፡፡ የሲሞንም ፡ ልጅ ፡ ዮሐንስ ፡ ሂርካኖስ ፡ ባገሩ ፡ ላይ ፡ ነገሠ ፡፡ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ አሪስቶቡሎስ ፡ ፩፡ አመት ፡ ብቻ ፡፡ እስክንድር ፡ ያኔዎስም ፡ ተከተለው ፡፡ እርሱም ፡ ሲሞት ፡ ምሽቱ ፡ አሌክሳንድራ ፡ ነገሠች ፡ በኋላም ፡ ልጆችዋ ፡ ሂርካኖስና ፡ አሪስቶቡሎስ ፡ ስለ ፡ መግዛት ፡ ተጻሉ ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡፡ በዚያ ፡ ዘመንም ፡ የሮማያ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ይሁዳ ፡ አገር ፡ ገቡ ፡፡ ፖምጴዮስም ፡ የሮምያ ፡ መኰንን ፡ ወደ ፡ የሩሳሌም ፡ ወደ ፡ መቅደስም ፡ ገባ ፡ ደር ፡ አልጐደውም ፡፡ ሂርካኖስንም ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ አደረገው ፡ ወንድሙን ፡ ግን ፡ አሪስቶቡሎስን ፡ መርኮ ፡ ወደ ፡ ሮማያ ፡ ወሰደው ፡፡ በዚህ ፡ ዘመንም ፡ የሄሮድስ ፡ ወገን ፡ ተነሣ ፡፡ ሄሮድስም ፡ ከኤዶም ፡ ከይስሐቅ ፡ ልጅ ፡ ከያዕቆብ ፡ ወንድምም ፡ ከትውልዱ ፡ ነበረ ፡፡ ኤዶማውያንም ፡ በዮሐንስ ፡ ሂርካኖስ ፡ ተሸንፈው ፡ ካይሁድ ፡ ወገን ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ሆኑ ፡፡ የሄሮድስም ፡ አባት ፡ አንቲጳቴር ፡ ተንኰለኛና ፡ ኃይለኛ ፡ ሁንዋልና ፡ ከሮምያ ፡ መኰንን ፡ ጋራ ፡ ወዳጅነት ፡ አደረገ ፡፡ በርሳቸውም ፡ ኃይል ፡ የከበረውን ፡ ሹመት ፡ አገኘ ፡ በይሁዳ ፡፡ ልጁ ፡ ሄሮድስ ፡ ግን ፡ ከርሱ ፡ በለጠ ፡፡ ከቄሳር ፡ ጋራ ፡ የነበረለቱን ፡ ወዳጅነት ፡ አጽንቶ ፡ እጅግ ፡ ደም ፡ አፈሰሰ ፡ በይሁዳ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ እስኪነግሥ ፡ ድረስ ፡፡

በዚህ ፡ ጊዜም ፡ እግዚአብሔር ፡ ዓለምን ፡ ሳይፈጥር ፡ ለሰው ፡ መድኃኒት ፡ የቍረጠ ፡ ዘመን ፡ ተፈጸመ ፡፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ አሁን ፡ በመንፈሳዊት ፡ ጨለማ ፡ ተቀመጠ ፡፡ አንደንድም ፡ ብቻ ፡ ከዚህና ፡ ከዚያ ፡ ተገኝቶ ፡ ተስፋ ፡ አደረገ ፡ ለመድኃኒት ፡ ከኃጢአትና ፡ ከሰይጣን ፡ ከዘላለምም ፡ ፍርድ ፡፡ ደር ፡ ይህችን ፡ መድኃኒት ፡ ያባቶች ፡ አለቆች ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ባሮችም ፡ ሁሉ ፡ ነገሥታትና ፡ ነቢያት ፡ ተስፋ ፡ አድርገዓት ፡ ነበሩ ፡ ነቢያትም ፡ ፬፻፡ አመት ፡ የሚያህል ፡ ዝማሉ ፡፡ በዚያ ፡ ዘመንም ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ገብሪኤል ፡ ወደንድ ፡ ካህን ፡ ወደ ፡ ዘካር

ያስ ፡ ተላከ ። ዘካርያስም ፡ ሽማግሌ ፡ ነበረ ። ምሽቱም ፡
ኤልሳቤጥ ፡ ሽመገለች ። እርሳቸውም ፡ በእግዚአብሔር ፡
ፊት ፡ ተመላለሱ ፡ ያለ ፡ ነውር ፡ ልጅም ፡ አልነበረላቸው
ም ። መልአክም ፡ ለዘካርያስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ትእዛ
ዝ ፡ ተስፋ ፡ አስደረገለት ፡ ልጅን ፡ እንዲወልድ ፡ የእግዚአ
ብሔር ፡ መለክተኛ ፡ የሚሆን ፡ ለዓለም ፡ መድኅን ፡ የሚ
ቀድም ፡ መንገዱንም ፡ የሚጸርግ ፡ የእሥራኤልም ፡ ወገን ፡
ልባቸውን ፡ ወደምላካቸው ፡ የሚመልስ ፡ ስሙም ፡ ዮሐን
ስ ። ዘካርያስም ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ምልክትን ፡ ሲፈልግ ፡ መ
ልአክ ፡ አለው ። አንተ ፡ ድዳ ፡ ትሆናላህ ፡ መናገርም ፡ አይ
ቻልህም ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ እስከሚሆንበት ፡ ቀን ፡ ድረስ ። አላ
መንህምና ፡ በነገሬ ፡ በጊዜው ፡ በሚፈጸም ፡፡ ዘካርያስም ፡
ድንገት ፡ ድዳ ፡ ሆነ ። ምሽቱም ፡ ኤልሳቤጥ ፡ ፀነሰች ፡ ሰ
ውነትዋንም ፡ ሰውራ ፡ ነበረች ፡ ፭፤ ወር ፡ እንደህ ፡ ስትል ።
እንደህ ፡ ሰራብኝ ፡ እግዚአብሔር ፡ በዚህች ፡ እኔን ፡ ባየበ
ት ፡ ቀን ፡ አሣሬን ፡ በሰው ፡ ዘንድ ፡ ሊዋጣው ። በስድስተ
ኛም ፡ ወር ፡ ተላከ ፡ ገብሪኤል ፡ መልአክ ፡ ከእግዚአብሔ
ር ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ናዝሬት ፡ ወደ ፡ ታጮች ፡ ቆንጆ ፡ ላንድ ፡ ሰ
ው ፡ ስሙን ፡ ዮሴፍ ፡ የሚሉት ፡ ከዷዊት ፡ ወገን ። እግዚአ
ብሔር ፡ ለዷዊት ፡ ተስፋ ፡ አስደርግዋልና ፡ ያለም ፡ መድኀ
ን ፡ ከወገቡ ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ ጊዜ ፡ እንደለው ። ይህችን
ም ፡ ተስፋ ፡ አሁን ፡ ፈጸመ ። የቆንጆይቱ ፡ ስምም ፡ መርያ
ም ፡ ነው ። መልአኩም ፡ ወደርስዋ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ አለ ። ደ
ስ ፡ ይበልሽ ፡ ጸጋ ፡ የመላብሽ ፡ ሆይ ። እግዚአብሔር ፡ ካን
ች ፡ ጋራ ፡ ነው ፡ ከሴቶች ፡ የተባረክሽ ፡ ሆይ ። እርስዋም ፡
ባየችው ፡ ጊዜ ፡ ደነገጸች ፡ ከነገሩ ፡ አሰበችም ፡ እንደህ ፡ ስ
ትል ። ምንድር ፡ ነው ፡ ይህ ፡ ሰላም ። መልአክም ፡ አላት ።
አትፍሪ ፡ መርያም ፡ ሆይ ። ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ጸጋ ፡
አገኘተሻልና ። እነሆም ፡ በሆድ ፡ ትፀንሻለሽ ፡ ልጅም ፡ ት
ወልጀለሽ ፡ ስሙንም ፡ የሱስ ፡ ትደዋለሽ ። ይህም ፡ ታላቅ ፡
ይሆናል ፡ የልዑል ፡ ልጅም ፡ ይባላል ፡ እግዚአብሔር ፡ አም
ላክም ፡ የዷዊትን ፡ ያባቱን ፡ ዙፋን ፡ ይሰጠዋል ፡ በያዕቆ
ብ ፡ ወገንም ፡ ይነግሣል ፡ ለዘላለም ። ለመንግሥቱም ፡ ፍ

ጻሚ ፡ የለውም ፡፡ ማርያምም ፡ አለቸው ፡ መልአኩን ፡፡
እንዴት ፡ ይሆናል ፡ ይህ ፡ ወንድ ፡ ሳላውቅ ፡፡ መልአኩም ፡
መለሰ ፡ አላትም ፡፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ያድርብሻል ፡ የልው
ል ፡ ኃይልም ፡ ያጸልሻል ፡፡ ስለዚህም ፡ ካንች ፡ የሚወለደ
ው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ይባለል ፡፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በእግ
ዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ አይሳንምና ፡፡ መርያምም ፡ አለች ፡፡
እነሆኝ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ባርያ ፡፡ እንደ ፡ ነገርህም ፡ ይሁን
ልኝ ፡፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ማርያም ፡ ፈጥና ፡ ተነሣች ፡ ወደ ፡
ኤልሳቤጥም ፡ ዘመድዋ ፡ ወደ ፡ ነበረች ፡ ሔደች ፡ ተሳለመ
ቻትም ፡፡ ኤልሳቤጥም ፡ የማርያምን ፡ ሰላምታ ፡ በሰማ
ች ፡ ጊዜ ፡ ፅንሱ ፡ በሆድዋ ፡ ተገለበጠ ፡፡ በኤልሳቤጥም ፡ መን
ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መላባት ፡ በታላቅ ፡ድምጽም ፡ጮኸች ፡ አለ
ችም ፡፡ አንች ፡ በሴቶች ፡ መኻከል ፡ የተባረክሽ ፡ ነሽ ፡ የሆ
ድሽም ፡ ፍሬ ፡ የተባረከ ፡ ነው ፡፡ ለኔም ፡ እንዴት ፡ ይገባኛል ፡
ወደኔ ፡ ትመጣ ፡ ዘንድ ፡ የጌታዬ ፡ እናት ፡ እነሆ ፡ የስላምሽ ፡
ድምጽ ፡ በጆርዮ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ፅንሱ ፡ ተዛልዋልና ፡ በደስ
ታ ፡ በሆዴ ፡፡ ብፅዕትም ፡ ነሽ ፡ ያመንሽ ፡፡ ላንች ፡ የተነገረ
ው ፡ ፍጻሚ ፡ ይሆንልሻልና ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡፡ ማ
ርያምም ፡ አለች ፡፡ ነፍሴ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ታላቅ ፡ ታድር
ገዋለች ፡፡ መንፈሴም ፡ ደስ ፡ የልዋል ፡ በእግዚአብሔር ፡ በ
መድኃኒቴ ፡፡ የባርያዪቱን ፡ መዋርድ ፡ አይትዋልና ፡፡ እነሆ ፡
ከዛሬ ፡ ጀምሮ ፡ ያመሰግኑኛል ፡ ትውልድ ፡ ሁሉ ፡፡ ብርቱ ፡
ድንቅ ፡ በኔ ፡ አድርጓልና ፡ ስሙም ፡ ቅዱስ ፡ ነው ፡፡ ምህረቱ
ም ፡ ለልጅ ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ ለሚፈሩት ፡፡ ኃይል ፡ አደረገ ፡ በ
ክንዱ ፡፡ ትዕቢተኞችንም ፡ በተነ ፡ በልባቸው ፡ አሳብ ፡፡ ብር
ቱችንም ፡ አወረደ ፡ ከዙፋናቸው ፡፡ የተዋረዱትንም ፡ ከ
ፍ ፡ ከፍ ፡ አደረጋቸው ፡፡ የተራቡትንም ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ አጸገባ
ቸው ፡ ባለጠጎችንም ፡ ባደ ፡ ሰደደቸው ፡፡ እሥራኤልን ፡ ባር
ያውን ፡ ረደው ፡፡ ምህረቱንም ፡ አሰበ ፡ ላባቶቻችን ፡ እን
ደለ ፡ ላብርሃም ፡ ለልጅ ፡ ልጁም ፡ ለዘላለም ፡፡ ማርያም
ም ፡ ከኤልሳቤጥ ፡ ዘንድ ፡ ፫፤ ወር ፡ የሚያህል ፡ ተቀመጠ
ች ፡ ወደ ፡ ቤትዋም ፡ ተመለሰች ፡፡ የኤልሳቤጥም ፡ ጊዜ ፡
ሲደርስ ፡ ወንድ ፡ ልጅን ፡ ወለደች ፡፡ ስሙንም ፡ ዮሐንስ ፡

ብላ ፡ ጸሬቸው ፡፡ ዘመዶቻቸውም ፡ ሲጠራጠሩ ፡ አባቱን
ም ፡ ሲጠይቁ ፡ ዘካርያስ ፡ ጻፈ ፡ አፉንም ፡ ከፈተ ፡ አለም ፡፡
ስሙ ፡ ዮሐንስ ፡ ይሆናል ፡፡ እግዚአብሔርንም ፡ አመሰገነ ፡፡
አሁንም ፡ ዮሴፍ ፡ የማርያም ፡ ጬኛ ፡ እርስዋ ፡ እንደ ፡ ፀነ
ሰች ፡ ሲያይ ፡ የመልአክንም ፡ ነገር ፡ ሳያውቅ ፡ ተጠራጥሮ ፡
ማርያምን ፡ ስውር ፡ ሊተዋት ፡ አለ ፡፡ ይህነንም ፡ ሲያስብ ፡
እነሆ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ በሕልም ፡ ታየለት ፡ አ
ለውም ፡፡ ዮሴፍ ፡ ሆይ ፡ የዳዊት ፡ ልጅ ፡ ጬኛህን ፡ ማርያ
ምን ፡ ከመውሰድ ፡ አትፍራ ፡፡ ከርስዋ ፡ የሚወለደው ፡ ከ
መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነውና ፡፡ ልጅም ፡ ትወልደለች ፡ ስሙን
ም ፡ የሱስ ፡ ትለዋለህ ፡ ወገኖቹን ፡ ከኃጢአታቸው ፡ ያድ
ናቸዋልና ፡፡ ዮሴፍም ፡ ከንቅልፉ ፡ ተነሥቶ ፡ የእግዚአብ
ሔር ፡ መልአክ ፡ እንደዘዘው ፡ አደረገ ፡፡ ጬኛውን ፡ ማርያ
ምን ፡ ወሰደት ፡ አላወቃትም ፡ የበክር ፡ ልጅዋን ፡ እስክት
ወልድ ፡ ድረስ ፡፡

ይህም ፡ የክርስቶስ ፡ መወለድ ፡ በቤተ ፡ ልሔም ፡ ሆነ ፡፡
እንደዚህ ፡ ሁንዋል ፡፡ አውጉስቶስ ፡ የሮምያ ፡ ቄሣር ፡ ትእዛ
ዝን ፡ አወጣ ፡ ለመንግሥቱ ፡ ሁሉ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በያገሩ ፡
ይጻፍ ፡ ዘንድ ፡፡ ስለዚህም ፡ ዮሴፍ ፡ ደግሞ ፡ ተነሣ ፡ ከማ
ርያም ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ልሔምም ፡ ሔደ ፡ ከዚያ ፡ ይጻ
ፉ ፡ ዘንድ ፡፡ እርሳቸውም ፡ ከዚያ ፡ ሳሉ ፡ የመውለድዋ ፡
ዘመን ፡ ደረሰ ፡፡ የበክር ፡ ልጅዋንም ፡ ወለደች ፡ ጠቀለለቸ
ውም ፡ በከብትም ፡ መብልያ ፡ ተወቸው ፡፡ ስፍራ ፡ አልነበረ
ላቸውምና ፡ በሚያድሩበት ፡፡ በዚያችም ፡ አገር ፡ እረኞች ፡
ይጠብቁ ፡ ነበሩ ፡ ይተጉም ፡ ነበሩ ፡ በየፈንታ ፡ የሌት ፡ ትጋ
ት ፡ ስለ ፡ መንጋቸው ፡፡ እነሆም ፡ የእግዚአብሔር ፡ መለ
ክተኛ ፡ በርሳቸው ፡ ዘንድ ፡ ቆሞ ፡ ነበረ ፡፡ የእግዚአብሔ
ርም ፡ ብርሃን ፡ በርሳቸው ፡ ወጣ ፡ ታላቅ ፡ ፍርሃትም ፡ ፈ
ሩ ፡፡ መልአኩም ፡ አላቸው ፡፡ አትፍሩ ፡፡ እነሆ ፡ እኔ ፡ ለሕ
ዝብ ፡ ሁሉ ፡ የሚሆን ፡ የምስራች ፡ እነግራችኋለሁና ፡ በደ
ስታ ፡፡ ዛሬ ፡ ተወልደላችኋልና ፡ ወድኃኒት ፡ እርሱም ፡ ክር
ስቶስ ፡ ጌታ ፡ በዳዊት ፡ አገር ፡፡ ድንገትም ፡ መጡ ፡ ከመል
አኩ ፡ ጋራ ፡ ብዙ ፡ ከሰማይ ፡ ጭፍሮች ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያ

መሰገኑ ፡ እንደሆ ፡ ሲሉ ፡፡ ምስጋና ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በአር ያም ፡ በምድር ፡ ላይም ፡ ሰላም ፡፡ በሰውም ፡ በጎ ፡ ፈቃድ ፡፡ እንዲሁም ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ተወለደ ፡፡ እርሱ ፡ ያለም ፡ ሁሉ ፡ ጌታ ፡ የእግዚአብሔርም ፡ የዘላለም ፡ ልጅ ፡ አምላ ክ ፡ ከአምላክ ፡ ያለ ፡ ብርሃንም ፡ ከብርሃን ፡ በርሱም ፡ ፍ ጥረት ፡ ሁሉ ፡ የተፈጠረበት ፡ የኛን ፡ ጠባይ ፡ ተቀበለ ፡ በድ ኅነትም ፡ በመከራም ፡ ተወለደ ፡፡ ጳውሎስ ፡ እንደሆ ፡ ይላ ልና ፡፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የመሰለ ፡ መቆ ማትን ፡ አልቈጠረም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ መተካከ ል ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ራሱን ፡ አወረደ ፡ እንደ ፡ ባርያም ፡ ሆነ ፡ እ ንደ ፡ ሰውም ፡ መሰለ ፡፡ የሰውንም ፡ ምሳሌ ፡ ወሰደ ፡ ራሱ ንም ፡ አወረደ ፡፡ ፊልጵስዮስ ፡ ፪፡ ፯፡፡ ደግሞም ፡ ይላል ፡፡ የ ጌታችንን ፡ የየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ጸጋ ፡ አውቃችኋል ፡፡ ስለ ላንተ ፡ ተቸገርዋልና ፡ እርሱ ፡ ባለጠጋ ፡ ሲሆን ፡ እላንተ ፡ ባለጠጎች ፡ ትሆኑ ፡ ዘንድ ፡ በችጋሩ ፡፡ ፪፡ ቆሮንቶስ ፡ ፰፡ ፱፡፡ ይህ ፡ ነገርም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ጠባያችንን ፡ እንደ ፡ ተቀበለ ፡ ቃልም ፡ ሥጋ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ምሥ ጢር ፡ ነው ፡ ከሰው ፡ አእምሮ ፡ ሁሉ ፡ የሚያልፍ ፡ ሁሉን ም ፡ ከሚያውቅ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በቀር ፡ ማንም ፡ አይ ችልም ፡ ይህነን ፡ ምሥጢር ፡ በጣም ፡ ያስጠልቅ ፡ ዘንድ ፡፡ ሰውም ፡ በከንቱ ፡ ይደክማል ፡ በዚህ ፡ ጥልቅ ፡ ገብቶ ፡ ቢ ጠይቅ ፡፡ አምላክ ፡ እንዴት ፡ ይሆናል ፡ ሰው ፡፡ እንደህም ፡ ያለ ፡ መጠየቅ ፡ ለአደም ፡ ልጅ ፡ አይገባም ፡፡ እርሱ ፡ አያ ውቅምና ፡ የሰውን ፡ ፍጥረት ፡ ሰው ፡ እንዴት ፡ ነው ፡ እንዴ ትም ፡ ሆነ ፡፡ ይልቁንም ፡ እንዴት ፡ ይችላል ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ሰው ፡፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ም ፡ ይህነን ፡ ምሥጢር ፡ ያስጠልቁ ፡ ዘንድ ፡ በፈተኑ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ መምህር ፡ እንደሆ ፡ አንድም ፡ እንደሆ ፡ ብሎ ፡ ተና ገረ ፡፡ የምሥጢርን ፡ ጥልቅ ፡ ግን ፡ አላገኙም ፡፡ አሁንም ፡ ትሕትና ፡ ካላለቀችባቸው ፡ አለማወቃቸውን ፡ ባስታወቁ ፡ "እኔም ፡ አውቀዋለሁ ፡ አንተ ፡ ግን ፡ አታውቀውም ፡" ባ ላሉ ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡፡ ያችም ፡ ጸላትነት ፡ ያችም ፡ ሐ ሜት ፡ ፍቅር ፡ ሁሉ ፡ የጠፋበት ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡ መኻ

ከል ፡ ከዚህ ፡ መከራከር ፡ የተነሣች ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ አልመጣችም ፡ ከሰይጣን ፡ እንጂ ፡፡ ደሮ ፡ በዚህ ፡ ፈንታ ፡ ሌላ ፡ መጠየቅ ፡ ይገባል ፡፡ እንዲህ ፡ ብለን ፡፡ በምን ፡ መክንያት ፡ አደረገ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይህነን ፡ ታላቅ ፡ ተአምራት ፡፡ ፍሬውም ፡ ምንድር ፡ ነው ፡፡ ምንድር ፡ ይጠቅማል ፡፡ እኔም ፡ ለራሴ ፡ ምንድር ፡ ላድርግ ፡ ይህነን ፡ ፍሬ ፡ ለነፍሴ ፡ አቀምስ ፡ ዘንድ ፡፡ በርሱም ፡ እድን ፡ ዘንድ ፡፡

የክርስቶስም ፡ ሥጋ ፡ መልበስ ፡ መክንያት ፡ እርሱ ፡ ያወጣልናል ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ በዮሐንስ ፡ ወንጌል ፡ ም ፡ ፫፡ ቍ ፡ ፲፮፡፡ እግዚአብሔር ፡ ዓለምን ፡ እንዲህ ፡ ወዶዋልና ፡ አንደኛውን ፡ ልጁን ፡ እስኪለውጥ ፡ ድረስ ፡፡ በርሱ ፡ የሚያምን ፡ ሁሉ ፡ እንዳይጠፋ ፡ የዘላለም ፡ ሕይወት ፡ ትሆንለት ፡ ዘንድ ፡ እንጂ ፡፡ ጳውሎስም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡፡ ሮሜ ፡ ፰፡ ፫፡፡ ለሕግ ፡ ኀይል ፡ አልነበረላትምና ፡ በሥጋ ፡ ደክማለችና ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጁን ፡ ሰደደ ፡ በኀጢአት ፡ ሥጋ ፡ ምሳሌ ፡ ስለ ፡ ኀጢአት ፡ በኀጢአት ፡ ሊፈርድ ፡ በሥጋው ፡፡ የሕግ ፡ ጽድቅ ፡ በኛ ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ሥጋ ፡ ፈቃድ ፡ የማንመላለስ ፡ እንደ ፡ መንፈስ ፡ ፈቃድ ፡ እንጂ ፡፡ ደግሞም ፡ ይላል ፡ ዕብራውያን ፡ ፪፡ ፲፬፡፡ ልጆች ፡ በሥጋና ፡ በደም ፡ ተገኝተዋልና ፡ እርሱ ፡ ደግሞ ፡ ሥጋና ፡ ደም ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ተከፈፈለ ፡፡ የሞትን ፡ ሥልጣን ፡ ያለውን ፡ በሞቱ ፡ ይሽር ፡ ዘንድ ፡፡ ይፈታም ፡ ዘንድ ፡ እልያን ፡ ከሞት ፡ ፍርሃት ፡ የተነሣ ፡ ተዋርደው ፡ የነበረትን ፡ ለባርነት ፡ ዕድሜያቸውን ፡ ሁሉን ፡፡

የሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ጠባያችነንና ፡ ባሕርያችነን ፡ ከታላቅ ፡ ፍቅሩ ፡ የተነሣ ፡ ሰውን ፡ ሁሉን ፡ ያድን ፡ ዘንድ ፡ ብሎ ፡ በተቀበለ ፡ ጊዜ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ሕግ ፡ በታች ፡ ወረደ ፡፡ እንዲህ ፡ ብልዋልና ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ አፍ ፡፡ የዘመኑ ፡ ፍጸሜ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጁን ፡ ላከ ፡ ከሴትም ፡ ተወለደ ፡፡ ከኦሪት ፡ በታችም ፡ ሆነ ፡፡ ከኦሪት ፡ በታች ፡ ያሉትን ፡ ይገዛ ፡ ዘንድ ፡፡ እ

ኛም ፡ የልጅነትን ፡ መዝገብ ፡ እንወስድ ፡ ዘንድ ፡፡ ገላትያ
ውያን ፡ ፬፡ ፬፡፡ ስለዚህም ፡ ፰፡ ቀን ፡ ከተወለደ ፡ በኋላ ፡ ተገ
ዘረ ፡፡ ስሙም ፡ "የሱስ ፡" ማለት ፡ የሚረዳ ፡ የሚያድን
ም ፡ ተባለ ፡፡ እርሱም ፡ ከሕፃንነቱ ፡ ጀምሮ ፡ እስኪሞት ፡
ድረስ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ በኛ ፡ ፈንታ ፡ ፈጸመ ፡፡ የ
ሕግም ፡ መርገም ፡ ስለኛ ፡ ተሸክሞ ፡ አስወገደ ፡፡ ሰው ፡ ሁ
ሉ ፡ ከሕፃንነቱ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሞቱ ፡ ድረስ ፡ ከክርስቶ
ስ ፡ ጋራ ፡ አንድነት ፡ ማድረግ ፡ ይችል ፡ ዘንድ ፡ ሕፃናታችን
ም ፡ በርሱ ፡ ይቀደሱ ፡ ዘንድ ፡፡

የማርያምም ፡ የመንጻትዋ ፡ ወራት ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡
እርስዋ ፡ ከዮሴፍ ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ሙሴ ፡ ሕግ ፡ ይዘውት ፡
ወጡ ፡ ወደ ፡ የሩሳሌም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ያቆሙ
ት ፡ ዘንድ ፡፡ መሥዋዕትንም ፡ አቀረቡ ፡ በሕግ ፡ እንደ ፡ ታዘ
ዙ ፡፡ እነሆም ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡ በየሩሳሌም ፡ ስምዖን ፡ የሚ
ሉት ፡ ስሙን ፡፡ ይህም ፡ ሰው ፡ ጻድቅ ፡ የዋህም ፡ ነበረ ፡፡
የእሥራኤልንም ፡ ደስታ ፡ ተስፋ ፡ አደረገ ፡፡ መንፈስ ፡ ቅዱ
ስም ፡ ነበረበት ፡፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ተገልጾለት ፡ ነበ
ረ ፡ ሞት ፡ እንደያይ ፡ እግዚአብሔር ፡ የቀባውን ፡ ሳያይ ፡፡
በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ደረሰ ፡ ወደ ፡ መቅደስ ፡፡ አባትና ፡ እና
ቱም ፡ ብላቴናውን ፡ የሱስን ፡ ይዘው ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ ያደር
ጉለት ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ሕግ ፡ ልማድ ፡፡ በክንዱ ፡ ተሸከመ
ው ፡ እግዚአብሔርንም ፡ አመሰገነ ፡ አለም ፡፡ ዛሬ ፡ ባርያ
ህን ፡ ትተዋለህ ፡ አቤቱ ፡ በሰላም ፡ እንደ ፡ ነገርህ ፡፡ ዓይኖ
ቼ ፡ አይተዋልና ፡ ማደንህን ፡ ያዘጋጀህውን ፡ ባሕዛብ ፡ ሁ
ሉ ፡ ፊት ፡፡ ብርሃን ፡ ሁኖ ፡ አሕዛብን ፡ ያበራ ፡ ዘንድ ፡ ለሕ
ዝብህም ፡ ለእሥራኤል ፡ ክብር ፡ ሊሆን ፡፡

የዚያን ፡ ጊዜም ፡ በቤተ ፡ ልሔም ፡ ሳሉ ፡ ሰብአ ፡ ሰገ
ል ፡ ከምሥራቅ ፡ መጡ ፡ ወደ ፡ የሩሳሌም ፡ ኢያሉ ፡፡ ወዴ
ት ፡ ነው ፡ አሁን ፡ የተወለደ ፡ ያይሁድ ፡ ንጉሥ ፡፡ ኮከቡን ፡
በምሥራቅ ፡ አይተናልና ፡ መጽተንማልና ፡ እንሰግድለት ፡
ዘንድ ፡፡ ሄሮድስ ፡ ንጉሥም ፡ ሰምቶ ፡ ደነገጸ ፡ የሩሳሌም
ም ፡ ሁሉ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡፡ የካህናትንም ፡ አለቆች ፡ የሕዝ
ብንም ፡ ጻፎች ፡ ሁሉን ፡ ሰበሰበ ፡ ጠየቃቸውም ፡፡ በወዴ

ት ፡ ይወለደል ፡ ክርስቶስ ፡ ብሎ ። እርሳቸውም ፡ አሉት ።
በቤተ ፡ ልሔም ፡ በይሁዳ ፡ ዕፃ ። እንደሀ ፡ ተጽፏዋልና ፡ በ
ሚክያስ ፡ በነቢይ ። አንቺም ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ የይሁዳ ፡ ም
ድር ፡ አታንሽም ፡ ከይሁዳ ፡ ከተሞች ። ካንቺ ፡ ይወጣልና ፡
ንጉሥ ፡ ወገኖቼን ፡ እሥራኤልን ፡ የሚጠብቅ ። ከዚያ ፡ በ
ኋላም ፡ ሄሮድስ ፡ ጸራቸው ፡ የሰገልን ፡ ሰዎች ፡ በስውር ፡
ከርሳቸውም ፡ ተረዳ ፡ የታያቸውን ፡ የኰከብን ፡ ዘመን ።
ሰደደቸውም ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ልሔም ፡ አላቸውም ። ሒዱ ፡
እጅግም ፡ ምርምሩ ፡ ስለ ፡ ተወለደው ፡ ሕፃን ። ባገኛችሁ
ትም ፡ ጊዜ ፡ ንገሩኝ ፡ እኔም ፡ መጥቼ ፡ እሰግድለት ፡ ዘን
ድ ። እርሳቸውም ፡ ከንጉሥ ፡ ሰምተው ፡ ሔዱ ። እነሆ
ም ፡ በምሥራቅ ፡ ያዩት ፡ ኰከብ ፡ መራቸው ፡ መጽቶ ፡ እ
ስኪቆም ፡ ድረስ ፡ ሕፃን ፡ ባለበቱ ፡ ላይ ። ከዚያም ፡ ደርሰ
ው ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ገቡ ። ሕፃንንም ፡ አገኙት ፡ ከናቱ ፡ ከማ
ርያም ፡ ጋራ ። ወድቀውም ፡ ሰገዱለት ። ሣፅናቸውንም ፡
ከፈቱ ፡ እጅ ፡ መንሻንም ፡ ሰጡት ፡ ወርቅ ፡ ዕጣንም ፡ ከር
ቤም ። በሕልምም ፡ ታያቸው ፡ ወደ ፡ ሄሮድስ ፡ እንደይመ
ለሱ ። ተመለሱም ፡ በሌላ ፡ መንገድ ፡ ወደገራቸው ። እር
ሳቸውም ፡ ከሔዱ ፡ በኋላ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ታ
የው ፡ ለዮሴፍ ፡ በሕልም ፡ እንደሀ ፡ ሲል ። ተነሣ ፡ ሕፃኑ
ን ፡ ይዘህ ፡ ከናቱ ፡ ጋራ ። ወደ ፡ ምሥርም ፡ ሽሽ ። በዚያም ፡
ተቀመጥ ፡ እስክናገርህ ፡ ድረስ ። ሄሮድስ ፡ ሕፃንን ፡ ይሻዋ
ልና ፡ ሊገለው ። እርሱም ፡ ተነሥቶ ፡ ወሰደ ፡ ሕፃኑንና ፡ እ
ናቲቱን ፡ በሌት ። ወደ ፡ ምሥርም ፡ ሔደ ፡ ከዚያም ፡ ተቀመ
ጠ ፡ ሄሮድስ ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ። ሄሮድስ ፡ ግን ፡ ባየ ፡ ጊ
ዜ ፡ የጥበብ ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ተሣለቁበት ፡ እጅግ ፡ ተቈ
ጣ ። ሰደም ፡ ገደለ ፡ ሕፃናትን ፡ ሁሉን ፡ በቤተ ፡ ልሔምና ፡
ባጠገብዋ ፡ የነበሩትን ፡ ፪፤ አመት ፡ የሆነውን ፡ ከዚያም ፡
ያነሰውን ፡ ከሰብአ ፡ ሰገል ፡ በጠየቀው ፡ ቊጥር ። ሄሮድስ
ም ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ታየ ፡ ለዮ
ሴፍ ፡ በሕልም ፡ በምሥር ፡ እንደሀ ፡ ሲል ። ተነሣ ፡ ውሰድ ፡
ሕፃኑንና ፡ እናቱን ፡ ወደ ፡ እሥራኤልም ፡ ምድር ፡ ሒድ ።
የሕፃኑን ፡ ነፍስ ፡ የሚሹ ፡ ሙተዋልና ። እርሱም ፡ ተነሥ

ቀ ፡ ወሰደ ፡ ሕፃኑንና ፡ እናቱን ፡ ወደ ፡ እሥራኤልም ፡ ም
ድር ፡ መጣ ፡፡ አርኬላዎስም ፡ ባባቱ ፡ በሄሮድስ ፡ ስፍራ ፡
በይሁዳ ፡ እንደ ፡ ነገሠ ፡ ሰምቶ ፡ ከዚያ ፡ እንደይሔድ ፡ ፈ
ራ ፡፡ በሕልምም ፡ ታየው ፡ ወደ ፡ ገሊላ ፡ ምድርም ፡ ሔደ ፡
በናዝሬትም ፡ ተቀመጠ ፡፡

የየሱስ ፡ ዕድሜም ፡ ፲፪፡ አመት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ አባት ፡
እናቱም ፡ ወጡ ፡ ወደ ፡ የሩሳሌም ፡ በፋሲካ ፡ በዓል ፡ እን
ደ ፡ ልማዳቸው ፡፡ የሱስንም ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ወሰዱ ፡፡
ወራቱም ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ሊመለሱ ፡ ቀረ ፡ ብላቴናው ፡
የሱስ ፡ በየሩሳሌም ፡፡ ዮሴፍም ፡ እናቱም ፡ አላወቁት
ም ፡፡ ይመስላቸው ፡ ነበረና ፡ ከባልንጀሮቻቸው ፡ ጋራ ፡ ያ
ለ ፡፡ ያንድ ፡ ቀንም ፡ መንገድ ፡ ሒደው ፡ ፈለጉት ፡ ከዘመ
ዶቻቸው ፡ ከሚያውቋቸውም ፡ ዘንድ ፡፡ ባላገኙትም ፡ ጊ
ዜ ፡ ወደ ፡ የሩሳሌም ፡ ሊሹት ፡ ተመለሱ ፡፡ ከ፫፡ ቀንም ፡ በ
ኋላ ፡ አገኙት ፡ በመቅደስ ፡ ተቀምጦ ፡ በመምህራን ፡ መኻ
ከል ፡ ሲሰማቸው ፡ ሲጠይቃቸውም ፡፡ የሰማውም ፡ ሁሉ ፡
አደነቀ ፡ ከማስተዋሉ ፡ ከምላሹም ፡ የተነሣ ፡፡ ባዩትም ፡
ጊዜ ፡ አደነቁ ፡፡ እናቱም ፡ አለቸው ፡፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ ለምን ፡
እንደዚህ ፡ አደረግህልን ፡፡ እነሆ ፡ አባትህ ፡ እኔም ፡ እኻነህ ፡
ተጨንቀን ፡፡ እርሱ ፡ ግን ፡ አላቸው ፡፡ ለምን ፡ ትሹኛላች
ሁ ፡፡ አታውቁምን ፡ እንደ ፡ ገባኝ ፡ እሆን ፡ ዘንድ ፡ ላባቴ ፡
በሆነው ፡፡ እርሳቸው ፡ ግን ፡ አላወቁም ፡ ያላቸውን ፡ ነገር ፡፡
ከርሳቸውም ፡ ጋራ ፡ ወረደ ፡ ወደ ፡ ናዝሬትም ፡ መጣ ፡፡ ለ
ርሳቸውም ፡ ይታዘዝ ፡ ነበረ ፡፡ እናቱም ፡ ይህነን ፡ ነገር ፡ ሁ
ሉን ፡ በልብዋ ፡ ጠበቀች ፡፡ የሱስም ፡ አደገ ፡ በጥበብ ፡ በ
ቁመትም ፡ በጸጋም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ በሰውም ፡
ዘንድ ፡፡ ከዚያም ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ ዕድሜው ፡ ፴፡ አመት ፡
እስኪሆን ፡ ድረስ ፡ የሆነለት ፡ እግዚአብሔር ፡ አላስጻፈል
ንም ፡፡ ከርሱም ፡ ያልመጣውን ፡ ወሬን ፡ አንቀበልም ፡፡

የሱስም ፡ በግልጽ ፡ ለማስተማር ፡ ሳይነሣ ፡ መለክተኛ
ው ፡ ዮሐንስ ፡ ተነሣ ፡ መንገዱን ፡ ሊጸርግ ፡ ለክርስቶስ ፡ ቃ
ልም ፡ ወደ ፡ ሰው ፡ ልብ ፡ መግባት ፡ ሊያበጅለት ፡፡ ይህች
ን ፡ መጸሪቱን ፡ ሊፈጽም ፡ ብሎ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ሰበከ ፡

አለም ። ንስሓ ፡ ግቡ ፡ ልባችሁን ፡ ልወጡ ፡ መንግሥተ ፡ ሰ ማያት ፡ ቀርባለችና ። ማለቱ ፡ እንደህ ፡ ነበረ ። ልባችሁ ፡ የሰውም ፡ ሁሉ ፡ ልብ ፡ በኃጢአት ፡ ኑርዋልና ፡ የኃጢአት ም ፡ መውደድ ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ከመግባት ፡ ይከለክላል ። መንግሥተ ፡ ሰማያትም ፡ እግዚአብሔር ፡ የሰውን ፡ ልብ ፡ ወደ ፡ ሚገዛበት ፡ የእግዚአብሔርም ፡ ፈቃድ ፡ ወደ ፡ ሚፈጸምበት ፡ ሰውም ፡ የዘላለም ፡ ሕይወ ትንና ፡ ደህንነት ፡ ወደ ፡ ሚቀምስበት ፡ ቀርባለች ። የዚህች ፡ መንግሥት ፡ ንጉሥም ፡ መጣ ። ተነሡ ፡ ተቀበሉት ፡ በሓደ ማኖት ፡ ከኃጢአትም ፡ ከመርገምም ፡ ሽሹ ፡ ወደርሱም ፡ ሒዱ ።

ይህነንም ፡ ነገር ፡ ሰምተው ፡ የተቀበሉት ፡ ተጠመቁ ፡ በ ዮርዳኖስ ፡ ወንዝ ። የጥምቀቱም ፡ ምሥጢር ፡ ይህ ፡ ነበረ ። ምልክት ፡ ነበረ ፡ ለልብ ፡ መለወጥ ። ሰው ፡ ኃጢአቱን ፡ ለ ዮሐንስ ፡ አስታውቆ ፡ ስለርሱም ፡ አዝኖ ፡ ዮሐንስ ፡ ወደ ፡ ወንዝ ፡ አገባው ፡ ከዚያም ፡ ከውኃ ፡ በታች ፡ አወረደው ፡ ወኃ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ እስኪሔድ ፡ ድረስ ። በኋላም ፡ ወጣ ። የሰው ፡ መግባት ፡ ወደ ፡ ውኃ ፡ መጠመቁም ፡ የሞት ፡ ምሳሌ ፡ ሆነ ። "እንደሁም ፡ የኃጢአት ፡ ሰውነት ፡ ይሙ ት ፡" ማለት ፡ ነበረ ። የሰውም ፡ መውጣት ፡ ከውኃ ፡ የት ንሣኤም ፡ የሕይወቱም ፡ ምሳሌ ፡ ሆነ ። "እንደሁም ፡ የበ ጐነት ፡ የእግዚአብሔርም ፡ ሰውነት ፡ ይነሣ ፡ ይድንም ፡" ማለቱ ፡ ነበረ ።

ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ ወደ ፡ ዮሐንስ ፡ መጡ ፡ ከርሱ ፡ ይጠመ ቁ ፡ ዘንድ ፡ በዮርዳኖስ ፡ ወንዝ ። ፈሪሳውያንና ፡ ሳዱቃ ውያን ፡ ደግሞ ፡ መጡ ፡ በመጠመቃቸው ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ ክብርን ፡ ያገኙ ፡ ዘንድ ። ፈሪሳወያንም ፡ የእግዚአብሔር ን ፡ ሕግና ፡ ያባቶቻቸውን ፡ ሥርዓት ፡ በመጠበቅ ፡ በሰው ፡ ዘ ንድ ፡ ጻድቃን ፡ ይባሉ ፡ ዘንድ ፡ የፈለጉ ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ። ልባቸው ፡ ግን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ራቀ ። የእግዚአብሔር ን ፡ ሕግ ፡ የሽማግሎችም ፡ ልማድ ፡ በሥጋ ፡ መጠን ፡ ጠበ ቁ ፡ ጸሎታቸውንም ፡ ጾማቸውንም ፡ ምጽዋዕታቸውንም ፡ በግልጽ ፡ አበዙ ። በታናሽና ፡ በታላቅ ፡ ትእዛዝም ፡ በታናሽ

ና ፡ በታላቅ ፡ ኃጢአትም ፡ መኻከል ፡ መለየት ፡ አደረጉ ።
የእግዚአብሔርንም ፡ ፍርድ ፡ የፍቅርንም ፡ የምህረትን
ም ፡ ነገር ፡ ሻሩ ።

የሳዱቃውያን ፡ መለየት ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ነበረ ። እርሳቸ
ው ፡ ከሞት ፡ በኋላ ፡ ባለች ፡ ሕይወት ፡ በትንሣኤም ፡ በመ
ናፍስትም ፡ አላመኑም ። ሰው ፡ ሲሞት ፡ ሥጋና ፡ ነፍስ ፡ ይ
ሞታሉ ፡ አሉ ። እንኪደህም ፡ የኃጢአትና ፡ የበጐነት ፡ ደመ
ወዜ ፡ የለም ፡ ሰው ፡ በዚህች ፡ ሕይወት ፡ ሳለ ፡ ከሚቀ
በለው ፡ በቀር ። ከዚህም ፡ ጋራ ፡ ትምርታቸው ፡ ተሰማማች ፡
እንደህ ፡ ሲሉ ። እንብላ ፡ እንጠጠም ፡ ነጋ ፡ እንሞታለን
ና ። ስለዚህም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ መጻሕፍት ፡ ኦሪትን ፡ ብ
ቻ ፡ ሌላ ፡ አልተቀበሉም ። በኦሪትም ፡ የሙታን ፡ ትንሣኤ ፡
በጣም ፡ አልተገለጠችምና ፡ እርሳቸው ፡ በኦሪት ፡ ከቶ ፡ እ
ንደልተገኘች ፡ አስተምረው ፡ ነበረ ።

እለዚህ ፡ ፪ ወገኖችም ፡ ፈሪሳውያንና ፡ ሳዱቃውያን ፡
ወደ ፡ ዮሐንስ ፡ መጥመቅ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ እርሱ ፡ ገሠጻቸ
ው ፡ ተጻየፈቸውም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ። እላንተ ፡ የባብ ፡ ት
ውልድ ፡ ማን ፡ አሳያችሁ ፡ ከሚመጣ ፡ ቍጣ ፡ እንድትሸ
ሹ ። አሁንም ፡ አድርጉ ፡ ፍሬ ፡ ለንስሓ ፡ የሚገባ ። አይም
ሰላችሁ ፡ በነፍሳችሁ ፡ ትሉ ፡ ዘንድ ። አባታችን ፡ አብርሃ
ም ፡ ነው ። እኔ ፡ ልንገራችሁ ። እግዚአብሔር ፡ ቻይ ፡ እንደ
ሆነ ፡ ከዚህ ፡ ደንጊያ ፡ ልጆችን ፡ ለማስነሣት ፡ ለአብርሃ
ም ። እነሆ ፡ ደግሞ ፡ ምሳር ፡ ተቀምጥዋል ፡ በዛፎች ፡ ስር ።
መልካምም ፡ ፍሬ ፡ የማታፈራ ፡ ዛፍ ፡ ሁሉ ፡ ትቈረጣለ
ች ፡ ወደሳትም ፡ ትጨመራለች ። ሰውም ፡ ዮሐንስን ፡ በጠ
የቁት ፡ ጊዜ ፡ "አንተ ፡ ማነህ ፡" ብለው ። እርሱ ፡ "እኔ ፡
ክርስቶስ ፡ አይደለሁም ፡" አለ ። አንተን ፡ ኤልያስ ፡ ነህ ፡
ሲሉ ። እርሱ ፡ አለ ። "አይደለሁም ።" ወይስ ፡ ያ ፡ ነቢይ
ን ። "አይደለም ።" እርሳቸውም ፡ አሉ ። ይህ ፡ ሁሉ ፡ ካ
ልሆንህ ፡ ምንው ፡ ታጠምቃለህ ። እርሱም ፡ መለሰ ፡ አለ
ም ። "እኔ ፡ ያዋጅ ፡ ነጋሪ ፡ ድምጽ ፡ ነኝ ፡ በምድረ ፡ በዳ ።
መንገድን ፡ አስናዱ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይሳይያስ ፡ ነቢይ ፡ እ
ንደለ ። እኔም ፡ አጠምቃችኋለሁ ፡ በውኃ ። ከኔ ፡ በኋላ ፡

ግን ፡ የሚመጣ ፡ እርሱ ፡ ከኔ ፡ ይበረታል ፡፡ የጫማውን ፡ ጠፍር ፡ የማይገባኝ ፡ ተጐንብሼ ፡ እፈታው ፡ ዘንድ ፡፡ እርሱም ፡ ያጠምቃችኋል ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስና ፡ በሳት ፡፡ መሾን ፡ በጁ ፡ ያለ ፡ አውድማውን ፡ የሚያነጻበት ፡፡ ስንዴውንም ፡ ይሰበስባል ፡ በጎተራው ፡ ገለባውን ፡ ግን ፡ ያቃጥለዋል ፡ በማጠፊ ፡ እሳት ፡፡"

አሁንም ፡ ደረሰ ፡ ያ ፡ ቀን ፡ እግዚአብሔር ፡ በፊት ፡ በነቢያት ፡ አፊ ፡ በትንቢት ፡ ተስፊ ፡ ስላስደረገ ፡፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጌታችን ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ በግልጽ ፡ ለተግባሩ ፡ እንዲቀባ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በርሱም ፡ እንዲገለጽ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሰራው ፡ እንደለም ፡ መድኃኒት ፡፡ የሱስ ፡ ወደ ፡ ዮርደኖስ ፡ ሔደ ፡ ከዮሐንስ ፡ ይጠመቅ ፡ ዘንድ ፡፡ ይህችም ፡ ጥምቀት ፡ የንስሓ ፡ መግባት ፡ ምልክት ፡ ነበረች ፡፡ የሱስም ፡ ሲጠመቅ ፡ ነፍሱን ፡ ኃጢአተኛ ፡ ሁና ፡ ቍጠረ ፡፡ አሁንም ፡ እርሱ ፡ ለራሱ ፡ ኃጢአትን ፡ ሳያውቅ ፡ የኛን ፡ ኃጢአት ፡ የርሱን ፡ ኃጢአት ፡ ቍጥሮት ፡ በኛ ፡ ፈንታ ፡ ተጠመቀ ፡፡ ዮሐንስም ፡ ሲያየው ፡ አድንቆ ፡ አለው ፡፡ ለኔ ፡ ይገባኛል ፡ ካንተ ፡ እጠመቅ ፡ ዘንድ ፡ አንተም ፡ እንዴት ፡ ትመጣለህ ፡ ወደኔ ፡፡ ሊከለክለውም ፡ ፈለገ ፡፡ ደግሞ ፡ የሱስ ፡ አለው ፡፡ አሁንስ ፡ ተወው ፡፡ እንደህ ፡ ይገባናልና ፡ ጽድቅን ፡ ሁሉን ፡ እንፈጽም ፡ ዘንድ ፡፡ ጽድቅም ፡ ማለት ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰው ፡ ዘንድ ፡ የሚፈልገው ፡ እግዚአብሔርም ፡ በሕጉ ፡ የገለጸውን ፡ ፈቃደን ፡ መፈጸም ፡፡ እንደሁም ፡ ለክርስቶስ ፡ ተገባ ፡ በ፲፡ ትእዛዛት እግዚአብሔር ፡ የፈለገውን ፡ ትግባር ፡ በጣም ፡ ሊያድርግ ፡ የከለከለውንም ፡ ኃጢአት ፡ በጣም ፡ ሊተው ፡፡ ይህም ፡ ብቻ ፡ አይበቃም ፡ ነበረ ፡፡ ከአደም ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ክርስቶስ ፡ ድረስ ፡ ከቶ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አልተገኘም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ የፈጸመ ፡ ኃጢአትንም ፡ የተወ ፡፡ እስከ ፡ ፍጻሜ ፡ ዓለም ፡ ድረስም ፡ አንድ ፡ አይገኝም ፡ የሚፈጽመው ፡ ሳይበድል ፡፡ በዚህም ፡ ታላቅ ፡ ዕዳ ፡ ሆነ ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡፡ ይህነንም ፡ ዕዳ ፡ ሁሉ ፡ ሊከፍል ፡ ክርስቶስ ፡ መጣ ፡ የኃጢአትን ፡ ዋጋ ፡ በሁሉ ፡ ፈንታ ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ ያልተ

ፈጸመም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ ይፈጽም ፡ ዘንድ ፡ በ
ሁሉ ፡ ፈንታ ፡ እውነተኛ ፡ መካከለኛ ፡ ሁኖ ፡ በእግዚአብሔ
ርና ፡ በሰው ፡ መካከል ፡፡ ከእግዚአብሔርም ፡ የተለየው
ን ፡ የሰውን ፡ ወገን ፡ ሁሉ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ሊያሰ
ማማ ፡ ሊያስታርቅም ፡ የአደምንም ፡ ልጆች ፡ ወደ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ሊመልሳቸው ፡፡ ለዚችም ፡ ለመድኃኒታችን ፡ ስ
ራ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ሥልጣን ፡ እንደ ፡ ተቀበለ ፡ አ
ሁን ፡ ሊገለጽ ፡ ነበረ ፡፡

የሱስም ፡ በዮርደኖስ ፡ ወንዝ ፡ ተጠመቀ ፡፡ ከተጠመቀ
ም ፡ በኋላ ፡ ከውኃ ፡ ወጣ ፡፡ እነሆም ፡ ሰማይ ፡ ተከፈተለ
ት ፡፡ የእግዚአብሔርም ፡ መንፈስ ፡ እንደ ፡ ርግብ ፡ ሲወር
ድ ፡ አየ ፡፡ በርሱም ፡ ተቀመጠ ፡፡ ከሰማይም ፡ ድምጽ ፡ መ
ጣ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ "ልጄ ፡ ወደጄ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ በርሱ ፡ የ
ወደድሁ ፡፡" በዚህም ፡ ነገር ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ለ
ልጁ ፡ ይመሰክራል ፡፡ የሰውም ፡ መድኃኒት ፡ ሁኖ ፡
ይቀበለዋል ፡፡ ለሹመቱም ፡ ይቀድሰዋል ፡ ይቀባው
ማል ፡፡ ይህ ፡ ነገርም ፡ በብዙ ፡ ምስክሮች ፡ ይጸናል ፡፡ እንዲ
ህ ፡ ይላልና ፡ ዳዊት ፡ መዝሙር ፡ ፵፭፤ ቍ ፡ ፮፤ ፯፡፡ ዙፋንህ ፡
አምላክ ፡ ሆይ ፡ ለዘላለም ፡ ነው ፡፡ የመንግሥትህም ፡ በት
ር ፡ የቀና ፡ በትር ፡ ነው ፡፡ እውነትንም ፡ ወደድህ ፡ ዐመፃን
ም ፡ ጸላህ ፡፡ ስለዚህ ፡ አምላክ ፡ ሆይ ፡ አምላክህ ፡ ቀባህ ፡
በደስታ ፡ ዘይት ፡ እንደንተ ፡ ካሉ ፡ ይልቅ ፡፡ ጳውሎስም ፡
ይላል ፡፡ ይህነን ፡ ነገር ፡ ይላል ፡ ስለ ፡ ልጁ ፡፡ ዕብራውያን ፡
፩፤ ፰፡፡ ደግሞ ፡ ይላል ፡ ክርስቶስ ፡ በትንቢት ፡ በይሳይያስ ፡
አፍ ፡፡ ይሳይያስ ፡ ፷፩፤ ፩፡፡ የእግዚአብሔር ፡ ያምላክ ፡ መ
ንፈስ ፡ በላየ ፡ ነው ፡ ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀባኝ ፡፡
እርሱም ፡ ላከኝ ፡ ለችጋረኞች ፡ የምስራች ፡ እነግር ፡ ዘ
ንድ ፡ ልባቸው ፡ የተሰበረትንም ፡ እፈውስ ፡ ዘንድ ፡፡ የታ
ሠረትንም ፡ በመፈታት ፡ ተስፈ ፡ አስደርግ ፡ ዘንድ ፡፡ በናዝ
ሬትም ፡ በመስጊድ ፡ ሁኖ ፡ ይህነን ፡ ስፍራ ፡ በደገመ ፡ ጊዜ ፡
እንዲህ ፡ አለ ፡፡ ዛሬ ፡ ይህ ፡ መጽሐፍ ፡ በጆሮዋችሁ ፡ ተፈጸ
መ ፡፡ ሉቃስ ፡ ፬፤ ፲፰፡፡ ጴጥሮስም ፡ ይላል ፡ በማስተማሩ ፡ በ
ቆርኔልዮስ ፡ ቤት ፡ ሳለ ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ይህነን ፡ የሱስ ፡

ናዝራዊውን ፡ ቀባ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በኃይልም ፡፡ የሐዋር
ያት ፡ ሥራ ፡ ፲፡ ፴፰፡፡ ዮሐንስ ፡ መጥመቅም ፡ ይላል ፡፡ እግዚ
አብሔር ፡ መንፈሱን ፡ ሰፍሮ ፡ እንደልሰጠው ፡፡ ዮሐንስ ፡ ፫፡
፴፬፡፡ ለዚችም ፡ መቀባት ፡ ምሳሌ ፡ ነበረ ፡ በብሉይ ፡ ሥርዓ
ት ፡፡ የእግዚአብሔር ፡ ባሮች ፡ እርሳቸውም ፡ ነገሥታትና ፡
ካህናት ፡ ነቢያትም ፡ ተግባራቸውን ፡ ሲይጀምሩ ፡ ተቀቡ ፡
በተቀደሰች ፡ ቅቤ ፡፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ መካከለኞችን ፡
ንጉሥ ፡ ካህንም ፡ ነቢይም ፡ ባንድ ፡ ለመሆን ፡ በሰውነቱ ፡
ተቀባ ፡፡ እለዚያም ፡ ለሚጠፋ ፡ ማገልገል ፡ በሚጠፋ ፡ ቅ
ቤ ፡፡ እርሱ ፡ ግን ፡ ለዘላለም ፡ ማገልገሉ ፡ በማይጠፋ ፡ ቅቤ ፡
በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡፡

አሁንም ፡ ትምህርቱን ፡ ሳይገባ ፡ መንፈስ ፡ ወሰደው ፡ ወ
ደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ከዚያ ፡ ሊ ፈት ን ፡ ከዲያብሎስ ፡፡ ከዚ
ያም ፡ ፵፡ ቀን ፡ ፵፡ ሌሊትም ፡ ጹሞ ፡ ተራበ ፡፡ ፈታኙም ፡
መጣበት ፡ አለውም ፡፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ሆ
ንህ ፡ በል ፡ እሌህ ፡ ደንጎች ፡ እንጀራ ፡ እንዲሆኑ ፡፡ እርሱ
ም ፡ መለሰለት ፡ አለውም ፡፡ ተጽፏዋል ፡፡ በንጀራ ፡ ብቻ ፡
ሰው ፡ እንደይድን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ካፉ ፡ በምት
ወጣ ፡ እንጅ ፡፡ ከዚያም ፡ ወሰደው ፡ ሰይጣን ፡ ወደ ፡ ቅድ
ስት ፡ አገር ፡ ወደ ፡ የሩሳሌም ፡፡ በቤተ ፡ መቅደስም ፡ ጫፉ ፡
ላይ ፡ አቆመው ፡ አለውም ፡፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ እን
ደ ፡ ሆንህ ፡ ሰውነትህን ፡ ጣል ፡ ወደ ፡ ታች ፡፡ ተጽፏዋልና ፡
እንዲያዝ ፡ መለክተኞቹን ፡ ስላንተ ፡ በጀቸው ፡ እንዲያን
ሡህ ፡፡ እግርህ ፡ በደንጊያ ፡ እንዳትሰናከል ፡፡ የሱስም ፡ አ
ለው ፡፡ ደግሞ ፡ ተጽፏዋል ፡፡ አምላክህን ፡ እግዚአብሔር
ን ፡ አትፈታተን ፡፡ ደግሞ ፡ ወሰደው ፡ ሰይጣን ፡ እጅግ ፡ ወ
ደ ፡ ረዘመ ፡ ተራራ ፡፡ ያለምንም ፡ ሁሉ ፡ መንግሥታት ፡ ክብ
ርዋንም ፡ አሳየው ፡፡ አለውም ፡፡ ይህነን ፡ ሁሉ ፡ እሰጥሃለ
ሁ ፡ ለኔ ፡ ሰግደህ ፡ ብትወድቅ ፡፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ክርስቶ
ስ ፡ አለው ፡፡ ራቅ ፡ ከኔ ፡ አንተ ፡ ሰይጣን ፡፡ ተጽፏዋልና ፡፡ ለ
እግዚአብሔር ፡ ላምላክህ ፡ ስገድ ፡፡ እርሱንም ፡ ብቻውን ፡
አምልክ ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ሰይጣን ፡ ተወው ፡፡ እነሆም ፡
መላእክት ፡ መጡ ፡ ሊያገለግሉት ፡ ማቴዎስ ፡ ፬፡፡

በዚህ ፡ ነገርም ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሰውነቱ ፡ ሁለተኛ ፡
አደም ፡ ሁኖ ፡ ይገለጻል ፡ መጀመርያ ፡ አደም ፡ የበደለ
ውን ፡ ለመሻር ፡ የመጣ ፡፡ እግዚአብሔርም ፡ መጀመርያ
ውን ፡ አደም ፡ ወደ ፡ ተድላ ፡ ገነት ፡ አስቀመጠው ፡ ሊሰራ
ው ፡ ሊጠብቀውም ፡፡ ከዛፉም ፡ ፍሬ ፡ ሁሉ ፡ ሊበላ ፡ አዘ
ዘው ፡ መልካምንና ፡ ክፉን ፡ ከሚያስታውቀው ፡ ዛፍ ፡ በ
ቀር ፡፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ አፍርሶ ፡ ከዚች ፡ አን
ዲት ፡ ዛፍ ፡ ግን ፡ ቢበላ ፡ ሞት ፡ ሊሙት ፡ ነበረ ፡፡ በዚህ ፡ ት
እዛዝም ፡ እግዚአብሔር ፡ የፈለገው ፡ ነገር ፡ ቃሊል ፡ ነበር ፡፡
መታዘዝ ፡ ብቻ ፡ ፈለገ ፡፡ ሰውም ፡ ገና ፡ ኃጢአትና ፡ ድካም ፡
አልነበረበትምና ፡ ወደ ፡ ኃጢአትም ፡ አልዘነበለም ፡፡ የእ
ግዚአብሔርንም ፡ ፍቅር ፡ አወቀ ፡ ስለዚህ ፡ ማሸነፉ ፡ ተቻ
ለው ፡፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ግን ፡ ከሰማያዊ ፡ ገነት ፡ መጥ
ቶ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ በዳ ፡ ወሰደው ፡ መ
ብል ፡ የሌለበት ፡፡ ካራዊትም ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፡ ቅዱስ ፡ ማርቆ
ስ ፡ እንደ ፡ ል ፡፡ መጀመርያ ፡ አደምም ፡ ልቡ ፡ የወደደውን ፡
መብል ፡ ሁሉ ፡ ባገኘው ፡ ፈንታ ፡ ሁለተኛ ፡ አደም ፡ ፵፡ ቀን ፡
፵፡ ሌሊትም ፡ ጾመ ፡፡ ጾሙም ፡ ብርቱ ፡ ጾም ፡ ነበረ ፡ አንደ
ችን ፡ አልቀመሰምና ፡፡ ሙሴም ፡ በውነት ፡ ፪፡ ጊዜ ፡ ከእግዚ
አብሔር ፡ ጋራ ፡ ሲሆን ፡ እርሱ ፡ ደግሞ ፡ ፵፡ ቀንና፡ ፵፡ ሌሊ
ት ፡ ሳይበላ ፡ ሳይጠጠም ፡ ይሰነብት ፡ ነበረ ፡፡ ደሮ ፡ እንደሁ ፡
አድርጎ ፡ አልተራበም ፡ እግዚአብሔርን ፡ በማየት ፡ ጸገበ ፡
እንጂ ፡፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ግን ፡ በሥጋና ፡ በነፍስ ፡ አንደ
ችን ፡ አልቀመሰም ፡ በጣም ፡ ጾመ ፡ እንጂ ፡፡ ኤልያስም ፡
እርሱ ፡ ደግሞ ፡ ፵፡ ቀን ፡ አርብዓ ፡ ሌሊትም ፡ ሳይበላ ፡ ሳይ
ጠጠም ፡ ኑሮ ፡ መንገዱን ፡ ሔደ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ ወደ ፡ ኮሬ
ብ ፡ ተራራ ፡፡ ደሮ ፡ ኤልያስ ፡ መልአክ ፡ በሰጠው ፡ መብል ፡
ኃይል ፡ አገኘ ፡ ለዚህ ፡ መንገድ ፡፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ግን ፡
የአደምን ፡ ኃጢአት ፡ የሰውንም ፡ ሁሉ ፡ ምድራዊ ፡ መመ
ኘት ፡ ሊያስታርቅ ፡ ብሎ ፡ እንደሁ ፡ ያለውን ፡ ኃይል ፡ አጠ ፡፡
ምንድር ፡ ይላልና ፡ ጳውሎስ ፡ ወደ ፡ ዕብራውያን ፡ ፬፡ ፲፭፡፡
የካህናት ፡ አለቃ ፡ የለነምና ፡ የማይችል ፡ ሕማም ፡ ይቀበ
ል ፡ ዘንድ ፡ ከድካማችን ፡ ጋራ ፡፡ በሁሉ ፡ የተፈተነ ፡ ነው ፡

እንጂ ፡ እንደኛ ፡ ከኀጢአት ፡ በቀር ፡፡ አሁንም ፡ የሱስ ፡ ፵፤ ቀንና ፡ ፵፤ ሌሊት ፡ አንደኛችን ፡ ካልቀመሰ ፡ በኋላ ፡ ተራበ ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሰይጣን ፡ ቀረበለት ፡፡ ይህም ፡ በክፉ ፡ ጊዜ ፡ ነበረ ፡፡ ሰይጣን ፡ ወደ ፡ ሔዋ ፡ መጣ ፡ በገነት ፡ እርስዋ ፡ ከአደም ፡ ጋራ ፡ ስትጸግብ ፡ በበጎ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡፡ በዚህ ፡ ለፊተኞች ፡ ወላጆቻችን ፡ ቃሊል ፡ የሆነ ፡ በሰይጣን ፡ ላይ ፡ ማሸነፍ ፡ ለሁለተኛ ፡ አደም ፡ ቸገረ ፡፡ ደግሞ ፡ እርሳቸው ፡ ጸግበው ፡ ወደቁ ፡፡ የሱስ ፡ ግን ፡ ተርቦ ፡ አሸነፈ ፡፡ ሲርብም ፡ ፈታኙ ፡ ወደርሱ ፡ ቀረበ ፡፡ ምናልባት ፡ በብርሃን ፡ መልአክ ፡ መልክ ፡ የሱስ ፡ እንደያውቀው ፡ ብሎ ፡፡ መንገድንም ፡ አሳየው ፡ ራቡን ፡ ለመቍርጥ ፡፡ "የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ሆንህ ፡ በል ፡ እሌህ ፡ ደንጎች ፡ እንጀራ ፡ እንዲሆኑ ፡፡" የሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ በውነት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ነበረ ፡፡ ደግሞ ፡ አሁን ፡ የትሕትና ፡ ጊዜ ፡ የመዋረድም ፡ ጊዜ ፡ ነበረ ፡ የልጅነት ፡ ጊዜ ፡ አይደለም ፡፡ ስለዚህም ፡ አሁን ፡ የደንጊያ ፡ መለወጥ ፡ በወደደ ፡ ያድነን ፡ ዘንድ ፡ ባልተቻለው ፡፡ እንዴት ፡ አሸነፈ ፡ የሱስ ፡ ፈታኙን ፡፡ እርሱ ፡ መለሰለት ፡ አለም ፡፡ ተጽፎዋል ፡፡ በንጀራ ፡ ብቻ ፡ ሰው ፡ እንደይድን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ እንጂ ፡ ካፉ ፡ በምትወጣ ፡፡ የሱስም ፡ "ተጽፎዋል ፡" ሲል ፡ የመንፈስን ፡ ሰይፍ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ያዘ ፡ ከርሱም ፡ ሰይጣን ፡ ይፈራል ፡፡ ከዚያም ፡ ወሰደው ፡ ሰይጣን ፡ ወደ ፡ ቅድስት ፡ አገር ፡ ወደ ፡ የሩሳሌም ፡ በቤተ ፡ መቅደስም ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡ አቆመው ፡፡ በዚህም ፡ ይታያል ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ልጁን ፡ እንዴት ፡ እጅግ ፡ አንደ ፡ አዋረደው ፡ ከመላእክትም ፡ በታች ፡ እንደ ፡ አደረገው ፡ ለሰይጣን ፡ እንኳ ፡ ኃይል ፡ ትቶት ፡ በተቀደሰ ፡ በየሱስ ፡ ሥጋ ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ፈቃዱ ፡ ሊወስደው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደስ ፡ ጫፍ ፡ ላይ ፡፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፡ በ፰፤ መዝሙር ፡፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ ትጐበኘው ፡ ዘንድ ፡፡ ጥቂት ፡ አሳነስኸው ፡ ከመላእክት ፡፡ ወደ ፡ ዕብራውያንም ፡ በ፪፤ ምዕራፍ ፡ ይላል ፡፡ ከመላእክት ፡ ጥቂት ፡ የተዋረደው ፡ እናያለን ፡ እርሱ ፡ የሱስ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡፡ ሰይጣንም ፡ የሱስን ፡ አለው ፡፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ሆንህ ፡ ሰውነትህን ፡ ጣል ፡

ወደ ፡ ታች ፡፡ ይህም ፡ የሰይጣን ፡ መፈተን ፡ ፪፤ መክን ያት ፡ ነበረለት ፡፡ ፩፤ ትዕቢትን ፡ ሊዘራ ፡ በክርስቶስ ፡ ል ብ ፡ እንዲሁም ፡ አድርጎ ፡ መድኃኒታችንን ፡ ሊሽር ፡፡ ፪፤ ሊገድለው ፡ ሰውነቱን ፡ ወደ ፡ ታች ፡ የጣለ ፡ እንደሆነ ፡፡ ሰይጣንም ፡ ክርስቶስ ፡ እንዲህ ፡ እንዲያደርግ ፡ አልተጠ ራጠረም ፡፡ በክርስቶስ ፡ አሳብ ፡ አድርጎበታልና ፡ ሰው ፡ ቢያዩት ፡ ከመቅደስ ፡ ራስ ፡ ወርዶ ፡ እንደ ፡ መጣባቸው ፡ ወ ደ ፡ ታች ፡ ያምኑበት ፡ ዘንድ ፡ እንደላቸው ፡፡ ሰይጣንም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አሰበ ፡፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በኃይሉ ፡ ያለ ፡ መንገድ ፡ በንፋስ ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡ ወደ ፡ መቅደሰ ፡ ጫ ፍ ፡ እርሱም ፡ አሁን ፡ እንዲይጠራጠር ፡ ይህ ፡ መንገድ ፡ በ ንፋስ ፡ አድርጎ ፡ እንዲቻለው ፡፡ መውረዱ ፡ ግን ፡ ከቶ ፡ እን ደይቀር ፡ ብሎ ፡ ምክሩን ፡ ደገፈ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንዲያምን ፡ አ ደትዋልና ፡፡ እንዲሁም ፡ ብሎ ፡ ጨመረ ፡፡ "ተጽፎዋልና ፡፡ እን ዲያዝ ፡ መልክተኞቹን ፡ ስላንተ ፡ በጀቸው ፡ እንዲያነሡህ ፡ እ ግርህ ፡ በደንጊያ ፡ እንዳትሰናከል ፡፡" ይህም ፡ ተስፈ ፡ ይገኛል ፡ መዝሙር ፡ ፺፩፡፡ ከዚያም ፡ ዳዊት ፡ ይላል ፡፡ መልክተኞቹን ፡ ስላንተ ፡ ያዛልና ፡ ይጠብቁህ ፡ ዘንድ ፡ በመንገድህ ፡ ሁሉ ፡፡ በጀቸውም ፡ ላይ ፡ ያነሡሃል ፡ እግርህ ፡ በደንጊያ ፡ እንዳትሰ ናከል ፡፡ ሰይጣን ፡ ተንኰለኛ ፡ ነውና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነ ገር ፡ እንዲያው ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ አያመሰክረውም ፡ እንደ ፡ ፈቃዱ ፡ እንጅ ፡፡ እንዲትንም ፡ ነገር ፡ ከዚህች ፡ ተስፈ ፡ ቆ ረጠ ፡ እርስዋም ፡ ይህች ፡ ናት ፡፡ በመንገድህ ፡ ሁሉ ፡፡ የ ዚህም ፡ ማለት ፡ ይህ ፡ ነው ፡፡ በእግዚአብሔር ፡ ሥርዓት ፡ ብትኖር ፡ እግዚአብሔርም ፡ ባደረገልህ ፡ መንገድ ፡ ብትሔ ድ ፡ መላእክቱ ፡ ይጠብቁሃል ፡፡ አሁንም ፡ የየሱስ ፡ ክርስቶ ስ ፡ መንገድ ፡ ሰይጣን ፡ እንደሳየው ፡ አልነበረም ፡፡ ስለዚ ህም ፡ የሱስ ፡ ይህነን ፡ ንገር ፡ ለመሻር ፡ ሌላውን ፡ ነገር ፡ ወ ሰደ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ ደግሞ ፡ ተጽፎዋል ፡፡ አምላክህን ፡ እግዚአብሔርን ፡ አትፈታተነው ፡፡ አሁንም ፡ ሰይጣን ፡ አ ደተ ፡ የሱስ ፡ ብርቱ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ በትሕትና ፡ በመታዘዝ ም ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ቃል ፡ የብርሃንን ፡ መልአክ ፡ መል

ክ፡ ትቶ፡ እንደ፡ ሰይጣን፡ አደረገ። ወደ፡ ረጅም፡ ተራራ፡ ወስዶት፡ ያለምን፡ ሁሉ፡ መንግሥታት፡ ክብርዋንም፡ አሳየው፡ አለውም። ይህነን፡ ሁሉ፡ እሰጥሃለሁ፡ ለኔ፡ ሰግደህ፡ ብትወድቅ። ከዚያ፡ ወዲያም፡ የሱስ፡ አለው። ራቅ፡ ከኔ፡ አንተ፡ ሰይጣን፡ ተጽፏዋና። ለእግዚአብሔር፡ ላምላክህ፡ ስገድ፡ እርሱንም፡ ብቻውን፡ አምልክ። እንዲህም፡ የሱስ፡ ሁለተኛ፡ አደም፡ ሁኖ፡ ሰይጣንን፡ አሸነፈ፡ ሰይጣንም፡ ተወው። እነሆም፡ መላእክት፡ መጡ፡ ሊያገለግሉት። ማቴዎስ፡ ፬።

አሁንም፡ የሱስ፡ ክርስቶስ፡ ማስተማሩን፡ ጀመረ። ወደ፡ ገሊላ፡ አገርም፡ ሒደ፡ ቅፍርናሆምን፡ መረጸ፡ ሊቀመጥበት። መጀመርያው፡ ቃሉም፡ የዮሐንስን፡ ስብከት፡ ተመሰለ፡ እንዲህ፡ ሲል። ንስሓ፡ ግቡ፡ መንግሥት፡ ሰማያት፡ ቀርባለችና። ደቀ፡ መዛሙርቱንም፡ መረጸ፡ ሊከተሉት፡ ቃሉንም፡ ሊዙት፡ ስራውንም፡ ሊያዩ፡ በኋላም፡ መለክተኞቹ፡ ሊሆኑ፡ የወንጌሉን፡ የምስራች፡ ያወጡ፡ ዘንድ፡ ወደ፡ ዓለም፡ ሁሉ። ብዙ፡ ሰዎችም፡ ወደርሱ፡ ተሰበሰቡ። ከርሳቸውም፡ ጋራ፡ ወደ፡ ተራራ፡ ወጣ፡ በላይም፡ ተቀምጦ፡ አስተማራቸው፡ እንዲህ፡ ብሎ፡ ሲጀምር። ብፁዓን፡ ናቸው፡ ድኆች፡ በመንፈስ። መንግሥተ፡ ሰማያት፡ ለርሳቸው፡ ናትና። 'ድኆችም፡ በመንፈስ፡' እሌህ፡ ናቸው፡ ከመንፈስ፡ ቅዱስ፡ ተምረው፡ በልባቸው፡ የሚያውቁ፡ እግዚአብሔርን፡ ደስ፡ የሚያሰኘውን፡ በጎ፡ ነገርን፡ ሁሉን፡ እንዳጡ። መንፈሳዊት፡ ድኅነቱንና፡ ችጋሩን፡ የሚያውቅ፡ ሰው፡ ከእግዚአብሔር፡ ይለምናልና፡ የሚለምንም፡ ይቀበላል። ስለዚህም፡ ይጨምራል፡ እንዲህ፡ ሲል። መንግሥተ፡ ሰማያት፡ ለርሳቸው፡ ናትና። ብፁዓን፡ ናቸው፡ የሚያዝኑ፡ (በኃጢአታቸው፡ መክንያት፡) እግዚአብሔርን፡ በድለውበታልና። እርሳቸው፡ በወንጌል፡ የምስራች፡ ደስ፡ ይላቸዋልና፡ ከውንጌል፡ ሲያውቁ፡ እግዚአብሔር፡ ኃጢአታቸውን፡ ሁሉን፡ እንዲያስቀርላቸው። ገሮችም፡ ልባቸው፡ የተዋረደ፡ ብፁዓን፡ ናቸው፡ ምድርን፡ ይወርሳሉና፡ አሁን፡ በሃይማኖት፡ በኋላም፡ በማየት፡ በተቀደሰች፡

ምድር ፡፡ ጽድቅንም ፡ ተናፋቀው ፡ የሚራቡ ፡ የሚጸሙ
ም ፡፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ጻድቃን ፡ ሁነው ፡ መቈጠር ፡
የሚሹ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ መጸደቅ ፡ ከመብላትና ፡ ከ
መጠጥ ፡ ይልቅ ፡ የሚፈልጉ ፡ እርሳቸውም ፡ ብፁዓን ፡ ናቸ
ው ፡፡ ይጸግባሉና ። የሚሹትን ፡ ጽድቅ ፡ በክርስቶስ ፡ ደም ፡
በጣም ፡ ያገኙታልና ፡ ያለ ፡ መግባር ፡ በሃይማኖት ፡ ብቻ ፡፡
መሓሮችም ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፡፡ እንደ ፡ ጳውሎስ ፡ በውነት ፡
ማለት ፡ የሚችሉ ፡፡ እኔ ፡ ታላቅ ፡ ኃጢአተኛ ፡ ነኝ ፡ ደሮ ፡ ም
ህረት ፡ አገኘሁ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ይቅር ፡ ያለልኝ ፡ ኃጢአ
ቴን ፡፡ እርሳቸውም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ምህረት ፡ የተቀበ
ሉት ፡ ምህረትም ፡ ለወንድሞቻቸው ፡ ሲያሳዩት ፡ ብፁዓ
ን ፡ ናቸው ፡፡ እርሳቸውም ፡ ምህረት ፡ ይደገምላቸዋል ፡፡ ብ
ፁዓን ፡ ናቸው ፡ ልባቸው ፡ የነጻ ፡ በክርስቶስ ፡ ደምና ፡ በመ
ንፈሱ ፡ በሃይማኖት ፡፡ እርሳቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያዩታ
ልና ፡፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፡ በወንጌል ፡ የተገኘ ፡ ዕርቅ ፡ የሚያ
ደርጉ ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በሰው ፡ መኻከል ፡ በሰዎችም ፡
እርሱ ፡ በርሳቸው ፡ መኻከል ፡፡ እርሳቸው ፡ የእግዚአብሔ
ር ፡ ልጆች ፡ ይባላሉና ፡፡ ስለ ፡ ጽድቅም ፡ የተሳደዱ ፡ ብፁዓ
ን ፡ ናቸው ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ለርሳቸው ፡ ናትና ፡፡ እ
ላንተ ፡ ብፁዓን ፡ ናችሁ ፡ በሰደብዋችሁ ፡ ባሳደድዋችሁም ፡
ጊዜ ፡፡ በላያችሁም ፡ ክፉን ፡ ነገር ፡ ሁሉን ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ በ
ሐሰት ፡ ስለኔ ፡፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ፡ ሐሤትም ፡ አድርጉ ፡፡ ዋጋ
ችሁ ፡ ታላቅ ፡ ነውና ፡ በሰማያት ፡፡ እንደህ ፡ አሳደዋልና ፡ ነ
ቢያትን ፡ በፊታችሁ ፡ የነበሩትን ፡፡

እንደህም ፡ ብሎ ፡ ሲናገር ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ዓ
ለም ፡ መድኃኒት ፡ ይገለጻል ፡ በዓለም ፡ ሊፈርድ ፡ እንደል
መጣ ፡ ዓለም ፡ በርሱ ፡ ሊድንበት ፡ እንጂ ፡፡ መድኃኒቱን ፡ ግ
ን ፡ ከለልባችን ፡ እንሻ ፡ ዘንድ ፡ እርሱ ፡ ያሳየናል ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ ከሰው ፡ ሁሉ ፡ የሚፈልገውን ፡ ነገር ፡ የሕግም ፡ ፍ
ጻሜ ፡ ምንድር ፡ ነው ፡፡ እርሱ ፡ ያስተምርናል ፡ ጽድቃችን ፡
ከፈሪሳውያን ፡ ጽድቅ ፡ ባይሻል ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ እንደንገባ ፡፡ መጽዋትም ፡ ቢሆን ፡ ጾምም ፡ ቢሆ
ን ፡ ከልብ ፡ ካልወጣ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድም ፡ ካልተ

ደረገ ፡ እንደርሱም ፡ ካልሆነ ፡ አንደኛችን ፡ አይጠቅምም ፡፡ የጸሎትም ፡ ሁሉ ፡ መሳሌ ፡ እንደህ ፡ ሲል ፡ ይሰጠናል ፡፡ "አባታችን ፡ ሆይ ፡ በሰማይ ፡ የምትኖር ፡፡ ስምህ ፡ ይቀደስ ፡፡ መንግሥትህ ፡ ትምጻ ፡፡ ፈቃድህ ፡ በምድር ፡ ትሁን ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ በሰማይ ፡፡ እንጀራችንን ፡ የሚበቃነን ፡ ስጠነ ፡ ዛሬ ፡፡ ደቅር ፡ በለነ ፡ በኛ ፡ ያለውን ፡ እኛ ፡ ደግመን ፡ ይቀር ፡ እንደ ምንል ፡ ለኛ ፡ ያለባቸውን ፡፡ ወደ ፡ መፈተንም ፡ አታግባን ፡ ከክፉ ፡ አድነን ፡ እንጂ ፡፡ ያንተ ፡ ነውና ፡ መንግሥት ፡ ኃይልም ፡ ምስጋናም ፡ ለዘላለም ፡፡ አሜን ፡፡" በዚህም ፡ ጸሎት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ የሰውም ፡ መሻት ፡ የእግዚአብሔርም ፡ ለሃይማኖት ፡ የሰጠው ፡ ተስፋ ፡ ሁሉ ፡ ይገኝ በታል ፡፡ ለሃይማኖትም ፡ የሰማይን ፡ መንገድ ፡ ያሳያል ፡፡ ሃይማኖት ፡ በመልመን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ አንድነት ፡ ያድርጋልና ፡፡

የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስብከቱን ፡ በተራራ ፡ ላይ ፡ ሲጨርስ ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ አደነቁ ፡ በትምርቱ ፡፡ ያስተምራቸው ፡ ነበረና ፡ ሥልጣን ፡ እንዳለው ፡ እንደ ፡ ጻፎችም ፡ አይደለም ፡፡

ከዚያ ፡ ወዲያም ፡ ያችን ፡ ምድር ፡ በትምህርቱ ፡ መላ ፡፡ ድንቅም ፡ ተአምራትም ፡ አደረገ ፡ ለሁሉም ፡ በጎ ፡ አደረገ ፡ በኃጢአታቸውም ፡ መዳን ፡ የፈለጉትን ፡ ሁሉ ፡ ወደር ሱ ፡ ጸራ ፡፡ በቀንና ፡ በሌሊትም ፡ አልደከመም ፡ መድኃኒታችነን ፡ በመስራት ፡፡ ምሳሌንም ፡ ሰጠ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ለሚያምኑበትም ፡ ሁሉ ፡ ፍለጋውን ፡ እንከተል ፡ ዘንድ ፡፡ ቍጥራቸውም ፡ ከበዛ ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ፲፪፡ መረጸ ፡ በዓለም ፡ ሁሉ ፡ ወንጌሉን ፡ ያስተምሩ ፡ ዘንድ ፡ ለ ታላቅ ፡ ስሙም ፡ ይመሰክሩ ፡ ዘንድ ፡፡ የ፲፪፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ስም ፡ ይህ ፡ ነው ፡፡ መጀመሪያው ፡ ሲሞን ፡ ጴጥሮስ ፡ የተባለ ፡ እንድርያስም ፡ ወንድሙ ፡፡ ያዕቆብም ፡ የዘብደዎስ ፡ ልጅ ፡ ዮሐንስም ፡ ወንድሙ ፡፡ ፊልጶስም ፡፡ በርተሎሚዎስም ፡፡ ቶማስም ፡ ማቴዎስም ፡ አጣሪ ፡፡ ያዕቆብም ፡ የእልፍዮስ ፡ ልጅ ፡ ልብደዎስም ፡ ተደዎስ ፡ የተባለ ፡፡ ሲሞንም ፡ ቀነናዊ ፡ ይሁዳም ፡ ያስቆሮቱ ፡ እርሱም ፡ ደግሞ ፡ ያስያዘው ፡፡ እርሳቸውንም ፡ በመምረጽ ፡ እንደ ፡ እግ

ዚአብሔር ፡ ሥርዓት ፡ አደረገላቸው ፡ ጳውሎስ ፡ እንዲል ፡፡
እዩ ፡ እንዴት ፡ ተጸራችሁ ፡ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፡፡ ከላንተ ፡ እ
ጅግ ፡ ጠቢባን ፡ የለባችሁምና ፡ በሥጋ ፡፡ እጅግም ፡ ኀያላ
ን ፡ የለባችሁም ፡፡ እጅግም ፡ የዘመድ ፡ ታላቅነት ፡ የላች
ሁም ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ መረጸ ፡ የዚህ ፡ ዓለም
ን ፡ ሰነፎች ፡ ጠቢባንን ፡ በርሳቸው ፡ ያሳፈር ፡ ዘንድ ፡፡ የዚ
ህ ፡ ዓለምንም ፡ ደካሞች ፡ መረጸ ፡ ኃያላንን ፡ ያሳፈር ፡ ዘ
ንድ ፡፡ የዘመድ ፡ ታላቅነት ፡ የሌላቸውንም ፡፡ በዚህ ፡ ዓለ
ም ፡ የተናቁትንም ፡ እግዚአብሔር ፡ መረጣቸው ፡ ያልተ
ቈጠሩትንም ፡ የተቈጠሩትን ፡ ከንቱ ፡ ያድርግ ፡ ዘንድ ፡፡
እንደይመካ ፡ ሥጋ ፡ ሁሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡፡ ፩፤ ቆሮ
ንቶስ ፡ ፩፤ ፳፯፤፡ ከ፲፪፤ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ከወንጌል ፡ እን
ደወቅናቸው ፡ አንድ ፡ በሥጋ ፡ የከበረ ፡ አልነበረም ፡፡ ሲሞ
ን ፡ ጴጥሮስና ፡ እንድርያስ ፡ ወንድሞች ፡ ዮሐንስና ፡ ያዕቆ
ብም ፡ ወንድሞች ፡ አፅማጆች ፡ ነበሩና ፡፡ ማቴዎስም ፡ አ
ጣሪ ፡ ነበር ፡፡ ያዕቆብም ፡ የእልፍዮስ ፡ ልጅ ፡ ልብዴዎስ
ም ፡ በሌላ ፡ ስፍራ ፡ ይሁዳ ፡ የተባለ ፡ ሲሞንም ፡ ቀነናዊ ፡
በሥጋ ፡ የየሱስ ፡ ዘመድ ፡ ነበሩ ፡፡ ስለ ፡ ሌሎችም ፡ አናው
ቅም ፡ ምንድር ፡ ነበሩ ፡ ወደ ፡ የሱስ ፡ ሳይመጡ ፡፡ ስለ ፡ አ
ካሔደቸውም ፡ ከወንጌል ፡ እናውቃለን ፡ ጌታችነን ፡ እጅ
ግ ፡ እንደደከሙት ፡ በሃይማኖታቸው ፡ መጒደል ፡ በልባቸ
ውም ፡ መክበድ ፡ ለማስተዋል ፡፡ ሥጋዊንም ፡ ክብር ፡ በ
መመኘታቸው ፡ በሌላ ፡ ሥጋዊ ፡ ነገርም ፡ በጠባያቸው ፡፡ የ
ሱስ ፡ ስንት ፡ ጊዜ ፡ ገሠጸ ፡ ጴጥሮስን ፡፡ የጴጥሮስ ፡ ልብ ፡ በ
ውነት ፡ ለክርስቶስ ፡ ተሰጠ ፡ የክርስቶስም ፡ መንፈስ ፡ በል
ቡ ፡ ሰራ ፡፡ ደር ፡ ኃጢአተኛና ፡ ሥጋዊ ፡ ጠባዩ ፡ ሁለጊዜ ፡ ወ
ደ ፡ ክፉ ፡ ዘነበለ ፡ በበጎ ፡ ነገርም ፡ አልጸናም ፡፡ ክርስቶስ ፡
ችሎቱንና ፡ ቸርነቱን ፡ በመጀመርያ ፡ በመርከብ ፡ ባሳየው ፡
ጊዜ ፡ መጽመደን ፡ ሲባርክለት ፡ የክርስቶስ ፡ መንፈስ ፡ ብ
ርሃን ፡ ሰደደ ፡ ወደ ፡ ልቡ ፡ እርሱም ፡ አለው ፡፡ አቤቱ ፡ ው
ጣ ፡ ከኔ ፡ እኔ ፡ ኃጢአተኛ ፡ ሰው ፡ ነኝና ፡፡ ጴጥሮስም ፡ በዕ
ድሜ ፡ ከቀሩ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ በለጠ ፡ እርሱም ፡ ስለ
ዚህ ፡ በሌሎች ፡ ፊንታ ፡ በስማቸውም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡

ተናገረ ፡፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የሱስ ፡ ጠየቃቸው ፡፡ ምንድር ፡ ይሉ
ኛል ፡ ሰዎች ፡ እኔ ፡ ማን ፡ እንድሆን ፡፡ እርሳቸው ፡ አሉ ፡፡
"መጥመቅ ፡ ዮሐንስ ፡ ነው ፡" የሚሉህ ፡ አሉ ፡፡ እኩሉም ፡
ኤልያስ ፡፡ እኩሉም ፡ ኤርምያስ ፡ ወይስ ፡ ከነቢያት ፡ አን
ድ ፡ ነው ፡፡ የሱስም ፡ አሁን ፡ ሲላቸው ፡፡ እላንተስ ፡ ምን ፡
ትላላችሁ ፡ እንደ ፡ ሆንሁ ፡፡ ሲሞን ፡ ጴጥሮስ ፡ አለው ፡፡ አ
ንተ ፡ ነህ ፡ ክርስቶስ ፡ የሕያው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡፡
የሱስም ፡ መለሰ ፡ እንዲሁም ፡ አለው ፡፡ ብፁዕ ፡ ነህ ፡ አን
ተ ፡ ሲሞን ፡ ሆይ ፡ የዮና ፡ ልጅ ፡፡ ሥጋና ፡ ደም ፡ አልገለጸል
ህምና ፡ ይህነን ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ የሰማዩ ፡ አባቴ ፡፡ እኔም ፡ እ
ልሃለሁ ፡፡ አንተ ፡ የደንጊያ ፡ ሰው ፡ ነህ ፡፡ በዚችም ፡ ደንጊ
ያ ፡ ላይ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኔን ፡ እሰራለሁ ፡፡ የገሃናም ፡ ደ
ጆችም ፡ አይጸኑባትም ፡፡ የመንግሥተ ፡ ሰማያትንም ፡
መክፈቻ ፡ እሰጥሃለሁ ፡፡ በምድር ፡ የምታሥረው ፡ በ
ሰማያትም ፡ የታሠረ ፡ ይሁን ፡፡ በምድርም ፡ የምትፈታ
ው ፡ በሰማያትም ፡ የተፈታ ፡ ይሁን ፡፡ ከዚያ ፡ ወዲያም ፡
አዘዘ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ ለማንም ፡ እንደይነገሩ ፡
የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡፡ ከዚያም ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡
ገለጸላቸው ፡ የሱስ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጊዜ ፡ እንደለ
ው ፡ ይሔድ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ የሩሳሌም ፡ ከዚያም ፡ ብዙ ፡
መከራ ፡ እንዲቀበል ፡ ከሽማግሎች ፡ ከካህናትም ፡ አለቆ
ች ፡ ከጻፎችም ፡፡ እንዲገሉትም ፡ በሰስተኛውም ፡ ቀን ፡ እ
ንዲነሣ ፡ ከሙታን ፡፡ ጴጥሮስም ፡ መለሰለት ፡ ይከለክለ
ውም ፡ ጀመረ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ አይድረስብህ ፡ አቤቱ ፡ ይ
ህ ፡ ይሆንብህ ፡ ዘንድ ፡፡ እርሱም ፡ ዙሮ ፡ ጴጥሮስን ፡ ገሠ
ጸው ፡ አለውም ፡፡ በኋላየ ፡ ሒድ ፡ አንተ ፡ ሰይጣን ፡፡ ዕን
ቅፋት ፡ ሁነህብኛልና ፡፡ ለእግዚአብሔር ፡ የሚሆነውን ፡ አ
ታስብምና ፡ የሰውን ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡፡ ማቴዎስ ፡ ፲፮፡ ፲፫፡፡
ይህ ፡ ነገርም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ነው ፡ ከርሱም ፡ አ
ንዲት ፡ ፊደል ፡ እንኳ ፡ የማይወድቅበት ፡ ሰማይና ፡ ምድ
ር ፡ እስኪያልፉ ፡ ድረስ ፡፡ ይህነንም ፡ ነገር ፡ የሚለውጠ
ው ፡ የሰውንም ፡ ትምህርት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ላ
ይ ፡ የሚያደርገው ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያስቈጣል ፡

የመድኀኒቱንም ፡ ቤት ፡ ባሸዋ ፡ ላይ ፡ ይመሰርታል ፡ እግዚ
አብሔርም ፡ ይፈርድበታል ። አሁንም ፡ በእግዚአብሔር ፡
ፈርሃት ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ጥቂት ፡ እንናገራለን ፡ እግዚአብሔ
ር ፡ እናስተውለው ፡ ዘንድ ፡ ጸጋውን ፡ በሰጠኝ ፡ መጠን ።

የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጌታችን ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ በጠየቃ
ቸው ፡ ጊዜ ። ማንው ፡ ይላሉ ፡ ሰዎች ፡ እኔን ፡ የሰውን ፡ ል
ጅ ። ልባቸውን ፡ ይፈትን ፡ ዘንድ ፡ ሃይማኖታቸውንም ፡ ያ
ጸና ፡ ዘንድ ፡ ብሎ ፡ ጠየቃቸው ። እርሳቸውም ፡ እርሱ ፡ እንደ ፡
ጠየቃቸው ፡ መለሱለት ፡ አሉም ። መጥመቅ ፡ ዮሐንስ ፡ ነ
ው ፡ የሚሉህ ፡ አሉ ። እኩሉም ፡ ኤልያስ ። እኩልም ፡
ኤርምያስ ፡ ወይስ ፡ ከነቢያት ፡ አንድ ። እንደዚህም ፡ ያለውን ፡
የሌላውን ፡ ሰውን ፡ ማለት ፡ መቀበል ፡ ለሃይማኖት ፡ አይ
በቃምና ፡ የሱስ ፡ ሁለተኛ ፡ ጠየቃቸው ፡ እንዲህ ፡ ሲል ።
እላንተ ፡ ግን ፡ ለራሳችሁ ። ምን ፡ ትላላችሁ ፡ እኔ ፡ እንደ ፡
ሆንሁ ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ሲሞን ፡ ጴጥሮስ ፡ በቁም ፡ ነገ
ር ፡ ከለልቡም ፡ በሁላቸውም ፡ ስም ፡ መለሰ ፡ አለውም ።
አንተ ፡ ነህ ፡ ክርስቶስ ፡ የሕያው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ።
የሱሰም ፡ መለሰ ፡ እንዲሁም ፡ አለው ። ብፁዕ ፡ ነህ ፡ ሲሞ
ን ፡ ሆይ ፡ የዮና ፡ ልጅ ። "ብፁዕ ፡ ነህ ፡" ሲል ፡ ማለቱ ፡ ይ
ህ ፡ ነው ። አንተ ፡ የነፍስህን ፡ መደን ፡ የነፍስህንም ፡ ደህን
ነት ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ መስጠት ፡ የማይችል ፡ በእግዚአብሔ
ር ፡ አገኘህ ። እንዲህ ፡ ይላልና ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ። ጻድቅ ፡
በሃይማኖት ፡ ይሐይዋል ፡ ሕይወትም ፡ የዘላለምም ፡ ድኅ
ንነት ፡ በሃይማኖቱ ፡ መጽደቅ ፡ ይሆንለታል ። የሱስ ፡ ክርስ
ቶስ ፡ ስሙን ፡ ሲሞን ፡ የዮና ፡ ልጅ ፡ ይለዋል ። ይህ ፡ ሥጋ
ዊ ፡ ስሙ ፡ ነበረ ፡ ካባቱ ፡ ከዮና ፡ በሥጋ ፡ ብቻ ፡ ተወልደ ፡
እንደ ፡ ተባለ ። ደሮ ፡ የዮና ፡ ልጅ ፡ ሁኖ ፡ ወይስ ፡ የማንም ፡
ልጅ ፡ ሁኖ ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ መግባት ፡ ባላገ
ኘ ፡ ሁለተኛ ፡ ካልተወለደ ። እንዲህ ፡ ይላልና ፡ ክርስቶስ ፡
ኒቆዲሞስን ። ማንም ፡ ሁለተኛ ፡ ያልተወለደ ፡ በውኃና ፡ በ
መንፈስ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ አይገባም ።
ከሥጋ ፡ የተወለደ ፡ ሥጋ ፡ ነውና ፡ ከመንፈስ ፡ ግን ፡ የተወለ
ደ ፡ መንፈስ ፡ ነው ። በእግዚአብሔር ፡ ቃልም ፡ 'ሥጋ ፡' የተ

ባለ ፡ ከአደም ፡ ኃጢአት ፡ በኋላ ፡ ከኃጢአትም ፡ በታች ፡ ሁ
ኖ ፡ በኃጢአትም ፡ ረክሶ ፡ ስለ ፡ ኃጢአትም ፡ ከዘላለም ፡
ሞት ፡ ኩነኔ ፡ በታች ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ማለት ፡ ነው ፡፡ የ
ሰው ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአተኛ ፡ ሰውነቱ ፡ ‘ሥጋ’ ፡ ይባላል ፡፡ ሁለ
ተኛ ፡ መወለዳችንም ፡ በውኃና ፡ በመንፈስ ፡ ነው ፡፡ ሕይወ
ቱም ፡ በመንፈስ ፡ በውሥታችን ፡ ያለ ፡ ሰውነታችን ፡ እርሱ
ም ፡ ፈቃዳችን ፡ መሻታችንም ፡ ልባችንም ፡ አእምሮዋችን
ም ፡ ሁሉ ፡ ኃይላችንም ፡ ሁሉ ፡ ቢለወጥ ፡ ቢታደስም ፡ የአ
ሮጌ ፡ የአደም ፡ ጠባያችን ፡ ቢጠፋ ፡ ያደ ስም ፡ የክርስቶስ ፡
ጠባይ ፡ ቢነሣ ፡ ከኃጢአትም ፡ ሸሽተን ፡ ኃጢአትንም ፡ ጸል
ተን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብንመለስ ፡ ይህ ፡ ሁለተኛ ፡ ል
ደት ፡ ይባላል ፡፡ የሥጋዊ ፡ የመጀመርያ ፡ አደም ፡ ልጆች ፡
የሰው ፡ ሁሉ ፡ አባት ፡ የሚሆን ፡ በርሱ ፡ በሁለተኛ ፡ ልደታ
ቸው ፡ በመንፈስ ፡ የሁለተኛ ፡ አደም ፡ ትውልድ ፡ ይእግዚ
አብሔርም ፡ ልጆች ፡ ይሆናሉ ፡፡ መንፈሳቸው ፡ ልባቸው
ም ፡ እርሳቸው ፡ ከዚህ ፡ በምድር ፡ ሲሆኑ ፡ ጊዜ ፡ ለእግዚ
አብሔር ፡ አንድነት ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ይታደሳሉ ፡፡ ወደ ፡ በ
ጐነት ፡ ሁሉ ፡ ፍጻሜ ፡ እስኪደርሱ ፡ ድረስ ፡ በሰማይ ፡፡ ሥ
ጋቸው ፡ ግን ፡ ገና ፡ በሞት ፡ ፍርድ ፡ በታች ፡ ሁኖ ፡ ወደ ፡ መ
ቃበር ፡ ሲሔድ ፡ ምድራዊ ፡ ባሕርዩ ፡ በሞት ፡ ይጠፋል ፡ እ
ስከ ፡ ኋለኛ ፡ ቀንም ፡ ድረስ ፡ ያርፋል ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡
የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ከሙታን ፡ ሲያስነሣቸው ፡ ብዕዕት ፡ ነፍ
ሳቸውም ፡ ወደ ፡ ሥጋዋ ፡ ብትገባ ፡ ሥጋቸው ፡ ደግሞ ፡ የታ
ደሰ ፡ ይሆናል ፡ ለትመሰገንም ፡ ለክርስቶስ ፡ ሥጋ ፡ ይመሰላ
ል ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ የምእመናን ፡ የሁለተኛ ፡ ልደታቸ
ው ፡ ፍጻሜ ፡ ይሆናል ፡ ሥጋቸውና ፡ ነፍሳቸው ፡ ድነው ፡ ሲ
ሆኑ ፡ ለዘላለም ፡ ሕይወት ፡፡ ይህም ፡ ሁለተኛ ፡ ልደት ፡ በቀ
ን ፡ መንገድ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ይመጣል ፡፡ እንዲህ ፡ ይ
ላልና ፡ ዮሐንስ ፡፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እርሱን ፡ ለተቀበሉ
ት ፡ ሥልጣን ፡ ሰጣቸው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጆች ፡ ይሆኑ ፡
ዘንድ ፡ በስሙ ፡ የሚያምኑ ፡፡ ከደም ፡ ያልተወለዱ ፡ ከሥ
ጋ ፡ ፈቃድም ፡ ከሰውም ፡ ፈቃድ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከእግዚአብ
ሔር ፡ የተወለዱ ፡፡ የዮሐንስ ፡ ወንጌል ፡ ፩፡ ፲፪፡ ፲፫፡፡ አሁን

ም ፡ ብንጠይቅ ። እግዚአብሔር ፡ እንዴት ፡ ይወልደል ፡ ልጀ
ቹን ። ጴጥሮስ ፡ መላሸን ፡ ይሰጠናል ፡ እንዲህ ፡ ሲል ። አ
ልተወለደችሁም ፡ ከሚጠፋ ፡ ዘር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከማይጠ
ፋ ። ከዘላለሙ ፡ ከሕያው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቃል ። ሥ
ጋ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ሣዕር ፡ ነውና ፡ የሰውም ፡ ክብር ፡ ሁሉ ፡
እንደ ፡ ሣዕር ፡ አበባ ። ሣዕርም ፡ ይደርቃል ፡ አበባም ፡ ይ
ረግፋል ። የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ግን ፡ ለዘላለም ፡ ይኖራ
ል ። በወንጌልም ፡ የተሰበከላችሁ ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነው ። ፩፤
ጴጥሮስ ፡ ፩፤ ፳፫። ይህ ፡ ነገርም ፡ እንዲህ ፡ ነው ። የእግዚአ
ብሔር ፡ ነገር ፡ እግዚአብሔር ፡ በመንፈሱ ፡ በሙሴ ፡ በነቢ
ያትም ፡ በሐዋርያትም ፡ አፍ ፡ የተናገረው ፡ ወደ ፡ ልባችን ፡
ቢገባ ፡ ሃይማኖትን ፡ ይሰራል ። እውነተኛ ፡ ሃይማኖትም ፡
በለዚህ ፡ ፫፤ ክፍል ፡ ይኖራል ። ፩፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነገ
ር ፡ ማወቅ ። ፪፤ የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ መቀበል ። ፫፤ ለ
እግዚአብሔር ፡ ነገር ፡ መታዘዝ ። እለዚህ ፡ ፫፤ ካልተገኙ ፡
ሃይማኖትም ፡ አይገኝም ። ጳውሎስም ፡ ይላል ። ሃይማ
ኖት ፡ ከመስማት ፡ ነው ፡ መስማትም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ነ
ገር ፡ ነው ። ሮሜ ፡ ፲፤ ፲፯። ሃይማኖትም ፡ በልባችን ፡ ቢኖር ፡
ልባችን ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ይለወጥበታል ።
እንዲህ ፡ ይላልና ፡ ጴጥሮስ ፡ በሐዋርያት ፡ ስራ ፡ ም ፡ ፲፭፤
ቍ ፡ ፱። እግዚአብሔር ፡ ልባቸውን ፡ አነጻ ፡ በሃይማኖት ።

ይህም ፡ ሁለተኛ ፡ ልደት ፡ በጴጥሮስ ፡ ጀመረ ። መንፈስ ፡
ቅዱስ ፡ በልቡ ፡ ሃይማኖትን ፡ ሰርትዋልና ፡ ክርስቶስ ፡ እን
ደለው ፡ ብፁዕ ፡ ነህ ፡ ሲሞን ፡ ሆይ ፡ የዮና ፡ ልጅ ። ሥጋና ፡
ደም ፡ አልገለጸልህምና ፡ ይህነን ፡ ነገር ። ነገር ፡ ግን ፡ የሰማ
ዩ ፡ አባቴ ። አሁንም ፡ ይጨምራል ። እኔም ፡ እልሃለሁ ።
አንተ ፡ ጴጥሮስ ፡ ነህ ። በዚችም ፡ ደንጊያ ፡ ላይ ፡ ቤተ ፡ ክር
ስቲያኔን ፡ እሰራለሁ ፡ የገሃናምም ፡ ደጆች ፡ አይጸኑባትም ።
"ጴጥሮስ ፡" ማለት ፡ በጽርዕ ፡ ቋንቋ ፡ 'የደንጊያ ፡ ሰው ፡' ነው ።
"ጴጥራ ፡" ግን ፡ 'ደንጊያ' ፡ ማለት ፡ ነው ። ስለ ፡ ሁለተኛ ፡ ልደ
ቱ ፡ ለሲሞን ፡ ለዮና ፡ ልጅ ፡ አዲስ ፡ ስም ፡ ይወጣለታል ፡ በ
ሰማይ ፡ በሕይወት ፡ መጽሐፍ ፡ የተጻፈ ። ይህም ፡ ስም ፡ ስ
ለ ፡ ሃይማኖቱ ፡ 'ጴጥሮስ ፡' ሆነ ። ሃይማኖቱ ፡ በደንጊያ ፡ ላ

ይ ፡ ተመሰርትዋልና ፡ እርሱም ፡ ክርስቶስ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ደንጊያ ፡ የተባለ ። መዝሙር ፡ ፻፲፰፡ ፳፪። ይሳይያስ ፡ ፳፡ ፲፮። ማርቆስ ፡ ፲፪፡ ፲። ሉቃስ ፡ ፳፡ ፲፯። የሐዋርያት ፡ ስራ ፡ ፬፡ ፲፩። ሮሜ ፡ ፱፡ ፴፫። ፩፡ ጴጥሮስ ፡ ፪፡ ፯። ጳውሎስም ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይላል ። እለንተ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቤት ፡ ናችሁ ። ሌላውን ፡ መሠረት ፡ ይመሠርት ፡ ዘንድ ፡ ማንም ፡ አይችልም ፡ ከዚያ ፡ ከተመሠረተ ፡ በቀር ። እርሱም ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ። ፩፡ ቆሮንቶስ ፡ ፫፡ ፱፡ ፲፩። ደግሞም ፡ ይላል ። ዛሬ ፡ እንግዶች ፡ መጻተኞችም ፡ አይደላችሁም ። እላንተ ፡ የቅዱሳን ፡ አገር ፡ ወገን ፡ ናችሁ ። በሐዋርያትና ፡ በነቢያትም ፡ መሠረት ፡ ተመሠረታችሁ ፡ የማዘኑ ፡ ደንጊያ ፡ እርሱ ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የሚሆን ። ኤፌሶን ፡ ፪፡ ፲፱፡ ፳። አሁን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ነውና ፡ አልተጻላምም ፡ ይህ ፡ ነገርም ፡ ሊገጠም ፡ ነው ፡ ከሌላ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ። ክርስቶስም ፡ ጴጥሮስን ፡ ሲል ። በዚች ፡ ደንጊያ ፡ ላይ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኔን ፡ እመሠርታለሁ ፡ ማለቱ ፡ ይህ ፡ ነው ። አንተ ፡ ጴጥሮስ ፡ ነህ ። አሁን ፡ ባስታወቅህ ፡ በክርስቶስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ በሃይማኖትህ ፡ ተመሠርተሃልና ። አንተም ፡ በላዩ ፡ እንደ ፡ ተመሠረትህ ፡ እንደሁም ፡ ለሚያምኑብኝ ፡ ሁሉ ፡ የመድኃኒታቸው ፡ መሠረት ፡ እሆናለሁ ፡ የታመንሁ ፡ የጸናሁም ። ከገሃናምም ፡ ደጆች ፡ እጠብቃቸዋለሁ ፡ ድልም ፡ እስጣቸዋለሁ ፡ በሰይጣንም ፡ በኃይላቱም ፡ ሁሉ ፡ ላይ ። የገሃናም ፡ ደጆች ፡ ማለት ፡ የገሃናም ፡ ኃይላት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ከክርስቶስም ፡ ከመንግሥቱም ፡ ጋራ ፡ የሚጸሉ ፡ የሰውንም ፡ ማጥፋት ፡ የሚሹ ። እርሳቸውም ፡ ጴጥሮስን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሊያሸንፉት ፡ ቀረቡ ፡ ፫፡ ጊዜ ፡ ባንድ ፡ ሌሊት ፡ ክርስቶስን ፡ ሲክድ ፡ እንደያውቀው ፡ ብሎ ። ይህም ፡ ኃጢአት ፡ ታላቅ ፡ ነበር ፡ ታናሽም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የሚል ፡ የክርስቶስን ፡ ታላቅነት ፡ አያውቅም ፡ የኃጢአትንም ፡ ክፋት ፡ ሁሉ ፡ አያውቅም ። በዚያች ፡ ሌሊትም ፡ ጴጥሮስ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መሠረት ፡ ከሆነ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ በጠፋች ። ደግ ፡ እርሱ ፡ ባላመነ ፡ ጊዜ ፡ ክርስቶ

ስ ፡ ታመነ ፡፡ እርሱም ፡ ጌታውንና ፡ መድኃኒቱን ፡ ሲክድ ፡ ክርስቶስ ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩን ፡ አልካደም ፡፡ ጴጥሮስንም ፡ በመውደድ ፡ አልታወከም ፡፡ ጴጥሮስም ፡ ንስሓ ፡ ገብቶ ፡ በ ተመለሰ ፡ ጊዜ ፡ እርሱ ፡ በምህረቱ ፡ ተቀበለው ፡፡ ጴጥሮስ ም ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መሠረት ፡ በሆነ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያ ንም ፡ በጴጥሮስ ፡ ልታምን ፡ ነበረች ፡ እርሱንም ፡ የመድኃ ኒትን ፡ ተስፋ ፡ ልታደርግ ፡ ክርስቶስንም ፡ አይደለም ፡፡ የእ ግዚአብሔርም ፡ ነገር ፡ አሰት ፡ ቢሆን ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ሰ ውን ፡ ሁለግዜ ፡ ይገሥጻልና ፡ በሰው ፡ እንደይታመን ፡ ብ ሎ ፡ ክብርንም ፡ ሁሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ እንዲሰጥ ፡፡ ኤርምያስ ፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፡፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ እግዚ አብሔር ፡፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ርጉም ፡ ነው ፡ በሰው ፡ የሚ ታመን ፡ ሥጋውንም ፡ እጁን ፡ የሚያደርግ ፡ ልቡም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የሚርቅ ፡፡ ስለዚህም ፡ ኢለዚያ ፡ እጅ ግ ፡ ይስታሉ ፡ ጴጥሮስ ፡ ለራሱ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ለቤተ ፡ ክር ስቲያን ፡ ለመሠረት ፡ ተደረገ ፡ ብለው ፡ የሚያስተምሩ ፡፡ ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ ኢለዚያ ፡ ይስታሉ ፡ የሮሚያ ፡ ጳጳሳት ን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ መሠረት ፡ የሚያደርጉ ፡፡ በርሳ ቸው ፡ መኻከል ፡ ብዙ ፡ ይገኛሉና ፡ የሰይጣን ፡ ባሮች ፡ የነ በሩ ፡ ነፍሳቸውንም ፡ ለኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ የሰጡ ፡ ቤተ ፡ ክር ስቲያንን ፡ ለማጥፋት ፡ በመስራት ፡ ፈንታ ፡፡ ስለዚህም ፡ ያገራችን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ በ ተቀበለች ፡ ጊዜ ፡ አሁን ፡ ፲፫፻፤ አመት ፡ የሚሆን ፡ ከሮም ያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወጣች ፡፡ ክርስቶስንም ፡ ራስዋን ፡ ሊቀ ፡ ጳጳሳትዋንም ፡ ሁኖ ፡ ተቀበለች ፡፡ በክርስቶስ ፡ ቃል ም ፡ ተመራች ፡፡ የክርስቶስ ፡ ቃልም ፡ እንደ ፡ ብሩህ ፡ ብር ሃን ፡ በመኻከላችን ፡ ያበራል ፡ ወደ ፡ እውነትም ፡ ሁሉ ፡ ይመራናል ፡፡ በሰይጣንም ፡ በገሃነምም ፡ ደጆች ፡ ሁሉ ፡ ላ ይ ፡ ድል ፡ ይሰጠናል ፡፡

ጌታችንም ፡ ጴጥሮስን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ይጨምራል ፡፡ የ መንግሥተ ፡ ሰማያትም ፡ መክፈቻ ፡ እሰጥሃለሁ ፡፡ በምድ ር ፡ የምታሥረው ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያትም ፡ የታሠረ ፡ ይሁን ፡፡ በምድርም ፡ የምትፈታው ፡ በሰማይም ፡ የተፈ

ታ ፡ ይሁን ፡፡ በዚህ ፡ ነገርም ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በምሳሌ ፡ ያናገራል ፡፡ የሰማይ ፡ መክፈቻ ፡ ምንድር ፡ ነው ፡፡ ሰው ፡ በሃይማኖት ፡ ብቻ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ይገባልና ፡ ሃይማኖትም ፡ የሚደረግበት ፡ የሰማይ ፡ መክፈቻ ፡ ይሆናል ፡፡ እርሱም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ነው ፡ ሌላ ፡ የለም ፡፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃልም ፡ ለኃጢአተኞች ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ የምስራች ፡ ተናገረ ፡ ቢመለሱ ፡ ቢያምኑም ፡፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ ግን ፡ የዘላለምም ፡ ፍርድ ፡ ይቃየምላቸዋል ፡ ባያምኑ ፡፡ አሁንም ፡ ክርስቶስ ፡ የሰማይን ፡ መክፈቻ ፡ ጴጥሮስን ፡ ሲሰጥ ፡ ወንጌልን ፡ ለመስበክ ፡ ሾመው ፡፡ የወንጌልን ፡ ተስፋ ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ቃል ፡ ቅያሜ ፡ ሁሉ ፡ ለዓለም ፡ ይነግር ፡ ዘንድ ፡፡ አሁንም ፡ የሚከተል ፡ ነገር ፡፡ "በምድር ፡ የምታሠረው ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያትም ፡ የታሠረ ፡ ይሁን ፡፡ በምድርም ፡ የምትፈታው ፡ በሰማይም ፡ የተፈታ ፡ ይሁን ፡፡" ማለቱም ፡ ይህ ፡ ነው ፡፡ በወንጌል ፡ ሰብከህ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ብታስተምር ፡ እግዚአብሔር ፡ ለማስተማርህ ፡ ይመሰክራል ፡ ነገርህንም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ የሚሆን ፡ ያጸናዋል ፡፡ የእግዚአብሔር ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ነውና ፡ በዚህም ፡ ስፍራ ፡ ለጴጥሮስ ፡ ያለ ፡ ክርስቶስ ፡ ፈቃድ ፡ እንደ ፡ ፈቃዱ ፡ ሰውን ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ያገባው ፡ ዘንድ ፡ ሥልጣን ፡ አይሰጥም ፡፡ በወንጌል ፡ እንደ ፡ ተገለጸ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ከመምህሩ ፡ አይበልጥምና ፡ በርያም ፡ ከጌታው ፡ አይበልጥም ፡ ማቴዎስ ፡ ፲፡ ፳፬፡፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጌታችን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑም ፡ ሁሉ ፡ ጌታ ፡ የሐዋርያትም ፡ ጌታ ፡ እርሱ ፡ እውነተኛ ፡ ነው ፡ የደዊት ፡ መክፈቻ ፡ ያለው ፡፡ እርሱም ፡ ቢከፍት ፡ ማንም ፡ አይዘጋም ፡ እርሱም ፡ ቢዘጋ ፡ ማንም ፡ አይከፍትም ፡፡ የዮሐንስ ፡ ራእይ ፡ ፫፡ ፯፡፡ የየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ መክፈቻ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ የሚከፍትበት ፡ የሚዘጋበትም ፡ የተገለጸ ፡ በጀችንም ፡ ያለ ፡ ቃሉ ፡ ሁንዋልና ፡፡

ክርስቶስም ፡ የሰማይን ፡ መክፈቻ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡

ሁሉ ፡ እጅ ፡ ሰጠው ፡፡ ለጴጥሮስ ፡ ብቻ ፡ ይህች ፡ ሥልጣን ፡ አልተሰጠችምና ፡ ለሐዋርያት ፡ ሁሉ ፡ እንጅ ፡፡ እንደህ ፡ ይላልና ፡ በዮሐንስ ፡ ወንጌል ፡ ም ፡ ፳፡ ቍ ፡ ፳፩፡፡ የሱስም ፡ አላቸው ፡፡ ሰላም ፡ ለላንተ ፡ ይሁን ፡፡ አብ ፡ እንደ ፡ ላከኝ ፡ እንደሁም ፡ እኔ ፡ እልካችኋለሁ ፡፡ ይህነንም ፡ ብሎ ፡ እፍ ፡ አለባቸው ፡ አላቸውም ፡፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ተቀበሉ ፡፡ ኃጢአቱንም ፡ የተዋችሁለት ፡ ቀረችለት ፡፡ የያዛችሁበትም ፡ ሰው ፡ ተያዘችበት ፡፡ በዚህ ፡ ነገርም ፡ ይገለጻል ፡ ወንጌልን ፡ ለመስበክ ፡ ሰማይንም ፡ ለመክፈትና ፡ ለመዝጋት ፡ እርሱ ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ ነውና ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይፈለጋል ፡ ያለርሱም ፡ አይሆንም ፡፡ ስለዚህ ፡ ጌታችን ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ ሳይልካቸው ፡ የመክፈቻንም ፡ ሹመት ፡ ሳይሰጣቸው ፡ እፍ ፡ ብሎ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ሰጣቸው ፡፡ ከሐዋርያት ፡ ዘመንም ፡ በኋላ ፡ ይህ ፡ ሹመት ፡ ወደ ፡ ቀሳውስት ፡ ወደ ፡ ኤጲስቆጶሳትም ፡ ወደ ፡ ጳጳሳትም ፡ በሥርዓት ፡ አለፈ ፡፡ ሁላቸው ፡ በኃይላቸው ፡ ሁሉ ፡ ወንጌልን ፡ ሊሰብኩ ፡ ናቸውና ፡ ሰውንም ፡ ሁሉን ፡ በክርስቶስ ፡ ፊንታ ፡ ሊለምኑ ፡፡ "ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ታረቁ ፡" ብለው ፡፡ ያ ፡ መምህር ፡ ግን ፡ ቄስ ፡ ቢሆን ፡ ወይስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወይስ ፡ ጳጳስ ፡ ወይስ ፡ መነክሴም ፡ የክርስቶስ ፡ መንፈስ ፡ የማይኖርበት ፡ ቢፈታም ፡ ቢገዝትም ፡ ዝምብሎ ፡ ነው ፡፡ እርሱ ፡ ነውና ፡ የክርስቶስ ፡ ነገር ፡ የሚደርስበት ፡ ሲል ፡፡ ወዮላችሁ ፡ እላንተ ፡ ጻፎች ፡ ፈሪሳውያንም ፡ ግብዞች ፡፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ትዘጋላችሁና ፡ በሰው ፡ ፊት ፡፡ እላንተ ፡ አትገቡምና ፡ የሚገቡትንም ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፡ አተውም ፡፡ ማቴዎስ ፡ ፳፫፡ ፲፫፡፡ ለቄስም ፡ ለመምህርም ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነገር ፡ ደረሰ ፡ ለሕዝቅኤል ፡ ለነቢይ ፡ ያለው ፡፡ አንተ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆይ ፡፡ እኔ ፡ ለእሥራኤል ፡ ቤት ፡ ተመልካች ፡ አድርጌ ፡ ሾምሁህ ፡፡ ካፌ ፡ የምትሰማውን ፡ ነገር ፡ ሁሉን ፡ በትእዛዜ ፡ ትነግራቸው ፡ ዘንድ ፡፡ እኔም ፡ ዐመፀኛውን ፡፡ አንተ ፡ ዓመፀኛ ፡ ሆይ ፡ ሞት ፡ ትሞታለህ ፡ ስል ፡፡ አንተም ፡ ይህነን ፡ ነገሬን ፡ ባትነገረው ፡ ዓመፀኛ ፡ ባመፃው ፡ ይገሠጽ ፡ ዘንድ ፡ ዓመፀኛስ ፡ ባመፃው ፡

መክንያት ፡ ይሞታል ፡ ደሙን ፡ ግን ፡ ከእጅህ ፡ እፈልጋለሁ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ዓመፀኛውን ፡ ስለ ፡ ዓመፃው ፡ ብትገሥጸው ፡ ከክፋቱ ፡ ይመለስ ፡ ዘንድ ፡ ከክፋቱም ፡ ባይመለስ ፡ እርሱ ፡ ስለ ፡ ኃጢአቱ ፡ ይሞታል ፡ አንተ ፡ ግን ፡ ነፍስህን ፡ አደንህ ፡፡ ሕዝቅኤል ፡ ፴፫ ፡ ፰ ፡ ፱፡፡

የሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ጴጥሮስን ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ አዘዘ ፡ ለማንም ፡ እንዳይናገሩ ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡፡ ይህችን ፡ ትምርት ፡ ለማስተማር ፡ ጊዜ ፡ ገና ፡ አልደረሰምና ፡ ክርስቶስ ፡ ከሙታን ፡ አልተነሣምና ፡፡ እርሳቸውን ፡ ግን ፡ የመንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ምሥጢር ፡ አስተማራቸው ፡፡ ከዚያ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ ይገልጽላቸው ፡ ሆነ ፡ የሱስ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጊዜ ፡ እንደለው ፡ ይሔድ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ የሩሳሌም ፡ ብዙም ፡ መከራ ፡ እንደ ፡ ቀበል ፡ ከሽማግሎች ፡ ከካህናትም ፡ አለቆች ፡ ከጻፎችም ፡፡ እንዲገድሉትም ፡ በሦስተኛ ፡ ቀንም ፡ እንዲነሣ ፡፡ ጴጥሮስም ፡ መለሰለት ፡ ይከለክለውም ፡ ጀመረ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ አይድረስብህ ፡ አቤቱ ፡ ይህ ፡ ይሆንብህ ፡ ዘንድ ፡፡ እርሱም ፡ ዙሮ ፡ ጴጥሮስን ፡ ገሠጸው ፡ አለውም ፡፡ በኋላዬ ፡ ሒድ ፡ አንተ ፡ ሰይጣን ፡ ዕንቅፋት ፡ ሁነህብኛልና ፡፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ አታስብምና ፡ የሰውን ፡ ብቻ ፡ እንጅ ፡፡ ይህ ፡ የጌታችን ፡ ነገር ፡ ብርቱ ፡ ተግሣጽ ፡ ነው ፡ ለደቀ ፡ መዝሙሩ ፡፡ የጴጥሮስ ፡ ልብ ፡ በጣም ፡ ገና ፡ አልታደሰምና ፡ ከኃጢአቱም ፡ ጋራ ፡ ሊጋደል ፡ ነበረ ፡፡ ባሕርዩም ፡ እንዲያው ፡ ቃሊል ፡ ሁና ፡ ቶሎ ፡ ታወከ ፡ ወዲህና ፡ ወዲያ ፡፡ ሰይጣንም ፡ ይህነን ፡ አውቆ ፡ ልቡን ፡ እንዲነፋ ፡ ፈለገ ፡ እንደ ፡ ስንዴ ፡፡ ደሮ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለርሱ ፡ ጸለዩ ፡ ሃይማኖቱ ፡ እንዳ ይጨርስ ፡፡ ሉቃስ ፡ ፳፪ ፡ ፴፩፡፡ ሰይጣንም ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ በጴጥሮስ ፡ መክንያት ፡ የክርስቶስን ፡ ስራ ፡ ይሽር ፡ ዘንድ ፡ ፈተነ ፡፡ ጴጥሮስ ፡ አሁን ፡ የክርስቶስን ፡ ቸርነት ፡ ቀምሶ ፡ ወደ ፡ ትዕቢት ፡ ዘነበለ ፡ ራሱንም ፡ ወደ ፡ ማክበር ፡፡ ስለዚህም ፡ ክርስቶስን ፡ ሊመክር ፡ ሥልጣን ፡ ያለው ፡ መሰለው ፡፡ የክርስቶስም ፡ መንገድ ፡ በሕማማት ፡ በመስቀልም ፡ እንደሆነ ፡ ሥጋው ፡ አልወደደም ፡ በክብርና ፡ በምድራዊ ፡ ም

ስጋና ፡ አንድ ። ስለዚህም ፡ ክርስቶስን ፡ ሊከለክል ፡ ጀመረ ። የሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ በብርቱ ፡ ነገር ፡ ገሠጸው ፡ ልቡን ፡ ሊያዋርድ ፡ ወደ ፡ ትሕትናም ፡ ሊወስደው ።

የጌታችን ፡ ጥበብና ፡ ፍቅር ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ በመግሠጽ ፡ እጅግ ፡ ያስደንቃል ። የነፍሳቸው ፡ መሻት ፡ እንደ ፡ ፈለገው ፡ እንደዚህ ፡ አደረገላቸው ፡ ሁለግዜ ። ደግ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ገና ፡ አልፈሰሰባቸውምና ፡ ትዕግሥቱን ፡ እጅግ ፡ ፈተኑ ። ይህ ፡ ከሌላ ፡ ነገር ፡ ይልቅ ፡ ባንድ ፡ ነገር ፡ በዛ ። በሃይማኖታቸው ፡ መጉደል ። ኃይሉን ፡ ካዩ ፡ ፍቅሩንም ፡ ካወቁ ፡ በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ተጠራጠሩ ፡ መከራ ፡ ሲመጣ ፡ ምናልባት ፡ እንደደረደቸው ። ማርቆስ ፡ ፱፡ ፴፫። ማቴዎስ ፡ ፲፯፡ ፳። ፲፯፡ ፲፯። ደግሞ ፡ ክብርን ፡ ስለ ፡ መመኘታቸው ፡ ደከመ ። ማቴዎስ ፡ ፳፡ ፳። ማርቆስ ፡ ፲፡ ፴፭። ስላልተቀደሰም ፡ ቍጣቸው ። ሉቃስ ፡ ፱፡ ፵፮። ደግ ፡ እርሳቸው ፡ ከለልባቸው ፡ በክርስቶስ ፡ ተጣበቁ ፡ ክርስቶስንም ፡ ከለልባቸው ፡ ወደዱት ፡ ሁሉንም ፡ ትተው ፡ እርሱን ፡ ተከተሉ ። ስለዚህም ፡ እርሱ ፡ ደግሞ ፡ ወደዳቸው ፡ ገንዘቡም ፡ ሁነው ፡ ቍጠራቸው ፡ ፍቅሩንም ፡ በልባቸው ፡ አፈሰሰ ። ነፍሱንም ፡ ስለርሳቸው ፡ ለወጠ ። ልቡንም ፡ በጣም ፡ ከፈተላቸው ፡ ወንጌልንም ፡ ለመስበክ ፡ በመጽሪት ፡ አከበራቸው ። ተስፋም ፡ አስደረገላቸው ፡ መንፈሱን ፡ ይሰድላቸው ፡ ዘንድ ፡ ከርሳቸውም ፡ ጋራ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ሁለግዜ ። መጋደላቸውም ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ ወደርሱ ፡ ሊወስዳቸው ። በፍርድም ፡ ቀን ፡ በእሥራኤል ፡ መፍረደን ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ይከፍል ፡ ዘንድ ። ማቴዎስ ፡ ፲፱፡ ፳፯። የዮሐንስ ፡ ወንጌል ፡ ፯፡ ፴፱። ፲፫፡ ፩። ፲፯፡ ፱። ፲፡ ፲፱።

ደግ ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እርሱ ፡ እግዚአብሔር ፡ በገነት ፡ ለአደምና ፡ ለሄዋ ፡ ተስፋ ፡ ስላስደረገላቸው ፡ የሴት ፡ ዘር ፡ ሁንዋልና ፡ የባብ ፡ ራስ ፡ ለመቀጥቀጥ ፡ የመጣ ። የባብና ፡ የዘሩ ፡ ጸላትነት ፡ ሁሉ ፡ ደረሰበት ። ፈሪሳውያንና ፡ ሳዱቃውያን ፡ ካህናትና ፡ ጻፎችም ፡ የሕዝብም ፡ ሽማግሎች ፡ ከሕዝብ ፡ ጋራ ፡ ጸሉት ፡ ሊገድሉትም ፡ ፈለጉ ። ደግ ፡ ጊዜው ፡ ሳይደርስ ፡ አልሆነላቸውም ። እንዲሁም ፡ ነበሩ ፡ ክርስቶ

ቱ ፡ በሲሞን ፡ ልጅ ፡ አኅልፎ ፡ ይሰጠው ፡ ዘንድ ፡፡ የሱስም ፡
ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ አብ ፡ ሁሉን ፡ በጁ ፡ እንደ ፡ ሰጠው ፡፡ ከእግ
ዚአብሔርም ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር
ም ፡ እንዲሔድ ፡፡ ከራት ፡ ተነሣ ፡ ልብሱንም ፡ አኖረ ፡ የ
ሚያብስበትንም ፡ ጨርቅ ፡ ወሰደ ፡ ታጠቀበትም ፡፡ በመታ
ጠቢያውም ፡ ውኃ ፡ አፈሰሰ ፡፡ ያፅብም ፡ ጀመረ ፡ የደቀ ፡
መዛሙርቱን ፡ እግር ፡፡ በታጠቀበትም ፡ ጨርቅ ፡ ያደርቀው ፡
ጀመረ ፡ ወደ ፡ ሲሞን ፡ ጴጥሮስም ፡ መጣ ፡፡ ያም ፡ አለው ፡፡
አቤቱ ፡ አንተን ፡ እግሬን ፡ ታፅብልኛለህ ፡፡ የሱስም ፡ መለ
ሰለት ፡ አለውም ፡፡ እኔ ፡ የምሰራውን ፡ አንተ ፡ አታውቀ
ውም ፡ ዛሬ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ኋላ ፡ ታውቀዋለህ ፡፡ ጴጥሮስም ፡
አለው ፡፡ እግሬን ፡ አታፅብልኝም ፡ ለዘላለም ፡፡ የሱስም ፡
መለሰለት ፡ አለውም ፡፡ ካላፀብሁህ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ አንድነ
ት ፡ የለህም ፡፡ ሲሞን ፡ ጴጥሮስም ፡ አለው ፡፡ ጌታ ፡ ሆይ ፡
እግሬን ፡ ብቻ ፡ አታፅብልኝ ፡ እጄንም ፡ ራሴንም ፡ እንጂ ፡፡
የሱስም ፡ አለው ፡፡ ሀማም ፡ የገባ ፡ አይሻም ፡ እግሩን ፡ ከ
መታፀብ ፡ በቀር ፡፡ ሁለንትናው ፡ ንጹሕ ፡ ነውና ፡፡ እላንተ
ም ፡ ንጹሓን ፡ ናችሁ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሁላችሁ ፡ አይደላችሁ
ም ፡፡ ያውቅ ፡ ነበረና ፡ አኅልፎ ፡ የሚሰጠውን ፡ ስለዚህ
ም ፡ አላቸው ፡፡ ሁላችሁ ፡ ንጹሓን ፡ አይደላችሁም ፡፡ እግ
ራቸውንም ፡ አፅቦ ፡ ልብሱን ፡ ወሰደ ፡፡ ደግሞም ፡ ተቀመ
ጠ ፡ አላቸውም ፡፡ አወቃችሁን ፡ ያደረግሁባችሁትን ፡፡ እላ
ንተ ፡ ትሉኛላችሁ ፡ መምሕር ፡ ጌታም ፡፡ መልካምም ፡ ት
ላላችሁ ፡ እኔ ፡ እንደሁ ፡ ነኝና ፡፡ እንኪያስ ፡ እኔ ፡ ጌታ ፡ መ
ምህርም ፡ ስሆን ፡ ካፀብሁ ፡ እግራችሁን ፡፡ እላንተም ፡ ደግ
ሞ ፡ ይገባችኋል ፡ የባልንጀራችሁን ፡ እግር ፡ ታፅቡ ፡ ዘንድ ፡
እርሱ ፡ በርሳችሁ ፡ በፍቅርና ፡ በትሕትና ፡ ታገለግሉ ፡ ዘን
ድ ፡ እርሱ ፡ በርሳችሁ ፡፡ ምሳሌ ፡ ሰጥቻችኋለሁና ፡ እኔ ፡ በ
ላንተ ፡ እንደደረግሁ ፡ እላንተም ፡ ደግሞ ፡ ታደርጉ ፡ ዘን
ድ ፡፡ እውነት ፡ እላችኋለሁ ፡፡ ባርያ ፡ ከጌታው ፡ አይበልጥ
ም ፡ መልክተኛም ፡ ከላከው ፡፡ እላንተም ፡ ይህነን ፡ ብታው
ቁ ፡ ብፁዓን ፡ ናችሁ ፡ ብታደርጉት ፡፡ የዮሐንስ ፡ ወንጌል ፡
፲፫፡፡ ሲቀመጡም ፡ ሲበሉም ፡ አለ ፡፡ እውነት ፡ እላችኋለ

ሁ ፡፡ ከላንተ ፡ አንድ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጠኛል ፡፡ እጅግም ፡ አ
ዘኑ ፡፡ ከርሳቸውም ፡ ኢያንዳንዱ ፡ ይለው ፡ ጀመረ ፡፡ አንዳ
ች ፡ እኔ ፡ እሆን ፡ አቤቱ ፡፡ እርሱም ፡ መለሰ ፡ አለም ፡፡ እ
ጁን ፡ የሚጠልቅ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ወጹ ፡ እቃ ፡ እርሱ ፡
ያስያዘኛል ፡፡ የሰው ፡ ልጅም ፡ ይሔደል ፡ ስለርሱ ፡ እንደ ፡
ተጻፈ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ወዮለት ፡ ለዚያ ፡ ሰው ፡ በጁ ፡ የሚሰ
ጥ ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡፡ ያ ፡ ሰውስ ፡ ባይወለድ ፡ መልካም ፡ ነበ
ረለት ፡፡ ይሁዳም ፡ አሳልፎ ፡ የሚሰጠው ፡ መለሰ ፡ አለው
ም ፡፡ አንዳች ፡ እኔ ፡ እሆን ፡ መምህር ፡ ሆይ ፡፡ አለውም ፡፡
አንተ ፡ አልህ ፡፡ ማቴዎስ ፡ ፳፮፡ ፳፭፡፡

ጌታችንም ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በተያዘበት ፡ ሌሊት ፡ እን
ጀራ ፡ ወሰደ ፡ ቈረሰውም ፡ ባመሰገነ ፡ ጊዜ ፡፡ አለም ፡ እን
ኩ ፡ በሉም ፡፡ ይህ ፡ ነው ፡ ሥጋዬ ፡ ስለላንተ ፡ የሚሰበር ፡፡
ይህነን ፡ አድርጉት ፡ ለማስታሰቤ ፡፡ እንዲሁም ፡ ጽዋውን ፡
ወሰደ ፡ ራታቸውን ፡ ከበሉ ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ ይህ ፡
ጽዋዕ ፡ አዲስ ፡ ሥርዓት ፡ ነው ፡ በደሜ ፡፡ ይህነን ፡ አድርጉ ፡
በምትጠጡት ፡ ጊዜ ፡ ለማስታሰቤ ፡፡ ፩፡ ቆሮንቶስ ፡ ፲፩፡
፳፭፡፡ እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የቍርባንን ፡ ሥ
ርዓት ፡ ሰራ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ለምእመናንም ፡ ሁሉ ፡
ለዘላለም ፡፡ ጳውሎስም ፡ ይላል ፡፡ ይህነን ፡ እንጀራ ፡ ስት
በሉት ፡ ጊዜ ፡ ይህነንም ፡ ጽዋዕ ፡ ስትጠጡት ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡
የጌታን ፡ ሞት ፡ ተናገሩ ፡ እርሱ ፡ እስኪመጣ ፡ ድረስ ፡፡ የ
ቍርባንም ፡ ምሥጢር ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ነው ፡ በውነትም ፡
ለሚያምን ፡ ሰማይና ፡ ምድር ፡ በርሱ ፡ ይገናኙበታል ፡፡ እግ
ዚአብሔርና ፡ ሰውም ፡ አንድነት ፡ ያደርጉበታላ ፡፡ ክርስቶ
ስና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ አንድ ፡ ሥጋ ፡ ሁነው ፡ ምእምናን
ም ፡ ሁሉ ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡ አንድ ፡ ላንድ ፡ ብልት ፡ እ
ንዲሆኑ ፡ ይገለጻሉ ፡፡ ደሮ ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ለሃይማኖት ፡ ብቻ ፡
ነው ፡፡ በውነትም ፡ የማያምን ፡ እንጀራና ፡ ወይን ፡ ፃጅ ፡
ብቻ ፡ ይቀምሳል ፡፡ ለሥጋ ፡ አይለወጥምና ፡ ለነፍስ ፡ ብቻ ፡
እንጅ ፡፡ የነፍስም ፡ አፍ ፡ እርሱ ፡ ሃይማኖት ፡ ነው ፡፡

ይሁዳም ፡ ከክርስቶስ ፡ ጋራ ፡ ከበላ ፡ በኋላ ፡ ቶሎ ፡ ወ
ጣ ፡፡ ሌሊትም ፡ ሆነ ፡፡ የሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ከ፲፩፡ ደቀ ፡

መዛሙርቱ ፡ ጋራ ፡ ለብቻው ፡ ሲቀመጥ ፡ ልቡን ፡ ከፈተላቸው ፡፡ አፉም ፡ ፈሰሰ ፡ በመልካም ፡ ነገር ፡ ደስ ፡ የሚያሰኛቸው ፡ ልባቸውንም ፡ በሚያጸና ፡ በፍቅርና ፡ በሃይማኖት ፡ ስለሚመጣ ፡ መከራና ፡ ጨንቀት ፡ ሁሉ ፡ ክርስቶስ ፡ ከርሳቸው ፡ ዘንድ ፡ ከተለየ ፡ በኋላ ፡ ለርሳቸው ፡ መድረስ ፡ ጊዜ ፡ ያለው ፡፡ ደህ ፡ ሁሉ ፡ ደገኛል ፡ በዮሐንስ ፡ ወንጌል ፡ በ፲፫፡ ፲፬፡ ፲፭፡ ፲፮፡ ምዕራፍ ፡፡ ፲፯፡ ምዕራፍም ፡ ከዚህ ፡ ደክተል ፡፡

ደህነን ፡ ነገር ፡ ተናገረ ፡ የሱስ ፡፡ ዓይኑንም ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ሰቀለ ፡ አለም ፡፡ አባት ፡ ሆይ ፡ ጊዜ ፡ እነሆ ፡ ደረሰ ፡፡ ልጅህን ፡ አመስግን ፡ ልጅህም ፡ ደግሞ ፡ ያመሰግንህ ፡ ዘንድ ፡፡ እንደስገዛህው ፡ በሥጋ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ የዘላለምን ፡ ሕደወት ፡ ደሰጥ ፡ ዘንድ ፡ ለሰጠህው ፡ ሁሉ ፡፡ የዘላለምም ፡ ሕደወት ፡ ደህች ፡ ናት ፡፡ ያውቁህ ፡ ዘንድ ፡ አንተ ፡ ብቻህ ፡ እውነተኛ ፡ አምላክ ፡ እንደ ፡ ሆንህ ፡ የላክህውንም ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስን ፡፡ እኔ ፡ አመሰገንሁህ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡፡ የሰጠህኝንም ፡ ስራ ፡ አድርገው ፡ ዘንድ ፡ ፈጸምሁ ፡፡ ዛሬም ፡ አመስግነኝ ፡ አንተ ፡ አባት ፡ ሆይ ፡ ባንተ ፡ ዘንድ ፡ ከጥንት ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ ወደንተ ፡ ዘንድ ፡ በነበረልኝ ፡ ምስጋና ፡፡ ስምህን ፡ ገለጽሁ ፡ ካለም ፡ ለሰጠህኝ ፡ ሰዎች ፡፡ ላንተ ፡ ነበሩ ፡ ለኔም ፡ ሰጠህኝ ፡፡ ቃልህንም ፡ ጠበቁ ፡፡ ዛሬም ፡ አወቁ ፡ የሰጠህኝ ፡ ሁሉ ፡ ካንተ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡፡ የሰጠህኝን ፡ ነገር ፡ ሰጥቻቸዋለሁና ፡፡ እርሳቸውም ፡ ተቀበሉ ፡፡ በውነትም ፡ አወቁ ፡ እኔ ፡ ካንተ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ወጣሁ ፡ አንተም ፡ እንደ ፡ ላክህኝ ፡ አመኑ ፡፡ እኔም ፡ ስለርሳቸው ፡ እለምናለሁ ፡፡ ላለም ፡ አለምንም ፡ ለሰጠህኝ ፡ እንጅ ፡፡ ያንተ ፡ ናቸውና ፡፡ ለኔም ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ እርሱ ፡ ላንተ ፡ ነው ፡፡ ያንተውም ፡ እርሱ ፡ ለኔ ፡ ነው ፡፡ እኔም ፡ በርሳቸው ፡ ተመስግኛለሁ ፡፡ እኔም ፡ ደግሞ ፡ በዓለም ፡ አልኖርም ፡ እርሳቸው ፡ ግን ፡ ባለም ፡ ናቸው ፡፡ እኔም ፡ ወደንተ ፡ እመጣለሁ ፡፡ ቅዱስ ፡ አባቴ ፡ ሆይ ፡ በስምህ ፡ ጠብቃቸው ፡ እሌህን ፡ የሰጠህኝን ፡፡ አንድ ፡ ደሆኑ ፡ ዘንድ ፡ እንደኛ ፡፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ሳለሁ ፡ በዓለም ፡ በስምህ ፡ እጠብቃቸው ፡ ነበርሁ ፡፡ እሌህን ፡ የሰጠህኝን ፡ ፈጽሜ ፡ ጠበቅኋቸው ፡፡ ከርሳቸውም ፡

አንድ ፡ የጠፋ ፡ የለም ፡ ከጥፋት ፡ ልጅ ፡ በቀር ፡ መጽሐፍ ፡
ይፈጸም ፡ ዘንድ ። ዛሬም ፡ ወደንተ ፡ እመጣለሁ ። ይህነን
ም ፡ ባለም ፡ ሁኜ ፡ እናገራለሁ ፡ ደስታዬ ፡ በርሳቸው ፡ እን
ዲፈጸም ፡ እኔም ፡ ቃልህን ፡ ሰጠኋቸው ፡ ዓለምም ፡ ጸላቸ
ው ፡ ካለም ፡ አይደሉምና ፡ እኔም ፡ ካለም ፡ እንዳይደለ
ሁ ። ካለም ፡ ታወጣቸው ፡ ዘንድ ፡ አለምንም ፡ ከክፉ ፡ ት
ጠብቃቸው ፡ ዘንድ ፡ እንጂ ። ካለም ፡ አይደሉምና ፡ እኔ
ም ፡ ካለም ፡ እንዳይደለሁ ። በውነትህ ፡ ቀድሳቸው ። ቃ
ልህ ፡ እርስዋ ፡ እውነተ ፡ ናትና ። ወደለም ፡ እንደ ፡ ላክሀ
ኝ ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ወደለም ፡ እልካቸዋለሁ ። ስለርሳቸው
ም ፡ ራሴን ፡ እቀድሳለሁ ፡ እርሳቸው ፡ ደግሞ ፡ የተቀደሱ ፡
ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ በውነት ። ስለለዚህም ፡ ብቻ ፡ የምለምን ፡
አይደለሁም ። በቃላቸውም ፡ ስለሚያምኑብኝ ፡ ሁሉ ፡ እ
ንጅ ። ሁሉ ፡ አንድ ፡ እንዲሆኑ ። አንተ ፡ በኔ ፡ እንደለህ ፡
አባት ፡ ሆይ ፡ እኔም ፡ ባንተ ። እርሳቸውም ፡ ደግሞ ፡ አን
ድ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ በኛ ። ዓለምም ፡ ያምን ፡ ዘንድ ፡ እን
ደ ፡ ላክሀኝ ። እኔም ፡ የሰጠሀኝን ፡ ምስጋና ፡ ሰጠኋቸው ፡
አንድ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ እኛም ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ። እኔ ፡
በርሳቸው ፡ አንተም ፡ በኔ ። ባንድ ፡ ፍጹማን ፡ ይሆኑ ፡ ዘን
ድ ፡ ዓለምም ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ላክሀኝ ። እንደ ፡
ወደድኻቸውም ፡ እኔን ፡ እንደ ፡ ወደድሀኝ ። አባት ፡ ሆይ ፡
እለዚህ ፡ የሰጠሀኝ ፡ እፈልጋለሁ ፡ እኔ ፡ ወደለሁበት ፡ ዘን
ድ ፡ እርሳቸውም ፡ ደግሞ ፡ ደኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ። የ
ሰጠኸኝን ፡ ክብር ፡ ያዩ ፡ ዘንድ ። አንተ ፡ ወደሀኛልና ፡ ዓለ
ም ፡ ሳይፈጠር ። ጻድቅ ፡ አባት ፡ ሆይ ፡ ዓለም ፡ አያውቅህ
ም ፡ እኔ ፡ ግን ፡ አውቅኻለሁ ። እሌህም ፡ አወቁ ፡ አንተ ፡
እንደ ፡ ላክሀኝ ። ስምህንም ፡ አስታወቅኋቸው ፡ ደግሞ
ም ፡ አስታውቀዋቸዋለሁ ፡ የወደድሀኝ ፡ ውድ ፡ በርሳቸ
ው ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ እኔም ፡ በርሳቸው ።

ይህነንም ፡ ብሎ ፡ የሱስ ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋራ ፡ ወ
ጣ ፡ የቅድሮንም ፡ ወንዝ ፡ ተሻገረ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ዘይት ፡
አጠገብ ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ የሱስ ፡ አላቸው ። ሁላችሁ ፡
ትሰናከሉብኛላችሁ ፡ በዚች ፡ ሌሊት ። ተጽፏልና ። እረ

ኛውን ፡ እመታለሁ ፡ የመንጋውም ፡ በጎች ፡ ይበተናሉ ፡፡ በ
ተነሣሁም ፡ ጊዜ ፡ እቀድማችኋለሁ ፡ ወደ ፡ ገሊላ ፡፡ ጴጥሮ
ስም ፡ መለሰ ፡ አለውም ፡፡ ሁሉ ፡ ቢሰናከሉብህ ፡ እኔ ፡ ግ
ን ፡ አልሰናከልብህም ፡፡ የሱስም ፡ አለው ፡፡ እውነት ፡ እ
ልሃለሁ ፡፡ በዚች ፡ ሌሊት ፡ ደሮ ፡ ፪ ጊዜ ፡ ሳይጮህ ፡ አንተ ፡
አስቀድመህ ፡ ፫ ጊዜ ፡ እንድትክደኝ ፡፡ ጴጥሮስም ፡ አለ
ው ፡፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ እሞታለሁ ፡ እንጂ ፡ አልክድህም ፡ ከ
ቶ ፡፡ እንደሁም ፡ አሉ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ሁሉ ፡፡ ከዚያ
ም ፡ በኋላ ፡ የሱስ ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋራ ፡ ወደንድ ፡
ጌተሴማኔ ፡ ወደሚባል ፡ አታክልት ፡ ገባ ፡፡ ደቀ ፡ መዛሙር
ቱንም ፡ አለ ፡፡ ተቀመጡ ፡ ከዚህ ፡ ሒጄ ፡ እስክጸልይ ፡ ድረ
ስ ፡ ከዚያ ፡፡ ከርሱ ፡ ጋራም ፡ ወሰደ ፡ ጴጥሮስንና ፡ የዘብዴ
ዎስን ፡ ልጆች ፡፡ ያዝንም ፡ ይተክዝም ፡ ጀመረ ፡ አላቸውም ፡፡
ነፍሴ ፡ አዘነች ፡ እስከ ፡ ሞት ፡ ድረስ ፡፡ ከዚህ ፡ ተቀመጡ ፡
ከኔም ፡ ጋራ ፡ ትጉ ፡፡ ጥቂትም ፡ ፈቀቅ ፡ አለ ፡፡ በግምባሩ
ም ፡ ሰገደ ፡ ኢየጸለየ ፡ እንደህም ፡ ኢያለ ፡፡ አባቴ ፡ ሆይ ፡
ይቻል ፡ እንደሆንስ ፡ ይህች ፡ ጽዋ ፡ ከኔ ፡ ትለፍ ፡፡ ነገር ፡ ግ
ን ፡ እኔ ፡ እንድወድ ፡ አይደለም ፡፡ አንተ ፡ እንድትወድ ፡
እንጂ ፡፡ ወደ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ መጣ ፡ ተኝተውም ፡
አገኛቸው ፡፡ ጴጥሮስንም ፡ አለው ፡፡ እንደህን ፡ አልቻላች
ሁም ፡ ትተጉ ፡ ዘንድ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ አንዲት ፡ ሰዓት ፡፡ ጸል
ዩ ፡ ትጉም ፡ ወደ ፡ ፈተና ፡ እንዳትወድቁ ፡፡ መንፈስ ፡ ተዘጋ
ጅቶዋል ፡፡ ሥጋ ፡ ግን ፡ ደካማ ፡ ነው ፡፡ ደግሞም ፡ ሁለተኛ ፡
ሔደ ፡ ጸለየም ፡ እንደህ ፡ ሲል ፡፡ አባቴ ፡ ሆይ ፡ ይህች ፡ ጽዋ ፡
ሳልጠጣት ፡ ከኔ ፡ ታልፍ ፡ ዘንድ ፡ የማይችል ፡ እንደሆን ፡
ፈቃድህ ፡ ትሁን ፡፡ መጣም ፡ ደግሞም ፡ ተኝተው ፡ አገኛቸ
ው ፡፡ ዓይኖቻቸው ፡ በንቅልፍ ፡ ከብደው ፡ ነበረና ፡፡ ተዋቸው
ና ፡ ደግሞ ፡ ሔደ ፡ ሦስተኛመ ፡ ጸለየ ፡ የቀደመውንም ፡ ነገ
ሩን ፡ አለ ፡፡ ከሰማይም ፡ መልአክ ፡ ለርሱ ፡ ታየው ፡ ሊያጸ
ናው ፡፡ እጅግም ፡ ተጋደለ ፡ ከሞት ፡ ጋራ ፡፡ ይጸልይም ፡ ነበ
ር ፡ በጽኑ ፡ ጻር ፡፡ ወዙም ፡ እንደ ፡ ደም ፡ ነጠብጣብ ፡ በም
ድር ፡ ላይ ፡ ወረደ ፡፡ ተነሥቶም ፡ ወደ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡
መጣ ፡ አላቸውም ፡፡ እንጊደህ ፡ ተኙ ፡ ረፉም ፡፡ እነሆች ፡

ጊዜዪቱ ፡ ደረሰች ። የሰው ፡ ልጅም ፡ ይሰጣል ፡ በኃጢአተ
ኞች ፡ እጅ ። ተነሡ ፡ እንሒድ ። እነሆ ፡ አሁን ፡ ደረሰ ፡ አ
ሳልፎ ፡ የሚሰጠኝ ።

ይሁዳም ፡ ወሰደ ፡ ጭፍራ ፡ ወታደርም ፡ ከካህናት ፡ አለ
ቆች ፡ ከፈሪሳውያንም ። ወደዚያም ፡ መጡ ፡ ፋናና ፡ የን
ጬት ፡ መብራት ፡ ይዘው ፡ ጋሻና ፡ ጦርም ። የሱስም ፡ ባ
ወቀ ፡ ጊዜ ፡ የሚመጣበትን ፡ ሁሉ ፡ ወጣ ፡ አላቸውም ።
ማንን ፡ ትሻላችሁ ። መለሱለት ፡ አሉትም ። የሱስን ፡ የ
ናዝሬቱን ። የሱስም ፡ አላቸው ። እኔ ፡ ነኝ ። ይሁዳም ፡ ያ
ስያዘው ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ቁሞ ፡ ነበር ። እኔ ፡ ነኝም ፡ ባላ
ቸው ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ኋላቸው ፡ ተመለሱ ፡ በምድር ፡ ላይም ፡ ወ
ደቁ ። ደግሞም ፡ ጠየቃቸው ፡ እንደዪህ ፡ ሲል ። ማንን ፡ ትሻላ
ችሁ ። እርሳቸውም ፡ አሉ ። የሱስን ፡ የናዝሬቱን ። የሱስ
ም ፡ መለሰ ፡ አላቸውም ። አልኋችሁ ። እኔ ፡ ነኝ ። እኔንም ፡
ትሹኝ ፡ እንደ ፡ ሆናችሁ ፡ እለዚህን ፡ ተው ፡ ይሒዱ ፡ ዘንድ ።
አሳልፎ ፡ የሰጠውም ፡ ምልክት ፡ ይሰጣቸው ፡ ነበር ፡ እን
ዲህ ፡ ሲል ። የምስመው ፡ እርሱ ፡ ነው ፡ ያዙትም ። የዚ
ያን ፡ ጊዜም ፡ መጣ ፡ ይሁዳ ፡ ወደ ፡ የሱስ ፡ አለም ። ደህ
ና ፡ ነህን ፡ መምሕር ፡ ሆይ ። ሳመውም ። የሱስም ፡ አለ
ው ። ወዳጄ ፡ ሆይ ፡ ለምን ፡ ነገር ፡ መጣህ ። ይሁዳ ፡ ሆይ ፡
በመሳም ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ አሳልፈህ ፡ ትሰጣለህን ። የዚ
ያን ፡ ጊዜም ፡ መጡ ፡ እጃቸውንም ፡ ጫኑ ፡ በየሱስ ፡ ላይ ፡
ያዙትም ። ሲሞን ፡ ጴጥሮስም ፡ እጁን ፡ ዘረጋ ፡ ሰይፋን
ም ፡ መዘዘ ፡ የካህናትንም ፡ አለቃ ፡ ባርያውን ፡ መታው ።
የቀኝ ፡ ጀሮውንም ፡ ቈረጠው ። የዚያም ፡ ባርያ ፡ ስም ፡
ማልኮስ ፡ ነበረ ። የሱስ ፡ ግን ፡ አለው ። ሰይፍህን ፡ መል
ስ ፡ ወደፎቱ ። ሰይፍን ፡ የሚመዝ ፡ በሰይፍ ፡ ይጠፋልና ።
ወይስ ፡ የማልችልን ፡ ይመስልሃል ፡ እለምን ፡ ዘንድ ፡ ወ
ደባቴ ፡ ከመላእክት ፡ ከ፲፪፡ ሌጌዎን ፡ የሚበዛ ፡ ይሰድል
ኝ ፡ ዘንድ ። ነገር ፡ ግን ፡ እንዴት ፡ ይፈጸማሉ ፡ መጻሕፍት ።
እንዲህ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ይገባልና ። ጀሮውንም ፡ ዳሶ ፡ አዳ
ነው ። የሱስም ፡ አለ ፡ ወደርሱ ፡ ለመጡት ፡ ለካህናት ፡ አ
ለቆች ፡ ለመቅደስም ፡ አዛዦች ፡ ለሽማግሎችም ። በሌባ ፡

እንድትወጡ ፡ በሰይፍና ፡ በበትር ፡ መጣችሁ ፡፡ ሁልግዜም ፡ እኔ ፡ ከላንተ ፡ ጋራ ፡ ነበርሁ ፡ በመቅደስ ፡፡ እጃችሁንም ፡ አልዘረጋችሁብኝም ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ይህች ፡ ጊዜያችሁ ፡ ናት ፡ የጨለማውም ፡ ሥልጣን ፡፡ እርሳቸውም ፡ ወሰዱት ፡ ይዘውትም ፡ መጡ ፡ ወደ ፡ ካህናት ፡ አለቃ ፡ ቤትም ፡ አገቡት ፡፡ ሲሞን ፡ ጴጥሮስም ፡ ከርሑቅ ፡ ተከተለው ፡፡ ሌላ ፡ ደቀ ፡ መዝሙርም ፡ በካህናት ፡ አለቃ ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ለበረኛዪቱ ፡ ነገራት ፡ ጴጥሮስንም ፡ አስገባው ፡፡ በረኛዪቱም ፡ ጴጥሮስን ፡ አለች ፡፡ አንተም ፡ ደግሞ ፡ ከዚያ ፡ ሰው ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ወገን ፡ ነህ ፡፡ ያም ፡ አለ ፡፡ እኔ ፡ አይደለሁም ፡፡ ባሮችም ፡ ጭፍሮችም ፡ እሳት ፡ አንድደው ፡ ነበሩ ፡ ብርድ ፡ ነበረና ፡፡ ይሞቁም ፡ ነበሩ ፡፡ ጴጥሮስም ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ቁሞ ፡ ይሞቅ ፡ ነበረ ፡፡ የካህናት ፡ አለቆች ፡ ግን ፡ ጻፎችም ፡ ሸንጎም ፡ ሁሉ ፡ ይሹ ፡ ነበሩ ፡ በየሱስ ፡ ላይ ፡ ያሰትን ፡ ምስክር ፡ ሊገድሉት ፡፡ አላገኙምም ፡፡ ብዙም ፡ ያሰት ፡ ምስክሮች ፡ መጡ ፡ አላገኙምም ፡፡ ከዚያ ፡ በኋላም ፡ ፪፡ ያሰት ፡ ምስክሮች ፡ መጡ ፡ አሉም ፡፡ ይህ ፡ አለ ፡፡ ቤተ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አፍርሼ ፡ በሦስተኛ ፡ ቀን ፡ እሰራዋለሁ ፡፡ የካህናትም ፡ አለቃ ፡ ተነሣ ፡ እንዲሁም ፡ አለ ፡፡ አንዷችን ፡ አትመልስምን ፡ እሌህ ፡ በሚመሰክሩብህ ፡፡ የሱስም ፡ ዝማለ ፡፡ የካህናት ፡ አለቃም ፡ መለሰ ፡ አለም ፡፡ እምልሃለሁ ፡ በሕያው ፡ እግዚአብሔር ፡ እንድትነግረን ፡፡ አንተ ፡ ክርስቶስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ሆንህ ፡፡ የሱስም ፡ አለው ፡፡ አንተ ፡ አልህ ፡፡ ደግሜም ፡ እላችኋለሁ ፡፡ ከዛሬ ፡ ጀምራችሁ ፡ እንድታዩ ፡ የሰውን ፡ ልጅ ፡ ሲቀመጥ ፡ በኃይል ፡ ቀኝ ፡ ሲመጣም ፡ በሰማይ ፡ ደመና ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ልብሱን ፡ ቀደደ ፡ የካህናት ፡ አለቃ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ እነሆ ፡ ሰደበ ፡፡ ምን ፡ አግደን ፡ እንጊዴህ ፡ ወደ ፡ ምስክር ፡፡ እነሆ ፡ አሁን ፡ ሰማችሁ ፡ ስድቡን ፡፡ እንጊዴህ ፡ ምን ፡ ትላላችሁ ፡፡ እርሳቸው ፡ ግን ፡ መለሱ ፡ እንዲህም ፡ አሉ ፡፡ ይህ ፡ ሞት ፡ ይገባዋል ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ተፏበት ፡ በፊቱ ፡ ጸፏትም ፡ ሌሎችም ፡ መቱት ፡ ፊቱን ፡ ሸፍነው ፡ እንዲህም ፡ አሉ ፡፡ ንገረን ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፡ ማነው ፡ የጸፋ

ህ ፡፡ ጴጥሮስም ፡ በታችኛው ፡ ቤት ፡ ሳለ ፡ ከካህናት ፡ አለ
ቃ ፡ ባሮች ፡ አንዷቱ ፡ መጣች ፡፡ ጴጥሮስንም ፡ በሳት ፡ ይሞ
ቅ ፡ ዘንድ ፡ ተቀምጦ ፡ ስታየው ፡ አስተዋለችው ፡ አለች
ም ፡፡ አንተም ፡ ደግሞ ፡ ከናዝሬቱ ፡ ከየሱስ ፡ ጋራ ፡ ነበር
ህ ፡፡ እርሱ ፡ ግን ፡ ካደ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ አላውቀውም ፡ አ
ላስተውለውምም ፡ አንች ፡ የምትዪውን ፡፡ ሜዳም ፡ ወ
ጣ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ደጅ ፡፡ ዶሮም ፡ ጮኸ ፡፡ ሌላዪቱም ፡ ባር
ያ ፡ አየችው ፡ ደግማ ፡፡ ለቆሙትም ፡ ትል ፡ ጀመረች ፡፡
ይህም ፡ ከርሳቸው ፡ ወገን ፡ ነው ፡፡ እርሱ ፡ ግን ፡ ደግሞ ፡
ካደ ፡፡ ከዚያም ፡ የቆሙ ፡ ጥቂት ፡ ቆይተው ፡ ጴጥሮስን ፡
አሉት ፡፡ አንተ ፡ በውነት ፡ ከርሳቸው ፡ ወገን ፡ ነህ ፡፡ አ
ንተም ፡ ደግመህ ፡ የገሊላ ፡ ሰው ፡ ነህና ፡፡ ነገርህም ፡ ነገራ
ቸውን ፡ ይመስላል ፡፡ እርሱ ፡ ግን ፡ ይረግም ፡ ይምልም ፡
ጀመረ ፡፡ እኔ ፡ አላውቀውም ፡ ይህነን ፡ ሰው ፡ የምትሉት
ን ፡፡ ደግሞ ፡ ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ዶሮ ፡ ጮኸ ፡፡ ጌታም ፡ ተመል
ሶ ፡ ጴጥሮስን ፡ ተመለከተ ፡፡ ጴጥሮስም ፡ አሰበ ፡ የሱስ ፡
ያለውን ፡ ነገር ፡፡ ዶሮ ፡ ፪፡ ጊዜ ፡ ሳይጮህ ፡ እንድትክድ
ኝ ፡ ፫፡ ጊዜ ፡፡ ወደ ፡ ሜዳም ፡ ወጣ ፡ መራራ ፡ ልቅሶም ፡
አለቀሰ ፡፡

በጸባም ፡ ጊዜ ፡ ተማከሩ ፡ የካህናት ፡ አለቆች ፡ ሁሉ ፡ የ
ሕዝብም ፡ ሽማግሎች ፡ በየሱስ ፡ ላይ ፡ ይገድሉት ፡ ዘንድ ፡፡
አሠሩትም ፡ ይዘውትም ፡ ሔዱ ፡ አሳልፈውም ፡ ሰጡት ፡ ለ
ጴንጤኑ ፡ ለጲላጦስ ፡ ለሮሜ ፡ ሹማቸው ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜ
ም ፡ ይሁዳ ፡ አሳልፎ ፡ የሰጠው ፡ እንደ ፡ ተፈረደበት ፡ ባየ ፡
ጊዜ ፡ አዘነ ፡ ፴፡ ብርም ፡ መለሰው ፡ ወደ ፡ ካህናት ፡ አለቆ
ች ፡ ወደ ፡ ሽማግሎችም ፡፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ ንጹሕ ፡ ደም ፡
አሳልፌ ፡ በመስጠቴ ፡ ክፉ ፡ አደረግሁ ፡፡ እርሳቸውም ፡ አ
ሉ ፡፡ እኛን ፡ ምን ፡ አግደነ ፡፡ አንተ ፡ እወቅ ፡፡ እርሱም ፡ ያ
ነን ፡ ብር ፡ በቤተ ፡ መቅደስ ፡ ጣለና ፡ ሔደ ፡ ታንቆም ፡ ሞ
ተ ፡፡ የካህናት ፡ አለቆችም ፡ ብሩን ፡ ወሰዱ ፡ እንዲህም ፡
አሉ ፡፡ አይገባነም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሣፅን ፡ እንጨ
ምረው ፡ ዘንድ ፡፡ የደም ፡ ዋጋ ፡ ነውና ፡፡ ተማከሩም ፡ የሸ
ቃ ፡ ሰሪ ፡ ምድርም ፡ ገዙበት ፡ ለንግዳ ፡ መቃበር ፡፡ ስለዚህ

ም ፡ ያች ፡ ምድር ፡ የደም ፡ መቃበር ፡ ተባለች ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡፡

ጲላጦስም ፡ ወደ፡ይሁድ ፡ ወጣ ፡ አለም ፡፡ ምን ፡ ኃጢአ ት ፡ ትናገራላችሁ ፡ በዚህ ፡ ሰው ፡፡ እርሳቸውም ፡ ያጣሉ ት ፡ ጀመሩ ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡፡ ይህነን ፡ አገኘነ ፡ ሕዝብን ፡ ሲ ገለብጥ ፡፡ ግብርም ፡ እንደ፡ይሰጥ ፡ ለቄሳር ፡ ይከለክላል ፡ እርሱም ፡ ክርስቶስ ፡ ንጉሥ ፡ እንደሆነ ፡ ይላል ፡፡ ይህ ፡ ክ ፉ ፡ ካላደረገ ፡ ወደንተ ፡ ባላመጣነው ፡፡ ጲላጦስም ፡ አላ ቸው ፡ ውሰዱት ፡ እላንተ ፡ ፍረዱበትም ፡ እንደ ፡ ሕጋች ሁ ፡፡ አይሁድም ፡ አሉ ፡፡ ለኛ ፡ አይገባነም ፡ ማንንም ፡ እ ንገድል ፡ ዘንድ ፡፡ ጲላጦስም ፡ ደግሞ ፡ ገባ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሱስንም ፡ ጸራ ፡ አለውም ፡፡ አንተን ፡ ነህ ፡ ያይሁ ድ ፡ ንጉሥ ፡፡ የሱስም ፡ መለሰለት ፡ አለውም ፡፡ አንተን ፡ ከልብህ ፡ ይህነን ፡ ትናገራለህ ፡ ወይስ ፡ ሌሎች ፡ ያሉህ ፡ ስ ለኔ ፡፡ ጲላጦስም ፡ መለሰ ፡ አለም ፡፡ በውኑ ፡ እኔ ፡ አይሁ ደዊን ፡ ነኝ ፡፡ ወገኖችህ ፡ የካህናትም ፡ አለቆች ፡ ወደኔ ፡ አ መጡህ ፡፡ ምን ፡ አድርገሃል ፡፡ የሱስም ፡ መለሰ ፡ አለው ም ፡፡ መንግሥቴ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ አይደለችም ፡፡ መንግ ሥቴስ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ብትሆን ፡ ሎሌቼ ፡ ይወጉልኝ ፡ ነበሩ ፡ ወደ ፡ አይሁድ ፡ እንዳልሰጥ ፡፡ አሁንም ፡ መንግሥ ቴ ፡ ከዚህ ፡ አይደለችም ፡፡ ጲላጦስም ፡ አለው ፡፡ እንኪ ያስ ፡ አንተ ፡ ንጉሥ ፡ ነህ ፡፡ የሱስም ፡ መለሰ ፡ አለም ፡፡ አ ንተ ፡ ትላለህ ፡፡ እኔም ፡ በውነት ፡ ንጉሥ ፡ ነኝ ፡፡ እኔ ፡ ስለ ዚህ ፡ ተወለድሁ ፡ ስለዚህም ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ መጣሁ ፡ ለ ውነት ፡ እመሰክር ፡ ዘንድ ፡፡ ከውነትም ፡ የሆነ ፡ ሁሉ ፡ ቃ ሌን ፡ ይሰማል ፡፡ ጲላጦስም ፡ አለው ፡፡ እውነት ፡ ምንድ ር ፡ ነው ፡፡ ይህነንም ፡ ብሎ ፡ ደግሞ ፡ ወጣ ፡ ወደ ፡ አይሁ ድ ፡ አላቸውም ፡፡ እኔስ ፡ አላገኘሁበትም ፡ አንዲት ፡ ነገር ፡ ስንኳ ፡ የሚያስኰንነው ፡፡ የካህናት ፡ አለቆችም ፡ እጅግ ፡ አጣሉት ፡፡ ጲላጦስ ፡ ግን ፡ ደግሞ ፡ ጠየቀው ፡ እንዲህ ፡ ሲ ል ፡፡ አንደች ፡ አትመልስምን ፡፡ እይ ፡ ስንት ፡ ይመሰክሩ ብሃል ፡፡ የሱስ ፡ ግን ፡ አንደች ፡ አልመለሰለትም ፡ ጲላጦ ስ ፡ ደግሞ ፡ እስኪደንቅ ፡ ድረስ ፡፡ እርሳቸው ፡ ግን ፡ ይጸኑ ፡

ነበረ ፡ እንደዚህ ፡ ሲሉ ፡፡ ሕዝብን ፡ አወከ ፡ ኢያስተማረ ፡ በ
ይሁዳ ፡ ሁሉ ፡ ከገሊላ ፡ ጀምሮ ፡ እስከዚህ ፡ ድረስ ፡፡ ጲላ
ጦስ ፡ ግን ፡ ገሊላን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ጠየቀ ፡ የገሊላ ፡ ሰው ፡
እንደ ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡፡ ባወቀም ፡ ጊዜ ፡ ከሄሮድስ ፡ ግዛት ፡ እ
ንደ ፡ ሆነ ፡ ወደ ፡ ሄሮድስ ፡ ሰደደው ፡፡ እርሱም ፡ ደግሞ ፡ በ
የሩሳሌም ፡ ነበረ ፡ በዚያች ፡ ወራት ፡፡ ሄሮድስም ፡ የሱስን ፡
ባየ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አለው ፡፡ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡
ይመኝ ፡ ነበረና ፡ ያየው ፡ ዘንድ ፡፡ እጅግ ፡ ነገር ፡ በርሱ ፡ ስ
ለ ፡ ሰማ ፡፡ ተስፋም ፡ ያድርግ ፡ ነበረ ፡ ታአምራት ፡ ያይ ፡
ዘንድ ፡ እርሱ ፡ የሚያድርጋትን ፡፡ እጅግ ፡ ነገርንም ፡
ጠየቀው ፡ እርሱ ፡ ግን ፡ ምንም ፡ አልመለሰለትም ፡፡ የ
ካህናትም ፡ አለቆች ፡ ቁመው ፡ እጅግ ፡ አጣሉት ፡፡ ሄሮ
ድስም ፡ አቃለለው ፡ ከሠራዊቱ ፡ ጋራ ፡ አፌዙበትም ፡፡
ብልጭልጭ ፡ የሚልም ፡ ልብስ ፡ አለበሱት ፡፡ መልሶም ፡
ወደ ፡ ጲላጦስ ፡ ሰደደው ፡፡ ጲላጦስና ፡ ሄሮድስም ፡ በዚያ ፡
ቀን ፡ ወዳጆች ፡ ሆኑ ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡፡ ቀድሞ ፡ በማኸላ
ቸው ፡ ጽል ፡ ነበረና ፡፡ ጲላጦስ ፡ ግን ፡ ጸራ ፡ የካህናትን ፡ አለ
ቆች ፡ የሕዝብንም ፡ ታላላቆች ፡ ከሕዝብ ፡ ጋራ ፡፡ አላቸው
ም ፡፡ ይህነን ፡ ሰው ፡ ወደኔ ፡ አመጣችሁት ፡ ሕዝቡን ፡ እን
ዲያውክ ፡፡ በፊታችሁም ፡ እነሆ ፡ መረመርሁት ፡ መክንያ
ትም ፡ አላገኘሁበትም ፡ በምታጣሉት ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በዚ
ህ ፡ ሰው ፡፡ ሄሮድስ ፡ ስንኳ ፡፡ ወደርሱ ፡ ሰድጀችሁ ፡ ነበር
ሁና ፡፡ እነሆም ፡ ያደረገው ፡ ነገር ፡ የለም ፡ ሞት ፡ የሚገባ
በት ፡፡ እኔም ፡ ስለዚህ ፡ ቀጥቼ ፡ ልስደደው ፡፡ በየፋሲካ ፡ በ
ዓልም ፡ ሁሉ ፡ ለሸም ፡ ልማድ ፡ ነበረው ፡ ለሕዝብ ፡ አን
ዲን ፡ የታሠረውን ፡ የወደዱትን ፡ ይተውላቸው ፡ ዘንድ ፡፡
የዚያን ፡ ጊዜም ፡ አንድ ፡ የታሠረ ፡ ነበረ ፡ የታወቀ ፡ በረባ
ን ፡ የሚባል ፡፡ እርሳቸውም ፡ ተከማይተው ፡ ሳሉ ፡ አላቸ
ው ፡ ጲላጦስ ፡፡ ማንን ፡ ትወዷላችሁ ፡ እተውላችሁ ፡ ዘን
ድ ፡ በረባንን ፡ ወይስ ፡ የሱስን ፡ ክርስቶስ ፡ የሚባለውን ፡፡
ያውቅ ፡ ነበረና ፡ የካህናት ፡ አለቆች ፡ በቅናት ፡ አሳልፈው ፡
እንደ ፡ ሰጡት ፡፡ እርሱም ፡ በወንበር ፡ ተቀምጦ ፡ ሳለ ፡ ላ
ከችበት ፡ ምሽቱ ፡ እንደዚህ ፡ ስትል ፡፡ ተጠንቀቅ ፡ በዚህ ፡ ጻ

ድቅ ፡ ክፉ ፡ አትስራ ፡፡ ዛሬ ፡ እጅግ ፡ መከራ ፡ ተቀብያለሁ
ና ፡ በሕልሜ ፡ ስለርሱ ፡፡ የካህናት ፡ አለቆች ፡ ግን ፡ ሽማግ
ሎችም ፡ ሕዝብን ፡ እሺን ፡ እንዲሉ ፡ አደረጓቸው ፡፡ ይለ
ምኑ ፡ ዘንድ ፡ በረባንን ፡ ለማደን ፡ ክርስቶስንም ፡ ለመግደ
ል ፡፡ ሹሙም ፡ መለሰ ፡ እንደህም ፡ አለ ፡፡ ከሁለቱ ፡ ማና
ቸውን ፡ እተውላችሁ ፡ ዘንድ ፡ ትሻላችሁ ፡፡ እርሳቸውም ፡
አሉ ፡፡ በረባንን ፡፡ ጲላጦስም ፡ አላቸው ፡፡ ምን ፡ ልስራበ
ት ፡ በየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሚባለው ፡፡ ሁሉም ፡ አሉ ፡፡ ይ
ሰቀል ፡፡ ሹምም ፡ አለ ፡፡ ምን ፡ ክፉ ፡ አደረገ ፡፡ እርሳቸው ፡
ግን ፡ ጩኸት ፡ አበዙ ፡ እንደህ ፡ ሲሉ ፡፡ ይሰቀል ፡፡ ይሰቀ
ል ፡፡ ጲላጦስም ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ አንዳች ፡ እንደይረባ ፡፡ ነገር ፡
ግን ፡ ሁከት ፡ እንዲበዛ ፡ ብቻ ፡፡ ውኃ ፡ አመጣ ፡ እጁንም ፡
ታጠበ ፡ በሕዝብ ፡ ፊት ፡ እንደህ ፡ ሲል ፡፡ እኔ ፡ ንጹሕ ፡ ነኝ ፡
በዚህ ፡ ጻድቅ ፡ ደም ፡፡ እላንተ ፡ እወቁ ፡፡ ሕዝብም ፡ ሁሉ ፡
መለሱ ፡ እንደህም ፡ አሉ ፡፡ ደሙ ፡ በኛና ፡ በልጆቻችን ፡ ላ
ይ ፡ ይሁን ፡፡ ጲላጦስም ፡ ወደደ ፡ ሕዝብን ፡ ደስ ፡ ያሰኛቸ
ው ፡ ዘንድ ፡፡ በረባንንም ፡ ተወላቸው ፡ የሱስንም ፡ ተገርፎ ፡
ይሰቀል ፡ ዘንድ ፡ ሰጠ ፡፡ ጭፍሮችም ፡ ይዘውት ፡ ሔዱ ፡ ወ
ደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ ጭፍራንም ፡ ሁሉ ፡ አከማቹበት ፡፡ ጲላ
ጦስም ፡ ወሰደ ፡ የሱስን ፡ ገረፈውም ፡፡ ጭፍሮችም ፡ ቃይ ፡
ሐርን ፡ አለበሱት ፡ የሾህም ፡ ዘውድ ፡ ጉንጉኑ ፡ በራሱም ፡
ላይ ፡ ደፉበት ፡፡ ሰላምም ፡ ይሰጡት ፡ ጀመሩ ፡ እንደህ ፡ ሲ
ሉ ፡፡ ደህንነት ፡ ትሁንልህ ፡ ያይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡፡ ዘንግ
ንም ፡ ሰጡ ፡ በቀኙ ፡፡ በጉልበታቸውም ፡ ተንበርክከው ፡ ሰ
ገዱለት ፡፡ ራሱንም ፡ በዘንግ ፡ መቱት ፡ ተፉበትም ፡ ተሣለቁ
በትም ፡፡ ጲላጦስ ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ ወጣ ፡ አላቸው
ም ፡፡ እነሆ ፡ እኔ ፡ አወጣላችኋለሁ ፡ ሜዳ ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡
እንደላገኘሁበት ፡ አንዲት ፡ የሚያስኰንነው ፡ መክንያት ፡
ስንኳ ፡፡ የሱስም ፡ ወጣ ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ የሾህ ፡ አክሊልን ፡ ቃ
ይ ፡ ልብስንም ፡ ለብሶ ፡፡ ጲላጦስም ፡ አላቸው ፡፡ እነሆት ፡
ያሰው ፡፡ ባዩትም ፡ ጊዜ ፡ የካህናት ፡ አለቆች ፡ ሎሌልታቸ
ውም ፡ ጮሁ ፡ እንደህ ፡ ሲሉ ፡፡ ስቀለው ፡ ስቀለው ፡፡ ጲላ
ጦስም ፡ አላቸው ፡፡ እላንተ ፡ ወስዳችሁ ፡ ስቀሉት ፡፡ እኔ ፡

ኃጢአት ፡ ኦላገኘሁበትምና ፡፡ አይሁድም ፡ መለሱለት ፡ አ
ሉትም ፡፡ ሕግ ፡ አለነ ፡ በሕጋችንም ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ ሞ
ት ፡ ይገባዋል ፡፡ ራሱን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ አድርጓል
ና ፡፡ ጲላጦስም ፡ ይህነን ፡ ነገር ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ፈ
ራ ፡፡ ደግሞ ፡ ገባ ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤት ፡ የሱስንም ፡፡ "አን
ተ ፡ ከወዴት ፡ ነህ ፡" አለው ፡፡ የሱስ ፡ ግን ፡ መላሽ ፡ አልሰ
ጠውም ፡ ጲላጦስም ፡ አለው ፡፡ አትናገረኝምን ፡፡ አታው
ቅምን ፡ እንደ ፡ ቻለኝ ፡ እሰቅልህ ፡ ዘንድ ፡ እተውህም ፡ ዘን
ድ ፡፡ የሱስም ፡ መለሰ ፡ አለም ፡፡ በኔ ፡ ባይቻልህ ፡ ከሰማ
ይ ፡ ካልተሰጠህ ፡፡ ስለዚህም ፡ ላንተ ፡ አሳልፎ ፡ የሰጠኝ ፡
ኃጢአቱ ፡ ይበልጣል ፡፡ ከዚያ ፡ ጀምሮ ፡ ወደደ ፡ ጲላጦስ ፡
ይተወው ፡ ዘንድ ፡፡ አይሁድ ፡ ግን ፡ ይጮሁ ፡ ነበረ ፡ እንደዬህ ፡
ሲሉ ፡፡ ይህነን ፡ ብተወው ፡ የቄሣር ፡ ወደጅ ፡ አይደለህም ፡፡
ራሱን ፡ ንጉሥ ፡ የሚያደርግ ፡ ሁሉ ፡ የቄሣር ፡ ጸላት ፡ ነው
ና ፡፡ ጲላጦስም ፡ ይህነን ፡ ነገር ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ የሱስን ፡ አ
ወጣው ፡ ወደ ፡ ሜደ ፡፡ በወንበርም ፡ ተቀመጠ ፡፡ አይሁድ
ንም ፡ አላቸው ፡፡ እነሆ ፡ ንጉሣችሁ ፡፡ እርሳቸው ፡ ግን ፡ ጮ
ሁ ፡ እንደዬህ ፡ ሲሉ ፡፡ አስወግደው ፡ ስቀለው ፡፡ ጲላጦስ
ም ፡ አላቸው ፡፡ ንጉሣችሁንን ፡ ልስቀለው ፡፡ የካህናት ፡ አ
ለቆችም ፡ መለሱ ፡ አሉትም ፡፡ ንጉሥ ፡ የለነም ፡ ከቄሣ
ር ፡ በቀር ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፡ ሊሰቀ
ል ፡፡ ጭፍሮችም ፡ ገፈፉት ፡ ያለበሱትን ፡ ቀይ ፡ ሐር ፡ የርሱ
ንም ፡ ልብስ ፡ አለበሱት ፡፡ ሊሰቅሉትም ፡ ወሰዱት ፡፡ አን
ዱንም ፡ መንገድ ፡ አላፊን ፡ ጕተቱት ፡ ሲሞን ፡ የሚባል ፡
የቀሬኑ ፡ ከሜደ ፡ ሲመጣ ፡ እርሱም ፡ የስክንድሮስና ፡ የ
ሩፎስ ፡ አባት ፡ መስቀሉን ፡ ይሸከም ፡ ዘንድ ፡፡ ከሕዝብ
ም ፡ እጅግ ፡ ሰዎች ፡ ይከተሉት ፡ ነበረ ፡ ሴቶችም ፡ ያለቀ
ሱለት ፡ የነበረ ፡፡ የሱስም ፡ ወደርሳቸው ፡ ተመለሰ ፡ አለ
ም ፡፡ እላንተ ፡ የየሩሳሌም ፡ ልጆች ፡ ለኔ ፡ አታልቀሱልኝ ፡፡
ነገር ፡ ግን ፡ አልቅሱ ፡ ለራሳችሁ ፡ ለልጆቻችሁም ፡፡ እነኋ
ት ፡ ቀን ፡ ትመጻለችና ፡ የሚሉባት ፡ ለመካኖች ፡ ምስጋና ፡
ይገባቸዋል ፡ ላልወለደም ፡ ሆድ ፡ ላላጠባም ፡ ጡት ፡፡ የዚ

ያን ፡ ጊዜም ፡ ይጀምራሉ ፡ ይሉ ፡ ዘንድ ፡ ተራሮችን ፡፡ በላ ያችን ፡ ውደቁ ፡፡ ኰረፍቶችንም ፡፡ ድፈኑን ፡፡ በርጥብ ፡ እን ጨት ፡ እንዲህ ፡ የሚደረግ ፡ ከሆነ ፡ በደረቀውስ ፡ እንዴ ት ፡ ይሆን ፡፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ደግሞ ፡ ሌሎችን ፡ ፪ ክፉ ፡ ያ ደረጉ ፡ ሊገልዋቸው ፡ አወጡ ፡፡ በደረሱም ፡ ጊዜ ፡ ጕልጐ ታ ፡ ወደሚሉት ፡ ቦታ ፡ ትርጓሜውም ፡ የራስ ፡ አጥንት ፡ ቦታ ፡፡ በከርቤ ፡ የተደባለቀ ፡ መጣጣ ፡ ሰጡት ፡፡ ቀመሰና ፡ እምቢ ፡ አለ ፡ ሊጠጠ ፡፡ ከዚያም ፡ ሰቀሉት ፡ ክፉ ፡ አድ ራጎችንም ፡፡ አንዱን ፡ በቀኙ ፡ ሁለተኛውንም ፡ በግራው ፡፡ የሱስንም ፡ በመኻከላቸው ፡፡ መጽሐፍ ፡ ሊፈጸም ፡ የሚ ል ፡፡ ከኃጥኣን ፡ ጋራ ፡ ተቈጠረ ፡፡ የሱስ ፡ ግን ፡ አለ ፡፡ አባ ቴ ፡ ሆይ ፡ ስረይላቸው ፡፡ የሚያድርጉትን ፡ አያውቁምና ፡፡ ልብሱንም ፡ ተካፈሉ ፡ ዕፃውም ፡ ተጣጣሉበት ፡ በነቢይ ፡ የተባለ ፡ ይፈጸም ፡ ዘንድ ፡፡ ልብሶቼን ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡ ተካፈሉ ፡ በቀሚሴም ፡ ዕፃ ፡ ተጣጣሉ ፡፡ ሕዝቡም ፡ ቁመ ው ፡ አዩት ፡፡ በሰቀሉትም ፡ ጊዜ ፡ ፫ ሰዓት ፡ ነበር ፡፡

ከዚያም ፡ ተቀመጡ ፡ የጠበቁት ፡፡ አለቆችም ፡ ከሕዝ ብ ፡ ጋራ ፡ አፌዙበት ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡፡ ሌሎችን ፡ አድንዋ ልና ፡ ራሱንም ፡ ያድን ፡ እርሱ ፡ ክርስቶስ ፡ እግዚአብሔ ር ፡ የመረጠው ፡ ከሆነ ፡፡ ጭፍራውም ፡ ደግሞ ፡ ያፌዙበ ት ፡ ነበሩ ፡ ወደርሱም ፡ ቀረቡ ፡ መጣጣም ፡ አቀረቡለት ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡፡ አንተስ ፡ ያይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ እንደ ፡ ሆን ህ ፡ ራስህን ፡ አድን ፡፡ ደግሞም ፡ ጽፈት ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ ተ ጻፈ ፡ የሞቱን ፡ መክንያት ፡ የሚናገር ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ ይህ ፡ ነው ፡ የሱስ ፡ የናዝሬቱ ፡ ያይሁድ ፡ ንጉሥ ፡፡ ይህነ ንም ፡ ጽፈት ፡ ካይሁድ ፡ ብዙ ፡ አነበቡት ፡ የሱስ ፡ የተሰ ቀለበት ፡ ስፍራ ፡ ቅርብ ፡ ነበረና ፡ ላገር ፡፡ ተጽፎም ፡ ነበር ፡ በብራእሥጥ ፡ ልሳን ፡ በፅርዕም ፡ በሮምም ፡፡ ያይሁድም ፡ ካህናት ፡ አለቆች ፡ ጲላጦስን ፡ አሉት ፡፡ አትጽፍ ፡ እርሱ ፡ ያይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እርሱ ፡ እንደ ለ ፡፡ እኔ ፡ ያይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ ነኝ ፡፡ ጲላጦስም ፡ መለሰ ፡ እ ለም ፡፡ የጻፍሁትን ፡ ጻፍሁ ፡፡ በየሱስ ፡ መስቀልም ፡ አጠ

ገብ ፡ ቆመው ፡ ነበረ ፡ እናቱ ፡ የናቱም ፡ እት ፡ ማርያም ፡ የ
ቀላዮጳ ፡ ምሽት ፡፡ ማርያምም ፡ የመግደላዊቱ ፡፡ የሱስ
ም ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ እናቱን ፡ የቆመውንም ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩ
ን ፡ የወደደውን ፡፡ እናቱን ፡ አላት ፡፡ አንቺ ፡ ሴት ፡ እነሆት ፡
ልጅሽ ፡፡ ደቀ ፡ መዝሙሩንም ፡ አለው ፡፡ እነኋት ፡ እናት
ህ ፡፡ ከዚያችም ፡ ሰዓት ፡ ጀምሮ ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ ወደ ፡
ቤቱ ፡ ወሰዳት ፡፡ ከክፉ ፡ አድራጎችም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ከተ
ሰቀሉት ፡ አንዱ ፡ ሰደበው ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ አንተስ ፡ ክር
ስቶስ ፡ እንደ ፡ ሆንህ ፡ ራስህን ፡ አድን ፡ እኛንም ፡፡ ሁለተኛ
ውም ፡ መለሰ ፡ ገሠጸውም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ አንተ ፡ እግ
ዚአብሔርን ፡ አትፈራምን ፡ አንተ ፡ እንደዚህ ፡ ባለ ፡ ኵነ
ኔ ፡ ሳለህ ፡፡ እኛስ ፡ በውነት ፡ ፍዳችነን ፡ ተቀበልነ ፡ በሚገባ
ነ ፡ ብናድርግ ፡፡ ይህ ፡ ግን ፡ አንዳች ፡ ክፉ ፡ አልሰራም ፡፡ የ
ሱስንም ፡ አለው ፡፡ አስበኝ ፡ አቤቱ ፡ ወደ ፡ መንግሥትህ ፡ በ
መጣህ ፡ ጊዜ ፡፡ የሱስም ፡ አለው ፡፡ በውነት ፡ እልሃለሁ ፡፡
ዛሬ ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ እንድትሆን ፡ በገነት ፡፡ ፮፡ ሰዓትም ፡ ጊዜ ፡
ነበረ ፡፡ ጨለማም ፡ ሆነ ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ሁሉ ፡ እስከ ፡ ፱፡
ሰዓት ፡ ድረስ ፡፡ ፀሓይቱም ፡ ጨለመች ፡፡ በ፱፡ ሰዓት ፡ ጊዜ
ም ፡ ጮኸ ፡ የሱስ ፡ በታላቅ ፡ ድምጽ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ ኤ
ሎሄ ፡ ኤሎሄ ፡ ለማ ፡ ሰበቅታኒ ፡፡ ትርጓሜ ፡ ይህ ፡ የሚሆ
ን ፡፡ አምላኬ ፡ አምላኬ ፡ ለምን ፡ ተውሀኝ ፡፡ ሕዝብም ፡
ከዚያ ፡ ከቆሙት ፡ ወገን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ አሉ ፡፡ ይህስ ፡ ኤ
ልያስን ፡ ይጸራል ፡፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ የሱስ ፡ ባወቀ ፡ ጊ
ዜ ፡ በመጽሐፍ ፡ ያለው ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ተፈጸመ ፡ አለ ፡፡ እ
ኔ ፡ ተጸማሁ ፡፡ ከዚያም ፡ እቃ ፡ ተቀምጦ ፡ ነበረ ፡ መጻጻ ፡
የመላበት ፡፡ አንድም ፡ ከርሳቸው ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ፈጠነ ፡
ሰፍነግንም ፡ ወሰደ ፡ መጻጻም ፡ መላባት ፡ በዘንግ ፡ ላይም ፡
አደረጋት ፡፡ አጠጠውም ፡፡ ሌሎች ፡ ግን ፡ አሉ ፡፡ ተውት ፡
እናያ ፡ ኤልያስ ፡ መጥቶ ፡ ያድነው ፡ እንደሆን ፡፡ መጣጣ
ውንም ፡ በቀመሰ ፡ ጊዜ ፡ የሱስ ፡ አለ ፡፡ ተፈጸመ ፡፡ ሁለተ
ኛ ፡ ጊዜም ፡ በታላቅ ፡ ድምጽ ፡ ጮኸ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ አባ
ት ፡ ሆይ ፡ በጅህ ፡ መንፈሴን ፡ አደራ ፡ እሰጣለሁ ፡፡ ይህነን
ም ፡ ብሎ ፡ ራሱን ፡ አዘነበለ ፡ ነፍሱንም ፡ ሰጠ ፡፡

እነሆም ፡ የመቅደስ ፡ መጋረጇ ፡ በሁለት ፡ ተቀደደ ፡ ከላ
ይ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ታች ፡ ድረስ ፡፡ ምድርም ፡ ተናወጸች ፡፡
ደንጎችም ፡ ተሰነጠቁ ፡፡ መቃበሮችም ፡ ተከፈቱ ፡፡ ብዙም ፡
ከቅዱሳን ፡ በድኖች ፡ የተኙት ፡ ተነሡ ፡፡ ከመቃበሬቸው
ም ፡ ወጡ ፡ ከትንሣኤው ፡ በኋላ ፡፡ ወደ ፡ ቅድስት ፡ አገር
ም ፡ ገቡ ፡ ለብዞችም ፡ ታዩ ፡፡ የመቶ ፡ አለቃም ፡ ከርሱም ፡ ጋ
ራ ፡ የነበሩ ፡ የሱስን ፡ ሲጠብቁ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ መናወጹን ፡ የሆነ
ውንም ፡ ሁሉ ፡ እጅግ ፡ ፈሩ ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡፡ በውነት ፡ ይህ ፡
ሰው ፡ ጻድቅ ፡ የእግዚአብሔርም ፡ ልጅ ፡ ነበረ ፡፡ ተከማችተ
ውም ፡ የነበሩት ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ይህነን ፡ ሁሉ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡
ደረታቸውን ፡ ኢየመቱ ፡ ተመለሱ ፡፡ ከሚያውቁትም ፡ ሰ
ዎች ፡ ርቀው ፡ ቁመው ፡ ነበሩ ፡፡ ሴቶችም ፡ ይከተሉት ፡ የ
ነበሩ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ከገሊላ ፡ ይህነን ፡ ያዩ ፡ ነበሩ ፡፡ ከርሳቸ
ውም ፡ ማርያም ፡ መግደላዊት ፡ ማርያምም ፡ የያዕቆብ ፡
የዮሴም ፡ እናት ፡ የዘብዴዎስም ፡ የልጆቹ ፡ እናት ፡፡ አይሁ
ድ ፡ ግን ፡ ሥጋቸው ፡ እንደይድር ፡ በመስቀል ፡ ላይ ፡ በሰን
በት ፡ ዓርብ ፡ ቀን ፡ ነበረና ፡፡ የዚያም ፡ ሰንበት ፡ ቀን ፡ ታላ
ቅ ፡ ነበረና ፡፡ ጲላጦስን ፡ ለመኑት ፡ ጭናቸው ፡ ይሰበሩ ፡ ዘ
ንድ ፡ ይወርዱም ፡ ዘንድ ፡፡ ጭፍሮችም ፡ መጡ ፡ የፊተኛው
ንም ፡ የኋለኛውንም ፡ ጭን ፡ ሰበሩ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የተሰቀ
ሉትን ፡፡ ወደ ፡ የሱስም ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ባዩም ፡ ጊዜ ፡ እ
ንደ ፡ ሞተ ፡ ጭኑን ፡ አልሰበሩም ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ከ
ጭፍሮች ፡ ጐኑን ፡ በጦር ፡ ወጋው ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ወ
ጣ ፡ ደምና ፡ ውኃ ፡፡ በመሸም ፡ ጊዜ ፡ ዓርብ ፡ ነበረችና ፡ ከ
ሰንበት ፡ በፊት ፡፡ መጣ ፡ ዮሴፍ ፡ ያርማትያ ፡ ባለ ፡ ሃይማ
ኖትም ፡ ለየሱስም ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ ነበረ ፡ ደር ፡ ተሰውሮ ፡
አይሁድን ፡ ስለ ፡ ፈራ ፡፡ እርሱም ፡ መካሪ ፡ ነበረ ፡ የተባበ
ረም ፡ አልነበረም ፡ በምክሬቸው ፡ በስራቸውም ፡፡ እርሱ
ም ፡ ደግሞ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ ተስፋ ፡ አደረ
ገ ፡፡ ይህም ፡ ደፍሮ ፡ ወደ ፡ ጲላጦስ ፡ መጣ ፡ የየሱስንም ፡
ሥጋ ፡ ለመነው ፡፡ ጲላጦስ ፡ ግን ፡ ተደነቀ ፡ ቶሎ ፡ እንደ ፡ ሞ
ተ ፡፡ የመቶንም ፡ አለቃ ፡ ወደርሱ ፡ ጸሬ ፡፡ ከርሱም ፡ አስተ
ዋለ ፡ ሙቶ ፡ እንደሆነ ፡ ቶሎ ፡፡ ነገሩም ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡ ከ

መቶ ፡ አለቃ ፡ ሥጋውን ፡ ለዮሴፍ ፡ ሰጠው ፡፡ ዮሴፍም ፡ በፍታውን ፡ ገዛ ፡ አወረደውም ፡፡ ደግሞ ፡ መጣ ፡ ኒቆዲሞስ ፡ የመጣው ፡ በሌት ፡ አስቀድሞ ፡፡ የተቀላቀለም ፡ ከርቤ ፡ ከሰብር ፡ ጋራ ፡ ፻፡ ረጥል ፡ የሚያህል ፡ አመጣ ፡፡ የየሱስንም ፡ ሥጋ ፡ ወሰዱ ፡ በበፍታም ፡ ጠቀለሉት ፡ ከሽቱ ፡ ጋራ ፡ እንደይሁድ ፡ ልማድ ፡ በመቀበሪያቸው ፡፡ በዚያም ፡ ስፍራ ፡ አዲስ ፡ መቃብር ፡ ነበረ ፡ ዮሴፍ ፡ ያስወቀረው ፡ በደንጊያ ፡፡ በርሱ ፡ ጨመሩ ፡ የየሱስን ፡ ሥጋ ፡ ስለ ፡ አይሁድ ፡ ዓርብ ፡ መቃበሩ ፡ ቀርብዋልና ፡፡ ታላቅ ፡ ደንጊያውንም ፡ ገጠሙ ፡ በመቃብር ፡ አፍ ፡ ሔዱም ፡፡ የቀደሚም ፡ አጽቢያ ፡ ነበረ ፡፡ ደግሞም ፡ ሴቶች ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የመጡ ፡ ከገሊላ ፡ ተከተሉት ፡፡ መቃበሩንም ፡ አዩ ፡ እንዴትም ፡ እንደ ፡ ተጨመረ ፡ ሥጋው ፡፡ ተመለሱም ፡ አዘጋጁም ፡ ሽቱንና ፡ ሰብርን ፡፡

በነጋውም ፡ ካርብ ፡ በኋላ ፡ በሚሆነው ፡ ተሰበሰቡ ፡ የካህናት ፡ አለቆች ፡ ፈሪሳውያንም ፡ ወደ ፡ ጲላጦስ ፡፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡፡ ጌታ ፡ ሆይ ፡ አሰብን ፡ ያጥፊዩ ፡ እንዲለ ፡ ሕያው ፡ ሳለ ፡፡ ከ፫፡ ቀን ፡ በኋላ ፡ እነሣለሁ ፡፡ እዘዝ ፡ መቃበሩ ፡ እንዲጠበቅ ፡ እስከ ፡ ፫፡ ቀን ፡ ድረስ ፡፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ በሌት ፡ መጽተው ፡ እንዳይሰርቁት ፡፡ ሕዝብንም ፡ እንዳይሉ ፡ ከሙታን ፡ እንደ ፡ ተነሣ ፡፡ የኋለኛዩቱም ፡ ጥፋት ፡ ከፊተኛዩቱ ፡ እንዳይከፋ ፡፡ ጲላጦስም ፡ አላቸው ፡፡ ጠባቆች ፡ አልዋችሁ ፡፡ ሒዱችሁ ፡ መቃበርን ፡ አጽኑ ፡ እንድታውቁ ፡፡ እርሳቸውም ፡ ሔዱ ፡ መቃበርንም ፡ አጸኑ ፡ አስጠበቁትም ፡፡ ደንጊያውንም ፡ አተሙ ፡፡

የየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሞት ፡ በመስቀል ፡ ካለም ፡ ፍጥረት ፡ ጀምሮ ፡ እስካለም ፡ ፍጻሚ ፡ ድረስ ፡ ከሆነና ፡ ከሚሆን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ይበልጣል ፡፡ የእግዚአብሔር ፡ ምክር ፡ ስለ ፡ መድኃኒታችን ፡ በርሱ ፡ ተፈጸመ ፡ መድኃኒታችንንም ፡ በርሱ ፡ አበጀ ፡፡ እግዚአብሔር ፡ በሕጉ ፡ የፈለገውን ፡ መታዘዝ ፡ በኛ ፡ ፈንታ ፡ በሕይወቱ ፡ ሁሉ ፡ ከታዘዘ ፡ በኋላ ፡ የኃጢአትን ፡ ዋጋ ፡ ሁሉ ፡ በኛ ፡ በኃጥኣን ፡ ፈንታ ፡ ተቀብሎ ፡ በኛ ፡ ፈንታ ፡ ተረገመ ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ ተለየ ፡

መርገምም ፡ ሆነ ፡ ለኃጢአታችን ፡ የሚገባውን ፡ ዋጋ ፡ ሁ
ሉ ፡ እስኪቀበል ፡ ድረስ ፡ በሞቱ ። ስለዚህም ፡ የነፍሱ ፡
መከራ ፡ ከሥጋው ፡ መከራ ፡ በለጠ ። በጌተሴማኒ ፡ ሲለም
ን ፡ ይህ ፡ ጽዋ ፡ እንዲያልፍ ፡ ከርሱ ፡ ብሎ ፡ ያባት ፡ ፈቃድ ፡
ቢሆን ። ይህ ፡ ጽዋ ፡ ሌላ ፡ አልነበረም ፡ የእግዚአብሔር ፡
ቍጣ ፡ እንጅ ፡ ወደ ፡ ታችኛው ፡ ገሃነም ፡ የሚቃጠል ፡ የሕ
ግም ፡ መርገም ፡ ኃጢአትን ፡ ሁሉን ፡ የሚከተል ። ዕዳች
ን ፡ ሁሉ ፡ በርሱ ፡ ተቈጥርዋልና ፡ የገሃነም ፡ እሳት ፡ ርጉ
ማን ፡ ለዘላለም ፡ የሚቃጠሉበት ፡ በነፍሱ ፡ ነደደ ። መለ
ኮቱም ፡ ካልደገፈው ፡ ሰውነቱ ፡ ቢጠፋበት ፡ ነበረ ። በሰው
ነቱም ፡ አንዲት ፡ ጥቂት ፡ ኃጢአት ፡ በተገኘ ፡ እርሱ ፡ ለራ
ሱ ፡ ለዘላለም ፡ ቢኖር ፡ ነበር ፡ በዚህች ፡ በገሃነም ፡ ጭንቀ
ት ። በመለኮቱም ፡ መክንያት ፡ የሰውነቱ ፡ መከራና ፡ ሞ
ት ፡ ለዘላለም ፡ መድኃኒታችን ፡ ተበጀ ፡ ስለሚያምንበት ፡
ሰው ፡ ሁሉ ። እንደህም ፡ ሆነ ፡ የነፍሱ ፡ መከራ ፡ በጉልጉ
ታ ። በንጨት ፡ የተሰቀለ ፡ ሁሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሕግ ፡
ርጉም ፡ ሆነ ። ሰውም ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛ
ዝ ፡ ስላልጠበቀ ፡ ተረግምዋልና ፡ ክርስቶስም ፡ በተቀደሰ
ች ፡ ሰውነቱ ፡ መርገማችንን ፡ ከኛ ፡ ዘንድ ፡ ሊያስወግድ ፡
በማይጨርስ ፡ ፍቅሩ ፡ በወደደ ፡ ጊዜ ፡ እርሱም ፡ ተረገም ፡
በንጨት ፡ ተሰቅሎ ። ማን ፡ ይችላል ፡ ይናገር ፡ ዘንድ ፡ ያን
ን ፡ ጭንቀት ፡ ያነንም ፡ መከራ ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የተቀበ
ለውን ፡ በጮኸ ፡ ጊዜ ። አምላኬ ፡ አምላኬ ፡ ለምን ፡ ተ
ውኸኝ ። ይህም ፡ ነገሩ ፡ የምሥጢራት ፡ ሁሉ ፡ ምሥጢር ፡
የሚሆን ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ልጁን ፡ እንደ ፡ ተወ ፡ የ
መድኃኒታችነን ፡ ፍጻሜ ፡ ያደርጋል ። ለዚህ ፡ ምልክት ፡
ሊሆን ፡ የቤተ ፡ መቅደስ ፡ መጋረጃ ፡ ተቀደደ ፡ የክርስቶስ ፡
ሰውነት ፡ በሞቱ ፡ በተቀደደ ፡ ጊዜ ። ኃጢአት ፡ እርሱ ፡ በእ
ግዚአብሔርና ፡ በሰው ፡ መካከል ፡ መለዮት ፡ የነበረ ፡ ተሽ
ርዋልና ። አሁንም ፡ መንገድ ፡ ተከፈተ ፡ ወደ ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ወደ ፡ ዘላለምም ፡ ደህንነት ፡ ለሚያምን ፡ ሁሉ ። ይ
ህነንም ፡ መድኃኒት ፡ ልናገኝ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ይፈለጋ
ል ። ያለዚህም ፡ አይሆንም ። እርሱም ፡ ይህ ፡ ነው ፡ እግዚ

አብሔር ፡ ተስፋ ፡ ስላስደረገ ፡ በዘካርያስ ፡ በነቢይ ። ም ፡ ፲፪፤ ቍ ፡ ፲። እንደዚህ ፡ ሲል ። በዳዊት ፡ ቤት ፡ እርስዋም ፡ እውነተኞዪቱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በመንፈሳዊቱም ፡ የሩ ሳሌም ፡ ወገኖች ፡ ላይ ፡ የጸጋና ፡ የጸሎትን ፡ መንፈስ ፡ አፈ ሳለሁ ። እኔንም ፡ ይመለከቱኛል ፡ የወጉኝ ፡ ያለቀሱብኛል ም ፡ ባንድ ፡ ልጁ ፡ እንደሚያለቅስ ፡ ሰው ። ያዝኑብኛል ም ፡ ሰው ፡ እንዲያዝን ፡ የበኵር ፡ ልጁ ፡ ሲሞትበት ።

የዚህች ፡ ትንቢት ፡ ማለት ፡ ይህ ፡ ነው ። የሱስ ፡ ክርስቶ ስ ፡ በነቢይ ፡ በዘካርያስ ፡ አፍ ፡ ይናገረናል ፡ ጊዜ ፡ እንደለ ው ፡ መንፈሱን ፡ በውነት ፡ ለሚያምኑ ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ። ይ ህነን ፡ የክርስቶስን ፡ መንፈስ ፡ የጸጋና ፡ የጸሎት ፡ መንፈ ስ ፡ ይለዋል ። እርሱ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጸጋ ፡ ይሰጠናል ና ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘውን ፡ ጸሎት ፡ ልና ድርግ ። በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ጸጋ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ብን ለምን ፡ የክርስቶስን ፡ መድኃኒት ፡ እንዲገልጽ ፡ በልባች ን ፡ እግዚአብሔር ፡ የነፍሳችንን ፡ ዓይን ፡ ይከፍትልናል ፡ ወደ ፡ ክርስቶስ ፡ እናይ ፡ ዘንድ ፡ በልባችንም ፡ እናውቅ ፡ ዘ ንድ ፡ እርሱ ፡ በኃጢአታችን ፡ መክንያት ፡ ብቻ ፡ ይህነን ፡ መከራ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ተቀበለ ፡ በኃጢአታችንም ፡ መክን ያት ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ሞተ ። ይህነንም ፡ አውቆ ፡ የሚያም ን ፡ እንዲህ ፡ ይላል ። ክርስቶስን ፡ እንዲህ ፡ አድርገው ፡ ያ ሠቃዩት ፡ ያሠሩትም ፡ የተላገጹበትም ፡ የተፉበትም ፡ በግ ፊም ፡ የፈረዱበት ፡ የገረፉትም ፡ ያስነወሩትም ፡ የሰቀሉ ትም ፡ የገደሉትም ፡ አይሁድ ፡ ብቻ ፡ አልነበሩም ። እኔ ፡ ነኝ ፡ እንጂ ፡ በኃጢአቴ ፡ የዚህ ፡ ሁሉ ፡ መክንያት ፡ የሆን ሁ ። በኃጢአቴ ፡ ሁሉ ፡ በትዕቢቴ ፡ በጸላትነቴም ፡ በሐሜ ቴም ፡ በዝሙቴም ፡ በርኵሰቴም ፡ ክብትን ፡ በመመኘቴ ም ፡ ባለማመኔም ፡ ባለመታዘዜም ፡ በሀኬቴም ፡ በክፋቴ ም ፡ ሁሉ ፡ ከሕፃንነቴ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ አሁን ፡ ድረስ ፡ በ ማሰቡም ፡ በነገርም ፡ በስራም ፡ ባደረግሁ ፡ አሁንም ፡ በል ቤ ፡ ባለው ፡ ሳውቀውም ፡ ሳላውቀውም ፡ ክርስቶስን ፡ አሰቀልሁት ፡ አስገደልሁትም ። ይህ ፡ ማለቱ ፡ ነው ፡ ሲ ል ። መእምናን ፡ እኔን ፡ እርሳቸው ፡ የወጉኝን ፡ ይመለከ

ቱኛል ፡፡ ስለ ፡ ኃጢአታቸውም ፡ ያዝናሉ ፡ በኃጢአታቸው ፡ ገድለውኛልና ፡፡ ይህ ፡ እውነተኛ ፡ ሃይማኖት ፡ ነው ፡፡ በ ክንቱ ፡ ያለውን ፡ ክርክር ፡ እግዚአብሔር ፡ ስላልገለጸው ፡ ምሥጢር ፡ አይወድም ፡፡ ደሮ ፡ ስለ ፡ ኃጢአቱ ፡ ያዝናል ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ሐዘን ፡፡ ከኃጢአትም ፡ ኃሪ ፡ ይጸላል ፡ ክር ስቶስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ያለምም ፡ ሁሉ ፡ ጌታ ፡ ስ ለ ፡ ሰው ፡ ኃጢአት ፡ የምስጋናውን ፡ ዙፋን ፡ በሰማይ ፡ ትት ዋልና ፡ በኃጢአቱም ፡ መክንያት ፡ ሞተ ፡፡ ይህም ፡ ሃይማ ኖት ፡ ስለኛ ፡ በተሰቀለ ፡ ክርስቶስ ፡ ይመካል ፡፡ በውነት ፡ የሚያምን ፡ ያውቃልና ፡ እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ኃጢአቱ ፡ ከቶ ፡ እንደይፈርድበት ፡፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ ሁሉ ፡ በኛ ፡ ፈንታ ፡ በክርስቶስ ፡ ከፈሰሰ ፡ በኋላ ፡ ወደኛ ፡ አደደር ስም ፡፡ ክርስቶስ ፡ በኛ ፡ በኃጥኣን ፡ ፈንታ ፡ ኃጥእ ፡ ሁኖ ፡ ተ ቈጥርዋልና ፡ ኃጢአታችን ፡ ኃጢአቱ ፡ ሁኖ ፡ ሲቈጥር ፡ እ ርሱም ፡ የኃጢአታችን ፡ ዋጋ ፡ በኛ ፡ ፈንታ ፡ ሲቀበል ፡፡ እ ኛ ፡ እንጊዴህ ፡ በሃይማኖት ፡ እርሱን ፡ ዋሳችን ፡ ሁኖ ፡ ብን ቈጥረው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ከኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ ንጹ ሓን ፡ ሁነን ፡ እንቈጠራለን ፡፡ የክርስቶስም ፡ ጽድቅ ፡ ሁ ሉ ፡ እርሱ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ ለመፈጸም ፡ የሰራ ፡ ሁሉ ፡ ገንዘባችን ፡ ሁኖ ፡ ይቈጠራል ፡፡ እኛም ፡ ስለዚህ ፡ በ እግዚአብሔር ፡ ፍርድ ፡ ጻድቃን ፡ ሁነን ፡ ቅዱሳንም ፡ ፍጹ ማንም ፡ ሁነን ፡ እንቈጠራለን ፡፡ እንደሀ ፡ ክርስቶስ ፡ በ ፍቅሩ ፡ ነፍሱን ፡ ለወጠ ፡ ስለ ፡ በጎቹ ፡ እንዲሁም ፡ እኛ ፡ ነፍሳችነን ፡ እንለውጣለን ፡ ስለርሱ ፡ በሃይማኖት ፡፡ በው ነትም ፡ የሚያምን ፡ እንዴህ ፡ ይላል ፡፡ "የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ከፍጥረቴ ፡ ያልነበረልኝ ፡ ሕያውትን ፡ ሃይማኖ ት ፡ በልቤ ፡ ሰራ ፡ የወንጌሉን ፡ ነገር ፡ በከፈተልኝ ፡ ጊዜ ፡፡ በሃይማኖትም ፡ ክርስቶስን ፡ እቀበላለሁ ፡፡ እርሱ ፡ ራሱ ን ፡ ለወጠ ፡ ስለኔ ፡ እርሱም ፡ ገንዘቤ ፡ ነው ፡፡ የኔ ፡ አምላ ክ ፡ የኔም ፡ ነቢይ ፡ የኔም ፡ አስተማሪ ፡ የኔም ፡ ካህን ፡ የኔ ም ፡ ንጉሥ ፡ የኔም ፡ መድኃኒት ፡ ለዘላለም ፡፡ እርሱም ፡ የሰራ ፡ ሁሉ ፡ ገንዘቤ ፡ ነው ፡፡ እርሱ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ ሲፈጽም ፡ በፈንታዬ ፡ እኔ ፡ ፈጸምሁት ፡፡ እርሱም ፡

በፊንታዬ ፡ ሲሰቀል ፡ እኔ ፡ ተሰቀልሁ ፡፡ እርሱም ፡ በስፍራ
ዬ ፡ ሲሞት ፡ እኔ ፡ ሞትሁ ፡ እርሱም ፡ ሲነሣ ፡ እኔ ፡ ከርሱ ፡
ጋራ ፡ ተነሣሁ ፡ እርሱም ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ሲወጣ ፡ እኔ ፡ ከ
ርሱ ፡ ጋራ ፡ ወጣሁ ፡፡ እርሱ ፡ በኔ ፡ ነውና ፡ እኔም ፡ በርሱ ፡
ነኝ ፡፡ እርሱም ፡ የኔ ፡ ገንዘብ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንዲሁም ፡ እ
ኔ ፡ ደግሞ ፡ ገንዘቡ ፡ ሆንሁ ፡፡ እኔ ፡ የርሱ ፡ ፍጥረት ፡ ነኝ ፡ ደ
ግሞ ፡ በዚህ ፡ አልደነሁም ፡፡ እርሱ ፡ ግን ፡ ራሱን ፡ ስለኔ ፡ ሲ
ለውጥ ፡ ነፍሴንና ፡ ሥጋዬን ፡ ሁለንተናዬንም ፡ ተዋጀ ፡ በደ
ሙ ፡፡ ኃጢአቴን ፡ ኃጢአቱ ፡ ሁኖ ፡ ቈጠረው ፡ ዕዳዬንም ፡
ዕዳው ፡፡ ስለዚህም ፡ ኃጢአቴ ፡ ሁሉ ፡ ተሻረ ፡ ዕዳዬም ፡ ተ
ከፈለ ፡ በሞቱ ፡፡ እንግዴህ ፡ ወይህም ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ አደገባ
ኝም ፡ በኃይሌ ፡ ሁሉ ፡ በማሰብም ፡ በመናገርም ፡ በምግባ
ርም ፡ ሁሉ ፡ ላመሰግነው ፡ እንጂ ፡ ሁለግዜ ፡፡"

ይህም ፡ በውነት ፡ የመስቀል ፡ ቃል ፡ ነው ፡ ቅዱሳን ፡ ሐ
ዋርያት ፡ እንደስተማሩት ፡፡ ጳውሎስም ፡ ይላል ፡ ፩ ፡ ቆሮን
ቶስ ፡ ፪ ፡ ፩ ፡፡ እኔም ፡ ወደላንት ፡ በመጣሁ ፡ ጊዜ ፡ ወንድሞ
ቼ ፡ ሆይ ፡ ነገር ፡ በማበርታት ፡ አልመጣሁም ፡ በሰውም ፡
ጥበብ ፡ አላስተማርኋችሁም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትምር
ት ፡፡ በራሴም ፡ አልፈረድሁም ፡ አንደችን ፡ አውቅ ፡ ዘንድ ፡
በመካከላችሁ ፡ ከየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በቀር ፡ እርሱንም ፡
የተሰቀለውን ፡፡ እንዲሁም ፡ ይላል ፡ ለገላትያን ፡ ሰዎች ፡፡
እኔ ፡ አልመካም ፡ በጌታችን ፡ በየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መስቀ
ል ፡ እንጅ ፡፡ በርሱ ፡ ዓለም ፡ የተሰቀለልኝ ፡ እኔም ፡ ለዓለ
ም ፡፡ ገላትያን ፡ ፯ ፡ ፲፬ ፡፡ እርሱም ፡ የመስቀል ፡ እንጨት ፡
አይደለም ፡ የመስቀልም ፡ ምልክት ፡ የመስቀል ፡ ትምር
ት ፡ እንጂ ፡ አሁን ፡ እንደሳየነ ፡፡ የመስቀል ፡ ቃል ፡ የመስ
ቀልም ፡ ትምርት ፡ መድኃኒታችን ፡ ነው ፡ ወደ ፡ ልባችን ፡
ብቻ ፡ ቢገባ ፡፡ ደግሞ ፡ የመስቀል ፡ ቃል ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
ላልተማሩ ፡ ሁለተኛም ፡ ላልተወለዱ ፡ ሰዎች ፡ስንፍናና ፡
ዕንቅፋት ፡ ነው ፡፡ እንዴህ ፡ በጳውሎስ ፡ ዘመን ፡ ነበረ ፡ እስ
ካሁን ፡ ድረስም ፡ እንዴህ ፡ ሁኖ ፡ ኖረ ፡፡ ፩ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ፩ ፡
፲፰ ፡፡ ሰው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቅድስና ፡ የራሱንም ፡ ኃጢ
አት ፡ ባያውቅ ፡ የመጸደቃችንንም ፡ ነገር ፡ አያስተውልም ፡

እግዚአብሔር ፡ እንዲያው ፡ እንዲያጸድቀን ፡ በሃይማኖ ት ፡ ብቻ ፡ ያለ ፡ ምግባር ፡፡ የክርስቶስን ፡ ምግባር ፡ አይቈ ጥርምና ፡ ከንቱም ፡ ሁኖበታልና ፡ በመደገም ፡ ቅዱሳንንም ፡ በመሳም ፡ ለቅዱሳንም ፡ በመስገድ ፡ በልመናቸውም ፡ በጸ ሎቱም ፡ በትጋቱም ፡ በጾሙም ፡ ለድኆችም ፡ ወርቅና ፡ ብ ሩርን ፡ በመስጠት ፡ መጸደቅ ፡ ይፈልጋል ፡፡ ይህ ፡ ግን ፡ የሰይ ጣን ፡ ነገር ፡ ነው ፡ የሰውን ፡ ልብ ፡ በጨለማ ፡ የሚመላ ፡ የ መስቀልን ፡ ነገር ፡ እንደያስተውል ፡፡ ስንት ፡ ጊዜ ፡ ይናገራ ልና ፡ እግዚአብሔር ፡ በቅዱስ ፡ ቃሉ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአ ተኛ ፡ ሁንዋልና ፡ በምግባሩ ፡ መጸደቅ ፡ እንደይችል ፡፡ ስን ት ፡ ጊዜም ፡ ይላል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በወንጌልና ፡ በነቢያ ት ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በሃይማኖት ፡ ብቻ ፡ እንዲጸድቅ ፡ በም ግባርም ፡ አይደለም ፡፡ ደሮ ፡ ከኢሳይያስ ፡ ቀን ፡ ጀምሮ ፡ እ ስካሁን ፡ ድረስ ፡ የወንጌል ፡ መልክተኞች ፡ እንዲህ ፡ ብለ ው ፡ ያለቅሳሉ ፡፡ አቤቱ ፡ ማን ፡ ያምናል ፡ በትምርታችን ፡፡ ለማንም ፡ ተገለጸ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ክንድ ፡፡

ለዚህም ፡ ነገር ፡ አንዲት ፡ ምዕራፍ ፡ ከኢሳይያስ ፡ ትን ቢት ፡ እንጨምራለን ፡፡ ኢሳይያስ ፡ ፶፫ ። እንዲህ ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡፡

" እነሆ ፡ ባርያዬ ፡ መልካም ፡ ይገዛል ፡ ግሩምም ፡ እጅግ
" ም ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላል ፡፡ ብዞችም ፡ ይሰናከሉበታል ፡፡ መ
" ልኩ ፡ ከሰው ፡ መልክ ፡ ይከፋልና ፡ ማየቱም ፡ ከአደም ፡
" ልጆች ፡ ማየት ፡ ይናቃል ፡፡ ደሮ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ብዙ ፡ አሕ
" ዛብን ፡ ይረጫቸዋል ፡ ነገሥታት ፡ እንኳ ፡ አፋቸውን ፡ በ
" ፊቱ ፡ እስኪዘጉ ፡ ድረስ ፡፡ የምስራች ፡ ያልተናገረላቸው ፡
" ደስ ፡ ብለው ፡ ያዩታል ፡፡ ያልሰሙትም ፡ ያስተውሉታል ፡፡
" ነገር ፡ ግን ፡ ማን ፡ ያምናል ፡ ስብከታችንን ፡፡ ለማንስ ፡ ይገለ
" ጻል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ክንድ ፡፡ በፊቱ ፡ ይሠርጻልና ፡ እን
" ደ ፡ ጫፍ ፡ እንደ ፡ ሥርም ፡ ከደረቀች ፡ ምድር ፡፡ መልክና ፡
" ውበት ፡ አልነበረለትም ፡፡ እኛ ፡ አየነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ው
" ብ ፡ የለውም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝን ፡፡ እርሱም ፡ ከሰው ፡ የ
" ተናቀ ፡ ያልከበረም ፡ ነበር ፡ የጻር ፡ ሰው ፡ ከደዌም ፡ ጋራ ፡
" የተዋወቀ ፡ እርሱም ፡ ተናቀ ፡ ሰው ፡ ፊቱን ፡ ከርሱ ፡ እስኪ

“ ሰውር ፡ ድረስ ፡ ስለዚህ ፡ አላከበርነውም ፡፡ እርሱ ፡ ግን ፡
“ በውነት ፡ የኛን ፡ ሕማም ፡ ወሰደ ፡ የኛንም ፡ ቍስል ፡ ተሸ
“ ከመ ፡፡ እኛም ፡ እንደ ፡ ተቀሠፈው ፡ ከእግዚአብሔር
“ ም ፡ እንደ ፡ ተመታ ፡ እንደ ፡ ተሠቀየም ፡ ቈጠርነው ፡፡ ነ
“ ገር ፡ ግን ፡ በክፋታችን ፡ መክንያት ፡ ተወጋ ፡ በኀጢአታች
“ ንም ፡ መክንያት ፡ ተቀጠቀጠ ፡፡ የደህንነታችንም ፡ መቅሠ
“ ፍት ፡ በላየው ፡ ነው ፡ በቍስሉም ፡ እኛ ፡ ተፈወስነ ፡፡ እ
“ ኛ ፡ ሁላችን ፡ በስሕተት ፡ እንደሚጠፋ ፡ በጎች ፡ ተቅበዘበ
“ ዝነ ፡ ሁሉ ፡ ኢየራሱ ፡ የብቻውን ፡ መንገድ ፡ ጠበቀ ፡፡ ደ
“ ሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሁላችንን ፡ ኀጢአት ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡
“ ጣለው ፡፡ እርሱም ፡ በተጨነቀ ፡ በተሠቀየም ፡ ጊዜ ፡ አ
“ ፉን ፡ አልከፈተም ፡ ወደ ፡ ማረጃ ፡ እንደ ፡ ሚጐቱት ፡ በ
“ ግ ፡፡ እንደ ፡ በግም ፡ ጸጕሩን ፡ በሸላቹ ፡ ፊት ፡ ዝም ፡ እን
“ ደሚል ፡ አፉንም ፡ አልከፈተም ፡፡ በጭንቀትና ፡ በፍርድ ፡
“ ተነጠቀ ፡፡ ማን ፡ ይናገራል ፡ ትውልዱን ፡፡ ከሕያዋን ፡ ም
“ ድር ፡ ተነጥቅዋልና ፡ በሕዝቤ ፡ ክፋት ፡ መክንያት ፡ በተ
“ ሠቀየ ፡ ጊዜ ፡፡ መቃበሩን ፡ ባመፀኞች ፡ መኻከል ፡ ሊሰ
“ ጡት ፡ ወደዱ ፡ በሞቱ ፡ ግን ፡ በከበሩ ፡ ሰዎች ፡ መኻከል ፡
“ ሆነ ፡፡ በማንም ፡ ግፍ ፡ አላደረገምና ፡ አሰትም ፡ ባፉ ፡ ከ
“ ቶ ፡ አልተገኘም ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ እንዴህ ፡ በሕማ
“ ም ፡ ይቀጠቅጠው ፡ ዘንድ ፡ ፈቀደ ፡፡ ሕይወቱን ፡ ስለ ፡ ኀ
“ ጢአት ፡ ለመሥዋት ፡ ከሰጠው ፡ በኋላ ፡ ዘር ፡ ይሆንለታ
“ ል ፡ ዕድሚውንም ፡ ያስረዝማል ፡ የእግዚአብሔርም ፡ ፈ
“ ቃድ ፡ በጁ ፡ ይበጃል ፡፡ ከነፍሱ ፡ ድካም ፡ ፍሬውን ፡ ያያ
“ ል ፡ ይጸግባልም ፡፡ እርሱም ፡ ጻድቅ ፡ ባርያየ ፡ በውቀቱ ፡
“ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ያጸድቃል ፡ ኀጢአታቸውን ፡ ተሸክምዋል
“ ና ፡፡ ስለዚህም ፡ ታላቅ ፡ ሕዝብን ፡ እሰጠዋለሁ ፡ ለምር
“ ኮ ፡፡ ብርቱችም ፡ ፈንታው ፡ ይሆኑለታል ፡፡ ሕይወቱን ፡ ለ
“ ሞት ፡ ሰጥትዋልና ፡ ከክፉ ፡ አድራጎችም ፡ ጋራ ፡ ተካከ
“ ሎ ፡ ተቈጠረ ፡ የብዙዎችንም ፡ ኀጢአት ፡ ተሸከመ ፡ ለክፉ ፡
“ አድራጎችም ፡ ለመነ ፡፡ ”

የኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ በመቃበር ፡ አልኖረም ፡ ጥፋትን
ም ፡ አላየም ። መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በዳዊት ፡ አፍ ፡ ከ፲፻፡ አ
መት ፡ የሚበዛ ፡ ክርስቶስ ፡ ሳይመጣ ፡ ትንቢትን ፡ ተናገ
ረ ፡ እንደህ ፡ ሲል ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ። ነፍሴን ፡ በመቃበ
ር ፡ አተዋትም ። ጻድቅህን ፡ ጥፋትን ፡ ለማየት ፡ አተወ
ውምና ። መዝሙር ፡ ፲፮፡ ፲። ጴጥሮስም ፡ በጴንጤቆስቴ ፡
ቀን ፡ በየሩሳሌም ፡ ይህነን ፡ የዳዊትን ፡ ትንቢት ፡ ሲናገር ፡
ይላል ። እላንት ፡ ሰዎች ፡ ወንድማማች ፡ ይገባል ፡ ለላን
ት ፡ ይባል ፡ ዘንድ ፡ በግልጥ ፡ ስለ ፡ ዳዊት ፡ ስላባቶች ፡ አለ
ቃ ። እንደረፈ ፡ እንደ ፡ ተቀበረም ፡ መቃበሩም ፡ በኛ ፡ ዘን
ድ ፡ ነው ፡ እስከ ፡ ዛሬ ። ነቢይ ፡ ግን ፡ ነበረና ። ባወቀም ፡ ጊ
ዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ መሐላ ፡ እንደ ፡ ማለለት ፡ ክርስቶስን ፡
እንዲያስነሣ ፡ ከወገቡ ፡ ፍሬ ፡ በዙፋኑ ፡ ይቀመጥ ፡ ዘን
ድ ። አስቀድሞ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ተናገረ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ትን
ሣኤ ። ነፍሱ ፡ በሲኦል ፡ አትቀርምና ፡ ሥጋውም ፡ ጥፋት
ን ፡ አያይምና ። ይህነን ፡ የኢየሱስን ፡ እግዚአብሔር ፡ አስነሣ
ው ። እኛም ፡ ሁላችን ፡ እንመሰክራለን ። የሐዋርያት ፡ ስ
ራ ፡ ፪፡ ፳፱።

ጌታችንም ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሳይሞት ፡ ለደቀ ፡ መዛ
ሙርቱ ፡ ተስፈ ፡ እንደስደረገላቸው ፡ በሶስተኛ ፡ ቀን ፡ ከ
ሞቱ ፡ በኋላ ፡ እንደ ፡ ነሣ ፡ እንደህ ፡ ሆነ ። ባርብ ፡ ሙትዋል
ና ፡ በእሑድም ፡ ማልደ ፡ ከሙታን ፡ ተነሣ ።

የክርስቶስ ፡ የትንሣኤው ፡ ምሥጢር ፡ እንደ ፡ ሞቱ ፡ ም
ሥጢር ፡ ታላቅ ፡ ነው ። በሞቱ ፡ መዋረዱ ፡ ተጨረሰ ፡ ከት
ንሣኤውም ፡ ከፍ ፡ ማለቱ ፡ ጀመረ ። እንደህ ፡ ይላልና ፡
ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ ፊልጵሲዩስ ፡ ፪፡ ፯። የኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡
ራሱን ፡ አዋረደ ፡ እንደ ፡ ባርያም ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡ ሰውም ፡
መሰለ ። የሰውንም ፡ ምሳሌ ፡ ወሰደ ፡ ራሱንም ፡ አወረደ ፡
ታዘዘም ፡ እስከ ፡ ሞት ፡ ድረስ ። ሞቱም ፡ የመስቀል ፡
ሞት ። ስለዚህም ፡ እግዚአብሔር ፡ አላቀው ፡ እጅግ ። የ
ክርስቶስም ፡ ትንሣኤ ፡ የምግባሩ ፡ ሁሉ ፡ መኅተም ፡ ነ
ው ። በመኅተም ፡ የጽሕፈት ፡ እውነት ፡ እንደ ፡ ገለጽ ፡ ነገር
ም ፡ ሁሉ ፡ እንዲጸናበት ፡ እንደህም ፡ እግዚአብሔር ፡ አ

ብ ፡ ልጁን ፡ በማስነሣት ፡ የልጁን ፡ ምግባር ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ መድኃኒት ፡ በጣም ፡ እንደ ፡ ተቀበለው ፡ ገለጸው ። እንደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ስራ ፡ አጸናው ፡ በምድርም ፡ በሰማይም ፡ በገሃናምም ፡ ፊት ። ክርስቶስ ፡ ካልተነሣ ፡ ሃይማኖታችን ፡ ከንቱ ፡ በሆነ ። እርሱ ፡ ግን ፡ ሲነሣ ፡ ሃይማኖታችን ፡ መሠረቱን ፡ አገኘ ። በክርስቶስም ፡ ትንሣኤ ፡ እኛ ፡ ኃይል ፡ አገኘን ፡ ላዲስ ፡ ሕይወት ፡ ለልባችንም ፡ መታደስ ። እርሱ ፡ ይላልና ። እኔ ፡ ሕያው ፡ ነኝና ፡ እናንተም ፡ ሕያዋን ፡ ትሆናላችሁ ። የዮሐንስ ፡ ወንጌል ፡ ፲፬፡ ፲፱። ጳውሎስም ፡ ይላል ። እኛ ፡ በርሱ ፡ የምናምን ፡ በርሱም ፡ የተጠመቅን ፡ በጥምቀት ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ተቀበርን ፡ በሞቱ ። ክርስቶስ ፡ ከሙታን ፡ እንደ ፡ ተነሣ ፡ በአብ ፡ ክብር ። እንደዚሁም ፡ እኛ ፡ ደግሞ ፡ እንመላለስ ፡ ዘንድ ፡ ባዲስ ፡ ሕይወት ። ሮሜ ፡ ፮፡ ፬። ደግሞም ፡ ይላል ፡ በዚያች ፡ ምዕራፍ ፡ ከ፰፡ ቍጥር ፡ ጀምሮ ። ከክርስቶስ ፡ ጋራ ፡ ከሞትን ፡ እናምናለን ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ደግሞ ፡ በሕይወት ፡ እንድንኖር ። አውቀናልም ፡ ክርስቶስ ፡ ከሙታን ፡ እንደ ፡ ተነሣ ፡ ደግሞም ፡ አይሞትም ። ሞትም ፡ አይገዛውም ። ሙትዋልና ፡ ለኃጢአት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ እርሱ ፡ የሚሐይው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ይሐይዋል ። እንደዚሁም ፡ እናንተ ፡ ደግሞ ፡ ዕወቁ ፡ ከኃጢአት ፡ እንደ ፡ ሞታችሁ ፡ ሕያዋንም ፡ እንደ ፡ ሆናችሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በክርስቶስ ፡ የሱስ ፡ በጌታችን ። በክርስቶስ ፡ ትንሣኤም ፡ እኛ ፡ ተስፋ ፡ አገኘን ፡ የኛ ፡ ሥጋ ፡ ሲሞት ፡ ነፍሳችን ፡ ከኃጢአት ፡ ነጽታ ፡ ከክርስቶስ ፡ ጋራ ፡ እንድትኖር ፡ ሥጋችንም ፡ በኋለኛ ፡ ቀን ፡ በክርስቶስ ፡ ኃይል ፡ እንዲነሣ ፡ በምስጋና ፡ የክርስቶስንም ፡ የከበረውን ፡ ሥጋው ፡ መስሎ ። እንዲህ ፡ ይላልና ፡ ጳውሎስ ፡ ፩፡ ቆሮንቶስ ፡ ፲፭፡ ከ፲፯፡ ቍጥር ፡ ጀምሮ ። ክርስቶስ ፡ ካልተነሣ ፡ ሃይማኖታችሁ ፡ ከንቱ ፡ ነው ። እናንተም ፡ ደግሞ ፡ በኃጢአታችሁ ፡ አላችሁ ። በክርስቶስም ፡ ያንቀላፉ ፡ ጠፉ ፡ ፈጽመው ። ክርስቶስንም ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ሕይወት ፡ ብቻ ፡ ተስፋ ፡ ብናደርገው ፡ ከሰው ፡ ሁሉ ፡ ይልቅ ፡ እኛ ፡ የተጠቃን ፡ ሆን ። አሁን ፡ ግን ፡ ክርስቶስ ፡ ከሙታን ፡ ተነሣ ፡ ላንቀላፉትም ፡ ሁሉ ፡ መጀ

መርያ : ሆነ :: ሞትም : በሰው : እንደ : ሆነ :: በሰውም : እ ንደሁ : የሙታን : ትንሣኤ : ሆነ :: ሁሉም : በአደም : እን ደ : ሞቱ : እንደሁም : በክርስቶስ : ሁሉ : ይነሣሉ :: እን ደሁም : ይላል : በፊልጵስዩስ : ፫፤ ፳፡፡ እኛ : የምናምን : አ ገራችን : በሰማይ : ናት :: ከዚያም : እንጠብቃለን : መድ ኃኒታችነን : ጌታችነንም : የሱስ : ክርስቶስን :: እርሱ : የሚ ለውጥ : የተዋረደውን : ሥጋችነን :: ምሳሌም : የሚያደር ገው : ለከበረው : ሥጋው : በኃይሉ : ታላቅነት :: በርስዋ : ሁሉን : የሚያስገዛለት :: ደግሞም : ይላል : ፩፤ ተሳሎን ቄ : ፬፤ ፲፫፡፡ ታውቁ : ዘንድ : እወደለሁ : ወንድሞቼ : ሆይ : ስላንቀላፉ : ሰዎች :: እንደደገባ : ታዝኑ : ዘንድ : ተስፋ : የሌላቸው : ሰዎች : እንዲያዝኑ :: የሱስ : ሙቶ : እንደ : ተነሣ : ካመንነ :: እንደሁም : በየሱስ : ያንቀላፋትን : እግ ዚአብሔር : ያመጣቸዋል : ከርሱ : ጋራ :: ይህ : ነው : የም ንላችሁ : የጌታችን : ነገር :: እኛ : ሕያዋን : ሁነን : የምንቀ ር : ጌታ : ሲመጣ : ጊዜ : ያንቀላፋትን : አንቀድምም :: እ ርሱ : ጌታ : ያዛልና : በመላእክትም : አለቃ : ድምጽ : በእ ግዚአብሔርም : መለከት : ከሰማይ : ይመጣል :: በክርስ ቶስም : የሞቱ : አስቀድመው : ይነሣሉ :: በኋላቸውም : እኛ : ሕያዋን : ሁነን : የቀረነ : እንነጠቃለን : ከርሳቸው : ጋ ራ : ባንድ : በደመና : ጌታን : ለመቀበል : በንፋስ :: እንደ ሁም : እንሆናለን : ከጌታ : ጋራ : ሁለግዜ ::

ነገር : ግን : የሚነሡ : ሙታን : ሁሉ : ከክርስቶስ : ጋራ : አ ይሆኑም :: የርሱ : ገንዘብ : ያሉ : ብቻ : እንጅ :: የቀሩት : ለ ፍርድ : ይነሣሉ : ክርስቶስ : እንደ ሊ :: ጊዜ : ትመጣለች : የ ሚሰሙባት : በመቃበር : ያሉት : ሁሉ : ቃሉን :: መልካም ም : የሰሩ : ይወጣሉ : ለሕይወት : ትንሣኤ :: ክፉ : ግን : የሰሩ : ለኩነኔ : ትንሣኤ :: የዮሐንስ : ወንጌል : ፭፤ ፳፰፡፡ ስለዚህም : ይላል : ቅዱስ : ጳውሎስ :: ንቃ : በኃጢአት : መቃበር : የተኛህ : ከሙታንም : ተነሣ :: ክርስቶስም : ያ ብራልሃል :: ኤፌሶን : ፭፤ ፲፬፡፡

የሱስ : ክርስቶስ : ተነሥቶ : ለደቀ : መዛሙርቱ : በታየ : ጊዜ : እጅግ : ደስ : አላቸው :: በሞቱ : መክንያት : የደከ

መች ፡ ሃይማኖታቸው ፡ በትንሣኤው ፡ ደነች ፡ ጸናችም ፡፡ ከትንሣኤውም ፡ በኋላ ፡ ፵፡ ቀን ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ኖረ ፡ ብዙ ፡ ጊዜም ፡ ታየላቸው ፡ ተናገራቸውም ፡ አስተማራቸውም ፡ ገሠጻቸውም ፡ አጸናቸውም ፡ በሁሉም ፡ ለመልእክታቸው ፡ አሰናደቻቸው ፡፡ ከ፭፻፡ የሚበዙ ፡ ምእመናን ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ አዩት ፡፡ ሁላቸውን ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋራ ፡ ምስክሮችን ፡ አደረጋቸው ፡ ለትንሣኤው ፡፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ሲታይ ፡ አላቸው ፡፡ ሰላም ፡ ይሁንላችሁ ፡፡ አብ ፡ እንደ ፡ ላከኝ ፡ እንደሁም ፡ እኔ ፡ እልካችኋለሁ ፡፡ ይህንንም ፡ ብሎ ፡ እፍ ፡ አለባቸው ፡ አላቸውም ፡፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ተቀበሉ ፡፡ ኃጢአቱን ፡ የምትተዉለት ፡ ቀረችለት ፡፡ የምታያዙበትም ፡ ተያዘችበት ፡፡ የዮሐንስ ፡ ወንጌል ፡ ፳፡ ፳፩፡፡ ከዚህ ፡ ነገርም ፡ ይገለጻል ፡ ለወንጌል ፡ ማገልገልም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንዲፈለግ ፡፡ ያ ፡ ቄስ ፡ ያም ፡ መምሕር ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እፍ ፡ ብሎ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱሱን ፡ ያልሰጠለት ፡ በከንቱ ፡ ያስተምራል ፡ በከንቱም ፡ ይፈታል ፡ ያሥራልም ፡፡

ደቀ ፡ መዛሙርቱንም ፡ አላቸው ፡፡ እንዲህ ፡ ተጻፈ ፡ እንደሁም ፡ ተገባ ፡ ለክርስቶስ ፡ መከራ ፡ እንዲቀበል ፡ ከሙታንም ፡ እንዲነሣ ፡ በሶስተኛ ፡ ቀን ፡፡ በስሙም ፡ ይሰብካል ፡ በንስሓ ፡ ኃጢአትም ፡ በማስተስረይ ፡ ባሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ከየሩሳሌም ፡ ጀምሮ ፡፡ አላንትም ፡ በዚህ ፡ ምስክሮች ፡ ናችሁ ፡፡ እኔም ፡ እነሆ ፡ እልክላችኋለሁ ፡ ያባቴን ፡ ተስፋ ፡፡ እላንት ፡ ግን ፡ ተቀመጡ ፡ በየሩሳሌም ፡ ከተማ ፡ እስክትለብሱ ፡ ድረስ ፡ ከላይ ፡ ኃይል ፡፡ ተሰጠኝም ፡ ኃይል ፡ ሁሉ ፡ በሰማይና ፡ በምድር ፡፡ ስለዚህም ፡ ሒዱ ፡ ወደለም ፡ ሁሉ ፡ ስበኩም ፡ በወንጌል ፡ ለፍጥረት ፡ ሁሉ ፡፡ አጥመቋቸውም ፡ በአብና ፡ በልጅ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ስም ፡፡ በርሱም ፡ ያዘዝኋችሁን ፡ ሁሉ ፡ መጠበቅ ፡ አስተምርዋቸው ፡፡ የሚያምንም ፡ የሚጠመቅም ፡ ይድናል ፡፡ የማያምን ፡ ግን ፡ ይኰነናል ፡፡ እነሆም ፡ እኔ ፡ ከላንት ፡ ጋራ ፡ ነኝ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ እስከ ፡ ዓለም ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፡፡

ከርሳቸውም ፡ ጋራ ፡ ሳለ ፡ አዘዛቸው ፡ ከየሩሳሌም ፡ እ

ንደደወጡ ፡ ደጅ ፡ ደጸኑ ፡ እንጅ ፡ ያብን ፡ ተስፈ ፡ ከኔ ፡ የሰ
ማችሁትን ፡፡ ዮሐንስም ፡ በውኃ ፡ አጠመቀ ፡፡ እላንተ ፡ ግ
ን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ትጠመቃላችሁ ፡ ከጥቂት ፡ ቀን ፡ በ
ኋላ ፡፡ ተከማችተውም ፡ ጠየቁት ፡ አሉትም ፡፡ አቤቱ ፡ በ
ዚህን ፡ ወራት ፡ ትመልሳለህ ፡ መንግሥትን ፡ ለእሥራኤል ፡፡
እርሱም ፡ አላቸው ፡፡ አልተሰጣችሁም ፡ ዘመኑን ፡ ጊዜው
ንም ፡ ታውቁ ፡ ዘንድ ፡ አብ ፡ በሥልጣኑ ፡ ያደረጋትን ፡፡ ነ
ገር ፡ ግን ፡ ኃይል ፡ ትቀበላላችሁ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በወረ
ደባችሁ ፡ ጊዜ ፡፡ ለኔም ፡ ትመሰክራላችሁ ፡ በየሩሳሌም ፡
በይሁደም ፡ ሁሉ ፡ በሰማርያም ፡ እስከ ፡ ምድር ፡ ደርም ፡
ድረስ ፡፡ ወደ ፡ ቢታንያም ፡ አወጣቸው ፡ እጁንም ፡ ዘረጋ
ና ፡ ባረካቸው ፡፡ እርሱም ፡ ሲባርካቸው ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለ ፡
እርሳቸው ፡ ኢያዩት ፡፡ ደመናም ፡ ተቀበለቸው ፡፡ ካይናቸ
ውም ፡ ተሰወረ ፡፡ ወደ ፡ ሰማይም ፡ ወጣ ፡፡ ወደ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ አብም ፡ ወደ ፡ ቀኙ ፡ ተቀመጠ ፡፡ እርሳቸውም ፡ ሲ
መለከቱ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ እርሱ ፡ ሲወጣ ፡፡ እነሆም ፡ ፪፥ ሰ
ዎች ፡ ቆመው ፡ ነበረ ፡ በርሳቸው ፡ ዘንድ ፡ ነጭ ፡ ለብሰው ፡
ሲልዋቸው ፡፡ እላንተ ፡ የገሊላ ፡ ሰዎች ፡ ለምን ፡ ቆማች
ኋል ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ኢያያችሁ ፡፡ ይህ ፡ የሱስ ፡ አሁን ፡ ከ
ላንተ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ የወጣ ፡ እንዲሁም ፡ ተመልሶ ፡ ይመ
ጣል ፡ እንደያችሁት ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ሲወጣ ፡፡ እርሳቸው
ም ፡ ሰገዱለት ፡፡ ከደብረ ፡ ዘይትም ፡ ተመለሱ ፡ ወደ ፡ የ
ሩሳሌም ፡ በታላቅ ፡ ደስታ ፡፡ ሁለግዜም ፡ በመቅደስ ፡ ያመ
ሰግኑ ፡ ደባርኩም ፡ ነበረ ፡ እግዚአብሔርን ፡፡

ጌታችንም ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ከወጣ ፡ በኋላ ፡ የ፲፩፥ ሐዋ
ርያት ፡ መጀመርያ ፡ ተግባራቸው ፡ ይህ ፡ ነበረ ፡ በይሁደ ፡ ባ
ስቆሮታዊ ፡ ፈንታ ፡ ሌላውን ፡ ባልንጀራቸውን ፡ ደመርጹ ፡
ዘንድ ፡ ለክርስቶስ ፡ ስም ፡ የሚመሰክር ፡ በወንጌልም ፡
የሚሰብክ ፡፡ ሁለትንም ፡ አድርገው ፡ ከጸለዩ ፡ በኋላ ፡ ዕፃ
ውን ፡ ጣሉባቸው ፡ ማትያስም ፡ ሐዋርያ ፡ ሆነ ፡ በይሁ
ደ ፡ ፈንታ ፡፡

፲፪፥ ሐዋርያትም ፡ ተጸምደው ፡ ነበረ ፡ ባንድ ፡ ለጸሎት
ና ፡ ለልመና ፡፡ ልባቸው ፡ ነፍሳቸውም ፡ ማሰባቸውም ፡ አ

ንድ ፡ ነበረ ፡ ከተመሰገነ ፡ ክርስቶስ ፡ ጋራ ፡፡ እርሱ ፡ በርሳቸ
ውም ፡ ፍጹምት ፡ አንድነት ፡ ነበረችላቸው ፡ በመካከላቸ
ው ፡፡ ፈቃዳቸውም ፡ አንድ ፡ ነበረ ፡ በሕይወታቸው ፡ ሁሉ ፡
ክርስቶስን ፡ ያመሰግኑት ፡ ዘንድ ፡፡ ጉድያቸውም ፡ አንድ ፡
ነበረ ፡ ይለብሱ ፡ ዘንድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ያለርሱ ፡ ያል
ቻላቸው ፡ መጸራታቸውን ፡ ተግባራቸውንም ፡ ወደ ፡ ይጀም
ሩት ፡ ዘንድ ፡ መፈጸም ፡ ሲቀር ፡፡ ተስፋቸውም ፡ አንድ ፡
ነበረ ፡ እርሱም ፡ የክርስቶስ ፡ ቃል ፡ እንደህ ፡ ሲል ፡፡ እኔ ፡
አብን ፡ እለምናለሁ ፡ እርሱም ፡ ይሰጣችኋል ፡ ሌላውን ፡
የሚያጸናችሁትን ፡ (በዮናኒ ፡ ጳራቅሌጦስ ፡ የተባለ ፡ መን
ፈስ ፡ ቅዱስን ፡) ከላንት ፡ ጋራ ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ለዘላለም ፡፡
ይህነንም ፡ ፈቃዳቸውን ፡ ይህችንም ፡ ጉድያቸውን ፡ ተስፋ
ቸውንም ፡ ልመናውን ፡ አድርገውት ፡ ጌታቸውን ፡ አስታወ
ቁት ፡፡ እርሱም ፡ ሰማ ፡፡ ፶፤ ቀን ፡ በተፈጸመ ፡ ጊዜ ፡ ሁሉ ፡
ባንድ ፡ ነበሩ ፡ በስፍራቸው ፡፡ ድንገትም ፡ ከሰማይ ፡ ድም
ጽ ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡ ዓውሎ ፡ ንፋስ ፡፡ ተቀምጠወበት ፡ የነበሩ
ትንም ፡ ቤት ፡ ሁሉ ፡ መላው ፡፡ የተከፋፈሉም ፡ የሳት ፡ መላ
ሶች ፡ ታዩላቸው ፡፡ ከርሳቸውም ፡ በያንዳንዳቸው ፡ ተቀመ
ጡባቸው ፡፡ በሁሉም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መላባቸው ፡፡ ይ
ናገሩም ፡ ዘንድ ፡ ጀመሩ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋ ፡ መንፈስ ፡ እ
ንደ ፡ ሰጣቸው ፡ ይናገሩ ፡ ዘንድ ፡፡ በየሩሳሌምም ፡ ሰዎች ፡
ነበሩ ፡ የተቀመጡ ፡ አይሁድ ፡ በጎ ፡ ሰዎች ፡፡ ከሰማይ ፡ በታ
ች ፡ ካሉም ፡ ካሕዛብ ፡ ሁሉ ፡፡ ይህም ፡ ድምጽ ፡ በሆነ ፡ ጊ
ዜ ፡ ሁሉ ፡ ተሰበሰቡ ፡ ባንድ ፡፡ ከርሳቸው ፡ ኢያንዳንዱ ፡ ይ
ሰማቸው ፡ ነበረና ፡ ሲናገሩ ፡ በቋንቋው ፡፡ ሁሉም ፡ ደነገጡ ፡
አደነቁም ፡ እንደህ ፡ ሲሉ ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡፡ እሌህ ፡ የ
ሚናገሩ ፡ ሁሉ ፡ የገሊላ ፡ ሰዎች ፡ አይደሉምን ፡፡ እንዴት ፡
እኛ ፡ ኢያንዳንዳችን ፡ እንሰማቸዋለን ፡ ሲናገሩ ፡ በተወለ
ድነበት ፡ ቋንቋ ፡፡ እኛ ፡ ዓጀም ፡ ለሚጡኒም ፡፡ በወንዞች ፡
ማኸልም ፡ የተቀመጥን ፡ በይሁድም ፡ በቀጰደቅያም ፡፡ ጶን
ጦስም ፡ እስያም ፡ ፍርጊያም ፡ ጰንፌልያም ፡፡ ምሥርም ፡
ደወለ ፡ ልብያም ፡ ወደ ፡ ቀሬዋን ፡ የቀረበች ፡፡ ሮምም ፡ ከ
ኛ ፡ ጋራ ፡ የሚኖሩ ፡ አይሁድም ፡ መጻተኞችም ፡፡ ከአቅረ

ጥስም ፡ ያሉ ፡፡ ዓረብም ፡፡ እንሰማቸዋለን ፡ ሲናገሩ ፡ በቋ
ንቋችን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ታላቅ ፡ ስራ ፡፡ ሁሉም ፡ ፈሩ ፡
ተደነቁም ፡ እንዴህ ፡ ሲሉ ፡ እርሶ ፡ በርሳቸው ፡፡ እንጃ ፡ ይ
ህ ፡ ምንድር ፡ ይሆናል ፡፡ ሌሎች ፡ ግን ፡ ያፌዙ ፡ ነበሩ ፡ አሉ
ም ፡፡ እሌህ ፡ በጉስ ፡ ጸጅ ፡ ሰከሩ ፡፡ ጴጥሮስ ፡ ግን ፡ ቆመ ፡
ከ፲፩፡ ጋራ ፡ ድምጹንም ፡ ከፍ ፡ አደረገ ፡ እንዴህ ፡ ሲልም ፡
ተናገራቸው ፡፡ እላንተ ፡ ሰዎች ፡ አይሁድ ፡ በየሩሳሌም ፡ የ
ምትኖሩ ፡ ሁላችሁ ፡፡ ይህ ፡ በላንተ ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ይሁ
ን ፡፡ ነገሬንም ፡ አድምጹ ፡፡ እሌህ ፡ የሰከሩ ፡ አይደሉም ፡ እ
ላንት ፡ እንደላችሁ ፡፡ ከቀኑ ፡ ሶስተኛ ፡ ሰዓት ፡ ናትና ፡፡ ነገር ፡
ግን ፡ ይህ ፡ የተባለ ፡ ነው ፡ በነቢዩ ፡ በዮኤል ፡፡ በኋለኛዪቱ ፡
ቀን ፡ ይሆናል ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡፡ ከመንፈሴ ፡ አፈሳለ
ሁ ፡ በሥጋ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡፡ ወንዶችም ፡ ሴቶችም ፡ ልጆቻች
ሁ ፡ ትንቢት ፡ ይናገራሉ ፡፡ ሕፃናታችሁም ፡ ራእይ ፡ ያያሉ ፡፡
ሽማግሎቻችሁም ፡ ሕልምን ፡ ያልማሉ ፡፡ በወንዶችም ፡ በ
ሴቶችም ፡ ባሮቼ ፡ በዚያች ፡ ወራት ፡ መንፈሴን ፡ አፈሳለ
ሁ ፡፡ ትንቢትም ፡ ይናገራሉ ፡፡ ተአምራትንም ፡ እሰጣለ
ሁ ፡ ከላይ ፡ ከሰማይ ፡፡ ምልክትንም ፡ በምድር ፡ በታች ፡፡
ደምም ፡ እሳትም ፡ የጢስም ፡ ጭጋግ ፡፡ ፀሓይቱ ፡ ወደ ፡ ጨ
ለማ ፡ ትለወጣለች ፡ ጨረቃውም ፡ ወደ ፡ ደም ፡፡ ሳይመጣ ፡
የእግዚአብሔር ፡ ታላቅ ፡ ቀን ፡፡ ይሆናልም ፡ የእግዚአብ
ሔርን ፡ ስም ፡ የሚጸራ ፡ ሁሉ ፡ ይድናል ፡፡ እላንት ፡ የእ
ሥራኤል ፡ ሰዎች ፡ ይህነን ፡ ነገር ፡ ስሙ ፡፡ የሱስ ፡ የናዝሬ
ቱ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የሆነ ፡ ሰው ፡፡ በላንት ፡ ዘንድ ፡ የተ
ገለጸ ፡ በተአምራት ፡ በኃይልም ፡ በምልክትም ፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ያደረጋት ፡ በርሶ ፡ በመኻከላችሁ ፡ እላንት ፡ እንድ
ታውቁ ፡፡ ይህነን ፡ በተወሰነው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ምክር ፡
በተቀደመውም ፡ እውቀቱ ፡ አሳልፈችሁ ፡ ሰጣችሁት ፡ በ
ኃጢአተኞች ፡ እጅ ፡፡ ሰቀላችሁትም ፡ ገደላችሁትም ፡፡ ይህ ፡
እግዚአብሔር ፡ ያስነሣው ፡ ነው ፡ የሞትን ፡ ማሠርያ ፡ ፈት
ቶ ፡፡ እርሶ ፡ ይደዘው ፡ ዘንድ ፡ አልቻለውምና ፡፡ ዳዊት
ም ፡ ስለርሶ ፡ ይላልና ፡፡ እግዚአብሔርን ፡ በፊቴ ፡ አኖርሁ
ት ፡ ሁለግዜ ፡ በቀኜ ፡ ነውና ፡ እንደልታወክ ፡፡ ስለዚህም ፡

ልቤን ፡ ደስ ፡ አለው ፡ መላሴም ፡ ሐሤት ፡ አደረገ ። ሥጋዬ
ም ፡ በተስፋ ፡ ያድራል ። ነፍሴን ፡ በመቃብር ፡ አተዋትም
ና ፡ ቅዱስህንም ፡ አተውምና ፡ ጥፋትን ፡ ያይ ፡ ዘንድ ። የ
ሕይወትንም ፡ መንገድ ፡ አሳይህኝ ። ደስታም ፡ አጸገብህ
ኝ ፡ ከፊትህ ፡ ዘንድ ። እላንተ ፡ ሰዎች ፡ ወንድማማች ፡ ለ
ላንተ ፡ ይገባል ፡ ይባል ፡ ዘንድ ፡ በግልጥ ፡ ስለ ፡ ደዊት ፡ ስላ
ባቶች ፡ አለቃ ። እንደረፈ ፡ እንደ ፡ ተቀበረም ። መቃብሩ
ም ፡ በኛ ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡ እስከ ፡ ዛሬ ። ነቢይ ፡ ግን ፡ ነበረ
ና ። ባወቀም ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ መሐላ ፡ እንደ ፡ ማ
ለለት ፡ ክርስቶስን ፡ እንዲያስነሣ ፡ ከወገቡ ፡ ፍሬ ፡ በዙፋ
ኑ ፡ ይቀመጥ ፡ ዘንድ ። አስቀድሞ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ያነን ፡ ተና
ገረ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ትንሣኤ ። ነፍሱ ፡ በሲኦል ፡ አትቀር
ምና ፡ ሥጋውም ፡ ጥፋትን ፡ አያይምና ። ይህነን ፡ የሱስን ፡
እግዚአብሔር ፡ አስነሣው ። እኛም ፡ ሁላችን ፡ ለርሱ ፡ እ
ንመሰክራለን ። አሁንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቀኝ ፡ ከፍ ፡
ከፍ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስንም ፡ ተስፋ ፡ በወሰደ ፡
ጊዜ ፡ ከአብ ። ይህነን ፡ አፈሰሰው ፡ እላንተ ፡ ዛሬ ፡ የምታ
ዩትን ፡ የምትሰሙትንም ። ደዊት ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ አልወ
ጣምና ፡ እርሱ ፡ አለ ፡ እንጂ ። ጌታ ፡ ጌታዬን ፡ አለው ። በ
ቀኜ ፡ ተቀመጥ ፡ ጸላቶችህን ፡ እስክጥል ፡ ድረስ ፡ ለግርህ ፡
መቀመጫ ። እንግዴህ ፡ በውነት ፡ ይወቅ ፡ የእሥራኤል ፡
ወገን ፡ ሁሉ ። እግዚአብሔር ፡ እንደደረገው ፡ ይህነን ፡ የሱ
ስን ፡ እላንተ ፡ የሰቀላችሁትን ፡ ጌታ ፡ መሢሕም ።

ይህነንም ፡ ነገር ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ልባቸው ፡ ተወጋ ። ጴጥ
ሮስንም ፡ አሉት ፡ የቀሩትንም ፡ ሐዋርያት ። ምን ፡ እንስ
ራ ፡ እላንተ ፡ ሰዎች ፡ ወንድሞች ። ጴጥሮስም ፡ አላቸው ።
ንስሐ ፡ ግቡ ። ከላንትም ፡ ሁሉ ፡ ኢያንዳንዳችሁ ፡ ተጠመ
ቁ ፡ በየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ኃጢአት ፡ ለማስተስረይ ።
የመንፈስ ፡ ቅዱስንም ፡ ጸጋ ፡ ትቀበላላችሁ ። ተስፋው ፡ ለ
ላንት ፡ ነውና ፡ ለልጆቻችሁም ፡ ገና ፡ በሩቅም ፡ ላሉ ፡ ሁሉ ፡
እግዚአብሔር ፡ አምላካችን ፡ ለሚጸራቸው ። በሌላ ፡ ነገር
ም ፡ እጅግ ፡ ነገራቸው ፡ ጴጥሮስ ፡ እንዲህም ፡ ሲል ፡ ለመና
ቸው ። ደኑ ፡ ከዚች ፡ ዓመፀኛ ፡ ትውልድ ። ከርሳቸውም ፡

ነገሩን ፡ አስተውለው ፡ የተቀበሉ ፡ ተጠመቁ ። በዚያም ፡ ቀን ፡ ከምእምናን ፡ ተጨመሩ ፡ ፴፻፡ ነፍስ ፡ የሚያህል ። ጸንተውም ፡ ኖሩ ፡ በሐዋርያት ፡ ትምህርት ፡ ባንድነትም ፡ እንጀራም ፡ በመቍረስ ፡ በጸሎትም ። በሰውም ፡ ሁሉ ፡ ፍርሃት ፡ ሆነ ። ተአምራትም ፡ እጅግም ፡ ድንቅ ፡ ተደረገ ፡ በሐዋርያት ፡ እጅ ፡ በየሩሳሌም ። ያመኑትም ፡ ሁሉ ፡ ባንድ ፡ ነበሩ ። ያላቸውም ፡ ሁሉ ፡ ባንድነት ፡ ነበረ ። ግዛታቸውንም ፡ ዕቃቸውንም ፡ ይሸጡ ፡ ነበሩ ። ለሁሉም ፡ ይከፍሉት ፡ ነበሩ ፡ ለያንደንዱ ፡ የሚሹትን ፡ ያህል ። ደግሞም ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ በመቅደስ ፡ ጸንተው ፡ ይኖሩ ፡ ነበሩ ። እንጀራም ፡ ባንድ ፡ ይቈርሱ ፡ ነበሩ ፡ ከዚህና ፡ ከዚያ ፡ በቤታቸው ። እንጀራቸውንም ፡ በሉ ፡ በደስታ ፡ በጽሩም ፡ ልቡና ። እግዚአብሔርን ፡ ኢያመሰገኑ ። ጸጋም ፡ ነበረላቸው ፡ በሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ፊት ። እግዚአብሔርም ፡ የሚድኑትን ፡ ጨመረ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ።

እንደሁም ፡ የየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጉባዔ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑም ፡ ተጀመረች ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በመፍሰስ ። በኃይሉ ፡ የሐዋርያት ፡ ልብ ፡ ታደሰ ፡ ጸናም ፡ እንዲደፈራ ፡ ከሰውና ፡ ከሰይጣን ፡ ጸላትነት ፡ ሁሉ ። በርሱ ፡ ነው ፡ የቻላቸው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ምሥጢርና ፡ ትምህርት ፡ ያወቁ ፡ ዘንድ ፡ ይናገሩበትም ፡ ዘንድ ። በኃይሉም ፡ ባልተማሩ ፡ ቋንቋች ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ አመሰገኑ ። በርሱም ፡ ኃይል ፡ ትንቢትን ፡ ተናገሩ ። በርሱም ፡ ኃይል ፡ ድውያንን ፡ አደኑ ፡ ሙታንንም ፡ አስነሡ ። በርሱም ፡ ኃይል ፡ ሥጋቸውን ፡ ኃጢአትንም ፡ ዓለምንም ፡ ዲያብሎስንም ፡ አሸነፉ ፡ ሕይወታቸውንም ፡ ለክርስቶስ ፡ ወንጌል ፡ ሠዉ ። በሐዋርያት ፡ አፍ ፡ የተናገረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነገራቸውን ፡ ወደሚሰሙት ፡ ወደሚቀበሉትም ፡ ልብ ፡ ገባ ፡ ልባቸውንም ፡ ለክርስቶስ ፡ አስገዛ ። ማን ፡ ይችላልና ፡ ያለርሱ ፡ የሰውን ፡ ልብ ፡ ይለውጥ ፡ ዘንድ ፡ ኃጢአተኛውንም ፡ ሰው ፡ ጻድቅን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ። እንዲህ ፡ ይላልና ፡ እግዚአብሔር ። ሻንቅላ ፡ ሰው ፡ ይችላልን ፡ ቍርበቱን ፡ ይለውጥ ። ዘንድ ፡ ወይስ ፡ ነብርን ፡ ይችላል ፡ የቍርበቱን ፡ ዝንጕርጕርነት ፡ ይለውጥ ፡ ዘ

ንድ ፡፡ እንደሁም ፡ እላንተ ፡ በጎ ፡ መስራት ፡ አትችሉም ፡ ክፉን ፡ ለመደችሁና ፡፡ ኤርምያስ ፡ ፲፫ ፳፫ ፡፡ ስለዚህም ፡ ሰውን ፡ መምለስ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ታላቅ ፡ ተአምራት ፡ ነው ፡፡ አዲስ ፡ ፍጥረትም ፡ ይባላል ፡፡ ፪ ቆሮንቶስ ፡ ፭ ፲፯ ፡፡ ሁለተኛም ፡ ልደት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ብቻ ፡ የሚደረግ ፡፡ የዮሐንስ ፡ ወንጌል ፡ ፩ ፲፫ ፡፡ ፫ ፭ ፡፡ እነሆም ፡ እዩ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ስራ ፡፡ ጴጥሮስ ፡ እርሱ ፡ በቀደም ፡ ከሠጋው ፡ ድካም ፡ የተነሣ ፡ ክርስቶስን ፡ ፫ ጊዜ ፡ ባንድ ፡ ሌሊት ፡ የካደ ፡ አሁን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ኃይል ፡ በክርስቶስ ፡ ጸላቶች ፡ ፊት ፡ ይቆማል ፡ እርሳቸውንም ፡ ክርስቶስን ፡ ፶፪ ቀን ፡ አስቀድመው ፡ የሰቀሉትን ፡ አሁን ፡ በግልጽ ፡ ይላቸዋል ፡፡ ይህነን ፡ የሱስን ፡ የናዝሬቱን ፡ እላንት ፡ የሰቀላችሁትን ፡ የገደላችሁትንም ፡ እግዚአብሔር ፡ ጌታንና ፡ መሢሕን ፡ አደረገው ፡፡ እነሆም ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ኃይል ፡፡ ፴፯ ከክርስቶስ ፡ ጸላቶች ፡ ይህነን ፡ ነገር ፡ ሲሰሙ ፡ ንስሓ ፡ ይገባሉ ፡ ስለ ፡ ኃጢአታቸውም ፡ ያዝናሉ ፡፡ በክርስቶስም ፡ ያምናሉ ፡፡ ይጠመቃሉም ፡ የክርስቶስንም ፡ መንፈስ ፡ ሰጥወታ ፡ ይቀበላሉ ፡፡ ይህ ፡ ነው ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ኃይል ፡ የመስቀል ፡ ትምርትም ፡ ኃይል ፡ ጳውሎስ ፡ እንደ ፡ ል ፡፡ የክርስቶስ ፡ የመስቀሉ ፡ ነገር ፡ በጥፎች ፡ ዘንድ ፡ ስንፍና ፡ ነው ፡፡ በኛ ፡ ዘንድ ፡ ግን ፡ በደነው ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ ነው ፡፡ እንደህ ፡ የፊተኞች ፡ ምእምናን ፡ በመስቀል ፡ ነገር ፡ ደኑ ፡፡ ሃይማኖታቸውም ፡ ሕያው ፡ ነበረና ፡ በጎ ፡ ፍሬን ፡ አፈራ ፡፡ የሃይማኖትም ፡ ፍሬ ፡ በርሳቸው ፡ ይህ ፡ ነበር ፡፡ ፩ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማገልገል ፡ ገቡ ፡ እንደህ ፡ ሲጠይቁ ፡ ሐዋርያትን ፡ ምን ፡ እንስራ ፡ እላንት ፡ ሰዎች ፡ ወንድሞች ፡፡ ፪ ፍቅር ፡፡ በፊት ፡ ሐዋርያትን ፡ ጸሉ ፡ ክርስቶስን ፡ እንደ ፡ ጸሉት ፡፡ አሁን ፡ ግን ፡ ወንድሞቻቸውን ፡ አደረጓቸው ፡፡ ፫ ትሕትና ፡፡ ምን ፡ እንስራ ፡ ሲሉ ፡፡ እኛ ፡ መንገደችነን ፡ አናውቅም ፡፡ እላንት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንገድ ፡ አሳዩን ፡ ማለት ፡ ነው ፡፡ ፬ የክርስቶስን ፡ ስም ፡ በጸላቶቹ ፡ መኻከል ፡ አስታወቁ ፡ በጥምቀታቸው ፡ ከሰውም ፡ አላፈሩም ፡ ክርስቶስን ፡ በውነ

ት ፡ ወደዋልና ፡፡ ፫፡፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነገር ፡ መታዘዝ ፡ ከ
ሐዋርያት ፡ አፍ ፡ ለሰሙት ፡፡ ፬፡፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ስጦ
ወታ ፡ ተቀበሉ ፡ በርሱም ፡ ለበጎ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ኃይል ፡ አገ
ኙ ፡፡ ፭፡፡ አንድነት ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡፡ ፮፡ መጽናት ፡ በሐ
ዋርያት ፡ ትምርት ፡ በቍርባንም ፡ በጸሎትም ፡፡ ፯፡፡ የዚህ ፡
ዓለም ፡ ነገር ፡ ተቀደሰላቸው ፡ በሃይማኖት ፡ በፍቅርም ፡ በ
ምስጋናም ፡፡ በዚህም ፡ ይገለጸል ፡ ክርስቶስ ፡ ለጴጥሮስ ፡
የሰጠውን ፡ ተስፋ ፡ እንደ ፡ ፈጸመ ፡፡ በዚህ ፡ ደንጊያ ፡ በሃይ
ማኖት ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ ቤት ፡ ክርስቲያኔን ፡ እመሠርታ
ለሁ ፡፡ የጴጥሮስ ፡ ትምርት ፡ ስለ ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እር
ሳቸው ፡ የሰቀሉት ፡ እግዚአብሔርም ፡ ያስነሣው ፡ ከፍ
ም ፡ ያደረገው ፡ የቤት ፡ ክርስቲያን ፡ መሠረት ፡ ሆነ ፡፡ ሰው ፡
እርሱን ፡ በመቀበል ፡ ድነዋልና ፡፡

የእግዚአብሔር ፡ ጥበብ ፡ የቤት ፡ ክርስቲያንን ፡ መጀመር
ያ ፡ አደረገ ፡ በጴንጤቆስጤ ፡፡ ባይሁድ ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡ ባ
ል ፡ ነበረና ፡፡ መዘከር ፡ ሁንዋልና ፡ ስለ ፡ ሕግ ፡ መስሬት ፡ በ
ሲና ፡ ተራራ ፡ ላይ ፡ አምሳ ፡ ቀን ፡ ከፋሲካ ፡ በኋላ ፡፡ በዚያ
ም ፡ ቀን ፡ ደግሞ ፡ የመከርን ፡ መጀመርያ ፡ ሊያመጡ ፡ ነበ
ሩ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ መቅደስ ፡ ደቀደስ ፡ ዘ
ንድ ፡፡ እግዚአብሔር ፡ የእሥራኤልን ፡ ወገን ፡ የአሕዛብ ፡
ሁሉ ፡ መጀመርያ ፡ አደረገ ፡ በተስፋም ፡ ቀደሳቸው ፡፡ አሁ
ንም ፡ በየባላቸው ፡ የእሥራኤል ፡ ወገኖች ፡ ሁሉ ፡ ከየስፍራ
ቸው ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ የሩሳሌም ፡ ሊመጡ ፡ ከዚያም ፡ ለእግ
ዚአብሔር ፡ ሊሠው ፡ ነበሩ ፡፡ ስለዚህ ፡ እግዚአብሔር ፡ መ
ንፈሱን ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ አፈሰሰ ፡፡ ፰፡ ሊገልጽበት ፡ የምሳሌ ፡
ሁሉ ፡ ፍጻሜ ፡ እንደ ፡ ደረሰ ፡ በክርስቶስና ፡ በቤት ፡ ክርስ
ቲያኑ ፡፡ ክርስቶስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፍጥረት ፡ በኵር ፡ ከ
ሙታን ፡ መጀመርያ ፡ ተብልዋልና ፡፡ የዮሐንስ ፡ ራእይ ፡ ፫፡
፲፬፡፡ ፩፡ ቆሮንቶስ ፡ ፲፭ ፡ ፳፡፡ ምእምናን ፡ ደግሞ ፡ የእግዚአ
ብሔር ፡ ፍጥረት ፡ በኵራን ፡ ደባላሉ ፡፡ ያዕቆብ ፡ ፩፡ ፲፰፡፡
እግዚአብሔርም ፡ በዚያ ፡ ቀን ፡ መንፈሱን ፡ ለማፍሰስ ፡ ፱፡
መክንያት ፡ ደህ ፡ ነበረ ፡ የክርስቶስ ፡ ወሬ ፡ የወንጌልም ፡
ትምርት ፡ ቶሎ ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ ሊወጣ ፡፡ አይሁድ ፡

በዚያ ፡ ቀን ፡ ከስፍራ ፡ ሁሉ ፡ በየሩሳሌም ፡ ተሰብስበዋል ና ፡ በክርስቶስም ፡ ያመኑ ፡ እንግዶች ፡ ወደ ፡ ቤታቸው ፡ በ ተመለሱ ፡ ጊዜ ፡ የወንጌልን ፡ ትምርት ፡ ባገራቸው ፡ ሊያስ ተምሩ ፡ ነበሩ ፡፡ እንደዚህ ፡ በሮምያ ፡ ከተማ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲ ያን ፡ ተገኘች ፡ አንድ ፡ ሐዋርያ ፡ ወደ ፡ ሮምያ ፡ ሳይመጣ ፡ በቅላውዲዮስ ፡ ዘመን ፡፡ የሐዋርያት ፡ ስራ ፡ ፲፰፡ ፩፡፡ ጳው ሎስም ፡ መልእክቱን ፡ ወደ ፡ ሮምያ ፡ ሰዎች ፡ በጻፈ ፡ ጊዜ ፡ በቆሮንቶስ ፡ ሲቀመጥ ፡ ሐዋርያ ፡ ወደ ፡ ሮምያ ፡ ገና ፡ አይ መጣም ፡ ነበረ ፡፡

በየሩሳሌምም ፡ የነበረች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በእግዚአ ብሔር ፡ በረከት ፡ ጸንታ ፡ አደገች ፡፡ ሐዋርያት ፡ ሁሉ ፡ በመ ጀመርያ ፡ በየሩሳሌም ፡ ተቀመጡ ፡ ኢያስተማሩ ፡፡ እግዚ አብሔርም ፡ እጅግ ፡ ተአምራት ፡ አድርግዋልና ፡ በሐዋርያ ት ፡ እጅ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ የምእምናን ፡ ቍጥር ፡ በዛ ፡፡ ጥቂ ት ፡ ቀንም ፡ ከጴንጤቆስጤ ፡ በኋላ ፡ ቍጥራቸው ፡ ፶፱፡ ወንድ ች ፡ ነበሩ ፡፡ የሐዋርያት ፡ ስራ ፡ ፬፡ ፬፡፡ አሁንም ፡ የክርስቶስ ፡ ጸላቶች ፡ ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ የካህናት ፡ አለቆች ፡ እጅግ ፡ ተ ቈጡ ፡ ወደ ፡ ሸንጎም ፡ ጸርዋቸው ፡ ጴጥሮስንና ፡ ዮሐንስን ፡ ሐንካሳውን ፡ ሰው ፡ ያደኑትን ፡ ጠየቋቸውም ፡ እንዲህ ፡ ሲ ሉ ፡፡ በማን ፡ ስም ፡ በምንም ፡ ሥልጣን ፡ አደረጋችሁ ፡ ይህ ነን ፡፡ ጴጥሮስና ፡ ዮሐንስ ፡ ግን ፡ በፊታቸው ፡ ለየሱስ ፡ ክር ስቶስ ፡ ስም ፡ መስክረው ፡ አሉ ፡፡ በማንም ፡ ደህንነት ፡ የ ለም ፡ በሌላው ፡፡ ሌላ ፡ ስምም ፡ አልተሰጠም ፡ ለሰው ፡ ከሰማይ ፡ በታች ፡ በርሱ ፡ ይድን ፡ ዘንድ ፡ የሚቻል ፡ የየሱ ስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ እንጂ ፡፡ አሁንም ፡ የካህናት ፡ አለቆ ችና ፡ ሽማግሎች ፡ ሊከለክልዋቸው ፡ ፈለጉ ፡ እንደልተቻ ላቸውም ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ሕዝብ ፡ እንዲያው ፡ ሰደድዋ ቸው ፡፡ ሐዋርያትም ፡ ወደ ፡ ጉባኤያቸው ፡ በተመለሱ ፡ ጊ ዜ ፡ የሆነባቸውንም ፡ በተናገሩ ፡ ጊዜ ፡ ሁላቸው ፡ ቃላቸው ን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከፍ ፡ አደረጉ ፡ ተባብረውም ፡ ጸ ለዩ ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡፡ ጌታ ፡ ሆይ ፡ አንተ ፡ አምላክ ፡ ነህ ፡ የ ፈጠርህ ፡ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ ባሕርንም ፡ በርስዋ ፡ የሚኖ ረውንም ፡ ዓለምንም ፡ ሁሉን ፡፡ በባርያህ ፡ በዳዊት ፡ አፍ ፡

ያልህ ፡፡ ለምን ፡ ተሰበሰቡ ፡ አሕዛብ ፡ ሕዝብም ፡ ከንቱ ፡ ተ
ናገሩ ፡፡ የምድርም ፡ ነገሥታት ፡ ተነሡ ፡፡ አለቆቹም ፡ ባን
ድ ፡ ተካማቹ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ በመሢሑም ፡፡ በው
ነት ፡ ተሰብስበዋልና ፡ በቅዱስ ፡ ልጅህ ፡ በየሱስ ፡ በቀባሀ
ው ፡ ላይ ፡፡ ሄሮድስ ፡ ጲላጦስም ፡ የጴንጤኑ ፡ ካሕዛብ ፡ ከ
እሥራኤልም ፡ ወገን ፡ ጋራ ፡፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ እጅህ ፡ ም
ክርህም ፡ አስቀድማ ፡ ያዘጋጀችውን ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡፡ አ
ሁንም ፡ አቤቱ ፡ ተመልከት ፡ ወደ ፡ ቍጣቸው ፡፡ ለባሮችህ
ም ፡ ስጥ ፡ ይናገሩ ፡ ዘንድ ፡ በሁሉ ፡ ድፍረት ፡ እጅህን ፡ ዘር
ግተህ ፡ ለመፈወስ ፡፡ ተአምራትም ፡ ድንቅም ፡ ይሁን ፡ በየ
ሱስ ፡ በቅዱስ ፡ ልጅህ ፡ ስም ፡፡ እንደሁም ፡ በለመኑ ፡ ጊ
ዜ ፡ ተከማችተው ፡ የነበሩበት ፡ ስፍራ ፡ ተናወጸ ፡፡ ሁሉ
ም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ መሉ ፡፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ነገር ፡
ተናገሩ ፡ በድፍረት ፡፡ ላመኑትም ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ልብ ፡ አ
ንዲት ፡ ነፍስም ፡ ነበረላቸው ፡፡ አንድም ፡ የሚል ፡ አልነበ
ረም ፡ ከከብቱ ፡፡ ይህ ፡ ገንዘቤ ፡ ነው ፡፡ ሁሉ ፡ ለርሳቸው ፡
ለባልንጀሮቻቸውም ፡ ባንድነት ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡፡ በመካከ
ላቸውም ፡ ነዳያን ፡ አልነበሩም ፡፡ እርሻም ፡ ቤትም ፡ የነበ
ረላቸው ፡ ሸጡት ፡ የሸያጩንም ፡ ዋጋ ፡ አመጡ ፡ በሐዋርያ
ትም ፡ እግር ፡ ታች ፡ አስቀመጡት ፡፡ ይህችም ፡ አንድነት ፡
የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፍሬ ፡ ነበረች ፡፡ ሁላቸው ፡ አንድ ፡ ክር
ስቶስ ፡ ነበረላቸው ፡ ሁላቸውም ፡ ክርስቶስን ፡ ወደዱ ፡ ስ
ለ ፡ ክርስቶስም ፡ ወንድሞቻቸውን ፡ ወደዱ ፡፡ ወዴት ፡ ትገኛ
ለች ፡ ይህች ፡ አንድነት ፡ በዘመናችን ፡፡ ደሮ ፡ መንግሥተ ፡
ሰማያት ፡ በምድር ፡ ሁና ፡ እርሻውን ፡ ትመስላለች ፡ በጎና ፡
ክፉ ፡ ዘር ፡ የተዘራበት ፡ ማቴዎስ ፡ ፲፫፤ ፳፬፡፡ የክፋትም ፡
ዘር ፡ በመጀመርያዪቱ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንኳ ፡ አልቀረ
ም ፡፡ ሰይጣን ፡ በብርሃን ፡ መልአክ ፡ መልክ ፡ ያጠፋት ፡ ዘ
ንድ ፡ ፈለገ ፡፡ ደሮ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በሐዋርያት ፡ ኑሮ ፡ ተ
ንኰሉን ፡ ገለጸ ፡፡ ያችን ፡ ቅድስት ፡ አንድነት ፡ በመካከላ
ቸው ፡ የነበረችን ፡ ሁላቸው ፡ አንድ ፡ ልብ ፡ አንዲት ፡ ነፍ
ስም ፡ የነበረባት ፡ እርስዋን ፡ ሊሽር ፡ ብሎ ፡ የ፩፤ ሰው ፡ ል
ብ ፡ መላበት ፡፡ እርሳቸውም ፡ እርሻ ፡ ነበረላቸው ፡ ሸጡት

ም ፡ ከዋጋውም ፡ ክፍልን ፡ ወሰዱ ፡ ወደ ፡ ሐዋርያትም ፡ እግር ፡ አመጡት ፡ እንደ ፡ ዋጋው ፡ ሁለንትናው ፡ አደረጉት ፡ ክፍሉ ፡ በጀቸው ፡ ሲኖር ፡፡ እንዲህም ፡ አድርገው ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንደ ፡ ቅዱሳን ፡ ሊቈጠሩ ፡ ማለታቸው ፡ ነበር ፡፡ አሁን ፡ እግዚአብሔር ፡ በነገር ፡ ሁሉ ፡ እውነትን ፡ ውደድ ፡ የውነት ፡ አምላክ ፡ ሁንዋልና ፡፡ እንደዚህ ፡ ባለች ፡ በቅድስት ፡ አንድነት ፡ አሰትን ፡ ግብዝነትንም ፡ ሁሉ ፡ ይጸላል ፡፡ ይህም ፡ እንደይበዛ ፡ ጴጥሮስ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ኀይል ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፍርድ ፡ ፈረደባቸው ፡፡ በአናንያስ ፡ አስቀድሞ ፡ በኋላም ፡ በምሽቱ ፡ በሰፊራ ፡፡ ሁለታቸው ፡ በጴጥሮስ ፡ ቃል ፡ ወደቁ ፡ ሞቱም ፡፡ ታላቅ ፡ ፍርሃትም ፡ መጣ ፡ በጉባኤ ፡ ሁሉ ፡ ይህንን ፡ ነገር ፡ በሰሙት ፡ ሁሉ ፡፡ እግዚአብሔር ፡ በመኻከላቸው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ተገልጥዋልና ፡፡ እርሱ ፡ የሚል ፡፡ እላንተ ፡ ቅዱሳን ፡ ሁኑ ፡ እኔ ፡ እግዚአብሔር ፡ አምላካችሁ ፡ ቅዱስ ፡ ነኝና ፡፡

ያይሁድ ፡ ቀናትም ፡ በቤተ ፡ ክርስትያን ፡ ላይ ፡ ጸናች ፡ እግዚአብሔር ፡ በሐዋርያት ፡ እጅ ፡ እጅግ ፡ ድንቅ ፡ እንደ ፡ ሰራ ፡ ሐዋርያትም ፡ በታላቅ ፡ ድፍረት ፡ ሁለግዜ ፡ በመቅደስ ፡ እንደ ፡ አስተማሩ ፡ የክርስቲያንም ፡ ቍጥር ፡ እንደ ፡ በዛ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡፡ ሕዝብ ፡ ሐዋርያትን ፡ አከበርዋቸው ፡ ስላደረጉ ፡ ተአመራት ፡፡ አለቆቻቸው ፡ ግን ፡ ጸልዋቸው ፡፡ የአይሁድም ፡ ታላቅ ፡ ሸንጎ ፡ ተከፈፈለ ፡ ከመካሮች ፡ አያሌ ፡ ፈሪሳውያን ፡ ነበሩና ፡ አያሌም ፡ ሰዱቃውያን ፡፡ የካህናት ፡ አለቆች ፡ ግን ፡ ከሰዱቃውያን ፡ ወገን ፡ ነበሩ ፡፡ እርሳቸውም ፡ እጅግ ፡ ተቈጡ ፡ ሐዋርያት ፡ ለክርስቶስ ፡ ትንሣኤ ፡ እንደ ፡ መሰከሩ ፡ እርሳቸው ፡ በትንሣኤ ፡ ሁሉ ፡ አላመኑምና ፡፡ አንድ ፡ ቀንም ፡ ሐዋርያት ፡ ባስተማሩ ፡ ጊዜ ፡ የካህናት ፡ አለቆች ፡ ሎሌልታቸውን ፡ ወደ ፡ መቅደስ ፡ ሰደዱ ፡ አስያዝዋቸውም ፡ ወደ ፡ ግዞትም ፡ ጣልዋቸው ፡፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ ግን ፡ በሌሊት ፡ ፈታቸው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መቅደስም ፡ ለማስተማር ፡ ሰደዳቸው ፡፡ በተከተለው ፡ ቀንም ፡ ጭፍሮችና ፡ የካህናት ፡ አለቆች ፡ አደነቁ ፡ ግዞትን ፡ ተዘግቶ ፡ ሐዋርያትን ፡ ባላገኙበት ፡ ጊዜ ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ሰ

ው ፡ መጣላቸው ፡ የሚላቸው ፡፡ እለዚያ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡
ግዞት ፡ የጣላቿቸው ፡ በመቅደስ ፡ ቁመው ፡ ሕዝብን ፡ ያ
ስተምራሉ ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ሔደ ፡ አለቃ ፡ ከጭፍሮች ፡
ጋራ ፡ አመጥዋቸውም ፡ በግድም ፡ አይደለም ፡ ሕዝብን ፡ ስ
ለ ፡ ፈሩ ፡ እንደይወግርዋቸው ፡፡ ባመጥዋቸውም ፡ ጊዜ ፡ አ
ቆምዋቸው ፡ በሸንጎ ፡፡ የካህናትም ፡ አለቃ ፡ ጠየቃቸው ፡
እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ ቍርጥ ፡ ነገር ፡ አልነገርናችሁምን ፡ እንዳ
ታስተምሩ ፡ በዚህ ፡ ስም ፡፡ እነሆም ፡ የሩሳሌምን ፡ ፈጽማ
ችሁ ፡ መላችኋት ፡ በትምርታችሁ ፡፡ የዚያንም ፡ ሰው ፡ የየ
ሱስን ፡ ደም ፡ ታመጡብን ፡ ዘንድ ፡ ትሻላችሁ ፡፡ ጴጥሮስ
ም ፡ ከሐዋርያት ፡ ጋራ ፡ መለሱ ፡ አሉም ፡፡ ለእግዚአብሔ
ር ፡ እንታዘዝ ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ፡ ከሰው ፡ ይልቅ ፡፡ ያባቶቻ
ችን ፡ አምላክ ፡ የሱስን ፡ አስነሣ ፡ እላንተ ፡ የገደላችሁት
ን ፡ በንጨት ፡ ላይ ፡ ሰቅላችሁ ፡፡ ይህነንም ፡ በቀኙ ፡ ከፍ ፡
አደረገው ፡ እግዚአብሔር ፡ ራስ ፡ መድኃኒትም ፡ አድርጎት ፡
ለእሥራኤል ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፡ ንስሓ ፡ የኃጢአትም ፡ ማስ
ተስረይ ፡፡ እኛም ፡ ምስክሮች ፡ ነን ፡ ለርሱ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡፡
መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ምስክር ፡ ነው ፡ እግዚአብሔር ፡ የሰ
ጠው ፡ ለታዘዙት ፡፡ ይህ ፡ ነገርም ፡ ልባቸውን ፡ ወጋው ፡ ሊ
ገድልዋቸውም ፡ ፈለጉ ፡፡ ደር ፡ በሸንጎ ፡ መለየት ፡ ነበረ ፡ በ
ፈሪሳውያንና ፡ በሰዱቃውያን ፡ መኻከል ፡፡ አንድ ፡ ሰው
ም ፡ ተነሣ ፡ በሸንጎ ፡ እርሱም ፡ ፈሪሳዊ ፡ ስሙም ፡ ገማል
ያል ፡ የኦሪት ፡ ታላቅ ፡ መምሕር ፡፡ በሕዝቡ ፡ ሁሉ ፡ ዘንድ ፡
የከበረ ፡፡ ሐዋርያትም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይወጡ ፡ ዘንድ ፡ አ
ዘዘ ፡ አላቸውም ፡፡ እላንት ፡ ሰዎች ፡ የእሥራኤል ፡ ወገን ፡
በራሳችሁ ፡ እወቁ ፡ በለዚህ ፡ ሰዎች ፡ በምታደርጉት ፡ ነገ
ር ፡፡ ከዚህም ፡ ወራት ፡ አስቀድሞ ፡ ቴዎስ ፡ ተነሣ ፡ እንዴ
ህ ፡ ሲል ፡ ስለ ፡ ራሱ ፡፡ እኔ ፡ ታላቅ ፡ ነኝ ፡፡ ፬፻፤ የሚሆኑ ፡ ሰ
ዎችም ፡ ተከተሉት ፡፡ ሞተም ፡፡ የተከተሉትም ፡ ሁሉ ፡ ተ
ፈቱ ፡ እንደ ፡ ምናምንም ፡ ሆኑ ፡፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ተነሣ ፡
ይሁዳ ፡ የገሊላ ፡ ሰው ፡ ግብር ፡ በተጻፈበት ፡ ዘመን ፡፡ እጅ
ግ ፡ ሰዎችንም ፡ በኋላው ፡ ሳበ ፡፡ እርሱም ፡ ጠፋ ፡፡ የታዘ
ዙትም ፡ ሁሉ ፡ ተበተኑ ፡፡ አሁንም ፡ እላችኋለሁ ፡፡ ራቁ ፡

ከለዚህ ፡ ሰዎች ፡ ተውዋቸውም ፡፡ ይህ ፡ ምክር ፡ ይህም ፡
ስራ ፡ ከሰው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ፈጥኖ ፡ ይፈታል ፡፡ ከእግዚአብ
ሔር ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አይቻላችሁም ፡ ታፈርሱት ፡ ዘን
ድ ፡፡ ደግሞ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ ስትጣሉ ፡ እንዳትገ
ኙ ፡፡ ነገሩንም ፡ ሰሙት ፡፡ ሐዋርያትንም ፡ ጸሩ ፡ መትዋቸ
ውም ፡፡ ነገርዋቸውም ፡ እንደይናገሩ ፡ በየሱስ ፡ ስም ፡፡ ለ
ቀቅዋቸውም ፡፡ እርሳቸው ፡ ግን ፡ ደስ ፡ ብለዋቸው ፡ ሔደ ፡
ከሸንጎ ፡ ፊት ፡፡ ተገብተዋቸዋልና ፡ ደናቁ ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ስ
ሙ ፡፡ ሁለግዜም ፡ አይለዩም ፡ ነበሩ ፡ በመቅደስ ፡ በቤት
ም ፡ ሁሉ ፡ ሲያስተምሩ ፡ ሲሰብኩም ፡ በየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡፡
በዚያም ፡ ወራት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ማኸል ፡ ሹማም
ት ፡ ገና ፡ አልነበሩም ፡፡ ከክርስቶስ ፡ ጋራ ፡ ሁነው ፡ የነበሩ ፡
ወንጌልንም ፡ ያስተምሩ ፡ ዘንድ ፡ ይልካቸው ፡ የነበረ ቸ
ው ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ኃይልም ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡
መሠረት ፡ ያስቀምጡት ፡ የነበሩ ፡ ፲፪፡ ሐዋርያት ፡ የ ቤ ተ ፡
ክ ር ስ ቲ ያ ን ፡ ጠ ባ ቆ ች ፡ ነበሩ ፡ መ ም ሕ ራ ን ም ፡ መንፈ
ስ ፡ ቅዱስ ፡ የመራቸው ፡ ወደ ፡ እውነት ፡ ሁሉ ፡፡ ሐዋርያት
ም ፡ ክርስቶስ ፡ ሳይሞት ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ይከራከሩ ፡ ነበ
ሩ ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡ በመኻከላቸው ፡ ሲጠይቁ ፡፡ ማን ፡
ይበልጣል ፡ በመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡፡ ክርስቶስም ፡ የትሕ
ትና ፡ ምሳሌ ፡ ሰጣቸው ፡ እርሱ ፡ የሁላቸውን ፡ እግር ፡ ሲያ
ፅብ ፡፡ በትምህርቱም ፡ ሁለግዜ ፡ ከትዕቢት ፡ ክብርንም ፡
ከመመኘት ፡ ከለከላቸው ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡፡ ሰው ፡ አባቶ
ች ፡ አይልዋችሁ ፡፡ አባታችሁ ፡ አንድ ፡ ነውና ፡ እርሱም ፡
እግዚአብሔር ፡፡ መምህራንንም ፡ አይልዋችሁ ፡፡ መምህ
ራችሁ ፡ አንድ ፡ ነውና ፡ እርሱም ፡ ክርስቶስ ፡፡ ክብርም ፡
የሚሻ ፡ ከላንተ ፡ ያገልገል ፡፡ ታላቅ ፡ መሆንም ፡ የሚፈል
ግ ፡ በመኻከላችሁ ፡ የሁሉ ፡ ባርያ ፡ ይሁን ፡፡ ክርስቶስም ፡
ከወጣ ፡ በኋላ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስንም ፡ ከተቀበሉ ፡ በኋላ ፡
ይህ ፡ የክብር ፡ መመኘት ፡ ጠፋ ፡፡ ያንን ፡ ነገር ፡ ታላቅ ፡ ክብ
ር ፡ ቍጠሩት ፡ ስለ ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ደናቁ ፡ ዘንድ ፡፡ ደ
ሮ ፡ የክርስቲያን ፡ ቍጥር ፡ ሲበዛ ፡ ሥርዓትን ፡ አሹ ፡፡ ለክ
ርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ አንድነት ፡ ነበረላቸው ፡ በገንዘባቸው ፡ ሁ

ሉ ፡ ይህነንም ፡ መጠበቅ ፡ በመጀመርያ ፡ የሐዋርያት ፡ ተግባር ፡ ነበረ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ አልቻላቸውም ፡ ትምርታቸው ፡ እንደይጐዲ ፡፡ ስለዚህም ፡ ዲያቆናት ፡ አደረጉ ፡ የጉባኤን ፡ ገንዘብ ፡ ለመጠበቅ ፡፡ ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ ስለ ፡ ባልቴቶች ፡፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወገን ፡ ፮፤ ነበሩና ፡ በይሁዳ ፡ ከተወለዱ ፡ አይሁድ ፡ በአሕዛብ ፡ መኻከለም ፡ ከተወለዱ ፡ አይሁድ ፡ በክርስቶስ ፡ያመኑ ፡፡ ካሕዛብ ፡ ገና ፡ አልገቡምና ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡፡ አሁንም ፡ ለንግዶች ፡ ወንድሞች ፡ ካሕዛብ ፡ መኻከል ፡ ደስ ፡ ያሰኙ ፡ ዘንድ ፡ በለው ፡ ጉባኤ ፡ በሐዋርያት ፡ ምክር ፡ ፯፤ ሰዎች ፡ ካረማውያን ፡ መኻከል ፡ ከነበሩ ፡ መረጹ ፡ እርሳቸውም ፡ የታወቁ ፡ በጎ ፡ ምስክርም ፡ የነበረላቸው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ጥበብም ፡ የመላባቸው ፡፡ እሌህም ፡ ናቸው ፡ የተመረጹ ፡፡ እስጢፋኖስ ፡ ሃይማኖት ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ የመላበት ፡ ሰው ፡፡ ፊልጶስም ፡ አብሮኮሮስም ፡ ኒቃኑርም ፡ ጢሞንም ፡ ጰርሚናስም ፡፡ ኒቆላዎስም ፡ መጻተኛ ፡ አገሩም ፡ አንጾኪያ ፡፡ በሐዋርያትም ፡ ፊት ፡ አቆሞዋቸው ፡ በጸለዩም ፡ ጊዜ ፡ እጃቸውን ፡ ጫኑባቸው ፡፡ የእግዚአብሔርም ፡ ነገር ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አለ ፡ የደቀ ፡ መዛሙርትም ፡ ቍጥር ፡ እጅግ ፡ በዛ ፡፡ እጅግም ፡ ሰዎች ፡ ከካህናት ፡ ወገን ፡ ለሃይማኖት ፡ ተገዙ ፡፡

ከለዚያም ፡ ፯፤ ዲያቆናት ፡ አንድ ፡ በለጠ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ኃይል ፡ በሃይማኖትም ፡፡ እርሱም ፡ እስጢፋኖስ ፡፡ እርሱም ፡ የተማረ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡ ካይሁድና ፡ ካረማውያን ፡ ጋራ ፡ ተከራከረ ፡ ብልሃቱንም ፡ ይናገርበትም ፡ የነበረውን ፡ መንፈስ ፡ ይቋቋሙ ፡ ዘንድ ፡ አልቻሉም ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ሰዎችን ፡ አመጡ ፡ እንዲህ ፡ የሚሉ ፡፡ እኛ ፡ ሰማነ ፡ ሲናገር ፡ የስድብ ፡ ነገር ፡ በሙሴ ፡ ላይ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ላይ ፡፡ ሕዝብም ፡ ጻፎችም ፡ ሽማግሎችም ፡ ደነገጹ ፡፡ ተነሥተውም ፡ ነጠቁት ፡ ወደ ፡ ጉባኤም ፡ አመጡት ፡፡ ያሰት ፡ ምስክሮችንም ፡ አስነሡበት ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡፡ ይህ ፡ ሰው ፡ አይተውም ፡ መናገር ፡ የስድብን ፡ ነገር ፡ በዚህ ፡ በተቀደሰ ፡ ስፍራ ፡ ላይ ፡ በኦሪትም ፡ ላይ ፡፡ ሲል ፡ ሰምተነዋልና ፡፡ የሱስ ፡ የናዝሬቱ ፡ ይህነን ፡ ስፍራ ፡ ያፈርሳል ፡ ሕጉን

ም ፡ ይለውጣል ፡ ሙሴ ፡ የሰጠነን ፡፡ በጉባኤም ፡ የተቀመ
ጡ ፡ ሁሉ ፡ አዩት ፡፡ ፊቱንም ፡ አዩት ፡ እንደ ፡ መልአክ ፡ ፊ
ት ፡፡ የካህናትም ፡ አለቃ ፡ ጠየቀው ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ በው
ኑ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡፡ እስጢፋኖስም ፡ በምላሹ ፡
ታሪክን ፡ ተናገራቸው ፡ እግዚአብሔር ፡ ኪዳኑን ፡ እንደደረገ ፡
ካባቶች ፡ ጋራ ፡ ለእሥራኤልም ፡ ሕጉን ፡ እንደ ፡ ሰጠ ፡፡ ደ
ሮ ፡ እርሳቸው ፡ አልጠበቁትም ፡፡ ሙሴንም ፡ አደከሙ ፡፡
እግዚኣብሔርም ፡ መቅደስን ፡ እንደ ፡ ሰጣቸው ፡ እርሳቸ
ው ፡ ግን ፡ አረከሱት ፡፡ ሳሎሞንም ፡ ለመቅደስ ፡ ቤት ፡ እ
ንደ ፡ ሠራ ፡ ደሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ አያድርም ፡ እ
ጅ ፡ በሠራው ፡ ቤት ፡፡ ነቢዩ ፡ እንደለ ፡፡ ሰማይ ፡ ዙፋኔ ፡ ነ
ው ፡ ምድሪቱም ፡ የግሬ ፡ መኖርያ ፡ ናት ፡፡ ምን ፡ ቤት ፡ ት
ሠሩኛላችሁ ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡፡ ምንስ ፡ ስፍራ ፡ ነው ፡
የማርፍበት ፡፡ እጄ ፡ ይህነን ፡ ሁሉ ፡ የፈጠረች ፡ አይደለች
ምን ፡፡ እላንት ፡ አንገት ፡ ደንደኖች ፡ ልባችሁም ፡ ያልተገ
ዘረ ፡ ጆርዋችሁም ፡፡ እላንትም ፡ ሁለግዜ ፡ ትጠላላችሁ ፡
መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ እላንትም ፡ እንደባቶቻችሁ ፡፡ ማነው ፡
ከነቢያት ፡ ያላሳደዱት ፡ አባቶቻችሁ ፡ ገደሉትም ፡፡ አስቀ
ድመው ፡ የተናገረትን ፡ የዚህን ፡ ጻድቁን ፡ መምጣት ፡ ዛ
ሬ ፡ እላንት ፡ አሳልፈችሁ ፡ የሰጣችሁት ፡ የገደላችሁት
ም ፡፡ ሕግን ፡ አልሰደብሁም ፡፡ ሕግንም ፡ ተቀበላችሁ ፡ በመ
ላእክት ፡ ማገልገል ፡ አልጠበቃችኋትምም ፡፡

ይህነንም ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ልባቸው ፡ ተወጋ ፡ ጥርሳቸውን
ም ፡ አፏጩ ፡ በርሱ ፡፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ መልቶበት ፡ ነ
በረና ፡ እስጢፋኖስ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ተመለከተ ፡ የእግዚአ
ብሔርንም ፡ ክብር ፡ አየ ፡ የሱስንም ፡ ቆሞ ፡ በእግዚአብ
ሔር ፡ ቀኝ ፡፡ አለም ፡፡ እነሆ ፡ አያለሁ ፡ ሰማያት ፡ ተከፍተ
ው ፡ የሰው ፡ ልጅም ፡ ቆሞ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቀኝ ፡፡ ሁሉ
ም ፡ በታላቅ ፡ ቃል ፡ ጮሁ ፡ ጆርዋቸውም ፡ ደፈኑ ፡፡ አንድ ፡ ጊ
ዜም ፡ ተነሡበት ፡ ባንድ ፡ ካገሩም ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ አወጡ
ት ፡፡ ወገሩትም ፡፡ ምስክሮችም ፡ ልብሳቸውን ፡ አኖሩ ፡ ባን
ድ ፡ ጎበዝ ፡ እግር ፡ ስሙን ፡ ሳውል ፡ የሚሉት ፡፡ እስጢፋ
ኖስም ፡ ሲወግሩት ፡ ጸለየ ፡ አለም ፡፡ ጌታ ፡ የሱስ ፡ ሆይ ፡

መንፈሴን ፡ ተቀበል ፡፡ በጕልበቱም ፡ ተንበረከከ ፡ በታላ
ቅ ፡ ቃልም ፡ ጮኸ ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ፡፡ አቤቱ ፡ ይህችን ፡ ኃጢ
አት ፡ አትቊጠርባቸው ፡፡ ይህነንም ፡ ብሎ ፡ አንቀላፋ ፡፡
እስጢፋኖስም ፡ መጀመርያ ፡ ሰማዕት ፡ ነበረ ፡ ስለ ፡ የሱ
ስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ደሙን ፡ ያፈሰሰ ፡ ሕይወቱንም ፡ ያል
ወደደ ፡ እስከ ፡ ሞት ፡ ድረስ ፡፡ እኛንም ፡ ያሳፍርናል ፡ እ
ኛ ፡ ብንበርድ ፡ በክርስቶስ ፡ ክርስቶስንም ፡ በመውደድ ፡ ባን
ቃጠል ፡፡ እርሱንም ፡ ነፍሱን ፡ ለመስቀል ፡ ሞት ፡ የሰጠው
ን ፡ ስለኛ ፡ ኃጢአተኞች ፡ እኛ ፡ በኃይል ፡ ሁሉ ፡ እንወደው ፡
ዘንድ ፡ አይገባነምን ፡፡ ምነው ፡ ለኃጢአት ፡ ትገዛለህ ፡ ክ
ርስቶስን ፡ ለሰቀለው ፡፡ ስለዚህም ፡ እንደዚህ ፡ እንላለን ፡፡ እ
ስጢፋኖስ ፡ ቢሆን ፡ ወይስ ፡ ማንም ፡ ቢሆን ፡ ከቅዱሳን ፡
ቊጥር ፡ እንሰግድላቸው ፡ ዘንድ ፡ ወይስ ፡ እንለምናቸው ፡
ዘንድ ፡ አይገባናም ፡፡ ደግ ፡ አንድ ፡ ትእዛዝ ፡ አለን ፡ መን
ፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሲልን ፡ ዕብራውያን ፡ ፲፫ ፯ ያካሔዳቸው
ን ፡ ፍጻሜ ፡ ተመልከቱ ፡ ሃይማኖታቸውንም ፡ ተከተሉ ፡፡
በስጢፋኖስ ፡ ሞትም ፡ የክርስቲያን ፡ ጉባኤ ፡ እጅግ ፡ የ
ተጐዳች ፡ መሰለች ፡፡ ደግ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዳለ ፡ በነቢ
ይ ፡ በይሳይያስ ፡ አፍ ፡፡ መንገዳችሁ ፡ መንገዴ ፡ አይደለም ፡፡
አሳቤም ፡ አሳባችሁ ፡ አይደለም ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሰማይ ፡ ከ
ምድር ፡ ከፍ ፡ በሚል ፡ መጠን ፡ መንገዴም ፡ ከመንገዳች
ሁ ፡ ከፍ ፡ ይላል ፡ አሳቤም ፡ ካሳባችሁ ፡፡ ይሳይያስ ፡ ፶፭
፰ ፱ እንደዚህ ፡ ሆነ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ደግሞ ፡፡ እስጢ
ፋኖስ ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ታላቅ ፡ ስደት ፡ ሆነ ፡ በምእምናን ፡
ላይ ፡ በዚህም ፡ መክንያት ፡ ምእምናን ፡ ተበተኑ ፡ በይሁ
ዳና ፡ በሰማርያ ፡ አገር ፡ ከሐዋርያት ፡ በቀር ፡፡ የተበተኑም ፡
በወንጌል ፡ ሰበኩ ፡፡ ፊልጶስ ፡ ደግሞ ፡ እርሱም ፡ አንድ ፡
ከለዚያ ፡ ፯ ዲያቆናት ፡ ወደ ፡ ሰማርያ ፡ ደረሰ ፡ የክርስ
ቶስንም ፡ ወንጌል ፡ ሲያስተምር ፡ እጅግ ፡ ታምራትንም ፡
ሲያደርግ ፡፡ ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ ደስ ፡ አላቸው ፡ አመኑም ፡ በ
ክርስቶስ ፡ ተጠመቁም ፡፡ አንድም ፡ ታላቅ ፡ አስማተኛ ፡ ስ
ሙን ፡ሲሞን ፡ የሚሉት ፡ ከዚያ ፡ ነበረ ፡ ከብዙ ፡ ዘመን ፡
ጀምሮ ፡፡ ሕዝብንም ፡ ያስታቸው ፡ ነበር ፡ በማስማቱ ፡፡ ይ

ሉትም ፡ ነበሩ ። ይህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ታላቅ ፡ ኃይል ፡ ነው ። የየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ኃይል ፡ ግን ፡ በፊልጶስ ፡ የሰራ ፡ ከሲሞን ፡ ከሰይጣንም ፡ ኃይል ፡ እንደ ፡ በለጠ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ሕዝቡም ፡ እርሱን ፡ ትተውት ፡ ወደ ፡ ፊልጶስ ፡ እንደ ፡ ሔደ ። የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሲሞን ፡ ደግሞ ፡ በክርስቶስ ፡ አመነ ። ደሮ ፡ አላመነም ፡ በክርስቶስ ፡ ከኃጢአት ፡ በሚያድን ፡ በክርስቶስ ፡ ኃይል ፡ እንጅ ፡ ታላቅ ፡ ታአምራትን ፡ በሚያደርግ ። ተጠመቀም ። ባየም ፡ ጊዜ ፡ ታአምራት ፡ ኃይልም ፡ ታላቅ ፡ ሁና ፡ የምትደረግ ፡ በፊልጶስ ፡ ተደነቀ ። በየሩሳሌምም ፡ የተቀመጡ ፡ ሐዋርያት ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ የሰማርያ ፡ ሰዎች ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ተቀበሉ ፡ ጴጥሮስንና ፡ ዮሐንስን ፡ ሰደዱላቸው ። እለዚያም ፡ ወደርሳቸው ፡ ሲደርሱ ፡ ጸለዩባቸው ፡ እጀቸውንም ፡ ጫኑባቸው ፡ ምንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ በምእምናን ፡ ላይ ፡ ወደቀ ። ሲሞን ፡ አስማተኛ ፡ ግን ፡ ይህነን ፡ ሲያይ ፡ ብርን ፡ አመጣ ፡ ለሐዋርያት ፡ ለርሱ ፡ ደግሞ ፡ ኃይልን ፡ ይሸጡ ፡ ዘንድ ፡ ብሎ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ መስጠት ፡ እርሱ ፡ ደግሞ ፡ ይችል ፡ ዘንድ ። እርሱ ፡ አስብዋልና ፡ የመንፈስ ፡ ነገር ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ገንዘብ ፡ እንደሻየጥ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አሁንም ፡ እንደያስቡ ፡ መንግሥት ፡ ሰማያት ፡ በመጽዋዕት ፡ እንደገዛ ፡ ቂስም ፡ የኃጢአትን ፡ ፍትሐት ፡ በሸማና ፡ በብር ፡ ለመሸጥ ፡ ሥልጣን ፡ እንደለው ። ጴጥሮስ ፡ ግን ፡ ለርሱ ፡ እንደርሱም ፡ ለሚያስብ ፡ ሁሉ ፡ እንደህ ፡ አለ ። ብርህ ፡ ካንተ ፡ ጋራ ፡ ይረገም ። የእግዚአብሔርን ፡ ጸጋ ፡ በከብት ፡ እገዛው ፡ ብለህ ፡ አስበሃልና ። ከዚህም ፡ ነገር ፡ ክፍል ፡ ርስትም ፡ የለህም ። ልብህ ፡ የቀና ፡ አይደለምና ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ። አሁንም ፡ ንስሓ ፡ ግባ ፡ ከክፋትህ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ለምን ፡ ምናልባት ፡ ይተውልህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የልብህን ፡ አሳብ ። አይቼብሃለሁና ፡ መራራ ፡ ነገር ፡ የግፍም ፡ ትብትብ ። ሲሞንም ፡ መለሰ ፡ አለም ። እላንት ፡ ለመኑልኝ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እላንት ፡ ካላችሁት ፡ አንዳች ፡ እንዳያገኘኝ ። ደሮ ፡ ሲሞን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አልተመለሰም ። ጴጥሮስም ፡ የለመነለት ፡ እንደሆን ፡ አ

ልጠቀምለትም ፡፡ ይህ ፡ አስማተኛ ፡ ሲሞን ፡ ከዚያ ፡ ወዲ
ያ ፡ እጅግ ፡ ጸላትነት ፡ አድርጓልና ፡ በክርስቶስና ፡ በቤተ ፡
ክርስቲያን ፡ ላይ ፡ መጨረሻውም ፡ ጥፋቱ ፡ ከመጀመርያ
ው ፡ ከፋ ፡፡

ሐዋርያትም ፡ ወደ ፡ የሩሳሌም ፡ ተመለሱ ፡ በመንገዳቸ
ውም ፡ በወንጌል ፡ ሰበኩ ፡ በሰማርያ ፡ አገር ፡፡ የእግዚአ
ብሔርም ፡ መልአክ ፡ ፊልጶስን ፡ ሰደደ ፡ ወደ ፡ ጋዛ ፡ ወደሚ
ወስደው ፡ መንገድ ፡፡ ፊልጶስም ፡ ተነሥቶ ፡ ሔደ ፡፡ እነሆ
ም ፡ አንድ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡ ጀንደረባ ፡ የሕንደ
ኬ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንግሥት ፡ ብላቴንጌታ ፡ ታላቅ ፡ ሰውም ፡፡
በከብትዋም ፡ ሁሉ ፡ የሠለጠነ ፡ ነበረ ፡፡ ይህም ፡ መጣ ፡ ወ
ደ ፡ የሩሳሌም ፡ ሊሰግድ ፡፡ ተመለሰም ፡ በሰረገላ ፡ ተቀም
ጦ ፡ ኢያነበበ ፡ የነቢዩን ፡ የይሳይያስን ፡ መጻፍ ፡፡ መንፈስ ፡
ቅዱስም ፡ ፊልጶስን ፡ አለው ፡፡ ሒድ ፡ ተከተልም ፡ ይህነ
ን ፡ ሰረገላ ፡፡ በደረሰም ፡ ጊዜ ፡ ሰማው ፡ ይሳይያስን ፡ ሲያ
ነብ ፡፡ አለውም ፡፡ ታውቃለህን ፡ የምታነበውን ፡፡ እርሱ
ም ፡ አለ ፡፡ ይህ ፡ እንዴት ፡ ይቻለኛል ፡ አውቅ ፡ ዘንድ ፡ ማ
ንም ፡ ያላስተማረኝን ፡፡ ፊልጶስንም ፡ ለመነው ፡ ወደ ፡ ሰ
ረገላው ፡ ወጥቶ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይቀመጥ ፡ ዘንድ ፡፡ የመጻ
ፍ ፡ ስፍራ ፡ ግን ፡ ያነበው ፡ የነበረ ፡ ይህ ፡ ነበር ፡፡ እንደ ፡ በ
ግ ፡ ተነዳ ፡ ሊታረድ ፡፡ በግም ፡ ዝም ፡ እንዲል ፡ ጸጕሩን ፡ በ
ሚቈርጠው ፡ ፊት ፡ እንዲሁም ፡ እርሱ ፡ አፉን ፡ አልከፈተ
ም ፡፡ በትሕትናም ፡ ፍርዱ ፡ ከፋ ፡ ከፋ ፡ አለ ፡፡ ትውልደን
ም ፡ ማን ፡ ይችላል ፡ ይናገር ፡ ዘንድ ፡፡ ሕይወቱ ፡ ከምድር ፡
ተነጥቀዋልና ፡፡ ጀንደረባውም ፡ መለሰ ፡ ፊልጶስንም ፡ አለ
ው ፡፡ እለምንሃለሁ ፡ ትነግረኝ ፡ ዘንድ ፡ ይህነን ፡ ስለ ፡ ማ
ን ፡ ይናገራል ፡ ነቢይ ፡፡ ስለ ፡ ራሱ ፡ ወይስ ፡ ስለ ፡ ሌላው ፡፡
ፊልጶስም ፡ አፉን ፡ ከፈተ ፡ ያንንም ፡ የተጻፈውን ፡ ሊያስተ
ምረው ፡ ጀመረ ፡ ስለ ፡ የሱስ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡፡ እርሳቸውም ፡
ሲሔዱ ፡ በመንገድ ፡ ወደ ፡ ውኃ ፡ ደረሱ ፡፡ ጀንደረባውም ፡
አለ ፡፡ እነሆ ፡ ውኃ ፡ ማነው ፡ የሚከለክለኝ ፡ እንዳልጠ
መቅ ፡፡ ፊልጶስም ፡ አለ ፡፡ በፍጹም ፡ ልብህ ፡ ብታምን ፡
ይገባል ፡፡ መለሰም ፡ አለም ፡፡ እኔ ፡ አምናለሁ ፡ የሱስ ፡ ክ

ርስቶስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ እንደሆነ ፡፡ ሰረገላውም ፡
ደቆም ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፡፡ ፊልጶስና ፡ ጀንደረባውም ፡ ወረ
ደ ፡ ወደ ፡ ውኃ ፡ አጠመቀውም ፡፡ ከውኃውም ፡ በወጡ ፡
ጊዜ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ፊልጶስን ፡ ነጠቀው ፡ ጀ
ንደረባውም ፡ አላየውም ፡፡ እርሱ ፡ ግን ፡ መንገዱን ፡ ሔደ ፡
በደስታ ፡፡ ፊልጶስም ፡ በአስዱድ ፡ ተገኘ ፡ ሲዞር ፡ አገሩን ፡
ሁሉ ፡ ያስተምርም ፡ ነበር ፡ ወደ ፡ ቄሣርያ ፡ እስኪመጣ ፡
ድረስ ፡፡

አሁንም ፡ ጊዜ ፡ ደረሰ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲ
ያን ፡ ለደህንነትዋ ፡ ለመዝረጋትዋም ፡ ያደረገላት ፡፡ አንዱ
ን ፡ ሰውን ፡ አስነሣ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ኃይል ፡ በልቡ ፡ የ
ተገለጸበት ፡ ክርስቶስም ፡ የመረጸው ፡ ያሰናደውም ፡ ይህ
ና ፡ አቃ ፡ ይሆንለት ፡ ዘንድ ፡ ስሙን ፡ ሊያስተምር ፡ በሮም
ያ ፡ መንግሥት ፡ ሁሉ ፡፡ የወንጌልንም ፡ ትምህርት ፡ ለት
ውልድ ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ ሊያወጣ ፡ የሰው ፡ ነገር ፡ እንደይ
ሆን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነገር ፡ እንጅ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
ሁሉ ፡ የምትናርበት ፡ ለዘላለም ፡፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ያ ፡ ጎበ
ዝ ፡ ነበረ ፡ እስጢፋኖስን ፡ በገደሉት ፡ ጊዜ ፡ የገዳዮቹን ፡ ል
ብስ ፡ የጠበቀ ፡ በብራይሥጥም ፡ ሳውል ፡ በዮናኒም ፡ ጳ
ውሎስ ፡ የተባለ ፡፡ እርሱም ፡ በቂሊቂያ ፡ ከተማ ፡ በታርሶ
ስ ፡ ተወለደ ፡፡ ወላጆቹም ፡ ዕብራውያን ፡ ነበሩ ፡ ከብንያም
ን ፡ ወገን ፡፡ እርሱም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ ከተቀደሙ
ት ፡ ትምርት ፡ ጋራ ፡ ተማረ ፡፡ ካደገም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ የሩሳ
ሌም ፡ ሔደ ፡ ወደ ፡ ፈሪሳውያንም ፡ ጉባኤ ፡ ገባ ፡ ከገማል
ኤልም ፡ ዘንድ ፡ ተማረ ፡ በኦሪትም ፡ ትምህርት ፡ በፈሪሳ
ውያንም ፡ ጽድቅ ፡ በረታ ፡፡ እንደ ፡ አውቀቱም ፡ እግዚአ
ብሔርን ፡ አገለገለ ፡ ያለ ፡ ነውር ፡፡ የክርስቲያንም ፡ ጉባ
ኤ ፡ በፊት ፡ አይቶ ፡ እርሳቸው ፡ የሱስን ፡ የተሰቀለውን ፡
እንደ ፡ አመለኩት ፡ እስጢፋኖስንም ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ እን
ደ ፡ ተናገረ ፡ ስለ ፡ ኦሪት ፡ ስለ ፡ መቅደስም ፡ ሳውል ፡ እጅ
ግ ፡ ተቈጣ ፡፡ የመስቀል ፡ ቃል ፡ ገና ፡ እንቅፋት ፡ ነበረለት
ና ፡፡ ክርስቶስ ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ሁኖ ፡ መስሎታል ፡፡ ለክርስቶ
ስም ፡ ማገልገል ፡ ጣዖትን ፡ እንደ ፡ ማምለክ ፡ ቈጠረው ፡፡

ስለዚህም ፡ እጅግ ፡ ተቈጣ ፡ በክርስቶስ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡፡ እግዚአብሔርንም ፡ ደስ ፡ ሊያሰኘው ፡ ብሎ ፡ ያጥፋቸው ፡ ዘንድ ፡ ፈለገ ፡፡ ጉባኤዎቻቸውንም ፡ አፈረሰ ፡፡ ወደ ፡ ቤታቸውም ፡ ገባ ፡ ወንደችንም ፡ ሴቶችንም ፡ ጎቶ ፡ ወደ ፡ ግዞት ፡ ጨመራቸው ፡፡ ትርፋንም ፡ ሊያደርግ ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ካህናት ፡ አለቃ ፡ ሔደ ፡ ጽፈትንም ፡ ፈለገ ፡ ወደ ፡ ደማስቆ ፡ ላደሁድ ፡ ጉባኤ ፡ ሁሉ ፡፡ በክርስቶስ ፡ መንገድ ፡ ያሉትን ፡ ሰዎች ፡ ቢያገኝ ፡ ወንደችንም ፡ ሴቶችንም ፡ አሥሮ ፡ ያመጣቸው ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ የሩሳሌም ፡፡ ደር ፡ እንደት ፡ ደላል ፡ ደሳይያስ ፡፡ ተማከሩ ፡ ምክራችሁም ፡ ከንቱ ፡ ደሁን ፡፡ ተናገሩ ፡ ነገራችሁም ፡ አደድረስ ፡፡ አማኑኤል ፡ ከዚህ ፡ ነውና ፡፡ ደሳይያስ ፡ ፱፡ ፲፡፡ ደህ ፡ ደረሰ ፡ ስለ ፡ ሳውል ፡ ደግሞ ፡፡ በመንገድ ፡ ሁኖ ፡ ወደ ፡ ደማስቆ ፡ ሲቀርብ ፡ ድንገት ፡ ብርሃን ፡ በራ ፡ በላየው ፡ ከሰማይ ፡፡ ጳውሎስም ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ወደቀ ፡ ድምፅንም ፡ ሰማ ፡ የሚለው ፡፡ ሳውል ፡ ሆይ ፡ ሳውል ፡ ሆይ ፡ ለምን ፡ ታሳደኛለህ ፡፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ደገለጻል ፡ የክርስቶስ ፡ ፍቅር ፡፡ የክርስቶስን ፡ ወደጆች ፡ የሥጋውን ፡ ብልቶች ፡ የሚጸላ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸላቱ ፡ ሁኖ ፡ ደቈጥራል ፡፡ ጳውሎስ ፡ ምእምናንን ፡ ባሳደደቸው ፡ ጊዜ ፡ ክርስቶስ ፡ አለው ፡፡ ለምን ፡ ታሳደኛለህ ፡፡ ሳውልም ፡ አለው ፡፡ አንተ ፡ ማነህ ፡ አቤቱ ፡፡ ጌታም ፡ አለው ፡፡ እኔ ፡ የሱስ ፡ ነኝ ፡ አንተ ፡ የምታሳደኝ ፡፡ የተሳለም ፡ ብረት ፡ አንተ ፡ ብትረግጥ ፡ ላንተ ፡ ደብስሃል ፡፡ ሳውልም ፡ ኢየፈራ ፡ ኢየተንቀጠቀጠም ፡ አለው ፡፡ አቤቱ ፡ ምን ፡ ትሻለህ ፡ አደርግ ፡ ዘንድ ፡፡ ደህነንም ፡ ብሎ ፡ ልቡ ፡ ተለወጠ ፡፡ ጌታውም ፡ ምንድር ፡ ትሻለህ ፡ ጠየቀ ፡፡ በፊት ፡ ጸላቱ ፡ የነበረ ፡ አሁን ፡ ጌታውን ፡ ደቈጥረዋል ፡፡ ልቡንም ፡ በጣም ፡ ለክርስቶስ ፡ ሰጠው ፡፡ እርሱም ፡ ሲጠደቅ ፡ ጌታ ፡ መለሰለት ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ ተነሣና ፡ ሒድ ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡፡ ከዚያም ፡ ትሰማለህ ፡ ታደርገው ፡ ዘንድ ፡ የሚገባህን ፡፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ ከርሱ ፡ ጋረ ፡ ባንድ ፡ የነበሩት ፡ ተደንቀው ፡ ቆሙ ፡፡ ድምፅን ፡ ኢየሰሙ ፡ ማንንም ፡ ሳያዩ ፡፡ ሳውልም ፡ ከምድር ፡ ተነሣ ፡ ዓደኖቹም ፡ ተከፍተው ፡ ማንን ፡ ሳያደ ፡፡ መርተው

ም ፡ ወደ ፡ ደማስቆ ፡ አገቡት ፡፡ ፫፡ ቀንም ፡ ተቀመጠ ፡ ሳያ
ይ ፡ ሳይበላም ፡ ሳይጠጠም ፡፡ በደማስቆም ፡ አንድ ፡ ደቀ ፡
መዝሙር ፡ ነበረ ፡ ስሙን ፡ ሐናንያ ፡ የሚሉት ፡፡ ጌታም ፡
በሕልም ፡ አለው ፡፡ ሐናንያ ፡ ሆይ ፡፡ እርሱም ፡ አለ ፡፡ እኔ
ሆኜ ፡ አቤቱ ፡፡ ጌታም ፡ አለው ፡፡ ተነሥተህ ፡ ሒድ ፡ በመን
ገድ ፡ ቅን ፡ መንገድ ፡ በምትባል ፡፡ በይሁዳ ፡ ቤትም ፡ ኢኻ ፡
አንድ ፡ ሰው ፡ ስሙን ፡ ሳውል ፡ የሚሉት ፡ አገሩም ፡ ጠር
ሴስ ፡ እነሆ ፡ ይጸልያልና ፡፡ በሕልሙም ፡ አየ ፡ አንድ ፡ ሰ
ው ፡ ስሙን ፡ ሐናንያ ፡ የሚሉት ፡ ሲገባ ፡ እጁንም ፡ ሲጫን
በት ፡ በላየው ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡፡ ሐናንያም ፡ መለሰ ፡ አለ
ም ፡፡ አቤቱ ፡ ፈጽሜ ፡ ሰማሁ ፡ ከብዙ ፡ ሰዎች ፡ የዚህን ፡
ሰው ፡ ነገር ፡ ስንት ፡ ክፉ ፡ እንደደረገ ፡ በጻድቃንህ ፡ በየሩ
ሳሌም ፡፡ ከዚህም ፡ ትእዛዝ ፡ አለው ፡ ከካህናት ፡ አለቃ ፡
ያሥር ፡ ዘንድ ፡ ስምህን ፡ የሚጸሩን ፡ ሁሉ ፡፡ ጌታም ፡ አለ
ው ፡፡ ሒድ ፡ ይህ ፡ ለኔ ፡ የተመረጸ ፡ ከብት ፡ ነውና ፡ ስሜ
ን ፡ ይሸከም ፡ ዘንድ ፡ ባሕዛብ ፡ ፊት ፡ በነገሥታትም ፡ በእ
ሥራኤል ፡ ልጆችም ፡፡ እኔም ፡ አሳየዋለሁ ፡ የሚቀበለው
ን ፡ መከራ ፡ ስለ ፡ ስሜ ፡፡ ሐናንያም ፡ ሔደ ፡ ወደ ፡ ቤትም ፡
ገባ ፡፡ እጁንም ፡ ጫነበት ፡ አለውም ፡፡ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ ሳ
ውል ፡ ጌታ ፡ የሱስ ፡ ወደንተ ፡ ላከኝ ፡ በመንገድ ፡ የታየል
ህ ፡ ስትመጣ ፡፡ ታይ ፡ ዘንድ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ይመላ
ብህ ፡ ዘንድ ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ካይኑ ፡ ወደቀ ፡ እንደ ፡ ቅ
ርፊት ፡ ያለ ፡ አየም ፡፡ ተነሥቶም ፡ ተጠመቀ ፡፡ መብል
ም ፡ በተቀበለ ፡ ጊዜ ፡ በረታ ፡፡ አሁንም ፡ ሁለተኛ ፡ ተወል
ደ ፡ መልእክቱን ፡ ጀመረ ፡፡ ሳውልም ፡ በደማስቆ ፡ ካሉ ፡
ከደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ጋራ ፡ ባንድ ፡ ሆነ ፡ አያሌ ፡ ቀን ፡ ሲጸ
ሊ ፡ በሃይማኖትም ፡ ሲጸና ፡፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በክርስቶ
ስ ፡ አስተማረ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡፡ የሰ
ሙትም ፡ ሁሉ ፡ አደነቁ ፡ አሉም ፡፡ በየሩሳሌም ፡ ይህነን ፡
ስም ፡ የሚጸሩን ፡ ሁሉ ፡ ያጠፋ ፡ ይህ ፡ አይደለምን ፡፡ ስለ
ዚህም ፡ ወደዚህ ፡ መጣ ፡ አሥሮ ፡ ሊወስዳቸው ፡ ወደ ፡ ካህ
ናት ፡ አለቆች ፡፡ ሳውልም ፡ ኃይል ፡ ይጨመርለት ፡ ነበረ ፡ በ
ደማስቆ ፡ የነበሩትንም ፡ አይሁድ ፡ ያውክ ፡ ነበረ ፡ ሲገል

ጥ ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ሆነ ። ብዙ ፡ ቀንም ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ አይሁድ ፡ ተማከሩ ፡ አንድ ፡ ሁነው ፡ ይገድሉት ፡ ዘንድ ። ሰውልም ፡ አወቀ ፡ እንደ ፡ ተማከሩበት ። ያገር ም ፡ ደጅ ፡ ሁሉ ፡ ጠበቁት ፡ በሌት ፡ በቀንም ፡ ይገድሉት ፡ ዘንድ ። ደቀ ፡ መዛሙርትም ፡ በሌት ፡ ወሰዱት ፡ ከቀጥር ም ፡ ላይ ፡ በንቀብ ፡ አወረዱት ። ሳውልም ፡ ወደ ፡ ዓረብ ፡ አገር ፡ ሔደ ፡ ወደ ፡ ደማስቆም ፡ ተመለሰ ። ከዚያም ፡ ወደ ያ ፡ ወደ ፡ የሩሳሌም ፡ ወጣ ፡ ጴጥሮስንም ፡ አየ ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ፲፭፡ ቀን ፡ ተቀመጠ ። ደግሞም ፡ ያዕቆብን ፡ የጌታው ን ፡ ወንድም ፡ አየ ። ገላትያን ፡ ፩፡ ፲፰። ወደ ፡ የሩሳሌም ም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ወደደ ፡ ከምእምናን ፡ ጋራ ፡ ባንድ ፡ ይ ሆን ፡ ዘንድ ። ሁሉም ፡ ይፈሩት ፡ ነበረ ፡ ሳያምኑት ፡ እር ሱ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ እንደ ፡ ሆነ ። በርናባስም ፡ ወሰደው ፡ ወደ ፡ ሐዋርያትም ፡ አገባው ፡ አጫወታቸውም ፡ ጌታውን ፡ በመንገድ ፡ እንደየ ፡ እንደ ፡ ተናገረውም ። እንደ ፡ ተጋደ ለም ፡ በደማስቆ ፡ በየሱስ ፡ ስም ። እርሳቸውም ፡ እግዚአ ብሔርን ፡ አመሰገኑበት ። ከርሳቸውም ፡ ጋራ ፡ ተቀመጠ ፡ ሲገባ ፡ ሲወጣም ፡ በየሩሳሌም ፡ ሲጋደልም ፡ በየሱስ ፡ በጌ ታ ፡ ስም ። አይሁድንም ፡ ተናገረ ፡ ተከራከራቸውም ፡ አራ ማውያንንም ። አንድ ፡ ቀንም ፡ በየሩሳሌም ፡ ሲጸልይ ፡ በ መቅደስ ፡ ነፍሱ ፡ ተነጠቀ ፡ የሱስንም ፡ አየ ፡ የሚለው ። ቶሎ ፡ ውጣ ፡ ከየሩሳሌም ፡ ለኔ ፡ የምትመሰክረውን ፡ አ ይቀበሉህምና ። ሳውልም ፡ ጳውሎስ ፡ የተባለ ፡ አለው ። አቤቱ ፡ እርሳቸው ፡ ያውቃሉ ፡ እኔ ፡ እመታ ፡ አሥርም ፡ እ ንደ ፡ ነበርሁ ፡ በመስጊድ ፡ ሁሉ ፡ ባንተ ፡ የሚያምኑትን ፡ ሁሉ ። የሰማዕትህም ፡ የእስጢፋኖስ ፡ ደም ፡ በፈሰሰ ፡ ጊ ዜ ፡ እኔ ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ቁሜ ፡ ተባብርም ፡ ነበርሁ ፡ የገ ደሉትንም ፡ ልብስ ፡ ጠበቅሁ ። ጌታም ፡ አለው ። ሒድ ። እኔ ፡ እልክሃለሁና ፡ ሩቅ ፡ አገር ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ። የሐዋር ያት ፡ ስራ ፡ ፳፪፡ ፲፯። በዚህም ፡ በጌታው ፡ መገለጽ ፡ ጸንቶ ፡ እርሱ ፡ ከሰው ፡ ሁሉ ፡ ጸላትነት ፡ አልፈራም ፡ በደስታ ፡ የ ጌታውን ፡ ወንጌል ፡ ሰበከ ፡ እንጅ ። አይሁድ ፡ ግን ፡ ሊገድ ሉት ፡ ወደዱ ። አሁንም ፡ ጳውሎስ ፡ ነፍሱን ፡ ለክርስቶስ ፡

ሊጠብቅ ፡ ብሎ ፡ ተሰወረ ፡ ወንድሞችም ፡ ወደ ፡ ቂሣርያ ፡ ሸኙት ፡ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ጠርሴስ ፡ ሔደ ።

አሁንም ፡ የክርስቶስ ፡ ጉባኤ ፡ በይሁዳ ፡ ሁሉ ፡ የነበረች ፡ በገሊላም ፡ በሰማርያም ፡ ዕርቅ ፡ ነበረላት ። ተሰርታም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፍርሃት ፡ ተመላለሰች ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ማጽናት ፡ መላባት ።

ጴጥሮስም ፡ በይሁዳ ፡ አገር ፡ ዞረ ፡ ወንጌልን ፡ ለማስተማር ። ወደ ፡ ቅዱሳንም ፡ በልዳ ፡ ወደ ፡ ኖሩት ፡ ሲደርስ ፡ አንድ ፡ ኤንያ ፡ የሚሉት ፡ መፃጉዕ ፡ ሰው ፡ ፰ ፡ አመት ፡ ታሞ ፡ የነበረ ፡ በየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ከሕማሙ ፡ አደነው ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ በያፋ ፡ ለልዳ ፡ በምትቀርብ ፡ አንዲት ፡ በክርስቶስ ፡ ያመነች ፡ ሃይማኖትዋንም ፡ በፍቅርዋ ፡ የገለጸች ፡ ሴት ፡ ነበረች ፡ ስምዋም ፡ ጣቢታ ፡ ማለቱ ፡ ምዳቋ ። እርስዋም ፡ ታመመች ፡ ሞተችም ። የያፋም ፡ ምእምናን ፡ ወደ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወደ ፡ ልዳ ፡ ሰደዱ ፡ ጴጥሮስን ፡ ኢያስለመኑት ፡ እምቢ ፡ እንዳይል ፡ ወደርሳቸው ፡ ከመምጣት ። ጴጥሮስም ፡ ተነሣ ፡ ከርሳቸውም ፡ ጋራ ፡ ሔደ ። ወደ ፡ ያፋም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ደርብ ፡ አወጡት ፡ ምዳቋ ፡ ወደ ፡ ነበረችበት ። በፊቱም ፡ ቆሙ ፡ ባልቴቶች ፡ ሁሉ ፡ ኢያለቀሱ ፡ ኢያሳዩትም ፡ ቃሚሶችን ፡ ልብሶችንም ፡ ምዳቋ ፡ ለርሳቸው ፡ ለድኆችም ፡ ያደረገቻቸው ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ሳለች ። ጴጥሮስም ፡ ሁላቸውን ፡ አወጣ ፡ ወደ ፡ ሜዳ ። ተንበረከከም ፡ ጸለየም ። ወደ ፡ በድንም ፡ ተመለሰ ፡ አለም ። ጣቢታ ፡ ሆይ ፡ ተነሺ ። እርስዋም ፡ ዓይንዋን ፡ ከፈተች ፡ ጴጥሮስንም ፡ ባየች ፡ ጊዜ ፡ ተቀመጠች ። እርሱ ፡ ግን ፡ እጇን ፡ ሰጣት ፡ አስነሣትም ። ከዚያም ፡ የነበሩትን ፡ ቅዱሳን ፡ ባልቴቶችንም ፡ ጸራ ፡ ሕያውትን ፡ ሁና ፡ በፊታቸው ፡ አቆማት ። ይህም ፡ ወሬ ፡ የታወቀ ፡ ሆነ ፡ በያፋ ፡ ሁሉ ፡ ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ በጌታ ፡ አመኑ ። ጴጥሮስም ፡ አያሌ ፡ ቀን ፡ ተቀመጠ ፡ በያፋ ፡ ወደንድ ፡ ሰው ፡ ስምዖን ፡ የተባለ ፡ የቆርበት ፡ ፋቂ ። መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እስኪያዘው ፡ ድረስ ፡ አሕዛብን ፡ በወንጌል ፡ ያስተምር ፡ ዘንድ ።

ቂሣርያ ፡ አንዲት ፡ መልካም ፡ ከተማ ፡ ነበረች ፡ ያንድ ፡

ቀን ፡ መንገድ ፡ የሚያህል ፡ ከያፋ ፡ በባሕር ፡ አጠገብ ፡ የነ
በረች ። ሄሮድስ ፡ ይሠራት ፡ ይሸልማትም ፡ ነበር ፡ ስምዋን
ም ፡ ቂሣርያ ፡ ብሎ ፡ ጸራት ፡ ቂሣር ፡ አውጉስቶስን ፡ ሊያከ
ብርባት ፡ እርሱ ፡ የቂሣር ፡ ወዳጅ ፡ ነበረና ። ከዚያም ፡ ለሮ
ምያ ፡ ቂሣር ፡ አንዲት ፡ ሌጌዎን ፡ ነበረች ፡ ወታደሮችዋ ፡ ከ
ኢጣልያ ፡ የነበሩ ፡ ስለዚህም ፡ ኢጣሊቂ ፡ ተባለች ። በር
ስዋ ፡ መኻከልም ፡ አንድ ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ ነበር ፡ ቆርኔሌ
ዎስ ፡ የሚሉት ። እርሱም ፡ ደህና ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡ ያይሁድ
ን ፡ የሃይማኖታቸውን ፡ ትምርት ፡ የተማረ ፡ እግዚአብሔ
ርንም ፡ የፈራ ፡ ከቤቱ ፡ ሰዎቹ ፡ ጋራ ። እጅግ ፡ መጽዋዕት
ም ፡ ሰጠ ። ክርስቶስን ፡ ግን ፡ በክርስቶስም ፡ ያለ ፡ ሃይማ
ኖት ፡ እርሱም ፡ ብቻ ፡ የሚያጸድቅ ፡ የሚያድንም ፡ አያ
ውቅም ፡ ነበረ ። እርሱም ፡ በራእይ ፡ አየ ፡ በግልጥ ፡ በቀ
ኑ ፡ በ፱፡ ሰዓት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መልአክ ፡ ወደርሱ ፡ ሲ
ገባ ፡ ሲለውም ። ቆርኔሌዎስ ፡ ሆይ ። እርሱም ፡ በተመለከ
ተው ፡ ጊዜ ፡ በፈራም ፡ ጊዜ ፡ አለ ። ምንድር ፡ ነው ፡ ጌታ ፡
ሆይ ። መልአክም ፡ አለው ። ጸሎትህ ፡ መጽዋዕትህም ፡
በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ መጣ ፡ ለመታሰብ ፡ ሁለግዜ ። አ
ንተ ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ መግባት ፡ ትፈልጋለህና ፡
አታገኘውምም ፡ የሰማይን ፡ መንገድ ፡ አታውቅምና ። አ
ሁንም ፡ አንዱን ፡ መንገድ ፡ ያሳይሃል ፡ እግዚአብሔር ። ሰ
ዎችን ፡ ላክ ፡ ወደ ፡ ያፋ ። ሲሞንንም ፡ ጴጥሮስ ፡ የሚባለ
ውን ፡ አስመጣ ። እርሱም ፡ እንግድነት ፡ መጥትዋል ፡ ወደ
ንድ ፡ ሰው ፡ ስምዖን ፡ የቆርበት ፡ ፋቂ ፡ ወደሚሉት ። ቤቱ
ም ፡ በባሕር ፡ አጠገብ ። እርሱም ፡ ይናገርሃል ፡ ታደርገው ፡
ዘንድ ፡ የሚገባህን ፡ ነገር ። መልአኩም ፡ ቆርኔሌዎስን ፡ ይ
ናገረው ፡ የነበረ ፡ በሔደ ፡ ጊዜ ፡ ቆርኔሌዎስ ፡ ጸራ ፡ ፪፡ ከባ
ሮቹ ፡ አንዱም ፡ አለቃ ፡ የሚወደውን ፡ መልካምም ፡ ምግ
ባር ፡ ያለውን ። አጫወታቸውም ፡ መልአክ ፡ ያለውን ፡ ሁሉ
ን ፡ ወደ ፡ ያፋም ፡ ሰደዳቸው ። በነጋውም ፡ እርሳቸው ፡ ሲሔ
ዱ ፡ በመንገድ ፡ ወደገርም ፡ በቀረቡ ፡ ጊዜ ፡ ጴጥሮስ ፡ ወደ ፡ ሰ
ገነት ፡ ወጣ ፡ ይጸልይ ፡ ዘንድ ፡ በ፮፡ ሰዓት ። ተራበም ፡ ሊበ
ላም ፡ ወደደ ። እሊያም ፡ መብል ፡ ሲያበጁ ፡ ነፍሱ ፡ ተነጠ

ቀት ፡ ራእይም ፡ አየ ። እነሆም ፡ ሰማዮች ፡ ተከፍተው ፡ አየ ፡ መጐናጸፊያም ፡ ሲወርድ ፡ እንደ ፡ ታላቅ ፡ ልብስ ፡ ወደ ፡ ምድርም ፡ ደርሶ ፡ ታሥሮ ፡ በ፬፤ ወገን ። የምድርም ፡ እንስሳ ፡ ሁሉ ፡ ነበረበት ፡ አራዊትም ፡ የሚንቀሳቀሰውም ፡ የሰማይም ፡ ዖፎች ። ድምጽም ፡ ወደርሱ ፡ መጣ ፡ እንደህ ፡ ሲል ። ተነሣ ፡ ጴጥሮስ ፡ ሆይ ፡ አርደህም ፡ ብላ ። ጴጥሮስም ፡ አለ ። አይሆንም ፡ አቤቱ ፡ ርኩስ ፡ የሚያስጸይፍም ፡ ከቶ ፡ በልቼ ፡ አላውቅምና ። ድምጽም ፡ ደግሞ ፡ ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ወደርሱ ፡ መጣ ፡ እንደህ ፡ ሲል ። እግዚአብሔር ፡ ያነጻውን ፡ አንተ ፡ አታርክሰው ። ይህም ፡ ሆነ ፡ ፫፤ ጊዜ ፡ እቃውም ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ተመለሰ ። የዚህም ፡ ራእይ ፡ ማለት ፡ ይህ ፡ ነበረ ። እግዚአብሔር ፡ ለጴጥሮስ ፡ በምሳሌ ፡ ገለጸ ፡ በኦሪት ፡ ስለ ፡ ኀጢአት ፡ የተሰራ ፡ መለየት ፡ በፍጥረትና ፡ በፍጥረት ፡ መካከል ፡ ባይሁድና ፡ ባሕዛብም ፡ መካከል ፡ እንዲህ ፡ እንደ ፡ ተሻረ ። ክርስቶስም ፡ ዓለምን ፡ ሁሉን ፡ በደሙ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ አስታርቅዋልና ፡ ምድር ፡ ሁሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነጻች ፡ ተቀደሰችም ። ሰውም ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ለመግባት ፡ ተጸራ ። የእግዚአብሔር ፡ ድምጽም ፡ ፫፤ ጊዜ ፡ እንደ ፡ ተሰማ ፡ ይህነን ፡ ነገር ፡ በጣም ፡ ወደ ፡ ጴጥሮስ ፡ ልብ ፡ ሊያገባ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ሊያስተምረውም ፡ ቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ልጅም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ የምድርን ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ በወንጌል ፡ ማደናቸው ፡ እንደ ፡ ፈቀደች ። ጴጥሮስም ፡ በልቡ ፡ ሲያስብ ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ያየው ፡ ራእይ ። እነኋቸው ፡ ሰዎች ፡ ቆርኔሌዎስ ፡ የላካቸው ፡ የስምዖንን ፡ ቤት ፡ ጠየቁ ። በደጅም ፡ ቆሙ ። ደግሞ ፡ ጸሩ ፡ ይጠይቁ ፡ ዘንድ ፡ ሲሞን ፡ ጴጥሮስ ፡ የሚባለው ፡ ከዚያ ፡ እንግድነት ፡ መጥቶ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብለው ። ጴጥሮስም ፡ ሲያስብ ፡ ባየው ፡ ራእይ ፡ መንፈስ ፡ አለው ። እነሆ ፡ ፫፤ ሰዎች ፡ ይሾኻል ። ነገር ፡ ግን ፡ ተነሣና ፡ ሒድ ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ውረድም ፡ አትጠራጠርም ። እኔ ፡ ለክያቸዋለሁና ። ጴጥሮስም ፡ በወረደ ፡ ጊዜ ፡ ከቆርኔሌዎስ ፡ ወደ ፡ ተላኩ ፡ ሰዎች ፡ አለ ። እነሆ ፡ እኔ ፡ ነ

ኝ ፡ የምትሹኝ ፡፡ ምን ፡ መክንያት ፡ ነው ፡ የመጣችሁበ
ት ፡፡ እርሳቸውም ፡ አሉ ፡፡ ቆርኔሌዎስ ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ በ
ጎ ፡ ሰው ፡ እግዚአብሔርንም ፡ የሚፈራ ፡ ስለ ፡ በጕነቱም ፡
የታወቀ ፡ ባይሁድ ፡ ወገን ፡ ሁሉ ፡፡ ቅዱስ ፡ መልአክ ፡ አዘ
ዘው ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ያስመጣህ ፡ ዘንድ ፡ ካንተም ፡ ነገር ፡ ይ
ሰማ ፡ ዘንድ ፡፡ ጴጥሮስም ፡ ጸራቸው ፡ እንግድነትም ፡ ተቀ
በላቸው ፡፡ በነጋውም ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ወጣ ፡፡ ኢያሌ ፡
ወንድሞችም ፡ በያፈ ፡ ካሉ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ሔዱ ፡፡ በነጋው
ም ፡ ወደ ፡ ቂሣርያ ፡ ገቡ ፡፡ ቆርኔሌዎስም ፡ ይጠብቃቸው ፡
ነበር ፡ ዘመዶቹንም ፡ ወዳጆቹንም ፡ የቀረቡትን ፡ ጸራ ፡፡ ጴ
ጥሮስም ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ ደጎለው ፡ ቆርኔሌዎስን ፡፡ ወደግሩ
ም ፡ ወድቆ ፡ ሰገደለት ፡፡ ጴጥሮስ ፡ ግን ፡ አስነሣው ፡ እንዲ
ህ ፡ ሲል ፡፡ ተነሣ ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡ ሰው ፡ ነኝና ፡፡ ገባም ፡ ከር
ሱ ፡ ጋራ ፡ ኢየተናገረ ፡፡ እጅግ ፡ ሰዎች ፡ አገኘ ፡ ከርሱ ፡ ዘን
ድ ፡ ተከማችተው ፡፡ አላቸውም ፡፡ እላንተ ፡ ታውቃላችሁ ፡
ላይሁዲዊ ፡ ሰው ፡ እንዲደገባ ፡ ይገናኝ ፡ ዘንድ ፡ ይገባም ፡ ዘ
ንድ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ወገን ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ አሳ
የኝ ፡ ማንንም ፡ ከሰው ፡ ርኩስ ፡ ነው ፡ የሚያስጸይፍም ፡
ነው ፡ እንዳልል ፡፡ ስለዚህም ፡ መጣሁ ፡ ሳልጠራጠር ፡ ብ
ጠሩኝ ፡፡ አሁንም ፡ እጠይቃችኋለሁ ፡፡ ለምን ፡ ምክንያት ፡
አስመጣችሁኝ ፡፡ ቆርኔሌዎስም ፡ አለ ፡፡ ካራት ፡ ቀን ፡ ጀ
ምሬ ፡ እስከዚች ፡ ሰዓት ፡ ድረስ ፡ ጾመኛ ፡ ነበርሁ ፡ ስጸል
ይ ፡ በቤቴ ፡ በ፱፡ ሰዓት ፡፡ አንድ ፡ ሰውም ፡ በፊቴ ፡ ቆመ ፡ ነ
ጭ ፡ ልብስ ፡ ለብሶ ፡፡ አለኝም ፡፡ ቆርኔሌዎስ ፡ ሆይ ፡ ጸሎት
ህ ፡ ተሰማችልህ ፡፡ መጽዋዕትህም ፡ ታሰበችልህ ፡ በእግዚ
አብሔር ፡ ፊት ፡፡ አሁንም ፡ ወደ ፡ ያፈ ፡ ላክ ፡ ሲሞንንም ፡
ጴጥሮስ ፡ የሚባለውን ፡ አስመጣ ፡፡ እርሱም ፡ እንግድነ
ት ፡ ተቀምጥዋል ፡ በቆርበት ፡ ፊቂው ፡ በስምዖን ፡ ቤት ፡ በ
ባሕር ፡ አጠገብ ፡፡ እርሱም ፡ መጥቶ ፡ ይናገርሃል ፡፡ የዚያ
ን ፡ ጊዜም ፡ ላክሁብህ ፡፡ አንተም ፡ በጎ ፡ አደረግህ ፡ በመ
ምጣትህ ፡፡ አሁንም ፡ እነሆ ፡ እኛ ፡ ሁላችን ፡ አለን ፡ ከዚ
ህ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እንሰማ ፡ ዘንድ ፡ አንተ ፡ የታ
ዘዝህበትን ፡ ሁሉ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡፡ ጴጥሮስም ፡

አፏን ፡ ከፈተ ፡ አለም ፡፡ አሁን ፡ በውነት ፡ አወቅሁ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ ለሰው ፡ ፊት ፡ እንደ ያድላ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ በሕዝ ብ ፡ ሁሉ ፡ እርሱን ፡ የሚፈራው ፡ ቅን ፡ ነገርንም ፡ የሚያ ደርገው ፡ እርሱ ፡ በርሱ ፡ ዘንድ ፡ የተቀበለ ፡ ነው ፡፡ ወደ ፡ እሥራኤል ፡ ልጆች ፡ የላከው ፡ ነገር ፡ የምስራች ፡ ይነግራቸ ው ፡ ዘንድ ፡ በደህንነት ፡ በየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እርሱም ፡ የ ሁሉ ፡ ጌታ ፡ የሚሆን ፡ ታውቃላችሁ ፡፡ የህችም ፡ የምስራ ች ፡ በይሁዳ ፡ ሁሉ ፡ ተሰማች ፡ ከገሊላ ፡ ጀምሮ ፡ ዮሐን ስ ፡ ካስተማረበት ፡ ጥምቀት ፡ በኋላ ፡፡ ስለ ፡ የሱስ ፡ ስለ ፡ ናዝሬቱ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀብቶታልና ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በኃይልም ፡፡ የዞረ ፡ መልካምም ፡ ያደረገ ፡ ሰይጣንም ፡ ያ ሸነፋቸውን ፡ ሁሉ ፡ የፈወሰ ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ነበረና ፡፡ እኛም ፡ ምስክሮች ፡ ነን ፡ ላደረገው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በይሁዳ ፡ አገር ፡ በየሩሳሌምም ፡፡ እርሱንም ፡ ገደሉት ፡ በ ንጨት ፡ ላይ ፡ ሰቅለው ፡፡ ይህነንም ፡ እግዚአብሔር ፡ አስነ ሣው ፡ በሶስተኛ ፡ ቀን ፡ አስገለጸውም ፡፡ ለሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ አይደላም ፡ ለኛ ፡ እንጂ ፡ አስቀድሞ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ለ ተመረጽነ ፡ ምስክሮች ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የበላነ ፡ የጠጠነም ፡ ከሙታን ፡ ከተነሣ ፡ በኋላ ፡፡ ሕዝብንም ፡ እናስተምር ፡ ዘን ድ ፡ አዘዘነ ፡ እንመሰክርም ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እ ግዚአብሔር ፡ የመረጠው ፡ በሕያዋንና ፡ በሙታን ፡ ይፈር ድ ፡ ዘንድ ፡፡ ለርሱም ፡ ይመሰክራሉ ፡ ነቢያት ፡ ሁሉ ፡ በር ሱ ፡ የሚያምን ፡ ሁሉ ፡ እንዲወስድ ፡ የኃጢአቱን ፡ ስርየ ት ፡ በስሙ ፡፡

ጴጥሮስም ፡ ይህነን ፡ ሲናገር ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወረደ ፡ ነገረን ፡ በሰሙት ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡፡ ያመኑትም ፡ ከግዝረት ፡ ወገን ፡ ከጴጥሮስ ፡ ጋራ ፡ የመጡ ፡ ደነገጡ ፡፡ ባሕዛብ ፡ ደግ ሞ ፡ ፈስዋልና ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስጥወታ ፡፡ በሌላ ፡ ቋ ንቋ ፡ ሲናገሩ ፡ ሰምተዋቸዋልና ፡፡ እግዚአብሔርንም ፡ እ ጅግ ፡ አከበሩ ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ መለሰ ፡ ጴጥሮስ ፡ አለ ም ፡፡ በውኑ ፡ ማንም ፡ ይከለክላልን ፡ ውኃ ፡ እንዳይጠመ ቁ ፡ እሌህ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ የተቀበሉት ፡ እኛ ፡ ደግመ ን ፡ እንደ ፡ ተቀበልነው ፡፡ በጌታ ፡ ስምም ፡ ይጠመቁ ፡ ዘን

ድ ፡ አዘዛቸው ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ለሙኑት ፡ አያሌ ፡ ቀን ፡ ከርሳቸው ፡ ዘንድ ፡ እንደ ቀመጥ ፡፡

እለዚህ ፡ ሰዎች ፡ ያሕዛብ ፡ መጀመርያ ፡ ነበሩ ፡ በየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ያመኑ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ሕዝብም ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ የሆኑ ፡፡ የርሳቸውም ፡ ወሬ ፡ ወደ ፡ የሩሳሌም ፡ ሲደርስ ፡ ካይሁድ ፡ ወገን ፡ የነበሩ ፡ ምእምናን ፡ አላስተወሉትም ፡፡ ከርሳቸውም ፡ መኻከል ፡ አያሌ ፡ ሰዎች ፡ ጴጥሮስን ፡ ተጻሉት ፡ ወደልተገዘሩ ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ ከርሳቸውም ፡ ጋራ ፡ አንድነት ፡ እንደደረገ ፡፡ ጴጥሮስ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሲናገራቸው ፡ ሲላቸውም ፡፡ እግዚአብሔር ፡ የጸጋውን ፡ አንድነት ፡ ከሰጣቸው ፡ ለኛ ፡ እንደ ፡ ሰጠ ፡ ባመኑ ፡ ጊዜ ፡ በጌታ ፡ በየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡፡ እኔ ፡ ማን ፡ ነኝ ፡ እችል ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለመከልከል ፡፡ ይህነን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ዝማሉ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ አመሰገኑ ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡፡ እንዲህ ፡ በውነትን ፡ እግዚአብሔር ፡ ላሕዛብ ፡ ደግሞ ፡ ሰጣቸው ፡ ንስሓ ፡ ለሕይወት ፡፡

የዚያን ፡ ጊዜም ፡ የወንጌል ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ስፍራ ፡ ደግሞ ፡ ተዘረጋ ፡፡ የተበተኑ ፡ ከእስጢፋኖስ ፡ ሞት ፡ በኋላ ፡ በመጣ ፡ መከራ ፡ መጡ ፡ ወደ ፡ ፊንቄ ፡ ወደ ፡ ቆጵሮስም ፡ ወደ ፡ አንጾኪያም ፡፡ እርሳቸው ፡ ግን ፡ ማንንም ፡ አላስተማሩም ፡ በወንጌል ፡ አይሁድን ፡ እንጅ ፡፡ ከርሳቸው ፡ ግን ፡ አያሌ ፡ ነበሩ ፡ ከቆጵሮስ ፡ ወገን ፡ ከቂሬኔም ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ አራማውያንን ፡ ደግሞ ፡ ያስተማሩ ፡ የየሱስ ፡ ክርስቶስንም ፡ ወንጌል ፡ የሰበኩዋቸው ፡፡ የጌታ ፡ እጅም ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፡ ሰዎችም ፡ ቍጥራቸው ፡ እጅግ ፡ የሚሆን ፡ ወደ ፡ ጌታ ፡ ተመለሱ ፡፡ የዚህ ፡ ወሬም ፡ ተሰማ ፡ በየሩሳሌም ፡ ባለች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡፡ በርናባስንም ፡ ሰደዷት ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡፡ በመጣም ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ጸጋ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ደሳለው ፡ ሁሉንም ፡ አጸናቸው ፡ በጌታ ፡ ደኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ልባቸው ፡ ጸንተው ፡፡ እርሱ ፡ ጻድቅ ፡ ሰው ፡ ነበረና ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የመላበት ፡ ሃይማኖትም ፡፡ እጅግ ፡ ሰዎችም ፡ ተሰበሰቡ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡፡ ደግሞ ፡ ወጣ ፡ በርናባስ ፡ ወ

ደ ፡ ጠርሴስ ፡ ሳውልን ፡ ሊሻ ፡፡ ባገኘውም ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ ይዞት ፡ መጣ ፡፡ አንድ ፡ አመትም ፡ ተቀመጡ ፡ በዚያች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡፡ እጅግ ፡ ሰዎችንም ፡ አስተማሩ ፡ ስለዚህም ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ በአንጾኪያ ፡ አስቀድመው ፡ ክርስቲያን ፡ ተባሉ ፡፡ በዚያችም ፡ ወራት ፡ ወረዱ ፡ ነቢያት ፡ ከየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡፡ በሐዋርያት ፡ ዘመን ፡ የክርስቶስ ፡ መንፈስ ፡ አያሌን ፡ ምእምናን ፡ በትንቢት ፡ መላ ፡ ምስክሮች ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ባላመኑ ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡፡ ከለዚያ ፡ ነቢያትም ፡ አንድ ፡ ስሙ ፡ አገቦስ ፡ የተባለ ፡ ተነሣ ፡ በመንፈስም ፡ አስታወቀ ፡ ታላቅ ፡ ራብ ፡ እንዲሆን ፡ በዓለም ፡ ሁሉ ፡፡ እርሱም ፡ የሆነ ፡ ባቀላውድዮስ ፡ ቄሣር ፡ ዘመን ፡፡ አሁንም ፡ የወንድሞች ፡ ፍቅር ፡ ተገለጸ ፡፡ የየሩሳሌም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ድኃይቱ ፡ ነበረችና ፡ አይሁድ ፡ ቀምተዋቸዋልና ፡ ኢብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ሁሉ ፡ መስጠት ፡ አከማቹ ፡ እንደ ፡ ችሎታቸው ፡፡ ከየሩሳሌም ፡ የዘላለም ፡ ገንዘብ ፡ ወጥቶላቸዋልና ፡ እርሳቸው ፡ ታናሽ ፡ ነገር ፡ ቍጠሩት ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ገንዘብ ፡ ይመልሱላቸው ፡ ዘንድ ፡፡ እርሳቸውም ፡ ማገልገላቸውን ፡ በየሩሳሌም ፡ ወደሉት ፡ ሽማግሎች ፡ ሰደዱት ፡ በሳውልና ፡ በበርናባስ ፡ እጅ ፡፡ ሳውልም ፡ አስቀድሞ ፡ ይቀማቸው ፡ ነበር ፡፡

የዚያን ፡ ጊዜም ፡ አዲስ ፡ ስደት ፡ ሆነ ፡ በየሩሳሌም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ላይ ፡፡ ሄሮድስ ፡ አግሪጳ ፡ ንጉሥ ፡ አይሁድን ፡ ደስ ፡ ያሰኛቸው ፡ ዘንድ ፡ አያሌን ፡ ከምእምናን ፡ ሠቀያቸው ፡፡ ያዕቆብን ፡ የዘበዴዎስን ፡ ልጅ ፡ የዮሐንስንም ፡ ወንድም ፡ በሰይፍ ፡ ገደለው ፡፡ ያም ፡ አይሁድን ፡ ደስ ፡ እንደሳያቸው ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ጨመረበት ፡ ጴጥሮስን ፡ ሲይዝ ፡ ደግሞ ፡፡ ይህም ፡ በ፵፬ ፡ አመት ፡ ነበረ ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ ከዕርገቱም ፡ በኋላ ፡ ፲፩ ፡ አመት ፡ አያሌ ፡ ቀን ፡ ከፋሲካ ፡ በፊት ፡፡ ደግሞ ፡ ጴጥሮስ ፡ በግዞት ፡ በሰንሰለት ፡ ታሥሮ ፡ ሲቀመጥ ፡ ከ፬ ፡ ወታደር ፡ መኻከል ፡ የጠበቁት ፡ የሥረት ፡ ቤትም ፡ እጅግ ፡ ጸንቶ ፡ ተዘግቶ ፡ ተጠብቆም ፡ የክርስቲያን ፡ ጉባኤ ፡ በቀንና ፡ በሌሊት ፡ ስለርሱ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለመኑ ፡፡ እግዚአብሔርም ፡ መልአኩን ፡

በሌሊት ፡ ሰደደው ፡ ጠባቂዎችን ፡ በንቅልፍ ፡ መትቶ ፡ ሰንሰለትንም ፡ ፈትቶ ፡ ደጅንም ፡ ሁሉ ፡ ከፍቶ ፡ ጴጥሮስን ፡ ያወጣ ፡፡ ጴጥሮስም ፡ ወደ ፡ ዮሐንስ ፡ ማርቆስ ፡ እናት ፡ ማርያም ፡ ወደ ፡ ተባለች ፡ ወደ ፡ ቤትዋ ፡ መጣ ፡ ከዚያም ፡ የተሰበሰቡ ፡ ምእምናን ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገኑበት ፡፡ ሄሮድስ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ቂሣርያ ፡ ሒደ ፡ ከጢሮስና ፡ ከሲደና ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ጾር ፡ ሊያደርግ ፡ አሰበ ፡፡ እለዚያም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ታረቁ ፡፡ ባንድ ፡ ቀንም ፡ ሄሮድስ ፡ የንጉሥ ፡ ልብስ ፡ ለበሰ ፡ በዙፋኑም ፡ ተቀመጠ ፡ ነገርም ፡ ተናገራቸው ፡፡ ሕዝቡም ፡ ጮሁ ፡፡ ይህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ነው ፡ የሰው ፡ ቃል ፡ አይደለም ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአክ ፡ መታው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ አልሰጠምና ፡፡ ትልም ፡ ፈላበትና ፡ እርሱ ፡ ሞተ ፡፡ የእግዚአብሔር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አደገ ፡ በዛም ፡፡

በርናባስና ፡ ሳውል ፡ ግን ፡ ወደ ፡ የሩሳሌም ፡ ሲደርሱ ፡ መልእክታቸውን ፡ ፈጸሙ ፡፡ ከዚያም ፡ በተመለሱ ፡ ጊዜ ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ወሰዱ ፡ ዮሐንስን ፡ ማርቆስ ፡ የተባለውን ፡፡ እርሱም ፡ ጴጥሮስ ፡ የመንፈሳዊ ፡ ልጁ ፡ የሚለው ፡ በኋላም ፡ ወንጌልን ፡ የጻፈ ፡፡

ባንጾኪያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ነቢያትና ፡ መምሕራን ፡ ነበሩ ። ከርሳቸውም ፡ በርናባስ ። ስምዖንም ፡ ኒግር ፡ የተባለ ። ሉኪዩስም ፡ የቄሬናው ። ማናይንም ፡ ከሄሮድስ ፡ ካራተኛ ፡ አለቃ ፡ ጋራ ፡ ያደገ ። እርሳቸውም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሲያገለግሉ ፡ ሲጾሙም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አለ ። ልዩልኝ ፡ በርናባስንና ፡ ሳውልን ፡ ለጸራኋቸው ፡ ስራ ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ጾሙ ፡ ጸለዩም ፡ እጃቸውንም ፡ ጫኑባቸው ፡ ሰደድዋቸውም ። እሌህም ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተልከው ፡ ወደ ፡ ሰልውቂያ ፡ መጡ ። ከዚያም ፡ በመርከብ ፡ ወደ ፡ ቆጵሮስ ፡ ሰረሩ ። በቆጵሮስም ፡ ፪፡ ከተሞች ፡ ነበሩ ፡ የገቡባቸው ፡ ያንዲት ፡ ስም ፡ ሰላሚስ ፡ የሁለተኛዪቱም ፡ ስም ፡ ጳፎስ ። በሰላሚስም ፡ ወንጌልን ፡ አስተማሩ ፡ ባይሁድ ፡ መስጊድ ። ደሴቱንም ፡ ሁሉ ፡ በዞሩ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ጳፎስም ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ አስማተኛውን ፡ ሰው ፡ አገኙ ፡ አሰ

ተኛ ፡ ነቢይ ፡ ካይሁድ ፡ ወገን ፡ ስሙም ፡ ባሪያሱ ፡ ኤሊማ
ስም ። ይህነን ፡ በመኰንን ፡ በሰርጊዮስ ፡ ጳውሎስ ፡ ቤት ፡
አገኙ ። ይህ ፡ ሰርጊዮስ ፡ ጳውሎስ ፡ ደህና ፡ ሰው ፡ አስተዋይ
ም ፡ ነበረ ፡ ጳውሎስንና ፡ በርናባስንም ፡ አስመጣ ፡ የእግዚ
አብሔርን ፡ ነገር ፡ ከርሳቸው ፡ ሊሰማ ። ኤሊማስ ፡ ግን ፡ አ
ስማተኛ ፡ ከሰይጣን ፡ ወገን ፡ የነበረ ፡ እጅግ ፡ ተከራከራቸ
ው ፡ የሹሙንም ፡ ልብ ፡ ሊያጠፋ ፡ ፈለገ ፡ የእግዚአብሔ
ር ፡ ነገር ፡ በልቡ ፡ እንደ ደገባ ። ጳውሎስ ፡ ግን ፡ መንፈስ ፡
ቅዱስን ፡ መልቶ ፡ ተመለከተው ፡ አለውም ። አንተ ፡ ሸን
ግላ ፡ የመላብህ ፡ ተንኰልም ፡ ሁሉ ፡ የሰይጣን ፡ ልጅ ፡ የ
ጽድቅም ፡ ሁሉ ፡ ጸላት ። አይበቃህምን ፡ የእግዚአብሔር
ን ፡ መንገድ ፡ የቀናቺውን ፡ ማጥፋት ። አሁንም ፡ እነሆ ፡ የ
እግዚአብሔር ፡ እጅ ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ ነው ። ዕውር ፡ ሁን ፡ ፀ
ሓይንም ፡ አትይ ፡ እስከ ፡ ጊዜው ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ወደ
ቀቹበት ፡ ጽጋግ ፡ ጨለማም ። ይዞርም ፡ ጀመረ ፡ መሪውን
ም ፡ ለመነ ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ሹሙ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ የተደረ
ገውን ፡ ተአምራት ፡ አመነ ፡ አደነቀም ፡ የእግዚአብሔርን ፡
ትምርት ።

ከጳፎስም ፡ በሔደ ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስ ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የ
ነበሩት ፡ በጰንፊልያ ፡ አገር ፡ ወዳለች ፡ ወደ ፡ ጰርጌ ፡ ደረሱ ።
ዮሐንስ ፡ ማርቆስ ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ ተለይቶ ፡ ወደ ፡ የሩሳሌ
ም ፡ ተመለሰ ። እርሳቸውም ፡ ከጰርጌ ፡ አልፈው ፡ ወደ ፡
አንጾኪያ ፡ የጲሲዲያ ፡ አገር ፡ ወደምትሆን ፡ ደረሱ ። ጳ
ውሎስም ፡ ሁለግዜ ፡ አይሁድ ፡ ወደ ፡ ተቀመጡበት ፡ አገ
ር ፡ ሲደርስ ፡ እርሳቸውን ፡ ከማስተማር ፡ ጀመረ ፡ ከርሳቸ
ውም ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ አለፈ ። እንዲህም ፡ በጲሲዲያ ፡ አ
ንጾኪያ ። በሰንበት ፡ ቀን ፡ ወደ ፡ አይሁድ ፡ መስጊድ ፡ ገብተ
ው ፡ ተቀመጡ ። የኦሪትም ፡ የነቢያትም ፡ ክፍል ፡ ከተነበ
በ ፡ በኋላ ፡ የመስጊድ ፡ አለቆች ፡ ላኩ ፡ ወደርሳቸው ፡ እን
ዲህ ፡ ሲሉ ። እላንት ፡ ሰዎች ፡ ወንድሞች ፡ መናገር ፡ ሕዝ
ብንም ፡ መምከር ፡ ብትወዱ ፡ ተናገሩ ። ጳውሎስም ፡ ተነ
ሣ ፡ በጁም ፡ ጠቀሳቸው ፡ እንዲህ ፡ ሲልም ፡ ጀመረ ። እላ
ንተ ፡ ሰዎች ፡ የእሥራኤል ፡ ወገን ፡ እግዚአብሔርንም ፡

የምትፈረት ፡ ሁሉ ፡ ስሙ ፡፡ እንደህም ፡ ብሎ ፡ የእሥራኤልን ፡ ወገን ፡ ታሪክ ፡ አወጣላቸው ፡ ከምሥር ፡ ከመውጣታቸው ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ደዊት ፡ መንግሥት ፡ ድረስ ፡፡ ስለ ፡ ደዊትም ፡ ሲናገር ፡ የክርስቶስን ፡ ነገር ፡ አገባ ፡ የደዊት ፡ ልጅ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ዮሐንስ ፡ መጥመቁም ፡ እንደ ፡ መሰከረለት ፡ በየሩሳሌምም ፡ ያሉ ፡ አይሁድ ፡ የሱስን ፡ ሊያጠፉ ፡ ብለው ፡ እንደ ፡ ሰቀሉት ፡ ባለማወቃቸው ፡፡ እንደሁም ፡ አድርገው ፡ ስለርሱ ፡ የተጻፈውን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ፈጸሙት ፡፡ እግዚአብሔርም ፡ ከሙታን ፡ አስነሣው ፡፡ ነገሩንም ፡ እንደህ ፡ ብሎ ፡ ጨረሰ ፡፡ አሁንም ፡ በላንተ ፡ ዘንድ ፡ የታወቀ ፡ ይሁን ፡ እለንት ፡ ሰዎት ፡ ወንድማማች ፡ በዚህ ፡ እንደ፡ነገርላችሁ ፡ የኃጢአት ፡ ማስተስረይ ፡፡ በሙሴ ፡ ኦሪትም ፡ በተጻፈቸው ፡ ሥርዓት ፡ ሁሉ ፡ አትችሉም ፡ ትጸደቁ ፡ ዘንድ ፡፡ በዚህ ፡ ግን ፡ የሚያምን ፡ ሁሉ ፡ ይጸደቃል ፡፡ አሁንም ፡ ተጠንቀቁ ፡ እንደ፡ይመጣባችሁ ፡ በነቢያት ፡ የተባለ ፡፡ እዩ ፡ እላንት ፡ ቸልተኞች ፡ ተደነቁም ፡ ተሻሩም ፡፡ በዘመናችሁ ፡ እኔ ፡ ስራ ፡ እሰራለሁ ፡ የማታምኑትን ፡ ማንም ፡ ቅሉ ፡ ቢነግራችሁ ፡፡

እርሳቸውም ፡ ከመስጊድ ፡ ሲወጡ ፡ ለመንዋቸው ፡ አሕዛብ ፡ በሚመጣው ፡ ቅደሜ ፡ ደናገርዋቸው ፡ ዘንድ ፡ ይህነን ፡ ነገር ፡፡ ጉባኤም ፡ በተፈታ ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስንና ፡ በርናባስን ፡ ካይሁድ ፡ እጅግ ፡ ሰዎች ፡ ተከተሉት ፡ ስደተኞችም ፡ ካሕዛብ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የፈሩ ፡፡ የነገርዋቸው ፡ እሺ ፡ ያሰኝዋቸው ፡፡ ይጸኑ ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ነገር ፡ ከጳውሎስ ፡ አፍ ፡ የሰሙት ፡ በዚህች ፡ መስጊድ ፡ ከንቱ ፡ አልሆነም ፡፡ በሁለተኛውም ፡ ቅደሜ ፡ ተሰበሰቡ ፡ ያገር ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ ለመስማት ፡፡ አሁን ፡ ግን ፡ ሰይጣን ፡ ተቈጣ ፡ አይሁድ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ የተሰበሰቡትን ፡ ቅናት ፡ መላባቸው ፡፡ የጳውሎስንም ፡ ነገር ፡ አፈረሱ ፡ ኢየተቃወሙ ፡ ኢየተሳደቡም ፡፡ ጳውሎስና ፡ በርናባስም ፡ በግልጥ ፡ በቁም ፡ ነገርም ፡ አልዋቸው ፡፡ አስቀድመን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ ለላንት ፡ እንናገር ፡ ዘንድ ፡ ተገባን ፡፡ አሁን ፡ ግን ፡ ስትገፏት ፡ በ

ነፍሳችሁም ፡ ስትፈርዱ ፡ እንደይገባችሁ ፡ የዘላለም ፡ ሕይ
ወት ፡ እነሆ ፡ እኛ ፡ ወደሕዛብ ፡ እንመለሳለን ። እንደዚህ ፡
አዞናልና ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደዚህ ፡ ሲል ። ብርሃን ፡ አደረ
ግሁህ ፡ ላሕዛብ ፡ መድኀኒት ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ እስከ ፡ ምድ
ር ፡ ደርቻ ፡ ድረስ ። አሕዛብም ፡ ይህነን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ደ
ሳላቸው ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ነገር ፡ አመሰገኑ ። ለዘላለ
ምም ፡ ሕይወት ፡ የተዘጋጁ ፡ ሁሉ ፡ አመኑ ። የእግዚአብ
ሔርም ፡ ነገር ፡ በዝያች ፡ ዙርያ ፡ ሁሉ ፡ ተዘረጋ ። አይሁ
ድ ፡ ግን ፡ አስነሡ ፡ የሚገዙትን ፡ ሴቶች ፡ ምግባራቸውም ፡
ያመረውን ፡ ያገሩንም ፡ አለቆች ፡ ሁከትም ፡ አስነሡ ፡ በ
ጳውሎስና ፡ በበርናባስ ፡ ላይ ። ካገራቸውም ፡ አወጥዋቸ
ው ። እርሳቸው ፡ ግን ፡ ክርስቶስ ፡ በቀደም ፡ እንደዘዛቸው ፡
አረገፏት ፡ የግራቸውን ፡ ትብያ ፡ ወደ ፡ ኢቆኒዮምም ፡ መ
ጡ ። ደቀ ፡ መዛሙርትም ፡ ደስታውን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን
ም ፡ መሉ ። በኢቆኒዮምም ፡ ሆነ ፡ ወደ ፡ አይሁድ ፡ መስጊ
ድ ፡ በገቡ ፡ ጊዜ ፡ ሰዎች ፡ ተሰበሰቡ ፡ ጳውሎስና ፡ በርናባስ
ም ፡ እንደዚህ ፡ ተናገሩ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ እስኪያምኑ ፡ ድረስ ፡
ካይሁድና ፡ ካረማውያን ። ያልታዘዙ ፡ ያላመኑም ፡ አይሁ
ድ ፡ ግን ፡ አስነሡ ፡ አስከፉም ፡ ያሕዛብን ፡ ልብ ፡ በወንድ
ሞች ፡ ላይ ። እንደዚሁም ፡ ተቀመጡ ፡ ከዚያ ፡ ረጅም ፡ ዘ
መን ፡ ሲጋደሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለጸጋው ፡ ነገር ፡ የሚመ
ሰክር ፡ የሚሰጥም ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ተአምራት ፡ ድንቅም ፡
በጃቸው ። ያገርም ፡ ሰዎች ፡ ተከፈሉ ። እኩሌቶችም ፡ ካ
ይሁድ ፡ ጋራ ፡ ሆኑ ፡ እኩሌቶችም ፡ ከሐዋርያት ፡ ጋራ ። ያ
ሕዛብና ፡ ያይሁድ ፡ መኳንት ፡ ግን ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ካለቆቻ
ቸው ፡ ጋራ ፡ ያጕሰቍልዋቸው ፡ ይወግርዋቸውም ፡ ዘንድ ።
ያነንም ፡ አወቁ ፡ ኰበለሉም ፡ ወደ ፡ ሊቃዎኒያ ፡ አገር ፡ ወ
ደ ፡ ልስጥራ ፡ ወደ ፡ ደርባም ፡ በዙርያቸውም ፡ ወደሉት ፡ አ
ገር ፡ መጡ ። ከዚያም ፡ የምስራችን ፡ ተናገሩ ። በልስጥራ
ም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበር ፡ እግሩ ፡ የተመመ ፡ ተቀምጦ ፡ አ
ንካሳ ፡ ከናቱ ፡ ሆድ ፡ ጀምሮ ፡ ከቶ ፡ አልሔደም ። ይህም ፡
ሰማ ፡ ጳውሎስ ፡ ሲናገር ። ጳውሎስም ፡ በተመለከተው ፡
ባየም ፡ ጊዜ ፡ ሃይማኖት ፡ እንደለው ፡ ይድን ፡ ዘንድ ፡ በታ

ላቅ ፡ ድምጽ ፡ አለው ፡፡ በግርህ ፡ ቀንተህ ፡ ቁም ፡፡ ተነሥቶ
ም ፡ ተመላለሰ ፡፡ ሕዝብም ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስ ፡ ያደረገ
ውን ፡ ድምጻቸውን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ አደረጉ ፡ በሊቃዎኒያ ፡ ቋ
ንቋም ፡ አሉ ፡፡ አማልክት ፡ ሰዎችን ፡ መሰሉ ፡ ወደኛም ፡
ወረዱ ፡፡ በርናባስንም ፡ መልኩ ፡ ስላመረ ፡ ድያ ፡ ያማል
ክት ፡ ንጉሥ ፡ አሉት ፡፡ ጳውሎስንም ፡ መልኩ ፡ ያላመረ
ውን ፡ ሄርሜን ፡ ያማልክት ፡ ነጋሪ ፡ አሉት ፡ እርሱ ፡ ነውና ፡
ነገርን ፡ የሰራ ፡፡ የድያ ፡ ካህንም ፡ ባገራቸው ፡ ፊት ፡ የነበ
ረ ፡ በርዮች ፡ አመጣ ፡ አክሊሎችም ፡ ወደገር ፡ ደጅ ፡ ሊ
ሠውላቸውም ፡ ወደደ ፡ ከሕዝብ ፡ ጋራ ፡፡ ሐዋርያትም ፡ ይ
ህነን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስና ፡ በርናባስ ፡ ልብሳቸውን ፡
ቀደዱ ፡ ወደ ፡ ሕዝብም ፡ አፈጠኑ ፡ ኢየጮሁ ፡ ኢያሉም ፡፡
እላንት ፡ ሰዎች ፡ ለምን ፡ ይህነን ፡ ትሰራላችሁ ፡፡ እኛም ፡
ሰዎች ፡ ነነ ፡ እንደላንት ፡ የተካከልናችሁ ፡ በሞት ፡፡ ወንጌ
ልንም ፡ እናስተምራችኋለን ፡ ተመለሱ ፡ ዘንድ ፡ ከለዚህ ፡
ሐሳውት ፡ አማልክት ፡ ወደ ፡ ሕያው ፡ አምላክ ፡ ሰማይን
ና ፡ ምድርን ፡ ባሕርንም ፡ ዓለምንም ፡ ሁሉ ፡ በርሱም ፡ ያ
ለውን ፡ ሁሉ ፡ የፈጠረው ፡፡ ባለፈውም ፡ ትውልድ ፡ አሕ
ዛብን ፡ ሁሉ ፡ የተወ ፡ በመንገዳቸው ፡ ይሔዱ ፡ ዘንድ ፡፡ ከ
ዚህም ፡ ጋራ ፡ ራሱን ፡ አልተወም ፡ ያለ ፡ ምስክር ፡፡ ለኛ ፡
በጎ ፡ ሲያደርግ ፡፡ ሲሰጠነም ፡ ከሰማይ ፡ ዝናም ፡ ፍሬ ፡ የሚ
ሆንበትንም ፡ ጊዜ ፡ ልባችንንም ፡ መላ ፡ መበል ፡ ደስታም ፡፡
ደህነንም ፡ ብለው ፡ የግድ ፡ አስተውዋቸው ፡ አሕዛብን ፡ እ
ንደ ደሠውላቸው ፡፡ አይሁድ ፡ ግን ፡ መጡ ፡ ካንጾኪያ ፡ ከ
ኢቆኒዩምም ፡፡ አሕዛብንም ፡ እሺ ፡ አሰኝዋቸው ፡ ጳው
ሎስንም ፡ ወገሩት ፡ ካገርም ፡ ወደ ፡ ሜዳ ፡ ጐተቱት ፡፡ የሞ
ትም ፡ መሰላቸው ፡፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ግን ፡ የጳውሎስን ፡
ነገር ፡ ሰምተው ፡ በክርስቶስ ፡ ያምኑ ፡ የነበሩ ፡ ከበውት ፡
ሳሉ ፡ ተነሥቶ ፡ ወደገር ፡ ገባ ፡፡ በነጋውም ፡ ወጣ ፡ ከበርናባ
ስ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ደርባ ፡፡ በዚያቺም ፡ አገር ፡ አስተማሩ ፡ እ
ጅግ ፡ ሰዎችንም ፡ ደቀ ፡ መዛሙርትን ፡ አደረጉ ፡፡ ተመለሱ
ም ፡ ወደ ፡ ሊስጥራ ፡ ወደ ፡ ኢቆኒዩምም ፡ ወደ ፡ ጲሲዲያ ፡
አንጾኪያም ፡፡ ያጸኑ ፡ ዘንድ ፡ የደቀ ፡ መዛሙርትን ፡ ል

ብ ፡ ይመክርዋቸውም ፡ ነበረ ፡ እንደ ጸኑ ፡ በሃይማኖት ፡ ሲ
ሉ ፡፡ በብዙ ፡ መከራ ፡ ይገበናል ፡ እንገባ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡፡ በጀቸውም ፡ ሾሙላቸው ፡ ቀሳ
ውስት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ሁሉ ፡፡ ጾሙም ፡ ጸለዩላቸው
ም ፡፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ላመኑበት ፡ አደራ ፡ ሰጥዋቸው ፡፡
በጲሲዲያም ፡ ከዞሩ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ጰንፊልያ ፡ መጡ ፡፡ በ
ጰርጌም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ ተናገሩ ፡ ወደ ፡ አጠልያ
ም ፡ ወረዱ ፡፡ ከዚያም ፡ በባሕር ፡ ሰረሩ ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡
ወደ ፡ ተቀበሉባት ፡ ስፍራ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጸጋ ፡ በፈጸ
ሙት ፡ ስራ ፡፡ በመጡም ፡ ጊዜ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰዎ
ች ፡ ሁሉ ፡ ተሰበሰቡ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ያደረገውን ፡ ነገር ፡
ሁሉ ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ነገሩ ፡፡ ላሕዛብም ፡ የሃይማኖት ፡
ደጅ ፡ እንደ ፡ ተከፈተ ፡፡ ከዚያም ፡ ተቀመጡ ፡ አያሌ ፡ ቀን ፡
ከደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ጋራ ፡፡

እንደ፡ህም ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ተዘረጋች ፡ በ
ሐዋርያት ፡ ማገልገል ፡ ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ በጳውሎስና ፡ በ
በርናባስ ፡ ማገልገል ፡ በይሁዳ ፡ በሰማርያም ፡ በሶርያም ፡
በታናሽ ፡ እስያም ፡፡ ጉባኤ ፡ ለጉባኤ ፡ ተጨምራ ፡ ተተከለ
ች ፡ ሐዋርያትም ፡ ወደ ፡ ደረሱበት ፡ ስፍራ ፡ ሁሉ ፡ ወንጌል
ንም ፡ ወደ ፡ ሰበኩበት ፡ ተቀበሉት ፡፡ አሕዛብም ፡ ተመለ
ሱ ፡ ከከንቱ ፡ አማልክት ፡ ወደ ፡ ሕያው ፡ አምላክ ፡፡ ካይ
ሁድም ፡ ታላቅ ፡ ሕዝብ ፡ በርሱ ፡ አመኑ ፡ በመስቀሉ ፡ በሞ
ቱ ፡ ከኃጢአታቸው ፡ ባደናቸው ፡፡ የሕግን ፡ መርገም ፡ ባስ
ወገደ ፡ ከነፍሳቸው ፡ እርሱ ፡ ስለኛ ፡ በውነት ፡ ስለሚያም
ኑ ፡ ሁሉ ፡ መርገም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ አደሮች ፡ ጉ
ባኤዎች ፡ ሲጨመሩ ፡ በተቀደሙት ፡ መካከል ፡ ክርክር ፡
ተነሣ ፡ እንደ፡ህም ፡ ያለው ፡ ክርክር ፡ ታላቅ ፡ መለየት ፡ ማ
ስነሣት ፡ የቻለው ፡ በክርስቲያንና ፡ በክርስቲያን ፡ መካከ
ል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ካላስቀመጠው ፡፡ ያም ፡ ክርክር ፡ በ
ዚያ ፡ ዘመን ፡ የጀመረ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ከቶ ፡ አልጨረ
ሰም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መጀመርያ ፡ መክንያቱ ፡ እን
ኳ ፡ እንደለቀ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ቀን ፡ ድረስ ፡ በስ
ፍራ ፡ ሁሉ ፡ የወንጌል ፡ ትምርት ፡ ወደ ፡ ተገኘችበት ፡ የሃ

ይማሮት ፡ ጠባቆች ፡ ይጋደሉበታል ፡፡ የዚህ ፡ ክርክርም ፡ ነ
ገር ፡ ይህ ፡ ነው ፡፡ በክርስቶስ ፡ የሚያምን ፡ ሁሉ ፡ ከኦሪት ፡
በታች ፡ ነውን ፡ ወይስ ፡ አይደለም ፡፡ ሰውም ፡ በኦሪት ፡ ተግ
ባር ፡ ይጸደቃልን ፡ ወይስ ፡ በሃይማኖት ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ክርስ
ቶስ ፡ ምግባር ፡፡

የተቀደሙት ፡ ምእምናን ፡ በክርስቶስ ፡ ሳያምኑ ፡ የ፪፤
ወገን ፡ ነበሩ ፡ አይሁድና ፡ አሕዛብ ፡፡ እለዚህ ፡ ፪ም ፡ ከ
ለልባቸው ፡ በክርስቶስ ፡ ሲያምኑ ፡ ፩፤ ሆኑ ፡ በክርስቶስ ፡
አንዲት ፡ አዲስ ፡ ፍጥረት ፡፡ አሮጌ ፡ ነገር ፡ ፈጽሞ ፡ ሔደ ፡
ሁሉም ፡ ታደሰ ፡፡ ደሮ ፡ ካይሁድ ፡ ብዙ ፡ ነበሩ ፡ ሃይማኖታ
ቸውን ፡ በስም ፡ ብቻ ፡ የለወጡ ፡ በውነትም ፡ ክርስቲያን ፡
አልሆኑም ፡፡ ከርሳቸውም ፡ ክፍል ፡ በፊት ፡ ፈሪሳውያን ፡
ነበሩ ፡፡ እርሳቸውም ፡ ሲያምኑ ፡ በክርስቶስ ፡ ክርስቶስ
ን ፡ ያይሁድን ፡ ንጉሥ ፡ አሰቡት ፡ በምስጋና ፡ የሚገዛ ፡ ጊ
ዜም ፡ ያለው ፡ ታይቶ ፡ አይሁድንም ፡ ከመከራ ፡ ሁሉ ፡ አ
ድኖ ፡ ያለምን ፡ መንግሥት ፡ ሁሉ ፡ በምስጋና ፡ ሊሰጣቸ
ው ፡፡ እርሳቸውም ፡ ትዕቢተኞች ፡ ነበሩ ፡ ራሳቸውን ፡ በእ
ግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ያከበሩ ፡ ካሕዛብ ፡ የተሻሉ ፡ ሲመ
ስላቸው ፡፡ እግዚአብሔርም ፡ በምግባራቸው ፡ ካሕዛብ ፡
እንደ ፡ መረጣቸው ፡ ስለ ፡ በጕነታቸውም ፡ የተቀበሉ ፡
እንደ ፡ ሆኑ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ መሰላቸው ፡፡ እርሳ
ቸውም ፡ በፊት ፡ ሲያዩ ፡ አሕዛብ ፡ የክርስቲያን ፡ ሃይማኖ
ት ፡ እንደ ፡ ተቀበሉ ፡ በሃይማኖታቸውም ፡ የመንፈስ ፡ ቅ
ዱስን ፡ ስጥወታ፤ አይነቁ ፡ በኋላም ፡ ፈለጉ ፡ ያመኑ ፡ አሕዛ
ብ ፡ ደግሞ ፡ ኦሪትን ፡ እንዲጠብቁ ፡ ከወንጌል ፡ ጋራ ፡ ያለ
ዚህ ፡ የነፍሳቸው ፡ መዳን ፡ አይሆንም ፡ ብለው ፡፡ እንዲህ
ም ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ከይሁዳ ፡ አገር ፡ መጡ ፡ ወደ ፡ አንጾኪ
ያ ፡ ጳውሎስና ፡ በርናባስ ፡ ከዚያ ፡ በተቀመጡ ፡ ጊዜ ፡ ወን
ድሞችንም ፡ አስተማሩ ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡፡ ካልተገዘራችሁ ፡
እንደ ፡ ሙሴ ፡ ሥርዓት ፡ አትችሉም ፡ ትድኑ ፡ ዘንድ ፡፡ ማ
ለታቸውም ፡ ይህ ፡ ነበር ፡፡ ሃይማኖታችሁ ፡ በክርስቶስ ፡ አ
ይጠቅምላችሁም ፡ በኦሪት ፡ የታዘዘውን ፡ ተግባር ፡ ባትጠ
ብቁ ፡፡ የርሳቸው ፡ ጽድቅ ፡ በኦሪት ፡ ስራ ፡ ነበረ ፡ በሃይማኖ

ት ፡ አይደለም ፡ ስለዚህም ፡ የክርስቶስ ፡ የመስቀሉ ፡ ጸላ
ቶች ፡ ሁነው ፡ ተገለጹ ። ጽልም ፡ ክርክርም ፡ ሆነ ፡ ለጳው
ሎስና ፡ ለበርናባስ ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ጥቂት ፡ ያይደለ ። ያ
ንጾኪያም ፡ ጉባኤ ፡ ተማከረ ፡ ጳውሎስና ፡ በርናባስ ፡ ከር
ሳቸውም ፡ ጋራ ፡ ሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ይሔዱ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ የ
ሩሳሌም ፡ ወደ ፡ ሐዋርያት ፡ ወደ ፡ ሽማግሎችም ፡ ስለዚ
ህ ፡ ክርክር ። ከጉባኤም ፡ የተላኩት ፡ ወደ ፡ ፊንቂ ፡ ወደ ፡
ሰማርያም ፡ ሔዱ ፡ ነገርዋቸውም ፡ ያሕዛብን ፡ መመለ
ስ ። ታላቅ ፡ ደስታም ፡ አደረጉ ፡ ለወንድሞች ፡ ሁሉ ። ወ
ደ ፡ የሩሳሌምም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ተቀበልዋቸው ፡ ጉባኤ
ው ፡ ሐዋርያትም ፡ ቀሳውስትም ። እግዚአብሔርም ፡ ባደ
ረገው ፡ ሁሉ ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ አጫወትዋቸው ። የዚያ
ን ፡ ጊዜም ፡ ተነሡ ፡ አያሌ ፡ ከፈሪሳውያን ፡ መንገድ ፡ ያመ
ኑ ፡ እንደህ ፡ ሲሉ ። ይገባል ፡ ትገዝርዋቸው ፡ ዘንድ ፡ ታዝ
ዋቸውም ፡ ዘንድ ፡ የሙሴን ፡ ሕግ ፡ እንዲጠብቁ ። ሐዋር
ያትም ፡ ቀሳውስትም ፡ ተከማቹ ፡ ይህነን ፡ ነገር ፡ ያዩ ፡ ዘን
ድ ። እጅግም ፡ ክርክር ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ተነሣ ፡ ጴጥሮስ ፡ አላቸ
ውም ። እላንት ፡ ወንድሞች ፡ ሰዎች ፡ ታውቃላችሁ ፡ ባለፈ
ው ፡ ዘመን ፡ በኛ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ መረጠ ፡ እግዚአብሔር ፡
አሕዛብ ፡ ካፌ ፡ ይሰሙ ፡ ዘንድ ፡ የወንጌልን ፡ ነገር ፡ ያም
ኑም ፡ ዘንድ ። ልብንም ፡ የሚያውቅ ፡ እግዚአብሔር ፡ መ
ሰከረላቸው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ በሰጣቸው ፡ ጊዜ ፡ ለኛ ፡
እንደ ፡ ሰጠነ ፡ ደግሞ ። በርሳቸውና ፡ በኛ ፡ መኻከልም ፡ መ
ለየትን ፡ አላደረገም ፡ ልባቸውንም ፡ በሃይማኖት ፡ አነጻ
ው ። አሁንም ፡ ለምን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ትፈታተናላች
ሁ ፡ ቀምበርስ ፡ ትጫናላችሁ ፡ በደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ጫን
ቃ ፡ አባቶቻችን ፡ እኛም ፡ እንሸከመው ፡ ዘንድ ፡ የማንች
ለውን ፡ ቀምባር ፡ እርሱም ፡ የኦሪት ፡ ቀምበር ፡ ማንም ፡
ሊፈጽም ፡ የማይችለው ። በጌታ ፡ በየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ጸ
ጋ ፡ እንዲያው ፡ በሚሆን ፡ ያለ ፡ ምግባር ፡ ለሃይማኖት ፡
እንድንድን ፡ እናምናለን ፡ እንደለዚያ ። ሰዎችም ፡ ሁሉ ፡
ዝማሉ ። ጳውሎስና ፡ በርናባስም ፡ሲያጫውቱ ፡ ሰሙ ፡
ተአምራትን ፡ ድንቅንም ፡ እግዚአብሔር ፡ ያደረገውን ፡

ባሕዛብ ፡፡ ዝምም ፡ ካሉ ፡ በኋላ ፡ መለሰ ፡ ያዕቆብ ፡ የጌታ
ው ፡ ወንድም ፡ የተባለ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ እላንት ፡ ሰዎ
ች ፡ ወንድሞች ፡ ስሙኝ ፡፡ ሲሞን ፡ አስቀድሞ ፡ ተናግርዋ
ልና ፡ እግዚአብሔር ፡ ወገኑን ፡ ከአሕዛብ ፡ ማኸል ፡ እንደ ፡
ጉበኘው ፡ ለስሙም ፡ እንደ ፡ ወሰደው ፡፡ ይህም ፡ ይሰማማ
ል ፡ ለነቢያት ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ ከዚ
ህ ፡ በኋላ ፡ እመለሳለሁ ፡ እሰራለሁም ፡ የዳዊትን ፡ ቤት ፡ የ
ወደቀውን ፡ የፈረሰውንም ፡ ተመልሼ ፡ እሰራለሁ ፡ አቆ
መዋለሁም ፡፡ እግዚአብሔርን ፡ ይሹ ፡ ዘንድ ፡ የቀሩት ፡ ሰ
ዎች ፡ አሕዛብም ፡ ሁሉ ፡ ስሜ ፡ በርሳቸው ፡ የተጸራው ፡፡
ይህነን ፡ ሁሉ ፡ ያደረገ ፡ እግዚአብሔር ፡ አለ ፡፡ የታወቀ ፡ ነ
ውና ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስራው ፡ ሁሉ ፡፡
ስለዚህም ፡ እኔ ፡ እፈርዳለሁ ፡ እንዳታደክሙ ፡ ካሕዛብ ፡
የተመለሱትን ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ እንልክ
ባቸው ፡ ከጣዖታት ፡ ርኵሳት ፡ ይርቁ ፡ ዘንድ ፡ ከዝሙት
ም ፡ ከታነቀም ፡ ከደምም ፡፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ከጣዖታት ፡ ማ
ምለክ ፡ ጋራ ፡ ነበረና ፡ ከጣዖታት ፡ ማምለክም ፡ ጋራ ፡ አን
ድነት ፡ እንዳይሆንላቸው ፡ ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ ስለዚያ ፡ ዘመ
ን ፡ ተሰጠ ፡ የሐዋርያት ፡ ምክር ፡ ሁኖ ፡ በምእምናን ፡ ሁ
ሉ ፡ ካይሁድና ፡ ካሕዛብ ፡ በነበሩ ፡ አንድነት ፡ ይደረግ ፡ ዘ
ንድ ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡፡ ይህ ፡ ትእዛዝ ፡ በቃ ፡ ካይሁድ ፡
ወገንም ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ ምእምናን ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ አይሹም ፡ ነበ
ሩ ፡ ከፍቅር ፡ በቀር ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ አዩ ፡ ሐዋርያት ፡
ቀሳውስትም ፡ ከጉባኤ ፡ ጋራ ፡ ከርሳቸው ፡ ይመርጹ ፡ ዘንድ ፡
ሰዎችን ፡ ይሰዷም ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ ከጳውሎስና ፡
ከበርናባስ ፡ ጋራ ፡፡ እርሳቸውም ፡ ይሁዳ ፡ በርሳበ ፡ የተባለ ፡
ሲላስም ፡ በለቲኒ ፡ ሲልዋኑስ ፡ የተባለ ፡፡ እርሳቸውም ፡ ከ
ወንድሞች ፡ በፊት ፡ ነበሩ ፡፡ በጃቸውም ፡ ጻፉ ፡ ይህነን ፡ ነገር ፡፡
ከሐዋርያት ፡ ከቀሳውስትም ፡ ከወንድሞችም ፡ ወደ ፡ ወ
ንድሞች ፡ ካሕዛብ ፡ ወገን ፡ ባንጾኪያ ፡ በሶርያም ፡ በቂል
ቂያም ፡፡ ደስ ፡ ይበላችሁ ፡፡ ከኛ ፡ ሰዎች ፡ መጥተው ፡ እን
ደወኳችሁ ፡ ልባችሁንም ፡ እንደ ፡ ለወጡት ፡ ሰምተናልና ፡
በነገራቸው ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡፡ ትገዘሩ ፡ ዘንድ ፡ ኦሪትንም ፡

ትጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ፡፡ እኛ ፡ ያላዘዝናቸውን ፡፡ አየነም ፡
ባንድ ፡ በተሰበሰብነ ፡ ጊዜ ፡ ሰዎችን ፡ እንመርጽ ፡ ዘንድ ፡ የ
ምንሰደቸው ፡ ወደላንተ ፡ ከወደጀቻችን ፡ ከበርናባስና ፡ ከጳ
ውሎስ ፡ ጋራ ፡፡ ነፍሳቸውን ፡ የለወጡ ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ ጌታ
ችን ፡ ስለ ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡፡ ይሁደንና ፡ ሲላስን ፡
ላክነ ፡፡ እርሳቸውም ፡ ይነግርዋችኋል ፡ ባፈቸው ፡ ይህነን ፡
ነገር ፡፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ፈቅድዋልና ፡ እኛም ፡ ፈቅደናል ፡
ትርፍ ፡ ሸክም ፡ እንደንጭንባችሁ ፡ ከዚህ ፡ ከሚገባችሁ ፡
ነገር ፡ በቀር ፡፡ ትርቁ ፡ ዘንድ ፡ ለጣዖት ፡ ከመሥዋት ፡ ከደ
ምም ፡ ከታነቀም ፡ ከዝሙትም ፡፡ ከዚህ ፡ ራሳችሁን ፡ ብ
ጠብቁ ፡ መልካም ፡ ታድርጋላችሁ ፡፡ ጤና ፡ ይስጣችሁ ፡፡ በ
ዚህ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ይታያል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በሐዋርያት ፡
አፍ ፡ እንደደወድ ፡ በክርስቶስ ፡ የሚያምኑ ፡ በባርነት ፡ እ
ንደኖሩ ፡ ደር ፡ አርነታቸውን ፡ በወንጌል ፡ እንደ ጠብቁ ፡፡ በ
ግዝረት ፡ በሌላም ፡ በሕግ ፡ በታዘዘ ፡ ነገር ፡ አንድንምና ፡ በ
ሃይማኖት ፡ አንጅ ፡ በሃይማኖትም ፡ የሚጸደቁ ፡ ቢወደ ፡
ሕግን ፡ በመጠበቅ ፡ ይጸደቁ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እጅ
ግ ፡ ያሳዝናሉ ፡ የክርስቶስን ፡ ደም ፡ ከንቱ ፡ ያደርጋሉና ፡፡
ክርስቶስም ፡ ያደረገውን ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ መድኃኒታችን ፡ ዝ
ም ፡ እንደሚል ፡ ይቈጥራሉ ፡፡ ክርስቶስም ፡ አይጠቅምላ
ቸውም ፡፡

ከየሩሳሌምም ፡ የተላኩ ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ ደረሱ ፡፡ ሕ
ዝብንም ፡ ሁሉ ፡ በሰበሰቡ ፡ ጊዜ ፡ መልእክቱን ፡ ሰጥዋቸ
ው ፡፡ ባነበቡትም ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ደሳላቸው ፡ ልባቸውም ፡
ጸና ፡፡ ይሁደና ፡ ሲላስ ፡ ግን ፡ ነቢያት ፡ ነበሩና ፡ ደስ ፡ አሰኝ
ዋቸው ፡ ወንድሞችን ፡ በጅግ ፡ ነገርም ፡ አጸንዋቸው ፡፡ በር
ሳቸውም ፡ ዘንድ ፡ አያሌ ፡ ቀን ፡ ከተቀመጡ ፡ በኋላ ፡ በደኅ
ና ፡ ሔደ ፡ ከወንድሞች ፡ ወደ ፡ ሐዋርያት ፡፡ ሲላስ ፡ ግን ፡
ወደደ ፡ ከዚያ ፡ ይቀመጥ ፡ ዘንድ ፡፡ ጳውሎስና ፡ በርናባስ
ም ፡ ተቀመጡ ፡ ባንጻኪያ ፡ አስተማሩም ፡ የምስራችንም ፡
ነገሩ ፡ ደግሞ ፡ ከሌሎች ፡ ከብዙ ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ በእግዚአ
ብሔር ፡ ነገር ፡፡ ከብዙ ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ ጳውሎስ ፡ አለው ፡
በርናባስን ፡፡ ና ፡ እንመለስ ፡ እንጐብኛቸውም ፡ ወንድሞቻ

ችነን ፡ ባስተማርነበት ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ እንዴት ፡ ናቸው ። በርናባስም ፡ ወደደ ፡ ይወስድ ፡ ዘንድ ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ዮሐንስን ፡ ማርቆስ ፡ የተባለውን ። ጳውሎስ ፡ ግን ፡ ወደደ ፡ እንዳይወስዱ ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ደህነን ፡ ከርሳቸው ፡ የተለየውን ፡ በጳንፊልያ ፡ ከርሳቸውም ፡ ጋራ ፡ ያልመጣ ፡ ወደ ፡ ስራ ። በመካከላቸውም ፡ መከፋፈት ፡ ሆነ ፡ እስኪለዩ ፡ ድረስ ። በርናባስም ፡ ማርቆስን ፡ ወሰደ ፡ በመርከብም ፡ ሰረረ ፡ ወደ ፡ ቆጵሮስም ፡ ሔደ ። ጳውሎስ ፡ ግን ፡ ሲላስን ፡ መረጠ ፡ ቸኩሎም ፡ ሔደ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ ወደ ፡ ወንድሞች ። በሶርያም ፡ በቂልቂያም ፡ ዞረ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትንም ፡ አጸና ። ከዚህ ፡ ነገር ፡ ይገለጻል ፡ ሰማዮችም ፡ እንደይነጹ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በመላእክቱም ፡ ስንፍናውን ፡ እንዲያገኝ ። ኢዮብ ፡ ፬፡ ፲፰። ፲፭፡ ፲፭። ወዴት ፡ ይገኛልና ፡ ሰው ፡ ከጳውሎስ ፡ የሚበልጥ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ። ወዴት ፡ ይገኛሉ ፡ ፪፡ ክርስቲያናት ፡ ወንድሞች ፡ የእግዚአብሔርም ፡ መለክተኞች ፡ በፍቅር ፡ የተጸመዱ ፡ ጳውሎስና ፡ በርናባስ ፡ ተጸምደው ፡ እንደ ፡ ነበሩ ። ደሮ ፡ እሌህ ፡ ፪፡ ወንድሞች ፡ አንድ ፡ አካል ፡ የነበሩ ፡ በክርስቶስ ፡ ላያሌ ፡ ቀን ፡ ተለዩ ፡ ስለ ፡ ሶስተኛ ፡ ወንድም ፡ ስለ ፡ ማርቆስ ። ማርቆስም ፡ በውነት ፡ በፊት ፡ በጎ ፡ አላደረገም ፡ በጳንፊልያ ፡ ሲለይ ፡ ከሐዋርያት ፡ ስለዚህም ፡ የጳውሎስ ፡ ቍጣ ፡ አሁን ፡ አልከፋም ። በኋላም ፡ እሌህ ፡ ፫፡ በታላቅ ፡ ፍቅር ፡ ተሰማሙ ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ። የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ አልተዋቸውምና ፡ የክርስቶስን ፡ ስራ ፡ በጃቸው ፡ ያጠፉ ፡ ዘንድ ፡ በጸላትናት ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ።

አሁንም ፡ ጳውሎስ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ኃይል ፡ ከሲላስ ፡ ጋራ ፡ መንገዴን ፡ ሔደ ፡ ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ባሕዛብ ፡ መካከል ፡ ወንጌልን ፡ ሊያስተምር ። ወደ ፡ ልስጥራና ፡ ወደ ፡ ደርባም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ አንዱን ፡ ደህናውን ፡ ደቀ ፡ መዝሙርን ፡ አገኙ ፡ ስሙም ፡ ጢሞቴዎስ ። ያመነች ፡ ያይሁዳዊት ፡ ሴት ፡ ስምዋም ፡ ኤውኒቄ ፡ ልጅዋ ፡ የናቱም ፡ እናት ፡ ሎኢስ ፡ ነበረች ። እሌህም ፡ ፪፡ ሴቶች ፡ ጢሞቴዎስን ፡ ያሳድ

ጉ ፡ ነበረ ፡ በትግሣጽና ፡ በምክር ፡ ለእግዚአብሔር ፡፡ ጳው ሎስም ፡ ይለዋል ፡፡ አንተ ፡ ከሕፃንነትህ ፡ ጀምረህ ፡ ተምረ ሃልና ፡ የተቀደሰችን ፡ መጽሐፍ ፡ የምትችል ፡ ጠቢብ ፡ ታደ ርገህ ፡ ዘንድ ፡ ለዘላለም ፡ መድኃኒት ፡ በየሱስ ፡ ክርስቶ ስ ፡ ሃይማኖት ፡፡ ፪፤ ጢሞቴዎስ ፡ ፫፤ ፲፭፡፡ አባቱም ፡ አረማ ዊ ፡ ነበር ፡፡ ጢሞቴዎስም ፡ በጎ ፡ ምስክር ፡ ነበረለት ፡ በል ስጥራና ፡ በኢቆኒዮም ፡ ከሚኖሩ ፡ ወንድሞች ፡፡ ይህነን ፡ ወ ደደ ፡ ጳውሎስ ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ያወጣ ፡ ዘንድ ፡ በወንጌ ል ፡ ስብከት ፡ ይረዳቸው ፡ ዘንድ ፡፡ ላይሁድም ፡ እንዲያስን ክል ፡ ገዘረው ፡፡ ከዚያ ፡ የነበሩት ፡ አይሁድ ፡ ሁሉ ፡ አባቱ ን ፡ አውቀውት ፡ ነበሩና ፡ አረማዊ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡፡

አገሩንም ፡ ሁሉን ፡ ሲዞሩ ፡ አዘዝዋቸው ፡ ይጠብቁ ፡ ዘን ድ ፡ የታዘዘውን ፡ ትእዛዝ ፡ ከሐዋርያት ፡ ከቀሳውስትም ፡ በየሩሳሌም ፡ ከሚኖሩ ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ አብያተ ፡ ክር ስቲያናት ፡ ጸኑ ፡ በሃይማኖት ፡፡ በቍጥርም ፡ በዙ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡፡

አሁንም ፡ ወደ ፡ ታናሽ ፡ እስያ ፡ ሊሔዱ ፡ ወደዱ ፡ ደግ ፡ እርሳቸው ፡ እንደ ፡ ፈቃዳቸው ፡ አልቻሉም ፡፡ የቤተ ፡ ክር ስቲያን ፡ መስራትና ፡ መዝረጋት ፡ ማጽናትም ፡ መፈጸም ም ፡ የሰው ፡ አይደለም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስራ ፡ ነው ፡ እ ንጅ ፡፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ መልእክተኛ ፡ ጌታው ፡ ወደ ፡ ሚሰደው ፡ ይሔደል ፡፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ቃሉን ፡ በጊዜ ው ፡ ወደሚወድ ፡ ይልካል ፡ ሲልከውም ፡ ይላል ፡፡ ዛሬ ፡ ቃሌን ፡ ብትሰሙ ፡ ልባችሁን ፡ አታጽኑ ፡፡ በበጎ ፡ ጊዜም ፡ የ ማይሰማ ፡ የመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ደጅ ፡ ይዘጋበታል ፡፡ መ ግባትንም ፡ አያገኝም ፡፡

እግዚአብሔር ፡ ቃሉን ፡ አሁን ፡ ወደ ፡ ያሬት ፡ ልጆች ፡ መስደድ ፡ ፈቀደው ፡ ስለዚህ ፡ ሐዋርያትን ፡ ከሌላ ፡ መንገ ድ ፡ ከለከላቸው ፡፡ ባለፉም ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ አፍሪጊያና ፡ ወ ደ ፡ ገላትያ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ተከለከሉ ፡ ነገር ፡ እን ዳይናገሩ ፡ በእስያ ፡፡ ወደ ፡ ሚስያም ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ዞሩ ፡ ወደ ፡ ቢቲንያ ፡ ይሔዱ ፡ ዘንድ ፡፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ አል ተዋቸውም ፡፡ ከሚስያም ፡ ባለፉ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ጥሮዋስ ፡

መጡ ፡፡ ጥራዎስም ፡ በባሕር ፡ አጠገብ ፡ ኑራለችና ፡ ከዚያ ፡ ሊመለሱ ፡ ነበረ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሌላውን ፡ መንገድ ፡ ካ ላሳያቸው ፡፡ አሁንም ፡ ለጳውሎስ ፡ በሌሊት ፡ ራእይ ፡ ታ የለት ፡፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡ ከማቄዶኒያ ፡ ቁሞ ፡ የለመነ ው ፡ እንደህ ፡ ሲል ፡፡ ወደ ፡ መቄዶንያ ፡ እለፍ ፡ እርደነም ፡፡ ደህነንም ፡ ራእይን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ፈለጉ ፡ ወደ ፡ መቄዶኒያ ፡ ይሻገሩ ፡ ዘንድ ፡፡ አውቀዋልና ፡ እግዚአ ብሔር ፡ እንደ ፡ ጸራቸው ፡ ከዚያ ፡ ሊያስተምሩ ፡፡ ከጥራዎ ስም ፡ ጀምሮ ፡ ሉቃስ ፡ ከርሳቸው ፡ ጋሪ ፡ ሔደ ፡ እሌህም ፡ ባንድ ፡ ነበሩ ፡፡ ጳውሎስ ፡ ሲላስም ፡ ጢሞቴዎስም ፡ ሉ ቃስም ፡፡

ከጥራዎስም ፡ ሰረሩ ፡ ወደ ፡ ሳሞትራኪም ፡ መጡ ፡፡ በነ ጋውም ፡ ሔዱ ፡ ወደ ፡ ኔያጶሊስ ፡ በመቄደኒያ ፡ ያለች ፡፡ ከዚ ያም ፡ ወደ ፡ ፊልጲስ ፡ እርስዋም ፡ የመቄደንያ ፡ ከተማ ፡ ኮሎኒያም ፡ የምትሆን ፡፡ በዚቺም ፡ አገር ፡ አያሌ ፡ ቀን ፡ ተቀመጡ ፡፡ በሰንበትም ፡ ወጡ ፡ካገር ፡ ወደ ፡ ሜደ ፡ ስትሪ ሞን ፡ ወደ ፡ ሚሉት ፡ ወንዝ ፡ ጸሎት ፡ ይደረግበት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ለመደው ፡ ስፍራ ፡፡ በተቀመጡም ፡ ጊዜ ፡ ተናገሩ ፡ ከ ዚያ ፡ ለጸሎት ፡ ለተሰበሰቡት ፡ ሴቶች ፡፡ አንዲት ፡ሴትም ፡ ስምዋን ፡ ሉዲያ ፡ የሚልዋት ፡ ቃይ ፡ ሐርም ፡ የምትሸጥ ፡ ከቲያቲራ ፡ አገር ፡ ለእግዚአብሔር ፡ የምትገዛ ፡ ሰማች ፡፡ እግዚአብሔርም ፡ ልብዋን ፡ ከፈተ ፡ ከጳውሎስ ፡ የተባለ ውን ፡ ታስተውል ፡ ዘንድ ፡፡ እርስዋም ፡ በተጠመቀች ፡ ጊ ዜ ፡ ከቤት ፡ ሰቦችዋ ፡ ጋሪ ፡ ለመኑቻቸው ፡ እንደህ ፡ ስትል ፡፡ ያወቃችሁስ ፡ እንደሆን ፡ እኔ ፡ በጌታ ፡ እንደመንሁ ፡ ወደ ፡ ቤቴ ፡ ግቡና ፡ ተቀመጡ ፡፡ የግድም ፡ አለቻቸው ፡ እንደህ ም ፡ ሆነ ፡፡ እርሳቸውም ፡ ወደ ፡ ጸሎት ፡ ሲሔዱ ፡ አንዲት ፡ ቀንጀዱቱ ፡ ተከተለቻቸው ፡ የሚያናግራት ፡ መንፈስ ፡ ያደ ረባት ፡፡ በመናገርዋም ፡ ለጌቶችዋ ፡ እጅግ ፡ ጥቅም ፡ ትጠ ቅም ፡ ነበረች ፡፡ አሁን ፡ ሰይጣን ፡ በዚች ፡ ሴቲቱ ፡ አፍ ፡ ይ ተነኮልባቸው ፡ ዘንድ ፡ አሻ ፡፡ ደሮ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጠ በቃቸው ፡ በሰይጣን ፡ ወጽመድ ፡ እንደደወድቁ ፡፡ ይህች ም ፡ ሴቲቱ ፡ ሐዋርያትን ፡ አያሌ ፡ ጊዜ ፡ ተከተለች ፡ ከጸሎ

ት ፡ ሲመጡ ፡ እንዲህም ፡ ስትል ፡ ጮሀች ፡፡ እሌህ ፡ ሰዎች ፡ የልዑል ፡ አምላክ ፡ ባሮች ፡ ናቸው ፡፡ እርሳቸውም ፡ ያስተምርዋችኋል ፡ የመድኃኒትን ፡ መንገድ ፡፡ ሰይጣንም ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ለትዕቢት ፡ ሊያስታቸው ፡ ነበር ፡ ደግሞ ፡ በትዕቢት ፡ ፈንታ ፡ ለትሕትና ፡ ሆነለት ፡ ለጳውሎስ ፡፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ አዝኖ ፡ ወደዚያ ፡ መንፈስ ፡ ተመልሶ ፡ አለው ፡፡ አዝሃለሁ ፡ በየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስም ፡ ከርስዋ ፡ ትወጣ ፡ ዘንድ ፡፡ በዚያም ፡ ጊዜ ፡ ወጣ ፡፡ አሁንም ፡ ሰይጣን ፡ ተቈጥቶ ፡ ጌቶችዋን ፡ አሳወከ ፡ በሐዋርያት ፡ ላይ ፡፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ የመጠቀማቸው ፡ ተስፋ ፡ እንደ ፡ ተቈረጠ ፡ ጳውሎስንና ፡ ሲላስን ፡ ያዝዋቸው ፡፡ በገቢያም ፡ ጐተትዋቸው ፡ ወደ ፡ አለቆች ፡፡ ወደ ፡ ጭፍሮችም ፡ ባመጥዋቸው ፡ ጊዜ ፡ አሉ ፡፡ እሌህ ፡ ፪፡ ሰዎች ፡ አገራችንን ፡ እጅግ ፡ አወኩ ፡ እርሳቸውም ፡ አይሁድ ፡ ናቸው ፡፡ እንቀበለውም ፡ ዘንድ ፡ እናደርገውም ፡ ዘንድ ፡ የማይገባነውን ፡ ሕግ ፡ ይናገራሉ ፡፡ እኛ ፡ የሮም ፡ ሰዎች ፡ ነን ፡፡ ሕዝብም ፡ ተነሣባቸው ፡፡ ጭፍሮችም ፡ ልብሳቸውን ፡ አስገፈፉ ፡ በሽመልም ፡ አስመትዋቸው ፡፡ እጅግም ፡ ካቈሰልዋቸው ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ግዞት ፡ ቤት ፡ ጣልዋቸው ፡፡ የግዞትንም ፡ ጠባቂ ፡ አዘዙት ፡ ተጠንቅቆ ፡ ይጠብቃቸው ፡ ዘንድ ፡፡ በዚህም ፡ ትእዛዝ ፡ በታዘዘ ፡ ጊዜ ፡ አጋዛቸው ፡ ወደ ፡ ውስጡ ፡ ግዞት ፡፡ እግራቸውንም ፡ አጸና ፡ በንጨት ፡፡ በመንፈቀ ፡ ሌሊትም ፡ ይጸልዩ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ያመሰግኑ ፡ ነበሩ ፡ ጳውሎስና ፡ ሲላስ ፡፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ልባቸውን ፡ በመከራቸው ፡ አጽንቶታልና ፡ በሐዝን ፡ ፈንታ ፡ ያመሰግኑ ፡ ይመኩም ፡ ዘንድ ፡፡ እሥሮችም ፡ ሰምዋቸው ፡፡ ድንገትም ፡ ታላቅ ፡ መናወጥ ፡ ሆነ ፡፡ እግዚአብሔር ፡ መስክሮላቸዋልና ፡፡ የግዞትም ፡ መሠረት ፡ ተናወጠ ፡ ደጆችም ፡ ሁሉ ፡ ተከፈቱ ፡፡ እሥራትም ፡ ለታሠሩት ፡ ሁሉ ፡ ተፈታላቸው ፡፡ የግዞትም ፡ ጠባቂ ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ግዞትንም ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ደጅ ፡ ሁሉ ፡ ተከፍቶ ፡ ሰይፉን ፡ መዘዘ ፡ ራሱን ፡ ይገድል ፡ ዘንድ ፡፡ የታሠሩት ፡ የኰበለሉ ፡ መስሎታልና ፡፡ ጳውሎስም ፡ በታላቅ ፡ ድምጽ ፡ ጮሀበት ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ በራስህ ፡ ክፉ ፡ አታድርግ ፡፡ እ

ኛ ፡ ሁላችን ፡ ከዚህ ፡ ነን ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ አውቆ ፡ እሌ
ህ ፡ ሰዎች ፡ ማን ፡ እንደሆኑ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሰዎች ፡ ነበ
ሩና ። እርሳቸውንም ፡ እንደ ፡ በደላቸው ፡ ፈራ ፡ አዘነም ፡
ስለ ፡ ኃጢአቱ ። መብራትንም ፡ ወስደ ፡ ተነሣ ፡ ኢየተንቀ
ጠቀጠም ፡ ገባ ። ሰግደም ፡ ወደቀ ፡ ለጳውሎስና ፡ ለሲላስ ።
ወደ ፡ ሜዳም ፡ አወጣቸው ። አለም ። ጌቶቼ ፡ ሆይ ፡ ምን
ድር ፡ ይገባኛል ፡ አደርግ ፡ ዘንድ ፡ እንድድን ። እርሳቸው
ም ፡ አሉት ። በጌታ ፡ በየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እመን ፡ ትድናለ
ህም ፡ ቤትህም ፡ ሁሉ ። የጌታንም ፡ ነገር ፡ ነገሩት ፡ በቤቱ ፡
ላሉትም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ የዘላለም ፡
መድኃኒት ፡ ያመጡለትን ፡ ሰዎች ፡ ወድዋቸዋልና ፡ ወሰደ
ቸው ፡ በሌት ፡ ቍሥላቸውንም ፡ አጠበላቸው ። የዚያን ፡
ጊዜም ፡ ተጠመቀ ፡ እርሱ ፡ የቤቱም ፡ ሰዎች ። ወደ ፡ ቤቱ
ም ፡ አወጣቸው ፡ ማዕድም ፡ አቀረበላቸው ። ይሳለውም ፡
እርሱ ፡ የቤቱም ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ። በእግዚአብሔር ፡ ስላ
መኑ ። እውነተኛ ፡ ደስታ ፡ አዘን ፡ የሌለበት ፡ በውነተኛ ፡ ሃ
ይማኖት ፡ ይገኛልና ፡ ብቻ ። ያለም ፡ ደስታ ፡ ሁሉ ፡ ግን ፡ ከን
ቱ ፡ ነው ፡ ጢስንም ፡ ይመስላል ። የእግዚአብሔር ፡ ደስታ
ም ፡ ከኃጢአት ፡ ስርየት ፡ የሚነሣ ፡ ሁለጊዜ ፡ ይኖራል ።

የፊልጶስ ፡ አለቆችም ፡ ማልደው ፡ ጭፍሮችን ፡ ሰደዱ ፡
እንደዚህ ፡ ሲሉ ። አውጣ ፡ እለዚያን ፡ ፪፡ ሰዎች ። እርሳቸ
ው ፡ ፈርተዋልና ፡ በሌሊት ፡ ከሆነ ፡ መናወጥ ፡ የተነሣ ። የ
ግዞትም ፡ ጠባቂ ፡ የምስራች ፡ ነገረው ፡ ጳውሎስን ፡ እንደ
ህ ፡ ሲል ። አለቆች ፡ ላኩ ፡ ትወጡ ፡ ዘንድ ። አሁንም ፡ ው
ጡ ፡ በደህናም ፡ ሒዱ ። ጳውሎስ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ በ
ሁሉ ፡ በመለክተኞቹ ፡ ይመሰገን ፡ ዘንድ ፡ ብሎ ፡ አላቸው ፡
በግልጽ ፡ መቱን ፡ እኛ ፡ የሮም ፡ ሰዎች ፡ ስንሆን ። ያለ ፡ ፍር
ድም ፡ በደሉን ፡ በግዞትም ፡ ጣሉን ። አሁንም ፡ በሥውር ፡
ያወጡናልን ። አይሆንም ። እርሳቸው ፡ መጥተው ፡ ያው
ጡን ፡ እንጂ ። ጳውሎስ ፡ በጠርሴስ ፡ ተወልድዋልና ፡ የጠር
ሴስ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ሥልጣን ፡ ከተቀበሉ ፡ በኋላ ፡ የሮም ፡
ባላገሮች ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ። የሮምም ፡ ባላገሮች ፡ ከሌላ ፡
ፍርድ ፡ በታች ፡ አልነበሩም ፡ ከቄሣር ፡ እንጂ ፡ ከሮምም ፡

ጉባኤ ፡ በታች ። ከለዚህም ፡ ሌላ ፡ ፈራጅ ፡ አልፈረደባቸ
ውም ። ጭፍሮችም ፡ የጳውሎስን ፡ ነገር ፡ ላለቆች ፡ ነገሩ ።
እለዚያም ፡ የሮም ፡ ሰዎች ፡ እንደሆኑ ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ፈ
ሩ ፡ ወደርሳቸውም ፡ መጡ ፡ አወጥዋቸውም ። ከከተማ
ም ፡ ይወጡ ፡ ዘንድ ፡ ለመንዋቸው ። ከግዞትም ፡ ከወጡ ፡
በኋላ ፡ ገቡ ፡ ወደ ፡ ሉድያ ። ወንድሞችንም ፡ አይተው ፡ አ
ጸንዋቸው ፡ ወጡም ።

ይዞሩም ፡ በነበሩ ፡ ጊዜ ፡ ባምፊጶሊስ ፡ ባጶሎንያም ፡ ወ
ደ ፡ ተሳሎንቄ ፡ መጡ ። ከዚያም ፡ ያይሁድን ፡ መስጊድ ፡ አ
ገኙ ። ጳውሎስም ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ ገባ ፡ ወደርሳቸው ። ሶ
ስት ፡ ሰንበትም ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ነገር ፡ ነገራቸው ፡ ኢ
የከፈተ ፡ ኢየገለጸም ፡ ክርስቶስ ፡ እንዲገባው ፡ ሕማማ
ትን ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ ከሙታንም ፡ ይነሣ ፡ ዘንድ ፡ እንዲህ
ም ፡ ሲል ። ይህ ፡ ክርስቶስ ፡ የሱስ ፡ ነው ፡ እኔ ፡ የማስተም
ራችሁ ፡ እርሱን ። ከርሳቸውም ፡ አያሌ ፡ ሰዎች ፡ አመኑ ።
ከጳውሎስና ፡ ከሲላስም ፡ ጋራ ፡ ሆኑ ። ከአረማውያንም ፡
ከመልካም ፡ ሰዎች ፡ እጅግ ፡ ብዙ ። ከሴቶችም ፡ ከታላለቆ
ች ፡ ጥቂት ፡ ያይደሉ ። አይሁድ ፡ ግን ፡ ያላመኑበት ፡ ቀኑባ
ቸው ፡ ክፉ ፡ ሰዎችን ፡ ከገቢያ ፡ እስኪሰበስቡባቸው ፡
ድረስ ። አገርንም ፡ አወኩ ። በያሶንም ፡ ቤት ፡ እንግድነ
ት ፡ የመጡበት ፡ ቆሙ ፡ ሲሹዋቸው ፡ ወደ ፡ ሕዝብ ፡ ይወስ
ድዋቸው ፡ ዘንድ ። ባላገኙዋቸውም ፡ ጊዜ ፡ ያሶንን ፡ ጉተ
ቱ ፡ ሌሎችንም ፡ ሰዎች ፡ ከወንድሞች ፡ ወደገር ፡ አለቆች ።
እንደህ ፡ ሲሉም ፡ ጮሁ ። እሌህ ፡ ናቸው ፡ ዓለምን ፡ ያወ
ኩ ፡ ደግሞም ፡ ወደህ ፡ መጡ ። ያሶንም ፡ ተቀበላቸው ። እ
ሌህም ፡ ሁሉ ፡ ያድርጋሉ ፡ የቄሣርን ፡ ትእዛዝ ፡ የሚጸላ ፡
እንደህ ፡ ሲሉ ። ሌላ ፡ ንጉሥ ፡ አለ ፡ የሱስ ፡ የሚሉት ። ሕ
ዝብንም ፡ ያገርንም ፡ አለቆች ፡ አሳወኩ ፡ ይህነን ፡ ነገር ፡ በ
ሰሙ ፡ ጊዜ ። ከያሶንም ፡ ከቀረትም ፡ ምላሽ ፡ ተቀበሉ ፡
ለቀቅዋቸውም ። ወንድሞችም ፡ የዚያን ፡ ጊዜን ፡ በሌሊ
ት ፡ ሰደድዋቸው ፡ ጳውሎስንና ፡ ሲላስን ፡ ወደ ፡ ቤሬያ ። ከ
ዚያም ፡ ወደ ፡ አይሁድ ፡ መስጊድ ፡ ገቡ ። እርሳቸውም ፡
የከበሩ ፡ ነበሩ ፡ በተሳሎኒቄ ፡ ከሚኖሩት ፡ ይልቅ ። ተቀበለ

ዋልና ፡ ነገራቸውን ፡ በፍጹም ፡ ልባቸው ፡፡ ሁልግዜም ፡ መረመሩ ፡ መጻሕፍትን ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ እንዲህ ፡ እንደሆነ ፡፡ ከርሳቸውም ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አመኑ ፡፡ ካረማውያንም ፡ እጅግ ፡ ከተመረጡትም ፡ ሴቶች ፡፡ ወንዶችም ፡ ጥቂት ፡ ያይደሉ ፡፡ አይሁድም ፡ በተሳሎንቄ ፡ ያሉት ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስ ፡ በቤሪያ ፡ እንዲስተማረ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ ወደዚያ ፡ ደግሞ ፡ መጡ ፡ ሰዎችንም ፡ አናወጡ ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ሰደዱ ፡ ወንድሞች ፡ ጳውሎስን ፡ ይሔድ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡፡ ሲላስና ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ግን ፡ ከዚያ ፡ አያሌ ፡ ቀን ፡ ተቀመጡ ፡፡ ጳውሎስንም ፡ የተከተሉት ፡ ይዘውት ፡ ሔዱ ፡ ወደ ፡ አቴና ፡ ወደ ፡ አቲካ ፡ ከተማ ፡ የጽርዕ ፡ ጥበብ ፡ ሁሉ ፡ ወደተከማቸችባት ፡ አገር ፡፡ ያሸኙትም ፡ የነበሩት ፡ ሔደው ፡ ከርሱ ፡ መልእክትን ፡ ወሰዱ ፡ ወደ ፡ ሲላስና ፡ ወደ ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ፈጥነው ፡ ወደርሱ ፡ ይመጡ ፡ ዘንድ ፡፡ ሔዱም ፡፡ ጳውሎስ ፡ ግን ፡ ሲጠብቃቸው ፡ ባቴና ፡ ሰውነቱ ፡ ተቈጣበት ፡ በራሱ ፡ አገሪቱን ፡ አይትዋልና ፡ ብዙ ፡ ጣዖት ፡ እንደመለከች ፡፡ አይሁድንም ፡ አስተማረ ፡ የተገዙትንም ፡ በጉባኤ ፡ በገቢያም ፡ የሚያገኘውን ፡ ሁልግዜ ፡፡ ከኤጲቆሮስም ፡ ከስቶኣም ፡ ፈሎሶፎች ፡ ይጋደሉት ፡ ነበሩ ፡፡ ሌሎችም ፡ እንዲህ ፡ አሉ ፡፡ ምን ፡ ይሻል ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ዘሪ ፡ ይል ፡ ዘንድ ፡፡ ሌሎችም ፡ አሉ ፡፡ ይህ ፡ ያስተምረናል ፡ ያዲሶች ፡ አማልክትን ፡ ትምህርት ፡፡ ያስተምራቸው ፡ ነበረና ፡ በየሱስ ፡ በትንሣኤውም ፡፡ ወደ ፡ ሸንጎም ፡ አርዮስ ፡ ፈጎስ ፡ ወደ ፡ ሚሉት ፡ ቦታ ፡ ወሰዱት ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡፡ አንችልምን ፡ እናውቅ ፡ ዘንድ ፡ ይህነን ፡ አዲስ ፡ ትምህርት ፡፡ ጆሮዋችን ፡ ባዲስ ፡ ነገር ፡ ትደክማለችና ፡፡ እኛም ፡ እንወዳለን ፡ እናውቅ ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ ምንድር ፡ ነው ፡፡ የአቴና ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ወደርስዋ ፡ የመጡትን ፡ እንግዶች ፡ አይለዩም ፡ ነበሩና ፡ ለሌላ ፡ ነገር ፡ እንግዳ ፡ ነገር ፡ ሊሰሙ ፡ ሊናገሩም ፡ እንጅ ፡፡ ጳውሎስም ፡ ባርዮስ ፡ ፈጎስ ፡ ማኸል ፡ በቆመ ፡ ጊዜ ፡ አለ ፡፡ እላንት ፡ ያቴና ፡ ሰዎች ፡ አይቻችኋለሁ ፡ በስራችሁ ፡ ሁሉ ፡ ያማልክትን ፡ ማምለክ ፡ እንድትበዙ ፡፡ እኔ ፡ ሳልፍ ፡ አይቻለሁና ፡ የምታመልኩበትን ፡ መሠ

ውያ ፡ በርሱ ፡ የተጻፈ ፡ የሚል ፡፡ ላልተወቀ ፡ አምላክ ፡፡
ይህም ፡ የምታመልኩት ፡ የማታውቁትም ፡ ይህነን ፡ እኔ ፡
አስታውቃችኋለሁ ፡፡ ዓለምን ፡ የፈጠረ ፡ አምላክ ፡ በርስዋ ፡
ያለውንም ፡ ሁሉ ፡፡ እርሱ ፡ የሰማይና ፡ የምድር ፡ ጌታ ፡
ነውና ፡ እጅ ፡ በሰራው ፡ መቅደስ ፡ አይኖርምም ፡ የሰው
ም ፡ እጅ ፡ አያገለግለውም ፡፡ ማንንም ፡ አይሻም ፡፡ እር
ሱ ፡ ይሰጣል ፡ አንድ ፡ ለሁሉ ፡ ሕይወትንና ፡ እስትንፋስ
ን ፡፡ እርሱም ፡ ፈጠረ ፡ አሕዛብን ፡ ሁሉ ፡ ካንድ ፡ ሰው ፡ ይ
ኖሩ ፡ ዘንድ ፡ በምድር ፡ ፊት ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡፡ በየጊዜውም ፡
ዘመኑን ፡ ሰራ ፡ ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ስፍራቸውንም ፡ ይኖሩበ
ት ፡ ዘንድ ፡፡ እግዚአብሔርን ፡ እንዲሹት ፡ እንዲፈልጉት
ም ፡ ምናልባት ፡ ያገኙት ፡ እንደሆን ፡፡ ከኛ ፡ ከሁላችን ፡ የ
ራቀ ፡ አይደለምና ፡፡ እኛ ፡ በርሱ ፡ እንኖራለንና ፡ እንንቀሳቀሳ
ለንም ፡ እንገኛለንም ፡፡ ከላንት ፡ ቅኔ ፡ ከሚያደርጉ ፡ ሰዎች ፡
እንዳሉ ፡፡ እኛ ፡ የርሱ ፡ ዘመዶች ፡ ነን ፡፡ እኛስ ፡ ያምላክ ፡
ዘመዶች ፡ ከሆነ ፡ አይገባም ፡ እንል ፡ ዘንድ ፡ ወርቅም ፡ ሆ
ነ ፡ ብርም ፡ ሆነ ፡ የተቀረጸም ፡ ደንጊያ ፡ በሰው ፡ ብልሃት ፡
ባሳቡም ፡፡ ይህ ፡ አምላክን ፡ ይመስላል ፡፡ ያነንም ፡ የድን
ቍርናውን ፡ ወራት ፡ እግዚአብሔር ፡ አሳለፈ ፡፡ አሁን ፡ ግ
ን ፡ ሰውን ፡ ሁሉን ፡ አዘዘ ፡ ንስሓ ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፡ በየቦታ
ቸው ፡፡ ባለሙ ፡ የሚፈርድበትን ፡ ቀን ፡ አቁምዋልና ፡ በቅ
ን ፡ ፍርድ ፡ ባንድ ፡ ሰው ፡ እጅ ፡ በመረጸው ፡፡ ሃይማኖትን
ም ፡ ለሁሉ ፡ ሰጠው ፡ እርሱን ፡ በማስነሣቱ ፡ ከሙታን ፡፡
በሙታንም ፡ መነሣት ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ አኰሴታቸው ፡ አፌ
ዙ ፡፡ እኰሴታቸውም ፡ አሉ ፡፡ ይህነንም ፡ ደግሞ ፡ እንሰማ
ሃለን ፡፡ እንደሁም ፡ ወጣ ፡ ጳውሎስ ፡ ከመኻከላቸው ፡፡
ከሰዎችም ፡ ተከፈለው ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ሆኑ ፡ አመ
ኑም ፡፡ ከርሳቸውም ፡ አንዱ ፡ ዲዮናስዮስ ፡ ነበረ ፡ አንድ ፡
ካርዮስ ፡ ፋጎስ ፡ ፈራጆች ፡፡ አንዲት ፡ ሴትም ፡ ስምዋን ፡ ደ
ማሪስ ፡ የሚሏዋት ፡ ሌሎችም ፡ ከርሳቸው ፡፡ ስለዚህም ፡
ስለ ፡ አርዮስፋጎስ ፡ ዲዮናስዮስ ፡ እጅግ ፡ ሐሰት ፡ ተጻፈ ፡፡
እውነት ፡ ሁኖ ፡ ስለርሱ ፡ የምናውቀው ፡ ይህ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡
በሐዋርያት ፡ ስራ ፡ የተጻፈ ፡ ዲዮናስዮስም ፡ የቆሮንቶስ ፡

ኤጲስቆጶስ ፡ ስለርሱ ፡ የሚል ፡፡ እርሱ ፡ ባቴና ፡ ላለች ፡ ቤ
ተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዓት ፡ እንደደረገ ፡፡

የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ከመቄዶንያ ፡ ተመልሶ ፡
ከጳውሎስ ፡ ጋራ ፡ ባቴና ፡ ተገናኘ ፡፡ እርሱንም ፡ ቶሎ ፡ ላ
ከ ፡ ወደ ፡ ተሳሎንቄ ፡ መጀመርያዪቱንም ፡ መልእክቱን ፡
ጽፎላቸው ፡ በጢሞቴዎስ ፡ እጅ ፡ ሰደደት ፡ ልባቸውን ፡ ለ
ማጽናት ፡ ለማቅናትም ፡ የተሳሎንቄ ፡ ጉባኤ ፡ እጅግ ፡ መ
ከራ ፡ ስለ ፡ ተቀበለች ፡ ካይሁድ ፡፡ ይህም ፡ ሆነ ፡ ከክርስቶ
ስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ በ፶፤ አመት ፡፡

ጢሞቴዎስንም ፡ ከላከው ፡ በኋላ ፡ ጳውሎስ ፡ ለብቻው ፡
አቴናን ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ቆሮንቶስ ፡ አገር ፡ ሔደ ፡፡ ይህችም ፡
ያካያ ፡ ምድር ፡ ታላቅ ፡ ከተማ ፡ ነበረች ፡ እጅግ ፡ ነጋደች ፡
እጅግም ፡ ፈሎሶፎች ፡ የነበሩባት ፡፡ በ፪፤ ወገን ፡ ባሕር ፡ ደ
ረሰባት ፡ ፪፤ ሚና ፡ የሚሉትም ፡ መርከቦች ፡ የሚቀመጡበ
ት ፡ ቦቶች ፡ ነበሩላት ፡ ያንዲ ፡ ስም ፡ ከንኽሬያ ፡ ያንዲም ፡
ሌኻዮን ፡፡ ከእስያም ፡ የመጡ ፡ መርከቦች ፡ በከንኽሬያ ፡
ተቀመጡ ፡ ከኢጣልያ ፡ ግን ፡ የመጡ ፡ በሌኻዩን ፡ ተቀመ
ጡ ፡፡ እንዲሁም ፡ ኑራ ፡ የሮም ፡ መንግሥት ፡ ብልሃት ፡ ሁ
ሉ ፡ ከነግድ ፡ ጋራ ፡ በርስዋ ፡ ተከማቸች ፡፡ ደሮ ፡ ይህች ፡ ከ
ተማ ፡ ከብልሃትና ፡ ከባለጠግነት ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ፡ በመንፈሳ
ዊ ፡ ጨለማ ፡ ተቀመጠች ፡፡ የጣዖት ፡ ማምለክ ፡ ከዝሙ
ት ፡ ጋራ ፡ ሁንዋልና ፡ ያፍሮዲቴ ፡ ማምለክ ፡ ከዚህ ፡ ከዝ
ሙት ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ፡ በዛ ፡ ከሌላ ፡ ስፍራ ፡ ይልቅ ፡፡ በዚህ
ም ፡ ስፍራ ፡ እግዚአብሔር ፡ ታላቅ ፡ ጉባኤ ፡ ይመርጽለት ፡
ነበረ ፡ ጳውሎስንም ፡ ላከ ፡ ይሰበስባቸው ፡ ዘንድ ፡ ወንጌል
ን ፡ በመስበክ ፡፡

ወደ ፡ ቆሮንቶስም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ አንደን ፡ አይሁዳዊ ፡
ሰውን ፡ አገኘ ፡ ስሙ ፡ አኩላስ ፡ ከምሽቱ ፡ ከጵርስኪላ ፡
ጋራ ፡፡ አኩላስም ፡ በጶንጦስ ፡ ተወለደ ፡ በብዙ ፡ አገርም ፡
ይዞር ፡ ነበረ ፡፡ ወደ ፡ ቆሮንቶስም ፡ ሳይደርስ ፡ በሮምያ ፡ ተቀ
መጠ ፡ አቅላውዲዩስ ፡ ቄሣር ፡ አይሁድን ፡ እስኪያዛቸ
ው ፡ ድረስ ፡ ከሮምያ ፡ ይወጡ ፡ ዘንድ ፡፡ ጳውሎስም ፡ ከር
ሳቸው ፡ ካኩላስና ፡ ከጵርስኪላ ፡ ጋራ ፡ ተቀመጠ ፡ ከስራቸ

ው ፡ ወገን ፡ ነበረና ፡ ይሰራም ፡ ነበር ፡ ስራቸውም ፡ የድን
ኳን ፡ ሽማ ፡ ነበረ ። ቅደሜ ፡ ቅደሜም ፡ አስተማረ ፡ በጉባ
ኤ ፡ አይሁድንና ፡ አረማውያንን ። ከመቄደንያም ፡ በመ
ጡ ፡ ጊዜ ፡ ሲላስና ፡ ጢሞቴዎስ ፡ ጳውሎስ ፡ በነገሩ ፡ በረ
ታ ። ለአይሁድም ፡ መሰከረ ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ሆ
ነ ። በተጠናወቱትም ፡ በተሳደቡትም ፡ ጊዜ ፡ ልብሱን ፡ አ
ራገፈ ፡ አላቸውም ። ደማችሁ ፡ በራሳችሁ ፡ ላይ ፡ ይሁን ።
እኔ ፡ ንጹሕ ፡ ነኝ ፡ ከነፍሳችሁ ። ወንጌልን ፡ አስተምርያች
ኋለሁና ፡ እላንት ፡ አልተቀበላችሁትም ፡ ብቻ ፡ ከንጊዴህ ፡
ወዴህ ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ እሔዳለሁ ። ከዚያም ፡ ወጥቶ ፡ ገ
ባ ፡ ወደንድ ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ ስሙ ፡ ዩስጦስ ፡ ለእግዚአብሔ
ር ፡ የሚገዛ ። ቤቱም ፡ ወደ ፡ መስጊድ ፡ ቀረበ ። ክርስጶስ
ም ፡ የመስጊድ ፡ አለቃ ፡ አመነ ፡ በጌታ ፡ ከቤቱ ፡ ሰዎች ፡ ሁ
ሉ ፡ ጋራ ። ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ ከቆሮንቶስ ፡ ወገን ፡ በሰሙ ፡
ጊዜ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትምህርት ፡ አመኑ ፡ ተጠመቁ
ም ። ጌታም ፡ ጳውሎስን ፡ አለ ፡ በሌሊት ፡ በሕልም ። አ
ትፈራ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ተናገር ፡ ዝምም ፡ አትበል ። እኔ ፡ ካን
ተ ፡ ጋራ ፡ ነኝና ፡ ማንም ፡ እጁን ፡ የሚጥልብህ ፡ የለምና ፡
ክፉ ፡ ሊያደርግብህ ። በዚህ ፡ አገር ፡ ታላቅ ፡ ወገን ፡ አለኝ
ና ። የጳውሎስ ፡ ልብም ፡ ከዚህ ፡ ከጌታው ፡ ነገር ፡ የተነሣ ፡
በጸና ፡ ጊዜ ፡ ደስ ፡ ብሎ ፡ የተቀበለውን ፡ ድካምና ፡ መከ
ራ ፡ ያይሁድንም ፡ ጸላትነት ፡ ታገሠ ፡ ወንጌልንም ፡ በመስ
በክ ፡ አልደከመም ። በቆሮንቶስም ፡ የተቀመጠበት ፡ ጊ
ዜ ፡ ሁሉ ፡ ፩ ፡ አመት ፡ ከ፮ ፡ ወር ፡ ነበረ ። ጋልዮንም ፡ አደ
ስ ፡ ሹም ፡ ባካያ ፡ ላይ ፡ በተሾመ ፡ ጊዜ ፡ አይሁድ ፡ ተባብ
ረው ፡ በጳውሎስ ፡ ተነሡ ። ሊያሸንፉበት ፡ ተስፈ ፡ አድር
ገዋልና ። ጳውሎስንም ፡ ወሰዱት ፡ ወደ ፡ መቀመጫው ፡
እንዲህ ፡ ሲሉ ። ይህ ፡ ሰዎችን ፡ ያባብላል ፡ እግዚአብሔ
ርን ፡ ያመልኩ ፡ ዘንድ ፡ ያለ ፡ ሥርዓት ። ጳውሎስም ፡ በ
ወደደ ፡ ጊዜ ፡ አፉን ፡ ይከፍት ፡ ዘንድ ፡ ጋልዮን ፡ አይሁድ
ን ፡ አላቸው ። የመበደልና ፡ የመበደል ፡ ቢሆን ፡ ወይስ ፡ ሌ
ላ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ መልካም ፡ ነበረ ፡ እሰማችሁ ፡ ዘንድ ። በ
ሌላ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ መጣላት ፡ ስለሚሆን ፡ ስለ ፡ ስም ፡ ስለ ፡

ሕግም ፡ እላንት ፡ እወቁ ፡ እላንት ፡ አይሁድ ፡፡ እኔ ፡ በዚ
ህ ፡ ነገር ፡ አልፈርድምና ፡፡ ከዚያ ፡ ወዲያም ፡ አስወጣቸ
ው ፡ ከወንበሩ ፡ ፊት ፡፡ አሬማውያንም ፡ ሁሉ ፡ ሶስቴኔስ
ን ፡ ያዙት ፡ የመስጊድን ፡ አለቃ ፡ በወንበር ፡ ፊትም ፡ መቱ
ት ፡ ባይሁድ ፡ ተቈጥተዋልና ፡ ጋልዮንም ፡ አንዷችን ፡ አላ
ለም ፡፡ ጳውሎስም ፡ እጅግ ፡ ቀን ፡ በቆሮንቶስ ፡ ከተቀመ
ጠ ፡ በኋላ ፡ ወንድሞችን ፡ ተሰናበተና ፡ ሔደ ፡ ከርሱም ፡ ጋ
ራ ፡ ጵርስኪላና ፡ አኪላስ ፡ ራሱን ፡ ተላጭቶ ፡ በክንክሬ
ያ ፡፡ ስለት ፡ ነበረበትና ፡፡ ወደ ፡ ኤፌሶንም ፡ ደረሰ ፡፡ እለ
ዚያውንም ፡ ከዚያ ፡ ተዋቸው ፡፡ እርሱ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ጉባ
ኤ ፡ ገባ ፡ ለአይሁድም ፡ ተናገረ ፡፡ እርሳቸውም ፡ ለመኑት ፡
እጅግ ፡ ቀን ፡ በርሳቸው ፡ ዘንድ ፡ ሊኖር ፡ ልመናቸውን ፡ ግ
ን ፡ አልሰማም ፡፡ ተሰናበታቸውም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ ደገባ
ል ፡ የሚመጣውን ፡ ባል ፡ በየሩሳሌም ፡ አደርግ ፡ ዘንድ ፡፡
ደግሞ ፡ ወደላንት ፡ እመለሳለሁ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃ
ድ ፡፡ ከኤፌሶንም ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ቂሣርያ ፡ መጣ ፡፡ ወደ ፡
የሩሳሌምም ፡ ወጣ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ሰላምን ፡ ሰ
ጠ ፡፡ ወደ ፡ አንጾኪያም ፡ ወረደ ፡፡ ስለዚህም ፡ ወደ ፡ አንጾ
ኪያ ፡ ስለ ፡ መምጣቱ ፡ ይናገራል ፡ በመልእክቱ ፡ ወደ ፡ ገ
ላትያ ፡ ሰዎች ፡ ምዕራፍ ፡ ፪፡ ቍጥር ፡ ፲፩፡፡ ባንጾኪያም ፡ ከ
ጴጥሮስና ፡ ከበርናባስ ፡ ጋራ ፡ ተገናኘ ፡ ለጊዜም ፡ ከርሳቸ
ው ፡ ጋራ ፡ ተጻላ ፡፡ በላይም ፡ ያልነ ፡ ስለ ፡ ጳውሎስና ፡ ስ
ለ ፡ በርናባስ ፡ መጻላት ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡ ለጊዜ ፡ ሲጻሉ ፡
ደህ ፡ በዚህ ፡ ስፍራ ፡ ደግሞ ፡ እውነት ፡ ነው ፡፡ ሰው ፡ ሁ
ሉ ፡ ኃጢአተኛ ፡ ነው ፡ ካንድ ፡ ሰው ፡ በቀር ፡ እርሱም ፡
የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ ኃጢአተኞች ፡ ሁሉ ፡ ቅዱሳን ፡
ሐዋርያቱ ፡ ሳይቀሩ ፡ የሞተ ፡ ክብርና ፡ ምስጋና ፡ ሁሉ ፡ ለ
ዘላለም ፡ ለርሱ ፡ ብቻ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ለሰው ፡ ግን ፡ ነው
ርና ፡ ኃፍረት ፡፡ በዚህ ፡ የሐዋርያት ፡ ትምህርት ፡ ይጸናል ፡፡
ሮሜ ፡ ፫፡ ፳፬፡ ፳፫፡፡ የጴጥሮስና ፡ የበርናባስም ፡ ኃጢአት ፡
እንዲህ ፡ ሆነ ፡፡ በየሩሳሌም ፡ በሐዋርያትና ፡ በቀሳውስት ፡
በጉባኤም ፡ ሲኖደስ ፡ የተሰራ ፡ ዕርቅ ፡ ካይሁድና ፡ ካሕዛብ ፡
በወጡ ፡ ክርስቲያን ፡ መኻከል ፡ ኦሪትን ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ፡

ይህ ፡ ዕርቅ ፡ እጅግ ፡ አልጸናም ፡፡ እለዚያ ፡ ሰዎች ፡ ከፈሪ
ሳውያን ፡ ወገን ፡ በስም ፡ ክርስቲያን ፡ የሆኑ ፡ ቅናት ፡ ተቀበ
ሉ ፡ በልባቸው ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ አሕዛብ ፡ በወንጌል ፡ እንደ ፡
ተከፈፈሉ ፡ እንደርሳቸው ፡ ሳይገዘሩ ፡ ኦሪትንም ፡ ሳይጠ
ብቁ ፡፡ በየሩሳሌምም ፡ የነበሩ ፡ ሐዋርያት ፡ ያይሁድ ፡ ሥር
ዓት ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ እንዲላፈረሱ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ በርሳቸውና ፡
በጳውሎስ ፡ መኻከል ፡ መለየት ፡ ሊያደርጉ ፡ አሕዛብንም ፡
ሊናውጹ ፡ ፈለጉ ፡ እንዲህ ፡ በማለት ፡፡ ባትገዘሩ ፡ ኦሪትን
ም ፡ ባጠብቁ ፡ አትጸድቁም ፡፡ ከርሳቸውም ፡ ትምህርት ፡ አ
ያሌ ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ መጡ ፡ ጳውሎስ ፡ ከጴጥሮስና ፡ ከበ
ርናባስ ፡ ጋራ ፡ ከዚያ ፡ ሲሆን ፡ ከያዕቆብም ፡ ከየሩሳሌም ፡
ተላክነ ፡ ብለው ፡፡ አሁንም ፡ እርሳቸው ፡ ሳይመጡ ፡ ጴጥ
ሮስና ፡ በርናባስ ፡ ካሕዛብ ፡ ከወጡ ፡ ክርስቲያናት ፡ ጋራ ፡
ተገናኙ ፡ ከርሳቸውም ፡ ጋራ ፡ በሉ ፡ ጠጡም ፡ የሃይማኖት
ን ፡ አንድነት ፡ ሲጠብቁ ፡፡ እልያ ፡ ግን ፡ ከመጡ ፡ በኋላ ፡ ጴ
ጥሮስና ፡ በርናባስ ፡ ካሕዛብ ፡ ጋራ ፡ አልተገናኙም ፡ ሲገናኙ
ም ፡ አሕዛብን ፡ እንደ ፡ አይሁድ ፡ ሊኖሩ ፡ ሊያደርጉም ፡ ፈ
ለግዋቸው ፡፡ ጴጥሮስ ፡ እንዲህ ፡ አድርጎ ፡ ጀመረ ፡ በርናባ
ስም ፡ ተከተለው ፡ ሌሎችም ፡ ካይሁድ ፡ ወገን ፡ የነበሩ ፡
ተከተልዋቸው ፡፡ ይህም ፡ ነገር ፡ እጅግ ፡ ክፉ ፡ ሆነ ፡፡ ስለ ፡
ግብዞት ፡ ካይሁድ ፡ ወገን ፡ እርሳቸውን ፡ ደስ ፡ ያሰኝዋቸ
ው ፡ ዘንድ ፡ ካይነተኞች ፡ ክርስቲያናት ፡ ጋራ ፡ ካሕዛብ ፡ ወ
ገን ፡ በሃይማኖት ፡ የሆነችን ፡ አንድነት ፡ አፈርሰዋታልና ፡፡
ስለዚህም ፡ ጳውሎስ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የመላበት ፡ ስለ ፡
ወንጌልም ፡ ሁለግዜ ፡ የቃጠለ ፡ አድልዎ ፡ ገጽ ፡ ሳያደርግ ፡
ጴጥሮስን ፡ ታላቅ ፡ ወንድሙን ፡ በፍቅር ፡ ብርታት ፡ ገሠጸ
ው ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ በሁሉ ፡ ፊት ፡ በሁሉ ፡ ፊትም ፡ በድል
ዋልና ፡፡ አንተ ፡ አይሁዳዊ ፡ ስትሆን ፡ ባሕዛብ ፡ ወግ ፡ ታደር
ጋለህ ፡ ባይሁድና ፡ ባሕዛብ ፡ ማኸልም ፡ አትለይም ፡፡ አሁ
ን ፡ ለምን ፡ የግድ ፡ ትላለህ ፡ አሕዛብ ፡ ወደይሁድ ፡ ሥርዓ
ት ፡ ደገቡ ፡ ዘንድ ፡፡ እለዚህስ ፡ ፈሪሳውያን ፡ እውነት ፡ ቢ
ሉ ፡ ጽድቅም ፡ ከሃይማኖት ፡ ብቻ ፡ ባይመጣ ፡ ከኦሪት ፡ እ
ንጅ ፡ እኛ ፡ እነሆ ፡ ከፍጥረታችን ፡ አይሁድ ፡ ሁነን ፡ ጻድ

ቃን ፡ በሆነ ፡ ኃጥኣንም ፡ አይደለም ፡ አሕዛብ ፡ አይደለነም
ና ፡ ከቶም ፡ አንድነት ፡ ባይሆን ፡ ነበር ፡ በኛና ፡ ባሕዛብ ፡
መኻከል ፡ አንተ ፡ በፊት ፡ አንድነት ፡ እንደደረግህ ፡ እናደ
ርገውም ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ አስተማርህ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ እኛ ፡
እናውቃለን ፡ ሰው ፡ ኦሪትን ፡ በመስራት ፡ እንዲጸደቅ ፡ በ
የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሃይማኖት ፡ እንጅ ፡፡ ስለዚህም ፡ እኛ ፡
እናምናለን ፡ በየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡
እንጸደቅ ፡ ዘንድ ፡ ኦሪትንም ፡ በመስራት ፡ አይደለም ፡፡ ኦሪት
ን ፡ በመስራት ፡ ከቶ ፡ ሥጋ ፡ አይጸደቅምና ፡፡ ሃይማኖት ፡ ግ
ን ፡ ባያጸድቅ ፡ ኦሪትንም ፡ አለመጠበቃችን ፡ ኃጢአት ፡ ቢ
ቈጠርብን ፡ ክርስቶስም ፡ የኃጢአት ፡ አገልጋይ ፡ በሆነ ፡፡
ይህ ፡ አይሁን ፡፡ ያፈረስሁትን ፡ ተመልሼ ፡ የምሰራው ፡ ከ
ሆንሁ ፡ በራሴ ፡ መሰከርሁ ፡ ትእዛዝን ፡ በማፍረሴ ፡፡ ገላ
ትያን ፡ ፪፤ ፲፩፤ እስከ ፡ ፲፰፤ ድረስ ፡፡ ጴጥሮስም ፡ ይህነን ፡ የ
ጳውሎስን ፡ ነገር ፡ ሰምቶ ፡ አዘነ ፡ ወደ ፡ ሃይማኖቱ ፡ ትምህ
ርትም ፡ ተመለሰ ፡፡ አንድነቱም ፡ የበርናባስም ፡ አንድነት ፡
ከጳውሎስ ፡ ጋራ ፡ ጸናች ፡፡ እንጊዴህ ፡ ወዴህም ፡ ሁለግዜ ፡
እንደ ፡ ወንድሞች ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡ ተገናኙ ፡፡ እለዚያ ፡
አሰተኞች ፡ መምህራን ፡ ግን ፡ እለዚያ ፡ ፈሪሰውያን ፡ በስ
ም ፡ ብቻ ፡ ክርስቲያን ፡ የተባሉ ፡ አልደከሙም ፡ ወንጌል
ን ፡ ሃይማኖትንም ፡ በመከልከል ፡ በጳውሎስም ፡ እጅግ ፡
ድካም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ መለየት ፡ ሰሩ ፡፡ የእግዚ
አብሔር ፡ መንፈስ ፡ ግን ፡ የርሱን ፡ ስራ ፡ ጠበቀ ፡፡ በቅዱሳ
ን ፡ ሐዋርያት ፡ አፍም ፡ ገሠጻቸው ፡ አለዚያን ፡ አሰተኞች ፡
መምህራንን ፡፡ በመጻሕፍታቸውም ፡ የሃይማኖትን ፡ ምሳ
ሌ ፡ ሰጠነ ፡ ለኛ ፡ ለምእምናንም ፡ ሁሉ ፡ ለዘላለም ፡ እው
ነትና ፡ ሐሰት ፡ ሁሉ ፡ የሚገለጽበት ፡፡ የመጻሕፍትም ፡
ትምርት ፡ ሁሉ ፡ ባንድ ፡ ቃል ፡ ይናራል ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ ክ
ርስቶስ ፡ የሕግ ፡ ፍጻሜ ፡ ነው ፡፡ በርሱም ፡ የሚያም
ን ፡ ሁሉ ፡ ይጸደቃል ፡፡ ሮሜ ፡ ፲፤ ፬፡፡

ጳውሎስም ፡ አያሌ ፡ ቀን ፡ ባንጾኪያ ፡ ከተቀመጠ ፡ በኋ
ላ ፡ ወደ ፡ ኤፌሶን ፡ ይመለስ ፡ ዘንድ ፡ ወጣ ፡፡ ተሻገረም ፡
ወደ ፡ ገላትያና ፡ ወደ ፡ ፍርጊያም ፡ መጣ ፡፡ በገላትያም ፡ አ

ወደ ፡ ገላትያና ፡ ወደ ፡ ፍርጊያም ፡ መጣ ፡፡ በገላትያም ፡ አ
ስቀድሞ ፡ ወንጌልን ፡ አስተማረ ፡፡ አሁንም ፡ ደቀ ፡ መዛ
ሙርትን ፡ ሁሉ ፡ አጸና ፡፡ እርሱም ፡ ከዚያ ፡ ሲዞር ፡ አን
ድ ፡ አይሁዳዊ ፡ ስሙን ፡ አጵሎስ ፡ የሚሉት ፡ አገሩም ፡
እስክንድርያ ፡ ተናጋሪ ፡ ሰውም ፡ በእስክንድርያም ፡ የተ
ማረ ፡፡ እርሱ ፡ ወደ ፡ ኤፌሶን ፡ መጣ ፡፡ መጻፉ ፡ ቅዱስን
ም ፡ ለመተርጐም ፡ ብርቱ ፡ ነበረ ፡፡ በእግዚአብሔርም ፡ መ
ንገድ ፡ ተማረ ፡፡ በሚቃጠልም ፡ መንፈስ ፡ አስተማረ ፡ የእ
ግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡፡ ደግ ፡ የዮሐንስን ፡ ጥምቀት ፡ ብቻ ፡
አወቀ ፡፡ ይህም ፡ በጉባኤ ፡ በስብከቱ ፡ ሲገለጽ ፡ አኩላስ
ና ፡ ጵርስኪላም ፡ በሰሙት ፡ ጊዜ ፡ ወሰዱት ፡ አስታወቁት
ም ፡ የጌታን ፡ መንገድ ፡ የተሻለ ፡ ማስታወቅ ፡፡ እርሱም ፡
ወደ ፡ አካያ ፡ ማለፉ ፡ በወደደ ፡ ጊዜ ፡ ወንድሞች ፡ ስለር
ሱ ፡ጻፉ ፡ ወደ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ይቀበሉት ፡ ዘንድ ፡፡ ወ
ደርሳቸውም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ጠቀመ ፡ በጸጋ ፡ ላመ
ኑ ፡ ሰዎች ፡፡ ዘወትር ፡ አይሁድን ፡ ይገሥጽ ፡ ነበረና ፡ ጽኑ ፡
ትግሣጽ ፡ በክርክር ፡፡ ከመጽሐፉ ፡ ቅዱስ ፡ ኢየገለጠ ፡ የሱ
ስ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡፡

አጵሎስም ፡ በቆሮንቶስ ፡ ሳለ ፡ ጳውሎስ ፡ የዚያን ፡ አገ
ር ፡ ላይ ፡ ላዩን ፡ ዞረ ፡ ወደ ፡ ኤፌሶንም ፡ መጣ ፡፡ ከዚያ
ም ፡ ደቀ ፡ መዛሙርትን ፡ አገኘ ፡ አላቸውም ፡፡ መንፈስ ፡
ቅዱስን ፡ ተቀበላችሁን ፡ ባመናችሁ ፡ ጊዜ ፡፡ እርሳቸው ፡ ግ
ን ፡ አሉት ፡፡ መቀበልስ ፡ ይቀርና ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንደ
ለ ፡ ስንኳ ፡ ከቶ ፡ አልሰማነም ፡፡ እንደርሳቸውም ፡ ያሉት
ን ፡ ሰዎች ፡ ብዙ ፡ አየነ ፡ እኛም ፡ ደግሞ ፡ በዘመናችን ፡፡ በ
ውኑ ፡ የተጠመቁ ፡ በዙ ፡ አሉ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ግን ፡ የ
ተጠመቁ ፡ ወዴት ፡ ይገኛሉ ፡፡ ስለ ፡ ጌታችን ፡ መቀባት ፡
በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እጅግ ፡ ይከራከራሉ ፡ በከንቱ ፡፡ ነገር ፡
ግን ፡ ስለ ፡ ራሳቸው ፡ መቀባት ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
አያስቡም ፡፡ ባካሔዳቸውም ፡ ይገልጻሉ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱ
ስ ፡ እንደሌለባቸው ፡ መንፈስ ፡ ርኩስ ፡ እንጂ ፡፡ ጳውሎ
ስም ፡ ምንድር ፡ ይላል ፡፡ የሚችል ፡ የለም ፡ ይል ፡ ዘንድ ፡
የሱስ ፡ ጌታዬ ፡ ነው ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንጂ ፡፡ ፩፡ ቆ

ሮንቶስ ፡ ፲፪፡ ፫። ክርስቲያንም ፡ ማለት ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የተቀባ ፡ ሰው ፡ ነው ። በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ያልተቀባ ፡ ክርስቲያን ፡ ቢባል ፡ እርሱ ፡ በውነት ፡ ክርስቲያን ፡ አይደለም ።

ጳውሎስም ፡ የኤፌሶንን ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ አላቸው ። በምን ፡ ተጠመቃችሁ ። እርሳቸውም ፡ አሉ ። በዮሐንስ ፡ ጥምቀት ። ጳውሎስም ፡ አለ ። ዮሐንስስ ፡ አጠመቀ ፡ በንስሓ ፡ ጥምቀት ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ለሕዝብ ። ያምኑ ፡ ዘንድ ፡ ከርሱ ፡ በኋላ ፡ በሚመጣው ። ያውም ፡ በክርስቶስ ፡ የሱስ ። ይህንንም ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ተጠመቁ ፡ በጌታ ፡ በየሱስ ፡ ስም ። ጳውሎስም ፡ እጁን ፡ በጸሎት ፡ በጫነባቸው ፡ ጊዜ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ወረደላቸው ። በልዩ ፡ ቋንቋም ፡ ተናገሩ ። ትንቢትንም ፡ ተናገሩ ። ሰዎችም ፡ ፲፪፡ ያህል ፡ ነበሩ ።

ጳውሎስም ፡ ወደ ፡ አይሁድ ፡ መስጊድ ፡ ገባ ፡ ከዚያም ፡ በግልጥ ፡ ፫፡ ወር ፡ ሰበከላቸው ፡ ሲያስተምራቸው ፡ በእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ። ሰዎች ፡ ግን ፡ ልባቸውን ፡ ባጸኑ ፡ ጊዜ ፡ አንቢንም ፡ ባሉ ፡ ጊዜ ፡ ለማመን ፡ ይህንንም ፡ መንገድ ፡ በሰደቡ ፡ ጊዜ ፡ በጉባኤ ፡ ፊት ፡ ከርሳቸው ፡ ራቀ ። ምእምናንም ፡ ከርሳቸው ፡ ለየ ። ዕለት ፡ ዕለትም ፡ ተናገረ ፡ በትምህርት ፡ ቤት ፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ ጢራኖስ ፡ የሚሉት ፡ ገንዘብ ፡ በነበረ ። ይህም ፡ ሆነ ፡ ፪፡ አመት ፡ በታናሽ ፡ እስያ ፡ የኖሩት ፡ ሁሉ ፡ እስኪሰሙ ፡ ድረስ ፡ የጌታን ፡ ነገር ፡ እርሳቸውም ፡ አይሁድ ፡ አረማውያንም ። እግዚአብሔርም ፡ ነገረን ፡ ጳውሎስ ፡ ያስተማረበቱን ፡ አጸናው ፡ ታላቅ ፡ ኃይልም ፡ አደረገ ፡ በጳውሎስ ፡ እጅ ። ከገላው ፡ እስኪ ወስደ ፡ ድረስ ፡ መጠምጠምያውን ፡ መሐረምያውንም ፡ በድውያንም ፡ ላይ ፡ ጫኑበት ፡ ከርሳቸውም ፡ ደዌያቸው ፡ ወጣ ፡ ክፉ ፡ አጋንንትም ፡ ወጡ ። ካይሁድም ፡ ሰዎች ፡ አስማተኞች ፡ መጡ ፡ የሚዞሩ ። እርሳቸውም ፡ የክርስቶስ ፡ የስሙን ፡ ኃይል ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ በማስማታቸው ፡ ፈተኑት ፡ ባንድ ፡ ክፉ ፡ መንፈስ ፡ ባደረበት ፡ ሰው ። የጌታን ፡ ስም ፡ ጸሩበት ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ። እናምልሃለን ፡ በየሱስ ፡

ጳውሎስ ፡ በሚያስተምርበት ፡፡ እለዚህም ፡ አስማተኞች ፡
፯፥ ወንድሞች ፡ ነበሩ ፡ የስቄዋ ፡ የካህናት ፡ አለቃ ፡ ልጆ
ች ፡፡ ክፉም ፡ መንፈስ ፡ መለሰ ፡ አላቸውም ፡፡ የሱስንስ ፡
አውቀዋለሁ ፡ ጳውሎስንም ፡ ባርያውን ፡ ተረድቸዋለሁ ፡፡
ነገር ፡ ግን ፡ እላንተ ፡ እለማን ፡ ናችሁ ፡፡ ገንዘቤ ፡ አይደላ
ችሁምን ፡፡ ያሰውም ፡ ክፉ ፡ መንፈስ ፡ ያደረበት ፡ ተነሣባ
ቸው ፡ ገዛቸውም ፡ አሸነፋቸውም ፡ ከዚያ ፡ ቤት ፡ እስኪ
ሸሹ ፡ ድረስ ፡ ራቁታቸው ፡ ተቋስለው ፡፡ ይህም ፡ ነገር ፡ በተ
ሰማ ፡ ጊዜ ፡ የጌታው ፡ ስም ፡ እጅግ ፡ ተመሰገነ ፡፡ ካመኑት
ም ፡ እጅግ ፡ ሰዎች ፡ መጡ ፡ ኃጢአታቸውንም ፡ ያደረጉትን ፡
ተናገሩ ፡፡ እጅግም ፡ አስማት ፡ ያደረጉ ፡ ያስማትን ፡ መ
ጻፋቸውን ፡ ክታባቸውንም ፡ አመጡ ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ፊ
ትም ፡ አቃጠሉት ፡ ዋጋውም ፡ ፶፻፥ ብር ፡፡ ያስማት ፡ መ
ጻፉ ፡ ጣዖት ፡ ነውና ፡ በርሱም ፡ የሚያምን ፡ አረማዊ ፡ ነ
ው ፡፡ በእግዚአብሔርም ፡ ለሚያምን ፡ አይገባም ፡ በክ
ታብ ፡ በተጻፈው ፡ ወይስ ፡ በሌላ ፡ አስማት ፡ ያምን ፡
ዘንድ ፡፡

ይህ ፡ ነገርም ፡ ከሆነ ፡ በኋላ ፡ ጳውሎስ ፡ አሰበ ፡ በልቡ ፡
ወደ ፡ መቄደኒያ ፡ ወደ ፡ አካያም ፡ ያልፍ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ የ
ሩሳሌምም ፡ ይሔድ ፡ ዘንድ ፡ እንዴህ ፡ ሲል ፡፡ ወደዚያም ፡
ከደረስሁ ፡ በኋላ ፡ ሮምያን ፡ እይ ፡ ዘንድ ፡ ይገባኛል ፡ ደግ
ሞ ፡፡ ወደ ያም ፡ ሳይሔድ ፡ መጀመርያዪቱን ፡ መልእክት ፡
ጻፈ ፡ ለቆሮንቶስ ፡ ጉባኤ ፡ በጢሞቴዎስ ፡ እጅም ፡ ሰደደው ፡፡
ይህም ፡ ሆነ ፡ በፋሲካ ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ በ፶፱፥
አመት ፡፡ ከዚህም ፡ ወደያ ፡ ሁከት ፡ ሆነ ፡ በኤፌሶን ፡ በጳ
ውሎስ ፡ መክንያት ፡፡ በኤፌሶን ፡ ታላቅ ፡ መቅደስ ፡ ነበረ ፡
አርጤምስ ፡ ለሚልዋት ፡ ጣዖት ፡ የተሰራ ፡ እርሱም ፡ እ
ጅግ ፡ ድንቅ ፡ ስራ ፡ ነበር ፡ በብልሃት ፡ ሁሉ ፡ የተሰራ ፡፡ ይህ
ንንም ፡ መቅደስ ፡ ለማየት ፡ በርሱም ፡ አርጤምስን ፡ ለማ
ምለክ ፡ ከታናሽ ፡ እስያ ፡ ሁሉ ፡ ከሌላ ፡ ስፍራም ፡ ሰዎች ፡ መ
ጡ ፡፡ በዚህም ፡ መክንያት ፡ ኤፌሶን ፡ እንደ ፡ የሩሳሌም ፡ ስለ
ክርስቲያን ፡ እንደ ፡ መካም ፡ ስለ ፡ እስላሞች ፡ እንደርሳቸ
ው ፡ ላረማውያን ፡ ሆነች ፡፡ ብዙ ፡ ብልሃተኞችም ፡ ስራተኞች ፡

ከዚያ ፡ ነበሩ ፡ በብሩር ፡ የሰሩ ፡፡ እንዲሁም ፡ ከርሳቸው ፡ ዴሜ
ጥሮስ ፡ የሚሉት ፡ የአርጤምስ ፡ መቅደስ ፡ ምሳሎችን ፡ ሰራ ፡
በብሩር ፡ ለእንግዶችም ፡ ሼጠው ፡ በዚህም ፡ ስራ ፡ እጅግ ፡ ይ
ረባ ፡ ነበረ ፡፡ ምእምናን ፡ ግን ፡ በበዙ ፡ ጊዜ ፡ ሰው ፡ ታጣ ፡ የ
መቅደስን ፡ ምሳሌ ፡ የሚገዛ ፡ የስራተኞችም ፡ ጥቅም ፡ ሔደ ፡፡
ስለዚህም ፡ ድሜጥሮስ ፡ ሰበሰበ ፡ ይህነን ፡ ስራ ፡ የሚሰሩን ፡
ሁሉ ፡፡ አላቸውም ፡፡ እላንት ፡ ሰዎች ፡ ታውቃላችሁ ፡ ጥቅ
ማችን ፡ ከዚህ ፡ ስራ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡፡ እይታችኋልም ፡ ሰም
ታችኋልም ፡ በኤፌሶን ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ በታናሽ ፡ እስያ ፡
ሁሉ ፡ እንጂ ፡ ይህ ፡ ጳውሎስ ፡ እጅግ ፡ ሰዎች ፡ መልስዋል ፡
እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ እሌህ ፡ በጅ ፡ የተሰሩ ፡ አማልክት ፡ አይ
ደሉም ፡፡ ይህም ፡ ብቻ ፡ የሚያስጨንቅን ፡ አይደለም ፡ የ
ሚያሳዝነንም ፡፡ የታላቂቱ ፡ ያርጤምስ ፡ አማልክት ፡ መቅ
ደስ ፡ ምናምን ፡ ይሆናል ፡ እንጂ ፡፡ ደግሞም ፡ ይቀራል ፡ ታ
ላቅነትዋ ፡ እስያ ፡ ሁሉ ፡ ዓለምም ፡ የሚያመልክዋት ፡፡ ይ
ህነንም ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ቍጣ ፡ መላባቸው ፡ ጮሁም ፡ እን
ዲህ ፡ ሲሉ ፡፡ ታላቅ ፡ ናት ፡ የኤፌሶን ፡ አርጤምስ ፡፡ አገር
ም ፡ ሁሉ ፡ ታወከ ፡ ወደ ፡ ሸንጎም ፡ ፈጥነው ፡ ሁሉ ፡ መ
ጡ ፡፡ ነጠቁም ፡ ጋይዮስንና ፡ አርስጠርኮስን ፡ የመቄዶንያ ፡
ሰዎች ፡ የጳውሎስን ፡ ባልንጀሮች ፡፡ ጳውሎስ ፡ ግን ፡ ወደ ፡
ሕዝብ ፡ ይገባ ፡ ዘንድ ፡ በወደደ ፡ ጊዜ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡
አልተዉትም ፡፡ ሌሎችም ፡ ከታናሽ ፡ እስያ ፡ አለቆች ፡ ወዳ
ጆቹ ፡ ሲለምኑት ፡ ላኩበት ፡ ራሱን ፡ እንዳይሰጥ ፡ ወደ ፡
ሸንጎ ፡፡ ካሕዛብም ፡ አያሌ ፡ እንዲህ ፡ ጮሁ ፡ ሌሎችም ፡ በ
ሌላ ፡ ነገር ፡፡ ጉባኤውም ፡ ደንግጠው ፡ ነበሩ ፡ ሌሎችም ፡ አ
ያውቁም ፡ ነበሩ ፡ ስለ ፡ ምን ፡ ተሰበሰቡ ፡፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ አ
ሌክሰንድሮስን ፡ አይሁዳዊ ፡ እንጥረኛውን ፡ ጎተቱት ፡፡ እር
ሱም ፡ የጳውሎስ ፡ ጸላት ፡ ሁኖ ፡ በጳውሎስ ፡ ላይ ፡ ክፉ ፡
ሊናገር ፡ ብሎ ፡ በጁ ፡ ጠቀሰ ፡፡ ሕዝብ ፡ ግን ፡ ባወቀ ፡ ጊዜ ፡
እርሱ ፡ አይሁዳዊ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጬኸታቸውን ፡ አበዙ ፡ ፪፡
ሰዓት ፡ የሚሆን ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡፡ ታላቅ ፡ ናት ፡ አርጤም
ስ ፡ ኤፌሶኒቱ ፡፡ ያገርም ፡ ጸፊ ፡ ሰዎችን ፡ ዝም ፡ አሰኛቸ
ው ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ እላንት ፡ የኤፌሶን ፡ ሰዎች ፡ ማነው ፡

የማያውቅ ፡ ሰው ፡ የኤፌሶን ፡ ሰዎች ፡ አገር ፡ እንድታመ
ልክ ፡ የታላቂቱን ፡ ያርጤምስን ፡ ማምለክ ፡ ጣዖትዋንም ።
ይህንንም ፡ ማስተው ፡ አይቻልም ። ዝምም ፡ ብትሉ ፡ ይሻ
ላል ። ምንምን ፡ አታደርጉ ፡ በሁከት ። እሌህን ፡ ሰዎች ፡
አምጥታችኋልና ፡ የመቅደሳችሁን ፡ እቃ ፡ ያልሰረቁ ፡ አም
ላካችሁንም ፡ ያልሰደቡ ። ዲሜጥሮስና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ያሉ
ት ፡ ሰራተኞች ፡ ግን ፡ በማንም ፡ ላይ ፡ ነገር ፡ እንደላቸው ፡
እነሆ ፡ ፈራጆች ፡ በገቢያ ፡ አለቆችም ። እርሱ ፡ በርሳቸው ፡
ይከራከሩ ። ሌላ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ትሹ ፡ እንደ ፡ ሆን ፡ በጉባኤ ፡
ሕግ ፡ ይሰራ ። ስለዚህም ፡ ነገር ፡ ጸጥታ ፡ ይገባናል ። ሁከት ፡
ቢነሣ ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ መክንያት ፡ አልተገኘምና ፡ የሚገባን ፡
እንመልስበት ፡ ዘንድ ፡ በዚህ ፡ ክርክር ። ይህንንም ፡ ብሎ ፡
ሕዝብን ፡ ሰደደ ።

ሁከትም ፡ ጸጥ ፡ ካለ ፡ በኋላ ፡ ጳውሎስ ፡ ደቀ ፡ መዛሙር
ትን ፡ ጾራ ፡ ባረካቸውም ፡ ተሰናበታቸውም ፡ ወደ ፡ መቄዶ
ኒያም ፡ ይሔድ ፡ ዘንድ ፡ ወጣ ። በስፍራም ፡ ሁሉ ፡ አብያ
ተ ፡ ክርስቲያናትን ፡ አጸና ፡ ወንጌልንም ፡ አስተማረ ። ወ
ደ ፡ ያላድስም ፡ መጣ ፡ በርስዋም ፡ ተቀመጠ ፡ ፫ ፡ ወር ። በ
የሩሳሌምም ፡ ላሉት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ረዴትን ፡ ለቀ
መ ። አያሌንም ፡ መልእክቶችን ፡ ጻፈ ። ክፉም ፡ ምክር ፡
በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ካይሁድ ፡ አስቦ ፡ ሳለ ፡ ወደ ፡ ሶርያ ፡ ለመሔ
ድ ፡ ከቆሮንቶስ ፡ ወጥቶ ፡ በባሕር ፡ አልሔደም ፡ በምድር ፡
እንጂ ፡ በመቄዶኒያ ። ከርሱም ፡ ጋራ ፡ ነበሩ ፡ ሶሲጳጤር ፡
ከቤሬያ ። ከተሳሎንቄ ፡ ወገንም ፡ አርስጠርኮስ ፡ ሴኩንዱ
ስም ። ከደርቤ ፡ ወገንም ፡ ጋይዮስ ፡ ጢሞቴዎስም ፡ ከታና
ሽ ፡ እስያ ፡ ወገንም ፡ ጢኪቆስ ፡ ጥረፊሞስም ። እሌህም ፡
ከጳውሎስና ፡ ከሉቃስ ፡ በፊት ፡ አልፈው ፡ ወደ ፡ ጥራዎስ ፡
መጡ ። ጳውሎስ ፡ ግን ፡ ከሉቃስ ፡ ጋራ ፡ በፊልጲስ ፡ የፋሲ
ካውን ፡ ባል ፡ አደረገ ። ከዚያም ፡ በባሕር ፡ ሰሮ ፡ ወደ ፡ ጥራ
ዎስ ፡ ሔደ ፡ ከለዚያም ፡ ጋራ ፡ ተገናኘ ። ከዚያም ፡ ሰረሩ ፡
ወደ ፡ አሶስ ፡ ወደ ፡ ሚጢሊኒም ፡ ወደ ፡ ኪዮስም ፡ ወደ ፡ ሳ
ሞስም ፡ ወደ ፡ ጥሮጊልዮንም ፡ ወደ ፡ መሊጥያም ፡ ለኤፌ
ሶን ፡ የምትቀርብ ። የኤፌሶንም ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡

ቀሳውስት : አስመጣ : ወደ : ባሕር : ደርቻ : አላቸውም ::
እላንት : ታውቃላችሁ : ወደ : ታናሽ : እስያ : ከገባሁበት :
ከመጀመርያ : ቀን : ጀምሬ : እንዴት : ነበርሁ : ከላንት :
ጋራ :: እግዚአብሔርን : አገለግል : ነበርሁ : በፍጹም : ል
ብ : በትሕትናም :: በብዙ : እንብም : በደረሰብኝም : መከ
ራ : ባይሁድ : ክፋት :: ከሚሰማማችሁም : ነገር : አንዳች
ን : አልከለከልኋችሁም : እናገረችሁ : ነበርሁ : እንጅ : አ
ስተምራችሁም : ነበርሁ : በግልጥ : በጉባኤም : በቤትም ::
ስመሰክር : ላይሁድ : ላረማውያንም : ወደ : እግዚአብሔ
ር : በመመለስ : በጌታችንም : በየሱስ : ክርስቶስ : ሃይማ
ኖት :: አሁንም : እኔ : በመንፈስ : ታሥርያለሁ : ወደ : የሩ
ሳሌም : እሔድ : ዘንድ : ሳላውቅ : ምን : የሚሆንብኝን :
በርስዋ :: መንፈስ : ቅዱስ : ግን : ባገር : ሁሉ : ይመሰክራ
ል : እንዴህ : ሲል :: እሥራትና : መከራ : ይቆይሃል : ከዚ
ያ :: ነገር : ግን : ይህነን : መክን ያት : አድርጌ : አልቈጥር
ም :: ሕይወቴም : እንኳ : በኔ : ዘንድ : የከበረች : አይደለ
ችም : ሩጫዬን : እስክፈጽም : ድረስ : በደስታ : መልእክ
ቴንም : ከጌታ : የየሱስ : የተቀበልኋትን : እመሰክር : ዘን
ድ : በእግዚአብሔር : ጸጋ : ወንጌልን :: አሁንም : እነሆ :
አውቃለሁ : ሁላችሁ : ደግሞ : ፊቴን : እንዳታዩ :: እላን
ት : የዞርኋችሁ : ሳስተምራችሁ : የእግዚአብሔርን : መን
ግሥት :: ስለዚህም : እኔ : እመስክርላችኋለሁ : በዚህ : ቀ
ን : ንጹሕ : እንደ : ሆንሁ : ከሁላችሁ : ደም :: የእግዚአብ
ሔርን : ምክር : ሁሉ : ከማስተማር : አልተከለከልሁም
ና :: አሁንም : ተጠንቀቁ : ለራሳችሁ : ለመንጋውም : መን
ፈስ : ቅዱስ : በርስዋ : ላይ : የሾማችሁ : ኤጲስቆጶሳት : አ
ድርጎ : የእግዚአብሔርን : ቤተ : ክርስቲያን : ትጠብቁ : ዘ
ንድ : በደሙ : የዋጀትን :: ይህነን : እኔ : አውቃለሁና : ከ
ሔድሁ : በኋላ : የሚነጥቁ : ተኵሎች : እንዲገቡባችሁ :
ለመንጎች : የማያዝኑ :: ከላንትም : የሚነሡ : ሰዎች : አ
ሉ : ጠማማ : ነገር : የሚነገሩ : ደቀ : መዛሙርትን : ወደ :
ኋላቸው : ይስቡ : ዘንድ :: ስለዚህም : ንቁ : አስባችሁ : እ
ንደልተውሁ : ፫፤ አመት : ሌትና : ቀን : እላንትን : ከማስ

ተማር ፡ በንብ ፡ ከላንት ፡ ኢያንደንደችሁን ፡፡ አሁንም ፡ ወን
ድሞቼ ፡ ሆይ ፡ አደራ ፡ ሰጥቻችኋለሁ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለ
ጸጋውም ፡ ነገር ፡ የሚችል ፡ ይሰራችሁ ፡ ዘንድ ፡ ርስትንም ፡
ይሰጣችሁ ፡ ዘንድ ፡ ከሚቀደሱ ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ፡፡ ወርቅ ፡ ግ
ን ፡ ብሩርም ፡ ሆነ ፡ ልብስም ፡ ሆነ ፡ ከማንም ፡ አልሻሁ
ም ፡፡ እላንትም ፡ ታውቃላችሁ ፡ እሌህ ፡ እጆቼ ፡ ለምሻ
ው ፡ ነገር ፡ ከኔ ፡ ጋራ ፡ ላሉትም ፡ እንደገለገሉ ፡፡ ሁሉንም ፡
ገለጥሁላችሁ ፡ እንደህ ፡ እንደገባችሁ ፡ ትደክሙ ፡ ዘንድ ፡
ለድኆችም ፡ ትሰጡ ፡ ዘንድ ፡፡ አስባችሁ ፡ የጌታን ፡ የየሱ
ስን ፡ ቃል ፡ እርሱ ፡ ብልዋልና ፡፡ የሚሰጥ ፡ ይመሰገናል ፡ ከ
ሚወስድ ፡ ይልቅ ፡፡

ጳውሎስም ፡ ይህነን ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ በጕልበቱ ፡ ተንበረከከ ፡
ከሁሉ ፡ ጋራ ፡ ጸለየም ፡፡ ሁላቸውም ፡ አለቀሱ ፡ እጅግ ፡
በጳውሎስም ፡ አንገት ፡ ላይ ፡ ወደቁ ፡ ሳሙትም ፡፡ ይልቁን
ም ፡ አዝነው ፡ ባለው ፡ ነገር ፡ እንጊደህ ፡ ደግሞ ፡ ፊቴን ፡ አ
ታዩም ፡፡ እስከ ፡ መርከብም ፡ ድረስ ፡ ሸኙት ፡፡

ከዚያም ፡ ሰረረ ፡ ወደ ፡ ቆስም ፡ መጡ ፡፡ ወደ ፡ ርደስም ፡
ወደ ፡ ጳጥሪ.ም ፡፡ ቆጵርስንም ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ተው ፡ ወደ ፡ ጢ
ሮስም ፡ መጡ ፡፡ ከዚያም ፡ ተቀመጡ ፡ ከደቀ ፡ መዛሙር
ት ፡ ጋራ ፡ ፯፡ ቀን ፡፡ እርሳቸውም ፡ በትንቢት ፡ መንፈስ ፡ ለ
ጳውሎስ ፡ የሚሆነውን ፡ ነገር ፡ በየሩሳሌም ፡ አውቀዋልና ፡
ለመኑት ፡ ወደዚያ ፡ እንደይወጣ ፡፡ ከዚያም ፡ በጸሎት ፡
ከተሰናበቱ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ጵቶልማይስ ፡ ደረሱ ፡ ፩፡ ቀንም ፡
ተቀመጡ ፡ በወንድሞች ፡ ዘንድ ፡፡ በነጋውም ፡ ወረደ ፡ ወ
ደ ፡ ቂሣርያ ፡፡ ወደ ፡ ወንጌላዊም ፡ ወደ ፡ ፊልጶስ ፡ ቤት ፡ ገ
ቡ ፡፡ እርሱም ፡ ከ፯፡ ዲያቆናት ፡ አንድ ፡ የነበረ ፡፡ ፬፡ ሴቶ
ች ፡ ልጆች ፡ ነበሩለት ፡ እርሳቸውም ፡ ደናግል ፡ ትንቢትን ፡
የተናገሩ ፡፡ ከዚያም ፡ በተቀመጡ ፡ ጊዜ ፡ አጋቦስ ፡ ነቢይ ፡
መጣላቸው ፡ ከይሁዳ ፡ አገር ፡ የጳውሎስን ፡ ዝናር ፡ ወሰ
ደ ፡ ታጠቀባትም ፡ እጁንና ፡ እግሩን ፡ አለም ፡፡ እንደህ ፡ ይ
ላል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡፡ የዚህን ፡ ዝናር ፡ ባለቤት ፡ ሰው ፡
እንደህ ፡ ያሥሩታል ፡ አይሁድ ፡ በየሩሳሌም ፡፡ ላሕዛብም ፡
እጅ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጡታል ፡፡ ከጳውሎስም ፡ ጋራ ፡ የነበሩ ፡

ይህነን ፡ ነገር ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ ለመኑት ፡ ወደ ፡ የሩሳሌም ፡ እንደይወጣ ። ደሮ ፡ ጳውሎስ ፡ ፈቃዱ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ የበረታ ፡ መለሰላቸው ፡ አላቸውም ። ለምን ፡ ታለቅሳላችሁ ፡ ልቤንም ፡ ትሰብሩታላችሁ ። እኔ ፡ የጨከንሁ ፡ ነኝና ፡ ለሡራት ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ለሞትም ፡ እንጂ ፡ በየሩሳሌም ፡ ስለ ፡ ጌታ ፡ ስለ ፡ የሱስ ፡ ስም ። ባይታዘዛቸውም ፡ ዝማሉ ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ። የጌታ ፡ ፈቃድ ፡ ይሁን ።

ወደ ፡ የሩሰሌምም ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ወንድሞች ፡ በፍቅር ፡ ተቀበልዋቸው ። በያዕቆብም ፡ ቤት ፡ ከቀሳውስት ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ፡ ተገናኘ ፡ ጳውሎስ ። እግዚአብሔርም ፡ ባሕዛብ ፡ መኻከል ፡ በጁ ፡ ያደረገውን ፡ ነገር ፡ ነገሬቸው ። እርሳቸውም ፡ ይህነን ፡ በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገኑ ፡ አሉትም ። ታያለህን ፡ ወንድም ፡ ሆይ ፡ ስንት ፡ አእላፋት ፡ ካይሁድ ፡ ናቸው ፡ ያመኑ ። እርሳቸውም ፡ ሁሉ ፡ ለኦሪት ፡ የሚቀኑ ፡ ናቸው ። ስላንተም ፡ ሰምተዋል ፡ እንድታስተምር ፡ አይሁድን ፡ ሁሉ ፡ ባሕዛብ ፡ መኻከል ፡ ያሉትን ፡ ከሙሴ ፡ ሥርዓት ፡ ደርቁ ፡ ዘንድ ፡ እንዲህ ፡ ኢያለህ ። ልጆቻቸውን ፡ እንዳይገዝሩ ፡ በሕግም ፡ እንዳይመላለሱ ። እንጊዲህስ ፡ ምን ፡ ይሁን ። የግድ ፡ ሕዝብ ፡ ሳይሰበሰቡ ፡ አይቀሩም ። ይሰማሉና ፡ እንደ ፡ መጣህ ። አሁንም ፡ ይህነን ፡ የምንልህን ፡ ነገር ፡ አድርግ ። ከኛ ፡ ዘንድ ፡ ፬ ፡ ሰዎች ፡ አሉ ፡ በራሳቸው ፡ ስለት ፡ ያለባቸው ። እሊህንም ፡ ውሰድና ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ንጻ ። ሰጥላቸውም ፡ ራሳቸውን ፡ እንዲላጩ ። እንዲሁም ፡ የሆነ ፡ እንደሆን ። ላይሁድም ፡ አይሁደዊ ፡ እንድትሆን ፡ አይሁድን ፡ ታገኛለህ ። ሁሉም ፡ ያውቃሉ ፡ ስላንተ ፡ የሚጣላቸው ፡ ወሬ ፡ ሁሉ ፡ አሰት ፡ እንደሆነ ። አንተ ፡ እንደ ፡ ተሰማማህ ፡ እንጂ ፡ ሕግንም ፡ ጠባቂ ፡ እንደ ፡ ሆንህ ። ስላመኑት ፡ አሕዛብ ፡ ግን ፡ እኛ ፡ ጸፍነላቸው ፡ አዘዝናቸውም ፡ እንዲይጠብቁ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ሰውነታቸውን ፡ ከመጠበቅ ፡ በቀር ፡ ለጣዖት ፡ ከታረደው ፡ ከደምም ፡ ከታነቀውም ። ከዝሙትም ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ወሰደ ፡ ጳውሎስ ፡ ሰዎችን ። በነጋውም ፡ ነጻ ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ። ወደ ፡ መቅደስም ፡ ገባ ፡ ኢየተወራ ፡ የመንጻቱ ፡

ቀን ፡ ሲፈጸም ፡ መሥዋት ፡ ያቀርብ ፡ ዘንድ ፡ ሁሉ ፡ ኢየሩ
ሳሌም ፡ ቢመጡ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አገኙ ፡ ሥራው ፡ ኢየሩ
ሱ ። እንደሁም ፡ ተጠንቅቆ ፡ ምናልባት ፡ አይሁድን ፡ ባያስ
ታርቃቸው ፡ ብሎ ። ነገር ፡ ግን ፡ አልተጠቀመበትም ። ሰባ
ት ፡ ቀንም ፡ በተፈጸሙ ፡ ጊዜ ፡ አዩት ፡ በመቅደስ ፡ ከእስ
ያ ፡ የመጡ ፡ አይሁድ ፡ ሕዝብንም ፡ ሁሉን ፡ አወኩ ፡ እጃቸ
ውንም ፡ ጣሉበት ፡ ኢየጮሁ ፡ እንደሁም ፡ ኢያሉ ። እላን
ት ፡ ሰዎች ፡ ከእሥራኤል ፡ ወገን ፡ እርዱን ። ይህ ፡ ነው ፡ ሰ
ውን ፡ ሁሉን ፡ የሚያስተምር ፡ በየስፍራው ፡ ሕዝብን ፡ የሚ
ጠላ ፡ ትምርት ፡ ኦሪትንም ፡ ይህንም ፡ ስፍራ ። አረማውያ
ንንም ፡ ወደ ፡ መቅደስ ፡ አገባቸው ። ይህንም ፡ የተቀደሰ
ውን ፡ ስፍራውን ፡ አረከሰው ። (አይተው ፡ ነበረና ፡ ባገር ፡ ከ
ርሱ ፡ ጋራ ፡ አስቀድመው ፡ ጠረፊሞስን ፡ የኤፌሶንን ። ጳ
ውሎስም ፡ ያገባው ፡ ወደ ፡ መቅደስ ፡ መሰላቸው ።) ምሉ ፡
አገርም ፡ ሁሉ ፡ ታወከች ፡ ሕዝብም ፡ ተሰበሰቡ ፡ ጳውሎስን
ም ፡ ያዙት ፡ ከመቅደስ ፡ ወደ ፡ሜደም ፡ አወጡት ። የዚያ
ን ፡ ጊዜም ፡ ደጆ ፡ ሁሉ ፡ ተዘጋ ። እርሳቸውም ፡ ሊገድሉ
ት ፡ ሲሹ ፡ ወሬ ፡ ደረሰ ፡ ወደ ፡ የሻለቃው ፡ በጭፍራ ፡ ላይ ፡
ሁሉ ፡ የተሾመ ፡ የሩሳሌም ፡ ፈጽማ ፡ እንደ ፡ ታወከች ።
እርሱም ፡ በዚያው ፡ ጊዜ ፡ ጭፍራውን ፡ ወሰደ ፡ የመቶ ፡ አ
ለቆችም ፡ ሲሮጥም ፡ ደረሰባቸው ። እርሳቸው ፡ ግን ፡ ባዩ ፡
ጊዜ ፡ የሻለቃውን ፡ ጭፍሮችንም ፡ ጳውሎስን ፡ በመምታት ፡
ታገሡ ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ የሻለቃው ፡ ወደርሱ ፡ ቀረበ ፡ ያዘ
ውም ፡ በ፪፤ ሰንሰለትም ፡ ይታሠር ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ። ጠየቀ
ም ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ምንስ ፡ አደረገ ፡ ብሎ ። አያሌም ፡ እ
ንዲህ ፡ አያሌም ፡ እንዲህ ፡ ጮኹ ። የሰራውንም ፡ ስሬ ፡
ማወቅ ፡ ባልተቻለው ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ጩኸት ፡ ብዛት ፡ ወደ ፡
ከተማ ፡ ይወስዱት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ። ወደ ፡ ከተማውም ፡
ማውጫ ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ተሸከሙት ፡ ጭፍሮች ፡ ስለ ፡ ሕዝ
ቡ ፡ ጭንቀት ። እጅግ ፡ ሰዎች ፡ ይከተሉት ፡ ነበረና ፡ ኢየጮ
ሁ ፡ እንዲህ ፡ ብለው ። አውጡት ። ወደ ፡ ከተማውም ፡
ሲወስዱት ፡ ጳውሎስ ፡ አለው ፡ የሻለቃውን ። ትሰማኛለ
ህን ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ብነገርህ ። እርሱም ፡ አለ ። በጽርዕ ፡
ቋንቋ ፡ ታውቃለህን ። አንተ ፡ የምስር ፡ ሰው ፡ አይደለህም ፡

ን ፡ ከዚህ ፡ ዘመን ፡ አስቀድመህ ፡ ሁከት ፡ ያደረግህ ፡ ወደ ፡
ምድረ ፡ በዳም ፡ ያወጣህ ፡ ፵፻፡ ሰዎች ፡ ከወንበዴች ፡ ወገ
ን ፡፡ ጳውሎስም ፡ አለ ፡፡ እኔስ ፡ አይሁዳዊ ፡ ሰው ፡ ነኝ ፡ አ
ገሬም ፡ ጠርሴስ ፡ ነው ፡፡ ከቂልቅያ ፡ አገር ፡ የታወቀች ፡ በ
ታላቅነት ፡፡ እለምንሃለሁም ፡ እንድታዘኝ ፡ ለሕዝቡ ፡
እናገር ፡ ዘንድ ፡፡ ባዘዘውም ፡ ጊዜ ፡ በማውጫ ፡ ላይ ፡ ቆ
መ ፡ ጳውሎስ ፡ ሕዝብንም ፡ በጁ ፡ ጠቀሰ ፡፡ እጅግም ፡ ጸጥ
ታ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ነገራቸው ፡ በዕብራይስጥ ፡ ቋንቋ ፡ እንዲህ ፡
ብሎ ፡ ሲጀምር ፡፡ እላንት ፡ ሰዎች ፡ ወንድሞች ፡ አባቶች
ም ፡ ስሙ ፡ ነገሬን ፡ ዛሬ ፡ የምናገራችሁትን ፡፡ ሕዝብም ፡
በሰሙ ፡ ጊዜ ፡ በዕብራይስጥ ፡ ቋንቋ ፡ እንደ ፡ ናገራቸው ፡
ጸጥታውን ፡ አበዙ ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ነገራቸው ፡ እር
ሱ ፡ ማን ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ አስቀድሞ ፡ መመለሱም ፡ እንዴ
ት ፡ ሆነ ፡ ክርስቶስም ፡ እንደ ፡ ታየለት ፡ እንደለውም ፡፡ ሒ
ድ ፡ እኔ ፡ እልክሃለሁና ፡ ሩቅ ፡ አገር ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡፡ ይ
ህንንም ፡ ብሎ ፡ አይሁድ ፡ ጸጥታቸውን ፡ አፈረሱ ፡ ቃላቸው
ንም ፡ አነሡ ፡ ተባብረው ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡፡ እንዲህ ፡ ያለው
ን ፡ ከምድር ፡ አውጡት ፡፡ አይገባምና ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ በሕ
ይወት ፡፡ እርሳቸውም ፡ ሲጮሁ ፡ ልብሳቸውንም ፡ ሲጥሉ ፡
ትብያንም ፡ ሲበትኑ ፡ ወደ ፡ ንፋስ ፡ የሻለቃው ፡ አዘዘ ፡ ጭ
ፍሮችን ፡ ወደ ፡ ከተማ ፡ ይወስዱት ፡ ዘንድ ፡ ባለንጋም ፡ ይ
ገርፉት ፡ ዘንድ ፡ ይመረምሩትም ፡ ዘንድ ፡ ሊያውቅ ፡ በም
ን ፡ መክንያት ፡ እርሳቸው ፡ እንዲህ ፡ ይጮሁበታል ፡፡ ለመ
ግረፍም ፡ የፈጥኝ ፡ ባሠሩት ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስ ፡ ለመቶ ፡ አ
ለቃ ፡ አለ ፡ ለማስገረፍ ፡ ቁሞ ፡ ለነበረው ፡፡ ይገባችኋልን ፡
ባለመፍረድ ፡ ቅንም ፡ ሳይሆን ፡ የሮምን ፡ ሰው ፡ ትገርፉ ፡
ዘንድ ፡፡ የመቶ ፡ አለቃም ፡ ይህነን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ መጣ ፡
ለሻለቃውም ፡ ነገረው ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ምን ፡ ትሻለህ ፡ ታ
ደርግ ፡ ዘንድ ፡ በዚህ ፡ ሰው ፡፡ ሮማዊ ፡ ነው ፡፡ የሻለቃውም ፡
ወደርሱ ፡ ቀረበ ፡ አለውም ፡፡ ንገረኝ ፡ ሮማዊ ፡ እንደሆንህ ፡
አንተ ፡፡ እርሱም ፡ አለ ፡፡ አዎን ፡፡ ያም ፡ ሊፈትነው ፡ አለ ፡፡
እኔ ፡ በብዙ ፡ ከብት ፡ ገዛሁት ፡ ይህችን ፡ የሮምን ፡ ባላገር
ነት ፡፡ ጳውሎስም ፡ አለ ፡፡ እኔ ፡ ግን ፡ የሮም ፡ ባላገር ፡ ሆን

ሁ ፡ በመወለዴ ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ከርሱ ፡ ራቁ ፡ ገርፈው
ት ፡ ሊመረምሩት ፡ የነበሩ ፡፡ የሻለቃውም ፡ ደግሞ ፡ ፈራ ፡
ሲሰማ ፡ ሮማዊ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ስላሠረው ፡፡ በነጋውም ፡
የሰሩውን ፡ ነገር ፡ ማወቅ ፡ በወደደ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ምንስ ፡
ደከሰሰል ፡ ካይሁድ ፡ ብሎ ፡ ከሥራቱ ፡ ፈታው ፡ የካህናት ፡
አለቆችንም ፡ ከሸንጎ ፡ ጋራ ፡ አስመጣ ፡ ጳውሎስንም ፡ ወ
ሰደ ፡ ወደ ፡ መኻከላቸውም ፡ አቆመው ፡፡ ጳውሎስም ፡ ሸ
ንጎን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ አለ ፡፡ እላንተ ፡ ወንድማማች ፡ ሰዎች ፡
እኔ ፡ በውነተኛ ፡ ሕሊናዬ ፡ ተመላለስሁ ፡ በእግዚአብሔር ፡
ፊት ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡፡ ሐናንያ ፡ ግን ፡ የካህናት ፡ አ
ለቃ ፡ ይህነን ፡ ሲሰማ ፡ በፊቱ ፡ ቁመው ፡ የነበሩትን ፡ አፉ
ን ፡ ይመቱት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፡፡ ጳውሎስም ፡ አለው ፡፡ እ
ግዚአብሔር ፡ ይምታህ ፡ አንተ ፡ የተላሰንህ ፡ ግድግዳ ፡፡
አንተ ፡ ተቀምጠህን ፡ ትፈርድብኛለህ ፡ በሕግ ፡፡ ያለ ፡ ሕግ
ም ፡ ታዛለህን ፡ እመታ ፡ ዘንድ ፡፡ የቆሙት ፡ ግን ፡ አሉ ፡፡
የእግዚአብሔርን ፡ ካህናት ፡ አለቃውን ፡ ትሰድባለህን ፡፡ ጳ
ውሎስም ፡ አለ ፡፡ አላውቅም ፡ ነበርሁ ፡ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፡
የካህናት ፡ አለቃ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡፡ ተጽፏዋልና ፡፡ የሕዝብህ
ን ፡ አለቃ ፡ አትርገም ፡ ትብሎ ፡፡ አሁንም ፡ ጳውሎስ ፡ ባየ ፡
ጊዜ ፡ ሸንጎ ፡ እንደ ፡ ተከፈለ ፡ እኩሌታቸውም ፡ ሳዱቃው
ያን ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ እኩሌታቸውም ፡ ፈሪሳውያን ፡ በመንፈ
ስ ፡ ቅዱስ ፡ ጥበብን ፡ አደረገ ፡፡ በሸንጎ ፡ መኻከልም ፡ ጮ
ሀ ፡ እንደዪህ ፡ ሲል ፡፡ እላንተ ፡ ወንድማማች ፡ ሰዎች ፡፡ እ
ኔ ፡ ፈሪሳዊ ፡ የፈሪሳዊም ፡ ልጅ ፡ ነኝ ፡፡ ስለ ፡ ትንሣኤ ፡ ሙ
ታንም ፡ ተስፋ ፡ በኔ ፡ ይፈረድብኛል ፡፡ ይህም ፡ እውነት ፡ ነ
በረ ፡፡ ከሙታን ፡ በተነሣ ፡ ክርስቶስ ፡ አምንዋልና ፡ በዚህ
ም ፡ ሃይማኖት ፡ መክንያት ፡ ከሰሡት ፡፡ ይህነንም ፡ ባለ ፡
ጊዜ ፡ ጥል ፡ ሆነ ፡ በፈሪሳውያንና ፡ በሳዱቃውያን ፡ መኻከ
ል ፡፡ የካህናትም ፡ አለቃ ፡ ከሳዱቃውያን ፡ ወገን ፡ ነበረ ፡፡
ታላቅ ፡ ጩኸትም ፡ ሆነ ፡፡ የፈሪሳውያንም ፡ ወገን ፡ ተነሡ ፡
ስለርሱ ፡ ይጣሉ ፡ ዘንድ ፡ እንደዪህ ፡ ሲሉ ፡፡ በዚህ ፡ ሰው ፡
ላይ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አናገኝም ፡፡ አንድ ፡ መንፈስ ፡ ነግሮት ፡ እ
ንደሆን ፡ እንጂ ፡ ወይስ ፡ መልአክ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አን

ጣላ ። እጅግ ፡ ጥልም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የሻለቃው ፡ ፈራ ፡ ጳ
ውሎስን ፡ ከመኻከላቸው ፡ እንዳይነጥቁት ። ጭፍራውን
ም ፡ አዘዘ ፡ ከመኻከላቸው ፡ ጠልፈው ፡ ይወስዱት ፡ ዘን
ድ ፡ ወደ ፡ ከተማውም ፡ ያገቡት ፡ ዘንድ ። በምትመጣው
ም ፡ ሌሊት ፡ ጌታ ፡ በጳውሎስ ፡ ዘንድ ፡ ቆመ ፡ አለም ። በር
ታ ፡ ጳውሎስ ፡ ሆይ ፡ አትፍራም ። በየሩሳሌም ፡ እንደ ፡ መ
ሰከርህልኝ ፡ እንዲሁ ፡ ደግሞ ፡ በሮምያ ፡ ትመሰክርልኝ ፡ ዘ
ንድ ፡ ጊዜ ፡ አለህ ፡ በዚህም ፡ በጌታው ፡ ነገር ፡ ጸንቶ ፡ ጳው
ሎስ ፡ የሚመጣበትን ፡ መከራ ፡ የመንገዱንም ፡ ድካም ፡
ሁሉ ፡ በደስታ ፡ ታገሠ ።

በጻባም ፡ ጊዜ ፡ ከ፵፤ የሚበዙ ፡ አይሁድ ፡ ተማማሉ ፡ እ
ንጀራ ፡ እንዳይበሉ ፡ ውኃም ፡ እንዳይጠጡ ፡ ጳውሎስን ፡
እስኪገድሉት ፡ ድረስ ። እርሳቸውም ፡ መጡ ፡ ወደ ፡ ካህ
ናት ፡ አለቆችና ፡ ወደ ፡ ሽማግሎች ፡ አልዋቸውም ። እኛ ፡
ተማምለናል ፡ አንዳችን ፡ እንዳንቀምስ ፡ ጳውሎስን ፡ ሳን
ገድል ። አሁንም ፡ እላንት ፡ ለሻለቃው ፡ ንገሩት ፡ ከሸንጎ ፡
ጋራ ፡ ወደላንት ፡ ያወጣው ፡ ዘንድ ፡ ነጋ ፡ እንደምትወዱ ፡ ነ
ገሩን ፡ በውነት ፡ መመርመር ፡ ስትመስሉለት ። እርሱም ፡
ወደላንት ፡ ሳይደርስ ፡ እኛ ፡ እንገድለዋለን ። ደሮ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ መልእክተኛውን ፡ ጠበቀ ። የጳውሎስ ፡ የቱ ፡ ል
ጅ ፡ በሰማ፡ ጊዜ ፡ ምክራቸውን ፡ መጣ ፡ ገባም ፡ ወደ ፡ ከተ
ማ ፡ ለጳውሎስም ፡ ነገረው ። ጳውሎስም ፡ ጸራ ፡ ከመቶ ፡
አለቆች ፡ አንዱን ፡ አለውም ። ይህነን ፡ ብላቴና ፡ ውሰድ ፡
ወደ ፡ የሻለቃው ። የሚነግረው ፡ ነገር ፡ አለውና ። እርሱ
ም ፡ ወሰደው ፡ አገባውም ፡ ወደ ፡ የሻለቃው ፡ አለም ። የ
ታሠረ ፡ ጳውሎስ ፡ ጸራኝ ፡ ለመነኝም ፡ ወደንተ ፡ አግባው ፡
ዘንድ ፡ ይህነን ፡ ብላቴና ፡ የሚነግርህ ፡ ነገር ፡ አለውና ። የሻ
ለቃውም ፡ ብላቴናውን ፡ በጁ ፡ ያዘው ፡ ለብቻውም ፡ ወሰ
ደው ፡ ጠየቀውም ፡ አለውም ። ምንድር ፡ ነው ፡ የምትነግ
ረኝ ። ብላቴናውም ፡ አለው ። አይሁድ ፡ ፈጽመው ፡ ተማ
ከሩ ፡ ይለምኑህ ፡ ዘንድ ፡ ጳውሎስን ፡ ለማውረድ ፡ ነጋ ፡
ወደ ፡ ፍርድ ፡ ሸንጎ ። ነገሩን ፡ በውነት ፡ መመርመር ፡ እንዲ
ወዱ ። አንተ ፡ ግን ፡ አታመንባቸው ። ሸምቀውበታልና ፡ ከ

፳፩፡ ሰው ፡ የሚበዙ ፡ ከርሳቸው ፡ ወገን ፡ የተማማሉ ፡ እን
ደይበሉ ፡ እንደይጠጡም ፡ ሰይገድሉት ፡፡ አሁንም ፡ እርሳ
ቸው ፡ ተዘጋጅተዋል ፡ ካንተም ፡ ምላሽን ፡ ይጠብቃሉ ፡፡ የ
ሻለቃው ፡ ግን ፡ ብላቴናውን ፡ ሰደደው ፡፡ አዘዘውም ፡ ለማ
ንም ፡ እንደይነገር ፡ ይህነን ፡ ወሬ ፡ እንደወጣለት ፡፡ ከመ
ቶ ፡ አለቆችም ፡ ፪፡ ጸሪ ፡ አላቸውም ፡፡ ፳፫፡ ወታደር ፡ አዝጋ
ጁ ፡ ወደ ፡ ቂሣርያ ፡ ይሒዱ ፡ ዘንድ ፡ ፸፡ ፈረሰኞችም ፡ ፪፻፡
ወርዋሮችም ፡ በሌት ፡ በሶስተኛ ፡ ሰዓት ፡፡ እንስሳም ፡ ው
ስዱ ፡ ጳውሎስን ፡ ሊያስቀመጡበት ፡ ያድርሱትም ፡ ዘንድ ፡
ወደ ፡ ፊልክስ ፡ ወደ ፡ ሹሙ ፡፡ መልእክትንም ፡ ጻፈ ፡ እን
ዴህ ፡ ሲል ፡፡ ከቀላውዴዎስ ፡ ሊሲያስ ፡ ወደ ፡ ጽኑ ፡ ፊልክ
ስ ፡፡ ደስ ፡ ይበልህ ፡፡ ይህነን ፡ ሰው ፡ አይሁድ ፡ ያዙት ፡ ሊገድ
ሉትም ፡ ፈለጉ ፡፡ እኔም ፡ ከጭፍራ ፡ ጋራ ፡ ደረስሁ ፡ አደን
ሁትም ፡ ሮማዊ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባወቅሁ ፡ ጊዜ ፡፡ በወደድሁ
ም ፡ ጊዜ ፡ አውቅ ፡ ዘንድ ፡ የሚያሳጡትን ፡ መክንያት ፡ ወ
ደ ፡ ሸንጎቸው ፡ አመጣሁት ፡፡ ሲያሳጡትም ፡ አገኘኋቸው ፡
በሕጋቸው ፡ ነገር ፡፡ መበደል ፡ አላገኘሁበትም ፡ ወደ ፡ ሞ
ት ፡ ወደ ፡ እሥራትም ፡ የሚያደርሰው ፡፡ ባወቅሁም ፡ ጊ
ዜ ፡ ክፉ ፡ ምክር ፡ እንደ ፡ ተማከሩበት ፡ በዚህ ፡ ሰው ፡ ወ
ደንተ ፡ ሰደድሁት ፡፡ ጸላቶቹንም ፡ አዘዝሁ ፡ በፊትህ ፡ ይከ
ሱት ፡ ዘንድ ፡፡ ወታደርም ፡ እርሱ ፡ እንደዘዛቸው ፡ ጳውሎ
ስን ፡ በሌት ፡ ወሰዱት ፡ ይዘውትም ፡ መጡ ፡ ወደ ፡ አንቲጳ
ጥሪስ ፡፡ በነጋውም ፡ አሰናበቱ ፡ ፈረሰኞችን ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡
ይሒዱ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ሰፈርም ፡ ተመለሱ ፡፡ እሌህም ፡ መ
ጡ ፡ ወደ ፡ ቂሣርያ ፡ መልእክትንም ፡ ሰጡ ፡ ለሹም ፡፡ ጳ
ውሎስንም ፡ በፊቱ ፡ አቀሙት ፡፡ መልእክትንም ፡ ባነበበ ፡
ጊዜ ፡ ጠየቀው ፡ እንዴህ ፡ ሲል ፡፡ ከወዴት ፡ አገር ፡ ነህ ፡ አን
ተ ፡፡ ከቂልቅያም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ አለው ፡፡ እ
ንሰማሃለን ፡ ከሳሾችህ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡፡ አዘዘም ፡
ይጠብቁት ፡ ዘንድ ፡ በሄሮድስ ፡ ቤት ፡፡ ከ፭፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡
የጳውሎስ ፡ ከሳሾች ፡ ከየሩሳሌም ፡ ወረዱ ፡ ወደ ፡ ቂሣር
ያ ፡ ጳውሎስን ፡ ይከሱ ፡ ዘንድ ፡፡ እርሳቸውም ፡ የካህናት ፡
አለቃ ፡ ከሽማግሎች ፡ ጋራ ፡ ነበሩ ፡፡ የሮም ፡ ተናጋሪም ፡ ጠር

ጡሉስ ፡ የሚሉት ፡ በዋጋ ፡ ወሰዱ ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡፡ አ
ሁን ፡ መክንያት ፡ አልተገኘምና ፡ ጳውሎስን ፡ ለመክሰስ ፡
አሰት ፡ አወጡበት ፡ እርሱንም ፡ በዓለም ፡ ሁሉ ፡ በየረሳ
ሌምም ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ እንደ ፡ ከለከል ፡ አጣሉት ፡፡ እ
ንደ ፡ ሕጋቸውም ፡ ይፈርዱበት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ደር ፡ የሻለ
ቃው ፡ እንደ ፡ ከለከላቸው ፡፡ ደህነንም ፡ ከሚጻፎጥ ፡ ነገር ፡
ጋራ ፡ ተናገረ ፡ ስለ ፡ ቅኑ ፡ ሹሙን ፡ ሲያመሰግኑት ፡፡ ፊልክ
ስ ፡ ግን ፡ እጅግ ፡ ግፈኛ ፡ ነበረ ፡ ስለ ፡ ግፉም ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡
በኋላ ፡ ሹመቱ ፡ ተሻረ ፡፡ ጠርጡሎስም ፡ ጳውሎስን ፡ ከከሰ
ሰው ፡ በኋላ ፡ ጳውሎስ ፡ በውነት ፡ ተናገረ ፡ ነፍሱንም ፡ አነ
ጻ ፡ የሆነውን ፡ በየውሃት ፡ ሲናገር ፡ ሃይማኖቱንም ፡ አካ
ሔዱንም ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በሰው ፡ ፊት ፡፡ ፊልክስም ፡
የክርስቲያንን ፡ መንገድ ፡ አውቆ ፡ ቁም ፡ ምለሽ ፡ አልመ
ለሰላቸውም ፡ አላቸው ፡ እንጅ ፡፡ ሊሲያስ ፡ የሻለቃው ፡
ሲመጣ ፡ ነገራችሁን ፡ አውቃለሁ ፡፡ የመቶንም ፡ አለቃ ፡ አዘ
ዘ ፡ ጳውሎስን ፡ ይጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ ወዳጆቹንም ፡ እንደይከለ
ክልበት ፡ ለማገልገል ፡፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ መጣ ፡ ፊልክስ ፡
ከኃጢአተኛዪቱ ፡ ከምሽቱ ፡ ድሩሲላ ፡ ጋራ ፡ ጳወሎስንም ፡
አስመጡ ፡ ይሰሙት ፡ ዘንድ ፡፡ እርስዋም ፡ አይሁዳዊት ፡ ነ
በረች ፡፡ እርሳቸውም ፡ ለመጫወት ፡ ብለው ፡ ሊሰሙት ፡
ነበረ ፡ ከክርስቶስ ፡ ሃይማኖት ፡፡ ጳውሎስ ፡ ግን ፡ በመንፈ
ስ ፡ ቅዱስ ፡ ኃይል ፡ ተናገራቸው ፡ ስለ ፡ ጽድቅ ፡ ስለ ፡ ንጽሕና
ም ፡ ስለ ፡ ሚመጣውም ፡ ፍርድ ፡፡ ደህነንም ፡ ሲሰማ ፡ ፊ
ልክስ ፡ ፈራ ፡ ስለ ፡ ኃጢአቱ ፡፡ ደሮ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እን
ዳለ ፡፡ ዛሬ ፡ ድምጼን ፡ ብትሰሙ ፡ ልባችሁን ፡ አታጽኑ ፡፡
እርሱ ፡ አልጠበቀም ፡፡ ያች ፡ ታላቅና ፡ ብርቱ ፡ 'ዛሬ ፡' አለ
ፈችበት ፡ ልቡን ፡ ሳይመልስ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡፡ ፊልክ
ስም ፡ ጳውሎስን ፡ አለው ፡፡ አሁንስ ፡ ሒድ ፡ በጎ ፡ ጊዜ ፡ ባ
ገኘ ፡ አስጸራሃለሁ ፡፡ ከዚህም ፡ ጋራ ፡ ተስፋ ፡ አደረገ ፡ እ
ጅ ፡ መንሻ ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ ከጳውሎስ ፡ ወዳጆች ፡ አርነ
ት ፡ ቢያወጣው ፡፡ ጳውሎስም ፡ እንደሁ ፡ ያለውን ፡ ማድረ
ግ ፡ ነቅዋልና ፡ የፊልክስ ፡ ወዳጅነት ፡ አለቀ ፡፡ ከ፪፤ አመት
ም ፡ በኋላ ፡ ጶርቅዮስ ፡ ፊስጦስ ፡ ተቀበለ ፡ የፊልክስን ፡ ሹ

መት ። ፊልክስም ፡ ወድዋልና ፡ አይሁድን ፡ ደስ ፡ ለማሰኘ ት ፡ ጳውሎስን ፡ ታሥሮ ፡ ተወው ።

ፊስጦስም ፡ ወደ ፡ የሩሳሌም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ የጳውሎ ስ ፡ ጸላቶች ፡ ከሰሱት ። ወደ ፡ የሩሳሌምም ፡ ሊያስመጣ ው ፡ ከዚያም ፡ ሊፈርድበት ፡ ለመኑት ። እንዲህም ፡ ብለ ው ፡ በመንገድ ፡ ሊገድሉት ፡ አሰቡ ። ፊስጦስ ፡ ግን ፡ ከሳ ሾቹን ፡ ወደ ፡ ቂሣርያ ፡ ሊሔዱ ፡ አዘዛቸው ። ከርሱም ፡ ጋ ራ ፡ ወረዱ ፡ ሊፈርድበትም ፡ በወደደ ፡ ጊዜ ፡ አይሁድ ፡ እ ጅግ ፡ ታላቅ ፡ መክንያት ፡ አመጡ ፡ በጳውሎስ ፡ ላይ ፡ እ ውነት ፡ ያድርጉት ፡ ዘንድ ፡ ያልቻላቸው ። እርሱም ፡ ሲማ ጕት ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ያይሁድን ፡ ሕግ ፡ መቅደስንም ፡ ቂ ሣርንም ፡ አንዷች ፡ አልበደልሁም ። ፊስጦስ ፡ ግን ፡ አይሁ ድን ፡ ደስ ፡ ያሰኝ ፡ ዘንድ ፡ በወደደ ፡ ጊዜ ፡ ጳውሎስን ፡ አ ለ ። ትወዷለህን ፡ ወደ ፡ የሩሳሌም ፡ ትወጣ ፡ ዘንድ ፡ ከዚ ያም ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ትፈራረድ ፡ ዘንድ ። ጳውሎስ ፡ ግን ፡ ያ ይሁድን ፡ ተንኰል ፡ አውቆ ፡ አለው ። እኔ ፡ ቁሚያለሁ ፡ በ ቂሣር ፡ ፍርድ ፡ እፈራረድበት ፡ ዘንድ ፡ የሚገባኝ ። አይሁ ድን ፡ በምንም ፡ አልበደልሁም ፡ አንተ ፡ ደግሞ ፡ እንድታ ውቅ ። እኔ ፡ በድዬ ፡ እንደ ፡ ሆንሁ ፡ ክፉም ፡ አድርጌ ፡ እን ደ ፡ ሆንሁ ፡ ለሞት ፡ የሚገባ ፡ ከሞት ፡ የሚምረኝ ፡ አይኑ ር ። እሌህ ፡ የሚከሱኝ ፡ መክሰስ ፡ ዝምብሎ ፡ እንደ ፡ ሆ ነ ፡ ለማንም ፡ አይቻለውም ፡ ለርሳቸው ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጠ ኝ ፡ ዘንድ ። እኔም ፡ በቂሣር ፡ ተማጽኘለሁ ። የዚያን ፡ ጊዜ ም ፡ ፊስጦስ ፡ ከሚመክሩት ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ተጫወተ ፡ መ ለሰም ፡ አለም ። በቂሣርስ ፡ ከተማጸንህ ፡ ወደ ፡ ቂሣር ም ፡ ትሔዷለህ ። አያሌ ፡ ቀንም ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ አግሪጳ ፡ የገሊላ ፡ ንጉሥ ፡ ከምሽቱ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ቂሣርያ ፡ መጡ ፡ ፊስጦስን ፡ ያዩት ፡ ዘንድ ። እርሱም ፡ ጳውሎስን ፡ አወጣ ላቸው ፡ አግሪጳ ፡ ሊሰማው ፡ በፈለገ ፡ ጊዜ ። ጳውሎስም ፡ በቅድስት ፡ ድፍረት ፡ እጅን ፡ ዘረጋ ፡ ደናገር ፡ ዘንድ ፡ ካይ ሁድ ፡ ስለ ፡ ተከሰሰበት ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አለም ። አግሪጳ ፡ ን ጉሥ ፡ ሆይ ። ሰውነቴን ፡ የተመሰገነ ፡ አደርጋለሁ ፡ ዛሬ ፡ በ ፊትህ ፡ ተናገርያለሁና ። ደልቁንም ፡ አውቃለሁና ፡ እንድ

ታውቅ ፡ ያይሁድን ፡ ሕግ ፡ ልማዳቸውንም ። ስለዚህም ፡
እለምንሃለሁ ፡ ትሰማኝ ፡ ዘንድ ፡ በዝግምታ ። አተዳደጌ ፡
ከሕፃንነቴ ፡ ጀምሬ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቀድሞም ፡ የ
ነበርሁባትን ፡ ከወገኖቼ ፡ ጋራ ፡ በየሩሳሌም ፡ አይሁድም ፡
ሁሉ ፡ ያውቁታል ። አስቀድመው ፡ ያወቁኝ ፡ የወደዱ ፡ እ
ንደ ፡ ሆን ፡ ይመሰክሩ ። ፈሪሳዊ ፡ ነበርሁና ፡ እንደ ፡ ሐጋች
ን ፡ መጠን ፡ የበረታች ፡ መለየት ፡ የምትሆን ፡ ከሌላ ፡ መ
ለየት ፡ ይልቅ ። አሁንም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ላባቶ
ቻችን ፡ በሆነችው ፡ ተስፋ ፡ ተከስሼ ፡ ቁሚያለሁ ። በርሱ
ም ፡ ፲፪ ፡ ነግድ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመልካሉ ፡ ሁለግዜ ፡
ሌትና ፡ ቀን ፡ ወደርሱ ፡ ይደርሱ ፡ ዘንድ ፡ ተስፋ ፡ አድርገው ።
ስለዚህችም ፡ አለኝታ ፡ አግሪጳ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ካይሁድ ፡
እከሰሳለሁ ። ስለምን ፡ ይሆናል ፡ አለመታመን ፡ በላንት ፡
ዘንድ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሙታንን ፡ እንዲያስነሣ ። እኔ ፡ ግ
ን ፡ ደግሜ ፡ በሰውነቴ ፡ ይመስለኝ ፡ ነበርሁ ፡ ብዙ ፡ አደር
ግ ፡ ዘንድ ፡ የናዝሬቱን ፡ የየሱስን ፡ ስም ፡ የሚጣላ ። ይህ
ንንም ፡ ደግሞ ፡ በየሩሳሌም ፡ አደረግሁት ። ከቅዱሳን ፡ ብ
ዙን ፡ ሰዎች ፡ በግዞት ፡ ጨመርኋቸው ፡ ሥልጣንን ፡ ወስጄ ፡
በካህናት ፡ አለቆች ። ሲገልዋቸውም ፡ ፍርድ ፡ የማስፈር
ድባቸው ፡ እኔ ፡ ነበርሁ ። በመስጊድም ፡ ሁሉ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡
መከራ ፡ አስቀብላቸው ፡ ነበርሁ ፡ የግድም ፡ እላቸው ፡ ነበ
ርሁ ፡ ይሰድቡ ፡ ዘንድ ። እጅግም ፡ አበድሁባቸው ፡ ፈጽ
ሜም ፡ አሳደቸው ፡ ነበርሁ ፡ ወደ ፡ እንግዳ ፡ አገር ። በዚህ
ም ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ደማስቆ ፡ በሔድሁ ፡ ጊዜ ፡ በካህናት ፡ አ
ለቆች ፡ ትእዛዝ ፡ በሥልጣናቸውም ። በኩል ፡ ቀን ፡ በመ
ንገድ ፡ አየሁ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ከሰማይ ፡ ብርሃን ፡ ከፀሐይ ፡
ብልጫታ ፡ የሚበልጥ ፡ በዙርያዬም ፡ በራ ፡ ከኔም ፡ ጋራ ፡ በ
ነበሩት ፡ ዙርያ ። ሁላችንም ፡ በወደቅን ፡ ጊዜ ፡ በምድር ፡ ላ
ይ ፡ ድምጽ ፡ ሰማሁ ፡ ሲነግረኝ ፡ ሲለኝም ፡ በዕብራይስጥ ፡ ቋ
ንቋ ። ሳውል ፡ ሳውል ፡ ለምን ፡ ታሳደኛለህ ። በተሳለ ፡ ችን
ካር ፡ ላይ ፡ ብትርግጥ ፡ ባንተ ፡ ይከፋብሃል ። እኔም ፡ አል
ሁ ። አንተ ፡ ማነህ ፡ አቤቱ ። እርሱም ፡ አለ ። እኔ ፡ የሱስ ፡
ነኝ ፡ የምታሳደኝ ። ነገር ፡ ግን ፡ ተነሣና ፡ ቁም ፡ በግርህ ። እ

ኜም ፡ ስለዚህ ፡ ታደቼሃለሁና ፡ እሾምህ ፡ ዘንድ ፡ አገልጋ
ይ ፡ ምስክርም ፡ ባየሀው ፡ ነገር ፡ በምገልጥልህም ፡፡ ዛሬ
ም ፡ ወደርሳቸው ፡ ከምሰድህ ፡ ከሕዝብና ፡ ካሕዛብ ፡ አድ
ንሃለሁ ፡፡ ዓይናቸውን ፡ ትከፍት ፡ ዘንድ ፡ እንዲመለሱ ፡
ከጨለማ ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ ለሰይጣንም ፡ ከመገዛት ፡ ወደ ፡
እግዚአብሔር ፡፡ ይወስዱም ፡ ዘንድ ፡ የኃጢአታቸውን ፡ ስ
ርየት ፡ ርስትንም ፡ ከሚቀደሱ ፡ ጋራ ፡ ቤኔ ፡ ሃይማኖት ፡፡ አ
ሁንም ፡ አግሪጳ ፡ ንጉሥ ፡ ሆይ ፡ ዓመፀኛ ፡ አልሆንሁም ፡
ከሰማይ ፡ ለታየኝ ፡ ነገር ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ በደማስቆ ፡ አስተማ
ርሁ ፡ አስቀድሜ ፡ በየሩሳሌምም ፡ በይሁደም ፡ አገር ፡ ሁ
ሉ ፡፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ላሕዛብ ፡፡ ንስሓ ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፡ ይ
መለሱም ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ለንስሓ ፡ የሚገ
ባ ፡ ነገር ፡ ኢያደረጉ ፡፡ ስለዚህም ፡ ነገር ፡ ያዙኝ ፡ አይሁድ ፡
በመቅደስ ፡ ሊገሉኝም ፡ አሰቡ ፡፡ ከእግዚአብሔርም ፡ ዘን
ድ ፡ ረዴት ፡ ተቀበልሁ ፡፡ እስከዚህ ፡ ቀንም ፡ ድረስ ፡ ቆም
ሁ ፡ ስመሰክር ፡ ለታናሽም ፡ ለታላቅም ፡፡ ምንም ፡ አልተ
ናገርሁም ፡ ነቢያት ፡ ከተናገሩት ፡ ነገር ፡ የወጣ ፡ ሙሴም ፡
ደግሞ ፡፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ እንደለው ፡ የክርስቶስ ፡ ሕማማ
ት ፡፡ መጀመርያም ፡ እንዲሆን ፡ ከሙታን ፡ ከሚነሡ ፡፡ ያ
ስተምሩበትም ፡ እንደለው ፡ ለሕዝብና ፡ ላሕዛብ ፡፡

ጳውሎስም ፡ ይህነን ፡ ለመንጻቱ ፡ በተናገረ ፡ ጊዜ ፡ ፊስጦ
ስ ፡ አለ ፡ በታላቅ ፡ ድምጽ ፡፡ አንተ ፡ አበድህ ፡ ጳውሎስ ፡
ሆይ ፡፡ ብዙ ፡ መጻሕፍትን ፡ ተማርህ ፡ እስክታብድ ፡ ድረስ ፡፡
እርሱ ፡ ግን ፡ አለ ፡፡ አላበድሁም ፡ ጽኑ ፡ ፊስጦስ ፡ ሆይ ፡ ነ
ገር ፡ ግን ፡ እናገራለሁ ፡ በውነትና ፡ በውቀት ፡፡ ንጉሥ ፡ ደግ
ሞ ፡ ይህነን ፡ በፊቱ ፡ በድፍረት ፡ የምናገርበትን ፡ ነገር ፡ ያ
ውቃልና ፡፡ ተረድቻለሁና ፡ ከዚህ ፡ ነገር ፡ አንዷች ፡ ከርሱ ፡ እ
ንደይሰወር ፡፡ ይህ ፡ በስውር ፡ አልሆነምና ፡፡ አግሪጳ ፡ ንጉ
ሥ ፡ ሆይ ፡ ነቢያትን ፡ ታምናለህን ፡፡ እኔ ፡ አውቃለሁ ፡ እን
ድታምናቸው ፡፡ አግሪጳ ፡ ግን ፡ ጳውሎስን ፡ አለው ፡፡ ጥቂ
ት ፡ ቀረህ ፡ ክርስቲያን ፡ ልታድርገኝ ፡፡ ጳውሎስም ፡ አለ ፡፡
ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ እለምናለሁ ፡ በጥቂት ፡ በጅግ
ም ፡ ላንተ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ዛሬ ፡ እኔን ፡ ለሚሰሙኝ ፡ ሁ

ሉ ፡ እንጅ ፡ እንደኔ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ከዚህ ፡ ከሥራቱ ፡ በቀ ር ፡፡ ይህነንም ፡ ነገር ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሥ ፡ ተነሣ ፡ ሹምም ፡ በርኒቂም ፡ የንጉሥ ፡ ምሽት ፡ ከርሳቸውም ፡ ጋራ ፡ ተቀምጠ ው ፡ የነበሩት ፡፡ ለብቻቸውም ፡ በሆኑ ፡ ጊዜ ፡ እርሶ ፡ በርሳ ቸው ፡ አሉ ፡፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ምንም ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አላደረገ ም ፡ ለሞት ፡ ለሥራትም ፡ የሚያደርሰው ፡፡ አግሪጳም ፡ ፌ ስጦስን ፡ አለው ፡፡ ይህ ፡ ሰው ፡ ይፈታ ፡ ዘንድ ፡ ይገባ ፡ ነበ ር ፡ በቄሣር ፡ ባልተማጸነ ፡፡ ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ ፌስጦስ ፡ ጳ ውሎስን ፡ ሰደደ ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ ወደ ፡ ቄሣር ፡ እርሶም ፡ ኔሮን ፡ የተባለ ፡፡ አንድም ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ ዩልዩስ ፡ የ ሚሉት ፡ በመንገድ ፡ ጠበቀው ፡ ከሌሎች ፡ ከታሠሩት ፡ ሰ ዎች ፡ ጋራ ፡፡ ለጳውሎስም ፡ በጎ ፡ አደረገ ፡ ከቀሩት ፡ ይል ቅ ፡፡ የጳውሎስም ፡ ወደጆች ፡ ሉቃስና ፡ አርስጠርኮስ ፡ ከተ ሳሎንቄ ፡ ከርሶ ፡ ጋራ ፡ ሔዱ ፡፡ ከቄሣርያም ፡ ሰረሩ ፡ ባድ ራሚቲ ፡ መርከብ ፡ እስከ ፡ ሚራ ፡ ድረስ ፡፡ ከዚያም ፡ ሌ ላ ፡ መርከብ ፡ ከስክንድርያ ፡ የመጣች ፡ አገኙ ፡ በርስዋ ም ፡ ሔዱ ፡ ወደ ፡ ሜሊቴ ፡ ማልጣም ፡ ወደ ፡ ተባለች ፡ ደሴ ት ፡ እስኪቀርቡ ፡ ድረስ ፡ ከዚያም ፡ ሰበረች ፡፡ በማልጣ ም ፡ ከከረሙ ፡ በኋላ ፡ ሌላውን ፡ መርከብ ፡ አገኙ ፡ ወደ ፡ ኢጣልያ ፡ ወደ ፡ ሶስት ፡ ኽዋኒት ፡ የወሰደቻቸውን ፡፡ ከዚያ ም ፡ በምድር ፡ ሔዱ ፡ እስከ ፡ ሮም ፡ ድረስ ፡፡ በመንገዳቸ ውም ፡ ከቄሣርያ ፡ እስከ ፡ ሮም ፡ እሌህን ፡ ስፍሮች ፡ አገኙ ፡፡ በፊት ፡ ወደ ፡ ሰይደ ፡ ደረሶ ፡ ከዚያም ፡ ቆጵሮስን ፡ በግራ ፡ ትተው ፡ በቂልቂያና ፡ በጰንፌልያ ፡ አለፉ ፡ ወደ ፡ ሚራም ፡ በሉቂያ ፡ ወደለች ፡ ደረሶ ፡ መርከባቸውንም ፡ ለወጡ ፡፡ ከ ዚያም ፡ እጅግ ፡ ቀን ፡ ሰረው ፡ ወደ ፡ ግኒደስ ፡ ደረሶ ፡ ከዚያ ም ፡ ወደ ፡ አቅሬጥስ ፡፡ ከዚያም ፡ ከክረምት ፡ ከንፋስም ፡ በባሕርም ፡ እጅግ ፡ መከራ ፡ ተቀበሉ ፡፡ ከአቅሬጥስም ፡ ሰ ረው ፡ በክላውዴ ፡ አለፉ ፡ ከዚያም ፡ በጅግ ፡ ድካም ፡ በጅ ግ ፡ መከራም ፡ በጅግ ፡ ፍርሃትም ፡ በግድ ፡ ወደ ፡ ማልጣ ፡ ሲቀርቡ ፡ መርከባቸው ፡ ፈረሰች ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ ድነው ፡ ወ ደ ፡ ደሴት ፡ ወደ ፡ ማልጣ ፡ ደረሶ ፡፡ ከዚያም ፡ እጅግ ፡ ቸርነ ት ፡ ተቀበሉ ፡ ከማልጣ ፡ ሰዎች ፡ ከሹምም ፡ ጴብልዩስ ፡ ከ

ተባለው ፡፡ ጳውሎስም ፡ ከዚያ ፡ የጌታን ፡ ስም ፡ ሲያስተም ር ፡ እጅግ ፡ ድውያንን ፡ ፈወሰ ፡ በጌታ ፡ ስም ፡፡ ከ፫፡ ወር ም ፡ በኋላ ፡ ማልጣን ፡ ትተው ፡ በሌላ ፡ መርከብ ፡ ሔዱ ፡ ወደ ፡ ሲራኩስ ፡ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ሬጊዩም ፡ ከዚያም ፡ ወ ደ ፡ ጱቴዎሊ ፡፡ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ፫፡ ኸዋኒት ፡ ከዚያም ፡ ወ ንድሞችን ፡ አገኙ ፡ ከሮም ፡ ወርያቸውን ፡ ሰምተው ፡ ሊቀ በልዋቸው ፡ የመጡ ፡፡ ጳውሎስም ፡ እርሳቸውን ፡ ባያቸ ው ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገነ ፡ ልቡም ፡ በረታ ፡፡ በ ሮምም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠ ፡ እ ሥርኞችን ፡ ለሠራዊት ፡ አለቃ ፡፡ ጳውሎስን ፡ ግን ፡ አሰናብቶ ት ፡ ነበረ ፡ ይቀመጥ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ፈቃዱ ፡ ከሚጠብቀ ው ፡ ወታደር ፡ ጋራ ፡ እጁ ፡ በሰንሰለት ፡ ወደ ፡ ታሠረበት ፡፡ ቄሣር ፡ ኔሮን ፡ መጀመርያ ፡ ጊዜ ፡ እስኪፈርድበት ፡ እስኪ ፈታውም ፡ ድረስ ፡፡

በሮምም ፡ አንዲቱን ፡ ታላቅ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ አገ ኘ ፡ በቀደም ፡ መልእክቱን ፡ ይጽፍላት ፡ ወደ ፡ ነበረ ፡ ከቆር ንቶስ ፡ ዘንድ ፡፡ ከርሳቸውም ፡ ጋራ ፡ ከተገናኘ ፡ በኋላ ፡ ወ ደ ፡ አይሁድ ፡ መስጊድ ፡ ገባ ፡ ነገረንም ፡ የሥራቱንም ፡ መ ክንያት ፡ የወንጌልንም ፡ ትምርት ፡ ነገራቸው ፡፡ በወንጌል ም ፡ ሲናገር ፡ እንደ ፡ ወትሮ ፡ ሆነ ፡፡ ተከፍለው ፡ ነገሩን ፡ ተቀ በሉ ፡ የቀሩትም ፡ አላመኑበትም ፡፡ እንጊዲህም ፡ ወዲህ ም ፡ ፈጽሞ ፡ የወንጌል ፡ ትምርት ፡ ላሕዛብ ፡ ሆነች ፡፡

ሮምም ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ያለም ፡ ሁሉ ፡ ከተማ ፡ ነበረ ች ፡፡ የሮምም ፡ መንግሥት ፡ በታወቀች ፡ ምድር ፡ ሁሉ ፡ ተ ዘረጋች ፡ በኤውሮጳ ፡ በስያም ፡ ባፍሪቃም ፡፡ የወንጌል ም ፡ ትምርት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከየሩሳሌም ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ ከደረሰች ፡ በኋላ ፡ ከሮም ፡ ወጥታ ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ መግባትን ፡ አገኘች ፡፡ ጳውሎስም ፡ ስለዚህ ፡ እጅግ ፡ ተናፍ ቆ ፡ ነበር ፡ አስቀድሞ ፡ በሮም ፡ የክርስቶስን ፡ ስም ፡ የክር ስቶስንም ፡ መድኃኒት ፡ ያስታውቅ ፡ ዘንድ ፡፡ አሁንም ፡ ወ ዲያ ፡ ደርሶ ፡ መታሠሩ ፡ መክንያት ፡ ሆነለት ፡ ወደለም ፡ ሁሉ ፡ የወጣውን ፡ ትምርቱን ፡ ለማጽናት ፡፡ ከዚያም ፡ አ ያሌን ፡ ከመልእክቶቹ ፡ ጻፈ ፡ ወደ ፡ ኤፌሶን ፡ ወደ ፡ ፊል

ጵስዮስም ፡ ወደ ፡ ቆሎሳይስም ፡ ወደ ፡ ፊልሞንም ፡፡ በሮ
ምም ፡ ከተማ ፡ የክርስቶስን ፡ ትምህርት ፡ ባይሁድና ፡ ባረ
ማውያን ፡ መኻከል ፡ አስተማረ ፡ በታናሾችም ፡ በታላቆች
ም ፡ ከቄሣርም ፡ ከቤተሰቦቹ ፡ ደግሞ ፡ አያሌ ፡ እስኪያም
ኑ ፡ ድረስ ፡፡

ቄሣሮችም ፡ የተባሉ ፡ የሮም ፡ ነገሥታት ፡ ከክርስቶስ ፡
ልደት ፡ ጀምረው ፡ እስከ ፡ ጳውሎስ ፡ ሞት ፡ ድረስ ፡ በሮ
ም ፡ የነገሡ ፡ እሌህ ፡ ናቸው ፡፡

፩፡፡ ቄሣር ፡ አውጉስቱስ ፡ ነገሠ ፡ እስከ ፡ ፲፬፡ አመት ፡
ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡፡

፪፡፡ ቄሣር ፡ ቲቤርዮስ ፡ ነገሠ ፡ ከልደት ፡ በኋላ ፡ ከ፲፬፡ አ
መት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፴፯፡ አመት ፡ ድረስ ፡፡

፫፡፡ ቄሣር ፡ ከሊጉላ ፡ ነገሠ ፡ ከልደት ፡ በኋላ ፡ ከ፴፯፡ ጀ
ምሮ ፡ እስከ ፡ ፵፩፡ አመት ፡ ድረስ ፡፡

፬፡ ቄሣር ፡ ቅላውዲዮስ ፡ ነገሠ ፡ ከልደት ፡ በኋላ ፡ ከ፵፩፡
አመት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፶፬፡ አመት ፡ ድረስ ፡፡

፭፡ ቄሣር ፡ ኔሮን ፡ ነገሠ ፡ ከልደት ፡ በኋላ ፡ ከ፶፬፡ አመት ፡
ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፷፰፡ አመት ፡ ድረስ ፡፡

ቄሣር ፡ ኔሮንም ፡ በመንግሥቱ ፡ መጀመርያ ፡ ደኅና ፡ ሰ
ው ፡ ነበረ ፡፡ መካሮቹ ፡ ግን ፡ እጅግ ፡ ሲያመሰግኑት ፡ ፈቃዱ
ንም ፡ ሁለግዜ ፡ ሲፈጽሙት ፡ ሳይመክሩት ፡ ከፋ ፡፡ እናቱ
ን ፡ ምሽቱንም ፡ መምህሩንም ፡ አስገደለ ፡ በኃጢአትም ፡
ሁሉ ፡ ወደቀ ፡፡ ጳውሎስም ፡ ፪፡ አመት ፡ በሮም ፡ ታሥ
ሮ ፡ ተቀመጠ ፡ ወንጌልን ፡ ሲያስተምር ፡ በ፷፪፡ ፷፫፡ አ
መት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡፡ በ፷፫፡ አመትም ፡
ተፈታ ፡ ወደ ፡ ታናሽ ፡ እስያም ፡ ሔደ ፡ ወደ ፡ ኒቆጶሊስ ፡
ወደ ፡ ገላትያም ፡ ወደ ፡ አቅሬጥስም ፡፡ ተመልሶም ፡ ወደ ፡
እስጳንያ ፡ ሔደ ፡ ከዚያ ፡ ደግሞ ፡ የወንጌልን ፡ ትምህርት ፡
ሊዘርጋ ፡ ብሎ ፡፡ ደሮ ፡ የቄሣር ፡ ሰዎች ፡ ያዙት ፡ ወደ ፡ ሮ
ምም ፡ ወሰዱት ፡ ከዚያም ፡ ኔሮን ፡ ራሱን ፡ በሰይፍ ፡ አስቆ
ረጠው ፡ ከልደት ፡ በኋላ ፡ በ፷፯፡ አመት ፡፡ አያሌ ፡ ወራት
ም ፡ አስቀድሞ ፡ በ፷፬፡ አመት ፡ ኔሮን ፡ አብዶ ፡ ለመጫወ
ት ፡ ብቻ ፡ ሮምን ፡ ከተማውን ፡ አነደደት ፡ ፱፡ ቀንም ፡ ተቃ

ጠለች ፡፡ ሰውም ፡ በዚህ ፡ መክንያት ፡ ሲቈጡ ፡ ቄሣርን ም ፡ ሲጸሉት ፡ ክርስቲያንን ፡ አጣለ ፡ እርሳቸው ፡ ከተማ ውን ፡ እንደነደድዋት ፡፡ አሁንም ፡ የሁሉ ፡ ጸላትነት ፡ የሁ ሉም ፡ ቍጣ ፡ በክርስቲያን ፡ ላይ ፡ ወደቀ ፡፡ እጅግ ፡ ብርቱ ፡ ሞትም ፡ አወጡባቸው ፡፡ ተከፈለውን ፡ ወደ ፡ አርዌ ፡ ለም ድ ፡ አግብተው ፡ ሰፋዋቸው ፡ እንደሁም ፡ ለውሾች ፡ ጣልዋቸ ው ፡ ይነጠቁ ፡ ይነከሱም ፡ ይዋጡም ፡ ዘንድ ፡፡ ተከፈለው ንም ፡ በሰምዕ ፡ በቅቤም ፡ በሌላም ፡ በሚቃጠል ፡ ነገር ፡ ቀ ብዋቸው ፡ በንጨትም ፡ አሠርዋቸው ፡ በሌሊትም ፡ አነደ ድዋቸው ፡ ባደባባይ ፡ ለመንገድ ፡ አላፊች ፡ ያብሩ ፡ ዘን ድ ፡፡ ይህም ፡ መከራ ፡ ፫፡ ወይስ ፡ ፬፡ አመት ፡ ኖረ ፡፡ ኔሮን ፡ ግን ፡ ከሁሉ ፡ ተጸልቶ ፡ ራሱን ፡ ገደለ ፡ ፷፰፡ አመት ፡ ከልደ ት ፡ በኋላ ፡፡

በዚያ ፡ መሳደድም ፡ ጴጥሮስ ፡ መጋደሉን ፡ ጨረሰ ፡ በሮ ም ፡ ከተማ ፡ ኔሮን ፡ ሲያሰቅለው ፡፡ ስለርሱም ፡ እጅግ ፡ ተጻ ፈ ፡ እውነት ፡ ያልሆነ ፡፡ እውነት ፡ የሚመስል ፡ ይህ ፡ ነው ፡፡ ፵፡ አመት ፡ የሚያህል ፡ ከልደት ፡ በኋላ ፡ ጴጥሮስ ፡ ከየሩ ሳሌም ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ አንጾኪያ ፡ መጣ ፡፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ም ፡ በጶንጦስ ፡ በገላትያም ፡ በቀጳደቂያም ፡ በቢቲኒያም ፡ በወንጌል ፡ አስተማረ ፡፡ በልደት ፡ አመትም ፡ ፷፫፡ የሚያ ህል ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ ደረሰ ፡ ከዚያም ፡ ባመት ፡ ፷፬፡ ከጳውሎ ስ ፡ ጋራ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ሞተ ፡ ጳውሎስ ፡ ራሱ ፡ በሰይፍ ፡ ተ ቈርጦ ፡ ጴጥሮስም ፡ ተሰቅሎ ፡፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ፪፡ መ ልእክቶች ፡ ጻፈ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የቀደሳቸው ፡ ለሰው ም ፡ ሁሉ ፡ ለዘመንም ፡ ሁሉ ፡ የጠበቃቸው ፡፡ ቅዱስ ፡ ማር ቆስም ፡ ከጳውሎስና ፡ ከበርናባስ ፡ ጋራ ፡ ከሔደ ፡ በኋላ ፡ ጴጥሮስን ፡ ተከተለው ፡፡ ጴጥሮስም ፡ እጅግ ፡ ወደታልና ፡ ል ጁን ፡ ይለዋል ፡ ፩፡ መልእክቱ ፡ ፭፡ ፲፫፡፡ ማርቆስም ፡ የጌታ ችንን ፡ ወንጌል ፡ ከጴጥሮስ ፡ አፍ ፡ እርሱ ፡ በሮም ፡ ሲሆን ፡ ሰምቶ ፡ እንደ ፡ ጻፈው ፡ ይላል ፡ ቅሌሜንስ ፡ (አቅሌመንጦ ስ ፡) ከስክንድርያ ፡፡ እንደሁም ፡ ሉቃስ ፡ የጌታችንን ፡ ወን ጌል ፡ ከጳውሎስ ፡ አፍ ፡ ሰምቶት ፡ እንደ ፡ ጻፈው ፡ ይላሉ ፡ ሌሎች ፡ መጻሕፍትንም ፡ አይቶ ፡፡

በዚያ ፡ ዘመንም ፡ አይሁድ ፡ ያዕቆብን ፡ የጌታችንን ፡ ወንድም ፡ በየሩሳሌም ፡ ገደሉት ። ያዕቆብ ፡ የየሩሳሌምን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጠበቀ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አገርም ፡ አልሔደም ። ስለዚህም ፡ በማይጉደ ፡ ሥርዓት ፡ ያይሁድን ፡ ወግ ፡ ጠበቀ ፡ ወንጌልን ፡ ሲያስተምር ፡ እንደ ፡ ጳውሎስና ፡ እንደ ፡ ጴጥሮስ ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ሁኖ ። እርሱም ፡ መልእክቱን ፡ ሲጽፍ ፡ እለዚያን ፡ አይሁድ ፡ ገሠጸ ፡ በስም ፡ ክርስቲያን ፡ የሆኑ ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ ግን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ነገር ፡ በመታዘዝ ፡ በጎ ፡ ስራም ፡ በመስራት ፡ ያልገለጹ ። እርሳቸውም ፡ አሉ ። እኛ ፡ በሃይማኖት ፡ እንጸደቃለን ፡ በምግባር ፡ አይደለም ። አሁንም ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ እንደያው ፡ እውነት ፡ ነው ፡ ጳውሎስም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ይናገራል ። እሌህ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ ሃይማኖትን ፡ አያውቁም ፡ ነበሩ ። የሚያጸድቅ ፡ ሃይማኖት ፡ ጳውሎስም ፡ ስለሚናገር ፡ የልብ ፡ ሕይወት ፡ ነውና ፡ የልብም ፡ አንድነት ፡ ከክርስቶስ ፡ ጋራ ፡ ያለርሱም ፡ ሰው ፡ ከቶ ፡ አይድንም ፡ ያለርሱም ፡ በውነት ፡ በጎ ፡ የሚሆን ፡ ስራ ፡ መስራት ፡ አይቻልም ። የሚጸደቅም ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ ሃይማኖት ፡ ብቻ ፡ ይጸደቃል ፡ በተግባርም ፡ አይደለም ። በሰው ፡ ፊት ፡ ግን ፡ ሃይማኖት ፡ ከቶ ፡ አይገለጽም ፡ በተግባር ፡ እንጂ ። እለዚያ ፡ ሰዎች ፡ ግን ፡ እናምናለን ፡ በሃይማኖትም ፡ እንጸደቃለን ፡ ያሉ ፡ ባፉቸው ፡ ብቻ ፡ አመኑ ፡ የሃይማኖት ፡ ዕውቀት ፡ የሃይማኖትም ፡ ትምህርት ፡ ነበረላቸው ፡ የሃይማኖት ፡ ባሕሪ ፡ ግን ፡ የሃይማኖትም ፡ ኃይል ፡ አልገባቸውም ። ስለዚህም ፡ ያዕቆብ ፡ ይላል ። ሃይማኖት ፡ ያለ ፡ ምግባር ፡ አያጸድቅም ። ደሮ ፡ የጳውሎስ ፡ ሃይማኖት ፡ ከቶ ፡ አይገኝም ፡ ከበጎ ፡ ስራ ፡ ጋራ ፡ እንጂ ። የያዕቆብም ፡ ማለት ፡ ይህ ፡ ነው ። ለእግዚአብሔር ፡ ነገር ፡ በመታዘዝ ፡ የርሱንም ፡ ፈቃድ ፡ በማድረግ ፡ ሃይማኖታችሁን ፡ ግለጡ ፡ እውነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ። ያለዚህ ፡ ሃይማኖታችሁ ፡ በከንፈራችሁ ፡ ብቻ ፡ ኑርዋልና ፡ ዝምብሎ ፡ ነው ፡ አይጠቅምም ፡ አያጸድቅምም ። ጳውሎስ ፡ ደግሞ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ። የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ በመናገር ፡ አትኖርም ፡ በኃይል ፡ እንጂ ። አሁ

ንም ፡ አይሁድ ፡ ይህነን ፡ ሐዋርያ ፡ በመጀመርያ ፡ አከበሯ
ት ፡ ያዕቆብንም ፡ ጻድቅ ፡ አሉት ፡ ጸላትነታቸው ፡ በክርስቲያ
ን ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡ እስኪበዛ ፡ ድረስ ፡፡ ጳውሎስም ፡ ወደ ፡ ሮም ፡
ከሔደ ፡ በኋላ ፡ የካህናት ፡ አለቃ ፡ ሐናንያ ፡ እርሱም ፡ ደግ
ሞ ፡ አናኖስ ፡ የተባለ ፡ አስያዘው ፡ ወደ ፡ ሸንጎም ፡ አስመጣ
ው ፡፡ ከዚያም ፡ መክሰሳቸው ፡ እውነት ፡ ሁኖ ፡ ባልተገለ
ጸ ፡ ጊዜ ፡ በመቅደስ ፡ ጠፈር ፡ ላይ ፡ ወሰዱት ፡ ከዚያ ፡ በሕ
ዝብ ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡ ክርስቶስን ፡ ሊክድ ፡ ብለው ፡ ፈቢካ ፡
ሁንዋልና ፡፡ እርሱ ፡ ግን ፡ ከዚያ ፡ በኃይል ፡ ለክርስቶስ ፡ መ
ሰከረ ፡፡ የሕዝብም ፡ አለቆች ፡ ተቈጥተው ፡ አስጣሉት ፡
ወደ ፡ ታች ፡ በታችም ፡ አስወገሩት ፡፡ እርሱም ፡ ሳይሞት ፡
ተንበርክኮ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ ለመነላቸው ፡፡ አቤቱ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ አብ ፡ እኔ ፡ እለምንላቸዋለሁ ፡፡ የሚያድርጉት
ን ፡ አያውቁምና ፡፡ አንድ ፡ ካህንም ፡ ይህነን ፡ ሰምቶ ፡ አ
ላቸው ፡ ተው ፡ ምንድር ፡ ታድርጋላችሁ ፡፡ ይህ ፡ ጻድቅ ፡ ሰ
ው ፡ ስለላንት ፡ ይጸልያል ፡፡ ደሮ ፡ እለዚያ ፡ አቡደን ፡ አልሰ
ሙም ፡ በታላቅ ፡ እንጨት ፡ ራሱን ፡ ቀጥቅጠው ፡ ገደሉት ፡
እንጅ ፡፡ ይህም ፡ ሆነ ፡ በልደት ፡ አመት ፡ ፷፪ ፡ ወይስ ፡ ፷፫ ፡፡

አሁንም ፡ የነቢያት ፡ ትንቢት ፡ ስለ ፡ መድኃኒታችን ፡ ተ
ፈጸመ ፡፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅም ፡ በባርነት ፡ መልክ ፡ በ
ምድር ፡ ተመላለሶ ፡ በመስቀል ፡ ስለ ፡ ኃጢአታችን ፡ ሞ
ተ ፡፡ ከሙታንም ፡ ተነሣ ፡፡ ሐዋርያትንም ፡ ላከ ፡፡ ወደ ፡ ሰ
ማይም ፡ ወጣ ፡፡ መንፈሱንም ፡ በሐዋርያት ፡ ላይ ፡ ሰደደ ፡፡
ከእሥራኤል ፡ ወገኖችም ፡ የተመረጹትን ፡ ወደ ፡ ጉባኤ
ው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰበሰበ ፡፡ እርሳቸውም ፡ የወ
ንጌልን ፡ ኃይል ፡ የክርስቶስንም ፡ የስሙን ፡ ታላቅነት ፡ ባ
ሕዛብ ፡ መካከል ፡ አወሩት ፡፡ ብዙ ፡ አእላፋትም ፡ የክርስ
ቶስን ፡ መድኃኒት ፡ በሃይማኖት ፡ ተቀብለው ፡ በሰው ፡ መ
ካከል ፡ አዲስ ፡ ወገን ፡ ሆኑ ፡ የክርስቶስ ፡ የሁለተኛ ፡ አደ
ም ፡ ትውልድ ፡፡ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ በም
ድር ፡፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡፡ እርሳቸውም ፡ የዘላለምን ፡

ወንጌል ፡ ከሐዋርያት ፡ አፍ ፡ ከጀቸውም ፡ ተቀበሉ ፡፡ ክር ስቶስም ፡ ተስፋ ፡ አስደረገላቸው ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ደኖር ፡ ዘንድ ፡ በቃሉም ፡ በመንፈሱም ፡ ደምራቸው ፡ ዘንድ ፡ እ ስከ ፡ ዓለም ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፡፡

እግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ደሰጥ ፡ የነበረውን ፡ ተስፋ ፡ አሁን ፡ ፈጽምዋልና ፡ ባደሁድ ፡ ላይ ፡ የተናገረውን ፡ ቅያሜውን ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ ሊፈጽም ፡ ነበር ፡፡ እርሱ ፡ በ ምህረቱ ፡ የእሥራኤልን ፡ ወገን ፡ አስቀድሞ ፡ ካሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ መረጸ ፡ ሕዝቡ ፡ ደሆኑለት ፡ ዘንድ ፡ እርሱም ፡ ማለ ላቸው ፡ አምላካቸው ፡ ደሆንላቸው ፡ ዘንድ ፡፡ በሙሴ ፡ አ ፍም ፡ አላቸው ፡፡ በመንገዴ ፡ ብትመላለሱ ፡ ሥርዓቴንም ፡ ብትጠብቁ ፡ በደህንነት ፡ ትኖራላችሁ ፡ በፊቴ ፡፡ እምቢ ፡ ግ ን ፡ ብትሉ ፡ ሕጌንም ፡ ብታፈርሱ ፡ እኔንም ፡ ብትጣሉኝ ፡ ኤኔም ፡ ከፊቴ ፡ ዘንድ ፡ እጥላችኋላሁ ፡ በምድር ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ባሕዛብም ፡ ሁሉ ፡ መኻከል ፡ እበትናችኋለሁ ፡፡ እላ ንትም ፡ ሕዝቤ ፡ የነበራችሁ ፡ በምህረቴ ፡ ስለ ፡ ኃጢአታች ሁ ፡ የተጣላችሁ ፡ ትሆናላችሁ ፡፡ ሕዝቤም ፡ ያልሆነውን ፡ እመርጻለሁ ፡ ሕዝቤ ፡ ደሆን ፡ ዘንድ ፡፡ አሁንም ፡ አደሁድ ፡ አ ንድ ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ የተጣሉ ፡ ነበሩ ፡ ወደ ፡ ባቢሎን ፡ በተማ ረኩ ፡ ጊዜ ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ አዘነላ ቸው ፡ ወደ ፡ አገራቸውም ፡ መለሳቸው ፡ መቅደሱም ፡ መ ለሰላቸው ፡፡ በባሮቹም ፡ ሁሉ ፡ አፍ ፡ በብዙ ፡ ምሳሌም ፡ በብዙ ፡ ነገርም ፡ ከተናገራቸው ፡ በኋላ ፡ በዘመን ፡ ፍጻሜ ፡ የተወደደውን ፡ ልጁን ፡ ሰደደላቸው ፡፡ ደር ፡ የሱስ ፡ ክርስቶ ስ ፡ ወደ ፡ ወገኖቹ ፡ ገብቶ ፡ ወገኖቹ ፡ አልተቀበሉትም ፡ ጸሉ ት ፡ እንጅ ፡ ጣሉትም ፡ ሰቀሉትም ፡፡ በልባቸውም ፡ መጥ ማማት ፡ ጸሩ ፡፡ ደሙ ፡ በላያችን ፡ በልጆቻችን ፡ ላደም ፡ ደሁን ፡፡ እንዴሁም ፡ ሆነ ፡ እርሳቸው ፡ እንደ ፡ ወደዱት ፡ ነ ቢያትም ፡ ክርስቶስም ፡ እንደ ፡ ተነበዩት ፡፡

ገሥዩስ ፡ ፍሎሩስ ፡ በደሁዳ ፡ ላይ ፡ የተሾመ ፡ ከኔሮን ፡ በታች ፡ ክፉ ፡ ባደረገባቸው ፡ ጊዜ ፡ በልደት ፡ አመት ፡ ፷፮፤ አደሁድ ፡ ዐመፁ ፡ ከሮም ፡ መንግሥት ፡፡ የሶርያ ፡ ሹምም ፡ አሁን ፡ በየሩሳሌም ፡ ላይ ፡ መጣ ፡ ከሠራዊቱ ፡ ጋራ ፡ ከበ

ባትም ፡፡ ደሮ ፡ አይሁድ ፡ መቶት ፡ ስልፍንም ፡ አደረጉ ፡፡ ቄ
ሣር ፡ ኔሮንም ፡ ይህነን ፡ ሲሰማ ፡ የሠራዊቱን ፡ አለቃ ፡ ወስ
ጳስያኑስን ፡ ሰደደባቸው ፡፡ ያም ፡ ብዙ ፡ አምቦችን ፡ ከርሳቸ
ው ፡ ወሰደ ፡፡ የሩሳሌምን ፡ ግን ፡ ሳይወስድ ፡ ኔሮን ፡ ሞተ ፡፡
ወስጳስያኑስም ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ ተመለሰ ፡ ጥቂት ፡ ቀንም ፡ በ
ኋላ ፡ ነገሠ ፡፡ ልጁን ፡ ግን ፡ ቲቶስን ፡ በይሁዳ ፡ አገር ፡ ተወ ፡
ጦሩን ፡ ይጨርስ ፡ ዘንድ ፡፡ ቲቶስም ፡ ሠራዊቱን ፡ ወደ ፡ የ
ሩሳሌም ፡ ወሰዳቸው ፡ ከተማውንም ፡ በፋሲካ ፡ በዓል ፡
ከበባት ፡ ሰው ፡ በመላባት ፡ ጊዜ ፡፡ አይሁድም ፡ እርሱ ፡ በ
ርሳቸው ፡ ተለዩ ፡ በመኻከላቸውም ፡ እጅግ ፡ ደምን ፡ አፈ
ሰሱ ፡፡ ፫፡ መለያታቸውም ፡ በከተማ ፡ በቤተ ፡ መቅደስም ፡
እርሱ ፡ በርሳቸው ፡ ቀሙ ፡ ገደሉም ፡ አጐሰቈሉም ፡፡ ባን
ድ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ አንድነትን ፡ አደረጉ ፡ እምቢ ፡ በማለት ፡
ለሮም ፡ ሰዎች ፡ ይገዙ ፡ ዘንድ ፡፡ ቲቶስ ፡ ግን ፡ ቸር ፡ ነበረላቸ
ው ፡፡ የሩሳሌምንም ፡ ያፈርስ ፡ ዘንድ ፡ አልወደደም ፡፡ እር
ሳቸውም ፡ ካዘኑ ፡ እርሱ ፡ ባዘነላቸው ፡፡ እርሳቸው ፡ ግን ፡
በኃጢአታቸው ፡ ደፈሩ ፡ ረደትንም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ከሰ
ማይ ፡ ጠበቁ ፡ ባለመታዘዛቸው ፡ ዋጋ ፡፡ አሁንም ፡ ታላቅ ፡
ራብ ፡ ሆነ ፡ በከተማ ፡፡ አያሌ ፡ ሰዎች ፡ ሸሹ ፡፡ የሮም ፡ ወታ
ደሮች ፡ ግን ፡ አስቀድሞ ፡ በማርዋቸው ፡ አሁን ፡ ምህረት ፡
አያውቁም ፡ ነበረ ፡፡ ወደርሳቸው ፡ የሸሹትን ፡ አይሁድ ፡
ባገር ፡ ፊት ፡ ሰቀልዋቸው ፡፡ በጊዜም ፡ ፳፻፡ አይሁድን ፡ ሰ
ቀሉ ፡ በየሩሳሌም ፡ ፊት ፡፡ አንዲት ፡ ሴትም ፡ ከታላላቆ
ች ፡ ወገን ፡ ልጅዋን ፡ ገድላ ፡ ስትበላው ፡ ተገኘች ፡ ከራብ ፡
የተነሣ ፡፡ ተርበውም ፡ የሞቱ ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ነበሩ ፡፡

የሩሳሌምም ፡ እጅግ ፡ ብርቱ ፡ ተሠርታ ፡ ነበረች ፡፡ በዙር
ያዋ ፡ ሁሉ ፡ አያሌ ፡ ብርቶች ፡ መከበብዮች ፡ ካምቦችና ፡
ከግምቦች ፡ ጋራ ፡ ነበሩ ፡፡ የሮም ፡ ወታደሮች ፡ ግን ፡ በዚህ ፡
ሁሉ ፡ በዙርያ ፡ ሌላ ፡ ብርቱ ፡ ቅጥር ፡ አደረጉ ፡ ታላቆችን
ም ፡ ግምቦች ፡ ሰሩ ፡ በንጬትና ፡ በብረት ፡ ያገርን ፡ ቅጥሮ
ች ፡ የሚያፈርሱበት ፡ ታላቅ ፡ ደንጊያውንም ፡ ወደገር ፡ የ
ሚጥሉበት ፡፡ አይሁድም ፡ እጅግ ፡ ደከሙ ፡ የሮምን ፡ ጭ
ፍሮች ፡ ሊከለክሉ ፡ እጅግ ፡ ብልሃትም ፡ እጅግ ፡ ኃይልም ፡

አደረጉ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ጸላቶቻቸው ፡ በጥቂት ፡ በጥቂት ፡ ገቡ ፡ ወደ ፡ መቅደስም ፡ ቀረቡ ፡፡ ቲቶስም ፡ በብርቱ ፡ ቃል ፡ ወታደሮቹን ፡ ሁሉን ፡ ለመቅደስ ፡ ሊያዝኑ ፡ አዘዛቸው ፡፡ ደሮ ፡ ያይሁድ ፡ ጭፍሮች ፡ በመቅደስ ፡ ውሥጥ ፡ አዘምተዋልና ፡ በቲቶስ ፡ ላይ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ሮማዊ ፡ እሳት ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ መቅደስ ፡ ጣለው ፡ መቅደስም ፡ ነደደ ፡ ሁሉም ፡ እስኪፈጅ ፡ ድረስ ፡ ተቃጠለ ፡፡ የክርስቶስም ፡ ትንቢት ፡ እንደዬህ ፡ ሲል ፡ ተፈጸመ ፡፡ ደንጊያ ፡ በደንጊያ ፡ ላይ ፡ አይኖርም ፡፡ የሮም ፡ ጭፍሮችም ፡ በየሩሳሌም ፡ በዚያ ፡ ጦር ፡ የገደልዋቸው ፡ አይሁድ ፡ ፲፻፻፻፡ የመረኩትም ፡ ፻፻፻፡ ነበሩ ፡፡ የክርስቲያን ፡ ጉባኤ ፡ ግን ፡ በጦር ፡ መጀመርያ ፡ ከየሩሳሌም ፡ ሸሹ ፡ በዮርደኖስ ፡ ማደም ፡ ጸላ ፡ በሚልዋት ፡ አገር ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠበቃቸው ፡ መጸጀም ፡ አደረገላቸው ፡፡

አሁንም ፡ ካይሁድ ፡ የወጡ ፡ ክርስቲያናት ፡ መቅደሳቸው ፡ ከፈረሰ ፡ በኋላ ፡ ወገኖቻቸውም ፡ ከተበተኑ ፡ በኋላ ፡ ግንደኞች ፡ አልተከለከሉም ፡ አንድነትን ፡ ከማድረግ ፡ ከወንድሞቻቸው ፡ ጋራ ፡፡ ክርስቶስም ፡ ስለዚህ ፡ በጅ ፡ የተሰራችን ፡ መቅደስ ፡ አፈረሳት ፡ በጅ ፡ ያልተሰራችን ፡ መንፈሳዊት ፡ መቅደሱን ፡ በሰው ፡ ልብ ፡ ያለቸውንም ፡ መንግሥቱን ፡ መልካም ፡ ይሰራት ፡ ዘንድ ፡፡ ከርሳቸውም ፡ ብዙ ፡ አንድነትን ፡ አደረጉ ፡ ካሕዛብ ፡ ከወጡ ፡ ክርስቲያን ፡ ጋራ ፡፡ ተከፍለው ፡ ግን ፡ በጣም ፡ ወደ ፡ ወንጌል ፡ ብርሃን ፡ አልደረሱም ፡፡ እርሳቸውም ፡ ለራሳቸው ፡ ቤተ ፡ መቅደስን ፡ ሰሩ ፡ የሩሳሌም ፡ ወደ ፡ ነበረችበት ፡ ቦታ ፡ ኤልያ ፡ ከጲቶሊና ፡ በተባለች ፡ አገር ፡፡ እርሳቸውም ፡ መናፈቃን ፡ ሁነው ፡ ተቈጠሩ ፡ በ፪፡ ወገንም ፡ ተለዩ ፡ እኩሌታቸውም ፡ ኤቢዮናውያን ፡ እኩሌታቸውም ፡ ናዝሬናውያን ፡ ተባሉ ፡፡ እርሳቸውም ፡ ያይሁድን ፡ ወግ ፡ እንደ ፡ ቸሎታቸው ፡ ተከተሉ ፡ እስከ ፡ ሃድርያኖስ ፡ ቄሣር ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡፡

ከሐዋርያትም ፡ የቀረ ፡ የሩሳሌም ፡ ከተደመሰሰች ፡ በኋ

ላ ፡ ዮሐንስ ፡ ነው ፡፡ እርሱም ፡ በታናሽ ፡ እስያ ፡ ባብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መኻከል ፡ ዞረ ፡ ወንጌልን ፡ ሲያስተምር ፡ ምእምናንንም ፡ ሲያጸና ፡ ሲጠብቃቸውም ፡ እስከ ፡ ሸምግ ልናው ፡ ድረስ ፡፡

እሌህም ፡ ቄሣሮች ፡ ነበሩ ፡ ከኔሮን ፡ በኋላ ፡ እስከ ፡ ዮሐ ንስ ፡ ሞት ፡ ድረስ ፡፡

፩፡፡ ገልባ ፡ ኦቶንም ፡ ዊተልዩስም ፡፡ ኔሮን ፡ ሲሞት ፡ እለዚ ህ ፡ ፫፤ የሠራዊት ፡ አለቆች ፡ ነበሩ ፡፡ ከሶስታቸውም ፡ ኢያ ንደንዱ ፡ ሊነግሥ ፡ ፈለገ ፡ ለሁላቸው ፡ ግን ፡ አልሆነም ፡፡

፪፡፡ ቄሣር ፡ ወስጳስያኑስ ፡ ነገሠ ፡ ከልደት ፡ ኣመት ፡ ከ ፷፱፤ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፸፱፤ ድረስ ፡፡

፫፡፡ ቄሣር ፡ ቲቱስ ፡ ነገሠ ፡ ከ፸፱፤ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፹፩፤ ድረስ ፡፡

፬፤ ቄሣር ፡ ደሚቲያኑስ ፡ ነገሠ ፡ ከ፹፩፤ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፺፮፤ ድረስ ፡፡

፭፤ ቄሣር ፡ ነርዋ ፡ ነገሠ ፡ ከ፺፮፤ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፺፰፤ ድ ረስ ፡፡

ከለዚህ ፡ ሁሉም ፡ ደሚቲያኑስ ፡ ከፋ ፡፡ እርሱም ፡ የወስ ጳስያኑስ ፡ ልጅ ፡ የቲቱስም ፡ ወንድም ፡ ነበረ ፡፡ ባካሔዱ ፡ ግ ን ፡ በስራውም ፡ ኔሮን ፡ መሰለ ፡፡ ሰውንም ፡ ሁሉን ፡ በድልዋ ልና ፡ ከሰው ፡ ሁሉ ፡ ፈራ ፡፡ ስለ ፡ ንጉሥም ፡ ከደዊት ፡ ትው ልድ ፡ ወሬ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ መረመረ ፡ በክርስቲያ ንና ፡ ባይሁድ ፡ መኻከል ፡ ምናልባት ፡ ሰው ፡ እንደልቀረ ፡ ንጉሥ ፡ ሊሆን ፡ ጊዜ ፡ ላለው ፡፡ በኋላም ፡ ፪፤ ሰዎች ፡ ተገኙ ፡ የየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ዘመዶች ፡ በሥጋ ፡ የነበሩ ፡፡ እርሳቸው ንም ፡ አስመጣቸው ፡፡ እጆቻቸውን ፡ ግን ፡ ሲያይ ፡ ቆርበታ ቸው ፡ እንደ ፡ ሸከረ ፡ እንደ ፡ በረታም ፡ ከጅግ ፡ ስራ ፡ የተነ ሣ ፡ ድኅነታቸውንም ፡ ሲሰማ ፡ እንዲያው ፡ ሰደዳቸው ፡፡ ስለዚህ ፡ ግን ፡ ክርስቲያንን ፡ ሁሉን ፡ ማሳደድ ፡ አልተወ ም ፡፡ ከቄሣር ፡ ዘመዶች ፡ እንኳ ፡ አያሌን ፡ አስገደለ ፡ ክር ስቲያን ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡፡ ዮሐንስንም ፡ ሐዋርያውን ፡ ከኤፌሶ ን ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ እንደስመጣ ፡ ይላሉ ፡ ከዚያም ፡ ሁኖ ፡ ወ ደ ፡ ታላቅ ፡ ድስት ፡ የፈላ ፡ ዘይት ፡ የመላበት ፡ አስገባው ፡

ለዮሐንስም ፡ እንደ፡ደጉደ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ጳጥሞስ ፡ ደ
ሴት ፡ ሰደደው ፡፡ በጳጥሞስም ፡ ሲሆን ፡ ጌታችን ፡ ታየለት ፡
ተግሣጹንም ፡ ሰጠው ፡ ለ፯፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ በታና
ሽ ፡ እስያ ፡ ለነበሩ ፡፡ እስከ ፡ ኋለኛ ፡ ዘመንም ፡ ለቤተ ፡ ክ
ርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ የሚሆነ
ውን ፡ ነገር ፡ ሁሉን ፡ መጋደልዋን ፡ መከራዋንም ፡ ድልዋን
ም ፡ ክብርዋንም ፡ ገለጸለት ፡፡ ዮሐንስም ፡ ይህነን ፡ ከጻፈ ፡
በኋላ ፡ ደሚቲያኑስ ፡ ሞተ ፡፡ ምሽቱ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ታናሽ ፡
ወረቀት ፡ በመሬት ፡ አገኘታለችና ፡ ደሚቲያኑስ ፡ እርስዋን ፡
ካያሌ ፡ ታላላቆች ፡ ጋራ ፡ ደገድሉ ፡ ዘንድ ፡ ትእዛዝ ፡ የጻ
ፈበት ፡፡ ይህነንም ፡ ባወቀች ፡ ጊዜ ፡ ለወደጀችዋ ፡ ተናገረ
ች ፡፡ እርሳቸውም ፡ ባንድ ፡ ወደ ፡ አደራሹ ፡ ገብተው ፡ ገደሉ
ት ፡፡ በርሱም ፡ ፈንታ ፡ ነርዋ ፡ በመንግሥት ፡ ዙፋን ፡ ተቀመ
ጠ ፡፡ እርሱም ፡ ደህና ፡ ቄሣር ፡ ነበረ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡
ከርሱ ፡ በታች ፡ ጥቂት ፡ ዕረፍት ፡ አገኘች ፡፡ ደሮ ፡ እጅግ ፡
አልኖረም ፡ ፭፡ አመት ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡፡ በዚያም ፡ ወራት ፡
ዮሐንስ ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ኤፌሶን ፡ ተመለሰ ፡ ከዚያም ፡ ሞ
ተ ፡ ምእምናንን ፡ ወትሩ ፡ ከመከረ ፡ በኋላ ፡ እንደህ ፡ ሲ
ል ፡፡ ሕፃናቴ ፡ ሆይ ፡ እርሱ ፡ በርሳችሁ ፡ ተዋደዱ ፡፡

ስለ ፡ ጌታችን ፡ ሐዋርያት ፡ ከተጻፈ ፡ ወደኛም ፡ ከደረሰ ፡
ወሬ ፡ እውነት ፡ የሚመስል ፡ ደህ ፡ ነው ፡ ያጻፍነ ፡፡ ሌላ ፡
ወሬም ፡ ብዙ ፡ አለ ፡ እውነት ፡ የሌለበት ፡ ሰውንም ፡ ለማ
ክበር ፡ ብቻ ፡ ክፉ ፡ ትምርትንም ፡ ለማጽናት ፡ የተጻፈ ፡፡ ለ
ኛ ፡ ግን ፡ ደበቃል ፡ እናውቅ ፡ ዘንድ ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ቃ
ሉን ፡ እንደ ፡ ሰጠ ፡ በሐዋርያትና ፡ በወንጌላውያን ፡ ባፉ
ቸውና ፡ በጽፈታቸውም ፡ ትምርት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡
እንደ ፡ መሰረተ ፡ ለዘወተርም ፡ እንደ ፡ ገዛባት ፡፡ በዚህ ፡ ቃ
ል ፡ ነውና ፡ የቀደሙ ፡ ምእምናን ፡ የደኑበት ፡ የበረቱበ
ትም ፡፡ ስለርሱም ፡ ሕደወታቸውን ፡ አልወደዱም ፡ እስከ ፡
ሞት ፡ ድረስ ፡፡ ደማቸውንም ፡ አፈሰሱ ፡ በደስታ ፡፡ በዚህ ፡
ቃል ፡ እርሱን ፡ አውቀውታልና ፡ አስቀድሞ ፡ የወደደነ ፡ ነፍ
ሱንም ፡ ስለኛ ፡ የለወጠ ፡፡ ደህ ፡ ቃልም ፡ ከሐዋርያት ፡ ዘ
መን ፡ ወደህ ፡ ከሰው ፡ ቃል ፡ ጋራ ፡ በተደበለቀ ፡ ጊዜ ፡ ጨ

ለማ ፡ ሆነ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡፡ የክርስቶስ ፡ መንፈስ ፡ ሸ
ሸ ፡ የክርስቶስ ፡ ስም ፡ ብቻ ፡ ቀረ ፡፡

ያደ፡ስ ፡ ሥርዓትም ፡ መጻሕፍት ፡ ከብሉይ ፡ መጻሕ
ፍት ፡ ጋሪ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ሁኖ ፡ የተቈጠረ ፡ ከ
ሰውም ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ ከበጎም ፡ ከክፉም ፡ የተለዩ ፡ እሌ
ህ ፡ ናቸው ፡፡

፩። የማቴዎስ ፡ ወንጌል ፡፡
፪። የማርቆስ ፡ ወንጌል ፡፡
፫። የሉቃስ ፡ ወንጌል ፡፡
፬። የዮሐንስ ፡ ወንጌል ፡፡
፭። የሐዋርያት ፡ ስራ ፡ በቅዱ፡ስ ፡ ሉቃስ ፡ የተጻፈ ፡፡
፮፡ የጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ ሰዎች ፡፡
፯፡ ፰። የጳውሎስ ፡ ፪፡ መልእክቶች ፡ ወደ ፡ ቆሮንቶስ ፡ ሰዎች ፡፡
፱። የጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ ገላትያ ፡ ሰዎች ፡፡
፲። የጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ ኤፌሶን ፡ ሰዎች ፡፡
፲፩። የጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ ፊልጵስዩስ ፡ ሰዎች ፡
፲፪። የጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ ቈሎሳይስ ፡ ሰዎች ፡፡
፲፫፡ ፲፬፡ የጳውሎስ ፡ ፪፡ መልእክቶች ፡ ወደ ፡ ተሳሎንቄ ፡ ሰዎች ፡፡
፲፭፡ ፲፮። የጳውሎስ ፡ ፪፡ መልእክቶች ፡ ወደ ፡ ጢሞቴዎስ ፡፡
፲፯። የጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ ቲቶስ ፡፡
፲፰፡ የጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ ፊልሞን ፡፡
፲፱፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ ዕብራውያን ፡፡
፳፡ የያዕቆብ ፡ ካቶሊካዊት ፡ መልእክት ፡፡
፳፩፡ ፳፪፡ የጴጥሮስ ፡ ፪፡ ካቶሊካውያን ፡ መልእክቶች ፡፡
፳፫፡ ፳፬፡ ፳፭። የዮሐንስ ፡ ፫፡ መልእክቶች ፡፡
፳፮፡ የይሁዳ ፡ ካቶሊካዊት ፡ መልእክት ፡፡
፳፯። የዮሐንስ ፡ ራእይ ፡ አጶካልጵሲስ ፡ ἀποκάλυψις የተባለች ፡፡

መጀመርያ ፡ ክፍል ፡ ተጨረሰች ፡፡

፩፡ ቆሮንቶስ ፡ ፫፡ ፲፩።

ማንም ፡ አይችልም ፡ ሌላውን ፡ መሠረት ፡ ይመሠርት ፡
ዘንድ ፡ ከዚያ ፡ ከተመሠረተው ፡ በቀር ። እር
ሱም ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ።

የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ታሪክ፡

ሁለተኛ ፡ ክፍል ፡፡

እርሱም ፡

የቤት ፡ ክርስቲያን ፡ ታሪክ፡

ከዮሐንስ ፡ ከሐዋርያ ፡ ሞት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘመናችን ፡
ድረስ ፡፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ ከ፻፡ አመት ፡
ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፲፰፻፷፩፡ ድረስ ፡፡

ዮሐንስ ፡ ፲፰፡ ፴፮።

መንግሥቴ ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ አይደለችም ፡፡

መቅደም ::

አሁንም ፡ በጥቂት ፡ ቃል ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ታሪክ ፡ እንናገራለን ፡ ከዮሐንስ ፡ ከሐዋርያ ፡ ሞት ፡ ጀምረን ፡ እስከ ፡ ዘመናችን ፡ ድረስ ፡፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ ከ፩፡ አመት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፲፰፷፩፡ ድረስ ፡፡

ደህነንም ፡ ታሪክ ፡ በ፰፡ ክፍል ፡ እንከፍላለን ፡፡

፩፡፡ መጀመርያ ፡ ክፍል ፡፡ ከዮሐንስ ፡ ከሐዋርያ ፡ ሞት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ታላቅ ፡ ቈንስታንቲኖስ ፡ እስከ ፡ መንግሥቱ ፡ መጀመርያ ፡ ድረስ ፡፡ ካመት ፡ ፩፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፫፻፲፪፡ ድረስ ፡፡

፪፡፡ ሁለተኛ ፡ ክፍል ፡፡ ከቈንስታንቲኖስ ፡ ከመንግሥቱ ፡ መጀመርያ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሮም ፡ ጳጳስ ፡ እስከ ፡ ታላቅ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ሹመት ፡ ድረስ ፡፡ ካመት ፡ ፫፲፪፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፭፺፡ ድረስ ፡፡

፫፡፡ ሶስተኛ ፡ ክፍል ፡፡ ከታላቅ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ከሮም ፡ ጳጳስ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፈረንጅ ፡ ንጉሥ ፡ እስከ ፡ ታላቅ ፡ ከርል ፡ እስከ ፡ ሞቱ ፡ ድረስ ፡፡ ከልደት ፡ አመት ፡ ፭፺፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፰፲፬፡ ድረስ ፡፡

፬፡፡ አራተኛ ፡ ክፍል ፡፡ ከፈረንጅ ፡ ንጉሥ ፡ ከታላቅ ፡ ከርል ፡ ከሞቱ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሮም ፡ ጳጳስ ፡ እስከ ፡ ሰባተኛ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ድረስ ፡፡ ካመት ፡ ፰፲፬፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፲፻፸፫፡ ድረስ ፡፡

፭፡፡ አምስተኛ ፡ ክፍል ፡፡ ከሮም ፡ ጳጳስ ፡ ከሰባተኛ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሮም ፡ ጳጳስ ፡ እስከ ፡ ስምንተኛ ፡ ቦኒፋኪዮስ ፡ ድረስ ፡፡ ከልደት ፡ አመት ፡ ከ፲፻፸፫፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፲፪፺፬፡ ድረስ ፡፡

፮፡፡ ስድስተኛ ፡ ክፍል ፡፡ ከሮም ፡ ጳጳስ ፡ ከስምንተኛ ፡

ቦኒፋኪዩስ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መታደስ ፡ ድረስ ፡፡ ካመት ፡ ፲፪፺፬፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፲፭፲፯፡ ድረስ ፡፡

፯፡፡ ሰባተኛ ፡ ክፍል ፡፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከመታደስዋ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ መዘረጋትዋ ፡ ድረስ ፡፡ ከልደት ፡ አመት ፡ ከ፲፭፲፯፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡፲፯፹፱፡ ድረስ ፡፡

፰፡፡ ስምንተኛ ፡ ክፍል ፡፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከመዘረጋትዋ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዘመናችን ፡ ድረስ ፡፡ ከ፲፯፹፱፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፲፰፵፩፡ ድረስ ፡፡

የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
ታሪክ ፡

መጀመርያ ፡ ክፍል ፡፡

ከዮሐንስ ፡ ከሐዋርያ ፡ ሞት ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ታላቅ ፡ ቈን
ስታንቲኖስ ፡ መንግሥት ፡ ድረስ ፡፡

ከልደት ፡ አመት ፡ ፻፤ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፫፻፴፯፤ ድረስ ፡፡

በዚህ ፡ ዘመን ፡ የነገሡ ፡ ቄሣሮች ፡ እሌህ ፡ ናቸው ፡፡

፩፡፡ ትራያኑስ ፡ ካመት ፡ ፺፰፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፻፲፯፡ ድረስ ፡፡

፪፡ ሃድርያኑስ ፡ ከ፻፲፯፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፻፴፰፡ ድረስ ፡፡

፫፡፡ አንቶኒኑስ ፡ ጺዩስ ፡ ከ፻፴፰፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፻፷፩፡ ድረስ ፡፡

፬፡፡ ማርቆስ ፡ አውሬልዩስ ፡ ከ፻፷፩፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፻፹፡ ድረስ ፡፡

፭፡፡ ኮሞዱስ ፡ ከ፻፹፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፻፺፪፡ ድረስ ፡፡

፮፡፡ ጰርቲናክስና ፡ ዩልያኑስ ፡ ባንድ ፡ ነገሡ ፡ ከ፻፺፪፡ ጀምረው ፡ እስከ ፡ ፻፺፫፡ ድረስ ፡፡

፯፡፡ ሰጵቲምዩስ ፡ ሴቤሩስ ፡ ከ፻፺፫፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፪፲፩፡ ድረስ ፡፡

፰፡፡ ከረካላ ፡ ከ፪፲፩፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፪፲፯፡ ድረስ ፡፡

፱፡፡ ማክሪኑስ ፡፡ ፪፲፰፡፡

፲፡፡ ሄልዮገባሎስ ፡ ከ፪፲፰፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፪፳፪፡ ድረስ ፡፡

፲፩፡፡ እስክንድር ፡ ሴቤሮስ ፡ ከ፪፳፪፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፪፴፭፡ ድረስ ፡፡

፲፪፡፡ መክሲሚኑስ ፡ ከ፪፴፭፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፪፴፰፡ ድረስ ፡፡

፲፫፡፡ ጎርዲያኑስ ፡ ከ፪፴፰፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፪፵፬፡ ድረስ ፡፡

፲፬፡፡ ፊልጶስ ፡ ዓረብ ፡ ከ፪፵፬፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፪፵፱፡ ድረስ ፡፡

፲፭፡፡ ዴኪዩስ ፡ ከ፪፵፱፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፪፶፩፡ ድረስ ፡፡

፲፮፡፡ ገሉስ ፡ ከ፪፶፩፡ እስከ ፡ ፪፶፫፡ ድረስ ፡፡

፲፯፡፡ ኤሚልያኑስ ፡ ፪፶፫፡፡

፲፰፡፡ ባሌርያኑስ ፡ ፪፶፫፡ እስከ ፡ ፪፶፯፡፡

፲፱:: ገሉኑስ :: ፪፵፯፡ እስከ ፡ ፪፶፰::
፳:: ቀላውዲዮስ ፡ ጎቲኩስ :: ፪፶፰፡ እስከ ፡ ፪፷::
፳፩:: አውሬልያኑስ ፡ ፪፷፡ እስከ ፡ ፪፷፭::
፳፪:: ታኪቱስ :: ፪፷፮::
፳፫፡ ፍሎርያኑስ :: ፪፷፮::
፳፬፡ አውሬልዮስ ፡ ጵሮቡስ :: ፪፷፮፡ እስከ ፡ ፪፸፪::
፳፭፡ ካሩስ :: ፪፸፪፤ እስከ ፡ ፪፸፫::
፳፮:: ኑሜርያኑስ ፡ ፪፸፫፡ ፪፸፬::
፳፯:: ዲዮቅሌጥያኑስ ፡ ፪፸፬፡ እስከ ፡ ፫:፭፡
፳፰:: ታላቅ ፡ ቆንስታንቲኖስ ፡ ፫:፯፤

መጀመርያ ፡ ምዕራፍ ፡፡

የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መዝረጋትና ፡ መከራ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡፡

፩፡፡ መዝረጋትዋ ፡፡

በዚህ ፡ ዘመን ፡ የወንጌል ፡ ትምህርት ፡ ወደ ፡ ብዙ ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ብዙ ፡ አሕዛብም ፡ ደረሰ ፡ በቀደም ፡ ያላወቁት ፡፡ ከጶንጦስ ፡ ጴጥሮስ ፡ አስቀድሞ ፡ ያስተምር ፡ ከነበረበት ፡ ወንጌል ፡ ወደ ፡ ጶርቲያ ፡ ወደ ፡ ሜዲያም ፡ ወደ ፡ ፋርስ ፡ ምድርም ፡ ደረሰ ፡ ከይሁደም ፡ ወደ ፡ ምሥር ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ዓረብ ፡ ምድርም ፡፡ በምሥርም ፡ ቅዱስ ፡ ማርቆስ ፡ እጅግ ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ ተቀመጠ ፡ በወንጌልም ፡ እንደስተማረ ፡ ጴጥሮስና ፡ ጳውሎስ ፡ ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ደባላል ፡፡

ከሮምም ፡ ወንጌል ፡ ወጣ ፡ ወደ ፡ ከርታጎ ፡ ለሮምም ፡ ወደ ፡ ተገዛች ፡ አፍሪቃ ፡ ሁሉ ፡፡ በኤውሮጳም ፡ ጋልያ ፡ ናት ፡ አሁን ፡ ፈረንሳዎች ፡ ያሉባት ፡ ምድር ፡ ወንጌልን ፡ ከሮም ፡ መጥቶ ፡ የተቀበለች ፡፡ ፯፡ መምህራን ፡ በጋልያ ፡ የወንጌልን ፡ ትምህርት ፡ አስተማሩ ፡ እጅግ ፡ ሰዎችም ፡ በክርስቶስ ፡ አመኑ ፡፡ ደግሞም ፡ ወደ ፡ እንግሊጣር ፡ ደረሰች ፡ የክርስቶስ ፡ ሃይማኖት ፡፡

፪፡፡ መከራዋ ፡፡

ነገር ፡ ግን ፡ የክርስቶስ ፡ ትንቢት ፡ ለክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ የሰጠው ፡፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ ጭንቀት ፡ እንዲያገኙ ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በመከራ ፡ ብቻ ፡ እንዲገቡ ፡ ከሰውም ፡ ሁሉ ፡ የተጸሉ ፡ እንዲሆኑ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ደግሞ ፡ ተፈጸመ ፡፡ የክርስቶስ ፡ መንግሥት ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ወገን ፡ አልነበረችምና ፡፡ በክርስቶስ ፡ የሚያምኑ ፡ የብርሃን ፡ ልጆች ፡ ናቸውና ፡ ከጨለማ ፡ ጋራ ፡ አንድነት ፡ ለ

ሌላቸው ፡ የጨለማንም ፡ ስራ ፡ ሁሉ ፡ የሚገሥጹ ። በዚያ ፡ ዘመንም ፡ የክርስቶስ ፡ ሃይማኖት ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ነበረች ። የሮም ፡ ቄሣሮች ፡ የሰውን ፡ ሃይማኖት ፡ ሁሉን ፡ አልከለከሉም ፡ ከመንግሥታቸው ፡ ሃይማኖት ፡ ጋራ ፡ ባይጸላ ፡ የሮምንም ፡ ሰዎች ፡ ባይከለክል ፡ ከሃይማኖታቸውና ፡ ከወጋቸው ። ደሮ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለዚህ ፡ መጥትዋልና ፡ ዓለምን ፡ ሁሉን ፡ በወንጌል ፡ ባለች ፡ ሃይማኖት ፡ ያድን ፡ ዘንድ ። ስለዚህም ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ ባልንጀሮቻቸውን ፡ የወንጌልን ፡ ትምርት ፡ አስተማርዋቸው ፡ ከጣዖታቸውም ፡ ከኃጢአታቸውም ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ሕያው ፡ አምላክ ፡ ወደ ፡ ልጁም ፡ ወደ ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሊመለሱ ፡ መከርዋቸው ። እርሳቸውም ፡ ባካሔዳቸው ፡ ትምህርታቸውን ፡ ሊያጸኑ ፡ ተጋደሉ ። በዚህም ፡ ሁሉ ፡ የሰውን ፡ ሁሉን ፡ እንደርሳቸው ፡ ያልሆነውን ፡ ጸላትነታቸውን ፡ አስነሡ ፡ ታላቆችና ፡ ታናሾችም ፡ ጥቢባንና ፡ ድናቍርት ፡ ሁሉ ፡ ጸልዋቸው ። ከሌሎች ፡ ይልቅም ፡ ካህናት ፡ ሲያዩ ፡ እጅግ ፡ ሰዎች ፡ የጣዖታትን ፡ ማምለክ ፡ ትተው ፡ ወደ ፡ ክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ እንደመለሱ ። ቄሣሮችም ፡ ባያዝኑላቸው ፡ ተቈጡ ፡ ሲያዩ ፡ የክርስቲያን ፡ ሰዎች ፡ ለቄሣር ፡ አምድና ፡ ሥእል ፡ እንደይሰግዱ ፡ እንደያመልክዋቸውም ።

በትራያኑስ ፡ ዘመን ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ስደት ፡ መጣች ፡ በክርስቲያን ፡ ላይ ። ትራያኑስ ፡ በሌላ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የተመሰገነ ፡ ንጉሥ ፡ ነበረ ። ብርቱ ፡ ቅኝም ፡ ቸርም ፡ የውነትም ፡ ወደጅ ፡ ጠቢብም ። ደሮ ፡ የክርስቲያንን ፡ ነገር ፡ አያስተውልም ፡ ነበረ ፡ እጅግ ፡ መከራም ፡ አመጣባቸው ። እርሱም ፡ አንዱን ፡ መኰንን ፡ ጵሊንዩስ ፡ የሚሉትን ፡ በቢቲንያ ፡ በጶንጦስም ፡ ላይ ፡ ሾመ ። ይህም ፡ ደግሞ ፡ እንደ ፡ ትራያኑስ ፡ በሌላ ፡ ስራው ፡ ሁሉ ፡ ደህና ፡ ሰው ፡ ነበረ ። ጵሊንዩስ ፡ በሹመቱ ፡ እጅግ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰዎች ፡ አገኘ ። የሕዝብም ፡ ወሬ ፡ ስለርሳቸው ፡ እንዲህ ፡ ነበረ ። ክርስቲያን ፡ የተባሉ ፡ ሰዎች ፡ ለጣዖታት ፡ አይሰግዱምና ፡ አምላክ ፡ የላቸውም ። በስውርም ፡ ይሰበሰባሉ ፡ ባጉባኤያቸው ፡ ኃጢአትን ፡ ሁሉን ፡ ለመስራት ። ጵሊንዩስም ፡ በዚህ ፡ ወሬ ፡

እንዲያው ፡ አልታመነም ፡ መረመረ ፡ እንጂ ፡፡ በፊትም ፡ ክርስቲያን ፡ የነበሩትን ፡ በኋላም ፡ የካዱትን ፡ ሰዎች ፡ ጠየቀ ፡፡ እውነትንም ፡ በጣም ፡ ያገኝ ፡ ዘንድ ፡ ብሎ ፡ ፪ ሴቶች ፡ ዲያቆናት ፡ ሠቃየ ፡ ደር ፡ ግን ፡ ከርሳቸው ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ አልሰማም ፡፡ የሰማው ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነበረ ፡፡ በየሳምንት ፡ ባንድ ፡ ቀን ፡ ክርስቲያኖች ፡ ተሰበሰቡ ፡ ቅኔንም ፡ ዘመሩ ፡ ላምላካቸው ፡ ለክርስቶስ ፡፡ እርሱ ፡ በርሳቸውም ፡ ተባበሩ ፡ ለኃጢአትም ፡ አይደለም ፡ ከኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ ለመሸሸት ፡ በጎ ፡ ነገርንም ፡ ሁሉ ፡ ለማድረግ ፡ እንጂ ፡፡ በማታም ፡ ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ተሰበሰቡ ፡ ጥቂት ፡ እራትን ፡ ባንድ ፡ ለመቅመስ ፡፡ አሁንም ፡ ጵሊንዩስ ፡ ይህነን ፡ ለትራያኑስ ፡ ጻፈ ፡ ጠየቀት ፡ ምንድር ፡ ሊያደርግባቸው ፡ እንዴህም ፡ ሲል ፡፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ክርስቲያንን ፡ እንዲያው ፡ አዘዝኋቸው ፡ ያገርን ፡ ልማድ ፡ ሊከተሉ ፡፡ የመንግሥትንም ፡ ሥርዓት ፡ እንደያፈርሱ ፡፡ የቄሣርንም ፡ ዐምድ ፡ ሊያመልኩ ፡ ክርስቶስንም ፡ ሊረግሙ ፡፡ እንደህም ፡ ባያደርጉ ፡ በሞት ፡ ተቃየምኋቸው ፡፡ ፫ ጊዜም ፡ ከተናገርኋቸው ፡ በኋላ ፡ እርሳቸውም ፡ እምቢ ፡ ካሉ ፡ እንደ ፡ ሕግ ፡ ገደልኋቸው ፡፡ ትራያኑስም ፡ የጵሊንዩስን ፡ ማድረግ ፡ በክርስቲያን ፡ ላይ ፡ አመሰገነ ፡ እንደህም ፡ ብሎ ፡ ጨመረ ፡፡ ክርስቲያንን ፡ አትፈልግ ፡፡ ስለርሳቸውም ፡ አትጠይቅ ፡፡ ቢከሰሱ ፡ ግን ፡ መከሰሳቸውም ፡ እውነት ፡ ቢሆን ፡ ይፈረድባቸው ፡፡

በዚያ ፡ ጊዜም ፡ የክርስቲያን ፡ ልብ ፡ ተፈተነ ፡ በስምም ፡ ክርስቲያን ፡ ከነበሩ ፡ ብዙ ፡ ተገኙ ፡ የካዱ ፡ ወደ ፡ ጣዖትም ፡ የተመለሱ ፡፡ ባውነት ፡ ያመኑ ፡ ግን ፡ ሕይወታቸውን ፡ የከበረችን ፡ አልቈጠርዋትም ፡ በክርስቶስም ፡ ጸኑ ፡፡ ከርሳቸውም ፡ ብዙ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖታቸው ፡ ተገደሉ ፡፡ አንድም ፡ ከርሳቸው ፡ ስምዖን ፡ ነበረ ፡ የጌታችን ፡ ዘመድ ፡ የናዝሬናውያንም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በኤልያ ፡ ካጲቶሊና ፡ ዕድሜውም ፡ ፻፳ ዓመት ፡ ነበረ ፡፡ አያሌ ፡ ቀን ፡ ገረፏት ፡ እርሱም ፡ ታገሠ ፡ ፈራጆቹ ፡ እስኪያደንቁ ፡ ድረስ ፡፡ በኋላም ፡ ሰቀሉት ፡፡ እርሱም ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ ሃይማኖቱን ፡ በክርስቶስ ፡ አስታወቀ ፡፡

እንዲሁም ፡ ኢግናትዮስ ፡ ያንጾኪያ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ሞተ ፡ በልደት ፡ አመት ፡ ፻፱። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ትራያኑስ ፡ ከጦር ፡ ተመለሰ ፡ በህንድ ፡ ካደረገ ፡፡ ወደ ፡ አንጾኪያም ፡ ሲደርስ ፡ ኢግናትዮስን ፡ ከሰሎት ፡ ቄሣርም ፡ አስመጣው ፡ ጠየቀውም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ አንተ ፡ እንደምን ፡ ፀመፀኛ ፡ ነህ ፡ ትእዛዛችንን ፡ አፈርሰህ ፡ ሌሎች ፡ ሰዎችንም ፡ ለዚህች ፡ ስንፈና ፡ ታስታቸዋለህ ፡ ጥፋታቸው ፡ ለሚሆንባቸው ፡፡ ኢግናትዮስም ፡ አለ ፡፡ ቴኦፎሮስን ፡ እንዲህ ፡ ብለህ ፡ አትናገር ፡ ክፉች ፡ መናፍስት ፡ ሁሉ ፡ ራቁ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ባሮች ፡ ማሠርያቸውንም ፡ ሁሉ ፡ እቈርጣለሁ ፡ በክርስቶስ ፡ በሰማዩ ፡ ንጉሢ ፡ ረዳት ፡ በልቤ ፡፡ ትራያኑስም ፡ አለው ፡፡ በል ፡ ማነው ፡ ይህ ፡ ቴኦፎሮስ ፡፡ ኢግናትዮስም ፡ መለሰለት ፡ ሲል ፡፡ እርሱ ፡ ነው ፡ ክርስቶስን ፡ በልቡ ፡ የሚሸከመው ፡፡ ትራያኑስ ፡ ጠየቀው ፡ አለውም ፡፡ አንተ ፡ አማልክት ፡ በኛ ፡ ደግመው ፡ ያደሩ ፡ ድልንም ፡ የሚሰጡን ፡ በጸላቶቻችን ፡ ላይ ፡ አይመስልህምን ፡፡ ኢግናትዮስም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለሰለት ፡፡ አንተ ፡ ትስታለህ ፡፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ ብቻ ፡ ነውና ፡ እርሱም ፡ ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ የፈጠረ ፡፡ አንድ ፡ ክርስቶስም ፡ መንግሥቱ ፡ ርስቴ ፡ የምትሆን ፡፡ እርሱም ፡ ኃጢአቴን ፡ ካስደረገው ፡ ጋራ ፡ የሰቀለው ፡ የሰይጣንንም ፡ ክፋትና ፡ ተንኰል ፡ በልባቸው ፡ እርሱን ፡ ለሚሸከሙት ፡ ከግራቸው ፡ በታች ፡ የጣለላቸው ፡፡ ትራያኑስም ፡ መልሶ ፡ ጠየቀው ፡፡ እርሱም ፡ በልብህን ፡ ያኖራል ፡ የተሰቀለ ፡፡ ኢግናትዮስም ፡ መለሰ ፡ አለም ፡፡ አዎን ፡፡ ተጽፏልና ፡፡ እኔ ፡ አድርባቸዋለሁ ፡ እመላለስባቸዋለሁም ፡፡ ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ ትራያኑስ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ፈረደበት ፡፡ ኢግናትዮስ ፡ የተሰቀለውን ፡ በልቡ ፡ እንዲሸከም ፡ ብልዋልና ፡ እኛ ፡ እናዛለን ፡ ታሥሮ ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ ከዚያም ፡ ሕዝቡን ፡ ለመጫወት ፡ ላራዊት ፡ እንዲጥሉት ፡ ለመብላታቸው ፡፡ እንዲህም ፡ ሆነበት ፡፡ ኢግናትዮስም ፡ ስለ ፡ ጌታው ፡ ስም ፡ በደስታ ፡ ሞተ ፡፡

በሃድርያኑስ ፡ ዘመንም ፡ ጥቂት ፡ የተሻለ ፡ ነበረ ፡፡ ደሮ ፡ አይሁድ ፡ ዐምፀዋልና ፡ በየሩሳሌም ፡ በርሳቸው ፡ መ

ክንያት ፡ መከራ ፡ መጣ ፡ በክርስቲያን ፡ ላይ ፡፡ እርሳቸው ፡
ከእግዚአብሔር ፡ የተላከውን ፡ መሢሕ ፡ ያልተቀበሉ ፡ ስ
ለ ፡ መናቁም ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ የተበተኑ ፡ ገና ፡ ሌላ
ውን ፡ መሢሕ ፡ ጠበቁ ፡፡ በዚያ ፡ ዘመንም ፡ አንድ ፡ አሰተ
ኛ ፡ መሢሕ ፡ መጣ ፡ በር ፡ ኮኽባ ፡ የሚሉት ፡ ማለቱም ፡
የኮከብ ፡ ልጅ ፡፡ እርሶ ፡ ብልዋልና ፡፡ የበልዓም ፡ ትንቢት ፡
ሲል ፡፡ ኮከብ ፡ ከያዕቆብ ፡ ይወጣል ፡፡ ለመሢሕ ፡ የተባለ ፡
በኔ ፡ ተፈጸመ ፡፡ እርሱም ፡ አይሁድን ፡ ላመፀ ፡ አስነሣቸ
ው ፡ ተስፋም ፡ አስደረገላቸው ፡ ከሮም ፡ ቀምበር ፡ ያድናቸ
ው ፡ ዘንድ ፡ ለምስጋናም ፡ ለክብርም ፡ ለመንግሥትም ፡
ከፍ ፡ ያደርጋቸው ፡ ዘንድ ፡፡ አይሁድም ፡ ይህነን ፡ አሰተኛ
ውን ፡ መሢሓቸውን ፡ በደስታ ፡ ተቀበሉት ፡ በይሁዳ ፡ አገር
ም ፡ በሶርያም ፡ የነበሩ ፡ ሸፈጡ ፡ ክርስቲያንም ፡ ከርሳቸ
ው ፡ ጋራ ፡ አልሸፈጡምና ፡ በሰይፍ ፡ ገደልዋቸው ፡፡ ሃድር
ያኑስ ፡ ግን ፡ ዘምቻ ፡ አደረገ ፡ በበርኮኽባ ፡ ላይ ፡ መታው
ም ፡ ካይሁድም ፡ ፶፰፻፻ ገደለ ፡፡

በአንቶኒኑስ ፡ ጲዮስ ፡ ዘመንም ፡ ደግሞ ፡ መሳደድ ፡ ሆ
ነ ፡ በክርስቲያን ፡ ላይ ፡፡ በቄሣር ፡ ፈቃድም ፡ አይደለም ፡ ከ
ሮም ፡ በራቀ ፡ አገር ፡ እንጂ ፡ በሕዝብና ፡ ክርስቲያንን ፡ በ
ሚጸሉ ፡ መኳንንት ፡፡ በመናወጽ ፡ በሳትም ፡ በራብም ፡ በ
ውኃም ፡ በሕማምም ፡ መከራ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ባገር ፡ ላ
ይ ፡ ክርስቲያን ፡ የዚህ ፡ ሁሉ ፡ መክንያት ፡ ሁነው ፡ ተቈ
ጠሩ ፡፡

በማርቆስ ፡ ኣውሬልዩስ ፡ ዘመንም ፡ ፬ ጊዜ ፡ ታላቅ ፡
መሳደድና ፡ መከራ ፡ ሆነ ፡ በክርስቲያን ፡ ላይ ፡፡ ይህ ፡ ቄሣ
ርም ፡ እጅግ ፡ አዋቂ ፡ ነበረ ፡ እንደ ፡ ዕውቀቱም ፡ በጎ ፡ ነበ
ረ ፡፡ ደሩ ፡ ጥበቡ ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ ጥበብ ፡ ሁንዋልና ፡ የ
ወንጌልን ፡ ነገር ፡ አላስተወለም ፡፡ ስለዚህም ፡ ክርስቲያን
ን ፡ ጸላ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖትም ፡ በደስታ ፡ ሙተው ፡ ባያቸ
ው ፡ ጊዜ ፡ እቡደት ፡ መሰሉት ፡፡ በኃይልም ፡ በብርታትም ፡
ስንፍና ፡ ከመሰለው ፡ ሃይማኖት ፡ ሊመልሳቸው ፡ ፈለገ ፡፡
መኳንንቱንም ፡ ክርስቲያንን ፡ ይሹ ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖ
ታቸውም ፡ ይፈርዱባቸው ፡ ዘንድ ፡ አዘዛቸው ፡፡

በዚህ ፡ ዘመንም ፡ ባመት ፡ ፻፷፫ ዩስቲኖስ ፡ ሰማዕት ፡ የተባለ ፡ በሮም ፡ ሞተ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡፡ እርሱም ፡ በሴኬም ፡ አረማዊ ፡ ሁኖ ፡ ተወለደ ፡ ጥበብም ፡ ይፈልግ ፡ ነበረ ፡ በብዙ ፡ ሰዎች ፡ ወገን ፡፡ ባያሌም ፡ ወገን ፡ ከፊሎሶፎች ፡ ፈለገ ፡ ልቡ ፡ ግን ፡ አልጸገበም ፡ አንድን ፡ ሽማግሌን ፡ እስኪያገኝ ፡ ድረስ ፡ ክርስቶስን ፡ የሚያስታውቀው ፡፡ ወደ ፡ ክርስቶስም ፡ ተመልሶ ፡ በወንጌል ፡ ዕረፍትን ፡ አገኘ ፡ ለልቡ ፡፡ ከዚያ ፡ ወዲያም ፡ ሁልጊዜ ፡ ለክርስቶስ ፡ መሰከረ ፡፡ ሁለት ፡ መጻሕፍትንም ፡ ጻፈ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ከመከሰስዋ ፡ ለማንጻት ፡፡ መጀመርያውንም ፡ ባመት ፡ ፻፵፱ ላንቶኒኑስ ፡ ጲዩስ ፡ ሰጠው ፡፡ ያም ፡ ቄሣር ፡ ያነን ፡ መጽሐፍ ፡ አንብቦት ፡ በጎ ፡ አደረገ ፡ ለክርስቲያኖች ፡፡ ሁለተኛውን ፡ መጽሐፉን ፡ ለማርቆስ ፡ ኣውሬልዩስ ፡ ሰጠ ፡፡ ዲሩ ፡ ይህ ፡ ቄሣር ፡ ልቡን ፡ አለወጠም ፡፡ ዩስቲኑስን ፡ አስያዘ ፡ እንጂ ፡፡ የቄሣርም ፡ መምህር ፡ ሩስቲኩስ ፡ የተባለ ፡ ፈረደበት ፡፡ ዩስቲኖስ ፡ ብልዋልና ፡፡ በፊሎሶፎች ፡ ሁሉ ፡ ዕረፍት ፡ እንዳላገኘ ፡ ለነፍሱ ፡ በክርስቶስ ፡ ሃይማኖት ፡ እንጂ ፡፡ ሩስቲኩስ ፡ ጠየቀው ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ አንተ ፡ ሰነፍ ፡ ይህችን ፡ ሃይማኖት ፡ ትከተላለህን ፡፡ ዩስቲኖስም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መለሰለት ፡፡ አዎን ፡ ክርስቲያንን ፡፡ እከተላለሁ ፡ ትምርታቸው ፡ እውነት ፡ ነውና ፡፡ ሩስቲኩስ ፡፡ ትምርታቸው ፡ ምንድር ፡ ነው ፡፡ ዩስቲኖስ ፡፡ እኛ ፡ እናመናለን ፡ ባንድ ፡ አምላክ ፡ የሰማይና ፡ የምድር ፡ ፈጣሪ ፡፡ በየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ልባቸውን ፡ ለሰጡት ፡ መድኃኒታቸው ፡ የሰውም ፡ ሁሉ ፡ ፈራጅ ፡ የሚሆን ፡፡ እኔ ፡ አንሳለሁ ፡ ስለርሱ ፡ እንደሚገባው ፡ እናገር ፡ ዘንድ ፡፡ ነቢያት ፡ ግን ፡ ስለርሱ ፡ ተናገሩ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ መምጣቱን ፡ አያሌ ፡ መቶ ፡ አመት ፡ አስቀድሞ ፡ የተነበዩት ፡፡ ሩስቲቡስ ፡፡ አንተ ፡ እውነትን ፡ ያለህ ፡ ቢመስልህ ፡ ከራስህ ፡ ጀምሬ ፡ እስከ ፡ እግርህ ፡ ድረስ ፡ ብገርፍህ ፡ ብሠቅይህም ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ እንድትገባ ፡ ይመስልሃለን ፡፡ ዩስቲኖስ ፡፡ የምትቀይምብኝን ፡ እንኳ ፡ ብቀበል ፡ የምእምናን ፡ ሁሉ ፡ ርስት ፡ አይቀርብኝም ፡፡ ይህነን ፡ በውነት ፡ አውቃለሁ ፡፡ ሩስቲኩስ ፡፡

ታዘዙ ፡ ላማልክትም ፡ ሠው ፡ ወይስ ፡ ያለ ፡ ምህረት ፡ ት ሠቀያላችሁ ፡፡ ፀስቲናስ ፡፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ አእምሮው ፡ ደህ ና ፡ የሚሆን ፡ እውነተኛ ፡ ሃይማኖትን ፡ በስሕተትና ፡ በሸን ግልና ፡ ፈንታ ፡ አይለውጥም ፡፡ እኛም ፡ እንወደለን ፡ በየ ሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ መክንያት ፡ መከራ ፡ እንቀበል ፡ ዘንድ ፡ ለዘላለምም ፡ ደህንነት ፡ እንገባ ፡ ዘንድ ፡፡ ከፀስቲናስ ፡ ጋ ራም ፡ ባንድ ፡ የታሠሩ ፡ ፯ ሰዎች ፡ ነገሩን ፡ አጸኑ ፡፡ እንዴ ህ ፡ ሲሉ ፡፡ ተግባርህን ፡ ቸኵል ፡ እኛ ፡ ክርስቲያን ፡ ነንና ፡ ለጣዖታትም ፡ መሥዋት ፡ አንችልም ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ መኰንን ፡ እንዴህ ፡ ብሎ ፡ ፈረደ ፡፡ ላማልክት ፡ ከመሥዋ ት ፡ ለቄሣርም ፡ ለፈቃዱ ፡ ከመታዘዝ ፡ እምቢ ፡ ያሉ ት ፡ እንደ ፡ ሕግ ፡ በፊት ፡ ይገረፉሉ ፡ በኋላም ፡ ራሳቸው ፡ ይ ቈረጣል ፡፡ እለዚያ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመስግነው ት ፡ ወደ ፡ ግዞታቸው ፡ ተመለሱ ፡ ጥቂትም ፡ በኋላ ፡ ራሳቸ ው ፡ ተቈረጠ ፡፡

በስሚርናም ፡ የክርስቲያን ፡ ማሳደድ ፡ እጅግ ፡ በረታ ፡ ባመት ፡ ፻፷፯፡፡ የስሚርና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ኤጲስቆጶ ስ ፡ ስሙ ፡ ጶሊቃርጶስ ፡ የሐዋርያ ፡ የዮሐንስ ፡ ደቀ ፡ መ ዝሙር ፡ የነበረ ፡ በዚህ ፡ ማሳደድ ፡ ሞተ ፡፡ ሕዝብም ፡ ሞ ቱን ፡ እንደ ፡ ፈለጉ ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ በፊት ፡ ተሰወረ ፡ በስው ርም ፡ በቀንና ፡ በሌሊት ፡ ጸለየ ፡ ስለ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያ ናት ፡ ሁሉ ፡፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ሎሌው ፡ እርሱ ፡ የነበረበትን ፡ ቦ ታ ፡ ለመኰንን ፡ አስታወቀው ፡ ያም ፡ ሎላልቱን ፡ ሊያዙ ት ፡ ሰደደ ፡፡ ጶሊቃርጶስም ፡ ሳይሔድ ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ፪ ሰዓት ፡ በጸሎት ፡ ኖረ ፡፡ በኋላም ፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ስፍራ ፡ ወ ሰዱት ፡፡ በመንገደቸውም ፡ አንዱን ፡ ከመኳንንት ፡ አገኙ ት ፡ ጶሊቃርጶስን ፡ ወደ ፡ ሰረገላው ፡ ያገባ ፡ በሚጻፍጥም ፡ ነገር ፡ የመከረው ፡ እንዴህ ፡ ሲል ፡፡ ቄሣር ፡ ጌታችን ፡ በማ ለት ፡ በመሥዋዕትም ፡ ምን ፡ ኃጢአት ፡ አለበት ፡፡ ሌላ ም ፡ ነገር ፡ ጨመረበት ፡፡ ጶሊቃርጶስ ፡ ግን ፡ አላቸው ፡፡ የም ትመክሩኝን ፡ ነገር ፡ አላደርግም ፡፡ ይህነን ፡ ሲል ፡ ከሰረገ ላ ፡ አውጥተውት ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ጣሉት ፡ እግሩ ፡ እስኪ ሰበር ፡ ድረስ ፡፡ ወደ ፡ ሸንጎም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ ሸንጎም ፡ አለ

ው ። ማል ፡ ክርስቶስንም ፡ ርገም ፡ እኔም ፡ እፈታሓለሁ ።
ጶሊቃርጶስም ፡ መለሰለት ፡ እንደህ ፡ ሲል ። አሁን ፡ ፹፮፡
አመት ፡ በማገልገሉ ፡ ነኝ ፡ እርሱም ፡ ቸርነት ፡ ብቻ ፡ አደረ
ገልኝ ። እርሱንም ፡ ጌታዬን ፡ መድኀኒቴንም ፡ አሁንን ፡ ልር
ገመው ። ሹም ፡ ደግሞ ፡ ሲመክረው ፡ ለሕይወቱ ፡ ሊያዝ
ን ፡ ብሎ ፡ ጶሊቃርጶስ ፡ አለው ። እንኪያስ ፡ ብትወዱ ፡ ታ
ውቁኝ ፡ ዘንድ ፡ እኔ ፡ ምንድር ፡ ነኝ ፡ ብላችሁ ፡ ዕወቁት ።
እኔ ፡ ክርስቲያን ፡ ነኝ ። ትምህርቴንም ፡ ማወቅ ፡ ብትወ
ዱ ፡ ጊዜን ፡ አድርጉልኝ ። ሹሙም ፡ ሊያድነው ፡ ፈልግዋ
ልና ፡ አለው ። ሕዝብን ፡ ብቻ ፡ እሺ ፡ አሰኛቸው ፡ እኔም ፡
አድንሃለሁ ። ጶሊቃርጶስም ፡ መለሰለት ፡ አለም ። አንተ
ን ፡ ብቻ ፡ ልናገር ፡ ነበርሁ ፡ መኳንንትን ፡ ማክበር ፡ ሃይማ
ኖታችን ፡ ያዝናልና ። እለዚያ ፡ ግን ፡ እቡደን ፡ ሁነው ፡ አ
ይገባቸውም ፡ የሃይማኖትን ፡ ነገር ፡ ይሰሙት ፡ ዘንድ ። ሹ
ምም ፡ ጶሊቃርጶስ ፡ በሃይማኖት ፡ እንደ ፡ ጸና ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡
ባዋጅ ፡ ነጋሪ ፡ አፌ ፡ አስጸራ ። ጶሊቃርጶስ ፡ ክርስቲያን ፡
ሁኖ ፡ ነፍሱን ፡ አስታወቀ ። ሕዝብም ፡ አሁን ፡ መለሶ ፡ አ
ሉም ። ይህ ፡ የኃጢአት ፡ መምህር ፡ ነው ። የክርስቲያን
ም ፡ አባት ፡ ያማልክታችንም ፡ ጸላት ፡ ላማልክት ፡ መስገ
ድና ፡ መሠዋትም ፡ በመከልከል ፡ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ያስተማ
ራቸው ። አሁንም ፡ እንጨትን ፡ ደርድረው ፡ እርሱን ፡ ለ
ማንደድ ፡ በንጨት ፡ ያሥሩት ፡ ዘንድ ፡ ፈለጉ ፡ እርሶ ፡ ግ
ን ፡ አለ ። ተውኝ ፡ ብቻ ። በሳት ፡ ስለርሱ ፡ ልቃጠል ፡ ኃይ
ል ፡ የሰጠኝ ፡ እርሱም ፡ ኃይል ፡ ይሰጠኛል ፡ በሳት ፡ ጸንቼ ፡
ልቆም ። እሳትንም ፡ ሲያነዱ ፡ ጸለየ ፡ እንደህ ፡ ሲል ። አ
ቤቱ ፡ ሁሉን ፡ የምትችል ፡ አምላክ ፡ የተወደደ ፡ ልጅህ ፡
የየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አባት ፡ በርሶ ፡ ዕውቀትህን ፡ የተቀበ
ልነ ። የመላእክትም ፡ የፍጥረትም ፡ ሁሉ ፡ ጌታ ፡ የሰው
ም ፡ ሁሉ ፡ በፊትህም ፡ የሚኖሩ ፡ የጻድቃን ፡ ጌታ ። እኔ ፡ አ
መሰግንሃለሁ ፡ በዚህ ፡ ቀን ፡ በዚች ፡ ሰዓትም ፡ አክብረሀኛ
ልና ፡ ወደ ፡ ምስክሮችህ ፡ ቍጥር ፡ ልገባ ፡ የመሢሕን ፡ ጽዋ
ዕ ፡ እጠጠ ፡ ዘንድ ።

በዚህ ፡ ዘመንም ፡ የነበረች ፡ ሁለተኛ ፡ መሰደድ ፡ በገል

ያ ፡ በፍርንሲስ ፡ ምድር ፡ ነበረች ፡ በልዮንና ፡ በዬና ፡ በል
ደት ፡ አመት ፡ ፻፷፯። ከዚያም ፡ የሕዝብ ፡ ጸላትነት ፡ በክ
ርስቱያን ፡ ላይ ፡ እጅግ ፡ ብርቱ ፡ ነበረ ፡፡ የኀጢአት ፡ ሁሉ ፡
መክንያት ፡ አመጡባቸው ፡፡ የቄሣር ፡ ሹምም ፡ በሥቃ
ይ ፡ ብቻ ፡ መረመራቸው ፡ በግድ ፡ ኀጢአታቸውን ፡ ሊያስታ
ውቁ ፡ ብሎ ፡፡ አንድ ፡ ሰውም ፡ ከከበረ ፡ ዘመድ ፡ ይህነን ፡
ሰምቶ ፡ መጣ ፡ ለክርስቲያን ፡ ንጽሕና ፡ ሊመሰክር ፡ የመ
ክሰስም ፡ አሰት ፡ ሊገልጽ ፡ ብሎ ፡፡ መኰንን ፡ ግን ፡ አልሰ
ማውም ፡ ጠየቀው ፡ እንጀ ፡ እርሱ ፡ ደግሞ ፡ ክርስቲያን ፡
እንደ ፡ ሆነ ፡ ብሎ ፡፡ ክርስቲያን ፡ ነኝ ፡ ሲልም ፡ እርሱን ፡ ደ
ግሞ ፡ ወደ ፡ ግዞት ፡ ጨመረ ፡፡ አያሌ ፡ ባሮችም ፡ አረማው
ያን ፡ ሁነው ፡ በክርስቲያን ፡ ጌቶቻቸው ፡ ላይ ፡ መሰከረ ፡
ያ ፡ የተከሰሱበት ፡ ኃጢአት ፡ እውነት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡፡ የክ
ርስቲያን ፡ ጸላቶችም ፡ ይህነን ፡ ሰምተው ፡ አሰቡ ፡ መበደ
ል ፡ ሁሉ ፡ ሥቃይም ፡ መከራም ፡ ሞትም ፡ ሁሉ ፡ በክርስ
ቲያን ፡ ላይ ፡ ያደርሱት ፡ ዘንድ ፡ እንዲገባ ፡፡ ለማንምም ፡
አላዘኑም ፡፡ ክርስቲያን ፡ ግን ፡ ይህነን ፡ ሁሉ ፡ በትእግሥ
ት ፡ ተሸከሙ ፡፡ በትእግሥትም ፡ አሸነፉ ፡ በመከራቸው
ም ፡ በሃይማኖት ፡ ጸኑ ፡ ነጹም ፡፡ በልዮን ፡ የነበረች ፡ ቤተ ፡
ክርስቲያን ፡ ኤጲስቆጶስዋ ፡ ጶቲኖስ ፡ የተባለ ፡ ዕድሜው
ም ፡ ፺፤ አመት ፡ የነበረ ፡ እርሱ ፡ ደግሞ ፡ በፍርድ ፡ ክርስቶ
ስን ፡ ታመነ ፡፡ በጠየቁት ፡ ጊዜ ፡ ማነው ፡ የክርስቲያን ፡ አ
ምላክ ፡ ብለው ፡ እርሱ ፡ መለሰ ፡ እንዴህ ፡ ሲል ፡፡ እላን
ት ፡ ታውቁት ፡ ዘንድ ፡ ጊዜ ፡ አላችሁ ፡ ቢገባችሁ ፡፡ አሁን
ም ፡ ሁላቸው ፡ ተቍጥተውት ፡ ወቀዩት ፡ ፪፤ ቀንም ፡ በኋ
ላ ፡ በግዞት ፡ ሞተ ፡፡ ብዙም ፡ ሞቱ ፡ በሥቃይ ፡ ብዙም ፡ በ
ግዞት ፡ ሞቱ ፡፡ እርሳቸው ፡ ግን ፡ በሞቱ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ሰዎ
ች ፡ በምስክራቸው ፡ ለክርስቶስ ፡ ተገዙ ፡ በሞቱትም ፡ ፈን
ታ ፡ ገቡ ፡፡ አንድ ፡ ብላቴናም ፡ ዕድሜው ፡ ፲፭፤ አመት ፡ የነ
በረ ፡ ስሙም ፡ ጶንቲኩስ ፡ የሚሉት ፡ አንዲት ፡ ቆንደ
ም ፡ ብላንዲና ፡ የተባለች ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ የሞቱ ፡ በሃ
ይማኖታትውም ፡ ብርታት ፡ ሰውን ፡ ሁሉን ፡ አስደነቁ ፡ የኢ

ግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ በድካማቸው ፡ በርትታለችና ። ግን
ድ ፡ አገርም ፡ ክርስቲያን ፡ ያልበዙበት ፡ አንድ ፡ ኀብዝ ፡ ተ
ያዘ ፡ ስሙ ፡ ስምፎርያኑስ ፡ የተባለ ፡ ኪቤሌ ፡ የተባለ
ች ፡ ያምላኪቱ ፡ በዓል ፡ ባደረጉ ፡ ጊዜ ። የኪቤሌ ፡ ካህና
ትም ፡ ጣዖትዋን ፡ በሰረገላ ፡ ሁና ፡ አዞሩት ፡ ባገር ። የመንገ
ድ ፡ አላፊችም ፡ ሁሉ ፡ የኪቤሌ ፡ ሰረገላ ፡ ሲያልፍ ፡ በጕ
ልበታቸው ፡ ሰገደላት ፡ ስምፎርያኑስም ፡ ብቻውን ፡ ቈምዋ
ል ። አሁንም ፡ እንደ ፡ ማምለካቸው ፡ ከልካይ ፡ ያዙት ፡
ወደ ፡ ሹምም ፡ ወሰዱት ። ሹምም ፡ ጠየቀው ፡ እንዲህ ፡
ሲል ። አንተ ፡ ክርስቲያን ፡ ነህን ። እርሱም ፡ መለሰ ፡ አለ
ም ። እኔ ፡ ክርስቲያን ፡ ነኝ ። በሰማይም ፡ ለሚገዛ ፡ ለው
ነተኛ ፡ አምላክ ፡ እሰግደለሁ ፡ ለዚህች ፡ ጣዖት ፡ ግን ፡ መ
ስገድ ፡ አልችልም ፡ ብተውኝም ፡ ሳልፈራ ፡ እቀጠቅጣታለ
ሁ ። አሁንም ፡ ሹሙ ፡ ክርስቶስን ፡ ያስክደው ፡ ዘንድ ፡ ፈ
ተነው ። ያም ፡ ባልጠቀመ ፡ ጊዜ ፡ ራሱን ፡ ሊቈርጡት ፡ አ
ዘዘ ። ወደ ፡ ሞትም ፡ ሲወስዱት ፡ እናቱ ፡ አለቸው ። ል
ጄ ፡ ሆይ ፡ ልጄ ፡ ሆይ ። ሕያው ፡ አምላክ ፡ በልብህ ፡ ይኑር ።
ጽኑ ፡ ሁን ። በውነት ፡ ወደ ፡ ሕይወት ፡ ከሚወስደው ፡ ሞ
ት ፡ መፍራት ፡ ለኛ ፡ አይገባነም ። ልብህ ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ በላ
ይ ፡ ይሁን ፡ በሰማይም ፡ ወደ ፡ ሚገዛ ፡ ተመልከት ። ዛሬ
ም ፡ ሕይወትን ፡ አይወስዱብህም ፡ ሕይወትህ ፡ ለበጎ ፡ ትለ
ወጥልሃለች ፡ እንጂ ። በብፁዕ ፡ መለወጥህ ፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡
ዛሬ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ሕይወት ፡ ትገባለህ ።

ቄሣር ፡ ቀሞዱስ ፡ ለራሱ ፡ ክርስቲያንን ፡ አልጸላም ፡
ደሮ ፡ ከርሱ ፡ በታች ፡ የተሾሙ ፡ መኳንንት ፡ አንድ ፡ አን
ድ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ በክርስቶስ ፡ ስለ ፡ ማመናቸው ፡
አሳደዱ ።

ከርሱም ፡ በኋላ ፡ የነገሠ ፡ ቄሣር ፡ ሰጵቲሚዮስ ፡ ሴቤ
ረስ ፡ ተከፋሎ ፡ ወደጅ ፡ ነበረላቸው ። አንድ ፡ ክርስቲያን ፡
ባርያው ፡ ስሙ ፡ ጵሮክሉስ ፡ ከሕማሙ ፡ አድኖታልና ፡ በር
ሱም ፡ መክንያት ፡ ክርስቲያንን ፡ ከሕዝቡ ፡ ቍጣ ፡ ጠበቃ
ቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ አረማውያንን ፡ ከለከለ ፡ ማምለካቸ

ውን ፡ ከመለወጥ ፡፡ በዚህም ፡ መክንያት ፡ የክርስቲያን ፡
ጸላቶች ፡ በመኳንንት ፡ መኻከል ፡ ማሳደደቸውን ፡ አልተ
ውም ፡፡

እንደሁም ፡ ነበረ ፡ በከረካላ ፡ ዘመን ፡ እርሱ ፡ ስለ ፡ ሃ
ይማኖት ፡ ሁሉ ፡ ያልጠየቀ ፡፡ በዚህ ፡ ዘመንም ፡ ብዙ ፡ ሞ
ቱ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ በሮማዊት ፡ አፍሪቃ ፡፡ የኑሚዲያ ፡ ጋ
ዥ ፡ ሰቱርኒኑስ ፡ ባመት ፡ ፪፻፫ ፡ አያሌን ፡ ክርስቲያንን ፡
ወደርሱ ፡ አስመጣ ፡ አላቸውም ፡፡ ቄሣሮቻችን ፡ ሰጵቲሚ
ዩስና ፡ ከረካላ ፡ ይምርዋችኋል ፡ በፈቃደችሁ ፡ ወደ ፡ አማ
ልክታችን ፡ ብትመለሱ ፡ ብቻ ፡፡ አንድ ፡ ከመኻከላቸው ፡
እርሱም ፡ ስጴራቱስ ፡ መለሰለት ፡፡ እኛ ፡ ማንንም ፡ አል
በደልነም ፡ ማንንም ፡ አልሰደብነም ፡ ስለ ፡ ክፋታችሁ
ም ፡ ያደረጋችሁብነ ፡ ሁሉ ፡ አመሰገናችሁ ፡፡ ስለ ፡ ሁሉ
ም ፡ እውነተኛውን ፡ ጌታንና ፡ ንጉሥን ፡ እናከብራለን ፡፡ ሹ
ሙም ፡ አለው ፡፡ እኛ ፡ ደግሞ ፡ አምላክን ፡ እንፈራለን ፡፡
በጌታችንም ፡ በቄሣር ፡ ጋኔን ፡ እንምላለን ፡፡ ስለ ፡ ደህንነቱ
ም ፡ እንጸልያለን ፡ ለላንት ፡ ደግሞ ፡ ይህ ፡ ይገባችኋል ፡ ታድ
ርጉት ፡ ዘንድ ፡፡ ስጴራቱስም ፡ መለሰ ፡ አለም ፡፡ እኔ ፡ የዚ
ህ ፡ ዓለም ፡ ጋዥ ፡ ጋኔኑን ፡ አላውቅም ፡፡ ደሮ ፡ በሰማይ ፡ ያ
ለውን ፡ አምላኬን ፡ አመልከዋለሁ ፡ ሰው ፡ ያላየውን ፡ ከ
ቶ ፡ የማይታይንም ፡፡ ከቶ ፡ ምንም ፡ አልሰረቅሁም ፡ ከማን
ምም ፡፡ ከመግዛቴም ፡ ሁሉ ፡ የሚገባውን ፡ ግብር ፡ እሰጣለ
ሁ ፡ ቄሣርንም ፡ ጌታዬ ፡ እንዲሆን ፡ አስታውቀዋለሁ ፡፡ ማ
ምለክ ፡ ግን ፡ አንዱን ፡ ጌታዬን ፡ ብቻ ፡ እችላለሁ ፡ አመል
ከው ፡ ዘንድ ፡ እርሱም ፡ የነገሥታት ፡ ንጉሥ ፡ ያሕዛብም ፡
ሁሉ ፡ ጌታ ፡ የሚሆን ፡፡ ሹምም ፡ ክርስቲያናትን ፡ እስከ ፡
ነጋ ፡ ወደ ፡ ግዞት ፡ አስመለሳቸው ፡፡ ሁለተኛም ፡ ሲመጡ ፡
ደግሞ ፡ መከራቸው ፡ የሶስት ፡ ቀንም ፡ ጊዜ ፡ አደረገላቸ
ው ፡ ሊያስቡ ፡ ብሎ ፡፡ ስጴራቱስ ፡ ግን ፡ በቀረጥ ፡ ስም ፡
መለሰለት ፡ እንደህ ፡ ሲል ፡፡ እኔም ፡ ክርስቲያን ፡ ነኝ ፡ ሁ
ላችንም ፡ ክርስቲያናት ፡ ነን ፡፡ ከጌታችንም ፡ ከየሱስ ፡ ክር
ስቶስ ፡ ሃይማኖት ፡ አንርቅም ፡፡ እንደ ፡ ፈቃደችሁም ፡ አድ

ርጉ ፡፡ ራሳቸውም ፡ ይቈረጥ ፡ ዘንድ ፡ ተፈረደባቸው ፡፡ ሳይ
ሞቱም ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገኑ ፡፡

አያሌ ፡ አመትም ፡ በኋላ ፡ በከርታጎ ፡ ስቴቦካቱስ ፡ ሳ
ቱርኒስም ፡ ሴኩርደሉስም ፡ ብላቴኖች ፡ ጰርጲትዋና ፡
ፌሊኪታስም ፡ ሴቶች ፡ ሁላቸው ፡ ገና ፡ ያልተጠመቁ ፡ ክ
ርስቲያኖች ፡ ሁነው ፡ ተያዙ ፡፡ እርሳቸውም ፡ ሳይጠመቁ ፡
ለተጠመቁ ፡ ሁሉ ፡ ምሳሌን ፡ ሰጡ ፡ በሃይማኖታቸው ፡ ብር
ታት ፡፡ ከሌሎችም ፡ ይልቅ ጰርጲትዋ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
ብርቱ ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ ትመስላለች ፡፡ ዕድሜዋ ፡ ፳፪ አመ
ት ፡ ነበረ ፡ ልጅም ፡ ነበረላት ፡ ያጠባችው ፡፡ የጰርጲትዋ ፡
አባትም ፡ አረማዊ ፡ ነበረ ፡ እናትዋ ፡ ግን ፡ ክርስቲያን ፡ ነ
በረች ፡፡ አባትዋም ፡ ከሞትዋ ፡ ፈራ ፡ ክርስቲያንም ፡ ሁ
ና ፡ እንደይገድልዋት ፡ እንደ ፡ ታላቅ ፡ ነውርም ፡ ቈጠረው ፡
ለዘመዱ ፡፡ ወደ ፡ ፍርድ ፡ ቤትም ፡ ባገብዋቸው ፡ ጊዜ ፡ አሮ
ጌ ፡ አባትዋ ፡ መጣላት ፡ እንድትክድም ፡ እጅግ ፡ ለመና
ት ፡፡ እርስዋ ፡ ግን ፡ ከዚያ ፡ የነበረውን ፡ እቃ ፡ አሳየቸው ፡
እንዴህ ፡ ስትል ፡፡ ለዚህ ፡ ዕቃ ፡ ሌላውን ፡ ስም ፡ ልስጠው
ን ፡ ከሚገባው ፡ ስም ፡ በቀር ፡፡ እርሱም ፡ አላት ፡፡ አይደ
ለም ፡፡ እርስዋም ፡ አለች ፡፡ እንዴሁም ፡ እኔ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡
ልናገራችሁ ፡ አልችልም ፡ ክርስቲያኒቱ ፡ እንደሆንሁ ፡ እን
ጅ ፡፡ በግዞትም ፡ በነበሩ ፡ ጊዜ ፡ ተጠመቁ ፡፡ ጰርጲትዋም ፡
አለች ፡፡ ስጠመቅ ፡ ጊዜ ፡ መንፈስ ፡ ሌላውን ፡ ነገር ፡ እንደ
ልለምን ፡ አለኝ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ትዕግሥትን ፡ እንጅ ፡፡
ወደ ፡ ሌላ ፡ ግዞትን ፡ ወሰድዋቸው ፡ እጅግ ፡ ክፉ ፡ የነበረ
በት ፡፡ እኔ ፡ እጅግ ፡ ፈራሁ ፡ አለች ፡ ከቶ ፡ እንዴህ ፡ ያለ
ውን ፡ ጨለማ ፡ አላየሁምና ፡ እጅግም ፡ ተጨነቅሁ ፡ ከዚያ
ም ፡ ከታሠረት ፡ ብዛት ፡ በተነሣ ፡ ሙቀት ፡ በወታደርም ፡
ክፋት ፡ ደግሞም ፡ በተካዜዬ ፡ ስለ ፡ ልጄ ፡፡ የቤተ ፡ ክርስቲ
ያን ፡ ዲያቆናት ፡ ግን ፡ በግዞት ፡ ያቈረብዋቸው ፡ ለክርስቲ
ያናት ፡ እሥሮች ፡ የተሻለውን ፡ ቦታ ፡ በግዞት ፡ ቤት ፡ ገዙ
ላቸው ፡ ከሌሎች ፡ እሥሮች ፡ ወደ ፡ ተለዩበት ፡፡ ጰርጲትዋ
ም ፡ አሁን ፡ ልጅዋን ፡ አጠባች ፡ ለናትዋም ፡ አደራ ፡ ሰጠ

ቸው ፡ ዘመያችዋንም ፡ አጸናች ፡ እጅግም ፡ ደስ ፡ አለች ፡፡ ሳይፈርደም ፡ አባትዋ ፡ ወደርስዋ ፡ ቸኵሎ ፡ አላት ፡፡ ልጄ ፡ ሆይ ፡ እለምንሻለሁ ፡ ለሺበቴ ፡ እዘኝ ፡ ላባትሽ ፡ እዘኝ ፡ አባትሽ ፡ እባል ፡ ዘንድ ፡ ቢገባኝ ፡፡ እስከዚህ ፡ ዕድሜሽ ፡ ድረስ ፡ አሳድጌሻለሁና ፡ ከወንድማማችሽም ፡ ሁሉ ፡ አከብሬሻለሁና ፡፡ አሁን ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ፊት ፡ እንደዚህ ፡ አታስነውሪኝ ፡፡ እናትሽን ፡ እይ ፡ እክስትሽንም ፡ እይ ፡ ልጅሽንም ፡ እይ ፡ እርሱም ፡ አይኖርም ፡ አንቺ ፡ ብትሞቺ ፡፡ ታላቅ ፡ አሳብሽን ፡ ትይ ፡ ሁላችንን ፡ እንዳታጥፊ ፡፡ ከሁላችንም ፡ እንጊዜህ ፡ ማንም ፡ በግልጥ ፡ ይናገር ፡ ዘንድ ፡ አይደፍርም ፡ እንደዚህ ፡ የሞትሽ ፡ እንድትሆኝ ፡፡ እንዲህም ፡ ሲል ፡ እጅዋን ፡ ነሣ ፡ በጅግ ፡ እንብም ፡ አልቀሶ ፡ በግርዋ ፡ ወደቀ ፡ ልጄም ፡ አላላትም ፡ እመቤቱ ፡ እንጅ ፡፡ እርስዋም ፡ ላባትዋ ፡ ሺበት ፡ አዘነች ፡ እርሱ ፡ ከዘመድዋ ፡ ሁሉ ፡ ብቻውን ፡ ቀርትዋልና ፡ ጣዖታትን ፡ ያመለከ ፡ ደስም ፡ ያላለው ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ በተቀበለች ፡ መከራዋ ፡፡ አባትዋንም ፡ አለች ፡፡ በፍርድ ፡ ስቀም ፡ ጊዜ ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚወደው ፡ ይሆናል ፡፡ ይህነንም ፡ ዕወቅ ፡ እኛ ፡ በኃይላችን ፡ እንዲኖር ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ እንጅ ፡፡ ሲፈርደባቸውም ፡ አባትዋ ፡ ደግሞ ፡ መጣ ፡ ሊፈትን ፡ ብሎ ፡ ምናልባት ፡ ልብዋን ፡ እንደይለውጥ ፡፡ ሹምም ፡ ጰርጴትዋን ፡ አላት ፡፡ እዘኝ ፡ ላባትሽ ፡ ሽምግልና ፡ እዘኝ ፡ ለልጅሽ ፡ ሕፃንነቱም ፡፡ ሠዊ ፡ ለቄሣሮች ፡ ደህንነት ፡፡ እርስዋም ፡ መለሰች ፡፡ ይህነን ፡ አላደርግም ፡፡ እርሱ ፡፡ ክርስቲያኒቱን ፡ ነሽ ፡፡ እርስዋ ፡፡ አዎን ፡፡ ክርስቲያኒቱ ፡ ነኝ ፡፡ አሁንም ፡ ፍርድዋ ፡ የሁላቸውም ፡ ፍርድ ፡ ተቈረጠ ፡፡ በቀረበም ፡ በቄሣር ፡ በዓል ፡ ሁላቸው ፡ ለሕዝብና ፡ ለወታደሮች ፡ ሁሉ ፡ ለጫወታ ፡ ካራዊት ፡ ጋራ ፡ ሊታገሉ ፡ ነበሩ ፡፡ በደስታም ፡ ወደ ፡ ግዞታቸው ፡ ተመለሱ ፡፡ ጰርጴትዋም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ ካባትዋ ፡ ልጅዋን ፡ ለመነች ፡ ልታጠባው ፡ ብላ ፡ እርሱ ፡ ግን ፡ ነሣላት ፡፡ ፊሊቢታስም ፡ በግዞት ፡ ሁና ፡ ስትወልድ ፡ የሥሮች ፡ ጠባቂ ፡ አላት ፡፡ አሁን ፡ አንቺ ፡ ምፅሽ ፡ እንደዚህ ፡ ብርቱ ፡

ቢሆንብሽ ፡ ምንድር ፡ ይሆናል ፡ ብለሽ ፡ ላራዊት ፡ ቢጣሉ
ሽ :: እርስዋም ፡ እንዲህ ፡ ስትል ፡ መለሰች :: አሁንስ ፡ መ
ከራዬን ፡ እኔ ፡ እቀበለዋለሁ :: በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ሌላ ፡ ይ
ሆናል ፡ ስለኔ ፡ የሚቀበለው ፡ እኔም ፡ ስለርሱ ፡ መከራ ፡ እ
ቀበላለሁና :: እንዲሁም ፡ በትዕግሥትና ፡ በሃይማኖት ፡ በ
ምስጋናም ፡ ለሞታቸው ፡ ደረሱ :: አራዊትም ፡ ከነከስዋቸ
ው ፡ በኋላ ፡ ለሞትም ፡ ሲቀርቡ ፡ በክርስቲያን ፡ ፍቅር ፡ አ
ቅፈው ፡ የወንድሞችን ፡ ሳም ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡ ተሳሳ
ሙ ፡ ተሰናበቱም ፡ ለዘላለም ፡ ሕይወት ::

እስክንድር ፡ ሴቤሮስም ፡ የክርስቲያንን ፡ መንገድ ፡
ወደደ ፡ እንደ ፡ ዕውቀቱ :: እርሱም ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክ ፡
እንደ ፡ ሆነ ፡ ከብዙ ፡ ከሌሎች ፡ አማልክት ፡ ጋራ ፡ አሰበ ::
ለክርስቶስም ፡ ዐምድን ፡ አደረገ :: የክርስቶስንም ፡ ቃል ፡
እንዲህ ፡ ሲል :: ሰው ፡ ሊያድርግላችሁ ፡ እንድትወዱ ፡ እላ
ንትም ፡ እንዲህ ፡ አድርጉላቸው :: ይህነን ፡ ቃል ፡ ባምባው ፡
ቅጥር ፡ በሃውልትም ፡ በደንጊያ ፡ ወቅሮት ፡ አስጻፈው ::

ከርሱ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ የነገሠ ፡ ቄሣር ፡ መክሲሚኑስ ፡ ት
ራክስ ፡ ክርስቲያንን ፡ ጸላ ፡ አሳደዳቸውም ::

በፊልጶስ ፡ ዓረብ ፡ ዘመንም ፡ ለክርስቲያን ፡ ዕረፍት ፡
ሆነ :: እርሱም ፡ ክርስቲያንን ፡ ወደደ ፡ እንደ ፡ እስክንድር ፡
ሴቤሩስ :: አያሌም ፡ የሚሉ ፡ አሉ :: ይህ ፡ ቄሣር ፡ ክርስ
ቲያን ፡ እንደ ፡ ሆነ :: ደሮ ፡ ይህ ፡ እውነት ፡ ሁኖ ፡ አይመስ
ልም ::

በዴኪዩስ ፡ ዘመንም ፡ ታላቅ ፡ መሳደድ ፡ ሆነ ፡ በክርስቲ
ያን ፡ ላይ ፡ ከልደት ፡ አመት ፡ ከ፪፻፵፱፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡
፪፻፶፩፡ ድረስ :: እግዚአብሔርም ፡ ይህነን ፡ መከራ ፡ አስመ
ጣ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ላይ ፡ የተኙትን ፡ ያነቃቸው ፡ ዘን
ድ ፡ የረከሱትንም ፡ ያነጻቸው ፡ ዘንድ ፡ ባለ ፡ ሁለት ፡ ልብ
ንም ፡ ወይስ ፡ ሊመልስ ፡ ወይስ ፡ ከመንጋ ፡ ሊቈርጣቸ
ው :: የተመረጹም ፡ ጸኑ ፡ በዚህ ፡ መከራ ፡ ደግሞ :: ከቀሩ
ም ፡ ብዙ ፡ ካዱ ፡ ያነን ፡ ስም ፡ በርሱ ፡ ብቻ ፡ የዘላለም ፡ ደ
ህንነታችን ፡ የተገኘ ::

የቄሣርም ፡ የዴኪዩስ ፡ ፈቃድ ፡ ይህ ፡ ነበር ፡ የክርስቲያ

ንን ፡ ወገን ፡ በጣም ፡ ያጠፈ ፡ ዘንድ ፡፡ ስለዚህም ፡ ታላ
ቅ ፡ መመርመን ፡ አዘዘ ፡ የተገኘውንም ፡ ክርስቲያን ፡ ሁ
ሉ ፡ የጣዖታትን ፡ ማምለክ ፡ አዘዛቸው ፡፡ እምቢ ፡ ብለ
ው ፡ እንደሆኑ ፡ መኳንንት ፡ እርሳቸውን ፡ በቅያሜ ፡ በሥ
ቃይም ፡ ሊያገዱ ፡ ነበረ ፡፡ ይህም ፡ ምናልባት ፡ የማይጠቅ
ም ፡ እንደሆን ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ቀሳውስትም ፡ ዲያቆናት
ም ፡ ከታላቆችም ፡ በክርስቶስ ፡ ያመኑ ፡ ሊሞቱ ፡ ነበረ ፡፡
ሲሸሹም ፡ ገንዘባቸው ፡ ለመንግሥት ፡ ሊወስዲባቸው ፡ አ
ዘዘ ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ክርስቲያን ፡ ከተባሉ ፡ ከዙ ፡ ካዱ ፡፡
ብዙ ፡ መኳንንትም ፡ ነበረ ፡ መግደልን ፡ ያልወደደ ፡ ከብት
ን ፡ እንጅ ፡፡ ወረቀትንም ፡ ጻፈ ፡ ለክርስቲያን ፡ የቄሣርን ፡ ት
እዛዝ ፡ እንደ ፡ ፈጸሙ ፡ የሚል ፡፡ ብዙ ፡ ባላ ፡ ሁለት ፡ ልቦ
ች ፡ ነበረ ፡ አሰት ፡ ኃጢአትን ፡ ያልቍጠረት ፡ ያሰቡም ፡ ባለ
ቤታቸው ፡ ብቻ ፡ ባይሠው ፡ እንደ ፡ ታዘዙም ፡ ባያድርጉ ፡ በ
ደህንነታቸውም ፡ ቢኖሩ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ግድ ፡ የለም ፡፡ የክር
ስቶስንም ፡ ነገር ፡ አላሰቡትም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ ያለውን ፡
ነገር ፡ ሁሉን ፡ የማይክድ ፡ እኔንም ፡ የማይከተል ፡ ደቀ ፡
መዝሙሬ ፡ አይሆንም ፡፡ ብዙም ፡ ወደ ፡ ግዞት ፡ ተጨመረ ፡
ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ሳይሞቱ ፡ ግን ፡ ክርስቶስን ፡ ካዱ ፡፡ በነፍ
ሳቸው ፡ ግን ፡ ኃይል ፡ ያጡ ፡ በውነትም ፡ ልባቸውን ፡ ለክር
ስቶስ ፡ ደሰጡት ፡ የነበረ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ በድካ
ማቸው ፡ በረታች ፡፡ እንዲሁም ፡ አንድ ፡ አሽከር ፡ ስሙ ፡
ዲዮስቆርስ ፡ ዕድሜው ፡ ፲፭፡ አመት ፡ የነበረ ፡ ሹምን ፡ በ
ምላሹ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ያስደነቀው ፡ እስኪፈታው ፡ ድ
ረስ ፡፡

ቄሣርም ፡ ከሌሎች ፡ ይልቅ ፡ ኤጲስቆጶሳትን ፡ መግደል ፡
ፈለገ ፡፡ በዚህም ፡ ስደት ፡ በመጀመርያ ፡ የሮም ፡ ኤጲስቆጶ
ስ ፡ ፈቢያኑስ ፡ የሰማዕትን ፡ ሞት ፡ ሞተ ፡፡ ብዙ ፡ ኤጲስቆጶ
ሳትም ፡ ካብያተ ፡ ክርስቲያናታቸው ፡ ተሰወረ ፡ ስለ ፡ ፍርሃ
ት ፡ አይደለም ፡ ሕይወታቸውን ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ደህንነት ፡
ሊጠብቁ ፡ ብለው ፡ እንጅ ፡፡ እንዲህም ፡ አደረገ ፡ ኪኪልዩ
ስ ፡ ቂጵርያኑስ ፡ የከርታጎ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡፡ ከተሰወረበት ፡
ስፍራ ፡ ግን ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ወትሮ ፡ ጻፈ ፡ ለነፍሳቸው

ም ፡ ደህንነት ፡ ጠየቀ ፡ መከራቸውም ፡ ገሠጻቸውም ፡ አጸና ቸውም ፡፡ ይህም ፡ ስደት ፡ ኖረ ፡ ከልደት ፡ አመት ፡ ፪፵፱፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፪፶፩፡ ድረስ ፡ ሶስት ፡ አመት ፡፡ ዴኪዩስም ፡ ጾር ፡ አደረገ ፡ ጎቶች ፡ ከሚሉት ፡ ሕዝብ ፡ ጋራ ፡ በዚህ ፡ ጾርም ፡ ሞተ ፡፡ በዚህ ፡ መክንያትም ፡ ክርስቲያን ፡ ጥቂት ፡ ዕረፍ ት ፡ አገኙ ፡ ከጋሉስና ፡ ወሉስያኑስ ፡ መንግሥት ፡ በታች ፡ እስከ ፡ ፪፶፪፡ ድረስ ፡፡ በዚህ ፡ አመት ፡ ቸነፈር ፡ በሮም ፡ መንግሥት ፡ ሁሉ ፡ ዘረጋ ፡ በርሱም ፡ በራብም ፡ እጅግ ፡ ሰ ዎች ፡ ሞቱ ፡፡ የዚህንም ፡ መክንያት ፡ አሕዛብ ፡ እንደ ፡ ወ ትሮ ፡ ክርስቲያንን ፡ ቈጠሩ ፡፡ ቄሣርም ፡ አዘዘ ፡ ሰው ፡ ሁ ሉ ፡ ለጣዖታት ፡ መሥዋዕትና ፡ ጸሎት ፡ ሊያድርግ ፡ አማል ክታቸውን ፡ እሺ ፡ ያሰኙ ፡ ዘንድ ፡ መቅሠፍታቸውን ፡ ለማ ሳለፍ ፡፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ አሕዛብ ፡ ክርስቲያንን ፡ ተቈጡ ፡ ጣዖታታቸውን ፡ እንዲያመልኩ ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡፡ ቂጵርያኑስ ም ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከሮማዊት ፡ አፍሪቃ ፡ የነበረትን ፡ አብ ያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መከራቸው ፡ በዚህ ፡ ስደት ፡ ሊጸኑ ፡ መታመናቸውንም ፡ በጣም ፡ በክርስቶስ ፡ ሊደድርጉ ፡ በስ ደታቸውም ፡ የወንድሞችን ፡ አንድነት ፡ እንደደረሱ ፡፡ በ ሮም ፡ ከተማ ፡ የነበረ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ቆርኔልዩስ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖቱ ፡ ሞተ ፡፡ በርሱም ፡ ፈንታ ፡ የተሾመ ፡ ኤጲስቆጶ ስ ፡ ሉኪዩስ ፡ ደግሞ ፡ አያሌ ፡ ቀን ፡ ኑሮ ፡ ተገደለ ፡፡ ጋሉስ ፡ ግ ን ፡ እጅግ ፡ ደክሞ ፡ በጾር ፡ በሽፍጥም ፡ የክርስቲያንን ፡ ማ ሳደድ ፡ ተወ ፡ ባመት ፡ ፪፶፫፡ ተገደለ ፡፡ ለክርስቲያንም ፡ ጥ ቂት ፡ ዕረፍት ፡ ሆነ ፡፡

ቄሣር ፡ ዋሌርያኑስም ፡ ከ፪፶፫፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፪፶፱፡ ድረስ ፡ የነገሠ ፡ በመንግሥቱ ፡ መጀመርያ ፡ ለክርስቲያን ፡ በጎ ፡ አደረገ ፡፡ ባመት ፡ ፪፶፯፡ ግን ፡ ያሳደቸው ፡ ዘንድ ፡ ጀመ ረ ፡፡ በዚያም ፡ ዘመን ፡ ቂጵርያኑስን ፡ የከርታጎን ፡ ኤጲስቆ ጶስ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖቱ ፡ ገደሉት ፡፡ በመጀመርያው ፡ ሹሙ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ብቻ ፡ ሰደደው ፡ ኩሩቢስ ፡ ወደ ፡ ሚሉ ት ፡ አገር ፡ የክርስቲያንን ፡ ጉባኤም ፡ መሰብሰብ ፡ ከለከ ለ ፡፡ ደሮ ፡ ምንድር ፡ ይችላል ፡ ከመሬት ፡ የተፈጠረ ፡ ሰው ፡ ከፈጣርዩ ፡ ላይ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡፡ ቂጵርያኑስም ፡ በሥጋ ፡

ከቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ የተለየ ፡ ነበረ ፡ በመንፈስ ፡ ግን ፡ ግን
ድነታቸው ፡ ኖረ ። ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ሰደዱ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖታ
ቸው ፡ በተራራ ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ብረትም ፡ ደንጊያውንም ፡
ደቍፈሩ ፡ ዘንድ ፡ እጅግ ፡ ሊያስደክምዋቸው ፡ ሊያስጨን
ቋቸውም ፡ ብለው ። ቂጵርያኑስ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ መሻታቸው ፡
ምግብና ፡ ልብስ ፡ አከማቾ ፡ የተከማቸውንም ፡ ሰደደላ
ቸው ። ለሥጋቸውም ፡ ሲያስብ ፡ ለነፍሳቸው ፡ የሚፈለገ
ውን ፡ ነገር ፡ መጠበቅ ፡ አልተወም ። ቁሣርም ፡ ወደ ፡ ተራሮ
ች ፡ ለሰደዷቸው ፡ ክርስቲያኖች ፡ ከዚያ ፡ ይሰሩ ፡ ይደክሙ
ም ፡ ዘንድ ፡ ቂጵርያኑስ ፡ እንዲህ ፡ ጻፈላቸው ። በተራሮች ፡
ጕድጓድ ፡ ሥጋ ፡ በምንጻፍና ፡ በሞኻደ ፡ አያርፍም ፡ በክ
ርስቶስ ፡ ማጽናትና ፡ በደስታው ፡ እንጂ ። በስራም ፡ የደከ
ሙ ፡ ብልቶች ፡ በመሬት ፡ ይተኛሉ ። ደሮ ፡ ከክርስቶስ ፡ ጋ
ራ ፡ ከዚያ ፡ መኝታ ፡ መከራ ፡ አይቈጠርም ። የሚደ ፡ ሰ
ውነታችሁ ፡ በድፍ ፡ ቢከደን ፡ የውሥጥ ፡ ሰውነታችሁ ፡ በ
መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይነጻ ። እንጀራስ ፡ አጣችሁ ፡ ሰው ፡ ግን ፡
በንጀራ ፡ ብቻ ፡ አይኖርም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እን
ጂ ። ስትበርዱም ፡ ልብስ ፡ የላችሁም ። ክርስቶስን ፡ ግን ፡
የሚለብስ ፡ ሰው ፡ ልብስና ፡ ሽልም ፡ አያልቅበትም ። ቍ
ርባንንም ፡ መቀበል ፡ አሁን ፡ ባይቻላችሁ ፡ ለሃይማኖታች
ሁ ፡ አይጐደም ። ከሁሉ ፡ የተሻለውን ፡ ቍርባንን ፡ ትቀበላ
ላችሁና ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ የከበረውን ፡ መሥዋት ፡ ት
ሠዋላችሁ ፡ ልባችሁን ፡ ብታቀርቡለት ። መጽሐፍ ፡ ቅዱ
ስ ፡ ይለልና ። የተሰበረው ፡ የተደቈሰም ፡ ልብ ፡ ምሥዋዕ
ት ፡ ነው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኝ ። ለቀሳውስት
ም ፡ ቂጵርያኑስ ፡ እንዲህ ፡ ይጽፈል ። የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
ታላቅ ፡ ክፍል ፡ ምሳልያችሁን ፡ ተከተሉ ። ከላንተ ፡ ጋራ ፡
ሃይማኖታቸውን ፡ አስታውቀዋልና ፡ ከላንተ ፡ ጋራም ፡ ተቀ
ጽለዋልና ። እርሳቸውም ፡ በብርቱ ፡ ፍቅር ፡ ማሠርያ ፡ ከ
ላንተ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ናቸው ። የፍቅርም ፡ ማሠርያ ፡ ግዞት
ና ፡ ተራራ ፡ አይፈቱባቸውም ፡ መንጎችም ፡ ከጠባቂቻቸው ፡
ዘንድ ፡ አይለዩም ። የሚያሸንፍ ፡ ልቡና ፡ ኃይል ፡ ሆይ ፡ ያላ
ችሁ ። በልባችሁም ፡ ያለ ፡ ድል ፡ ሆይ ፡ በተራሮች ፡ ጕድጓ

ደች ፡ ትመላለሱ ፡ ዘንድ ፡ ሥጋ ፡ ታሥሮ ፡ ልብ ፡ ግን ፡ የሚ
ሠለጥን ፡ አውቃችሁ ፡ ክርስቶስ ፡ ከላንት ፡ ዘንድ ፡ እንደ
ሆን ፡ በባሮቹ ፡ ትዕግሥትም ፡ ደስ ፡ እንዲል :: በፍላጎቹ ፡
በመንገደቹም ፡ ሒደችሁ ፡ ወደ ፡ ዘላለም ፡ መንግሥቱ ፡ የ
ምትገቡ ::

ቄሣርም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ በማሳደድ ፡ እንደልጉደ
ት ፡ አየ :: ኤጲስቆጶሳትን ፡ ቀሳውስትንም ፡ መንጋቸውን
ም ፡ በለየ ፡ ጊዜ ፡ ሁላቸው ፡ በየስፍራቸው ፡ የወንጌልን ፡
ትምርት ፡ ዘረጉ ፡ ባካሔደቸውም ፡ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ለሃይ
ማኖት ፡ አስገዙ :: ይህነን ፡ አይቶ ፡ ባመት ፡ ፪፻፵ ፡ አዘዘ ፡
ኤጲስቆጶሳትን ፡ ቀሳውስትንም ፡ ዲያቆናትንም ፡ እንዲያ
ው ፡ በሰይፍ ፡ ይገድሉ ፡ ዘንድ ፡ ሊቃውንትና ፡ ታላላቆችን
ም ፡ ክብራቸውን ፡ ሹመታቸውንም ፡ ገንዘባቸውንም ፡ ከር
ሳቸው ፡ ይወስዱ ፡ ዘንድ ፡ ከዚያ ፡ ወዲያም ፡ እርሳቸው ፡
ደግሞ ፡ ክርስቲያን ፡ ኑረው ፡ እንደሆኑ ፡ እርሳቸውንም ፡
በሰይፍ ፡ ይገድሉት ፡ ዘንድ :: የከበሩም ፡ ሴቶች ፡ ገንዘባ
ቸው ፡ ተይዞ ፡ ካገራቸው ፡ ይፈልሱ ፡ ዘንድ :: ቄሣርንም ፡
ባምባው ፡ የሚያገለግሉት ፡ ክርስቱያናት ፡ የቄሣር ፡ ገንዘ
ብ ፡ ሁነው ፡ ታሥረው ፡ ሉብርቱ ፡ ተግባር ፡ ሊሔዱ ፡ ነበሩ ::
የዚያን ፡ ጊዜም ፡ የሮምን ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ሲክስቱስ ፡ አራ
ትንም ፡ ከዲያቆናቱ ፡ ገደሉ :: አያሌ ፡ ቀንም ፡ በኋላ ፡ በቂ
ጵርያኑስ ፡ በከርታጎ ፡ ሲሆን ፡ ጊዜ ፡ ፈረደበት ፡ የሮም ፡ አ
ማልክትም ፡ ጸላት ፡ ሁንዋልና ፡ ገደሉት :: መጨረሻው ፡ ቃ
ሉ ፡ ይህ ፡ ነበረ :: እግዚአብሔር ፡ ይመስገን ::

ባሌርያኑስም ፡ ከፋርስ ፡ ጋራ ፡ ጾር ፡ ባደረገ ፡ ጊዜ ፡ ፋር
ሳውያን ፡ መቱት ፡ ማረኩትም ፡ ገደሉትም ፡ ባመት ፡ ፪፻፶ ::
ልጁም ፡ ገሌኑስ ፡ በመንግሥቱ ፡ ተከተለው :: ያም ፡ ስለ ፡
ሃይማኖትና ፡ ስለ ፡ መንግሥቱ ፡ መግዛት ፡ አላሰበምና ፡ ለ
ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጠቀመ :: ትእዛዝን ፡ ሰጠ ፡ የታሠሩ ፡
ክርስቲያናት ፡ ሁሉ ፡ ሊፈቱ ፡ ያፈለስዋቸውም ፡ ሊመለሱ ፡
ካብያተ ፡ ክርስቲያናትም ፡ የወሰዱ ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉ ፡ ሊመ
ለሱላቸው :: በዚህም ፡ ትእዛዝ ፡ ለክርስቲያናት ፡ ሥልጣ
ንን ፡ ሰጠ ፡ እንደ ፡ ሃይማኖታቸው ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአ

ብሔርንም ፡ ያመልኩ ፡ ዘንድ ። አሁንም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ከስደታቸው ፡ ዕረፍት ፡ አገኙ ፡ እስከ ፡ ዲዮቅሌትያኖስ ፡ መንግሥት ፡ ድረስ ።

ዲዮቅሌትያኖስም ፡ ካመት ፡ ፪፻፹፬፤ እስከ ፡ ፫፻፭፤ ድረስ ፡ ነገሠ ። በመንግሥቱም ፡ መጀመርያ ፡ እርሱ ፡ ብቻውን ፡ ነገሠ ፡ ፪፤ አመት ። ከ፪፻፹፮፤ ጀምሮ ፡ መክሲሚያኖስ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ነገሠ ። ከ፪፻፺፫፤ ጀምሮም ፡ ከጋሌርዮስና ፡ ከቈንስታንቲዮስ ፡ ኽሎሮስ ፡ ጋራ ፡ ነገሠ ፡ ፬፤ ቄሣሮች ፡ ከርሳቸውም ፡ ሁለት ፡ ታላቆች ፡ ዲዮቅሌቲያኖስና ፡ መክሲሚያኖስ ፡ አለዚህ ፡ ፪ም ፡ አውጉስቶስ ፡ ተባሉ ። ፪፤ ታናሾችም ፡ ቄሣሮች ፡ ብቻ ፡ የተባሉ ፡ ጋሌርዮስና ፡ ቈንስታንቲዮስ ፡ ክሎሮስ ። ቈንስታንቲዮስ ፡ ክሎሮስም ፡ የታላቅ ፡ ቈንስታንቲኖስ ፡ አባት ፡ ሆነ ። ዲዮቅሌትያኖስም ፡ ከመክሲምያኖስ ፡ ጋራ ፡ በኢጣልያና ፡ ባፍሪቃ ፡ በስያም ፡ ላይ ፡ ገዙ ፡ የጋሌርዮስም ፡ ግዛት ፡ ኢሊርያ ፡ የቈንስታንትዮስ ፡ ክሎሮስ ፡ ግዛትም ፡ ጋልያ ፡ ስጳንያም ፡ እንግልጣርም ፡ ሆነ ። ከሁላቸውም ፡ ዲዮቅሌትያኖስ ፡ በለጠ ፡ ባልንጀሮቹ ፡ በርሱ ፡ ፈቃድ ፡ ብቻ ፡ ተሹመዋልና ።

ዲዮቅሌትያኖስም ፡ በመጀመርያው ፡ ክርስቲያንን ፡ አላሳደዳቸውም ፡ እስከ ፡ ፫፻፫፤ ድረስ ። ጋሌርዮስ ፡ የክርስቲያን ፡ ጸላት ፡ ነበረና ፡ የዲዮቅሌትያኖስም ፡ አማች ። እርሱም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ አስቀድሞ ፡ ዲዮቅሌትያኖስን ፡ ለመነ ፡ የክርስቲያንን ፡ ሃይማኖት ፡ እንዲከለክል ። እርሱ ፡ ግን ፡ እምቢ ፡ አለው ፡ ክርስቲያን ፡ እጅግ ፡ በዝተዋልና ፡ በማሳደድም ፡ ሁሉ ፡ አይጠፉም ፡ ብሎት ። ደሮ ፡ ጋሌርዮስ ፡ ልመናውን ፡ ወትሮ ፡ ሲደግም ፡ እርሱ ፡ በመጨረሻ ፡ እሺ ፡ አለው ፡ ባመት ፡ ፫፻፫፤ ዲዮቅሌትያኖስ ፡ ከጋሌርዮስ ፡ ጋራ ፡ በኒቆሜዲያ ፡ በቢቲንያ ፡ በተገናኙ ፡ ጊዜ ። ለክርስቲያናት ፡ በዚያች ፡ ከተማ ፡ እጅግ ፡ የተዋበች ፡ መቅደስ ፡ ነበረችላቸው ። አረማውያንም ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ማልደው ፡ በግድ ፡ በዚህ ፡ መቅደስ ፡ ገቡ ፡ ያገኙበትንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መጻሕፍት ፡ ሁሉ ፡ አቃጠሉ ፡ መቅደስንም ፡ ቀምተው ፡ አፈረሱት ። ነጋም ፡ ይህነን ፡ ትእዛዝ ፡ ተጽፎ ፡ ባደባ

ባይ : በገቢያም : ሁሉ : አወጡት :: የቤተ : ክርስቲያንን : መሰብሰብ : ሁሉ : ሊከለክሉ : ቤተ : መቅደሳቸውንም : ሊያፈርሱ : የመጽሐፍ : ቅዱስ : እርሱም : የብሉይና : ያዲስ : ኪዳን : መጻሕፍትን : ሁሉ : ሊያነዱ : ታላቆች : ክርስቲያናትም : ባይክዱ : ሹመታቸው : ክብራቸውም : ሊሻር : ክርስቲያንም : ሁሉ : በፍርድ : ሊሠቀዩ : ታናሾች : ክርስቲያናትም : አርነታቸው : ጠፍቶ : ባሮች : ሊሆኑ :: ባሮች : ክርስቲያናትም : ባይክዱ : ከቶ : አርነት : እንደይ ወጡ ::

ይህነን : ትእዛዝ : ሰይጣን : በጅግ : ተንኰል : አስደረገ :: መጽሐፍ : ቅዱስ : ከጠፋ : ቤተ : ክርስቲያንም : ሁሉ : ብጠፋ : ነበረች :: ደሮ : እግዚአብሔር : ጉባኤውን : ጠበቀ :: ይህ : መከራ : ሳይመጣ : መጽሐፍ : ቅዱስ : እጅግ : ተዘርግትዋልና : በሮም : መንግሥትም : በንግደ : አገርም : በልዩ : ልዩ : ቋንቋም :: የሮምም : ሹማምት : ሁሉ : ያንድ : ልብ : አልነበሩም :: ለክርስቲያን : እጅግ : ክፉ : ያላሰበ : ሹም : ሁሉ : እጅግ : አልመረመረም : ስለ : መጻሕፍታቸው :: ብዙም : ከክርስቲያናት : ለሚመረምር : ሹም : በመጽሐፍ : ቅዱስ : ፈንታ : የመናፈቃንን : መጻሕፍት : ሰጡት :: አያሌ : ግን : ሰውን : ፈርተው : መጽሐፍ : ቅዱስ : ለሚመረምሩ ፤ አረማውያን : አሳልፈው : ሰጡት :: ሌሎች : ግን : እንደ ያው : እምቢ : አሉ : ከመስጠት :: ሕይወታቸውንም : መስጠት : ስለ : ክርስቶስ : መረጹ : መጻሕፍትን : ከመስጠት : ፈንታ ::

ባንዲት : አገርም : በኑሚዲያ : አንዲት : ጉባኤ : ክርስቲያን : የነበረ : ተያዘች :: በዲያቆን : ቤተ : ተሰብስበው : ነበረ : ቄስ : ወደ : አስተማሪቸውበት : ቍርባንንም : ወደ : ተቀበሉበት :: ተይዘውም : ወደ : ከርታጎ : ወደ : ፍርድ : ሔዱ : በመንገደቸው : ቅኔ : ሲዘምሩ : ለእግዚአብሔር : ምስጋና :: ከርሳቸውም : ብዙን : ሠቀዩ : የተሰወረውን : ነገር : የተሸሸገውንም : መጽሐፍ : ሊያውቁበት :: አንድም : ተሠቅዮ : ጸራ : እንዴህ : ሲል :: እላንተ : ትበድላላችሁ : እላንተ : ክፎች :: ንጹሐንን : ትቀደላችሁና :: እኛ :

ወንበዶች ፡ አይደለነምና ፡፡ ማንንም ፡ አልሸነግልነም ፡፡ አምላኬ ፡ ሆይ ፡ ማረኝ ፡፡ አመሰግንሃለሁ ፡ አቤቱ ፡፡ ኃይል ፡ ስጠኝ ፡ ይህነን ፡ መከራ ፡ ስለ ፡ ስምህ ፡ እታገሥ ፡ ዘንድ ፡፡ ባሮችህን ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ግዞት ፡ አርነት ፡ አውጣቸው ፡፡ አመሰግንሃለሁ ፡ ማመስገንም ፡ አልችልም ፡፡ የመንግሥትን ፡ አምላክ ፡ አመሰግናለሁ ፡፡ የዘላለም ፡ መንግሥት ፡ ትገለጻለች ፡ የማትጠፋም ፡ መንግሥት ፡፡ ጌታችን ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፡ እኛ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ነን ፡፡ ላንተም ፡ እንገዛለን ፡ አንተም ፡ ተስፋችን ፡ ነህ ፡፡ ሹሙም ፡ ባለው ፡ ጊዜ ፡፡ ምነው ፡ የቄሣርን ፡ ትእዛዝ ፡ አልጠበቅህም ፡፡ እርሱ ፡ መለሰለት ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ እኔ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ የተማርሁበትን ፡ እርሱን ፡ ብቻ ፡ እጠብቃለሁ ፡፡ ስለዚህ ፡ ሕግም ፡ እሞታለሁ ፡ በዚህ ፡ ሕግም ፡ እፈጸማለሁ ፡ ሌላ ፡ የለም ፡፡ ሌላ ፡ ሰውም ፡ በተሠቀየ ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ጸለየ ፡፡ እርዳኝ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆይ ፡ እለምንሃለሁ ፡ ማረኝም ፡፡ ነፍሴንም ፡ ጠብቅ ፡ መንፈሴንም ፡ አጽና ፡ እንዳላፈር ፡፡ ለመታገሥም ፡ ኃይል ፡ ስጠኝ ፡፡ ዲያቆንንም ፡ ጉባኤ ፡ በቤቱ ፡ ተሰብስበው ፡ ወደ ፡ ነበሩ ፡ ሹም ፡ አለው ፡፡ ምነው ፡ ተቀበልሃቸው ፡፡ እርሱም ፡ ተሠቅዮ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ መለሰለት ፡፡ ወንድሞቼን ፡ መቀበል ፡ እንጅ ፡ ሌላ ፡ አይቻለኝም ፡፡ ሹሙ ፡፡ የቄሣርን ፡ ትእዛዝ ፡ ግን ፡ ልትጠብቅ ፡ ነበርህ ፡፡ ዲያቆን ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ከቄሣር ፡ ይበልጣል ፡፡ ሹሙ ፡፡ መጻሕፍት ፡ ቅዱሳት ፡ አሉን ፡ በቤትህ ፡፡ ዲያቆን ፡፡ አሉኝ ፡ በልቤ ፡፡ በታሠረት ፡ መካከልም ፡ አንዲት ፡ ክርስቲያን ፡ ሴት ፡ ነበረች ፡ ቢክቶርያ ፡ የተባለች ፡ አባትዋ ፡ ወንድምዋም ፡ አረማውያን ፡ የነበሩ ፡፡ ወንድምዋም ፡ ፎርቱናትያኑስ ፡ ይመጣ ፡ ነበር ፡ ለመካድ ፡ እሺ ፡ ሊያሰኛት ፡ ሊያስፈታትም ፡፡ እርስዋ ፡ ግን ፡ ስትጸና ፡ ወንድምዋ ፡ አለ ፡፡ እርስዋ ፡ ልብ ፡ የላትም ፡፡ እርስዋ ፡ ግን ፡ አለች ፡፡ ይህ ፡ ልቤ ፡ ነው ፡፡ እርሱንም ፡ ከቶ ፡ አልለውጥም ፡፡ ሹሙም ፡ በጠየቃት ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ ከወንድምሽ ፡ ጋራ ፡ ትሔጂለሽን ፡፡ እርስዋም ፡ እንዲህ ፡ ስትል ፡ መለሰች ፡፡ እንኳን ፡፡ እኔ ፡ ክርስቲያን ፡ ነኝና ፡፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ት

ኣዛዥ ፡ የሚያድርጉ ፡ እርሳቸው ፡ ወንድሞቼ ፡ ናቸው ፡፡ አንድ ፡ ታናሽ ፡ አሽከርም ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፡ ስሙ ፡ ሂላርያኖስ ፡፡ ሹሙም ፡ በቅያሚው ፡ ቶሎ ፡ ሊያስፈራው ፡ ብሎ ፡ ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ በዚህ ፡ ሕፃንም ፡ ብርቱ ፡ ሁኖ ፡ ተገለጸ ፡፡ ሹምን ፡ ብልዋልና ፡፡ እንደ ፡ ፈቃደኛችሁ ፡ አድርጉ ፡፡ እኔ ፡ ክርስቲያን ፡ ነኝና ፡፡

የግዞት ፡ ቤቶችም ፡ ሁሉ ፡ በክርስቲያን ፡ እሥሮች ፡ መሉ ፡ አዲስ ፡ ትእዛዝ ፡ ሲወጣ ፡ የሚል ፡፡ ከሥሮች ፡ የሚሠዉ ፡ ሁሉ ፡ ሊፈቱ ፡፡ የቀሩትም ፡ ሁሉ ፡ በግድ ፡ ላማልክት ፡ ሊሠዉ ፡፡ በዚህም ፡ ትእዛዝ ፡ ላይ ፡ አራተኛ ፡ ተጨመረ ፡ ባመት ፡ ፫፻፬ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ ሊሠዉ ፡ ያዘዘ ፡፡ አሁንም ፡ አሳዳጆች ፡ የክርስቲያንን ፡ ሃይማኖት ፡ ፈጽመን ፡ ሻርነ ፡ አሉ ፡፡ ደሮ ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ የሃይማኖት ፡ ድል ፡ መንሣት ፡ ቀረበ ፡፡

ቆንስታንቲዩስ ፡ ኽሎሮስ ፡ እርሱ ፡ ከ፬ ቄሣሮች ፡ አንድ ፡ የነበረ ፡ ክርስቲያንን ፡ ወደደ ፡፡ ስለ ፡ ሃይማኖትም ፡ መከራ ፡ ይቀበሉ ፡ የነበሩትን ፡ አከበራቸው ፡ ከሌሎች ፡ ይልቅም ፡ ታመነባቸው ፡፡ ላምላኩ ፡ የታመነ ፡ ያልሆነ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ለንጉሥም ፡ ከቶ ፡ የታመነ ፡ አይሆንም ፡ አለ ፡፡ በመንግሥቱም ፡ በጋልያ ፡ በስጳንያም ፡ በእንግልጣርም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እጅግ ፡ መከራ ፡ አልተቀበለችም ፡፡

ዲዮቅሌትያኖስና ፡ መክሲሚያኖስ ፡ ባመት ፡ ፫፻፭ መንግሣቸውን ፡ አስቀመጡ ፡ ጋሌርዮስና ፡ ቆንስታንቲዮስ ፡ ኽሎሮስም ፡ በስፍራቸው ፡ ቄሣሮች ፡ አውጉስቶች ፡ ሆኑ ፡፡ ሴቤሩስም ፡ መክሲሚኑስም ፡ ቄሣሮች ፡ ሆኑ ፡፡ ሴቤሩስም ፡ በኢጣልያ ፡ መክሲሚኑስም ፡ በእስያ ፡፡ መክሲሚኑስም ፡ እንደ ፡ ጋሌርዮስ ፡ ነበረ ፡ የክርስቲያን ፡ ጸላት ፡፡ እርሱም ፡ አዲስ ፡ ስደት ፡ አደረገ ፡ በክርስቲያን ፡ ላይ ፡፡ ወደ ፡ ገብያ ፡ የመጣ ፡ ምግብና ፡ መጠጥ ፡ ሁሉ ፡ ለጣዖታት ፡ ወደ ፡ ተሠዋ ፡ ውኃ ፡ ወይስ ፡ ፀጅ ፡ ያግቡበት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፡፡ በዚህም ፡ ትእዛዝ ፡ አያሌ ፡ ደም ፡ ፈሰሰ ፡፡

ቆንስታንቲዮስ ፡ ኽሎሮስም ፡ ሞተ ፡፡ ባመት ፡ ፫፻፮ ልጁ

ም ፡ እርሱ ፡ በኋላ ፡ ታላቅ ፡ የተባለ ፡ ቆንስታንቲኖስ ፡ በመንግሥቱ ፡ ተከተለው ፡፡ መክሰንቲዩስም ፡ ኢጣልያንና ፡ አፍሪቃን ፡ ወሰደ ፡ ከሴቬረስ ፡፡ ባመትም ፡ ፫፻፯፡ ሊቂኒዩስ ፡ ቄሣር ፡ ሆነ ፡ በኢሊርያ ፡ ላይ ፡፡

ጋሌርዮስም ፡ እርሱ ፡ ይህነን ፡ ስደት ፡ አስቀድሞ ፡ ያስነሣው ፡ በጅግ ፡ ብርቱ ፡ ሕማም ፡ ወደቀ ፡ ሲታመምም ፡ ጊዜ ፡ ከክርስቲያን ፡ አምላክ ፡ ፈራ ፡ እጅግ ፡ በድሎታልና ፡ የክርስቲያንም ፡ ሃይማኖት ፡ በስደቱ ፡ ሁሉ ፡ እንደልተጐዳ ፡ አይቶዋልና ፡ ስለዚህም ፡ ባመት ፡ ፫፻፲፩፡ ትእዛዝን ፡ አወጣ ፡ ክርስቲያን ፡ በቄሣሮች ፡ ምህረት ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንደ ፡ ሃይማኖታቸው ፡ ሊያመልኩት ፡ የርሳቸውንም ፡ የክርስቲያንን ፡ አምላክ ፡ ሊለምኑ ፡ ለቄሣሮች ፡ ለመንግሥትም ፡ ለራሳቸውም ፡ ደህንነት ፡ መንግሥት ፡ ሁሉ ፡ በደህንነት ፡ ትኖር ፡ ዘንድ ፡፡

አሁንም ፡ አየነ ፡ አሕዛብ ፡ በግድ ፡ ያደረጉትን ፡ ነገር ፡ በክርስቲያን ፡ ላይ ፡ ክርስቶስም ፡ ጉባኤውን ፡ እንደ ፡ ጠበቃት ፡ እንደትጐደበት ፡፡ ደግ ፡ ሰይጣን ፡ በግድ ፡ ብቻ ፡ አልሰራም ፡ በክርስቲያን ፡ ላይ ፡ በውቀትም ፡ እንጅ ፡፡ ባሮቹን ፡ አስነሥተዋቸዋል ፡ ፊሎሶፎችን ፡ ቅኔ ፡ አድራጎችንም ፡ ተናጋሮችንም ፡ ሌሎች ፡ ጻፎችንም ፡ መጻሕፍት ፡ ይጽፉ ፡ ዘንድ ፡ ሰውን ፡ ከሃይማኖት ፡ ሊከለክሉባቸው ፡ ሃይማኖትንም ፡ ሊያፈርሱባቸው ፡፡

ከለዚህ ፡ ጽላቶችም ፡ በጽፈት ፡ መጐደት ፡ የፈለገ ፡ አንድ ፡ ቅኔ ፡ አድራጊ ፡ ሉቂያኖስ ፡ የተባላ ፡ ነበረ ፡፡ እርሱም ፡ በመጽሐፉ ፡ በክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ በሃይማኖትም ፡ ሁሉ ፡ ተላገጸ ፡፡

ሌላ ፡ ጸላትም ፡ በክርስቲያን ፡ ላይ ፡ የጻፈ ፡ ኬልሱስ ፡ ነበረ ፡ እርሱም ፡ ፊሎሶፊስ ፡፡ የሃይማኖት ፡ ትምርት ፡ ለርሱ ፡ ስንፍና ፡ መሰለው ፡፡ የሃይማኖትም ፡ ኃይለኛ ፡ ነገር ፡ ከሁሉ ፡ የከበረ ፡ እርሱም ፡ ክርስቶስ ፡ ለኃጢአተኞች ፡

እንደ ፡ መጣ ፡ ለጻድቃን ፡ አይደለም ፡ ለዚህ ፡ ሰው ፡ ዕንቅ
ፋት ፡ ሆነ ፡፡

ሶስተኛም ፡ ሰው ፡ በሃይማኖት ፡ ላይ ፡ የጻፈ ፡ ደግሞ ፡ ከ
ፈሎሶፎች ፡ ወገን ፡ ነበረ ፡ ስሙም ፡ ጶርፈርዮስ ፡፡

አራተኛም ፡ ሰው ፡ በሃይማኖት ፡ ላይ ፡ የጻፈ ፡ የቄሣር ፡
እንደኔ ፡ ነበረ ፡ በፊት ፡ በቢቲንያ ፡ በኋላም ፡ በእስክንድርያ ፡
ላይ ፡ ተሹሞ ፡፡ ስሙም ፡ ሂሮቅሌስ ፡፡ እርሱም ፡ ክርስቶ
ስን ፡ ካንድ ፡ አስማተኛ ፡ አጶሊናሪስ ፡ ከሚሉት ፡ ጋራ ፡ አ
ስተካክለው ፡ ከጢያና ፡ አገር ፡፡

ከለዚህ ፡ ጸላቶች ፡ ጻፎችም ፡ በቀር ፡ ማርቀስ ፡ አውሬ
ልዩስ ፡ ቄሣር ፡ ባለቤቱ ፡ በክርስቲያን ፡ ላይ ፡ ጻፈ ፡፡

ነገር ፡ ግን ፡ እለዚህ ፡ ጸላቶች ፡ ሁሉ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን
ን ፡ በመጕደት ፡ ፈንታ ፡ እጅግ ፡ ጠቀሙላት ፡፡ የእግዚአብ
ሔርን ፡ ቃል ፡ አጽንተውታልና ፡ እንደሂ ፡ ሲል ፡፡ የመስቀ
ል ፡ ቃል ፡ ለሚጠፉ ፡ስንፍና ፡ ነው ፡፡ ለኛ ፡ ግን ፡ ለምንድን
በት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ የእግዚአብሔርም ፡ ጥበ
ብ ፡ ነው ፡፡

ሁለተኛ ፡ ምዕራፍ ።

ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዓት ፡ በዚህ ፡ ዘመን ።
ስለ ፡ ተግሣጽም ። ስለ ፡ መለየትም ።

፩፤ ስለ ፡ ሥርዓት ።

የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዓት ፡ ባንድ ፡ ግዜ ፡ ፍጽምት ፡ አልሆነችም ። ክርስቶስና ፡ ሐዋርያት ፡ ስለርስዋ ፡ በቍርጥ ፡ ነገር ፡ የተገለጸውን ፡ ትእዛዝ ፡ አልሰጡምና ። ክርስቶስ ፡ ግን ፡ በወንጌልና ፡ በሐዋርያት ፡ ቃሉን ፡ ሰጠ ። በቃሉም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ለሚለምኑት ፡ ሁሉ ፡ ይሰጠው ፡ ዘንድ ፡ በመንፈሱም ፡ ምእምናንን ፡ ሁሉ ፡ በጊዜም ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ እውነት ፡ ሁሉ ፡ ይመራቸው ፡ ዘንድ ፡ ተስፋ ፡ አስደረገላቸው ። ደህ ፡ ነገርም ፡ ታላቅ ፡ ነው ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መቀበል ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ መምሪት ። ሥርዓት ፡ በዘመን ፡ ሁሉ ፡ በሰውም ፡ ባገርም ፡ ሁሉ ፡ አንዲት ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ አትችልም ፡ ትለወጣለች ፡ እንጂ ። የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ለዘላለምም ፡ አይለወጥም ።

፪፤ በሐዋርያት ፡ ዘመን ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንደዚህ ፡ ያለች ፡ አንድነት ፡ ነበረችባት ፡ ሁላቸው ፡ አንድ ፡ ሥጋ ፡ እንዲት ፡ ነፍስም ፡ እስኪሆኑ ፡ ድረስ ። ክርስቲያናትም ፡ ሁሉ ፡ በክርስቶስ ፡ ከቶ ፡ አልተለዩም ። ሁላቸው ፡ ያደም ፡ ልጆች ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ በሥጋ ፡ ሁላቸውም ፡ ለራሳቸው ፡ ያለ ፡ ክርስቶስ ፡ የጠፉ ፡ ኃጥአን ፡ እንደ ፡ ነበሩ ። እንደሁም ፡ በሃይማኖት ፡ ሁላቸው ፡ ባንድ ፡ ክርስቶስ ፡ ደኑ ። ሁላቸውም ፡ ባንድ ፡ መጽሬት ፡ ተጸሩ ። ባንድ ፡ ደምም ፡ ጸደቁ ። ባንድ ፡ መንፈስም ፡ ነጹ ፡ ተቀደሱም ። ጴጥሮስም ፡ ለሚያምን ፡ ሁሉ ፡ አለ ። እላንት ፡ የመንግሥትና ፡ የክህነት ፡ ወገን ፡ ናችሁ ፡ የተመረጠችም ፡ የተቀደሰችም ፡ ትውልድ ። ትገልጡ ፡ ዘንድ ፡ ከጨለማ ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ የጸራ

ችሁን ፡ ስራ ፡ በመደነቅ ፡፡ ፩፤ ጴጥሮስ ፡ ፬፤ ፬፤፤ ስለዚህች ፡ አ ንድነትም ፡ ይናገራል ፡ የዮሐንስ ፡ ወንጌል ፡ ፲፯፤ ፳፤ ፳፩፤ ፳፪፤ ፳፫፤፤ የሐዋርያት ፡ ስራ ፡ ፬፤ ፴፪፤፤ ሮሜ ፡ ፲፪፤ ፭፤፤ ፩፤ ቆሮ ንቶስ ፡ ፲፤ ፲፯፤፤ ኤፌሶን ፡ ፬፤ ፫፤ ፬፤ ፭፤ ፮፤፤ በዚችም ፡ አንድ ነት ፡ ክርስቶስ ፡ ብቻ ፡ ሊገዛ ፡ ነበረ ፡ ከክርስቶስና ፡ ከሚያ ምን ፡ ሁሉ ፡ መኻከል ፡ ከቶ ፡ ማንም ፡ እንዳይገባ ፡ የሚለ ያቸው ፡፡ ክርስቶስ ፡ ሁሉ ፡ በሁሉም ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡፡ ገላ ትያን ፡ ፫፤ ፳፯፤ ፳፰፤፤ ቆሎሰይስ ፡ ፫፤ ፲፤ ፲፩፤፤

፪፤፤ ሁላቸውም ፡ አንድ ፡ ሥጋ ፡ ሁነው ፡ በክርስቶስ ፡ ለ ዚህ ፡ ሥጋ ፡ ግን ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ብልቶች ፡ ነበሩ ፡ ባንድ ፡ መ ንፈስ ፡ የተሰማሙ ፡፡ ይህም ፡ መንፈስ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስጦ ታ ፡ እንደ ፡ ፈቃዱ ፡ ሰጠ ፡ ለየብልት ፡ ሁሉ ፡፡ ፩፤ ቆሮንቶ ስ ፡ ፲፪፤ ፯፤ ኤፌሶን ፡ ፬፤ ፯፤፤ ሮሜ ፡ ፲፪፤ ፬፤ ፭፤ ፮፤ ፯፤፤

፫፤፤ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ በሐዋርያት ፡ ዘመን ፡ መስጠቱ ን ፡ እንደ ፡ ሰጠው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ልትሰራበት ፡ እንዲ ህም ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መልእክት ፡ ሆነች ፡፡ ፩፤ ቆሮን ቶስ ፡ ፲፪፤ ፳፰፤፤ ኤፌሶን ፡ ፬፤ ፲፩፤፤ እንዲሁም ፡

፬፤ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ የተሾሙ ፡ የጌታች ን ፡ ሐዋርያት ፡ ነበሩ ፡፡ እርሳቸውም ፡ ከጌታ ፡ የተላኩ ፡ ነበሩ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ በመስበካቸው ፡ በማስተማሪ ቸውም ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ መጀመርያ ፡ ያደረገ ፡ በመ ጽሐፋቸው ፡ ምእምናንን ፡ ሁሉ ፡ የሚመራቸው ፡ እስከ ፡ ዓለም ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፡፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ መዝረ ጋት ፡ የርሳቸው ፡ ልዩ ፡ መልእክት ፡ ነበረ ፡፡

፭፤፤ ከሐዋርያትም ፡ በቀር ፡ ነቢያት ፡ ነበሩ ፡፡ በቤተ ፡ ክ ርስቲያን ፡ በመጀመርያ ፡ ዘመን ፡፡ ደሮ ፡ የትንቢት ፡ መስ ጠት ፡ ሰው ፡ የሚመጣወን ፡ ነገር ፡ በፊት ፡ የሚያውቅበ ት ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ኃይልም ፡ እን ጂ ፡ ለብርቱ ፡ መንፈሳዊ ፡ መናገር ፡፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሰ ውን ፡ መንፈሳዊ ፡ ዓይን ፡ ሲከፍት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነ ገር ፡ በሕይወት ፡ ያይ ፡ ዘንድ ፡ በልቡም ፡ የመንፈስ ፡ እሳ ት ፡ ሲሰጥ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ይቃጠል ፡ ዘንድ ፡፡ አፉንም ፡ ሲከፍት ፡ የሚገባውን ፡ ነገር ፡ ሰው ፡ ሳያስብ ፡ በሕይወት

ና ፡ በኀይል ፡ ይናገር ፡ ዘንድ ። ፩፡ ቆሮንቶስ ፡ ፲፬፡ ፩፡ እስከ ፡ ፭። ፳፬፡ ፳፭፡ ፳፰።

፫፫። ደግሞም ፡ ወንጌላውያን ፡ ነበሩ ፡ ካገር ፡ ወደገር ፡ የዞሩ ፡ በወንጌል ፡ ያስተምሩ ፡ ዘንድ ፡ በክርስቲያን ፡ ጉባ ኤዎች ። እንደሁም ፡ ፊልጶስ ፡ በርናባስም ፡ ሲላስም ፡ ጢ ሞቴዎስም ፡ ቲቶስም ፡ ነበሩ ። ኢለዚያም ፡ የጌታችንን ፡ ታሪክና ፡ ትምርት ፡ ከልደቱ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዕርገቱ ፡ ድረ ስ ፡ የጻፉት ፡ ማቴዎስ ፡ ማርቆስም ፡ ሉቃስም ፡ ዮሐንስም ፡ ወንጌላውያን ፡ ተባሉ ።

፬፬። በየቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ሁሉ ፡ የተሾሙ ፡ ጠባቆ ች ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ሽማግሎች ፡ ወይስ ፡ ቀሳውስት ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ተባሉ ። ቄስም ፡ በ ዮናኒ ፡ ቋንቋ ፡ ጵሬስቢተሮስ ፡ ማለት ፡ ሽማግሌ ፡ ይባላል ። ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ለመጠበቅ ፡ ብላቴኖችን ፡ አልወሰዱ ምና ፡ ሽማግሎችን ፡ እንጂ ፡ የሰውን ፡ ማድረግ ፡ ያለምንም ፡ ነገር ፡ ያወቁትን ፡ በክርስቶስም ፡ ተፈትነው ፡ የጸኑ ፡ የጥበብና ፡ የመምራትንም ፡ ስጥወታ ፡ የተቀበሉ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ። ተግባራቸው ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ነበረና ። ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ሊጠብቁ ፡ ነበረና ፡ በጇቸው ፡ የታመኑባቸው ፡ የምእምናን ፡ ነፍስ ፡ ሁሉ ፡ ለክርስቶስ ፡ እንዲሆን ፡ እንዲኖርም ፡ በሰ ይጣን ፡ እጅም ፡ እንዳይወድቅ ። ክርስቲያንም ፡ የተባለ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በኀጢአት ፡ በጨለማም ፡ እንዲደኖር ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ እግዚአብሔርን ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ልጅ ፡ የሱ ስ ፡ ክርስቶስን ፡ ወደ ፡ ማወቅ ፡ እንዲደርስ ። በዚህም ፡ ብ ርሃን ፡ እንዲመላለስ ። ክርስቲያንም ፡ ሁሉ ፡ በአካሔዱ ፡ የወንጌልን ፡ ትምርት ፡ እንዲያከብር ። በቤተ ፡ ክርስቲያ ንም ፡ ያሰት ፡ ትምርት ፡ የሰውም ፡ ትእዛዝ ፡ እንዳይነሣ ፡ ምእምናንን ፡ ለማሳት ። የክርስቶስ ፡ ጉባኤ ፡ ታድግ ፡ ዘ ንድ ፡ እንጂ ፡ ትፈጽምም ፡ ዘንድ ፡ በርሱ ፡ ራስዋ ፡ በሚ ሆን ፡ ክርስቶስ ። ስለዚህም ፡ ቄስ ፡ ጰደሚን ፡ የመንጋ ፡ ጠባቂ ፡ ኢጲስቆጶስም ፡ ጠባቂ ፡ ይባላል ። እርሳቸው ም ፡ በሐዋርያት ፡ ዘመን ፡ አንድ ፡ ነበሩና ። ቄስም ፡ አንዳ ንድ ፡ ጊዜ ፡ ጵሬስቢተሮስ ፡ ተባለ ፡ ስለ ፡ ሽምግልናው ፡ ስ

ለ ፡ ጥበቡም ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ስለ ፡ ተግባሩ ፡፡ ሁላቸውንም ፡ ጴጥሮስ ፡ የክርስቶስ ፡ ሐዋርያ ፡ በሽምግልናው ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡፡ በላንት ፡ ዘንድ ፡ ያሉትን ፡ ቅሬስቢትሮች ፡ እለምናቸዋለሁ ፡ እኔ ፡ ቅሬስቢትርስ ፡ እንደርሳቸው ፡፡ ለክርስቶስ ፡ሕማም ፡ የምመሰክር ፡ አንድነትም ፡ ያለኝ ፡ ለሚገለጠው ፡ ክብር ፡፡ እላንት ፡ የታመናቹሁባትን ፡ የክርስቶስን ፡ መንጋ ፡ ትጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ እጅግም ፡ ትጐብኙዋቸው ፡ ዘንድ ፡ በግድም ፡ አይደለም ፡ በልብ ፡ ፈቃድ ፡ እንጂ ፡፡ ረብ ፡ ለማገኘት ፡ አይደለም ፡ በርኅራኄ ፡ እንጂ ፡፡ እንደ ፡ ጌቶች ፡ በርስት ፡ ላይ ፡ ያሉ ፡ አይደለም ፡፡ ለመንጎች ፡ ምሳሌ ፡ እንደምትሆኑ ፡ እንጂ ፡፡ የጠባቆች ፡ አለቃ ፡ ሲገለጥ ፡ ጊዜ ፡ የማይጠፋውን ፡ የክብርን ፡ አክሊል ፡ ትቀበሉ ፡ ዘንድ ፡፡ ፩፡ ጴጥሮስ ፡ ፭፡ ፩፡ እስከ ፡ ፬፡፡

ሌላ ፡ ነገርም ፡ ስለ ፡ ቀሳውስትና ፡ ስለ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ስለ ፡ አንድነታቸውም ፡ ስለ ፡ ተግባራቸውም ፡ ይገኛል ፡ በሐዋርያት ፡ ሥራ ፡ ምዕራፍ ፡ ፳፡ ፲፯፡ ፳፰፡፡ ፩፡ ጢሞቴዎስ ፡ ፫፡ ፩፡ እስከ ፡ ፯፡፡ ቲቶስ ፡ ፩፡ ፭፡ ፮፡ ፯፡ ፰፡ ፱፡፡

፭፭፡፡ በመጀመርያው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ሰዎች ፡ ተገኙ ፡ ቀሳውስት ፡ ሳይሆኑ ፡ የማስተማርን ፡ ስጥወታ ፡ የተቀበሉ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስለዚህም ፡ ለማስተማር ፡ ተጸሩ ፡፡ ጳውሎስ ፡ ይላልና ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ሲናገር ፡፡ እርሱ ፡ ሰጠ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ አያሌ ፡ ሐዋርያት ፡ አያሌም ፡ ነቢያት ፡ ሌሎችመ ፡ ወንጌላውያን ፡፡ ሌሎችም ፡ ጠባቆች ፡ አስተማሮችም ፡፡ ቅዱሳን ፡ ይፈጽሙ ፡ ዘንድ ፡ ማገልገልን ፡ ለማድረግ ፡ የክርስቶስንም ፡ ስራ ፡ ለመስራት ፡፡ ሁላችን ፡ እስክንደርስ ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ ሃይማኖት ፡ አንድነት ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ልጅ ፡ ወደ ፡ ማወቅ ፡፡ እስከ ፡ ፍጹምም ፡ ተስፋ ፡ ድረስ ፡ እስከ ፡ ክርስቶስ ፡ አካል ፡ ፍጻሜ ፡ የሚያህል ፡፡ ኤፌሶን ፡ ፬፡ ፲፩፡ ፲፪፡ ፲፫፡፡

፭፮፡፡ ከለዚያም ፡ በቀር ፡ ዲያቆናት ፡ ተገኙ ፡ በሐዋርያት ፡ ዘመን ፡፡ ዲያቆንም ፡ ማለት ፡ አገልጋይ ፡ ነው ፡፡ እርሳቸውም ፡ በመጀመርያ ፡ በድኆች ፡ መክንያት ፡ ብቻ ፡ በየሩሳሌም ፡ ተሾሙ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ የሥጋዋን ፡ መ

ሻት ፡ ያበጀ ፡ ዘንድ ፡ ሐዋርያትም ፡ ለመንፈስዋ ፡ ብቻ ፡ ያስቡ ፡ ዘንድ ፡፡ በጥቂት ፡ በጥቂት ፡ ግን ፡ ጥቅማቸው ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በዝቶ ፡ ተግባራቸውም ፡ በዛ ፡፡ ለሥጋም ፡ ብቻ ፡ አልሆኑም ፡ ለነፍስም ፡ እንጂ ፡ በትምርት ፡ እንደ ፡ እስጢፋኖስ ፡ እንደ ፡ ፊልጶስም ፡፡ ደግሞም ፡ ዲያቆኒሶች ፡ ማለት ፡ ሴቶች ፡ ዲያቆኖች ፡ ነበሩ ፡ የሚያምኑትን ፡ ሴቶች ፡ መሻት ፡ ሊጠብቁ ፡፡ ከክርስቶስ ፡ ጉባኤ ፡ አንዷች ፡ እንዲደጉድል ፡ ክርስቲያንም ፡ ሁሉ ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ወንጌልን ፡ እንዲያውቅ ፡ የክርስቶስንም ፡ ፈቃድ ፡ እንዲፈጽም ፡ በርሱም ፡ እንዲድን ፡፡ ስለርሳቸውም ፡ ጳውሎስ ፡ ይናገራል ፡ ስለ ፡ እጲስቆጶሳት ፡ ከተናገረ ፡ በኋላ ፡፡ ፩፡ ጢሞቴዎስ ፡ ፫፡ ፰፡ እስከ ፡ ፲፫፡፡ ፭፡ ፱፡ ፲፡፡

ለሁላቸውም ፡ የጳውሎስ ፡ ነገር ፡ ደረሰ ፡ ሲል ፡፡ ስጥወታ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነው ፡ መንፈስ ፡ አንድ ፡ ሲሆን ፡፡ ለማገልገልም ፡ ልዩነት ፡ አለው ፡ እግዚአብሔር ፡ እርሱ ፡ አንድ ፡ ሲሆን ፡፡ ኀይልም ፡ ልዩ ፡ ነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሁሉን ፡ የሚያደርግ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሁሉ ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ ነው ፡፡ ለኢያንዳንዷም ፡ ይሰጠዋል ፡ ከመንፈስ ፡ የሚገባውን ፡ ያህል ፡፡ ፩፡ ቆሮንቶስ ፡ ፲፪፡ ፬፡ ፭፡ ፯፡ ፰፡፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ማገልገል ፡ የተሾሙ ፡ ሁሉ ፡ ባንድ ፡ ምክር ፡ በፊት ፡ ተመረጹ ፡ ሕዝብና ፡ ቀሳውስት ፡ ባንድ ፡ ሲማከሩ ፡፡ ከተመረጹም ፡ በኋላ ፡ በጸሎት ፡ እጃቸውን ፡ በራሳቸው ፡ ላይ ፡ ጫኑ ፡፡ የእግዚአብሔርንም ፡ መንፈስና ፡ በረከት ፡ በላያቸው ፡ ለመኑ ፡ እንዲሁም ፡ ቀደስዋቸው ፡፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ አለቆች ፡ ምንም ፡ አላደረጉም ፡ ከሕዝብ ፡ ጋራ ፡ እንጂ ፡፡

ይህችም ፡ ሥርዓት ፡ ከሐዋርያት ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ በጥቂት ፡ በጥቂት ፡ ተለወጠች ፡፡ ቀሳውስት ፡ በተሰበሰቡ ፡ ጊዜ ፡ በጉባኤያቸው ፡ 'ሲኖደስ' ፡ በሚሉት ፡ አንዷን ፡ ከመካከላቸው ፡ ለጊዜ ፡ መሪያቸው ፡ ሁኖ ፡ መረጹት ፡፡ በየጉባኤም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መሪን ፡ አደረጉ ፡፡ በኋላም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በቀሳውስት ፡ ጉባኤ ፡ ከሕዝብና ፡ ከቀሳውስት ፡ የተመረጸ ፡ መሪ ፡ ለወትሮ ፡ መሪ ፡ ሁኖ ፡ ኖረ ፡፡ እርሱም ፡ ብቻውን ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ተባለ ፡ የወንድሞቹ ፡ የቀሳውስት ፡ ጠባቂ ፡፡ እን

ደሁም ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በጥቂት ፡ በጥቂት ፡ ከቀሳውስት ፡ ተለየ ፡ ቀሳውስትም ፡ ከሕዝብ ፡ ተለዩ ፡ በሐዋርያት ፡ ዘመን ፡ አንድ ፡ የነበሩ ፡፡ እንደሁም ፡ ባደ ስ ፡ ሥርዓት ፡ ብሉይን ፡ ሥርዓት ፡ ተከተሉ ፡፡ ባደ ስ ፡ ሥርዓት ፡ የክርስቲያን ፡ ጉባኤ ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ዕፃ ፡ ሁኑ ው ፡ የቀሳውስትና ፡ የነገሥታት ፡ ወገን ፡ ነበሩ ፡ በብሉይ ፡ ግን ፡ የሌዊ ፡ ወገን ፡ ብቻ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ዕፃ ፡ ሁኖ ፡ ተቈጠረ ፡ በእሥራኤል ፡ በኵርነት ፡ ፈንታ ፡ እግዚአብሔር ፡ መርጾታልና ፡፡ ከዚህ ፡ ወገንም ፡ የሐሮንን ፡ ልጆች ፡ ቀሳውስትን ፡ አደረጋቸው ፡ እርሳቸውም ፡ ከሕዝባቸው ፡ ተለዩ ፡፡ እንደሁም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከሐዋርያት ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡፡ ቀሳውስት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሆኑ ፡ ካህናት ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ ባደሁድ ፡ ወገን ፡፡ ኤጲስቆጶስም ፡ እንደ ፡ ካህናት ፡ አለቃ ፡፡ ዲያቆናትም ፡ እንደ ፡ ሌዋውያን ፡፡

ደግሞም ፡ አንዳንድ ፡ አዲስ ፡ ማገልገል ፡ ገባ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡፡ በርሱም ፡ ሥርዓት ፡ በዛ ፡፡ የዲያቆናትም ፡ ተግባር ፡ በበዛ ፡ ጊዜ ፡ ሁለተኞች ፡ ዲያቆናት ፡ የተባሉ ፡ አደረጉ ፡ ዲያቆናትን ፡ የረዱ ፡፡ አንባቦችንም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚያነቡ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንንም ፡ መጻሕፍት ፡ የሚጠብቁ ፡፡ አኮሉቶችንም ፡ ተካታዮች ፡ ማለታቸው ፡፡ ኤጲስቆጶስን ፡ የሚከተሉ ፡ የሚረዱትም ፡፡ ኤክሶርኪስታንንም ፡ ማለት ፡ ክፎችን ፡ መናፍስት ፡ በጸሎት ፡ ከሰው ፡ የሚያውጡ ፡፡ በረኞችንም ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ቤት ፡ የሚከፍቱ ፡ የሚዘጉም ፡ የሚያነጹትም ፡ የሚጠብቁትም ፡፡

አሁንም ፡ እንናገራለን ፡ ስለ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መሰማማት ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡፡ ክርስቶስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ አንዲት ፡ ሁና ፡ አደረጋት ፡ መለየትም ፡ አላደረገባትም ፡ ለክርስቲያንም ፡ ጉባኤ ፡ ሁሉ ፡ አንዲት ፡ ተስፋ ፡ አንዲትም ፡ ጸጋ ፡ ነበረችላት ፡፡ የክርስቶስ ፡ ተስፋ ፡፡ "፪፡ ወይስ ፡ ፫፡ በስሜ ፡ ባንድ ፡ ወደ ፡ ተሰበሰቡበት ፡ ስፍራ ፡ ሁሉ ፡ እኔ ፡ በመካከላቸው ፡ ነኝ" ፡፡ በዚህም ፡ ልዩነት ፡ አልነበረም ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡

ወንጌል ፡ በፊት ፡ ወደ ፡ ከተሞች ፡ ደርስዋልና ፡ ከከተሞ ችም ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ ወደ ፡ መንደርም ፡፡ እንዲሁም ፡ በያገር ፡ በየመንደርም ፡ የነበሩ ፡ ኢብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ቀሳውስትን ፡ አደረጉላቸው ፡ እሌህም ፡ በከተማ ፡ ከኖረ ፡ ከኤጲስቆጶስ ፡ በታች ፡ ሆኑ ፡፡ የታናሾችም ፡ ከተሞች ፡ ኤ ጲስቆጶሳት ፡ ሁሉ ፡ ከሜትሮጶሊስ ፡ ከታላቆች ፡ ከተሞች ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ሜጥሮጶሊታኖች ፡ ወይስ ፡ ማጥራኖች ፡ የ ሜትሮጶሊሶች ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ከተባሉ ፡ በታች ፡ ነበሩ ፡፡ ከለዚህም ፡ ሜጥሮጶሊሶች ፡ ፭፡ ነበሩ ፡ ከቀሩት ፡ የበለጡ ፡ እርሳቸውም ፡ ሮም ፡ አንጾኪያም ፡ እስክንድርያም ፡ ኤፌሶንም ፡ ቆሮንቶስም ፡፡ ክርክርም ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ አስጠየቁ ፡ በለዚያ ፡ ከተሞች ፡ እንዴት ፡ ያስተምራሉ ፡ ከዚያ ፡ ሐዋርያት ፡ እጅግ ፡ ወደ ፡ ተቀመጡባቸው ፡ ከተ ሞች ፡ ብለው ፡፡ ከሁሉም ፡ የከበረች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሮም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ነበረች ፡፡ ሮም ፡ የሮም ፡ መንግ ሥት ፡ ሁሉ ፡ ከተማ ፡ ነበረችና ፡፡ ከዚያም ፡ እለዚያ ፡ ፪፡ ታላቆች ፡ ሐዋርያት ፡ ጴጥሮስና ፡ ጳውሎስ ፡ ለወንጌል ፡ መ ስክረው ፡ ሞቱ ፡፡ የምዕራብም ፡ ታላቅ ፡ ክፍል ፡ ወንጌልን ፡ ከሮምያ ፡ ወጥቶ ፡ ተቀበሉ ፡፡ ስለዚህም ፡ ይህች ፡ ቤተ ፡ ክ ርስቲያን ፡ ከሌላ ፡ ይልቅ ፡ ታመነች ፡፡

አብያተ ፡ ክርስቲያናትም ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ በሮም ፡ መ ንግሥት ፡ ሁሉ ፡ አንድነት ፡ ነበረላቸው ፡፡ በመልእክትም ፡ በሚዞሩ ፡ ክርስቲያኖች ፡ ወንድሞች ፡ ተገናኙ ፡፡ ማንም ፡ ክርስቲያን ፡ ወደ ፡ ሩቅ ፡ አገር ፡ መሔድ ፡ በወደደ ፡ ጊዜ ፡ አደራ ፡ መልእክትን ፡ ፈለገ ፡ ከኤጲስቆጶስ ፡ ወደ ፡ አብ ያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ሁሉ ፡፡ ይህችም ፡ መልእክት ፡ መሰከ ረችለት ፡ እርሱ ፡ ወንድም ፡ እንዲሆን ፡ ለክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ የክርስቲያንም ፡ ልብ ፡ ሁሉ ፡ ቤቱም ፡ ተከፈተለት ፡፡

በሮምም ፡ መንግሥት ፡ በየክፍልዋ ፡ የነበሩ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ክርክር ፡ ወይስ ፡ ሌላ ፡ ጉዳይ ፡ ቢሆንላቸ ው ፡ ባንድ ፡ ተሰበሰቡ ፡ ባንድ ፡ ይማከሩ ፡ ዘንድ ፡፡ እንዲህ ፡ ያለችም ፡ ብዙ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ የተሰበሰቡባት ፡ ጉባኤ ፡ በዮናኒ ፡ ቋንቋ ፡ ሲኖደስ ፡ ተባለች ፡፡ ማለቱ ፡ መሰ

ብሰብ :: እሌህም ፡ ሲኖዶች ፡ ጥቂት ፡ ዘመን ፡ ከሐዋርያት ፡ በኋላ ፡ ጀመሩ :: በየላይስ ፡ ምድርም ፡ ሲኖዶች ፡ ቶሎ ፡ ለሥርዓት ፡ ሆኑ :: በየጊዜም ፡ ተሰበሰቡ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ከቀሳውስትና ፡ ከሕዝቡ ፡ ጋራ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስንም ፡ መስጠት ፡ ለመኑ ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ጉዳይ ፡ ሁሉ ፡ ተማከሩ :: በግሪ ፡ አፍሪቃም ፡ በቀጳደቂያም ፡ ፪፻፤ አመት ፡ የሚያህል ፡ ከልደት ፡ በኋላ ፡ እለዚያ ፡ ሲኖዶች ፡ በያመት ፡ በያመት ፡ ተሰበሰቡ :: አሁንም ፡ በክርስቶስ ፡ መንፈስ ፡ በፍቅርም ፡ በትሕትናም ፡ ቢሰበሰቡ ፡ መልካም ፡ በሆነ ፡ ይህም ፡ የክርስቶስ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ' በ ስሜ ' ፡ ሲል ፡ እንዲህ ፡ ሲል :: ሁለት ፡ ወይስ ፡ ሶስት ፡ በ ስሜ ፡ በተሰበሰቡ ፡ ጊዜ ፡ እኔ ፡ በመካከላቸው ፡ ነኝ :: ደሮ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ አልሆነም :: ባንድ ፡ በተሰበሰቡ ፡ ጊዜ ፡ በሐሜት ፡ በቅናትም ፡ በጸላትነትም ፡ በትዕቢትም ፡ ተሰበሰቡ ፡ የክርስቶስም ፡ መንፈስ ፡ አልገዛም ፡ ያለም ፡ የሰይጣንም ፡ መንፈስ ፡ እንጅ ::

ሲኖዶችም ፡ የተማከሩትን ፡ የቈረጡትንም ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ስፍራ ፡ ሰደዱት :: በሩቅ ፡ አገርም ፡ የነበሩትን ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ አስታውቁበት ::

እንዲህም ፡ የክርስቶስ ፡ ጉባኤ ፡ በታላቅ ፡ በሮም ፡ መንግሥት ፡ ሁሉ ፡ በምድርም ፡ ሁሉ ፡ ተዘረጋች :: ልዩ ፡ ልዩ ፡ አሕዛብ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሰዎችም ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ስፍራም ፡ አስቀድሞ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ልማድ ፡ የነበረላቸው ፡ አሁንም ፡ ገና ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋ ፡ ባንድ ፡ የተናገሩ ፡ አንድ ፡ ክርስቶስ ፡ አንድ ፡ አምላክም ፡ አንድ ፡ ሃይማኖትም ፡ ሆናላቸው :: ስለዚህም ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡ አለ :: እኔ ፡ አምናለሁ ፡ ባንዲት ፡ ቅድስትና ፡ ካቶሊካዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በቅዱሳንም ፡ አንድነት :: ይህችን ፡ አንድነት ፡ ግን ፡ በመንፈስ ፡ ብቻ ፡ ከፈለጏት ፡ ካደረጏትም ፡ መልካም ፡ በሆነ :: በሥጋ ፡ ግን ፡ በመልክም ፡ ሲፈልጏት ፡ ጸላትነትና ፡ ሞት ፡ ሆነበት :: እንዲህ ፡ ይላልና ፡ ክርስቶስ :: በሚያደ ፡ በሥጋ ፡ መልክም ፡ በማድረግ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ እርስዋም ፡ አይነተኛ ፡ ቤተ ፡

ክርስቲያን ፡ አትመጣም ፡፡ የሚልም ፡ የለም ፡፡ እነሆ ፡ እ ርስዋ ፡ በዚህ ፡ ናት ፡ ወይስ ፡ እነሆ ፡ ከዚያ ፡፡ እነሆ ፡ የእግ ዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ በውሥጣችሁ ፡ በሰው ፡ መንፈስ ፡ ናት ፡፡ ሉቃስ ፡ ፲፯፤ ፳፩፡፡ በውነትም ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቴ ፡ የ ሚሆኑትን ፡ በፍሬያቸው ፡ ታወቋቸዋላችሁ ፡፡ የሚለኝ ፡ ሁ ሉ ፡፡ አቤቱ ፡ አቤቱ ፡ በስሜም ፡ የተጠመቀ ፡ ባፉም ፡ በሥ ጋውም ፡ ክርስቲያን ፡ ያለው ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ የሚገባ ፡ አይደለም ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ የሚያደርግ ፡ በሰማይ ፡ ያለውን ፡ ያባቴን ፡ ፈቃድ ፡፡ ማቴዎስ ፡ ፯፤ ፳፤ ፳፩፡፡ በዚህ ፡ ነገርም ፡ ክርስቶስ ፡ ይለያል ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በውነት ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ክርስቲያንም ፡ ያሉትን ፡ በስም ፡ ብቻ ፡ ካሉት ፡፡ በውነት ፡ ክርስቲያን ፡ ያሉ ፡ እርሳቸው ፡ ብ ቻ ፡ የክርስቶስ ፡ ጉባኤ ፡ ናቸው ፡፡ ቅድስትና ፡ ካቶሊ ካዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡፡ እርሳቸው ፡ የሰማዩ ፡ አባ ት ፡ ፈቃደን ፡ ያደርጋሉና ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ እግዚአብሔር ም ፡ ወደ ፡ እውነተኛ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይገባሉ ፡፡ እርሳቸ ውም ፡ ብቻቸው ፡፡ ክርስቲያን ፡ ግን ፡ የተባሉ ፡ ሁሉ ፡ በስ ምና ፡ ባፍ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚሆኑ ፡ ሁሉ ፡ የምትታይ ፡ ቤ ተ ፡ ክርስቲያን ፡ ናቸው ፡ ክርስቶስ ፡ መርበብን ፡ የመሰላት ፡ በነና ፡ ክፉ ፡ ዓሣ ፡ የመላበት ፡ ማቴዎስ ፡ ፲፫፤ ፵፯፤ እስከ ፡ ፶፡፡ በምትታይ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የማታይ ፡ ቤት ፡ ክር ስቲያን ፡ አለች ፡፡ እርስዋን ፡ ብልቶችዋንም ፡ እግዚአብ ሔር ፡ ብቻ ፡ ፈጽሞ ፡ ያውቃል ፡ በክፉልም ፡ እርሳቸው ፡ ይ ታወቃሉ ፡ በፍርያቸው ፡ በሃይማኖታቸውና ፡ ባካሔዳቸው ፡፡ እርሳቸውም ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ናቸው ፡ በክርስቶስ ፡፡ ያለለ ዚህም ፡ ያለማታይ ፡ ያለ ፡ ቅድስትና ፡ ካቶሊካዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ደህንነት ፡ የለም ፡ በሰማይና ፡ በምድር ፡፡

ከዚያ ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ ግን ፡ ብምትታይ ፡ በማታይም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መኻከል ፡ መልካም ፡ አለዩምና ፡ ታላ ቅ ፡ ስሕተት ፡ ተነሣ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እጅግ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ የመጣበት ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡፡ ይህነንም ፡ ስሕተት ፡ በመ ጀመርያ ፡ ጊዜ ፡ ፈጽመን ፡ እናገኛለን ፡ በቁም ፡ ነገር ፡ በቅ ዱስ ፡ ቂጵርያኖስ ፡ መጻሕፍት ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡

አንድነት ፡ በጻፈው ፡ መጽሐፉ ፡፡ በዚህም ፡ መጽሐፉ ፡ ቂጵ ርያኖስ ፡ የምትታይን ፡ የማታይንም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባንድ ፡ ደብልቆ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡፡ ክርስቶስ ፡ ለሐዋርያ ት ፡ መንፈስ ፡ ቅዱሱን ፡ ሰጠ ፡፡ ሐዋርያትም ፡ ኤጲስቆጶሳ ትን ፡ ሰጡት ፡ እጅ ፡ በመጫን ፡ ኤጲስቆጶስም ፡ ለሚከ ተለው ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አሳልፎ ፡ ይሰጠዋል ፡፡ ኤጲስቆጶስ ም ፡ ከተገኘባት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በቀር ፡ መንፈስ ፡ ቅዱ ስ ፡ አይገኝም ፡፡

በዚህም ፡ ካቅዱስ ፡ ቂጵርያኖስ ፡ ነገር ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በኤጲስቆጶስ ፡ እጅ ፡ ታሥሮ ፡ ይመስላል ፡፡ ደሮ ፡ እንዴት ፡ ይላል ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለራሱ ፡ በዮኤል ፡ በነቢይ ፡ በሐዋ ርያትም ፡ በጴጥሮስና ፡ በጳውሎስ ፡ አፍ ፡፡ እንዲህ ፡ ይላ ል ፡፡ የእግዚአብሔርን ፡ ስም ፡ የሚጸራ ፡ ሁሉ ፡ ይድናል ፡፡ ዮኤል ፡ ፫፤ ፭፡፡ የሐዋርያት ፡ ስራ ፡ ፪፤ ፳፩፡፡ ሮሜ ፡ ፲፤ ፲፫፡፡ በዚህም ፡ የቂጵርያኖስ ፡ ስሕተት ፡ ይገለጣል ፡፡ ኤጲስቆጶ ስ ፡ ሁሉ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ባይኖርበት ፡ ለራሱ ፡ ይጠፋ ል ፡፡ ወንጌልንም ፡ ቢሰብክ ፡ እግዚአብሔር ፡ በቃሉ ፡ መን ፈሱን ፡ መስጠት ፡ ይችላል ፡፡ በጎ ፡ ኤጲስቆጶስም ፡ በጸሎ ትና ፡ በሃይማኖት ፡ በሚያምን ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ እጁን ፡ ቢጫ ን ፡ ያ ፡ በሃይማኖቱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ይቀበላል ፡ በኤጲ ስቆጶስ ፡ እጅ ፡፡ እንዲህም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እንደ ፡ ሌላ ፡ ክ ርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ሥርዓት ፡ ታሠረ ፡ እግ ዚአብሔር ፡ ግን ፡ በኤጲስቆጶስ ፡ ፈቃድ ፡ አልታሠረም ፡፡

በዚያም ፡ አንድ ፡ ስሕተት ፡ ብቻ ፡ አልኖረም ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡፡ አንዲት ፡ የምትታይ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አ ንዱን ፡ ኤጲስቆጶስን ፡ ፈለገች ፡ ደግሞ ፡ ከቀሩት ፡ ኤ ጲስቆጶሳት ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ የሚሆን ፡፡ ምነው ፡ በሰማ ይ ፡ የሚኖር ፡ ያ ፡ ታላቅ ፡ የካህናት ፡ አለቃ ፡ እርሱ ፡ በደ ሙ ፡ ወደ ፡ መጋረጃ ፡ ውሥጥ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የገባ ፡ የዘላ ለምንም ፡ መድኃኒት ፡ ያደረገ ፡ በደሙ ፡ ለሁላችን ፡ እርሱ ም ፡ በማያኑ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መኻከለኛ ፡ አለቃም ፡ ራስም ፡ እርሱ ፡ ለብቻው ፡ የሆነ ፡ ተስፋም ፡ ያስደረገ ፡ ከ ውነተኛ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጋራ ፡ ደኖር ፡ ዘንድ ፡ እስከ ፡

ዓለም ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ። ምነው ፡ እርሱ ፡ ላባቶቻችን ፡ አልበቃም ።

ወደትስ ፡ ተገኘ ፡ ያ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ይኾም ፡ ዘንድ ፡ ጊዜ ፡ የነበረለት ። ምላሽ ። በሮም ። እንደዩ ፡ ብልዋልና ፡ ቂጵርያኖስ ። ጴጥሮስ ፡ በሐዋርያት ፡ መኻከል ፡ የበለጠ ፡ ነበረ ። የሱስም ፡ አለው ። አንተ ፡ ጴጥሮስ ፡ ነህ ፡ በዚህም ፡ ደንጊያ ፡ ላይ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኔን ፡ እሠራለሁ ፡ የገሃነምም ፡ ደጆች ፡ አይጸኑባትም ። እኛም ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ አስቀድመን ፡ ተናገርን ። ክርስቶስም ፡ ጴጥሮስን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ መሠረት ፡ እንደላደረገ ፡ አየነ ። ደሮ ፡ ቂጵርያኑስ ፡ እንደዩ ፡ አለ ። ክርስቶስ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ጴጥሮስን ፡ በቀረት ፡ ሐዋርያት ፡ ላይ ፡ ሾመ ። ይህም ፡ ስሕተት ፡ ሆነ ። እንደሁም ፡ ጨመረ ፡ ቂጵርያኑስ ፡ ከሌሎች ፡ ጋራ ፡ ሲል ። በሮም ፡ ያለች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የጴጥሮስ ፡ መቀመጫ ፡ ነበረች ። ጴጥሮስም ፡ የርስዋ ፡ መጀመርያ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ነበረ ። እርሱም ፡ እንደ ፡ በለጠ ፡ በሐዋርያት ፡ መኻከል ፡ ክርስቶስም ፡ በላያቸው ፡ እንደደረገው ፡ እንደሁም ፡ የጴጥሮስ ፡ ተከታዮች ፡ የሮም ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ የበልጣሉ ፡ ከቀረት ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ በላያቸውም ፡ ተሾሙ ።

የሮምም ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ይህነን ፡ ነገር ፡ አስበው ፡ እጅግ ፡ ትዕቢተኞች ፡ ሆኑ ። ክርስቶስ ፡ ግን ፡ አለ ። በመኻከላችሁ ፡ ታላቅ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ የሚወድ ፡ የሁላችሁ ፡ ባርያ ፡ የሁን ። ማለቱ ፡ እንደዩ ፡ ነው ። እርሱ ፡ በርሳችሁ ፡ መበላለጥ ፡ አትሹ ፡ በፍቅርና ፡ በትሕትና ፡ ተቀደደሙ ፡ እንጅ ።

የሮም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ቢክቶር ፡ የእስያን ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ሁሉን ፡ ገዘተ ፡ በልደት ፡ አመት ፡ ፻፺፰ ስለ ፡ ታናሽ ፡ ነገር ፡ ፋሲካውን ፡ አላደረጉምና ፡ ከሮም ፡ ጋራ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ። ተርቱልያኑስም ፡ ይላል ። የሮም ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ራሳቸውን ፡ የኤጲስቆጶሳት ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ያደርጋሉ ። እስጢፋኑስም ፡ የሮም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እንደ ፡ ቢክቶር ፡ አደረገ ። በታናሽ ፡ እስያና ፡ በግሪክ ፡ አፍሪቃ ፡ የነበ

ሬትን ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ስለ ፡ ታናሽ ፡ ነገር ፡ ገዘታቸው ፡፡

በዚያ ፡ ዘመን ፡ ግን ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ሁሉ ፡ ለሮም ፡ መንፈስ ፡ ገና ፡ አልተገዙም ፡፡ ኢሬኔዎስ ፡ የልዮን ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ቢክቶርን ፡ ገሠጸ ፡ ስለ ፡ አለመውደዱ ፡ ስለ ፡ ትዕቢቱም ፡፡ ቂጵርያኑስም ፡ ባለቤቱ ፡ ለእስጢፋኖስ ፡ ለሮም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በሲኖዶሱ ፡ ስም ፡ ጻፈ ፡ ወንድም ፡ ለወንድሙ ፡ እንደ ፡ ጽፈ ፡ እስጢፋኖስንም ፡ በፍቅርና ፡ በኃይል ፡ ገሠጸው ፡፡ እንደዚሁም ፡ ፊርሚልያኖስ ፡ የቄሣርያ ፡ በቀጳዶቂያ ፡ ያለች ፡ ኤጲስቆጶስ ፡፡

፪፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተግሣጽ ፡፡

ከመጀመርያ ፡ ጀምሮ ፡ ወደምትታይ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በጎችና ፡ ክፎች ፡ ሰዎች ፡ ገቡ ፡ አስቀድመን ፡ እንደልነ ፡፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ጠባቆች ፡ አልቻላቸውም ፡ የሰውን ፡ ልብ ፡ ይመረምሩ ፡ ዘንድ ፡ ክፎችንም ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከመግባት ፡ ይከለክልዋቸው ፡ ዘንድ ፡፡ ሐዋርያትም ፡ ይህነን ፡ ካልቻላቸው ፡ እርሳቸውም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የመላባቸው ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ይልቅ ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡ ለሌሎች ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሌላቸው ፡ እንደ ፡ ሮም ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ቢክቶርና ፡ እስጢፋኖስ ፡፡ እሌህ ፡ እውነትኞችን ፡ ክርስቲያን ፡ ያወጡ ፡ ዘንድ ፡ ፈለጉ ፡ ስለ ፡ ታናሽ ፡ ክርክር ፡፡ እርሳቸው ፡ ግን ፡ ለራሳቸው ፡ ሳይወጡ ፡ ተቀመጡ ፡፡ ደሮ ፡ ይህ ፡ ክፋት ፡ ሥርዓት ፡ አልሆነም ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡፡ ሥርዓታቸውም ፡ እንደህ ፡ ነበረ ፡፡ በጥምቀት ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የገባ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ተስፋና ፡ ስለት ፡ ሊያደርግ ፡ ነበረ ፡ በግልጽ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ፊት ፡፡ የሰይጣንን ፡ መንግሥት ፡ ከሰይጣን ፡ ስራ ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ፡ ሊክድ ፡ እግዚአብሔርም ፡ በሚወደው ፡ ሕይወትና ፡ አካሔድ ፡ ሊኖር ፡፡ ይህነንም ፡ ስለት ፡ ያፈረሰ ፡ በታላቅ ፡ ኃጢአትም ፡ የኖረ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁኖ ፡ አልተቈጠረምና ፡ ገዘተው ፡ ከጉባኤያቸው ፡ አወጡት ፡ ንስሐ ፡ እስ

ኪገባ ፡ ድረስ ፡ በንስሐም ፡ እስኪመለስ ፡ ድረስ ፡፡ ሥርዓ
ትም ፡ አደረጉ ፡ ለንስሓ ፡፡ በተገዘቱ ፡ ጊዜ ፡ ቀን ፡ ተሰሬላ
ቸው ፡ ስንት ፡ ወሬት ፡ ሊቀመጡ ፡ የሆኑ ፡ መመለስ ፡ ቢወ
ዱ ፡፡ በልብሳቸውም ፡ በጾማቸውም ፡ ንስሓቸው ፡ ሊገለጽ ፡
ነበር ፡፡ እንደ ፡ ካቴኵሜኖችም ፡ ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ሊማሩ ፡
ሊፈተኑም ፡ ነበሩ ፡፡ ከተፈተኑም ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ ተ
ቍረጠላቸው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚገቡበት ፡ በግ
ልጽም ፡ ኀጢአታቸውን ፡ አስታወቁ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር
ም ፡ ጸለዩ ፡ ስለ ፡ ሰርየታቸው ፡ የጉባኤንም ፡ የቀሳውስት
ንም ፡ ልመና ፡ ፈለጉ ፡፡ ንስሓቸውም ፡ በጎ ፡ ሁኖ ፡ ከተ
ቀበለ ፡ ኤጲስቆጶስና ፡ ቀሳውስት ፡ እጃቸውን ፡ ጫኑባቸ
ው ፡ የወንጌልንም ፡ ተስፋ ፡ ነገርዋቸው ፡ እንደሁም ፡ እን
ደ ፡ ተፈቱ ፡ ተቀበልዋቸው ፡ በምእምናን ፡ ጉባኤ ፡፡ ከዚህ
ም ፡ ጋራ ፡ ትምህርት ፡ አልቀረም ፡፡ ደግ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በነ
ፍሳቸው ፡ ተጕደበት ፡ ወደምትታይ ፡ ጉባኤ ፡ ወደ ፡ ቄስ
ም ፡ ወደ ፡ ኤጲስቆጶስም ፡ ሲመለሱ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔ
ር ፡ ግን ፡ አልተመለሱም ፡፡ ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ በሥጋ ፡ ብቻ ፡
ንስሓ ፡ አደረጉ ፡ ሲጾሙ ፡ ባፊቸውም ፡ በልብሳቸውም ፡ ሲ
ያዝኑ ፡ በልባቸው ፡ ግን ፡ በኀጢአት ፡ ኖሩ ፡ ጸኑም ፡፡ ለጴጥ
ሮስም ፡ ለቀሩትም ፡ ሐዋርያት ፡ ስለ ፡ ተሰጠ ፡ ስለ ፡ መንግሥ
ት ፡ ሰማያት ፡ መክፈቻ ፡ አስቀድመን ፡ ተናገርን ፡፡ ወደ ፡ መን
ግሥተ ፡ ሰማያትም ፡ ከመግባት ፡ ከመመለስም ፡ ማንም ፡
አልተከለከለም ፡፡ እርሱ ፡ ለብቻው ፡ በውነት ፡ መከልከል
ና ፡ መቀበል ፡ የሚችል ፡ ሰውንም ፡ ሁሉን ፡ ወደርሱ ፡ ይመጣ ፡
ዘንድ ፡ የጸራው ፡ ያዘዘውም ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ያለም ፡
መድኀኒትና ፡ ፈራጅ ፡ ሁለግዜ ፡ ይገኛልና ፡ ለሰውም ፡ ሁ
ሉ ፡ እርሱ ፡ ይቀርባል ፡ ከኤጲስቆጶስ ፡ ከቄስም ፡ ከጉባኤ
ም ፡ ይልቅ ፡፡

በዚያ ፡ ዘመንም ፡ ክርክር ፡ ሆነ ፡ ሰርየት ፡ ስለሚገኝ
በት ፡ ኀጢአት ፡ ለሞትም ፡ ስለማያድርስ ፡ ሰርየት
ም ፡ ሰለማይገኝበት ፡ ለሞትም ፡ ስለሚያድርስ ፡ ኀ
ጢአት ፡፡ ሰርየት ፡ የማይገኝለት ፡ ኀጢአት ፡ ይህ ፡ ተቈጠ
ረ ፡፡ የሃይማኖት ፡ ክደት ፡ ሸንግልናም ፡ መስረቅም ፡ ዝሙ

ትም ፡ ምንዝንም ፡ ደህነንም ፡ የሚመስል ፡፡ አሁንም ፡ አ
ያሌ ፡ ነበሩ ፡ የሚሉ ፡፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ደገባል ፡ ለኃ
ጢአተኛ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ተስፋ ፡ ታስደርግ ፡ ዘንድ ፡ ንስሓ ፡
ቢገባ ፡ ቢመለስም ፡ ኃጢአቱ ፡ ሁሉ ፡ እንዲቀር ፡፡ ሌሎች ፡
ግን ፡ አሉ ፡፡ ወደ ፡ ሞት ፡ የሚያደርሰውን ፡ ኃጢአት ፡ ያ
ደረገው ፡ ኃጥእ ፡ ሁሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ፍርድ ፡ ደቀር ፡
ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አይገባምና ፡ የምህረት ፡ ተስፋ ፡ ታ
ስደርግለት ፡ ዘንድ ፡፡

፫፤ ስለ ፡ መለየት ፡፡

በዚህ ፡ ዘመን ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ፪፤ መለየት ፡ ነበሩ ፡
አንዲት ፡ የፌሊኪሲሙስ ፡ በክርታጎ ፡ በሮማዊት ፡ አፍሪ
ቃ ፡ አንዲትም ፡ የኖዋትያኑስ ፡ መለየት ፡ በሮም ፡፡

የፌሊኪሲሙስም ፡ መለየት ፡ እንዲህ ፡ ነበረች ፡፡ ቂ
ጵርያኑስ ፡ በክርታጎ ፡ ቄስ ፡ ሲሆን ፡ ከክርታጎ ፡ ኀባኤ ፡ ከቀ
ሳውስትም ፡ ተመረጸ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ደሆን ፡ ዘንድ ፡ በዚያ
ች ፡ ከተማ ፡፡ ለቂጵርያኑስም ፡ ጸላቶች ፡ ነበሩ ፡ የተቀኑት ፡
እርሱ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡፡ ከጸላቶቹም ፡ ፫፤ ቀሳው
ስት ፡ ነበሩ ፡ ከወደጆቻቸው ፡ ጋራ ፡ ቂጵርያኑስን ፡ እጅግ ፡
የተጻሉ ፡ ሊሾሩትም ፡ የፈለጉ ፡፡ ከርሳቸውም ፡ አንድ ፡ ኖ
ዊቱስ ፡ የተባለ ፡ ነበረ ፡ እጅግ ፡ ቅናተኛ ፡ ቄስ ፡ ለክርታጎ ፡ በ
ምትቀርብ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከቂጵርያኑስ ፡ በታች ፡ የነበ
ረ ፡፡ ያም ፡ ኖዋቱስ ፡ አንደን ፡ ፌሊኪሲሙስ ፡ የሚሉትን ፡
ለዲያቆን ፡ ቀደሰው ፡ ብርቱን ፡ ሰውን ፡ የቂጵርያኑስ ፡ ጸላ
ት ፡፡ ቂጵርያኑስም ፡ በዚህ ፡ ማድረጉ ፡ ኖዋቱስን ፡ አጣለ ፡
ፌሊኪሲሙስን ፡ ግን ፡ አልሻረም ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ የዴ
ኪዩስ ፡ ማሳደድ ፡ ጀመረ ፡ በፊት ፡ እንደልነ ፡፡ ቂጵርያኑስ
ም ፡ ለጊዜ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ተሸሸጎ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያ
ኑን ፡ በስውር ፡ ጠበቀ ፡፡ ጸላቶቹም ፡ አሰትን ፡ ተናግረው ፡
በፍርሃት ፡ መክንያት ፡ አጣሉት ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ብዙ ፡
ሰዎች ፡ በጉባኤው ፡ መጡ ፡ በመሳደድ ፡ መጀመርያ ፡ የካ
ዱ ፡ ለጣዖትም ፡ የሠው ፡ ወይስ ፡ እንደ ፡ ሠው ፡ ሊመሰከ

ሩ ፡ ወረቀትን ፡ የተቀበሉ ፡ ከሹማቸው ፡፡ አርሳቸውም ፡ አዝነው ፡ ተመለሱ ፡ ፍትሐትንም ፡ ከቂጵርያኑስ ፡ ፈለጉ ፡፡ ቂጵርያኑስ ፡ ግን ፡ የወንጌልን ፡ ተስፋ ፡ ይናገራቸው ፡ ዘንድ ፡ አልተቻኮለም ፡፡ ይጸኑ ፡ ዘንድ ፡ እንጂ ፡ ንስሓቸውንም ፡ እውነት ፡ ሁኖ ፡ ይገልጹ ፡ ዘንድ ፡ መከራቸው ፡ ያ ፡ መከራ ፡ እስኪጨርስ ፡ ድረስ ፡ እርሱም ፡ ከኤጲስቆጶሳቱና ፡ ከቀሳውስቱ ፡ ከጉባኤውም ፡ ጋራ ፡ ነገራቸውን ፡ እስኪመረምር ፡ ድረስ ፡፡ እስከዚያ ፡ ድረስም ፡ ከቍርባን ፡ ከለከላቸው ፡፡ እለዚያ ፡ ሰዎችም ፡ በጸላቶቹ ፡ ጸኑ ፡ በቂጵርያኑስ ፡ ላይ ፡፡ አያሌም ፡ ሰማዕቶች ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ለሞት ፡ ይቀርቡ ፡ የነበሩ ፡ መከራም ፡ የተቀበሉ ፡ ቅዱሳንም ፡ ሁነው ፡ የተቈጠሩ ፡ ይህችን ፡ ጾላትነት ፡ በቂጵርያን ፡ ላይ ፡ አበዙ ፡፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ክርስቶስን ፡ ካስታወቁ ፡ በኋላ ፡ ለሰይጣን ፡ አገለገሉ ፡ ባለመውደድ ፡ በትዕቢትም ፡ ጥልንም ፡ በማብዛት ፡፡ የደኪዩስም ፡ ማሳደድ ፡ ሳይጨርስ ፡ ቂጵርያኑስ ፡ አያሌን ፡ ኤጲስቆጶሳትና ፡ ቀሳውስት ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰደደ ፡ የድኆችን ፡ መሻት ፡ ይመረምሩ ፡ ዘንድ ፡ በመሻታቸውም ፡ መጠን ፡ ይሰጥዋቸው ፡ ዘንድ ፡፡ እሌህም ፡ ወደ ፡ ጉባኤ ፡ ሲደርሱ ፡ ፊሊኪሲሙስ ፡ እጅግ ፡ ጥል ፡ አደረገባቸው ፡ ሰዎችንም ፡ በቂጵርያኑስ ፡ ላይ ፡ ያመፁ ፡ ዘንድ ፡ አወካቸው ፡፡ ስለዚህም ፡ ቂጵርያኑስ ፡ ባመት ፡ ፪፻፶፩፤ ወደ ፡ ከርታጎ ፡ ከተመለሰ ፡ በኋላ ፡ የዚያን ፡ ምድር ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ሁሉ ፡ ሰበሰበ ፡ ለሲኖደስ ፡፡ በዚህችም ፡ ሲኖደስ ፡ የካዱትን ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ መቀበል ፡ ተማከሩ ፡ የፈሊኪሲመስንም ፡ ወገን ፡ ገዘቱ ፡፡ ጥቂት ፡ ወራትም ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ይህች ፡ መለየት ፡ ጠፋች ፡፡

ሁለተኛ ፡ መለየትም ፡ የኖዋትያኑስ ፡ መለየት ፡ በሮም ፡ ነበረች ፡፡ ኖዋትያኑስም ፡ አረማዊ ፡ ሁኖ ፡ በታመመ ፡ ጊዜ ፡ በሃይማኖት ፡ ደነ ፡ ከሕማሙ ፡፡ የሮምም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ፈቢያኑስ ፡ አጠመቀው ፡ በኋላም ፡ ቀደሰው ፡ ቄስ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡፡ ለጊዜም ፡ ከክህነቱ ፡ ዐረፈ ፡ በብሕትና ፡ የትምህርትንም ፡ መጽሐፍ ፡ ጻፈ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ በስም ፡ ብቻ ፡ ክርስቲያን ፡ የነበሩ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አ

ኀደ ፡ በዙ ፡ ብሕትናውን ፡ ትቶ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰበከ ፡ ጉባኤንም ፡ የረከሱትን ፡ ብልቶችዋ ፡ ከመካከልዋ ፡ ታው ጣቸው ፡ ዘንድ ፡ በመከራም ፡ ጊዜ ፡ የካዱትን ፡ እንደትቀ በላቸው ፡ መከራት ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ፋቢያኑስ ፡ የሮ ም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ሞተ ፡፡ ያም ፡ ኖዋቱስ ፡ የከርታጎ ፡ ቄስ ፡ የቂጵርያኑስ ፡ ጸላት ፡ መጥቶ ፡ ከኖዋትያኑስ ፡ ጋራ ፡ አንድ ነት ፡ አደረገ ፡፡ ኖዋትያኑስንም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ይሆን ፡ ዘን ድ ፡ እሺ ፡ አሰኘው ፡፡ ሌሎች ፡ ቀሳውስት ፡ ግን ፡ ከኤጲስ ቆጶሳትና ፡ ከጉባኤ ፡ ጋራ ፡ ቆርኔልዮስን ፡ መረጹ ፡ ለኤጲስ ቆጶሳቸው ፡ እለዚያም ፡ ፪ ፡ ባንድ ፡ ተጻሉ ፡፡ ሁለታቸውም ፡ ወደ ፡ ሌሎች ፡ ጉባኤዎች ፡ ሰደዱ ፡ ወደ ፡ ከርታጎ ፡ ወደ ፡ እ ስክንድርያም ፡ ወደ ፡ እንጾኪያም ፡ የሌሎችንም ፡ ምክር ፡ ይሰሙ ፡ ዘንድ ፡፡ የከርታጎ ፡ ኤጲስቆጶስም ፡ ቂጵርያኑስ ፡ ብርቱ ፡ ነገር ፡ ጻፈ ፡ በኖዋትያኑስ ፡ ላይ ፡፡ ዲዮናስዮስ ፡ ግን ፡ የስክንድርያ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ባይነተኛ ፡ ፍቅር ፡ ኖዋትያኑስ ን ፡ መከረ ፡ ደሮ ፡ እርሱ ፡ አልሰማም ፡፡ በዚህ ፡ ክርክር ፡ ግ ን ፡ የሁላቸው ፡ ስሕተት ፡ ይገለጻል ፡፡ ሁላቸው ፡ የጳውሎ ስን ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ጽድቅ ፡ አላስተዋሉም ፡ የክ ርስቶስንም ፡ ነገር ፡ ስለምትታይ ፡ ስለማትታይም ፡ ቤተ ፡ ክ ርስቲያኑ ፡፡ ኖዋትያኑስም ፡ አለ ፡፡ ለሞት ፡ የሚያደርሰው ን ፡ ኀጢአት ፡ ላደረገው ፡ ሰው ፡ የሰርዮትን ፡ ተስፋ ፡ ያስደ ርጉለት ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ይቀበሉት ፡ ዘንድ ፡ አይገባም ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ያውቃልና ፡ ኀጢ አታቸው ፡ ያስቀርላቸው ፡ እንደሆን ፡ ወይስ ፡ አይደለም ፡፡ ጸላቶቹ ፡ ግን ፡ ከአርቶደክሳውያን ፡ አሉ ፡፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክር ስቲያን ፡ ከመግባት ፡ ሰውን ፡ ብትከለክለው ፡ ከዘላለም ፡ ደህንነት ፡ ትከለክለዋለህ ፡፡ ኖዋትያኑስም ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ክ ርስቲያን ፡ ተናግሮ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡፡ እውነተኛ ፡ ቤተ ፡ ክርስ ቲያን ፡ ንጽሕትና ፡ ቅድስት ፡ ናት ፡፡ ብልቶችዋም ፡ ንጹሓን ና ፡ ቅዱሳን ፡ ናቸው ፡፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ሁሉ ፡ ኀጢአተ ኞችን ፡ ከመካከልዋ ፡ ባታውጣ ፡ ባለቤትዋ ፡ ርክስት ፡ ት ሆናለች ፡፡ ስለዚህም ፡ የኖዋትያኑስ ፡ ወገን ፡ ካታሮች ፡ ማ ለት ፡ ንጹሓን ፡ ተባሉ ፡፡ አርቶደክሳውያን ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡

አሉ ፡፡ እንክርደድና ፡ ስንዴ ፡ በዚህ ፡ ሕይወት ፡ ባንድ ፡ ናቸ ው ፡ ክርስቶስም ፡ በፍርድ ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡ ይለያቸዋል ፡፡ ደር ፡ ጳውሎስ ፡ የውነተኞች ፡ ክርስቲያንን ፡ ጉባኤ ፡ ንጽሕትና ፡ ቅድስት ፡ በክርስቶስ ፡ ይላታል ፡ በመንፈስ ፡ መጋደል ፡ ሳይ ቀር ፡ ከኃጢአት ፡ ጋራ ፡ እስከ ፡ ሞት ፡ ድረስ ፡፡ በስምም ፡ ብቻ ፡ ክርስቲያን ፡ ያሉ ፡ እንክርደድም ፡ ክርስቶስ ፡ በወን ጌል ፡ ይጸራቸዋል ፡ በሃይማኖት ፡ ወደ ፡ መንግሥቱ ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፡፡ ክርስቶስ ፡ ይላልና ፡፡ ብዙ ፡ ተጸሩ ፡፡ ጥቂት ፡ ግን ፡ ተመረጹ ፡፡ የተጸሩም ፡ የምትታይ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ናቸ ው ፡፡ የተመረጹ ፡ ግን ፡ የማትታየ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ና ቸው ፡፡

ሁላቸውም ፡ ኢየመንገደቸው ፡ ሲስቱ ፡ አርቶደክሳውያ ን ፡ በሲኖደስ ፡ በሮም ፡ ሲሰበሰቡ ፡ ባመት ፡ ፩፻፩፡ የኖዋትያ ኑስን ፡ ወገን ፡ ገዘቱ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ወገን ፡ በዚህ ፡ አል ጠፋም ፡ ለብቻቸው ፡ ግን ፡ ኖሩ ፡፡ ኤጲስቆጶሳትም ፡ ነበሩላ ቸው ፡ ለስድስት ፡ መቶ ፡ አመት ፡ ከክርስቶስ ፡ በኋላ ፡ እ ስኪቀርቡ ፡ ድረስ ፡፡

ሶስተኛ ፡ ምዕራፍ ፡፡

የክርስቲያን ፡ ሕይወትና ፡ አካሔድ ፡ የክርስቲያንም ፡ ማምለክ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡፡

፩፡ ስለ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕይወትና ፡ አካሔድ ፡፡

በዚህ ፡ ዘመን ፡ ሃይማኖትን ፡ የተቀበሉ ፡ በርሱ ፡ ተለወጡ ፡ አዲሶችም ፡ ሰዎች ፡ ሆኑበት ፡፡ ይህም ፡ እጅግ ፡ ተገለጸ ፡፡ አስቀድመው ፡ ጣዖታትን ፡ ባመለኩ ፡ ጊዜ ፡ በርኩስት ፡ ሁሉ ፡ ይኖሩ ፡ ነበሩ ፡፡ በክርስቶስ ፡ ግን ፡ ካመኑ ፡ በኋላ ፡ ከኃጢአት ፡ ማገልገል ፡ ከሰይጣንም ፡ መንግሥት ፡ ተሰናበቱ ፡፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትም ፡ ባረማውያን ፡ መኻከል ፡ ብርሃናትን ፡ መሰሉ ፡ በጨለማ ፡ መኻከል ፡ የሚያበሩ ፡፡ በዚያ ፡ ዘመንም ፡ ለግብዝነት ፡ እጅግ ፡ መክንያት ፡ አልነበረም ፡ በሌላ ፡ ዘመን ፡ እንደ ፡ ተገኘ ፡፡ የብዙም ፡ ልብ ፡ በታላቅ ፡ መከራ ፡ ተፈተነ ፡፡ ደግሞ ፡ የሁሉ ፡ ልብ ፡ አልተፈተነም ፡ ግብዝነትም ፡ ሁሉ ፡ አልተከለከለም ፡፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሃይማኖትን ፡ የተቀበሉ ፡ የቀደመውን ፡ ተግባራቸውን ፡ ሊተው ፡ ነበሩ ፡፡ በተግባራቸው ፡ ግን ፡ ምግባቸውም ፡ ቀረ ፡፡ የክርስቲያንም ፡ ጉባኤ ፡ መኻታቸውን ፡ ጠብቃ ፡ እንደ ፡ ችሎትዋ ፡ መገበቻቸው ፡፡ ይህም ፡ ለብዙ ፡ ተግባራቸውን ፡ ላልወደዱ ፡ ሰዎች ፡ መክንያት ፡ ሆነ ፡ ክርስቲያን ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡፡ በክርስቲያንና ፡ በረማውያን ፡ መኻከልም ፡ ታላቅ ፡ መለየት ፡ ሁንዋልና ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አሰቡ ፡ ካረማውያን ፡ መኻከል ፡ ከወጡ ፡ በኋላ ፡ ካለምም ፡ ከኃጢአትም ፡ እንደ ፡ ወጡ ፡ በልባቸውም ፡ የነበረውን ፡ ዓለም ፡ አልጠበቁም ፡ ከኃጢአትም ፡ ጋራ ፡ አልተጋደሉም ፡ ያሸነፉ ፡ ይመስላቸው ፡ ነበረና ፡፡ ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ ልባቸው ፡ ሳይለወጥ ፡ ተጠመቁ ፡ ኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ በጥምቀት ፡ ውኃ ፡ የጠፋባቸው ፡ መሰላቸው ፡ እንጂ ፡፡ ከጥምቀትም ፡ ወዲያ ፡ ኃጢአት ፡ ሁ

ሉ ፡ አይጉደኑም ፡ አሉ ፡፡ ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ ሃይማኖትን ፡ ወ ደዱ ፡ ደግ ፡ ከጥምቀት ፡ ፈሩ ፡ ወደ ፡ ሞትም ፡ ሳይቀርቡ ፡ አልተጠመቁም ፡ የወደዱትን ፡ ኀጢአት ፡ ከጥምቀት ፡ ወ ዲያ ፡ በግድ ፡ ሊተውት ፡ እንደ ይሆኑ ፡ ፈርተዋልና ፡፡ ደህና ች ፡ መመህራንም ፡ እጅግ ፡ ጠበቁ ፡ ከዚህ ፡ ስሕተት ፡፡ በስ ብከታቸውም ፡ በጽፈታቸውም ፡ ሰዎችን ፡ መከሩ ፡ የሃይ ማኖትን ፡ ነገርና ፡ ትምርት ፡ ብቻ ፡ እንዳይዙ ፡ የሃይማኖትን ም ፡ ኃይልና ፡ ሕይወቱን ፡ እንጂ ፡፡ ደግ ፡ ባለቤታቸው ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ሳቱ ፡ የምትታይንና ፡ የማትታይን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሳይለዩ ፡፡ የክርስቲያን ፡ ዕውቀት ፡ የክርስቲያንም ፡ ኃይ ል ፡ ከዘመን ፡ ለዘመን ፡ ሊበዛ ፡ ነበረ ፡ እንደ ፡ ቀን ፡ ብርሃ ን ፡ ጨለማውንም ፡ ሁሉን ፡ ሊያሸንፍ ፡ ነበር ፡፡ አይነተኛ ፡ ሃይማኖትም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ከጅግ ፡ ድካም ፡ ጋራ ፡ ተገኘ ፡ ክ ፉ ፡ ልማድም ፡ በጥቂት ፡ በጥቂት ፡ ብቻ ፡ ተሸነፈ ፡፡

የክርስቲያን ፡ አንድነትም ፡ እጅግ ፡ ጽኑ ፡ ሁኖ ፡ ተመ ሰከረ ፡ በፍቅራቸው ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡፡ ላረማውያን ፡ አዲስ ፡ ነገር ፡ ነበረ ፡ ክርስቲያን ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡ እን ደ ፡ ዘመዶች ፡ እንደ ፡ ወንድሞችና ፡ እቶች ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡፡ ለዚህችም ፡ አንድነት ፡ ምልክት ፡ ሆነ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ ከተጠመቀ ፡ በኋላ ፡ በሳም ፡ እንደ ፡ ተገናኘ ፡ ከክርስቲያን ፡ ጋራ ፡፡ የወንድሞችም ፡ ፍቅር ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ እጅግ ፡ ተቃጠለ ፡፡ በየጉባኤ ፡ ሁሉ ፡ ክርስቲያናት ፡ እንደ ፡ ችሎታ ቸው ፡ ወርቅና ፡ ብር ፡ ሰበሰቡ ፡ ለድኆቻቸው ፡ ለንግደች ም ፡ ለሽማግሎችም ፡ ለባልቴቶችም ፡ ለድውያንም ፡ በ ወንጌልም ፡ መክንያት ፡ ለታሠሩ ፡፡ ለጸሎትና ፡ ለምስጋና ም ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ቃል ፡ ለመስማት ፡ ወደ ፡ ጉባኤ ፡ የመጣ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ችሎቱ ፡ የፍቅርን ፡ መስጠት ፡ ሰጠ ፡ በየእሑድ ፡፡ ይህም ፡ ከሌላ ፡ ይልቅ ፡ የቤቶች ፡ ተግባር ፡ ነበረ ፡ ለሚሾትን ፡ ክርስቲያናት ፡ በሥጋ ፡ መሻታቸው ፡ ሁ ሉ ፡ በፍቅርና ፡ በትሕትና ፡ ያገለግሉ ፡ ዘንድ ፡፡ እርሳቸው ም ፡ በግልጽ ፡ አያስተምሩም ፡ ነበሩ ፡፡ ደግ ፡ በስውር ፡ ያደ ረጉት ፡ የፍቅር ፡ ማገልገላቸው ፡ ያለ ፡ ድምጽ ፡ አስተማረ ፡ በሰውም ፡ መካከል ፡ እንደ ፡ መብራት ፡ አበራ ፡፡ ስለ ፡ እ

ንግዶችም ፡ መሸት ፡ ለቀሙ ፡፡ የመቄዶንያ ፡ ያካያም ፡ አብ ያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ አስቀድሞ ፡ እንደ ፡ ለቀሙ ፡ ለየሩሳ ሌም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንዲሁም ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡፡ የ ለዚያም ፡ ጉደይ ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ሌሎች ፡ አ ብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ጾሙ ፡ በጾምም ፡ ያልበሉትን ፡ የ ምግባቸውን ፡ ፈንታ ፡ ለድኆች ፡ ወንድሞቻቸው ፡ ሰጡ ት ፡፡ እንደህም ፡ አደረጉ ፡ በከርታጎ ፡ ብዙ ፡ ክርስቲያን ፡ በ ኑሚድያ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ በታሠሩ ፡ ጊዜ ፡፡ የከርታጎ ፡ ወ ንድሞቻቸው ፡ ለርሳቸው ፡ የፍቅራቸውን ፡ መስጠት ፡ ለቀ ሙ ፡ ከጾምም ፡ ከጉዳያቸውም ፡ ከትርፋቸውም ፡ ባገኙ ት ፡ ወርቃቸው ፡ የታሠሩትን ፡ ወንድሞች ፡ አስፈትዋቸ ው ፡፡ ቸነፈርም ፡ ወይስ ፡ ሌላ ፡ ብርቱ ፡ ሕማምና ፡ ሞት ፡ ላ ገር ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ አረማውያን ፡ እጅግ ፡ ፈሩ ፡ ክርስቲያ ን ፡ ግን ፡ ድውያንን ፡ ጠበቁ ፡ የርሳቸውንም ፡ ድውያን ፡ ብ ቻ ፡ አይደለም ፡ ያረማውያንንም ፡ እንጂ ፡፡ ሙታንንም ፡ ቀ በሩ ፡ አረማውያን ፡ እንደ ያው ፡ ባደባባዮች ፡ ላሬዊት ፡ የተውዋቸው ፡፡ ብዙ ፡ ክርስቲያንም ፡ ሞቱ ፡ ድውያንንና ፡ ሙታንን ፡ ካገለገለ ፡ በኋላ ፡ ጥዋፍንም ፡ መሰሉ ፡ ለሌላ ፡ የሚያበሪ ፡ ለራሱ ፡ ግን ፡ የሚፈጅ ፡፡

የክርስቶስም ፡ ባሮች ፡ በርሱ ፡ ከሰይጣን ፡ ባርነት ፡ ወጥ ተው ፡ የመንፈስን ፡ አርነት ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ልጅነ ት ፡ ያገኙ ፡ እርሳቸው ፡ በመንፈሱ ፡ ተማሩ ፡ ከእግዚአብ ሔር ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ለተሰራ ፡ ለሰው ፡ ሥርዓት ፡ ሁ ሉ ፡ ደገዙ ፡ ዘንድ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ታዘው ፡ ለሰውም ፡ አይ ደለም ፡፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ለሚወጣ ፡ ግን ፡ እም ቢ ፡ ይሉ ፡ ዘንድ ፡፡ በዚህ ፡ መጠንም ፡ ክፉ ፡ ጫወታ ፡ ጠፋ ፡ የኃጢአት ፡ ተግባርም ፡ የሰውን ፡ ነፍስ ፡ የሚጐደው ፡ ተ ው ፡፡ በብዙ ፡ ነገርም ፡ ተጠራጠሩ ፡ ከኃጢአትና ፡ ከበጎ ፡ ነ ገር ፡ በመካከል ፡ ሁኖ ፡ የመሰላቸው ፡ ለክርስቲያን ፡ ቢገ ባ ፡ ወይስ ፡ አይገባም ፡ ብለው ፡፡ ያገርን ፡ ሹመት ፡ ይቀበ ሉ ፡ ዘንድ ፡ ወይስ ፡ ጾርን ፡ ያድርጉ ፡ ዘንድ ፡ ወይስ ፡ እጅ ግ ፡ ከብት ፡ ወይስ ፡ ያለም ፡ ክብር ፡ ይሆንላቸው ፡ ዘንድ ፡ እንዲገባቸው ፡ ወይስ ፡ አይደለም ፡ ተጠራጠሩ ፡፡

የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ያለምን ፡ ፍትወትና ፡ መርዓት ፡ ጸልትዋልና ፡ በመብላትና ፡ በመጠጥ ፡ በመቀበልና ፡ በመስጠትም ፡ በድካምና ፡ በረፍትም ፡ በመንገርና ፡ ዝም ፡ በማለትም ፡ በኀዘንና ፡ በደስታም ፡ በሕይወትና ፡ በሞትም ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያከብሩ ፡ ዘንድ ፡ በዚህ ፡ ተጋደሉ ፡፡ ከሰውም ፡ መኻከል ፡ አልሸሹም ፡ ባለም ፡ ኖሩ ፡ እንጅ ፡ በዚች ፡ ክፋኢትና ፡ ጠማማች ፡ ትውልድ ፡ ያበሩ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ መብራቶች ፡ ባለም ፡፡ ለጊዜ ፡ ብቻ ፡ ተሰወሩ ፡ ልባቸውን ፡ ይሰበስቡ ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ በጸሎትና ፡ በጾም ፡ ልባቸውንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ያሰናዱ ፡ ዘንድ ፡፡

ነገር ፡ ግን ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ የሃይማኖትን ፡ ጽድቅ ፡ መልካም ፡ አላስተዋሉምና ፡ ድንግልናውን ፡ እጅግ ፡ አከበሩ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ደስ ፡ እንደ ፡ ያሰኘው ፡ ከመጋባት ፡ ይልቅ ፡ ብለዋልና ፡፡ በዚህና ፡ በሌላ ፡ ነገር ፡ ሰይጣን ፡ ገባ ፡ በመልአክ ፡ መልክ ፡፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ የጽድቅን ፡ ትርፍ ፡ ያውጡ ፡ ዘንድ ፡ ብለዋል ፡ ያልታዘዙትንም ፡ ነገር ፡ ቢያድርጉ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ወጡ ፡፡ ይህም ፡ ከሌላ ፡ ስንፍና ፡ ሁሉ ፡ ይበልጣል ፡፡ ስለዚህም ፡ ክርስቶስ ፡ ይላል ፡፡ እንደ ፡ ሕፃናት ፡ ባትሆኑ ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ አትገቡም ፡፡

አንደንድ ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ የርኵት ፡ መንፈስ ፡ ተገለጸ ፡ የሰውን ፡ ቀምበር ፡ በመንፈሳቸው ፡ ይሸከሙ ፡ ዘንድ ፡ እምቢ ፡ ያለ ፡፡ የሞንታኑስ ፡ ወገን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ባዘዙ ፡ ጊዜ ፡ የጾም ፡ ሥርዓትን ፡ ያድርጉ ፡ ዘንድ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ እምቢ ፡ አሉ ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡፡ እንዲህ ፡ በሚሆን ፡ በጾምና ፡ በሌላ ፡ ነገር ፡ ለክርስቲያን ፡ ባዲስ ፡ ሥርዓት ፡ ትእዛዝ ፡ አይገባም ፡፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንዲያድርገው ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ እንዲያስተምረው ፡ ያድርግ ፡ እንጅ ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ጾምን ፡ አላዘዘም ፡ ካንድ ፡ ጾም ፡ በቀር ፡ እርሱም ፡ ይህ ፡ ነው ፡፡ ኃጢአትን ፡ አንተው ፡ ዘንድ ፡፡

እንዲሁም ፡ መምህራን ፡ በጣም ፡ አላለቀም ፡ የክርስ

ቲያንን ፡ መጋባት ፡ ያመሰገኑት ፡፡ የስክንድርያ ፡ ክሌ
ሜንተስ ፡ ይላልና ፡ ድንግልናውን ፡ አክብረው ፡ መጋባ
ት ፡ የሚንቁትን ፡ ሰዎች ፡፡ በውነት ፡ ክርስቲያን ፡ ለሚሆ
ን ፡ ሰው ፡ ሐዋርያት ፡ ምሳሎቹ ፡ ናቸው ፡፡ ሰውም ፡ በውነት ፡
ብርቱ ፡ ሰው ፡ ሁኖ ፡ አይገለጽም ፡ በብሕትንት ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡
ያ ፡ ከሌሎች ፡ ሰዎች ፡ ላይ ፡ ያሸንፈል ፡ ባለ ፡ መሸት ፡ ሁኖ ፡ አ
ባትም ፡ ሁኖ ፡ በመፈተን ፡ ሁሉ ፡ ምሽቱንና ፡ ልጀቹን ፡ ቤተ፡
ሰቦቹንም ፡ ከብቱንም ፡ ከመጠበቅ ፡ የሚደርስለት ፡ እግዚ
አብሔርን ፡ ከመውደድ ፡ ሳይርቅ ፡ የሚጸና ፡፡ ያላገባ ፡ ግን ፡
ከብዙ ፡ መፈተን ፡ ይሸሻል ፡፡ ራሱን ፡ ብቻ ፡ ጠብቀት ፡ ከርሱ ፡
ደዋርደል ፡ የራሱን ፡ ደህንነትስ ፡ አንደንድ ፡ ጊዜ ፡ ከተከለ
ከለ ፡ ባካሔደ ፡ ግን ፡ ከርሱ ፡ ይልቅ ፡ ከሚጠቅም ፡ በውነ
ትም ፡ ታናሽ ፡ ምሳሌ ፡ ከሚሆን ፡ ሁሉን ፡ የሚጠብቅ ፡ የ
እግዚአብሔር ፡፡ ስለ ፡ ክርስቲያንም ፡ እመቤት ፡ ይላል ፡፡
እናት ፡ የልጆች ፡ ምስጋና ፡ ናት ፡፡ የወንድ ፡ መስጋናም ፡
ምሽቱ ፡ ናት ፡፡ ወንድና ፡ ልጀቹም ፡ የቤት ፡ ምስጋና ፡ ናቸ
ው ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ የሁላቸው ፡ ምስጋና ፡ ነው ፡፡

ተርቱልያኑስም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡፡ አንድነት ፡ ሆይ ፡ በሁ
ለት ፡ ምእምናን ፡ መካከል ፡ የምትሆኝ ፡ አንዲት ፡ ተስፋ
ም ፡ አንዲት ፡ መናፈቅም ፡ አንዲት ፡ ሥርዓትም ፡ ለሕይወ
ታቸው ፡ አንድም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ማገልገል ፡ ላላቸው ፡፡
ሁለታቸው ፡ እንደ ፡ ወንድምና ፡ እት ፡ ናቸው ፡ እርሱ ፡ በ
ርሳቸው ፡፡ መንፈስና ፡ ሥጋ ፡ አልተለየባቸውም ፡ ሁለቱ ፡
ባንድ ፡ ሥጋ ፡ ናቸውና ፡፡ ባንድ ፡ በጉልበታቸው ፡ ተንበርክ
ከው ፡ ይጸልያሉ ፡ ይጾማሉም ፡ ባንድ ፡፡ እርሱ ፡ በርሳቸው
ም ፡ ያስተምራሉ ፡ ይመካከራሉም ፡ ይታገሣሉም ፡፡ ባን
ድም ፡ ናቸው ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በጌታውም ፡ እራት ፡፡
ጭንቀትንም ፡ ስደትንም ፡ ደስታውንም ፡ ሁሉ ፡ እርሱ ፡ በ
ርሳቸው ፡ ይከፋፈላሉ ፡፡ አንድም ፡ ከባልንጀራው ፡ አንደ
ቸን ፡ አይሸሽገም ፡ አንድም ፡ ከባልንጀራው ፡ አይሸሽም ፡
ድውያንንም ፡ በግልጽ ፡ ይጐበኛሉ ፡ ድኆቸንም ፡ በግልጽ ፡
ይረደሉ ፡፡ መዝሙርንም ፡ ቅኔንም ፡ ይዘምራሉ ፡፡ እርሱ ፡
በርሳቸውም ፡ ይቀደደማሉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡፡

ክርስቶስም ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ አይቶ ፡ ሰምቶም ፡ ደስ ፡ ይለዋል ፡፡ እንዲሁም ፡ ላሉት ፡ ሰላሙን ፡ ይሰድላቸዋል ፡፡ ሁለታቸውም ፡ ወደሉበት ፡ እርሱም ፡ ከዚያ ፡ ነው ፡፡ እርሱም ፡ ወደለበት ፡ ከዚያ ፡ ሰይጣን ፡ የለም ፡፡

ለሴትም ፡ ሽልም ፡ አዩ ፡ ለክርስቲያን ፡ እንዲገባ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ሥጋም ፡ እንዲህ ፡ ይለብስ ፡ ዘንድ ፡ ለኃጢአት ፡ እንደያስጐምጅ ፡ ለንጽሕናም ፡ እንዲረባ ፡፡ በልብሳቸውም ፡ ተጠነቀቁ ፡ የማይገባ ፡ ሽልም ፡ ሁሉ ፡ እንዲርቅ ፡ ከዚህም ፡ የተረፈውን ፡ ገንዘባቸውን ፡ ለድኆች ፡ ሰጡ ፡፡

በክርስቲያንና ፡ ባረማውያንም ፡ መኻከል ፡ መጋባት ፡ አልወደደም ፡፡ ከክርስቲያን ፡ መዋደድ ፡ ከጅግም ፡ ክርስቲያን ፡ ስራ ፡ እንደደከለክላቸው ፡፡ ሁለታቸው ፡ ግን ፡ አረማውያን ፡ ሁነው ፡ በተጋቡ ፡ ጊዜ ፡ በኋላም ፡ አንድ ፡ ካመነ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተመልሶ ፡ መጋባትን ፡ አልፈቱም ፡ አረማዊ ፡ ባይፈታው ፡፡

መጋባትም ፡ እንዲህ ፡ ሆነ ፡፡ የመጋባትን ፡ ሥርዓት ፡ በመኰንን ፡ ፊት ፡ ካደረጉ ፡ በኋላ ፡ ሙሽራና ፡ ሙሽሪዪቱ ፡ ባንድ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሒደው ፡ የጌታውን ፡ እራት ፡ ባንድ ፡ ተቀበሉ ፡ መስጠትም ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰጡ ፡ ቄስም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ በረከት ፡ በላያቸው ፡ ለመነላቸው ፡ እንደህም ፡ የተቀደሰች ፡ መጋባት ፡ ጸንታ ፡ ሆነች ፡፡

የክርስቲያንም ፡ የሕይወቱ ፡ ነፍስ ፡ ሁና ፡ የተቈጠረ ፡ እርሱ ፡ ጸሎት ፡ ነበረ ፡፡ በጸሎት ፡ ነው ፡ የክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ ክህነት ፡ የተገለጸበት ፡ ኃይሉም ፡ ያልተናገረ ፡፡ በልብ ፡ ጸሎት ፡ ነው ፡ ያለምና ፡ የመንፈስ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በርሱ ፡ የተቀደሰላቸው ፡፡ መጋደላቸውም ፡ ይህ ፡ ነበረ ፡ ሕይወታቸው ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ያልተቈረጠ ፡ ጸሎት ፡ ይሆንላቸው ፡ ዘንድ ፡፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፡ ኦሪጌኔስ ፡ አደማንቲዮስ ፡ ስለ ፡ ጳውሎስ ፡ ነገር ፡ ፩፤ ተሳሎኒቄ ፡ ፭፤ ፲፯፤፤ ጸልዩ ፡ ሳተውት ፡፡ ጸሎትንና ፡ ስራውን ፡ መልካም ፡ የሚያገጥመው ፡ ሳይተው ፡ ይጸልያል ፡፡ እንዲህ ፡ ብቻ ፡ የጳውሎስን ፡ ነገር ፡ ፈጽመናልና ፡ ሕይወታችን ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ጸሎት ፡ ብቻ ፡ ቢሆን ፡፡ ጸሎትም ፡ የተባለ ፡ የውነተኛ ፡ የታላቅም ፡ ጸሎታችን ፡ ክፍል ፡

ብቻ ፡ ቢሆን ፡፡ አይምሰልን ፡ ቃላት ፡ እንደ ፡ ተማርነ ፡ እንና ገረው ፡ ዘንድ ፡ በተሰራ ፡ በጸሎት ፡ ጊዜ ፡፡ የጳውሎስን ፡ ነ ገር ፡ 'ሳተው ፡ ጸልዩ' ፡ ሲል ፡ መልካም ፡ ብናስተውል ፡ ሕይ ወታችን ፡ ሁሉ ፡ ሳተወው ፡ 'አባታችን ፡ ሆይ ፡ በሰማይ ፡ የ ምትኖር' ፡ ትላለች ፡፡ እንደህም ፡ ያለች ፡ ሕይወት ፡ በምድ ር ፡ አይደለችም ፡ በሰማይ ፡ እንጅ ፡ አካሔድዋ ፡ ይሆን ፡ ዘ ንድ ፡ ይገባልና ፡፡ እኛም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ዙፋን ፡ ልንሆ ን ፡፡ መንግሥተ ፡ እግዚአብሔር ፡ በለዚያ ፡ ሁሉ ፡ ትኖራለ ችና ፡ የሰማዩ ፡ ሰው ፡ የክርስቶስ ፡ ሥኤል ፡ በልባቸው ፡ ያ ለ ፡ በርሱም ፡ ሰማያውያን ፡ የሚሆኑ ፡፡ የእስክንድርያ ም ፡ ክሌሜንቶስ ፡ ይላል ፡፡ ጸሎት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋ ራ ፡ መመላለስ ፡ ነው ፡፡ ድምጻችን ፡ እንኳ ፡ በግድ ፡ ብቻ ፡ ቢሰማ ፡ ከንፈራችንንም ፡ ሳንከፍት ፡ ዝምም ፡ ብለን ፡ እ ግዚአብሔርን ፡ ስንናገር ፡ በውሥጣችን ፡ እንጮሃለን ፡፡ ው ሥጣችንን ፡ ሁሉ ፡ ወደርሱ ፡ ማቅናት ፡ እግዚአብሔር ፡ ወ ትሮ ፡ ይሰማልና ፡፡ መልካምም ፡ የሚጸሊ ፡ በስፍራ ፡ ሁሉ ፡ ይጸልያል ፡ ጸሎቱ ፡ ሳይገለጽ ፡ ለሕዝብ ፡ ዓይን ፡፡ እርሱም ፡ ሲመላለስ ፡ ከሰዎችም ፡ ጋራ ፡ ተግባሩን ፡ ሲያድርግ ፡ በጸ ጥታም ፡ ሲያነብ ፡ የሚገባውንም ፡ ስራ ፡ ሁሉ ፡ ሲሰራ ፡ ወ ትሮ ፡ ይጸልዩል ፡፡ በነፍሱም ፡ ማሰድ ፡ እንኳ ፡ እግዚያብ ሔርን ፡ ቢያስብ ፡ ብቻ ፡፡ ባልተሰማም ፡ መናፈቅ ፡ ወደ ፡ አ ብ ፡ ቢጸራ ፡ አብ ፡ ቅርብ ፡ ነው ፡ ከርሱ ፡ ጋራም ፡ ነው ፡ በተ ናገረው ፡ ጊዜ ፡፡

ደሮ ፡ ይህ ፡ የወትሮ ፡ ጸሎት ፡ በልብ ፡ ሲኖር ፡ ያፏ ፡ ጸሎ ት ፡ በየጊዜው ፡ አልቀረም ፡፡ ያደሁድ ፡ ሥርዓት ፡ አስቀድ ሞ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ እንደህ ፡ ተከተልዋቸው ፡ ክርስቲያን ፡ ደግሞ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ በሶስተኛ ፡ በስድስተኛም ፡ በዘጠኝ ኛም ፡ ሰዓት ፡፡ ይህም ፡ ሥርዓት ፡ ሰውን ፡ ለጊዜው ፡ ሊያ ሥረ ፡ አልነበረም ፡ ጸሎትን ፡ ለማስነሣት ፡ እንጅ ፡ በምድ ራዊ ፡ ተግባራቸው ፡ ጸሎትን ፡ ለመርሳት ፡ ስለ ፡ ተፈተኑ ፡ ክ ርስቲያናት ፡፡ የቀረም ፡ ታላቅ ፡ ተግባራቸው ፡ ሁሉ ፡ የቀን ፡ ሁሉ ፡ መጀመርያና ፡ መጨረሻ ፡ ምሳቸውም ፡ ዕራታቸው ም ፡ ጉባእያቸውም ፡ ሌላም ፡ ነገር ፡ በጸሎት ፡ ተጀመረና ፡

ተጨረሰ ፡፡ ሰውም ፡ ለራሱ ፡ ብቻ ፡ አልጸለያም ፡ ለቤተ ፡ ክ
ርስቲያንም ፡ ሁሉ ፡ ለምእምናንም ፡ ሁሉ ፡ እንጅ ፡ ክርስ
ቶስ ፡ እንደስተማረን ፡ እንል ፡ ዘንድ ፡፡ አባቴ ፡ ሆይ ፡ አይ
ደለም ፡ አባታችን ፡ ሆይ ፡ እንጅ ፡ በሰማይ ፡ የምትኖር ፡፡
ከሌላም ፡ ይልቅ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ለማንበብ ፡ ጸ
ለዩ ፡ መንፈስ ፡ ቀደ.ስንም ፡ ለመኑ ፡ ያለርሱ ፡ ያ ፡ ቃል ፡ ወ
ደ ፡ ልባቸው ፡ አልገባምና ፡፡

፪፡፡ እግዚአብሔርን ፡ በግልጽ ፡ ስለ ፡ ማምለክ ፡ በክርስቲያን ፡ ጉባኤ ፡፡

ያደ.ስ ፡ ሥርዓት ፡ ማገልገል ፡ ከሁሉ ፡ ይልቅ ፡ መንፈሳ
ዊ ፡ ሁኖ ፡ ለቦታ ፡ ለጊዜም ፡ ለሥጋዊ ፡ መልክና ፡ ማድረግ
ም ፡ አልታሠረም ፡፡ ስለዚህም ፡ አረማውያን ፡ አደነቁ ፡ በ
ክርስቲያን ፡ ዘንድ ፡ ሁሉ ፡ ታጥትዋልና ፡ መቅደስ ፡ መሠው
ያም ፡ ሥእልም ፡ ጣዖትም ፡፡ ኦሪጌኔስም ፡ መለሰላቸው ፡
እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ የእግዚአብሔር ፡ መቅደስና ፡ መልክ ፡ የ
ክርስቶስ ፡ ሰውነት ፡ ናት ፡ የክርስቶስም ፡ መንፈስ ፡ ያለባ
ቸው ፡ ምእምናን ፡ ሁሉ ፡፡

ክርስቲያንም ፡ በሃይማኖት ፡ በፍቅርም ፡ በተስፋም ፡ የነ
በረላቸውን ፡ አንድነት ፡ በጸሎትና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃ
ል ፡ በመስማት ፡ ያጸኑ ፡ ዘንድ ፡ ባንድ ፡ ተሰበሰቡ ፡፡ ለመሰ
ብሰብም ፡ ቦታውን ፡ ሁሉን ፡ የተቀደሰ ፡ ሁኖ ፡ ቍጠሩት ፡፡
ክሌሚንቶስም ፡ ይላል ፡፡ የተመረጹት ፡ ጉባኤ ፡ እርሳቸ
ው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተባሉ ፡ ናቸው ፡ ቦታም ፡ አይደለ
ም ፡፡ ዩስቲኑስ ፡ ሰማዕትም ፡ በማርቆስ ፡ አውሬልዩስ ፡ ፍ
ርድ ፡ ሲሆን ፡ የሮም ፡ ሹም ፡ ሬስቲኩስ ፡ በጠየቀው ፡ ጊ
ዜ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ ወዴት ፡ ትሰበሰባላችሁ ፡፡ መለሰለ
ት ፡፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ወደሚወድ ፡ ወደሚችልበትም ፡ ስፍራ ፡፡
እላንትም ፡ ታስባላችሁን ፡ እኛ ፡ ሁላችን ፡ ባንድ ፡ ስፍራ ፡
እንድንሰበሰብ ፡፡ አይደለም ፡፡ የክርስቲያን ፡ አምላክ ፡ ባ
ንድ ፡ ስፍራ ፡ አልተወሰነምና ፡ እርሱ ፡ ያልታየ ፡ አምላክ ፡
ሰማይንና ፡ ምድርን ፡ ይመላል ፡ እንጅ ፡ ምእምናንም ፡ በ
ስፍራ ፡ ሁሉ ፡ ያመልኩታል ፡፡ ዩስቲኑስም ፡ አለው ፡ እር

ሱ ፡ በሮም ፡ ሲሆን ፡ አያሌ ፡ ክርስቲያን ፡ ወትሮ ፡ ወደ ፡ ማ ደርያው ፡ እርሱ ፡ ወደሚያድርበት ፡ እንዲሰበሰቡ ፡ ስብከ ቱንና ፡ ትምርቱን ፡ ይሰሙ ፡ ዘንድ ፡፡ ወደ ፡ ሌሎች ፡ ወደ ፡ ጉባኤ ፡ ቦቶች ፡ አልሔድሁምና ፡ አለ ፡፡

በጥቂት ፡ በጥቂትም ፡ ቦቶችን ፡ አሰናዱ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲ ያን ፡ መሰብሰብ ፡፡ የፊተኛውም ፡ ስራ ፡ ያደረጉበት ፡ ከ ፍ ፡ ያለው ፡ መቀመጫ ፡ ወይስ ፡ መቆምያ ፡ ነበረ ፡ መጽሐ ፍ ፡ ቅዱስን ፡ ለማንበብ ፡ ለስብከትም ፡፡ ደግሞም ፡ ለጌታ ው ፡ እራት ፡ ለቍርባን ፡ ሳድቃውን ፡ ሰሩ ፡፡ ይህ ፡ ሳድ ቃም ፡ በተርቱልያኑስ ፡ ዘመን ፡ ኣራ ፡ ወይስ ፡ አልታሬ ፡ ማ ለት ፡ መሠውያ ፡ ተባለ ፡፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትም ፡ በረ ፈታቸው ፡ ጊዜ ፡ የተለዩትን ፡ ቤቶች ፡ ሠሩ ፡ ለእግዚአብሔ ር ፡ ማገልገል ፡፡

በዚያ ፡ ዘመንም ፡ ክርስቲያን ፡ ሥእልን ፡ አላደረጉ ም ፡ በመቅደሳቸው ፡፡ እግዚአብሔርን ፡ ፈርተውታልና ፡ ተጠነቀቁ ፡ የርሱን ፡ ማምለክ ፡ እንዳይደበልቁ ፡ ጣዖታት ን ፡ ከማምለክ ፡ ጋራ ፡፡ ያምላክን ፡ ሥእል ፡ አላደረጉም ፡ እርሱ ፡ መንፈስ ፡ ነውና ፡ እርሱም ፡ ማምለኩን ፡ በመንፈ ስና ፡ በውነት ፡ ይፈልጋል ፡፡ የክርስቶስንም ፡ ሥእል ፡ ከማ ድረግ ፡ ፈሩ ፡ ደግሞ ፡ ክርስቶስን ፡ እንደያስቍጡ ፡ ብለ ው ፡፡ አረማውያን ፡ ነበሩ ፡ እንጂ ፡ ክርስቲያንም ፡ አይደ ሉም ፡ የክርስቶስን ፡ ሥእል ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ የጀመሩ ፡ እርሳቸውም ፡ ክርስቶስን ፡ የወደዱ ፡ አረማውያን ፡ ከታ ላላቆቻቸውም ፡ ጋራ ፡ ያስተካከሉት ፡፡ እንደዚህም ፡ አደረ ገ ፡ ቄሣር ፡ እስክንድር ፡ ሴቬሩስ ፡፡ ክርስቶስን ፡ እንደ ፡ ዕ ውቀቱ ፡ ወደታልና ፡ ምስሉንም ፡ አስደረገ ፡ ካጶሎንና ፡ ከ ሶክራቴስ ፡ ከጵላቶንም ፡ ካሪስቶቴሌስም ፡ አምሳል ፡ አ ጠገብ ፡ አኖረው ፡፡ ሌሎች ፡ አረማውያንም ፡ ሥእልን ፡ ሰ ሩ ፡ ለክርስቶስና ፡ ለጴጥሮስ ፡ ለጳውሎስም ፡ እለዚያ ፡ ደህና ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፡ ብለዋልና ፡፡

ክርስቲያንም ፡ የሥእሎቻቸውን ፡ መጀመርያ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አላደረጉም ፡ በቤታቸው ፡ እንጂ ፡ በጣዖታ ት ፡ ፈንታ ፡፡ በማኅተማቸው ፡ በቃቸውም ፡ በመንደቃቸው ፡

አምሳል ፡ አደረጉ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ነገር ፡፡ ከዚያ ፡ ወደ ፡ ያም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ መንደቅ ፡ አምሳልን ፡ አደረጉ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ በኤልዊራ ፡ የተሰበሰበች ፡ ሲኖደስ ፡ ይህነን ፡ ባመት ፡ ፫፻፭ ከለከለች ፡ እንዲህ ፡ ስትል ፡፡ የምታመልኩት ፡ የምትሰግዱለትም ፡ ነገር ፡ አትሣሉት ፡ በመንደቃችሁ ፡፡

የመስቀልን ፡ ምልክት ፡ ያድርጉ ፡ ዘንድ ፡ ቶሎ ፡ ጀመሩ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡፡ በተርቱልያኑስ ፡ መጻሕፍት ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ይገኛል ፡ ይታወቅማል ፡፡ የዚያ ፡ ዘመን ፡ ክርስቲያን ፡ በዚህች ፡ ምልክት ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ በተሰቀለው ፡ በየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ አስታወቁት ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሰዎች ፡ ደግሞ ፡ ተገኙ ፡ ይህችን ፡ ምልክት ፡ በሃይማኖት ፡ ፈንታ ፡ የቈጠሯት ፡ ልባቸውን ፡ ያለወጡ ፡ ኃጢአታቸውንም ፡ ያልተው ፡፡ ይህች ፡ ምልክት ፡ ያድነናል ፡ ሌላ ፡ ነገርም ፡ አይፈለግም ፡ ብለዋልና ፡፡

ስለ ፡ ማምለክ ፡ ጊዜያትና ፡ ስለ ፡ በዓላት ፡፡

በዚህ ፡ ዘመን ፡ በመጀመርያ ፡ ጊዜያቸው ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ነበረላቸው ፡፡ ዕለት ፡ ዕለትም ፡ ለጸሎትና ፡ ለስብከት ፡ ተሰበሰቡ ፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ስራቸው ፡ ሔዱ ፡ ጊዜያቸው ፡ ሁሉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ተቀድስዋልና ፡፡ ሕይወታቸውንም ፡ ሁሉን ፡ ሲሰሩ ፡ ሳይሰሩም ፡ አንድ ፡ ሰንበት ፡ ሁኖ ፡ ቈጠሩት ፡፡ ባይሁድ ፡ የነበረ ፡ ሕግ ፡ ሁሉ ፡ በክርስቶስ ፡ ከተፈጸመ ፡ በኋላ ፡ አሮጌ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አለፈ ፡ ሁሉም ፡ አዲስ ፡ ሆነ ፡፡ ፪፡ ቆሮንቶስ ፡ ፭፡ ፲፯፡፡ ቈሎሳይስ ፡ ፪፡ ፲፮፡ ፲፯፡፡ ልባቸውንም ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ለማጽናት ፡ ብለው ፡ አንደንድ ፡ ቀን ፡ ከሌላ ፡ ይልቅ ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡ አሳሰቡ ፡ የጌታውን ፡ ነገር ፡፡ ይህም ፡ ሁሉ ፡ በመጀመርያ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆነ ፡፡ በየሳምንት ፡ በመጀመርያ ፡ ቀን ፡ የደስታውን ፡ በዓል ፡ አደረጉ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ትንሣኤ ፡፡ በርሱም ፡ አልጾሙም ፡ ተንበርክከውም ፡ አልጸለዩም ፡ ቁመው ፡ እንጂ ፡፡ ክርስቶስ ፡ በኃጢአቱ ፡ የወደቀውን ፡ ሰው ፡ በትንሣኤ

ው፡ መልሶ፡ አስነሡቶታልና፡ ብለው፡፡ በየርቡዕም፡ በያርብ ም፡ የክርስቶስን ፡ ሕማማት ፡ ታሰቡ ፡ በለዚያም ፡ ቀን፡ ጾሙ፡ ለጸሎትም፡ ተሰበሰቡ፡ የክርስቶስን ፡ ሕማማት ፡ ለመታሰብ ፡፡ የዚያን፡ ጊዜም ፡ ስለ ፡ ሰንበት ፡ ክርክር ፡ ሆነ፡ በመሥራቅና፡ በርብ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መኻ ከል ፡፡ የመሥራቅም፡ አብያተ፡ ክርስቲያናት፡ የብሉይን፡ ነገር፡ ካደ̣ስ ፡ ነገር፡ ጋራ፡ ባንድ፡ ደብልቀውት፡ ቀደሚን፡ እንደ፡ ሰንበት፡ አከበሩት፡ ፪፤ ሰንበቶችም፡ ነበሩላቸው፡፡ ያርብ፡ አብያተ፡ ክርስቲያናት ፡ ግን፡ አንደ̣ን ፡ ብቻ ፡ አከ በሩት፡ እርሱም፡ እሁድ ፡፡

ካመት ፡ በዓላት ፡ መጀመርያ ፡ ያከበሩት ፡ ፋሲካ፡ ነበረ፡፡ ካይሁድም ፡ ወጥተው፡ የነበሩ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲ ያናት፡ በምሥራቅ ፡ ካሕዛብ ፡ ወጥተው ፡ ከነበሩ ፡ አብያ ተ፡ ክርስቲያናት ፡ ባርብ ፡ ተለዩ ፡፡ የምሥራቅ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት፡ ፋሲካቸውን፡ ካይሁድ፡ ጋራ፡ ባንድ፡ ጊዜ፡ አከበሩ፡ በሌሊት ፡ በ፲፬ና፤ በ፲፭፤ ቀን፡ መኻከል፡ ኒሳን፡ በተባለ፡ ወር ፡፡ ከዚያም፡ በተከተለው ፡ ቀን፡ የክርስቶስ ን፡ ሕማማትና፡ ሞት፡ አሰቡ፡፡ በሶስተኛውም ፡ ቀን፡ የክ ርስቶስን፡ ትንሣኤ ፡፡ የምዕራብ፡ አብያተ፡ ክርስቲያናት፡ ግን፡ ካረማውያን፡ ወጥተው ፡ የነበሩ፡ እንደዚህ ፡ አላደረጉ ም ፡ ካይሁድ ፡ ጋራ፡ ፋሲካቸውን፡ እንዲያደርጉት ፡፡ ያመ ት፡ ባልም፡ ስለ፡ ትንሣኤ፡ ባደረጉ፡ ጊዜ፡ አንድ፡ እሁድ፡ አደረጉለት ፡ አንድ፡ ዓርብም፡ ለንስሓ፡ ለጾምም፡ የክርስ ቶስም፡ ሞት፡ ለመታሰብ፡፡ ደግሞ፡ ታላቅ፡ ነገር፡ አላደረጉበት ም፡ በየሳምንት፡ በየሳምንት፡ ለክርስቶስ፡ ሞትና፡ ትን ሣኤ፡ ተስበዋልና ፡፡ በልደት ፡ አመትም ፡ ፻፶፬፤ የስሚር ና፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ፆሊቃርጶስ፡ ከሮም፡ ኤጲስቆጶስ፡ ካኒኬ ቱስ ፡ ጋራ ፡ በተገናኙ፡ ጊዜ፡ ክርክር ፡ ተነሣ፡ ስለ፡ ፋሲካ፡ በዓል ፡፡ ፆሊቃርጶስም ፡ የቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ የሐዋርያ ፡ ደ ቀ፡ መዝሙር ፡ የነበረ፡ አኒኬቱስን ፡ አለው ፡፡ ባይሁድ፡ ፋሲካ፡ ጊዜ፡ ዮሐንስ፡ ደግሞ ፡ ፋሲካውን፡ አደረገ፡፡ አኒ ኬቱስ፡ ግን፡ ፆሊቃርጶስን፡ አለው፡፡ በሮም ፡ የቀደሙት፡ ሐዋርያት ፡ ምንም ፡ እንደዚህ ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ አላደረጉ

ም ። ነገር ፡ ግን ፡ እሌህ ፡ ፪፡ በዚህ ፡ ታናሽ ፡ ክርክር ፡ መለየ ትን ፡ አላደረጉም ። ሁለታቸው ፡ ኢየልማዳቸው ፡ በዓል ን ፡ አደረጉ ፡ አንድነታቸው ፡ ሳይፈርስ ። በኋላ ፡ ግን ፡ ባመ ት ፡ ፻፺፡ ታላቅ ፡ ክርክር ፡ ስለ ፡ ፈሲካ ፡ ጊዜ ፡ ተነሣ ። በዚ ህ ፡ ክርክር ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ በ፪፡ ወገን ፡ ተከፈ ሉ ። ባንድ ፡ ወገን ፡ እለዚያ ፡ አይሁድን ፡ የተከተሉ ፡ እ ርሳቸውም ፡ የታናሽ ፡ እስያ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ነበ ሩ ፡ በራሳቸውም ፡ ጶሊክራቴስ ፡ የኤፌሶን ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ነበረ ። በሁለተኛውም ፡ ወገን ፡ የሮም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲ ያት ፡ ከቄሣርያ ፡ ከየሩሳሌምም ፡ ከጢሮስም ፡ ከስክንድ ርያም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ጋራ ፡ ነበሩ ። የስያም ፡ አ ብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ እንዲህ ፡ አሉ ። ፈሲካውን ፡ ካይሁ ድ ፡ ተቀብለናልና ፡ አይሁድንም ፡ በጊዜያቸው ፡ እንከተ ል ፡ ዘንድ ፡ ይገባናል ። ከሮምም ፡ ጋራ ፡ የነበሩ ፡ እንዲህ ፡ አሉ ። ያይሁድን ፡ ፈሲካ ፡ እኛ ፡ አልተቀበልነም ። ጌታችን ፡ በ፲፫፡ ኒዛን ፡ እራቱን ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋራ ፡ በላ ፡ በሚ መጣውም ፡ ቀን ፡ እርሱ ፡ ራሱን ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ለወጠ ፡ እርሱ ፡ ባለቤቱ ፡ ፈሲካ ፡ ሁኖ ። በዚህም ፡ ያይሁድን ፡ ፈ ሲካ ፡ ሻረ ። የስያም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ አሉ ። ከ፲፬፡ ኒዛን ፡ በኋላ ፡ የሚከተል ፡ ቀን ፡ የሕማማት ፡ በዓ ል ፡ ይሁን ። የሮምም ፡ ሰዎች ፡ አሉ ። ሁለግዜ ፡ በዓርብ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ። እለዚያም ፡ ሲሉ ። ከሕማማት ፡ በኋላ ፡ በሶስተኛ ፡ ቀን ፡ የክርስቶስ ፡ የትንሣኤው ፡ በዓል ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ፡ ብለው ። እለዚህ ፡ አሉ ። ይህ ፡ በ ሁድ ፡ ብቻ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ።

የሮምም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ቢክቶር ፡ ስለዚህ ፡ ታናሽ ፡ ነገር ፡ የስያውን ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ገዘታቸው ። ደር ፡ ግ ን ፡ ኢሬኔዎስ ፡ በዚህ ፡ ማድረጉ ፡ እጅግ ፡ ገሠጸው ።

ከትንሣኤው ፡ በዓልም ፡ በፊት ፡ ጾም ፡ አደረጉ ። ይህ ም ፡ ጾም ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ሥርዓት ፡ የሚያደርጉለት ። ነገር ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ርዝመቱ ፡ ሰውን ፡ ሁሉን ፡ እንደ ፡ ፈቃዱ ፡ ተው ት ። ባንዳንድ ፡ አገርም ፡ ይህነን ፡ ጾም ፡ እንደ ፡ ክርስቶ ስ ፡ ጾም ፡ ሊያደርጉት ፡ ብለው ፡ የ፵፡ ቀኍጥርንም ፡ ሊጠብ

ቁ ፡ ብለው ፡ ፵፤ ሰዓት ፡ አደረጉ ፡፡ ከለዚህ ፡ ፵፤ ሰዓትም ፡ ፵፤ ቀን ፡ ሆኑ ፡፡

የፋሲካ ፡ በዓልም ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ የ፶፤ በዓል ፡ ደግሞ ፡ አደረጉ ፡፡ እርሱም ፡ ያበዓል ፡ ፶፤ ቀን ፡ ከትንሣኤ ፡ በኋላ ፡ የሆነውን ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ መምጣት ፡ ያስታስብ ፡፡ እለዚህም ፡ ፶፤ ቀን ፡ ፩፤ በዓል ፡ ሁኖ ፡ ቈጠሯት ፡፡ በርሳቸውም ፡ አልጾሙም ፡ ቈመውም ፡ ብቻ ፡ ጸለዩ ፡፡ በብዙ ፡ አገርም ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ቍርባንን ፡ አደረጉ ፡፡ በኋላም ፡ ከሌህ ፡ ፶፤ ቀን ፡ ፪፤ መረጹ ፡ በዓላት ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ እርሳቸውም ፡ የርገትና ፡ የጳራቅሌጦስ ፡ በዓል ፡ ሆኑ ፡፡

ሌሎች ፡ በዓላትም ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ባብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ሁሉ ፡ አልተቀደሱም ፡ ባንደንድ ፡ ስፍራ ፡ ብቻ ፡ የኤጲፋኒያስ ፡ በዓል ፡ ተቀደሰ ፡፡ ባንደንድ ፡ ስፍራም ፡ መናልባት ፡ የልደትን ፡ በዓል ፡ ይቀድሱ ፡ ዘንድ ፡ ጀመሩ ፡፡

ስለ ፡ ክርስቲያን ፡ ማምለክ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡፡

የማምለክ ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ ጸሎትና ፡ ምስጋና ፡ ትምርትም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ነበረ ፡፡ ለትምህርትም ፡ መሠረት ፡ የብሉይና ፡ ያዲስ ፡ መጻሕፍት ፡ አደረጉ ፡፡ ይህንም ፡ አነበቡ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በሚያውቅበት ፡ ቋንቋ ፡፡ ስለዚህም ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ቋንቋ ፡ ተተረጐመ ፡፡ ከማንበብም ፡ በኋላ ፡ ስብከት ፡ ተከተለ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ማለት ፡ የሚያወጡበት ፡ ሰውንም ፡ ሁሉን ፡ በዚህ ፡ ቃል ፡ የተናገረውን ፡ ነገር ፡ በልቡ ፡ ይቀበለው ፡ ዘንድ ፡ የሚመክሩበት ፡፡

ዝማሬንም ፡ አደረጉ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡፡ ስለርሱም ፡ የዳዊትን ፡ መዝሙርት ፡ ወሰዱ ፡ አዲስ ፡ ቅኔንም ፡ አደረጉ ፡፡

ስለ ፡ ምሥጢራት ፡፡

ክርስቶስ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ፪፤ ምሥጢራት ፡ ሰጠ ፡ አንድነት ፡ የሚጸናባቸው ፡ በርሱና ፡ በርሳቸው ፡ መኻከ

ል ፡ እርሱ ፡ በርሳቸውም ፡ በመካከላቸው ፡፡ ጥምቀትን ፡ አደረገ ፡ ወደዚች ፡ አንድነት ፡ ለመግባት ፡ ምልክት ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡፡ የጌታውንም ፡ እራት ፡ ቊርባን ፡ የሚሉት ፡ ይህችን ፡ አንድነት ፡ ለማጽናት ፡ ምልክት ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡፡

ወደ ፡ ጥምቀትም ፡ የመጡ ፡ ሰዎች ፡ ሳይጠመቁ ፡ አያሌ ፡ ወራት ፡ ሊቈዩ ፡ ነበሩ ፡ ለመፈተን ፡ ትምርትንም ፡ ለመቀበል ፡፡ እርሳቸውም ፡ ከቴኩሜኖች ፡ ተባሉ ፡ ማለት ፡ የሚሰሙ ፡ ሰዎች ፡፡ እርሳቸውም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ የሃይማኖትንም ፡ ትምርት ፡ ለመስማት ፡ ብቻ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገቡ ፡ ወደ ፡ ቊርባን ፡ አልተውዋቸውም ፡፡

በስክንድርያም ፡ ሰዎችን ፡ አሳደጉ ፡ ከቴኩሜኖችን ፡ ለማስተማር ፡፡ እርሳቸውም ፡ ከቴኬቶች ፡ ተባሉ ፡፡

በዚያ ፡ ዘመንም ፡ ስምቦሎን ፡ የሚሉትን ፡ ነገር ፡ አደረጉ ፡ የሃይማኖት ፡ ማስታወቅ ፡ ማለት ፡ የሚሆን ፡፡ እርሱም ፡ ከቴኩሜኖችን ፡ ለመፈተን ፡ ነበረ ፡ ሳይጠመቁ ፡ እርሱን ፡ ሊረዱ ፡ በግልጽም ፡ ሊያስታውቁት ፡ ነበሩ ፡ በርሱ ፡ ይገለጽ ፡ ዘንድ ፡ እርሳቸው ፡ የአርቶደክሳዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ትምርት ፡ እንደ ፡ ተከተሉ ፡ ከመናፍቃንም ፡ ሊለዩበት ፡፡ አንድ ፡ ስምቦሎን ፡ የሐዋርያት ፡ ስምቦሎን ፡ ተባለ ፡ እንደዚህ ፡ የሚል ፡፡

" እኔ ፡ አምናለሁ ፡ ሁሉን ፡ በሚችል ፡ በእግዚአብሔር ፡
" አብ ፡ የሰማይና ፡ የምድር ፡ ፈጣሪ ፡፡

" ባንድ ፡ ልጁም ፡ በየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በጌታችን ፡፡ የተ
" ረገዘ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡፡ የተወለደም ፡ ከማርያም ፡ ድ
" ንግል ፡፡ መከራም ፡ የተቀበለ ፡ በጲላጦስ ፡ በጴንጤናዊ ፡
" ዘመን ፡፡ የተሰቀለም ፡፡ የሞተም ፡፡ ወደ ፡ ሢኦልም ፡ የ
" ወረደ ፡፡ በሦስተኛም ፡ ቀን ፡ ከሙታን ፡ የተነሣ ፡፡ ወደ ፡
" ሰማይም ፡ የወጣ ፡፡ ሁሉንም ፡ ወደ ፡ ሚችል ፡ ወደ ፡ እግ
" ዚአብሔር ፡ አብ ፡ ወደ ፡ ቀኙ ፡ የተቀመጠ ፡፡ ከዚያም ፡ የ
" ሚመለስ ፡ በሕያዋንና ፡ በሙታን ፡ ሊፈርድ ፡፡

" አምናለሁም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡፡ ባንደ.ትም ፡ ቅድስ

“ ትና ፡ ካቶሊካዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡፡ በቅዱሳንም ፡ አ
“ ንድነት ፡፡ በኃጢአትም ፡ ስርየት ፡፡ በሥጋም ፡ ትንሣኤ ፡፡
“ በዘላለምም ፡ ሕይወት ፡፡ ”

ይህነን ፡ ስምቦሎን ፡ ክቴኩሜኖች ፡ ተቀበሉ ፡፡ እርሱን ም ፡ በልባቸው ፡ ሊይዙት ፡ በጥምቀታቸውም ፡ ጊዜ ፡ በግ ልጽ ፡ ሊያስታውቁት ፡ ነበረ ፡፡ በግልጽም ፡ የሰይጣንን ፡ ያ ለምንም ፡ የሥጋውንም ፡ ስራ ፡ ሁሉን ፡ ሊክዱ ፡ እግዚአ ብሔርንም ፡ ለማገልገል ፡ ተስፋ ፡ ሊያስደርጉ ፡ ነበረ ፡፡

በመጀመርያም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡ ተጠመቀ ፡ የገላ ው ፡ ሁላንትና ፡ እንደ ፡ ወረደ ፡ በውኃ ፡ ታች ፡ ድውያን ፡ ግ ን ፡ በመርጨት ፡ ተጠመቁ ፡፡ በጥምቀትም ፡ ጊዜ ፡ የተባ ለ ፡ ነገር ፡ በስፍራ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ አልነበረም ፡፡ ባንድ ፡ ስ ፍራም ፡ ቀሳውስት ፡ እንዲያው ፡ በየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስ ም ፡ ብቻ ፡ አጠመቁ ፡፡ በሌላ ፡ ስፍራም ፡ በአብና ፡ በልጅ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ስም ፡፡ ደሮ ፡ ቃሉ ፡ ልዩ ፡ ሲሆን ፡ መ ንፈስ ፡ አንድ ፡ ነበረ ፡፡

በዚህ ፡ ዘመንም ፡ ክርክር ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ ሕፃናት ፡ ጥም ቀት ፡፡ ኢሬኔዎስም ፡ ይላል ፡፡ ክርስቶስ ፡ መጣ ፡ ሰውን ፡ ሁሉን ፡ በሰውነቱ ፡ ያድን ፡ ዘንድ ፡፡ ሁሉም ፡ በርሱ ፡ ሁለተ ኛ ፡ ይወለዱ ፡ ዘንድ ፡ ለእግዚአብሔር ፡፡ ሕፃናትንም ፡ ዐሽ ክሮችንም ፡ ብላቴኖችንም ፡ ጕልማሶችንም ፡ ሽማግሎች ንም ፡፡ ስለዚህም ፡ በዕድሜ ፡ ሁሉ ፡ አለፈ ፡፡ እርሱም ፡ ለ ሕፃናት ፡ ሕፃን ፡ ሆነ ፡ ሕፃናትን ፡ ይቀድስ ፡ ዘንድ ፡፡ ላሽክ ሮችም ፡ ዐሽክር ፡ ሆነ ፡ ዐሽክሮችን ፡ ይቀድስ ፡ ዘንድ ፡፡ ለ ሁሉም ፡ ምሳሌ ፡ ሆነ ፡ ሁላቸውንም ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቀ ደሳቸው ፡፡ ስለዚህም ፡ ይገባል ፡ ሕፃናትን ፡ ወደ ፡ ክርስቶ ስ ፡ አንድነት ፡ እናቀርባቸው ፡ ዘንድ ፡፡ ተርቱልያኑስ ፡ ግን ፡ የሕፃናትን ፡ ጥምቀት ፡ ሊከለክል ፡ ፈለገ ፡፡ ክርስቶስ ፡ አላ ዘዘውምና ፡ ሕፃናትም ፡ ካልተማሩ ፡ አያምኑም ፡ ሳያም ኑም ፡ ጥምቀታቸው ፡ አይገባቸውም ፡ ብልዋል ፡፡

ደሮ ፡ ግን ፡ የሕፃናት ፡ ጥምቀት ፡ አሸነፈች ፡፡ በካርታጎ ፡ በተሰበሰበች ፡ ሲኖደስ ፡ ባመት ፡ ፪፻፶፪፤ ፳፫፤ ኤጲስቆጶሳት ፡ ባንድ ፡ ሁነው ፡ የሕፃናት ፡ ጥምቀት ፡ ከሁሉ ፡ የተቀበለ

ች ፡ ሆነች ፡፡ አንድ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ፊዲስ ፡ የሚሉት ፡ ጠየ ቃቸው ፡፡ ምንድር ፡ ይገባል ፡ ሕፃናትን ፡ ቶሎ ፡ ማጥመቅ ፡ በመወለዳቸው ፡ ጊዜ ፡ ወይስ ፡ ፰፡ ቀን ፡ መቈየት ፡ በብሉ ይ ፡ ሥርዓት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡፡ ሲናይስም ፡ መለሱለት ፡ በቂ ጵርያኑስ ፡ አፌ ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡፡ ሕፃናት ፡ በኀጢአት ፡ ተ ወልደዋልና ፡ ወደ ፡ ክርስቶስ ፡ ቶሎ ፡ አምጥዋቸው ፡ በጥ ምቀት ፡ አትቈዩም ፡ እርሱ ፡ ቶሎ ፡ ያድናቸው ፡ ዘንድ ፡፡

ለሚጠመቁም ፡ ሕፃናት ፡ ዋሶችን ፡ አደረጉ ፡ ተስፋ ያስደረጉ ፡ ሕፃናትን ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ ባደጉም ፡ ጊዜ ፡ በ ትምርትና ፡ በማሳደግ ፡ ወደ ፡ ክርስቶስ ፡ ይወስድዋቸው ፡ ዘንድ ፡፡

ሕፃናትም ፡ በተጠመቁ ፡ ጊዜ ፡ ለመንፈሳዊት ፡ ክህነታ ቸው ፡ በሜሮም ፡ ተ ቀ ቡ ፡፡ ቄስም ፡ እጁን ፡ ጫነባቸው ፡ ሲ ጸልይ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንፈሱን ፡ ለሕፃን ፡ እንዲሰድ ፡ እንደሁም ፡ ጥምቀት ፡ ጸንታ ፡ ተቈጠረች ፡፡ እንዲህ ፡ በመ ጀመርያ ፡ ሆነ ፡፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ብቻቸው ፡ እ ጅ ፡ በመጫን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ መስጠት ፡ እንዲችሉ ፡ ባስተማሩ ፡ ጊዜ ፡ ቄስ ፡ አጠመቀ ፡ ብቻ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ ግ ን ፡ የጅ ፡ መጫን ፡ ቀረ ፡፡

ሕፃንም ፡ ከተጠመቀ ፡ በኋላ ፡ ወተትና ፡ ማር ፡ ተቀበለ ፡ ለምሳሌ ፡ እርሱ ፡ ሲያምን ፡ የሰማያዊ ፡ ከነዐን ፡ ወራሽ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ወተትና ፡ ማር ፡ የሚፈስበት ፡ ማለት ፡ የወን ጌል ፡ ደህንነት ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ሚገኝበት ፡፡ በኋላም ፡ የሰላ ምን ፡ ሳም ፡ ተቀበለ ፡፡

ሌላ ፡ ክርክርም ፡ ተነሣ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ መናፈ ቃን ፡ ጥም ቀ ት ፡ የሚጠቅም ፡ እንደሆን ፡ ወይስ ፡ አይደ ለም ፡፡ በታናሽ ፡ እስያም ፡ እጅግ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያና ት ፡ ነበሩ ፡ እንዲህ ፡ ያሉ ፡፡ አይጠቅምም ፡ ለመናፈቃን ፡ አንድነት ፡ የላቸውምና ፡ ከአርቶደክሳውያን ፡ ጋራ ፡ ከርሳ ቸውም ፡ የተጠመቀ ፡ ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ይጠመቅ ፡ ዘንድ ፡ ይ ፈለጋል ፡፡ የሮም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ግን ፡ አሉ ፡፡ በ ክርስቶስ ፡ በሥላሴም ፡ ስም ፡ የተጠመቁ ፡ ሁሉ ፡ ጥምቀ ታቸው ፡ ደህና ፡ ነው ፡፡ የእግዚአብሔር ፡ ስም ፡ ነውና ፡ ጥ

ምቀትን ፡ የሚቀድስ ፡ የመናፈቃንም ፡ ክፋት ፡ አይጐዳው ም ። ይህ ፡ ነገር ፡ በ፩፤ ሲኖዶች ፡ በኢቈኒዩምና ፡ በሲነዷ ፡ ጸና ።

ተርቱልያኑስ ፡ ግን ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ጻፈ ፡ የሮምንም ፡ ሥ ርዓት ፡ አልተቀበለም ፡ የመናፈቃንን ፡ ጥምቀት ፡ ጥምቀት ፡ ሁኖ ፡ ሳይቈጥር ። በአፍሪቃም ፡ በከርታጎ ፡ ሲኖደስ ፡ ተሰ በሰበች ፡ ፸፤ ኤጲስቆጶሳትም ፡ በራሳቸውም ፡ አግሪጲኑስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ የመናፈቃንን ፡ ጥምቀት ፡ አልተቀበሉም ። በ ዚህም ፡ የሮም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እስጢፋኖስ ፡ ባመት ፡ ፪፻፶፫፤ ተቈጥቶ ፡ የታናሽ ፡ እስያ ፡ የቀጳደቂያም ፡ የገላትያም ፡ የቂልቂያም ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ሁሉ ፡ ገዘታቸው ። በከርታጎ ም ፡ ባመት ፡ ፪፻፶፮፤ ፩፤ ሲኖዶች ፡ ሆኑ ፡ ባንድም ፡ ፲፰፤ ባን ድም ፡ ፸፩፤ ኤጲስቆጶሳት ፡ ተሰበሰቡ ፡ በቂጵርያኑስ ፡ በታ ች ፡ እርሳቸውም ፡ ሁሉ ፡ የተርቱልያኑስን ፡ ነገር ፡ አጸኑ ፡ የ መናፈቃን ፡ ጥምቀት ፡ አይጠቅምም ፡ ብለው ፡ መድገም ም ፡ ይፈልጋል ። ቂጵርያኑስም ፡ እስጢፋኖስን ፡ እጅግ ፡ ገ ሠጸ ። እስጢፋኖስም ፡ በትዕቢቱ ፡ አንድነትን ፡ ፈታ ፡ ከከ ርታጎ ፡ ጋራ ፡ የነበረች ። ቂጵርያኑስ ፡ ግን ፡ ደግሞ ፡ ሲኖደስ ን ፡ ፹፯፤ ኤጲስቆጶሳት ፡ የነበሩበት ፡ ሰበሰበ ፡ በርሳቸውም ፡ የመጀመርያውን ፡ ነገሩን ፡ አጸና ። ወደ ፡ ፊርሚልያኖስም ፡ ጻፈ ፡ እርሱም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ሆነ ። ዲዮናስዮስ ፡ ግን ፡ የስክንድርያ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እለዚህን ፡ ፪፤ ወገን ፡ ሊ ያስታርቅ ፡ ወደደ ፡ ስለዚህም ፡ እስጢፋኖስን ፡ ለመነ ፡ ፍቅ ርና ፡ አንድነት ፡ ያድርግ ፡ ዘንድ ፡ ካብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ጋራ ። ደርሶ ፡ መከራና ፡ ስደት ፡ ተመለሱላቸው ፡ እንዲህም ፡ ክርክር ፡ ቀረ ።

ስለ ፡ ጌታ ፡ እራት ፡ ስለ ፡ ቍርባን ። ስለ ፡ ፍቅር ፡ እራትም ።

በዚህ ፡ ዘመን ፡ እሌህ ፡ ፪፤ እራቶች ፡ ባንድ ፡ ነበሩ ። የጌ ታ ፡ እራት ፡ ቍርባንም ፡ የተባለ ፡ እርሱም ፡ የክርስቶስ ፡ ሥጋና ፡ ደም ፡ አንድነት ፡ ምሳሌ ፡ ነበረ ፡ የክርስቶስም ፡ ብ ልቶች ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ። ይህን ፡ ባንድ ፡ ከተቀበሉ ፡ በ

ኋላ ፡ እርሳቸው ፡ ባንድ ፡ ኑረው ፡ የፍቅርን ፡ እራት ፡ ‘አጋ
ጼ’ ፡ የሚሉትን ፡ በሉ ፡ የወንድሞችን ፡ ፍቅር ፡ እርሶ ፡ በር
ሳቸው ፡ ሊያጸኑ ፡፡ ያጋጼ ፡ ሥርዓት ፡ ግን ፡ ቶሎ ፡ ጠፈ ፡ ብ
ዙ ፡ ሰዎች ፡ ከንቱ ፡ አድርገውታልና ፡፡ ስለ ፡ ፍቅርም ፡ የተሰ
ራ ፡ እርሳቸው ፡ ለመብላትና ፡ ለመጠጥ ፡ ብቻ ፡ ቈጠሩት ፡፡
የጌታችን ፡ እራት ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ የምስጋና ፡ እራት ፡
ነበረ ፡ ጳውሎስም ፡ ኤውኻሪስቲያ ፡ εὐχαριστία እንደለ
ው ፡፡ ቄስ ፡ እንጀራና ፡ የወይን ፡ ጸጅ ፡ በሳድቃ ፡ ዘንድ ፡ ሲ
ያንሣ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በጉባኤ ፡ ስም ፡ አመሰገነ ፡ ስለ ፡
ፍጥረቱ ፡ ሁሉ ፡፡ እርሶም ፡ የፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ፈጣሪ ፡ ሆኖ ፡
ልጁን ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ደህንነት ፡ እንደ ፡ ለወጠ ፡፡ ምእምናን
ንም ፡ ሁሉ ፡ ኢያንዳንዱ ፡ ባለቤቱ ፡ እንጀራና ፡ ጸጅ ፡ አመ
ጡ ፡ እንደ ፡ መስጠታቸው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ጉባኤ ፡፡ ስለ
ዚህም ፡ ቍርባን ፡ ተባለ ፡ ማለቱ ፡ መስጠት ፡፡ ደህነንም ፡
ለእግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ አቀረቡ ፡ ከምስጋና ፡ ጋራ ፡ እን
ደህ ፡ የሚያምን ፡ ሁሉ ፡ ሁለንትናውን ፡ ለእግዚአብሔር ፡
አቀረበ ፡ እንደ ፡ ተቀደሰች ፡ ምሥዋዕት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ካ
ህን ፡ ሆኖ ፡ ስለዚህም ፡ ቍርባን ፡ ተባለ ፡፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ከ
ዚህ ፡ ስም ፡ ስሕተት ፡ ተወለደ ፡ የሮም ፡ ቀሳውስት ፡ እንዴ
ህ ፡ ሲሉ ፡፡ እኛ ፡ በቍርባን ፡ ጊዜ ፡ ወትሮ ፡ የተሰቀለውን ፡
የሞተውንም ፡ ክርስቶስ ፡ እናቀርባለን ፡፡
በቍርባን ፡ ጊዜ ፡ የወሰዱት ፡ እንጀራ ፡ የወትሮ ፡ እንጀ
ራ ፡ ነበረ ፡ እርሶንም ፡ ቀደሶ ፡፡ ካይሁድ ፡ ወገን ፡ ግን ፡ የወ
ጡ ፡ ክርስቲያናት ፡ ያይሁድንም ፡ ሥርዓት ፡ በቍርባን ፡ የ
ጠበቁ ፡ ከፈሲካም ፡ ጋራ ፡ ብቻ ፡ የቈረቡ ፡ ሌላ ፡ እንጀራ ፡
አልወሰዱም ፡ ያልመጸጸውን ፡ እንጅ ፡፡
በመጀመርያም ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ አቈረቡ ፡ በኋላም ፡ በየእ
ሁድ ፡ በየእሁድ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በግልጽ ፡ ባመለኩ ፡ ጊ
ዜ ፡፡ ዲያቆናትም ፡ አገልግለው ፡ ለተሰበሰቡ ፡ ሁሉ ፡ እንጀ
ራና ፡ ጸጅ ፡ አቀረቡ ፡፡ በኋላም ፡ ከተረፈ ፡ ከተቀደሰ ፡ እንጀ
ራና ፡ ጸጅ ፡ ለንግደችና ፡ ለድውያን ፡ ለሥሮችም ፡ ወሰዱት ፡
ወደ ፡ ጉባኤ ፡ መምጣት ፡ ያልቻላቸው ፡፡ ባያሌ ፡ አብያት ፡
ክርስቲያናት ፡ ግን ፡ እንዴህ ፡ አደረጉ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ቍር

ባንን ፡ ይበሉ ፡ ዘንድ ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ጉባኤ ፡ ባልሆነ ፡ ጊ
ዜ ። በየእሁድ ፡ ጉባኤ ፡ ከተፈታ ፡ በኋላ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከ
ተቀደሰው ፡ እንጀራ ፡ ክፍሉን ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ወሰደ ፡ ከርሱ ፡
ጋራ ፡ ከርሱም ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ከጸሎትና ፡ ከምስጋና ፡ ጋ
ራ ፡ በላ ። እንዲህም ፡ አሉ ፡ ተርቱልያኑስና ፡ ቂጵርያኑስ ።
እንጀራችነን ፡ የሚበቃነን ፡ ስጠነ ፡ ዛሬ ፡ ስንጸልይ ፡ ይህ ፡
ማለቱ ፡ ነው ፡ ስለ ፡ ቍርባን ፡ እንድንጸልይ ። ከዚህም ፡
በሮም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ያ ፡ ስሕተት ፡ ሆ
ነ ፡ ቍርባንን ፡ እንዲቍርጡ ፡ ቄስም ፡ ላይደል ፡ ሰው ፡ ሁ
ሉ ፡ እንጀራ ፡ ብቻ ፡ እንዲሰጡ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ።

በሙታንም ፡ መክንያት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ልቅሶ ።

በሞት ፡ የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ተገለ
ጸ ፡ ካረማውያንም ፡ አለመስተስፈት ፡ ተለየ ። እንዲህም ፡
ይላል ፡ ቂጵርያኑስ ። እግዚአብሔር ፡ ካለም ፡ ጸርቶ ፡ ከ
ኛ ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ወሰደቸው ፡ ሐዘን ፡ አይገባነም ። እኛ ፡
አውቀናልና ፡ እርሳቸው ፡ እንደልጠፉ ፡ ቀደሙነ ፡ እንጂ ።
ከኛም ፡ ተሰናበቱ ፡ እኛ ፡ እንከተላቸው ፡ ዘንድ ። ከኛም ፡
ተለይተው ፡ እንደ ፡ ሰረሩ ፡ ወደርሳቸው ፡ መናፈቅ ፡ ይገባና
ል ፡ ማልቀስ ፡ ግን ፡ አይገባነም ። አልቅሰንም ፡ ጥቁር ፡ ል
ብስ ፡ ስለ ፡ ሞታቸው ፡ እንድንለብስ ፡ አይገባነም ። እርሳ
ቸው ፡ አሁን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ የምስጋናውን ፡ ልብ
ስ ፡ ለብሰውታልና ። አረማውያንም ፡ በውነት ፡ እንደይከ
ሱነ ፡ ስለርሳቸው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ በሕይወት ፡
እንዳሉ ፡ የሚላቸው ፡ እንድናለቅስ ፡ ስለ ፡ ጠፉ ፡ ሰዎች ፡
እንዲያለቅሱ ። በቃልም ፡ ለምናስታውቀው ፡ ሃይማኖት ፡
በልባችን ፡ መመስከር ፡ እናጸናው ፡ ዘንድ ፡ ይገባናል ። እ
ኛ ፡ በተስፋ ፡ የምንኖር ፡ ክርስቶስም ፡ ስለኛ ፡ መከራ ፡ እ
ንደ ፡ ተቀበለ ፡ እንደ ፡ ተነሣም ፡ የምናምን ፡ በክርስቶስ
ም ፡ የምንኖር ፡ በርሱም ፡ መክንያት ፡ በርሱም ፡ ሁነን ፡ የ
ምንነሣ ፡ ምነው ፡ እኛ ፡ እምቢን ፡ እንላለን ፡ ከዚህ ፡ ዓለ
ም ፡ ከመሰናበት ፡ ወይስ ፡ ስለ ፡ ወገኖቻችን ፡ የተሰናበቱ ፡
እንደ ፡ ጠፉ ፡ እናለቅሳለን ፡ ክርስቶስ ፡ እርሱም ፡ ጌታችን

ና ፡ አምላካችን ፡ ሲያዝን ፡ ሲልንም ፡፡ እኔ ፡ ትንሣኤና ፡ ሕ
ይወት ፡ ነኝ ፡፡ በኔ ፡ የሚያምን ፡ ቢሞት ፡ ይሐይዋል ፡፡ የ
ሚሐይውም ፡ የሚያምንብኝም ፡ ከቶ ፡ አይሞትም ፡፡ ም
ነው ፡ እኛ ፡ እንቸኰልም ፡ የሰማዩን ፡ አገራችንን ፡ ልናይ ፡
ካባቶቻችንም ፡ ጋራ ፡ ልንገናኝ ፡፡ ከዚያ ፡ ከተወደዱ ፡ ሰዎ
ች ፡ ታላቅ ፡ ቍጥር ፡ ይጠብቁናል ፡፡ የርሳቸው ፡ የዘላለም ፡
ደህንነታቸውን ፡ ያገኙ ፡ ስለኛ ፡ ደህንነትም ፡ ብቻ ፡ ገና ፡ የ
ሚያስቡ ፡፡ ታላቅ ፡ ደስታ ፡ ሆይ ፡ ለርሳቸውና ፡ ለኛ ፡ እርሳ
ቸውን ፡ ለማየት ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ለመገናኘት ፡ ስንደርስ ፡፡
  ልባቸውም ፡ እንዲህ ፡ ሁኖ ፡ በየቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባመ
ት ፡ አንድ ፡ ቀን ፡ አደረጉ ፡ በሃይማኖት ፡ ስለ ፡ ሞቱ ፡ ሁሉ ፡
በሞቱ ፡ ቀን ፡፡ በዚያ ፡ ቀንም ፡ የሞተው ፡ ዘመዶችና ፡ ወ
ዳጆች ፡ ቍርባን ፡ አደረጉ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የነበረችላቸውን ፡
አንድነት ፡ ያጸኑ ፡ ዘንድ ፡ የሞተውንም ፡ ገና ፡ እንደሚኖ
ር ፡ የጉባኤም ፡ ብልት ፡ እንደሚሆን ፡ ቍጥረውት ፡ የርሱ
ን ፡ ፈንታ ፡ ወደ ፡ ቍርባን ፡ አመጡ ፡፡ ቄስም ፡ ለሞተው ፡ ዕ
ረፍት ፡ ለመነ ፡፡ በዚህም ፡ ሥርዓት ፡ በጎና ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ባን
ድ ፡ ደበለቁ ፡ እግዚአብሔር ፡ ስላልገለጸ ፡ ነገር ፡ ሲቈርቡ ፡
ሲጸልዩም ፡፡
  ይህም ፡ ከሌሎች ፡ ይልቅ ፡ ለሰማዕቶች ፡ ደረሰ ፡ ደማቸ
ው ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ የፈሰሰ ፡፡ እርሳቸውም ፡ ከሌሎች ፡
ይልቅ ፡ ተመሰገኑ ፡፡ የርሳቸውም ፡ የሞቱበት ፡ ቀን ፡ እን
ደ ፡ ልደታቸው ፡ ቀን ፡ ተቈጠረ ፡ ለዘላለም ፡ ድህንነት ፡ ተ
ወልደዋልና ፡ ብለው ፡፡ በዚያ ፡ ቀንም ፡ ያ ፡ ሰማዕት ፡ ክር
ስዋ ፡ ዘንድ ፡ የነበረ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተሰበሰበች ፡ ቄስ
ም ፡ የሰማዕትን ፡ ታሪክ ፡ አወጣ ፡ ሃይማኖቱን ፡ እንደ ፡ አ
ስታወቀ ፡ መከራውንም ፡ እንደ ፡ ተቀበለ ፡ እንደ ፡ ሞተ
ም ፡፡ ከዚያ ፡ ወዲያም ፡ ቍርባንን ፡ አደረጉ ፡ የርሱን ፡ አን
ድነት ፡ ያጸኑት ፡ ዘንድ ፡፡

አራተኛ፡ምዕራፍ።

የክርስቲያን፡ትምርት፡ታሪክ፡

የክርክርም፡ታሪክ፡

በዚህ፡ዘመን።

፩፡፡ ስለ፡መናፍቃን።

ስለ፡ኤብዮናውያንና፡ስለ፡ናዝራውያን፡በፊት፡ተናገ
ርን። አሁንም፡

I. ስለ፡ግኖስቲኮች፡

እንናገራለን።

ግኖስቲኮችም፡የውቀት፡ሰዎች፡ማለት፡ነው። እርሳቸ
ውም፡እንደህ፡ተባሉ፡በሃይማኖት፡ብቻ፡አልጸገቡምና፡
ሃይማኖትንም፡ናቁ፡ዕውቀትንም፡ፈለጉ። ዕውቀትንም፡
እግዚአብሔር፡ያልገለጸውን። እርሳቸውም፡በሐዋርያ
ት፡ዘመን፡ፈጽመው፡ተነሡ፡ሐዋርያትም፡በመጻሕፍ
ታቸው፡ከርሳቸው፡ጋራ፡ተጋደሉ። ጳውሎስም፡ብዙ፡
ጊዜ፡ስለርሳቸው፡ደናገራል፡ደግሞም፡በመልእክቱ፡ወ
ደ፡ቆሎሳይስ፡ም፡፪፡ ቍ፡፲፡ ፲፰። እርሳቸውም፡ያረማ
ውያንና፡ያይሁድን፡ያሰተኛ፡ፍልስፍና፡ከክርስቲያን፡
ትምርት፡ጋራ፡ደበለቁ፡እንደህም፡የውነት፡መንገድ፡
ጠፋባቸው።

እርሳቸውም፡እንደህ፡ሲሉ፡ጠየቁ። እንዴት፡ደሰማ
ማል፡የሚጨርስና፡የማይጨርስ፡ነገር። እንዴትም፡ሆ
ነ፡የፍጥረት፡መጀመርያ። እንዴትም፡ይችላል፡እግዚ
አብሔር፡እርሱ፡መንፈስ፡የሚሆን፡ፈጣሪ፡ይሆን፡ዘን
ድ፡ከርሱ፡ጋሪ፡አንድነት፡ለሌለው፡ለሥጋዊ፡ዓለም።
እግዚአብሔርም፡ፍጹም፡ቢሆን፡ከወዴት፡ይመጣል፡
በዚህ፡ዓለም፡ያለ፡ጉድል፡ሁሉ። ቅዱስ፡አምላክም፡
የሰው፡ፈጣሪ፡ቢሆን፡ከወዴት፡ይመጣል፡ክፉ። እንደ

ትም ፡ ተለዩ ፡ የሰዎች ፡ ጠባያት ፡፡ ለዚህ ፡ መጠየቅም ፡ ም ላሽን ፡ ፈለጉ ፡፡ ከዚህም ፡ በጥቂት ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ግኖስቲኮ ች ፡ ወገኖት ፡ እንናገራለን ፡፡

1. ስለ ፡ ኬሪንቶስ ፡ ወገን ፡፡

ኬሪንቶስ ፡ በኤፌሳን ፡ ተቀመጠ ፡ ዮሐንስ ፡ ሐዋርያ ፡ ከ ዚያ ፡ ደግሞ ፡ ሲቀመጥ ፡፡ የርሱም ፡ ትምርት ፡ እንደ፡ህ ፡ ነበ ረ ፡፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ብዙ ፡ መላእክት ፡ በብዙ ፡ ወ ገንም ፡ ወጡ ፡ ታላቆችና ፡ ታናሾች ፡፡ በታናሾች ፡ መላእክት ም ፡ በራሳቸው ፡ አንድ ፡ አለቃ ፡ ሆነ ፡ በርሳቸውም ፡ ዓለም ፡ ተፈጠረ ፡ የሙሴ ፡ ሕግም ፡ ተሰጠ ፡፡ ኬሪንቶስም ፡ በየሱስ ፡ በሰው ፡ በክርስቶስም ፡ መካከል ፡ ለየ ፡፡ የሱስም ፡ ሰው ፡ ሁኖ ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከዮሴፍና ፡ ከማርያም ፡ ተወለ ደ ፡ አለ ፡፡ ስለ ፡ ጽድቁ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ ጥበቡም ፡ ክርስቶስ ፡ ያለም ፡ ማደን ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ተመረጸ ፡፡ በተጠመቀም ፡ ጊዜ ፡ ከዮሐንስ ፡ መጥመቅ ፡ ሰማይ ፡ ተከፈተ ፡ የእግዚአብ ሔር ፡ ቃልም ፡ በርግብ ፡ ምሳሌ ፡ ወረደ ፡ አደረበትም ፡፡ የ እግዚአብሔር ፡ ቃልም ፡ ከመናፍስት ፡ ሁሉ ፡ የሚበልጥ ፡ መንፈስ ፡ ሁኖ ፡ የሱስ ፡ በርሱ ፡ በሁላቸው ፡ ላይ ፡ ተሾመ ፡ ብሎ ፡፡ የመስቀል ፡ ትምርት ፡ ለኬሪንቶስ ፡ ስንፍና ፡ ነበረ ፡ እንደ፡ህ ፡ ሲል ፡፡ የሱስ ፡ በታላቅነቱ ፡ ዓለምን ፡ አደነ ፡ በመ ዋረዱም ፡ አይደለም ፡፡ የሱስም ፡ ሳይሰቀል ፡ የእግዚአብሔ ር ፡ ቃል ፡ ከርሱ ፡ ተለየ ፡ ብልዋልና ፡፡ እርሱም ፡ አስተማ ረ ፡ ክርስቶስ ፡ ሊመጣ ፡ ጊዜ ፡ እንደለው ፡ ፲፻፡ አመት ፡ በ ምድር ፡ ላይ ፡ ይገዛ ፡ ዘንድ ፡፡ ይህም ፡ በሰባተኛ ፡ ሺህ ፡ አ መት ፡ ካለም ፡ ፍጥረት ፡ በኋላ ፡ ይሆናል ፡ አለ ፡፡ እርሱ ፡ አስተምርዋልና ፡ እንደ፡ህ ፡ ሲል ፡፡ ያለም ፡ ፍጥረት ፡ ምሳ ሌ ፡ ነው ፡ ላለም ፡ ታሪክ ፡፡ ዓለም ፡ በ፯፡ ቀን ፡ ተፈጥርዋል ና ፡ በሰባተኛውም ፡ ቀን ፡ የሰንበት ፡ የረፍትም ፡ ቀን ፡ ነበ ረ ፡ እንደ፡ህም ፡ ዓለም ፡ ፯፡ ሺህ ፡ አመት ፡ ሊኖር ፡ ነው ፡ ሰ ባተኛውም ፡ ሺህ ፡ አመት ፡ የሰንበትና ፡ የረፍት ፡ ዘመን ፡ ይሆናል ፡ ብልዋል ፡፡

2. ስለ ፡ ባሲሊደስ ፡ ወገን ፡፡

ባሲሊደስ ፡ ፻፴፤ አመት ፡ የሚያህል ፡ ክልደት ፡ በኋላ ፡ በምስርና ፡ በሶርያ ፡ ተቀመጠ ፡ ከልጁ ፡ ከኢሲደሮስ ፡ ጋራ ፡፡ ትምርቱም ፡ እንደህ ፡ ነበረ ፡፡ እንደህ ፡ አለ ፡፡

እግዚአብሔር ፡ ሳይገለጽ ፡ በኃይሎቹ ፡ ተዘረጋ ፡ እርሳቸውም ፡ ብዙ ፡ ናቸው ፡ በየ፫፤ የተከፈሉ ፡፡ በሁሉ ፡ ላይ ፡ እለዚህ ፡ ፫፤ ናቸው ፡፡ መንፈስ ፡፡ ቃልም ፡፡ ማሰብም ፡፡ ጥበብም ፡፡ ኃይልም ፡፡ ጽድቅም ፡፡ ሰላምም ፡፡ እሌህ ፡ ፫፤ እርሳቸው ፡ ከወጡ ፡ ከምንጫቸው ፡ ጋራ ፡ መጀመርያ ፡ ኦግደዋስ ፡ (ማለት ፡ ስምንት ፡) ናቸው ፡፡ ይህችም ፡ ኦግደዋስ ፡ የባሕሪ ፡ ሁሉ ፡ ሥር ፡ ናት ፡ ሁሉ ፡ ከርስዋ ፡ ወጥትዋልና ፡፡ ከዚችም ፡ ከመጀመርያዪቱ ፡ ከታላዊቱም ፡ ኦግደዋስ ፡ እጅግ ፡ ታናሾች ፡ ኦግደዋሶች ፡ ወጡ ፡ ሁላቸውም ፡ አንድ ፡ መሳሌል ፡ ናቸው ፡ ፫፻፷፭፤ ማዕረጋት ፡ ያለበት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ሕይወትና ፡ ኃይል ፡ በርሱ ፡ የሚወርድበት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ እስኪደርስ ፡ ድረስ ፡፡ ማዕረግም ፡ ሁሉ ፡ ኢያንደንዱ ፡ ፩፤ ኦግደዋስ ፡ ነው ፡፡ ሁሉም ፡ ባንድ ፡ አብረክሰስ ፡ ተባለ ፡ በዮናኒ ፡ ፊደላት ፡ ἀβραξας ቢቈጠር ፡ ፫፻፷፭፤ የሚሆን ፡፡ ይህም ፡ የብርሃን ፡ መንግሥት ፡ ተባለ ፡፡ በርስዋም ፡ ፊት ፡ ለፊት ፡ የጨለማ ፡ መንግሥት ፡ ነበረች ፡ ሂሌ ፡ ὕλη የተባለች ፡ ማለት ፡ ሕይወት ፡ የሌለበት ፡ በሕሪ ፡፡ ከብርሃን ፡ መንግሥትም ፡ አያሌ ፡ ከኦግደዋሶች ፡ ወድቀው ፡ ከሂሌ ፡ ጋራ ፡ ተደበለቁ ፡፡ በዚህም ፡ መደበለቅ ፡ ያለም ፡ ፍጥረት ፡ ሆነ ፡ በወደቁም ፡ መላእክት ፡፡ የርሳቸውም ፡ አለቃ ፡ አንድ ፡ ከለዚህ ፡ ከወደቁ ፡ መላእክት ፡ ያለም ፡ ፈጣሪ ፡ ሆነ ፡፡ እርሱ ፡ ካምላክ ፡ በታች ፡ ሁኖ ፡ አምላክም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ ግዝቶ ፡ እርሱ ፡ ዓለምን ፡ ፈጠረ ፡፡ በእግዚአብሔርም ፡ ጥበብ ፡ ሕይወት ፡ ሁሉ ፡ በሂሌ ፡ ታሥሮ ፡ ስለ ፡ ኃጢአቱ ፡ መከራ ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ ጊዜ ፡ አለው ፡ በጥቂት ፡ በጥቂት ፡ እስኪነሣ ፡ ድረስ ፡፡ የደንጊያ ፡ ሕይወት ፡ የተቈረጠለትን ፡ ዘመን ፡ በደንጊያ ፡ ትኖራለች ፡ አርነት ፡ ወጥታ ፡ ወደ ፡ ተክል ፡ እስክትገባ ፡ ድረስ ፡፡ በተክልም ፡ ዘመንዋን ፡ ከተቀመጠች ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ እንስሳ ፡ ት

ፈልሳለች ፡ ከታናሽ ፡ እንስሳም ፡ ወደ ፡ ታላቁ ፡ ወደ ፡ ሰው ፡ እስክትደርስ ፡ ድረስ ፡፡ ያም ፡ የወደቁት ፡ መላእክት ፡ አለ ቃ ፡ አርኾን ፡ ተባለ ፡ ማለቱ ፡ አለቃ ፡፡ እርሱም ፡ የእግ ዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ አያውቅም ፡ ሳያውቀው ፡ ግን ፡ የእግ ዚአብሔርን ፡ ፈቃድ ፡ ይፈጽማል ፡፡ ያይሁድ ፡ ሕዝብም ፡ ይህነን ፡ አርኾን ፡ እግዚአብሔር ፡ ሁኖ ፡ አሰቡት ፡፡ በመ ኻከላቸው ፡ የነበሩ ፡ መንፈሳውያን ፡ ግን ፡ እርሱን ፡ አ ወቁት ፡፡

የባሲሊደስም ፡ ትምርት ፡ ስለ ፡ መድኃኒት ፡ እንደህ ፡ ብ ሎ ፡ ነበረ ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ መንፈሳውያንን ፡ ሰዎች ፡ ሊያድናቸው ፡ በፈቀደ ፡ ጊዜ ፡ በመጀመርያ ፡ ኦግደዋስ ፡ በሪ ሱ ፡ ያለውን ፡ መንፈሱን ፡ ላከ ፡ ይህም ፡ ከሰው ፡ ከየሱስ ፡ ጋራ ፡ ተዋሀደ ፡ የሱስ ፡ በዮርደኖስ ፡ በተጠመቀ ፡ ጊዜ ፡፡ አሁ ንም ፡ አርኾን ፡ የሱስን ፡ አይቶ ፡ መንፈስ ፡ እንደደረበት ፡ ወደ ፡ ዕውቀት ፡ ደረሰ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ልዑልም ፡ ተገዛ ፡፡ ባለምም ፡ ያሉትን ፡ ፫፡ ወገን ፡ የሚሌ ፡ ወገንና ፡ የመንፈስ ፡ ወገን ፡ ለየ ፡፡ የመንፈስንም ፡ ወገኖች ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ ይ መጡ ፡ ዘንድ ፡ አልከለከላቸውም ፡፡ ለባሲሊደስም ፡ ለር ሱ ፡ ደግሞ ፡ የመስቀል ፡ ቃል ፡ ስንፍና ፡ ነበረ ፡ እንደህ ፡ ብ ልዋልና ፡፡ በየሱስ ፡ ያድር ፡ የነበረ ፡ መንፈስ ፡ መከራ ፡ በቀ ረበ ፡ ጊዜ ፡ ራቀ ፡ የሱስንም ፡ ሰው ፡ ብቻ ፡ ሁኖት ፡ ለመከ ራ ፡ አሰናበተው ፡፡

ባሲሊደስም ፡ የጳውሎስን ፡ ትምርት ፡ ሰው ፡ በሃይማኖ ት ፡ ብቻ ፡ ያለ ፡ መግበር ፡ ይጸድቃል ፡ ሲል ፡ ካደ ፡፡ የሰው ፡ ኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ የኃጢአት ፡ ደመወዜ ፡ በሚሆን ፡ በመከ ራ ፡ ይከፈላል ፡ ይሻራልም ፡ አለ ፡፡ ሃይማኖትም ፡ የእግዚ አብሔርን ፡ ነገር ፡ መመለከትና ፡ መቀበል ፡ ነው ፡ ብልዋል ፡፡

የምግባሩ ፡ ትምርት ፡ ብርቱ ፡ ነበረ ፡፡ መንፈሳዊ ፡ ሰው ፡ ደጋደል ፡ ዘንድ ፡ ነበረ ፡ ባሕርዩን ፡ ሁሉን ፡ ሊያነጻ ፡ ከኃጢ አት ፡ ከሚሌ ፡ ነገርም ፡ ሁሉ ፡፡ መጋባትንም ፡ እንደ ፡ ሌሎ ች ፡ ግኖስቲኮች ፡ አልናቀም ፡፡

3. የዋለንቲኖስ ፡ ወገን ።

ዋለንቲኖስም ፡ በምስር ፡ ተወለደ ፡ ወደ ፡ ሮምም ፡ ሒደ ፡ ትምህርቱን ፡ ከዚያ ፡ አስተማረ ። የርሱም ፡ ትምርት ፡ የባሲሊደስን ፡ መሰለ ፡ አንደንድ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ልዩ ፡ ነበረ ።

የባሕሪ ፡ ሁሉ ፡ ምንጭ ፡ ዋለንቲኖስ ፡ ቢቶስ ፡ ብሎ ፡ ጸሬው ፡ ማለቱ ፡ ጫርስ ፡ የሌለው ፡ ጉድጓድ ። ከርሱም ፡ የወጡትን ፡ ኃይሎች ፡ አዮኖችን ፡ ብሎ ፡ ጸሬቸው ። አዮንም ፡ *αἰὼν* ማለት ፡ ዓለም ፡ ነው ። እርሳቸውም ፡ በየ፪ ፡ ተጸመደ ፡ ተባትና ፡ አንስት ። ሁላቸውም ፡ ተወሰኑ ። በወሰናቸውም ፡ በሥርዓታቸውም ፡ ከኖሩ ፡ ደህንነት ፡ በጸናች ። የብርሃንም ፡ መንግሥት ፡ በዋለንቲኖስ ፡ ጵሌሮማ ፡ *πλήρωμα* ተባለች ፡ ማለቱ ፡ ምላት ። ከጵሌሮማም ፡ አያሌ ፡ አዮኖች ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ወደ ፡ ሂሌ ፡ ወደ ፡ ጨለማ ፡ መንግሥት ፡ ወደቁ ፡ ሂሌንም ፡ እንደ ፡ ያው ፡ የሞተች ፡ ሕይወትና ፡ መንቀሳቀስ ፡ የሌለበት ፡ አሳንቀሩ ። ከለዚህም ፡ ከወደቁ ፡ አዮኖች ፡ አንዲት ፡ አንስት ፡ አዮን ፡ ነበረች ፡ ሶፊያ ፡ ማለት ፡ ጥበብ ፡ የተባለች ። እርስዋም ፡ ከሂሌ ፡ ጋሬ ፡ ከመገናኘትዋ ፡ ባለም ፡ ያለ ፡ ሕይወት ፡ ሁሉ ፡ መጣች ። እንደህም ፡ ፫ ፡ የጣባያት ፡ ወገን ፡ ሆኑ ። ፩ ፡ መንፈሳውያን ፡ የጵሌሮማ ፡ ወገን ። ፪ ፡ ነፍሳውያንም ፡ የፍጥረት ፡ ወገን ፡ እንደ ፡ ፈቃደቸው ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ጵሌሮማ ፡ ወይስ ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ወደ ፡ ሂሌ ፡ መሔድ ፡ የቻላቸው ። ፫ ፡ ሥጋውያንም ፡ የሂሌ ፡ የሰይጣንም ፡ ወገን ። በዚህ ፡ ፍጥረት ፡ ላይም ፡ አንድ ፡ አዮን ፡ ተሾመ ፡ ያምላክ ፡ ያልተፈጸመ ፡ ምሳሌ ፡ እርሱም ፡ ደሚውርጎስ ፡ ተባለ ፡ ማለት ፡ ፈጣሪ ፡ በርሱ ፡ ዓለም ፡ ተፈጥርዋልና ። በሂሌ ፡ ላይም ፡ አንድ ፡ ባሕሪ ፡ ይገዛል ፡ እርሱም ፡ ሰይጣን ፡ ነው ። ይህ ፡ ዓለምም ፡ የላየኛ ፡ ዓለም ፡ የጵሌሮማ ፡ ምሳሌ ፡ ሊሆን ፡ ነበረ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ፍጹም ፡ አልሆነም ። ደሚውርጎስ ፡ ግን ፡ ሰውን ፡ ሲፈጥር ፡ እንደርሱ ፡ የሆነውን ፡ ነፍስ ፡ ሰጠው ። ደር ፡ ያች ፡ ሶፊያ ፡ ከሶቲር ፡ እርሱም ፡ የሚያድን ፡ አዮን ፡ ከሚሆን ፡ የተቀበለቸውን ፡ መንፈስ ፡ ለሰው ፡ ሰጠች ፡ እንደህም ፡ ሰው ፡ በ፫ ፡ ጠባያት ፡ ሆነ ፡ ሥጋዊ ፡ በሥጋ ፡ ነፍሳዊም ፡ በነፍስ ፡ መንፈሳዊም ፡ በመንፈስ ። የሰ

ው ፡ ልጆችም ፡ ሁሉ ፡ የለዚህ ፡ ፫፤ ወገን ፡ ናቸው ፡፡ ሶቴር
ም ፡ መንፈሳውያንና ፡ ነፍሳውያን ፡ ሰዎች ፡ ሊያድን ፡ ፈ
ቀደ ፡ ስለዚህም ፡ ሁለግዜ ፡ ከደሚውርጎስ ፡ ጋራ ፡ ሰራ ፡ ደ
ሚውርጎስ ፡ ሳያውቀው ፡፡ የብሉይ ፡ መጻሕፍትንም ፡ ሰ
ጠ ፡ አያሌ ፡ ተርጉም ፡ ያለው ፡ ስለለዚህ ፡ ፫፤ ወገኖች ፡፡ ደ
ሚውርጎስም ፡ አንድ ፡ ክርስቶስን ፡ አደረገ ፡ ከሰማያዊ ፡
ኤቴር ፡ ባሕሪ ፡ ሥጋውን ፡ ያደረገለት ፡ ምድራዊ ፡ እንደይ
ሆን ፡፡ ነፍስም ፡ ሰጠው ፡ ከፍጥረቱ ፡፡ ደሮ ፡ እርሱ ፡ ያልቻለ
ው ፡ ሶቴር ፡ አደረገ ፡፡ ክርስቶስ ፡ በዮርደኖስ ፡ በተጠመቀ ፡
ጊዜ ፡ ሶቴር ፡ በርግብ ፡ ምሳሌ ፡ መጥቶ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ተዋ
ሀደ ፡፡ ይህም ፡ መዋደድ ፡ ነው ፡ ሰው ፡ የሚድንበት ፡ የክር
ስቶስ ፡ ሞትም ፡ አይደለም ፡፡ ለዋለንቲኖስም ፡ እንደ ፡ ባሲሊ
ደስ ፡ እንደ ፡ ኬሪንቶስም ፡ እንደ ፡ ግኖስቲኮችም ፡ ሁሉ ፡ የ
መስቀል ፡ ትምህርት ፡ ዕንቅፋት ፡ ነበረና ፡፡ እንዲህ ፡ ይላል
ና ፡ ዋለንቲኖስ ፡፡ ክርስቶስ ፡ መከራውን ፡ ስይቀበል ፡ ሶቴ
ር ፡ ከርሱ ፡ ተለይቶ ፡ ወደ ፡ ጵሌሮማ ፡ ተመለሰ ፡፡ ክርስቶስ
ም ፡ ሲሞት ፡ ነፍሱ ፡ ወደ ፡ ደሚውርጎስ ፡ ሔደ ፡ ከርሱም ፡
ሥልጣንንና ፡ ሹመትን ፡ በስሙ ፡ ተቀበለ ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡
ላይ ፡፡ መንፈሱ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ሶቴር ፡ ወጣ ፡ በርሱም ፡ የሚ
ድኑ ፡ መንፈሳውያን ፡ ሁሉ ፡ ወደዚያ ፡ ይከተሉታል ፡፡

የዋለንቲኖስ ፡ ወገንም ፡ ታላቆች ፡ መምህራን ፡ እለዚህ ፡
ናቸው ፡፡ ሄራክሌዎን ፡ ከስክንድርያ ፡ ጵቶልሚዎስም ፡
ማርቆስም ፡ በርደሳኔስም ፡፡

4. ስለ ፡ ኦፌታውያን ፡፡ ማለት ፡ የባብ ፡ ወገን ፡፡

የርሳቸው ፡ ትምርት ፡ ግንደንድ ፡ ነገር ፡ የዋለንቲኖስን ፡ ት
ምርት ፡ ይመስላል ፡ ደሮ ፡ ከርሱ ፡ ይልቅ ፡ ከወንጌል ፡ ይር
ቃል ፡፡ እርሳቸውም ፡ ደግሞ ፡ በትምርታቸው ፡ አሉ ፡ ከሕ
ደወት ፡ ክፍል ፡ እንደ ፡ ወደቀ ፡ ከጵሌሮማ ፡ ወደ ፡ ሂሌ ፡፡
የጵሌሮማም ፡ ሶፊያ ፡ ተገናኙች ፡ ከታቸኞች ፡ አዮኖች ፡ ጋ
ራ ፡፡ ኦፌታውያን ፡ ግን ፡ ፈጣሪዩን ፡ ያልደባኦት ፡ አሉት ፡፡
እርሱም ፡ የጵሌሮማ ፡ ጸላት ፡ ነው ፡ በጸላትነቱም ፡ ይኖራ
ል ፡ ሶፊያ ፡ እስክትሸረው ፡ ድረስ ፡፡ ያልደባኦት ፡ ግን ፡ ሳ

ደወድ ፡ በግድም ፡ ለሶፊያና ፡ ለጵሌሮማ ፡ ይገዛል ፡፡ እርሱ
ም ፡ ወደ ፡ ታች ፡ ወደ ፡ ሂሌ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ ምሳሌው ፡ በሂሌ ፡
ሆነ ፡ እርሱም ፡ የባብ ፡ መንፈስ ፡፡ ከያልደባኦትም ፡ ፯፡ መ
ላእክት ፡ ተወለዱ ፡ የ፯፡ ከዋክብት ፡ መናፍስት ፡ የሚሆ
ኑ ፡፡ እለዚህም ፡ እንደ ፡ እንስሳ ፡ የሆነውን ፡ ሰውን ፡ ፈጠ
ሩ ፡ ያልደባኦት ፡ መንፈሱን ፡ እስኪሰጠው ፡ ድረስ ፡፡ ሰው
ም ፡ የያልደባኦትን ፡ መንፈስ ፡ ሲቀበል ፡ ይህ ፡ መንፈስ ፡
ከያልደባኦት ፡ ራቀ ፡፡ በዚህም ፡ ሰው ፡ ከርሱ ፡ በላይ ፡ እ
ንደ ፡ ሆነ ፡ ተቈጥቶ ፡ ከለከለው ፡ መልካምንና ፡ ክፋን ፡ ከ
ሚያስታውቀው ፡ ዛፍ ፡ እንዳይበላ ፡፡ ሶፊያ ፡ ግን ፡ በባብ ፡
መንፈስ ፡ ሰውን ፡ ላለመታዘዝ ፡ አታለለቸው ፡ የሰውን ፡ ዓ
ይንም ፡ ከፈተች ፡፡ እንዲህም ፡ በለዚህ ፡ ሰዎች ፡ ትምህር
ት ፡ የሰው ፡ መጀመርያ ፡ ኀጢአት ፡ ኀጢአት ፡ አልሆነም ፡
በጎ ፡ ስራ ፡ እንጂ ፡፡ መውደቅም ፡ አይደለም ፡ መነሣት ፡
እንጂ ፡፡ ስለዚህም ፡ እሌህ ፡ ሰዎች ፡ እባባውያን ፡ ተባ
ሉ ፡ የባብን ፡ መንፈስ ፡ ስላከበሩ ፡፡ እንዲህም ፡ ትምህርታ
ቸው ፡ በመስደብ ፡ በክፉትም ፡ ባመፃም ፡ መላ ፡ ወደ ፡ ር
ኵሰትም ፡ ሁሉ ፡ ወሰዳቸው ፡ እለዚያን ፡ የባብን ፡ ልጆች ፡

5. ስለ ፡ በሲሊደስ ፡ አሰተኛ ፡ ወገን ፡፡ በባሲሊደስ ፡ ስም ፡
ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የሚጸላ ፡ ትምርት ፡ ያስተማሩ ፡፡

እርሳቸውም ፡ ዷሚውርጎስ ፡ የልዑል ፡ አምላክ ፡ ጸላ
ት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብለው ፡ አስተማሩ ፡፡ መንፈስ ፡ ግን ፡ የሥ
ጋውን ፡ ምሳሌ ፡ ብቻ ፡ ለበሰ ፡ ሰውን ፡ ያድን ፡ ዘንድ ፡፡ አ
ይሁድም ፡ ይሰቅሉት ፡ ዘንድ ፡ በወደዱ ፡ ጊዜ ፡ ሲሞንን ፡ ከ
ኪሬኔ ፡ በርሱ ፡ ፈንታ ፡ አሰቀለ ፡ እርሱ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ብርሃ
ን ፡ መንግሥት ፡ ተመለሰ ፡፡

እሌህ ፡ ሰዎችም ፡ ደቄቶች ፡ ተባሉ ፡፡ ማለት ፡ በምሳ
ሌ ፡ የሚያምኑ ፡ ግብዞች ፡፡

6. የሴት ፡ ያደም ፡ ልጅ ፡ ወገን ፡፡

እርሳቸውም ፡ አስተማሩ ፡ ሴት ፡ የመንፈሳውያን ፡ ሁ
ሉ ፡ አባት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ሶፊያም ፡ አስወለደቸው ፡ ባቤል ፡

ፈንታ ፡፡ ሴትም ፡ በኋለኛ ፡ ዘመን ፡ በየሱስ ፡ አካል ፡ ተወለደ ፡፡

7. የቃደል ፡ ወገን ፡፡

እርሳቸውም ፡ የደፈሩ ፡ ዘንጎች ፡ ነበሩ ፡፡ በብሉይ ፡ መጻሕፍት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጸላቶች ፡ የተባሉ ፡ ሁሉ ፡ ወዳጆቻቸውን ፡ አደረጉ ፡ ስለዚህም ፡ ቃደልን ፡ ላለቃቸው ፡ መረጹ ፡፡ ይሁደንም ፡ አስቆሮታዊን ፡፡

8. የሳቱርኒኑስ ፡ ወገን ፡፡

ሳቱርኒኑስ ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ አስተማረ ፡፡ በብርሃንና ፡ በጨለማ ፡ መንግሥቶች ፡ መኻከል ፡ ፯፡ ታቸኞች ፡ መላእክት ፡ የከዋክብት ፡ መናፍስት ፡ ናቸው ፡፡ እርሳቸውም ፡ ከጨለማ ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ ተጸልተው ፡ ክፍልዋን ፡ ወሰዱ ፡ በርሱም ፡ ይህ ፡ ዓለም ፡ ሆነ ፡ እለዚህ ፡ ፯፡ የተከፋፈሉበት ፡፡ አለቃቸውም ፡ ያይሁድ ፡ አምላክ ፡ ነበረ ፡፡ ሁልጊዜም ፡ ከሰይጣንና ፡ ከመንግሥቱ ፡ ጋራ ፡ ተጻሉ ፡ እርሳቸውም ፡ የሚሰሩ ፡ ሰይጣን ፡ ያፈርሳል ፡፡ ጥቂት ፡ ብርሃንም ፡ ይወድቅባቸዋል ፡ መልክ ፡ ያለው ፡ በርሱም ፡ የብርሃን ፡ ምሳሌ ፡ አደረጉ ፡፡ ለርሱም ፡ መንፈስ ፡ የለውም ፡ እግዚአብሔር ፡ ከመንፈሱ ፡ እስኪሰጠው ፡ ድረስ ፡፡ ይህም ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ክፍል ፡ ከሂሌ ፡ ጋራ ፡ ሊጋደል ፡ ክርኩሰትም ፡ ሁሉ ፡ ሊነጻ ፡ ነው ፡ ዘመኑ ፡ እስኪደርስ ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ መንግሥት ፡ ይመለስ ፡ ዘንድ ፡፡ የሳቱርኒኑስ ፡ መድኃን ፡ ደግሞ ፡ የሥጋ ፡ ምሳሌ ፡ ብቻ ፡ ለበሰ ፡፡ እርሱና ፡ ወገኑም ፡ መጋባትን ፡ ከለከሉ ፡ ብህትናውንም ፡ አዘዙ ፡፡

9. ስለ ፡ ታትያኑስና ፡ ስለ ፡ እንክራቲቶች ፡ ወገን ፡፡

ታትያኑስ ፡ በአሲርያ ፡ የተወለደ ፡ በሮም ፡ ኖረ ፡ ተናጋሪ ፡ ሁኖ ፡፡ ከዚያም ፡ ዩስቲኖስ ፡ ሰማዕት ፡ አስተምሮት ፡ ወደ ፡ ክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ገባ ፡፡ በዩስቲኖስ ፡ ዘመንም ፡ ኦርቶዶክሳዊ ፡ ሁኖ ፡ ተቀመጠ ፡፡ ዩስቲኖስ ፡ ግን ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ግኖስቲኮስ ፡ ሆነ ፡፡ እንዲህ ፡ ብሎም ፡ አስተማረ ፡፡

የሰው ፡ ነፍስ ፡ ከሂሌ ፡ ተፈጠረች ፡ ስለዚህ ፡ ልትሞት ፡ ኖት ፡ መንፈስ ፡ በክርስቶስ ፡ ባይገባባት ። ታትያኑስም ፡ መጋባትን ፡ ጸላ ፡ እንደ ፡ ሰይጣን ፡ ስራ ። ሰውም ፡ የሥጋውን ፡ መሻት ፡ ይከለክል ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፡ ስለዚህም ፡ እንክራቲቴስ ፡ ተባለ ፡ ማለቱ ፡ የሥጋውን ፡ መሻት ፡ የሚከለክል ፡ በሥጋውም ፡ ላይ ፡ የሚገዛ ።

እንደሁም ፡ ፱ልፀስ ፡ ከስያኑስና ፡ ሴቬሬስ ፡ ነበረ ።

10. ሌሎች ፡ ግኖስቲኮች ፡ ሕግን ፡ የጸሉ ። እርሳቸውም ፡ ቃርጶክራቴስ ፡ ኤጲፋኔስም ፡ የጵሮዲኮስም ፡ የኒቆላዎስም ፡ የሲሞንም ፡ ያንቲተክቶችም ፡ ወገኖች ።

እሌህም ፡ ሁሉ ፡ ሕግንና ፡ ሥርዓትን ፡ ጸሉ ። የክርስቲያንም ፡ አርነት ፡ ለኀጢአት ፡ ለማገልገል ፡ ሊሰሬ ፡ ነበሬ ።

11. ስለ ፡ መርቂዮንና ፡ ስለ ፡ ወገኑ ።

መርቂዮን ፡ ከቀሬ ፡ ግኖስቲኮች ፡ ሁሉ ፡ ተሻለ ። እርሱም ፡ በውቀቱ ፡ የሳተ ፡ ከልቡ ፡ ይልቅ ፡ ይመስላል ። አባቱም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ነበረ ፡ በሲኖጴ ፡ በጶንጦስ ፡ በ፻፵፡ አመት ፡ የሚያህል ፡ ከልደት ፡ በኋላ ። መርቂዮንም ፡ በመጀመርያ ፡ ኦርቶደክሳዊ ፡ ነበረ ። ነገር ፡ ግን ፡ አንደንድ ፡ ነገር ፡ በቤት ፡ ክርስቲያን ፡ ትምርት ፡ አገኘ ፡ ያልተገጠመላት ። እርሱም ፡ ሌላ ፡ ትምርት ፡ አወጣ ፡ ከቤት ፡ ክርስቲያንም ፡ ተገዘተ ። የትምርቱ ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነበረ ።

፩፡ ነገር ፡ አለ ፡ ከዘላለም ፡ ለዘላለም ፡ በመኻከላቸው ፡ ጸላትነት ፡ ያለባቸው ። እግዚአብሔር ፡ ለዑልና ፡ መንግሥቱ ፡ ባንድ ፡ ወገን ፡ ሂሌም ፡ በሁለተኛ ፡ ወገን ። በሁለታቸውም ፡ መኻከል ፡ ዴሚውርጎስ ፡ ይኖራል ፡ እርሱም ፡ ያለም ፡ ፈጣሪ ፡ ያይሁድም ፡ አምላክ ። የሂሌም ፡ አለቃ ፡ ሰይጣን ፡ ነው ። ዴሚውርጎስም ፡ ከሂሌና ፡ ከሰይጣን ፡ ጋራ ፡ ተጋደለ ፡ ድልም ፡ አልነሣም ። እግዚአብሔር ፡ ልዑል ፡ ግን ፡ የሰውን ፡ ሥጋ ፡ ለብሶ ፡ በሥጋውም ፡ ሰውን ፡ አደነ ። የሱስም ፡ መከራውን ፡ በመቀበል ፡ በርሱ ፡ በውነት ፡ የሚ

ያምኑበትን ፡ ያድናል ። መከራው ፡ ግን ፡ በማየት ፡ ብቻ ፡ ነበረ ፡ በውነት ፡ መከራ ፡ አልተቀበለም ።

መርቂዮንም ፡ የብሉይ ፡ ሥርዓት ፡ መጻሕፍትን ፡ አላስተዋላቸውምና ፡ የዲሚውርጎስ ፡ ስራ ፡ ናቸው ፡ አለ ። ከሐዋርያትም ፡ ጳውሎስን ፡ ብቻ ፡ ተቀበለ ። የርሱም ፡ ምግባር ፡ ብርቱ ፡ ነበረ ፡ ከዓለም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ሰው ፡ ሊሸሽ ፡ ፈለገ ፡ በፍጥረትም ፡ እንዲደረክስ ።

የመርቂዮን ፡ ወገንም ፡ መምህራን ፡ ማርቆስ ፡ ሉቃስም ፡ አጴሌስም ፡ ከመርቂዮን ፡ ትምርት ፡ እጅግ ፡ አልራቁም ።

II. ስለ ፡ ማኑ ፡ ስለ ፡ ማኒኬዮችም ።

ማኒም ፡ አንድ ፡ መናፈቅ ፡ ነበረ ፡ ባመት ፡ ፪፻፸፡ በፋርስ ፡ መንግሥት ፡ የተነሣ ፡ የክርስቲያንን ፡ ሃይማኖት ፡ ከፋርስ ፡ ሃይማኖት ፡ ጋራ ፡ መደብለቅ ፡ የፈለገ ፡ እንዲሁም ፡ ትምርቱን ፡ ሰራ ፡ የግኖስቲኮችን ፡ ትምህርት ፡ የመሰለች ። ክርስቲያንም ፡ ሊቀበሉት ፡ ብሎ ፡ እርሱ ፡ ያ ፡ ጰራቅሊጦስ ፡ ክርስቶስ ፡ ለደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ተስፋ ፡ ስላስደረገላቸው ፡ የክርስቶስም ፡ ሐዋርያ ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ አለ ። እርሱም ፡ ብልህና ፡ አዋቂ ፡ ነበረ ፡ መልካምንም ፡ አምሳል ፡ አደረገ ። የፋርስ ፡ ንጉሥም ፡ ሻጱር ፡ በመጀመርያ ፡ መልካም ፡ ተቀበለው ። የፋርስ ፡ ካህናት ፡ ግን ፡ አሳደዱት ። እርሱም ፡ ወደ ፡ ህንድና ፡ ወደ ፡ ጪን ፡ ሸሸ ። ሻጱርም ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ማኑ ፡ ተመለሰ ፡ የሻጱር ፡ ልጅም ፡ ሆርሙዝ ፡ ተቀበለው ፡ ባመት ፡ ፪፸፪። ከ፩፡ አመትም ፡ በኋላ ፡ ቤህረም ፡ ነገሠ ፡ እርሱም ፡ በመጀመርያ ፡ በጎ ፡ አደረገለት ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ጸላው ። የፋርስንም ፡ ካህናት ፡ ሰበሰበ ፡ ከማኑ ፡ ጋራ ፡ ይከራከሩ ፡ ዘንድ ፡ እርሳቸውም ፡ ማኑን ፡ መናፈቅ ፡ ሁኖ ፡ ገለጹት ። ባልካደም ፡ ጊዜ ፡ ገድለውት ፡ ቍርበቱን ፡ ገፈፉበት ፡ መሉትም ፡ ወገኑንም ፡ ለማስፈራት ፡ በከተማ ፡ ደጅ ፡ ፊት ፡ ሰቀሉት ፡ ባመት ፡ ፪፸፯።

የርሱም ፡ ትምርት ፡ የግኖስቲኮች ፡ ትምርት ፡ ዘመድ ፡ ነበረች ። እንዲሁም ፡ አለ ። ፩፡ ባሕርዮች ፡ አሉ ፡ የዘላለ

ም ፡ እርሳቸውም ፡ አንድ ፡ በጎ ፡ ባሕሪ ፡ እርሱም ፡ እግዚ
አብሔር ፡፡ አንድም ፡ ክፉ ፡ ባሕሪ ፡ እርሱም ፡ ሰይጣን ፡ የ
ፋርስ ፡ ወገን ፡ አህሪማን ፡ የሚሉት ፡፡ እግዚአብሔር ፡ አ
ብም ፡ የብርሃን ፡ ንጉሥ ፡ ነው ፡፡ በጎ ፡ ነገርም ፡ ሁሉ ፡ ከር
ሱ ፡ ዘንድ ፡ ይመጣል ፡፡ ከርሱም ፡ ፲፪ ፡ አዮኖች ፡ ወጡ ፡ በ
ጎ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የመላባቸው ፡፡ የጨለማ ፡ ሥልጣናት ፡ ግ
ን ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡ ተጸልተው ፡ ፀብ ፡ ሲያድርጉ ፡ እ
ርሱ ፡ በርሳቸው ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ መንግሥት ፡ ቀረቡ ፡ ጥቂ
ት ፡ ብርሃንም ፡ ወደቀባቸው ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ጥላቸው
ን ፡ ረስተው ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ መንግሥት ፡ ሊገቡ ፡ ተጋደሉ ፡
የብርሃንን ፡ ክፍል ፡ ይወስዱ ፡ ዘንድ ፡፡ ስለዚህም ፡ እግዚ
አብሔር ፡ አንዲት ፡ አዮንን ፡ እርስዋም ፡ የሕይወት ፡ እ
ናት ፡ የሆነች ፡ ከባሕርዩ ፡ አስወጣት ፡ የብርሃንን ፡ መንግ
ሥት ፡ ወሰን ፡ ትጠብቅ ፡ ዘንድ ፡፡ ከርስዋም ፡ መጀመርያ ፡
ሰው ፡ ተወለደ ፡ እርሱም ፡ ፭ ፡ ጽሩዓንን ፡ ጠባያት ፡ እሳት
ን ፡ ብርሃንንም ፡ አየርንም ፡ ውኃውንም ፡ መሬትንም ፡
ለብሶ ፡ ለመጋደል ፡ ወጣ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ የጨለማ ፡ ሥልጣ
ናት ፡ ባሸነፉት ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሕያውን ፡ መንፈ
ሱን ፡ አስወጣ ፡ ይረደው ፡ ዘንድ ፡፡ ያም ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡
መንግሥት ፡ መለሰው ፡፡ ከሰው ፡ እቃ ፡ ጦር ፡ ግን ፡ ክፍል ፡
ወደቀ ፡ የጨለማም ፡ ሥልጣናት ፡ ከብርሃኑ ፡ ክፍልን ፡ ዋ
ጡ ፡ ይህም ፡ ከሂሌ ፡ ጋራ ፡ የተደበለቀች ፡ ያለም ፡ ነፍስ ፡
ሆነች ፡፡ እርስዋንም ፡ ደግሞ ፡ ያድን ፡ ዘንድ ፡ ብሎ ፡ ሕያ
ው ፡ መንፈስ ፡ ሁለግዜ ፡ ይሰራል ፡፡ ያልወደቀውንም ፡ ብር
ሃን ፡ ወደ ፡ ፀሐይ ፡ ወደ ፡ ጨረቃም ፡ ወደ ፡ ከዋክብትም ፡
አኖረ ፡ ከዚያ ፡ የወደቀችን ፡ ሕይወት ፡ ሁሉ ፡ ከሞት ፡ ያ
ድን ፡ ዘንድ ፡፡ ይህ ፡ ብርሃንም ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ተባለ ፡ ከመ
ጀመርያ ፡ ሰው ፡ ወጥትዋልና ፡፡ አሁንም ፡ የጨለማ ፡ ኃይ
ሎች ፡ ብርሃናቸው ፡ ሁሉ ፡ እንዳይሔድ ፡ ብለው ፡ የርሳቸ
ውን ፡ ብርሃን ፡ የፍጥረትን ፡ ነፍስ ፡ ለቀሙ ፡ አለቃቸውም ፡
የመጀመርያውን ፡ ሰው ፡ ምሳሌ ፡ አደረገበት ፡፡ ይህችም ፡
ምሳሌ ፡ ሰው ፡ ሆነች ፡ እርሱም ፡ አደም ፡ ብርሃንና ፡ ጨለ
ማ ፡ የሚገናኙበት ፡ ታናሽ ፡ ዓለምም ፡ ያለው ፡፡

የማኑም ፡ ትምርት ፡ ስለ ፡ ገነት ፡ ስለ ፡ መጀመርያ ፡ ኃጢአትም ፡ ኃጢአት ፡ እንደልሆነ ፡ ስለ ፡ ማደንም ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ የግኖስቲኮች ፡ ዓለማዊ ፡ ጥበባቸው ፡ ይመስላል ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ቃል ፡ በጣም ፡ ይጻላል ፡፡

የማኑ ፡ ወገንም ፡ ማኒኬዎች ፡ የተባሉ ፡ ራሳቸውን ፡ ክርስቲያን ፡ ሲሉ ፡ ክርስቲያንን ፡ ገሊላውያን ፡ አልዋቸው ፡፡ ማኑም ፡ ተነሣ ፡ ከርሶ ፡ በኋላ ፡ ሙሐመድ ፡ እንደ ፡ ተነሣ ፡ ራሱን ፡ ጰራቅሊጦስ ፡ ብሎ ፡ ክርስቲያንንም ፡ ሰድቦ ፡ መጻሕፍታቸውን ፡ እንደ ፡ አጠፋ ፡ የርሱንም ፡ ትምህርት ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ትምርት ፡ አደረገ ፡ የርሱንም ፡ ቍርኣን ፡ የመሠረት ፡ መልእክት ፡ አለው ፡፡

በማኑም ፡ ጉባኤ ፡ ፪፡ ወገን ፡ ነበሩ ፡ የውሥጡ ፡ የሚ ደም ፡ የተባሉ ፡፡ የሚደም ፡ የማኑ ፡ መጻሕፍት ፡ ሊሰሙ ፡ ነበሩ ፡ ምሥጢራቸውን ፡ ግን ፡ አልተማሩም ፡ የውሥጡ ፡ ግን ፡ የተመረጹ ፡ ነበሩ ፡ ፍጹማንም ፡ ካህናትም ፡ ተባሉ ፡፡ እርሳቸውም ፡ በድንግልና ፡ ሊኖሩ ፡ ታዘዙ ፡ ከፍጥረትም ፡ አንዳችን ፡ እንደይበድሉ ፡ እንስሳም ፡ እንደይገድሉ ፡ አታክልትንም ፡ እንደይሰብሩ ፡፡ እለዚህም ፡ ካህናት ፡ ምግባቸውን ፡ ከጉባኤ ፡ ተቀበሉ ፡፡ ማኑም ፡ ጰራቅሊጦስ ፡ ተብልዋልና ፡ እንደ ፡ ክርስቶስም ፡ ፲፪፡ ሐዋርያት ፡ መረጸ ፡፡ ከሞቱም ፡ በኋላ ፡ ይህች ፡ ሥርዓት ፡ ተጠበቀች ፡ ወትሮ ፡ ፲፪፡ አለቆች ፡ ባራሳቸው ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ በ፲፪፡ ላይም ፡ አንድ ፡ የሁሉ ፡ አለቃ ፡ ሁኖ ፡ በማኑ ፡ ፈንታ ፡፡ ከለዚያም ፡ ፲፪፡ በታች ፡ ፸፪፡ ቀሳውስትና ፡ ዲያቆናት ፡ ወንጌላውያንም ፡ የተባሉ ፡ ተሾሙላቸው ፡፡

፪፡፡ ስለ ፡ ክርስቲያን ፡ ትምህርት ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡፡

የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የጉባኤው ፡ መድኃኒትና ፡ ጌታ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ሲወጣ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ቃሉን ፡ ሰጠ ፡ በሐዋርያት ፡ አፍ ፡፡ ይህ ፡ ቃልም ፡ ባፋቸው ፡ ከተሰበከ ፡ በኋ

ላ ፡ በመንፈስና ፡ በኀይል ፡ ብዙ ፡ ኀጥኣንም ፡ በርሱ ፡ ወደ ፡
እግዚአብሔር ፡ ከተመለሱ ፡ በኋላ ፡ ይህነን ፡ ቃሉን ፡ በ
ጽሕፈት ፡ ለምእመናን ፡ ሁሉ ፡ ለዘመንም ፡ ሁሉ ፡ እስከ ፡
ዓለም ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፡ ጠበቀው ። አሁንም ፡ ሐዋርያ
ት ፡ ይህነን ፡ ቃል ፡ አወቁ ፡ የክርስቶስም ፡ መንፈስ ፡ በስብ
ከታቸው ፡ ከስሕተት ፡ ጠበቃቸው ፡ የርሳቸውን ፡ ነገር ፡ ከ
እግዚአብሔር ፡ ነገር ፡ ጋራ ፡ እንዳይደበልቁ ፡ መንፈስም ፡
በርሳቸው ፡ ያስጻፈ ፡ የሰው ፡ ነገር ፡ እንዳይሆን ፡ የክርስቶ
ስ ፡ የሕያውም ፡ አምላክ ፡ ነገር ፡ እንጂ ፡ ለዘላለም ፡ የሚ
ኖር ። ይህ ፡ ቃልም ፡ ብቻ ፡ የክርስቶስ ፡ ጽሩ ፡ ቃል ፡ ነው ፡
በሌላም ፡ በሰው ፡ መጽሐፍ ፡ እንደዚህ ፡ ጽሩ ፡ አይገኝም ።
ስለዚህም ፡ እርሱ ፡ የክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ መሪ ፡ ነው ፡ በመ
ንገዳቸው ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ዘላለም ፡ ደህንነት ፡ እስኪደርሱ ፡
ድረስ ። ነገር ፡ ግን ፡ እንዴት ፡ አለ ፡ ክርስቶስ ። እንዲህ ፡ ና
ት ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ዘርን ፡ የ
ሚጣል ፡ በምድር ፡ ላይ ። ይተኛልም ፡ ይነሣልም ፡ ሌትም ፡
ቀንም ፡ ዘሩም ፡ ይበቈላል ፡ ያድጋልም ፡ እንዲላወቀ ፡ እ
ርሱ ። ምድሪቱ ፡ ብቻዋን ፡ ታወጣለችና ፡ በፍሬ ። በመጀ
መርያ ፡ ሣዕር ። ደግሞም ፡ እሸት ። ደግሞም ፡ ስንዴ ፡ ት
መላለች ፡ በሸት ፡ ማርቆስ ፡ ፬፡ ፳፮፡ ፳፯፡ ፳፰። የክርስቶ
ስ ፡ ዕውቀትና ፡ ሕይወት ፡ በክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ ልብ ፡ በቤ
ት ፡ ክርስቲያንም ፡ መኻከል ፡ በድንገት ፡ አልተፈጸመም
ና ፡ ሊያድግ ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኀይል ፡ ከኀ
ጢአትና ፡ ከስሕተት ፡ ጋራ ፡ በመጋደል ። ስለዚህ ፡ እናያለ
ን ፡ በመጀመርያ ፡ ዘመን ፡ የክርስቲያን ፡ ዕውቀት ፡ በመጀ
መርያ ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ነበረች ፡ በጣምም ፡ እንደልተለየች ፡
ካልነጻ ፡ ከሰው ፡ ትምህርት ። ደሮ ፡ ይህ ፡ ሳይቀር ፡ የክርስ
ቶስ ፡ ቃል ፡ አደረባቸው ፡ መንፈሱም ፡ መራቸው ፡ ከብርሃ
ን ፡ ወደ ፡ ብርሃን ። እርሱም ፡ በመጋደል ። ይህ ፡ መጋደል
ም ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ አጅግ ፡ ሆነ ፡ ከገኖስቲኮች ፡ ጋራ ። ከ
ርሳቸውም ፡ ጋራ ፡ ሲከራከሩ ፡ ሲጋደሉም ፡ እርሳቸው ፡ ለ
ራሳቸው ፡ የወንጌልን ፡ ብርሃን ፡ ሊፈልጉ ፡ ሊማሩም ፡ ነበ
ሩ ። ይህነንም ፡ ሲሹ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱ

ስ ፡ ወደ ፡ እውነት ፡ ሁሉ ፡ መሬቸው ፡ እንደ ፡ ሃይማኖታቸ ው ፡ መጠን ።

የቤት ፡ ክርስቲያንም ፡ መምህራን ፡ የ፪፤ ወገን ፡ ነበሩ ። ያንድ ፡ ወገን ፡ መምህራን ፡ በየውሃት ፡ ብቻ ፡ መኖር ፡ ፈለ ጉ ፡ ሲመረምሩም ፡ እጅግ ፡ ተጠነቀቁ ፡ ሃይማኖት ፡ እንደይ ጉደ ፡ በውቀት ። የሁለተኛ ፡ ወገንም ፡ መምህራን ፡ ሃይማ ኖት ፡ ሳይቀር ፡ እጅግ ፡ መረመሩ ፡ ዕውቀትን ፡ ሊያገኙ ፡ የ ክርስቲያንንም ፡ ትምህርት ፡ ለጥቢባን ፡ አረማውያን ፡ ሊ ያበጁ ፡ ከጥቢባን ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፡ ሰዎችን ፡ ለሃይማኖት ፡ ያገኙ ፡ ዘንድ ። የመጀመርያ ፡ ወገንም ፡ መምህራን ፡ በሮ ም ፡ በአፍሪቃም ፡ በታናሽ ፡ እስያም ፡ ነበሩ ፡ እንደ ፡ ጶሊቃ ርጶስ ፡ ከስሚርና ። ጳጲያስም ፡ ከሄራጶሊስ ። ኢሬኔዎስ ም ፡ ተርቱልያኑስም ። በርሳቸው ፡ መኻከልም ፡ የሚበል ጥ ፡ ኢሬኔዎስ ፡ ነው ። እርሱም ፡ በመጽሐፉ ፡ ከግኖስቲ ኮች ፡ ጋራ ፡ ሲጋደል ፡ እንደይህ ፡ ይላል ።

ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በምድር ፡ ሁሉ ፡ በመሠረት ፡ ትምህ ርትዋ ፡ አንዲት ፡ ናት ። ሃይማኖትዋም ፡ አንዲት ፡ ናት ። ይህነንም ፡ ትምናለች ፡ አንድ ፡ ልብና ፡ አንዲት ፡ ነፍስ ፡ እ ንደላት ፡ ታስታውቀውማለች ፡ አንድ ፡ አፉ ፡ ብቻ ፡ እንደ ላት ። ፀሐይም ፡ እርሱም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስራ ፡ ባለም ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ እንደሆን ፡ እንደህም ፡ የውነት ፡ ትምህር ት ፡ ወደ ፡ ስፍራ ፡ ሁሉ ፡ ብርሃኑን ፡ ይሰደል ፡ ሰውንም ፡ ሁ ሉን ፡ ያብራል ፡ እውነትን ፡ ወደ ፡ ማወቅ ፡ ይደርሱ ፡ ዘንድ ፡ የሚወዱትን ። ከቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ አለቆች ፡ መንገር ፡ መልካም ፡ የሚያውቅ ፡ እንኳ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ አይችልም ፡ አያውቅምም ፡ ሌላም ፡ ትምህርትን ፡ ማስተማር ፡ አይ ችልም ፡ ከክርስቶስ ፡ እርሱ ፡ መምህራችን ፡ ከሚሆን ፡ ማንም ፡ አይበልጥምና ። የመንገርም ፡ ስጥወታ ፡ የሚያ ጣ ፡ ከተቀበለው ፡ ትምህርት ፡ አንደች ፡ አያልቅበትም ፡ ሃ ይማኖት ፡ ሁሉ ፡ አንዲት ፡ ናትና ። ያም ፡ አእምሮ ፡ ደህና ፡ የሚሆን ፡ እግዚአብሔርንም ፡ የሚፈራ ፡ እውነትንም ፡ የሚወድ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሰው ፡ ሥልጣን ፡ የሰጠውን ፡ ነገር ፡ በደስታ ፡ ያስባል ፡ ወደ ፡ ዕውቀቱም ፡ ሊደርስ ፡ ደጋ

ደላል ፡፡ ዕለት ፡ ዕለትም ፡ ተምሮ ፡ በርሱ ፡ ያድጋል ፡፡ እር ሱ ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ነው ፡ በግልጽ ፡ በቁም ፡ ነገርም ፡ የተነገረ ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ የተሰወረ ፡ ምሥጢርም ፡ አይደለም ፡፡ ፍቅር ፡ የሌለበት ፡ ዕውቀት ፡ ይነፋልና ፡ ፍቅርም ፡ ብቻ ፡ ይጠ ቅማል ፡ ጳውሎስ ፡ እንዳለ ፡፡

ከግኖስቲኮች ፡ ጸላቶች ፡ ግን ፡ አያሌ ፡ ክርስቲያን ፡ ባለ ቤታቸው ፡ ወደ ፡ ስሕተት ፡ ወደቁ ፡፡ እርሳቸውም ፡ የሞን ታኑስ ፡ ወገን ፡ ናቸው ፡፡

ሞንታኑስም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበር ፡ ባመት ፡ ፻፶፤ የሚያ ህል ፡ በፍሪጊያ ፡ ሁኖ ፡ ካረማውያንም ፡ ተመልሶ ፡ የክርስቲያ ንን ፡ ሃይማኖት ፡ የተቀበለ ፡፡ በሃይማኖትም ፡ እጅግ ፡ የቃጠ ለ ፡፡ ያለምን ፡ ነገር ፡ ኖቀ ፡ ለልቡም ፡ ዕረፍት ፡ የለውምና ፡ የሥጋና ፡ የመንፈስ ፡ ነገር ፡ ደበለቀ ፡፡ እርሱ ፡ በሃይማኖት ና ፡ በፍቅር ፡ ሲቃጠል ፡ በኃይልም ፡ ሲናገር ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፡ ነቢይ ፡ ሁኖ ፡ የቈጠሩት ፡፡ በዚህም ፡ ትዕቢቱ ፡ ተነሣ ፡ እር ሱም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ተላከ ፡ አሰበ ፡ ቤተ ፡ ክር ስቲያንን ፡ ያነጻ ፡ ዘንድ ፡ አዲስ ፡ ነገርንም ፡ ያወጣ ፡ ዘን ድ ፡፡ ከሕማምም ፡ የተነሣ ፡ በተነበየ ፡ ጊዜ ፡ እርሱ ፡ ከወ ገኑ ፡ ጋራ ፡ አሰቡ ፡ ይህ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡፡ ፪፤ ሴቶችም ፡ የዚህ ፡ ወገን ፡ ሆኑ ፡ እርሳቸውም ፡ ጵርስኪ ላና ፡ መክሲሚላ ፡፡

የሞንታኑስ ፡ ወገንም ፡ ትምርት ፡ ይህ ፡ ነበረ ፡፡ የእግዚአ ብሔር ፡ መንግሥት ፡ ታድጋለች ፡ ካለመፈጸምም ፡ በጥቂት ፡ በጥቂት ፡ በማዕረግ ፡ ወደ ፡ ፍጻሜ ፡ ትደርሳለች ፡፡ የመንግ ሥተ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ሕፃንነት ፡ ባባቶች ፡ አለቆች ፡ ዘ መን ፡ ነበረ ፡፡ ዐሸከርናዋም ፡ በሕግና ፡ በነቢያት ፡ ዘመን ፡ የጕብዝም ፡ ዕድሜዋ ፡ በወንጌል ፡ ዘመን ፡ ጕልማስናዋም ፡ በሞንታኑስ ፡ ዘመን ፡፡ በርሱ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ፈሰዋልና ፡፡ ሞንታኑስም ፡ ጰራቅሊጦስ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ብለዋልና ፡፡ በዚህ ፡ ትምርትም ፡ እጅግ ፡ እውነት ፡ ነበረ ፡፡ መንግሥተ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወደ ፡ ውሥጥ ፡ ባታድግ ፡ ወ ደ ፡ ሚደም ፡ ባትዘረጋ ፡ ክፉ ፡ ነውና ፡ ሃይማኖትም ፡ ሕያ ው ፡ አይደለም ፡፡ ስለዚህም ፡ እርሳቸው ፡ በጣም ፡ መናፈ

ቃን ፡ ሁነው ፡ አልተቈጠሩም ፡ እንደ ፡ ተሳቱ ፡ ወንድሞች ፡ አ
ንጅ ፡፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ በነቢያት ፡ ልታድግ ፡ ይገባል ፡ አ
ሉ ፡፡ እግዚአብሔርም ፡ ነቢያቱ ፡ በሞንታኑስ ፡ ወገን ፡ እን
ደ ፡ ሰጠ ፡ በርሳቸውም ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ታላቅ ፡ ስጥወ
ታ ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ ለክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ መሰላቸው ፡፡ እር
ሳቸውም ፡ እጅግ ፡ ጾሙ ፡ ጾምንም ፡ በትእዛዝ ፡ በቤተ ፡
ክርስቲያን ፡ ያበዙ ፡ ዘንድ ፡ ፈለጉ ፡ ሌሎች ፡ መምህራን
ም ፡ ስለዚህ ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ተከራከሩ ፡ ለጊዜ ፡፡ ነገር ፡
ግን ፡ በኋላ ፡ ሞንታኑስን ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ተከተሉት ፡ በቤተ ፡
ክርስቲያን ፡፡ እርሳቸውም ፡ እጅግ ፡ ወደዱ ፡ ለሃይማኖት ፡
ለመመስከር ፡ ይሞቱ ፡ ዘንድ ፡፡ እርሳቸውም ፡ ሰውን ፡ ሁ
ሉን ፡ ከሁለተኛ ፡ መጋባት ፡ ከለከሉ ፡ ወንድም ፡ ወይስ ፡ ሴ
ት ፡ ሲሞት ፡ ሁለተኛውን ፡ መጋባት ፡ ኃጢአትን ፡ አደረጉ
ት ፡፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ለዚህ ፡ ዓለም ፡ ብቻ ፡ አልተዋደዱም
ና ፡ ብለው ፡ ለዘላለም ፡ ሕይወትም ፡ እንጅ ፡፡

ይች ፡ ወገንም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በበዛች ፡ ጊዜ ፡ አያ
ሌ ፡ መምህራን ፡ እጅግ ፡ ብርቱ ፡ ተናገሩባቸው ፡ ይገዝትዋ
ቸውም ፡ ዘንድ ፡ ፈለጉ ፡፡ ኢሬኔዎስ ፡ ግን ፡ አስታረቃቸው ፡
ከኤሌውትሮስ ፡ ከሮም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ካብያተ ፡ ክርስቲ
ያናትም ፡ ጋራ ፡ ጵሪክስያስ ፡ ከታናሽ ፡ እስያ ፡ ወደ ፡ ሮም ፡
እስኪመጠ ፡ ድረስ ፡፡ እርሱም ፡ ባጣላቸው ፡ ጊዜ ፡ ተገዘ
ቱ ፡ ለብቻቸውም ፡ ኖሩ ፡፡

የቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ መምህራን ፡ ሁለተኛ ፡ ወገን ፡ እ
ርሳቸውም ፡ የእስክንድርያ ፡ መምህራን ፡ ሃይማኖት ፡ ሳይቀ
ር ፡ ዕውቀትን ፡ እጅግ ፡ ፈለጉ ፡፡ በእስክንድርያም ፡ የክቴኬ
ቶች ፡ መድረሳ ፡ ነበረች ፡ መምህራን ፡ የክርስቲያንን ፡ ትም
ህርት ፡ የተማሩባት ፡ እጅግም ፡ የመረመሩባት ፡ ከቴኬቶ
ች ፡ የሚያጠምቁባት ፡ መምህራን ፡ ሁልግዜ ፡ የበጁ ፡ ይሆ
ኑ ፡ ዘንድ ፡ ላረማውያንና ፡ ለመናፍቃን ፡ መልስ ፡ ይሰጡ ፡
ዘንድ ፡ ስለ ፡ ወንጌል ፡ ትምህርት ፡፡ የዚችም ፡ የክቴኬ
ቶች ፡ መድረሳ ፡ አስተማሮች ፡ ጳንቴኖስ ፡ ነበረ ፡ ክሌሜን
ቶስም ፡ ኦሪጌኔስም ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ይችን ፡ መድረሳ ፡
ሲባርክ ፡ ብዙ ፡ ብላቴኖች ፡ ይማሩ ፡ ዘንድ ፡ ወደርስዋ ፡ መ

ጡ ። በቤት ፡ ክርስቲያንም ፡ ለማስተማር ፡ ነፍሳቸውን ፡ ያሰናዱ ፡ ዘንድ ፡ የወደዱ ፡ ወደዚያ ፡ መጡ ፡ ከዚያም ፡ ተ ማሩ ። ሃይማኖትንም ፡ በውቀት ፡ ማስተማር ፡ የርሳቸው ፡ ተግባር ፡ ሁንዋልና ፡ ባለቤታቸው ፡ በዚህ ፡ እጅግ ፡ ዕው ቀትን ፡ ፈለጉ ።

ክሌሜንቶስም ፡ ይላል ። ላዋቂ ፡ ሃይማኖት ፡ ይፈለጋል ፡ ለነፍሱ ፡ ሕይወት ፡ የሥጋ ፡ ሕይወትም ፡ እስትንፋስን ፡ እ ንድትሻ ። ሃይማኖት ፡ ግን ፡ እንዲያው ፡ መምሰል ፡ አይደ ለችም ። በልብ ፡ የሚሆን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ መቀ በል ፡ እንጅ ፡ ለርሱም ፡ እሺ ፡ ማለት ፡ በልብ ። አለማመ ንም ፡ የሰው ፡ መጕደል ፡ ነው ። በልጅም ፡ የሚያምን ፡ የ ዘላለም ፡ ሕይወት ፡ አለው ። ምእምናንም ፡ ሕይወትን ፡ ያገኙ ፡ እንዲሆኑ ፡ ምንድር ፡ ይተርፋባቸዋል ፡ ከዘላለም ፡ ሕይወት ፡ የሚበልጥ ።

ስለ ፡ ት ም ር ት ም ፡ ዕ ው ቀ ት ፡ ይላል ። ትምርትና ፡ አ ካሔድ ፡ አንድ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ይገባል ። ዛፍ ፡ ከፍሬው ፡ ይታወቃልና ፡ ባበባውና ፡ በቅጸሉም ፡ አይደለም ። ዕውቀት ም ፡ ከፍሬና ፡ ካካሔድ ፡ ትመጣለች ፡ ከትምህርትና ፡ ካበባ ም ፡ አይደለም ። የክርስቲያንም ፡ ዕውቀት ፡ ትምርት ፡ ብ ቻ ፡ አይደለም ፡ ያ ፡ ብርሃን ፡ እንጅ ፡ በነፍስ ፡ የሚነሣ ፡ ለ እግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ከመታዘዝ ፡ ሁሉንም ፡ የሚያ በራ ፡ ለሰውም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ የሚያስታውቀው ፡ ራሱን ፡ ፍጥረትንም ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ አንድነት ። ዓይን ፡ ለ ሥጋ ፡ እንዲሆን ፡ እንዲህም ፡ ዕውቀት ፡ ለመንፈስ ፡ ነው ። የውቀት ፡ ምንጫም ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ነው ፡ ማለት ፡ ብ ሉይና ፡ አዲስ ፡ መጽሐፍ ፡ ሌላ ፡ የለም ።

አረማውያንና ፡ አይሁድም ፡ ሲሉ ። የክርስቲያን ፡ ወገ ን ፡ ብዙ ፡ ናቸውና ፡ ዕውቀት ፡ ወደ ፡ ተገኘበት ፡ አይታወቅ ም ፡ ብለው ፡ ክሌሜንቶስ ፡ እንዲህ ፡ አለ ። እኛ ፡ በሰው ፡ ምስክር ፡ አናምንም ፡ ሰው ፡ ይፈርዷልና ፡ እኛ ፡ ደግመን ፡ መፍርድ ፡ እንደምንችል ። ባይበቃም ፡ አሳባችንን ፡ እን ል ፡ ዘንድ ፡ ለነገርነው ፡ ነገር ፡ ምስክር ፡ እንሰጥ ፡ ዘንድ ፡ ሊፈልጉ ፡ ከሰው ፡ ምስክር ፡ አንሻም ። ደር ፡ እኛ ፡ የነገር

ነውን ፡ ነገር ፡ እናጽናልን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ነገር ፡ በርሱ ም ፡ ብቻ ፡ ጽኑ ፡ ይሆናል ። በዚህም ፡ መጠን ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ የቀመሱት ፡ ብቻ ፡ ምእመናን ፡ ይባላሉ ። በርሱ ፡ ግን ፡ ያደጉ ፡ እውነትንም ፡ በጣም ፡ ያወቁ ፡ እርሳቸው ፡ አ ዋቆች ፡ ሆኑ ። ለመጽሐፍ ፡ ዕውቀትም ፡ የሚያምን ፡ ልብ ፡ ይፈለጋል ። የሚያምንም ፡ ልብ ፡ የተከፈተውን ፡ ዓይን ፡ ይመስላል ። ያለርሱ ፡ አይታወቅምና ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ የተባለ ። ከዚህ ፡ ጋራም ፡ ሌላ ፡ ዕውቀት ፡ ይፈለጋል ፡ የሰ ውን ፡ ብልሃትና ፡ ጥበብ ፡ እንድታውቅ ፡ የእግዚአብሔር ን ፡ ነገር ፡ ላረማውያንና ፡ ለመናፈቃን ፡ ታበጀው ፡ ዘንድ ፡ እንዲጠቅምላቸው ። ዐዋቂ ፡ ክርስቲያንም ፡ ያረማውያ ንን ፡ ጥበብ ፡ እንዲያውቅ ፡ ክሌሜንቶስ ፡ ይፈልጋል ፡ ያለ ዚህ ፡ አያይምና ፡ እግዚአብሔር ፡ ባረማውያንም ፡ መኻ ከል ፡ እንደ ፡ ሰራ ፡ አራማውያንን ፡ ወንጌልን ፡ ለመቀበል ፡ ያሰናደቸው ፡ ዘንድ ። ያረማውያንም ፡ ጥበብ ፡ ያለም ፡ ጥ በብ ፡ ሁኖ ፡ ወደ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ አያደርስም ፡ አ ንደንድ ፡ ብልጭልጭተ ፡ ግን ፡ ከውነት ፡ አለበት ፡ እግዚአ ብሔር ፡ የጠበቀላቸው ፡ በርሱ ፡ መክንያት ፡ ይናፈቁ ፡ ዘን ድ ፡ ወደዚያ ፡ ፀሓይ ፡ በወንጌል ፡ ወደሚያበራ ፡ ይህነንም ፡ ላረማውያን ፡ ማሳየት ፡ ይገባል ።

ይህችም ፡ ዕውቀት ፡ ከሃይማኖትና ፡ ከየውሃት ፡ ካልተ ለየች ፡ ባልጉደች ፡ በትሕትናም ፡ በኖረች ። ነገር ፡ ግን ፡ ታ ላቅ ፡ መፈተን ፡ ነበረ ፡ ሃይማኖትንና ፡ ዕውቀትን ፡ ይለዩ ፡ ዘንድ ። ይህ ፡ ግን ፡ ሳይቀር ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ የቤተ ፡ ክ ርስቲያኑ ፡ አለቃ ፡ ለርሳቸው ፡ ከውቀት ፡ ስጥወታ ፡ ታላቅ ፡ ክፍልን ፡ ሰጠ ፡ ለክሌሜንቶስና ፡ ለኦሪጌኔስ ፡ የወደደውን ም ፡ በረከት ፡ ሰጠበት ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እርሳቸው ፡ የ ተቀበሉትን ፡ እውቀት ፡ በረቡ ፡ ጊዜ ።

የክሌሜንቶስንም ፡ ትምርት ፡ ኦሪጌኔስ ፡ ደቀ ፡ መዝሙ ሩ ፡ ከርሱ ፡ ይልቅ ፡ አወጣው ። ኦሪጌኔስም ፡ አለ ። እግዚ አብሔር ፡ ቃሉን ፡ ሰጠ ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ። በሃይማኖት ም ፡ ብቻ ፡ ይህነን ፡ ቃል ፡ የሚቀበል ፡ በርሱ ፡ ከኃጢአቱ ፡

ይነጻል ፡ ይድናልም ። በዚህም ፡ ሃይማኖት ፡ ሰው ፡ እግዚ
አብሔርን ፡ ቢለምን ፡ ቃሉንም ፡ ቢመረምር ፡ ያችን ፡ እው
ነተኛዪቱን ፡ ጥበብ ፡ ያገኛል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነገር ፡ የሚ
ታወቅባት ። ስለ ፡ ሃይማኖትም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ። ሃይማ
ኖት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ ባፈችን ፡ ብቻ ፡ መቀበል ፡
ማለት ፡ አይደለም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሃይማኖት ፡ ሕይወት ፡ ነ
ው ። ያመነበት ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ ልባችን ፡ ይገባል ፡ ልባችነን
ም ፡ ወደርሱ ፡ ይለውጣል ፡ በበጎ ፡ ስራችንም ፡ ይገለጻል ።
ዕውቀት ፡ ግን ፡ ማየት ፡ ነው ፡ ከሃይማኖትም ፡ እጅግ ፡ ይ
በልጣል ። ይህነንም ፡ ሲል ፡ ኦሪጌኔስ ፡ ለስሕተት ፡ ቀረበ ፡
የጳውሎስን ፡ ነገር ፡ ፩፡ ቆሮንቶስ ፡ ፫፡ ሲያስተምር ። ኦሪጌ
ኔስም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ እጅግ ፡ መረመረ ፡ ነገር
ም ፡ ከርሱ ፡ አውጥቶ ፡ አስተማረ ፡ እጅግ ፡ መልካም ፡ የ
ነበረ ። ነገር ፡ ግን ፡ ይህነን ፡ ቃል ፡ ሲያበራ ፡ ስሕተት ፡ አል
ቀረም ፡ መጽሐፉ ፡ ቅዱስ ፡ በማስተማር ። ነገሩ ፡ እንዲህ ፡
ነበረ ። መጽሐፉ ፡ ቅዱስ ፡ ሁሉ ፡ ብሉይና ፡ አዲስ ፡ የርሱ
ም ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ ፫፡ ማለት ፡ አለው ። በዚህም ፡ የእግዚአ
ብሔር ፡ ቃል ፡ የሰውን ፡ ባሕሪ ፡ ይመስላል ። ሰውም ፡ በ፫፡
ክፍል ፡ እንዲኖር ፡ በመንፈስ ፡ በነፍስም ፡ በሥጋም ፡ እን
ዲህ ፡ ነው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ደግሞ ። አንድ ፡ ሥጋ
ዊ ፡ ማለት ፡ አለው ፡ የሚያነበው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ማስታዋ
ል ፡ የሚችል ፡ እርሱም ፡ የጽፈት ፡ ማለት ። አንድም ፡ ነ
ፍሳዊ ፡ ማለት ፡ አለው ፡ ምእምናን ፡ ብቻ ፡ የሚያውቁ ፡
በሃይማኖታቸው ፡ ለዚህ ፡ ዓለም ፡ ሰዎችም ፡ የተሰወረ ።
ሶስተኛም ፡ ማለት ፡ መንፈሳዊ ፡ ነው ፡ ላዋቆች ፡ ብቻ ፡
የሚሆን ፡ የሚያስተውሉትም ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ። በዚህ
ም ፡ በኦሪጌኔስ ፡ ትምርት ፡ ደግሞ ፡ እውነትና ፡ ስሕተ
ት ፡ ተደበለቀበት ። ያ ፡ ግን ፡ እውነት ፡ ነው ። የእግዚአብ
ሔር ፡ ቃል ፡ ባሕርን ፡ ይመስላል ፡ ዕውቀት ፡ ሕይወትም ፡
ደህንነትም ፡ የሚመላበት ። ወደርሱም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱ
ስ ፡ ብርሃን ፡ የሚገባ ፡ በልቡም ፡ መግባት ፡ የሚሰጠው ፡
ሁሉ ፡ ደህንነቱ ፡ አይወሰንም ፡ አይጨረስምም ። እርሱ

ን ፡ ግን ፡ የማያውቅ ፡ ልቡ ፡ ባዷ ፡ ነው ፡ ነፍሱም ፡ ትርባለች ፡ ራቡም ፡ ባንዷች ፡ አይቫርም ፡ ለዘላለም ፡ ይሠቅይዋል ፡ እንጂ ፡፡

የክርስቲያን ፡ ትምህርት ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ባሕሪ ፡፡

እግዚአብሔር ፡ እንዷለ ፡ በሰው ፡ ነፍስ ፡ ሁሉ ፡ ተጻፈ ፡፡ እግዚአብሔርም ፡ በሰው ፡ ባሕሪ ፡ ሁሉ ፡ ምስክርን ፡ ሰጠ ፡ ለርሱ ፡ የሚመሰክር ፡፡ ይህነን ፡ ደግሞ ፡ የዚያን ፡ ዘመን ፡ መምህራን ፡ አሉ ፡፡ ደሮ ፡ እግዚአብሔርን ፡ እናውቅ ፡ ዘንድ ፡ አንችልም ፡ እግዚአብሔር ፡ ነፍሱን ፡ ሳይገልጽ ፡ ክሌሜንቶስ ፡ ይላል ፡፡

ቴዎፊሎስም ፡ ያንጾኪያ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡፡ በፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተገለጸ ፡ ይህነን ፡ መግለጽ ፡ ግን ፡ ለመቀበል ፡ የሰው ፡ ልብ ፡ እንዲነጻ ፡ ይፈለጋል ፡፡ ልቡ ፡ ግን ፡ በጨለማ ፡ ቢኖር ፡ እግዚአብሔርን ፡ በፍጥረቱ ፡ አያይም ፡፡

አረማውያን ፡ በጠየቁ ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡፡ አምላካችሁ ፡ ወዴት ፡ ነው ፡ አሳይን ፡ ቴዎፊሎስ ፡ መለሰላቸው ፡፡ አንተ ፡ ሰውነትህን ፡ አሳይኝ ፡ እኔም ፡ አምላኬን ፡ አሳይሃለሁ ፡፡ የነፍስህን ፡ ዓይን ፡ እንዲያይ ፡ አሳይኝ ፡ የልብህም ፡ ጆሮ ፡ እንዲሰማ ፡፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ ዓይን ፡ አለውና ፡ ፀሐይን ፡ ሊያይ ፡ ዕውር ፡ ግን ፡ አያይውም ፡፡ እግዚአብሔርስ ፡ ሁሉን ፡ ፈጠረ ፡ በስራው ፡ ሁሉ ፡ እርሱ ፡ ይታወቅ ፡ ዘንድ ፡ ያልታየች ፡ ነፍስ ፡ እንድታወቅ ፡ ከስራዋ ፡፡ ሕይወትም ፡ ሁሉ ፡ እርሱን ፡ ትገልጻለች ፡ የርሱም ፡ እስትንፋስ ፡ ዓለምን ፡ ሁሉን ፡ ያሐይዋል ፡፡ ያለዚህም ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ ምናምን ፡ ሁኖ ፡ ቢጠፋ ፡ ነበር ፡፡ ሰውም ፡ እርሱን ፡ ሳይገልጽ ፡ መንገር ፡ አይችልም ፡፡ ደሮ ፡ የልብህ ፡ ጨለማ ፡ ብቻ ፡ መክንያት ፡ ነው ፡ ይህነን ፡ መገለጽ ፡ እንዷትይ ፡፡ ስለዚህም ፡ እልሃለሁ ፡፡ ራስህን ፡ የነፍስህንም ፡ ዓይን ፡ ብቻ ፡ መፈወስ ፡ ለሚችል ፡ ለውነተኛ ፡ ባለ ፡ መድኃኒት ፡ ሰጠው ፡ እርሱም ፡ እግዚአብሔር ፡፡

እንደህም ፡ አሉ ፡ የስክንድርያ ፡ ክሌሜንቶስና ፡ ተርቱልያኑስ ፡፡

ክርስቶስም ፡ ይላል ፡፡ እግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ነው ፡፡ የዮሐንስ ፡ ወንጌል ፡ ፬ ፳፬ ፡፡ መንፈስም ፡ ማለት ፡ በሰው ፡ ሕዋሳት ፡ የማይታወቅ ፡ ህላዌ ፡፡ ተርቱልያኑስ ፡ ግን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እጅግ ፡ ረቂቅ ፡ ገላ ፡ እንደለው ፡ የሥጋም ፡ አይደለም ፡ ከኤቴር ፡ እንጅ ፡ ያለ ፡ ይመስለው ፡ ነበር ፡፡ ገላም ፡ ማለት ፡ የባሕሪ ፡ መኖርያና ፡ ልብስ ፡ በስፍራ ፡ የሚኖር ፡፡

ኦሪጌኔስ ፡ ግን ፡ እንደህ ፡ አለ ፡፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ የምንናገር ፡ ሁሉ ፡ ምሳሌ ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ በፍቅር ፡ የተደረገ ፡፡

ኖዋትያኑስም ፡ ይላል ፡፡ የእግዚአብሔርን ፡ ባሕሪ ፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡ ያውቃል ፡ ወደ ፡ ሰው ፡ ልብም ፡ ሁሉ ፡ ይገባል ፡ ይነገር ፡ ዘንድ ፡ ግን ፡ አይቻለውም ፡፡

አሁንም ፡ እግዚአብሔር ፡ ሲል ፡ ሰው ፡ በእግዚአብሔር ፡ መልክና ፡ ምሳሌ ፡ እንደ ፡ ተፈጠረ ፡ እንደህም ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሰው ፡ ምሳሌ ፡ ይናገራል ፡፡ ይህነን ፡ ነገር ፡ ግን ፡ መርቂዮን ፡ አልወደደም ፡ ስለዚህም ፡ ተርቱልያኑስ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ በመጽሐፉ ፡ ተከራከረ ፡፡ ነገራቸውም ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ ነበረ ፡ ስለ ፡ ጽድቅም ፡፡ መርቅዮን ፡ ብልዋልና ፡፡ እግዚአብሔር ፡ አይቈጣም ፡፡ ተርቱልያኑስ ፡ ግን ፡ አሳያው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቸርነት ፡ ከጽድቁ ፡ እንደይለይ ፡ በርሱም ፡ ፍቅርና ፡ ጽል ፡ ጸጋና ፡ ቍጣም ፡ እንደለው ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ግን ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡ እንደይጸላ ፡ ይሰማማል ፡ እንጅ ፡፡

ስለ ፡ ፍጥረት ፡፡

ስለ ፡ ፍጥረትም ፡ የክርስቲያን ፡ መምህራን ፡ አስተማሩ ፡ ቅዱስ ፡ ሐዋርያ ፡ እንሚል ፡ በዕብራውያን ፡ ፲፩፡ ፫፡፡ በሃይማኖት ፡ እናውቃለን ፡ ዓለም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ተፈጠረ ፡ ከማይታየውም ፡ የሚታየው ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡፡ ስለዚህ ፡ ነገርም ፡ ተከራከሩ ፡ ከግኖስቲኮች ፡ ጋራ ፡፡ ግኖስቲኮች ፡ ብለዋልና ፡፡ ዓለም ፡ የተፈጠረበት ፡ ሂሌ ፡ ከዘላለም ፡ ነው ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡፡ እንደችም ፡ ካልነበ

ረ ፡ አንድችም ፡ ባልሆነ ፡፡ በዚች ፡ ሥጋዊት ፡ ጥበባቸው ፡ ላይ ፡ የክርስቲያን ፡ መምህራን ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ ገለጹ ፡ እንደህ ፡ ሲሉ ፡፡ አእምሮ ፡ ሁሉ ፡ የማያስጠልቀው ፡ ነገር ፡ የሰውም ፡ ማሰብ ፡ የማይደርስበት ፡ በሃይማኖት ፡ በልባችን ፡ እንቀበለዋለን ፡ እግዚአብሔር ፡ አንድችን ፡ እንደ ይፈልግ ፡ ምንም ፡ ይፈጥርበት ፡ ዘንድ ፡፡ ከዘላለም ፡ የሚኖርም ፡ እግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ነውና ፡፡ እርሱም ፡ አንድች ፡ ሳይሆን ፡ ዓለምን ፡ ሁሉ ፡ በቃሉ ፡ ፈጠረው ፡፡

አሁንም ፡ ሌላ ፡ ሳች ፡ ተነሣ ፡ እርሱም ፡ ሀርሞጌኔስ ፡ የሚሉት ፡፡ ትምህርቱም ፡ እንደህ ፡ ነበረ ፡፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ አንድች ፡ ካልሆነ ፡ ምንም ፡ ክፉ ፡ ባይነሣ ፡፡ ፍጥረትም ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ በጎ ፡ በሆነ ፡፡ ባለምም ፡ ያለ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አይደለም ፡ ከፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ በፊት ፡ ከሚሆን ፡ ከማቴርያ ፡ እንጀ ፡፡

ኢሬኔዎስና ፡ ተርቱልያኑስም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ተከራከሩ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ሲያውጡበቅ ፡ ያለ ፡ ሌላ ፡ ፊሎሶፊያ ፡፡

ኦሪጌኔስ ፡ ግን ፡ ከዚያ ፡ ይልቅ ፡ አሰበ ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስም ፡ አልኖረም ፡፡ እርሱም ፡ እንደህ ፡ አለ ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ከቶ ፡ ዝምብሎ ፡ ሳይሰራ ፡ አልኖረም ፡፡ ይህ ፡ ዓለምም ፡ በጊዜው ፡ ተፈጠረ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ እንደለ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከዚህ ፡ ዓለም ፡ አስቀድሞ ፡ ሌላ ፡ ፍጥረትም ፡ ነበረ ፡፡ እግዚአብሔርም ፡ ከዘላለም ፡ ልጁን ፡ እንደ ፡ ወለደ ፡ እንደሁም ፡ ወትሮ ፡ በልጁ ፡ ይገለጽ ፡ ነበረ ፡፡

በዚህ ፡ ነገርም ፡ ሜቶዲዩስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ከኦሪጌኔስ ፡ ጋራ ፡ ተጻላ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የኦሪጌኔስን ፡ ነገር ፡ አላስተዋለምና ፡ አላሸነፈበትምም ፡፡

ስለ ፡ ሥላሴ ፡፡

በዚያ ፡ ዘመንም ፡ የሥላሴ ፡ ትምህርት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገና ፡ አልበሰለም ፡ አልተፈጸመምም ፡ መሠረቱ ፡ ግን ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጸና ፡፡ በቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ መ

ምህሬን ፡ ታወቀ ፡፡ ይህ ፡ ትምህርትም ፡ ከመድኀኒታችን ፡ ትምህርት ፡ ጋራ ፡ ተሰማማ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሰው ፡ ፈጣሪያ ፡ ማደን ፡ ቀደሸም ፡፡ እርሱም ፡ አብና ፡ ልጅ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡፡ የሃይማኖትም ፡ ትምህርት ፡ በዚህ ፡ መሠረት ፡ ላይ ፡ ተሰራ ፡፡ ደሮ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ የዚህ ፡ ነገር ፡ እውነት ፡ ከስሕተት ፡ ጋራ ፡ ሊጋደል ፡ ነበረ ፡፡ መምህራንም ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ አልነበረበትም ፡፡

የዚች ፡ ትምርት ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ መለኮት ፡ ነበረ ፡፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ጋራ ፡ እንደሆነ ፡፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስም ፡ ልጅ ፡ ቃል ፡ ተባለ ፡ ማለቱም ፡ ይህ ፡ ነው ፡፡ ሰው ፡ ሲናገር ፡ ያልታየች ፡ ነፍሱ ፡ በቃሉ ፡ እንድትገለጽ ፡ እንደሁም ፡ ያልታየ ፡ አምላክ ፡ በክርስቶስ ፡ ይገለጻል ፡፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃልም ፡ ባይሁድና ፡ ባረማውያን ፡ ዘንድ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ትምህርት ፡ ነበረ ፡፡ የክርስቲያንም ፡ መምህራን ፡ ከርሳቸው ፡ አንዳንድ ፡ ነገር ፡ ሲቀበሉ ፡ ከሃይማኖት ፡ ነገርም ፡ ጋራ ፡ ሲደበልቁት ፡ የሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ ተጕደችበት ፡፡

አሁንም ፡ መናፈቃን ፡ ተነሡ ፡ የሥላሴን ፡ ትምህርት ፡ የካዱ ፡፡ አንድም ፡ ጵራክስያስ ፡ የሚሉት ፡ ሰማዕት ፡ ነበረ ፡ አስቀድሞ ፡ በማርቀስ ፡ አውሬልዩስ ፡ ዘመን ፡ መከራ ፡ የተቀበለ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡፡ እርሱም ፡ መናፈቅ ፡ ሆነ ፡ እንደህ ፡ ሲል ፡፡ ክርስቶስ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ዘንድ ፡ አይለይም ፡ እርሱም ፡ አብ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡፡ ስለ ፡ ሰውነቱ ፡ ብቻ ፡ ልጅ ፡ ይባላል ፡፡ የተወለደም ፡ መከራም ፡ የተቀበለ ፡ የተሰቀለም ፡ የሞተም ፡ አብ ፡ ነው ፡፡ እንደ ፡ ጵራክስያስም ፡ ኖኤቱስ ፡ ከስሚርና ፡ ደግሞ ፡ አስተማረ ፡፡ እርሳቸውም ፡ እንደህ ፡ ሲሉ ፡ ክርስቶስን ፡ ከአብ ፡ ጋራ ፡ ሊያስተካክሉት ፡ ሊያከብሩትም ፡ መሰላቸው ፡፡

ከለዚህ ፡ የከፋ ፡ ግን ፡ ቴዎዶቱስና ፡ አርቴሞን ፡ ነበሩ ፡ እንደህ ፡ ያሉ ፡፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አምላክ ፡ አይደለም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ኀይል ፡ ብቻ ፡ በርሱ ፡ በረታች ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ ይልቅ ፡ በሌላ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ከሰው ፡ ሁሉ ፡ አይለይም ፡፡

እንደህም ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ነበረ ፡ አሎጎች ፡ የተባሉ ፡ ማለት ፡ ቃል ፡ የሌላቸው ። የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ የክርስቶስን ፡ የመለኮቱን ፡ ትምህርት ፡ ክደውታልና ። እርሳቸውም ፡ የዮሐንስን ፡ ወንጌል ፡ አልተቀበሉም ፡ ስለ ፡ ቃል ፡ ትናገራለችና ።

ደግሞም ፡ ጳውሎስ ፡ ከሳሞሰታ ፡ የዚህ ፡ ወገን ፡ ሰው ፡ ነበረ ። እርሱም ፡ ባመት ፡ ፪፻፷ ፡ የሚያህል ፡ ያንጾኪያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ነበረ ። እርሱም ፡ የጼኖቢያ ፡ የጳልሚራ ፡ ንግሥት ፡ ወዳጅ ፡ ነበረ ፡ ያለምን ፡ ክብርና ፡ መርዓት ፡ ከክርስቶስ ፡ ፍቅር ፡ ይልቅ ፡ ወደደ ፡ ክርስቶስም ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ አይበልጥም ፡ አለ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ እንጂ ፡ በርሱ ፡ ከሌላ ፡ ሰው ፡ ይልቅ ፡ የበረታች ።

ባንደኛትም ፡ ባመት ፡ ፪፻፷፬ ፡ በንጾኪያ ፡ በተሰበሰበች ፡ ሲኖደስ ፡ ቄስ ፡ መልኪዮን ፡ የጳውሎስን ፡ ስሕተት ፡ ገለጸ ። እርሱ ፡ ግን ፡ አልተሻረም ። ጼኖቢያ ፡ ወዳዋለችና ። አውሬልያኑስ ፡ ቄሣር ፡ ግን ፡ ባሸነፈት ፡ ጊዜ ፡ ሻረው ።

ቤርሎስም ፡ የቦስራ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ናፈቀ ፡ እንደህ ፡ ሲል ። የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ አልተወለደም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ባሕሪ ፡ ዘንድ ፡ ብልጭልጭ ፡ ሳይፈስ ፡ ወደ ፡ ሰው ፡ ገላ ። ባመት ፡ ፪፻፵፬ ፡ ሲኖደስ ፡ ስለርሱ ፡ ተሰበሰበች ፡ በቄሣርያ ፡ ከዚያም ፡ ኦሪጌኔስ ፡ ከቤሮሎስ ፡ ጋራ ፡ ሲመጉት ፡ ቤርሎስ ፡ አዝኖ ፡ ወደ ፡ ሃይማኖት ፡ ተመለሰ ።

እንደህም ፡ ሳቤልዩስ ፡ ባፍሪቃ ፡ የነበረ ፡ ባመት ፡ ፪፻፶ ፡ የሚያህል ። የርሱም ፡ ትምርት ፡ ስለ ፡ ሥላሴ ፡ እንደህ ፡ ነበር ። አብና ፡ ልጅ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ አንድ ፡ ባሕሪ ፡ ናቸው ፡ አንድ ፡ አካልም ። ነገር ፡ ግን ፡ ያ ፡ ፩ ፡ አምላክ ፡ በ፫ ፡ መልክ ፡ ተገለጸ ፡ በፍጥረት ፡ በመድኃኒትም ፡ በመቀደስም ፡ ፀሐይ ፡ ደግሞ ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ በ፫ም ፡ እንደ ፡ ገለጽ ፡ በፀሐይ ፡ ባሕሪ ፡ በመልኩም ፡ በኃይሉም ።

ከለዚህ ፡ መናፍቃን ፡ ትምህርትም ፡ የክርስቲያን ፡ ትምህርት ፡ ተለየች ። አንድ ፡ ያልታየ ፡ የማይታደም ፡ አምላ

ክ ፡ ነው ፡ አሉ ፡፡ እርሱም ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡፡ ከር ሱም ፡ ከዘላለም ፡ ተወለደ ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ሳይፈጠር ፡ የ እግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ባሕርዩውም ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ከእ ግዚአብሔር ፡ አብ ፡ ጋራ ፡ አካሉ ፡ ግን ፡ ለብቻው ፡ ነው ፡፡ በርሱም ፡ የማይታይ ፡ አምላክ ፡ ይገለጻል ፡ በርሱም ፡ ፍጥ ረት ፡ ሁሉ ፡ ተፈጠረ ፡፡ ስለዚህም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ይባላል ፡ ለዘላለምም ፡ ይኖራል ፡፡

በዚህ ፡ ነገርም ፡ አብያት ፡ ክርስቲያናት ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ነበሩ ፡፡ ታናሽ ፡ መለየት ፡ ግን ፡ አልቀረም ፡ በምሥራቅና ፡ በምዕራብ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መኻከል ፡፡

በምስራቅ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትም ፡ መኻከል ፡ የኦሪ ጌኔስ ፡ ትምርት ፡ እጅግ ፡ ተዘረጋች ፡፡ እግዚአብሔር ፡ በዳ ዊት ፡ አፍ ፡ ሲል ፡፡ አንተ ፡ ልጄ ፡ ነህ ፡ ዛሬ ፡ ወለድሁህ ፡፡ ኦሪጌኔስ ፡ ይህ ፡ ዛሬ ፡ ያለ ፡ ጊዜ ፡ ያለ ፡ ዘመንም ፡ ነው ፡ ከ ዘላለም ፡ አለ ፡፡ ደግሞ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ከአብ ፡ ባ ሕሪ ፡ እንደ ፡ ተወለደ ፡ አላለም ፡ ያምላክ ፡ ባሕሪ ፡ እንዲ ደከፈል ፡ ብሎ ፡፡ አብንና ፡ ልጅን ፡ አላስተካከለም ፡ እር ሱ ፡ በርሳቸው ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ ልጅና ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ከፍ ፡ እንዲሉ ፡ እንዲሁም ፡ አብ ፡ ከ ፍ ፡ ይላል ፡ ከርሳቸው ፡፡ ስለዚህም ፡ ኦሪጌኔስ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡፡ ወደ ፡ ልጅ ፡ እንጸልይ ፡ ዘንድ ፡ አይገባነም ፡ ወደ አብ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በልጁ ፡ በየሱስ ፡ ክርስቶ ስ ፡ ስም ፡፡

ተርቱልያኑስ ፡ ግን ፡ መለየት ፡ አላደረገም ፡ ባካል ፡ እን ጂ ፡ በባሕሪ ፡ ቍጥር ፡ ሁላቸው ፡ አንድ ፡ ናቸው ፡ አለ ፡፡ ደ ሮ ፡ ልጅ ፡ ከአብ ፡ በታች ፡ ነው ፡ አለ ፡፡ እንዲህም ፡ የምዕ ራብ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡፡

ባንጾኪያም ፡ ባመት ፡ ፪፻፷፱፤ በተሰበሰበች ፡ ሲኖደስ ፡ የ ሳቤልዩስን ፡ ስሕተት ፡ ሲረግሙ ፡ አንድ ፡ ነገርንም ፡ ረገ ሙ ፡ ደግሞ ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ የተቀበሉ ፡ ቢኒቂያ ፡ እርሱ ም ፡ ሆሞውስዮን ፡ ማለቱ ፡ በባሕሪ ፡ አንድ ፡ የሚሆን ፡፡ ያንድ ፡ ባሕሪ ፡ እንዲሆን ፡ ልጅ ፡ ከአብ ፡ ጋራ ፡፡ እንዲህ ም ፡ የሲኖደስ ፡ የሰውም ፡ ቃል ፡ ሁሉ ፡ ይለወጣል ፡ የተ

ፈጸመ ፡ ነገር ፡ የለምና ፡ ከሰማይ ፡ በታች ፡ ከእግዚአብሔ ር ፡ ነገር ፡ በቀር ፡፡

እንደሁም ፡ ዲዮናስዮስ ፡ የስክንድርያ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ የኦሪጌኔስ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ የነበረ ፡ በሳቤልያኖች ፡ ላይ ፡ ሲጽፍ ፡ ሆሞውስዮንን ፡ ረገመ ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ የሮም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ዲዮናስዮስ ፡ በጽፈቱ ፡ ስለዚህ ፡ ገሠጸው ፡፡ የስክንድርያም ፡ ዲዮናስዮስ ፡ የነገረን ፡ ማለ ት ፡ ለወንድሙ ፡ ለሮም ፡ ዲዮናስዮስ ፡ ከፈተለት ፡ በትሕ ትናም ፡ በፍቅርም ፡ ይህነን ፡ ነገርን ፡ ትቶ ፡ ዕርቅ ፡ ጸና ፡፡

ስለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ግን ፡ ትምርታቸው ፡ ገና ፡ አል በሰለችም ፡፡ እርሳቸውም ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስጥወታ ፡ ታላቅ ፡ ክፍል ፡ የተቀበሉ ፡ በልባቸው ፡፡ ዩስቲኑስ ፡ ሰማዕ ትም ፡ አለ ፡፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ መልአ ክ ፡ ነው ፡ ከየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ የተላከ ፡ የእግዚአብሔ ር ፡ ኃይል ፡ ከክፉ ፡ መንፈስ ፡ ምእምናንን ፡ የሚጠብቅ ፡፡ ኦሪጌኔስም ፡ ይላል ፡፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የጸጋ ፡ ስጥወታ ፡ ሁሉ ፡ ምንጭ ፡ ነው ፡ መጀመርያም ፡ ባሕሪ ፡ ከእግዚአብ ሔር ፡ አብ ፡ በልጁ ፡ የተወለደ ፡፡

ስለ ፡ ሰው ፡ ጠባይዕ ፡፡

ይህችም ፡ ትምርት ፡ ከመናፍስት ፡ ትምህርት ፡ ጋራ ፡ ት ገጠማለች ፡፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ብልዋልና ፡ የዚያ ፡ ዘመን ም ፡ መምህራን ፡ ተቀበሉት ፡ ፪፡ ወገን ፡ መናፍስት ፡ እንደ ሉ ፡ በጎችና ፡ ክፎች ፡ እርሳቸውም ፡ መላእክትና ፡ ሰይጣ ናት ፡፡ በጎ ፡ ሰዎችም ፡ አንድነት ፡ እንዳላቸው ፡ ከመላእ ክት ፡ ጋራ ፡ ክፎችም ፡ አንድነት ፡ እንዳላቸው ፡ ከሰይጣ ናት ፡ ጋራ ፡፡ በሰይጣንም ፡ ማሳት ፡ ኃጢአትና ፡ ሞት ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ እንደ ፡ ገባ ፡፡

በዚህ ፡ ነገርም ፡ በትምህርት ፡ ስለ ፡ ክፉ ፡ ተከራከሩ ፡ ከ ግኖስቲኮች ፡ ጋራ ፡፡ ግኖስቲኮች ፡ ክፉ ፡ ሁሉ ፡ በግድ ፡ ከማ ቴርያ ፡ ከሂሌም ፡ መጣ ፡ ብለዋልና ፡፡ የክርስቲያን ፡ መም ህራን ፡ ግን ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ትምህርት ፡ ሊያስቱም

ሩ ፡ ነበሩ ፡ ክፉ ፡ ሁሉ ፡ እንደልመጣ ፡ ፍቃድ ፡ ባላቸው ፡ ፍጥረቶች ፡ በፈቃዳቸው ፡ እንጅ ፡፡

ተርቱልያኑስም ፡ አለ ፡፡ አደም ፡ በተፈጠረ ፡ ጊዜ ፡ ኃይል ፡ ሁሉ ፡ ነበረለት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ምሳሌ ፡ በመንፈሱ ፡ ይገልጽ ፡ ዘንድ ፡፡ ይህ ፡ ኃይል ፡ ግን ፡ አልተገለጸም ፡፡ በፈቃዱ ፡ ሊገልጸው ፡ ነበረ ፡ እንጅ ፡፡ የእግዚአብሔርም ፡ ስራ ፡ በሰው ፡ ልብ ፡ ስለ ፡ ንጽሕናው ፡ ገና ፡ ባንደች ፡ አልተከለከለም ፡፡ በእግዚአብሔር ፡ አንድነትም ፡ ከኖረ ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ምሳሌ ፡ በጠባዩ ፡ ከሰራ ፡ ባልሞተ ፡ ወደ ፡ ዘላለም ፡ ሕይወት ፡ ደህንነት ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ መላችባት ፡ በደረሰ ፡፡ መጀመርያውም ፡ ኃጢአቱ ፡ ይህ ፡ ነበረ ፡ ሰው ፡ ፈቃዱን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ በታች ፡ እንደላደረገ ፡ በላዩው ፡ እንጅ ፡ በዚህ ፡ ኃጢአትም ፡ ሰው ፡ ከኃጢአትና ፡ ከጥፋት ፡ መግዛት ፡ በታች ፡ ተገዛ ፡፡ ኃጢአትም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሰው ፡ ጠባይዕ ፡ ከገባ ፡ በኋላ ፡ ጠባዩን ፡ ሁሉን ፡ አረከሰ ፡ መለየትም ፡ አደረገበት ፡ በእግዚአብሔር ፡ አንድነት ፡ ፈንታ ፡፡ ከእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ጋራ ፡ የነበረች ፡ ከሰይጣን ፡ ጋራ ፡ አንድነት ፡ ሆነችለት ፡፡ የሰውም ፡ ሁሉ ፡ አባት ፡ ኃጢአቱን ፡ አሳልፎ ፡ ለትውልዱ ፡ ሁሉ ፡ አስቀረው ፡፡ የአደም ፡ ነፍስ ፡ የሰው ፡ ሁሉ ፡ ምንጭ ፡ ነበረችና ፡ የሰው ፡ ነፍስ ፡ ሁሉ ፡ በዘር ፡ መጠን ፡ ባደም ፡ ኑራለችና ፡፡ በዚህም ፡ ኃጢአት ፡ በጉነት ፡ ሁሉ ፡ በጣም ፡ አልጠፋም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስራ ፡ ነውና ፡ ተጨለመ ፡ እንጅ ፡፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድም ፡ የሚሆን ፡ አይጠፋም ፡ ይጨለማል ፡ እንጅ ፡ መጨለም ፡ ይችላልና ፡ እግዚአብሔር ፡ አይደለምና ፡፡ መጥፋት ፡ ግን ፡ አይቻለም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ነውና ፡፡ እግዚአብሔርም ፡ ብቻ ፡ ያለ ፡ ኃጢአት ፡ ነው ፡ ክርስቶስም ፡ በሰውነቱም ፡ ያለ ፡ ኃጢአት ፡ ነው ፡፡ ክርስቶስ ፡ ደግሞ ፡ አምላክ ፡ ነውና ፡፡ ስለዚህም ፡ የሰው ፡ ነፍስ ፡ ሁሉ ፡ ያለ ፡ ዕዳ ፡ አይደለችም ፡ ሁሉ ፡ ያለ ፡ በጎ ፡ ዘር ፡ አይደለችምና ፡፡ ደግሞ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ የሰው ፡ የከፋውን ፡ ጠባዩን ፡ መልወጥ ፡ ይችላል ፡፡

የስክንድርያም ፡ ክሌሚንቶስ ፡ እንደዚህ ፡ አለ ፡፡ ሰው ፡ በ

ፈቃዱ ፡ በኃይሉም ፡ ብቻ ፡ ኃጢአትን ፡ ማሸነፍ ፡ አይችል ም ። በልቡ ፡ ሁሉ ፡ ግን ፡ ቢጋደል ፡ እግዚአብሔር ፡ ኃይሉ ን ፡ ይሰጠዋል ፡ በርሱም ፡ ያሸንፋል ።

ኦሪጌኔስም ፡ ኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ ከፍጥረት ፡ መለየት ፡ እን ደ ፡ ተነሣ ፡ መሰለው ። ፍጡራንም ፡ ሁሉ ፡ በመጀመርያ ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ በኋላም ፡ እንደ ፡ ተለዩ ፡ እርሱ ፡ በር ሳቸው ፡ ሁሉም ፡ ብቸኝነቱን ፡ ፈለገ ። አሁንም ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ በጎ ፡ ነበረ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ አይደለ ም ። እግዚአብሔርም ፡ ብቻ ፡ በራሱ ፡ በጎ ፡ ነው ፡ ፍጥረት ፡ ግን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ በጎ ፡ ነው ። መኖሩ ፡ ሁሉ ፡ ከ እግዚአብሔር ፡ ነውና ። ለብቻውም ፡ መኖር ፡ ለራሱም ፡ መኖር ፡ በፈለገ ፡ ጊዜ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተለየ ፡ ኃጢአት ም ፡ ተነሣ ። አሁንም ፡ የእግዚአብሔር ፡ የጥበቡና ፡ የኃይ ሉ ፡ ሥራ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ መለየትን ፡ ኃጢአትንም ፡ ጥፋትን ም ፡ ሁሉን ፡ ይሽር ፡ ዘንድ ። ኦሪጌኔስም ፡ እንደዚህ ፡ አለ ። በወደቀ ፡ ሰው ፡ በጠበዩ ፡ ፫፤ ጠባያት ፡ ናቸው ። የመንፈ ስ ፡ የነፍስም ፡ የሥጋም ። ከእግዚአብሔር ፡ የወጣ ፡ መን ፈሳዊ ፡ ነው ። ከዚህ ፡ ዓለም ፡ ሕይወትም ፡ የወጣ ፡ ነፍሳ ዊ ፡ ነው ። ከሥጋም ፡ የሚወጣ ፡ ሥጋዊ ፡ ነው ። እሌህ ፡ ፫ም ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ይገኛሉ ፡ ባንድም ፡ አንድ ፡ በሌላም ፡ ሌላ ፡ ከርሳቸው ፡ ይገዛል ።

ስለ ፡ ሰው ፡ ማደን ።

በዚያ ፡ ዘመንም ፡ ከግኖስቲኮች ፡ ጋራ ፡ በመከራከር ፡ አ ንደንድ ፡ ብርሃን ፡ አገኙ ፡ በዚች ፡ ትምርት ፡ ደግሞ ። ከለ ዚያ ፡ ግኖስቲኮች ፡ ጋራም ፡ ሲከራከሩ ፡ የክርስቶስ ፡ ገላ ፡ የሥጋ ፡ ገላ ፡ አልነበረም ፡ የኤቴር ፡ እንጅ ፡ ወይስ ፡ የሥ ጋ ፡ ገላ ፡ ምሳሌ ፡ ብቻ ፡ ያሉ ፡ ወይስ ፡ ክርስቶስ ፡ በመላኮ ቱ ፡ ብቻ ፡ አደነነ ፡ በሰውነቱ ፡ አይደለም ፡ ብለው ። እር ሳቸው ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ትምህርት ፡ ስለ ፡ ሰውነቱ ፡ እውነት ፡ አጸኑባቸው ።

ኢግናትዩስም ፡ ግኖስቲኮችን ፡ እንደዚህ ፡ አለ ። የላን ት ፡ ክርስቶስ ፡ መትሐት ፡ ነው ። ተርቱልያኑስም ፡ ደቂ

ቶችን ፡ አላቸው ፡፡ ምነው ፡ ክርስቶስን ፡ እኩል ፡ አሰትን ፡ ታድርጉታላችሁ ፡፡ እርሱስ ፡ በጣም ፡ እውነት ፡ ነበረ ፡፡

የዚያን ፡ ዘመንም ፡ ክርስቲያን ፡ ክርስቶስ ፡ በገላው ፡ ያልተዋበ ፡ መሰላቸው ፡፡ ክርስቶስ ፡ በባርያ ፡ መልክ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ጳውሎስ ፡ እንዲል ፡ ፊልጵስዩስ ፡ ፪፡፡

የስክንድርያ ፡ ክሌሜንቶስ ፡ ግን ፡ ክርስቶስ ፡ በውነት ፡ ያልታመመ ፡ በጠባዩ ፡ በፈቃዱ ፡ ብቻ ፡ ሕማምን ፡ የተቀበለ ፡ መሰለው ፡፡

ኢሬኔዎስም ፡ እንደዚህ ፡ አለ ፡፡ በክርስቶስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ የሰውን ፡ ገላ ፡ ብቻ ፡ ተቀበለ ፡ የሰውን ፡ ነፍስ ፡ አይደለም ፡ በነፍስም ፡ ስፍራ ፡ መለኮቱ ፡ ሆነ ፡፡

ዩስቲኑስ ፡ ሰማዕትም ፡ ሰውን ፡ በ፫፡ ክፍል ፡ ክፍሎት ፡ ሥጋ ፡ ነፍስም ፡ መንፈስም ፡ የክርስቶስ ፡ ነፍስና ፡ ሥጋ ፡ የሰው ፡ ጠባይዕ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ አለ ፡ በመንፈሱም ፡ ፈንታ ፡ ቃል ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡፡

ተርቱልያኑስ ፡ ግን ፡ እንደዚህ ፡ አለ ፡፡ ክርስቶስ ፡ የሰውነታችንን ፡ ጠባይዕ ፡ ሁሉ ፡ ከኃጢአት ፡ በቀር ፡ ተቀበለ ፡ እንዲሁም ፡ ቃል ፡ ፈጽሞ ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡፡ ሰውም ፡ በ፪፡ ክፍል ፡ ብቻ ፡ ይኖራል ፡ በገላና ፡ በነፍስ ፡፡

የኦሪጌኔስ ፡ ትምህርትም ፡ ስለዚህ ፡ የተርቱልያኑስን ፡ ትምህርት ፡ መሰለ ፡፡ እርሱ ፡ ግን ፡ ሰውን ፡ በ፫፡ ክፍሎት ፡ ክርስቶስ ፡ ይህነን ፡ ሁሉን ፡ ከጠባያችን ፡ እንደ ፡ ተቀበለ ፡ ብልዋል ፡፡ ሌላ ፡ ትምርት ፡ ግን ፡ ለዚህ ፡ አዋቂ ፡ ነበረ ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጋራ ፡ ያልተሰማማ ፡፡

ስለ ፡ መድኃኒት ፡፡

ኢሬኔዎስም ፡ እንደዚህ ፡ ይላል ፡፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ አብን ፡ ይገልጽልን ፡ ዘንድ ፡ ቻለው ፡ እኛም ፡ ባልተማርን ፡ እርሱ ፡ ባለቤቱ ፡ መምህር ፡ ሁኖ ፡ ካልመጣልን ፡፡ ሰው ፡ ሊለምድ ፡ ነበረ ፡ እግዚአብሔርን ፡ በልቡ ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ሊለመድ ፡ ነበረ ፡ በሰው ፡ ማኸል ፡ ያድር ፡ ዘንድ ፡፡ በሁለታቸውም ፡ መኻከል ፡ ለመጣ ፡ መኻከለኛ ፡ የሁለታቸው ፡ ዘመድ ፡ ይሆን ፡ ዘን

ድ ፡ ተገባለት ፡ በሁለታቸው ፡ መኻከል ፡ አንድነትን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡፡ በዕድሜም ፡ ሁሉ ፡ ሊያልፍ ፡ ነበረ ፡ ዕድሜን ፡ ሁሉን ፡ ሊቀድስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ምሳሌ ፡ እርስዋ ፡ ፍጽምት ፡ ቅድስና ፡ የምትሆን ፡፡ በሰውም ፡ ጠባይዕ ፡ ሁኖ ፡ የኃጢአተኛውን ፡ ጠባይዕ ፡ የመሰለ ፡ በኃጢአት ፡ ላይ ፡ ፈረደ ፡፡ ሰውን ፡ ግን ፡ ይመስለው ፡ ዘንድ ፡ አዘዘው ፡፡ የሰው ፡ ወገን ፡ ግን ፡ የሰይጣን ፡ እሥሮች ፡ ነበሩ ፡ ክርስቶስም ፡ ቤዛ ፡ ሁኖ ፡ በሥሮች ፡ ፈንታ ፡ ተለወጠ ፡፡ ክፉ ፡ በላያችን ፡ ገዛ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ገንዘብ ፡ የነበርነ ፡፡ እግዚአብሔርም ፡ በግድ ፡ አላደነነም ፡ በቅን ፡ እንጂ ፡፡ ግንዘቡን ፡ በተበዣ ፡ ጊዜ ፡፡ ሰው ፡ ሁኖ ፡ የሰውን ፡ ጸላት ፡ ካላሸነፈ ፡ ጸላትም ፡ በቅን ፡ ባልተሸነፈ ፡፡ አምላክም ፡ ሁኖ ፡ መድኃኒትን ፡ ካልሰጠነ ፡ ይህ ፡ መድኃኒት ፡ ባልጸናልነ ፡፡

ዩስቲኑስ ፡ ሰማዕትም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡፡ ሕግ ፡ ሰውን ፡ ሁሉን ፡ ረገመች ፡፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ አልቻለምና ፡ በጣም ፡ ይፈጽማት ፡ ዘንድ ፡፡ ክርስቶስ ፡ ግን ፡ ይህነን ፡ መርገም ፡ በኛ ፡ ፈንታ ፡ ተሸክሞት ፡ ከኛ ፡ ዘንድ ፡ አስወገደው ፡፡

ባንድ ፡ መልእክትም ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ለዲዮግኔት ፡ የተጻፈ ፡ እጅግ ፡ መልካም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ ጻፊው ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ያለም ፡ ሁሉ ፡ ጌታና ፡ ፈጣሪ ፡ ሰውን ፡ በመውደድ ፡ ይመላል ፡ በትዕግሥትም ፡፡ እንዲህ ፡ ነበረ ፡ እንዲህም ፡ ነው ፡ እንዲህም ፡ ይሆናል ፡ ለዘላለም ፡ እርሱ ፡ ቻር ፡ የማይቈጣም ፡ እርሱም ፡ ብቻው ፡ በጎ ፡ የሚሆን ፡፡ እርሱም ፡ ታላቁን ፡ የማይናገርም ፡ ምክርን ፡ ተማከረ ፡ ለልጁም ፡ ብቻ ፡ አስታወቀው ፡፡ ይህ ፡ ምክርም ፡ በርሱ ፡ በተሰወረበት ፡ ጊዜ ፡ እርሱ ፡ እኛን ፡ እንዲያስብልን ፡ ይመስል ፡ ነበረ ፡፡ ባለፈ ፡ ዘመንም ፡ እንደ ፡ ፈቃዳችን ፡ ተወነ ፡ መመኛታችነን ፡ እንከተል ፡ ዘንድ ፡፡ ይህም ፡ በኃጢአታችን ፡ ደስ ፡ እንዲል ፡ አይደለም ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ተገልጸናልና ፡ ሕይወታችን ፡ እንዲደገባነ ፡ ስለ ፡ ምግባራችን ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ እንዲገባነ ፡፡ ድካማችነንም ፡ አለመቻላችነንም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ለመግባት ፡ ከገለጽነ ፡ በኋላ ፡ በእግዚአብሔር ፡

ኃይል ፡ እንድንችለው ፡፡ የኃጢአታችን ፡ ሚዛን ፡ ግን ፡ በ
መላ ፡ ጊዜ ፡ ፈጽሞም ፡ በተገለጸ ፡ ጊዜ ፡ ሥቃይና ፡ ሞት ፡
ደመወዜያችን ፡ ሁኖ ፡ እንዲጠብቀን ፡ እርሱ ፡ አልጸላነ
ም ፡ አላወጣነምም ፡ ታገሠ ፡ እንጂ ፡፡ እርሱ ፡ ባለቤቱ ፡ ኃ
ጢአታችንን ፡ በላየው ፡ ወስዷ ፡ እርሱም ፡ ባለቤቱ ፡ አንድ ፡
ልጁን ፡ በፈንታችን ፡ ቤዛ ፡ አድርጎት ፡ ለወጠው ፡ እርሱን ፡
ቅዱሱን ፡ በኃጢአት ፡ ፈንታ ፡፡ ምንድር ፡ ነበረና ፡ ሌላ ፡ ኃ
ጢአታችንን ፡ መሸፈን ፡ የቻለው ፡ ከጽድቁ ፡ በቀር ፡፡

ለለዚያም ፡ ክርስቲያን ፡ መደንና ፡ መቀደስ ፡ የተሰ
ማማ ፡ ነበረ ፡፡ ክርስቶስ ፡ ንጉሥ ፡ ሁኖ ፡ ተቈጠረ ፡ የሰይ
ጣንን ፡ መንግሥት ፡ ያፈረሰ ፡ የተማረኩትንም ፡ አርነት ፡
ያወጣቸው ፡፡ እንዲሁም ፡ የሰይጣን ፡ ወታደር ፡ በፊት ፡ የ
ነበረ ፡ አሁን ፡ የክርስቶስ ፡ ወታደርና ፡ ካህናት ፡ ሆኑ ፡፡

የሮም ፡ ክሌሜንቶስ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡፡ ምንድር ፡ እን
ኪያ ፡ ልናድርግ ፡ ወንድሞቼ ፡ ሆይ ፡፡ ልንታክትን ፡ በበጐነ
ት ፡ ፍቅርንም ፡ ልንተውን ፡፡ ይህ ፡ እግዚአብሔር ፡ አይተ
ው ፡ ከቶ ፡ ይሆንብን ፡ ዘንድ ፡፡ በማይታክት ፡ ልብ ፡ በሚቃ
ጠልም ፡ መንፈስ ፡ በጎ ፡ ነገርን ፡ ሁሉን ፡ እናድርግ ፡ ዘንድ ፡
ልንጋደል ፡ እንጂ ፡፡ የሁሉ ፡ ፈጣሪና ፡ ጌታ ፡ በስራው ፡ ደስ ፡
ይላልና ፡፡

የዲዮግኔትም ፡ መልእክት ፡ ጻፊ ፡ እንደህ ፡ ይላል ፡፡ ም
ን ፡ ያህል ፡ ደስ ፡ ትላለህ ፡ ይህነን ፡ መድኃኒትህን ፡ ብታው
ቅ ፡ እንዴትም ፡ እጅግ ፡ ትወደዋለህ ፡ እርሱን ፡ አስቀድሞ ፡
እጅግ ፡ ብርቱ ፡ የወደደህ ፡፡

ደህም ፡ ሁሉ ፡ በሃይማኖት ፡ እንዲሆን ፡ ኢሬኔዎስ ፡
አስተማረ ፡፡

ስለ ፡ ፈጻሚ ፡፡

በዚህ ፡ ዘመንም ፡ ብዙ ፡ ክርስቲያናት ፡ ተስፋ ፡ አደረጉ ፡
ዓለም ፡ ፯፤ ሺህ ፡ አመት ፡ ከኖረ ፡ በኋላ ፡ ክርስቶስ ፤ እን
ዲመጣ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ሰንበት ፡ ማለት ፡ የረፍ
ት ፡ ዘመን ፡ እንዲሰጥ ፡ ዓለምም ፡ ሁሉ ፡ የክርስቶስ ፡ ሃይ
ማኖትና ፡ ምስጋና ፡ እንዲመላበት ፡፡ ይህነን ፡ ካመኑት ፡ ክ

ርስቲያን ፡ ጳጵያስ ፡ ኢሬኔዎስም ፡ ዩስቲኑስ ፡ ሰማዕትም ፡ ኔጶስም ፡ ነበሩ ፡፡ የስክንድርያ ፡ የሮምም ፡ መምህራን ፡ ግን ፡ አልተቀበሉትም ፡፡

ስለ ፡ ትንሣኤ ም ፡ አስተምረው ፡ ካግኖስቲኮች ፡ ጋራ ፡ በመጋደል ፡ ጸኑ ፡፡ ግኖስቲኮችም ፡ ማቴርያን ፡ ሁሉን ፡ ያጠፉ ፡ ዘንድ ፡ ነበሩ ፡ ስለዚህም ፡ የክርስቲያን ፡ መምህራን ፡ አሳይዋቸው ፡፡ ክርስቶስ ፡ የምእምናንን ፡ ሥጋ ፡ ይጠፈ ፡ ዘንድ ፡ እንደይተወው ፡ ያስነሣዋል ፡ እንጀ ፡ ይለውጠውማል ፡ ለተመሰገነ ፡ ገላው ፡ ይመስል ፡ ዘንድ ፡፡

፫፡ የቤት ፡ ክርስቲያን ፡ የታላቆች ፡ መምህራንዋ ፡ ታሪክ ፡፡

I. የሐዋርያት ፡ ዘመን ፡ አባቶች ፡፡

1. የሮም ፡ ክሌሜንቶስ ፡፡

ስለርሱም ፡ ጳውሎስ ፡ ይናገራል ፡ ፊልጵስዩስ ፡ ፬፡ ፫፡፡ እርሱም ፡ የሮም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ሆነ ፡፡ እርሱም ፡ ከጻፈ ፡ መጻሕፍት ፡ ፪፡ መልእክቶች ፡ ብቻ ፡ ቀረልን ፡ ወደ ፡ ቆሮንቶስ ፡ የጻፈ ፡፡ ሌላ ፡ መጽሐፍም ፡ በስሙ ፡ የተጻፈ ፡ በውነት ፡ የርሱ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አይመስልም ፡፡

2. ሀርማስ ፡፡

ጳውሎስም ፡ ስለርሱ ፡ ጻፈ ፡ በሮሜ ፡ መልእክት ፡ በ፲፮፡ ምዕራፍ ፡፡ ከርሱም ፡ ፩፡ መጽሐፍ ፡ ቀረልን ፡ እረኛ ፡ የተባለ ፡፡

3. 4. ስለ ፡ ኢግናትዩስና ፡ ስለ ፡ ጶሊቃርጶስ ፡ በላይ ፡ ተናገርን ፡፡

II. አጶሎጌቶች ፡፡

የቤት ፡ ክርስቲያን ፡ መምህራን ፡ ስለ ፡ ክርስቲያን ፡ ባረማውያን ፡ ላይ ፡ መጉታው ፡ የጻፉ ፡ ክርስቲያንን ፡ ከመከሰሳቸው ፡ ያነጽዋቸው ፡ ዘንድ ፡፡

1. ኳድራቱስ ፡ ወንጌላዊ ።

እርሱም ፡ እንደህ ፡ አለ ። የጌታችን ፡ ታምራት ፡ ሁለግዜ ፡ ታየ ፡ እውነት ፡ ነበረና ። በርሱ ፡ የተፈወሱ ፡ ከሙታንም ፡ የተነሡ ፡ ሁለግዜ ፡ በሰው ፡ ማየት ፡ ነበረ ፡ ክርስቶስ ፡ በምድር ፡ ሲኖር ፡ ከርገቱም ፡ በኋላ ። ከርሳቸውም ፡ አያሌ ፡ ወደ ፡ ዘመናችን ፡ ደረሱ ።

2. አሪስቲደስ ።

3. ዮስቲኑስ ፡ ሰማዕት ።

ስለርሱም ፡ በቅድም ፡ ተናገርነ ። እርሱም ፡ ፪ ፡ መጻሕፍትን ፡ ጻፈ ፡ ክርስቲያንን ፡ ካረማውያን ፡ መክሰስ ፡ ያነጻቸው ፡ ዘንድ ፡ አንድም ፡ ከትሪፎ ፡ ጋራ ፡ መጫወት ፡ የተባለ ።

4. ታትያኑስ ፡ የዩስቲኑስ ፡ የሰማዕት ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ።
ስለርሱም ፡ ተናገርነ ።

5. አቴናጎራስ ።

እርሱም ፡ መጽሐፍን ፡ ስለ ፡ ክርስቲያን ፡ ጽፎ ፡ ለቄሣር ፡ ለማርቆስ ፡ አውሬልዮስ ፡ ሰጠው ።

6. ሀርምያስ ።

7. ቴዎፊሎስ ፡ ያንጾኪያ ፡ ኤጲስቆጶስ ።

8. ሄጌሲጶስ ።

እርሱም ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ታሪክ ፡ በ፭ ፡ መጻሕፍት ፡ ጻፈ ።

9. ሚሊቶ ፡ የሰርደስ ፡ ኤጲስቆጶስ ።

10. ቀላውዲዩስ ፡ አጶሊናሪስ ፡ የሄራጶሊስ ፡ ኤጲስቆጶስ ።

11. ኢሬኔዎስ ፡ በልዮን ፡ በፍርንሳዎች ፡ አገር ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ የነበረ ።

እርሱም ፡ የጶሊቃርጶስ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ነበረ ። እርሱም ፡ ከብዙ ፡ መምህራን ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ከነበሩ ፡ ይበልጣል ። አንዱን ፡ ታላቅ ፡ መጽሐፍን ፡ በመናፈቃን ፡ ላይ ፡ ጻፈ ።

12. ሂጶሊቱስ ፡ የኢሬኔዎስ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡፡

13. ተርቱልያኑስ ፡ ባፍሪቃ ፡፡

እርሱም ፡ አረማዊ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ ተናጋሪ ፡ ነበረ ፡ በፍርድ ፡ ልቡም ፡ የቃጠለ ፡፡ የክርስቲያንም ፡ ሃይማኖት ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ ሁሉን ፡ ለሃይማኖት ፡ ለመታዘዝ ፡ እሺ ፡ ያሰደኝ ፡ ዘንድ ፡ ወደደ ፡፡ እርሱም ፡ ብዙ ፡ መጻሕፍትን ፡ ጻፈ ፡ ወደኛ ፡ የደረሱ ፡ እስካሁን ፡ ድረስም ፡ ፍርያቸውን ፡ የሚያፈሩ ፡፡

14. ቂጵርያኑስ ፡ የከርታጎ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡፡

የርሱንም ፡ ታሪክ ፡ ደግሞ ፡ በላይ ፡ ጻፍነው ፡፡ ከርሱም ፡ የተጻፏ ፡ ብዙ ፡ መጻሕፍት ፡ ደረሱልን ፡፡

15. አርኖቢዮስ ፡፡ ተናጋሪ ፡፡

እርሱም ፡ ከሕልም ፡ የተነሣ ፡ ኃጢአትን ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ክርስቶስ ፡ ተመለሰ ፡፡ ፯፤ መጻሕፍትንም ፡ ጻፈ ፡ ባረማውያን ፡ ላይ ፡፡

16. ካዮስ ፡፡ 17. ኖዋትያኑስ ፡፡

እሌህ ፡ ፪፤ በሮም ፡ አንዱ ፡ ቄስ ፡ አንዱም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ነበሩ ፡፡

18. ሚኑኪዮስ ፡ ፌሊክስ ፡ የሮም ፡ ተናጋሪ ፡፡

19. ቲቱስ ፡ ፍላዊዮስ ፡ ክሌሜንቶስ ፡ የስክንድርያ ፡ ከቴኬቴስ ፡፡

እርሱ ፡ ገና ፡ አረማዊ ፡ በነበረ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ዕውቀትን ፡ ፈለገ ፡ በብዙ ፡ አገርም ፡ ዞረ ፡ ያገኘው ፡ ዘንድ ፡፡ ብዙ ፡ መምህራንም ፡ ነበሩለት ፡ አንድ ፡ በየላደስ ፡ አንድም ፡ በቀደሌሶርያ ፡ አንድም ፡ በኢጣልያ ፡ አንድም ፡ በሶርያ ፡ በኋላም ፡ ከሁላቸው ፡ የበለጠ ፡ አዋቂ ፡ በምስር ፡ አገኘው ፡ እርሱንም ፡ ጳንቴኖስ ፡፡ ጳንቴኖስም ፡ ከምስር ፡ ከተሰናበተ ፡ በኋላ ፡ ክሌሜንቶስ ፡ በርሱ ፡ ስፍራ ፡ ከቴኬቴስ ፡ ሆነ ፡፡ እርሱም ፡ ክርስቲያንንና ፡ አረማውያንን ፡ ለማስተማር ፡ የጻፈ ፡ እጅግ ፡ ነው ፡፡

20. ኦሪጌኔስ : አደማንቲኖስ ::

እርሱም : በስክንድርያ : ተወለደ : ባመት : ፻፹፭። እርሱም : በዚህ : ዘመን : ከነበሩ : ከክርስቲያን : መምህራን : ሁሉ : ይበልጣል : በውቀቱ :: አባቱና : እናቱም : ክርስቲያን : ነበሩ :: ልጃቸውንም : እግዚአብሔርን : ለመፍራትና : ለመውደድ : አሳደጉት :: አባቱም : ሌዎኒደስ : ልጁን : ዕለት : ዕለት : ከመጽሐፍ : ቅዱስ : ክፍልን : ሊማር : አዘዘው : ኦሪጌኔስም : በርሱ : እጅግ : ደስ : አለው :: የተማረውንም : ነገር : ሁሉ : ትርጓሜውን : መረመረ :: በዐሸክርነቱም : የክሌሜንቶስ : ደቀ : መዝሙር : ነበረ :: ልቡም : በበጐነት : ነገር : ሁሉ : ተጋድሎ : አንድ : ጊዜ : የክርስቶስን : ነገር : ሳያስተውል : ነፍሱን : ጃንደርቦ : አደረገ : ስለ : መንግሥተ : ሰማያት : ብሎ :: በኋላ : ግን : መጽሐፍ : ቅዱስን : ያተኻለ : ባወቀ : ጊዜ : ስለዚች : ስሕተቱ : አዘነ :: የኦሪጌኔስ : አባትም : ሌዎኒደስ : በታሠረ : ጊዜ : ስለ : ሃይማኖትም : በሞተ : ጊዜ : እርሱ : ደግሞ : ይሞት : ዘንድ : ፈለገ :: እናቱ : ግን : ከለከለቸው :: ሌዎኒደስም : ከሞተ : በኋላ : መኰንን : ከብቱን : ሁሉን : ወሰደ : የኦሪጌኔስም : እናት : ከ፯፡ ልጆችዋ : ጋራ : ተቀመጠች : መምገባቸውንም : ሳነች :: የዚያን : ጊዜም : ኦሪጌኔስ : ዕድሜው : ፲፯፡ አመት : ሁኖ : በማስተማር : እጅግ : ደከመ : ይረዳት : ዘንድ :: በማሳደድም : ጊዜ : ኦሪጌኔስ : ከቴኼቴስ : ሆነ : በስክንድርያ :: እግዚአብሔርም : ብዙ : ጊዜ : ከሞት : ጠበቀው :: በኋላም : ብዙ : አረማውያን : ሲመረምሩ : የክርስቲያንን : ነገር : ከኦሪጌኔስም : ጋራ : ሲመጕቱ : እርሱ : ፊሎሶፊያን : ተማረ : ከአሞኒዮስ : ሰካስ : ያረማውያን : ዕውቀት : መልካም : ያውቅ : ዘንድ : አረማውያንንም : ለክርስቶስ : ይረባ : ዘንድ : ብሎ :: በዚህም : እግዚአብሔርንና : ሰውን : በመውደድ : እግዚአብሔር : እጅግ : ባረከው : ብዙ : ሰዎችም : ከጠቢባን : ወገን : ከታላቆቸም : በትምርቱ : ለሃይማኖት : ተገዙ :: አንደሁም : አንድ : አምብሮስዮስ : የሚሉት : አስቀድሞ : የክርስቲያንን : ሃይማኖት : ስንፍናውን : ይቈጥራት : ነበረ :

ኦሪጌኔስን ፡ እስኪሰማ ፡ ድረስ ፡፡ ከርሱም ፡ ተማረ ፡ ክርስ
ቲያንም ፡ ሆነ ፡ ገንዘቡንም ፡ ሁሉን ፡ ሰጠ ፡ ኦሪጌኔስን ፡ በ
ማስተማሩ ፡ ይረደው ፡ ዘንድ ፡፡ ኦሪጌኔስም ፡ ሸማግሌ ፡ ሲ
ሆን ፡ ዕብራይስጥን ፡ ተማረ ፡ ብሉይ ፡ መጽሐፍን ፡ መልካ
ም ፡ ያስተውል ፡ ዘንድ ፡ ብሎ ፡፡ ስራውንም ፡ ስለ ፡ መው
ደዱ ፡ ኦሪጌኔስ ፡ አደማንቲዮስ ፡ ተባለ ፡ ማለቱም ፡ እንደ ፡
አልማዝ ፡ የሚበርታ ፡፡ ስለ ፡ መጽሐፉ ፡ ቅዱስም ፡ ሁሉ ፡
ጻፈ ፡ ትምርቱን ፡ ያስተምር ፡ ዘንድ ፡፡

ነገር ፡ ግን ፡ ኦሪጌኔስ ፡ አንድ ፡ ጸላትን ፡ አገኘ ፡ ስለ ፡ መ
ንፈሱና ፡ ስለ ፡ እውቀቱ ፡ የተቀናበት ፡ እርሱም ፡ ዲሜትር
ዮስ ፡ የስክንድርያ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡፡ የኦሪጌኔስ ፡ ወዳጆች ፡
የየሩሳሌም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እስክንድር ፡ የቂሣርያም ፡ ኤ
ጲስቆጶስ ፡ ቴዎክቲስቶስ ፡ ለምነውታልና ፡ በቤተ ፡ ክርስቲ
ያናቸው ፡ ይሰብክ ፡ ዘንድ ፡፡ እርሱም ፡ ቄስ ፡ አልነበረምና ፡
ቀሰሱት ፡ ባመት ፡ ፪፻፳፰፡፡ ስለዚህም ፡ ዲሜትርዮስ ፡ እጅ
ግ ፡ ተቈጣ ፡ ቅደሲውንም ፡ ሻረ ፡ በሲኖደስም ፡ ገዘተው ፡፡
አሁንም ፡ መለየት ፡ ሆነ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በኦሪጌኔስ ፡
መክንያት ፡፡ የስክንድርያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከሮም ፡ ጋ
ራ ፡ ከመካከላቸው ፡ አወጡት ፡ በከናዐን ፡ ግን ፡ በዐረቢ
ያም ፡ በፊንቂያም ፡ በአካያም ፡ የነበሩ ፡ አብያተ ፡ ክርስ
ቲያናት ፡ ተቀበሉት ፡፡ ኦሪጌኔስ ፡ ግን ፡ የረገሙትን ፡ ጸላቶ
ቹን ፡ ባረከ ፡ በክፉም ፡ ፈንታ ፡ በጎን ፡ መለሰላቸው ፡፡ በዴኪ
ዮስ ፡ ማሳደድም ፡ ሕይወቱን ፡ ሰጠ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ባ
መት ፡ ፪፻፶፬፡ ዕድሜው ፡ ፷፱፡ አመት ፡ ሲሆን ፡፡

21. ሄራክለስ ፡፡

እርሱ ፡ የኦሪጌኔስ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ነበረ ፡ ዲሜትርዮ
ስንም ፡ በኤጲስቆጶስና ፡ ተከተለ ፡፡

22. ዲዮናስዮስ ፡፡

እርሱም ፡ ደግሞ ፡ የኦሪጌኔስ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ በትም
ርት ፡ የክርስቶስም ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ በየውሃት ፡ ነበረ ፡ ሄ
ራቅለስንም ፡ ተከትሎ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ሆነ ፡ በስክንድርያ ፡
ባመት ፡ ፪፻፵፯፡፡

23. ጎርጎርዮስ ፡ ታውማቱርጎስ ፡ የታምራት ፡
አድራጊ ፡ የተባለ ፡፡

እርሱም ፡ ደግሞ ፡ የኦሪጌኔስ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ነበረ ፡ በትምርቱም ፡ ሃይማኖትን ፡ ተቀበለ ፡፡ ፳፤ አመት ፡ ከኦሪጌኔስ ፡ ጋራ ፡ ከተቀመጠ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ጶንጦስ ፡ ተመልሶ ፡ የጶንጦስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ሆነ ፡፡ እጅግ ፡ ሰዎችም ፡ በርሱ ፡ ሃይማኖትን ፡ ስለ ፡ ተቀበሉ ፡ እርሱ ፡ ታውማቱርጎስ ፡ ተባለ ፡፡

24. ሜቶድዮስ ፡ የኦሊምጶስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡፡

25. ጳምፊሎስ ፡ የቄሣርያ ፡ ቄስ ፡፡

እርሱም ፡ የኦሪጌኔስ ፡ ወዳጅ ፡ ነበር ፡፡ ማስተማርያንም ፡ አደረገ ፡ በቄሣርያ ፡ እጅግ ፡ መጻሕፍትንም ፡ ለቀመ ፡ የቤት ፡ ክርስቲያን ፡ ቀሳውስት ፡ ሊማሩባቸው ፡፡ ሰውንም ፡ ሁሉን ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ መማር ፡ የወደደውን ፡ ረዳ ፡ በዲዮክሌትያኖስ ፡ ስደትም ፡ሞተ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ባመት ፡ ፫፻፱፡፡

26. ፒሲኪዮስ ፡ የምስር ፡ ኤጲስቆጶስ ፡፡

እርሱም ፡ ባመት ፡ ፫፻፫፤ ወይስ ፡ ፫፻፱፤ በዲዮክሌትያኖስ ፡ ስደት ፡ ሞተ ፡፡

የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ታሪክ ፡

ሁለተኛ ፡ ክፍል ፡

ከታላቅ ፡ ቆንስታንቲኖስ ፡ ከመንግሥቱ ፡ መጀመርያ ፡ ጀምሮ ፡

እስከ ፡ ሮም ፡ ጳጳስ ፡ እስከ ፡ ታላቅ ፡ ጎርጎርዮስ ፡

ሹመት ፡ ድረስ ፡፡

ከልደት ፡ አመት ፡ ፫፲፪፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፭፺፩፡ ድረስ ፡፡

በዚህ ፡ ዘመን ፡ የነገሡ ፡ ቄሣሮች ፡ እሌህ ፡ ናቸው ፡፡

ታላቅ ፡ ቈንስታንቲኖስ ፡ ካመት ፡ ፫፻፮ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፫፴፯ ድረስ ፡፡

ልጆቹም ፡፡ ቈንስታንቲኖስ ፡ ፫፴፯ እስከ ፡ ፫፵፡፡
ቈንስታንስ ፡ ፫፴፯ እስከ ፡ ፫፶፡፡
ቈንስታንቲዎስ ፡ ፫፴፯ እስከ ፡ ፫፷፡፡

ዩልያኖስ ፡ የክርስቲያን ፡ ጸላት ፡ ፫፷፡፡ እስከ ፡ ፫፷፫፡፡

ዮዊያኖስ ፡ ፫፷፫ ፫፷፬፡፡

መጀመርያ ፡ ዋለንቲኒያኖስ ፡ በምዕራብ ፡፡

ዋለንስም ፡ በምሥራቅ ፡ ፫፷፬ እስከ ፡ ፫፸፰፡፡

ግራቲያኖስና ፡ ሁለተኛ ፡ ዋለንቲኒያኑስ ፡ በምዕራብ ፡ ፫፸፰ እስከ ፡ ፫፺፪፡፡ ታላቅ ፡ ቴዎደስዩስም ፡ በምሥራቅ ፡ ከ፫፸፱ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፫፺፬ ድረስ ፡፡ ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ ቴዎደስዩስ ፡ ብቻውን ፡ ነገሠ ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ ፫፺፭፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ መንግሥት ፡ ተከፈለች ፡ በ፪ ልጆቹ ፡፡

አርካድዮስ ፡ በምሥራቅ ፡ ፫፺፭ እስከ ፡ ፬፻፰፡፡

ሆኖርዩስ ፡ በምዕራብ ፡ ፫፺፭ እስከ ፡ ፬፳፫፡፡

ሁለተኛ ፡ ቴዎደስዮስ ፡ በምሥራቅ ፡ ፬፻፰፡፡ እስከ ፡ ፬፶፡፡

ሶስተኛ ፡ ዋለንቲኒያኑስ ፡ በምዕራብ ፡ ፬፳፭፡፡

ጹልኼርያ ፡ ንግሥት ፡ ከማርቂያኖስ ፡ ጋራ ፡ ፬፶፡፡ እስከ ፡ ፬፶፫፡፡

መክሲሙስ ፡ በምሥራቅ ፡ ፫፶፭፡፡

ማዮርያኑስ ፡ ፬፶፯፡፡

ሌዎን ፡ ትራክስ ፡ ፬፶፯፡፡

ሁለተኛ ፡ ሌዎን ፡ ካባቱ ፡ ከዜኖ ፡ ጋራ ፡ ፬፸፬፡፡

ሮሙሉስ ፡ አውጉስቱሉስ ፡ የሮም ፡ ኋለኛ ፡ ቄሣር ፡ በምዕራብ ፡፡ በርሱ ፡ ዘመንም ፡ ባመት ፡ ፬፸፮ ኦድዋክር ፡ የ

ኀቶች ፡ ንጉሥ ፡ የሮምን ፡ መንግሥት ፡ በምዕራብ ፡ አፍር
ስዋልፍ ፡ በሮምም ፡ ነገሠ ፡፡

መጀመርያ ፡ አንስታስዮስ ፡ ፬፺፩፡፡
መጀመርያ ፡ ዩስቲኑስ ፡ ፭፲፰፡፡
መጀመርያ ፡ ዩስቲኒያኑስ ፡ ፭፳፯፡፡
ሁሉተኛ ፡ ዩስቲኑስ ፡ ፭፷፭፡፡
ሁለተኛ ፡ ቲቤርዩስ ፡ ፭፸፰፡፡
ማውሪትዮስ ፡ ፭፹፪፡፡

መጀመርያ ፡ ምዕራፍ ።

ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መዝረጋትና ፡ መከራ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ።

፩፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መዝረጋትና ፡ መከራ ፡ በሮም ፡ መንግሥት ።

፩፡፩፡ የሮም ፡ ቄሣሮች ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያደረጉትን ፡ ነገር ።

በዚህ ፡ ዘመን ፡ በመጀመርያ ፡ ታላቅ ፡ መጋደል ፡ ሆነ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባሮም ፡ መንግሥት ፡ እስክትገዛ ፡ ድረስ ። ድል ፡ ሳታንሣ ፡ መከራ ፡ ልትቀበል ፡ ነበረች ።

ቄሣር ፡ ጋሌርዮስ ፡ ፫፲፩ ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ዘመዱ ፡ ካዩስ ፡ ጋሌርዮስ ፡ ዋሌርዮስ ፡ መክሲሚኑስ ፡ በስያ ፡ ሁሉ ፡ ነገሠ ። እርሱም ፡ የክርስቲያን ፡ ታላቅ ፡ ጸላት ፡ ነበረ ፡ አሳደደቸውም ። እርሳቸው ፡ ግን ፡ በክፉ ፡ ፈንታ ፡ በጎ ፡ አደረጉ ፡ በቸነፈርና ፡ በራብ ፡ ጊዜ ፡ የተራቡትን ፡ መገቡ ። ስለዚህም ፡ አረማውያን ፡ የክርስቲያንን ፡ አምላክ ፡ አመሰገኑ ። አያሌ ፡ ክርስቲያንም ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ሞቱ ፡ በኤሜሳ ፡ በስክንድርያም ፡ ባንጾኪያም ። ይህም ፡ የዚያ ፡ ዘመን ፡ ስደት ፡ መጨረሻ ፡ ነበረ ። ከምዕራብ ፡ ረዴት ፡ መጥታለችና ።

ቆንስታንቲኖስ ፡ ባመት ፡ ፫፻፮ ፡ ባባቱ ፡ በቆንታንቲዎስ ፡ ክሎሮስ ፡ ፈንታ ፡ ነገሠ ። ስለ ፡ ክርስቲያንም ፡ እንደ ፡ ኣባቱ ፡ አሰበ ፡ ለራሱም ፡ ባረማውያን ፡ አማልክት ፡ አመነ ፡ መክሴንቲዩስን ፡ እስኪያሸንፍ ፡ ድረስ ። መክሴንቲዩስም ፡ ባለቤቱ ፡ የኢጣልያ ፡ ያፍሪቃም ፡ መንግሥት ፡ ወሰደ ፡ እጅግም ፡ ክፉ ፡ ግፈኛም ፡ ነበረ ። የተገዙትም ፡ ሁሉ ፡ ክርስቲያንና ፡ አረማውያን ፡ ጸሉት ፡ ስለ ፡ ክፋቱ ። ቆንስታንቲኖስም ፡ አዘመተው ። መክሴንቲዩስም ፡ ያረማ

ውያን ፡ ማምለክ ፡ ሁሉ ፡ ሲያድርግ ፡ አማልክት ፡ ሁሉ ሊረዱት ፡ ብሎ ፡ ቈንስታንቲኖስ ፡ አዝኖ ፡ ተክዞ ፡ እንዴህ ፡ ሲል ። ማን ፡ ይረዳኛል ፡ እንኪያስ ። በሌሊትም ፡ በሕልም ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ሲያይ ፡ የነበልባል ፡ መስቀል ፡ ታየለት ፡ በሰማይ ፡ መልአክም ፡ በአጠገቡ ፡ የሚለው ፡ በ ዚ ህ ፡ አሸንፈ ። በሚመጣም ፡ ቀን ፡ ይችንም ፡ ራእዩን ፡ በሠራዊቱ ፡ ላይ ፡ አየ ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ በሠራዊቱ ፡ ባንዴራ ፡ የመስቀልን ፡ ምልክት ፡ አስደረገ ፡ ከክርስቶስ ፡ ስም ፡ ጋራ ፡ የመክሴንቲዩስንም ፡ ሠራዊት ፡ መትቶ ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ ከተማ ፡ ገባ ፡ ምኀሌውንም ፡ በገቢያ ፡ አቆመ ፡ ባንዲራውን ፡ በጁ ፡ የሚዝ ፡ የመስቀል ፡ ምልክት ፡ የነበረበት ፡ በታቹም ፡ የተጻፈ ። በዚህ ፡ በሚያድን ፡ ምልክት ፡ በውነተኛ ፡ ድፍረት ፡ ምልክት ፡ እኔ ፡ ከተማችሁን ፡ ከግፍ ፡ ቀምበር ፡ አደንኋት ።

ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ፩ ጊዜ ፡ ትእዛዝን ፡ ሰጠ ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ ሥልጣን ፡ እንደለው ፡ አምላኩን ፡ እንደ ፡ ወደደው ፡ ያመልክ ፡ ዘንድ ፡ ለመንግሥቱ ፡ ሁሉ ፡ ዕረፍት ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ የሰዎችም ፡ አማልክት ፡ ሁሉ ፡ ለቄሣሮችም ፡ በጎ ፡ እንደ ሆኑ ። በዚህ ፡ ነገርም ፡ ቈንስታንቲኖስ ፡ ከሊኪኒዩስ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነበረ ። ሊኪኒዩስም ፡ የቈንስታንቲኖስን ፡ እት ፡ ቈንስታንቲያን ፡ ምሽቱ ፡ አድርጎ ፡ አገባት ። ሊኪኒዩስም ፡ በመክሲሚኑስ ፡ ላይ ፡ ጾር ፡ አደረገ ፡ መክሲሚኑስም ፡ ጥቂት ፡ ወራት ፡ በኋላ ፡ በጠርሲስ ፡ ሲሞት ፡ ቈንስታንቲኖስና ፡ ሊኪኒዩስ ፡ ብቻቸውን ፡ ቄሣሮች ፡ ነበሩ ። አሁን ፡ ግን ፡ እሌህ ፡ ፪ ተጻሉ ፡ እርሶ ፡ በርሳቸው ፡ ባመትም ፡ ፫፻፲፬ ቈንስታንቲኖስ ፡ በሊኪኒዩስ ፡ ላይ ፡ አሸነፈ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሁለታቸው ፡ ታረቁ ። ሊኪኒዩስም ፡ ክርስቲያንን ፡ መጽላት ፡ ጀመረ ፡ የመንግሥቱ ፡ ክርስቲያን ፡ ቈንስታንቲኖስን ፡ ከርሱ ፡ ይልቅ ፡ የወደዱ ፡ ሲመስለው ። በኋላም ፡ ባመት ፡ ፫፻፳፫ ሁለተኛ ፡ ጾር ፡ ሆነ ፡ በለዚህ ፡ ፪ መካከል ። ቈንስታንቲኖስም ፡ ሊኪኒዩስን ፡ አሸንፎት ፡ ለብቻው ፡ ነገሠ ፡ በሮም ፡ መንግሥት ፡ ሁሉ ። አሁንም ፡ ቈንስታንቲኖስ ፡ ለራሱ ፡ ገና ፡ ክርስቲያን ፡ አልሆነም ፡ ደሮ ፡ የክርስቲ

ያን ፡ አምላክ ፡ ከሌሎች ፡ አማልክት ፡ ሁሉ ፡ የበለጠ ፡ መ
ሰለው ፡፡ በግድም ፡ አረማውያንን ፡ አልከለከለም ፡ ጣዖ
ታትን ፡ በግልጽ ፡ ከማምለክ ፡ ሰውን ፡ ሁሉን ፡ ተወ ፡ አን
ድ ፡ እንደ ፡ ልማዱ ፡ አምላኩን ፡ ያከብር ፡ ዘንድ ፡፡ ሊኪኒ
ዩስን ፡ ግን ፡ ካሸነፈው ፡ በኋላ ፡ መንግሥቱን ፡ ሁሉን ፡ ለእ
ግዚአብሔር ፡ መግዛት ፡ ሰጠው ፡ ራሱንም ፡ የእግዚአብሔ
ር ፡ ባርያ ፡ ሁኖ ፡ ቈጠረው ፡፡ ደግ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ማገ
ልገል ፡ በመንፈስና ፡ በውነት ፡ አላወቀም ፡ ስለዚህም ፡ በ
ኃጢአቱ ፡ ኖረ ፡፡ የዚህም ፡ ታላቅ ፡ መክንያት ፡ የዚያ ፡ ዘመ
ን ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ነበሩ ፡፡ ለርሳቸው ፡ አሁን ፡ የሚገባ ፡ ስ
ራ ፡ ይህ ፡ ኑርዋልና ፡ ቆንስታንቲኖስን ፡ በወንጌል ፡ ያስተም
ሩት ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔርም ፡ የሚፈልገው ፡ ማገልገል ፡
ያሳዩት ፡ ዘንድ ፡ ደግ ፡ በዚህ ፡ ፈንታ ፡ በማይገባ ፡ መጠን ፡
አከበሩት ፡፡ አንድም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እንዲህ ፡ አለው ፡፡ እ
ግዚአብሔር ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በፍጥረቱ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ሹሞ
ህ ፡ በሚመጣ ፡ ዓለም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ጋራ ፡ ትገዛ ፡
ዘንድ ፡ ጊዜ ፡ አለህ ፡፡ ቆንታንቲኖስም ፡ ባለቤቱ ፡ በዚች ፡
ማስመሳል ፡ ተቈጥቶ ፡ ኤጲስቆጶስን ፡ አለ ፡፡ እንዲህ ፡ ያ
ለ ፡ ድፍረት ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ እንደይገባ ፡ ደግ ፡ ለ
ቆንስታንቲኖስ ፡ ሊለምን ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸጋውን ፡ እንዲ
ሰጠው ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በሚመጣም ፡ የእግዚአብሔር ፡
ባርያ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡፡

ቆንስታንቲኖስም ፡ የክርስቲያንን ፡ ማምለክ ፡ ከሌላ ፡
ይልቅ ፡ ወደደው ፡ አከበረውም ፡፡ ኤጲስቆጶሳትንም ፡ አ
ከበረ ፡ የተዋቡትንም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ አሠራ ፡፡
ክብትም ፡ ሰጠ ፡ ለቤት ፡ ክርስቲያን ፡ በመንግሥቱም ፡ ሁ
ሉ ፡ የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ እንዲገዛ ፡ ወደደ ፡፡ ደግ ፡ ሰ
ውን ፡ ሁሉን ፡ ሃይማኖትን ፡ ለመቀበል ፡ አላገደቸውም ፡፡
በማስተማር ፡ እንጅ ፡ በምስክርም ፡ ወንጌልን ፡ ይዘርጉ
ት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፡፡ ከጣዖታትም ፡ መቅደሶች ፡ አያሌን ፡
አስፈረሰ ፡ አረማውያን ፡ በርሳቸው ፡ ቁሣርን ፡ በበደሉ ፡ ጊ
ዜ ፡ ስለ ፡ ማምለካቸው ፡ ግን ፡ አይደለም ፡፡ በኒቅያ ፡ በሲ
ኖደስ ፡ ኤጲስቆጶሳትን ፡ መከረ ፡ እንደይቀኑ ፡ እርሱ ፡ በር

ሳቸው ፡ ክብር ፡ ሲያገኙ ፡ በቀናትም ፡ መለየት ፡ እንደ ያደ
ርጉ ፡ ላረማውያንም ፡ የክርስቶስን ፡ ስም ፡ ሊሰድቡ ፡ መ
ክንያት ፡ እንዳይሰጡ ፡፡ አረማውያንም ፡ ወደ ፡ ሃይማኖት ፡
ይደርሳሉ ፡ የክርስቲያን ፡ መሆን ፡ በነገር ፡ ሁሉ ፡ ደግ ፡ ቢመ
ስላቸው ፡፡ ትምርትም ፡ ለሁሉ ፡ እንደ ይጠቅም ፡ አወቁ ፡፡
አያሌ ፡ ሰዎችም ፡ ሃይማኖትን ፡ ይቀበላሉ ፡ በጊዜ ፡ ምግ
ብ ፡ ቢያገኙ ፡ ከክርስቲያናት ፡፡ ሌሎችም ፡ እሺ ፡ ይላሉ ፡
ኤጲስቆጶሳት ፡ ከጸላቶቻቸው ፡ ቢጠብቅዋቸው ፡፡ ሌሎች
ም ፡ በነ ፡ እንግድነት ፡ ብትቀበልዋቸው ፡፡ ሌሎችም ፡ አ
ጅ ፡ መንግ ፡ ቢያገኙ ፡፡ ትምርትን ፡ የሚወዱ ፡ ጥቂት ፡ ናቸ
ውና ፡ የውነትም ፡ ወዳጆች ፡ እጅግ ፡ አይገኙም ፡፡

ቈንስታንቲኖስም ፡ ኤጲስቆጶሳትን ፡ እንደዚህ ፡ ብሎ ፡ ሲ
መክራቸው ፡ ግብዝነት ፡ ለመብዛት ፡ አገለገለ ፡፡ ብዙ ፡ ሰ
ዎች ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ግብዞች ፡ ሆኑ ፡ እውነተኞች ፡ ክርስ
ቲያናት ፡ ግን ፡ ጥቂት ፡ ሆኑ ፡፡ ቈንስታንቲኖስም ፡ ባለቤቱ ፡
ከሃይማኖት ፡ ኃይል ፡ በልቡ ፡ ጥቂት ፡ ቀመሰ ፡፡ ዕድሜው ፡
፲፬፤ አመት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ እርሱ ፡ ገና ፡ አልተጠመቀም ፡፡
ኃጢአቱ ፡ እንደ ይከለክል ፡ ፈርትዋልና ፡፡ በልቡም ፡ ታላቅ ፡
ኃጢአት ፡ ኖረበት ፡፡ ሁለተኛዪቱ ፡ ምሽቱ ፡ ፈውስታ ልጁ
ን ፡ ክርስጶስን ፡ በመንዝር ፡ መክንያት ፡ ከሰሰች ፡ ስለዚህ
ም ፡ ተቈጥቶ ፡ አስገደለው ፡፡ ሄሌናም ፡ እናቱ ፡ ስለዚህ ፡
በገሠጸቸው ፡ ጊዜ ፡ በኋላም ፡ ያ ፡ መክሰስ ፡ ሐሰት ፡ እንደ ፡
ሆነ ፡ በተገለጸ ፡ ጊዜ ፡ ምሽቱን ፡ ገደለ ፡፡ የቱንም ፡ የቈንስታ
ንቲያ ፡ ልጅን ፡ ደግሞ ፡ አስገደለ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ከርሱ ፡ በፈ
ራ ፡ ጊዜ ፡፡ በዚህ ፡ ሁሉም ፡ በውነተኛ ፡ በልብ ፡ ሃይማኖት ፡
ሰርየትን ፡ ከለመነ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ልቡ ፡ ዕረፍት ፡ ባገ
ኘ ፡ በጣምም ፡ በተለወጠ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ኤጲስቆጶሳቱ ፡ ከ
ኃጢአቱ ፡ እንቅልፍ ፡ አላስነሡትም ፡ የሰውን ፡ ክብር ፡ ወ
ደዋልና ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ይልቅ ፡፡

ቈንስታንቲኖስም ፡ ለሞቱ ፡ እንዲቀርብ ፡ ባሰበ ፡ ጊዜ ፡ በኒቆ
ሚድያ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በኤውሴቢዮስ ፡ ተጠመቀ ፡ ጥቂት ፡
ቀንም ፡ በኋላ ፡ ሞተ ፡ ባመት ፡ ፫፻፴፯፤ መንግሥቱንም ፡ ለ፫፤

ልጆቹ ፡ አሰነበተ ፡ ቈንስታንቲኖስና ፡ ቈንስታንስ ፡ በምዕራብ ፡ ሊገዙ ፡ ቈንስታንቲዎስ ፡ ግን ፡ በምሥራቅ ።

አልያ ፡ ፪፤ ወንድማማች ፡ ግን ፡ ቈንስታንቲኖስና ፡ ቈንስታንስ ፡ ተጸልተው ፡ ጾርን ፡ አደረጉ ፡ እርሶ ፡ በርሳቸው ፡ ቈንስታንቲኖስ ፡ የሞተበት ፡ ባመት ፡ ፫፵።

አሁንም ፡ ቈንስታንቲዎስ ፡ የምሥራቅ ፡ ሁሉ ፡ ጌታ ፡ ሁኖ ፡ ቈንስታንስ ፡ በምዕራብ ፡ ሆነ ። መግኔንቲዮስም ፡ በቈንስታንስ ፡ ላይ ፡ ባመፀ ፡ ጊዜ ፡ ቈንስታንስ ፡ በጾር ፡ ሞተ ፡ ባመት ፡ ፫፶። ቈንስታንቲዎስም ፡ የሮም ፡ መንግሥት ፡ ሁሉ ፡ ለብቻው ፡ ጌታ ፡ ሁኖ ፡ ቀረ ። እርሶም ፡ እንደ ፡ አባቱ ፡ ጠቢብ ፡ አልነበረምና ፡ ያረማውያንን ፡ ጣዖት ፡ ማምለክ ፡ በግድ ፡ ሊሽር ፡ ብሎ ፡ ባመት ፡ ፫፵፩፤ ትእዛዝ ፡ ሰጠ ፡ እንደ ህ ፡ የሚል ። የጣዖታት ፡ ሃይማኖት ፡ ይጨረስ ፡ የምሥዋዕታቸውም ፡ ማበድ ፡ ይሻር ። በ፫፵፪፤ ሁለት ፡ ቄሣሮች ፡ አዘዙ ፡ ያረማውያን ፡ መቅደስ ፡ ሁሉ ፡ እንዲዘጋ ፡ ብለው ። በ፫፶፮ም፤ ምሥዋዕትንና ፡ ጣዖታትን ፡ ማምለክ ፡ ሁሉ ፡ ሲከለክል ፡ ይህችን ፡ ትእዛዝ ፡ በሚያፈርስ ፡ ሞት ፡ አደረገበት ። ይህም ፡ በስሙ ፡ በዩልያኖስም ፡ ስም ፡ ሆነ ፡ ዩልያኖስ ፡ እንኳ ፡ በስውር ፡ አረማዊ ፡ ሲሆን ፡ በዚህ ፡ ነገርም ፡ ጸላትነቱ ፡ በዛ ። ቈንስታንቲዎስም ፡ ብዙ ፡ ከጣዖት ፡ መቅደሶች ፡ አስፈረሰ ፡ ብዙም ፡ ቀማ ፡ ከብታቸውንም ፡ ወይስ ፡ ላብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ወይስ ፡ ለወዳጆቹ ፡ በነጻ ፡ ለነገሩት ፡ ሰጠ ። ስለዚህም ፡ እጅግ ፡ ሰዎች ፡ ከታላቆች ፡ ወገን ፡ ያረማውያንን ፡ መቅደስ ፡ ይቀሙ ፡ ዘንድ ፡ ፈለጉ ፡ የራሳቸውን ፡ መመኛት ፡ ያጸግቡ ፡ ዘንድ ። ቄሣርም ፡ በዚህ ፡ መክንያት ፡ ሌላ ፡ ትእዛዝ ፡ ሊሰጥ ፡ ነበረ ፡ ይህነን ፡ መቀማት ፡ የሚከለክል ፡ ባመት ፡ ፫፵፮፤ እንደ ህ ፡ ሲል ። ባገር ፡ ደጅ ፡ ሁሉ ፡ በሜዳ ፡ ያሉትን ፡ መቅደሶች ፡ እንዳያፈርሶ ፡ ይጠብቋቸው ፡ እንጂ ።

አያሌ ፡ መምህራንም ፡ ቈንስታንቲዎስን ፡ መልካም ፡ አድርገው ፡ ገሠጹ ። ፊላርዩስም ፡ እንደ ህ ፡ አለው ። በመንግሥት ፡ ወርቅ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መቅደስ ፡ ታከብደላችሁ ፡ ካረማውያንም ፡ መቅደሶች ፡ የቀማችሁ ፡ ከሰውም ፡ በግድ ፡

የወሰዷችሁ ፡ በቅሥፈም ፡ ያገኟችሁትን ፡ ክብት ፡ ለእግዚ
አብሔር ፡ ትኖላችሁ ፡፡ አታናስዩስም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡
ስለ ፡ ቈንስታንቲዎስ ፡ ስለ ፡ አሪዎስ ፡ ወገንም ፡ ሁሉ ፡፡ እ
ርሳቸው ፡ ለራሳቸው ፡ በሃይማኖታቸው ፡ እንደያምኑ ፡ በ
ዚህ ፡ ይገለጻል ፡ ግድ ፡ ያድርጋሉና ፡ ሰውን ፡ ባለመውደደ
ቸው ፡ እንዲያግዱ ፡ ለሃይማኖት ፡፡ እንዲሁም ፡ ሰይጣን ፡
ደግሞ ፡ ሰው ፡ ቢቀበለው ፡ በምሳርና ፡ በሰይፈ ፡ ይገባል ፡፡
መድኃኒታችን ፡ ግን ፡ የዋህ ፡ ነው ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ ማን
ም ፡ ይከተለኝ ፡ ዘንድ ፡ ቢወድ ፡ ደቀ ፡ መዝሙሬም ፡ ይ
ሆን ፡ ዘንድ ፡ ቢወድ ፡ መስቀሉን ፡ ይውሰድ ፡፡ ማንንም ፡
አያገደውም ፡፡ ሰውም ፡ ባይወደው ፡ ክርስቶስ ፡ ይተወዋ
ል ፡፡ እውነት ፡ በሰይፈና ፡ በጾር ፡ አትሰበክምና ፡ ወይስ ፡ በ
ሠራዊት ፡ ኃይል ፡ በምክርና ፡ በመቀበል ፡ እንጂ ፡፡

ነገር ፡ ግን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መምህራን ፡ ሁሉ ፡ እን
ዲህ ፡ ብለው ፡ አልተናገሩም ፡፡ ብዙ ፡ ነበሩና ፡ ቄሣር ፡ እን
ደ ፡ ወደደው ፡ የተናገሩት ፡፡ እንዲህ ፡ ብልዋልና ፡ ማተርኑስ ፡
፪፡ ቄሣሮችን ፡ ቈንስታንስንና ፡ ቈንስታንቲዎስን ፡፡ የመቅደ
ሶችን ፡ ሸልም ፡ ትወስዱ ፡ ዘንድ ፡ አትፍሩ ፡፡ የመቅደሶች
ንም ፡ ባለጠግነት ፡ ሁሉ ፡ ለላንትና ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ር፡ብ
ዕ ፡ ረቡት ፡፡ ማተርኑስም ፡ ያረማውያንን ፡ ማምለክ ፡ ሁ
ሉ ፡ በግድ ፡ ሊሸሩ ፡ መከራቸው ፡፡ እንዲሁም ፡ ጌዎርጊዮ
ስ ፡ የስክንድርያ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በስክንድርያ ፡ አደረገ ፡፡

በዚህ ፡ ማድረግም ፡ አይነተኞች ፡ ክርስቲያኖች ፡ አልበዙ
ም ፡ ባረማውያን ፡ ብዙ ፡ ነበሩ ፡ እንጂ ፡ ጣዖታትን ፡ በማ
ምለክ ፡ የበረቱ ፡ ብቻ ፡፡ እርሳቸውም ፡ ጊዜያቸውን ፡ ጠበ
ቁ ፡ ጸላትነታቸውን ፡ ይገልጹ ፡ ዘንድ ፡፡ ይህም ፡ ሆነላቸው ፡
በዩልያኖስ ፡ ቄሣር ፡ መግዛት ፡፡

ዩልያኖስም ፡ የቈንስታንቲኖስ ፡ የወንድሙ ፡ ልጅ ፡ ነበ
ረ ፡፡ ቈንስታንቲኖስም ፡ ወንድሙን ፡ ገደለ ፡ እንደያመፅበ
ት ፡ ፈርትዋልና ፡፡ ቈንስታንቲዎስም ፡ እጅግ ፡ ጥል ፡ አደረ
ገ ፡ በዘመዶቹ ፡ ዩልያኖስንም ፡ ከመንግሥ ፡ ይከለክል ፡ ዘ
ንድ ፡ ፈለገ ፡፡ ስለዚህም ፡ እርሱን ፡ ከጋሉስ ፡ ከወንድሙ ፡
ጋራ ፡ ለክህነት ፡ አሳደጋቸው ፡፡ በግድም ፡ በጽልም ፡ ሁንዋ

ልና ፡ ዩልያኖስ ፡ ሃይማኖትን ፡ መጽላት ፡ ቶሎ ፡ ጀመረ ፡ ያረማውያንንም ፡ መምህራን ፡ ትምርት ፡ እጅግ ፡ ፈለገ ፡፡ በመጀመርያም ፡ በግልጽ ፡ ክርስቲያን ፡ ነበረ ፡ በስውር ፡ ግን ፡ በውነትም ፡ አረማዊ ፡፡ ወንድሙም ፡ ጋሉስ ፡ በቆንስታንቲዎስ ፡ ጸላትነት ፡ ፫፻፶፬፡ ሞተ ፡ በዚህም ፡ የዩልያኖስ ፡ ጸላትነት ፡ በክርስቲያን ፡ ላይ ፡ በዛ ፡፡ ደሮ ፡ እንደዚህ ፡ ግብዝ ፡ ነበረ ፡ እርሱ ፡ ፈጹም ፡ አረማዊ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ለኤጲስቆጶሳት ፡ ሚደዊ ፡ መልኩን ፡ ብቻ ፡ ላዩ ፡ በነ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁኖ ፡ እንደ ፡ መሰላቸው ፡፡

ባመት ፡ ፫፻፷፩፡ ዩልያኖስ ፡ ቄሣር ፡ ሆነ ፡፡ ከዚያም ፡ ጀምሮ ፡ እጅግ ፡ ደከመ ፡ በጣም ፡ የጣዖታትን ፡ ማምለክ ፡ ይመልስ ፡ ዘንድ ፡፡ ቆንስታንቲኖስና ፡ ቆንስታንቲዎስም ፡ ስለ ፡ ክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ያደረጉትን ፡ ነገር ፡ ሁሉን ፡ ይሽር ፡ ዘንድ ፡፡ እርሱም ፡ ባለቤቱ ፡ ያረማውያን ፡ የካህናታቸው ፡ አለቃ ፡ ሁኖ ፡ እጅግ ፡ ደከመ ፡ አማልክታቸውን ፡ ያገለግል ፡ ዘንድ ፡ ምሥዋዕትንም ፡ ይሠውላቸው ፡ ዘንድ ፡ ክርስቲያን ፡ እስኪላገጹበት ፡ ድረስ ፡፡ ዩልያኖስም ፡ እጅግ ፡ ጻፈ ፡ በክርስቲያን ፡ ላይ ፡፡ በጽሕፈቱም ፡ ካረማውያንና ፡ ከክርስቲያን ፡ መጻሕፍት ፡ መክንያትን ፡ ሰበሰበ ፡ ባንድም ፡ ደበለቀው ፡ ክርስቲያንን ፡ ለማጣላት ፡፡ በክርስቲያን ፡ መጻሕፍትም ፡ የተገኘውን ፡ በጎ ፡ ነገርን ፡ አረማውያን ፡ ይከተሉት ፡ ዘንድ ፡ መከራቸው ፡ እንደዚህ ፡ አድርገው ፡ የክርስቲያንን ፡ ሃይማኖት ፡ ይሽሩ ፡ ዘንድ ፡ ብሎ ፡፡ በዚህም ፡ አልኖረም ፡፡ በግድና ፡ በተንኰል ፡ ክርስቲያን ፡ ሊመለሱ ፡ ነበሩ ፡ ወደ ፡ ጣዖታት ፡፡ እጅግ ፡ ብርም ፡ ለድኆች ፡ ሰጠ ፡ እሺ ፡ ያሰኙቸው ፡ ዘንድ ፡፡ ያረማውያንንም ፡ ካህናት ፡ እጅግ ፡ አከበራቸው ፡ የበደላቸውንም ፡ ቀሠፈ ፡ የጣዖታትንም ፡ መቅደሶች ፡ ያፈረሱትን ፡ መልሶ ፡ አሠራቸው ፡፡ የተቀሙትንም ፡ ከብታቸውን ፡ ከክርስቲያን ፡ ወስደት ፡ ለጣዖታት ፡ መቅደሶች ፡ መለሰላቸው ፡ አረማውያን ፡ እንኳ ፡ እስኪገሥጹት ፡ ድረስ ፡፡

ክርስቶስንና ፡ ክርስቲያንንም ፡ ለመጽላት ፡ ብሎ ፡ ላይሁድ ፡ ወደጅነትን ፡ አደረገ ፡ ወደ ፡ የሩሳሌምም ፡ ይመለ

ሶ ፡ ዘንድ ፡ ከዚያም ፡ የተገለበጠውን ፡ መቅደሳቸውን ፡ አደስ ፡ ይሠሩት ፡ ዘንድ ፡ አዘዛቸው ፡ የክርስቶስን ፡ ትን ቢት ፡ በጣም ፡ ሊሽር ፡ ብሎ ፡ በየሩስሌም ፡ መቅደስ ፡ ደን ጊያ ፡ በደንጊያ ፡ ላይ ፡ እንደይኖር ፡ ሲል ፡፡ አጅግ ፡ ከብት ም ፡ ሰጠ ፡ አጅግም ፡ ደከመ ፡ ይህነን ፡ ፈቃዱን ፡ ለመፈጸ ም ፡፡ ደሮ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ እግዚአብሔር ፡ ከለከለው ፡፡ ስ ራተኞች ፡ በስፍራው ፡ በቆፈሩ ፡ በሰሩም ፡ ጊዜ ፡ ምድር ፡ ተናወጸች ፡ እሳትም ፡ ከምድር ፡ ወጥቶ ፡ የተጀመረውን ም ፡ ስራ ፡ አጥፍቶ ፡ ስራተኞችን ፡ አስፈራ ፡ ስራውም ፡ ቀ ረ ፡፡ አሁንም ፡ አይሁድን ፡ መከረ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ስለ ፡ እርነታቸው ፡ ያመሰግኑት ፡ ዘንድ ፡ ይለምኑትም ፡ ዘንድ ፡ ለርሱ ፡ ለጸሩም ፡ ለመቅደሳቸውም ፡ ያ ፡ ከፈርስ ፡ ጋራ ፡ የተጀመረ ፡ ጾር ፡ ሲጨርስ ፡ መልካም ፡ መቅደስ ፡ መሥራ ት ፡ እንዲችሉ ፡ የከበረችም ፡ ከተማ ፡ የሩሳሌም ፡ እር ሱ ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ በርስዋ ፡ መኖር ፡ የወደደ ፡፡

በክርስቲያን ፡ ላይም ፡ አጅግ ፡ ተንኰል ፡ አደረገ ፡፡ ብር ቱ ፡ ሊሆንባቸው ፡ ደምም ፡ ሊያፈስ ፡ አልወደደም ፡ የክር ስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ በመከራ ፡ እንዲደጉደ ፡ ተጠቀመ ፡ እ ንጅ ፡ ከመጀመርያ ፡ አይትዋልና ፡፡ የተሳደዱትን ፡ ኤጲስቆ ጶሳት ፡ ቈንስታንቲዎስ ፡ ስለ ፡ ሥላሴ ፡ ትምርት ፡ ያሳደዳቸ ውን ፡ ሊመለሱ ፡ አዘዛቸው ፡፡ ስለዚህም ፡ ብዙ ፡ መምህራ ን ፡ ወደገሪቸው ፡ ወደ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናታቸውም ፡ ተመ ለሱ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ አታናስዮስም ፡ በተመለስ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ እስክንድርያ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑም ፡ ተቈጥቶ ፡ ከለ ከለው ፡፡ እርሱን ፡ አጅግ ፡ ፈርትዋልና ፡ በትምርቱ ፡ ብዙ ፡ ካረማውያን ፡ የክርስቲያንን ፡ ሃይማኖት ፡ ስለ ፡ ተቀበሉ ፡፡ ሌሎች ፡ ኤጲስቆጶሳትና ፡ ቀሳውስት ፡ ከሌሎች ፡ መምህ ራን ፡ ጋራ ፡ አላሰባቸውም ፡ ተስፋ ፡ አድርግዋልና ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡ በሚያድርጉ ፡ መጣላት ፡ ሃይማኖታቸው ፡ እን ዲጠፋ ፡ ብሎ ፡፡

ዩልያኖስም ፡ ክርስቲያንን ፡ ከለከለ ፡ የቀደሙትን ፡ ያረ ማውያንን ፡ ፊሎሶፊያ ፡ ከማስተማር ፡፡ እንደህ ፡ አድርጎ ፡ ብልሃት ፡ ሁሉ ፡ በክርስቲያን ፡ ማኸል ፡ ያለቀ ፡ እንደሆን ፡

ብልዋል :: ወደስ ፡ የክርስቲያን ፡ ብላቴኖች ፡ ይህነን ፡ መ ማር ፡ ቢወደ ፡ ወደ ፡ አረማውያን ፡ መድረሶች ፡ በግድ ፡ ሊ ሔዱ ፡ ነበረ :: ስለዚህ ፡ ግን ፡ ፪ ታላቆች ፡ ተናጋሮች ፡ ሹመ ታቸውን ፡ ተሰናበቱ ፡ ሃይማኖታቸውን ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ :: እርሳቸውም ፡ ጵሮኤሬስዮስ ፡ በአቴና ፡ ዊክቶርዮስም ፡ በሮም ::

ያረማውያንም ፡ ዕውቀት ፡ በክርስቲያን ፡ መድረሶች ፡ ባለቀ ፡ ጊዜ ፡ ፪ ከክርስቲያን ፡ አዋቆች ፡ አጶሊናሪስ ፡ የተ ባሉ ፡ አባትና ፡ ልጅ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ታሪክና ፡ ትም ርት ፡ ለብላቴኖች ፡ አበጁት ፡ ባረማውያን ፡ ዕውቀት ፡ ፈንታ ::

ጥቂት ፡ ደምም ፡ ፈሰሰ ፡ ደግሞ :: ጌዎርጊዮስ ፡ የስክን ድርያ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ክፉ ፡ ሰው ፡ የነበረ ፡ ቆንስታንቲዎስ ፡ ባተናስዮስ ፡ ፈንታ ፡ በስክንድርያ ፡ የሾመው ፡ ባለማሰቡ ፡ አረማውያን ፡ አስቀድሞ ፡ እጅግ ፡ ያስቈጣ ፡ አሁን ፡ በሕ ዝቡ ፡ ሞተ ፡ በስክንድርያ ፡ ከድራኮኒዎስ ፡ ጋራ :: እንደሁ ም ፡ ማርቆስ ፡ ያሬቱሳ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ መከራ ፡ ተቀበለ ፡ አ ስቀድሞ ፡ ያረማውያንን ፡ መቅደስ ፡ አፈርስዋልና ::

ዩልያኖስም ፡ እጅግ ፡ ጊዜ ፡ ከነገሠ ፡ እንደ ፡ ቆንስታንቲ ኖስ ፡ ምናልባት ፡ እጅግ ፡ በጕዳ ፡ በቤተ ፡ ክረስቲያን :: ደ ሮ ፡ እግዚአብሔር ፡ የነገሥታት ፡ ንጉሥ ፡ ይህነን ፡ ጸላት ፡ ለጊዜው ፡ አደረገ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ በርሱ ፡ ይገሥጽ ፡ ዘንድ ፡ ለመጕዳትዋም ፡ አላደረገውም :: የርሱ ፡ ጊዜም ፡ ባለፈ ፡ ጊዜ ፡ ይህነንም ፡ መግሠጫውን ፡ በሳት ፡ ጣለው ::

ዩልያኖስ ፡ በፈረስ ፡ ላይ ፡ ባደረገ ፡ ጾር ፡ ሞተ :: ፈቃዱ ፡ እንዲህ ፡ ነበረ ፡ ያሸነፈ ፡ እንደሆን ፡ እጅግ ፡ ክፉ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ላይ :: በሞተ ፡ ጊዜም ፡ እጁ ን ፡ መሬት ፡ መልቶ ፡ መሬትን ፡ ወደ ፡ ንፋስ ፡ ጣለው ፡ እን ዲህ ፡ ሲል :: አንተ ፡ ገሊላዊ ፡ ሆይ ፡ አሸነፍህ :: ገሊላዊ ፡ ክ ርስቶስ ፡ ማለቱ ፡ ነበረ ::

ዮዊያኑስም ፡ ከዩልያኖስ ፡ በኋላ ፡ ተከተለ :: አንድ ፡ አመትም ፡ ብቻ ፡ ነገሠ :: እርሱም ፡ ክርስቲያን ፡ ሁኖ ፡ የ ኒቅያ ፡ ሃይማኖት ፡ ወደጅ ፡ ለሁሉም ፡ ቸር ፡ ነበረ :: አረማ

ውያንንም ፡ አላገደቸውም ፡ ለክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡፡

ከዮዊያኑስም ፡ በኋላ ፡ ፮፤ ወንድሞቹ ፡ ዋለንቲኒያኑስም ፡ በምዕራብ ፡ ዋለንስም ፡ በምሥራቅ ፡ ነገሡ ፡፡ ዋለንታኒያንም ፡ ቸር ፡ ነበረ ፡ አረማውያንንም ፡ በረፍት ፡ ተዋቸው ፡ እርሱም ፡ የኒቅያ ፡ ሃይማኖት ፡ ወገን ፡ ነበረ ፡፡ ዋለንስ ፡ ግን ፡ አረማውያንንና ፡ የኒቅያውን ፡ ወገን ፡ አሳደደ ፡፡ ግራትያኑስም ፡ አባቱን ፡ ዋሌንቲኒያኑስን ፡ ተከተለ ፡ ፫፻፷፯፤ እስከዚያ ፡ ዘመንም ፡ ድረስ ፡ ልማድ ፡ ነበረ ፡ ቄሣሮች ፡ የካህናት ፡ አለቆች ፡ ይባሉ ፡ ዘንድ ፡ ስለዚህም ፡ ዩሊያኖስ ፡ እጅግ ፡ ይሠው ፡ ነበረ ፡፡ ግራትያኑስ ፡ ግን ፡ ይህነን ፡ ልማድ ፡ ሻረ ፡፡ ባመትም ፡ ፫፹፮፤ ያረማውያንን ፡ ልማድ ፡ ወሰነ ፡፡

ሁለተኛ ፡ ዋለንቲኒያኑስም ፡ ወንድሙን ፡ ግራትያኑስን ፡ በመንግሥት ፡ ተከተለ ፡፡ በዚያ ፡ ዘመንም ፡ አረማውያን ፡ ስለ ፡ ማምለካቸው ፡ አዘኑ ፡ ቄሣርንም ፡ ለመኑት ፡ እንደ ፡ ልማዳቸው ፡ እንዲተውላቸው ፡፡ ደግሞ ፡ አምብሮስዮስ ፡ የሚላንድ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በበጎ ፡ ምክር ፡ ቄሣርን ፡ አጸና ፡ ልቡ ፡ እንዳይታወክ ፡፡ ላረማውያን ፡ እሺ ፡ እንደይል ፡፡

ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅም ፡ በቴዎደስዮስ ፡ መንግሥት ፡ መጀመርያ ፡ ቄሣርን ፡ መከረ ፡ አንዳችን ፡ በግድ ፡ እንዳያደርግ ፡ ባረማውያን ፡ ላይ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ ወንጌል ፡ ለብቻው ፡ ቢኖር ፡ በመንፈስ ፡ ኃይልም ፡ ቢሰበክ ፡ ወንጌል ፡ ባለቤቱ ፡ በኃይሉ ፡ ይገዛል ፡ በሰው ፡ ልብ ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡፡ ሰው ፡ ግን ፡ በውንድሙ ፡ ላይ ፡ ግድ ፡ ቢያደርግ ፡ ለሃይማኖት ፡ ሊያገደው ፡ ብሎ ፡ አይገባም ፡ አይጠቅምም ፡፡

ደግሞ ፡ ቄሣሮች ፡ ወትሮ ፡ አላደረጉም ፡ በዚህ ፡ ባፈ ፡ ወርቅ ፡ ምክር ፡፡ በቴዎደስዮስ ፡ ዘመንም ፡ እጅግ ፡ ሁከት ፡ ስለዚህ ፡ ሆነ ፡፡ እጅግ ፡ መቅደሶችን ፡ አፈረሰዋልና ፡ እጅግ ፡ ግድም ፡ አደረጉ ፡ ባረማውያን ፡ በቴዎደስዮስ ፡ ፈቃድ ፡ ያለ ፡ ፈቃዱም ፡፡ የቴዎደስዮስ ፡ ነገር ፡ ሁለግዜ ፡ አንድ ፡ አልነበረምና ፡፡ በዚህ ፡ መክንያትም ፡ ቴዎፊሎስ ፡ የስክንድርያ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እርሱም ፡ ሥጋዊ ፡ ሰው ፡ የጌታችንን ፡ ም

ሀረት ፡ ንቀ ፡ የክርስቲያንም ፡ ፍቅርና ፡ ጥበብ ፡ በጣም ፡ አ
ጥቶ ፡ ታላቅ ፡ ሁከት ፡ አደረገ ፡ በስክንድርያ ፡ ያረማውያን
ን ፡ መቅደስ ፡ ሲያፈርስ ፡ ከጫወታ ፡ ከመላገጽም ፡ ጋራ ፡ አ
ረማውያን ፡ ሁሉ ፡ እስኪቈጡ ፡ ድረስ ፡ እጅግ ፡ ደምም ፡
እስኪፈስ ፡ ድረስ ፡፡ እንዲሁም ፡ በብዙ ፡ ስፍራ ፡ ሆነ ፡፡ ቴ
ዎደስዮስም ፡ አያሌ ፡ ትእዛዛት ፡ ሰጠ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ በኋ
ላም ፡ ታላቅ ፡ መበደል ፡ ሁኖ ፡ ተቈጠረ ፡ በንጉሥ ፡ ላይ ፡ እ
ንደሚደርስ ፡ ሰው ፡ ጣዖታትን ፡ ቢያመልክ ፡፡
የቴዎደስዮስም ፡ ፪፡ ልጆች ፡ አርካድዮስና ፡ ሆኖርዩ
ስ ፡ ኃይል ፡ አልነበረላቸውም ፡ ያረማውያንን ፡ ማምለክ ፡
በጣም ፡ ይሽሩ ፡ ዘንድ ፡፡ ፪፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ በዚህ ፡ ዘመ
ን ፡ ነበሩ ፡ ከቴዎፊሎስ ፡ ነገር ፡ የተሻለውን ፡ ያደረጉ ፡፡ አ
ውጉስቲኑስ ፡ ክርስቲያንን ፡ መክርዋልና ፡ ለራሳቸው ፡
ለእግዚአብሔር ፡ በውነት ፡ ይገዙ ፡ ዘንድ ፡ በምሳሌም ፡ በ
ትምርትም ፡ በጸሎትም ፡ ይጋደሉ ፡ ዘንድ ፡ የወንድሞቻ
ቸውን ፡ ያረማውያንን ፡ ጣዖታት ፡ በልባቸው ፡ እንዲያፈ
ርሱ ፡ የደንጊያ ፡ የንጨትም ፡ የወርቅም ፡ መቅደሳቸውን ፡
በግድ ፡ ይወስዱባቸው ፡ ዘንድ ፡ ያፈርስዋቸውም ፡ ዘንድ ፡
አይገባም ፡ ብሎ ፡፡ እንዲህም ፡ ክሪሶስቶሞስ ፡ እርሱ
ም ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ባለጠጎችን ፡ ክርስቲያንን ፡ የሚለም
ን ፡ የክርስቲያንን ፡ አብያተ ፡ መቅደሶች ፡ መድረሶችንም ፡
ያበዙ ፡ ዘንድ ፡ እለዚያ ፡ አረማውያን ፡ ወንጌልን ፡ የማያ
ውቁ ፡ ሁሉ ፡ ትምህርትን ፡ ያገኙ ፡ ዘንድ ፡፡
በሮም ፡ መንግሥትም ፡ የነበሩ ፡ አረማውያን ፡ ካመት ፡
፬፻፡ ጀምረው ፡ ማምለካቸውን ፡ በግልጽ ፡ ተከልክሎባቸ
ዋልና ፡ በስውር ፡ ሊያደርጉት ፡ ነበሩ ፡፡
ዩስቲኒያኑስም ፡ አረማውያንን ፡ ፈለገ ፡ እጅግም ፡ መ
ረመራቸው ፡ ማምለካቸውን ፡ ፈጽሞ ፡ ይሽር ፡ ዘንድ ፡፡ አ
ያሌ ፡ ታላቆች ፡ ሰዎች ፡ በዚህ ፡ መክንያት ፡ ሞቱ ፡፡ ሌሎች
ም ፡ ወደ ፡ ፈርስ ፡ መንግሥት ፡ ሸሹ ፡፡ የቀሩትም ፡ ከለዚ
ያ ፡ ጋራ ፡ ክርስቲያናት ፡ ተብለው ፡ የክርስቲያንን ፡ ሕይወ
ት ፡ ያለቀባቸው ፡ ባንድ ፡ ተደበለቁ ፡፡

፪፪፤ አረማውያን ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ በክርስቲያን ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ጻፉ ፡ መጻሕፍት ፡፡ ስለ ፡ ክርስ ቲያን ፡ መምህራንም ፡ ምላሽ ፡፡

ዩልያኖስ ፡ ቄሣር ፡ እጅግ ፡ ጻፈ ፡ በክርስቲያን ፡ ላይ ፡፡ ይህም ፡ ባለማወቁ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ በጸላትነቱ ፡ እን ጅ ፡፡ እንደ ፡ ዓለም ፡ ታላላቆችና ፡ ጠቢባን ፡ የማያምኑ ፡ እርሱ ፡ በክርስቶስ ፡ መዋረድ ፡ ተሰናከለ ፡፡ የክርስቶስ ፡ መንግሥትንም ፡ መዋረድ ፡ አልወደደም ፡ የሥጋውን ፡ መዋ ረድ ፡ ሲያይ ፡ ለመንፈሱን ፡ ምስጋና ፡ ለማየት ፡ ዓይኑ ፡ አ ልተከፈተምና ፡፡ የወንጌልንም ፡ ትምርት ፡ ሁሉ ፡ ክፉ ፡ ፈ ቃዱ ፡ ስለ ፡ ጸላትነቱ ፡ ሳያስተውለው ፡ ተላገጸበት ፡፡

አያሌ ፡ መክሰስ ፡ አረማውያን ፡ ክርስቲያንን ፡ የከሰሱበ ት ፡ ይህ ፡ ነው ፡፡ አረማውያን ፡ አሉ ፡፡ የክርስቲያን ፡ ሃይማ ኖት ፡ አልተዘረጋም ፡ በነገሥታት ፡ ተድላ ፡ ገጽ ፡ እንጅ ፡፡ ደ ሮ ፡ ከክርስቶስ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ቆንስታንቲኖስ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ የሆነላቸው ፡ ሁሉ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ አሰት ፡ ሁኖ ፡ ተገለ ጸበት ፡፡ ደግሞ ፡ ስለ ፡ ክፉ ፡ አካሔዳቸው ፡ ሳይብዋቸው ፡ እርሳቸው ፡ በቅድስና ፡ ባመኑ ፡ ጊዜ ፡፡ ደሮ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ አረማውያን ፡ ያለ ፡ ፈቃዳቸው ፡ ለወንጌል ፡ በጉነት ፡ መ ሰከሩ ፡፡ ደግሞ ፡ የክርስቶስን ፡ ትምርት ፡ በተራራ ፡ ላይ ፡ ሁኖ ፡ ያስተማረውን ፡ ከሰሱ ፡ እንደህ ፡ ሲሉ ፡፡ ክርስቶስ ፡ እንደዘዘ ፡ ቢሆን ፡ ሰው ፡ እንዲደበቅል ፡ ክፉም ፡ በክፉ ፡ እንዳይመልስ ፡ ለሚለምነውም ፡ ሁሉ ፡ ቢሰጥ ፡ መንግሥ ት ፡ ሁሉ ፡ መኖር ፡ አትችልም ፡፡ አውጉስቲኑስ ፡ ግን ፡ እን ደህ ፡ ሲል ፡ መለሰላቸው ፡፡ የታዘዘው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለል ብ ፡ ይደርሳል ፡ ልባችን ፡ ወትሮ ፡ ለትሕትና ፡ ለምህረትም ፡ ለፍቅርም ፡ ሊገዛ ፡ ነውና ፡ በስራው ፡ ግን ፡ ክርስቶስ ፡ ወት ሮ ፡ ለጊዜ ፡ የተሻለውን ፡ ስራ ፡ እናደርግ ፡ ዘንድ ፡ ይፈልጋል ፡፡

አውጉስቲኑስም ፡ ያረማውያን ፡ መክሰስ ፡ ለምላሽ ፡ መ ጽሐፉን ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ ጻፈ ፡ በርሱ ም ፡ ያረማውያንን ፡ አፍ ፡ ዘጋ ፡፡

፫፫፡፡ ስለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ መኽልኽያ ፡ ሃይማኖትን ፡ የከለከለው ። ስለ ፡ ልዩ ፡ ልዩም ፡ መንገድ ፡ ሰው ፡ ወደ ፡ ሃይማኖት ፡ የደረሰበት ፡ በዚህ ፡ ዘመን ።

ታላቅ ፡ መኽልኽያ ፡ በውነትም ፡ ሰውን ፡ ወደ ፡ ክርስቶስ ፡ ከመምጣት ፡ የከለከለው ፡ እንደ ፡ ሁለግዜ ፡ በሰው ፡ ልብ ፡ ኖረ ። ሰው ፡ ኃጢአቱን ፡ ውደ ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ አል መጣም ። ለልዩ ፡ ልዩ ፡ ሰዎችም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገር ፡ ነበረለት ፡ ሊከለክለው ፡ ብሎ ። የተማሩ ፡ የሚመስሉ ፡ የክርስቲያን ፡ ጥበብ ፡ አይበቃም ፡ ነበር ። የተዋበ ፡ ነገርም ፡ የፈለጉ ፡ የሚጻፈጥም ፡ ነገር ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ብዙ ፡ እንደ ፡ ፈለጉት ፡ በወንጌል ፡ አላገኙትም ። ደግሞም ፡ ብዙ ፡ ነበሩ ፡ እንደዪህ ፡ ያሉ ። ሰው ፡ ሁሉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ እንደዪህ ፡ ደግሞ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሃይማኖትና ፡ ማምለክ ፡ ይፈለጋል ፡ አንድም ፡ ለሁሉ ፡ አይሆንም ። አምብሮስዮስ ፡ ግን ፡ የማይላንድ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እንደዪህ ፡ ላሉ ፡ ሰዎች ፡ እንደዪህ ፡ ይላቸዋል ። ኑ ፡ ብምድር ፡ ሁናችሁ ፡ የሰማይን ፡ አካሔድ ፡ ትማሩ ፡ ዘንድ ። ከዚህ ፡ ስንኖር ፡ አካሔዳችን ፡ በላይ ፡ ነው ። ያ ፡ የፈጠረኝ ፡ አምላክ ፡ እርሱ ፡ የሰማይን ፡ ምሥጢር ፡ ባለቤቱ ፡ ያስተምረኝ ፡ ነፍሱን ፡ እንኪ ፡ የማያውቅ ፡ ሰው ፡ ግን ፡ አይደለም ።

ወደ ፡ ሃይማኖት ፡ ሰውን ፡ የወሰደ ፡ መንገድ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነበረ ። ደሮ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መግባትን ፡ የፈለጉ ፡ ሁሉ ፡ ከኃጢአታቸው ፡ መመለስ ፡ አልወደዱም ። አውጉስቲኑስ ፡ እንደዪህ ፡ ይላል ። ስንት ፡ ናቸው ፡ ክርስቶስን ፡ የሚፈልጉ ፡ በምድራዊ ፡ መሻታቸው ፡ ብቻ ፡ በጎ ፡ ያድርግላቸው ፡ ዘንድ ፡ ብለው ። አንድ ፡ ተጸልቶ ፡ የቄስን ፡ ወደጅነትና ፡ ማስታረቅ ፡ ይለምናል ። አንድም ፡ ከግፈኛ ፡ ሰው ፡ ተጨንቆ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይሸሻል ። አንድም ፡ ይህነን ፡ ይለምናል ፡ ሌላም ፡ ሌላውን ። ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ እንደዪህ ፡ ባሉ ፡ ሰዎች ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ትምላለች ። የሱስን ፡ በየሱስ ፡ መክንያት ፡ የሚሹት ፡ ጥቂት ፡ ናቸው ።

አሁንም ፡ እንደዪህ ፡ ያሉ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ደግ ፡ ቄስ ፡ የመጡ ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ እርሱ ፡ ወደ ፡ ክርስቶስ ፡ የሚወስዳቸውን ፡ መንገድ ፡ አሳያቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ነበሩ ፡ እር

ሳቸውም ፡ የሚበዙ ፡ ቀሳውስትና ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ያለ ፡ ምርምር ፡ ልመናቸውን ፡ ያደረጉ ፡ እንዲያውም ፡ ያጠመቀዋቸው ፡፡ እንደሁም ፡ የተጠመቁ ፡ በስራቸው ፡ ክርስቶስን ፡ካዱ ፡፡ አንደንድም ፡ ነበረ ፡ እንደ ፡ ቆንስታንቲኖስ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኃይሉን ፡ ያሳየው ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፍርሃት ም ፡ የመጣበት ፡፡ ብዙም ፡ ነበሩ ፡ ዕረፍትን ፡ የፈለጉ ፡ ከኃጢአታቸው ፡ ለነፍሳቸው ፡፡ አሁንም ፡ ክርስቶስ ፡ ደላል ፡፡ እኔ ፡ አሳርፈችኋለሁ ፡፡ ስለዚህም ፡ እለዚያም ፡ በቁስ ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ ካልኖሩ ፡ ወደ ፡ ክርስቶስም ፡ ሒደው ፡ በርሱ ፡ ዕረፍትን ፡ ከፈለጉ ፡ ባገኙት ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ቀሳውስት ፡ ቃላቸውን ፡ ከክርስቶስ ፡ ቃል ፡ ይልቅ ፡ አክብረው ፡ ተሎ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፍታህ ፡ አሉ ፡ ሳይመረምሩ ፡ ሰውም ፡ በቃላቸው ፡ ቢጸና ፡ በኃጢአት ፡ እንቅልፍ ፡ ቢተኛ ፡ ነበር ፡ በወንጌል ፡ ግን ፡ ዕረፍትን ፡ ከኃጢአት ፡ አላገኝም ፡፡ አያሌም ፡ ነበሩ ፡ የሰውን ፡ ጥበብ ፡ ሁሉ ፡ ደፈትኑ ፡ የነበሩ ፡ በርሱ ፡ ዕረፍትን ፡ ያገኙ ፡ ዘንድ ፡ ለነፍሳቸው ፡ ያም ፡ ሁሉ ፡ እንደይጠቅም ፡ ባዩ ፡ ጊዜ ፡ አንዳችም ፡ ከወንጌል ፡ በቀር ፡ የነፍስን ፡ ራብ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ማጽገብ ፡ እንደይችል ፡ በተማሩ ፡ ጊዜ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወንጌልን ፡ ሰጣቸው ፡ በርሱም ፡ የዘላለምን ፡ ሕይወት ፡ አገኙ ፡፡ እንደህ ፡ አውጉስቲኑስና ፡ ሲኔስዮስ ፡፡

፪፤ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መዘረጋትና ፡ መከራ ፡ ከሮም ፡ መንግሥት ፡ በሚደ ፡፡

የክርስቲያንም ፡ ሃይማኖት ፡ አንደንድ ፡ ጊዜ ፡ ካገር ፡ ወደገር ፡ አለፈ ፡ በነጋደች ፡፡ አንደንድ ፡ ጊዜም ፡ ባረማውያን ፡ ማኻል ፡ በኖሩ ፡ ሞናክሶች ፡፡ አንደንድ ፡ ጊዜም ፡ በስደታቸው ፡ ክርስቲያን ፡ ተሳድደው ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ ሒዱ ፡ ወደ ፡ ደረሱበትም ፡ አገር ፡ በወንጌል ፡ አስተማሩ ፡፡ ብዙ ፡ ጊዜም ፡ ልዩ ፡ አሕዛብ ፡ ክርስቶስን ፡ ተቀበሉ ፡ ክርስቲያን ፡ የተባሉ ፡ የሮም ፡ ሰዎች ፡ ሲጸሉት ፡፡

በዚህ ፡ ዘመንም ፡ ብዙ ፡ አሕዛብ ፡ ከምሥራቅ ፡ ፈለሱ ፡

ወደ ፡ ምዕራብም ፡ መጡ ፡፡ የሮምንም ፡ መንግሥት ፡ አወ
ኩ ፡ አዲሶችንም ፡ መንግሥቶች ፡ ሠሩ ፡፡ እርሳቸውም ፡
ጎቶች ፡ ሁኖችም ፡ ዋንደሎችም ፡ ገርማኖችም ፡ ፈረንጆች
ም ፡፡ እርሳቸውም ፡ የሃይማኖትን ፡ ዘር ፡ በማኸላቸው ፡
ተቀበሉ ፡ በርሱም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሆነች ፡ በመኻከላ
ቸው ፡ በምዕራብ ፡፡ የሮምም ፡ መንግሥት ፡ በወደቀች ፡ ጊ
ዜ ፡ የርሳቸው ፡ መንግሥቶች ፡ የርሳቸውም ፡ ቤተ ፡ ክርስ
ቲያን ፡ ኃይለኞች ፡ ሁነው ፡ ቆሙ ፡፡ ሐዲስ ፡ ሕይወትንም ፡
ተቀበሉ ፡፡ እርሳቸውም ፡ ፈረንጆች ፡ የተባሉ ፡ ናቸው ፡፡

በፋርስ ፡ መንግሥትም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ነበረች ፡
መከራም ፡ ተቀበለች ፡ ከማጎችና ፡ ካይሁድ ፡፡ ቆንስታንቲ
ኖስም ፡ አደራ ፡ ጻፈላቸው ፡ ለፋርስ ፡ ንጉሥ ፡ ለሁለተኛ ፡
ሻጱር ፡፡ በለዚህ ፡ ፪ ፡ መንግሥቶችም ፡ በሮም ፡ መንግሥት
ና ፡ በፋርስ ፡ መንግሥት ፡ መኻከል ፡ ዕርቅ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡
ክርስቲያንም ፡ በፋርስ ፡ መንግሥት ፡ ዐረፉ ፡ በጥል ፡ ጊዜ ፡
ግን ፡ ተሳደዱ ፡፡ ክርስቲያን ፡ የሮም ፡ ወዳጆች ፡ ናቸው ፡ ብ
ለዋልና ፡፡ ደግሞ ፡ ሁሉግዜ ፡ ጸላትነት ፡ ነበረ ፡ በፋርስና ፡ በ
ክርስቲያን ፡ ሃይማኖትና ፡ ማምለክ ፡ መኻከል ፡፡ ከሁሉ
ም ፡ ይልቅ ፡ የተቈጡበት ፡ የመስቀል ፡ ትምህርት ፡ ነው ፡፡

መጀመርያ ፡ መሳደድም ፡ በፋርስ ፡ መንግሥት ፡ ባመት ፡
፫፻፫ ፡ ነበረ ፡ ንጉሥ ፡ ከክርስቲያን ፡ ዘንድ ፡ ግብር ፡ በፈለ
ገ ፡ ጊዜ ፡ ጣዖታትን ፡ እንዲያመልኩ ፡፡ የሰሌውቂያም ፡
ኤጲስቆጶስ ፡ ስምዖን ፡ የሚሉት ፡ እርሱም ፡ ሽማግሌ ፡ ይ
ህነን ፡ ግብር ፡ ከክርስቲያን ፡ ዘንድ ፡ ሊለቅም ፡ ነበረ ፡ ደ
ሮ ፡ ግን ፡ እርሱ ፡ እምቢ ፡ አለ ፡፡ ስለዚህ ፡ ስምዖን ፡ ሊሞ
ት ፡ ፈረደበት ፡፡ የክርስቲያንም ፡ ኤጲስቆጶሳትና ፡ ቀሳውስ
ት ፡ ሁሉ ፡ ሊሞቱ ፡ ኣብያተ ፡ ክርስቲያናትም ፡ ሊፈርሱ ፡ እ
ቃቸውም ፡ ሊረኰስ ፡ ነበር ፡፡ ስምዖንም ፡ ጉጓሺያታዛደስ
ም ፡ ፉሲቅም ፡ ሞቱ ፡ ከ፪ ፡ ቀሳውስት ፡ ጋራ ፡፡

በመጣውም ፡ አመት ፡ ፫፻፵፬ ፡ ስደት ፡ በረታች ፡፡ ክርስቲ
ያን ፡ ሁሉ ፡ ሊሞቱ ፡ ነበረ ፡ ብዞችንም ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡
ገደሉ ፡፡ ባመትም ፡ ፬፲፰ ፡ ደግሞ ፡ ተሳደዱ ፡ ከንጉሥ ፡ ከየ
ዝደገርድና ፡ ከዋራኔስ ፡ በታች ፡፡

በዚህ ፡ ዘመንም ፡ ወንጌል ፡ ወደ ፡ አርሜን ፡ መንግሥት ፡ ደረሰ ። ጎርጎርዮስ ፡ አብራሂ ፡ የተባለ ፡ ወንጌልን ፡ ከዚያ ፡ ሰበከ ፡ በማስተማሩም ፡ ያርሜን ፡ ንጉሥ ፡ ቲሪደቴስ ፡ ሃይማኖትን ፡ ተቀበለ ። ካመት ፡ ፬፻፤ በኋላም ፡ ሚዝሮብ ፡ እስከዚያ ፡ ድረስ ፡ ገና ፡ ባልተማሩ ፡ አስተማረ ። ላርሜን ፡ ወገንም ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ፊደላትና ፡ ጽፈት ፡ አል ነበራቸውምና ፡ ሚዝሮብ ፡ አዲስ ፡ ጽፈት ፡ አወጣላቸው ። መጽሐፍ ፡ ቅዱስንም ፡ ባርሜን ፡ ቋንቋ ፡ አስተረጐመ ።

ባርሜንና ፡ በፋርስ ፡ ምድር ፡ አጠገብ ፡ አንዲት ፡ ታናሽ ፡ መንግሥት ፡ ነበረች ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ኢቤርያ ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ጌዎርጊያ ፡ የተባለች ። አንዲት ፡ ክርስቲያኒቱ ፡ ወደ ፡ ያ ፡ ተማርካ ፡ ባርያዪቱ ፡ ሆነች ፡ ላንድ ፡ ባላገር ፡ ሰው ። ባካሔድዋም ፡ በስራዋም ፡ ለለዚያ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ምሳሌ ፡ ሆነች ። አንድ ፡ ሕፃንም ፡ በዚያ ፡ አገር ፡ በታመመ ፡ ጊዜ ፡ ላገር ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ አደረጎት ፡ እንደዚያ ፡ አገር ፡ ልማድ ፡ ማንም ፡ ለሕማሙ ፡ መድኃኒት ፡ ያወቀ ፡ ቢገኝ ፡ ያሳየው ፡ ዘንድ ፡ ብሎ ። መድኃኒትም ፡ ባልተገኘች ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ክርስቲያኒቱ ፡ ደግሞ ፡ ወሰዱት ። እርስዋ ፡ ግን ፡ አለች ። እኔ ፡ መድኃኒትን ፡ አላውቅም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ክርስቶስ ፡ አምላኬ ፡ መርደት ፡ ይችላል ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንኳ ፡ ባይችል ። እርስዋም ፡ ላሸከረ ፡ ክርስቶስን ፡ ለመነች ፡ ተሰማችም ፡ አሸከርም ፡ ደነ ። ያገር ፡ ንግሥትም ፡ ይህነን ፡ ወሬ ፡ ሰማች ። እርስዋም ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ በታመመች ፡ ጊዜ ፡ ክርስቲያኒቱን ፡ አስጸራች ። ያች ፡ ግን ፡ ታምራት ፡ አድራጊቱ ፡ አይደለሁም ፡ ብላ ፡ እምቢ ፡ አለች ፡ ከመምጣት ። ንግሥትም ፡ ባለቤትዋ ፡ ሰዎችዋ ፡ ባልጋ ፡ ወደ ፡ ክርስቲያኒቱ ፡ ይሸከምዋት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘቻቸው ። ክርስቲያኒቱም ፡ ጸለየች ፡ ለንግሥት ፡ መደን ፡ እርስዋም ፡ ደነች ። ንጉሥም ፡ ይህነን ፡ ሰምቶ ፡ መስጠትን ፡ ይሰጣት ፡ ዘንድ ፡ ወደደ ፡ ደር ፡ ምሽቱ ፡ አለቻው ። ያች ፡ ክርስቲያኒቱ ፡ እንደችን ፡ ከምድራዊ ፡ ክብት ፡ አትቀበልም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ይህነን ፡ ዋጋዋ ፡ ሁኖ ፡ ትቈጥራለች ፡ እኛ ፡ ከርስዋ ፡ ጋራ ፡ አምላክዋን ፡ ብናመልክ ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ንጉሥ ፡ ገና ፡

አልሰማም ፡፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ባደነ ፡ ጊዜ ፡ ጵጋግ ፡ ሁኖ ፡ ምድሪቱ ፡ ተጨለመች ፡፡ እርሱም ፡ ከሰዎቹ ፡ ዘንድ ፡ ተለየ ፡ በምድረ ፡ በዳ ፡ መንገዲም ፡ ጠፋበት ፡፡ አሁን ፡ ስለ ፡ ክርስቲያን ፡ አምላክ ፡ የሰማውን ፡ ነገር ፡ አስቦ ፡ ወደርሱ ፡ ጸሬ ፡ ስለትንም ፡ አደረገ ፡ እግዚአብሔር ፡ እርሱን ፡ በደህና ፡ ወደ ፡ ሰዎቹ ፡ ያደርሰው ፡ እንደሆነ ፡ እርሱን ፡ ያመልክ ፡ ዘንድ ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ጵጋግ ፡ ሔደ ፡ ምድሪቱም ፡ በሬች ፡ እርሱም ፡ ወደ ፡ ሰዎቹ ፡ ደረሰ ፡ የክርስቲያኒቱንም ፡ ነገር ፡ ተማረ ፡ ከምሽቱ ፡ ጋራ ፡፡ እርሱም ፡ ከምሽቱ ፡ ጋራ ፡ ሰዎቹን ፡ አስተማረ ፡ ንጉሥ ፡ ወንደችን ፡ ምሽቱም ፡ ሴቶችን ፡፡ በኋላም ፡ ንጉሥ ፡ ከሮም ፡ መንግሥት ፡ መምህራንን ፡ አስመጣ ፡ መንግሥቱም ፡ ሁሉ ፡ ሃይማኖትን ፡ ተቀበለች ፡፡

በዩስቲኑስና ፡ በዩስቲኒያኑስ ፡ ዘመንም ፡ የክርስቲያን ፡ ትምህርት ፡ ወደ ፡ ላዝዮችና ፡ ወደ ፡ አባስጎች ፡ ደረሰች ፡፡

ደግሞም ፡ ቴዎፊሎስ ፡ ህንደዊ ፡ ቆስማስም ፡ ወንጌልን ፡ በህንድ ፡ አስተማረ ፡፡

በዓረብ ፡ ምድረ ፡ በዳም ፡ በየመንም ፡ የክርስቲያን ፡ ትምህርት ፡ በሞናኮስት ፡ ተዘረጋች ፡፡

በዚህ ፡ ዘመንም ፡ ወንጌል ፡ ወደዚች ፡ ምድር ፡ ወደ ፡ አበሻ ፡ ደረሰች ፡፡ በቈንስታንቲኖስ ፡ ዘመን ፡ አንድ ፡ አዋቂ ፡ ከጢሮስ ፡ አገር ፡ ስሙን ፡ ሜሮጵዮስ ፡ የሚሉት ፡ በኤርትሬ ፡ ባሕር ፡ ዞረ ፡ ባሕርንና ፡ ምድርን ፡ ሰዎችንም ፡ ብልሃታቸውንም ፡ ይመረምር ፡ ዘንድ ፡፡ ወደ ፡ ደረቻም ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ በመርከቡ ፡ ያገር ፡ ሰዎች ፡ ቀመኞች ፡ ሁነው ፡ የመርከብን ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ከሜሮጵዮስ ፡ ጋራ ፡ ገደልዋቸው ፡ ለ፪ ፡ ብላቴኖች ፡ ብቻ ፡ አዘነው ፡ ስማቸውን ፡ ፍሬሜንትዮስና ፡ ኤዴስዮስ ፡ የሚሉት ፡፡ ሁላታቸውንም ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ አመጥዋቸው ፡፡ ንጉሥም ፡ ወደ ፡ ቤቱ ፡ ተቀበላቸው ፡፡ ኤዴስዮስንም ፡ አሳላፊዩን ፡ አደረገው ፡ ፍሬሜንቲዮስም ፡ ጸፊው ፡ ሆነ ፡፡ ንጉሥም ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ንግሥቱ ፡ ፍሬሜንቲዮስን ፡ ታመነች ፡ ልጅዋን ፡ ሐፄን ፡ ያሳድገው ፡

ዘንድ ፡ ፍሩሜንቲዮስም ፡ ያዪ ፡ እንደኔ ፡ ወደስ ፡ ራስ ፡ እንደሆነ ፡ ይላሉ ፡፡ ፍሩሜንትዮስም ፡ የቻለውን ፡ አደረገ ፡ የሃይማኖትን ፡ ዘር ፡ ባበሻ ፡ ይዘራ ፡ ዘንድ ፡፡ ከሌላ ፡ አገርም ፡ ለመጡ ፡ ነጋዶች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ አሰራ ፡ ከርሳቸውም ፡ ጋራ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመለከ ፡ ቄስ ፡ አልተገኘምና ፡፡ ንጉሥም ፡ በኋላ ፡ ሁለታቸውን ፡ አሰነበተ ፡ ወደገራቸው ፡ ይመለሱ ፡ ዘንድ ፡፡ ኤዴስዮስም ፡ ወደ ፡ ጢሮስ ፡ ሔደ ፡ ከዚያም ፡ ቄስ ፡ ሁኖ ፡ ተቀመጠ ፡፡ ፍሩሜንትዮስ ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ አገርም ፡ ፈርመናቶስና ፡ አበ ፡ ሰላማ ፡ የተባለ ፡ ዕረፍት ፡ አልነበረለትም ፡ ያበሻ ፡ መንግሥት ፡ በክርስቶስ ፡ እስትድን ፡ ድረስ ፡፡ ወደ ፡ እስክርድርያም ፡ ሔደ ፡ ከዚያም ፡ አትናስዮስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ሆነ ፡ ባመት ፡ ፫፳፯፡፡ ካታናስዮስም ፡ ኤጲስቆጶስን ፡ ለመነ ፡ ላበሻ ፡ አታናስዮስም ፡ ከፍሩሜንትዮስ ፡ የሚሻል ፡ አይገኝም ፡ ብልዋልና ፡ እርሱን ፡ ቀደሰ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ለዚች ፡ አገር ፡፡ ያም ፡ ተመለሰ ፡፡ ባበሻም ፡ በወንጌል ፡ አስተማረ ፡ እንደሆም ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መጀመርያ ፡ ባበሽ ፡ ሆነ ፡፡ በኋላም ፡ ቴዎፊሎስ ፡ ህንደዊ ፡ መጣ ፡ እርሱም ፡ የአርዮስ ፡ ወገን ፡ ነበረ ፡፡ ቆንስታንቲዎስም ፡ በኋላ ፡ የኒቅያ ፡ ወገን ፡ ባበሻ ፡ ያሳድድ ፡ ዘንድ ፡ ብሎ ፡ ያበሻውን ፡ ንጉሥ ፡ ፍሩሜንትዮስን ፡ ወደ ፡ እስክንድርያ ፡ እንደሰደው ፡ ጌዎርግዮስ ፡ ሃይማኖቱን ፡ ይመረምር ፡ ዘንድ ፡ ጻፈለት ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አልሆነለትም ፡፡

በዩስቲኑስና ፡ በዩስቲኒያኑስ ፡ ዘመንም ፡ ያይሁድ ፡ ንጉሥ ፡ ዙንዋስ ፡ የሚሉት ፡ በዓረብ ፡ አገር ፡ በየመን ፡ ክርስቲያንን ፡ አሳደደ ፡፡ ያበሻ ፡ ንጉሥም ፡ ይህነን ፡ ሰምቶ ፡ ጾር ፡ አደረገ ፡ በዙንዋስ ፡ ላይ ፡ መታውም ፡ መንግሥቱንም ፡ ወስደ ፡ ክርስቲያንን ፡ አብርሃም ፡ የተባለውን ፡ አነገሠ ፡፡ ከዚያ ፡ ወዲያም ፡ አብርሃም ፡ ሲሞት ፡ ዙንዋስ ፡ ተመልሶ ፡ መግዛቱን ፡ ወሰደ ፡ ክርስቲያንንም ፡ አሳደደ ፡ ከመጀመርያው ፡ ጊዜ ፡ ይልቅ ፡፡ ያበሻ ፡ ንጉሥ ፡ ግን ፡ ሁለተኛ ፡ ተመለሰ ፡ ዙንዋስንም ፡ ገደለ ፡ ሌላውንም ፡ መኰንን ፡ ሾመ ፡ በዚያ ፡ አገር ፡ ላይ ፡፡

ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መዘረጋት ፡ በኤውሮጳ ። አን
ድ ፡ መልእክተኛ ፡ በኢርላንድ ፡ ወንጌልን ፡ ያስተማረ ፡
ጳትሪክዩስ ፡ ነበረ ። እርሱም ፡ በስኮትላንድ ፡ ተወለደ ።
አባቱም ፡ ዲያቆን ፡ ሁኖ ፡ በወንጌል ፡ አስተማረው ፡ ነገር ፡
ግን ፡ የወንጌልን ፡ ኃይል ፡ አልተማረም ፡ ወደ ፡ መከራ ፡ እስ
ኪደርስ ፡ ድረስ ። ዕድሜውም ፡ ፲፯፡ አመት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡
የባሕር ፡ ሌቦች ፡ መጡ ፡ ሰርቀውም ፡ ወሰዱት ፡ ከርሳቸ
ው ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ኢርላንድ ፡ ከዚያም ፡ ለንጉሥ ፡ ሼጡት ።
ያገርም ፡ ሰዎች ፡ አረማውያን ፡ ነበሩ ። ንጉሥም ፡ እረኛ ፡
አደረገው ፡ በመንጎቹ ፡ ላይ ። አሁንም ፡ በብቸነቱ ፡ ጊዜ ፡
ከለልቡ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ተመለሰ ፡ ለተማረውም ፡
ወንጌል ፡ አሰበ ። ልቡንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ አጸና ። ፯፡
አመትም ፡ ከተቀመጠ ፡ በኋላ ፡ ፮፡ ግዜ ፡ በሕልም ፡ ታዘዘ ፡
ባንድ ፡ መንግድ ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ይሸሽ ፡ ዘንድ ፡ ከዚያም ፡
ወደገርህ ፡ የሚወስድህ ፡ መርከብ ፡ ኑርዋልና ፡ ብሎ ። ይህ
ንንም ፡ ትእዛዝ ፡ ተከትሎ ፡ ወደገሩ ፡ ደረሰ ። ፲፡ አመትም ፡
ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ተሰርቆ ፡ ወደ ፡ ገልያ ፡ መ
ጠ ፡ ወደ ፡ ፈረንሳዎች ፡ አገር ። የክርስቲያንም ፡ ነጋዶች ፡
አርነት ፡ አወጡት ፡ ወደገሩም ፡ ሰደዱት ። ከዚያም ፡ ሰዎ
ቹን ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ አሰኛቸው ፡ በመምጣቱ ። ጳትሪክዩስ ፡
ግን ፡ ዕረፍት ፡ አልነበረለትም ፡ በሕልሙም ፡ ታዘዘ ፡ ወ
ደ ፡ ኢርላንድ ፡ ይመለስ ፡ ዘንድ ፡ ከዚያም ፡ ያነን ፡ ስራ ፡ ይ
ሰራ ፡ ዘንድ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለርሱ ፡ ደሙን ፡ ያፈሰሰ ። አሁን
ም ፡ ወደ ፡ ገልያ ፡ ሔደ ፡ ከበጎ ፡ ቀሳውስትና ፡ ሞናኮስት
ም ፡ ተጨምሮ ፡ ተማረ ። ከዚያ ፡ በኋላም ፡ ወደ ፡ ኢርላን
ድ ፡ ሔደ ፡ ወንጌልንም ፡ አስተማረ ። የሕዝብም ፡ ካህናት ፡
አሳደዱት ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ የብዙ ፡ ሰዎችን ፡ ል
ብ ፡ ከርሳቸውም ፡ አያሌ ፡ መኳንንት ፡ ወደርሱ ፡ መለሰ ።
ወንጌልንም ፡ ተቀብለው ፡ ምድርን ፡ ሰጡት ፡ ጳትሪክዩስ ፡
በርስዋ ፡ ገዳምን ፡ የሰራበት ። ሞናኮስትንም ፡ አሳደገ ፡
አስተማረም ፡ በዚያ ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ወንጌልን ፡ ያስተምሩ ፡
የነበሩ ።

በዚያ ፡ ዘመንም ፡ የክርስቲያን ፡ ትምርት ፡ ወደ ፡ ጎቶ

ች ፡ ደግሞ ፡ ደረሰች ፡፡ እርሳቸውም ፡ አንድ ፡ ወገን ፡ ነበሩ ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ከምሥራቅ ፡ ወጥተው ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ የ ሔዱ ፡ የሮምንም ፡ መንግሥት ፡ ያወኩዋት ፡ የሮምንም ፡ ከተማ ፡ የቀሙ ፡ በኋላም ፡ በኤውሮጳ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁነ ው ፡ የተቀመጡ ፡፡ ክርስቲያንም ፡ ገና ፡ ሳይሆኑ ፡ ወደ ፡ ሮ ም ፡ መንግሥት ፡ ገብተው ፡ እጅግ ፡ ሰዎችን ፡ ቀሳውስት ፡ ሳ ይቀሩ ፡ መረኩ ፡ የተመረኩትም ፡ የመረኳቸውን ፡ በወንጌ ል ፡ አስተማሩ ፡፡ እጅግም ፡ ለርሳቸው ፡ ያደረገ ፡ ኡልፌለ ስ ፡ ነው ፡ የርሳቸው ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ የሆነ ፡ ከቍንስታንቲኖ ስ ፡ ዘመንም ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ዋለንስ ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ በ መኻከላቸው ፡ ያስተማረ ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ቃል ፡ ወ ደ ፡ ቋንቋቸው ፡ ያስተረጐመ ፡፡ ዮሐንስ ፡ አፈ ፡ ወርቅም ፡ ለ ትምርታቸው ፡ ሰራ ፡፡ እርሱ ፡ የቍንስታንቲኒያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳ ስ ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ያ ፡ የመጡትን ፡ ኀቶች ፡ አስተማረ ፡ ወንጌልንም ፡ ለመስበክ ፡ ቀደሳቸው ፡፡

ሁለተኛ ፡ ምዕራፍ ።

ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዓት ።
ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ተግሣጽ ።
ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ መለየት ፡
በዚያ ፡ ዘመን ።

፩፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዓት ፡ ታሪክ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ።

፪፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መስማማት ፡ ከመንግሥት ፡ ጋራ ።

የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መሆን ፡ ከሮም ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ተለወጠ ። መንግሥት ፡ አስቀድማ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጸላት ፡ ነበረች ፡ ክርስቲያንም ፡ እጅግ ፡ ጊዜ ፡ ተሳደደ ፡ ተጨነቁም ። አሁን ፡ ግን ፡ ቈንስታንቲኖስ ፡ የክርስቲያንን ፡ ሃይማኖት ፡ ከተቀበለ ፡ በኋላ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገዥ ፡ ባረማውያንም ፡ አምልኮ ፡ ላይ ፡ ሆነች ። አሁንም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የመላባት ፡ ከሆነች ፡ እጅግ ፡ መጠቀም ፡ በቻለች ፡ መንግሥትም ፡ ሁሉ ፡ በጥቂት ፡ በጥቂት ፡ የክርስቲያን ፡ መንግሥት ፡ በሆነች ። የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ኀይል ፡ ግን ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጥቂት ፡ ሲሆን ፡ ያለምም ፡ ነገር ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ነገር ፡ ጋራ ፡ ሲደበለቅ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ንጽሕና ፡ ተጐዳችበት ።

ቈንስታንቲኖስም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መፍረድ ፡ አልወደደም ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ፍርድ ፡ ለኤጲስቆጶሳት ፡ ሊተወው ፡ ወደደ ፡ እንጂ ። ባመትም ፡ ፪፲፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ሰው ፡ ሲማጸን ፡ ከኤጲስቆጶሳት ፡ ፍርድ ፡ ወደ ፡ ቄሣር ፡

ፍርድ ፡ እርሱ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡፡ የኤጲስቆጶሳት ፡ ፍርድ ፡ እንዲህ ፡ ይቍጠር ፡ ክርስቶስ ፡ ባለቤቱ ፡ እንደ ፈረደ ፡፡ ደግሞ ፡ ቆንስታንቲኖስ ፡ ደግሞ ፡ በሮም ፡ መንግሥት ፡ ላይ ፡ የተሾመ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ባርያ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ወደደ ፡ የርሱን ፡ ማገልገል ፡ ያበዛ ፡ ዘንድ ፡፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ ከኤጲስቆጶሳት ፡ ጋራ ፡ ሲበላ ፡ እርሱ ፡ በመጫወት ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ፡፡ እኔ ፡ ደግሜ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ነኝ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሜደ ፡ ያለው ፡ ነገር ፡ ጠባቂ ፡፡ 'ኤጲስቆጶስ' ፡ ማለቱ ፡ ጠባቂ ፡ ነውና ፡፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሜዳ ፡ የሚሆን ፡ ማለት ፡ መንግሥት ፡ ነው ፡፡ የቆንስታንቲኖስ ፡ ማለትም ፡ ይህ ፡ ነበረ ፡፡ እላንተ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጠባቆች ፡ እንድትሆኑ ፡ እንደሁም ፡ እኔ ፡ የመንግሥት ፡ ጠባቂ ፡ ነኝ ፡፡ ይህነንም ፡ ነገሩን ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ አስተረጐሙ ፡ እርሱ ፡ እንደለ ፡፡ እኔ ፡ እንደላንተ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ነኝ ፡፡ እላንተ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ውሥጣዊን ፡ ነገር ፡ እርሱንም ፡ ትምርትና ፡ ማምለክ ፡ ትጠብቃላችሁ ፡ እኔም ፡ የሜደዊን ፡ ነገርዋን ፡ እጠብቃለሁ ፡ እርሱም ፡ መግዛትዋንና ፡ ሜደዊ ፡ ሥርዓትዋን ፡፡ እንኪያስ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡ በተጻሉ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ትምርት ፡ ቆንስታንቲኖስ ፡ ማስታረቃቸውን ፡ ተግባሩን ፡ አደረገ ፡፡ ስለዚህም ፡ ለመታረቅ ፡ መከራቸው ፡ ባልሰሙም ፡ ጊዜ ፡ በቸሎቱ ፡ የነበረውን ፡ አደረገ ፡፡ በመንግሥቱ ፡ ሁሉ ፡ ከተገኙ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ሰበሰበ ፡ በርሳቸው ፡ ጉባኤም ፡ የተቍረጠውን ፡ ነገር ፡ ሕግን ፡ ቍጠሩት ፡ ለመንግሥቱ ፡ ሁሉ ፡፡ ይህነንም ፡ ሕግ ፡ የጠበቁ ፡ ክርስቲያን ፡ የመንግሥቱ ፡ በረከት ፡ ሆነላቸው ፡፡ ያልጠበቁት ፡ ግን ፡ የመንግሥትን ፡ ሕግ ፡ እንደ ፡ በደሉ ፡ ተቍጠሩ ፡፡

አሁንም ፡ እንዴት ፡ ሆነ ፡፡ የኤጲስቆጶሳት ፡ ጉባኤ ፡ በተሰበሰቡ ፡ ጊዜ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ የ፲፤ ወገን ፡ ነበሩ ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡ የተከራከሩ ፡፡ በዚያም ፡ ክርክር ፡ እለዚያ ፡ ፲፤ አንድ ፡ ካልሆኑ ፡ ያሸነፈው ፡ ወገን ፡ ነገር ፡ ለትእዛዝ ፡ ሆነ ፡፡ አሁንም ፡ ሥርዓት ፡ እንዲህ ፡ ሆነ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ብቻ ፡ የትምርትን ፡ ነገር ፡ እንደ ቍርጡ ፡፡ ደግሞ ፡ እንዲህ ፡ አ

ልሆነም ፡፡ ቄሣሮችና ፡ ወገኖቻቸው ፡ የወደዱት ፡ ትምህር
ት ፡ ሁለግዜ ፡ አሸነፈ ፡ ኤጲስቆጶሳትም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ የቄ
ሣርን ፡ ባለምዋልነት ፡ ፈለጉ ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጸጋ ፡ ይ
ልቅ ፡፡ እንዲህ ፡ ይገለጻል ፡ በኒቅያ ፡ ሲኖዶስ ፡ የምሥራቅ ፡
ኤጲስቆጶሳት ፡ የጉባኤን ፡ ነገር ፡ እንዳልተቀበሉ ፡ ስለ ፡ ቆ
ንስታንቲኖስ ፡ ፈቃድ ፡ ካልሆነ ፡፡ ሁለተኛም ፡ ቴዎዶስዮስ ፡
በመጀመርያ ፡ ሲኖዶስ ፡ በኤፌሶን ፡ አለ ፡፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ያ
ልሆነ ፡ በሲኖዶስ ፡ እንደይናገር ፡፡ ደግ ፡ ግን ፡ የቄሣር ፡ ቤት ፡
ሰዎች ፡ የቄርሎስ ፡ ወዳጆች ፡ የነበሩ ፡ አታለሉት ፡ እርሱ ፡
እሺ ፡ እስኪላቸው ፡ ድረስ ፡፡

ኤጲስቆጶሳትም ፡ ሁሉ ፡ ዝም ፡ አሉም ፡ ለመንግሥ
ት ፡ መግዛት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡፡ የጵሉስዩም ፡ ኢሲዶር
ስ ፡ ቴዎደሮስን ፡ ጻፈ ፡፡ ለመንግሥት ፡ ዕረፍት ፡ እንደይሆ
ን ፡ እርሱ ፡ የቤተ ፡ ሰዎቹን ፡ ክርክር ፡ ባይከለክል ፡፡ ሂላር
ዩስም ፡ የጶዋቴ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ቆንስታንቲዎስን ፡ አለው ፡፡
እርሰዎ ፡ ስለዚህ ፡ ይገዛሉ ፡ ይጠብቁማል ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በ
ደህና ፡ አርነት ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ዕ
ረፍት ፡ አይመለስም ፡ ቍስሉም ፡ አይድንም ፡ ሰው ፡ ሁ
ሉ ፡ ከባርነት ፡ ወጥተው ፡ እንደ ፡ ልባቸው ፡ ሃይማኖት ፡ ሳ
ይኖሩ ፡፡ ለውነተኛ ፡ ሃይማኖትም ፡ እንኳ ፡ ግድ ፡ ቢጨመ
ር ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ቢከለክልዎ ፡ እንዲህ ፡ ሲልዎ ፡፡ እግዚ
አብሔር ፡ ያለም ፡ ሁሉ ፡ ጌታ ፡ ነው ፡ እርሱ ፡ በግድ ፡ የተደ
ረገውን ፡ መታዘዝ ፡ አይሻም ፡ የተገደውንም ፡ ሃይማኖት ፡
ማስታወቅ ፡ አይወድም ፡፡ እርሱም ፡ ግብዝነትን ፡ ይጸላ
ል ፡ በቅንም ፡ ማምለክ ፡ ብቻ ፡ ይፈልጋል ፡፡

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ መንግሥት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ምግብ
ና ፡ መኖር ፡ ጠበቀች ፡፡ ቆንስታንቲኖስ ፡ ባመት ፡ ፫፻፳፩፡ በትእ
ዛዝ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥልጣን ፡ ሰጠ ፡ ርስትን ፡ ለመ
ቀበል ፡፡ በዚህ ፡ መክንያትም ፡ ብዙ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያ
ናት ፡ እጅግ ፡ ባለጠጎች ፡ ሆኑ ፡፡ ያለምን ፡ ነገር ፡ የወደዱ ፡
ኤጲስቆጶሳት ፡ እጅግ ፡ ከብት ፡ ለቀሙ ፡ ከሞቱ ፡ ሰዎች ፡
እሺ ፡ ያሰኙቸው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ያወርሱ ፡ ዘንድ ፡፡
በዘመኑም ፡ በኃጢአት ፡ ይኖር ፡ የነበረ ፡ ሰው ፡ ሲሞት ፡ ከ

ብቱን፡ለቤተ፡ክርስቲያን፡ሰጠ፡በዚህ፡መስጠት፡የነፍሱን፡ዕረፍት፡ይገዛ፡ዘንድ። በኋ፡መምህራን፡ግን፡እንደዚህ፡ሥልጣናቸው፡አላደረጉም፡ብዙ፡ጊዜም፡ርስትን፡አልተቀበሉም፡ሰው፡በሰጡት፡ጊዜ። ስለዚህም፡ከክፎች፡ተጸሉ። ስላዚህም፡አፈ፡ወርቅንና፡አውጉስቲኑስን፡ጸሉ፡እሌህ፡፪፤ አብያተ፡ክርስቲያናታቸውን፡ባለጠጎች፡አላደረጉምና። ደህና፡ኤጲስቆጶሳትም፡ለቤተ፡ክርስቲያን፡የተሰጠውን፡ግንዘብ፡ፋቅርን፡በማድረግ፡ፈጁት። እለዚህም፡ላብያተ፡ክርስቲያናታቸው፡ልዩን፡ቤት፡ሰሩ፡ለንገዶች፡ለነዲያንም፡ለደከሙም፡ሸማግሎች፡ለድውያንም፡አባትና፡እናት፡ለሌላቸውም፡አሽከሮች፡ለሁላቸው፡ረዴት። እንዲህም፡ባሲልዮስ፡የቂሣርያ፡ኤጲስቆጶስ፡ታላቅ፡ቤትን፡ሠራ፡ከተማውን፡የመሰለች፡ባሲልያስም፡የተባለች። በዚች፡ቤትም፡ለንግዶችና፡ለነዲያን፡ለድውያንም፡የሚሹት፡ረዴት፡ሁሉ፡ተገኝበት። ይች፡ቤትም፡በበሲልዮስ፡አገር፡በቄሣርያ፡ነበረች፡እርሱም፡ለቤተ፡ክርስቲያን፡ሁሉ፡ከርሱ፡በታች፡ለነበረች፡እንዲህ፡ያለውን፡የፋቅርን፡ቤት፡አሠራ።

ቆንስታንቲኖስም፡ለቤተ፡ክርስቲያን፡በጎ፡ሊያድርግ፡ብሎ፡ቀሳውስትንና፡ኤጲስቆጶሳትን፡ከልዩ፡ልዩ፡ከመንግሥት፡ማገልገልና፡ግብር፡ፈታቸው። ደህ፡ግን፡ለቤተ፡ክርስቲያንና፡ለመንግሥት፡ክፉ፡ሆነ። ብዙ፡ሰዎች፡ነበሩና፡የመንግሥትን፡ማገልገል፡ያልወደዱ፡ስለዚህም፡ወደ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ደቀደሱ፡ዘንድ፡መጡ።

ቆንስታንቲኖስም፡ለቤተ፡ክርስቲያን፡ትፈርድ፡ዘንድ፡ሥልጣን፡ሰጣት። በዚህ፡መክንያትም፡ቀሳውስትና፡ኤጲስቆጶሳት፡ያለምን፡ነገር፡ለማድረግ፡ተጸሩ።

ኤጲስቆጶሳትና፡ቀሳውስት፡በዚህ፡ዘመን፡ተቻላቸው፡እጅግ፡ደጠቅሙ፡ዘንድ፡በምክራቸው፡በመጠበቃቸውም፡ከመኳንንት፡ኃራ፡ግፍ፡እንዳያደርጉ፡ሲከለክልዋቸው። እንደህም፡ባንጾኪያ፡ሆነ፡ባመት፡፫፹፯፤ ቄሣር፡ቴዎደስዮስ፡ግብርን፡ባበዛ፡ጊዜ፡ሁከት፡ሲነ

ሣ ፡፡ ስለዚህም ፡ ቄሣር ፡ ተቈጣ ፡ ሰውም ፡ ሁሉ ፡ ከቄሣ
ር ፡ ቍጣ ፡ ፈራ ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ያንጾኪያ ፡ ኤጲስቆጶ
ስ ፡ ፍላዊያኖስ ፡ የሚሉት ፡ እርሱም ፡ አሮጌና ፡ ድውይ ፡ የነ
በረ ፡ ወደ ፡ ቈንስታንቲኒያ ፡ ሔደ ፡ ወደ ፡ ቴዎደስዩስም ፡ ተ
ቸኵሎ ፡ አለውም ፡፡ እኔ ፡ የሁላችን ፡ ጌታ ፡ መልክተኛ ፡ ሁ
ኜ ፡ መጣሁ ፡ የርሱን ፡ ቃል ፡ እናገርዎ ፡ ዘንድ ፡ እንዲህ ፡ ሲ
ል ፡፡ ይቅር ፡ ብትሉ ፡ ለሰው ፡ የሰማዩ ፡ አባታችሁም ፡ ይቅ
ር ፡ ይላችኋል ፡፡ ይህነን ፡ ነገሩንም ፡ በፋሲካ ፡ መክንያት ፡
ሲያጸና ፡ ወደ ፡ ቄሣር ፡ ልብ ፡ ገባ ፡ ቄሣርም ፡ እንዲህ ፡ ሲ
ል ፡ ጮኸ ፡፡ እኔ ፡ ሰው ፡ ሁኜ ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ አድርጋለሁን ፡
በሰው ፡ ላይ ፡ ያለውን ፡ ቍጣዬን ፡ ብተው ፡ ያለም ፡ ሁሉ ፡
ጌታ ፡ ስለኛ ፡ የባርነት ፡ ምሳሌ ፡ የተቀበለ ፡ ቸርነትም ፡ ያደ
ረገላቸው ፡ ከርሳቸው ፡ የተሰቀለ ፡ እርሱ ፡ ስለ ፡ ሰቀሉት ፡
ወደባቱ ፡ ሲጸሊ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ ይቅር ፡ ብልላቸው ፡ የሚ
ያድርጉትን ፡ አያውቁምና ፡፡ ፍላዊያኖስንም ፡ አዘዘ ፡ ወ
ደ ፡ አንጾኪያ ፡ እንዲመለስ ፡ እንዲቸኵልም ፡ የምስራች
ን ፡ ይነግራቸው ፡ ዘንድ ፡ ፋሲካ ፡ ሳይደርስ ፡ ቄሣር ፡ ለሆነ
ው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ይቅር ፡ እንዲላቸው ፡ እንዲረሳውም ፡፡
እንዲህም ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ እጅግ ፡ ጊዜ ፡ የባልቴቶችና ፡
አባትና ፡ እናት ፡ የሌላቸው ፡ አሽከሮች ፡ ጠባቆች ፡ ሆኑ ፡፡
እንዲህም ፡ ሆነ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መሸሸጊዮች ፡ ሲ
ሆኑ ። የተሳደዱ ፡ ወዲያ ፡ ሸሹ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ካሳደጆቻቸ
ው ፡ ጋሪ ፡ እስኪያስታርቃቸው ፡ ድረስ ፡፡ ይህነን ፡ ልማድ ፡
ክርስቲያን ፡ ካረማውያንና ፡ ካይሁድ ፡ ተቀበሉ ፡ ከመቅደ
ሶቻቸው ፡፡ የቴዎደስዮስ ፡ ባለምዋል ፡ ኤውትሮጵዮስ ፡ እ
ርሱም ፡ ግፈኛ ፡ ሰው ፡ ቄሣርን ፡ እሺ ፡ አሰኘው ፡ ትእዛዝ
ን ፡ ሊሰጥ ፡ ይህነን ፡ ነገር ፡ የሚከለክል ፡፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ብ
ዙ ፡ ሰዎችን ፡ ኤውትሮጵዮስ ፡ ያሳደዳቸውን ፡ በቤተ ፡ ክር
ስቲያኑ ፡ ተቀብልዋልና ፡፡ በተከተለው ፡ አመት ፡ ግን ፡ ኤ
ውትሮጵዮስ ፡ ባለቤቱ ፡ መከሪን ፡ አገኝቶ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክ
ርስቲያን ፡ ሸሸ ፡ ከዚያም ፡ አደሪውን ፡ ፈለገ ፡ አፈ ፡ ወር
ቅም ፡ ከዚያ ፡ ተቀበለው ፡፡

ባመትም ፡ ፬፻፴፩፡ ትእዛዝ ፡ ተሰጠ ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡፡

ወደ ፡ ቤት ፡ ክርስቲያን ፡ ጋኻ ፡ ጾር ፡ ሳይዝ ፡ የሚሸሽ ፡ ሁሉ ፡ አደራ ፡ ይሆንለታል ፡ ማንምም ፡ በግድ ፡ አያውጣው ፡፡ ጋኻ ፡ ጾር ፡ ግን ፡ ይዞ ፡ በግድ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ክርስቲያን ፡ የሚገባ ፡ አደራውን ፡ ይፈልግ ፡ ዘንድ ፡ በግድ ፡ ያውጡት ፡፡ ባመት ፡ ፱፻፪፡ ሌላ ፡ ትእዛዝ ፡ ወጣ ፡ ያሚል ፡፡ ባርያ ፡ ወይስ ፡ ሎሌ ፡ ጋኻ ፡ ጾርን ፡ ሳይዝ ፡ አደራውን ፡ ቢፈልግ ፡ ወደ ፡ ቤት ፡ ክርስቲያን ፡ ይቀበሉት ፡ ቄስም ፡ ካንድ ፡ ቀን ፡ የሚበዛ ፡ አይቈይ ፡ የባርያውን ፡ ወይስ ፡ የሎሌውን ፡ ጌታ ፡ ይናገር ፡ ዘንድ ፡፡ ጌታው ፡ ወይስ ፡ የተበደለ ፡ ሁሉ ፡ በቤት ፡ ክርስቲያን ፡ መክንያት ፡ ይቅር ፡ ይለው ፡ ዘንድ ፡ ወደርሱም ፡ በቸርነት ፡ ይቀበለው ፡ ዘንድ ፡፡

፪፪፡ የቤት ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዓት ፡ በውሥጥዋ ፡፡

በዚህ ፡ ዘመንም ፡ በቤት ፡ ክርስቲያን ፡ የተለወጠ ፡ የተጨመረም ፡ ስለ ፡ መንግሥት ፡ መለወጥ ፡ ሆነ ፡፡

በዚህ ፡ ዘመንም ፡ ያች ፡ በቀደመው ፡ ዘመን ፡ የጀመረች ፡ ስሕተት ፡ በረታች ፡ የክህነት ፡ ወገን ፡ እንደ ፡ ተለዩ ፡ ከሕዝብ ፡ ወገን ፡፡ ስለዚህም ፡ ብዙ ፡ ቀሳውስትና ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ የክርስቲያንን ፡ ሕዝብ ፡ ይንቁ ፡ ዘንድ ፡ ማጋባትንም ፡ ሌላውንም ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ የሚያገባውን ፡ ንብረት ፡ ርኩስ ፡ ሁኖ ፡ ይቈጥሩ ፡ ዘንድ ፡ ራሳቸውንም ፡ ከሌሎች ፡ ያከብሩ ፡ ዘንድ ፡ የክርስቶስ ፡ ሎላልት ፡ ነኝ ፡ ሲሉ ፡ ሳያስቡም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሚኖርበት ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ የክርስቶስ ፡ ሎሌ ፡ የክርስቶስ ፡ ካህንና ፡ ንጉሥም ፡ እንዲሆን ፡፡

ባመትም ፡ ፫፻፭፡ በኤልዊራ ፡ የተሰበሰበች ፡ ሲኖደስ ፡ ኤጲስቆጶሳትን ፡ ቀሳውስትንም ፡ ዲያቆናትንም ፡ ከማጋባት ፡ ከለከለች ፡፡ በኒቅያ ፡ ሲኖደስም ፡ ሰዎች ፡ ነበሩ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ትእዛዝ ፡ የፈለጉ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ጰፍኑትዮስ ፡ እርሱም ፡ ኤጲስቆጶስና ፡ ሰማዕት ፡ ባሕታዊም ፡ የነበረ ፡ ይህነን ፡ ከለከለ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ ማጋባት ፡ ደግሞ ፡ የተቀደሰች ፡ ንብረት ፡ ናት ፡ ጳውሎስ ፡ እንደለ ፡፡ ያገቡም ፡ ቀሳውስት ፡ ደግሞ ፡ ይችላሉ ፡ በበኁ ፡ አካሒደቸው ፡ ይመ

ላለቡ ፡ ዘንድ ፡፡ ስለዚህም ፡ በላያቸው ፡ ቀምበር ፡ አይጫ
ን ፡ የሰው ፡ ድካም ፡ የማይችል ፡ ይሸከመው ፡ ዘንድ ፡፡ ነገር ፡
ግን ፡ በፊት ፡ የተሰራች ፡ ሥርዓት ፡ አልተለወጠችም ፡ ቄስ ፡
ከቀደሲው ፡ በኋላ ፡ ምሽትን ፡ እንዲያገባ ፡፡ የሮም ፡ ኤጲ
ስቆጶስ ፡ ሲሪኪዩስ ፡ ግን ፡ መጀመርያ ፡ ትእዛዝ ፡ አወጣ ፡
ለተቀደሰ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንደደገባ ፡ ምሽትን ፡ ያገባ ፡ ዘን
ድ ፡ እንዴህ ፡ ሲል ፡፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በሌላ ፡ በተቀደሰ ፡
ሥጋ ፡ አንጅ ፡ ይኖር ፡ ዘንድን ፡ ይችላል ፡፡ በዚህ ፡ ነገርም ፡
፪፤ ስሕተት ፡ ነበረ ፡፡ አንድ ፡ መጋባት ፡ ቅድስናውን ፡ አንድት
ክለክል ፡፡ ሁለተኛውም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በካህናት ፡ ብ
ቻ ፡ እንዲኖር ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሌሎች ፡ ነበሩ ፡ በዚህ ፡ የመጉ
ቱ ፡ ክርሳቸውም ፡ ዮዊንያኑስና ፡ ዊጊላንቲዩስ ፡፡

የካህናት ፡ መሆን ፡ ከሌሎች ፡ ክርስቲያን ፡ መሆን ፡ አን
ድ ፡ ጊዜ ፡ ከተወሰነ ፡ ከተለየም ፡ በኋላ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱ
ስ ፡ ኃይልም ፡ ወደ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እጅ ፡ በሰው ፡ አሳብና ፡
በሰው ፡ ትምህርት ፡ ከተሰጠ ፡ በኋላ ፡ ሰውም ፡ ሲያስተ
ምር ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እጁን ፡ በጫነ ፡ ጊዜ ፡ በቄስና ፡ በዲያቆ
ን ፡ ላይ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ በግድ ፡ እንዲ
መጣ ፡ እንዲገባም ፡ በቄስ ፡ ወይስ ፡ በዲያቆን ፡ ሰውነት ፡
በሌላም ፡ አይሆንም ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ክህነት ፡ የደረሱ ፡ ሰ
ዎች ፡ በዙ ፡ ለክህነት ፡ ያልተሰናደ ፡ ያልተማሩም ፡ መን
ፈስ ፡ ቅዱስም ፡ የሌለባቸው ፡፡ እርሳቸውም ፡ ተቀደሱ ፡፡
በኋላም ፡ ልባቸውን ፡ አኩበረው ፡ አሁን ፡ ደንቍርነታቸ
ው ፡ አለማወቃቸውም ፡ ርኵሰታቸውም ፡ ሁሉ ፡ ሳይቅር ፡
መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንዲኖርባቸው ፡ አሉ ፡ በልባቸው ፡፡ የ
ሚነገሩትንም ፡ የሚያድርጉትንም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ መንፈ
ስ ፡ ቅዱስ ፡ እንዲቀድሰው ፡ እንዲያጸናውም ፡፡ እንዴህ ፡
ካሉም ፡ ጋራ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ከናትያንዝ ፡ አፈ ፡ ወርቅም ፡
አውጉስቲኑስም ፡ እጅግ ፡ ተከራከሩ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ መድ
ረሶች ፡ ታጡ ፡፡ ፪፤ ታላቆች ፡ መድረሶች ፡ ነበሩ ፡ አንዲት ፡ በ
ስክንድርያ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ያ ፡ አዋቂ ፡ ዲ ዲሞስ ፡ ያስ
ተማረበት ፡፡ እርሱም ፡ ከሕፃንነቱ ፡ ጀምሮ ፡ ዕውር ፡ ሲሆ
ን ፡ ኩበዙ ፡ መምህራን ፡ በዘመኑ ፡ በውቀቱ ፡ በለጠ ፡፡ ደ

ግሞም ፡ ያንጾኪያ ፡ መድረሳ ፡ ጀመረች ፡ የታወቀች ፡ ትሆ ን ፡ ዘንድ ፡፡ ሌሎችም ፡ ክህነትን ፡ የፈለጉ ፡ ከኤጲስቆጶሳ ት ፡ ተማሩ ፡ እንደሁም ፡ አውጉስቲኑስና ፡ ኤውሴቢዮስ ፡ ከቁርኬሊ ፡ ብላቴኖችን ፡ ለክህነት ፡ አስተማሩ ፡፡

ያልተፈተነም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ክህነት ፡ እንዳይደርስ ፡ ብላ ፡ የኒቅያ ፡ ሲኖዶስ ፡ በ፱፡ ቃኖኑ ፡ አዘዘች ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ጥቂት ፡ ወራት ፡ ብቻ ፡ ከተቀመጠ ፡ በኋላ ፡ ቄስ ፡ ወይስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ እንዳይቀደስ ፡፡ ለመፈተን ፡ እ ጅግ ፡ ወራት ፡ ይፈለጋል ፡፡ በሰርዲካም ፡ ሲኖዶስ ፡ ባመት ፡ ፫፻፵፯፡ አዘዙ ፡ በ፲፡ ቃኖን ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡፡ ባለጠጋ ፡ ሰው ፡ ወይስ ፡ መፍረድ ፡ የተማረ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ እንዳይሆን ፡ ነባ ቢ ፡ ዲያቆንም ፡ ቄስም ፡ ካልሆነ ፡ በለዚያም ፡ ሹመቶ ች ፡ ኑሮ ፡ ካልተፈተነ ፡፡

በዚያ ፡ ዘመንም ፡ ያች ፡ ልማድ ፡ ገና ፡ አልጠፋም ፡ ኤ ጲስቆጶስና ፡ ቄስ ፡ ባለቀ ፡ ጊዜ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ከሕዝብ ፡ ጋ ራ ፡ አዲሶቹን ፡ እንዲመርጹ ፡፡ በዚህ ፡ ዘመንም ፡ የኤጲስቆ ጶስና ፡ የቄስ ፡ ሥርዓት ፡ ተጨምረው ፡ ተለዩ ፡ እርሶ ፡ በር ሳቸው ፡፡ የኤጲስቆጶስ ፡ ተግባር ፡ ብቻ ፡ ቅዳሴ ፡ ሆነ ፡ ቀሳ ውስትንና ፡ ሜሮምን ፡ እንዲቀድስ ፡ የተጠመቁትንም ፡ እ ንዲያጸና ፡ ለቀሳውስትም ፡ ሥልጣን ፡ እንዲሰጥ ፡ ኃጢአ ትን ፡ ይቅር ፡ ለማለት ፡፡ ኤጲስቆጶስም ፡ በዚህ ፡ እንደ ፡ በ ለጠ ፡ ከቄስ ፡ እንደሁም ፡ ቄስ ፡ በለጠ ፡ ከዲያቆን ፡፡ ዲያ ቆንም ፡ ካንባቢ ፡፡ ለዲያቆናትም ፡ አለቃ ፡ አደረጉላቸው ፡ ለብቻው ፡፡ ለቀሳውስትም ፡ የቀሳውስትን ፡ አለቃ ፡ ለብቻ ው ፡፡ አለዚህም ፡ ፪፡ የዲያቆናትንና ፡ የቀሳውስትን ፡ ጉዳ ይ ፡ ወደ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ያደርሶት ፡ ዘንድ ፡ ነበሩ ፡፡ ዲያቆኒ ሶችም ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ተሻሩ ፡፡

ነገር ፡ ግን ፡ አያሌ ፡ አዲሶች ፡ ሹመቶች ፡ ተነሡ ፡፡ በኽል ኬደን ፡ ሲኖዶስ ፡ ትእዛዝ ፡ ወጣ ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ ሁሉ ፡ አ ንድ ፡ ኦይቆኖሞስ ፡ እንዲሆንለት ፡ የቤት ፡ ክርስቲያን ን ፡ ገንዘብ ፡ የሚጠብቅ ፡ ኤጲስቆጶስም ፡ ከርሶ ፡ ጋራ ፡ የ ሚቈጥር ፡፡ ደግሞ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ ፈራጅ ፡ ተደረገ ፡ በመጣላት ፡ ሁሉ ፡ የሚፈርድላት ፡፡ ደግሞም ፡

ኖታርዮችን ፡ ተደረጉላት ፡ ማለት ፡ ቶሎ ፡ የሚጽፉ ፡ ጻፎች ፡፡ እርሳቸውም ፡ በሲኖደስ ፡ ሁሉ ፡ የተናገረውን ፡ ነገር ፡ የተሰራውንም ፡ የጸናውንም ፡ ትእዛዝ ፡ ሁሉ ፡ ተችኮሉ ው ፡ ሊጽፉ ፡ ነበሩ ፡፡ ደግሞም ፡ ድውያንን ፡ ለመርዳትና ፡ ለመጠበቅ ፡ ሙታንንም ፡ ለመቅበር ፡ ልዩ ፡ ሹመትን ፡ ሰሩ ፡፡

በከተሞች ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ነበሩ ፡ ባንዲት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ያገለገሉ ፡ ከቀሳውስትና ፡ ከዲያቆናት ፡ ጋራ ፡፡ አንዲት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ አትባቃምና ፡ ለከተማ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ ሌሎች ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ተሠሩ ፡ ከኤጲስቆጶስ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በታች ፡ የሆኑ ፡፡

የሜትሮጶሊታኖችም ፡ ሥርዓት ፡ በቀደመ ፡ ዘመን ፡ የተደረገች ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ጸናች ፡፡ በሜትሮጶሊስ ፡ በመንግሥት ፡ ክፍል ፡ ከተማ ፡ የነበረ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በሌሎች ፡ በክፍሉ ፡ ከነበሩ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ በላይ ፡ ነበረ ፡ ጠበቃቸውም ፡፡ በየክፍሉም ፡ ፬፡ ሲኖዶች ፡ ነበሩ ፡ በያመት ፡ ሜትሮጶሊታኖስም ፡ የኤጲስቆጶሳት ፡ አለቃ ፡ በሲኖደስ ፡ በላያቸው ፡ ተቀመጠ ፡ የምክርም ፡ መሪ ፡ ነበረ ፡፡ በሜትሮጶሊታኖችም ፡ መኻከል ፡ አያሌ ፡ ነበሩ ፡ ከሌሎች ፡ የበለጡ ፡ በኒቅያ ፡ ሲኖደስ ፡ እንደ ፡ ተባለ ፡፡ የሮም ፡ የእስክንድርያም ፡ ያንጾኪያም ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ሥልጣን ፡ እንደላቸው ፡ ከሌሎት ፡ በላይ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡፡ ለለዚህ ፡ ፫፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ደግሞ ፡ ፬፡ ተጨመሩ ፡ ፭፡ በቍስጥንጥንያ ፡ ፭ም ፡ በየሩሳሌም ፡፡ የቍስጥንጥንያም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ሥልጣን ፡ ተቀበለ ፡ በሁለተኛ ፡ ኦይኩሜኒቄ ፡ ሲኖደስ ፡ ፫፻፹፩፡ በቍስጥንጥንያ ፡ በተሰበሰበች ፡ መጀመርያ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ከሮም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በኋላ ፡፡ በኻልቤደንም ፡ ሲኖደስ ፡ ባመት ፡ ፬፻፶፩፡ ይህ ፡ ጸና ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡፡ አባቶቻችን ፡ በመጀመርያዪቱ ፡ ሮም ፡ ላለው ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ይህነን ፡ ክብር ፡ ሰጡ ፡ ሮም ፡ የምትገዛ ፡ ከተማ ፡ ናትና ፡ እንዲህም ፡ ባዲስ ፡ ሮም ፡ በቍስጥንጥንያ ፡ ያለ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ተካከለ ፡ ቍስጥንጥንያ ፡ የመንግሥት ፡ ሁሉ ፡ ከተማ ፡ የቄሣርም ፡ መኖርያ ፡ ናትና ፡፡ አሌህ ፡ ፭፡ ሜትሮጶሊ

ቃኖችም ፡ አሁን ፡ ጳትርያርኻት ፡ ተባሉ ፡ ያባቶች ፡ አለቆች ፡ ማለት ፡ የሚሆን ::

ይችም ፡ የክብር ፡ ሥርዓት ፡ በክርስቶስ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ እርሱ ፡ ገና ፡ በምድር ፡ ላይ ፡ ሲኖር ፡ አያሌ ፡ ጊዜ ፡ ክርክርን ፡ ያስነሣች ፡ አሁን ፡ የጅግ ፡ ክፋት ፡ ምንጭ ፡ ሆነች :: ስለዚህም ፡ ይላል ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ከናትያንዝ ፡ እርሱም ፡ ባለቤቱ ፡ ጳትርያርኽ ፡ የነበረ ፡ በቍስጥንጥንያ :: ወዮልን ፡ ስለ ፡ መቀደም ፡ በመቀመጥ ፡ በመኖርም ፡ በግድም ፡ ስለ ፡ መክበር :: ምነው ፡ እንደንታወቅ ፡ እንደንከብርም ፡ በቅድስና ፡ ብቻ :: አሁን ፡ ግን ፡ ያ ፡ መቀመጥ ፡ በቀኝ ፡ በግራም ፡ በመኻከልም ፡ በላይም ፡ በታችም ፡ ያም ፡ መሔድ ፡ በቀደምና ፡ ባንድ ፡ አጅግ ፡ መለያየት ፡ አደረገ ፡ በከንቱ ፡ በመኻከላችን ፡ ብዙም ፡ ወደ ፡ ጥፋት ፡ ጣለው :: የሮምም ፡ ጳትርያርኽ ፡ ሥልጣን ፡ በዛች ፡ በሌሎች ፡ ላይ :: የሮም ፡ ዕድሜ ፡ እንደ ፡ መንግሥት ፡ ከተማ ፡ እንደ ፡ ቤት ፡ ክርስቲያንም ፡ የሮምም ፡ ታላቅነትና ፡ ኃይል ፡ ለምዕራብ ፡ የሮምም ፡ ወሬ ፡ ስለ ፡ ጴጥሮስና ፡ ጳውሎስ ፡ በሮም ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ ያ ፡ ነገርም ፡ የሮም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ብቻውን ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ በምዕራብ ፡ ብዙ ፡ ጊዜም ፡ ከልዩ ፡ ወገን ፡ ሕዝብ ፡ የቄሣር ፡ ቤት ፡ እንደደከፈበት :: ይህ ፡ ሁሉ ፡ መክንያት ፡ ሆነ ፡ ከሮም ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ካልተወሰነች ፡ ትዕቢታቸው ፡ ጋራ ፡ የሮም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በቍስጥንጥንያ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ላይ ፡ እንደሸነፈ :: የቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ታላቅ ፡ መምህራን ፡ እንደ ፡ ቴዎደሬቶስ ፡ ዎጵታቱስም ፡ አውጉስቲኑስም ፡ ሮምን ፡ የጴጥሮስን ፡ መንበር አደረጉ ፡ የሮምንም ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ የጴጥሮስን ፡ ተከታዮች :: የሮም ፡ ኤጲስቆጶሳትም ፡ እንደ ፡ ዩልዩስ ፡ ሲሪክዩስም ፡ ኢኖኬንቲዩስም ፡ ደመሶሱስም ፡ ሌዎንም ፡ በትዕቢታቸው ፡ መክንያትን ፡ ሁሉን ፡ ተጠቀሙ ፡ ሹመታቸውን ፡ ያከብሩ ፡ ዘንድ ፡ ራሳቸውንም ፡ በቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ ስም ፡ ላለም ፡ ሁሉ ፡ ጌቶች ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ::

የቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ሁሉ ፡ አንድነት ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ ብለው ፡ እለዚያን ፡ ሲኖደችን ፡ አደረጉ ፡ ኦይኩሜኒ

ቆች ፡ የተባሉ ፡ ላለም ፡ ሁሉ ፡ የሚሆኑ ፡ ማለት ፡ የኤጲስቆጶሳት ፡ ሁሉ ፡ ጉባኤዎች ፡፡ እርሳቸውም ፡ በተቀደሙ ፡ ሲኖደች ፡ ምሳሌ ፡ ሆኑ ፡፡ በርሳቸውም ፡ ክርክርን ፡ ሁሉን ፡ መግጠም ፡ ለማምለክም ፡ ለተግሣጽም ፡ ለመኖርም ፡ ሥርዓትን ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ፈለጉ ፡፡ የተከራከሩበትንም ፡ ነገር ፡ መግጠም ፡ እውነተኛውንም ፡ አንድነት ፡ ማድረግ ፡ አልቻላቸውም ፡፡ የተከራከሩ ፡ ወገኖች ፡ ወደ ፡ ሲኖደስ ፡ ሳይገቡ ፡ አውቀዋልና ፡ ማሰባቸውን ፡ ትምርታቸውንም ፡ ማጽናት ፡ ብቻ ፡ ይፈልጉ ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ ወንድሞቻቸውን ፡ ከመስማት ፡ ይልቅ ፡፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ከናትያንዝ ፡፡ እውነት ፡ ልነገር ፡ እኔ ፡ ብችል ፡ ከኤጲስቆጶሳት ፡ ሲኖደስ ፡ እሸሻለሁ ፡ ሲኖደስ ፡ ሁሉ ፡ ለበጎ ፡ እንደ ፡ ተጨረሰች ፡ ከቶ ፡ አላየሁምና ፡፡ ሲኖደስ ፡ ሁሉ ፡ ክፉ ፡ ነገርን ፡ ለመሻር ፡ የተሰበሰበች ፡ በመሻር ፡ ፈንታ ፡ አበዛቸው ፡ የፀብና ፡ የመግዛት ፡ መውደድ ፡ በሲኖደስ ፡ ሁሉ ፡ ይገዛልና ፡ በርሱም ፡ ለተገኙ ፡ ሁሉ ፡ የሌሎችን ፡ ክፋት ፡ ከመሻር ፡ ይፈርድበት ፡ ዘንድ ፡ ይቀላል ፡፡

ነገር ፡ ግን ፡ ኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ ሳይቀር ፡ ክርስቲያን ፡ ሲኖደችን ፡ እንደ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስራ ፡ ቍጠሩት ፡ ቤት ፡ ክርስታያንን ፡ ይገዛባቸው ፡ ዘንድ ፡ ለሰውም ፡ ሁሉ ፡ እንደገባው ፡ የሲኖደስን ፡ ትእዛዝ ፡ ይቀበልና ፡ ይከተል ፡ ዘንድ ፡፡ እንዲህም ፡ ይላል ፡ አውጉስቲኑስ ፡፡ የሚከራከሩበት ፡ ነገር ፡ በሲኖደስ ፡ መማከር ፡ ብቻ ፡ አይሆንም ፡ ከሲኖደስ ፡ በተቀደመው ፡ ምርምር ፡ እንጂ ፡፡ ሲኖደስ ፡ የዚህ ፡ ምርምርን ፡ ፍሬ ፡ ያወጣል ፡ ብቻ ፡ ለዚህ ፡ ፍሬም ፡ ስልጣን ፡ ይሰጣል ፡፡ ስለዚህም ፡ ይችላል ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ክርክር ፡ በኦይኩማኒቆ ፡ ሲኖደስ ፡ እንዲገጠም ፡ የተቀደመው ፡ ምርምር ፡ በጣም ፡ አልበሰለምና ፡ ፍሬንም ፡ አላፈራምና ፡፡ እንዲህም ፡ ሲኖደስ ፡ ሁሉ ፡ ለጊዜ ፡ ነው ፡ የክርስቲያንን ፡ አውቀት ፡ በምርምራቸው ፡ የሆነ ፡ ለሁሉ ፡ ለመቀበል ፡ ሊያሠለጥን ፡ ሊያጸናውም ፡ ነው ፡፡ ለሰውም ፡ ሁሉ ፡ ይገባል ፡ በሲኖደስ ፡ የጸናውን ፡ ነገር ፡ ይቀበልና ፡ ይታዘዝለት ፡ ዘንድ ፡፡

አሁንስ ፡ የክርስቲያን ፡ ሣይማኖት ፡ ባሕሪ ፡ እንዲህ ፡ ነው ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ ትእዛዝ ፡ ብቻ ፡ ከመታዘዝ ፡ እንዲከለክል ፡ እግዚአብሔር ፡ ሳያዝ ፡፡ የሚያምን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የክርስቶስን ፡ ድምጽ ፡ ያውቃልና ፡ ከሰውም ፡ ድምጽ ፡ ይለየዋል ፡ የንግዴውንም ፡ ድምጽ ፡ ሳይከተል ፡ የክርስቶስን ፡ ድምጽ ፡ ብቻ ፡ ይሰማል ፡ ይከተለውማል ፡፡ የጳውሎስን ፡ ነገር ፡ አስቦ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ እላንተ ፡ በዋጋ ፡ ተገዛታችኋልና ፡፡ ለሰው ፡ ባሮች ፡ አትሁኑ ፡፡ የዮሐንስ ፡ ወንጌል ፡ ፲፡ ፬፡ ፭፡፡ ፩፡ ቆሮንቶስ ፡ ፯፡ ፳፫፡፡ አሁንም ፡ በሲኖዶስ ፡ የተሰበሰቡ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ሁሉ ፡ በክርስቶስ ፡ ስም ፡ ያልተሰበሰቡ ፡ ከርሳቸው ፡ ሁለግዜ ፡ ብዙ ፡ የነበረ ፡ በሥጋዊ ፡ ስማቸው ፡ ብቻ ፡ የመጡ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስንም ፡ ፈቃድ ፡ ያልጠየቁ ፡ ብዙ ፡ ጊዜም ፡ በቅዱሳን ፡ ወንድሞቻቸው ፡ በክርስቶስ ፡ ስም ፡ መጥተው ፡ በነበረ ፡ ላይ ፡ ያሸነፉ ፡ እንዲህ ፡ ያለች ፡ ሲኖዶስ ፡ ቃልዋን ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ታስቈጥር ፡ ዘንድ ፡ የሰውንም ፡ አሳብና ፡ ትምርት ፡ ሁሉ ፡ ለቃልዋ ፡ ታስገዛ ፡ ዘንድ ፡ በወደደች ፡ ጊዜ ፡ ትዕቢተኛ ፡ ሁና ፡ ወደ ፡ ስሕተት ፡ ወደቀች ፡፡

የሲኖዶችንም ፡ ትእዛዛት ፡ ሁሉ ፡ መሰብሰብ ፡ የጀመረ ፡ ዲዮናስዮስ ፡ እክሲጉውስ ፡ ነው ፡ እርሱም ፡ የሮም ፡ሞናክሴ ፡ ከ፭፻፡፡ በኋላ ፡ መጻፉን ፡ የጻፈ ፡፡

፪፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተግሣጽ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡፡

ከቀደመ ፡ ዘመን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዓትን ፡ ተቀበለች ፡ ታላቅ ፡ ኃጢአትን ፡ የሚያደርጉትን ፡ ሰዎች ፡ ካንድነትዋ ፡ ያወጡ ፡ ዘንድ ፡ ይገዝትዋቸውም ፡ ዘንድ ፡ ንስሐ ፡ እስኪገቡ ፡ ድረስ ፡ ንስሐም ፡ ሲገቡ ፡ ይቀበልዋቸው ፡ ዘንድ ፡፡ ከኖዋትያኑስም ፡ በኋላ ፡ ተለመደ ፡ ማንንም ፡ እንደይከለክሉ ፡ ንስሐ ፡ የሚገባውን ፡ ከፍትሐት ፡ በፊትም ፡ ሳይሆን ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ሆነ ፡፡

ንስሐ ፡ የሚገቡም ፡ ሰዎች ፡ በ፬፡ ወገን ፡ ተከፈሉ ፡፡ መጀመርያ ፡ ወገን ፡ እለዚያ ፡ ነበረ ፡ ወደ ፡ ጉባኤ ፡ ከመግባ

ት ፡ የተከለከሉ ፡፡ እርሳቸውም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ደ
ጅ ፡ ቁመው ፡ ነበረ ፡ ሲያለቅሱ ፡ የሚገቡትንም ፡ ክርስቲ
ያን ፡ ሲለምኑ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይለምኑላቸው ፡ ዘንድ ፡
ወደ ፡ ምድርም ፡ ሲሰግዱ ፡፡ ሁለተኛ ፡ ወገንም ፡ እለዚያ ፡
ነበረ ፡ ከልተጠመቁ ፡ ከከቴኩሚኖች ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ፡ የገቡ ፡
በልዩ ፡ ስፍራም ፡ የኖረ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ መንበብ
ና ፡ ስብከት ፡ ወደ ፡ ሰሙበት ፡፡ ሦስተኛ ፡ ወገናቸውም ፡ እ
ርሳቸው ፡ ነበረ ፡ ልዩ ፡ ጸሎት ፡ የሚጸልዩላቸው ፡ እርሳቸ
ው ፡ በጕልበታቸው ፡ ተንበርክከው ፡ ሲኖረ ፡፡ አራተኛ ፡ ወ
ገንም ፡ እልያ ፡ ነበረ ፡ ማምለክን ፡ ሁሉን ፡ ከክርስቲያ
ን ፡ ጋራ ፡ ባንድ ፡ ያደረጉ ፡ ከቍርባን ፡ በቀር ፡፡ አሁን ፡ ግ
ን ፡ ቃሊል ፡ አልሆነም ፡ ቍርባን ፡ ለማይገባቸውን ፡ ሰዎች ፡
ከቍርባን ፡ ይከለክሉ ፡ ዘንድ ፡ ታላቅ ፡ ቢሆኑ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡
አፈ ፡ ወርቅና ፡ አምብሮስዮስ ፡ ይችሉት ፡ ነበረ ፡፡

፫፡፡ የመለያየት ፡ ታሪክ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡፡

፩፩፤ የደናቱስ ፡ መለየት ፡፡

ደህች ፡ መለየት ፡ ባፍሪቃ ፡ ነበረች ፡ በተቀደመ ፡ ዘመንም ፡
በርም ፡ ለነበረች ፡ ለኖዋትያኑስ ፡ መለየት ፡ መሰለች ፡፡

፪፪፤ የሚሌትዮስ ፡ መለየት ፡፡

ደህችም ፡ መለየት ፡ በምሥር ፡ ሆነች ፡ ፪፤ ኤጲስቆጶሳ
ት ፡ እርሳቸውም ፡ ጴጥሮስ ፡ የስክንድርያ ፡ ጳጳስና ፡ ሚሌ
ትዮስ ፡ የኒቆጶሊስ ፡ ጳጳስ ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡ ሲጻሉ ፡፡

፫፫፤ የደመሶስና ፡ የውርቢኑስ ፡ የሮም ፡ ኤጲስቆ
ጶሳት ፡ መለየት ፡፡

በዚቺም ፡ መለየት ፡ ፪፤ ኤጲስቆጶሳት ፡ በትዕቢታቸው ፡
ባንድ ፡ ጊዜ ፡ የጴጥሮስ ፡ ወንበር ፡ የሚሉትን ፡ ፈለጉ ፡ ሁ
ከትንም ፡ አደረጉ ፡ በሮም ፡ ፻፴፯፤ ሰዎች ፡ የሞቱበት ፡፡ የ
ደመሶስ ፡ ትዕቢት ፡ ግን ፡ ውርቢኑስን ፡ አሸንፎት ፡ የመሶ
ስ ፡ ጳጳስ ፡ ሆነ ፡፡

ቦስተኛ ፡ ምዕራፍ ።

ስለ ፡ ክርስቲያን ፡ አካሔድና ፡ ማምለክ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ።

፩፤ የክርስቲያን ፡ አካሔድ ።

፩፩፤ ስለ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ አካሔድ ።

በዚህ ፡ ዘመን ፡ መጀመርያ ፡ በሮም ፡ መንግሥት ፡ በሆነ ች ፡ መለወጥ ፡ የታየች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እጅግ ፡ ረከሰ ች ። ቈሣር ፡ ክርስቲያን ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ የክርስቲያንንም ፡ ማምለክ ፡ የታዘዘውን ፡ ማምለክ ፡ ባደረገ ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገቡ ፡ ስለ ፡ ቈሣር ፡ ፈቃድ ፡ ስለ ፡ ክብራቸውም ፡ ስለ ፡ ምግባቸውም ፡ ስለ ፡ ሥጋዊት ፡ ሕይወታቸውም ፡ በልባቸውና ፡ ባካሔዳቸው ፡ አረማውያ ን ፡ የሚኖሩ ፡ ስማቸውንም ፡ ብቻ ፡ የለወጡ ። ብዙ ፡ ነበ ሩ ፡ ኃጢአታቸውን ፡ ብቻ ፡ ይጸገቡ ፡ ዘንድ ፡ ብለው ፡ ሞት ፡ ሳይደርስ ፡ የልተጠመቁ ። ብዙም ፡ ከተጠመቁ ፡ በኋላ ፡ ል ማድን ፡ ያደረጉት ፡ በያመት ፡ ፩፤ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይገቡ ፡ ዘንድ ፡ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ተቍረቡ ፡ በ ቍርባንም ፡ ብቻ ፡ በመስቀልም ፡ ምልክት ፡ የኃጢአታቸ ውን ፡ ብዛት ፡ ሁሉ ፡ ያጠፋ ፡ መሰላቸው ። ወንጌልን ፡ በመ ንበብም ፡ በመማርም ፡ በመከተልም ፡ ፈንታ ፡ አስማት ፡ አ ደረጉበት ።

በቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ እጅግ ፡ የጉደ ፡ ያ ፡ ቲላቅ ፡ ክር ክር ፡ ነበረ ፡ ስለ ፡ ትምርት ፡ በጽልና ፡ በቅናት ፡ በትዕቢት ም ፡ የሆነ ።

ያችም ፡ ስሕተት ፡ እጅግ ፡ ጉደች ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ እጅግ ፡ የበዛ ፡ ስለ ፡ ክህነት ። ቀሳውስት ፡ ከሕዝብ ፡ እንደ ፡ ተ ለዩ ። ስለዚህም ፡ ሕዝብ ፡ እንዲህ ፡ አሉ ። ስለ ፡ ቅድስና ፡ ስለ ፡ ንጽሕናም ፡ ስለ ፡ ፍቅርም ፡ ስለ ፡ ጽድቅም ፡ ስለ ፡ በ

ነ ፡ ነገርም ፡ ሁሉ ፡ የተባለ ፡ ነገር ፡ ለቄስ ፡ ይደርሳል ፡ ለሕዝ
ብም ፡ አይደለም ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡፡
ያለ ፡ ቅድስና ፡ ማንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ አያይም ፡፡

ነገር ፡ ግን ፡ ያ ፡ ሳይቅር ፡ የታዮች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እን
ዲህ ፡ ስትረክስ ፡ በስም ፡ ብቻ ፡ ክርስቲያን ፡ በነበሩ ፡ ሰዎ
ች ፡ ሕዝብ ፡ ቀረች ፡ ለክርስቶስ ፡ ያልታዮች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያ
ኑ ፡ በታዮች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተሰወሩ ፡ በጊዜም ፡ እን
ደ ፡ ብርሃናት ፡ የበሩ ፡፡ እንዲህም ፡ ብዙ ፡ እናያለን ፡ ከቤ
ተ ፡ ክርስቲያን ፡ መምህራን ፡ አካሔዳቸው ፡ ለኛ ፡ ደግሞ ፡
ለምሳሌ ፡ የሆነች ፡ በተሰጣቸው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ ለ
ኛ ፡ ደግሞ ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚሰጣን ፡ ብንለምነው ፡፡

ታሪክም ፡ አያሌን ፡ ሴቶች ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ያስታውቀ
ናል ፡ ክርስቶስን ፡ የወደዱት ፡ የተከተሉትም ፡፡ እንዲህ
ም ፡ የጎርጎርዮስ ፡ ከናትዚያንዝ ፡ እናት ፡ ኖና ፡ የሚል
ዋት ፡ ባልዋን ፡ እርሱም ፡ ደግሞ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ የሚሉት
ን ፡ ባካሔድዋ ፡ በጸሎትዋም ፡ ወደ ፡ ሃይማኖት ፡ ወሰደቸ
ው ፡፡ የበኵር ፡ ልጅዋን ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ከተወለደ ፡ በኋላ ፡
ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወሰደችው ፡ ወንጌልንም ፡ በጁ ፡
አኖረች ፡ በጸሎትም ፡ ለክርስቶስ ፡ ቀደሰችው ፡፡ እንዲህ
ም ፡ አንቱሳ ፡ ያፈ ፡ ወርቅ ፡ እናት ፡ ሞኒካም ፡ ያውጉ
ስቲኖስ ፡ እናት ፡ እግዚአብሔርን ፡ አገለገሉ ፡ ልጆቻቸው
ን ፡ ለክርስቶስ ፡ ሲያሳድጉ ፡፡

፬፮፡ ስለ ፡ አስቄጥስ ፡ ሕይወት ፡ ስለ ፡ ምንኵስናም ፡፡

በቀደመ ፡ ዘመን ፡ ክርስቲያን ፡ ካለም ፡ ጥፋት ፡ ጋራ ፡ ሲ
ጋደሉ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ካለም ፡ ተለዩ ፡ ያስቄጥስንም ፡ አካ
ሔድ ፡ ተከተሉ ፡ እጅግ ፡ ኢየጾሙ ፡ ከመጋባትም ፡ ሲርቁ ፡
ገንዘባቸውንም ፡ ለድኆች ፡ ሲሰጡ ፡ በምድረ ፡ በደም ፡
ሲኖሩ ፡፡ አስቄጥስም ፡ ሁሉ ፡ በምስር ፡ የበዙ ፡ ለብቻው ፡
ኖሩ ፡፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ግን ፡ ሥርዓታቸው ፡ ተለወጠች ፡ ከ
አስቄጥስም ፡ ሥርዓት ፡ ለምንኵስና ፡ ሆነች ፡፡ ይህም ፡ ሆ
ነ ፡ ባንቶንዮስ ፡ ስራ ፡፡

አንቶንዮስም ፡ ባመት ፡ ፪፻፶፩፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በ

ኋላ ፡ ቆማ ፡ በሚሉት ፡ አገር ፡ በምስር ፡ ተወለደ ፡፡ ወላጆ
ቹም ፡ በሃይማኖት ፡ አሳደጉት ፡ እጅግ ፡ መጽሐፍ ፡ ግን ፡ አ
ላወቀም ፡፡ እርሱም ፡ ዝምታውን ፡ ወደደ ፡ የእግዚአብሔር
ንም ፡ ነገር ፡ ማሰብ ፡ በርሱም ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡
በልቡ ፡ ሰራ ፡ ልቡን ፡ ካለም ፡ እንደ ፡ ለየው ፡፡ ክርስቶስ
ም ፡ ለባለጠጋ ፡ ብላቴና ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡
ገንዘብህን ፡ ሺጥ ፡ ለድኆችም ፡ ስጠው ፡ መጥተህም ፡ ተ
ከተለኝ ፡፡ ይህነን ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ ፈደሉ ፡ ለልቡ ፡ ወሰደ ፡ አ
ንቶንዮስ ፡ ገንዘቡንም ፡ ሸጥቶ ፡ ለድኆች ፡ ሰጠው ፡ ጥቂ
ትም ፡ ብቻ ፡ አስቀረ ፡ ለቱ ፡፡ እቱንም ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ በጎ ፡
ሴቶች ፡ ለማሳደግ ፡ አደራ ፡ ሰጣት ፡ የቀረውንም ፡ ከብቱ
ን ፡ ለድኆች ፡ ሰጠው ፡፡ እርሱም ፡ ወደ ፡ በረኻ ፡ ሒደ ፡ ያ
ስቄጥስን ፡ ሕይወት ፡ ጀመረ ፡፡ አንቶንዮስም ፡ በውነት ፡ እ
ግዚአብሔርን ፡ እሻ ፡ ማገልገሉም ፡ ፈለገ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከ
ሰው ፡ መኻከል ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ ሥርዓት ፡ መውጣ
ቱ ፡ ስሕተት ፡ ነበረ ፡ የመስቀልን ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ መጸደቃች
ን ፡ በሃይማኖት ፡ ብቻ ፡ ያለ ፡ ምግባር ፡ አላስተወለምና ፡፡
አሁንም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ሥርዓት ፡ ወጥቶ ፡ እጅግ ፡ መ
ጋደልን ፡ አገኘ ፡ ከሥጋው ፡ ከሰይጣንም ፡ ጋራ ፡ እጅግ ፡ ድ
ካምም ፡ ካለምስራት ፡ የተነሣ ፡፡ ሥጋው ፡ ሰደሰራ ፡ ልቡ
ም ፡ ብቻ ፡ በማሰብ ፡ በጸሎትም ፡ በመጋደልም ፡ ሲኖር ፡ እ
ርሱም ፡ ለብቻው ፡ ሁኖ ፡ ይህም ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያ
ላዘዘ ፡፡ እጅግ ፡ ዘመንም ፡ በብሕትነቱ ፡ ከተቀመጠ ፡ በኋ
ላ ፡ ብዙ ፡ አስቄጦች ፡ መጡለት ፡ እርሱም ፡ አስተማራቸ
ው ፡ የምስርም ፡ ምድረ ፡ በደ ፡ በስቄጦች ፡ ደሶች ፡ መላች ፡፡
ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ ምክሩን ፡ ይሰሙ ፡ ዘንድ ፡ መጡለት ፡
ማጽናትና ፡ ረዴትም ፡ ከርሱ ፡ ይፈልጉ ፡ ዘንድ ፡፡ እርሱም ፡
ሁላቸውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፍቅር ፡ አሳያቸው ፡ ላንድ ፡
ልጁ ፡ ያላዘነ ፡ ስለ ፡ ሁላችን ፡ የሰጠው ፡ እንጅ ፡፡ ዕድሜ
ውም ፡ ፻፭፡ አመት ፡ ሆነ ፡፡

ካንቶኒዮስም ፡ በኋላ ፡ ምንኵስና ፡ በምስር ፡ እጅግ ፡ በ
ዛች ፡፡ ከምስርም ፡ ባንቶኒዮስ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ወጥታ ፡
በየሩሳሌምና ፡ በሶርያ ፡ ተዘረጋች ፡፡ ባንቶኒዮስ ፡ መክንያ

ትም ፡ አስቄጦች ፡ በፊት ፡ ለብቻቸው ፡ ይኖሩ ፡ የነበሩ ፡ መ
ኖርያቸውን ፡ ባንድ ፡ አደረጉ ፡፡ እርሱ ፡ ግን ፡ ከሞተ ፡ በኋ
ላ ፡ ጳኰምዮስ ፡ ተነሣ ፡ ለሁላቸው ፡ ሥርዓትን ፡ ያደረገ ፡፡
እርሱም ፡ ባንዲት ፡ በኒል ፡ ባለች ፡ ደሴት ፡ ታላቅ ፡ ገዳ
ምን ፡ ሠራ ፡ በርሱም ፡ መነኰስትን ፡ ሰበሰበ ፡ በ፳፬ ፡ ክ
ፍልም ፡ ከፈላቸው ፡፡ በየክፍል ፡ ላይም ፡ አንድ ፡ አለቃው
ን ፡ ሾመ ፡ ስራቸውንም ፡ ለብቻው ፡ እርሱም ፡ የሁላቸ
ው ፡ አለቃ ፡ ወይስ ፡ አርኪመንድሪት ፡ ነበረ ፡፡ ገዳምም ፡
ቄኖቢዮን ፡ ተባለ ፡ መነኰስትም ፡ ቄኖቢቶች ፡ ተባሉ ፡፡ ከ
ለዚያም ፡ መነኰስት ፡ መናፈቃን ፡ ተነሡ ፡ ባመት ፡ ፫፻፶፯
የሚያህል ፡ ኤውኪቶች ፡ የተባሉ ፡ ሥርዓትን ፡ ሁሉን ፡
አፍርሰው ፡ ለልባቸው ፡ ፈቃድ ፡ ሁሉ ፡ ለኃጢአትም ፡ ሁ
ሉ ፡ የተሰጡ ፡፡

ሌሎች ፡ ሳቾችም ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ የኤውስታቲዎ
ስ ፡ ወገን ፡ ነበሩ ፡ ከሌሎች ፡ አስቄጦች ፡ እንዲበርቱ ፡ ያ
ሉ ፡፡ እርሳቸውም ፡ መጋባትን ፡ የቤትንም ፡ ሥርዓት ፡ ናቁ ፡
የመነኰስትን ፡ ልብስ ፡ ብቻ ፡ ሲለብሱ ፡ ሌላውን ፡ ልብ
ስ ፡ የለበሱትን ፡ ሰዎች ፡ ናቁ ፡፡ ምሽትንም ፡ ካጋባ ፡ ቄስ ፡
ቍርባን ፡ ለመቀበል ፡ እምቢ ፡ አሉ ፡፡ በመንደርም ፡ ቤተ ፡
ክርስቲያን ፡ ገና ፡ ካልተሠራች ፡ ማምለክም ፡ በሌላ ፡ ቤት ፡
ከሆነ ፡ ባለ ፡ ቤቱ ፡ ምሽት ፡ ያጋባ ፡ ከዚያ ፡ አልተቈረቡ
ም ፡፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንኳ ፡ በርሳቸው ፡ ረኩሰች ፡ ስለ
ዚህም ፡ ለብቻቸው ፡ አመለኩ ፡፡ የገንግራም ፡ ሲኖደስ ፡ ስ
ሕተታቸውን ፡ ገሠጸች ፡፡

ምንኩስናም ፡ አንዳንድ ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ ነበረላት ፡፡ ብዙ ፡
ሰዎች ፡ ከታላቆች ፡ ወገን ፡ ባለም ፡ ደክመው ፡ የነበሩ ፡ በ
ርስዋ ፡ ጊዜን ፡ አገኙ ፡ ለነፍሳቸው ፡ ለማሰብ ፡፡ የመነኰስ
ትም ፡ ጉባኤ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ ቢሾ ፡ በዙርያቸ
ው ፡ የነበሩትን ፡ ሰዎች ፡ ምሳሌን ፡ ሰጡ ፡፡ ብዙ ፡ ገዳሞች
ም ፡ አሽከሮችን ፡ ለማሳደግ ፡ እንግዶችንም ፡ ለመቀበል ፡
ነበሩ ፡፡ በምዕራብም ፡ አሕዛብን ፡ ለማስተማር ፡፡ ባሲልዮ
ስ ፡ ሥርዓትን ፡ አደረገ ፡ ለማሳደግ ፡ በገደሞች ፡፡ ነገር ፡ ግ

ን ፡ እጅግ ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ከመነኮሶች ፡ ተነሣ ። በትዕቢታቸ ው ፡ ለክርክር ፡ ሲገቡ ፡ ፅብም ፡ ሲያድርጉ ።

ብዙ ፡ መነኮሶችም ፡ እጅግ ፡ ደከሙ ፡ የጠባያቸውን ፡ መሻት ፡ በጣም ፡ ደገድሉ ፡ ዘንድ ። የስምዖን ፡ ወገን ም ፡ እንደሆ ፡ ነበሩ ፡ በዓምድ ፡ ለይ ፡ የቆሙ ፡ ማንቀሳቀ ስ ፡ ወደማይችሉበት ፡ እንደሆ ፡ አድርገው ፡ ፈቃደቸውን ፡ ደገዙ ፡ ዘንድ ።

ምንኵስናም ፡ ከምሥራቅ ፡ ወጣች ፡ ወደ ፡ ምዕራብም ፡ አለፈች ፡ ባታናስዮስ ፡ በኤውሴቢዮስም ፡ በሂሮኒሞስም ፡ በ አውጉስቲኑስም ። ምንኵስናንም ፡ በገልያ ፡ እጅግ ፡ ተቀበ ሉት ። ከስያኑስም ፡ የምሥራቅን ፡ ሥርዓት ፡ ለለዚያ ፡ ምናኵስት ፡ አደረገ ። ከርሱም ፡ በኋላ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ተነ ሣ ፡ ለምዕራብ ፡ ገደሞች ፡ ሌላ ፡ ሥርዓት ፡ ያደረገላቸው ፡ እርሱም ፡ ቤኔዲክቱስ ፡ ነበረ ። እርሱም ፡ ባመት ፡ ፬፻፹፩ ተወለደ ፡ በኢጣልያ ፡ ምድር ፡ ኑርስያ ፡ በተባለች ፡ አገር ። አያሌ ፡ ወራትም ፡ በሮም ፡ ከተቀመጠ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ምድ ረ ፡ በደ ፡ ሔደ ፡ ከሮማኑስም ፡ ጋራ ፡ ኖረ ፡ ባሕታዊ ፡ ሁኖ ፡ ከሮማኑስም ፡ ተምሮ ። በኋላም ፡ ገደሞችን ፡ ሠራ ፡ ብርቱ ፡ ሥርዓትም ፡ አደረገላቸው ። ከብርታቱም ፡ ጋራ ፡ የወንጌ ልን ፡ የሚጻፈጠውን ፡ ትምርቱን ፡ ደበለቀ ። በየገደም ፡ ሁሉ ፡ ፲፪፡ መነኮሶችን ፡ አኖረ ፡ ከ፩፡ መምህር ፡ በታች ። እ ለዚያም ፡ ገደሞች ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ እጅግ ፡ ጠቀሙ ፡ የወ ንጌልን ፡ ትምህርት ፡ በፈረንጆች ፡ አሕዛብ ፡ መካከል ፡ ደ ዘርጉ ፡ ዘንድ ።

ባዚያ ፡ ዘመንም ፡ አንድ ፡ መናክሴ ፡ ተነሣ ፡ በሮም ፡ ዮ ዊኒያኑስ ፡ የሚሉት ፡ የወንጌልን ፡ ትምህርት ፡ ጽሩ ፡ ሁ ኖ ፡ ያስተማረ ። ደሮ ፡ የዘመኑ ፡ ሰዎች ፡ ጥቂት ፡ ነበሩ ፡ የ ተቀበሉት ። እርሱም ፡ እንደሆ ፡ አለ ። የእግዚአብሔር ፡ ሕይወት ፡ አንዲት ፡ ናት ፡ ለምእምናን ፡ ሁሉ ፡ አንዲት ም ፡ አንድነት ፡ ከክርስቶስ ፡ ጋራ ፡ አንዲትም ፡ ሁለተኛ ፡ ል ደት ። ለውነተኞች ፡ ክርስቲያናት ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ነገር ፡ ነ ው ፡ አንድ ፡ መጽሬት ፡ አንድ ፡ ክብር ፡ የሰማዩም ፡ ገንዘ ብ ፡ ሁሉ ፡ ለሁሉ ፡ ነው ፡ የምድርም ፡ መሆናቸው ፡ በዚህ ፡

መለየት ፡ አያደርግላቸውም ፡፡ ስለዚህም ፡ ለሚያምኑ ፡ ሰዎች ፡ ቢያምኑ ፡ ብቻ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ነው ፡ ብሕትነትና ፡ መጋባት ፡ መብላትና ፡ ጾም ፡ ያለምም ፡ ገንዘብ ፡ መግዛትና ፡ አለመግዛት ፡፡ በእግዚአብሔር ፡ ዘንድም ፡ ፩፤ መለየት ፡ ብቻ ፡ ይቈጠራል ፡ እኛ ፡ የክርስቶስ ፡ ወገን ፡ ብንሆን ፡ ወይስ ፡ አይደለም ፡ ሌላ ፡ መለየት ፡ የለም ፡፡ በውነትም ፡ የሚያምኑ ፡ ሁሉ ፡ የክርስቶስ ፡ ወገን ፡ ናቸው ፡ አንዲት ፡ ገላ ፡ አንድ ፡ መንፈስም ፡፡ ስለ ፡ መጋባትም ፡ አለ ፡፡ እግዚአብሔር ፡ በገነት ፡ አደረገው ፡ ክርስቶስም ፡ ቀደሰው ፡ አከበረውም ፡፡ ስለ ፡ ጾምም ፡ አለ ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ዓለምን ፡ ሁሉን ፡ ስለርሱ ፡ ለምስጋናውም ፡ ፈጠረ ፡ ክርስቶስም ፡ ፍጥረትን ፡ ሁሉን ፡ ቀደሰ ፡ የሚንቀውም ፡ ኀጢአትን ፡ ያደርጋል ፡ ለጊዜም ፡ ለንፍሱ ፡ የሚጾም ፡ የማይጾምም ፡ አንድ ፡ ናቸው ፡ የሚጾምም ፡ በማይጾም ፡ አይፈረድ ፡፡ ዮዊኒያኑስም ፡ አለ ፡፡ በውነት ፡ የሚያምን ፡ በሃይማኖቱ ፡ ጸድቀ ፡ የዘላለም ፡ ደህንነት ፡ ጸንቷለቷለች ፡፡ ከዚህ ፡ የሚበልጥን ፡ ነገር ፡ መቀበል ፡ አይችልም ፡ ምንድር ፡ ይበልጣልና ፡ ከክርስቶስ ፡ ጋራ ፡ ካለች ፡ አንድነት ፡፡ በክርስቶስ ፡ ጸጋ ፡ ይኑር ፡ ብቻ ፡ ይህም ፡ ይሆናል ፡ በዚህ ፡ ጸጋ ፡ ልቡን ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ደግሞ ፡ ለክርስቶስ ፡ ቢቀድሰው ፡፡ ሃይማኖት ፡ ወደለችባት ፡ ሕይወት ፡ ሁሉ ፡ ታሸንፋለች ፡ በኀጢአት ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ኀጢአትንም ፡ ትከለክላለች ፡፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተወለደ ፡ ሁሉ ፡ ኀጢአት ፡ አያደርግምና ፡ ዮሐንስ ፡ እንዳለ ፡፡ በኀ ፡ ዛፍም ፡ ክፉ ፡ ፍሬን ፡ አያፈርም ፡ ክርስቶስ ፡ እንዳለ ፡፡

አያሌ ፡ ሰዎችም ፡ ነበሩ ፡ የዮዊንያኑስን ፡ ትምህርት ፡ የተቀበሉ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ጊዜ ፡ ገና ፡ አለደረሰም ፡ የወንጌል ፡ ብርሃን ፡ ብሩ ፡ እንዲያበራ ፡ በቤት ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡፡ ሰዎች ፡ ጨለማውን ፡ ወደዱ ፡ ጨልማም ፡ በዛ ፡፡ የሮም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ሲሪኪዮስ ፡ በሮም ፡ በተሰበሰበች ፡ ሲኖደስ ፡ ባመት ፡ ፫፻፺፤ ዮዊንያኑስን ፡ ወገዘ ፡፡

፩። ስለ፡ ክርስቲያን፡ ማምለክ፡ በዚህ፡ ዘመን፡፡

፩፩። ስለ፡ ክርስቲያን፡ ማምለክ፡ መሆን፡ ከክርስቲያን፡ ሕይወት፡ ጋራ፡፡

በዚህ፡ ዘመንም፡ አረ፡ ወርቅና፡ ኣውጉስቲኑስ፡ እጅግ፡ ተጋደሉ፡ ሰውን፡ አስተምረው፡ እግዚአብሔርን፡ ደስ፡ የሚያሰኘውን፡ ማምለክ፡ በሚታይ፡ መልክ፡ ብቻ፡ በሥጋም፡ የሚደረግ፡ በጊዜም፡ በስፍራም፡ የሚኖር፡ በጾፈትም፡ ሥርዓት፡ ለሚሰራ፡ ብቻ፡ የማይሆን፡ የመንፈስና፡ የውነት፡ የሚሆን፡ እንጅ፡ ሁለግዜ፡ በስፍራም፡ ሁሉ፡ ከልብም፡ የሚወጣ፡ ወደ፡ እግዚአብሔርም፡ የሚደርስ፡፡ ነገር፡ ግን፡ ያለም፡ መንፈስ፡ ገዛ፡ በክርስቲያን፡ ብዛት፡ ላይ፡ ስለዚህም፡ የርሳቸውን፡ ነገር፡ አልሰሙም፡፡

፩፪። ስለ፡ ማምለክ፡ ሸልም፡ ስለ፡ መቅደስ፡ ቤትም፡፡ ስለ፡ ሥእልም፡፡

በቀደመ፡ ዘመንም፡ ክርስቲያን፡ ካረማውያን፡ ጋራ፡ በተጋደሉ፡ ጊዜ፡ ክርስቲያን፡ ሁሉ፡ ሸልምን፡ ጸሉ፡ በቤተ፡ ክርስቲያን፡፡ የሮም፡ መንግሥት፡ ግን፡ የክርስቲያን፡ መንግሥት፡ በተባለች፡ ጊዜ፡ ሸልምን፡ ሥእልንም፡ ውበትንም፡ ሁሉ፡ ወደዱ፡፡ እጅግ፡ ወርቅም፡ ለቤተ፡ ክርስቲያን፡ መሸለም፡ ያመጡትን፡ ልባቸው፡ በንጺአት፡ ሲኖር፡ አረ፡ ወርቅ፡ አላቸው፡፡ ክርስቶስ፡ ወርቃችሁን፡ አደሻም፡ ልባችሁን፡ እንጅ፡፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ የወርቅ፡ ሰሪ፡ ስፍራ፡ አይደለችምና፡ የምላእክት፡ ጉባኤ፡ እንጅ፡፡ ስለዚህም፡ ነፍሳችሁን፡ እንፈልጋለን፡፡

የመቅደስ፡ ቤታቸው፡ በየሩሳሌም፡ መቅደስ፡ ምሳሌ፡ ተሰራ፡ በ፫፡ ተክፍሎ፡፡ መጀመርያ፡ ክፍልም፡ ለሰው፡ ሁሉ፡ ነበረ፡ የጉባኤ፡ ወገን፡ ያልነበሩ፡ አረማውያን፡ አይሁድም፡ የተገዘቱትም፡ ከዚያ፡ ኑረው፡ ስብከትን፡ ሰሙ፡፡ ከዚያ፡ ወዲያም፡ መቅደስ፡ ተከተለች፡ ያመኑ፡ የተጠመቁም፡ ሕዝብ፡ ወደ፡ ነበሩበት፡ ስፍራ፡፡ በኋላም፡ ቅዱስ፡ ቅዱሳን፡ የተባለ፡ ስፍራ፡ ለቍርባን፡ የነበረ፡ በመጋረጃና፡ በንጨት፡ ወይስ፡ በብረት፡ ከመቅደስ፡ የ

ተለየ ፡፡ ከዚያም ፡ መሠውያ ፡ ነበረ ፡ የኤጲስቆጶስም ፡ ዙፋን ፡ በዙርያም ፡ የቀሳውስት ፡ ወንበሮች ፡፡ ወደዚህ ፡ ስፍራም ፡ የተቀደሱ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገልጋዮች ፡ ብቻ ፡ ገቡ ፡፡

የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መሸለም ፡ በወርቅና ፡ በዕንቍ ፡ በከበረ ፡ ደንጊያም ፡ በሸለሙት ፡ በመስቀል ፡ ጀመረ ፡፡

የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥእል ፡ ግን ፡ በመጀመርያ ፡ እጅግ ፡ ክልክል ፡ አገኘ ፡፡ ቈንስታንቲኖስ ፡ ከዘመዱ ፡ ጋራ ፡ የማምለክን ፡ ሸልም ፡ እጅግ ፡ ሲወዱ ፡ ከርሳቸው ፡ ልማድ ፡ ወጣ ፡ ወደ ፡ መንግሥቱ ፡ ሁሉ ፡ ቤት ፡ ሁሉ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ሁሉ ፡ የሰውም ፡ ልብስ ፡ ሁሉ ፡ ተሣለ ፡ በክርስቶስ ፡ በደቀ ፡ መዛሙርቱም ፡ በኤጲስቆጶሳትም ፡ በሞቱም ፡ ሰማዕቶች ፡ በሌሎች ፡ ቅዱሳንም ፡ ሥእል ፡፡ ይህ ፡ ግን ፡ ባለመጋደል ፡ አልሆነም ፡፡ የቈንታንቲኖስ ፡ ወደጅ ፡ ኤውሴቢዮስ ፡ የቄሣርያ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አስቴርዮስም ፡ ያማስያ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ የክርስቶስን ፡ ሥእል ፡ እንዳያደርጉ ፡ መከሩ ፡ አምፌሎኪዮስም ፡ ገሠጻቸው ፡ የቅዱሳን ፡ ሥእል ፡ እንዲያደርጉ ፡ በዚህ ፡ ፈንታ ፡ አካሔዳቸውን ፡ በቅዱስ ፡ ስራ ፡ ይሸልሙ ፡ ዘንድ ፡ መከሩቸው ፡፡ እንደህም ፡ አፈ ፡ ወርቅና ፡ ኒሎስ ፡ አውጉስቲኑስም ፡፡

ካመትም ፡ ፫፻፡ በኋላ ፡ በምሥራቅ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ጀመሩ ፡ ለሥእል ፡ እንዲሰግዱ ፡ ሌዎንትዮስም ፡ የንያጶሊስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በመጽሐፉ ፡ ሊያጸናቸው ፡ ፈለገ ፡፡ ክሴናያስ ፡ ግን ፡ የሄራጶሊስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ባገሩ ፡ ከለከለው ፡፡

፻፫፡ ስለ ፡ ማምለክ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ በዓልም ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡፡

በዚህ ፡ ዘመንም ፡ አያሌ ፡ መምህራን ፡ ተገኙ ፡ ቀንን ፡ ሁሉ ፡ ያስተካክሉ ፡ ለክርስቲያንም ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመልኩ ፡ ዘንድ ፡ በነፍሳቸውም ፡ ዕለት ፡ ዕለት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ በዓል ፡ ያድርጉ ፡ ዘንድ ፡ እንዲገባቸው ፡ በዓልም ፡ ለወትሮ ፡ ማምለክ ፡ ብቻ ፡ ለማስታሰብያ ፡ እን

ደ፡ ተደረገ፡ ያስተማረ፡፡ እንደሁም፡ ሄሮኒሙስ፡ አፈ፡ ወ
ርቅም፡ ሶቅራቴስም፡ አስተማረ፡፡

የበዓልም፡ ሁሉ፡ ሥርና፡ መኻከለኛ፡ ክርስቶስ፡ ነበረ፡
በዚህ፡ ዘመን፡ ደግሞ፡ እርሱም፡ የተሰቀለ፡ የሞተም፡
የተነሣም፡ በተመሰገነም፡፡ ዓርብ፡ በዚህ፡ ዘመን፡ በብ
ዙ፡ ስፍራ፡ በዓል፡ ሆነ፡ ስራ፡ ያልተሰራበት፡ ሰውም፡ ወ
ደ፡ ቤተ፡ ክርስቲያን፡ ተሰብስቦ፡ ንስሓ፡ የገባበት፡ ለክር
ስቶስ፡ ሞትም፡ አሰበ፡፡ ባያሌ፡ አብያተ፡ ክርስቲያናት
ም፡ ተቍረቡ፡፡ በምሥራቅም፡ በብዙ፡ ስፍራ፡ ሰንበት፡
ከሑድ፡ ጋራ፡ ተቀደሰ፡፡ በላውዲቅያ፡ ሲኖደስም፡ ታዘዘ፡
በቅደሚ፡ መጽሐፍ፡ ቅዱስን፡ እንዲያነቡ፡ በቤተ፡ ክርስቲ
ያን፡ በሑድ፡ እንዲያነቡት፡፡ ክርክርም፡ ተነሣ፡ በዚያ፡
ጾም፡ የሚገባ፡ እንደሆን፡ ወይስ፡ አይደለም፡ ብለው፡፡
ደህና፡ መምህራን፡ ግን፡ በዚህ፡ ሰውን፡ ሁሉን፡ እንደ፡
ፈቃዱ፡ ተው፡ አልተከራከረበትም፡ እንደ፡ አምብሮስዩ
ስና፡ ሄሮኒሙስ፡ አውጉስቲኑስም፡፡ ኢኖኬንቲዩስ፡ ግን፡
የሮም፡ ኤጲስቆጶስ፡ በቅደሚ፡ እንዲጾሙ፡ አዘ፡፡

እሑድም፡ በዚህ፡ ዘመን፡ በትእዛዝ፡ ተቀደሰ፡ የላው
ዲቅያ፡ ሲኖደስ፡ አብያተ፡ ክርስቲያናትን፡ ቆንስታንቲኖስ
ም፡ መንግሥቱን፡ ሁሉን፡ አዘውታልና፡ ያ፡ ቀን፡ ለረፍ
ትና፡ ለማምለክ፡ እንዲሆን፡ ብለው፡፡

ስለ፡ አመት፡ በዓለት፡፡ ባመት፡ ፬፻፤ ሌላ፡ በዓል፡ ገ
ና፡ አልተሰራም፡ በቀደመ፡ ዘመን፡ ከተሰሩ፡ በዓለት፡
በቀር፡፡ እርሳቸውም፡ የክርስቶስ፡ ሞት፡ የክርስቶስም፡
ትንሣኤ፡ የክርስቶስ፡ ዕርገትም፡ የመንፈስ፡ ቅዱስም፡
በዓለት፡፡

ስለ፡ ፋሲካ፡ በዓልም፡ በዚህ፡ ዘመን፡ በመጀመርያ፡ ገ
ና፡ መለየት፡ ነበረ፡፡ ስለዚህም፡ በቆንስታንቲኖስ፡ ትእዛ
ዝ፡ በኒቅያ፡ ሲኖደስ፡ ሥርዓትን፡ አደረጉ፡ ያይሁድን፡ ሥ
ርዓት፡ ትተው፡ የትንሣኤ፡ በዓል፡ በሑድ፡ የመስቀልም፡
በዓል፡ ባርብ፡ ያደርጉ፡ ዘንድ፡፡ የስክንድርያም፡ ኤጲስ
ቆጶስ፡ ወትሮ፡ በኤጲፋኒያ፡ በዓል፡ የፋሲካን፡ ጊዜ፡ ሊ
ያስታወቅ፡ ነበረ፡፡ አያሌ፡ አብያተ፡ ክርስቲያናት፡ ግን፡

ደህነን ፡ ሥርዓት ፡ አልተቀበሉምና ፡ ካይሁድም ፡ ጋራ ፡ በኒዛን ፡ ወር ፡ በ፲፬፡ ቀን ፡ ፋሲካቸውን ፡ አደረጉ ፡ ስለዚህ ፡ የ፲፬፡ ቀን ፡ ሰዎች ፡ ተብለው ፡ ተገዘቱ ፡፡

የ፵፡ ቀንን ፡ ጾም ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ደግሞ ፡ አጸኑ ፡፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በንስሐ ፡ ካለምም ፡ ታድሎ ፡ በመሸሸት ፡ ነፍሱን ፡ እንዲያሰናዳ ፡ የትንሣኤን ፡ በዓል ፡ በሚገባ ፡ መጠን ፡ በደስታ ፡ ያደርገው ፡ ዘንድ ፡፡ በለዚህ ፡ ፵፡ ቀንም ፡ መጨረሻ ፡ ሳምንት ፡ ታላቅ ፡ ሳምንት ፡ ተብላ ፡ ለክርስቶስ ፡ ሕማማት ፡ ለመታሰብ ፡ ተለየች ፡፡ በዚችም ፡ ሳምንት ፡ ፫፡ ቀን ፡ ተለዩ ፡ እርሳቸውም ፡ አሙስ ፡ ስለ ፡ ቍርባን ፡ መታሰብ ፡ ዓርብም ፡ ስለ ፡ መስቀል ፡፡ ቅዳሜም ፡ ታላቅ ፡ ሰንበት ፡ ተባለ ፡፡ በርሱም ፡ ብዙ ፡ ተጠመቁ ፡ ከተሞችም ፡ ሁሉ ፡ በማተ ፡ በሩ ፡፡ ሰውም ፡ ሁሉ ፡ መብራት ፡ ይዞ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገባ ፡፡ የፋሲካውንም ፡ ጽዋት ፡ ጠበቀ ፡ በክርስቶስ ፡ ትንሣኤ ፡ ደስ ፡ ይለው ፡ ዘንድ ፡፡ ያም ፡ በዓል ፡ ፰፡ ቀን ፡ ኖረ ፡ አዲስ ፡ የተጠመቁም ፡ በዚያች ፡ ሳምንት ፡ ወትሮ ፡ ነጭ ፡ ልብስ ፡ ለበሱ ፡ ደስም ፡ አሉ ፡፡ በዚች ፡ ሳምንትም ፡ አዲስ ፡ እንደ ፡ ተወለዱ ፡ ሕፃናት ፡ ተቈጥረዋልና ፡ ስምንተኛው ፡ ቀን ፡ የሕፃናት ፡ ቀን ፡ ተባለ ፡፡ እለዚያም ፡ ፶፡ ቀን ፡ ከፋሲክ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ጴንጠቆስጤ ፡ ድረስ ፡ ፩፡ በዓል ፡ ሁነው ፡ ተቈጠሩ ፡ ፪፡ ቀንም ፡ የርገትና ፡ የጴንጠቆስጤ ፡ ቀን ፡ ከሌሎች ፡ ተለይተው ፡ በለጡ ፡፡

በዚህ ፡ ዘመንም ፡ ፪፡ በዓላት ፡ ተጨመሩ ፡ እርሳቸውም ፡ ኤጲፋኒያና ፡ የልደት ፡ በዓል ፡፡ ኤጲፋኒያም ፡ የዮናኒ ፡ ቋንቋ ፡ መገለጽ ፡ ማለት ፡ ሁኖ ፡ ፪፡ ልዩ ፡ መክንያት ፡ አደረጉ ፡ ለዚህ ፡ በዓል ፡፡ በምሥራቅ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ጥምቀት ፡ በምዕራብም ፡ ስለ ፡ መገለጹ ፡ ለሰብአ ፡ ሰግላን ፡፡ ደግሞም ፡ ስለ ፡ ኃይሉ ፡ መገለጽ ፡ በሰርግ ፡ በቃና ፡ በገሊላ ፡ ተቀደሰ ፡፡ ይህ ፡ በዓልም ፡ ከምሥራቅ ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ደረሰ ፡፡

የልደት ፡ በዓል ፡ ግን ፡ ከምዕራብ ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ መጣ ፡፡ ካመት ፡ ፫፶፡ በኋላ ፡ ጀመረ ፡፡

አንድ ፡ ሳምንትም ፡ ከልደት ፡ በኋላ ፡ የሮም ፡ መንግሥ

ት ፡ ያመትዋ ፡ መጀመርያ ፡ ነበር ፡ በዚህ ፡ መክንያትም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አስቀድሞ ፡ ፫፤ ቀን ፡ ለንስሓ ፡ አደረገ ች ፡ በኋላም ፡ የክርስቶስን ፡ ግዝረት ፡ በ፰፤ ቀን ፡ ከልደት ፡ በኋላ ፡ አሰበች ፡፡

፬፬፤ የማምለክ ፡ ስራ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡፡

የማምለክ ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ ይህ ፡ ነበረ ፡ የእግዚአብሔር ን ፡ ቃል ፡ ማንበብ ፡፡ በየጉባኤ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገ ልጋይ ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ክፍልን ፡ አነበበ ፡፡ በየበዓል ም ፡ የበዓልን ፡ መክንያት ፡ ከወንጌል ፡ አነበበ ፡፡

ስለ ፡ ስብከት ፡፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ አሳብ ፡ ስ ለ ፡ ስብከት ፡ አንድ ፡ አልነበረም ፡፡ ባንድ ፡ ስፍራ ፡ ታናስ ፡ ነገር ፡ አደረጉት ፡ የቄስን ፡ ስራ ፡ ጸሎትና ፡ መዝመር ፡ ማ ቍረብም ፡ ማጥመቅም ፡ ቍጠሩት ፡ ስብከትን ፡ ግድ ፡ የ ለም ፡ ብለው ፡፡ በሌላ ፡ ስፍራ ፡ ግን ፡ ስብከትን ፡ ከሌላ ፡ ማምለክ ፡ ሁሉ ፡ የሚበልጥ ፡ ቍጠሩት ፡ ቄስም ፡ በጎ ፡ ተ ናጋሪ ፡ ካልሆነ ፡ አልተቀበሉትም ፡፡

ለመዝመርም ፡ ሥርዓትን ፡ አደረጉ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡፡ ስ ለ ፡ መዝመሪቸውም ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ የተለቀሙት ን ፡ መዝሙሪትንና ፡ ምስጋናውን ፡ ደግሞ ፡ አዲስ ፡ የተሰ ራውን ፡ ቅኔ ፡ ወሰዱ ፡፡ አምብሮስዩስ ፡ የሚደላንድ ፡ ኤጲ ስቆጶስ ፡ ሂላርዩስም ፡ የጶዋቴ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ባሲልዮስ ም ፡ ሌሎችም ፡ እንዲህ ፡ አደረጉ ፡፡

ስለ ፡ ምሥጢራት ፡፡ ጌታችን ፡ ስለ ፡ ሃይማኖታችን ፡ አ ንድነት ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የሰጣቸውን ፡ ምሥጢራት ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ በክርስቲያን ፡ ብዛት ፡ እንደ ፡ ሥጋ ፡ መጠን ፡ ተቀ በሉ ፡ የሚታይን ፡ ከማይታይ ፡ ነገር ፡ ሳይለዩ ፡፡ እንዲህም ፡ ሆነ ፡ በጥምቀት ፡፡ ብዙ ፡ ወላጆች ፡ ፈርተው ፡ ልጆቻቸው ፡ የጥምቀትን ፡ ጸጋ ፡ በኃጢአት ፡ እንዳይሽሩ ፡ ቀዩ ፡ የልጆቻ ቸው ፡ ዕድሜ ፡ እስኪበስል ፡ ድረስ ፡፡ ሌሎችም ፡ እጅግ ፡ ቀዩ ፡ የኃጢአታቸውን ፡ መስፈር ፡ በፊት ፡ ሊመሉ ፡ በኋላ ም ፡ ተጠመቁ ፡ ኃጢአትን ፡ ማድረግ ፡ ባልቻሉ ፡ ጊዜ ፡ ለሞ ትም ፡ በቀረቡ ፡ ጊዜ ፡፡

ቍርባንንም ፡ ምሥዋዕት ፡ ሁኖ ፡ ሲቈጥሩት ፡ ሕዝቡ ፡ ተሳተኙ ፡ ቄስ ፡ ክርስቶስን ፡ ሁልግዜ ፡ ደግሞ ፡ እንደ ሠወው ፡ ሲያስቡ ::

አስቀድሞም ፡ የተጀመረውን ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ጨመሩ ፡ ቅዱሳንን ፡ እንደደገባ ፡ ያከብሩ ፡ ዘንድ :: በዓልንም ፡ ያደርጉላቸው ፡ ዘንድ :: አፅንታቸውንም ፡ የተባሉ ፡ እንኳ ፡ ጠበቁ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ አኖሩት ፡ ታመኑበትም ፡ ታምሬትንም ፡ ያደረጉ ፡ መሰላቸው :: በዚህ ፡ መክንያትም ፡ ታላቅ ፡ ክርክር ፡ ሆነ ፡ ለሄሮኒሙስ ፡ ከዊጊላንቲዩስ ፡ ጋራ ::

አንዲት ፡ ወገንም ፡ መናፈቃን ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ነበሩ ፡ ማርያም ፡ ድንግልን ፡ ያመለኩ :: እርሳቸውም ፡ ሴቶች ፡ ነበሩ ፡ በዐረብ ፡ ምድር ፡ ራሳቸውን ፡ የማርያም ፡ ካህናት ፡ ያደረጉ ፡ በዓልን ፡ አደረጉ ፡ ቂጣ ፡ የሚሠውበት ፡ ለማርያም :: እርሳቸውም ፡ ተገዘቱ ::

የቈንስታንቲኖስ ፡ እናት ፡ ሄሌና ፡ ከሌሎች ፡ ከንጉሥ ፡ ዘመዶች ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ የሩሳሌም ፡ ከሔደ ፡ በኋላ ፡ ክርስቶስ ፡ የነበረበትን ፡ ስፍራ ፡ ሁሉ ፡ ያዩ ፡ ዘንድ ፡ ብዙ ፡ ሌሎች ፡ ክርስቲያናት ፡ ተከተልዋቸው ፡ ሰውም ፡ አላለቀም ፡ በስፍራ ፡ ሁሉ ፡ የታወቀውን ፡ ያልታወቀውንም ፡ ነገር ፡ ያሳዩ :: በዚህ ፡ ነገር ፡ ደግሞ ፡ በጎ ፡ ከክፉ ፡ ጋራ ፡ ተደብልቆ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ መሰሉ ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ ተቀደሰ ፡ ስፍራ ፡ ከልብ ፡ ቅድስና ፡ ከበጎ ፡ ስራም ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ተሻለ :: ወደ ፡ ሩቅ ፡ አገርም ፡ ሒደው ፡ የክርስቶስን ፡ የቅዱሳኑም ፡ ቦታ ፡ ሲያዩ ፡ ከክርስቶስ ፡ ትእዛዝ ፡ ሁሉ ፡ ባገሬቸው ፡ የተፈቱ ፡ መሰላቸው ::

አራተኛ ፡ ምዕራፍ ፡

የክርስቲያን ፡ ትምህርት ፡ ታሪክ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡፡

፩፤ ስለ ፡ ትምህርት ፡ ሁሉ ፡ እንዲያው ፡፡

የክርስቲያን ፡ ትምርት ፡ ዕውቀት ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ በምርምርና ፡ በክርክር ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መካከል ፡ አደገች ፡፡ አስቀድሞ ፡ በሚደ ፡ ከነበረ ፡ ካረማውያንና ፡ ከመናፈቃን ፡ ጋራ ፡ ተከራከረ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ግን ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡ በሚለዩበት ፡ ነገር ፡ ተመጓጉቱ ፡፡ እግዚአብሔርም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑን ፡ ጠበቀ ፡ መሠረትዋ ፡ እንደደገለበጥ ፡ የሰውም ፡ ክፋት ፡ የሰውን ፡ ነገር ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ነገር ፡ ጋራ ፡ በትምርቱ ፡ ሲደበልቅ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጽሩ ፡ ኑሮ ፡ እንደይደበለቅ ፡ ከሰው ፡ ነገር ፡ ጋራ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ እንደደርቅ ፡፡

በዚህ ፡ ዘመንም ፡ ከሁሉ ፡ የሚበልጥ ፡ መምህር ፡ ትምርቱ ፡ እስከ ፡ ዘመናችን ፡ ድረስ ፡ እጅግ ፡ ፍሬን ፡ ያፈራ ፡ አውጉስቲኑስ ፡ ነበረ ፡፡ ሞኒካ ፡ የሚልዋት ፡ እናቱ ፡ በጸሎትና ፡ በንብ ፡ በጅግ ፡ መጋደልም ፡ ስለ ፡ ነፍሱ ፡ መድኃኒት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቀደሰቸው ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስም ፡ አስተማረቸው ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ እርስዋ ፡ በነፍሱ ፡ የሰራችውን ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ አረማዊ ፡ የነበረ ፡ አባቱ ፡ አፈረሰበት ፡፡ ዕድሜውም ፡ ፲፱፤ አመት ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ እርሱም ፡ በከርታጎ ፡ ሲኖር ፡ በኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ ወደቀ ፡፡ ከዚያ ፡ በኋላም ፡ ፊሎሶፊያን ፡ ተማረ ፡ በፊሎሶፊያ ፡ ኃይልም ፡ በፈቃዱ ፡ ላይ ፡ ሊገዛ ፡ ኃጢአቱንም ፡ ሊያሸንፍ ፡ ተስፋ ፡ አደረገ ፡፡ አሁንም ፡ መጋደል ፡ጀመረ ፡ ከኃጢአት ፡ ጋራ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ፊሎሶፊያ ፡ ኃይልን ፡ አልሰጠቸውም ፡፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ናቀ ፡ ከለልቡ ፡ ሁሉ ፡ ዕውቀትንና ፡ ደህንነትን ፡ ሲሻ ፡፡ ስለዚህም ፡ ማኒኬዎስ ፡ ሆነ ፡ በማኒኬዎች ፡ መለየት ፡ ምናልባት ፡ ያነን ፡ ለነፍሱ ፡ ሰላም ፡ መስጠት ፡ የሚችል ፡፡ ዕውቀት ፡ ባያገኝ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ፲፤ አመት ፡ ከማኒ ፡

ወገን ፡ ከተማረ ፡ በኋላ ፡ ትምርታቸው ፡ ሁሉ ፡ ስሕተት ፡ እንደ ፡ ሆነች ፡ አገኘ ፡፡ አሁንም ፡ ወደ ፡ ጽላቶን ፡ ፊሎሰፊያ ፡ ሔደ ፡፡ ይህችንም ፡ ፊሎሶፊያን ፡ እጅግ ፡ ወደደ ፡ በርስዋም ፡ ዕረፍትን ፡ ያገኝ ፡ ዘንድ ፡ ተስፋ ፡ አደረገ ፡፡ እርሱም ፡ በሕፃንነቱ ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ከክርስቲያን ፡ ሃይማኖትም ፡ ያወቀውን ፡ ነገር ፡ አስቦ ፡ ይህ ፡ ከጽላቶን ፡ ፊሎሶፊያ ፡ ጋራ ፡ እንዲገጠም ፡ መሰለው ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ዕውር ፡ እንዲፈርድ ፡ ስለ ፡ ቀለም ፡ እንዲህም ፡ አውጉስቲኑስ ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ፈረደ ፡ ስለ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡፡ ትሕትና ፡ ሃይማኖትም ፡ ፍቅርም ፡ አልነበረለትም ፡ ያለርሱ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ከማስተዋል ፡ የተዘጋ ፡፡ ያውጉስቲኑስም ፡ ተስፋ ፡ በኃጢአቱ ፡ ተሻረ ፡፡ ፊሎሶፊያው ፡ ከኃጢአቱ ፡ ያደነው ፡ ዘንድ ፡ አልቻላትምና ፡፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በኃጢአት ፡ ላይ ፡ ያሸነፈ ፡ በመሰለው ፡ ጊዜ ፡ ቶሎ ፡ ተመልሶ ፡ ወደቀበት ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ የልቡን ፡ ጥፋት ፡ ሲያይ ፡ የጳውሎስን ፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ ሮሜ ፡ ሰዎች ፡ አነበበ ፡ በርሱም ፡ የልቡ ፡ የኃጢአቱም ፡ ዕውቀት ፡ ጸና ፡፡ ለመዳንም ፡ የነበረለት ፡ መመኛቱ ፡ በረታ ፡፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ እንዲህ ፡ ሁኖ ፡ ባትክልቱ ፡ ሲቀመጥ ፡ እጅግ ፡ ብርቱ ፡ ልቅሶም ፡ ከልቡ ፡ ሲያለቅስ ፡ ሲጸልይም ፡ ሲልም ፡፡ አቤቱ ፡ እስከ ፡ መቼ ፡ ትቈጣለህ ፡ በኃጢአቴ ፡ ለዘላለምን ፡፡ ኃጢአቴን ፡ አታስብ ፡፡ እስከ ፡ መቼም ፡ ነጋ ፡ እላለሁ ፡፡ ምነው ፡ የኃጢአትን ፡ ባርነቴን ፡ አሁን ፡ አልጨርስም ፡፡ እንዲህ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ልቡን ፡ በከፈተ ፡ ጊዜ ፡ ድምጽን ፡ ሰማ ፡ የሚል ፡፡ እንካና ፡ አንብብ ፡ እንካና ፡ አንብብ ፡፡ ይህነን ፡ ድምጽ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ተቀበለው ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስንም ፡ ወስደ ፡ የጳውሎስን ፡ ነገር ፡ አገኘ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ በቀን ፡ እንሒድ ፡ በቅን ፡ ነገር ፡፡ በዘፈንና ፡ በስካርም ፡ አይደለም ፡፡ ፊቃደችነንም ፡ በመከተል ፡ አይደለም ፡ ርኵሰትንም ፡ ሐሜትንም ፡ ቅናትንም ፡፡ ጌታን ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ልበሱት ፡ እንጂ ፡ ሥጋችሁንም ፡ ጠብቁ ፡ በፍትወት ፡ እንዲደኖር ፡፡ ሮሜ ፡ ፲፫ ፡ ፲፫ ፡ ፲፬ ፡፡ ይህም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነገር ፡ ልቡን ፡ አበራ ፡ ኃጢአቱንም ፡ አስታወቀው ፡፡ ደግሞ

ም ፡ የኃጢአቱን ፡ መድኃኒት ፡፡ በርሱም ፡ ዕርቅና ፡ ዕረፍ
ት ፡ ወደ ፡ ልቡ ፡ ገባ ፡፡ ደስም ፡ አለ ፡ በእግዚአብሔር ፡ በ
መድኃኒቱ ፡፡ አሁንም ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ነገር ፡ አስታ
ውሎ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በልቡ ፡ ሲኖር ፡ አስተምሮታልና ፡
ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ማስተማር ፡ ቻለው ፡ የርሱም ፡ ታላ
ቅ ፡ ቃል ፡ ለውቀት ፡ ሁሉ ፡ ለመሠረት ፡ ያደረገው ፡ ይህ ፡
ነበረ ፡ ሲል ፡፡ ሃይማኖት ፡ ማስታዋልን ፡ ትቀደማለች ፡፡

፪፡ የልዩ ፡ ልዩ ፡ የሃይማኖት ፡ ትምርት ፡ ታሪክ ፡፡

፩፩፡ ስለ ፡ ቴዎሎጊያ ፡፡ የክርስቲያን ፡ ትምርት ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡፡

ስለ ፡ ሥላሴ ፡፡ ስለ ፡ ሥለሴ ፡ በቀደመ ፡ ዘመን ፡ የነበረ
ች ፡ ትምህርት ፡ አንድ ፡ አልነበረችም ፡ በፊት ፡ እንደየነ ፡፡
ኦሪጌኔስ ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርቱ ፡ ጋራ ፡ ይሉ ፡ ነበረ ፡፡ የእግዚ
አብሔር ፡ ልጅ ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አ
ብ ፡ እንደ ፡ ፈሰሰ ፡ ከአብ ፡ ባሕሪ ፡ ግን ፡ አልተወለደም ፡፡
የምዕራብ ፡ መምህራን ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ከ
አብ ፡ ባሕሪ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ከእግዚአብሔር ፡
አብም ፡ ባሕሪ ፡ ከዘላለም ፡ እንደ ፡ ተወለደ ፡ አሉ ፡፡ ስለ
ለዚህ ፡ ፪፡ ትምርቶችም ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ታላቅ ፡ መመጉ
ት ፡ ሆነ ፡፡ የክርስቲያንም ፡ ትምህርት ፡ ክርስቲያን ፡ ባልነበ
ረች ፡ ትምህርት ፡ ላይ ፡ አሸነፈች ፡፡ ይህ ፡ ክርክር ፡ በዚህ ፡ ዘ
መን ፡ ጀመረ ፡ በአርዮስ ፡ በስክንድርያ ፡ ቄስ ፡፡ አሪዮስም ፡
ትምርቱ ፡ አዲስ ፡ እንደሆነ ፡ አላሰበም ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡
የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ካልጀ
መረ ፡ ባይሆን ፡ ነበረ ፡ ወይስ ፡ ሁለተኛ ፡ አምላክ ፡ ብቻ ፡፡ አ
ሁንም ፡ ፩፡ አምላክ ፡ ብቻ ፡ አለ ፡ በርሱምና ፡ በፍጥረት ፡
መኻከል ፡ አንደኛ ፡ አደገባምና ፡ ብሎ ፡ እንኪያስ ፡ የእግ
ዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ፍጥረት ፡ ነው ፡፡ እርሱም ፡ የፍጥረት ፡
መጀመርያ ፡ ምንም ፡ ሳይሆን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡
የተፈጠረ ፡ ወይስ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ተወለደ ፡ ሲል ፡ ተ
ፈጠረ ፡ ማለት ፡ እንደሆን ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ከፍጥረቱ ፡

ሁሉ ፡ እንደ ለይ ፡ እንዲህም ፡ ይለያል ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡
ከእግዚአብሔር ፡ መፈጠር ፡ እንደ ይችል ፡፡ ስለዚህም ፡ እ
ግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ ባሕሪዩን ፡ አደረገ ፡ እርሱን ፡ እንዲ
ህ ፡ የሚመስለው ፡ ፍጥረት ፡ እንኳ ፡ እግዚአብሔርን ፡
መመሰል ፡ እንደሚችል ፡ በርሱም ፡ የቀረች ፡ ፍጥረት ፡ ሁ
ሉ ፡ ተፈጠረች ፡፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ግን ፡ ሲባል ፡ እ
ርሱ ፡ ከሌላ ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ እንደ በልጥ ፡ ማለት ፡ ነው ፡፡
አምላክም ፡ ብሎ ፡ አሪው ፡ ደር ፡ በአምላክ ፡ ምሳሌ ፡ ብ
ቻ ፡ የሚሆን ፡ አለ ፡፡ አሪዮስም ፡ እጅግ ፡ ብልህ ፡ አልነበረ
ምና ፡ አያውቅም ፡ ነበር ፡ ትምህርቱ ፡ እውነት ፡ እንደሆነ ፡
ወንጌል ፡ ሁሉ ፡ በተኳረበት ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ቤተ ፡
ክርስቲያኑን ፡ ጠበቀ ፡ በመንፈሱም ፡ ሰዎችን ፡ አስነሣ ፡
የአሪዮስን ፡ ስሕተት ፡ ከንቱ ፡ ሁና ፡ የገለጽዋት ፡ በመጽሐ
ፍ ፡ ቅዱስና ፡ በተቀደሰች ፡ አእምሮ ፡ የኳረትም ፡፡ እስ
ክንድርም ፡ የስክንድርያ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በፊት ፡ አሪዩስ
ን ፡ ገሠጸ ፡ በኋላም ፡ ባመት ፡ ፫፻፳፩፡ በምስር ፡ በተሰበሰ
በች ፡ ሲኖደስ ፡ ፻፡ መምህራን ፡ የተከማቹባት ፡ ያሪዮስን ፡
ሹመት ፡ ሻረ ፡ ገዘተውም ፡፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ አርዮስ ፡
መጻሕፍትን ፡ ጻፈ ፡ ትምርቱን ፡ የሚያስታውቅበት ፡፡ እ
ስክንድርም ፡ መልእክትን ፡ ጻፈ ፡ ለታላቆች ፡ ኤጲስቆ
ጶሳት ፡ ያሪዮስን ፡ ትምርት ፡ ስሕተት ፡ ሁና ፡ ያስታወቃቸ
ውን ፡፡ አርዮስም ፡ እርሱ ፡ ደግሞ ፡ ጻፈ ፡ የምሥራቅን ፡ ኤ
ጲስቆጶሳት ፡ ወዳጆቹን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡፡ አሁንም ፡ ፪፡ ኤ
ጲስቆጶሳት ፡ ነበሩ ፡ ኤውሴቢዮስ ፡ የተባሉ ፡ አንድም ፡ የ
ኒቆሚዲያ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ያሪዮስ ፡ ወዳጅ ፡ ትምርቱም ፡
ያሪዮስን ፡ ትምርት ፡ የመሰለች ፡፡ ኤውሴቢዮስም ፡ የቄሣር
ያ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ የቆንስታንቲኖስ ፡ ወዳጅ ፡ የተማረ ፡ ሰ
ውም ፡፡ የርሱም ፡ ትምህርት ፡ የዲዮኒስዮስን ፡ የኦሪጌኔ
ስ ፡ የደቀ ፡ መዝሙሩን ፡ ትምርት ፡ መሰለች ፡፡ እርሱም ፡
እስክንድርንና ፡ አሪዮስን ፡ ያስታርቅ ፡ ዘንድ ፡ ፈለገ ፡፡ ይ
ህም ፡ ሳይጠቅም ፡ ቆንስታንቲኖስ ፡ መልእክትን ፡ ሰደ ፡ ለ
እስክንድርና ፡ ላሪዮስ ፡ በሆስዮስ ፡ እጅ ፡ እርሱም ፡ የኮ
ርዶዋ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡፡ ቆንስታንቲኖስም ፡ በዚህ ፡ ክርክር ፡

ሁሉ ፡ አዘነ ፡ አላቸውም ፡፡ ሁለታቸው ፡ ወንድሞች ፡ ሁነ
ዋልና ፡ እንደ ይገባቸው ፡ በዚህ ፡ ታናሽ ፡ በመሰለው ፡ ነገር ፡
ይከራከሩ ፡ ዘንድ ፡፡ ደግ ፡ እንዲህ ፡ አልሆነም ፡ ያስታርቋቸ
ው ፡ ዘንድ ፡ ስለዚህም ፡ ታላቅ ፡ ሲኖዶስ ፡ ከመንግሥት ፡
ሁሉ ፡ በቈንስታንቲኖስ ፡ ትእዛዝ ፡ ተሰበሰበች ፡ ባመት ፡
፫፻፳፭ ወደ ፡ ኒቅያ ፡ በቢቲንያ ፡፡ ፫፻፲፰ ኤጲስቆጶሳትም ፡ ተ
ሰበሰቡ ፡ ከርሳቸውም ፡ ብዙ ፡ ከምሥራቅ ፡፡ ቈንስታንቲኖ
ስም ፡ ባለቤቱ ፡ ለመመጐት ፡ ገባ ፡፡ አሁንም ፡ ፪ ወገን ፡
ነበሩ ፡፡ ያንድ ፡ ወገንም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ከአብ ፡
ጋራ ፡ ሆሞውስዮስ ፡ ነው ፡ ያሉ ፡ ያንድ ፡ ባሕሪ ፡ ማለት ፡
የሚሆን ፡፡ እርሳቸውም ፡ የእስክንድርና ፡ የምዕራብ ፡
ወገን ፡፡ የሁለተኛ ፡ ወገን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ከአብ ፡
ባሕሪ ፡ የተለየ ፡ ባሕሪ ፡ ነው ፡ ተፈጠረም ፡ ያሉ ፡ እርሳ
ቸውም ፡ ያሪዮስና ፡ የኤውሴብዮስ ፡ ከኒቆሜድያ ፡ ወገ
ን ፡ ብዙ ፡ አልነበሩም ፡፡ በለዚህ ፡ ፪ መኻከልም ፡ ሶስተ
ኛ ፡ ወገን ፡ ነበረ ፡ ከኤውሴብዮስ ፡ ከቄሣርያ ፡ ጋራ ፡ የነበ
ሩ ፡ እርሳቸውም ፡ ብዙ ፡ ነበሩ ፡፡ እርሳቸውም ፡ አሉ ፡፡ የ
እግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ከአብ ፡ ጋራ ፡ ሆሞውስዮስ ፡ አይደለ
ም ፡ ሆሞዩስዮስ ፡ ነው ፡ እንጅ ፡ ማለት ፡፡ የልጅ ፡ ባሕሪ ፡
የአብን ፡ ባሕሪ ፡ ይመስላል ፡፡ እርሳቸውም ፡ ማስታረቅ ፡ ፈ
ለጉ ፡፡ እርሳቸውም ፡ በኤውሴቢዮስ ፡ ከቄሣርያ ፡ እጅ ፡ የ
ሃይማኖትን ፡ ምሳሌ ፡ አደረጉ ፡ በርሱ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ እ
ንዲህ ፡ ያሉበት ፡፡ እርሱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ አምላክ
ም ፡ ካምላክ ፡ ብርሃንም ፡ ከብርሃን ፡ ሕይወትም ፡ ከሕይ
ወት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የፍጥረትም ፡ ሁሉ ፡ መጀመርያ ፡ ወይ
ስ ፡ በኵር ፡ ካለምም ፡ ሁሉ ፡ አስቀድሞ ፡ ከአብ ፡ የተወ
ለደ ፡፡ ይህችም ፡ ምሳሌ ፡ ደህና ፡ ሆነች ፡ ደግ ፡ አንዳንድ ፡
መጨመርያ ፡ ቃል ፡ ፈለገች ፡ ካርዮስ ፡ ትምርት ፡ ፈጹም ፡
መለየት ፡ ትለይ ፡ ዘንድ ፡፡ አሁንም ፡ ቈንስታንቲኖስ ፡ ያ
ሪዮስን ፡ ስድብ ፡ አይቶ ፡ እንደ ፡ እስክንድር ፡ ወደደ ፡፡
እንዲህም ፡ የኒቅያ ፡ የሃይማኖት ፡ ምሳሌ ፡ ሆነች ፡ እን
ዲህ ፡ የምትል ፡፡

እኔ ፡ አምናለሁ ፡ ባንድ ፡ አምላክ ፡ ሁሉን ፡ በሚ
ችል ፡ አብ ፡ የሰማይና ፡ የምድር ፡ የሚታይም ፡ የ
ማይታይም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ፈጣሪ ።
ባንድ ፡ ጌታም ፡ በየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ እርሱም ፡
ብቻውን ፡ የተወለደ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ከ
አብ ፡ የተወለደ ፡ ካለም ፡ ሁሉ ፡ አስቀድሞ ። አ
ምላክ ፡ ከአምላክ ። ብርሃንም ፡ ከብርሃን ። እ
ውነተኛ ፡ አምላክ ፡ ከውነተኛ ፡ አምላክ ። የተወ
ለደም ፡ ያልተፈጠረ ። ያንድ ፡ ባሕሪ ፡ ሁኖ ፡ ከአ
ብ ፡ ጋራ ። ነገር ፡ ሁሉ ፡ በርሱ ፡ የሆነ ። እር
ሱም ፡ ስለኛ ፡ ሰዎች ፡ ስለ ፡ መድኃኒታችን ፡ ከሰ
ማይ ፡ ወረደ ፡ ሥጋም ፡ ለበሰ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡
ከማርያም ፡ ድንግል ። ሰውም ፡ ሆነ ። ደግሞ
ም ፡ ስለኛ ፡ ተሰቀለ ፡ በጲላጦስ ፡ በጴንጤናዊ ፡
ዘመን ። እርሱም ፡ መከራ ፡ ተቀበለ ፡ ተቀበረ
ም ። በሦስተኛውም ፡ ቀን ፡ ተነሣ ፡ በመጽሐፍ ፡
ቅዱስ ፡ እንደ ፡ ተባለ ። ወደ ፡ ሰማይም ፡ ወጣ ።
ወደ ፡ አብም ፡ ወደ ፡ ቀኙ ፡ ይቀመጣል ። በምስጋ
ናም ፡ ይመለስ ፡ ዘንድ ፡ ጊዜ ፡ አለው ፡ በሕያዋን
ና ፡ በሙታን ፡ ለመፍረድ ። መንግሥቱም ፡ መጨ
ረሻ ፡ የላትም ።
አምናለሁም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ። እርሱም ፡ ጌ
ታ ፡ የሕይወትም ፡ ሰጭ ፡ የሚሆን ። ከአብ ፡ የሚ
ወጣ ። ከአብና ፡ ከልጅ ፡ ጋራ ፡ ባንድ ፡ የሚሰግ
ዱለት ፡ የሚያመሰግኑትም ። እርሱም ፡ በነቢያት ፡
አፍ ፡ ተናገረ ። አምናለሁም ፡ ባንዲት ፡ ካቶሊካ
ዊትና ፡ አጶስቶሊካዊት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ። አስ
ታውቃለሁም ፡ አንዲትን ፡ ጥምቀት ፡ ለኃጢአት ፡
ስርየት ። ተስፋም ፡ አደርጋለሁ ፡ የሙታንን ፡ ትን
ሣኤ ። የሚመጣውንም ፡ ዓለም ፡ ሕይወት ።
ይህችንም ፡ ምሳሌ ፡ ብዙ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ተቀበሉ ። በ
መጀመርያም ፡ ፲፪ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ እምቢ ፡ አሉ ፡ ደሮ ፡ የ
ቄሣርን ፡ ቍጣ ፡ ፈርተዋልና ፡ ተቀበሉት ፡ የአሪዮስንም ፡

ትምርት : ወገዙ : ከ፪ ፡ በቀር :: እርሳቸውም : የመርማሪ
ካ : ኤጲስቆጶስ : ቴዎናስ : የሚሉት : የጵቶሌማይስም :
ኤጲስቆጶስ : ሴኩንደስ :: ያሪዮስ : ፪ ፡ ወደጆች : ግን : የኒ
ቆሚዲያ : ኤውሴቢዮስና : የኒቅያ : ቴዎግኒስ : ስለ : ዕር
ቅ : ብለው : የሃይማኖትን : ምሳሌ : ከመውገዝ : በቀር :
ተቀበሉት :: አሪዮስም : ከ፪ ፡ ምሳሌን : ካልተቀበሉ : ጋራ :
ካገራቸው : ተሳደደ :: የቀረም : ፪ ፡ ደግሞ : በኋላ : ተሳደ
ደ :: ከዚያ : ወዲያም : የቆንስታንቲኖስ : ቍጣ : ባሪዮ
ስ : ላይ : ባመት : ፫፻፳፰ ፡ አርፎ : አስመለሰው ::

አሁን : ግን : አታናስዮስ : ተነሣ : በመንፈስና : በኃይ
ል : በታላቅ : መጋደልም : በመከራም : እውነተኛውን :
ትምህርት : ስለ : ክርስቶስ : ስለ : መለኮቱ : አንድነት :
ከአብ : ጋራ : ኢየጠበቀ :: እርሱም : አለ :: የእግዚአብ
ሔር : ልጅ : መካከለኛችን : ይሆን : ዘንድ : አይችልም :
አንድነትም : ከእግዚአብሔር : ጋራ : ያደርግልን : ዘንድ :
አይችልም : እርሱም : ለራሱ : አምላክ : ከአብም : ጋራ :
አንድ : ባይሆን : ስለዚህም : በሆሞውስዮን : ትምርት :
የመድኀኒታችን : ትምህርት : ትኖራለች :: አታናስዮስ
ም : ጥቂት : ወራት : ከኒቅያ : ሲኖደስ : በኋላ : የሞተው
ን : እስክንድርን : በሹመቱ : ተከተለው :: ያሪዮስ : ወደ
ጆችም : በከንቱ : ከለመኑት : በኋላ : አሪዮስን : መልሶ
ት : ይቀበለው : ዘንድ : ቆንስታንቲኖስ : አዘዘው : ባይሰ
ማም : ተቆየመው : ካገሩ : ይሰደው : ዘንድ :: አታናስዮስ :
ግን : አልፈራም : ስለ : ክርስቲያን : አካሔዱም : ቆንስታ
ንቲኖስ : የዚያን : ጊዜ : ተወው :: ጸላቶቹ : ግን : ሁሉግዜ :
ሲከሱት : ባመት : ፫፻፴፭ ፡ ሲኖደስ : ተሰበሰበች : በጢሮስ :
በቆንስታንቲኖስ : ትእዛዝ : የቄሣርያ : ኤውሴቢዮስ : ሲፈ
ርድ :: ፈራጆቹ : ግን : ግፍ : አደረጉበት : ከዚያም : ወደ :
ቆንስታንቲኒያ : ወደ : ቄሣር : ሲሔድ : አሳደደት : ቄሣር :
ለስደት : እስኪያውጣው : ድረስ : ወደ : ትሪር : በንምሳ :
ምድር : ባመት : ፫፻፴፮ ። የዚያን : ጊዜም : በየሩሳሌም :
የቅዱስ : መቃበር : ቤት : ክርስቲያን : ቆንስታንቲኖስ : ያ
ሠራት : ተፈጸመች : ሲቀድስዋትም : ሲኖደስ : በየሩሳሌም :

ተሰበሰበች ፡ አሪዮስን ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አንድነት ፡ መልሰው ፡ የተቀበሉት ፡፡ ቆንስታንቲኖስም ፡ አሪዮስን ፡ ሊመረምር ፡ ብሎ ፡ ወደ ፡ ቆንስታንቲኒያ ፡ አስመጣው ፡፡ ከዚያም ፡ አሪዮስ ፡ የሃይማኖትን ፡ ምሳሌ ፡ አደረገ ፡ የኒቅያን ፡ ምሳሌ ፡ የሚመስል ፡ ትምህርቱም ፡ የተሰወረችበት ፡፡ ቆንስታንቲኖስም ፡ አስማለው ፡ እንደዚህ ፡ ምሳሌ ፡ ያስተምር ፡ ዘንድ ፡፡ ከዚያ ፡ ወዲያም ፡ ቆንስታንቲኖስ ፡ ተረድቶ ፡ አሪዮስ ፡ ደህና ፡ ክርስቲያን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ በግልጽ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወደ ፡ ክርስቲያን ፡ አንድነት ፡ ሊያስቀበለው ፡ ወደደ ፡፡ ያ ፡ ግን ፡ ሳይሆን ፡ አሪዮስ ፡ በድንገት ፡ ሞተ ፡ ባይነ ፡ ምድር ፡ ተቀምጦ ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ፈርደበታልና ፡፡

ቆንስታንቲኖስም ፡ ባመት ፡ ፫፴፯፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ቆንስታንቲዎስም ፡ ሲነግሥ ፡ እጅግ ፡ መከራ ፡ ደረሰ ፡ በኒቅያ ፡ ወገን ፡፡ ያሪዮስ ፡ ወገንም ፡ የሆሞዩስያኖች ፡ ወገንም ፡ የቆንስታንቲዎስ ፡ ሎሌሎችና ፡ ባለምዋሎች ፡ ነበሩ ፡ እሺ ፡ ያሰኙት ፡ ለንፈቂያቸው ፡፡

አታናስዮስም ፡ ከተሳደደ ፡ በኋላ ፡ አርያኖች ፡ ለስክንድርያ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጲስቆስ ፡ የሚሉትን ፡ ኤጲስቆጶስን ፡ ሰጡ ፡ በስክንድርያ ፡ ያልወደዱት ፡፡

የታላቅ ፡ ቆንስታንቲኖስ ፡ ልጅም ፡ ቆንስታንቲኖስ ፡ በምዕራብ ፡ የገዛ ፡ አታናስዮስን ፡ ወደ ፡ እስክንድርያ ፡ መለሰ ፡ ከዚያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በደስታ ፡ ተቀበለቸው ፡፡ ጸላቶቹ ፡ ግን ፡ ፬፡ ሲኖዶችን ፡ ሰበሰቡ ፡ ባንጾኪያ ፡ ከዚያም ፡ ፳፡ የሃይማኖትን ፡ ምሳሎች ፡ ሰሩ ፡ ክርስቶስ ፡ ሆሞዩስዮስ ፡ ነው ፡ ያሉባቸው ፡ በባሕርዩ ፡ አብን ፡ እንደ ፡ መስል ፡፡ ስለዚህም ፡ ሆሞዩስያኖች ፡ ወይስ ፡ መንፈቀ ፡ አርያኖች ፡ ደባላሉ ፡፡ እርሳቸውም ፡ ቆንስታንቲዮስን ፡ እሺ ፡ አሰኙት ፡ ሌላውን ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወደ ፡ እስክንድርያ ፡ ለመስደድ ፡ ባታናስዮስ ፡ ፈንታ ፡፡ ያም ፡ አንድ ፡ ሰውን ፡ ካሪዮስና ፡ ከሰይጣን ፡ ወገን ፡ ጎርጎርዮስ ፡ የሚሉት ፡ ሰደደ ፡ በግድም ፡ ከዚያ ፡ ሾመው ፡፡ ጎርጎርዮስም ፡ ከወታደር ፡ ጋራ ፡ በስክንድርያ ፡ በገባ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ደም ፡ ፈሰሰ ፡ ላታናስዮስም ፡ በግድ ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡ ሸሸ ፡ ለስክንድርያም ፡ በ

ሚቀርብ ፡ ቦታ ፡ ጥቂት ፡ ተሰወረ ፡ ለኤጲስቆጶሳትም ፡ ጻፈ ፡ በኋላም ፡ ባመት ፡ ፫፻፵፩፡ ወደ ፡ ሮም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወደ ፡ ዩልዩስ ፡ ሸሸ ። በሮምም ፡ ባመት ፡ ፫፻፵፪፡ ሲኖደስ ፡ ተሰበሰበች ፡ ላታናስዮስ ፡ የሆነች ። በኋላም ፡ ፪፡ ቄሣሮች ፡ ቆንስታንቲዎስና ፡ ቆንስታንስ ፡ ሲኖደስን ፡ ሰበሰቡ ፡ በሳርዲካ ፡ ከዚያም ፡ ፸፯፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ከምሥራቅ ፡ ብቻ ፡ ከ፫፱፡ የሚበዙም ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ከምዕራብ ፡ ተሰበሰቡ ። ይህ ፡ ግን ፡ ላንድነት ፡ አልሆነም ፡ ለመለየት ፡ እንጅ ። የምሥራቅ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ አታናስዮስንና ፡ ዩልዩስን ፡ ጸልተው ፡ ተለዩ ፡ ሌላውንም ፡ ሲኖደስ ፡ በፊሊጶጶሊስ ፡ በትራክያ ፡ ሰበሰቡ ።

የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ቆንስታንቲዎስና ፡ ቆንስታንስ ፡ አብረው ፡ አታናስዮስን ፡ አስመለሱ ፡ ወደ ፡ እስክንድርያ ፡ ባመት ፡ ፫፻፵፬፡ የስክንድርያ ፡ ወገን ፡ ጎርጎርዮስን ፡ ከገደሉት ፡ በኋላ ።

የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ የመርቄሎስና ፡ የፎቲኖስ ፡ ስሕተት ፡ ተነሣች ፡ የሰቤልዩስን ፡ ስሕተት ፡ መስላ ። ማርቄሎስም ፡ ያታናስዮስ ፡ ወዳጅ ፡ ሁኖ ፡ በቆንስታንቲኒያ ፡ በተሰበሰበች ፡ ሲኖደስ ፡ ተገዝቶ ፡ ወደ ፡ ሮምም ፡ ሸሸ ፡ ከዚያም ፡ በጎ ፡ ተቀበሉት ፡ ወደ ፡ ሹመቱም ፡ መለሱት ። ያሪዮስ ፡ ወገንም ፡ ሌላውን ፡ ሲኖደስ ፡ በ ሲ ር ሚ ዩ ም ፡ ሰበሰቡ ፡ ባመት ፡ ፫፻፶፩፡ ሁለታቸው ፡ የተሸረፈበት ። ፪፡ ሲኖደችም ፡ ተሰበሰቡ ፡ በአርሌስና ፡ በማይላንድ ። ከዚያም ፡ ያርያኖች ፡ ተንኰል ፡ ባታናስዮስ ፡ ወዳጆች ፡ አሸነፉ ፡ ካያሌ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ባቀር ፡ አታናስዮስን ፡ ከክፉ ፡ መከሰስ ፡ ያነጹት ፡ እርሳቸውም ፡ ኤውሴቢዮስ ፡ ከዌርኬሊ ፡ ሉኪፌርም ፡ ከካግሊያሪ ፡ ሂላርዩስም ፡ ከጵዋቴ ። ቄሣርም ፡ ሊቤርዩስንና ፡ ሆስዩስን ፡ አሳደደ ፡ አንዱን ፡ ወደ ፡ ቤሬአ ፡ አንዱንም ፡ ወደ ፡ ሲርሚዩም ። ባመትም ፡ ፫፻፶፯፡ አታናስዮስ ፡ ሶስተኛ ፡ ጊዜ ፡ ተሳደደ ፡ ከስክንድርያ ፡ ግፈኛ ፡ ሰውም ፡ ጌዎርጊስ ፡ የሚሉት ፡ በስፍራው ፡ ተሾመ ። አታናስዮስም ፡ አሁን ፡ በመናኰስት ፡ መኻከል ፡ በምድር ፡ ተሰወረ ።

አሁንም ፡ የኒቅያ ፡ ጸላቶች ፡ በመኻከላቸው ፡ እርሱ ፡ በ

ርሳቸው ፡ ተጸሉ ፡ ፪፤ ሰዎች ፡ ሲነሡ ፡ ያሪዮስን ፡ ትምርት ፡ በብርቱ ፡ ነገር ፡ ያጸኑት ። እርሳቸውም ፡ አኤትዮስና ፡ ደቀ ፡ መዝሙሩ ፡ ኤውኖሚዮስ ። በርሳቸው ፡ ላይም ፡ የኒሳ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ተከራከረ ፡ ከኒቅያ ፡ ወገን ፡ ያንቂራም ፡ በሲልዮስ ፡ የኒቅያ ፡ ጸላት ። ውርሳኪዎስና ፡ ዋለንስ ፡ ግን ፡ ኤውኖሚዮስንና ፡ አኤትዮስን ፡ ከሌሎች ፡ አርያኖች ፡ ከኒቅያኖችም ፡ ጋራ ፡ ማስታረቅ ፡ ፈለጉ ፡ በሲርሚዩምም ፡ ፫፻፶፯፤ በተሰበሰበች ፡ ሲኖደስ ፡ አዲስ ፡ ምሳሌን ፡ ሰሩ ፡ በር ሱም ፡ የክርክርን ፡ ነገር ፡ ተው ፡ አታናስዮስንም ፡ ወገዙ ፡ ሊቤርዮስንና ፡ ሆስዮስንም ፡ የተገዘቱትን ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ እሺ ፡ አሰኙ ፡ እርሳቸውም ፡ በመከራ ፡ መክንያት ፡ እሺ ፡ አልዋቸው ፡ አታናስዮስን ፡ ወደጀቸውን ፡ ይወግዙት ፡ ዘን ድ ። አሁን ፡ ግን ፡ ፪፤ አኩል ፡ አሪያኖች ፡ መጽሐፉን ፡ ጻፉ ፡ በዚች ፡ ሲኖደስ ፡ ላይ ፡ ስለዚህም ፡ ፪፤ ሌሎች ፡ ሲኖዶች ፡ ተ ሰበሰቡ ፡ ባንድ ፡ አመት ፡ በ፫፻፶፱፤ በሴሌውኪያና ፡ በሪሚ ኒ ። የኤውኖሚዮስ ፡ ወገንም ፡ አሸነፈች ፡ በቈሣር ፡ ቤተ ፡ ሰ ዮች ፡ መክንያት ፡ በቀንስታንቲኒያም ፡ ባመት ፡ ፫፻፷፤ ሌላ ፡ ሲኖደስ ፡ ተሰበሰበች ፡ ይህነን ፡ ያጸናችው ።

አሁንም ፡ እጅግ ፡ ክርክር ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ ጥልም ፡ መናወጽም ፡ እግዚአብሔር ፡ መከ ራን ፡ ሰደደ ፡ በርሱም ፡ አንድነት ፡ ሆነች ። ይህም ፡ በቀንስታ ንቲዎስ ፡ ሞትና ፡ በዩልያኖስ ፡ መንግሥት ፡ ሆነ ። ሁላቸ ውም ፡ ለጊዜ ፡ ክርክራቸውን ፡ ረስተው ፡ ባንድ ፡ ሃይማኖ ት ፡ አብረው ፡ ጸኑ ፡ ባንድ ፡ ጸላት ፡ ላይ ። ይህም ፡ ሆነ ፡ ባ መት ፡ ፫፻፷፪፤ በስክንድርያ ፡ ብዙ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ከአታና ስዮስ ፡ ጋራ ፡ በተሰበሰቡ ፡ ጊዜ ፡ የተሳቱትንም ፡ በተቀበሉ ፡ ጊዜ ፡ በክርስቲያን ፡ ምህረት ።

በዋለንስ ፡ መንግሥትም ፡ የኒቅያ ፡ ወገን ፡ ተሳደደ ። ዋ ለንስም ፡ ከኤውኖሚዎስ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ከኤውደክ ሲዎስ ፡ ተምርዋልና ። ነገር ፡ ግን ፡ ፫፤ ታላቆች ፡ መምህራ ን ፡ የቈሣርያ ፡ በሲልዮስ ፡ ወንድሙም ፡ የኒሳ ፡ ጎርጎርዮ ስ ፡ የዚህም ፡ ወደጅ ፡ የናትያንዝ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ለኒቅያ ፡ ትምህርት ፡ አገለገሉ ፡ በትምህርታቸው ። ዋለንስም ፡ በ

ግድ ፡ ባሲልዮስን ፡ ማሳደድ ፡ በወደደ ፡ ጊዜ ፡ አልቻለውም ፡ አታናስዮስንም ፡ ከስደቱ ፡ አስመለሰ ፡ እርሱም ፡ በረፈት ፡ በክርስቶስ ፡ አንቀላፈ ፡ ባመት ፡ ፫፻፹፫፡፡

በቴዎደስዮስ ፡ ዘመንም ፡ ይህች ፡ ትምርት ፡ በሮም ፡ መንግሥት ፡ ሁሉ ፡ አሸነፈች ፡፡ ጎርጎርዮስም ፡ ከናትያንዝ ፡ እስከዚያ ፡ ድረስ ፡ ባንድ ፡ ሰው ፡ ቤት ፡ የምእምናንን ፡ ጉባኤ ፡ በቍስጥንጥኒያ ፡ ለማምለክ ፡ የሰበሰበ ፡ ያሪያኖች ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ደሞፊሎስ ፡ ጳትሪያርክ ፡ ሁንዋልና ፡ እርሱ ፡ አሁን ፡ በደሞፊሎስ ፡ ስፍራ ፡ ጳትሪያርክ ፡ ሆነ ፡፡ እርሱ ፡ ግን ፡ ይህችን ፡ ሹመቱን ፡ ቶሎ ፡ አሰናበተ ፡፡ አሁንም ፡ በቍስጥንጥኒያ ፡ ሁለተኛ ፡ ኦይኩሜኒቄ ፡ ሲኖደስ ፡ ተሰበሰበች ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ፻፶፡፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ብቻ ፡ ከዚያ ፡ ተሰበሰቡ ፡፡ በዚች ፡ ሲኖደስም ፡ የኒቅያ ፡ ሃይማኖት ፡ ምሳሌ ፡ ጸናች ፡ የክርስቲያንም ፡ ትምህርት ፡ ስለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከአብና ፡ ከልጅ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ የሚሆን ፡ አጸንዋት ፡፡

በዚህ ፡ ዘመንም ፡ የምዕራብ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ጥቂት ፡ ሊለዩ ፡ ጀመሩ ፡ ከምሥራቅ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ በትምርት ፡ ስለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሥርጸት ፡፡ በምሥራቅ ፡ ከአብ ፡ የሚወጣ ፡ ሲሉ ፡ በምዕራብ ፡ በቶሌደ ፡ ሲኖደስ ፡ መጨመርያውን ፡ አደረጉ ፡ ከአብና ፡ ከልጅ ፡ የሚወጣ ፡ ሲሉ ፡፡

ያሪዮስ ፡ ትምርትም ፡ ከጎቶች ፡ ለጊዜ ፡ የተቀበለች ፡ ነበር ፡ በኋላም ፡ ዋንደሎች ፡ ወደ ፡ ከርታጎ ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ አፍሪቃም ፡ የገቡ ፡ አርያኖች ፡ ነበሩ ፡ እጅግ ፡ ምእምናንንም ፡ ገደሉ ፡፡

፲፪፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ አካልና ፡ ባሕሪ ፡ ትምርት ፡ ታሪክ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡፡

ያሪዮስ ፡ ወገን ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ የክርስቶስን ፡ መለኮት ፡ የካዱ ፡ እርሳቸውም ፡ የሰውነቱን ፡ ፍጽምነት ፡ ደግሞ ፡ ካዱ ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ሲያስተምሩ ፡፡ ቃል ፡ የሰውን ፡ ገላ ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ለበሰ ፡ የሰውን ፡ ነፍስ ፡ አደደላም ፡፡ በማርቄሎስ ፡ ትምርት ፡ ግን ፡ የቀደመ ፡ የኅቤልዩ

ስ ፡ በፎቲኖስም ፡ የጳውሎስ ፡ ከሳሞሰጣ ፡ ትምህርት ፡ ተመለሰች ።

ጎርጎርዮስ ፡ ከኒሳ ፡ ጎርጎርዮስም ፡ ከናትያንዝ ፡ እንደሁ ፡ ብለው ፡ አስተማሩ ። ቃል ፡ የሰውን ፡ ሁለንትና ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ አስተዋሀደ ። በዚህ ፡ መዋሀድ ፡ ግን ፡ ሁለት ፡ አልሆኑም ፡ አንድ ፡ እንጅ ፡ መዋሀድም ፡ እንደሁ ፡ ሆነ ፡ እንጨትና ፡ እሳት ፡ አንድ ፡ እንዲሆኑ ፡ በመቃጠል ።

ከዚችም ፡ ትምርት ፡ ጋራ ፡ ያጶሊናሪስ ፡ ትምርት ፡ ተጻለች ፡ እንደሁ ፡ ብሎ ። ቃል ፡ በክርስቶስ ፡ የሰውን ፡ ገላና ፡ ነፍስ ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ተቀበለ ፡ መንፈሱን ፡ አይደለም ፡ እንደሁ ፡ ሲል ። የሰውነት ፡ ሁለንትና ፡ ከመለኮት ፡ ጋራ ፡ ላንድ ፡ አካል ፡ መዋደድ ፡ አይሆንም ፡ ስለዚህ ፡ የሰው ፡ መንፈስ ፡ ከክርስቶስ ፡ ቀርቶ ፡ ቃልም ፡ በርሱ ፡ ፈንታ ፡ ሆነ ። ነገር ፡ ግን ፡ ኦርቶደክሳውያን ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ተምዋገቱ ፡ አታናስዮስም ፡ እንደሁ ፡ አለው ። እንዴት ፡ ሆነ ፡ ክርስቶስ ፡ ምሳልያችን ፡ ጠባዩ ፡ እንደ ፡ ጠባያችን ፡ ካልሆነ ። እርሱም ፡ የሰውን ፡ ጠባይዕ ፡ ሁለንትና ፡ ማደን ፡ ባልቻለው ፡ ሁለንትናውን ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ካላስተዋደደ ።

ያጶሊናሪስም ፡ ስሕተት ፡ ተወገዘች ፡ ባመት ፡ ፫፻፹፪፡ ክርክር ፡ ሳያልቅ ። ክርክርም ፡ በስክንድርያ ፡ መምህራንና ፡ ባንጾኪያ ፡ መምህራን ፡ መኻከል ፡ ነበረ ።

ቴዎደርስ ፡ ከሞጵስዌስቲያ ፡ እንደሁ ፡ አለ ። ክርስቶስ ፡ ሰውነታችንን ፡ በጣም ፡ ተቀበለ ፡ ከኃጢአት ፡ በቀር ፡ እንጅ ። ሰይጣንም ፡ ሲፈትነው ፡ እርሱ ፡ ሰይጣንን ፡ በመለኮቱ ፡ አላሸነፈውም ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ በፈቃዱ ፡ እንጅ ፡ እንደ ፡ ሰው ። መፈተንም ፡ እንደኛ ፡ ደረሰበት ፡ እኛም ፡ እንደርሱ ፡ እናሸንፍ ፡ ዘንድ ። ቃልም ፡ ከሰውነቱ ፡ ጋራ ፡ የሰውን ፡ ፈቃድ ፡ ደግሞ ፡ ተቀበለ ። ያለዚህ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደኛ ፡ ባልተጋደለ ። የክርስቶስም ፡ የሰውነቱ ፡ ዋጋ ፡ ነበረ ፡ ለመጋደሉ ፡ ለማሸነፋም ፡ በኃጢአትና ፡ በሰይጣን ፡ ላይ ። እንደሁም ፡ ሆነ ፡ ክርስቶስ ፡ እንዲችል ፡ ከትንሣኤው ፡ በኋላ ፡ መንፈሱን ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፡ ለሚያምኑበት ፡ ሁሉ ።

የስክንድርያ ፡ መምህራን ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ላይ ፡ ተከራከሩ ። እርሳቸውም ፡ የክርስቶስ ፡ የ፪፤ ጠባያቱን ፡ መዋደድ ፡ ድንቅና ፡ ታምራት ፡ ሁኖ ፡ አስተማሩት ። ስለዚህም ፡ በቋንቋቸው ፡ የሚያስደንቀወን ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ያልተገኘ ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ። ማርያም ፡ ያምላክ ፡ እናት ፡ ናት ። ማርያምም ፡ ቃልን ፡ ወለደች ፡ በሥጋ ፡ መጠን ። እግዚአብሔር ፡ ታመመ ። እግዚአብሔርም ፡ሞተ ። ሌላ ፡ ነገርም ፡ ይህነን ፡ የሚመስል ። በመጀመርያም ፡ በዚህ ፡ መዋደድ ፡ እርሳቸው ፡ ደግሞ ፡ ለዩ ፡ የሰውን ፡ ባሕሪ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ባሕሪ ፡ ደሮ ፡ ክርስቶስ ፡ እንዴት ፡ እንደ ፡ ተዋደደ ፡ የሰው ፡ አእምሮ ፡ ሁሉ ፡ ከቶ ፡ አያገኝም ።

አሁንም ፡ እለዚህ ፡ ፪፤ ወገኖች ፡ የስክንድርያና ፡ ያንጾኪያ ፡ ወገን ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ስራ ፡ እርሱም ፡ ፍቅር ፡ የሚሆን ፡ ከጠበቁ ፡ መለየት ፡ ባልሆነ ። ነገር ፡ ግን ፡ የራሳቸውን ፡ ነገር ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ነገር ፡ ጋራ ፡ ደብልቀው ፡ እስከ ፡ ዘመናችን ፡ ድረስ ፡ የኖረ ፡ መለየት ፡ ተነሣች ።

ይህችም ፡ መለየት ፡ ጀመረች ፡ በንስቶርዮስ ፡ ክርክር ። ንስቶርዮስም ፡ ሞነክሴ ፡ የነበረ ፡ ባንጾኪያ ፡ ቀሰሰ ፡ በኋላም ፡ ባመት ፡ ፬፻፳፰፤ የቆንስታንቲኒያ ፡ ጳትርያርክ ፡ ሆነ ። ይህችም ፡ ታላቅ ፡ ሹመት ፡ ነበረች ፡ እጅግም ፡ ጥበብና ፡ ደውሃት ፡ ትሕትናም ፡ ፈለገች ፡ ለንስቶርዮስ ፡ ያልነበረች ። በዚያ ፡ ዘመንም ፡ ማርያምን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ እናት ፡ ደሉ ፡ ዘንድ ፡ ልማድ ፡ ሆነ ። ንስቶርዮስም ፡ በመጀመርያ ፡ ተጠነቀቀ ፡ ይህነን ፡ ማለት ፡ በመከልከል ፡ እንደያሰንክል ። ቄሱ ፡ አናስታስዮስ ፡ እስኪጀምር ፡ ድረስ ፡ ደል ፡ ዘንድ ። ሰው ፡ ሁሉ ፡ ማርያምን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ እናት ፡ አይላት ፡ እርስዋ ፡ ሰው ፡ ነበረችና ፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ከሰው ፡ መወለድ ፡ አይችልም ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ አንድ ፡ በቆንስታንቲኒያ ፡ የሰበከ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ በስብከቱ ፡ እንዲህ ፡ አለ ። ውጉዝ ፡ ነው ፡ ማርያምን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ እናት ፡ የሚላት ። ከዚያ ፡ ጀምሮም ፡ ታላቅ ፡ ክርክር ፡ ጀመረ ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ መካከል ፡ ስ

ለ ፡ ማርያምና ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ጠባይዕ ። አሁንም ፡ ንስ
ቶርዮስ ፡ ደግሞ ፡ በዚህ ፡ እጅግ ፡ ዘመን ፡ የኖረ ፡ ቤተ ፡ ክር
ስቲያንም ፡ እጅግ ፡ የተጐዳችበት ፡ ክርክር ፡ ገባ ። ባመት
ም ፡ ፬፻፳፱፤ ቅርክሎስ ፡ ተንሣበት ፡ የሰውም ፡ ጸላትነት ፡
በንስቶርዮስ ፡ ላይ ፡ አስነሣበት ። አያሌንም ፡ ቀሳውስት ፡
በንስቶርዮስ ፡ ላይ ፡ የሰበኩ ፡ መናፈቃን ፡ ሁነው ፡ ንስቶር
ዮስ ፡ በሲኖደስ ፡ ገዘታቸው ። አሁን ፡ ግን ፡ ቄርሎስ ፡ የስክ
ንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ተነሣበት ፡ እርሱም ፡ ያለም ፡ መን
ፈስ ፡ የገዛበት ፡ በቆንስታንቲኒያም ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ የተቀና ፡
የርሱ ፡ እኩል ፡ ስለ ፡ ተቈጠረ ። እርሱም ፡ በመጀመርያ ፡
፬፤ መጻሕፍትን ፡ ጻፈ ፡ ስለዚህ ፡ ክርክር ፡ በንስቶርዮስ ፡
ላይ ፡ በርሱም ፡ ንስቶርዮስን ፡ አስቈጣ ፡ የጸላትነቱንም ፡
ነገር ፡ በፍቅር ፡ ምሳሌ ፡ አለበሰው ። ንስቶስርዮስን ፡ የክ
ርስቶስን ፡ መለኮት ፡ እንደ ፡ ካደ ፡ አደረገው ፡ በኋላ ፡ እ
ሌህ ፡ ፬፤ ሊቃነ ፡ ጳጳሳት ፡ የታረቁ ፡ መሰሉ ፡ ነገር ፡ ግን ፡
በቄርሎስ ፡ ቀሳውስት ፡ ፅቡ ፡ ተመልሶ ፡ በዛ ። ቄርሎስም ፡
የንስቶርዮስን ፡ ትምርት ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ጸላ ፡ መሰለ ፡
ደሮ ፡ የጽሉ ፡ መክንያት ፡ ቅናትና ፡ ትዕቢት ፡ ነበረ ፡ ንስቶርዮ
ስን ፡ ሊሸር ፡ ብልዋል ። ስለዚህም ፡ በስውር ፡ እጅግ ፡ ትንኩ
ል ፡ ሰራ ፡ ለንጉሥ ፡ ቤተ ፡ ሰቦች ፡ ሲጽፍ ፡ ለባለምዋሎቹም ፡
ሁሉ ፡ መስጠት ፡ ሲሰድ ፡ ከቀሳውስትም ፡ ከታላቆች ፡ መ
ኳንንትም ፡ ጋሬ ፡ ወደጅነት ፡ አደረገ ፡ በንስቶርዮስ ፡ ላይ ።
ቄርሎስም ፡ የሮም ፡ ኤጲስቆጶስን ፡ የኬሌስቲኑስን ፡ ረዴ
ት ፡ ለመነ ፡ ንስቶርዮስን ፡ ለመሻር ። በሮም ፡ ኤጲስቆጶሳ
ትም ፡ ዘንድ ፡ እርሳቸውም ፡ ክርስቶስን ፡ በትሕትና ፡ ያል
ተከተሉ ፡ ልማድ ፡ ሆነ ፡ እንደዩህ ፡ በተለመኑ ፡ ጊዜ ፡ እንደ
ሰሙ ፡ አሺም ፡ በማለታቸው ፡ ፈራጆች ፡ እንደሆኑ ፡ በቤ
ተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ ላይ ። ንስቶርዮስም ፡ እርሱ ፡ ደግ
ሞ ፡ ለሮም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ጻፈ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ወንድም ፡ እ
ንደ ጽፍ ፡ ለወንድሙ ፡ ስለዚህም ፡ ኬሌስቲኖስ ፡ ቄርሎስ
ን ፡ ሰማ ፡ ንስቶርዮስንም ፡ ጸላ ። በሮምም ፡ በተሰበሰበ
ች ፡ ሲኖደስ ፡ ንስቶርዮስ ፡ የገዘታቸውን ፡ ቀሳውስት ፡ ኬሌ
ስቲኑስ ፡ ፈታቸው ። ንስቶርዮስንም ፡ ተቃየመ ፡ በ፲፤ ቀን ፡ ስ

ሕተቱን ፡ በደክድ ፡ እንደ ሸረው ፡፡ በዚህ ፡ ነገርም ፡ ቄርሎስ ፡ እጅግ ፡ ደስ ፡ ብሎ ፡ ላንጾኪያ ፡ ጳትርያርክ ፡ ዮሐንስ ፡ ጳፈ ፡ ሲያስፈራው ፡ እርሱ ፡ ካብያተ ፡ ክርስቲያናቱ ፡ ጋራ ፡ ከምዕራብ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ እንደ ይለዩ ፡ ብሎ ፡፡ ያንጾኪያም ፡ ጳትርያርክ ፡ የዚያ ፡ አገርም ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ የኔስቶርዮስ ፡ ወደጆች ፡ ነበሩ ፡፡ ዮሐንስም ፡ ለመነው ፡ ዕርቅን ፡ እንዲያደርግ ፡ ስለ ፡ አንዲት ፡ ቃልም ፡ ስለ ፡ ማርያም ፡ እርስዋ ፡ የእግዚአብሔር ፡ እናት ፡ እንድትሆን ፡ ክርክርን ፡ ሊተው ፡ ለመታርቅም ፡ ሊክድ ፡፡ ነስቶርዮስም ፡ መለሰለት ፡ ሲል ፡ ለዚች ፡ አንዲት ፡ ቃል ፡ እሺ ፡ እንዲል ፡ ቄርሎስ ፡ ግን ፡ ትዕቢቱን ፡ እንደይተው ፡፡ እርሱም ፡ ፈለገ ፡ ደህነን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለኦይኩሜኒቄ ፡ ሲኖደስ ፡ እንዲያደርሱ ፡ ከዚያ ፡ ይመረመር ፡ ዘንድ ፡፡ ደሮ ፡ ቄርሎስ ፡ መቆየት ፡ አልቻለውም ፡፡ ባመት ፡ ፬፻፤ መልእክትን ፡ ጻፈለት ፡ ፲፪፤ ነገር ፡ በገለጸለት ፡ ይክደው ፡ ዘንድ ፡፡ ይህም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ባንጾኪያ ፡ ትምርት ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ነበረ ፡ ቴዎደሮስ ፡ እንደስተማረው ፡፡ አሁንም ፡ ይህ ፡ ክርክር ፡ ሁሉ ፡ በኔስቶርዮስ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ አልነበረም ፡ ባንጾኪያ ፡ ትምርት ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ እንጂ ፡፡ ያንጾኪያም ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ዮሐንስ ፡ ቴዎደሬቶስን ፡ በለዚህ ፡ ፲፪፤ የቄርሎስ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ሊመጉት ፡ ለመነው ፡ ቴዎደሬቶስም ፡ ተማጉተ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ክርክራቸው ፡ በዛበት ፡፡

ነስቶርዮስ ፡ በቄርሎስ ፡ ፲፪፤ አናቴማቲስሞች ፡ በተባሉ ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ሌሎች ፡ ፲፪፤ አናቴማቲስሞችን ፡ አደረገ ፡፡ ቄሣርም ፡ የቄርሎስንና ፡ የኬሌስቲኑስን ፡ ማድረግ ፡ አልወደደም ፡ እርሱ ፡ አደትዋልና ፡ ቄርሎስ ፡ ሌላውን ፡ ነገር ፡ እንደይሻ ፡ የነስቶርዮስን ፡ ጥፋት ፡ እንጂ ፡፡ ስለዚህም ፡ ነስቶርዮስ ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ ፈለገው ፡ ሲኖደስን ፡ ሰበሰበ ፡ በኤፌሶን ፡ ባመት ፡ ፬፻፴፤ ቄርሎስንም ፡ እጅግ ፡ ተቈጣ ፡ በቀደም ፡ ፈልግዋልና ፡ በቄሣርና ፡ በምሽቱ ፡ መካከል ፡ ፅብ ፡ ያስነሣ ፡ ዘንድ ፡፡

ቄርሎስና ፡ ኔስቶርዮስም ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ኤፌሶን ፡ ደረሱ ፡ የሮም ፡ መልእክተኞችና ፡ ያንጾኪያ ፡ ኤጲስቆጶሳ

ት ፡ ሳይመጡ ። ቄርሎስም ፡ ከምስር ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ እርሳ
ቸውም ፡ ሁላቸው ፡ እንደርሱ ፡ ካሉ ፡ ጋራ ፡ ብቻውን ፡ ነበረ ፡
ስለዚህም ፡ አልዘገየም ፡ ሲኖደስን ፡ በመሰብሰብ ። ነስቶር
ዮስ ፡ ግን ፡ እምቢ ፡ አለ ፡ ለመምጣት ፡ ያንጾኪያ ፡ ኤጲስቆ
ጶሳት ፡ ሰይመጡ ። አሁንም ፡ የቄርሎስ ፡ ሲኖደስ ፡ እርሱ ፡
ካሳሽና ፡ ፈራጅ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ የነበረባት ፡ ነስቶርዮስን ፡ ወገ
ዘች ። አያሌ ፡ ቀንም ፡ እርሳቸው ፡ ከጀመሩ ፡ በኋላ ፡ ያንጾኪ
ያ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ መጡ ፡ ሌላውንም ፡ ሲኖደስ ፡ አደረጉ ፡
ቄርሎስንና ፡ ሜምኖንንም ፡ የኤፌሶንን ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወገ
ዙ ፡ መናፍቃን ፡ ሁነው ። አሁንም ፡ ወሬ ፡ ወደ ፡ ቄሣር ፡ ደ
ረሰ ፡ እርሱም ፡ ኤጲስቆጶሳትን ፡ ሁሉ ፡ አዘዛቸው ፡ ባን
ድ ፡ ሲኖደስ ፡ ሊሰበሰቡ ፡ በረፍትም ፡ ሊመረምሩ ። ደሮ ፡
ቄርሎስ ፡ በትንኰሉ ፡ ይህን ፡ ከለከለ ፡ ወንደንድም ፡ በቍን
ስታንቲንያ ፡ እጅግ ፡ ወደ ፡ ከበረ ፡ ሞነክሴ ፡ በስውር ፡ ሰደ
ደ ፡ ያም ፡ ከሌሎች ፡ ከመናኵስቱ ፡ ጋራ ፡ ቄሣርን ፡ አስፈ
ራ ፡ እሺ ፡ አሰኘውም ፡ ቄርሎስን ፡ ያዝ ፡ ዘንድ ፡ ከኤጲ
ስቆጶሳቱ ፡ መልእክተኞች ፡ እንዲሰድ ፡ ወደ ፡ ቄሣር ። ይ
ህም ፡ ሆነ ። እለዚያም ፡ በትንኰላቸው ፡ የነስቶርዮስን ፡
ጸላቶች ፡ እጅግ ፡ አበዙ ። ከብዙ ፡ ትንኰልም ፡ ከብዙ ፡
ፅብም ፡ በኋላ ፡ የቄሣር ፡ ሹም ፡ የ፪ ወገን ፡ ኤጲስቆጶሳ
ት ፡ ባንድ ፡ ሰበሰበ ። ነስቶርዮስና ፡ ቄርሎስም ፡ ስለ ፡ ፀባ
ቸው ፡ በግድ ፡ ካወጥዋቸው ፡ በኋላ ፡ የሃይማኖትን ፡ ትምር
ት ፡ ምሳሌ ፡ አደረጉ ፡ የኤፌሶን ፡ ስምቦሎን ፡ የተባ
ለች ። ነስቶርዮስም ፡ ወደ ፡ ገዳሙ ፡ ተመለሰ ፡ አስቀድሞ ፡
ወደ ፡ ነበረበት ። ቄርሎስ ፡ ግን ፡ ከሜምኖን ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡
ሹመታቸው ፡ ተመለሱ ። ስለዚህም ፡ ዕርቅ ፡ አልሆነም ።
ቄርሎስም ፡ የቄሣርን ፡ ሰዎች ፡ በብሩ ፡ ገዛቸው ። ባመት ፡
፬፻፴፪ እሌህ ፡ ፪ ወገን ፡ ለማየት ፡ ታረቁ ፡ ባውነት ፡ አይደ
ለም ። ቄርሎስም ፡ እንዲህ ፡ አለ ። አንድ ፡ ክርስቶስ ፡ ከ፪
ጠባያት ፡ እንደሆነ ፡ በ፪ አይደለም ። አሁንም ፡ ነስቶርዮ
ስ ፡ ተወገዘ ፡ ወዳጆቹም ፡ ተውት ፡ ከ፫ በቀር ፡ እርሳቸው
ም ፡ የሞጵስዌስቲያ ፡ ሜሌቲዮስ ፡ የሂራጶሊስም ፡ እስክ
ንድር ፡ የጠርሲስም ፡ ሀላዲዮስ ፡ ሹመታቸው ፡ ስለርሱ ፡

የተሻረች ። ቄርሎስና ፡ ኬሌስቲኖስ ፡ ግን ፡ ገና፡ ዕረፍት ፡ አ
ልነበረላቸውም ፡ በጽላትነታቸው ፡ በንስቶርዮስ ፡ ላይ ፡ ንስ
ቶርዮስ ፡ በገደም ፡ ሲሆን ። ስለዚህም ፡ ቴዎደሮስን ፡ ለ
መኑ ፡ ከሰው ፡ ሁሉ ፡ መኻከል ፡ ያውጣው ፡ ዘንድ ። ቴዎ
ደስዮስም ፡ ባመት ፡ ፬፻፳፰፡ ወደ ፡ ሊብያ ፡ በረኻ ፡ አሳደደ
ው ፡ በመከራም ፡ሞተ ። ደር ፡ ይህ ፡ እንኳ ፡ ለቄርሎስ ፡
አልበቃም ፡ እርሱ ፡ የቴዎደሮስንና ፡ የዲዮደሮስን ፡ ትም
ርት ፡ ሁሉ ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ ፈለገ ። ስለዚህ ፡ ደግሞ ፡ ክር
ክርን ፡ ከጀመረ ፡ በኋላ ፡ ሞተ ፡ ባመት ፡ ፬፻፵፬።

ባቄርሎስም ፡ ፈንታ ፡ ዲዮስቆሮስ ፡ ተከተለው ። የዚ
ያን ፡ ጊዜም ፡ በቍስጠንጢኒያ ፡ በነበረ ፡ ሞናኰስት ፡ መ
ኻከል ፡ አንድ ፡ መምህር ፡ ነበረ ፡ ኤውቲኬስ ፡ የተባለ ፡
የቄርሎስ ፡ ወገን ፡ እጅግ ፡ ክርክር ፡ ያደረገ ፡ ባንጾኪያ ፡ ወ
ገን ፡ ላይ ። ቴዎደሬቶስም ፡ በርሱ ፡ ላይ ፡ መጽሐፏን ፡ ጻ
ፈ ፡ ዲዮስቆሮስም ፡ ስለዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ ከሰሰው ፡ በደ
ምናስ ፡ ባንጾኪያ ፡ ጳትርያርኽ ፡ ዘንድ ። በቴዎደሬቶስ
ም ፡ ጥልን ፡ አደረገ ። ኤውቲኬስ ፡ ግን ፡ ባመት ፡ ፬፻፵፰፡ ባ
ቍስጠንጢኒያ ፡ በተሰበሰበች ፡ ሲኖደስ ፡ ተፈትኖ ፡ መናፈቅ
ም ፡ ሁኖ ፡ ሲገኝ ፡ ተወገዘ ። በክርስቶስ ፡ ፩፡ ጠባይዕ ፡ ብ
ቻ ፡ እንደሌ ፡ የርሱም ፡ የገላው ፡ ባሕሪ ፡ እንደ ፡ ሌላ ፡ ሰው ፡
ገላ ፡ እንዳይደለ ፡ አስተምርዋልና ። ነገር ፡ ግን ፡ የቄሣር ፡ ባ
ለምዋሎች ፡ ሁሉ ፡ የኤውቲኬስና ፡ የዲዮስቆሮስ ፡ ወዳ
ጆች ፡ ነበሩ ፡ እጅግ ፡ መስጠት ፡ ከርሳቸው ፡ ዘንድ ፡ ተቀብ
ለዋልና ። ቄሣርም ፡ ደግሞ ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነበ
ረ ። እርሱም ፡ አዘዘ ፡ አዲስ ፡ ኦይኩሜኒኬ ፡ ሲኖደስ ፡ በ
ኤፌሶን ፡ ባመት ፡ ፬፻፵፱፡ ትሰበሰብ ፡ ዘንድ ፡ ከዲዮስቆ
ሮስ ፡ በታች ፡ የርሱም ፡ ወገን ፡ ብቻ ፡ ይመጡ ፡ ዘንድ ፡ ሌ
ሎችም ፡ የመጡ ፡ እንደሆን ፡ ምክርና ፡ ፍርድ ፡ እንደሌላ
ቸው ፡ ሊሰሙ ፡ እንጂ ፡ ብሎ ። እንዲህም ፡ ያች ፡ ሲኖደስ፡
በኤፌሶን ፡ ተሰበሰበች ፡ በታሪክ ፡ የወንበዴች፡ ሲኖደስ፡
የተባለች፡ በዲዮስቆሮስ፡ በኤጲስቆጶሳቱም፡ በወታደሮች
ም፡ ከዚያ ፡ ስለ ፡ ተሰራ ፡ ግፍ ። በርስዋም ፡ ዲዮስቆሮስ ፡
ግድን ፡ ሁሉን ፡ አደረገ ፡ ኤጲስቆጶሳትን ፡ እሺ ፡ ያሰኝ ፡ ዘ

ንድ ፡ ፍላዊያኖስም ፡ የቁንስጣንቲኒያ ፡ ጳትርያርኽ ፡ ደም ኖስም ፡ ያንጾኪያ ፡ ጳትርያርኽ ፡ ቴዎዶሬቶስም ፡ ሌሎች ም ፡ ብዙ ፡ ደህና ፡ መምህራን ፡ የነበሩ ፡ ተወገዙ ፡ ከሹመ ታቸውም ፡ ተሳደዱ ፡፡

ዲዮስቆሮስም ፡ እንዲህ ፡ በቊሣር ፡ ኃይልና ፡ በግፍ ፡ ሲ ገዛ ፡ የምሥራቅ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ ኤ ጲስቆጶስ ፡ ወደ ፡ ታላቅ ፡ ሌዎን ፡ ሰደዱ ፡፡ እርሱም ፡ ታላ ቅ ፡ የተባለ ፡ ስለ ፡ መንፈሱ ፡ ኃይል ፡፡ ለመኑትም ፡ ደህን ታቸውን ፡ ይጠብቅ ፡ ዘንድ ፡፡

የዚያን ፡ ጊዜም ፡ የምሥራቅ ፡ መንግሥት ፡ ተለወጠች ፡፡ ሁለተኛ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ሞተ ፡ ባመት ፡ ፬፻፶ ፡፡ ጴልኬርያም ፡ እቱ ፡ ተከተለቸው ፡ በመንግሥቱ ፡ ማርቅያኖስን ፡ ተጋብ ታ ፡፡ እርስዋም ፡ የፍላዊያኖስ ፡ ወዳጅ ፡ ነበረች ፡ የዲዮስ ቆሮስም ፡ ሥልጣን ፡ በቁንስጣንቲኒያ ፡ አለቀች ፡፡

አሁንም ፡ ሌላ ፡ ኦይኩሜኒኬ ፡ ሲኖዶስ ፡ በኒቅያ ፡ ተሰበ ሰበች ፡ ባመት ፡ ፬፻፶፩ ፡፡ ከዚያም ፡ ፮፻፴ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ተሰ በሰቡ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ምክራቸውን ፡ በጀመሩ ፡ ጊዜ ፡ ሁከ ት ፡ ሆነ ፡ በመካከላቸው ፡፡ ስለዚህም ፡ ሲኖዶስ ፡ ከዚያ ፡ ተነሥታ ፡ ወደ ፡ ኬልቄዶን ፡ ተነቀለች ፡፡ ከዚያም ፡ የዲዮስ ቆሮስ ፡ ወገን ፡ ሁሉ ፡ የንጉሥን ፡ ኃይል ፡ ፈርተዋልና ፡ አዘ ኑ ፡ ሌዎንም ፡ የሰጣቸውን ፡ ምሳሌ ፡ ተቀበሉ ፡ እንዲህ ፡ የ ሚል ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡፡

> አንድ ፡ ክርስቶስ ፡ እርሱም ፡ ልጅ ፡ ጌታም ፡ አንደኛ ም ፡ የተወለደ ፡ እንደ ፡ ታወቀ ፡ በ፪ ጠባያት ፡ የተ ዋደዱ ፡ ያለ ፡ መደበለቅ ፡ ያለ ፡ መለወጥም ፡ ያለ ፡ መሻርም ፡ ያለ ፡ መለየትም ፡ አንድ ፡ ክርስቶስ ፡ ሁ ኖ ፡ በሁለት ፡ ጠባያት ፡፡

ዲዮስቆሮስም ፡ ስለ ፡ ትምርቱና ፡ ስለ ፡ አካሔዱ ፡ ተከ ሰሰ ፡፡ በመዋረድ ፡ ፈንታ ፡ ግን ፡ እርሱ ፡ ሌዎንን ፡ ወገዘ ፡ ስ ለዚህም ፡ ተሻረ ፡፡

በዚች ፡ ሲኖዶስ ፡ ግን ፡ ዕርቅ ፡ አልሆነም ፡ በቤተ ፡ ክርስ ቲያን ፡፡ በየሩሳሌምም ፡ አንድ ፡ ሞነክሴ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ የ

ሚሉት ፡ የዲዮስቆሮስ ፡ ወገን ፡ የነበረ ፡ የየሩሳሌምን ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ዩበናሊስ ፡ የሚሉት ፡ ሻረው ፡፡ ባለቤቱም ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ ሁኖ ፡ በኬልቄዶን ፡ ወገን ፡ ተቈጣ ፡ በሳትና ፡ በሰይፍ ፡፡ በምስርም ፡ ታላቅ ፡ ሁከት ፡ ሆነ ፡፡ ከዚያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በ፪ ተለየች ፡ ፩ ወይስ ፡ ፪ ጠባይት ፡ ስለ ፡ ማለታቸው ፡ ባንድ ፡ ክርስቶስ ፡፡ በኋላም ፡ ጴጥሮስ ፡ ሞንጎስ ፡ ባንድ ፡ ጣባይዕ ፡ ትምህርት ፡ ያስተማረ ፡ የወገኑም ፡ አለቃ ፡ በምስር ፡ ቄሣር ፡ ዜኖንን ፡ ለማስታረቅ ፡ መከረው ፡ ዜኖንም ፡ እንደ ፡ ምክሩ ፡ መልእክትን ፡ ጻፈ ፡ በምስር ፡ ወደሉት ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡፡ ይህችም ፡ መልእክት ፡ መዋደጃ ፡ ተባለች ፡ በ፪ ወገን ፡ አንድነትን ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡ ብለው ፡፡ ደሮ ፡ አንድነት ፡ አልሆነም ፡ ጥል ፡ በዛበት ፡ እንጂ ፡፡

ከ፩ ጠባይዕ ፡ ወገን ፡ ፪ ሰዎች ፡ ተነሡ ፡ ክሴኖያስና ፡ ሴቤረስ ፡ ትምርታቸውን ፡ እጅግ ፡ የዘረጉ ፡፡ ባናስታስዮስ ፡ ዘመንም ፡ ትምርታቸው ፡ አሸነፈች ፡ በዩስቲኖስና ፡ በዩስቲኒያኑስ ፡ መንግሥት ፡ ግን ፡ የኬልቄዶን ፡ ትምህርት ፡፡ በዩስቲኒያኑስ ፡ መንግሥት ፡ ግን ፡ በመጨርሻዋ ፡ እጅግ ፡ ጥፋት ፡ ሆነ ፡ በንጉሡ ፡ ስንፍና ፡ እርሱ ፡ ባለማወቁ ፡ በትዕቢቱም ፡ የደከመ ፡ የመንግሥቱን ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ሁሉ ፡ ያገደቸው ፡ ዘንድ ፡ ፫ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አንድነት ፡ የሞቱትን ፡ መምህራን ፡ እርሳቸውም ፡ ቴዎደሮስ ፡ ቴዎደሬቶስም ፡ ኢባስም ፡ ከሞታቸው ፡ በኋላ ፡ ለመውገዝ ፡፡

የንስቶርዮስ ፡ ወገንም ፡ ከቀረች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከተወገዘች ፡ በኋላ ፡ በፋርስ ፡ መንግሥት ፡ ተዘረጋች ፡፡

ያንድ ፡ ጠባይዕ ፡ ወገንም ፡ በምስር ፡ ለራሳቸው ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስን ፡ መረጹላቸው ፡ ትምርታቸውም ፡ ወደ ፡ ኑቢያ ፡ ወደ ፡ ሃበሻም ፡ ደረሰች ፡ ወደ ፡ አርመን ፡ ምድርም ፡፡ ከርሳቸውም ፡ አንድ ፡ ሞነክሴ ፡ በሶርያ ፡ ተነሣ ፡ ያዕቆብ ፡ የሚሉት ፡፡ አያሌ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ከወገናቸው ፡ ቀደሱት ፡ ጳጳሳቸው ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡፡ እርሱም ፡ በጅግ ፡ ድካምና ፡ መከራ ፡ ዞረ ፡ በስፍራም ፡ ሁሉ ፡ ቀሳውስትና ፡ ኤጲስቆጶሳ

ት ፡ ቀደሰላቸው ፡ አለቃውንም ፡ ሰጠላቸው ፡ እርሱም ፡ ያ
ንጾኪያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ።

፫፫፤ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ትምርት ፡ ስለ ፡ ሰው ፡ በዚህ ፡ ዘመን ።

ይህች ፡ ትምህርት ፡ እጅግ ፡ ተመረመረች ፡ በምዕራብ ፡ አውጉስቲኑስና ፡ ጰላግዩስ ፡ ሲከራከሩበት ። ጰላግዩ ስም ፡ሞነክሴ ፡ ነበረ ፡ በንግለጣር ፡ የኃጢአትን ፡ ብርታት ፡ የሰውንም ፡ ጥፋት ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ የሕጉን ፡ መን ፈስ ፡ የክርስቶስንም ፡ ጸጋ ፡ ያላወቀ ። አውጉስቲኑስ ፡ ግ ን ፡ ከልቡ ፡ ይህነን ፡ ተማረ ፡ ከሕይወቱም ።

ጰላግዩስ ፡ በሮም ፡ ሁኖ ፡ አንድ ፡ ሰውን ፡ አየ ፡ እርሱ ም ፡ ተናጋሪ ፡ ኬሌስቲዩስ ፡ የሚሉት ። ያም ፡ ከኃጢአ ቱ ፡ ተመልሶ ፡ ሞነክሴ ፡ ሆነ ፡ ጰላግዩስንም ፡ ተከተለ ። እ ርሱም ፡ የጰላግዩስን ፡ ትምርት ፡ ሁሉን ፡ ተቀበለ ፡ ተናጋሪ ም ፡ ሁንዋልና ፡ ስለርሱ ፡ ተከራከረ ።

ጰላግዩስና ፡ ኬሌስቲዩስም ፡ ባመት ፡ ፬፻፲፩፤ አብረው ፡ ወ ደ ፡ ከርታጎ ፡ ሔዱ ። ጰላግዩስም ፡ ከዚያ ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ ከ ተቀመጠ ፡ በኋላ ፡ ተነሥቶ ፡ ሔደ ፡ ኬሌስቲዩስ ፡ ግን ፡ ኖረ ። እርሱም ፡ ከዚያ ፡ በመጋደሉ ፡ በነፍሱም ፡ ቅሎት ፡ ወዳጆ ችን ፡ አገኘ ፡ ስለዚህ ፡ ይቀሰስ ፡ ዘንድ ፡ ፈለገ ፡ በዚያችም ፡ ከተማ ፡ ቄስ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ። ነገር ፡ ግን ፡ ባመት ፡ ፬፻፲፪፤ ሲኖ ደስ ፡ ተሰብስባ ፡ በከርታጎ ፡ ጳውሊኑስ ፡ የሚሉት ፡ ዲያቆን ፡ አጣለው ፡ ስለ ፡ አስተማረ ፡ እንደዪህ ፡ ሲል ። ያደም ፡ ኃጢ አት ፡ የሰውን ፡ ወገን ፡ ሁሉ ፡ አልጐዳውም ፡ ራሱን ፡ ብቻ ፡ እንጂ ፡ ሕፃናትም ፡ ሁሉ ፡ ሲወለዱ ፡ በንጽሕና ፡ ይወለዳ ሉ ፡ አደም ፡ እንደ ፡ ተፈጠረ ። በዚህ ፡ ነገርም ፡ በመረመሩ ት ፡ ጊዜ ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አንድነት ፡ አወጡት ።

ጰላግዩስም ፡ ባመት ፡ ፬፻፲፭፤ ወደ ፡ የሩሳሌም ፡ ሔደ ፡ ሄ ሮኒሙስንም ፡ አገኝቶ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ክርክርን ፡ጀመረ ። በሄሮኒሙስ ፡ ዘንድም ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ያውጉስቲኑስ ፡ ደ ቀ ፡ መዝሙር ፡ ከሂስጳንያ ፡ ነበረ ፡ ስሙን ፡ ኦሮስዩስ ፡ የ

ሚሉት ፡፡ ሄሮኒሙስም ፡ በፊት ፡ መጽሐፍን ፡ ጻፈ ፡ በጰላ
ግዩስ ፡ ላይ ፡፡ ኦሮስዩስም ፡ በየሩሳሌም ፡ በተሰበሰበች ፡ ሲ
ኖደስ ፡ ጰላግዩስን ፡ ከሰሰ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ከዚያ ፡ የተሰበሰ
ቡ ፡ የጰላግዩስ ፡ ወዳጆች ፡ ነበሩ ፡ ስሕተቱንም ፡ ማየት ፡ አ
ልቻላቸውም ፡፡ ስሕተቱም ፡ ይህ ፡ ነበረች ፡፡ ሰው ፡ ቢወድ ፡
ይችላል ፡ ያለ ፡ ኀጢአት ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔር
ንም ፡ ትእዛዝ ፡ በጣም ፡ ይፈጽም ፡ ዘንድ ፡ ብሎ ፡፡ ይህም ፡
ነገር ፡ ስሕተት ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ባላዩ ፡ ጊዜ ፡ የሮም ፡ ኤጲስቆጶ
ስ ፡ ኢኖከንቲዩስ ፡ በዚህ ፡ ይፈረድ ፡ አሉ ፡፡ ሌላም ፡ በዲ
ዮስጶሊስ ፡ የተሰበሰበች ፡ ሲኖደስ ፡ ደግማ ፡ ጰላግዩስን ፡ አ
ነጻች ፡ ከመከሰሱ ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነበረ ፡፡

አሁንም ፡ ጰላግዩስ ፡ በምሥራቅ ፡ በነጻ ፡ ጊዜ ፡ ያፍሪቃ ፡
ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለሮም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ለኢኖከንቲዩስ ፡
ጻፈች ፡ የርሱንና ፡ የኬሌስቲዩስን ፡ ትምርት ፡ ይወግዝ ፡ ዘ
ንድ ፡፡ ኢኖከንቲዩስም ፡ ካፍሪቃ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ጋራ ፡ በ
ትምርት ፡ አንድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ መሰላቸው ፡፡ ደግ ፡ በጰላግ
ዩስ ፡ መፍረድ ፡ ሳይችል ፡ ሞተ ፡ ዞሲሞስም ፡ ተከተለው ፡
ባመት ፡ ፬፻፲፯፤ እርሱም ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ አልተማረምና ፡ ከ
ምሥራቅም ፡ መምህራን ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ኑርዋልና ፡ ጰላግዩ
ስንና ፡ ኬሌስቲዩስን ፡ አጸደቃቸው ፡ የፍሪቃ ፡ ኤጲስቆጶሳ
ትንም ፡ ወቀሰ ፡ እለዚህን ፡ ፪፤ ስለ ፡ ወገዙ ፡፡ እርሱም ፡
ለሁለታቸው ፡ ፍጹም ፡ ምስክር ፡ መሰከረላቸው ፡ ኦር
ቶደክሳውያን ፡ እንደ ሆኑ ፡፡ ያፍሪቃ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ግን ፡
በዚህ ፡ ነገሬ ፡ አልታወኩምና ፡ ምላሽ ፡ ጸፉለት ፡ ያሳዩበ
ት ፡ ዞሲሞስ ፡ ይህነን ፡ ነገር ፡ መልካም ፡ እንደልመረመረ ፡
እርሳቸውም ፡ ስለዚህ ፡ የፈረደውን ፡ ፍርድ ፡ እንደልተቀ
በሉ ፡፡ ዞሲሞስም ፡ አሁን ፡ ፈርቶ ፡ ሌላውን ፡ መልእክት ፡
ሰደደላቸው ፡ በርሱ ፡ የጻፈላቸው ፡ እንደሁ ፡ ሲል ፡፡ ይህ ፡ ነ
ገር ፡ ይቈይ ፡ እስከ ፡ ሌላ ፡ ጊዜ ፡፡ እርሳቸው ፡ ግን ፡ አልዘ
ገዩም ፡ ባመት ፡ ፬፻፲፰፤ ሲኖደስን ፡ ሰበሰቡ ፡ በከርታጎ ፡ በር
ሱም ፡ ፰፤ ቃኖናት ፡ አደረጉ ፡ ስለ ፡ አያሌ ፡ ትምርት ፡ እን
ደሀ ፡ አያሉ ፡፡

የሰው ፡ ሁሉ ፡ ጠባይዕ ፡ በመጀመርያ ፡ ሰው ፡ ኃጢአ

ት ፡ ረኵሶ ፡፡ ሞትም ፡ የኀጢአት፤ ደመወዜ ፡ ነው ፡፡ ጸ
ጋም ፡ የመንፈሳዊት ፡ ሕይወት ፡ መስጠት ፡ ነው ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ለልባችን ፡ የሚሰጥ ፡ በውነትም ፡ በጎ ፡ የ
ሚሆን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ከርሱ ፡ ብቻ ፡ ይመጣል ፡፡
አራተኛ ፡ ቃናንም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡፡ ውጉዝ ፡ ይሁን ፡ የ
ሚል ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ በክርስቶ
ስ ፡ የምታጸድቅን ፡ ያለፈውን ፡ ኀጢአት ፡ ለመስረይ ፡
ብቻ ፡ እንድትሆን ፡ ከሚመጣውም ፡ ኃጢአት ፡ ትጠ
ብቀን ፡ ዘንድ ፡ ለመርዳት ፡ እንዲይደል ፡፡
አምስተኛ ፡ ቃኖንም ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡፡ ውጉዝ ፡ ነው ፡ የ
ሚል ፡፡ ጸጋ ፡ በዚህ ፡ መጠን ፡ ብቻ ፡ ትረደናለች ፡ ኃጢ
አት ፡ እንዳናደርግ ፡ ዕውቀት ፡ ስትሰጠነ ፡፡ የእግዚአ
ብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ለማወቅ ፡ እናውቅ ፡ ዘንድ ፡ የ
ሚገባነን ፡ ነገር ፡ ልናደርገው ፡ ልንተወውም ፡፡ ነገር ፡ ግ
ን ፡ በልባችን ፡ አትሰጠነም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእ
ዛዝ ፡ እንወድ ፡ ዘንድ ፡ ችሎትንም ፡ እናደርገው ፡
ዘንድ ፡፡
ጳውሎስም ፡ ሲል ፡፡ ዕውቀት ፡ ይነፋል ፡ ፍቅር ፡ ግን ፡
ይሰራል ፡ ሰው ፡ ቢያምን ፡ ክርስቶስ ፡ ለሚነፋን ፡ ነገ
ር ፡ ብቻ ፡ ጸጋውን ፡ እንዲሰጠነ ፡ ለመስራት ፡ ግን ፡ እንዲ
ይሰጠነ ፡ ሁሉም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስጥወታ ፡ ሁንዋል
ና ፡ የሚገባንን ፡ ስራ ፡ ማወቅ ፡ ለማድረግም ፡ መው
ደድና ፡ ችሎት ፡፡ ዕውቀት ፡ እንደይነፋነ ፡ ፍቅር ፡ ይ
ሰራነ ፡ ዘንድ ፡ እንጂ ፡፡
በ፯፤ ቃኖን ፡ ያች ፡ ትምርት ፡ ደግሞ ፡ ተወገዘች ፡ ሰው ፡ ያ
ለ ፡ ጸጋ ፡ ባለቤቱ ፡ ያደረገው ፡ ዘንድ ፡ የሚችለው ፡ ስራ ፡ ጸ
ጋ ፡ መስራት ፡ እንድታቀለው ፡ ብቻ ፡ የምትል ፡፡ ክርስቶስ ፡
በዮሐንስ ፡ ወንጌል ፡ ፲፭፤ ፭፡፡ አይልምና ፡፡ ያለኔ ፡ አንደችን ፡
ታድርጉ ፡ ዘንድ ፡ ይቸግርላችኋል ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡፡ ያለኔ ፡ አን
ደችን ፡ ማድረግ ፡ አትችሉም ፡፡
ቄሣር ፡ ሆኖርዩስም ፡ ባመት ፡ ፬፻፲፰፤ አያሌ ፡ ትእዛዛት ፡
ሰጥትዋልና ፡ በጳላግዩስ ፡ ወገን ፡ ላይ ፡ ዞሲሞስ ፡ ፈራ ፡ ካ
ፍሪቃ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ጋራ ፡ አንድነት ፡ አደረገ ፡ ኬሌስቲ

ዩስንና ፡ ጰላግዩስንም ፡ ወገዘ ፡፡ ኤጲስቆጶሳትንም ፡ ሁሉ ፡ ይህነን ፡ መውገዝ ፡ ያጸኑት ፡ ዘንድ ፡ አዘዛቸው ፡፡ ፲፰፡ ኤጲስቆጶሳትም ፡ እምቢ ፡ ብለዋልና ፡ ሹመታቸው ፡ ተሻረች ፡፡

አንድ ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ በዚህ ፡ ክርክር ፡ ይህ ፡ ነበረ ፡፡ ስለ ፡ ሰው ፡ አርነት ፡፡ ጰላግዩስ ፡ አለ ፡፡ ይህ ፡ አርነት ፡ የሰው ፡ ፈቃድ ፡ ችሎት ፡ ነው ፡ በበጎና ፡ በክፉ ፡ መኻከለ ፡ ለመምረጽ ፡ ነፍሱንም ፡ ወይስ ፡ ለበጎ ፡ ወይስ ፡ ለክፉ ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፡፡ ከዚህ ፡ ሥር ፡ በጎና ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ሁሌጊዜ ፡ ይመጣል ፡ ብሎ ፡፡ አውጉስቲኑስ ፡ ግን ፡ አለው ፡፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ መካከል ፡ በበጎና ፡ በክፉ ፡ መኻከል ፡ በሰው ፡ ፈቃድ ፡ አይገኝም ፡፡ ሰውም ፡ ወትሮ ፡ በልቡ ፡ ባንዷች ፡ ይጸናል ፡ ማድረጉ ፡ ሳይደረግ ፡፡ ክፉና ፡ በጎ ፡ ካንዲት ፡ ሥር ፡ አይወጣም ፡፡ ክፉ ፡ ዛፍ ፡ በጎ ፡ ፍሬን ፡ አያፈራም ፡ በጎ ፡ ዛፍም ፡ ክፉ ፡ ፍሬን ፡ አያፈራም ፡፡ በጎ ፡ ሁሉ ፡ ከሚወጣው ፡ ሥር ፡ እርሱ ፡ እግዚአብሔርን ፡ መውደድ ፡ ነው ፡፡ የክፉ ፡ ሁሉ ፡ ሥር ፡ ግን ፡ የነፍሱን ፡ መውደድ ፡ ነው ፡፡ በዚያ ፡ መጠንም ፡ ሰው ፡ ወይስ ፡ በጎን ፡ ወይስ ፡ ክፉን ፡ ይፈጽማል ፡ በልቡ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፍቅር ፡ ቢገዛ ፡ ወይስ ፡ የራሱን ፡ መውደድ ፡ ቢገዛ ፡፡ የጰላግዩስ ፡ ትምርት ፡ ግን ፡ ስለ ፡ አርነት ፡ ፈቃድ ፡ አይገጠምም ፡፡ ለእግዚአብሔርና ፡ ለሞቱ ፡ ጻድቃንም ፡፡ እርሳቸው ፡ መምረጽ ፡ አይችሉምና ፡ በበጎና ፡ በክፉ ፡ መኻከል ፡ ለሰው ፡ ጥፋት ፡ ብቻ ፡ ይገጽማል ፡ ሰውም ፡ በቅድስና ፡ በሚያድግ ፡ መጠን ፡ መምረጽ ፡ ያልቅበታል ፡ በውነትም ፡ አርነት ፡ ይወጣል ፡ በጎ ፡ ነገርንም ፡ አለመጠራጠር ፡ በደስታ ፡ ያደርጋል ፡፡ በበጉነትም ፡ ፍጻሜ ፡ አርነትና ፡ ግድ ፡ አንድ ፡ ናቸው ፡፡ አእምሮ ፡ ላለው ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ በአርነት ፡ ያድርጋል ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሕግ ፡ ቢገዛ ፡፡ እንዲህ ፡ ያለችም ፡ አርነት ፡ አሁን ፡ አትገኝምና ፡ የሰው ፡ ፍጥረት ፡ እንደ ፡ ተጉደ ፡ ጥፋትም ፡ እንደ ፡ ገባበት ፡ ይገለጻል ፡፡ ክፉ ፡ አእምሮም ፡ ካለው ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ከባሕሪው ፡ ጋራ ፡ ይጸላል ፡፡ ከፍጥረቱም ፡ ጋራ ፡ አይገጠምም ፡፡ ሰውም ፡ የተፈጠረበት ፡ አርነት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከጠፋች ፡ በኋላ ፡ ሰው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ሕግ ፡ ርቅዋልና ፡ ባርነት ፡ አርነትን ፡

ተከተለች ፡፡ ሰውም ፡ ከፍጥረቱ ፡ እንደ ገባው ፡ ጠባዩን ፡ ለ በጎ ፡ ላምላካዊም ፡ ነገር ፡ ነፍሱን ፡ ሰጥቶ ፡ በውነተኛዪቱ ፡ አርነት ፡ ወትር ፡ በዝቶ ፡ እንደ ጸናባት ፡ እንደሁም ፡ ነፍሱ ን ፡ ለክፉ ፡ ሰጥቶ ፡ በክፉ ፡ ባርነት ፡ ወትር ፡ በዝቶ ፡ ይጸና በታል ፡፡ ክርስቶስ ፡ እንዳለ ፡፡ ኃጢአትን ፡ የሚያደርግ ፡ የ ኃጢአት ፡ ባርያ ፡ ነው ፡፡ ክፉም ፡ ደመወዙን ፡ ባለቤቱ ፡ ይ ከፍላል ፡ በጎም ፡ ባለቤቱ ፡፡

ጶላግዩስ ፡ ግን ፡ ከወገኑ ፡ ጋራ ፡ የሰውን ፡ የባሕሪውን ፡ ጥፋት ፡ አላመኑም ፡፡ የአደም ፡ ባሕሪ ፡ እንደ ፡ ሕፃናታችን ፡ ባሕሪ ፡ ነበረች ፡ ኃጢአትንም ፡ አደረገ ፡ ክፉን ፡ በመምረጽ ፡ እንዲህም ፡ ሕፃናታችን ፡ ወይስ ፡ ክፉን ፡ ወይስ ፡ በጎን ፡ ይመርጹ ፡ ዘንድ ፡ ይችላሉ ፡ አደም ፡ እንደ ፡ ቻለው ፡፡ የሰው ፡ ባሕሪም ፡ በአደም ፡ ኃጢአት ፡ አልተለወጠም ፡ ይላሉ ፡፡

ደግሞም ፡ ጶላግዩስ ፡ ሰውን ፡ በክፉና ፡ በበጎ ፡ መኻከል ፡ አስቀመጠው ፡፡ አውጉስቲኑስ ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡፡ ሰ ው ፡ በፍጥረቱ ፡ ሕግ ፡ የሚኖር ፡ ከበጎ ፡ ጋራ ፡ አንድነት ፡ አ ለው ፡፡ ከዚህ ፡ ሕግም ፡ የራቀ ፡ ከክፉ ፡ ጋራ ፡ አንድነት ፡ አ ለው ፡፡ መኻከለኛ ፡ መኖርያ ፡ የለውም ፡፡ በእግዚአብሔር ም ፡ አንድነት ፡ ያለ ፡ ብቻ ፡ በጎ ፡ ነው ፡ ከርሱ ፡ ግን ፡ የተለ የ ፡ ክፉ ፡ ነው ፡፡

የጶላግዩስ ፡ ወገን ፡ ግን ፡ አሉ ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ለሰው ፡ በጎን ፡ ለማድረግ ፡ ኃይልን ፡ ሁሉን ፡ ሰጠው ፡ አሁንም ፡ አን ድ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ይፈለጋል ፡፡ በዚህ ፡ በተሰጠው ፡ ኃይል ፡ በ ጎን ፡ እንዲሰራ ፡፡ መቻልም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ ነ ው ፡፡ መውደድና ፡ ማድረግ ፡ ግን ፡ ከሰው ፡ ዘንድ ፡ ነው ፡፡

አውጉስቲኑስም ፡ አለ ፡፡ የሰው ፡ ፈቃድ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ አንድነት ፡ ወጥቶ ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ ተለይቶ ፡ ሌላ ፡ ማድረግ ፡ አልቻለውም ፡ ክፉ ፡ እንጅ ፡፡ ስ ለዚህም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መመለስ ፡ አልቻለውም ፡ እግዚአብሔር ፡ አዲስ ፡ ጸጋ ፡ ካልሰጠው ፡፡

ያውጉስቲኑስና ፡ የጶላግዩስ ፡ ታላቅ ፡ መለየት ፡ በየት ምርታቸው ፡ ይህ ፡ ነው ፡፡ ጶላግዩስ ፡ ወደ ፡ ሰው ፡ ማድረግ ፡

ብቻ ፡ አዮ ፡ ክፉንም ፡ ወይስ ፡ በጎን ፡ ሁኖ ፡ በርሱ ፡ ቍጠረ ው ፡፡ አውጉስቲኖስ ፡ ግን ፡ የሰውን ፡ ልብ ፡ በእግዚአብሔ ር ፡ ቃልና ፡ መንፈስ ፡ ይመረምር ፡ ዘንድ ፡ ወደደ ፡፡

እንደዚህም ፡ ነበረ ፡ በየትምርታቸው ፡ ስለ ፡ አደም ፡ ኃጢ አት ፡፡ ጰላግዩስ ፡ ይላል ፡፡ አደም ፡ በገነት ፡ ሲፈተን ፡ ፈሬ ን ፡ በመመኘት ፡ ወደቀ ፡፡ አሁንስ ፡ ይህ ፡ መመኘት ፡ እን ዲያው ፡ ክፉ ፡ አልነበረም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተፈጥርዋል ና ፡ ደግ ፡ ይህነን ፡ መመኘት ፡ ተከትሎ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ማፍረሱ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ኃጢአቱ ፡፡

አውጉስቲኑስ ፡ ግን ፡ አለ ፡፡ ያደም ፡ ኃጢአት ፡ ታላቅነት ፡ ይህ ፡ ነው ፡ አርነቱን ፡ በጣርነት ፡ እንደ ፡ ለወጠ ፡፡ እርሱ ፡ ገ ና ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ሲሆን ፡ ከዚች ፡ አንድ ነት ፡ እንደ ፡ ወጣ ፡፡ ይህም ፡ በመጀመርያ ፡ በልቡ ፡ በእግዚ አብሔር ፡ እውነት ፡ ሲጠራጠር ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ም ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ሲወድ ፡ እግዚአብሔርም ፡ የከለከለ ውን ፡ ነገር ፡ ሲመኝ ፡፡ ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ክፉ ፡ ማድረግ ፡ ተከተለ ፡፡ የሰው ፡ ፈቃድ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ከተ ለየ ፡ በኋላ ፡ ጠባዩ ፡ ሁሉ ፡ በሁለት ፡ ተከፈለ ፡ ከዚህ ፡ መ ከፈልም ፡ የሥጋና ፡ የነፍስ ፡ ክፋት ፡ ሁሉ ፡ መጣ ፡ ሞት ም ፡ የኃጢአት ፡ ደመወዜ ፡ ሆነ ፡፡ ከመጀመርያ ፡ ሰውም ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ትውልዱ ፡ ሁሉ ፡ አለፈ ፡፡ በመጀመርያ ፡ ሰውም ፡ የራሱ ፡ መውደድ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተለይቶ ፡ የኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ ምንጭ ፡ አንደ ፡ ሆነ ፡ እንደዚህም ፡ በትው ልዱ ፡ ሁሉ ፡፡ ከዚህም ፡ የሕዋሳት ፡ መመኘት ፡ ተነሣ ፡፡ ሰ ው ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተለይትዋልና ፡ እግዚአብሔርም ፡ የሰውን ፡ መንፈስ ፡ እንዲዚህ ፡ ወዲህ ፡ አላጸገበምና ፡ ወ ደ ፡ ፍጥረት ፡ ዘነበለ ፡ ፍጥረትንም ፡ በእግዚአብሔር ፡ አል ተመኘም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተለይቶ ፡ እንጂ ፡፡

የጰላግዩስ ፡ ወገንም ፡ ሲሉ ፡፡ ይህ ፡ የሕዋሳት ፡ መመኘ ት ፡ ክፉ ፡ እንደይሆን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተፈጥርዋልና ፡ ሰ ውም ፡ መመኘቱን ፡ ከንስሳ ፡ ጋራ ፡ አንደ ፡ ተከፈለ ፡ አው ጉስቲኑስ ፡ መልካም ፡ መለሰላቸው ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ በን ስሳ ፡ ዘንድ ፡ መጋደል ፡ አይገኝም ፡ በመንፈስና ፡ በሥጋ ፡

መካከል ፡፡ ለሰው ፡ ግን ፡ በመንፈሱ ፡ በሕዋሳዊት ፡ ጠባዩ ፡ ላይ ፡ ደገዛ ፡ ዘንድ ፡ ደገባል ፡፡

አውጉስቲኑስም ፡ እንደዚህ ፡ ብሎ ፡ አስተማረ ፡፡ መጀመርያ ፡ ኃጢአት ፡ በአደም ፡ ብቻ ፡ እንደልተቈጠረ ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ አንጂ ፡፡ አደም ፡ የሰው ፡ ሁሉ ፡ አባት ፡ የሰው ፡ ሁሉም ፡ አለቃ ፡ ኑርዋልና ፡ የሰውም ፡ ሁሉ ፡ ዘመድና ፡ ጠባይዕ ፡ በዘር ፡ መጠን ፡ በርሱ ፡ ነበረ ፡፡

የጰላግዩስ ፡ ወገን ፡ ግን ፡ ደህነን ፡ የኃጢአትን ፡ ፈሬ ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ አውጉስቲኑስ ፡ እንደ ፡ አስተማረ ፡ ካዱት ፡ እንደዚህ ፡ ሲሉ ፡፡ ያንድ ፡ ሰው ፡ ኃጢአት ፡ በሌላ ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ መቈጠር ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ጽድቅ ፡ ጋራ ፡ ደጸላል ፡ ኃጢአትም ፡ ካባት ፡ ወደ ፡ ልጁ ፡ ማለፍ ፡ አደችልም ፡፡ አደምም ፡ ልጀቹን ፡ አልጐደቸውም ፡ በምሳሌው ፡ አንጂ ፡፡ በሰው ፡ ወገንም ፡ ኃጢአት ፡ እንደ ፡ በዛ ፡ እውነት ፡ ነው ፡፡ ደህም ፡ እንዲያው ፡ በልማድ ፡ ሆነ ፡፡ ጳውሎስ ፡ ግን ፡ ሲል ፡፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአተኛ ፡ እንዲሆን ፡ ሁሉም ፡ እንደ ፡ በደሉ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ሳይቀር ፡ ማለቱ ፡ እንደዚህ ፡ አይደለም ፡፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ደገኛሉና ፡ ኃጢአትን ፡ ያላደረጉ ፡ እንደ ፡ አቤል ፡ ደስሓቅም ፡ ያዕቆብም ፡ ማርያምም ፡፡ እንደዚህም ፡ የጰላግዩስ ፡ ወገን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ሻሩ ፡፡

ኃጢአትንም ፡ ቃሊል ፡ የሚቈጥር ፡ ሰው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ ደግሞ ፡ ቃሊል ፡ ደሆንለታል ፡፡ እንደዚህም ፡ ደገለጸል ፡ በጰላግዩስ ፡ ወገን ፡፡ የእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ መገለጹ ፡ ነው ፡ አሉ ፡ ሰውን ፡ ለማስተማር ፡ የበጎ ፡ ነገርንም ፡ ሁሉን ፡ ምሳሌን ፡ መስጠት ፡፡ ደህም ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ደገኛል ፡ ባረማውያን ፡ ባደሁድም ፡ ከርሳቸውም ፡ ደልቅ ፡ በክርስቲያን ፡፡ የዚህ ፡ ጸጋም ፡ ፈሬ ፡ ጽድቅ ፡ ነው ፡ ከፍጥረት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ በኦሪት ፡ ሕግም ፡ በታች ፡ በወንጌል ፡ ጸጋም ፡ በታች ፡፡

ጰላግዩስም ፡ ከወገኑ ፡ ጋራ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ የሰውን ፡ ፈቃድ ፡ በጎን ፡ ለማድረግ ፡ እንዲያገድ ፡ካደ ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ሰውን ፡ ካስተማረው ፡ ምሳሌንም ፡ ከሰጠው ፡ በኋላ ፡

ለራሱ ፡ ይተወዋል ፡ በጎን ፡ ወይስ ፡ ክፉን ፡ ይመርጽ ፡ ዘን
ድ ፡ አለ ፡፡

አውጉስቲኑስ ፡ ግን ፡ እንደህ ፡ አለ ፡፡ ምግባርን ፡ በመቍ
ጠር ፡ ጸጋ ፡ ይቫራል ፡፡ ጸጋም ፡ እንደ ፡ ያው ፡ እንደ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ መምረጽ ፡ ነው ፡፡ ሰውም ፡ አይችልም ፡ የእግዚአ
ብሔርን ፡ ጸጋ ፡ ይገብር ፡ ዘንድ ፡ ወይስ ፡ ይከለክለው ፡ ዘ
ንድ ፡፡ የእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ ሕይወት ፡ ነውና ፡ ወደ ፡ ሰ
ው ፡ ልብ ፡ ሳይገባ ፡ ሰው ፡ በኃጢአቱ ፡ ይኖራል ፡ ወደ ፡ ልቡ ፡
ግን ፡ ሲገባ ፡ ለኃጢአት ፡ የተገዛ ፡ ፈቃድ ፡ ይለወጣል ፡ ለእ
ግዚአብሔርም ፡ ይታዘዛል ፡፡

ምንድር ፡ ነበረች ፡ የክርስቶስ ፡ መድኃኒት ፡፡ በጶላግዩ
ስ ፡ ዘንድ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰውን ፡ በትምርቱና ፡ በምሳሌው ፡
ብቻ ፡ አደነው ፡ በሌላ ፡ የለም ፡፡ ደግሞ ፡ ብዙ ፡ ኃጢአትን ፡
ላደረጉ ፡ ሰዎች ፡ የኃጢአታቸው ፡ ስርየት ፡፡

አውጉስቲኑስ ፡ ግን ፡ እንደህ ፡ አለ ፡፡ የእግዚአብሔር ፡
ጸጋ ፡ ሰውን ፡ ሲያሳድግ ፡ ለመደኑ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕ
ግ ፡ ለልቡ ፡ ያስታውቀዋል ፡ እንደህም ፡ አድርጎ ፡ ይገልጽ
ለታል ፡ ኃጢአቱን ፡ ጥፋቱንም ፡ ባለቤቱ ፡ በኃይሉ ፡ እንደይ
ችል ፡ ሕግን ፡ ይፈጽም ፡ ዘንድ ፡፡ አሁንም ፡ ሰው ፡ በልቡ ፡
ኃጢአቱን ፡ ሲያውቅ ፡ ማደንን ፡ ይፈልጋል ፡ በማደንም ፡ ያ
ምናል ፡፡ በሃይማኖቱም ፡ የኃጢአቱን ፡ ስርየት ፡ ብቻ ፡ አይ
ቀበልም ፡ ከክርስቶስ ፡ ሕይወት ፡ ጋራ ፡ አንድነት ፡ ያደርጋ
ል ፡ እንጅ ፡፡ የክርስቶስም ፡ ሕይወት ፡ ይገባበታል ፡፡ ለነፍ
ሱም ፡ ጤና ፡ ይሆናል ፡ ከኃጢአቱ ፡ ሕማም ፡፡ አሁንም ፡
ፈቃዱ ፡ ይፈታል ፡ አርነትም ፡ ይወጣል ፡ አስቀድሞ ፡ የኃ
ጢአት ፡ ባርያ ፡ የነበረ ፡፡ ሰውም ፡ አሁን ፡ በፈቃዱ ፡ ለጽድ
ቅ ፡ ይገዛል ፡ በምታገለግል ፡ ፍቅር ፡፡ የእግዚአብሔርም ፡ ጸ
ጋ ፡ አምላካዊት ፡ ሕይወት ፡ በሰው ፡ ልብ ፡ የምትሠለጥን ፡
በፍቅር ፡ ስራ ፡ ትገለጸለች ፡፡ ይህም ፡ የሕግ ፡ የሚያሐይ
ው ፡ መንፈሱ ፡ በክርስቲያን ፡ ልብ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የ
ሚፈስ ፡ ፍቅር ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በዚች ፡ ሕይወት ፡
ሲኖር ፡ ወደ ፡ በጐነት ፡ ወደ ፡ ቅድስና ፡ ፍጻሜ ፡ አይደርስ
ም ፡ ኃጢአቱም ፡ በጣም ፡ አይተወውም ፡፡ ስለዚህ ፡ ወት

ር ፡ ከኃጢአት ፡ ጋራ ፡ መጋደል ፡ ይፈለጋል ። በመጋደልም ፡ እንደ ደደክም ፡ እስኪሞት ፡ ድረስ ፡ የማጽናት ፡ ጸጋ ፡ ይፈለጋል ። እርሱም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ለዘላለም ፡ ሕይወት ፡ የተመረጹ ፡ የሚታወቁበት ፡ ምልክታቸው ፡ ነው ።

ስለ ፡ ዘላለም ፡ መምረጽም ፡ ትምህርቱ ፡ ይህ ፡ ነበረ ። መጀመርያ ፡ ኃጢአት ፡ ከሰው ፡ ፈቃድ ፡ ተነሣ ፡ የተከተለው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሁሉ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ነው ፡ ዓለም ፡ ሳይፈጠር ፡ እንዲህ ፡ የወሰነው ። ይህችም ፡ ትምርት ፡ ስለ ፡ ዘላለም ፡ መምረጽ ፡ እንደትጐዳ ፡ እጅግ ፡ መጠንቀቅ ፡ ፈለገች ። አውጉስቲኑስም ፡ ይህነን ፡ አይቶ ፡ አያሌን ፡ መጻሕፍትን ፡ ጻፈ ፡ ሰውን ፡ ያስጠነቅቅ ፡ ዘንድ ።

የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ሌላ ፡ ወገን ፡ ሰዎች ፡ ተነሡ ፡ መኻከለኞች ፡ ባውጉስቲኑስና ፡ በጰላግዩስ ፡ መኻከል ፡ መንፈቀ ፡ ጰላግያኖች ፡ የተባሉ ። ከርሳቸውም ፡ የሚበልጥ ፡ መምህር ፡ አንድ ፡ ዮሐንስ ፡ ከሲያኑስ ፡ ነበረ ፡ የዮሐንስ ፡ አፈ ወርቅ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ወደ ፡ መሲልያ ፡ የመጣ ፡ ከዚያም ፡ ታላቅ ፡ ገዳም ፡ የታወቀም ፡ ያደረገ ።

አውጉስቲኑስም ፡ ሞተ ፡ ለጸጋ ፡ እንዲህ ፡ ከመሰከረ ፡ በኋላ ፡ ባመት ፡ ፬፳፱ በዕድሜም ፡ ፸፫ አመት ። ከሞቱ ፡ በኋላ ፡ ክርክር ፡ ስለ ፡ ትምርቱ ፡ አልቀረም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ባመት ፡ ፭፴ የሚያህል ፡ በምዕራብ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ተቀበሉት ።

፬፬ ስለ ፡ ምሥጢራት ፡ ትምህርት ፡ ታሪክ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ።

በዚህ ፡ ዘመን ፡ ስለ ፡ ምሥጢራት ፡ የጻፉ ፡ አፈ ፡ ወርቅና ፡ ኢሲደርስ ፡ አውጉስቲኑስም ፡ ቴዎደሮስም ፡ ጎርጎርዮስም ፡ የጰላግዩስ ፡ ወገንም ፡ ሌሎችም ፡ ናቸው ።

አውጉስቲኑስም ፡ በምሥጢራት ፡ ፪ ነገር ፡ ይለያል ። የሚታይ ፡ የማይታይም ። የሚታይም ፡ ምልክት ፡ ነው ፡ ለማይታይም ። የሚታይም ፡ ለሁሉ ፡ ይሆናል ፡ የማይታይ ፡ ግን ፡ ለሁሉ ፡ አይሆንም ።

የምሥጢራት ፡ ቍጥርም ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ በዛ ፡፡ ክርስ ቶስ ፡ ፪፤ ብቻ ፡ አደረገ ፡ ጥምቀትና ፡ ቍርባን ፡፡ አሁን ፡ ግ ን ፡ ፯፤ ሆኑ ፡ እሌህ ፡ ፭፤ ተጨምረዋልና ፡፡ የተጠመቁ ፡ ማ ጽናት ፡፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ያገልጋዮችዋ ፡ የሞናኵ ስትም ፡ ቅደሴ ፡፡ መጋባትም ፡፡ የሚሞቱም ፡ መቅባት ፡፡ ንስሓም ፡፡

፭፷፤ ስለ ፡ ፍ ጻ ሜ ፡ ት ም ር ት ፡፡

በዚህ ፡ ዘመንም ፡ ብዙ ፡ ሆኑ ፡ ያሉ ፡፡ የተረገሙ ፡ ሥቃ ይ ፡ በገሃናም ፡ ለዘላለም ፡ አይኖርም ፡ በርሶ ፡ ብዙ ፡ ይነ ጹበታል ፡ ለርሳቸውም ፡ የመንጻት ፡ እሳት ፡ ነው ፡፡ ከር ሶም ፡ በሕያዋን ፡ ጸሎት ፡ በንስሓም ፡ ይወጣሉ ፡ ወደ ፡ ሰ ማይም ፡ ያልፋሉ ፡፡ ከምሥራቅ ፡ መምህራንም ፡ አያሌ ፡ ነበሩ ፡ ያሉ ፡፡ የተረገሙ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ሥቃይ ፡ ከተቀበ ሉ ፡ በኋላ ፡ እርሳቸው ፡ ንስሓ ፡ ይገባሉ ፡ የእግዚአብሔር ም ፡ ምሀረት ፡ ለሁላቸው ፡ ይደርሳል ፡ ፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ እ ስክትድን ፡ ድረስ ፡፡ በዚህ ፡ ትምርትም ፡ ከዚያ ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ እጅግ ፡ መጉደት ፡ ሆነበት ፡፡

፫፡፡ ስለ ፡ ኦሪጌኔስ ፡ በ ዚ ህ ፡ ዘ መ ን ፡ የተነሣ ፡ ክርክር ፡፡

በዚህ ፡ ዘመን ፡ ብዙ ፡ መናፈቃን ፡ ነበሩ ፡ የኦሪጌኔስን ፡ ቃ ል ፡ አውጥተው ፡ የተናፈቁበት ፡ ስለዚህ ፡ ብዙ ፡ ሌሎች ፡ መምህራን ፡ የኦሪጌኔስን ፡ መጻሕፍት ፡ መማር ፡ ከለከሉ ፡፡

ከኦሪጌኔስም ፡ ወዳጆች ፡ እሌህ ፡ ነበሩ ፡፡ ኤውሴቢዮ ስ ፡ ከቂሣርያ ፡፡ ዲዲሞስም ፡ ከስክንድርያ ፡፡ ባሲልዮስ ም ፡፡ ጎርጎርዮስም ፡ ከኒሳ ፡፡ ጎርጎርዮስም ፡ ከናትያንዝ ፡፡ ዮሐንስም፡ ከየሩሳሌም ፡፡ሩፊኑስም ፡፡ ከጸላቶቹም ፡ እሌ ህ ፡ ነበሩ ፡፡ መርኬሎስ ፡፡ ጳኾሚዮስም ፡፡ ኤጲፋኒዮስ ም ፡፡ ሄሮኒሙስም ፡ ሌሎችም ፡፡

ሄሮኒሙስም ፡ በመጀመርያ ፡ ከሩፊኑስና ፡ ከዮሐንስ ፡ ጋራ ፡ በየሩሳሌም ፡ ባንድ ፡ ሁኖ ፡ የኦሪጌኔስ ፡ ወዳጅ ፡ ነ

በረ ። በኋላም ፡ ሰውን ፡ ፈርቶ ፡ ጸላቱ ፡ ሆነ ፡ ስለርሱም ፡ ከረፊኑስና ፡ ከዮሐንስ ፡ ጋራ ፡ ተጻላ ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ በምስር ፡ የነበሩ ፡ ምናክሮች ፡ ደግሞ ፡ ስለ ፡ ኦሪጌኔስ ፡ ተለዩ ። የኦሪጌኔስም ፡ ጸላቶች ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሥእል ፡ አድርገዋልና ፡ መናፈቃን ፡ ሁነው ፡ ተቍጠሩ ። ቴዎፊሎስም ፡ የስክንድርያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ በላያቸው ፡ ጻፈ ። እልያ ፡ ግን ፡ ተቃዋተው ፡ ወደ ፡ ቴዎፊሎስ ፡ አብደው ፡ ሲርጡ ፡ እርሱ ፡ በግብዝነቱ ፡ አስታረቃቸው ፡ ኦሪጌኔስንም ፡ ወገዘላቸው ። በኋላም ፡ ከስስቱ ፡ የተነሣ ፡ ከበጎ ፡ ሰው ፡ ከቄስ ፡ ኢሲደሮስ ፡ ጋራ ፡ ተጻለ ፡ እርሱም ፡ የኦሪጌኔስ ፡ ወዳጅ ፡ የነበረ ። ኢሲደሮስን ፡ ገዘተ ፡ ወገዘውም ። ያም ፡ ወደ ፡ መናኵስት ፡ ወደ ፡ ኦሪጌኔስ ፡ ወዳጆች ፡ ሸሸ ። ቴዎፊሎስም ፡ እርሱንና ፡ እርሳቸውን ፡ አሳደደ ፡ ኦሪጌኔስንም ፡ የኦሪጌኔስንም ፡ መጻሕፍት ፡ በስክንድርያ ፡ ባመት ፡ ፫፻፺፱፡ በተሰበሰበች ፡ ሲኖደስ ፡ ወገዘ ። እለዚያንም ፡ መናኵስት ፡ የኦሪጌኔስን ፡ መጻሕፍት ፡ የመረመሩትን ፡ ከምስር ፡ አወጣቸው ። እርሳቸውም ፡ ወደ ፡ ቈንስታንቲኒያ ፡ ሸሹ ። ከዚያም ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስ ፡ የግፉም ፡ ሁሉ ፡ ጸላት ፡ ሁኖ ፡ ተቀበላቸው ። አሁንም ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ በበጎ ፡ ስራው ፡ በብርታቱም ፡ በክፎች ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ቀሳውስት ፡ ወደ ፡ ኤጲስቆጶሳትም ፡ ወደ ፡ ሕዝብም ፡ ወደ ፡ ታናሾችና ፡ ወደ ፡ ታላቆች ፡ ወደ ፡ ንግሥት ፡ እንኳ ፡ ወደ ፡ ኤውደክሲያ ፡ በሚደርስ ፡ ለራሱ ፡ ብዙ ፡ ጸላቶች ፡ አደረገለት ። ቴዎፊሎስም ፡ ባለቤቱ ፡ ጸላቱ ፡ ነበረ ፡ እርሱ ፡ በፊት ፡ ቀሮታልና ፡ አሁንም ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ከርሱ ፡ ስለ ፡ በለጠ ፡ ተቀናበት ። አሁንም ፡ እልያ ፡ ሞናኵስት ፡ ወደርሱ ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ለቴዎፊሎስ ፡ መልእክትን ፡ ጻፈ ፡ ሲለምነው ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ እንዲታረቅ ፡ ይቅርም ፡ እንዲላቸው ። ቴዎፊሎስ ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ፈንታ ፡ ከሳሾችን ፡ ሰደደ ፡ በመናኵስት ፡ ላይ ፡ ወደ ፡ ቈንስታንቲኒያ ። ምናኵስትም ፡ እርሳቸው ፡ ደግመው ፡ አሁን ፡ ቴዎፊሎስን ፡ ከሰሱት ፡ ቄሣርም ፡ አፈ ፡ ወርቅን ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ፈራጅ ፡ አድርጎ ፡ ቴዎፊሎስን ፡ አስመጣ ።

ከዚያ ፡ ጀምሮም ፡ ቴዎፊሎስ ፡ ሌላ ፡ ነገርን ፡ አላሰበም ፡ አፈ ፡ ወርቅን ፡ ደኅር ፡ ዘንድ ፡ እንጅ ፡፡ ስለዚህ ፡ ሲኖደስን ፡ ሰበሰበ ፡ ኦሪጌኔስ ፡ የተወነዘበት ፡ አፈ ፡ ወርቅ ፡ ግን ፡ ለመውገዝ ፡ እምቢ ፡ አለ ፡፡ በዚህ ፡ መክንያትም ፡ ጸላቶቹ ፡ በዙ ፡ ቴዎፊሎስም ፡ በረታበት ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ቴዎፊሎስ ፡ በተንኰሉ ፡ ኤውዶክሲያን ፡ አስቈጣት ፡ ባፈ ፡ ወርቅ ፡ ላይ ፡ እንደህም ፡ ከኤጲስቆጶሳቱ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ቆንስታንቲኒያ ፡ ጋራ ፡ መጣ ፡ እንደ ፡ ተከሰሰም ፡ አይደለም ፡ እንደ ፡ ፈራጅ ፡ እንጅ ፡፡ ሲኖደስን ፡ ለቆንስታንቲኒያ ፡ በሚቀርብ ፡ በዛፍ ፡ ታች ፡ ሰበሰበ ፡ የቆንስታንቲኒያን ፡ ሕዝብ ፡ ፈርትዋልና ፡፡ የተሰበሰቡም ፡ ያፈ ፡ ወርቅ ፡ ጸላቶች ፡ ነበሩ ፡ እርሳቸውም ፡ ወገዙት ፡ ቄሣርም ፡ አሳደደው ፡ ወደ ፡ ሩቅ ፡ አገር ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ጥቂት ፡ ቀን ፡ እርሱ ፡ ከሔደ ፡ በኋላ ፡ ምድር ፡ ተናወጸች ፡ ንግሥትም ፡ ኤውዶክሲያ ፡ ፈርታ ፡ አስመለሰቸው ፡፡ አፈ ፡ ወርቅም ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ በደስታ ፡ ተቀበለቸው ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ፪፡ ወር ፡ ብቻ ፡ ተቀምጦ ፡ ንግሥቱን ፡ በጸየፈ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ኃጢአትዋ ፡ እርስዋ ፡ ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ አሳደደቸው ፡ ባመት ፡ ፬፻፬፡ ወደ ፡ ኩኩሶስም ፡ ሰደደቸው ፡ በኢሳውርያ ፡ ወደምትኖር ፡፡ ከዚያም ፡ አላረፈም ፡ የክርስቶስን ፡ መንግሥት ፡ ከመዝረጋት ፡ ባሕዛብ ፡ መኻከል ፡ ብርሃኑም ፡ እጅግ ፡ አበራ ፡፡ ስለዚህም ፡ ጸላቶቹ ፡ ተቀንተውበት ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ ስፍራ ፡ ሰደዱት ፡ ባመት ፡ ፬፻፯፡ በመንገዱም ፡ እጅግ ፡ አድክመውታልና ፡ በኮማኑ ፡ አገር ፡ ሞተ ፡ እንደህ ፡ ሲል ፡፡ ምስጋና ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ስለ ፡ ሁሉ ፡፡

የኦሪጌኔስም ፡ ክርክር ፡ አደስ ፡ ተነሣ ፡ በዩስቲኒያኑስ ፡ ዘመን ፡፡ አያሌ ፡ ጊዜም ፡ ከሰው ፡ ተወገዘ ፡ ነፍሱ ፡ በደህንነት ፡ ስትኖር ፡ በክርስቶስ ፡ በጌታው ፡ ዘንድ ፡፡

ስለ ፡ አያሌ ፡ መናፈቃን ፡ በዚህ ፡ ዘመን ።

፩፤ ስለ ፡ አውዲያኖች ።

አውዲዎስ ፡ አስቄጥስ ፡ ነበረ ፡ አካሔዱ ፡ ያለ ፡ ነውር ፡ የነበረ ። እርሱም ፡ ቀሳውስትንና ፡ ኤጲስቆጶሳትን ፡ ሲገሥጽ ፡ እርሳቸው ፡ ጸልተውት ፡ ገዘቱት ። አሁንም ፡ ብዙ ፡ ከቀሳውስትና ፡ ከሕዝቡ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ሆኑ ፡ ቀሰሱትም ፡ አለቃቸውንም ፡ አደረጉት ። እርሳቸውም ፡ ከሌላ ፡ ቤት ፡ ክርስቲያን ፡ ጋራ ፡ አንድነት ፡ አላደረጉም ። ፋሲካንም ፡ እንደ ፡ በቀደም ፡ ካይሁድ ፡ ጋራ ፡ አደረጉ ። አውዲዎስም ፡ አለቃቸው ፡ ወደ ፡ ሞስኮብ ፡ ምድር ፡ ከተሳደደ ፡ በኋላ ፡ ጎቶች ፡ ሥርዓቱን ፡ ለጊዜ ፡ ተቀበሉት ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ መለየታትው ፡ ጠፋ ።

፪፤ የሬቶርዮስ ፡ ወገን ፡ በስክንድርያ ፡ ያውቀት ፡ ጸላቶች ፡ እንደ ፡ ነበሩ ፡ ይባላል ።

፫፤ ማኒኬዎች ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ በሮም ፡ መንግሥት ፡ በፋርስም ፡ መንግሥት ፡ ተዘረጉ ። ወደ ፡ አፍሪቃም ፡ ወደ ፡ ገልያም ፡ ደረሱ ፡ ተሳደዱም ፡ እስከሚከተልም ፡ ዘመን ፡ ኖሩ ።

፬፤ የጵርስኪልያኑስ ፡ ወገን ፡ በስጳንያ ፡ የተነሡ ፡ ትምርታቸውም ፡ የማኒኬዎችን ፡ ትምርት ፡ የመሰለች ። እርሳቸውም ፡ በምዕራብ ፡ ተዘረጉ ፡ ተሳደዱም ። ጵርስኪልያኑስም ፡ ተገደለ ። ያም ፡ ሾፈጭ ፡ መክሲሙስ ፡ የንጉሥን ፡ ዙፋን ፡ የወሰደ ፡ የሁላቸውን ፡ ክብትና ፡ ሕይወት ፡ ፈለገ ። ማርቲኑስ ፡ ግን ፡ የቱር ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ቅዱስ ፡ ሰውም ፡ ከለከለው ።

የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
ታሪክ ፡

ሶስተኛ ፡ ክፍል ፡፡

ከሮም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ከታላቅ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ጀምሮ ፡
እስከ ፡

ቄሣር ፡ ታላቅ ፡ ካርል ፡ እስከ ፡ ሞቱ ፡ ድረስ ፡፡

ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ በኋላ ፡ ከ፭፻፺፤ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፰፻፲፬፤
ድረስ ፡፡

የዚህ ፡ ዘመን ፡ ነገሥታት ፡ እሌህ ፡ ናቸው ።

፩፡ በምሥራቅ ።

1. መውሪትዮስ ፡ እስከ ፡ ፮፻፪። ድረስ ።
2. ፎቃስ ፡ ከ፮፻፪። ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፮፻፲። ድረስ ።
3. ሄራክልዮስ ፡ ከ፮፻፲። ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፮፻፵፩፡ ድረስ ።
4. ሶስተኛ ፡ ቆንስታንቲኖስ ፡ ፮፻፵፩።
5. ሄራክሌዎናስ ፡ ፮፻፵፩።
6. ሁለተኛ ፡ ቆንስታንስ ፡ ፮፻፵፩፡ እስከ ፡ ፮፻፷፰።
7. አራተኛ ፡ ቆንስታንቲኖስ ፡ ጶጎናቶስ ፡ የተባለ ፡ ፮፻፷፰፡ እስከ ፡ ፮፻፹፭።
8. ሁለተኛ ፡ ዩስቲኒያኖስ ፡ ከ፮፻፹፭፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፮፻፺፭፡ ድረስ ።
9. ሌዎንቲዮስ ፡ ፮፻፺፭፡ እስከ ፡ ፮፻፺፰።
10. ሶስተኛ ፡ ቲቤርዮስ ፡ ፮፻፺፰፡ እስከ ፡ ፯፻፭።
11. ሁለተኛ ፡ ዩስቲኒያኖስ ፡ በቡልጋሮች ፡ ኃይል ፡ ተመልሶ ፡ ይነግሣል ፡ ፯፻፭። እስከ ፡ ፯፻፲፩።
12. ፊልጲኮስ ፡ ፯፻፲፩፡ እስከ ፡ ፯፻፲፫።
13. ሁለተኛ ፡ አናስታስዮስ ፡ ፯፻፲፫፡ እስከ ፡ ፯፻፲፮።
14. ሶስተኛ ፡ ቴዎዶስዮስ ፡ ፯፻፲፮።
15. ሶስተኛ ፡ ሌዎን ፡ ኢሳውሪኮስ ፡ ፯፻፲፮፡ እስከ ፡ ፯፻፵፩።
16. አምስተኛ ፡ ቆንስታንቲኖስ ፡ ቆጵሮኒሞስ ። ፯፻፵፩፡ እስከ ፡ ፯፻፸፭።
17. አራተኛ ፡ ሌዎን ፡ ኻዛርስ ፡ ፯፻፸፭፡ እስከ ፡ ፯፻፹። ምሽቱም ፡ ኢሬኔ ።
18. ስድስተኛ ፡ ቆንስታንቲኖስ ፡ ጶርፊሮጌኔቶስ ። ኢሬኔ ፡ እናቱ ፡ በርሱ ፡ ፈንታ ፡ ነገሠች ፡ ከ፯፻፹። ጀምራ ፡ እስከ ፡ ፯፻፺። ድረስ ። ከዚያም ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፯፻፺፯፡ ድረስ ፡ ቆንስታንቲኖስ ፡ ባለቤቱ ፡ ነገሠ ። የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ኢሬኔ ፡ ልጇዋን ፡ አስገደለች ።

19. ኢሬኔ ፡ የቈንስታንቲኖስ ፡ የጾርፊሮጌኔቶስ ፡ እናት ፡ ልጅዋን ፡ ካስገደለች ፡ በኋላ ፡ ነገሠች ፡ እስከ ፡ ፰፻፪ ድረስ ።

20. ኒኪፎሮስ ፡ ሎጎቴታ ፡ ፰፻፪ እስከ ፡ ፰፻፲፩።

21. ሚካኤል ፡ ረንካቤ ፡ ፰፻፲፩ እስከ ፡ ፰፻፲፫።

22. አምስተኛ ፡ ሌዎን ፡ አርሜኒኮስ ፡ ፰፻፲፫ እስከ ፡ ፰፻፳።

፪። በምዕራብ ። የፍርንጆች ፡ ነገሥታት ።

1. ሁለተኛ ፡ ክሎታር ፡ ፮፻፲፫ እስከ ፡ ፮፻፳፰።

2. ዳጎበርት ፡ ፮፻፳፰ እስከ ፡ ፮፻፴፰። እርሱም ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ መንግሥቱ ፡ በ፪ ልጆቹ ፡ ተከፈለች ።

3. ክሎድዊግ ፡ ፮፻፴፰ እስከ ፡ ፮፻፶፮።

4. ኤብሮደን ፡ ፮፻፶፮ እስከ ፡ ፮፻፹፩።

5. ጲጲን ፡ ከሄርስታል ፡ ፮፻፸፰።

6. ካርል ፡ መርቴል ፡ ፯፻፲፯።

7. ጲጲን ፡ እጭር ፡ ፯፻፵፩።

8 ታላቅ ፡ ካርል ፡ ፯፻፸፩ እስከ ፡ ፰፻፲፬ ድረስ ። በ፰፻ም ፡ ቄሣር ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ተቀባ ።

፫። የሮም ፡ ጳጳሳት ።

1. ታላቅ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ፭፻፺። እስከ ፡ ፮፻፬።

2. ሳቢኒያኑስ ፡ ፮፻፬ እስከ ፡ ፮፻፮።

3. ሦስተኛ ፡ ቦኒፋኪዩስ ፡ ፮፻፮።

4. አራተኛ ፡ ቦኒፋኪዩስ ፡ ፮፻፮ እስከ ፡ ፮፻፲፭።

5. ዴውስዴዲት ፡ ፮፻፲፭ እስከ ፡ ፮፻፲፰።

6. አምስተኛ ፡ ቦኒፋኪዩስ ፡ ፮፻፲፰ እስከ ፡ ፮፻፳፭።

7. ሆኖርዩስ ፡ ፮፻፳፭ እስከ ፡ ፮፻፴፰።

8. ሲዌሪኑስ ፡ ፮፻፴፰ እስከ ፡ ፮፻፵።

9. አራተኛ ፡ ዮሐንስ ፡ ፮፻፵። እስከ ፡ ፮፻፵፪።

10. ቴዎዶሮስ ፡ ፮፻፵፪ እስከ ፡ ፮፻፵፱።

11. ማርቲኑስ ፡ ፮፻፵፱ ፡ እስከ ፡ ፮፻፶፭።

12. ኤውጌኒዎስ ፡ ፮፻፶፭ እስከ ፡ ፮፻፶፯።

13. ዊታልያኑስ ፡ ፮፻፶፯ እስከ ፡ ፮፻፸፪።

14. አዴዎዳቱስ ፡ ፮፸፪፡ እስከ ፡ ፮፸፮፡፡
15. ዶምኑስ ፡ ፮፸፮፡ እስከ ፡ ፮፸፱፡፡
16. አጋቶ ፡ ፮፸፱፡ እስከ ፡ ፮፹፪፡፡
17. ሁለተኛ ፡ ሌዎን ፡ ፮፹፫፡፡
18. ሁለተኛ ፡ ቤኔዲክቱስ ፡ ፮፹፫፡ እስከ ፡ ፮፹፭፡፡
19. አምስተኛ ፡ ዮሐንስ ፡ ፮፹፮፡፡
20. ኮዋን ፡ ፮፹፮፡፡
21. ሰርጊዮስ ፡ ፮፹፮፡ እስከ ፡ ፯፻፩፡፡
22. ስድስተኛ ፡ ዮሐንስ ፡ ፯፻፩፡ እስከ ፡ ፯፻፭፡፡
23. ሰባተኛ ፡ ዮሐንስ ፡ ፯፻፭፡ እስከ ፡ ፯፻፯፡፡
24. ሲሲኒዮስ ፡ ፯፻፰፡፡
25. ቆንስታንቲኖስ ፡ ፯፻፰፡ እስከ ፡ ፯፲፭፡፡
26. ሁለተኛ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ፯፲፭፡ እስከ ፡ ፯፴፩፡፡
27. ሦስተኛ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ፯፴፩፡ እስከ ፡ ፯፵፩፡፡
28. ዘካሪያስ ፡ እስከ ፡ ፯፶፪፡፡
29. እስጢፋኖስ ፡ ፯፶፪፡
30. ሁለተኛ ፡ እስጢፋኖስ ፡ እስከ ፡ ፯፶፯፡፡
31. ጳውሎስ ፡ እስከ ፡ ፯፷፯፡፡
32. ሁለተኛ ፡ ቆንስታንቲኖስ ፡ ፯፷፰፡፡
33. ሦስተኛ ፡ እስጢፋኖስ ፡ እስከ ፯፸፫፡፡
34. ሃድርያኑስ ፡ እስከ ፡ ፯፺፭፡፡
35. ሦስተኛ ፡ ሌዎን ፡ እስከ ፡ ፰፲፮፡፡

መጀመርያ ፡ ምዕራፍ ፡፡

የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የመዘረጋትዋና ፡ የመከራዋ ፡ ታሪክ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡፡

፩፡ በኤውሮጳ ፡፡

ባለፈና ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ብዙ ፡ አሕዛብ ፡ ፈለሱ ፡ ከስያ ፡
ወደ ፡ ኤውሮጳ ፡ ከምሥራቅም ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡፡ እርሳቸ
ውም ፡ አራዊት ፡ ወታደሮች ፡ ብልሃት ፡ የሌላቸው ፡ ያል
ተማሩም ፡ በማምለካቸውም ፡ አራማውያን ፡ የነበሩ ፡፡
እርሳቸውም ፡ በክርስቶስ ፡ ዘመን ፡ ጌታችን ፡ በሰውነቱ ፡
በምድር ፡ ሲኖር ፡ ፍልሰታቸውን ፡ ጀመሩ ፡ መጀመርያውን
ም ፡ መኖርያቸውን ፡ በስያ ፡ ትተው ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ መ
ጡ ፡፡ ከዚያም ፡ ሲቀመጡ ፡ እግዚአብሔር ፡ በጥቂት ፡ በጥ
ቂት ፡ ለሮም ፡ መንግሥት ፡ አስገዛቸው ፡ መለክተኞቹን
ም ፡ ሰደደላቸው ፡ የወንጌልን ፡ ሰባኮች ፡ በርሳቸው ፡ ስብ
ከት ፡ የዘላለም ፡ መንግሥቱን ፡ በመካከላቸው ፡ ይዘርጋ
ት ፡ ዘንድ ፡፡ የሮም ፡ መንግሥት ፡ ኃይል ፡ አለቀች ፡፡ እርስ
ዋም ፡ በቀድሞ ፡ ባረማውያን ፡ ሥርዓት ፡ ትጀምር ፡ ነበረ
ች ፡ እግዚአብሔርም ፡ መግዛትን ፡ ይሰጣት ፡ ነበረ ፡ ባለም ፡
ሁሉ ፡ ላይ ፡ በመካከልዋ ፡ የክርስቶስ ፡ መንግሥት ፡ ትጀ
ምር ፡ ዘንድ ፡ ኃይልዋንም ፡ በሰው ፡ ልብ ፡ ትገልጽ ፡ ዘንድ ፡፡
ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ፫፻፡ አመት ፡ መከራ ፡ ከተቀበለች ፡ በ
ኋላ ፡ መንግሥቱን ፡ አሸነፈች ፡ ቄሣሮችም ፡ ለቤተ ፡ ክርስ
ቲያን ፡ አገልጋዮች ፡ ሆኑ ፡፡ እርሳቸውም ፡ ሁለቱን ፡ ቤተ ፡
ክርስቲያንን ፡ ከሮም ፡ መንግሥት ፡ ጋራ ፡ ባንድ ፡ ደበለቁ ፡፡
በዚህ ፡ መደበለቅም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተከለከለች ፡ በ
ውሥጥዋ ፡ ከማደግ ፡ መንግሥትንም ፡ ከማደስ ፡፡ ስለዚ
ህም ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚሆነውን ፡ ነገር ፡ ሁሉን ፡ እንዲ
ህ ፡ አበጀው ፡ በምሥራቅ ፡ የወንጌል ፡ ፀሓይ ፡ ሲጨልም ፡
በምዕራብ ፡ እንዲወጣ ፡፡ የሮሞም ፡ መንግሥት ፡ ለእስላ

ሞች ፡ ለበርበር ፡ በሆነች ፡ ጊዜ ፡ ሌሎች ፡ መንግሥቶች ፡ እንዲነሡ ፡ በክርስቶስም ፡ ብርሃን ፡ እንዲመላለሱ ፡ ክርሳቸውም ፡ ወንጌል ፡ በጊዜው ፡ እስኪወጣ ፡ ድረስ ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡፡ የዚህ ፡ መጀመርያ ፡ ባለፈ ፡ ዘመን ፡ ተደረገ ፡፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ በብዙ ፡ አገር ፡ ተተከለች ፡ እጅግ ፡ ደምም ፡ ፈሰሰ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ እጅግ ፡ ምስክሮችም ፡ ተነሡ ፡ በነገራቸው ፡ በጽፈታቸውም ፡ በሕይወታቸውም ፡ ለወንጌል ፡ የመሰከሩ ፡፡ እርሳቸውም ፡ አሁን ፡ በብርሃናቸው ፡ ሊያበሩ ፡ ነበሩ ፡ ባረማውያን ፡ ጨለማ ፡ መካከል ፡ ላደሉ ፡ ሕዝብም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ያስታውቁ ፡ ዘንድ ፡ ተጸሩ ፡፡

እሌህም ፡ ከምሥራቅ ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ የፈለሱ ፡ አሕዛብ ፡ በዚህ ፡ ዘመንም ፡ የክርስቲያንን ፡ ሃይማኖት ፡ የተቀበሉ ፡ ገርማኖች ፡ ይባላሉ ፡ ማለቱ ፡ የጾር ፡ ሰዎች ፡፡ እርሳቸውም ፡ የፍርንጆች ፡ ሁሉ ፡ አባቶች ፡፡ አንዲት ፡ ሕዝብ ፡ ክርሳቸው ፡ ቡርጉንደች ፡ የሚልዋቸው ፡ በ፬፻፲፩ ፡ አመት ፡ የሚያህል ፡ ሃይማኖትን ፡ ተቀበለች ፡ ካርያኖች ፡ መምህራን ፡፡ ባመትም ፡ ፭፻፮፤ ንጉሣቸው ፡ ሲጊስሙንድ ፡ የኒቅያን ፡ ትምርት ፡ ተቀበለ ፡ አዊቱስ ፡ ከሚሉት ፡ ኤጲስቆጶስ ፡፡

ከሌህ ፡ ቡርጉንደችም ፡ ሌላ ፡ ሕዝብ ፡ ፈራንኮች ፡ የተባሉ ፡ ከዚያ ፡ ዘመን ፡ በኋላ ፡ በብዙ ፡ ገርማኖች ፡ ላይ ፡ የገዛች ፡ ሃይማኖትን ፡ ተቀበለች ፡፡ የፈራንኮች ፡ ንጉሥ ፡ ኽሎድዊግ ፡ የቡርጉንደች ፡ ንጉሥን ፡ እት ፡ ምሽት ፡ አድርጎ ፡ አጋባት ፡፡ እርስዋም ፡ ኽሎቲልደ ፡ ክርስቲያኒቱ ፡ ሁና ፡ ባልዋን ፡ ታስታምን ፡ ዘንድ ፡ ደከሙች ፡ ጣዖታት ፡ እንዲደጠቅሙ ፡ ብላ ፡ ወደ ፡ ሃይማኖትም ፡ ትወስደው ፡ ዘንድ ፡ የክርስቲያን ፡ አምላክ ፡ እርሱም ፡ ብቻ ፡ በውነት ፡ አምላክ ፡ የሚሆን ፡ ሁሉን ፡ ይችላልና ፡ ብላታለች ፡፡ ኽሎድዊግ ፡ ግን ፡ እንደህ ፡ ሲል ፡ ፈረደ ፡፡ ያ ፡ አምላክ ፡ ለሕዝቡ ፡ በጸላቶቹ ፡ ላይ ፡ ኃይልና ፡ ድል ፡ የሚሰጥ ፡ ደህና ፡ ነው ፡፡ የሮም ፡ መንግሥት ፡ ግን ፡ ትፈርሳለችና ፡ አምላክዋ ፡ ደህና ፡ እንደይሆን ፡ ደገለጽበታል ፡፡ የብኵር ፡ ልጁ ፡ ግን ፡ በምሽቱ ፡ አምላክ ፡ ስም ፡

ተጠመቀ ፡፡ ሕፃንም ፡ ቶሎ ፡ ሲሞት ፡ የርሱ ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ክ
ርስቲያን ፡ አምላክ ፡ እውነት ፡ መሰለው ፡፡ በክሎቲልደ ፡
ልመና ፡ ግን ፡ ሁለተኛ ፡ ልጅም ፡ ደግሞ ፡ ተጠመቀ ፡፡ ያም ፡
ደግሞ ፡ በታመመ ፡ ጊዜ ፡ ኽሎድዊግ ፡፡ ይህ ፡ ደግሞ ፡ ይሞ
ታል ፡ አለ ፡፡ ኽሎቲልደ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለመነች ፡ ስ
ለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ ባረማውያን ፡ መኻከል ፡ ያድ
ነው ፡ ዘንድ ፡ ብላ ፡ ልመናዋም ፡ ተሰማ ፡፡ ደሮ ፡ ኽሎድዊ
ግ ፡ ለምሽቱ ፡ መስማትን ፡ አልሰጠም ፡ መከራ ፡ እስቲያገ
ኝ ፡ ድረስ ፡፡ ባመት ፡ ፬፻፺፯፡ ሠራዊቱ ፡ በጾር ፡ እጅግ ፡ መከ
ራ ፡ አገኙ ፡፡ ወደ ፡ አማለክቱም ፡ ሁሉ ፡ በከንቱ ፡ ከጸራ ፡ በ
ኋላ ፡ ስለ ፡ ክርስቲያን ፡ አምላክ ፡ የሰማውን ፡ ነገር ፡ አስ
ቦ ፡ ለመነው ፡ አሁን ፡ ይረደው ፡ ዘንድ ፡፡ ስለትም ፡ አደረ
ገ ፡ እግዚአብሔር ፡ ድልን ፡ ይሰጠው ፡ እንደሆን ፡ ያመልከ
ው ፡ ዘንድ ፡፡ እግዚአብሔርም ፡ ድልን ፡ ሰጥቶት ፡ ኽሎድ
ዊግ ፡ አመሰገነው ፡፡ ኽሎቲልደም ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ እጅግ ፡ ደ
ስ ፡ ብላ ፡ ሬሚጊዩስን ፡ የሬምስን ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ አስመጣ
ች ፡፡ ያም ፡ ኽሎድዊግን ፡ ሲያስተምር ፡ አሁን ፡ ልቡ ፡ ተከ
ፈተ ፡፡ ኽሎድዊግም ፡ ባመት ፡ ፬፻፺፯፡ በልደት ፡ ባል ፡ ተጠመ
ቀ ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ከ፴፻፡ የሚበዙ ፡ ከወታደሮቹ ፡ እን
ደ ፡ ተጠመቁ ፡ ይባላል ፡፡

ባመት ፡ ፭፻፶፬፡ የፈረንኮች ፡ ንጉሥ ፡ ኺልድቤርት ፡ ትእዛ
ዝን ፡ ሰጠ ፡ የጣዖታትን ፡ ማምለክ ፡ ሁሉን ፡ የከለከለበት ፡፡

በንግሊዝ ፡ ደሴቶችም ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ደግሞ ፡ ሃይ
ኖት ፡ ተዘረጋች ፡፡ አስቀድሞም ፡ እንደልነ ፡ ጳትሪኪዩስ ፡ በ
ኢርላንድ ፡ ብዙ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርቱን ፡ አስቀረ ፡ እርሱ ፡ በሞ
ተ ፡ ጊዜ ፡፡ እርሳቸውም ፡ የተጀመረውን ፡ የሃይማኖትን ፡ ስ
ራ ፡ ሰሩ ፡ የኢርላንድ ፡ ደሴት ፡ እስክትመላ ፡ በገደሞች ፡፡ እ
ርሳቸውም ፡ ሁሉ ፡ የሃይማኖት ፡ ማስተመርዮች ፡ ነበሩ ፡፡ በ
ብርታንያ ፡ ግን ፡ አሁን ፡ እንግልጣር ፡ በምትባል ፡ ደሴ
ት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አንግሎችና ፡ ሰክሶኖች ፡ በተባ
ሉ ፡ በንግዶች ፡ አሕዛብ ፡ እጅግ ፡ መከራ ፡ አገኝታ ፡ ለመጥ
ፋት ፡ ቀረበች ፡፡ እልያም ፡ አንግሎችና ፡ ሰክሶኖች ፡ ፯፡ መ
ንግሥቶችን ፡ አደረጉ ፡ በንግልጣር ፡ ደሴት ፡፡ ከ፯፡ ነገሥታ

ትም ፡ አንድ ፡ ኤደልበርት ፡ የኬንት ፡ ንጉሥ ፡ አንዲት ፡ ወ
ደዝር ፡ ከፈረንኮች ፡ ንጉሥ ፡ ምሽት ፡ አድርጎ ፡ አጋባት ፡
እርስዋም ፡ ክርስቲያን ፡ ሁና ፡ ኤጲስቆጶስዋን ፡ ከርስዋ ፡
ጋራ ፡ ወሰደች ፡ ንጉሥም ፡ አልከለከላትም ፡ አምላክዋን ፡
ታመልክ ፡ ዘንድ ፡፡ ታላቁ ፡ ጎርጎርዮስም ፡ ይህነን ፡ ዐውቆ ፡
ባመት ፡ ፭፻፺፯ ያንዲት ፡ ገደሙን ፡ መምህር ፡ አውጉስቲኑ
ስ ፡ የሚሉትን ፡ ከ፵ ፡ መነኰሳት ፡ ጋራ ፡ ሰደደ ፡ በንግልጣ
ር ፡ ወንጌልን ፡ ይሰብክ ፡ ዘንድ ፡፡ እርሳቸውም ፡ ወደ ፡ እንግ
ልጣር ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሥ ፡ ኤደልበርት ፡ ተቀበላቸው ፡
ከአውጉስቲኑስም ፡ ጋራ ፡ ተማከረ ፡ በሃይማኖት ፡ ስለ ፡ ማ
ስተማራቸው ፡ በቤት ፡ ይቀበላቸው ፡ ዘንድ ፡ ሳይደፍር ፡ በ
ሜዳ ፡ እንጅ ፡ አስማትን ፡ ፈርትዋልና ፡፡ ሲማከሩም ፡ ንጉ
ሥ ፡ ተዋቸው ፡ ያስተምሩ ፡ ዘንድ ፡ መኖርያንና ፡ ምግብን
ም ፡ ሰጣቸው ፡፡ እንዲህም ፡ ትምህርታቸውን ፡ ሲጀምሩ ፡
ንጉሥ ፡ በፊት ፡ ተማረ ፡ ተጠመቀም ፡፡ የርሱም ፡ ምሳሌ ፡
ኤያሌ ፡ ታምራትም ፡ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ እሺ ፡ አሰኙ ፡ ይጠመ
ቁ ፡ ዘንድ ፡ ባንዲትም ፡ በልደት ፡ ባል ፡ አውጉስቲኑስ ፡ ፲፻፡
የሚያህሉን ፡ ሰዎች ፡ ካረማውያን ፡ አጠመቀ ፡፡ የዚያን ፡
ጊዜም ፡ አውጉስቲኑስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ሁኖ ፡ ተቀደሰ ፡ በኋላ
ም ፡ ለሚትሮጶሊታን ፡፡ ጎርጎርዮስ ፡ ግን ፡ አልተወም ፡ ይ
መክረው ፡ ዘንድ ፡ ለትሕትና ፡ ለጥበብም ፡ በትዕቢት ፡ እን
ዳይወድቅ ፡ የመጽራቱንም ፡ ፍሬ ፡ ከታምራት ፡ እንዲያሻ ፡
ከደህና ፡ ትምህርት ፡ ከፍቅርም ፡ ከትሕትናም ፡ ምሳሌ ፡
እንጅ ፡፡

ነገር ፡ ግን ፡ አውጉስቲኑስ ፡ በንግልጣር ፡ ከቅድም ፡ ከተገ
ኙ ፡ ቀሳውስትና ፡ መነኰሳት ፡ ጋራ ፡ ዕርቅ ፡ አልጠበቀም ፡፡
እርሳቸውም ፡ ከድሮ ፡ ለብቻቸው ፡ ነበሩ ፡ አሁንም ፡ አው
ጉስቲኑስ ፡ ለሮም ፡ ጳጳስ ፡ ያስገዛቸው ፡ ዘንድ ፡ ፈለገ ፡፡ እ
ርሳቸው ፡ ግን ፡ አርነታቸውን ፡ መጠበቅ ፡ ወደዱ ፡፡ ያውጉስ
ቲኑስንም ፡ ትዕቢት ፡ አልወደዱም ፡፡ ስለዚህም ፡ አያሌ ፡
ዘመን ፡ ዘገዩ ፡ ከሮም ፡ ጳጳስ ፡ ጋራ ፡ አንድነትን ፡ ሳያ
ደርጉ ፡፡

የሃይማኖትን ፡ ትምህርት ፡ ግን ፡ መልካም ፡ አላስተማ

ረምና ፡ የተጠመቁንም ፡ ሁሉ ፡ አልፈተነም ፡ የክርስቲያ
ን ፡ ቍጥር ፡ እጅግ ፡ ሲበዛ ፡ ሃይማኖት ፡ ጥቂት ፡ ኖረች ፡ እ
ጅግ ፡ መጋደልም ፡ ሆነ ፡ እስክትገዛ ፡ ድረስ ፡ እስክትጸና
ም ፡ ድረስ ፡፡ ባመት ፡ ፮፻፴፫፡ አንድ ፡ የክርስቲያን ፡ ንጉሥ ፡
በጾር ፡ ሞተ ፡ አረማውያንም ፡ መግዛትን ፡ አገኙ ፡ ቤተ ፡ ክ
ርስቲያንም ፡ ተጨነቀች ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ካያሌ ፡ ወ
ራት ፡ በኋላ ፡ ረዳት ፡ ሰደደ ፡ ግንድ ፡ ሰው ፡ ከንጉሥ ፡ ዘመ
ድ ፡ ኦስዋልድ ፡ በሚሉት ፡፡ እርሱም ፡ ተማርኮ ፡ ነበረ ፡ በ
ኢርላንድ ፡ ከዚያም ፡ ሃይማኖትን ፡ ተማረ ፡ ተጠመቀም ፡
ክርስቶስንም ፡ ወደደ ፡፡ እርሱም ፡ አሁን ፡ ተመልሶ ፡ ዝ
ምቻውን ፡ አደረገ ፡ ባረማውያን ፡ ላይ ፡፡ ሳይወጉም ፡ የመ
ስቀልን ፡ ምልክት ፡ ተከለ ፡ በፊቱም ፡ ሰግደ ፡ ወደ ፡ እግዚ
አብሔር ፡ ጸሬ ፡ ድልን ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፡ ለቅን ፡ ነገር ፡ በጄ ፡፡
እግዚአብሔርም ፡ ተለምኖ ፡ ጸላቶቹን ፡ ከርሱ ፡ እጅግ ፡ የ
በለጡትን ፡ አሸነፈ ፡ ስለዚህም ፡ ልቡን ፡ ብርቱ ፡ አደረገ ፡ የ
ቻለውን ፡ ሁሉን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ያምላኩ ፡ ማምለክ ፡ በ
ሕዝቡ ፡ እስኪገዛ ፡ ድረስ ፡፡ ስለዚህም ፡ አንድ ፡ ብርቱን ፡
ሞነክሴን ፡ አስመጣ ፡ ከኢርላንድ ፡፡ ያ ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ሰው ፡
ድካም ፡ መዋረድ ፡ አልቻለውምና ፡ ሕዝቡ ፡ አልወደዱት
ም ፡ ነገሩንም ፡ አልተቀበሉም ፡ ሞናክሴም ፡ ወደገሩ ፡ ተመ
ለሰ ፡፡ በመናኵስትም ፡ ጉባኤ ፡ ያች ፡ ሕዝብ ፡ አርዌ ፡ ና
ት ፡ ደንቍሮም ፡ ትምህርትንም ፡ አትቀበልም ፡ አለ ፡፡ የ
ዚያን ፡ ጊዜም ፡ አ ይ ደ ን ፡ ተነሥቶ ፡ ወቀሰው ፡ ምህረት ፡
ስለሌለው ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ ለሕፃናት ፡ ወተት ፡ ይገባል ፡
ጴጥሮስ ፡ እንደለ ፡ ለዚች ፡ ሕዝብም ፡ ምህረት ፡ ትዕግሥ
ትም ፡ ይገባል ፡፡ እንዲህም ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ እርሱ ፡ ተመረጸ ፡
የወንጌል ፡ መለክተኛ ፡ ወደዚች ፡ ሕዝብ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡
ኤጲስቆጶስም ፡ ሁኖ ፡ ተቀደሰ ፡፡ እርሱም ፡ ኃይሉን ፡ ሁሉ
ን ፡ ሰጠ ፡ ወንጌልን ፡ ለማስተማር ፡ የክርስቶስንም ፡ ሃይ
ማኖት ፡ ለማጽናትና ፡ ለመዝረጋት ፡፡ ኦስዋልድም ፡ ፰፡ አ
መት ፡ ከነገሠ ፡ በኋላ ፡ ካሕዛብ ፡ ጋራ ፡ ባደረገው ፡ ጾር ፡ ሞ
ተ ፡ ባመት ፡ ፮፻፵፪፡ የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ግን ፡ አልተ
ከለከለችም ፡ ተዘረጋች ፡ እንጂ ፡፡

በንምሳ ፡ ምድርም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አስቀድሞ ፡ ተተክለች ፡፡ በንግደች ፡ አሕዛብ ፡ ግን ፡ ሁሉን ፡ በገለበጡ ፡ እጅግ ፡ ተጨነቀች ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ሴዌሪኑስ ፡ የሚሉት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ተላከ ፡ ለተጨነቁ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ረዴት ፡ ያመጣ ፡ ዘንድ ፡ ወንጌልንም ፡ ያስተምር ፡ ዘንድ ፡፡ አገሬንና ፡ ከብቱን ፡ ዘመዶቹንም ፡ ሥጋ ፡ የሚወደውንም ፡ ነገር ፡ ሁሉን ፡ ትቶ ፡ ዞረ ፡ ደናው ፡ በሚባል ፡ ወንዝ ፡ ካገር ፡ ወደገር ፡ ከድካምና ፡ ከመከራ ፡ ሁሉ ፡ ሳይፈራ ፡ ረዴት ፡ የሚሹትን ፡ ሁሉን ፡ ይረዳቸው ፡ ዘንድ ፡ በዚህም ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ብቻ ፡ አመሰገነ ፡ በምስጋናም ፡ አንቀላፋ ፡፡

ከዚያ ፡ ዘመንም ፡ ጀምሮ ፡ እጅግ ፡ ሞናኮስት ፡ የጳትሪክዩስ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ የርሳቸውም ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ አገራቸውን ፡ ትተው ፡ በንምሳ ፡ በፈረንኮችም ፡ ምድር ፡ ሃይማኖትን ፡ ዘረጉ ፡፡ እንዲህም ፡ የጀመረ ፡ ሰው ፡ ኮሉምባን ፡ ነበረ ፡ ፲፪ ደቀ ፡ መዛሙርትን ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ የወሰደ ፡ እርሳቸውንም ፡ ለብርቱ ፡ ሥርዓት ፡ ለጸሎትም ፡ ለትሕትናም ፡ ለመታዘዝም ፡ በእጅም ፡ ለመስራት ፡ አስለመደ ፡፡ ከርሳቸውም ፡ ጋራ ፡ ገደሞን ፡ ሠራ ፡ በዴር ፡ ባረማውያን ፡ መኻከል ፡፡ የድካማቸውንም ፡ እንጀራ ፡ ብቻ ፡ ሲበሉ ፡ ባፋቸውና ፡ በምሳሌያቸው ፡ አስተማሩ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ከክርስቲያንና ፡ ካሕዛብ ፡ ልጆቻቸውን ፡ እስኪሰጥዋቸው ፡ ድረስ ፡ ለማሳደግና ፡ ለማስተማር ፡፡ እንዲህም ፡ ያሉትን ፡ ገደሞች ፡ እጅግ ፡ ሠራ ፡ በየገደም ፡ ፲፪ መናኮስት ፡ ከ፩ መምህር ፡ ጋራ ፡፡ ስለ ፡ ብርቱ ፡ ልማዴም ፡ ስለ ፡ ተግሣጹምም ፡ እጅግ ፡ መጋደል ፡ ሆነለት ፡ ከሮም ፡ ጳጳሳት ፡ ከሲኖዶችም ፡ ከክርስቲያንና ፡ ካሕዛብም ፡ ጋራ ፡፡ ስለ ፡ ቅድስናው ፡ ግን ፡ ፈረት ፡፡

የኮሉምባንም ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ጋሉስ ፡ ባንድ ፡ ምድረ ፡ በደ ፡ በሀልቤትያ ፡ ምድር ፡ ገደምን ፡ ሠራ ፡ በዙርያም ፡ የነበሩ ፡ አሕዛብ ፡ በትምርቱ ፡ በእግዚአብሔር ፡ አመኑ ፡ በክርስቶስ ፡ ስምም ፡ ተጠመቁ ፡፡ አያሌ ፡ ሞናኮስትም ፡ ተከተሉ ፡ ከኢርላንድ ፡ የመጡ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ም

ድረ ፡ በደም ፡ ገደምን ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ በዙርያቸውም ፡ ወንጌልን ፡ ያስተምሩ ፡ ዘንድ ፡፡ ደግሞም ፡ አያሌ ፡ ኤጲስ ቆጶሳት ፡ ከፈራንኮች ፡ መንግሥት ፡ ለዚህ ፡ ስራ ፡ ነፍሳቸ ውን ፡ ሰጡ ፡፡ ከርሳቸውም ፡ መኻከል ፡ አንድ ፡ ኤጲስቆጶ ስ ፡ ነው ፡ ከሌሎች ፡ የበለጠ ፡ በዛይማኖቱ ፡ ክርስቶስንም ፡ በመውደዱ ፡፡ ሳይቀደስም ፡ የወርቅ ፡ ሰሪ ፡ ነበረ ፡ እንደዚህ ም ፡ ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ ነፍስ ፡ ጠቀመ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እ ስክትፈልገው ፡ ድረስ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡፡ ከዚ ያም ፡ ወዲያ ፡ በብዙ ፡ አሕዛብ ፡ መኻከል ፡ ወንጌልን ፡ አ ስተማረ ፡፡

አንድም ፡ መለክተኛ ፡ ከንግለጣር ፡ የመጣ ፡ በፍሪሶች ም ፡ መኻከል ፡ ያስተማረ ፡ እጅግም ፡ የደከመ ፡ የክርስቶ ስን ፡ ፍቅር ፡ ለዚህች ፡ ሕዝብ ፡ ያስታውቅ ፡ ዘንድ ፡ ዊሊ ብሮርድ ፡ ነው ፡፡

ከሁሉ ፡ ይልቅ ፡ ግን ፡ ቦኒፋኪዩስ ፡ አደረገ ፡ ወንጌል ን ፡ ለመዘረጋት ፡ በንምሳ ፡ ምድር ፡፡ እርሱም ፡ ስለዚህ ፡ የንምሳ ፡ ሐዋርያ ፡ ይባላል ፡፡ እርሱም ፡ በኪርቶን ፡ በንግ ልጣር ፡ ተወለደ ፡ ባመት ፡ ፯፻፡፡ ከሕፃንነቱሞ ፡ ጀምሮ ፡ የ እግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ ወደ ፡ እንደዚያ ፡ ዘመንም ፡ ልማ ድ ፡ ወደ ፡ ገደም ፡ ገባ ፡ ባመትም ፡ ፯፻፲፤ ወደ ፡ ሮም ፡ ሔደ ፡ ከጳጳስም ፡ ከሁለተኛ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ እጅ ፡ መጽሪቱን ፡ ተቀ በለ ፡ በንምሳ ፡ አገር ፡ በወንጌል ፡ ያስተምር ፡ ዘንድ ፡፡ ጳ ጳስ ፡ ጎርጎርዮስም ፡ ባመት ፡ ፯፻፳፫፤ ኤጲስቆጶስ ፡ ይሆን ፡ ዘ ንድ ፡ ቀደሰው ፡ ለንምሳ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አስማለው ም ፡ አደሮች ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ሁሉ ፡ የቅዱስ ፡ ጴ ጥሮስ ፡ እንደኔ ፡ ለሚሆን ፡ ብሎ ፡ ለሮም ፡ ጳጳስ ፡ ያስገዛቸ ው ፡ የሮምንም ፡ ትምህርትና ፡ ሥርዓት ፡ በጣም ፡ ይጠብቅ ፡ ዘንድ ፡፡ ቦኒፋኪዩስም ፡ ይህነን ፡ መሐላ ፡ በችሎቱ ፡ ሁሉ ፡ ፈጸመ ፡፡ እግዚአብሔርም ፡ እንዲህ ፡ አደረገው ፡ እለዚያ ፡ አሕዛብ ፡ ወንጌልን ፡ ሲቀበሉ ፡ በፊት ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ ባርነ ት ፡ እንዲገቡ ፡ በርሱም ፡ ሊያድጉ ፡ ለወንጌል ፡ የወንጌል ፡ አርነት ፡ በጣም ፡ ሳይሆንላቸው ፡፡ ያ ፡ አመት ፡ ፯፻፴፱፤ ሳይ ጨርስ ፡ ቦኒፋኪዩስ ፡ ፲፻፷፤ የሚያህል ፡ ከንምሳዎች ፡ አጠ

መቀ ። ላደ፡ ቦች ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትም ፡ ሁሉ ፡ ቀሳውስትና ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ሜትሮጶሊታኖችም ፡ ሰጣቸው ። ጲጲንንም ፡ ንጉሥ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ቀባው ፡ ባመት ፡ ፯፻፮።
ባመትም ፡ ፯፻፸፤ ደቀ ፡ መዝሙሩን ፡ ሉል ፡ የሚሉትን ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ሁኖ ፡ በስፍራው ፡ ከቀደሰው ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ፍሪስያ ፡ አረማውያን ፡ ሔደ ፡ ከዚያ ፡ በሽምግልናው ፡ ወንጌልን ፡ ሊያስተምር ፡ ሊሞትም ፡ ብሎ ። በብዙ ፡ ስፍራም ፡ ዙሮ ፡ አያሌን ፡ ሽህ ፡ አሕዛብ ፡ አጠመቀ ፡ አያሌም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትን ፡ ተከለ ። አረማውያን ፡ ግን ፡ በዚህ ፡ ተቈጥተው ፡ ገደሉት ፡ ባመት ፡ ፯፻፸፤ ዕድሜው ፡ ፸፫፤ ዓመት ፡ ሲሆን ። ብዙ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርትም ፡ ተከተሉት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ መዝረጋት ፡ የጠበቁ ፡ እንደ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ በኡትሬኽት ፡ ስቱርምም ፡ በፉልደ ፡ ብዙ ፡ ሌሎችም ።

ከገርማኖች ፡ አሕዛብም ፡ በንምሳ ፡ ምድር ፡ የተቀመጡ ፡ አንዲት ፡ ሕዝብ ፡ ነበረች ፡ በወንጌል ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ አመት ፡ የተቃወመች ፡ እርሳቸውም ፡ ሰክሶኖች ። ታላቅ ፡ ካርልም ፡ ለሃይማኖት ፡ አገደቻቸው ፡ በጦር ። ስለዚህም ፡ አያሌ ፡ ጊዜ ፡ ካደ፡ ፡ እስከ ፡ ፲፬፤ ድረስም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በመኻከላቸው ፡ አልጸናችም ። በርሳቸውም ፡ መኻከል ፡ ከዚያ ፡ ወዲያ ፡ አያሌ ፡ ጻድቃን ፡ መምህራን ፡ አስተማሩ ፡ እንደ ፡ ልዩድገር ፡ ዊልሃድም ።

ታላቅ ፡ ከርልም ፡ አዋሮችን ፡ ካሸነፈ ፡ በኋላ ፡ እርሳቸው ፡ ደግሞ ፡ የክርስቲያንን ፡ ጥምቀትና ፡ ስም ፡ ምምህራንንም ፡ ተቀበሉ ።

እንደዚህም ፡ የመንግሥተ ፡ ሰማያት ፡ ዘር ፡ ተዘሬ ፡ በለዚያ ፡ አሕዛብ ፡ መኻከል ። በተከተለውም ፡ ዘመን ፡ ሊበቊል ፡ ፍሬውንም ፡ ሊያፍሬ ፡ ጊዜ ፡ ነበረለት ።

፮፡ በስያና ፡ ባፍሪካ ።

ባለዚያ ፡ ቦቶች ፡ አሁን ፡ ታላቅ ፡ ፍርድ ፡ ተፈረደች ፡ ከእግዚአብሔር ። ብዙ ፡ አገሮች ፡ የወንጌል ፡ ብርሃን ፡ የነበረላቸው ፡ በዚህም ፡ ብርሃን ፡ ያልተመላለሱ ፡ አሁን ፡

ብርሃናቸው ፡ ጠፍቶ ፡ ሌሊት ፡ ሆነባቸው ፡፡ የእሥላም ፡ ጨረቃ ፡ በወንጌል ፡ ፀሐይ ፡ ፊንታ ፡ አሰተኛውን ፡ ብርሃን ፡ ሰጠች ፡፡

ሙሀመድ ፡ ባመት ፡ ፮፻፲፡፡ በዐረብ ፡ ምድር ፡ ተነሣ ፡ አዲስ ፡ ሃይማኖትንም ፡ አስተማረ ፡ ካይሁድ ፡ ከክርስቲያንም ፡ ከሌላም ፡ ይልቅ ፡ ከግኖስቲኮች ፡ መጻሕፍት ፡ ተለቅሞ ፡ የተደበለቀ ፡፡ እርሱም ፡ በመጀመርያው ፡ ባረማውያን ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ ተነሣ ፡ ክርስቲያንና ፡ አይሁድ ፡ ግን ፡ እርሳቸውም ፡ ሁለታቸው ፡ ደግመው ፡ በጨለማ ፡ የኖሩ ፡ በተቃወሙበት ፡ ጊዜ ፡ በርሳቸውም ፡ ላይ ፡ ሆነ ፡፡ በትምህርቱ ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ የእግዚአብሔር ፡ ታላቅነት ፡ ከሁሉ ፡ ይበልጣል ፡፡ ቅድስናው ፡ ግን ፡ ከጽድቁ ፡ ጋራ ፡ ጸጋውም ፡ አላስተማረም ፡ አንድነትም ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በሰው ፡ መካከል ፡ ወደ ፡ ትምርቱ ፡ አልደረሰችም ፡፡ በትምርቱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ምህረት ፡ ከቅድስናው ፡ ተልይታ ፡ ድካም ፡ ትመስላለች ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ኃጢአትን ፡ አይጸላም ፡ በኃጢአተኛ ፡ ላይም ፡ አይቈጣም ፡ ሐሳዊን ፡ ነቢዩን ፡ ብቻ ፡ ቢያከብር ፡፡ ብሉይና ፡ አዲስ ፡ መጻሕፍት ፡ ረከሱ ፡ ቢል ፡ አልተቀበላቸውም ፡ የርሱ ፡ አሰት ፡ እንዲገለጽባቸው ፡ ብሎ ፡፡ የሥላሴ ፡ ትምርትስ ፡ ባገሩ ፡ በነበሩ ፡ ክርስቲያን ፡ መካከል ፡ መልካም ፡ አላስተማሩምና ፡ ጣለው ፡፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ የዘላለም ፡ መወለዱ ፡ ከአብ ፡ ባሕሪ ፡ በሰው ፡ መጠን ፡ ብቻ ፡ ፈረደበት ፡ ስድብ ፡ ቈጠረው ፡ እግዚአብሔር ፡ አልተወለደምና ፡ አይወልድም ፡ ቢል ፡፡ ኃጢአትም ፡ አልቈጠረምና ፡ ከኃጢአትም ፡ መድኃኒት ፡ አይፈልግም ፡ አለ ፡ በነቢዩም ፡ የሚያምን ፡ ሁሉ ፡ የሥጋው ፡ መመኞት ፡ ሁሉ ፡ በገነት ፡ ለዘወትርም ፡ ይጸግባል ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ቢል ፡፡ ያለ ፡ ቅድስና ፡ ማንም ፡ እግዚአብሔርን ፡ አያይም ፡፡ ሥጋና ፡ ደምም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ አይወርስም ፡፡

እንዲህ ፡ ያለች ፡ ትምህርት ፡ የሥጋ ፡ ትምህርት ፡ ሁናለችና ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ ከሥጋ ፡ ተወልድዋልና ፡ ደስ ፡ ታሰኛለች ፡ ስለዚህም ፡ ቶሎ ፡ ተዘረጋች ፡፡ ከዚህም ፡ ጋራ ፡ የጋሻ ፡ ጦር ፡ ኃ

ደል ፡ መጣ ፡ የእግዚአብሔርም ፡ ፍርድ ፡ በተጨለመች ፡ ቤቱ ፡ ላይ ፡፡ በምስርና ፡ በሶርያ ፡ የነበሩ ፡ አንድ ፡ ጠባይዕ ፡ ብቻ ፡ በክርስቶስ ፡ እንደለ ፡ ያስተማሩ ፡ ከንጉሣቸው ፡ ጋራ ፡ ተጸልተዋልና ፡ ከሙሀመድና ፡ ከወገኑ ፡ ጋራ ፡ ተገናኙ ፡፡ መንግሥትንም ፡ ወደ ፡ መግዛት ፡ ረዱት ፡፡ እንዲህም ፡ የነስቶርያኖች ፡ ወገን ፡፡ እስላሞችም ፡፡ ከሮሜ ፡ መንግሥት ፡ ታላቅ ፡ ክፍልን ፡ ወሰዱ ፡ ባፍሪቃም ፡ የነበሩትን ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ በድንገት ፡ ሻሩ ፡ ባሕርንም ፡ ተሻግረው ፡ ወደ ፡ እስጳንያ ፡ አለፉ ፡ ወሰዱትም ፡ ወደ ፡ ፈረንኮችም ፡ መንግሥት ፡ ገቡ ፡ የፍርንጆችንም ፡ ሁሉ ፡ መግዛት ፡ ሊወስዱ ፡ ነበሩ ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈረንኮችን ፡ ረዳ ፡ በካርል ፡ ማርተል ፡ እጅ ፡ ታላቅ ፡ ወጋት ፡ ሁንዋልና ፡ በጦዋቴ ፡ በርሁም ፡ ካርል ፡ ማርተል ፡ የስላሞችን ፡ አለቃ ፡ ዓብዱ ፡ ረኽማንን ፡ ገደለ ፡ የስላሞችንም ፡ ኃይል ፡ በምዕራብ ፡ አፈረሰ ፡ ባመት ፡ ፯፴፪፡፡

በፈርስና ፡ በህንድ ፡ ምድርም ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ሃይማኖት ፡ ተዘረጋች ፡ በተሳደዱ ፡ በነስቶርያኖች ፡ እጅ ፡፡

ደግሞም ፡ በኑቢያ ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ የክርስቲያን ፡ መንግሥት ፡ ሆነች ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ በስላሞች ፡ ፈረሰች ፡፡

ሁለተኛ ፡ ምዕራፍ ፡

የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሥርዓትዋ ፡ ታሪክ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡፡

፩፤ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መገናኘት ፡ ከመንግሥት ፡ ጋራ ፡፡

በገርማኖች ፡ አሕዛብ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ሃይማኖትን ፡ በተቀበሉ ፡ መኻከል ፡ ሥርዓት ፡ አልተደረገችምና ፡ እርሳቸው ፡ ከሮም ፡ የወጣችን ፡ ሥርዓት ፡ ሊቀበሉ ፡ ነበረ ፡፡ የፍረንኮችና ፡ የሌሎች ፡ ገርማኖች ፡ ነገሥታት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መግዛት ፡ ፈለጉ ፡ ከሆነላቸውም ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እጅግ ፡ ክፉ ፡ በሆነ ፡፡ አንደንድ ፡ ጊዜ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ገንዘብ ፡ ወሰዱ ፡ ቀሳውስትንና ፡ ኤጲስቆጶሳትንም ፡ ሲሾሙ ፡ ባለምዋሎቻቸውን ፡ ሾሙ ፡ ትምርትን ፡ ያላወቁትን ፡ በኃጢአትም ፡ የኖሩትን ፡፡ ወይስ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ሹመት ፡ ሼጡ ፡ እጅግ ፡ ዋጋውን ፡ ለሰጠ ፡፡ እንዲህም ፡ የተሾመ ፡ የንጉሥ ፡ ሎሌ ፡ ሆነ ፡ እንደ ፡ ንጉሥም ፡ ፍርድ ፡ ሊያስተምር ፡ ነበረ ፡ እጅግ ፡ ግዜ ፡ ከክርስቶስ ፡ ፍቃድ ፡ የተለየ ፡፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ሲኖደች ፡ ከጳጳስ ፡ ጋራ ፡ ስለዚህ ፡ ተጋደሉ ፡ በመጋደላቸውም ፡ እንደህ ፡ ሆነ ፡ መግዛት ፡ ሁሉ ፡ በጊዜው ፡ ለጳጳሳት ፡ እንደሆነ ፡፡ ያም ፡ ደግሞ ፡ እጅግ ፡ ክፉት ፡ ያመጣ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መኻከል ፡፡

ሲኖደስም ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ አልተሰበሰበችም ፡ በንጉሥ ፡ ፈቃድ ፡ እንጂ ፡፡ በርስዋም ፡ የተቈረጠ ፡ ፈቃድ ፡ ሁሉ ፡ በንጉሥ ፡ ሥልጣን ፡ ታወቀ ፡፡ በኋላም ፡ ሲኖደች ፡ ከመንግሥት ፡ ጉባኤዮች ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ሆኑ ፡፡ ያገርም ፡ ሹማምትና ፡ ታላቆች ፡ ባንድ ፡ ተሰበሰቡ ፡ ከቀሳውስትና ፡ ከኤጲስቆጶሳት ፡ ጋራ ፡ የመንግሥትና ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ምክር ፡ ባንድ ፡ ተማከሩ ፡፡

፪፡፡ የቤት ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዓት ፡ በውሥጥዋ ።

በዚህ ፡ ዘመን ፡ የሞናክሮች ፡ ክብር ፡ በዛ ። በታላቆች ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትም ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ከቀሳውስታቸው ፡ ጋራ ፡ የመጽ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ኽሮድጋንግ ፡ የሚሉት ፡ ሥርዓት ፡ አደረጉላቸው ፡ እንደ ፡ ሞናኵስት ፡ ባንድ ፡ ደናሩ ፡ ዘንድ ። ይህችም ፡ ሥርዓት ፡ ቃኖን ፡ ተባለች ።

በ፪፡ ሲኖደችም ፡ ሥርዓት ፡ አደረጉ ፡ ለኤጲስቆጶሳት ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ሁሉ ፡ መንደሩን ፡ ሁሉን ፡ ይጐብኝ ፡ ዘንድ ፡ ቀሳውስትንና ፡ ሕዝብን ፡ ይመረምር ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ስለ ፡ ትምህርትም ፡ ስለ ፡ አካሔድም ።

በፍረንኮችም ፡ አገር ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ሁሉ ፡ ባገሩ ፡ ሁሉ ፡ በያመት ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ፍርድ ፡ ሊያደርግ ፡ ነበር ፡ በቤት ፡ ክርስቲያን ።

በዚህ ፡ ዘመንም ፡ የሮም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ኃይል ፡ እጅግ ፡ በዛች ፡ በታላቁ ፡ ጎርጎርዩስ ። እርሱም ፡ የቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ በሹመቱ ፡ ተከታይ ፡ ነኝና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉን ፡ አጠብቅ ፡ ዘንድ ፡ ይገባኛል ፡ አለ ። የርሱም ፡ ኃይል ፡ ታላቅ ፡ ነበረች ፡ እጅግም ፡ ሆነች ፡ በምግባሩ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ። ከዚህም ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ፡ እርሱ ፡ የራሱን ፡ ክብር ፡ እንዳይፈልግ ፡ መሰለው ። ለራሱ ፡ ትሑት ፡ ሁኖ ፡ መሰለ ፡ የሚፈልገውን ፡ ክብር ፡ ለቅዱስ ፡ ጴጥሮስና ፡ ለሹመቱ ፡ ፈለገ ፡ እንጂ ፡ ብሎ ። የስክንድርያ ፡ ጳጳስ ፡ ኤውሎግዮስ ፡ ጎርጎርዮስን ፡ ያለም ፡ ሁሉ ፡ ጳጳስ ፡ ሲለው ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ከለከለው ፡ እንደህ ፡ ሲል ። እኔ ፡ ማን ፡ እንድሆን ፡ አውቃለሁ ፡ አንተም ። አንተም ፡ በሹመትህ ፡ ወንድሜ ፡ ነህ ። በቅድስናህ ፡ ግን ፡ አባቴ ፡ ነህ ።

ከዮሐንስ ፡ ጻዋሚ ፡ ከቆንስታንቲኒያ ፡ ጳጳስ ፡ ጋራ ፡ እጅግ ፡ ተጸላ ፡ ያ ፡ ራሱን ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ኦይኩሜኒኮስ ፡ ብልዋልና ። ይህም ፡ ክርክር ፡ ያለ ፡ ቅናት ፡ አልነበረም ።

ባመትም ፡ ፮፻፯፡ የሮም ፡ ጳጳስ ፡ ምድራዊ ፡ ሹም ፡ ሆነ ፡ ጳጳን ፡ የሮምን ፡ ምድር ፡ ከሎንጎባርደች ፡ እጅ ፡ በወሰደ ፡ ጊዜ ፡ ለቅዱስ ፡ ጴጥሮስም ፡ በሰጣት ፡ ጊዜ ። ከዚያም ፡ ዘ

መን : ጀምረው : በቁም : ነገር : አሉ : እለዚያ : ጳጳሳት : እርሳቸው : በጴጥሮስ : ፈንታ : የቤተ : ክርስቲያን : ሁሉ : ራስ : እንዲሆኑ :: በሰው : ፍርድም : በታች : እንዲደደ ሉ : መንፈሳዊት : ሥልጣንም : ሁሉ : ከርሳቸው : ዘንድ : እንድትሆን ::

ሶስተኛ ፡ ምዕራፍ ፡፡

ስለ ፡ ክርስቲያን ፡ ሕይወት ፡ ስለ ፡ ክርስቲያንም ፡ ማምለክ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡፡

በዚህ ፡ ዘመን ፡ ሃይማኖትን ፡ በተቀበሉ ፡ በገርማኖች ፡ አሕዛብ ፡ የሃይማኖት ፡ ኃይል ፡ እጅግ ፡ አልተገለጸችም ፡፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ በጥቂት ፡ ሰዎች ፡ እጅ ፡ ብቻ ፡ ኑር ዋልና ፡ ከሰው ፡ ቃልም ፡ ጋራ ፡ እጅግ ፡ ተደበለቀ ፡፡ በታላቅ ፡ ካርልም ፡ ዘመን ፡ ጥቂት ፡ የተሻለ ፡ ሆነ ፡ እርሱ ፡ በዚህ ፡ በውነት ፡ ታላቅ ፡ ነበረና ፡ ስለ ፡ ሕዝቡ ፡ እጅግ ፡ አስብ ዋልና ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ ይማሩ ፡ ዘንድ ፡፡ አያሌም ፡ መምህራን ፡ ነበሩለት ፡ እጅግ ፡ የሰሩ ፡ የደከሙም ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡፡ ከሌላ ፡ ይልቅም ፡ አልኩን ፡፡ አልኩን ፡ ወደ ፡ ከንትርብሪ ፡ ጉባኤ ፡ በጻፈው ፡ መልእክቱ ፡ አላቸው ፡፡ የእግዚአብሔር ፡ ዕውቀት ፡ አይገኝም ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ እንጂ ፡፡ ዕውር ፡ ግን ፡ ዕውርን ፡ ቢመራ ፡ ሁላታቸው ፡ ወደ ፡ ጉድጓድ ፡ ይወድቃሉ ፡፡ ደር ፡ የጠቢባን ፡ ብዛት ፡ የሕዝብ ፡ ደህንነት ፡ ነው ፡፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ መምህራን ፡ ውሰዱላችሁ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንዳያልቅባችሁ ፡ የሕዝብም ፡ መሮች ፡ እንዳይጉድሉ ፡ የውነትም ፡ ምንጭ ፡ እንዳይደርቅ ፡፡ በማይንዝም ፡ በተሰበሰቦች ፡ ሲኖደስ ፡ ሥርዓትን ፡ አደረጉ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወይስ ፡ ቄስ ፡ ወይስ ፡ ሌላ ፡ ቢሆን ፡ በየእሁድ ፡ በየበዓልም ፡ ለሕዝቡ ፡ ይሰብክ ፡ ዘንድ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ እንዲያስታውሉት ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ በነ ፡ ቀሳውስት ፡ ጥቂት ፡ ነበሩ ፡ የተማሩ ፡ ማስተማርም ፡ የተቻላቸው ፡፡

በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ስብከት ፡ ባገር ፡ ቋንቋ ፡ ሁኖ ፡ ጸሎትና ፡ ዝማሬ ፡ በላቲን ፡ ቋንቋ ፡ ነበረ ፡፡ መዝመርንም ፡ በፍረንኮች ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ እጅግ ፡ ተማሩ ፡፡ ቆንስታንቲኖስ ፡ ቆጵሮኒሞስም ፡ ለጲጲን ፡ ለንጉሥ ፡ ኦርጋኖንን ፡ ለሙሲካ ፡ ሰድዋልና ፡ ዝማሬ ፡ በኦርጋኖን ፡ ተደረገ ፡ ማምለክም ፡ በርሱ ፡ እጅግ ፡ ያማረ ፡ ሆነ ፡፡

የሳተችም ፡ ሃይማኖት ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ እጅግ ፡ በዛች ፡

ሰው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ሳያውቅ ፡ ሳይመረምርም ፡ መታመኑን ፡ በፍጥረት ፡ አድርጓልና ፡፡ በእግዚአብሔር ም ፡ ያላመኑ ፡ ድንቅን ፡ ታአምራትን ፡ ሳያዩ ፡ ብዙ ፡ ነበሩ ፡፡ ስለዚህም ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ተሳቱ ፡ ድንቅን ፡ ማየት ፡ ሲፈልጉ ፡ ሐሰተኛ ፡ ድንቅን ፡ አዩ ፡ በወንጌልም ፡ የተገኘውን ፡ ድንቅ ፡ አላሰቡም ፡ ከኀጢአት ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ መለወጥ ፡ አልሆነላቸውምና ፡፡

እንደህም ፡ በምግባር ፡ መታመን ፡ በዛ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ እርሱም ፡ የሥጋ ፡ ስራ ፡ ማድረግ ፡ ከቶ ፡ የማይጠቅም ፡ ሰው ፡ በበጎ ፡ ልብ ፡ ባያደርገው ፡ እንደ ፡ ምጽዋት ፡ ለቤት ፡ ክርስቲያንም ፡ መስጠት ፡፡ ወደ ፡ የሩሳሌምም ፡ ወደ ፡ ሮምያም ፡ ወደ ፡ ሌላም ፡ ቅድስት ፡ ወደ ፡ ተባለች ፡ አገር ፡ መሔድ ፡፡ እጅግ ፡ ሰዎች ፡ ከቀሳውስትና ፡ ከሕዝብ ፡ ይህነን ፡ ሲያደርጉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ተጸደቁ ፡ ያመኑ ፡ ሕያውትን ፡ ሃይማኖት ፡ በክርስቶስ ፡ አያውቁም ፡ ነበሩና ፡፡

ቅዱሳንንና ፡ ማርያም ፡ ድንግልን ፡ ማክበር ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ በዝቶ ፡ በቤት ፡ ክርስቲያን ፡ የጣዖታት ፡ ማምለክ ፡ ተነሣ ፡፡ ጥቂት ፡ ሰዎች ፡ ብቻ ፡ ተገኙ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ያሰቡ ፡ ልባቸውንም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ብቻ ፡ ያኖሩ ፡፡ ባሕርያቸውም ፡ ወትሮ ፡ በኃጢአት ፡ ሲኖር ፡ መከራ ፡ በመጣ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ቅዱሳን ፡ ጸሩ ፡ ወደ ፡ መቃበራቸውም ፡ ሔዱ ፡ ለሥእላቸውም ፡ ሰገዱ ፡፡

በዚህ ፡ ዘመንም ፡ አያሌን ፡ አዲሶችን ፡ በዓላት ፡ ቀደሱ ፡፡ እርሳቸውም ፡ ፪፤ የማርያም ፡ በዓላት ፡ የመንጻትዋ ፡ በዓልና ፡ የዐርገትዋ ፡ በዓል ፡፡ ደግሞም ፡ የክርስቶስ ፡ ግዝረት ፡ በዓል ፡ ፰፤ ቀን ፡ ከልደቱ ፡ በኋላ ፡ በሮምም ፡ ያመት ፡ መጀመርያ ፡፡ ደግሞም ፡ የቅዱስ ፡ ሚካኤል ፡፡ ደግሞም ፡ የጴጥሮስና ፡ የጳውሎስ ፡ የሞታቸው ፡ በዓል ፡ የዮሐንስ ፡ ምጥመቅም ፡ የልደቱ ፡ በዓል ፡፡ ያንድርያስም ፡ የርሚግዩስም ፡ የማርቲኑስም ፡ በዓላት ፡፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ ቅዱሳንም ፡ በየሞቱበት ፡ አገር ፡ በዓል ፡ አደረጉላቸው ፡፡ አንድ ፡ በዓልም ፡ አደረጉ ፡ ለቅዱሳን ፡ ሁሉ ፡ ፩፤ ሳምንት ፡ ከጰራቅሊጦስ ፡ በዓል ፡ በኋላ ፡፡

ስለ ፡ ቍርባንም ፡ መሥጢር ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ በምዕራብ ፡ ያች ፡ ትምህርት ፡ ጸናች ፡ ቍርባን ፡ መሥዋዕት ፡ እንደ ሆነ ፡ የክርስቶስ ፡ ሞትና ፡ መሥዋዕቱ ፡ በመስቀል ፡ በቄስ ፡ እጅ ፡ የሚደገምበት ፡፡ እንደ ህም ፡ የወንጌል ፡ ትምህርት ፡ ስለ ፡ ቍርባን ፡ በዝታ ፡ ተጐዳች ፡፡ ቍርባንንም ፡ ስለ ፡ ሙታን ፡ ሠው ፡ በዚህ ፡ ዓለም ፡ በውነተኛ ፡ ሃይማኖት ፡ በ ክርስቶስ ፡ ከገሃናም ፡ እሳት ፡ ያልሸሹ ፡ ከሞታቸው ፡ በኋላ ፡ በቄስ ፡ ኃይል ፡ በመሥዋዕቱም ፡ ከዚያ ፡ እሳት ፡ ያወጡ ፡ ዘንድ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ሲል ፡ ያ ፡ እሳት ፡ እንደ ይጠፋ ፡፡ በዚህ ፡ በሰው ፡ ከንቱ ፡ ትምህርትና ፡ ማድረግ ፡ የ ክርስቶስ ፡ የዘላለም ፡ ቃሉ ፡ ባገልጋዮቹ ፡ ተሻረ ፡ እርሱ ፡ ሲል ፡፡ ሁለተኛ ፡ ያልተወለደ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መንግሥት ፡ እንደያይ ፡፡ ያባቱንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፈቃድ ፡ የማያደርግ ፡ ክርስቶስ ፡ በፍርድ ፡ ቀን ፡ የርሱ ፡ ገንዘብ ፡ ሁኖ ፡ እንደያውቀው ፡፡ በክርስቶስ ፡ ቃልም ፡ የተ ጨነቀ ፡ መንገድ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ የሚወስድ ፡ ሰፊ ፡ ሆነ ፡፡ የ ዚያን ፡ ጊዜም ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በዕድሜያቸው ፡ ሁሉ ፡ ል ባቸውን ፡ ላለምና ፡ ለሰይጣን ፡ ይሰጡ ፡ የነበሩ ፡ በሞቱ ፡ ጊዜ ፡ ከብታቸውን ፡ ለቄስ ፡ ለሰማይ ፡ ሸያጭ ፡ ሰጡት ፡ መ ግባትን ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ የገዙበት ፡ ሲመስላቸው ፡፡

የቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ተግሣጽ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ከፋ ች ፡፡ ለተገዘቱ ፡ ሰዎች ፡ የተደረገ ፡ ንስሐ ፡ የልብ ፡ መመለስ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ አልነበረም ፡ ጾምና ፡ ምጽዋት ፡ እን ጅ ፡፡ እርሱ ፡ ጽድቅ ፡ ሁኖ ፡ ተቈጥርዋልና ፡፡ በፍርዳቸው ም ፡ ልማድ ፡ ነበረና ፡ የበደለ ፡ ሰው ፡ የሰረቀ ፡ ወይስ ፡ የገ ደለ ፡ በመበደሉ ፡ ፈንታ ፡ ወርቅ ፡ ሲሰጥ ፡ ተፈታ ፡፡ ይህ ፡ ል ማድ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ገብቶ ፡ ሰው ፡ ከመገዘቱ ፡ ፍት ሐትን ፡ በወርቅ ፡ ገዛ ፡፡ ይህነን ፡ ትምርት ፡ ግን ፡ የዚያን ፡ ጊ ዜ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ገና ፡ አልተቀበሉም ፡ አያሌ ፡ ሲኖዶች ፡ ገሠጹት ፡ እንጅ ፡ ከለከሉትም ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ነበሩ ፡ ከቀሳውስትና ፡ ከሕዝብ ፡ በዚህ ፡ ስሕተት ፡ የኖሩ ፡ በሚመ ጣም ፡ ዘመን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይህነን ፡ ስሕተት ፡ በግል ጽ ፡ ተቀበለችው ፡ እንደ ፡ እውነት ፡ ትእዛዝም ፡ አደረ ገቸው ፡፡

አራተኛ ፡ ምዕራፍ ፡፡

የክርስቲያን ፡ ትምህርት ፡ ታሪክ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡፡

፩፤ በምዕራብ ፡፡

አንድ ፡ ከታላቆች ፡ መምህራን ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ታላቅ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ የሮም ፡ ጳጳስ ፡ ነበረ ፡፡ እርሱም ፡ በሮም ፡ ተወለደ ፡ ባመት ፡ ፭፻፵፤ ወይስ ፡ ፭፻፶፤ ከታላቅ ፡ ዘመድም ፡ ነበረ ፡ አያሌ ፡ አመትም ፡ ከቄሣር ፡ የተሾመ ፡ ሆነ ፡ በሮም ፡ ላይ ፡፡ ዕድሜው ፡ ግን ፡ ፴፤ አምት ፡ ሲሆን ፡ ሞናክሴ ፡ ሆነ ፡ ፮፤ ገደሞችንም ፡ ተከለ ፡ ባንዲቱም ፡ እርሱ ፡ ገባ ፡ በኋላም ፡ መምህርዋ ፡ ሆነ ፡፡ ጳጳስ ፡ ጶላግዩስ ፡ ግን ፡ ከገደም ፡ ወስደት ፡ ዲያቆኑ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ቀደሰው ፡፡ በኋላም ፡ መልክተኛውን ፡ አደረገው ፡ ወደ ፡ ቆንስታንቲኒያ ፡ በቄሣር ፡ ዘንድ ፡ ሊኖር ፡ በርሱ ፡ ፈንታ ፡፡ ጶላግዩስም ፡ ባመት ፡ ፭፻፹፱፤ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ በርሱ ፡ ስፍራ ፡ ጳጳስ ፡ ሆነ ፡፡ ከዚያም ፡ ጀምሮ ፡ እጅግ ፡ ሰራ ፡ ስለ ፡ ትምህርትና ፡ ስለ ፡ ሥርዓት ፡ ከሁሉም ፡ ይልቅ ፡ ስብከትን ፡ ወደደ ፡፡ ይህ ፡ የቄስና ፡ የኤጲስቆጶስ ፡ ተላቅ ፡ ተግባር ፡ ሁኖ ፡ ቈጠረው ፡ በግልጽ ፡ በስብከት ፡ ጉባኤን ፡ ያስተምር ፡ ዘንድ ፡ ስውንም ፡ ሁሉን ፡ ለብቻው ፡ በመጫወት ፡ ይመክር ፡ ዘንድ ፡፡ መጽሐፍን ፡ ጻፈ ፡ ለክህነት ፡ ሁሉ ፡ የጠባቂ ፡ ቃኖን ፡ የተባለ ፡፡ በርሱም ፡ ይናገራል ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጠባቂ ፡ ሁሉ ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፡ ስለሚገባው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡፡

የጎርጎርዮስ ፡ ትምርት ፡ ያውጉስቲኑስን ፡ ትምርት ፡ መሰለች ፡ ካውጉስቲኑስ ፡ መጻሕፍት ፡ ይቀዳ ፡ ነበረና ፡፡ ጎርጎርዮስ ፡ ባመት ፡ ፮፻፬፤ ሞተ ፡፡

ሌላ ፡ ታላቅ ፡ መምህርም ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ኢሲደሩስ ፡ ከሴዊልያ ፡ ነበረ ፡ እጅግ ፡ መጻሕፍትን ፡ የጻፈ ፡፡ እርሱ ፡ ደግሞ ፡ ያውጉስቲኑስን ፡ ትምህርት ፡ ተከተለ ፡፡

በእንግሊጣርና ፡ በኢርላንድ ፡ የመጽሐፍ ፡ መውደድ ፡ ታላቅ ፡ ነበረ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡፡ አንድ ፡ ታላቅ ፡ መምህር ፡ በ

እንግልጣር ፡ ቢደ ፡ ነበረ ፡ ባመት ፡ ፯፻፫፤ የተወለደ ፡ ባመ ትም ፡ ፯፻፴፭፤ የሞተ ፡፡ እርሱም ፡ ሞተ ፡ በምስጋና ፡ ሲዘ ምር ፡፡ ምስጋና ፡ ይሁን ፡ ለአብና ፡ ለልጅ ፡ ለመንፈስ ፡ ቅ ዱስም ፡፡

ቢደም ፡ በሞተ ፡ አመት ፡ ፯፻፴፭፤ ከርሶ ፡ የሚበልጥ ፡ መ ምህር ፡ ተወለደ ፡ እርሱም ፡ አልኩን ፡፡ ቄሣር ፡ ካርል ፡ በ መንግሥቱ ፡ ሁሉ ፡ የመምህራኑን ፡ አለማውቅ ፡ ሊሽር ፡ ዕ ውቀትንም ፡ ሊያበዛ ፡ ፈለገ ፡፡ ስለዚህም ፡ አዋቆች ፡ መ ምህራኑን ፡ ወደርሶ ፡ ሰበሰበ ፡ በርሳቸውም ፡ መኻከል ፡ አ ልኩን ፡ በለጠ ፡፡ ካርልም ፡ ባለቤቱ ፡ ከርሶ ፡ ተማረ ፡፡ በክ ርስቶስም ፡ እጅግ ፡ የተወደድህ ፡ መምህሬ ፡ አለው ፡፡ አል ኩንም ፡ እጅግ ፡ ከሰራ ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ ትምህርት ፡ ስለ ፡ ማስተማርም ፡ ባመት ፡ ፰፻፬፤ ሞተ ፡ በጰራቅሊጦስ ፡ በዓል ፡፡

በዚህ ፡ ዘመንም ፡ ክርክር ፡ ተነሣ ፡ በስጳንያ ፡ ስለ ፡ ክ ርስቶስ ፡፡ ይህም ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ መለኮት ፡ ነበረ ፡፡ ፪፤ መምህራን ፡ ነበሩ ፡ በስጳንያ ፡ የቶሌደ ፡ ሜትሮጶሊታ ን ፡ ኤሊጳንዱስ ፡ የተባለ ፡ የውርጌሊስ ፡ ኤጲስቆጶስም ፡ ፌ ሊክስ ፡ የሚሉት ፡ እንደህ ፡ ያሉ ፡፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሰ ውነቱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ እንደ ሆን ፡ በመቀበል ፡ ነ ው ፡ በመወለድ ፡ አይደለም ፡፡ በመለኮቱ ፡ ግን ፡ የእግዚአ ብሔር ፡ ልጅ ፡ ነው ፡ በዘላለም ፡ መወለዱ ፡ ከአብ ፡ ባሕሪ ፡፡ እንደህም ፡ ክርስቶስ ፡ በመለኮቱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ የባ ሕሪ ፡ ልጅ ፡ ሁኖ ፡ በሰውነቱም ፡ የጸጋ ፡ ልጅ ፡ አስተማሩ ፡፡

ከዚህ ፡ ትምርትም ፡ ጋራ ፡ የቴዎደርስን ፡ ትምርት ፡ ከመ ሰለች ፡ ከስላሞችም ፡ ጋራ ፡ በመጋደል ፡ ከተነሣች ፡ ፪፤ ሰዎ ች ፡ ተከራከሩ ፡ በስጳንያ ፡፡ አንድ ፡ ቄስ ፡ ቤያቱስ ፡ የሚሉ ት ፡ አንድም ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ኤቴርዩስ ፡ የሚሉት ፡፡

የፌሊክስ ፡ ትምህርትም ፡ ተወገዘች ፡ ፌሊክስም ፡ አዝ ኖ ፡ ካደ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ክደቱን ፡ ደገሞ ፡ ሻረ ፡፡ ከዚያም ፡ ወ ዲያ ፡ አልኩን ፡ በአኸን ፡ በተሰበሰበች ፡ ሲኖደስ ፡ በግል

ጵ ፡ ከፌሊክስ ፡ ጋራ ፡ ተምዋገተ ። ፌሊክስም ፡ የቤተ ፡ ክ
ርስቲያንን ፡ ትምርት ፡ ተቀበለ ፡ በአንድነታቸውም ፡ ኖረ ።

፪፤ በምሥራቅ ፡ በነበረች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

ካመተ ፡ ፯፻፤ በኋላ ፡ ዮሐንስ ፡ የደመስቀ ፡ ሞናክሴ፡ መጽሐፍን ፡ ጻፈ ፡ የኦርቶደክሳዊት ፡ ሃይማኖት ፡ ትምህርት ፡ የተባለ ። በርሱም ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ትምርት ፡ ከታላቆች ፡ መምህራን ፡ ተለቀመች ።

የምሥራቅ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ትምህርትዋ ፡ እጅግ ፡ አስተማርዋተ ፡ በገደሞች ። የአርዮስፋጎስ ፡ የሚሉት ፡ የዲዮናስዮስን ፡ መጻሕፍት ፡ ካራት ፡ መቶ ፡ አመት ፡ በኋላ ፡ የተጻፈ ፡ እጅግ ፡ ተማረ ፡ ያንድ ፡ ጠባይዕ ፡ ወገንም ፡ ምስክር ፡ ሁነው ፡ ቍጠርዋቸው ፡ ጸላቶቻቸው ፡ ግን ፡ አልተቀበልዋቸውም ፡ አታናስዮስና ፡ ቄርሎስ ፡ እለዚያን ፡ መጻሕፍት ፡ በየዘመናቸው ፡ አላወቁምና፡ በኋላቸው ፡ ተጻፉ ።

አንድ ፡ እጅግ ፡ የተማረ ፡ ሰው ፡ ባለ ፡ ማሰብም ፡ መክሲሙስ ፡ ነበረ ፡ ከ፮፻፤ አመት ፡ በኋላ ፡ የነበረ ፡ በፊትም ፡ የቄሣር ፡ መጀመርያ ፡ ጻፊ ፡ በኋላም ፡ ሞናክሴ ፡ የሆነ ፡ የኒሳም ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ያሰተኛ ፡ ዲዮናስዮስም ፡ መጻሕፍት ፡ ከሌላ ፡ ይልቅ ፡ የተማረ ።

ሁለት ፡ ታላቅ ፡ ክርክሮች ፡ ነበሩ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ በምሥራቅ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ። አንድ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ፈቃድ ፡ ሁለተኛም ፡ ሥእልን ፡ ስለ ፡ ማክበር ።

ቄሣር ፡ ሄራቅልዮስ ፡ ከፋርስ ፡ ጋራ ፡ በወጋ ፡ ጊዜ ፡ ከብዙ ፡ መምህራን ፡ ጋራ ፡ ተገናኘ ፡ አንድ ፡ ጠባይዕ ፡ ያስተማሩት ፡ በክርስቶስ ። ከርሳቸውም ፡ ጋራ ፡ ሲከራከር ፡ አሰበ ፡ ስለዚህ ፡ ያለ ፡ ክርክር ፡ ሁሉ ፡ ምናልባት ፡ እንዲጨርስ ፡ መምህራን ፡ ቢያስተምሩ ፡ አንዲት ፡ ኋይል ፡ እንደለ ፡ በክርስቶስ ፡ በመለኮቱና ፡ በሰውነቱ ፡ አንድ ፡ የሆነች ። የቍንስታንቲኒያን ፡ ጳትርያርክ ፡ ሰርግዩስን ፡ ስለዚህ ፡ በጠየቀ ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ ደግሞ ፡ ይህ ፡ መልካም ፡ እንዲሆን ፡ መሰለው ፡ ስለዚህም ፡ ሄራክልዩስ ፡ በማሰቡ ፡ ጸና ። አንድ ፡ ኤጲስቆጶስ

ም ፡ ቂሮስ ፡ ከፋሲስ ፡ እርሱ ፡ ደግሞ ፡ ይህነን ፡ ነገር ፡ ሲቀበል ፡ የስክንድርያ ፡ ጳትርያርክ ፡ ሆነ ፡ ባመት ፡ ፯፻ ፡፡ በርሱም ፡ ስራ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በምስር ፡ ያንድ ፡ ጠባይዕ ፡ በክርስቶስ ፡ ያስተማሩ ፡ ከቀረች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጋራ ፡ አንድነት ፡ አደረጉ ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ሶፍሮንዮስ ፡ የየሩሳሌም ፡ ጳትርያርክ ፡ ወደ ፡ እስክንድርያ ፡ መጥቶ ፡ የ፪ ጠባያትንም ፡ ትምርት ፡ አጽንቶ ፡ ባደስ ፡ ትምርት ፡ ተከራከረ ፡፡ ሰርግዩስ ፡ ግን ፡ ሁለታቸውን ፡ ዝምን ፡ ማለት ፡ መከራቸው ፡፡ ሰርግዩስም ፡ ከሮም ፡ ጳጳስ ፡ ጋራ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ አንድነት ፡ አደረገ ፡፡ እሌህም ፡ ፪ ወደዱ ፡ ሰው ፡ ያስተምር ፡ ዘንድ ፡ አንድ ፡ ክርስቶስ ፡ በ፪ ጠባያቱ ፡ መጠን ፡ ያምላካዊንና ፡ የሰውን ፡ ስራ ፡ እንዲያደርግ ፡፡ በኋላም ፡ ቄሣር ፡ ትእዛዝን ፡ ሰጠ ፡ የሃይማኖት ፡ ትምርት ፡ የተባለ ፡ በርሱም ፡ ሰውን ፡ ሁሉን ፡ ስለ ፡ አንድም ፡ ስለ ፡ ሁለትም ፡ ኃይል ፡ ከመናገር ፡ ከለከለ ፡፡ አሁንም ፡ ፪ ሰዎች ፡ መምህራን ፡ እጅግ ፡ ተጋደሉ ፡ ስለ ፡ ኢያትምህርታቸው ፡ አንድም ፡ መክሲሙስ ፡ ስለ ፡ ፪ ኃይልና ፡ ፈቃድ ፡ በክርስቶስ ፡ ቴዎድሮስም ፡ ከፋራን ፡ ስለ ፡ ፩ ኃይልና ፡ ፈቃድ ፡፡

ቴዎድሮስም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡፡ በክርስቶስ ፡ ሁሉን ፡ የፈቀደ ፡ ፈቃድ ፡ ያምላክ ፡ የቃል ፡ ፈቃድ ፡ ነበረ ፡ እርሱም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ለወትሮ ፡ የሰውን ፡ ጠባይዕ ፡ የተቀበለ ፡ ሰውም ፡ የሆነ ፡፡ መክሲሙስ ፡ ግን ፡ አለ ፡፡ ክርስቶስ ፡ እኛን ፡ ለማዳን ፡ በሰውነቱ ፡ ሁለንትና ፡ እንደኛ ፡ ሆነ ፡ አንዳች ፡ ሳይቀር ፡፡ የኛን ፡ ፈቃድ ፡ የኛንም ፡ ኃይል ፡ ተቀበለ ፡ ከኃጢአት ፡ በቀር ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ እንደለ ፡፡ ባካሉ ፡ አንድነት ፡ የሚሰራ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ነው ፡ ብሎ ፡፡ ከሆኖርዩስም ፡ በኋላ ፡ የተከተሉ ፡ የሮም ፡ ጳጳሳት ፡ እንደ ፡ መክሲሙስ ፡ አሉ ፡፡ እንዲሁም ፡ ያፍሪቃ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡፡

ባመትም ፡ ፯፻፰ ቄሣር ፡ ቆንስታንስ ፡ ሁለተኛ ፡ ትእዛዝ ፡ ስለዚህ ፡ ክርክር ፡ ሰጠ ፡ የሃይማኖት ፡ ምሳሌ ፡ የሚለው ፡፡ በርሱም ፡ ክርክር ፡ ሁሉ ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ተከለከለ ፡

የሚከራከርበትም : ሁሉ : ሹመቱ : ደኻር : ዘንድ : ተቀየ መበት :: ደግ : የቤተ : ክርስቲያን : ዕርቅና : ሰላም : በሰ ው : ኃይል : አይደረግም : በእግዚአብሔር : መንፈስ : ብ ቻ : እንጂ :: የሮም : ጳጳስ : ማርቲኑስ : የ፬ ፈቃድን : ት ምህርት : ያስተማሩ : ቤተ : ክርስቲያንንም : ሁሉን : ሊ ጠብቅ : ብሎ : በሮም : ሲኖደስን : ሰበሰበ : ፳ ቀኖኖች : የ ተደረጉባት : በጸላቶቹ : ላይ : ያንድ : ፈቃድንም : ትምህ ርት : ያስተማሩ : በዚህ : ተወገዙ :: ይህነንም : ነገር : ማር ቲኑስ : ለቆንስታንስ : ሰደደ :: የዚያን : ጊዜም : ማርቲኑ ስ : ወደጅነት : እንደደረገ : ካንድ : ዓመፀኛ : ጋራ : አሉ :: ስለዚህም : ታሞ : ሲሆን : ታሠረ : ወደ : ናክሶስ : ደሴት ም : ወሰዱት : እጅግ : ግፍም : አደረጉበት :: በኋላም : ወ ደ : ቆንስታንቲኒያ : ወሰዱት : በግፍም : ከፈረዱበት : በኋ ላ : ወደ : ኬርሶን : በሞስቆው : ምድር : ነተቱት : ከዚያ ም : እጅግ : መከራ : በትዕግሥት : ከተቀበለ : በኋላ : ሞ ተ :: መክሲሙስን : ደግሞ : አሠሩት : ወደ : ቆንስታንቲኒ ያም : ወሰዱት : ከዚያም : ትምህርቱን : ሳይለውጥ : ወ ደ : ቢዚያ : በትራክያ : ወሰዱት : ባመትም : ፯፳፬ መልሰ ው : ወደ : ቆንስታንቲኒያ : ጉተቱት : እጅግ : መከራም : ጨመሩበት : በርሱም : ሞተ ::

አሁንም : በግድ : አንድነት : አልሆነችም : መለየት : እን ጂ :: ከአዴዎደቱስ : ጀምሮ : የሮም : ቤተ : ክርስቲያ ን : ተለየች : ከምሥራቅ : ቤተ : ክርስቲያን :: ስለዚ ህም : ቆንስታንቲኖስ : ጶጎናቶስ : ቄሣር : ሲኖደስን : ኦይኩ ሜኒኬን : ሰበሰበ : በቆንስታንቲኒያ : በርስዋም : የ፪ ፈ ቃድ : ትምህርት : አሸነፈች :: በ፪ በተከተልዋትም : ሲኖ ደች : ጸናች ::

ባመት : ፯፲፩ ግን : አንድ : ዓመፀኛ : ፊሊጲኮስ : ሁለተ ኛውን : ዩስቲኒያኑስን : ገድሎት : መንግሥትን : ወሰደ :: እርሱም : ፩ ፈቃድ : በክርስቶስ : አምኖ : እልያ : ሲኖደ ች : ያጸንዋትን : ትምህርት : አፈረሰ :: እርሱ : ግን : ፪ አ መት : ብቻ : ከነገሠ : በኋላ : ሁለተኛ : አናስታስዮስ : ተከ ተለው : የርሱንም : ስራ : ገለበጠ ::

እንደሁም ፡ ደቅ ፡ ትምህርት ፡ በኦርቶዶክሳውያን ፡ መኻከል ፡ በሮም ፡ መንግሥት ፡ ጠፍቶ ፡ ቷናሽ ፡ ሕዝብ ፡ በልባኖስ ፡ ተራራ ፡ የኖረ ፡ ተቀበሉት ፡ ማረን ፡ ከተባለ ፡ ሞናክሴ ፡፡ እርሳቸውም ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ የማረን ፡ ወገን ፡ ይባላሉ ፡፡

ሥእልን ፡ ስለ ፡ ማክበር ፡ የሆነ ፡ ክርክር ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡፡ ለሥእሎች ፡ የሆነ ፡ ክብር ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ከሌላ ፡ ይልቅ ፡ በምሥራቅ ፡ በዛ ፡ ማክበራቸው ፡ ለማምለክ ፡ እስኪሆን ፡ ድረስ ፡፡ ስለዚህም ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ፀብ ፡ ሆነ ፡ ነገሥታትም ፡ እጅግ ፡ ግድ ፡ አደረጉ ፡ ሕዝብን ፡ እንደ ፡ ፈቃደቸው ፡ እግዚአብሔርን ፡ ወደ ፡ ማምለክ ፡ ያገደ ፡ ዘንድ ፡፡ እንደህ ፡ ሌዎን ፡ ኢሳውሪኮስ ፡ ቄሣር ፡ ጀመረ ፡ ሥእልን ፡ አምሳልንም ፡ ይከለክል ፡ ዘንድ ፡ ያለ ፡ ፍቅር ፡ ያለ ፡ ጥበብም ፡፡ ክርስቲያን ፡ የተባሉ ፡ ብዛትም ፡ በውነት ፡ ሥእልን ፡ እንደ ፡ አማልክትን ፡ አከበሩ ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ ብቻ ፡ የተገባውን ፡ ማገልገል ፡ ለሥእል ፡ አደረጉ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ነበሩ ፡ ሥእልን ፡ሲያዩ ፡ ክርስቶስን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ምሳሌ ፡ ያሰቡት ፡፡ እርሳቸውም ፡ እጅግ ፡ ተሰናከሉ ፡ ሥእላቸው ፡ ሲፈርስ ፡፡ ያም ፡ ማፍረስ ፡ እጅግ ፡ ጊዜ ፡ በሰው ፡ እጅ ፡ ሆነ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያላመለኩ ፡ ወይስ ፡ በሥእል ፡ ወይስ ፡ ያለ ፡ ሥእል ፡፡ ሌዎን ፡ ፲፭ ፡ አመት ፡ በሥእል ፡ ላይ ፡ ከሰራ ፡ በኋላ ፡ ሞተ ፡ ቆንስታንቲኖስ ፡ ቆጵሮኒሙስም ፡ ልጁ ፡ እርሱም ፡ ደግሞ ፡ የሥእል ፡ ጸላት ፡ የነበረ ፡ ተከተለው ፡ ባመት ፡ ፯፻፴፩ ፡፡ ዘመዱም ፡ አርታባስደስ ፡ ተነሥቶበት ፡ መንግሥቱን ፡ ወሰደ ፡ ሥእልንም ፡ ማክበር ፡ መለሰ ፡፡ ቆንስታንቲኖስ ፡ ግን ፡ ፯፻፴፬ ፡ አሸነፈው ፡ ሥእልንም ፡ በጣም ፡ ከመንግሥቱ ፡ ሁሉ ፡ ያጠፋ ፡ ዘንድ ፡ ፈቀደ ፡ ስለዚህም ፡ ባመት ፡ ፯፻፵፬ ፡ ሲኖደስን ፡ ኦይኩሜኒኬን ፡ ሰበሰበ ፡ ፫፻፴፰ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ የተሰበሰቡባት ፡ እርሳቸውም ፡ ሥእልን ፡ እንደ ፡ ጣዖትን ፡ የወገዙት ፡፡ ከዚያም ፡ ወዲያ ፡ እጅግ ፡ አበዱ ፡ በሥእል ፡ ላይ ፡ ወንድሞቻቸውንም ፡ በደሉ ፡፡ ከርሳቸው

ም ፡ ከሥእል ፡ ያልተሰናበቱ ፡ ወደ ፡ ግዞት ፡ ጨመሯ ፡ ገደል ዋቸውም ፡፡ ከሌህም ፡ ብዙ ፡ ሞናክሮች ፡ ነበሩ ፡፡

ቍስታንቲኖስ ፡ ቀጵሮኒሞስም ፡ ፴፡ አመት ፡ ግድ ፡ ካደረገ ፡ በኋላ ፡ በሥእል ፡ ላይ ፡ ልጁ ፡ አራተኛ ፡ ሌዎን ፡ ተከተለው ፡ በመንግሥቱ ፡ ባመት ፡ ፯፸፭፡፡ እርሱም ፡ አንዲት ፡ ሴትን ፡ ካቴና ፡ ስምዋን ፡ ኢሬኔ ፡ የሚሉት ፡ አገባት ፡፡ እርስዋም ፡ ሥእልን ፡ በማምለክ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ከመታዘዝ ፡ እንደ ፡ ተፈታች ፡ መስልዋታልና ፡ ሥእልን ፡ እጅግ ፡ አከበረች ፡፡ ሌዎንም ፡ የሥእል ፡ ጸላት ፡ ነበረ ፡ እንደ ፡ አባቱ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ብርቱ ፡ አልነበረም ፡ እንደርሱ ፡፡ ስለዚህም ፡ ኢሬኔ ፡ እጅግ ፡ ተቻለች ፡ ሥእልን ፡ ለመመለስ ፡ ታደርግ ፡ ዘንድ ፡፡ ባመትም ፡ ፯፹፡ ሌዎን ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ልጁ ፡ ቍስታንቲኖስ ፡ ጶርፌሮጌኒቶስ ፡ ሕፃን ፡ ሁኖ ፡ ተከተለው ፡ በሕፃንነቱም ፡ ኢሬኔ ፡ ነገሠች ፡ በርሱ ፡ ፈንታ ፡፡ እርስዋም ፡ አሁን ፡ በተንኰል ፡ ሰራች ፡ ፈቃድዋን ፡ ትፈጽም ፡ ዘንድ ፡፡ ሞናኰስትን ፡ አከበረች ፡ እርሳቸው ፡ ሁሉ ፡ የሥእል ፡ ወደጆች ፡ ኑረዋልና ፡ ኤጲስቆጶሳትንም ፡ አደረገቻቸው ፡፡

የቍስታንቲኒያም ፡ ጳትርያርክ ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ተራስዮስ ፡ የሥእል ፡ ታላቅ ፡ ወደጅ ፡ በስፍራው ፡ ተሾመ ፡፡ አሁንም ፡ ሌላ ፡ ሲኖደስ ፡ በቍስታንቲኒያ ፡ ተሰበሰበች ፡ ባመት ፡ ፯፹፯፡፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ተከልክለው ፡ በሥእል ፡ ጸላቶች ፡ ባመት ፡ ፯፹፯፡ በኒቅያ ፡ ተሰበሰቡ ፡ ከዚያም ፡ እንደ ፡ ኢሬኔ ፡ ፈቃድ ፡ የቀደመቸውን ፡ ሲኖደስ ፡ ነገር ፡ አፈረሱ ፡ የሥእልንም ፡ ማክበር ፡ መለሱ ፡፡ ይህችንም ፡ ሲኖደስ ፡ በምዕራብ ፡ ሊሾር ፡ ብሎ ፡ ቄሣር ፡ ካርል ፡ ባመት ፡ ፯፺፡ ፬፡ መጻሕፍትን ፡ ጻፈ ፡ በሥእል ፡ አፍራሾችና ፡ ባክባሮቹ ፡ ላይ ፡፡ ባመትም ፡ ፯፺፬፡ ሲኖደስ ፡ ተሰበሰበች ፡ በፍራንክፋርት ፡ በርስዋም ፡ የሥእል ፡ መሰገድና ፡ መገለገል ፡ ተወገዘ ፡፡

፬፡፡ ስለ ፡ መናፍቃን ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡፡

ከመናፈቃን ፡ ፩፡ ወገን ፡ ተነሣች ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ጳው

ሊኪያኖች ፡ የተባሉ ፡፡ እርሳቸውም ፡ ከማርቂዮን ፡ ከግኖ
ስቲቆች ፡ ወገን ፡ ይነሡ ፡ ነበሩ ፡ ትምህርታቸውም ፡ የማር
ቂዮንን ፡ ትምህርት ፡ መሰለች ፡፡ እርሳቸውም ፡ ጳውሊኪ
ያኖች ፡ ተባሉ ፡ የጳውሎስን ፡ የሐዋርያውን ፡ መጻሕፍት ፡
ብቻ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ተቀበሉ ፡፡

የቤት ፡ ክርስቲያን ፡
ታሪክ ፡

አራተኛ ፡ ክፍል ፡፡

ከታላቁ ፡ ካርል ፡ ከሞቱ ፡ ጀምሮ ፡

እስከ ፡ ሰባተኛ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ሹመት ፡ ድረስ ፡፡

ካመት ፡ ፰፻፲፬ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፲፻፸፫ ፡ ድረስ ፡፡

በዚህ ፡ ዘመን ፡ የነገሡ ፡ ነገሥታት ፡ እሌህ ፡ ናቸው ፡፡

፩፡ በምሥራቅ ፡፡

1. ሌዎን ፡ አርሜኒኩስ ፡ እስከ ፡ ፰፳፡ ድረስ ፡፡
2. ሁለተኛ ፡ ሚካኤል ፡ እስከ ፡ ፰፳፱፡ ድረስ ፡፡
3. ቴዎፊሎስ ፡ እስከ ፡ ፰፵፪፡ ድረስ ፡፡
4. ሶስተኛ ፡ ሚካኤል ፡ ከናቱ ፡ ከቴዎዶራ ፡ በታች ፡ እስከ ፡ ፰፷፯፡ ድረስ ፡፡
5. በርደስ ፡ እስከ ፡ ፰፷፯፡ ድረስ ፡፡
6. ባሲልዮስ ፡ ማቄዶን ፡ እስከ ፡ ፰፹፯፡ ድረስ ፡፡
7. ሌዎን ፡ ፊሎሶፎስ ፡ እስከ ፡ ፱፲፩፡ ድረስ ፡፡
8. አለክሰንድሮስ ፡ ፱፲፫፡፡
9. ስምንተኛ ፡ ቀንስታንቲኖስ ፡ ጶርፊሮጌኒቶስ ፡ እስከ ፡ ፱፶፱፡ ድረስ ፡፡
10. ሮማኑስ ፡ እስከ ፡ ፱፷፫፡ ድረስ ፡፡
11. ባሲልዮስና ፡ ቀንስታንቲኖስ ፡ ከናታቸው ፡ ከቴዎፋኒያ ፡ በታች ፡፡ ኒኬፎሮስ ፡ ፎቃስም ፡ ቴዎፋኒያን ፡ ያገባት ፡ ነገሡ ፡ እስከ ፡ ፱፷፱፡ ድረስ ፡፡
12. ዮሐንስ ፡ ዚሚስኬስ ፡ ከ፱፷፱፡ ጀምሮ ፡፡

፪፡ በምዕራብ ፡ እሌህ ፡ ታላቆች ፡ ነገሥታት ፡ ነበሩ ፡፡

1. ሉድዊግ ፡ ጻድቅ ፡ የፈራንኮች ፡ ንጉሥ ፡ እስከ ፡ ፰፵፡፡
2. ሎታር ፡ የሉድዊግ ፡ ልጅ ፡ ከወንድሞቹ ፡ ጋራ ፡ ስለ ፡ መንግሥት ፡ አያሌ ፡ ጊዜ ፡ ተጸላ ፡ እስከ ፡ ፰፶፭፡ ድረስም ፡ ነገሠ ፡፡
3. ሉድዊግ ፡ የንምሳ ፡ ንጉሥ ፡ ፰፵፫፡ እስከ ፡ ፰፸፮፡፡
4. ታላቅ ፡ አልፍሬድ ፡ የእንግልጣር ፡ ንጉሥ ፡ ፰፸፩፡ እስከ ፡ ፱፻፡፡
5. ታላቅ ፡ ኦቶ ፡ የንምሳ ፡ ንጉሥ ፡ ፱፷፪፡፡
6. ሁጎ ፡ ካጴት ፡ የፈረንሳዎች ፡ ንጉሥ ፡ ፱፹፯፡፡
7. ታላቅ ፡ ካኑት ፡ የደኖች ፡ ንጉሥ ፡ ፲፲፯፡፡

8. አራተኛ ፡ ሀይንሪኽ ፡ የንምሳ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፻፶፯፡፡
9. ፊሊጶስ ፡ የፈረንሰ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፻፷፡፡
10. ዊልያም ፡ ኖርማን ፡ የእንግሊጣር ፡ ንጉሥ ፡ ፲፻፷፮፡፡

በዚህ ፡ ዘመንም ፡ የነበሩ ፡ የሮም ፡ ጳጳሳት ፡ እሌህ ፡ ናቸው ፡፡

1. አራተኛ ፡ እስጢፋኖስ ፡፡ ፰፲፮፡፡
2. ጳሻሊስ ፡ ፰፲፯፡፡
3. ሁለተኛ ፡ ኤውጌኒዮስ ፡ ፰፳፬፡፡
4. አራተኛ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ፰፳፯፡፡
5. ሁለተኛ ፡ ሰርግዮስ ፡ ፰፵፬፡፡
6. አራተኛ ፡ ሌዎን ፡ ፰፵፯፡፡
7. ሶስተኛ ፡ ቤኔዲክቶስ ፡ ፰፶፭፡፡
8. ኒቆላዎስ ፡ ፰፶፰፡፡
9. ሁለተኛ ፡ ሀድርያኑስ ፡ ፰፷፯፡፡
10. ስምንተኛ ፡ ዮሐንስ ፡፡ ፰፸፪፡፡
11. ማሪን ፡ ፰፹፪፡፡
12. ሶስተኛ ፡ ሀድርያኑስ ፡ ፰፹፬፡፡
13. አምስተኛ ፡ እስጢፋኖስ ፡ ፰፹፭፡፡
14. ፎርሞሱስ ፡ ፰፺፩፡፡
15. ስድስተኛ ፡ ቦኒፋኪዮስ ፡፡ ፰፺፮፡፡
16. ስድስተኛ ፡ እስጢፋኖስ ፡ ፰፺፯፡፡
17. ሮማኑስ ፡፡ 18. ሁለተኛም ፡ ቴዎድሮስ ፡፡ 19. ዘጠኝኛም ፡ ዮሐንስ ፡፡ ፰፺፯፡፡
20. አራተኛ ፡ ቤኔዲክቶስ ፡፡ ፱፻፡፡
21. አምስተኛ ፡ ሌዎን ፡፡ 22. ክርስቶፎሮስም ፡ ፱፻፫፡፡
23. ሶስተኛ ፡ ሰርግዮስ ፡ ሌዎንን ፡ በግዞት ፡ የገደለ ፡፡ ፱፻፬፡፡
24. ሶስተኛ ፡ አናስታስዮስ ፡ ፱፲፫፡፡
25. ለውዶ ፡፡ 26. አሥረኛ ፡ ዮሐንስ ፡፡ ፱፲፬፡፡
27. ስድስተኛ ፡ ሌዎን ፡፡ 28. ሰባተኛም ፡ እስጢፋኖስ ፡፡ ፱፳፱፡፡
29. አሥራ ፡ አንደኛ ፡ ዮሐንስ ፡፡ ፱፴፩፡፡
30. ሰባተኛ ፡ ሌዎን ፡ ፱፴፮፡፡

31. ስምንተኛ ፡ እስጢፋኖስ ፡ ፱፴፱።
32. ሁለተኛ ፡ ማሪን ፡ ፱፵፪።
33. ሁለተኛ ፡ አጋጴቶስ ፡ ፱፵፮።
34. አሥራ ፡ ሁለተኛ ፡ ዮሐንስ ፡ ፱፶፭።
35. ስምንተኛ ፡ ሌዎን ።　36. አምስተኛም ፡ ቤኔዲክቱስ ፡ ፱፷፬።
37. አሥራ ፡ ሦስተኛ ፡ ዮሐንስ ። ፱፷፭።
38. ስድስተኛ ፡ ቤኔዲክቱስ ፡ ፱፸፪።
39. ሰባተኛ ፡ ቦኒፋኪዩስ ፡ ፱፸፬።
40. ሰባተኛ ፡ ቤኔዲክቱስ ፡ ፱፸፭።
41. አሥራ ፡ አራተኛ ፡ ዮሐንስ ፡ ፱፹፫።
42. ሰባተኛ ፡ ቦኒፋኪዩስ ፡ ፱፹፬።
43. አሥራ ፡ አምስተኛ ፡ ዮሐንስ ፡ ፱፹፭።
44. አምስተኛ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ፱፺፮።
45. ሁለተኛ ፡ ሲልበስተር ፡ ፱፺፱።
46. አሥራ ፡ ሰባተኛ ፡　47. አሥራ ፡ ስምንተኛ ፡ ዮሐንስ ። ፲፻፫።
48. አራተኛ ፡ ሰርግዩስ ። ፲፻፱።
49. ስምንተኛ ፡ ቤኔዲክቱስ ፡ ፲፻፲፪።
50. አሥራ ፡ ዘጠኝኛ ፡ ዮሐንስ ፡ ፲፻፳፬።
51. ዘጠኝኛ ፡ ቤኔዲክቱስ ፡ ፲፻፴፫።
52. ሦስተኛ ፡ ሲልበስተር ፡ ፲፻፵፬።
53. ስድስተኛ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ፲፻፵፭።
54. ሁለተኛ ፡ ክሌሜንስ ። ፲፻፵፮።
55. ሁለተኛ ፡ ደማሱስ ፡ ፲፻፵፰።
56. ዘጠኝኛ ፡ ሌዎን ፡ ፲፻፵፱።
57. ሁለተኛ ፡ ዊክቶር ፡ ፲፻፶፭።
58. ዘጠኝኛ ፡ እስጢፋኖስ ፡ ፲፻፶፯።
59. አሥረኛ ፡ ቤኔዲክቱስ ።　60. ሁለተኛ ፡ ኒቆላዎስ ። ፲፻፶፰።
61. ሁለተኛ ፡ እስክንድር ።　62. ሁለተኛ ፡ ሆኖርዩስ ፡ ፲፻፷፩።
63. ሰባተኛ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ፲፻፸፫።

መጀመርያ ፡ ምዕራፍ ፡፡

ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መዝረጋት ፡፡

በኤውሮጳ ፡ በሰሜን ፡ ፫ ፡ መንግሥቶች ፡ አሉ ፡ ስዌደን ፡ ኖርዌግንም ፡ ደንማርክም ፡ የተባሉ ፡፡ በዚህ ፡ ዘመንም ፡ ሃይማኖት ፡ ወደዚያ ፡ ደረሰች ፡፡

የደንማርክ ፡ ንጉሥ ፡ ሃረልድ ፡ ባመት ፡ ፰፻፳፮ ፡ ወደ ፡ ጳድቅ ፡ ሉድዊግ ፡ መጣ ፡ ተጠመቀም ፡፡ ወደገሩም ፡ በተመለሰ ፡ ጊዜ ፡ ሉድዊግ ፡ ፪ ፡ ሰዎች ፡ መምህራን ፡ አንስጋርንና ፡ ገውትበርትን ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ሰደደ ፡ በደንማርክ ፡ ወንጌለን ፡ ያስተምሩ ፡ ዘንድ ፡፡ አንድ ፡ ማስተማርያ ፡ አደረጉ ፡ ብላቴኖችን ፡ ወንጌልን ፡ ለመስበክ ፡ ያሳድጉበት ፡ ያስተምሩበትም ፡ ዘንድ ፡፡ ሌላ ፡ ማድረግ ፡ አልቻላቸውም ፡ ያገር ፡ ሕዝብ ፡ ብርቱ ፡ ነበሩና ፡ ጣዖታትን ፡ በማምለክ ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ሉድዊግ ፡ አንስጋርን ፡ ሰደደ ፡ ወደ ፡ ስዌደን ፡፡ አንስጋርም ፡ ሞናክሴን ፡ ዊትማርን ፡ ወደ፪ ፡ የነበረውን ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ወሰደ ፡፡ እጅግ ፡ እጅ ፡ መንሻውን ፡ ከርሳቸው ፡ ጋራ ፡ ወሰዱ ፡ ንጉሥ ፡ ሉድዊግ ፡ ጳድቅ ፡ የሰጣቸው ፡ ለስዌደን ፡ ንጉሥ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ወደ ፡ ስዌደን ፡ ደርቻ ፡ ሳይደርሱ ፡ መርከባቸው ፡ ፈረሰች ፡ ገንዘባቸውም ፡ በባሕር ፡ ጠፋ ፡ ሰዎችም ፡ በግድ ፡ ብቻ ፡ ዳኑ ፡፡ የስዌደን ፡ ንጉሥም ፡ በፍቅር ፡ ተቀበላቸው ፡፡ አንድ ፡ ሰውም ፡ ምድሩን ፡ ሰጣቸው ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ይሠሩበት ፡ ዘንድ ፡፡ ባመትም ፡ ፰፻፴ ፡ ተመለሱ ፡ ወደ ፡ ሉድዊግ ፡፡ ባመትም ፡ ፰፻፴፩ ፡ የሮም ፡ ጳጳስ ፡ አንስጋርን ፡ ቀደሰ ፡ ሜትሮጶሊታን ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ በለዚያ ፡ ፫ ፡ መንግሥቶች ፡ ለተተከሉ ፡ ለሚተክሉም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ሁሉ ፡፡ በሀምቡርግም ፡ ይኖር ፡ ዘንድ ፡ ከዚያም ፡ የሰሜን ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናትን ፡ ይጠብቅ ፡ ዘንድ ፡፡ ገውትበርትም ፡ ወደ ፡ ስዌደን ፡ ሒደ ፡ ነበረ ፡ ከዚያም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነገር ፡ በ፪ ፡ አደገ ፡፡ ሁከ

ት ፡ ግን ፡ በተነሣ ፡ ጊዜ ፡ ገውትበርት ፡ ሸሸ ፡ ከዚያም ፡ ፪፡ አመት ፡ አልተቻሉም ፡ ያስተምሩ ፡ ዘንድ ፡፡

አንስጋርም ፡ ባመት ፡ ፰፶፡፡ የሚያህል ፡ ወደ ፡ ደኖች ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ኤሪኽ ፡ ተላከ ፡ ከዚያም ፡ ቤት ፡ ክርስቲያንን ፡ ሠራ ፡ አስተማረም ፡ ያመኑትንም ፡ አጠመቀ ፡፡

ባመትም ፡ ፰፶፮፡ አንስጋር ፡ ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ስዌደን ፡ ሔደ ፡ ኤሪምበርትንም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ወሰደ ፡፡ ኦለፍም ፡ ወደ ፡ ተባለ ፡ ወደ ፡ ስዌደን ፡ ንጉሥ ፡ በደረሱ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሥ ፡ መልካም ፡ ተቀበላቸው ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ የጣዖታት ፡ ካህናት ፡ እጅግ ፡ ተቈጡባቸው ፡ ይከለክልዋቸውም ፡ ዘንድ ፡ ፈለጉ ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ የመንግሥት ፡ ታላላቆች ፡ ለጉባኤ ፡ ተሰበሰቡ ፡ ዕፃውንም ፡ ጣሉ ፡ ያውቁ ፡ ዘንድ ፡ የክርስቲያንን ፡ አምላክ ፡ ማምለክ ፡ እንደ ፡ ገባቸው ፡ ወይስ ፡ አይደለም ፡፡ አንስጋርም ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከወደጆቹ ፡ ጋራ ፡ በጸሎትና ፡ በልመና ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለመኑ ፡ የወንጌልን ፡ ነገር ፡ ያበጅ ፡ ዘንድ ፡፡ ዕፃም ፡ ለክርስቲያን ፡ ወደቀ ፡፡ አንድ ፡ ሽማግሌም ፡ ሕዝብን ፡ መከረ ፡ የአንስጋርን ፡ ትምህርት ፡ በደስታ ፡ እንዲቀበሉት ፡ እርሱ ፡ የሚያምኑበትን ፡ የሚረዳ ፡፡ ከዚያም ፡ ጀምሮ ፡ ወንጌል ፡ በስዌደን ፡ ተዘራ ፡፡ አንስጋርም ፡ እንዲህ ፡ ሳይደክም ፡ ስለ ፡ ወንጌል ፡ ሰራ ፡ እስከ ፡ ፰፷፭፡ ድረስ ፡፡ በደንማርክም ፡ እጅግ ፡ መጋደል ፡ ሆነ ፡ በክርስቲያንና ፡ ባረማውያን ፡ መካከል ፡ ታላቅ ፡ ካኑት ፡ ንጉሥ ፡ በምሽቱ ፡ ማስተማር ፡ ክርስቲያን ፡ እስኪሆን ፡ ድረስ ፡፡

በስዌደን ፡ ደግሞ ፡ የወንጌል ፡ መለክተኞች ፡ ተጋደሉ ፡ ጣዖታትን ፡ ከማምለክ ፡ ጋራ ፡ ኦለፍ ፡ ስኬት ፡ ኮኒንግ ፡ እስኪነግሥ ፡ ድረስ ፡ ከ፱፺፰፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፲፷፪፡ ድረስ ፡፡ ይህም ፡ ንጉሥ ፡ ከልልቡ ፡ ክርስቲያን ፡ ሆነ ፡ እጅግም ፡ አደረገ ፡ የወንጌልን ፡ መዝረጋት ፡ ያቀል ፡ ዘንድ ፡፡

የክርስቲያን ፡ ሃይማኖትም ፡ ከስዌደን ፡ ወደ ፡ ኖርዌገን ፡ አለፈች ፡፡ የኖርዌገን ፡ ንጉሥ ፡ ኦለፍ ፡ ቅዱስ ፡ የተባለ ፡ ቀሳውስትንና ፡ መጻሕፍትን ፡ አስመጣ ፡ ሕዝቡን ፡ ያስተምር ፡ ዘንድ ፡ የወታደረንም ፡ ጋሾች ፡ በመስቀል ፡ አስመለ

ከተ :: ከኖርዌገንም : ዘንድ : የክርስቲያን : ሃይማኖት : ወደ : ብዙ : ደሴቶች : ደረሰች ::

በዚህ : ዘመንም : ሃይማኖት : ተዘረጋች : በኽጻሮችና : በቡልጋሮች : መኻከል :: ፪፡ ሞናክሮች : ከምሥራቅ : በለዚያ : ምድር : በዞረ : ባስተማረም : ጊዜ : ስማቸው : ቄርሎስና : ሜቶዲዮስ : የሚልዋቸው : ወንድሞች :: እሌህ : ሁለትም : ለለዚያ : አሕዛብ : ፊደላትን : ሰጡ : ጽፈትና : ትምህርት : እንዲሆንላቸው : በቋንቋቸው :: በለዚህ : አሕዛብም : መኻከል : የተተከለች : ቤተ : ክርስቲያን : በኋላ : ለጅግ : ፀብ : መክንያት : ሆነች : በሮምና : በቆንስታንቲኒያ : ጳጳሳት : መኻከል :: ኢያንደንደቸው : ገንዘቤ : ናት : ብልዋልና ::

ከቡልጋሮችም : ምድር : ሃይማኖት : ወደ : ሞራዊያ : ደረሰች : በሜቶዲዮስ : ማስተማር :: ማምለካቸውም : ሁሉ : ባገሬቸው : ቋንቋ : ሲሆን : ኤጲስቆጶሳት : ሜቶዲዮስን : ከሰሱ : በለቲና : ቋንቋ : እንደላደረገው :: ጳጳስ : ዮሐንስ : ፰፡ ግን : በዚህ : አመሰገነው : ቍርባንንም : ብቻ : በለቲና : ቋንቋ : እንዲቀድስ : ፈለገው ::

በሜቶዲዮስም : ማስተማር : ወንጌል : ወደ : ቦሂሚያ : ደግሞ : ደረሰች : ባረማውያንም : ማምለክ : ላይ : አሸነፈች : ባመት : ፱፻፩ ::

በዚህ : ዘመንም : በወንደች : መኻከል : ቤተ : ክርስቲያን : ጀመረች : ንጉሣቸው : ክርስቲያን : በሆነ : ጊዜ ::

እንደሁም : የጶሎኒያ : የሞስቆብም : አሕዛብ : ወንጌልን : ተቀበሉ :: ደግሞም : የሁንጋርያ : ሕዝብ : በወንጌል : ተማረች :: ከዚያም : ሃይማኖት : ወደ : ትራንሲልዋኒያ : ወደ : ወላኽያም : አለፈች ::

ሁለተኛ ፡ ምዕራፍ ።

የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዓት ፡ በዚህ፡ ዘመን ።

በዚህ ፡ ዘመን ፡ የምዕራብ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሥርዓትን ፡ መጽሐፍ ፡ ተቀበለች ። ከዚህ ፡ ዘመንም ፡ በፊት ፡ አንዲት ፡ መጽሐፍ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ የተቀበለች ፡ ነበረች ፡ የዲዮናስዮስ ፡ ኤክሲጉውስ ፡ መጽሐፍ ። በርስዋም ፡ የሲኖዶች ፡ ቃኖናች ፡ ከሮም ፡ ጳጳሳት ፡ ትእዛዛት ፡ ጋራ ፡ ባንድ ፡ ተለቀሙ ። ካመትም ፡ ፯፻፡ በኋላ ፡ ኢሲዶሮስ ፡ የሴዊልያ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ይህችን ፡ መጽሐፍ ፡ አቀና ፡ አበዛትም ። ካመትም ፡ ፰፻፡ ወዲህ ፡ ሌላ ፡ በኢሲዶሮስ ፡ ስም ፡ የተጻፈች ፡ መጽሐፍ ፡ ወጣች ፡ አዲስ ፡ ትእዛዛትን ፡ ያወጣች ፡ አስቀድሞ ፡ ያልታወቁ ፡ በዚህም ፡ በታሪክ ፡ ሐሰት ፡ ሁነው ፡ የተገለጹ ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ባለማወቅ ፡ መግዛትን ፡ ያገኙ ። ሦስት ፡ ነገርም ፡ በዚህ ፡ መጽሐፍ ፡ በረታ ። ፩፡ ክርስቶስ ፡ ለሮም ፡ ጳጳስ ፡ ሥልጣን ፡ እንደ ፡ ሰጠ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ ላይ ። መፍረድም ፡ ሁሉ ፡ መጠበቅም ፡ ሁሉ ፡ ከነገሥታት ፡ ግፍ ፡ ለኤጲስቆጶሳት ፡ እንደ ሆን ፡ በሮም ፡ ጳጳስ ፡ እጅ ። ፪፡ የክብር ፡ ሥርዓት ፡ ታዘዘች ፡ ማዕረጋት ፡ እንደ ሆኑ ፡ ከዲያቆን ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ሮም ፡ ጳጳስ ፡ ድረስ ። ፫፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጠባቂ ፡ እርሱም ፡ ቄስ ፡ ኤጲስቆጶስም ፡ ጳጳስም ፡ በክርስቶስ ፡ ፈንታ ፡ ኑርዋልና ፡ በመንግሥት ፡ ሹማምት ፡ በታች ፡ አይደሉም ፡ በላይ ፡ እንጂ ። እነሆ ፡ የጳጳሳት ፡ ትዕቢት ። ባለም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ብለው ፡ ይህነን ፡ ያሰትን ፡ መጽሐፍ ፡ ሰሩ ፡ በወንጌልም ፡ ላይ ፡ አደረጉት ። ይህነንም ፡ አሰት ፡ በምዕራብ ፡ ተቀበሉ ፡ በውነቱም ፡ አልተጠራጠሩም ፡ እስከ ፡ ፲፰፻፶፬፡ ድረስ ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ አሰቱ ፡ ተገለጸ ።

የጳጳሳት ፡ ታሪክ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡፡

ያች ፡ መጽሐፍ ፡ ከተሰራች ፡ በኋላ ፡ ጳጳሳት ፡ ለግፋቸው ፡ ለትዕቢታቸውም ፡ ወሰን ፡ አላደረጉም ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ሉድዊግ ፡ ጳድቅ ፡ ለጳጳስ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜ ፡ ዝቅ ፡ አለ ፡፡ የቄሣር ፡ ልጆች ፡ ባባታቸው ፡ ላይ ፡ ባመፁ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ጳጳስም ፡ በሸሹ ፡ ጊዜ ፡ እርሱ ፡ ኃጢአታቸውን ፡ ቀደሰ ፡ አባታቸውንም ፡ ከልጆቹ ፡ በታች ፡ አደረገው ፡፡

ባመትም ፡ ፰፻፶፰፤ መጀመርያ ፡ ኒቆላዎስ ፡ ጳጳስ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ተሾመ ፡፡ እርሱም ፡ ከቀደሙት ፡ ጳጳሳት ፡ ይልቅ ፡ በረታ ፡፡ሎታርን ፡ የፍራንስን ፡ ንጉሥ ፡ ሌላውን ፡ ሴቲቱን ፡ ያገባ ፡ ዘንድ ፡ ከምሽቱ ፡ የተለየ ፡ ገዘተ ፡ ምሽቱን ፡ እስኪመልስ ፡ ድረስ ፡፡ ኒቆላዎስም ፡ ከሂንክማር ፡ ከሬምስ ፡ ሜትሮጶሊታን ፡ ጋራ ፡ ተጻለ ፡፡ ሂንክማር ፡ በሲኖደስ ፡ አንዱን ፡ ከኤጲስቆጶሳቱ ፡ ገዘተ ፡ ይህ ፡ ኤጲስቆጶስም ፡ ወደ ፡ ጳጳስ ፡ ተማፀነ ፡፡ ኒቆላዎስም ፡ የሂንክማርን ፡ የሲኖደስንም ፡ ፍርድ ፡ ሽሮ ፡ ያነን ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ወደ ፡ ሹመቱ ፡ መለሰው ፡፡

ከኒቆላዎስም ፡ በኋላ ፡ ሁለተኛ ፡ ሃድርያኑስ ፡ ጳጳስ ፡ ሁኖ ፡ ተሾመ ፡ ባመት ፡ ፰፻፷፯፡፡ እርሱም ፡ ከነገሥታትና ፡ ከሂንክማር ፡ ጋራ ፡ ተጻላ ፡፡ ሂንክማር ፡ የሎታርን ፡ ልጅ ፡ ካርልን ፡ ለመንግሥት ፡ ቀብቶ ፡ ቀደሰው ፡፡ ሃድርያኑስ ፡ ግን ፡ የካርልን ፡ ወንድም ፡ ማንገሥ ፡ ፈለገ ፡ ሂንክማርንም ፡ ገዘተ ፡ ካርልንም ፡ ሾረ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አልሆነለትም ፡፡ ሂንክማር ፡ ግን ፡ ዘመዴን ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ የነበረውን ፡ እርሱም ፡ ደግሞ ፡ ሂንክማር ፡ የተባለውን ፡ በገዘተ ፡ ጊዜ ፡ በሲኖደስ ፡ ሃድርያኑስ ፡ የተገዘተውን ፡ ወደ ፡ ሹመቱ ፡ መልሶት ፡ የገዘተውንም ፡ ሂንክማርን ፡ እርሱ ፡ ገዘተ ፡፡ ይህም ፡ ሁሉ ፡ በላይ ፡ በነገርነው ፡ በኢሲደሮስ ፡ በሥርዓቱ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደ ፡ ተሰራ ፡ ቃኖን ፡ የሆነ ፡ አለው ፡፡ ሂንክማር ፡ ግን ፡ ያ ፡ መጽሐፍ ፡ በገሃናም ፡ ተወለደ ፡ አለ ፡፡ ደሮ ፡ ጳጳሳት ፡ አሸነፉ ፡፡

የሮምም ፡ ጥፋት ፡ በየጳጳስ ፡ በዛ ፡፡ ሁለት ፡ ጋለሞቶች ፡ የሮም ፡ ሴቶች ፡ የኤጲስቆጶሳት ፡ አለቆች ፡ በሮም ፡ ወደጀ

ች ፡ የጳጳስን ፡ መምረጽ ፡ አደረጉ ፡፡ በርሳቸውም ፡ ፈቃድ ፡ ባመት ፡ ፱፻፫፤ ሦስተኛ ፡ ሰርግዩስ ፡ ጳጳስ ፡ ሁኖ ፡ ተሾመ ፡፡ ባመትም ፡ ፱፶፮፤ አሥሬ ፡ ሁለተኛ ፡ ዮሐንስ ፡ ጳጳስ ፡ ሆነ ፡ ዕድሜው ፡ ፲፰፤ አመት ፡ ሲሆን ፡፡ ደህም ፡ ሰው ፡ እጅግ ፡ ክፉ ፡ ነበረ ፡ አመንዝራም ፡፡ እርሱም ፡ ተሽሮ ፡ ስምንተኛ ፡ ሌዎን ፡ ጳጳስ ፡ ሆነ ፡፡ ባመትም ፡ ፱፹፳፤ ዮሐንስ ፡ ፲፪፤ ጳጳስ ፡ ሆነ ፡፡ እርሱም ፡ ከፈራንስ ፡ ንጉሥ ፡ ከሁጎ ፡ ከጼት ፡ ጋራ ፡ ተጸላ ፡፡ ከፈራንስ ፡ ንጉሥም ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ብርቱ ፡ ሰው ፡ አዋቂም ፡ ነበረ ፡ እርሱም ፡ ገርበርት ፡ የሬምስ ፡ ሜትሮጶሊታን ፡፡ ገርበርትም ፡ የጳጳሳትን ፡ ኃጢአት ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ገለጸ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ እርሱ ፡ ባመት ፡ ፱፮፱፤ ባለቤቱ ፡ ጳጳስ ፡ ሆነ ፡ ሁለተኛ ፡ ሲልበስተር ፡ ተብሎ ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ልቡን ፡ ከበጎ ፡ ለክፉ ፡ የለወጠ ፡ ይመስላል ፡ ባመትም ፡ ፲፻፱፤ ሞተ ፡፡ ከርሱም ፡ በኋላ ፡ አያሌ ፡ ክፎች ፡ ጳጳሳት ፡ ተከተሉ ፡ ከርሳቸውም ፡ አንድ ፡ አሽከር ፡ በኃጢአቱ ፡ የታወቀ ፡ ባመት ፡ ፲፻፵፭፤ ስሙን ፡ ቤኔዲክቱስ ፡ ፱፤ የሚሉት ፡፡ በርሱም ፡ ፈንታ ፡ ሌላውን ፡ ሦስተኛ ፡ ሲልበስተር ፡ የሚሉትን ፡ ጳጳስ ፡ ባደረጉ ፡ ጊዜ ፡ ቤኔዲክቱስ ፡ ሹመቱን ፡ ሼጠ ፡ ብር ፡ ያገኝ ፡ ዘንድ ፡ ብሎ ፡፡ አንድ ፡ ደህና ፡ ቄስም ፡ ገዛው ፡ ጳጳስ ፡ ሁኖ ፡ ስድስተኛ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ የተባለ ፡፡ ደሮ ፡ ቤኔዲክቱስ ፡ ሹመቱን ፡ ከሼጠ ፡ በኋላ ፡ አልተሰናበተውም ፡፡ አሁንም ፡ ፫፤ ጳጳሳት ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ነበሩ ፡፡ ሲልበስተር ፡ ቤኔዲክቱስም ፡ ጎርጎርዮስም ፡፡

የዚያን ፡ ጊዜም ፡ የንምሳ ፡ ንጉሥ ፡ ሦስተኛ ፡ ሀይንሪኽ ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ መጥቶ ፡ ሦስታቸውን ፡ ሻረ ፡ አዲስ ፡ ጳጳስንም ፡ ሾመ ፡ እርሱም ፡ ሦስተኛ ፡ ክሌሜንስ ፡ የተባለውን ፡፡

ባመትም ፡ ፲፻፵፱፤ ዘጠነኛ ፡ ሌዎን ፡ ጳጳስ ፡ ሆነ ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ተነሣ ፡ ጳጳሳትን ፡ ያበረታቸው ፡ ባለም ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ እርሱም ፡ ሂልድብራንድ ፡፡ እርሱም ፡ በቅድም ፡ የርያ ፡ ጠባቂ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይላሉ ፡ ኋላም ፡ ቄስ ፡ ሁኖ ፡ ከርሱ ፡ እጅግ ፡ ተማረ ፡፡ አንድም ፡ ከኤጲስቆጶሳት ፡ አለቆች ፡ በሮም ፡ የነበረ ፡ አለው ፡፡ አንተ ፡ ቅዱስ ፡ ሰይጣኔ ፡ ነህ ፡ ብሎት ፡፡ ባመትም ፡ ፲፻፶፱፤ ሁለተኛ ፡ ኒ

ቀላዎስ ፡ ጳጳስ ፡ ሆነ ፡ በሂልድብራንድ ፡ ኃይል ፡ ሥርዓትን ም ፡ አደረገ ፡ ጳጳስ ፡ ሁሉ ፡ በ፯፤ በሮም ፡ በሚኖሩ ፡ በኤጲ ስቆጶሳት ፡ አለቆች ፡ እንዲመረጽ ፡፡

ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መገናኘት ፡ ከመንግሥት ፡ ጋራ ፡፡

ብዙ ፡ ቀሳውስትና ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ አልወደዱም ፡ ሹመት ፡ ሁሉ ፡ በንጉሥ ፡ እንዲሆን ፡፡ በውነትም ፡ ይህ ፡ እጅግ ፡ ጊዜ ፡ ክፉ ፡ ሆነ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ንጉሥ ፡ እንደ ፡ ፈቃዱ ፡ በጎን ፡ ቄስ ፡ ወይስ ፡ በጎን ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ሲከለክል ፡ ክፉንም ፡ ሲሾም ፡፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ከተመረጹ ፡ በኋላ ፡ ለማጽናታቸው ፡ ለመቅደሳቸውም ፡ በትርንና ፡ ቀለበትን ፡ ተቀበሉ ፡ ከንጉሥ ፡፡ አሁንም ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ የሰማዩን ፡ መጽሬታቸውን ፡ ባይረሱ ፡ እጅግ ፡ ይጠቅሙ ፡ ዘንድ ፡ በተቻላቸው ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ እጅግ ፡ ጊዜ ፡ ሆነ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገልጋዮች ፡ የንጉሥን ፡ ማገልገል ፡ አስበው ፡ የክርስቶስን ፡ ማገልገል ፡ እንዲረሱ ፡፡ በዚህም ፡ ላይ ፡ ሌሎች ፡ ተነሡ ፡ ሹመታቸውን ፡ ከንጉሥ ፡ እጅ ፡ መቀበል ፡ ያልወደዱ ፡፡

ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዓት ፡ በውሥጥዋ ፡፡
ስለ ፡ ምንኩስና ፡፡

ምንክስና ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ከፍታለችና ፡ አያሌ ፡ ሰዎች ፡ ተነሡ ፡ ለበጎ ፡ ይመልሱት ፡ ዘንድ ፡ የስሩ፡፡ እንደህ ፡ ቤኔ ዲክቱስ ፡ ከ አኒያኔ ፡ በፈራንስ ፡ መንግሥት ፡ ባመት ፡ ፰፻፩፤ በኋላም ፡ የርሱ ፡ ስራ ፡ ሳይጠቅም ፡ በረኖና ፡ ዎደ ፡ ተጋደሉ ፡ ምንክስናውን ፡ ለማሻል ፡፡ አንዲት ፡ ታላቅ ፡ ገደም ፡ ተሠራች ፡ በክሊኒ ፡ ያስቈጦች ፡ ሕይወት ፡ እጅግ ፡ ያበረቱባት ፡፡ ይህችም ፡ ገደም ፡ በበጎ ፡ ስራዋ ፡ የታወቀች ፡ ሆነች ፡፡ ብዙ ፡ ገደሞችም ፡ ተሠሩ ፡ እንደርስዋ ፡ የሆኑ ፡ አንድነትም ፡ የነበረላቸው ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡፡

ሶስተኛ ፡ ምዕራፍ ።

የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ማምለክ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ።

በታላቅ ፡ ካርል ፡ ዘመን ፡ የወጣ ፡ ጥቂት ፡ ብርሃን ፡ ከር ሱ ፡ በኋላ ፡ ተጨለመ ። በዚህ ፡ ዘመን ፡ ረባኑስ ፡ ማውሩ ስ ፡ መጽሐፍን ፡ ጻፈ ፡ በጎን ፡ መንፈስ ፡ ያስነሣ ፡ ዘንድ ፡ በ ቤተ ፡ ክርስቲያን ። ነገር ፡ ግን ፡ ቃሉን ፡ አልሰሙም ። እን ደርሱም ፡ ፫ ሲኖዶች ፡ ማስተማርን ፡ ያዘዙ ። በዚህ ፡ ደገ ለጻል ፡ ብዙ ፡ ቀሳውስት ፡ መድገምን ፡ እንኳ ፡ እንደላወቁ ።

ሶስት ፡ ሞናክሶች ፡ ነበሩ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ክፍልን ፡ ያስተረጐሙ ፡ በቋንቋቸው ። እርሳቸው ም ፡ ኦትፍሪድ ፡ ሆትገርም ፡ ዊሊራምም ። አኀበርት ም ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ጸሎት ፡ አቀና ። ቅላውዲዩስ ም ፡ የቱሪን ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ከጳጳስ ፡ ጋራ ፡ ተጋደለ ፡ ሥእል ን ፡ ስለ ፡ ማክበር ። ‘ክብርና ፡ ምስጋና ፡ ሁሉ ፡ ለእግዚአብ ሔር ፡ ይሁን’ ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ከሁሉ ፡ ይ በልጣል ፡ አለ ። ስለዚህም ፡ ሥእልን ፡ ማክበር ፡ ሁሉ ፡ ኃ ጢአት ፡ ሁኖ ፡ ቈጠረው ። የሮም ፡ ጳጳስ ፡ መጀመርያ ፡ ጰ ሻሊስ ፡ ገዘተው ። ደሮ ፡ ሉድዊግ ፡ ጻድቅ ፡ ከጳጳስ ፡ ጸላት ነት ፡ ጠበቀው ።

ደግሞ ፡ ረቱርዩስ ፡ የቤሮና ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ በዚህ ፡ ዘመ ን ፡ የውነት ፡ ምስክር ፡ ሆነ ። ካመት ፡ ፱፻፷፫ ጀምሮ ፡ የቀ ሳውስትንና ፡ የሕዝብን ፡ ኃጢአት ፡ እጅግ ፡ ሲገሥጽ ፡ ያነን ፡ ትምርትንም ፡ ሲሾር ፡ ሰው ፡ በጾምና ፡ በምጽዋት ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥጋዊ ፡ ስራም ፡ እንዲጸድቅ ፡ የምትል ። ስለዚህም ፡ ቀሳውስትና ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ አሳደዱት ።

ነገር ፡ ግን ፡ እንዲህ ፡ ያለ ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ እጅግ ፡ አልጠቀመ ም ፡ እንደ ፡ አንዳንድ ፡ ብልጭልጭ ፡ ነበረ ፡ እንጂ ፡ ከፀሓ ይ ፡ ወደ ፡ ተጨለመች ፡ ዋሻ ፡ የምትወድቅ ። ቤተ ፡ ክርስቲ ያንም ፡ ተጨለመች ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነገር ፡ ከሰው ፡ ነገር ፡ በታች ፡ ብርሃንም ፡ ከንቅብ ፡ በታች ፡ ሁናለችና ። የዚያን ፡

ጊዜም ፡ ጳጳስ ፡ አሥራኛ ፡ ዮሐንስ ፡ ትእዛዝን ፡ አደረገ ፡ ሰ ው ፡ ሁሉ ፡ የሞተውን ፡ ሰው ፡ ከቶ ፡ ቅዱስ ፡ ሁኖ ፡ እንደይ ቈጥረው ፡ የሮም ፡ ጳጳስ ፡ በግልጽ ፡ ሳይቀድሰው ።

ስለ ፡ ኃጢአት ፡ መፍታትና ፡ ማሠር ።

በርሱ ፡ ደግሞ ፡ የዚህ ፡ ዘመን ፡ ትምህርት ፡ ወትሮ ፡ ብ ዝታ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ራቀች ። ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ከቀ ሳውስታቸውና ፡ ከኤጲስቆጶሳታቸው ፡ ፈርተዋልና ፡ ኃጢአ ት ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ ሔዱ ፡ ጳጳስም ፡ ሁላቸውን ፡ ፈታ ። ስለዚህም ፡ አያሌ ፡ ኤጲስቆጶሳትና ፡ ሜትሮጶሊታ ኖች ፡ ተከራከሩበት ።

አራተኛ ፡ ምዕራፍ ፡፡

የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የትምህርትዋ ፡ የክርክ ርዋም ፡ ታሪክ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡፡

፩፡፡ በምሥራቅ ፡፡

በምሥራቅና ፡ በምዕራብ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያን ፡ መኻከል ፡ የነበረ ፡ ክርክር ፡፡ የዚህ ፡ ታላቅ ፡ መክንያት ፡ ቅናት ፡ ነበረ ፡ በቍንስታንቲኒያ ፡ ጳትርያርክና ፡ በሮም ፡ ጳጳስ ፡ መኻከል ፡፡ ደግሞ ፡ አንዳንድ ፡ መለየት ፡፡ በምሥራቅ ፡ ቄስ ፡ ሁሉ ፡ ምሽትን ፡ ለመጋባት ፡ ሳይቀደስ ፡ ሥልጣን ፡ ነበረለት ፡ በምዕራብ ፡ የለም ፡፡ በምሥራቅ ፡ ጾም ፡ በቅዳሜ ፡ ተከለከለ ፡ በምዕራብ ፡ ግን ፡ ታዘዘ ፡፡ ደግሞም ፡ በትምህርት ፡ አንዳንድ ፡ መለየት ፡ ነበረ ፡፡ እንደዚህ ፡ በትምህርታቸው ፡ ስለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡፡ የምሥራቅ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከአብና ፡ ከልጅ ፡ እንደ ደለይ ፡ እንደያነስም ፡ ብላ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ መሆኑን ፡ በዘላለም ፡ ከአብ ፡ ብቻ ፡ አለው ፡ ብላለች ፡፡ ይህነንም ፡ እንደዚህ ፡ ገለጸች ፡፡ በኒቂያ ፡ ያደረጉትን ፡ በቍንስታንቲኒያም ፡ ያጸኑትን ፡ ስምቦሎን ፡ የሃይማኖትን ፡ ምሳሌ ፡ እንዲያው ፡ ተቀበሉ ፡፡ በምዕራብም ፡ በቶሌደና ፡ በአኸን ፡ የጨመረበትን ፡ ነገር ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከአብና ፡ ከልጅ ፡ ይወጣል ፡ ብለው ፡ በምሥራቅ ፡ አልተቀበሉም ፡፡ በምዕራብ ፡ ግን ፡ የአርዮስን ፡ ትምርት ፡ ሊሽሩ ፡ ነበሩ ፡ ስለዚህ ፡ አሉ ፡፡ የእግዚአብሔር ፡ ባሕሪ ፡ በሦስት ፡ አካላት ፡ አንድ ፡ ነውና ፡፡ ልጅና ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ አብን ፡ አይመስሉም ፡ ብቻ ፡ ከአብ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ናቸው ፡ እንጂ ፡ ስለዚህ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከአብ ፡ ብቻ ፡ አይወጣም ፡ ከልጅ ፡ መውጣት ፡ ሲቀር ፡ አብና ፡ ልጅ ፡ አንድ ፡ ናቸውና ፡፡ አሁንም ፡ ለሁለታቸው ፡ እውነት ፡ ነበረ ፡ ፍቅርም ፡ ካልቀረባቸው ፡ ባልተለዩ ፡፡ እውነታቸውም ፡ በ

ተገለጠላቸው ፡፡ ባመት ፡ ፰፻፷፰ ኢግናትዮስ ፡ የቆንስታን ቲኒያ ፡ ጳትርያርክ ፡ ብርቱ ፡ ተግሣጽ ፡ አድርጓልና ፡ በሰው ፡ ኃጢአት ፡ ላይ ፡ እርሱ ፡ ተጻላ ፡ ከንግሥት ፡ ከቴዎደራ ፡ ጋ ራ ፡፡ ለኢግናትዮስም ፡ ሌሎች ፡ ጸላቶች ፡ ነበሩና ፡ በቆንስ ታንቲኒያ ፡ በቀሳውስት ፡ መኻከል ፡ ከርሳቸውም ፡ አንድ ፡ የተገዘተ ፡፡ የንጉሥ ፡ ሰዎች ፡ ከሌሎች ፡ ጸላቶቹ ፡ ጋራ ፡ አ ንድነት ፡ አደረጉ ፡ አንደን ፡ ፎቲዮስ ፡ የንጉሥ ፡ ጻፊ ፡ የነበ ረውን ፡ ሾሙ ፡ ጳትርያርክ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ኢግናትዮስን ፡ በሲኖደስ ፡ ሽረውት ፡፡ ኢግናትዮስ ፡ ግን ፡ ከኒቆላዎስ ፡ ፩፡ ረዳ ትን ፡ ለመነ ፡፡ ኒቆላዎስም ፡ መልክተኞቹን ፡ ወደ ፡ ቆንስታ ንቲኒያ ፡ ሰደደ ፡ ይህነን ፡ ነገር ፡ ይመረምሩ ፡ ዘንድ ፡፡ እሌ ህ ፡ ግን ፡ ብርን ፡ ተቀብለዋልና ፡ ለፎቲዮስ ፡ ተናገሩ ፡፡ ኒቆ ላዎስም ፡ ይህነን ፡ ነገር ፡ ሰምቶ ፡ ሲኖደስን ፡ በሮም ፡ ሰበሰ በ ፡ በርስዋም ፡ መለክተኞቹን ፡ ከፎቲዮስ ፡ ጋራ ፡ የገዘቱ ባት ፡ ኢግናትዮስንም ፡ መለሱ ፡፡ ይህነንም ፡ ጽፈት ፡ ወደ ፡ ቆንስታንቲኒያ ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ ሰደደው ፡፡ ከዚያ ፡ ግን ፡ ተ ላገጹበት ፡፡ ፎቲዮስም ፡ በቆንስታንቲኒያ ፡ ሌላውን ፡ ሲ ኖደስ ፡ ሰበሰበ ፡ ኒቆላዎስንም ፡ የሮምንም ፡ ቤተ ፡ ክርስ ቲያን ፡ በርስዋ ፡ ገዘተ ፡ ስለ ፡ ስህተታቸው ፡ በመንፈስ ፡ ቅ ዱስ ፡ ትምህርት ፡ ብሎ ፡፡ ኒቆላዎስ ፡ ደግሞ ፡ እንደዚህ ፡ ተቀ በለው ፡ መጻሕፍትንም ፡ አስጻፈ ፡ በምሥራቅ ፡ ቤተ ፡ ክር ስቲያን ፡ ላይ ፡ እንደዚህም ፡ መለየታቸው ፡ ጸና ፡፡

ባመትም ፡ ፰፻፷፯ ሚካኤል ፡ ቄሣር ፡ በባሲልዮስ ፡ እ ጅ ፡ ሞተ ፡ ፎቲዮስም ፡ ባሲልዮስን ፡ ባላቈረበ ፡ ጊዜ ፡ ስ ለ ፡ መግደሉ ፡ ተሻረ ፡ ኢግናትዮስም ፡ ወደ ፡ ስፍራው ፡ ተ መለሰ ፡፡ አሁንም ፡ አንድነት ፡ በፈለገ ፡ ጊዜ ፡ ከሮም ፡ ጳጳ ስ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ሃድርያን ፡ ላከ ፡፡ ሃድርያንም ፡ በሮም ፡ ሲ ኖደስን ፡ ሰበሰበ ፡ በርስዋም ፡ የቆንስታንቲኒያን ፡ ሲኖደስ ፡ በፎቲዮስ ፡ የተሰበሰበችን ፡ ወገዘ ፡ ፎቲዮስንም ፡ ገዘቶ ት ፡ ኢግናትዮስን ፡ ተቀበለ ፡፡ አሁን ፡ ግን ፡ ክርክር ፡ ተነሣ ፡ ስለ ፡ ቡልጋርያ ፡ ሕዝብ ፡ ሃይማኖትን ፡ የተቀበሉ ፡ በቄርሎ ስና ፡ በሜቶድያስ ፡ ትምህርት ፡፡ ቆንስታንቲኒያ ፡ 'ይህች ፡ ሕዝብ ፡ ግንዘቤ ፡ ናት' ፡ ስትል ፡፡ ሮም ፡ 'የኔ ፡ ናት' ፡ አለች ፡፡

ደህኝ ፡ ክርክርም ፡ ስትኖር ፡ ኢግናትዮስ ፡ሞተ ፡፡ ፎቲዮስ ም ፡ ተመልሶ ፡ ተሾመ ፡፡ ወደጅነትም ፡ ሲፈልግ ፡ ከሮም ፡ ጳጳስ ፡ ከዮሐንስ ፡ ፰፤ ጋራ ፡ ዮሐንስ ፡ እሺ ፡ አለ ፡ ፎቲዮስ ፡ መበደሉን ፡ ቢያስታውቅ ፡ ቢያዝንም ፡ ቡልጋርያም ፡ ለሮ ም ፡ ቢተው ፡፡ ለዚህም ፡ ፎቲዮስ ፡ እምቢ ፡ ባለ ፡ ጊዜ ፡ ዮሐ ንስ ፡ ወገዘው ፡፡ አሁንም ፡ አንድነት ፡ የላቸውም ፡ ቄሣር ፡ ሌዎን ፡ ፊሎሶፎስ ፡ ፎቲዮስን ፡ እስኪሽር ፡ ድረስ ፡ ባመ ት ፡ ፰፻፺፩፤ ባመት ፡ ፲፻፶፬፤ የቆንስታንቲኒያ ፡ ጳትርያርክ ፡ ሚካኤል ፡ ኬሩላርዮስ ፡ ፀብን ፡ ደግሞ ፡ አስነሣው ፡፡ የዚ ያን ፡ ጊዜም ፡ ስለ ፡ ቍርባን ፡ እንጀራ ፡ ነበረ ፡፡ በምዕራብ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ካመት ፡ ፱፻፤ ወዲህ ፡ ጀመረች ፡ ለቍር ባን ፡ ያልመጸጸውን ፡ እንጀራ ፡ ትወስድ ፡ ዘንድ ፡፡ ኬሩላ ርዮስም ፡ አሁን ፡ በዚህ ፡ እጅግ ፡ ተቈጥቶ ፡ የምዕራብ ፡ ክርስቲያኖች ፡ የአይሁድ ፡ ወገን ፡ ናቸው ፡ አለ ፡ አ ጺሞች ንም ፡ አላቸው ፡፡ አሁንም ፡ ታላቅ ፡ ክርክር ፡ ተነሣ ፡ የቆን ስታንቲኒያ ፡ ቄሣርም ፡ ያስታርቃቸው ፡ ዘንድ ፡ ደከመ ፡ ነገ ር ፡ ግን ፡ አልሆነለትም ፡፡

፪፤ በምዕራብ ፡፡

በዚህ ፡ ዘመን ፡ በምዕራብ ፡ አንድ ፡ ታላቅ ፡ መምህር ፡ ረ ባኑስ ፡ ማውረስ ፡ ነበረ ፡፡ እርሱ ፡ በፉልዳ ፡ የነበረች ፡ የታ ላቅ ፡ ገደም ፡ መምህር ፡ ነበረ ፡፡ እርሱም ፡ እጅግ ፡ ጻፈ ፡ መ ጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ያበራ ፡ ዘንድ ፡፡ እንዲሁም ፡ የሀልበርስ ታድ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ሃይሞ ፡፡ አንድ ፡ ሞናክሴም ፡ ድሩትመ ር ፡፡ አንድም ፡ ታላቅ ፡ ፊሎሶፎስ ፡ በኢርላንድ ፡ ተነሣ ፡ ስ ሙን ፡ ዮሐንስ ፡ ስኮቱስ ፡ ኤሪጌና ፡ የሚሉት ፡፡ ሌሎችም ፡ በ ውቀታቸው ፡ የታወቁ ፡ መምህራን ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ እሌ ህ ፡ ናቸው ፡፡ የበርኬሊ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ኦቶ ፡፡ ገርበርትም ፡፡ የሻርትርም ፡ መምህር ፡ ፋልበርት ፡ የከንትርብሪም ፡ ሜት ሮጶሊታን ፡ ላንፍራንክ ፡፡ ቤርንጋርም ፡፡ ብሩኖም ፡፡

በዚህ ፡ ዘመንም ፡ ያውጉስቲኑስን ፡ መጻሕፍት ፡ ሁሉ ፡ ተቀበሉ ፡ እጅግ ፡ ሳይመረምርዋቸው ፡፡ ስለዚህም ፡ ትምር ቱን ፡ ስለ ፡ ዘላለም ፡ መምረጽ ፡ ጣሉት ፡፡ አንድም ፡ ጎት

ሻልክ ፡ የሚሉት ፡ ሞናክሴ ፡ ይህነን ፡ ትምርት ፡ ባስተማ
ረ ፡ ጊዜ ፡ ተገዝተ ፡ በግዞትም ፡ ሞተ ፡ ፳፩፡ አመት ፡ ከታሠ
ረ ፡ በኋላ ፡፡ ነትሻልክ ፡ ግን ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ሌሎች ፡ ተነ
ሡ ፡ ይህችን ፡ ትምህርት ፡ ያስተማሩ ፡ እንደ ፡ ራትራምኑስ ፡
ሉጱስ ፡፡

ሌላ ፡ ክርክርም ፡ ተነሣ ፡ ስለ ፡ ቍርባን ፡፡ ጳሻስዩስ ፡ ረድ
በርቱስ ፡ እርሱ ፡ ሞነክሴ ፡ የነበረ ፡ ባመት ፡ ፹፻፴፩፡ ትምርት
ን ፡ አወጣ ፡ እንደይህ ፡ ሲል ፡፡ ቍርባን ፡ ሲቀደስ ፡ የቍርባን ፡
እንጀራ ፡ በውነት ፡ እንጀራ ፡ ሁኖ ፡ አይኖርም ፡ የንጀራ ፡ ባ
ሕሪ ፡ በተአምራት ፡ ይጠፋል ፡ እንጀ ፡ ለማየትም ፡ ብቻ ፡ ለ
መቅመስም ፡ እንጀራ ፡ ይኖራል ፡ ምእምናንን ፡ እንዲያስ
ፈራ ፡፡ በባሕሪው ፡ መለወጥ ፡ ግን ፡ የክርስቶስ ፡ እውነተኛ ፡
ገላው ፡ ይሆናል ፡ ብሎ ፡፡ ይህነንም ፡ መጽሐፍ ፡ ለንጉሥ ፡
በሰጠ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሥ ፡ ራትራምኑስን ፡ ጠየቀ ፡ ስለ ፡ ትምር
ቱ ፡ እውነት ፡፡ ያም ፡ የጳሻስዮስ ፡ ትምርት ፡ እውነት ፡ እን
ዳይደለ ፡ ገለጸ ፡፡ የክርስቶስም ፡ ገላ ፡ በቍርባን ፡ ለምእ
ምናን ፡ ሃይማኖት ፡ እንዲከፈል ፡ እንጀራ ፡ እንጀራ ፡ ሲኖ
ር ፡ ሳይለወጥም ፡ አለ ፡፡ ዮሐንስ ፡ ስኮቱስ ፡ ኤሪጌናም ፡ ስ
ለዚህ ፡ ጻፈ ፡ በመጽሐፉም ፡ አለ ፡፡ የቍርባን ፡ ቅዳሴ ፡ መል
ክና ፡ ምልክት ፡ አራቡንም ፡ እንዲሆን ፡፡ ጳጳስ ፡ ግን ፡ የጳ
ሻስዩስ ፡ ረድበርቱስን ፡ ትምህርት ፡ እውነት ፡ እንደ ፡ ሆነ
ች ፡ ተቀበለ ፡ ከርስዋም ፡ የተለየችውን ፡ ገዘተ ፡፡

ባመትም ፡ ፲፻፵፱፡ ቤርንጋር ፡ በዚች ፡ በጳሻስዩስ ፡ ትም
ርት ፡ ላይ ፡ ተከራከረ ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስም ፡ ጋራ ፡ እንድት
ጻላ ፡ አሳየ ፡፡ በኋላም ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ ሲመጣ ፡ የኤጲስቆጶ
ሳት ፡ አለቆች ፡ በግድ ፡ አገዱት ፡ የረድበርትን ፡ ትምርት ፡ ይ
ቀበል ፡ የምልም ፡ ዘንድ ፡ ከፍርሃቱ ፡ የተነሣ ፡ በለዚያ ፡ ት
እዛዝ ፡ እንደይህ ፡ ሲል ፡፡ ቄስ ፡ ቍርባንን ፡ ከቀደሰ ፡ በኋላ ፡
እንጀራ ፡ በጣም ፡ ይለወጣል ፡ የሚቍርብም ፡ ሰው ፡ ሁ
ሉ ፡ የክርስቶስን ፡ እውነተኛ ፡ ገላ ፡ ባፉ ፡ ይቀበላል ፡ በጥርሱ
ም ፡ ይነክሰዋል ፡ በጕሮሮውም ፡ ይውጠዋል ፡ እንደ ፡ ሌላ ፡
መብልም ፡ ሁሉ ፡ ያደርግበታል ፡፡ እንደይህ ፡ ተጨለመች ፡ የ
ክርስቶስ ፡ ብርሃን ፡ ሲል ፡፡ የሚያድን ፡ እርሱ ፡ መንፈስ ፡

ነው :: ሥጋ : ግን : አይጠቅምም :: ቤርንጋርም : የዚያን : ጊዜ : በፍርሃት : መክንያት : በሃይማኖቱ : ደክሞ : የርሱን : የተሻለችውን : እውነተኛዪቱን : ትምህርት : ካደ : በጸላቶቹም : ተፈታ :: ነገር : ግን : ከሮም : ከተሰናበተ : በኋላ : ኋይሉ : ተመለሰች : እርሱም : በስሕተቱ : አዘነ : መጽሐፍንም : ጻፈ : በሮም : ትምርት : ላይ : እንደ ፡ ሲል :: ሮም : የሐዋርያት : ዙፋን : አይደለችም : የሰይጣን : እንጅ :: ከዚያም : በኋላ : ግን : ፪፤ ጎርጎርዮስ : ጳጳስ : ሁለተኛ : ጊዜ : ወደ : ሮም : አስመጣው : ከዚያም : ሁለተኛ : ጊዜ : በታላቅ : ፍርሃቱ : ካደ :: በኋላም : አዝኖ : ወደ : ታናሽ : ደሴት : ሔደ : ከዚያም : ታሪኩን : ጻፈ : በመጽሐፉም : ሰውን : ሁሉን : ለመነ : ስለ : ክህደቱ : ያዝንለት : ዘንድ : የእግዚአብሔርንም : ምህረት : ይለምንለት : ዘንድ ::

ስለ : መናፈቃን ::

በዚህ : ዘመንም : ጳውሊኪያኖች : በብዙ : ስፍራ : ተዘርግተው : ወደ : ምዕራብ : መጡ :: ባመት : ፬፲፤፤ በአኩታኒያ : ነበሩ :: ሰባት : አመትም : ከዚያ : ወዲያ : እንደርሳቸው : መናፈቃን : በኦርሌአንስ : ተገኙ : ከርሳቸውም : ፲፫፤ ስለ : ኑፋቄያቸው : ሞቱ ::

ሌሎች : መናፈቃንም : በዚህ : ዘመን : ባያሌ : ስፍራ : ተገኙ : ሁላቸውም : ከግኖስቲኮች : ትምህርት : የተቀበሉ : ይመስላሉ ::

የቤት ፡ ክርስቲያን ፡
ታሪክ ፡

አምስተኛ ፡ ክፍል ።

ከሰባተኛ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ ጀምሮ ፡
እስከ ፡ ስምንተኛ ፡ ቦኒፋኪዩስ ፡ ድረስ ።

ከልደት ፡ አመትም ፡ ከ፲፻፸፫ ፡ ጀምሮ ፡
እስከ ፡ ፲፫፻፫ ፡ ድረስ ።

በዚህ ፡ ዘመንም ፡ የነገሡ ፡ ነገሥታት ፡ እሊህ ፡ ናቸው ፡፡

፩፤ በምሥራቅ ፡፡

1. ኒኬፎርስ ፡ በታኒያቴስ ፡ ፲፻፸፰፡፡
2. እስክንድር ፡ ኮምኔኖስ ፡፡ ፲፻፹፩፡፡
3. አሌክስዮስ ፡ ፲፩፻፫፡፡
4. ዮሐንስ ፡ ኮምኔኖስ ፡ ፲፩፻፰፡፡
5. መጀመርያ ፡ ማኑኤል ፡ ኮምኔኖስ ፡ ፲፩፵፫፡፡
6. ሁለተኛ ፡ አሌክሲዮስ ፡ ኮምኔኖስ ፡ ፲፩፹፡፡
7. አንድሮኒኮስ ፡ ኮምኔኖስ ፡ ፲፩፹፫፡፡
8. ይስሐቅ ፡ አንጌሎስ ፡ ፲፩፹፭፡፡
9. ጎትፍሪድ ፡ ከቡልዮንና ፡ በልድዊን ፡ ወንድሙ ፡ የየሩሳሌም ፡ ነገሥታት ፡፡
10. ሳህለዲን ፡ የስላሞች ፡ ንጉሥ ፡ በምሥር ፡ ፲፩፸፩፡፡
11. ጀንጊስኻን ፡ የሞንጎሎች ፡ ንጉሥ ፡ ፲፪፻፪፡፡
12. ባልድዊንና ፡ ሀይንሪክ ፡ የላቲኖች ፡ ነገሥታት ፡ በቁንስታንታኒያ ፡፡ ፲፪፻፬፡፡
13. ቴዎደሮስ ፡ ለስካሪስ ፡ የሩም ፡ ንጉሥ ፡ በኒቅያ ፡ ፲፪፻፭፡፡
14. ሮበርት ፡ የላቲኖች ፡ ንጉሥ ፡ በቁንስታንቲኒያ ፡ ፲፪፳፩፡፡
15. ዮሐንስ ፡ ዋታጼስ ፡ የሩም ፡ ንጉሥ ፡ ፲፪፳፪፡፡
16. ሁለተኛ ፡ በልድዊን ፡ የላቲኖች ፡ ንጉሥ ፡ በቁንስታንቲኒያ ፡ ፲፪፳፬፡፡
17. ሁለተኛ ፡ ቴዎደሮስ ፡ ለስካሪስ ፡ የሩም ፡ ንጉሥ ፡፡ ፲፪፶፭፡፡
18. ሚኻኤል ፡ ጳሌዎሎጎስ ፡ የሩም ፡ ንጉሥ ፡ በቁንስታንቲኒያ ፡ ፲፪፷፩፤
19. ሁለተኛ ፡ አንድሮኒኮስ ፡ የሩም ፡ ንጉሥ ፡፡ ፲፪፹፫፡፡

፪፤ በምዕራብ ፡፡

1. ሀይንሪክ ፡ ፬፤ የንምሳ ፡ ንጉሥ ፡ ከ፲፻፷፪፤ ጀምሮ ፡፡
2. ሀይንሪክ ፡ ፭፤ የንምሳ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፩፻፭፡፡

3. ሉድዊግ ፡ ፯፤ የፈረንስ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፩፻፯፡፡
4. ሎታር ፡ ፫፤ የፈረንስ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፩፳፭፡፡
5. ሉድዊግ ፡ ፯፤ የፈረንስ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፩፴፯፡፡
6. ኮንረድ ፡ የንምሳ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፩፴፰፡፡
7. ፍሪድሪኽ ፡ ፩፤ የንምሳ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፩፶፪፤
8. ሀንሪ ፡ ፪፤ የእንግሊጣር ፡ ንጉሥ ፡ ፲፩፶፬፡፡
9. ፊልጶስ ፡ ፪፤ የፈረንስ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፩፹፡፡
10. ሀይንሪኽ ፡ ፮፤ የንምሳ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፩፺፩፤
11. ዮሐንስ ፡ አለምድር ፡ የእንግሊጣር ፡ ንጉሥ ፡ ፲፩፺፱፤
12. ፍሪድሪኽ ፡ ፪፤ የንምሳ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፪፲፭፡፡
13. ሀንሪ ፡ ፫፤ የእንግሊጣር ፡ ንጉሥ ፡ ፲፪፲፮፡፡
14. ሉድዊግ ፡ ፰፤ የፈረንስ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፪፳፫፡፡
15. ሉድዊግ ፡ ፱፤ ቅዱስ ፡ የሚሉት ፡ የፈረንስ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፪፳፮፡፡
16. ኮንረድ ፡ ፬፤ የንምሳ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፪፶፡፡
17. ኤድዋርድ ፡ ፩፤ የእንግሊጣር ፡ ንጉሥ ፡ ፲፪፸፪፡፡
18. ሩደልፍ ፡ ፩፤ የንምሳ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፪፸፫፡፡
19. ፊልጶስ ፡ ፫፤ የፈረንስ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፪፸፡፡
20. ፊልጶስ ፡ ፬፤ የፈረንስ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፪፹፬፡፡
21. አደልፍ ፡ የንምሳ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፪፺፩፡፡

፫፤ የሮም ፡ ጳጳሳት ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ እሌህ ፡ ናቸው ፡፡

1. ጎርጎርዮስ ፡ ፯፤ ፲፻፸፫፡፡
2. ክሌሜንስ ፡ ፲፻፹፡፡ ከጎርጎርዮስ ፡ ጋራ ፡፡
3. ቪክቶር ፡ ፫፤ ፲፻፹፯፡፡
4. ዑርባን ፡ ፪፤ ፲፻፹፰፡፡
5. ጳሻሊስ ፡ ፪፤ ፲፻፹፱፡፡
6. ግላስዩስና ፡ ጎርጎርዩስ ፡ ፰፤ ፲፩፲፰፤
7. ካሊክስቱስ ፡ ፲፩፲፱፡፡
8. ኬሌስቲኑስና ፡ ሆኖርዩስ ፡ ፪፤ ፲፩፳፬፡፡
9. ኢኖኬንቲዩስ ፡ ፪፡፡ አናክሌቱስ ፡ ፪፤ ፲፩፴፡፡
10. ኬሌስቲኑስ ፡ ፪፤ ፲፩፵፫፡፡

11. ሉኪዮስ ፡ ፪፤ ፲፩፵፬።
12. ኤውጌኒዮስ ፡ ፫፤ ፲፩፵፭።
13. አናስታስዮስ ፡ ፬፤ ፲፩፶፫።
14. ሀድርያን ፡ ፬፤ ፲፩፶፬።
15. እስክንድር ፡ ፫። ዊክቶርም ። ጳኻሊስም ። ከሊክስቱስም ። ፲፩፷።
16. ሉኪዮስ ፡ ፫፤ ፲፩፹፩።
17. ውርባኑስ ፡ ፫። ፲፩፹፭።
18. ጎርጎርዮስ ፡ ፰፤ ፲፩፹፯።
19. ክሌሜንስ ፡ ፫፤ ፲፩፹፰።
20. ኬሌስቲኑስ ፡ ፫፤ ፲፩፺፩።
21. ኢኖኬንቲዮስ ፡ ፫፤ ፲፩፺፰።
22. ሆኖርዮስ ፡ ፫፤ ፲፪፲፯።
23. ጎርጎርዮስ ፡ ፱፤ ፲፪፳፯።
24. ኬሌስቲኑስ ፡ ፬። ኢኖኬንቲዮስ ፡ ፬፤ ፲፪፵፩።
25. እስክንድር ፡ ፬፤ ፲፪፶፬።
26. ውርባኑስ ፡ ፬፤ ፲፪፷፩።
27. ክሌሜንስ ፡ ፬፤ ፲፪፷፭።
28. ጎርጎርዮስ ፡ ፲፤ ፲፪፸፩።
29. ኢኖኬንቲዮስ ፡ ፭። ሀድርያን ፡ ፭። ዮሐንስ ፡ ፳፩። ፲፪፸፯።
30. ኒቆላዎስ ፡ ፲፪፸፯።
31. ማርቲኑስ ፡ ፬፤ ፲፪፹።
32. ሆኖርዮስ ፡ ፬፤ ፲፪፹፯።
33. ኒቆላዎስ ፡ ፬፤ ፲፪፹፰።
34. ኬሌስቲኑስ ፡ ፭። ፲፪፺፬።
35. ቦኒፋኪዮስ ፡ ፰። ፲፪፺፬።

መጀመርያ፡ምዕራፍ።

ስለ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡መዠረጋት።

፩፡ በእስያ።

በዚህ፡ዘመን፡ታላቅ፡ሕዝብ፡ተነሣች፡በመኻከለኛ፡እስያ፡በዓለም፡ሁሉ፡የምትዘረጋ። የጨንም፡የህንድም፡የፈርስም፡መንግሥቶችን፡ገልብጠው፡ወደ፡ኤውሮጳ፡መጡ፡የኤውሮጳንም፡አሕዛብ፡ሊያስገዙ፡ቀረቡ፡ደር፡እግዚአብሔር፡ከለከላቸው። ይህች፡ሕዝብም፡የሞንጎሎት፡ሕዝብ፡ትባላለች። በመኻከላቸው፡የኔስቶርዮስ፡ወገን፡ወንጌልን፡አስተማረ፡ከርሳቸውም፡ብዙ፡ሃይማኖትን፡ተቀበሉ፡ነገር፡ግን፡ሃይማኖት፡ኃይለኛ፡አልነበረምና፡የእስላም፡ትምርት፡አሸነፈቸው።

፪፡ በኤውሮጳ።

በዚህ፡ዘመን፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ከጶሎኒያ፡ወደ፡ጶመራኒያ፡ገባች፡ኦቶም፡የበምበርግ፡ኤጲስቆጶስ፡ነፍሱን፡ሰጠ፡ያችን፡ሕዝብ፡ሁሉ፡ወደ፡ክርስቲያን፡ሃይማኖት፡ይወስድ፡ዘንድ። እጅግ፡ሰዎችንም፡አጠመቀ፡ብላቴኖችንም፡ወደርሱ፡ሰብስቦ፡አስተማራቸው። በእግዚአብሔርም፡በረከት፡ሆነለት፡በጥቂት፡ወራት፡በጶመራኒያ፡ሁሉ፡የወንጌልን፡ዘር፡ይዘራ፡ዘንድ፡

አንድ፡ቄስም፡ነበረ፡በዚህ፡ዘመን፡ካለማወቁ፡ከኃጢአቱም፡ወደ፡እግዚአብሔር፡የተመለሰ፡ከዚያም፡ጀምሮ፡የተቀበለውን፡ብርሃን፡ወደ፡አሕዛብ፡ወሰደ፡በርሳቸው፡መኻከል፡ያበራ፡ዘንድ። ስሙም፡ዊጶሊን፡ነው። በኋላም፡ወንጌልን፡በኦልደንቡርግ፡ሰበከ፡የኦልደንቡርግም፡ኤጲስቆጶስ፡ሆነ። ኬሌስቲኑስ፡፫፡ የሞናኵስትን፡ጉባኤዎች፡አደረገ፡የክርስቶስ፡ወታደር፡የተባሉ። እርሳቸውም፡በጋሻ፡ጾር፡ሃይማኖትን፡በሊፍላንድ፡አገር፡ሊዘርጉ፡ነበረ። እርሳቸውም፡የጵሩስያን፡ሕዝብ፡ወደ፡ቤተ፡ክርስቲያን፡ለማግባት፡አገድዋቸው።

ሁለተኛ ፡ ምዕራፍ ።

የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዓት ።

የጳጳሳት ፡ ታሪክ ።

በዚህ ፡ ዘመን ፡ መጀመርያ ፡ አንድ ፡ ጳጳስ ፡ ጀመረ ፡ በቀድሞት ፡ ጳጳሳት ፡ ሁሉ ፡ የበረታ ፡ ሌላ ፡ ነገርንም ፡ ያልወደደ ፡ የሮም ፡ ጳጳስ ፡ የእግዚአብሔር ፡ እንደኔ ፡ በምድር ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ አንጅ ። እርሱም ፡ ጳጳስ ፡ ሳይሆን ፡ ሂልድብራንድ ፡ ተባለ ፡ ከተሾመ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ስሙን ፡ ሰባተኛ ፡ ጎርጎርዮስ ፡ አለው ።

ጎርጎርዮስ ፡ ፯፡ እንደዚህ ፡ አለ ። የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥልጣን ፡ ብቻ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተሰራች ፡ ናት ። ሌላ ፡ ሥልጣን ፡ ሁሉ ፡ ከሰው ፡ ትዕቢት ፡ ተነሣች ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ተከክልዋልና ። እርሱም ፡ በምድር ፡ ያለች ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አለቃ ፡ ሁኖ ፡ መስሎት ፡ ሥልጣን ፡ ሁሉ ፡ በጄ ፡ ናት ፡ ለኔም ፡ ተሰጠች ፡ አለ ። እርሱም ፡ ፈቀደ ፡ የመንግሥት ፡ ሹማምት ፡ ሁሉ ፡ አንደኛችን ፡ እንደያስቡ ፡ አንደኛችንም ፡ እንደያደርጉ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ ያለ ፡ ፈቃደ ፡ ሥልጣናቸውንም ፡ ገንዘባቸውንም ፡ ሁሉን ፡ ለቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ እንዲሰጡ ፡ እርሱ ፡ በፈንታው ፡ ለተሾመ ። ለዚህም ፡ የማይታዘዝ ፡ የቅዱስ ፡ ጴጥሮስ ፡ መቅሠፍት ፡ ገባበት ፡ በጳጳስ ፡ እጅ ፡ እርሱ ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ የሚዘጋበት ። ትእዛዝንም ፡ አደረገ ፡ ቄስና ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ሁሉ ፡ ሹመቱን ፡ በብር ፡ ያገኘ ፡ ሹመቱ ፡ እንዲሻር ፡ ምሽትንም ፡ ያገባ ፡ እንዲሰደት ፡ ወይስ ፡ ከቅደሲው ፡ እንዲፈታ ። ባመትም ፡ ፲፻፸፭፡ በሲኖደስ ፡ የመንግሥትን ፡ ሹማምት ፡ ሁሉ ፡ ከለከለ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ አገልጋዮች ፡ ይሾሙ ፡ ዘንድ ። ነገር ፡ ግን ፡ አራተኛ ፡ ሀይንሪኽ ፡ ለጳጳስ ፡ መታዘዝ ፡ አልወደደም ፡ እርሱም ፡ ግፈኛ ፡ ንጉሥ ፡ ነበረ ፡ ስለ ፡ ግፏም ፡ ሰዎቹ ፡ አልወደዱትም ። ሀይንሪኽ ፡ በፊት ፡ የጳጳስ ፡ ወዳጅ ፡ ነበረ ፡ ጳጳስ ፡ እስኪከለክለው ፡ ድረስ ። የ

ዚያን ፡ ጊዜ ፡ ጳጳስ ፡ ሀይንሪኽን ፡ መግዘት ፡ ፈለገ ፡ ደሮ ፡ ሀይንሪኽ ፡ ጳጳስን ፡ ሻረ ፡ ብርቱንም ፡ መልእክት ፡ ለጳጳስ ፡ ጻፈ ። ጳጳስ ፡ ግን ፡ አሁን ፡ ሀይንሪኽን ፡ ወገዘ ፡ ሕዝቡን ም ፡ ከመታዘዝ ፡ ፈታ ። ሰዎችም ፡ ጎርጎርዮስን ፡ በገሠጹ ፡ ጊዜ ፡ ሲሉ ። ንጉሡን ፡ መግዘት ፡ መንግሥቱንም ፡ መሻ ር ፡ አይገባም ፡ ጎርጎርዮስ ፡ እንዲህ ፡ አላቸው ። ክርስቶ ስ ፡ ኃይል ፡ ከሰጠኝ ፡ በክፎች ፡ መናፍስት ፡ ላይ ፡ እንዴት ፡ ይመስላችኋል ፡ ሥልጣን ፡ እንደልሰጠኝ ፡ በሰይጣን ፡ ባሮ ች ፡ በነገሥታት ፡ ላይ ። ሀይንሪኽ ፡ ግን ፡ ከሕዝቡም ፡ ጋራ ፡ ተጸልትዋልና ፡ ጳጳስ ፡ ሁሉን ፡ ተቻለው ። አሁንም ፡ ሀይን ሪክ ፡ ፍትሐትን ፡ ፈለገ ፡ ከጳጳስ ፡ ስለዚህም ፡ ፲፻፸፯፤ በክረ ምት ፡ ብርድም ፡ እጅግ ፡ በጸና ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ ሔደ ። ከዚያም ፡ ጳጳስ ፡ ፫፤ ቀንና ፡ ፫፤ ሌሊት ፡ ንጉሡን ፡ በሜዳ ፡ ለብቻው ፡ በብርድ ፡ አስቀመጠው ፡ አረቁቱ ፡ ሁኖ ፡ በኋላ ም ፡ ወደርሱ ፡ አስመጣው ። ሀይንሪኽም ፡ ተስፋ ፡ ባስደረገ ለት ፡ ጊዜ ፡ ከጳጳስ ፡ ጋራ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ክብር ፡ ብ ቻ ፡ ይስራ ፡ ዘንድ ፡ ፈታው ። መንግሥቱንም ፡ መለሰለት ። አሁን ፡ ግን ፡ በኢጣልያና ፡ በንምሳ ፡ የነበሩ ፡ አሕዛቡ ፡ ን ጉሣቸውን ፡ ተቈጡ ፡ እንዲህ ፡ ስለ ፡ ተዋረደ ፡ ለጳጳስ ፡ አ ደ ስ ፡ ንጉሡንም ፡ መረጹ ፡ ጳጳስም ፡ አሰተኛ ፡ ሆነ ፡ ላደ ስ ፡ ንጉሥም ፡ የመንግሥትን ፡ አክሊል ፡ ሰደደ ። ሀይንሪ ኽም ፡ በኋላ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ በተዋጋ ፡ ጊዜ ፡ ገደለው ፡ በሲኖ ደስም ፡ በኢጣልያ ፡ የጳጳስን ፡ ሹመት ፡ ሻረ ፡ ሌላውን ም ፡ ጳጳስን ፡ አደረገ ። በኋላም ፡ ሀይንሪኽ ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ መ ጣ ፡ ከሠራዊቱ ፡ ጋራ ፡ ጳጳስንም ፡ ከበበ ፡ ወደ ፡ እምባው ፡ የሸሸ ፡ አንድ ፡ ታላቅ ፡ ወደጀ ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አገር ፡ ወደ ፡ ሳ ለርኖ ፡ እስኪወስደው ፡ ድረስ ። ከዚያም ፡ ሞተ ፡ ባመት ፡ ፲፻፹፭፤

የጳጳሳት ፡ ክብርና ፡ ኃይል ፡ እጅግ ፡ በዛች ፡ ጳጳስ ፡ ውር ባኑስ ፡ የምዕራብን ፡ ክርስቲያናት ፡ ሁሉን ፡ ወደ ፡ የሩሳሌ ም ፡ ይሰድ ፡ ዘንድ ፡ በጀመረ ፡ ጊዜ ፡ የጌታን ፡ መቃበር ፡ ከስ ላሞች ፡ እጅ ፡ ይወስዱ ፡ ዘንድ ። አንድ ፡ ባሕታዊ ፡ ጴጥሮ ስ ፡ ካሚንስ ፡ መጥትዋልና ፡ ጳጳስን ፡ ተናገረ ፡ እስላሞች ፡

የረሳሌምን ፡ እንደ ፡ ወሰዱ ፡ ቅዱስ ፡ ስፍራውንም ፡ እን ደ ፡ አረኰሱ ፡ እጅግም ፡ ብርቱ ፡ መከራ ፡ እንደ ፡ አደረጉ ፡ በክ ርስቲያን ፡ ላይ ፡ ብሎ ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ውርባኑስ ፡ ያነን ፡ ባሕታዊን ፡ ሰደደ ፡ ወደ ፡ ፍርንጆች ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ሰውን ፡ ሁ ሉን ፡ የተቀደሰውን ፡ ጾር ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ሊፈልግ ፡፡ ባመ ትም ፡ ፲፻፺፭፡ ጳጳስ ፡ ታላቅ ፡ ጉባኤን ፡ ሰበሰበ ፡ በጲያጨን ጻ ፡ በክለርሞንትም ፡፡ ወደዚህ ፡ ጾር ፡ የሚገባ ፡ ሰው ፡ ሁ ሉ ፡ ኀጢአቱ ፡ ቀረለት ፡ ቅዱስ ፡ ወታደርም ፡ ተባላ ፡፡ በመ ስቀልም ፡ ተመለከተ ፡ የመስቀልም ፡ ወታደር ፡ ሆነ ፡፡ ይህ ፡ ነገርም ፡ ወደዚያ ፡ ዘመን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ ልባቸው ፡ ገ ብትዋል ፡ ጳጳስንም ፡ እጅግ ፡ አከበረበት ፡፡

የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ጳጳስ ፡ ተጻላ ፡ ከፊሊጶስ ፡ ከፍራንስ ፡ ንጉሥ ፡ ጋራ ፡ ምሽቱን ፡ አውጥቶ ፡ ያንድ ፡ መኰንን ፡ ምሽ ት ፡ ስላሳታት ፡ ምሽቱን ፡ አድርግዋት ፡፡ ለያሌ ፡ ኤጲስቆጶ ሳትም ፡ ኀጢአቱን ፡ በነ ፡ አደረጉት ፡ አንድ ፡ ኢቮ ፡ የሚሉ ት ፡ ግን ፡ በኀጢአቱ ፡ ገሠጸው ፡ ስለ ፡ ተግሣጹም ፡ ንጉሥ ፡ ወደ ፡ ግዞት ፡ ጨመረው ፡፡ ጳጳስም ፡ ንጉሥን ፡ ገዘተ ፡፡

ጳሻሊስም ፡ ፪፡ ከ፬፡ ሀይንሪኽ ፡ ጋራ ፡ ተጋደለ ፡፡ የሀይንሪ ኽ ፡ ልጅም ፡ ሀይንሪኽ ፡ ፭፡ እርሱ ፡ በጳጳስ ፡ ሥልጣን ፡ ባባ ቱ ፡ ላይ ፡ የተነሣ ፡ ጳጳስን ፡ እሺ ፡ አለው ፡ መንግሥቱ ፡ እ ስኪጸና ፡ ድረስ ፡ በኋላም ፡ ጳጳስን ፡ ካለቆቹ ፡ ጋራ ፡ አሠረ ፡ ፈቃዱን ፡ ለማድረግ ፡ ተስፈ ፡ እስኪያስደርጉ ፡ ድረስ ፡፡ ጳጳ ስ ፡ ግን ፡ ከተፈታ ፡ በኋላ ፡ ተስፈውን ፡ አፈረሰ ፡፡

ባመትም ፡ ፲፻፳፪፡ ከሊክስቱስ ፡ ፪፡ ከንጉሥ ፡ ጋራ ፡ ተሰ ማማ ፡ ኤጲስቆጶሳትንና ፡ የገደሞችን ፡ መምህራን ፡ በሥ ርዓት ፡ የተመረጹ ፡ እንዲሆኑ ፡ ማጽናታቸውን ፡ ከንጉሥ ፡ እንዲቀበሉ ፡ ንጉሥ ፡ ይሾማቸው ፡ ዘንድ ፡ ለሹመታቸው ም ፡ ምልክት ፡ በትርን ፡ ይቀበሉ ፡ ዘንድ ፡፡ በዚህ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ደስ ፡ አለው ፡፡

ባመትም ፡ ፲፻፴፡ ሆኖርዩስ ፡ ፪፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ኢኖኬንቲ ዩስ ፡ ፪፡ ተመረጸ ፡፡ አንድ ፡ ከኤጲስቆጶሳት ፡ አለቆች ፡ ግን ፡ በብሩ ፡ የጳጳስን ፡ ሹመት ፡ ገዛ ፡ ስሙንም ፡ አናክሌቱስ ፡ ብሎ ፡ አወጣ ፡፡ ኢኖኬንቲዩስም ፡ ወደ ፡ ፍራንስ ፡ ሸሸቶ ፡ ካያ

ሌ ፡ ደህና ፡ ሰዎች ፡ ጋሬ ፡ ተገናኘ ፡ በርሳቸውም ፡ ቃል ፡ አሸ
ነፈ ፡፡ ወደ ፡ ሮምም ፡ ተመለሰ ፡፡

የዚያን ፡ ጊዜም ፡ በሮም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ አርኖልድ ፡ ከ
ብረሸያ ፡ የሚሉት ፡ በጳጳሳት ፡ ላይ ፡ ተነሣ ፡ ሲል ፡፡ ለቀ
ሳውስት ፡ ሁሉ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አገልጋዮች ፡ አደገባ
ም ፡ ያለም ፡ ክብትና ፡ ሹመት ፡ መግዛትም ፡ እንዲሆንላቸ
ው ፡፡ ለቄስ ፡ የሚገባው ፡ ለቄስ ፡ ይሁን ፡ ለሹምም ፡ የሚ
ገባ ፡ ለሹም ፡ ይሁን ፡፡ ኢኖኬንቲዮስም ፡ አርኖልድን ፡ ገዘ
ተ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ የሮም ፡ ሕዝብ ፡ እጅግ ፡ ወደዱት ፡ ሁከትን
ም ፡ አደረጉ ፡ በጳጳስ ፡ ላይ ፡ ይህም ፡ ኖረ ፡ እስከ ፡ ፲፩፻፶፭፤
ድረስ ፡፡

በሀድርያን ፡ ፬ም ፡ ዘመን ፡ ታላቅ ፡ መጋደል ፡ ጀመረ ፡ በጳ
ጳሳትና ፡ በነገሥታት ፡ መካከል ፡፡ ጳጳስ ፡ ፌሪድሪኽን ፡ ፩፤ ን
ጉሡን ፡ መንግሥቱን ፡ ከጳጳስ ፡ እንደ ፡ ተቀበለ ፡ አለው ፡፡
ከዚያም ፡ ዘመን ፡ ጀምሮ ፡ ፌሪድሪኽ ፡ ጳጳሳትን ፡ ማውረ
ድ ፡ ፈቀደ ፡፡ ስለዚህም ፡ የደፈሩትን ፡ የጳጳስን ፡ መልክተ
ኞች ፡ አልተቀበለም ፡፡ ጽፈትንም ፡ ሰደደ ፡ ወደ ፡ መንግሥ
ቱ ፡ ሁሉ ፡ የመንግሥቱን ፡ አክሊል ፡ ከጳጳስ ፡ ቸርነት ፡ እን
ደልተቀበለ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ እንጂ ፡ በመኳንንቱ ፡ መም
ረጽ ፡ ብሎ ፡፡ ንጉሥም ፡ ጳጳስን ፡ አስፈሬ ፡ በሠራዊቱ ፡ ታረ
ቀም ፡፡ ጳጳስም ፡ በኋላ ፡ በጽፈቱ ፡ ንጉሥን ፡ በገሠጸ ፡ ጊዜ ፡
በሚገባው ፡ መጠን ፡ እንደ ያከብረው ፡ ሲል ፡፡ ፌሪድሪኽ ፡
ብርቱ ፡ ተግሣጽ ፡ መለሰለት ፡ ክብርን ፡ ስለ ፡ መመኘቱ ፡ ስ
ለ ፡ ድፍረቱም ፡ በንጉሥ ፡ ላይ ፡፡

ሀድርያንም ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ የመሬጮች ፡ አለቆች ፡ በ፪፤ ወ
ገን ፡ ተከፈሉ ፡፡ አንዱ ፡ ወገን ፡ እስክንድርን ፡ ፫፤ መረጹ ፡
፩፤ ወገንም ፡ ቪክቶርን ፡፡ ንጉሥ ፡ ግን ፡ ሁለታቸውን ፡ አል
ተቀበለም ፡ ሲኖደስንም ፡ በጳቪያ ፡ ሰበሰበ ፡ አዲስ ፡ መም
ረጽ ፡ ያደርጉበት ፡ ዘንድ ፡፡ እስክንድርም ፡ በዚህ ፡ ተቈጥ
ቶ ፡ ቪክቶር ፡ እሺ ፡ ሲል ፡ አርሱ ፡ ተሾመ ፡ በሲኖደስ ፡ መ
ምረጽ ፡፡ እስክንድር ፡ ግን ፡ ሁላቸውን ፡ ገዘታቸው ፡፡

ይሀ ፡ ክርክርም ፡ በፌሪድሪኽ ፡ ፩፤ በሀይንሪኽ ፡ ፯፤ በልጁ ፡
አልተጨረሰም ፡፡ ባመትም ፡ ፲፩፻፺፤ የፌሪድሪኽ ፡ ፩፤ ምሽት ፡

ቆንስታንትያ ፡ ልጅዋን ፡ ፍሪድሪኽ ፡ ፪ ፡ ዕድሜው ፡ ፯ ፡ አመ ት ፡ ሲሆን ፡ ለጳጳስ ፡ አደራ ፡ ሰጠቸው ፡ ይጠብቀው ፡ ዘን ድ ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ጳጳስ ፡ ተጻላ ፡ ከንምሳ ፡ ታላቆች ፡ ጋራ ፡ ንጉሥን ፡ ስለ ፡ መምረጽ ። ታላቅ ፡ ኦቶንም ፡ የተመረ ጸውን ፡ ንጉሥ ፡ ገዘተ ፡ ባመት ፡ ፲፪፻፱ ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ፍ ሪድሪኽን ፡ ፪ ፡ አነገሠ ። ፍሪድሪኽ ፡ ፪ም ፡ ኢኖኬንቲዩስ ፡ ባ ለ ፡ ጊዜ ፡ ጸለትነት ፡ አላደረገም ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ልቡን ፡ ገለ ጸ ። ለሆኖርዩስ ፡ ፫ም ፡ ተስፋ ፡ አስደረገ ፡ ከሠራዊቱ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ የሩሳሌም ፡ ይሔድ ፡ ዘንድ ፡ ያም ፡ ሳይሆን ፡ ጳጳስ ፡ ሞተ ። ጎርጎርዮስ ፡ ፱ ፡ ግን ፡ ለስለቱ ፡ አሳሰበው ። ፍሪድሪ ኽም ፡ ተነሣ ፡ ይፈጽመው ፡ ዘንድ ። ነገር ፡ ግን ፡ ባመት ፡ ፲፪፳፯ ፡ ሠራዊቱ ፡ ሁሉ ፡ በሲቄልያ ፡ በተሰበሰቡ ፡ ጊዜ ፡ በታ ላቅ ፡ ሕማም ፡ በወታደሮቹ ፡ በተጀመረ ፡ ተከለከልሁ ፡ አ ለ ፡ ሠራዊቱንም ፡ ፈታ ፡ እርሱም ፡ ተመለሰ ። ጳጳስም ፡ አ ሁን ፡ ገዘተው ፡ በኋላም ፡ ፍሪድሪኽ ፡ ሔደ ፡ ወደ ፡ የሩሳሌ ም ፡ ከዚያም ፡ አሸንፎ ፡ የየሩሳሌምን ፡ መንግሥት ፡ አክ ሊል ፡ ባለቤቱ ፡ በራሱ ፡ ላይ ፡ አስቀመጠ ። ይህንም ፡ ወደ ፡ ኤውሮጳ ፡ አወራ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ። ይህ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ክንድ ፡ አደረገች ። ወደ ፡ ኤውሮጳም ፡ ከተመለሰ ፡ በኋላ ፡ ተ ፈታ ። ከጳጳስ ፡ ጋራም ፡ ታረቀ ። በኋላ ፡ ደግሞ ፡ ተጻሉ ፡ ሳ ይታረቁም ፡ ጳጳስ ፡ ሞተ ፡ ባመት ፡ ፲፪፵፩ ። ኢኖኬንቲዩስ ፡ ፬ም ፡ ደግሞ ፡ በጽሉ ፡ ንጉሥን ፡ አስጨነቀ ፡ እስከ ፡ ሞቱ ፡ ድረስ ፡ ባመት ፡ ፲፪፶ ።

ኢኖኬንቲዩስም ፡ ካንድ ፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ሮበርት ፡ ከሚሉ ት ፡ ጋራ ፡ ተጻላ ። ሮበርትም ፡ የጳጳስን ፡ ኀጢአት ፡ ገለጸለ ት ፡ እጅግም ፡ ገሠጸው ። ጳጳስም ፡ ጸላትነትን ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ ፈለገ ፡ በሮበርት ፡ ላይ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አልሆነለትም ።

ስለ ፡ ምንክስና ።

በዚህ ፡ ዘመን ፡ ሞናኵስት ፡ በዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩም ፡ አዲስ ፡ ወገን ፡ ሆኑ ፡ ከሞናኵስት ። ብዙ ፡ ሞናኵስትም ፡ ባገር ፡ ሁሉ ፡ ዞሩ ፡ ንስሓ ፡ ይሰብኩ ፡ ዘንድ ። ከሰምዋቸውም ፡ ሰ ዎች ፡ ብዙ ፡ ንስሓ ፡ ብቻ ፡ አላደረጉም ፡ ሞናኵስትም ፡ ሆ

ኑ ፡ እንጅ ፡፡ ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ ከድኅነታቸው ፡ የተነሣ ፡ ሞናኩስት ፡ ሆኑ ፡ እንጅራ ፡ ያገኙ ፡ ዘንድ ፡ ብለው ፡፡

ባለፈ ፡ ዘመንም ፡ የክሊኒ ፡ ሥርዓት ፡ ተሰራች ፡ ከርሱም ፡ አሁን ፡ እጅግ ፡ ብልሃትና ፡ ዕውቀት ፡ ወጣ ፡፡ በዚህ ፡ ዘመንም ፡ የኪስቴርቲዩም ፡ ሥርዓት ፡ ተሰራች ፡ ከርስዋም ፡ አንድ ፡ ሞነክሴ ፡ ተነሣ ፡ በኃይሉ ፡ በሕይወቱም ፡ ቅድስና ፡ ለዚያ ፡ ዘመን ፡ እጅግ ፡ በጎ ፡ ያደረገ ፡፡ አርሱም ፡ በርንሀርድ ፡ ከክሌርዋ ፡፡

ሌላ ፡ ሥርዓትም ፡ የካርቱዝ ፡ ሥርዓት ፡ ተባለች ፡ ብርቶች ፡ አስቄጦች ፡ የነበረባት ፡፡ ሌላ ፡ ሥርዓትም ፡ የካርሚል ፡ ተራራ ፡ ሥርዓት ፡፡

አንድ ፡ ሰውም ፡ ልጁ ፡ ከብርቱ ፡ ሕማም ፡ በዳነ ፡ ጊዜ ፡ የምንኵስና ፡ ሥርዓትን ፡ አደረገ ፡ ስለ ፡ ድውያን ፡፡ ሌላ ፡ ሰውም ፡ ሥርዓትን ፡ አደረገ ፡ ከስላሞች ፡ የተማረኩትን ፡ መንገደኞች ፡ በብር ፡ ይፈቱ ፡ ዘንድ ፡፡ ይህችም ፡ ሥርዓት ፡ የቅድስት ፡ ሥላሴ ፡ ሥርዓት ፡ ተባለች ፡፡

እጅግ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ሥርዓቶችም ፡ ተነሡ ፡ ለሞናኵስት ፡ ጳጳስ ፡ እስኪከለክል ፡ ድረስ ፡ አዲስ ፡ ሥርዓትን ፡ ከማድረግ ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ፪ ፡ ልዩ ፡ ሥርዓቶች ፡ ተነሡ ፡ በድኅነት ፡ ኑረው ፡ ወደገር ፡ ሁሉ ፡ የሚዞሩ ፡ ንስሐ ፡ ይሰብኩ ፡ ዘንድ ፡፡ አንድ ፡ የደሚኒኩስ ፡ አንድም ፡ የፍራንሲስኩስ ፡ ወገን ፡ ነበሩ ፡፡ የደሚኒኩስ ፡ ወገንም ፡ የሰባኮች ፡ ወገን ፡ ተባሉ ፡፡ ሁለታቸውም ፡ ነዳያን ፡ ሁነው ፡ በምጽዋት ፡ ብቻ ፡ ኖሩ ፡፡

፲ስተኛ ፡ ምዕራፍ ፡፡

የማምለክ ፡ ታሪክ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡፡

በዚህ ፡ ዘመንም ፡ የነፍስ ፡ መሻት ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ እጅግ ፡ ተገለጸ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የወንጌል ፡ ብርሃን ፡ አለቀ ፡፡ ስንት ፡ አእላፍ ፡ ወጡ ፡ ወደ ፡ የሩሳሌም ፡ የነፍሳቸውን ፡ ዕረፍት ፡ ከዚያ ፡ ያገኙ ፡ ዘንድ ፡፡ ስንት ፡ ሰዎችም ፡ ወደ ፡ ምንኵስና ፡ ገቡ ፡ ካለም ፡ ይሸሹ ፡ ዘንድ ፡ ብለው ፡ ዓለም ፡ በውሥጣቸው ፡ በልባቸው ፡ ሲኖር ፡፡ ስንት ፡ ሰዎችም ፡ ገንዘባቸውን ፡ ሰጡ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለገደሞችም ፡ ለድኆችም ፡ መንግሥተ ፡ ሰማያትን ፡ ይገዙበት ፡ ዘንድ ፡ ብለው ፡፡

ካመትም ፡ ፲፪፻፡፡ ወዲህ ፡ ታላቆች ፡ ማስተማርዮች ፡ ኡኒቬርሲታቶች ፡ የሚልዋቸው ፡ ተሠሩ ፡፡ ትምርትም ፡ በዛባቸው ፡፡ አያሌም ፡ ደህና ፡ መምህራን ፡ በሕዝብ ፡ ቋንቋ ፡ መስበክን ፡ጀመሩ ፡፡ ከርሳቸውም ፡ ቶማስ ፡ አኲናስ ፡ በርቶልድም ፡ ከአውግስቡርግ ፡ ጌበርቱስም ፡ አላኑስም ፡፡ ዋልደንሶችም ፡ የተባሉ ፡ ወገን ፡ ለሕዝብ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ በቋንቋቸው ፡ ሰጡ ፡፡ ሕዝብም ፡ በደስታው ፡ ተቀበሉት ፡፡ ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ ተባበሩ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ለመማር ፡ ቀሳውስታቸውም ፡ በከሰስዋቸው ፡ ጊዜ ፡ ኢኖኬንቲዩስ ፡ ከሳሾችን ፡ አልሰማም ፡፡ ወደለዚያም ፡ ሰዎች ፡ ጻፈ ፡ በቸር ፡ ነገር ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንደ መረምሩ ፡ መልካም ፡ እንደሆነ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እንደይገባ ፡ ያለ ፡ ሥርዓት ፡ ያለ ፡ ቄስም ፡ ለብቻቸው ፡ መሰብሰብ ፡፡ እርሳቸው ፡ ግን ፡ መሰብሰባቸውን ፡ አልተውም ፡ ቀሳውስት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ አያውቁም ፡ ነበሩና ፡፡ ስለዚህም ፡ ጳጳስ ፡ የኪስቴርቲዩም ፡ መነኰስት ፡ ይመረምርዋቸው ፡ ዘንድ ፡ አዘዛቸው ፡ በርሳቸውም ፡ ፍርድ ፡ መናፈቃን ፡ ሁነው ፡ ተገኙ ፡ ስለዚህም ፡ ግድ ፡ አደረጉባቸው ፡፡

እንደሁም ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ብዙ ፡ አቡደትን ፡ ከምናኵ

ስት ፡ ስንፍናቸውን ፡ ሁሉን ፡ ማድረግ ፡ በተውዋቸው ፡ ጊ
ዜ ፡ እሌህን ፡ ሰዎች ፡ የክርስቶስን ፡ ትእዛዝ ፡ ጠብቀው ፡
የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ የተማሩ ፡ ከለከሉ ፡፡ መጽሐፍ ፡
ቅዱስ ፡ እንዳይሆንላቸው ፡ በቋንቋቸው ፡ የወንጌል ፡ ክፍ
ል ፡ ብቻ ፡ አንጅ ፡ በላቲና ፡ ቋንቋ ፡፡

በዚህ ፡ ዘመንም ፡ ልማድ ፡ ሆነ ፡ ቍርባንን ፡ በክፍል ፡
ብቻ ፡ ያቍርቡ ፡ ዘንድ ፡፡ ይህም ፡ ልማድ ፡ ያንድ ፡ መልክ ፡
ቍርባን ፡ ተባለ ፡፡ ቀሳውስት ፡ ብቻ ፡ እንጀራውንና ፡ ፅጀ
ን ፡ ተቀበሉ ፡ ለሕዝብ ፡ ግን ፡ እንጀራ ፡ ብቻ ፡ ሰጡ ፡ በንጀ
ራ ፡ በክርስቶስ ፡ ገላ ፡ የክርስቶስ ፡ ደም ፡ ከሥጋው ፡ ጋራ ፡
ባንድ ፡ ይኖራል ፡ ብለዋልና ፡፡

የንስሓ ፡ ሥርዓትም ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ገና ፡ በሁሉ ፡ አል
ከፋም ፡፡ አያሌ ፡ መምህራን ፡ ነበሩ ፡ ያስተማሩ ፡ ንስሓ ፡
ለማየት ፡ በሥጋም ፡ ብቻ ፡ እንዳይሆን ፡ በልብ ፡ እንጅ ፡ ለ
እግዚአብሔር ፡ ብለው ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ አልጠቀመም ፡
የምትሠለጥን ፡ ትምርት ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ያች ፡ ኑራለች
ና ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡፡ የክርስቶስ ፡ ምግባር ፡ ብቻ ፡ አያድን
ም ፡ ሰው ፡ ምግባሩን ፡ ለክርስቶስ ፡ ምግባር ፡ ባይጨምር ፡፡

አራተኛ ፡ ምዕራፍ ።

የትምህርትና ፡ የክርክር ፡ ታሪክ ።

፩። በምሥራቅ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

በምሥራቅ ፡ ትምርት ፡ ሁለግዜ ፡ በዝታ ፡ አለቀች ። በለዚህ ፡ ፪፤ በምሥራቅና ፡ በምዕራብ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መኻከል ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ክርክር ፡ አደረጉ ፡ ምናልባት ፡ መገጠም ፡ እንደሆን ፡ ብለው ። ከምሥራቅም ፡ መምህራን ፡ ፲፪፤ ሰዎች ፡ አደረጉ ፡ ከርሳቸውም ፡ ፩፤ ኒኬታስ ፡ ነበረ ። ከምዕራብም ፡ ፩፤ ነበረ ፡ እርሱም ፡ አንሲልም ፡ የከንትርብሪ ፡ ሜትሮጶሊታን ። ሚካኤል ፡ ጳሌዎሎጎስም ፡ አንድነትን ፡ ፈለገ ፡ ከምዕራብ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጋራ ። ነገር ፡ ግን ፡ ጳጳሳት ፡ የምሥራቅ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንደርሳቸው ፡ ትሆን ፡ ዘንድ ፡ ፈልገዋልና ፡ አልሆነላቸውም ።

፪፤ በምዕራብ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

በዚህ ፡ ዘመን ፡ በምዕራብ ፡ አንደንድ ፡ ታላቅ ፡ መምህር ፡ ተነሣ ፡ ከርሳቸውም ፡ አያሌ ፡ ነበሩ ፡ ሁሉን ፡ የመረመሩ ፡ በኦርቶደክሳዊት ፡ ትምርትም ፡ ያልኖሩ ። ሌሎች ፡ ግን ፡ መመርመራቸውን ፡ ሁሉን ፡ ኦርቶደክሳዊት ፡ ትምርትን ፡ ለማጽናት ፡ አደረጉ ፡ የአውጉስቲኑስን ፡ ቃል ፡ አስበው ፡ ሲል ። ፊደስ ፡ ጵሬኬዲት ፡ ኢንተለክቱም ። ማለቱ ። ሃይማኖት ፡ ዕውቀትን ፡ ትቀድማለች ። አንድም ፡ መርማሪ ፡ ሮስኬሊኑስ ፡ ነበረ ። የርሱም ፡ ጸላት ፡ አንሲልም ፡ የከንትርብሪ ፡ ሜትሮጶሊታን ። አንሲልምም ፡ እጅግ ፡ የተማረ ፡ መምህር ፡ ነበረ ፡ አለም ። የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ መመርመር ፡ አይጠቅምም ፡ ሰው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ባይሐይው ፡ መኖርያው ፡ ሕይወቱም ፡ ደህንነቱም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ባይሻ ፡ በያገኝም ።

ከርሱም ፡ በኋላ ፡ በርንሀርድ ፡ ከክሌርቦ ፡ ተነሣ ፡ እርሱም ፡ አለ ። የእግዚአብሔር ፡ ነገር ፡ ባእምሮ ፡ መመጉ

ት ፡ በመናገርም ፡ ብዛት ፡ አይታወቅም ፡ በሕይወት ፡ ቅድስ
ና ፡ እንጅ ። የርሱም ፡ ጸሎት ፡ ወትሮ ፡ የሚጸሊ ፡ ይህ ፡ ነበ
ረ ፡ እንደህ ፡ ሲል ። አቤቱ ፡ ዕውቀትህን ፡ አስተምረኝ ፡ አ
ንተንና ፡ እኔን ፡ አውቅ ፡ ዘንድ ። እንደሁም ፡ አለ ። ክርስ
ቶስን ፡ በማንበብ ፡ ብቻ ፡ አቲዘውም ፡ በመከተል ፡ እ
ንጅ ።

ሌላ ፡ መምህርም ፡ አቤላርድ ፡ ነበረ ። እርሱም ፡ እጅ
ግ ፡ ሲመረምር ፡ ሞናክሮችንና ፡ ቀሳውስትንም ፡ ስላለማወ
ቃቸው ፡ ሲገሥጽ ፡ ባለቤቱ ፡ ከኦርቶደክሳዊት ፡ ትምርት ፡
ራቀ ።

ሌሎች ፡ መምህራንም ፡ ሮበርት ፡ ጺሌን ፡ ሁጎም ፡ ከቅ
ዱስ ፡ ዊክቶር ። ጊልበርትም ። ጴጥሮስ ፡ ሎምባርዱስ
ም ፡ እርሱም ፡ የቃላት ፡ መምህር ፡ የተባለ ። የርሱም ፡ ደ
ቀ ፡ መዝሙር ፡ ጴጥሮስ ፡ ከጶይቴ ፡ ሆነ ።

ሌሎች ፡ መምህራንም ፡ ጴጥሮስ ፡ ከጌሮኽ ፡ ዋልተርም ፡
ከማውሪታኒያ ፡ ነበሩ ።

ከርሳቸውም ፡ የሚበልጡ ፡ ፈራንሲስ ፡ ከሃሌስ ፡ ቦና
በንቱራም ፡ ታላቅ ፡ አልበርትም ፡ ቶማስ ፡ አኲናስ
ም ፡ ነበሩ ።

እሌህ ፡ መምህራንም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ፍርሃት ፡ ወጥ
ተው ፡ አልመረመሩም ። ቶማስ ፡ አኲናስም ፡ ባንደኛ ፡ ሲ
መረምር ፡ ዕውቀቱንም ፡ ሳያገኝ ፡ በጕልበቱ ፡ ተንበርክኮ ፡
እግዚአብሔርን ፡ ለመነ ፡ እንዲያስተምረው ። እግዚአብ
ሔርም ፡ ተለመነ ፡ የመንፈሱም ፡ ብርሃን ፡ ሰጣቸው ። ነገ
ር ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ነገር ፡ ከሰው ፡ ነገር ፡ በቤተ ፡ ክ
ርስቲያን ፡ ትምህርት ፡ አለዩምና ፡ እጅግ ፡ ጨለማ ፡ ቀረባ
ቸው ።

አንድ ፡ መምህርም ፡ ሮጀር ፡ ቤከን ፡ የሚሉት ፡ የመጽ
ሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ መጀመርያ ፡ ቋንቋች ፡ ዕብራይስጥና ፡ ዮናኒ ፡
ተማረ ፡ ወደ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ዕውቀት ፡ ይደርስ ፡ ዘን
ድ ፡ ብሎ ።

የመናፈቃን ፡ ታሪክ ፡፡

አያሌ ፡ መናፈቃን ፡ ነበሩ ፡ የግኖስቲኮች ፡ ዘመዶች ፡ ኤውኪቶችና ፡ ቦጎሚሎች ፡ የተባሉ ፡፡

ብዙ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ወገንም ፡ ነበሩ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ከታሮች ፡ ማለት ፡ ንጹሐን ፡ የተባሉ ፡፡ ንጽሕት ፡ ትምርት ፡ ከሰው ፡ ትምርት ፡ ጋራ ፡ ያልተደበለቀች ፡ በመኻከላችን ፡ ትገኛለች ፡ ወይስ ፡ ጉባኤያችን ፡ በክፉች ፡ ሰዎች ፡ አልረከሰችም ፡ ሲሉ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ የከታሮች ፡ ስም ፡ ደግሞ ፡ ስድብ ፡ ሁኖ ፡ ተቈጠረ ፡ ለብዙ ፡ ደህና ፡ ክርስቲያናት ፡ ባካሔዳቸው ፡ በትምህርታቸውም ፡ ከቀሩ ፡ ሰዎች ፡ የተሻሉ ፡ አወጡት ፡፡ ከርሳቸው ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ የግኖስቲኮች ፡ ወገን ፡ ነበሩ ፡፡

አንድ ፡ ሰውም ፡ ነበረ ፡ አልመሪኽ ፡ የሚሉት ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ ያስተማረ ፡፡ የነገር ፡ ሁሉ ፡ መሆን ፡ አምላክ ፡ ነው ፡ መልኩም ፡ ፍጥረት ፡ ነው ፡፡

ሌሎች ፡ መለያያትም ፡ ተነሡ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ማቅናት ፡ የፈለጉ ፡፡ እንዲህ ፡ አርኖልድ ፡ ከብሬሽያ ፡፡ እርሱም ፡ የአቤላርድ ፡ ደቀ ፡ መዝሙር ፡ ነበረ ፡ የቀሳውስትንም ፡ ጥፋትና ፡ ኃጢአት ፡ ገለጸ ፡ እጅግም ፡ ገሠጻቸው ፡፡ ትምህርቱም ፡ በሮም ፡ ከተወገዘች ፡ በኋላ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ተቀበልዋት ፡ በኋላም ፡ በግድ ፡ ወሰዱት ፡ በሳትም ፡ አንድደው ፡ ገደሉት ፡፡ እንዲህም ፡ ሆነ ፡ ለጴጥሮስ ፡ ከብሩይስ ፡ ከወገኑ ፡ ጋራ ፡፡ አያሌም ፡ መለያያት ፡ ነበሩ ፡ የሐዋርያት ፡ መለያያት ፡ የተባሉ ፡ የሐዋርያትን ፡ አካሔድና ፡ ድኅነትን ፡ ሊከተሉ ፡ ብለዋልና ፡፡ እንዲህ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ስጋሬሊ ፡ የሚሉት ፡ መለየት ፡ አደረገ ፡ ጉባኤውንም ፡ ያጶስቶሊኮች ፡ ወንድሞች ፡ አላቸው ፡፡ ከጳጳስ ፡ ግን ፡ ሥልጣን ፡ አልነበረለትምና ፡ ባመት ፡ ፲፫፻ ፡ በሳት ፡ ሞተ ፡፡

እሌህ ፡ መለያያትም ፡ ሁሉ ፡ አለፉ ፡ በሰው ፡ ቃል ፡ ላይ ፡ የርሳቸውን ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ አድርገዋልና ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ አንዲት ፡ ወገን ፡ ተነሣች ፡ ያላለፈች ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ተመሠርታለችና ፡፡ እርሳቸውም ፡ በልደንሶች ፡ የተባሉ ፡ መምህራቸው ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡ ጴጥሮስ ፡ በልዱስ ፡ የሚሉት ፡ ስለዚህም ፡ በልደንሶች ፡ ደባላሉ ፡፡ እርሱም ፡ ጻድ

ቅ ፡ ነጋደ ፡ ነበረ ፡፡ አንድ ፡ ጊዜም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ በላቲና ፡ ቋንቋ ፡ በደጉሙት ፡ ጊዜ ፡ ሲሰማ ፡ እርሱ ፡ አላስተ ዋለውምና ፡ አዘነ ፡ አያሌ ፡ ክፍልን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቃ ል ፡ ከቅዱሳን ፡ ሰዎችም ፡ ቃል ፡ በአዋቂ ፡ መምህር ፡ አሰተ ረጐመ ፡፡ ይህንንም ፡ ሲያነብ ፡ በጥቂት ፡ በጥቂት ፡ አደገ ፡ በ ውቀቱ ፡፡ ደሮ ፡ ገና ፡ በግልጽ ፡ ይነሣ ፡ ዘንድ ፡ አላለም ፡፡ ነገ ር ፡ ግን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከወደጆቹ ፡ ጋራ ፡ ሲቀመጥ ፡ አንድ ፡ ሰውም ፡ በመኻከላቸው ፡ ሲሞት ፡ ይህ ፡ ሞት ፡ የእግዚአ ብሔር ፡ መጽሬት ፡ ሁኖለት ፡ ወደ ፡ ልቡ ፡ ገባ ፡ ምንፈሳዊ ፡ ጉባኤንም ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ፡ አሰበ ፡ ሐዋርያትን ፡ የተከተ ሉ ፡ በድኅነት ፡ የክርስቶስንም ፡ ፈቃድ ፡ በማድረግ ፡፡ በል ደ.ስም ፡ ገንዘቡን ፡ ለነደያን ፡ ሰጠ ፡ አስተማሪቸውም ፡ ከ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡፡ የእግዚአብሔርንም ፡ መንግሥት ፡ ለመዝረጋት ፡ ይሰሩ ፡ ዘንድ ፡ መከሪቸው ፡፡ የልዮን ፡ ሜት ሮጶሊታን ፡ ግን ፡ በልደ.ስን ፡ ከለከለ ፡ መጽሐፈ ፡ ቅዱስን ፡ ከማስተማር ፡፡ በልደ.ስ ፡ ግን ፡ ሳይታዘዝ ፡ ለጳጳስ ፡ ለእስ ክንድር ፡ ፫፡ ጳፈ ፡ የመጽሐፈ ፡ ቅዱስንም ፡ ትርጉም ፡ ሰደ ደለት ፡ ጉባኤውንም ፡ እንዲያጸና ፡ ለመነው ፡፡ ደሮ ፡ ጳጳስ ፡ ልመናውን ፡ ነሣው ፡ የፈራንሲስኩስንም ፡ ሞነክሶች ፡ አዘ ዘ ፡ የሌህን ፡ ሰዎች ፡ ትምህርት ፡ ይመረምሩ ፡ ዘንድ ፡፡ እ ልያ ፡ ግን ፡ ናቅዋቸው ፡ ጳጳስንም ፡ እሺ ፡ አሰኙት ፡ ለዚች ፡ ጉባኤ ፡ ለመጽሐፈም ፡ ትርጉም ፡ ማጽናትን ፡ ይነሣባቸው ፡ ዘንድ ፡፡ ከዚያ ፡ ዘመንም ፡ ጀምሮ ፡ መጋደል ፡ ሆነ ፡ በበል ደ.ስና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ በተባለች ፡ መኻከል ፡፡ ጳጳስ ም ፡ ሉኪዩስ ፡ ፫፡ ገዘታቸው ፡ ስሕተትን ፡ ሳያገኝባቸው ፡፡

በልደንሶችም ፡ በትምርታቸው ፡ መጽሐፈ ፡ ቅዱስን ፡ ተ ከተሉ ፡፡ የመጽሐፈ ፡ ቅዱስም ፡ ትርጓሜ ፡ መጽሐፈ ፡ ቅዱ ስ ፡ ነው ፡ አሉ ፡፡ የሃይማኖትም ፡ ዕውቀት ፡ በሌላ ፡ አይገኝ ም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንጂ ፡፡ ስለዚህም ፡ የቅዱሳ ንንም ፡ ማክበር ፡ ከለከሉ ፡፡ በመጀመርያውም ፡ መሐላው ን ፡ እንኳ ፡ ጾርንም ፡ ከለከሉ ፡ ክርስቶስ ፡ ስላለ ፡፡ ነገሬቸ ሁ ፡ አዎን ፡ አዎን ፡ ይሁን ፡ አይደለምም ፡ አይደለም ፡፡ ክር ስ ፡ የሚያልፈ ፡ ከክፉ ፡ ነው ፡፡ ጸላቶቻቸውንም ፡ ውደዱ ፡፡

የበልደንሶችም ፡ ጸላቶች ፡ እንኳ ፡ እንዲህ ፡ አሉ ፡፡ በልደን ሶች ፡ በማድረጋቸው ፡ ሁሉ ፡ ደህና ፡ እንዲህኑ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስንም ፡ ፈጽመው ፡ እንዲያውቁ ፡፡ በዚህም ፡ በጸላቶ ቻቸው ፡ ምስክር ፡ እንኳ ፡ እርሳቸው ፡ የክርስቶስ ፡ ወገን ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ ተገለጹ ፡ ጸላቶቻቸው ፡ ግን ፡ ያለም ፡ ወገን ፡ የክርስቶስን ፡ ወገን ፡ ሁልጊዜ ፡ የሚጸሉ ፡፡

ጳጳስም ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ መናፈቃን ፡ የተባለች ፡ ወገን ፡ እ ሺ ፡ እንደትል ፡ የመስቀልን ፡ ጾር ፡ የሚሉት ፡ አደረገባቸው ፡ በሁላቸው ፡ ላይ ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ብዙ ፡ ሸሕ ፡ ከበነችና ፡ ከክፎች ፡ ሞቱ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰደፍ ፡ እውነትን ፡ ስ ለ ፡ ፈለጉ ፡ እውነትንም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስላላገኙ ፡፡ ባመትም ፡ ፲፪፻፲፫፡ ነርነርዮስ ፡ ፱፡ ለደሚኒኩስ ፡ ወገን ፡ ሞ ናክሶች ፡ ተግባር ፡ ደህነን ፡ አደረገላቸው ፡ ሰውን ፡ ሁሉን ፡ ደመረምሩ ፡ ዘንድ ፡ ማንንም ፡ ሲያገኙ ፡ መናፈቅ ፡ የሚሆ ን ፡ ለፍርድ ፡ ደሰጡት ፡ ዘንድ ፡፡ እንዲህም ፡ ሰይጣን ፡ ኀይ ሉን ፡ ሁሉን ፡ አደረገ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ብርሃን ፡ ደከለክ ል ፡ ዘንድ ፡ ክርስቲያንም ፡ የተባሉ ፡ በጨለማ ፡ ደኖሩ ፡ ዘንድ ፡፡

የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡

ታሪክ ፡

ስድስተኛ ፡ ክፍል ።

ከቦኒፋኪዩስ ፡ ፰ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡

እስከ ፡ መታደስዋ ፡ መጀመርያ ፡ ድረስ ፡

ካመት ፡ ፲፪፻፬ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፲፭፲፯ ፡ ድረስ ።

በዚህ ፡ ዘመን ፡ የነገሡ ፡ ነገሥታት ፡ እሌህ ፡ ናቸው ፡፡

፩፤ በምሥራቅ ፡፡

1. አንድሮኒኮስ ፡ ፫፡፡ ፲፫፳፰፡፡
2. ዮሐንስ ፡ ጰሌዎሎጎስ ፡ ፯፤ ፲፫፵፩፡፡
3. ታመርላን ፡ የሞንጎሎች ፡ ንጉሥ ፡ ፲፫፷፱፡፡
4. አሙረት ፡ የስላሞች ፡ ንጉሥ ፡ ፲፫፶፱፡፡
5. አንድሮኒኮስ ፡ ፬፤ ፲፫፺፡፡
6. ባያጼት ፡ የስላሞች ፡ ንጉሥ ፡ ፲፫፹፱፡፡
7. ዮሐንስ ፡ ጰሌዎሎጎስ ፡ ፯፤ ፲፬፳፬፡፡
8. ቈንስታንቲኖስ ፡ ፲፩፤ ፲፬፵፰፡፡

ቱርኮች ፡ ቈንስታንቲኒያን ፡ ወሰዷ ፡ ባመት ፡ ፲፬፶፫፤ የሮሞችንም ፡ መንግሥት ፡ ገለበጡ ፡፡

፪፤ የምዕራብ ፡ ነገሥታት ፡ እሌህ ፡ ናቸው ፡፡

1. ኤድዋርድ ፡ ፪፤ የእንግሊጣር ፡ ንጉሥ ፡ ፲፫፡፯፡፡
2. ሀይንሪኽ ፡ ፯፤ የንምሳ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፫፲፩፡፡
3. ሉድዊግ ፡ ፲፤ የፈረንስ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፫፲፬፡፡
4. ፊልጶስ ፡ ፭፤ የፈረንስ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፫፲፯፡፡
5. ኤድዋርድ ፡ ፫፤ የእንግሊጣር ፡ ንጉሥ ፡ ፲፫፳፯፡፡
6. ፊልጶስ ፡ ፮፤ የፈረንስ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፫፳፰፡፡
7. ታላቅ ፡ ሉድዊግ ፡ የሁንጋርያ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፫፵፪፡፡
8. ካርል ፡ ፬፤ የቦሄሚያ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፫፵፯፡፡
9. ካርል ፡ ፭፤ የፈረንስ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፫፷፬፡፡
10. ሪቻርድ ፡ ፪፤ የእንግሊጣር ፡ ንጉሥ ፡ ፲፫፸፯፡፡
11. ዌንጽል ፡ የቦሄሚያ ፡ ንጉሥ ፡፡ ፲፫፸፰፡፡
12. ካርል ፡ ፮፤ የፈረንስ ፡ ንጉሥ ፡፡ ፲፫፹፡፡
13. ሲጊስሙንድ ፡ የሁንጋርያ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፫፹፯፡፡
14. ሀንሪ ፡ ፬፤ የእንግሊጣር ፡ ንጉሥ ፡ ፲፫፺፱፡፡
15. ሀንሪ ፡ ፭፤ የእንግሊጣር ፡ ንጉሥ ፡ ፲፬፲፫፡፡
16. ሲጊስሙንድ ፡ የንምሳ ፡ ንጉሥ ፡፡ ፲፬፲፬፡፡

17. ሀንሪ ፡ ፮፡ የእንግሊጣር ፡ ንጉሥ ፡ ፲፬፳፪።
18. አልብረኽት ፡ ካውስትርያ ፡ ፲፬፴፰።
19. ኤድዋርድ ፡ ፭፡ የእንግሊጣር ፡ ንጉሥ ፡ ፲፬፷።
20. ሉድዊግ ፡ ፲፩፡ የፈራንስ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፬፷፩።
21. ፈርዲናንድ ፡ የስጳንያ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፬፸፬።
22. ሀንሪ ፡ ፯፡ የእንግሊጣር ፡ ንጉሥ ፡ ፲፬፹፪።
23. መክሲሚልያን ፡ የንምሳ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፬፺፫።
24. ሉድዊግ ፡ ፲፪፡ የፈራንስ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፬፺፰።
25. አማኑኤል ፡ የጶርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ ፲፬፺፰።
26. ሀንሪ ፡ ፰፡ የእንግሊጣር ፡ ንጉሥ ፡ ፲፭፰።
27. ክርስቲያን ፡ ፪፡ የደንማርክ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፭፲፫።
28. ፈራንሲስ ፡ የፈራንስ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፭፲፭።
29. ካርል ፡ የስጳንያ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፭፲፮።

የሮም ፡ ጳጳሳት ፡ እሊህ ፡ ናቸው ።

1. ቦኒፋኪዩስ ፡ ፰። ፲፪፺፬።
2. ቤኔዲክቱስ ፡ ፲፩፡ ፲፫፬።
3. ክሌሜንስ ፡ ፭፡ ፲፫፭።
4. ዮሐንስ ፡ ፳፪፡ ፲፫፲፮።
5. ቤኔዲክቱን ፡ ፲፪፡ ፲፫፴፬።
6. ክሌሜንስ ፡ ፮፡ ፲፫፵፪።
7. ኢኖኬንቲዩስ ፡ ፭፡ ፲፫፶፩።
8. ክሌሜንስ ፡ ፯፡ ፲፫፶፪።
9. ኡርባኑስ ፡ ፭፡ ፲፫፷፪።
10. ጎርጎርዮስ ፡ ፲፩፡ ፲፫፸።
11. ኡርባኑስ ፡ ፮፡ ፲፫፸፰። ከርሱ ፡ ጀምሮ ፡ ቤት ፡ ክርስቲያን ፡ በ፪፡ በሮም ፡ ጳጳሳት ፡ ተለየች ፡ አንደኛው ፡ በሮም ፡ ሲኖር ፡ አንድም ፡ ባዊኞን ።
12. ክሌሜንስ ፡ ፯፡ ባዊኞን ፡ ፲፫፸፱።
13. ቦኒፋኪዩስ ፡ ፱፡ በሮም ፡ ፲፫፹፱።
14. ቤኔዲክቱስ ፡ ፲፫፡ ባዊኞን ፡ ፲፫፺፭።
15. ኢኖኬንቲዩስ ፡ ፯፡ በሮም ፡ ፲፬፬።

16. ጎርጎርዮስ ፡ ፲፪፡ በሮም ፡ ፲፬፡፮፡፡
17. እስክንድር ፡ ፭፡ ፲፬፡፱፡፡
18. ዮሐንስ ፡ ፳፫፡ ፲፬፲፡፡
19. ማርቲኑስ ፡ ፭፡ ፲፬፲፯፡፡
20. ኤውጌንዩስ ፡ ፬፡ ፲፬፴፩፡፡
21. ፌሊክስ ፡ ፭፡ ፲፬፴፱፡፡
22. ኒቆላዎስ ፡ ፭፡ ፲፬፵፯፡፡
23. ከሊክስቱስ ፡ ፫፡ ፲፬፶፭፡፡
24. ጲዩስ ፡ ፪፡ ፲፬፶፰፡፡
25. ጳውሎስ ፡ ፪፡ ፲፬፷፬፡፡
26. ሲክስቱስ ፡ ፬፡ ፲፬፸፩፡፡
27. ኢኖኬንቲዩስ ፡ ፰፡ ፲፬፹፬፡፡
28. እስክንድር ፡ ፮፡ ፲፬፺፪፡፡
29. ጲዩስ ፡ ፫፡ ፲፭፡፫፡፡
30. ዩልዩስ ፡ ፪፡ ፲፭፡፫፡፡
31. ሌዎን ፡ ፲፡ ፲፭፲፫፡፡

መጀመርያ ፡ ምዕራፍ ።

ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መዝረጋት ።

በዚህ ፡ ዘመን ፡ ካመት ፡ ፲፬፺፪፤ ጀምሮ ፡ የስጳንያ ፡ ሰዎች ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ምድር ፡ አገኙ ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ በሰረሩ ፡ ጊዜ ። ይህችም ፡ ምድር ፡ አሜሪካ ፡ ተባለች ። የዚያች ፡ ምድርንም ፡ ሰዎች ፡ ሃይማኖት ፡ የተባለውን ፡ ነገር ፡ ለመቀበል ፡ በሰይፍ ፡ አገድዋቸው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በዚህ ፡ ማድረግ ፡ እንደች ፡ አልተጠቀመችም ። ለለዚያ ፡ ሰዎችም ፡ በሃይማኖት ፡ ፈንታ ፡ ባርነት ፡ አመጡባቸው ፡ እንጅ ።

በኤውሮጳም ፡ የሊቶኒያ ፡ ሕዝብ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተጨመረች ።

ሁለተኛ ፡ ምዕራፍ ።

የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዓት ።

የጳጳሳት ፡ ታሪክ ።

ቦኒፋኪዩስ ፡ ፰፤ እርሱም ፡ ትዕቢተኛ ፡ ግፈኛም ፡ ሰው ፡ የጳጳሳትን ፡ ታሪክ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ይጀምራል ። እጅግ ፡ ፀብ ፡ ነበረለት ፡ ከሮም ፡ ታላቆችና ፡ ከነገሥታት ፡ ጋራ ፡ ከሰውም ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ። ፊልጶስ ፡ ፬፤ የፍራንስ ፡ ንጉሥ ፡ በጦር ፡ ጊዜ ፡ ግብሩን ፡ ፈለገ ፡ ከመንግሥቱ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ። ቦኒፋኪዩስም ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ትእዛዝን ፡ አወጣ ፡ ሲል ። ግብርን ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚፈልግ ፡ ንጉሥ ፡ ሁሉ ፡ የሚሰጠውም ፡ ቄስ ፡ ሁሉ ፡ ውጉዝ ፡ ነው ፡ ብሎ ። ይህ ፡ ባመት ፡ ፲፪፺፯፤ ነበረ ። ይህነን ፡ ትእዛዝ ፡ ግን ፡ ያመጣውን ፡ የጳጳስን ፡ መልክተኛ ፡ ንጉሥ ፡ ንቆት ፡ ሰደደው ፡ በተመለሰም ፡ ጊዜ ፡ አሠረው ፡ ፲፫፻፩፤ ጳጳስም ፡ ንጉሥን ፡ ባመት ፡ ፲፫፻፪፤ በገዘተ ፡ ጊዜ ፡ ንጉሥ ፡ ታላቆቹን ፡ ሰበሰበ ፡ ጳጳስንም ፡ ስለ ፡ ኃጢአቱ ፡ ስለ ፡ ትዕቢቱም ፡ ከሰሰ ፡ ወደ ፡ ኦይኩሜኒኬ ፡ ሲኖደስም ፡ ተማጸነ ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ የንጉሥ ፡ መልክተኛ ፡ ጳጳስን ፡ ስለ ፡ ዓመፀው ፡ አሠረው ፡ ፈታውም ። ጳጳስም ፡ በኋላ ፡ አብዶ ፡ ሞተ ፡ ባመት ፡ ፲፫፻፫፤

ክቤኔዲክቱስም ፡ በኋላ ፡ የጳጳስ ፡ መራጮች ፡ የኤጲስ ቆጶሳት ፡ አለቆች ፡ እጅግ ፡ ተጨነቁ ፡ ስለ ፡ አዲስ ፡ ጳጳስ ። እርሳቸው ፡ የ፪፤ ወገን ፡ ነበሩና ። አንድ ፡ ወገን ፡ ከኢጣልያኖች ፡ ቦኒፋኪዩስን ፡ ይወዱ ፡ የነበሩ ፡ አንድ ፡ ወገንም ፡ የፊልጶስ ፡ የንጉሥ ፡ ወዳጆች ። የፍራንሲስ ፡ ወገን ፡ ግን ፡ በተንኮል ፡ አንድ ፡ ሜትሮጶሊታንን ፡ መረጹ ፡ እንደ ፡ ጸላታቸው ፡ ፈቃድ ። ነገር ፡ ግን ፡ እርሱን ፡ በፊት ፡ እሺ ፡ አሰኙት ፡ የንጉሥን ፡ ፈቃድ ፡ ሁሉ ፡ ያደርግ ፡ ዘንድ ። እንዲህም ፡ ተሾመ ፡ ጳጳስም ፡ ሁኖ ፡ ክሌሜንስ ፡ ፭፤ ተባለ ። እርሱም ፡ ፍራንሲስ ፡ ሁኖ ፡ ባገሩ ፡ ባዊኞን ፡ መኖርያውን ፡ አደረገ ።

ደህም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ከሌላ ፡ መክንያት ፡ ጋራ ፡ የጳጳሳትን ፡ ኃይል ፡ ያወርድ ፡ ዘንድ ፡ አገለገላ ፡፡

ባመት ፡ ፲፫፻፬፤ በተሰበሰበች ፡ ሲኖደስ ፡ ፊልጶስ ፡ ጳጳስን ፡ አገደ ፡ ከሞናኰስት ፡ አንዲቱን ፡ ሥርዓት ፡ ለመሻር ፡ እርስ ዋም ፡ የየሩሳሌም ፡ ቤት ፡ መቅደስ ፡ ወገን ፡ ሞነክሶች ፡ የ መቅደስ ፡ ጌቶች ፡ የተባሉ ፡፡

ክሌሜንስም ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ፪፤ አመት ፡ ጳጳስ ፡ አልነ በረም ፡ ከመራጮች ፡ መለየት ፡ የተነሣ ፡፡ ባመትም ፡ ፲፫፻፲፮፤ የፈራንሲስ ፡ ወገን ፡ አሸነፈ ፡ ዮሐንስ ፡ ፳፪ም ፡ ጳጳ ስ ፡ ሆነ ፡፡ እርሱም ፡ ከ ሉ ድ ዊ ግ ፡ ከንምሳ ፡ ንጉሥ ፡ ጋ ራ ፡ ተጻላ ፡፡ በፈራንሲስ ፡ ንጉሥም ፡ ኃይል ፡ በመርገሙ ፡ መረከው ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ የንምሳ ፡ መኳንንት ፡ ተባበ ሩ ፡ በጳጳስ ፡ ላይ ፡ ፱፤ መ ራ ጮ ች ፡ መ ኳ ን ን ት ን ፡ አደረ ጉ ፡ ንጉሣቸውን ፡ የሚመርጹና ፡ የሚጠብቁት ፡፡ ዮሐንስ ም ፡ ሞተ ፡ ፲፫፻፴፬፤ ቤኔዲክቱስ ፡ ፲፪፤ ተከተለው ፡፡ ከቤኔዲ ክቱስም ፡ በኋላ ፡ ክሌሜንስ ፡ መጣ ፡ እርሱም ፡ ሉድዊ ግን ፡ ሻረ ፡፡

ባመትም ፡ ፲፫፻፸፰፤ ኡርባኑስ ፡ ፮፤ ጳጳስ ፡ ሆነ ፡ እርሱም ፡ በሮም ፡ ተቀመጠ ፡፡ የፈራንሲስ ፡ መራጮች ፡ ግን ፡ ወደ ፡ አ ዊኞን ፡ ሸሹ ፡ ከዚያም ፡ ወደ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ ጻፉ ፡ ኡ ርባኑስ ፡ ርጉም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ሁሉ ፡ አፈራሺ ፡፡ ስለዚህም ፡ እርሳቸው ፡ ሌላውን ፡ ጳጳስ ፡ ሾ ሙ ፡ ክሌሜንስ ፡ ፯፤ የሚሉትን ፡፡

ይህ ፡ የምዕራብ ፡ ታላቅ ፡ መለየት ፡ ይባላል ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ፵፤ አመት ፡ በ፪፤ ጳጳሳት ፡ በተከፈለች ፡ ጊዜ ፡፡ ከሁለታቸውም ፡ ኢያንዳንዱ ፡ ሲል ፡፡ እኔ ፡ ብቻ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ራስና ፡ አለቃ ፡ የክርስቶስም ፡ እንደኔ ፡ በም ድር ፡ ነኝ ፡፡ የኔም ፡ ወገን ፡ ብቻ ፡ ትድናለች ፡፡ የዚያን ፡ ጊ ዜም ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ በልባቸው ፡ አሰቡ ፡ የሮም ፡ ትምር ት ፡ እንደህ ፡ የምትል ፡ አንዲት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አንድ ትሆን ፡ አንድ ፡ ክርስቶስም ፡ በሰማይ ፡ እንደህም ፡ አንድ ፡ ጳጳስ ፡ በምድር ፡፡ ይህ ፡ ትምህርት ፡ ሐሰት ፡ እንደ ሆን ፡፡ እ ንደሁም ፡ ሲያስቡ ፡ ጥፋትንም ፡ ሲያዩ ፡ በጳጳሳት ፡ መክ

ንያት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የገባ ፡ ሌላውንም ፡ ነገር ፡ ተ
ማረ ፡ እርሱም ፡ ይህ ፡ ነበረ ፡፡ እሌህ ፡ ጳጳሳት ፡ ከክርስቶ
ስ ፡ ቃልና ፡ ሥርዓት ፡ ራቁ ፡ የክርስቶስም ፡ የሐዋርያቱም ፡ ተ
ከታዮች ፡ አይደሉም ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ እናቶች ፡ አይ
ደሉም ፡ አፍራሾች ፡ እንጂ ፡ የሰይጣንም ፡ ባሮች ፡፡ አሁን
ም ፡ እሌህ ፡ ሰዎች ፡ በልባቸው ፡ እንዲህ ፡ ሲያስቡ ፡ ሲያዝኑ
ም ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ጥፋት ፡ ሲያዝኑ ፡ በእግዚአ
ብሔርም ፡ ቃል ፡ ሲያምኑ ፡ ሲመረምሩም ፡ የጳጳስን ፡ ቃል ፡
ተጠራጠሩ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ለመኑ ፡ ረዲትን ፡ ከሰማ
ይ ፡ እንዲሰድ ፡፡ እግዚአብሔርም ፡ ተለመነ ፡ ረዲትም ፡
በጥቂት ፡ በጥቂት ፡ ሰደደ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡
ረዲት ፡ ሳይመጣ ፡ የሰው ፡ ጥፋት ፡ ሊበዛ ፡ ነበረ ፡፡ ስለዚህ ፡
ሆነ ፡ አሁን ፡ አያሌ ፡ ጳጳሳት ፡ እንደ ፡ ተከተሉ ፡ በስስታቸ
ው ፡ በግፋቸውም ፡ በትዕቢታቸውም ፡ በሐሜታቸውም ፡
በኃጢአትም ፡ ሁሉ ፡ ከሌሎች ፡ የታወቁ ፡፡

ባመትም ፡ ፲፬፻፱፡ ሲኖደስ ፡ ተሰበሰበች ፡ በጲ.ሳ ፡ እጅ
ግ ፡ ሜትሮጶሊታኖች ፡ ኤጲስቆጶሳትም ፡ ቀሳውስትም ፡ መ
ምህራንም ፡ የተሰበሰቡበት ፡፡ ፪፡ ጳጳሳትም ፡ ተጸሩ ፡ ባይመ
ጡም ፡ ጊዜ ፡ ተገዘቱ ፡ ተሻሩም ፡ አዲስ ፡ ጳጳስም ፡ ተሾመ ፡
ስሙ ፡ እስክንድር ፡ ፭፡ የሚሉት ፡፡ እሊያ ፡ ፪፡ ጳጳሳት ፡
ግን ፡ አልታዘዙምና ፡ አሁን ፡ ፫፡ ነበሩ ፡ በ፪፡ ፈንታ ፡፡ መለ
የትም ፡ አልተጨረሰችም ፡፡ እስክንድርም ፡ ቶሎ ፡ ሞተ ፡ ሰ
ውም ፡ እንደለ ፡ በመርዝ ፡፡ አንድም ፡ ኮሳ ፡ የተባለ ፡ የ
ኤጲስቆጶሳት ፡ አለቃ ፡ የጳጳስም ፡ መሪ.ጭ ፡ በምርዝ ፡ ገ
ደለው ፡፡ እርሱም ፡ እስክንድርን ፡ ከገደለ ፡ በኋላ ፡ ጳጳስ ፡
ሆነ ፡ ዮሐንስ ፡ ፳፫፡ ተብሎ ፡፡ እርሱም ፡ አሁን ፡ አንደን ፡
ከጸላቶቹ ፡ የጳሪስ ፡ ኡኒቬርሲታስ ፡ ጳፌ ፡ ደልዩ ፡ የሚሉ
ት ፡ የጳጳስን ፡ መሪጭ ፡ አደረገ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ይህች ፡ ኡኒቬ
ርሲታስ ፡ በዚህ ፡ አልታረቀችም ፡፡ መምህራንዋ ፡ ከሌሎ
ች ፡ ደህና ፡ መምህራን ፡ ጋራ ፡ ወትሮ ፡ ጳፏና ፡ ሰበኩ ፡ የቤ
ተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ማቅናት ፡ ፈልገው ፡ በራስና ፡ በብ
ልቶች ፡ ብለው ፡፡ አሁንም ፡ የጲ.ሳ ፡ ሲኖደስ ፡ አልጠቀመ
ችምና ፡ ሌላውን ፡ ሲኖደስ ፡ በኮንስታንስ ፡ ሰበሰቡ ፡ ባ

መት ፡ ፲፬፲፬ ። ከቀደምዋት ፡ ሲኖዶች ፡ ሁሉ ፡ ይህች ፡ በለጠች ፡ አያሌ ፡ ሽሕ ፡ ኤጲስቆጶሳትና ፡ መምህራን ፡ ተከማችተውበታልና ። ከዚያም ፡ ፫ ነገር ፡ ነበረ ፡ የተመካከሩበት ። ፩ እልያን ፡ ፫ ጳጳሳትን ፡ ሊሽሩ ። ፪ የሁስን ፡ ክርክር ፡ ሊመረምሩ ። ፫ ቤት ፡ ክርስቲያንን ፡ በራስና ፡ በብልቶች ፡ ሊያቅኑ ። ጳጳስ ፡ ግን ፡ ፈርቶ ፡ ባመት ፡ ፲፬፲፭ ሸሸ ። አሁንም ፡ ጳጳስ ፡ ይህችን ፡ ሲኖደስ ፡ ይሽር ፡ ዘንድ ፡ ፈለገ ፡ ደሮ ፡ ሲኖደስ ፡ ሰውን ፡ ሁሉን ፡ አስታወቀች ፡ እንደህ ፡ ስትል ። በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በቆንስታንስ ፡ የተሰበሰበች ፡ ሲኖደስ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንደኔ ፡ ሁና ፡ ሥልጣንዋን ፡ ከክርስቶስ ፡ ተቀበለች ፡ ለሰውም ፡ ሁሉ ፡ ይገባል ፡ ይታዘዝላት ፡ ዘንድ ፡ ለሃይማኖት ፡ መለየትንም ፡ ለመሻር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ለማደስ ፡ በሚደርስ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ። በጳጳስ ፡ ነገርም ፡ ሲኖደስ ፡ ሁለንትናዋ ፡ አንድ ፡ ሁናለችና ፡ ፫ ጳጳሳት ፡ ተሻሩ ። አሁንም ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ማቅናት ፡ ፈለጉ ። ነገር ፡ ግን ፡ በሰይጣን ፡ ተንኰል ፡ ተለዩ ። ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዓት ፡ እንዲሻል ፡ የኃጢአትም ፡ ፍትሐት ፡ እንደይሸመት ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ የገባ ፡ ጥፋት ፡ ሁሉ ፡ እንዲሻር ፡ ፈለጉ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በመለየታቸው ፡ አልሆነላቸውም ።

አዲስ ፡ ጳጳስም ፡ ማርቲኑስ ፡ ፭ የሚሉት ፡ ተሾመ ። እርሱም ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ማቅናትና ፡ መታደስ ፡ አልወደደም ፡ ሲኖደስንም ፡ ለፈቃዱ ፡ እሺ ፡ አሰኝ ። ባመትም ፡ ፲፬፲፰ የኮንስታንስ ፡ ሲኖደስ ፡ ተፈታች ፡ ሌላ ፡ ሲኖደስም ፡ ተሰራች ፡ ፭ አመት ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ጳዊያ ፡ የምትሰበሰብ ። በጳዊያም ፡ ሕማም ፡ ሁንዋልና ፡ ወደ ፡ ሲዬና ፡ ተሰበሰቡ ፡ ከዚያም ፡ ጥቂት ፡ ከተቀመጡ ፡ በኋላ ፡ ተፈቱ ፡ ባመትም ፡ ፲፬፴፩ በባሲል ፡ ተሰበሰቡ ። በዚያም ፡ አመት ፡ መርቲኑስ ፡ ሙትዋልና ፡ ሌላ ፡ ጳጳስ ፡ ተሾም ፡ ስሙም ፡ ኤውጌኒዩስ ፡ ፬ ተባለ ። መለክተኛውንም ፡ ወደ ፡ ባሲል ፡ ላከ ። ያችም ፡ ሲኖደስ ፡ መልካም ፡ ስትጀምር ፡ ጳጳስ ፡ ተንኰልን ፡ አደረገ ፡ ማድረግዋን ፡ ያዘግየው ፡ ዘንድ ። ሲኖደስም ፡ እንደ ፡ ፈቃዱ ፡ ሳታድርግ ፡ ጳጳስ ፡ ፈታ

ቃ ፡ ባመት ፡ ፲፬፴፫፤ ጳጳስ ፡ ግን ፡ ተጨንቆ ፡ ከሲኖዶስ ፡ ጋ ራ ፡ ታረቀ ። ደችም ፡ ሲኖዶስ ፡ ብዙ ፡ ቃኖኖችን ፡ አደረገች ፡ ጳጳስን ፡ ደስ ፡ ያላሰኙ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ማቅናትም ፡ ደህና ፡ የሆኑ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ጳጳስ ፡ ሻራት ፡ ሌላም ፡ ሲኖደ ስ ፡ ሰበሰበ ፡ አንድነትን ፡ ለማድረግ ፡ ከሩሞች ፡ ጋራ ፡ ባመ ት ፡ ፲፬፴፮፤ አሁንም ፡ ፪፤ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡ የተጻሉ ፡ ሲ ኖዶች ፡ ነበሩ ፡ እርሱ ፡ በርሳቸውም ፡ የተገዛዘቱ ።

በባሲል ፡ ሲኖዶስም ፡ ተለዩ ። አንድ ፡ የበረቱ ፡ ወገን ፡ ነበ ረ ፡ አንድም ፡ የደከሙ ። የበረቱም ፡ መምህራን ፡ አዲስ ፡ ጳጳስን ፡ ሾሙ ፡ ፊሊክስ ፡ ፭፤ የሚሉት ። በዚህ ፡ ሲኖዶስ ም ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ልባቸውን ፡ ለወጡ ፡ የሰውን ፡ ጸላትነ ት ፡ ከመፍራት ፡ የሰውንም ፡ ክብር ፡ ከመውደድ ፡ የተነ ሣ ። እንደሁም ፡ ፍሬያቸው ፡ ከንቱ ፡ ነበረ ። እግዚአብሔ ር ፡ እንደህ ፡ አድርጎታልና ፡ የቤት ፡ ክርስቲያን ፡ መድኀኒ ት ፡ ከሰው ፡ እንደይመጣ ፡ ሰውም ፡ እንደይከብርበት ፡ እ ርሱ ፡ ብቻ ፡ እንዲታወቅ ፡ እንጂ ፡ እንደ ፡ መድኀኒት ፡ ሁሉ ፡ ምንጭ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያኑም ፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡ ረዳት ፡ የሚ ሆን ። አንድ ፡ መምህርም ፡ በባሲል ፡ በሲኖደስ ፡ ነበረ ፡ ኤ ኔያስ ፡ ሲልዊዩስ ፡ የሚሉት ። እርሱም ፡ እጅግ ፡ ብልሕ ፡ ነ በረ ፡ በመጀመርያም ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ደህንነት ፡ ሰራ ፡ ተናገረም ። በኋላ ፡ ግን ፡ ያለም ፡ መንፈስ ፡ አሸነፈው ፡ የጳ ጳስም ፡ ወዳጅ ፡ ሆነ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንንም ፡ ደህንነት ፡ ካደ ። የዚህም ፡ ማድረጉ ፡ ዋጋ ፡ የጳጳስ ፡ ሹመት ፡ ሆነ ። እርሱም ፡ ባመት ፡ ፲፬፶፰፤ ጳጳስ ፡ ሁንዋልና ፡ ሁለተኛ ፡ ጲ ዮስ ፡ ተባለ ። ከብዙ ፡ ከቀደሙት ፡ ጳጳሳት ፡ ከፋ ።

ነገር ፡ ግን ፡ ከሁሉ ፡ የሚከፋ ፡ ጳጳስ ፡ ሥጋውንና ፡ ነፍሱን ፡ ለሰይጣን ፡ የሼጠ ፡ የክርስቶስንም ፡ መንጋ ፡ አሳልፎ ፡ ለገ ሃነም ፡ የሰጣት ፡ እስክንድር ፡ ፮፤ ነበረ ፡ ባመት ፡ ፲፬፺፪፤ ጳጳስ ፡ የሆነ ። ሹመቱንም ፡ በወርቅ ፡ ደገዛ ፡ ነበረ ። ጳጳስ ም ፡ ሳይሆን ፡ በዝሙት ፡ ሁሉ ፡ ኖረ ። ከንዲት ፡ ሴት ፡ ፭፤ ል ጆች ፡ ወለደ ፡ ከርሳቸውም ፡ ፪፤ ይታወቃሉ ፡ በኀጢአታቸ ው ። አንዲት ፡ ሴት ፡ ልጁ ፡ ሉክሬትያ ፡ የሚልዋት ፡ ፩፤ ጊ ዜ ፡ ተጋባች ፡ አባትዋም ፡ እስክንድር ፡ እንደ ፡ ምሽቱ ፡ አጋ

ባባት ። አንድ ፡ ኃጢአት ፡ እርሱ ፡ ያላደረገው ፡ አልነበረም ፡ ፍትወትን ፡ ወይስ ፡ ብርን ፡ ያገኘበት ፡ ዘንድ ። ከኤጲስቆጶሳት ፡ አለቆቹም ፡ እርሱ ፡ ከልጁ ፡ ጋራ ፡ አያሌን ፡ በመርዝ ፡ ከገደሉ ፡ በኋላ ፡ ልጁ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ደግሞ ፡ መርዝ ፡ በፃ ጅ ፡ አደረገ ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ ከለዚያ ፡ አለቆች ፡ አባቱም ፡ ጳጳስ ፡ ይህነን ፡ ሳያውቅ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ይህንን ፡ መርዝ ፡ የነበረበትን ፡ ፃጅ ፡ ጠጠ ፡ ሞተበትም ፡ ባመት ፡ ፲፭፻፫።

ከርሱም ፡ በኋላ ፡ የተከተለ ፡ ጳጳስ ፡ ዩልዩስ ፡ ፪። ነበረ ፡ ወታደር ፡ ግፈኛ ፡ ሰውም ። ካያሌ ፡ መንግሥቶች ፡ ጋራ ፡ ተጻላ ፡ የሰውም ፡ ሁሉ ፡ ጸላት ፡ ነበረ ። በርሱም ፡ ላይ ፡ ሲኖደስን ፡ ሰበሰቡ ፡ በጲሳ ፡ ባመት ፡ ፲፭፲፩። ነገር ፡ ግን ፡ በከንቱ ። ጳጳስም ፡ በዚች ፡ ሲኖደስ ፡ ለይ ፡ ሌላውን ፡ ሲኖደስ ፡ አከማቸ ፡ እንደ ፡ ፈቃዱ ። እርሱም ፡ የግፉ ፡ ልቅ ፡ በሙላ ፡ ጊዜ ፡ ሞተ ፡ ባመት ፡ ፲፭፲፫። በስፍራውም ፡ ሌዎን ፡ ፲። ተከተለ ፡ ያለም ፡ የብልሃቱና ፡ የመርዓቱ ፡ ወዳጅ ። እርሱ ፡ ደግሞ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ መጠበቅ ፡ አልቻለውም ።

፻ስተኛ ፡ ምዕራፍ ፡፡

ስለ ፡ ምንኩስና ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡፡

በዚህ ፡ ዘመንም ፡ በምንኩስና ፡ ኀጢአት ፡ እጅግ ፡ በዝቶ ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ወገን ፡ የተኘለ ፡ መንፈስ ፡ ተነሣ ፡ የበዛውን ፡ ክፋት ፡ የገሠጸ ፡ ስለዚህም ፡ ተሰድበው ፡ በጋርደች ፡ ተባሉ ፡፡ በጋርደችም ፡ ማለት ፡ የሚጸልዩ ፡ ሰዎች ፡፡

በፍራንሲስኩስ ፡ ወገንም ፡ መለየት ፡ ሆነች ፡፡ በብርቶች ፡ ባልበረቱም ፡ ተከፈሉ ፡፡ ብርቶችም ፡ ያለምን ፡ ገንዘብ ፡ ሁሉን ፡ ንቀው ፡ ነዳያንም ፡ ሁነው ፡ ዞሩ ፡ ንስሓን ፡ ሲሰብኩ ፡፡ ከርሳቸውም ፡ አያሌ ፡ ተነሡ ፡ በትንቢት ፡ የተናገሩ ፡ የዘመናቸውንም ፡ ጥፋት ፡ ሲገሥጹ ፡ ሮምንም ፡ ባቢሎን ፡ ሲሉ ፡ ጊዜ ፡ እንደለ ፡ ባቢሎን ፡ እንድትፈርስ ፡ የመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ዘመንም ፡ እንደ ፡ መጣ ፡ በርሱም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ዕውቀት ፡ የሰውም ፡ ደህንነት ፡ እንደ ፡ ገዛ ፡ ባለም ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ አሉ ፡፡ እርሳቸውም ፡ በተሳደዱ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ንምሳ ፡ አገር ፡ ሸሹ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ጉባኤንም ፡ አደረጉ ፡ በነ ፡ ነገርን ፡ ለመስራት ፡ ለነዳያንም ፡ ለድውያንም ፡፡ አንድ ፡ ታላቅ ፡ ወገንም ፡ ከርሳቸው ፡ ተነሡ ፡ አንድ ፡ ገርሃርድ ፡ አለቃቸው ፡ የነበረላቸው ፡፡ ከርሳቸውም ፡ መኻከል ፡ ቶማስ ፡ ከኮምጰን ፡ ነበረ ፡፡ ይህች ፡ ጉባኤም ፡ እጅግ ፡ አደረገች ፡ ማስተማርን ፡ ታቅና ፡ ዘንድ ፡፡

አራተኛ ፡ ምዕራፍ ።

የትምህርትና ፡ የክርክር ፡ ታሪክ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ።

፩፤ በሮሞች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

በኣቶስ ፡ ተራራ ፡ እጅግ ፡ ሞናኵስት ፡ ነበሩ ፡ እስካሁን ፡ ድረስም ፡ ከዚያ ፡ የብዙ ፡ ሞናኵስት ፡ መቀመጫ ፡ ነው ። በዚህ ፡ ዘመንም ፡ በመካከላቸው ፡ አንዲት ፡ ስንፍና ፡ ተዘረጋች ፡ እንደዚህ ፡ ሲሉ ። ሰው ፡ ሁሉ ፡ ወትሮ ፡ ሳያንቀሳቀስ ፡ ወደ ፡ እንብርቱ ፡ ቢያይ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ወደ ፡ ማየት ፡ ይደርሳል ።

ሁለት ፡ ቄሣሮቻቸውም ፡ አንድሮኒኮስ ፡ ፪፤ ዮሐንስ ፡ ጰሌዎሎጎስም ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ፈተኑ ፡ አንድነትን ፡ ያድርጉ ፡ ዘንድ ፡ ከምዕራብ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከላቲኖች ፡ ጋራ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አልሆነላቸውም ።

፪፤ በምዕራብ ፡ በላቲና ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ።

በዚህ ፡ ዘመንም ፡ ታላቅ ፡ መጋደል ፡ ሆነ ፡ በጨለማና ፡ በሚመጣ ፡ ብርሃን ፡ መካከል ። እግዚአብሔርም ፡ እጅግ ፡ አደረገ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ መታደስ ፡ ያሰናድው ፡ ዘንድ ።

በዚህ ፡ ዘመንም ፡ የሮም ፡ የምሥራቅ ፡ መንግሥት ፡ በቱርኮች ፡ ኀይል ፡ ወደቀች ፡ ስለ ፡ ኀጢአትዋ ፡ ፈርሳ ። ከምሥራቅም ፡ እጅግ ፡ መምህራን ፡ ሸሽተው ፡ ወደ ፡ መዕራብ ፡ ደረሱ ፡ ብልሃታቸውንም ፡ በምዕራብ ፡ ዘረጉ ፡ እንደዚህም ፡ ዕውቀት ፡ በምዕራብ ፡ በኤውሮጳ ፡ በዛ ።

ደግሞም ፡ ባመት ፡ ፲፬፻፶፤ አንዲት ፡ ብልሃት ፡ ተገኘች ፡ እርስዋ ፡ ከሁሉ ፡ ይልቅ ፡ የምትጠቅም ፡ ዕውቀትን ፡ ለመዘረጋት ፡ እርስዋም ፡ በማኅተም ፡ መጻፍ ። በርሱ ፡ የሰው ፡ ጽሕፈት ፡ ቶሎ ፡ ወደ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ይደርሳል ። መማርንም ፡ እጅግ ፡ ያቀላል ።

እግዚአብሔርም ፡ የሰውን ፡ አሳብ ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ወደ ፡ ከዋክብት ፡ አኖረ ፡ ከዋክብትንም ፡ ዕውቀው ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ሔደ ፡ በመርከባቸውም ፡ በባሕር ፡ ሁሉ ፡ ይዞሩ ፡ ዘንድ ፡ ጀመሩ ፡ ካገርም ፡ ወደገር ፡ ከባሕርም ፡ ወደ ፡ ባሕር ፡ ከሕዝብም ፡ ወደ ፡ ሕዝብ ፡ ደረሱ ፡፡ እንዲሁም ፡ አድርገው ፡ ዕውቀታቸው ፡ በዛ ፡ መንገድም ፡ ተበጀ ፡ የወንጌል ፡ ዕውቀት ፡ በሚመጣ ፡ ዘመን ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ ሁሉ ፡ ይደርስበት ፡ ዘንድ ፡ ጊዜ ፡ የነበረለት ፡፡

እንዲህም ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ በባሕር ፡ በዞሩ ፡ ጊዜ ፡ ታላቅ ፡ ምድር ፡ ተገኘች ፡ በፊት ፡ ከቶ ፡ ያልታወቀች ፡ ሰውም ፡ በርስዋ ፡ ተገኘ ፡፡ ያች ፡ ምድርም ፡ አሜሪካ ፡ ተባለች ፡፡ ደግሞም ፡ በሰረሩ ፡ ጊዜ ፡ ባፍሪቃ ፡ ዙረው ፡ አዲስ ፡ መንገድን ፡ አገኙ ፡ ወደ ፡ ህንድ ፡ ወደ ፡ ሣበሻም ፡ አስቀድሞ ፡ ያልታወቀውን ፡ መንገድ ፡፡

አሁንም ፡ ያለም ፡ ዕውቀት ፡ መብዛት ፡ በጀመረች ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ዕውቀት ፡ ይደርሱ ፡ ዘንድ ፡ ተናፈቁ ፡፡ አያሌመ ፡ ፈተኑ ፡ መንገድን ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ለመመርመር ፡ ከጨለማም ፡ ኃሬ ፡ ይጋደሉ ፡ ዘንድ ፡፡ ከርሳቸውም ፡ እሌህ ፡ ናቸው ፡፡ ኦካም ፡ በእንግልጣር ፡ ደሪንዲስም ፡ ጴጥሮስ ፡ ደልዪ ፡ ኮርትሬስዩስም ፡ ገብርኤል ፡ ቢልም ፡፡ በእንግልጣርም ፡ ባመት ፡ ፲፱፻፱፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ተነሣ ፡ የንጉሡ ፡ ንስሓ ፡ አባት ፡ ስሙም ፡ ቶማስ ፡ ብራድወርደይን ፡ በእኩል ፡ ጸላግያኖች ፡ ትምርት ፡ ላይ ፡ የመጉተ ፡፡ ራይሙንዲስ ፡ ከሰቡንደ ፡ በተከራካሮች ፡ ላይ ፡ የክርስቲያን ፡ ትምህርት ፡ ወደ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ዕውቅት ፡ ያደርስ ፡ ዘንድ ፡ ጻፈ ፡፡

አያሌ ፡ መምህራንም ፡ ነበሩ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ደህንነት ፡ የሰሩ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ስራቸው ፡ በኩል ፡ ብቻ ፡ ነበረ ፡፡ እንደሀ ፡ የጳሪስ ፡ መምህራን ፡ ጌርሶምና ፡ ደልዪ ፡ አሉ ፡፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ቢመረምሩ ፡ ይጉደል ፡ እንደንድም ፡ ትምህርት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚያስተምርዋት ፡ ትሻርበታለችና ፡ አሉ ፡፡

ከዚያ ፡ ዘመንም ፡ ደህና ፡ ቀሳውስት ፡ ሕዝብን ፡ በቋንቋ

ቸው ፡ ያስተምሩ ፡ ዘንድ ፡ ጀመሩ ፡ ይሰብኩላቸውም ፡ ዘን
ድ ፡፡ መልካሚ ፡ የሚሰብኩ ፡ ጥቂት ፡ ነበሩ ፡ በዚህ ፡ ዘ
መን ፡ ለሕዝብም ፡ የሚጠቅሙ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ አያሌ ፡ ተገ
ኙ ፡ እንደ ፡ ታውለር ፡፡ የቀደሙ ፡ ቋንቋዎች ፡ የዮናኒና ፡ የ
ለቲና ፡ ቋንቋ ፡ ዕውቀት ፡ ላንደንድ ፡ ጠቀመ ፡ መጽሐፈ ፡ ቅ
ዱስን ፡ በመጀመርያው ፡ ቋንቋው ፡ ይመረምሩ ፡ ዘንድ ፡፡ እ
ንደ፡ህም ፡ ላውረንቲዩስ ፡ በላ ፡፡

አያሌም ፡ ምስክሮች ፡ ለወንጌል ፡ እውነት ፡ የመሰከሩ ፡
አሉ ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡፡ እንዲህ ፡ ዮሐንስ ፡ ወሰል ፡ ከግሮ
ኒንገን ፡፡ እርሱም ፡ እጅግ ፡ ተምርዋልና ፡ ባለ ፡ ክርክርና ፡
ያለም ፡ ብርሃን ፡ ተባለ ፡፡ ጳጳስ ፡ ሲለው ፡ አንዲት ፡ ቸርነ
ት ፡ ከርሱ ፡ ይለምን ፡ ዘንድ ፡ እርሱ ፡ መጽሐፈ ፡ ቅዱስን ፡
ለመነ ፡ በዮናኒና ፡ በዕብራይስጥ ፡ ቋንቋ ፡፡ እርሱም ፡ ስለ ፡
እውነተኛ ፡ ንስሓ ፡ ተከራከረ ፡ ስለ ፡ እውነተኛም ፡ ቤተ ፡ ክ
ርስቲያን ፡፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡፡ የ
ውነተኛ ፡ የቅዱሳን ፡ ጉባኤ ፡ እለዚያ ፡ ሰዎች ፡ ናቸው ፡፡ ባ
ንድ ፡ ሃይማኖት ፡ ባንድ ፡ ፍቅርም ፡ ባንድ ፡ አለኝተም ፡ ከ
ክርስቶስ ፡ እርሱን ፡ ብቻ ፡ ከሚሹት ፡ ከማይታይም ፡ አለ
ቃቸው ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ያሉ ፡ ሁሉ ፡፡ የሚታይ ፡ አለቃቸው ፡
ልዩ ፡ ልዩ ፡ ቢሆን ፡ የሮምንም ፡ ጳጳስ ፡ የሮምንም ፡ ቤተ ፡
ክርስቲያን ፡ ባያውቁ ፡ ግድ ፡ የለም ፡፡

እንደርሱም ፡ ዮሐንስ ፡ ቡርክሀርድ ፡ ከዌሰል ፡ ነበ
ረ ፡፡ የአውጉስቲኑስን ፡ መጻሕፍት ፡ ተማረ ፡ በርሳቸውም ፡
በዘመኑ ፡ ስሕተት ፡ ላይ ፡ ተመኙት ፡፡

እሌህ ፡ መምህራን ፡ ግን ፡ በትምህርታቸው ፡ ለጥቂት ፡
ሰዎች ፡ ብቻ ፡ ጠቀሙ ፡፡ ሁለት ፡ ግን ፡ ነበሩ ፡ ለብዙ ፡ የጠቀ
ሙ ፡ ብርሃናቸውም ፡ ወደ ፡ ሩቅ ፡ ስፍራ ፡ ለሩቅ ፡ ዘመን
ም ፡ ያበራ ፡፡ እርሳቸውም ፡ ዊክሊፍ ፡ በእንግልጣርና ፡
ሁስ ፡ በቦሂሚያ ፡ ናቸው ፡፡

ከሌህ ፡ ሁለትም ፡ መጀመርያ ፡ ዮሐንስ ፡ ዊክሊፍ ፡ በእ
ንግልጣር ፡ ነበረ ፡፡ በንግልጣርም ፡ የጳጳስ ፡ ኃይል ፡ እጅግ ፡
ታላቅ ፡ ሁኖ ፡ ዊክሊፍ ፡ ተነሣ ፡ ተከራከረበትም ፡፡ እርሱ
ም ፡ በክርክር ፡ ኃይለኛ ፡ ኑርዋልና ፡ ወንጌልኛ ፡ መምህ

ር ፡ ተባለ ። እርሱም ፡ በኦክስፎርድ ፡ በነበረች ፡ ዑኒቨርሲ ታስ ፡ አስተማረ ። የንግልጣርም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ባመ ት ፡ ፲፫፸፬፡ አያሌ ፡ መለክተኞች ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ ጳጳስ ፡ በሰ ደደች ፡ ጊዜ ፡ ዊክሊፍ ፡ ደግሞ ፡ ከርሳቸው ፡ አንድ ፡ ሆነ ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ እጅግ ፡ አየ ፡ ከሮም ፡ ጥፋት ። ከተመለ ሰም ፡ በኋላ ፡ በጅግ ፡ ብርቱ ፡ ነገር ፡ ተጋደለ ፡ ከጳጳስ ፡ ጋ ራ ። ይህም ፡ ክርክሩ ፡ ሞነክሮችን ፡ የሎንደንም ፡ ኤጲስ ቆጶስ ፡ እጅግ ፡ አስቈጣ ። ነገር ፡ ግን ፡ የለንከስትር ፡ ጋ ዢ ፡ ከንጉሥ ፡ ጋራ ፡ የሚገዛ ፡ ዊክሊፍን ፡ ጠበቀ ፡ ጸላቶ ቹ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ደገድሉት ፡ ዘንድ ፡ በወደዱ ፡ ጊዜ ። እርሱ ም ፡ እጅግ ፡ አደረገ ፡ አሽከሮችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ነገር ፡ ለማስተማር ፡ ስለዚህም ፡ እንደ ፡ ዕውቀቱ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅ ዱስን ፡ በእንግሊዝ ፡ ቋንቋ ፡ አስተረጐመ ፡ ባመት ፡ ፲፫፹፡። የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ የከንትርብሪ ፡ ሜትሮጶሊታን ፡ ሰው ን ፡ ሁሉን ፡ ይህነን ፡ ትርጐም ፡ የሚያነብ ፡ ገዘተ ። እነሆ ፡ የዕውሬን ፡ ዕውራን ፡ መሮች ፡ ከሚመሩት ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ጕ ድጓድ ፡ የሚወድቁ ። ጸላቶቹ ፡ እጅግ ፡ ደከሙ ፡ ይሽሩት ፡ ዘንድ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ ጠበቀው ፡ ባመትም ፡ ፲፫፹፬፡ ሙቶ ፡ ወደ ፡ አሸነፊች ፡ ጉባኤ ፡ በሰማይ ፡ ገባ ።

አያሌ ፡ ቀሳውስትም ፡ የዊክሊፍ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ሆ ኑ ፡ በንግልጣርም ፡ ዞሩ ፡ የርሱን ፡ ትምርት ፡ ይዘርጉ ፡ ዘን ድ ። ነገር ፡ ግን ፡ የማሳደድ ፡ እሳት ፡ ተቃጠለባቸው ፡ ብ ዙ ፡ ሰዎችም ፡ በሞታቸው ፡ የወንጌልን ፡ እውነት ፡ ሊመ ሰክሩ ፡ ነበሩ ።

የዊክሊፍም ፡ ትምህርት ፡ ከንግልጣር ፡ ወጥታ ፡ ወደ ፡ ቦሄሚያ ፡ መንግሥት ፡ ደረሰች ። በቦሄሚያም ፡ ከተማ ፡ በጵራግ ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ አንዲት ፡ አዲስ ፡ ዑኒቨርሲታስ ፡ ተሠራች ፡ አያሌ ፡ ሺሕ ፡ ብላቴኖች ፡ በክህነት ፡ በመፍረድ ም ፡ በመፈወስም ፡ በፊሎሶፊያም ፡ የተማረባት ፡ ባመት ፡ ፲፫፵፰። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ፫፡ የወንጌል ፡ ምስክሮች ፡ እር ሳቸውም ፡ ቀሳውስት ፡ በጵራግ ፡ ተነሡ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያ ንም ፡ ጥፋት ፡ ላይ ፡ ሰበኩ ። አንዲም ፡ ኮንራድ ፡ ካውስ ትሪያ ፡ ፲፫፷፱፡ የሞተ ። ሁለተኛውም ፡ ዮሐንስ ፡ ሚሊች ።

እርሱም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስና ፡ በኃይል ፡ ሰበከ ፡ ከድካም ፡ አልፈራም ፡ በመንፈሱም ፡ አያሌ ፡ ጊዜ ፡ ጸለቶቹን ፡ አስደነገጠ ፡ ፈቃዳቸውን ፡ በላየው ፡ ማድረግ ፡ እንዳይችሉ ፡፡ እርሱም ፡ የቀሳውስትን ፡ ጉባኤ ፡ አደረገ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ባንድ ፡ ቤት ፡ የሚኖሩ ፡ ወንጌልንም ፡ በመስበክ ፡ የተማሩ ፡ የወንጌልንም ፡ ዘር ፡ ባገራቸው ፡ የዘሩ ፡፡ እርሱም ፡ሞተ ፡ ባመት ፡ ፲፫፷፱፤ በጽራግ ፡፡ ሶስተኛም ፡ ከሌህ ፡ ምስክሮች ፡ ማቲያስ ፡ ከያኖ ፡ ነበረ ፡ የንጉሥ ፡ የንስሓ ፡ አባቱ ፡፡ ስለ ፡ ወንጌል ፡ ትምህርቱም ፡ ንጉሡ ፡ አሳደደው ፡ እርሱም ፡ ባመት ፡ ፲፫፺፬፤ ሞተ ፡፡

የዚያን ፡ ጊዜም ፡ የየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሰማዕት ፡ ዮሐንስ ፡ ሁስ ፡ በምስክሩ ፡ ተነሣ ፡፡ እርሱም ፡ ባመት ፡ ፲፫፷፫፤ ሁሲኔጽ ፡ በተባለች ፡ አገር ፡ ከነደያን ፡ ወላጆች ፡ ተወለደ ፡፡ በመከራም ፡ አደገ ፡ ተማረም ፡ እግዚአብሔርም ፡ እንደ ሀ ፡ ወደ ፡ ልብ ፡ የውሃት ፡ ወሰደው ፡፡ ክህንነትንና ፡ ፈሎሰፈያን ፡ በጽራግ ፡ ተማረ ፡ መምህራኑም ፡ ኦርቶደክሳውያን ፡ ተብለው ፡ ነበሩ ፡ እርሱም ፡ ደግሞ ፡ ተከተላቸው ፡ በጎም ፡ ተምርዋልና ፡ እርሱ ፡ ደግሞ ፡ ከኡኒዌርሲታስ ፡ መምህራን ፡ አንድ ፡ ሆነ ፡፡ ባመት ፡ ፲፫፺፮፡፡ ባመትም ፡ ፲፬፩፤ ፪፤ በጎ ፡ ሰዎች ፡ ከሕዝቡ ፡ አንዲት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ሠሩ ፡ ሕዝብን ፡ ለማስተማር ፡ ለስብከትም ፡ ብቻ ፡ ቤተ ፡ ልሔምም ፡ አልዋት ፡ ማለት ፡ የመንፈሳዊ ፡ እንጀራ ፡ ቤት ፡ ክርስቶስ ፡ የሚወልድበት ፡ በመንፈሳዊ ፡ ልደቱ ፡ በሰው ፡ ልብ ፡፡ በዚችም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁስ ፡ መጀመርያ ፡ ሰባኪ ፡ ሆነ ፡፡ በርስዋም ፡ ሲሰብክ ፡ የሕዝብን ፡ መኻት ፡ የሕዝብንም ፡ ንብረት ፡ ተማረ ፡፡ በቀሳውስትና ፡ በመምህራን ፡ በሞናክሶችም ፡ መክኒያት ፡ በሕዝብ ፡ የተዘረጋውን ፡ ጥፋት ፡ አየ ፡፡ በዚህም ፡ አዝኖ ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስንም ፡ ተምሮ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ በውነቱ ፡ መራው ፡፡ እርሱ ፡ ባለቤቱ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፡ በመጽሐፉ ፡፡ ቀድሚ ፡ ሥጋውን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘውን ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ አሰብሁ ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ ሚቃጠል ፡ እንጨት ፡ ከሳት ፡ ነጥቆ ፡ አደነኝ ፡ ወደ ፡ ክርስቶስ ፡ እውነትም ፡

ወደ ፡ እውቀቱም ፡ አደረሰኝ ። ልቤም ፡ በሚያድነኝ ፡ እሳት ፡ ተያዘ ፡ ከዚያም ፡ ጀምሮ ፡ በክርስቶስ ፡ መውደድ ፡ ይቃጠላል ።

ከዚያም ፡ ጀምሮ ፡ ስብከቱ ፡ የተሻለች ፡ ሆነች ፡ ወደ ፡ ሰው ፡ ልብም ፡ ገባች ። አካሔዱም ፡ ብርታትና ፡ ፍቅር ፡ አንድ ፡ የሆኑበት ፡ እጅግ ፡ መሰከረ ፡ ለትምህርቱ ፡ ጸላቶቹ ፡ እንኳ ፡ እንደ ፡ መሰከሩለት ። ከዚያ ፡ ዘመን ፡ አስቀድሞ ፡ አንድ ፡ ወታደር ፡ ባንድ ፡ መንደር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ያፈርስ ፡ ነበረ ፡ ወሬም ፡ ወጣ ፡ የቍርባን ፡ እንጀራ ፡ ከዚያ ፡ እንደ ፡ ተገኘ ፡ ከርሱ ፡ ደም ፡ የፈሰሰበት ። ይህ ፡ ወሬም ፡ የቀሳውስት ፡ ስራ ፡ ነበረ ፡ በርሱ ፡ ሊገለጽ ፡ የቍርባን ፡ እንጀራ ፡ በቄስ ፡ ቃል ፡ በክርስቶስ ፡ ገላ ፡ እንዲለወጥ ። የክርስቶስም ፡ ሥጋና ፡ ደም ፡ ባንድ ፡ እንዲኖሩ ፡ በንጀራ ፡ ብለው ። ስለዚህም ፡ ሰው ፡ እንደደኅ ፡ እንጀራና ፡ ፀጅ ፡ በቍርባን ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ። አሁንም ፡ የመንፈሳዊ ፡ ጨለማ ፡ ታላቅ ፡ ሁንዋልና ፡ ያልተማሩ ፡ ሕዝብ ፡ ታምራትን ፡ ሁሉን ፡ ሳይመረምሩ ፡ ተቀበሉ ። ጳጳስም ፡ ወደዚያች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለሚሔዱ ፡ ሰዎች ፡ ሁሉ ፡ የኃጢአትንና ፡ የንስሓውን ፡ ፈትሐት ፡ ሰጣቸው ፡ እጅግ ፡ ብርም ፡ ከዚያ ፡ መንገድ ፡ ሆነለት ፡ ለርሱና ፡ ላገር ፡ ቀሳውስት ። ሕዝብ ፡ ግን ፡ እጅግ ፡ ኃጢአት ፡ ጨመሩበት ፡ ስለ ፡ ፈትሐታቸው ። ስለዚህም ፡ የጵራግ ፡ ሜትሮጶሊታን ፡ ይህነን ፡ ነገር ፡ ከሁስና ፡ ከሌሎች ፡ ጋራ ፡ መረመረ ፡ አሰትም ፡ ሁኖ ፡ ገለጸው ። ሰውንም ፡ ሁሉን ፡ በመግዛት ፡ ከለከለ ፡ ወደዚያ ፡ ስፍራ ፡ ከመሔድ ። ይህም ፡ ባመት ፡ ፲፬፻፲፭፡ ሆነ ። ሁስም ፡ መልካም ፡ መጽሐፍን ፡ ጻፈ ፡ በዚያ ፡ ስሕተት ፡ ላይ ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ታላቅ ፡ ክርክር ፡ ተነሣ ፡ በቦሄሚያ ፡ ስለዚች ፡ ትምህርት ፡ ከዊክሊፍ ፡ ትምህርት ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ሁና ፡ የታወቀች ። የዚያ ፡ ዘመንም ፡ የጲሳ ፡ ሲኖደስ ፡ ተሰብስባ ፡ ነበረች ፡ ሜትሮጶሊታንም ፡ ከጳጳስ ፡ ጋራ ፡ ሲሆን ፡ ንጉሥ ፡ ዌንጽስላውስ ፡ ግን ፡ ከሲኖደስ ፡ ጋራ ፡ ሁስም ፡ ከሲኖደስ ፡ ጋራ ፡ ነበረ ፡ ተስፋ ፡ አድርገዋልና ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ደህንነት ፡ እንዲጠቅም ። በዚህ ፡ መክንያትም ፡ ሜትሮጶሊታኑ ፡ ጸላቱ ፡ ሆነ ። ያም ፡ ሁስ ፡

መናፈቅ ፡ ነው ፡ አለ ። ከዊክሊፍም ፡ ከሚሊችም ፡ መጻሕ
ፍት ፡ ፳፪ ፡ በሳት ፡ አቃጠለ ፡ ሁስንም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
በሌላ ፡ ስፍራም ፡ ከመስበክ ፡ ከለከለው ። በዚህ ፡ ማድ
ረጉም ፡ የሁስ ፡ ወዳጆች ፡ በሕዝብ ፡ መኻከል ፡ እጅግ ፡ ታ
ወኩ ። ሁስም ፡ ከመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ለስብከት ፡ እንደ ፡
ተጸራ ፡ በልቡ ፡ ታምኖ ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ለሜትሮጶሊታን ፡ እ
ሺ ፡ አላለም ። ጸላቶቹም ፡ ታምራትን ፡ ሊያደርግ ፡ ሲፈል
ጉት ፡ በታምራት ፡ ይመሰከር ፡ ዘንድ ፡ ብለው ፡ እርሱ ፡
እንደህ ፡ ሲል ፡ መለሰላቸው ። አሰተኛ ፡ መሢሕ ፡ ደግሞ ፡ ታ
ምራትን ፡ ያደርጋል ። ደር ፡ የክርስቶስ ፡ የደቀ ፡ መዝሙ
ሩ ፡ ምስክር ፡ ይህ ፡ ነው ። ነፍሱን ፡ ክደ ፡ ክርስቶስን ፡ የሚ
ከተል ። ሁስም ፡ እንዲህ ፡ አለ ። የዊክሊፍን ፡ መጽሐፍ ፡
አነባለሁ ፡ የሰውን ፡ ሁሉን ፡ መጽሐፍ ፡ እንደነብ ፡ ስመረ
ምረው ፡ በርሱም ፡ የተገኘ ፡ እውነት ፡ እስከሞት ፡ ድረስ ፡
እጠብቃለሁ ። እግዚአብሔርም ፡ ኃይልን ፡ ይሰጠኛል ፡ እር
ሱ ፡ ቢወድ ፡ በሞቴ ፡ የሰማዕቶቹን ፡ እክሊል ፡ ለመቀበል ።
ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ጳጳስ ፡ ከናጶሊስ ፡ ንጉሥ ፡ ጋራ ፡ ተጸል
ቶ ፡ ሰውን ፡ ሁሉን ፡ አዘዘ ፡ ወደ ፡ ናፖሊስ ፡ ለጾር ፡ ይሔድ ፡
ዘንድ ፡ ለሚሔዱትም ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአታቸውን ፡ ፈታላቸ
ው ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ሁስ ፡ ከወዳጁ ፡ ሂሮኒሙስ ፡ ከጵራ
ግ ፡ ከሚሉት ፡ ጋራ ፡ ተነሣ ፡ በዚህ ፡ ስሕተትና ፡ ጥፋት ፡ ላ
ይ ፡ ይሰብክ ፡ ዘንድ ፡ ለወንጌልም ፡ ይመስክር ፡ ዘንድ ። ም
ስክራቸውም ፡ ከንቱ ፡ አልነበረም ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ተቀበሉ
ት ፡ እንጅ ፡ የሰውንም ፡ ስሕተት ፡ ትተው ፡ በወንጌል ፡ አመ
ኑ ። ጳጳስም ፡ ሁስን ፡ ገዘተ ። አሁንም ፡ ሜትሮጶሊታኑ ፡
ጵራግን ፡ ከተማውን ፡ ገዘታት ፡ ሁስን ፡ እስኪታወጣ ፡ ድረ
ስ ፡ ከመኻከልዋ ። በዚህ ፡ ሁከትም ፡ ሁስ ፡ አንድ ፡ መጽ
ሐፍን ፡ ጻፈ ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚናገር ፡ በርሱም ፡
የሮምን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መርኰስ ፡ ሁሉ ፡ በወንጌል ፡ ብ
ርሃን ፡ ገለጸ ፡ እውነተኛውንም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እርስዋ
ም ፡ በክርስቶስ ፡ የሚቀደሱ ፡ ሰዎች ፡ ጉበኤ ፡ እንድትሆን ፡
አንድ ፡ ራስም ፡ ያላት ፡ እርሱም ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ሌ
ላ ፡ የለም ፡ ብሎ ። የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ጵራግን ፡ ትቶ ፡ ወደን

ድ ፡ ወደጁ ፡ ሔደ ፡ ከዚያም ፡ ስብከቱን ፡ በቦሄሚያ ፡ ቋን
ቋ ፡ ለሕዝብ ፡ ጻፈ ፡ በሜደም ፡ ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ ሰበከ ፡፡
የዚያን ፡ ጊዜም ፡ የኮንስታንስ ፡ ሲኖደስ ፡ ተሰብስባ ፡ ሁ
ስ ፡ ደግሞ ፡ ወደዚያ ፡ ተጸራ ፡ ይመረመር ፡ ይፈረድበትም ፡
ዘንድ ፡፡ ሲጊስሙንድም ፡ ንጉሥ ፡ ለደህንነቱ ፡ ይጠብቀ
ው ፡ ዘንድ ፡ በደህንነትም ፡ ይመልሰው ፡ ዘንድ ፡ ተስፋ ፡ አ
ስደረገለት ፡፡ ሁስ ፡ ግን ፡ በንጉሥ ፡ ነገር ፡ አልታመነም ፡ በእ
ግዚአብሔር ፡ እንጂ ፡ እንደህ ፡ ሲል ፡ ጉባኤውን ፡፡ የጸላቶ
ቼ ፡ ቍጥር ፡ ከክርስቶስ ፡ ጸላቶችን ፡ እርሱ ፡ በተሰቀለ ፡ ጊ
ዜ ፡ ከነበሩት ፡ ይበዛል ፡፡ እኔ ፡ ግን ፡ በእግዚአብሔር ፡ አም
ናለሁ ፡፡ እርሱም ፡ አእምሮ ፡ ይሰጠኛል ፡ በጸላትነት ፡ ላይ ፡፡
ኃይልንም ፡ ይሰጠኛል ፡ ግዞትንና ፡ ሞትን ፡ ለመናቅ ፡፡ በሞ
ቴ ፡ አመሰግነው ፡ ዘንድ ፡ ብችል ፡ እርሱ ፡ ያስቸኵለው ፡፡
ብመለስ ፡ ግን ፡ እርሱ ፡ ይጠብቀኝ ፡ ለውነት ፡ ሳይጉዱ ፡ እ
መለስ ፡ ዘንድ ፡፡ ሁለት ፡ ታላላቆችን ፡ ሰዎች ፡ ለሁስ ፡ ሰ
ጡ ፡ በመንገድ ፡ ይጠብቁት ፡ ዘንድ ፡፡ አንደኛቸውም ፡ እጅ
ግ ፡ የወደደው ፡ ወደጁ ፡ ነበረ ፡ ዮሐንስ ፡ ከኽሉን ፡፡
ሁስም ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ በኮንስታንስ ፡ ከተቀመጠ ፡ በኋላ ፡ ሳ
ደሰሙት ፡ ስሕተቱን ፡ እንዲክድ ፡ ፈለጉት ፡፡ እርሱ ፡ ግን ፡
እንደህ ፡ ብሎ ፡ መለሰ ፡፡ እኔ ፡ እሞት ፡ ዘንድ ፡ እወደለሁ ፡
አውቄ ፡ በስሕተት ፡ ከመኖር ፡ ይልቅ ፡፡ ሲኖደስም ፡ አልመ
ረመሩትም ፡ ሳይመረምሩት ፡ ወደ ፡ ግዞት ፡ ጨመሩት ፡ እ
ንጅ ፡፡ ንጉሥም ፡ ሊፈታው ፡ በፈለገ ፡ ጊዜ ፡ ጳጳስ ፡ ከለከለ
ው ፡ ሲል ፡፡ ለመናፈቅ ፡ ሁሉ ፡ የተሰጠ ፡ ተስፋና ፡ መሐላ ፡
ማፍረስ ፡ ኃጢአት ፡ ሁኖ ፡ አይቈጠርም ፡፡ በግዞትም ፡
እጅግ ፡ ሲታመም ፡ መክሰሳቸውን ፡ አመጡለት ፡፡ እርሱ ፡
ግን ፡ ተናጋሪውን ፡ ፈለገ ፡ ከመክሰሳቸው ፡ ያነጻው ፡ ዘን
ድ ፡ ነሡበትም ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ሁስ ፡ ዓይኑን ፡ ወደ ፡ ሰ
ማይ ፡ አቅንቶ ፡ አለ ፡፡ እንጊደህ ፡ አንተ ፡ ጌታዬ ፡ የሱስ ፡
ክርስቶስ ፡ ሆይ ፡ ጸራክሌቶሴና ፡ ፍራጄ ፡ ሁን ፡፡ ፍራጄም ፡
በቅርብ ፡ ዘመን ፡ ይፈርድባችኋል ፡፡ ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ ቀረ
ቡለት ፡ ብዙ ፡ ጊዜም ፡ ፈተኑት ፡ ከሃይማኖቱ ፡ ያወኩት ፡
ዘንድ ፡ እርሱ ፡ ግን ፡ ሁለግዜ ፡ ጸንቶ ፡ ኖረ ፡፡ በረፍትም ፡

በየውሃትም ፡ የክርስቶስን ፡ ስም ፡ ታምኖ ፡ አስታወቀ ፡፡
ሰባት ፡ ወርም ፡ በግዞት ፡ ከተቀመጠ ፡ በኋላ ፡ ፈረደ፡በት ፡፡
ሁስም ፡ መስማትን ፡ ለመኒ ፡ ከሲኖደስ ፡ ደሮ ፡ አልሰሙት
ም ፡ ስለዚህ ፡ አሁንም ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ ክርስቶስ ፡ ተማጸ
ነ ፡፡ ሲኖደስም ፡ ይህ ፡ መበደል ፡ ሁኖ ፡ ቊጠረበት ፡ ክርስቶ
ስ ፡ እንደ፡ደፈርድባቸው ፡ ሲመስላቸው ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜ
ም ፡ ለጸላቶቹ ፡ ጸለየ ፡ እግዚአብሔር ፡ ኃጢአታቸውን ፡ እ
ንደ፡ደቊጥርባቸው ፡፡ ፈርደቸውንም ፡ እንደ፡ህ ፡ ብለው ፡
ቊረጡ ፡፡ ሁስ ፡ የማይመልስ ፡ ነፈቂ ፡ ነውና ፡ በሳት ፡ ደሞ
ት ፡ ዘንድ ፡ ደገባዋል ፡፡ የንጨትንም ፡ መድብ ፡ አድርገው ፡
በመኻከሉ ፡ አሠረት ፡፡ ሁሉም ፡ ተንበርክኮ ፡ ነፍሱን ፡ ለ
እግዚአብሔር ፡ አደራ ፡ ሰጣት ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ አንድ ፡
መኰንን ፡ ደግሞ ፡ ሊክድ ፡ ፈለገው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሁስ ፡ በሃ
ይማኖቱ ፡ ጸና ፡፡ እንጨትንም ፡ አንድደው ፡ አቃጠሉበት ፡፡
የሁስ ፡ ወዳጅም ፡ ሄሮኒሙስ ፡ ከጵራግ ፡ እርሱ ፡ ደግ
ሞ ፡ ወደ ፡ ኮንታንስ ፡ መጣ ፡ ከዚያም ፡ ታሥሮ ፡ እጅግ ፡ ቀ
ን ፡ ከተቀመጠ ፡ በኋላ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ደከመ ፡ ካደም ፡፡ በ
ኋላ ፡ ግን ፡ በክደቱ ፡ አዘነ ፡ በግልጽም ፡ ስለ ፡ ክደቱ ፡ ንስሐ ፡
ገባ ፡ እርሱንም ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ እሳት ፡ ጨመረት ፡፡ በእሳ
ትም ፡ ሲሞት ፡ እግዚአብሔርን ፡ አመሰገነ ፡፡
ሁስም ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ሁከት ፡ ሆነ ፡ በ
ቦሄሚያ ፡፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ተነሡ ፡ በጳጳስ ፡ ላይ ፡ ሌላውን ፡
የተሻለውን ፡ ሥርዓት ፡ የፈለጉ ፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያናቸ
ው ፡፡ ንጉሥም ፡ ግድ ፡ ባደረገ ፡ ጊዜ ፡ እርሳቸው ፡ ዐመፁ ፡፡
ነገር ፡ ግን ፡ እርሳቸው ፡ ተለዩ ፡፡ እኵሌታቸውም ፡ ከባሲ
ል ፡ ሲኖደስ ፡ ጋራ ፡ ተሰማሙ ፡ እኵሌታቸውም ፡ ጾር ፡ አ
ደረጉ ፡፡ ይህ ፡ ጾርም ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ አልተጨረሰም ፡፡ ነ
ገር ፡ ግን ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ከጾር ፡ ተለደተው ፡፡ የሁስን ፡ የወ
ንጌልንም ፡ ትምርት ፡ በልባቸው ፡ ጠበቁት ፡ በዝምታም ፡
በስውርም ፡ ቊዩ ፡ እግዚአብሔር ፡ በስደት ፡ እስኪገልጻቸ
ው ፡ ድረስ ፡ በሚመጣው ፡ ዘመን ፡፡

የቤት ፡ ክርስቲያን ፡

ታሪክ ፡

ሶባተኛ ፡ ክፍል ፡፡

ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ከመታደስዋ ፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡

መዝረጋትዋ ፡ ድረስ ፡፡

ካመትም ፡ ፲፭፲፯፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፲፯፵፭፡ ድረስ ፡፡

በዚህ ፡ ዘመንም ፡ የነገሡ ፡ ነገሥታት ፡ እሊህ ፡ ናቸው ።

1. ካርሉ ፡ ፭ ፡ የንምሳና ፡ የስጳንያ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፭፳ ።
2. ክርስቲያን ፡ ፪ ፡ የስዊድንና ፡ የደንማርክ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፭፳ ።
3. ፍሪድሪኽ ፡ ፩ ፡ የደንማርክ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፭፳፫ ።
4. ጉስታውስ ፡ ዋሳ ፡ የስዊድን ፡ ንጉሥ ፡ ፲፭፳፫ ።
5. ፈርዲናንድ ፡ ካውስትርያ ፡ የሁንጋርያ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፭፳፮ ።
6. ኢዋን ፡ ፬ ፡ የሞስኮብ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፭፴፫ ።
7. ኤድዋርድ ፡ ፮ ፡ የእንግሊጣር ፡ ንጉሥ ፡ ፲፭፵፯ ።
8. ሀንሪ ፡ ፪ ፡ የፍራንስ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፭፵፯ ።
9. ሲጊስሙንድ ፡ ፪ ፡ የጶሎኒያ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፭፵፰ ።
10. ማርያም ፡ የእንግሊጣር ፡ ንግሥት ፡ ፲፭፶፫ ።
11. ፈርዲናንድ ፡ ፩ ፡ የንምሳ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፭፶፮ ።
12. ፊልጶስ ፡ ፪ ፡ የስጳንያ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፭፶፮ ።
13. ኤልሳቤጥ ፡ የእንግሊጣር ፡ ንግሥት ፡ ፲፭፶፰ ።
14. ፍሪድሪኽ ፡ ፪ ፡ የደንማርክ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፭፶፱ ።
15. ፍራንሲስ ፡ ፪ ፡ የፍራንስ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፭፶፱ ።
16. ኤሪክ ፡ ፲፬ ፡ የስዊድን ፡ ንጉሥ ፡ ፲፭፷ ።
17. ካርሉ ፡ ፱ ፡ የፍራንስ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፭፷ ።
18. መክሲሚልያን ፡ የሮም ፡ ንጉሥ ፡ ፲፭፷፪ ።
19. መክሲሚልያን ፡ ፪ ፡ የንምሳ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፭፷፪ ።
20. ዮሐንስ ፡ ፫ ፡ የስዊድን ፡ ንጉሥ ፡ ፲፭፷፰ ።
21. ሀንሪ ፡ ፫ ፡ የፍራንስ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፭፸፬ ።
22. ሩዶልፍ ፡ ፪ ፡ የንምሳ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፭፸፮ ።
23. ሀንሪ ፡ የጶርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ ፲፭፸፱ ።
24. ፊዎደር ፡ የሞስኮብ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፭፹፬ ።
25. ሲጊስሙንድ ፡ ፫ ፡ የጶሎንያ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፭፹፯ ።
26. ክርስቲያን ፡ ፬ ፡ የደንማርክ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፭፹፰ ።
27. ሀንሪ ፡ ፬ ፡ የፍራንስ ፡ ንጉሥ ። ፲፭፹፱ ።
28. ሲጊስሙንድ ፡ ፬ ፡ የጶሎንያ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፭፺፪ ።
29. ፊልጶስ ፡ ፫ ፡ የስጳንያ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፭፺፰ ።

30. ያዕቆብ ፡ ፩፡ የእንግሊጣር ፡ ንጉሥ ። ፲፮፻፫።
31. ካርል ፡ ፱፡ የስዊደን ፡ ንጉሥ ፡ ፲፮፻፬።
32. ሉድዊግ ፡ ፲፫፡ የፈራንስ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፮፻፲።
33. ጉስታውስ ፡ አደልፈ ፡ የስዊደን ፡ ንጉሥ ፡ ፲፮፻፲፩።
34. ማቲያስ ፡ የሁንጋርያ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፮፻፲፪።
35. ሚካኤል ፡ ሮማኖው ፡ የሞስኮብ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፮፻፲፫።
36. ፈርዲናንድ ፡ ፪፡ የንምሳ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፮፻፲፯።
37. ፍሪድሪኽ ፡ የቦሄሚያ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፮፻፲፱።
38. ፊልጶስ ፡ ፬፡ የስጳንያ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፮፻፳፩።
39. ቻርለስ ፡ ፩፡ የእንግሊጣር ፡ ንጉሥ ፡ ፲፮፻፳፭።
40. ውላዲስላውስ ፡ ፬፡ የጶሎንያ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፮፻፴፪።
41. ፈርዲናንድ ፡ ፫፡ የንምሳ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፮፻፴፯።
42. ዮሐንስ ፡ የጶርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ ፲፮፻፵።
43. ሉድዊግ ፡ ፲፬፡ የፈራንስ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፮፻፵፫።
44. ዮሐንስ ፡ ካሲሚር ፡ የጶሎኒያ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፮፻፵፰።
45. ፍሪድሪኽ ፡ ፫፡ የደንማርክ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፮፻፵፰።
46. ክሮምዌል ፡ የእንግሊጣር ፡ ጠባቂ ፡ ፲፮፻፶፫።
47. አልፎንስ ፡ ፮፡ የጶርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ ፲፮፻፶፮።
48. ካርል ፡ ፲፡ የስዊደን ፡ ንጉሥ ፡ ፲፮፻፶፬።
49. ሌዎጶልድ ፡ የንምሳ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፮፻፶፰።
50. ካርል ፡ ፲፩፡ የስዊደን ፡ ንጉሥ ፡ ፲፮፻፷።
51. ቻርለስ ፡ ፪፡ የእንግሊጣር ፡ ንጉሥ ፡ ፲፮፻፷።
52. ካርል ፡ ፪፡ የስጳንያ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፮፻፷፪።
53. ክርስቲያን ፡ ፭፡ የደንማርክ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፮፻፸።
54. ዮሐንስ ፡ የጶሎኒያ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፮፻፸፬።
55. ፌዎደር ፡ ፫፡ የሞስኮብ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፮፻፸፮።
56. ጴጥሮስ ፡ ፩፡ የሞስኮብ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፮፻፹፪።
57. ያዕቆብ ፡ ፪፡ የእንግሊጣር ፡ ንጉሥ ፡ ፲፮፻፹፭።
58. ዊልያም ፡ ፫፡ የእንግሊጣር ፡ ንጉሥ ፡ ፲፮፻፹፱።
59. ካርል ፡ ፲፪፡ የስዊደን ፡ ንጉሥ ፡ ፲፮፻፺፯።
60. ፍሪድሪኽ ፡ ፬፡ የደንማርክ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፮፻፺፱።
61. ፍሪድሪኽ ፡ ፩፡ የጵሩስያ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፯፻፩።
62. አና ፡ የእንግሊጣር ፡ ንግሥት ፡ ፲፯፻፪።

63. ዮሴፍ ፡ ፩፤ የንምሳ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፯፭።
64. ዮሐንስ ፡ ፭፤ የጶርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ ፲፯፮።
65. ካርል ፡ ፮፤ የንምሳ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፯፲፩።
66. ፍሪድሪኽ ፡ ዊልሄልም ፡ ፩፤ የጵረስያ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፯፲፫።
67. ጊዎርጊስ ፡ ፩፤ የእንግልጣር ፡ ንጉሥ ፡ ፲፯፲፬።
68. ሉድዊግ ፡ ፲፭፤ የፍራንስ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፯፲፭።
69. ኡልሪካ ፡ ኤሌዎኖራ ፡ የስዌደን ፡ ንግሥት ፡ ፲፯፲፰።
70. ፍሪድሪኽ ፡ ፩፤ የስዌደን ፡ ንጉሥ ። ፲፯፳።
71. ሉድዊግ ፡ ፪፤ የስጳንያ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፯፳፬።
72. ካታሪና ፡ ፪፤ የሞስኮብ ፡ ንግሥት ፡ ፲፯፳፭።
73. ጊዎርጊስ ፡ ፪፤ የእንግልጣር ፡ ንጉሥ ፡ ፲፯፳፯።
74. ጴጥሮስ ፡ ፪፤ የሞስኮብ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፯፳፯።
75. አና ፡ የሞስኮብ ፡ ንግሥት ፡ ፲፯፴።
76. ክርስቲያን ፡ ፮፤ የደንማርክ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፯፴።
77. ካርል ፡ የስጳንያ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፯፴፬።
78. ማርያም ፡ ቴሬስያ ፡ የንምሳ ፡ ንግሥት ፡ ፲፯፵።
79. ፍሪድሪኽ ፡ ፪፤ የጵረስያ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፯፵።
80. ኤልሳቤጥ ፡ የሞስኮብ ፡ ንግሥት ። ፲፯፵፩።
81. ካርል ፡ ፯፤ የንምሳ ፡ ንጉሥ ። ፲፯፵፪።
82. ፍራንሲስ ፡ ፩፤ የንምሳ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፯፵፭።
83. ፌርዲናንድ ፡ ፮፤ የስጳንያ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፯፵፮።
84. ዮሴፍ ፡ የጶርቱጋል ፡ ንጉሥ ፡ ፲፯፶።
85. አዶልፍ ፡ ፍሪድሪኽ ፡ የስዌደን ፡ ንጉሥ ፡ ፲፯፶፩።
86. ጊዎርጊስ ፡ ፫፤ የእንግልጣር ፡ ንጉሥ ፡ ፲፯፷።
87. ጴጥሮስ ፡ ፫፤ የሞስኮብ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፯፷፪።
88. ስታኒስላውስ ፡ የጶሎኒያ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፯፷፬።
89. ዮሴፍ ፡ ፪፤ የንምሳ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፯፷፭።
90. ክርስቲያን ፡ ፯፤ የደንማርክ ፡ ንጉሥ ። ፲፯፷፮።
91. ጉስታውስ ፡ ፫፤ የስዌደን ፡ ንጉሥ ። ፲፯፸፩።
92. ሉድዊግ ፡ ፲፮፤ የፍራንስ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፯፸፬።
93. ማርያም ፡ የጶርቱጋል ፡ ንግሥት ፡ ፲፯፸፯።
94. ፍሪድሪኽ ፡ ዊልሄልም ፡ ፪፤ የጵረስያ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፯፹፮።
95. ካርል ፡ ፬፤ የስጳንያ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፯፹፰።

96. ሌዎጶልድ ፡ ፪፤ የንምሳ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፯፺፡፡
97. ጉስታውስ ፡ አደልፍ ፡ ፬፤ የስዌደን ፡ ንጉሥ ፡ ፲፯፺፩፡፡
98. ፍራንሲስ ፡ ፪፤ የንምሳ ፡ ንጉሥ ፡ ፲፯፺፪፡፡

ሰባት ፡ መቶ ፡ አመት ፡ ከክርስቶስ ፡ ልደት ፡ አስቀድሞ ፡ እግዚአብሔር ፡ በነቢዩ ፡ በይሳይያስ ፡ አፍ ፡ የምእምናንን ፡ ጉባኤ ፡ አላት ፡፡ ተነሺ ፡ ብሪም ፡ ብርሃንሽ ፡ መጥትዋልና ፡ የእግዚአብሔርም ፡ ምስጋና ፡ በላየሽ ፡ ወጥትዋልና ፡፡ እነሆ ፡ ጨለማ ፡ የምድርን ፡ ፊት ፡ ሸፈነ ፡ ጽጋግም ፡ አሕዛብን ፡ ነገር ፡ ግን ፡ በላይሽ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይወጣል ፡ ምስጋናውም ፡ በላየሽ ፡ ያበራል ፡፡ የዚህችም ፡ ትንቢት ፡ በታላቅ ፡ ክፍል ፡ ተፈጸመች ፡ ጌታችን ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ በወረደ ፡ ጊዜ ፡ በሐዋርያት ፡ አፍም ፡ ወንጌሉን ፡ በየሩሳሌም ፡ ባሰበከ ፡ ጊዜ ፡፡ በኋላቸው ፡ ግን ፡ ጨለማ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በዛች ፡ ከ፲፱፤ አመትም ፡ በዝታ ፡ ኖረች ፡፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ኃይልም ፡ ብርሃን ፡ መውጣት ፡ አልተቻላትም ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ እግዚአብሔር ፡ ብርሃንን ፡ አወጣ ፡ ከጨለማ ፡ መኻከል ፡ በያፌት ፡ ልጆችም ፡ ላይ ፡ የወንጌል ፡ ብርሃን ፡ አበራች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያኒቱም ፡ ታደሰች ፡፡

ይህም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ስራ ፡ ነው ፡፡ እርሱም ፡ ሰውን ፡ እንደ ፡ እቃው ፡ ብቻ ፡ አደረገ ፡ ስለዚህም ፡ ክብር ፡ ሁሉ ፡ ለርሱ ፡ ይገባል ፡፡ ከለዚያ ፡ ሰዎች ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንደ ፡ እቃው ፡ ያገለገሉት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ለማብራትና ፡ በማቅናት ፡ እሌህ ፡ ይበልጣሉ ፡፡ ሉተርና ፡ ሜላንኽቶን ፡ በንምሳ ፡፡ ጽዊንግሊና ፡ ከልዊንም ፡ በሄልዌትያ ፡፡ ክረንመርና ፡ ሪድሌም ፡ ለቲመርም ፡ በእንግልጣር ፡፡ እርሳቸውም ፡ ብቻቸው ፡ አልነበሩም ፡፡ እግዚአብሔር ፡ በዚያ ፡ ዘመን ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ አስነሣ ፡ እንጂ ፡ በኤውሮጳ ፡ ሁሉ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ጉዳይ ፡ ያወቁ ፡ የወንጌልንም ፡ ትምህርት ፡ በሐዋርያት ፡ መጸሐፍት ፡ እንደ ፡ ተሰጠ ፡ ከሰው ፡ መጨመርያ ፡ ነጽቶ ፡ ከስውር ፡ ወደ ፡ ግልጥ ፡ ያወጡ

ት ። ክርሳቸውም ፡ የሚበለጥ ፡ ማርቲን ፡ ሉተር ፡ ነበረ ።
እርሱም ፡ ባመት ፡ ፲፬፹፫፧ በደህና ፡ ወላጆች ፡ ተወለደ ፡
አይስሌበን ፡ በሚልዋት ፡ አገር ። በሰክሰን ፡ ምድር ። እር
ሱም ፡ ከሕፃንነቱ ፡ ጀምሮ ፡ ዕድሜው ፡ ፰፧ አመት ፡ ሲሆን ፡
ተማረ ፡ አባቱ ፡ ወደ ፡ መድረሳ ፡ ወደ ፡ ማስተማርያ ፡ አግብ
ቶት ። በመከራ ፡ በየውሃትም ፡ አድጎ ፡ ከተማረ ፡ በኋላ ፡
የመምህርን ፡ ማዕረግ ፡ ደብተራ ፡ የሚመስል ፡ መጊስተር
ም ፡ የሚሉት ፡ ካገኘ ፡ በኋላ ፡ አባቱ ፡ ፍርድን ፡ እንዲማር ፡
እንዲያስተምርም ፡ ፈራጅም ፡ እንዲሆን ፡ ወደደ ። የዚያ
ን ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ በልቡ ፡ ሰራ ፡ ልቡን
ም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ለመቀበል ፡ አሰናደወ ። ባመት ፡
፲፭፭፧ እርሱ ፡ በመንገድ ፡ ሲሆን ፡ ነጐድጓድ ፡ መብረቅ ፡ ሆ
ነ ፡ መብረቅም ፡ አንዱን ፡ ባጠገቡ ፡ የሔደውን ፡ ወዳጁን ፡ ገ
ድሎት ፡ ሉተርን ፡ ወደ ፡ ምድር ፡ ጣለ ። ከተነሣም ፡ በኋላ ፡
ከሞት ፡ እንደ ፡ ዳነ ፡ ባየ ፡ ጊዜ ፡ በልቡ ፡ ስለ ፡ ሞቱ ፡ ከሞ
ትም ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ ሚመጣው ፡ ፍርድ ፡ አሰበ ። ለሞቱ
ም ፡ ልቡን ፡ ያሰናድው ፡ ዘንድ ፡ ብሎ ፡ ያለምን ፡ ሕይወት ፡
ካደ ፡ ወደ ፡ ምንኵስናም ፡ ገባ ። በገደምም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ሁ
ሉ ፡ ብርቱ ፡ መጋደልን ፡ ተጋደለ ፡ የታዘዘውንም ፡ ያልታዘዘ
ውንም ፡ ተግባር ፡ አደረገ ፡ በምግባሩ ፡ ይጸድቅ ፡ ዘንድ ፡ ልቡ
ንም ፡ ከኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ ያነጻ ፡ ዘንድ ፡ ብሎ ። ሉተር ፡ እ
ንደ ፡ ሞናኵስት ፡ ብዛት ፡ አልነበረምና ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ ክ
ብርን ፡ የሚሹ ፡ ከሰውም ፡ ጻድቃን ፡ ደባሉ ፡ ዘንድ ፡ ብቻ ፡
የሥጋቸውን ፡ ንጽሕና ፡ በሰው ፡ ፊት ፡ የሚሰሩ ፡ የልባቸውን ፡
መርኵስ ፡ ሳይጠብቁ ። ነገር ፡ ግን ፡ ሉተር ፡ ከእግዚአብሔር ፡
ፍርድ ፡ ፈራ ። እግዚአብሔር ፡ የልብን ፡ አሳብና ፡ መሻ
ት ፡ እንዲያይ ፡ እንዲፈርድበትም ፡ አውቅዋልና ። ስለዚ
ህም ፡ ልቡን ፡ ከሥጋዊ ፡ መሻት ፡ ሁሉ ፡ ከኃጢአትም ፡ ሁ
ሉ ፡ ያነጻ ፡ ዘንድ ፡ ፈለገ ። የእግዚአብሔርን ፡ መንገድ ፡
ግን ፡ አያውቅም ፡ ነበረ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ትምህርት ፡
በዚያ ፡ ዘመን ፡ የሚያስተምረባት ፡ ከወንጌል ፡ እጅግ ፡
ርቃለችና ። ሰውም ፡ በተግባሩ ፡ በጾም ፡ በድካምም ፡ በ
ምጽዋዕትም ፡ በመከራም ፡ በመገረፍም ፡ ይጸድቃል ፡ አ

ሉ ፡፡ ሉተር ፡ ይህነን ፡ ሁሉ ፡ በራሱ ፡ አብዝቶ ፡ ዕረፍት ፡ አ
ላገኘም ፡ ለነፍሱ ፡፡ ሥጋውን ፡ ሲያደክም ፡ ሲገሥጸውም ፡
ሲገርፈውም ፡ የልቡ ፡ ኀጢአት ፡ በረታበት ፡ ክፉ ፡ አሳብ
ም ፡ አልተሸነፈም ፡ በመጋደሉ ፡ ሁሉ ፡ በረታ ፡ እንጂ ፡፡ ስ
ለዚህም ፡ ሉተር ፡ በእግዚአብሔር ፡ ማሰብን ፡ አልቻለው
ም ፡ በፍርሃትና ፡ በመንቀጥቀጥ ፡ እንጂ ፡፡ ሉተርም ፡ ባለ
ቤቱ ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡፡ ማንም ፡ ከቶ ፡ በም
ንኩስና ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ከደረሰ ፡ እኔ ፡ በደረስሁ ፡ እጅግ ፡
በምንኩስና ፡ በኖርሁ ፡ ራሴን ፡ ለሞት ፡ ባደረስሁ ፡ ሥጋዬ
ን ፡ በማድከም ፡፡ ይህም ፡ ሁሉ ፡ ሲበዛ ፡ ሉተርም ፡ ለማየ
ት ፡ እጅግ ፡ ደህና ፡ ሞናክሴ ፡ ሲሆን ፡ በሰውም ፡ ፊት ፡ ጽ
ድቅ ፡ ሁኖ ፡ በተቈጠረ ፡ ሁሉ ፡ በተመላለሰ ፡ ጊዜ ፡ የልቡ ፡
ኀጢአት ፡ በዛ ፡ ጭንቀቱም ፡ ፍርሃቱም ፡ ኀዘኑም ፡ ወዴት ፡
እኖራለሁ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ብሎ ፡፡ ማን ፡ ይረደኛ
ል ፡ ከኀጢአቴ ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ ቍጣ ፡፡ ከዚህም ፡ ከ
ሐዘኑ ፡ የተነሣ ፡ ሉተር ፡ በጅግ ፡ ብርቱ ፡ ሕማም ፡ ወደቀ ፡፡
ላንድ ፡ ሽማግሌም ፡ ሞነክሴ ፡ በተናዘዘ ፡ ጊዜ ፡ ጭንቀቱ
ንም ፡ ባስታወቀው ፡ ጊዜ ፡ ያ ፡ የወንጌልን ፡ ማጽናት ፡ አጸ
ናው ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ ተስፋውን ፡ አትጣል ፡ እመን ፡ ብ
ቻ ፡ በሐዋርያት ፡ ሃይማኖት ፡ የምናምን ፡ እንዲህ ፡ ብላን ፡፡
እኔ ፡ አምናለሁ ፡ በኀጢአት ፡ ሰርየት ፡፡ ይህም ፡ የዚ
ያን ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ልቡ ፡ ገባ ፡ ደሮ ፡ አልጸናበትም ፡፡ እግዚአብ
ሔር ፡ ቃሉን ፡ እስኪከፍትለት ፡ ድረስ ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡
አንድ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡ የብዙ ፡ ገደሞች ፡ አለቃ ፡ ስሙም ፡ ስታ
ውጲጽ ፡ እርሱም ፡ የሉተርን ፡ መጋደል ፡ አወቀ ፡ ባለቤቱ ፡
በፊት ፡ እንደ ፡ ሉተር ፡ ይጋደል ፡ ነበረና ፡ በሃይማኖትም ፡
የነፍሱን ፡ ዕረፍት ፡ አገኘ ፡፡ እርሱም ፡ ባየው ፡ ጊዜ ፡ አለ
ው ፡፡ ወንድሜ ፡ ሆይ ፡ እግዚአብሔርን ፡ አሁን ፡ ደስ ፡ ታሰ
ኝ ፡ ዘንድ ፡ አሁንም ፡ ከኀጢአትህ ፡ ትነጻ ፡ ዘንድ ፡ አትሻ ፡
አይሆንልህምና ፡፡ አሁን ፡ ብቻ ፡ የኢየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ በሃ
ይማኖት ፡ ጸንተህ ፡ ያዘው ፡ የርሱንም ፡ ጸጋ ፡ በኀጢአትህ ፡
ሰርየት ፡ ተቀበል ፡ ይህም ፡ ሃይማኖት ፡ ፍቅር ፡ በልብህ ፡ ይ
ሰራል ፡ ፍቅርም ፡ ብቻ ፡ ይችላል ፡ እውነተኛውን ፡ ንስሓ ፡

እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘውን ፡ ይሰራ ፡ ዘንድ ። ፈርሃት ፡ ግን ፡ አይችለውም ።

ይህ ፡ ነገረም ፡ እውነት ፡ ነው ። በፍርሃት ፡ በናዝን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፍርድ ፡ የገሃናምንም ፡ ሥቃይ ፡ ስንፈራ ፡ ስለ ፡ ራሳችን ፡ ብቻ ፡ እናዝናለን ። ይህም ፡ ንስሓ ፡ ከኃጢአት ፡ አይነጻም ። እግዚአብሔርን ፡ ግን ፡ ብንወድ ፡ የንስሓችንና ፡ ያዘናችን ፡ መክንያት ፡ ይህ ፡ ነው ፡ እግዚአብሔርን ፡ እንደ ፡ በደልነው ። ወደጅም ፡ ወዳጁን ፡ መበደል ፡ እንደደወድ ፡ እንደሁም ፡ ሰው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ወዳጅ ፡ ቢሆን ፡ ቢበድለው ፡ እጅግ ፡ ብርቱ ፡ አዘን ፡ ያዝናል ። ይህ ፡ አዘንም ፡ ብቻ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ ያሰኛል ።

የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ሉተር ፡ የጳውሎስን ፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ ሮሜ ፡ ሰዎች ፡ መረመረ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ቃሉን ፡ ከፈተለት ። አስቀድሞም ፡ እጅግ ፡ ጊዜ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ መርምሮ ፡ አላስተወለውም ፡ እንደ ፡ ሰው ፡ ትምህርት ፡ መርምሮታልና ፡ ያባቶችን ፡ ትርጓሜ ፡ ብቻ ፡ ሲይዝ ፡ የሮም ፡ ጳጳስ ፡ እንደዘዘው ። አሁን ፡ አንድ ፡ ቃል ፡ ታላቅ ፡ ሆነለት ፡ ወደ ፡ ልቡም ፡ ገባ ፡ ጳውሎስ ፡ ሲል ፡ ሮሜ ፡ ፩፡ ፲፯። የእግዚአብሔር ፡ ጽድቅ ፡ በወንጌል ፡ ይገለጻል ፡ ከሃይማኖት ፡ ወደ ፡ ሃይማኖት ፡ እንደ ፡ ተጻፈ ። ጻድቅ ፡ በሃይማኖት ፡ ይሐይዋል ። ይህነን ፡ ነገር ፡ ሲመረምር ፡ በልቡ ፡ ተጠራጠረ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ። ምንድር ፡ ነው ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጽድቅ ። አሁንም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የተቀበሉት ፡ ትምህርት ፡ እንዲህ ፡ ነበረ ። የእግዚአብሔር ፡ ጽድቅ ፡ ይህ ፡ ነው ። በነ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔር ፡ ሰውን ፡ በሕጉ ፡ ያዘዘው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፈቃድ ፡ መፈጸም ፡ ጽድቅ ፡ ነው ። ሉተርም ፡ ይህነን ፡ ነገር ፡ አስቦ ፡ አላስተወለም ፡ እንዴት ፡ ይችላል ፡ ኃጢአተኛ ፡ ሰው ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ይጸድቅ ፡ ዘንድ ፡ ጻድቅም ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ። የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ የእግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ገለጸለት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጽድቅ ፡ ያ ፡ ጽድቅ ፡ እንደ ሆን ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሚያምን ፡ ሰው ፡ የሚሰጠው ። ያ ፡ ጽድቅም ፡ በወንጌል ፡ ይገለጻል ፡ እግዚአብሔርም ፡ በክርስቶስ ፡ ለሃይ

ማኖት ፡ ይሰጠዋል ፡፡ ክርስቶስ ፡ መድኃኒታችን ፡ ሁኖ ፡ በፈ
ንታችን ፡ ያደረገው ፡ ሁሉ ፡ እርሱ ፡ ጽድቃችን ፡ ነው ፡፡ በው
ነትም ፡ የሚያምን ፡ ሁሉ ፡ ክርስቶስን ፡ እንደ ፡ መድኃኒ
ቱ ፡ የሚቀበለው ፡ ሰው ፡ የክርስቶስን ፡ ሁለንትና ፡ ይቀበላ
ል ፡ እንደሁም ፡ ጽድቁ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ፡ በክርስቶስም ፡
ይጸድቃል ፡፡ ዬሬሚያስ ፡ እንደህ ፡ ይላልና ፡ ስለ ፡ ክርስቶ
ስ ፡ በትንቢቱ ፡፡ ይህ ፡ ይሆናል ፡ ስሙ ፡ የሚጸራበት ፡፡ יְהוָה
צִדְקֵנוּ ይሆዋህ ፡ ጺድቄኑ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጽድቃችን ፡፡ ከ
ዚያ ፡ ዘመንም ፡ ጀምሮ ፡ የሉተር ፡ ጭንቀት ፡ ሸሸ ፡ በሣይ
ማኖቱ ፡ አሸንፏዋልና ፡ ለእግዚአብሔርም ፡ በደስታ ፡ አገለ
ገለ ፡፡ ባመትም ፡ ፲፭፻፰ ፡ የሰክሰን ፡ ጋዢ ፡ ፍሪድሪክ ፡ ጠቢ
ብ ፡ የተባለ ፡ ዊትንበርግ ፡ ወደ ፡ ተባለች ፡ ከተማው ፡ ወሰ
ደው ፡ በዚያም ፡ በነበረች ፡ ኡኒቬርሲታስ ፡ መምህር ፡ ይሆ
ን ፡ ዘንድ ፡ ኮመው ፡ ፊሎሶፊያን ፡ ያስተምር ፡ ዘንድ ፡፡ ባ
መትም ፡ ፲፭፻፲ ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ ወደ ፡ ጳጳስ ፡ ተላከ ፡ ስለ ፡ ስታ
ውጺጽ ፡ ተግባር ፡፡ ወደ ፡ ያም ፡ በደረሰ ፡ ጊዜ ፡ እጅግ ፡ አደነ
ቀ ፡ አዘነም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጥፋት ፡ በጳጳስ ፡ አብያ
ተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ባየው ፡፡ ወደ ፡ ዊትንበርግም ፡ ከተመለ
ሰ ፡ በኋላ ፡ ሁለተኛውን ፡ ማዕረግ ፡ ደክቶር ፡ የሚሉትን ፡ አ
ገኘ ፡ ጋዡም ፡ የክህነትን ፡ መምህር ፡ አደረገው ፡ በኡኒቬር
ሲታስ ፡ ባመት ፡ ፲፭፻፲፪ ፡ ከዚያም ፡ ጀምሮ ፡ ልቡ ፡ ተቃጠለ ፡
ለወንጌል ፡ በመምሰክር ፡፡ እርሱመ ፡ ጀመረ ፡ የእግዚአብ
ሔርን ፡ ቃል ፡ ያስተምር ፡ ዘንድ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁ
ሉ ፡ ከብዙ ፡ ዘመን ፡ አስቀድሞ ፡ ልማድ ፡ ሲሆን ፡ የሰው
ን ፡ ቃል ፡ ያባቶችን ፡ ቃል ፡ ማስተማር ፡፡ ሉተር ፡ አይተዋል
ና ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የገባ ፡ ጥፋት ፡ ሁሉ ፡ በዚህ ፡
መክንያት ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ገባ ፡ የሰው ፡ ቃል ፡ ከእግዚአብ
ሔር ፡ ቃል ፡ ጋራ ፡ እንደ ፡ ተደበለቀ ፡፡ የክርስቶስ ፡ ጉባኤ ፡ በ
ክርስቶስ ፡ በሐዋርያቱም ፡ በነቢያቱም ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ ተመ
ሠርታ ፡ ስትሆን ፡፡ ሉተርም ፡ በዚህ ፡ ቃል ፡ ጸንቶ ፡ እግዚአ
ብሔር ፡ አጸንቶታልና ፡ በእግዚአብሔር ፡ ተጸራ ፡ የዘመኑ
ን ፤ መንፈሳዊት ፡ ጨለማ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የገዛች ፡ ኃ
ይልዋን ፡ ታፈርስ ፡ ዘንድ ፡፡ በዊትንበርግም ፡ እግዚአብሔ

ር ፡ ስራውን ፡ ባረከ ፡ ከዚያም ፡ መምህራንና ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ እጅግ ፡ የበዙ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ይወዱ ፡ ዘንድ ፡ ያስተውሉትም ፡ ዘንድ ፡ ኃይሉንም ፡ በልባቸው ፡ ይቀበሉት ፡ ዘንድ ፡ ጀመሩ ፡፡ አሁን ፡ የእግዚአብሔርና ፡ የቃሉ ፡ ጸላቶች ፡ ያነን ፡ ክርክር ፡ ጀመሩ ፡ መጨረሻው ፡ የውነት ፡ ድል ፡ መንሣት ፡ ከስሕተት ፡ ላይ ፡ የሆነ ፡፡

የሮም ፡ ጳጳስ ፡ ሌዎን ፡ ፲፡ ያለም ፡ የብልሃቱ ፡ የብልጭልጩም ፡ የመርዓቱም ፡ ወደጅ ፡ ነበረ ፡፡ ስለዚህም ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ቤቶች ፡ እጅግ ፡ የተዋበችም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ በሮም ፡ ሠራ ፡፡ ስለዚህም ፡ ስራ ፡ ስለማይጸገብም ፡ መኘቱ ፡ ብርን ፡ ያገኝ ፡ ዘንድ ፡ ብሎ ፡ ወደለም ፡ ሁሉ ፡ ሰደደ ፡ የኃጢአትን ፡ ስርየት ፡ የንስሓንም ፡ ፍትሐት ፡ ይሼጥ ፡ ዘንድ ፡፡ መለክተኞቹም ፡ ወደ ፡ ሰክስን ፡ መጡ ፡ ከርሳቸውም ፡ አንድ ፡ ቴጽል ፡ የሚሉት ፡ እጅግ ፡ ደፋሪ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡ ወንጌልን ፡ እጅግ ፡ ያስነወረ ፡ በማድረጉ ፡፡ እርሱ ፡ ሣፅን ፡ ይዝዋልና ፡ በጫንቃው ፡ የሚሸከመው ፡ ስለ ፡ ፍትሐትም ፡ የተቀበለውን ፡ ብር ፡ ሁሉን ፡ ወደርሱ ፡ አገባ ፡፡ በሣፅንም ፡ ስድብ ፡ ተጻፈ ፡ እንደህ ፡ የሚል ፡፡ ብር ፡ ወደ ፡ ሣፅን ፡ ሲገባ ፡ ጊዜ ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ነፍስ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ይገባል ፡፡ ቴጽልም ፡ ከዊትንበርግ ፡ ወደ ፡ ማይርቅ ፡ አገር ፡ ሲደርስ ፡ ኢያሌ ፡ ሰዎች ፡ ከሉተር ፡ ከንስሓ ፡ ልጆቹ ፡ ከርሱ ፡ ፍትሐትን ፡ ገዙ ፡፡ ለመቍረብም ፡ ወደ ፡ ሉተር ፡ በመጡ ፡ ጊዜ ፡ ፍትሐትን ፡ ከቴጽል ፡ ገዛነ ፡ አሉት ፡፡ ሉተር ፡ ግን ፡ አላቍረባቸውም ፡፡ አሁንም ፡ የፍትሐትን ፡ ትምህርት ፡ በወንጌል ፡ እንደ ፡ ተገኘች ፡ አወጣት ፡ ስለርስዋም ፡ የተነሣችን ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ያሸነፈችን ፡ ስሕተት ፡ ገለጸ ፡ ገሠጻትም ፡ በስብከቱ ፡፡ በዚያ ፡ ጊዜም ፡ ባመት ፡ ፲፭፻፲፯፡ በዊተንበርግ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ደጅ ፡ ፺፭፡ ቃላት ፡ በወረቀት ፡ ጽፎ ፡ አጸና ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሊያያቸው ፡ ሊያነባቸውም ፡፡ እሌህ ፡ ቃላትም ፡ ስለ ፡ ፍትሐት ፡ ስለ ፡ ንስሓም ፡ ተናገሩ ፡፡ ከርሳቸውም ፡ ኢያሌ ፡ እሌህ ፡ ናቸው ፡፡

፩፡፡ ጌታችን ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ንስሓ ፡ ግቡ ፡ ሲል ፡፡ ፈቃደ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ የምእምናን ፡ ሕይወት ፡ ሁሉ ፡ በምድ

ር ፡ ሲኖሩ ፡ ወትሮ ፡ አንዲኑ ፡ የማይጨርስን ፡ ንስሐ ፡ እንዲያደርጉ ፡፡
፯፡፡ ጳጳስ ፡ ኃጢአትን ፡ መስረይ ፡ አይችልም ፡ በዚህ ፡ ልክ ፡ እንጂ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈጽሞ ፡ የሰረየውን ፡ ኃጢአት ፡ ስርየቱን ፡ እንዲገልጽ ፡ እንዲያጸናም ፡፡
፳፩፡፡ የንስሐን ፡ ፍትሐት ፡ የሚሰብኩ ፡ ይስታሉ ፡ እንዴህ ፡ በማለት ፡፡ ሰው ፡ በጳጳስ ፡ ፍትሐት ፡ ከሥቃይ ፡ ሁሉ ፡ እንዲፈታ ፡ እንዲድንም ፡፡
፳፭፡፡ ጳጳስ ፡ ያለቸውን ፡ ሥልጣን ፡ ለመፍታትና ፡ ለማሠር ፡ ይህቹ ፡ ሥልጣን ፡ ለኤጲስቆጶስ ፡ ሁሉ ፡ ለቄስም ፡ ሁሉ ፡ በየቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ በየስፍራውም ፡ በየሰዎቹም ፡ አለችው ፡፡
፳፯፡፡ ብር ፡ ወደ ፡ ሣፅን ፡ ሲገባ ፡ ነፍስ ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ትገባለች ፡ የሚሉ ፡ የሰውን ፡ ጨወታ ፡ ያስተምራሉ ፡፡
፴፪፡፡ በንስሐ ፡ ፍትሐት ፡ በጽፈቱ ፡ የዘላለም ፡ መድኃኒታቸው ፡ እንደ ፡ ተረደላቸው ፡ የሚመስላቸው ፡ ከመምህራኖቸው ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ ሰይጣን ፡ ይወርዳሉ ፡፡
፷፪፡፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እውነተኛ ፡ መዝገብ ፡ የኃጢአት ፡ ስርየት ፡ ክርሶ ፡ የሚገኝበት ፡ ቅዱስ ፡ ወንጌል ፡ ነው ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መስጋናና ፡ ጸጋ ፡ የሚገልጽ ፡፡
፺፬፡፡ መምህራንና ፡ ቀሳውስት ፡ ሁሉ ፡ ክርስቲያንን ፡ ይምከሩ ፡ ራሳቸውን ፡ ክርስቶስን ፡ በመከራ ፡ በሞትም ፡ በገሃነምም ፡ ይከተሉ ፡ ዘንድ ፡ እንዲቸኩሉ ፡፡
፺፭፡፡ በብዙ ፡ መከራም ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ እንዲገቡ ፡ በፍትሐትም ፡ መክንያት ፡ በኃጢአታቸው ፡ እንደይጸኑ ፡፡

እሌሀ ፡ ፺፭፡ ቃላትም ፡ ቶሎ ፡ ታትመው ፡ በኤውሮጳ ፡ ሁሉ ፡ ተዘረጉ ፡፡ እጅግ ፡ ሰዎችም ፡ መረመርዋቸው ፡፡ ጳጳስ ፡ ግን ፡ እጅግ ፡ አላሰበበትም ፡ እርሶ ፡ ይህ ፡ ክርክር ፡ በሌላ ፡ መክንያት ፡ በሉተርና ፡ በቴጽል ፡ መኻከል ፡ ብቻ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ይመስለው ፡ ነበረና ፡፡ የቴጽል ፡ ወደጆች ፡ ግን ፡ የጨለማም ፡ ወገን ፡ ሁሉ ፡ አሁን ፡ በሉተር ፡ ላይ ፡ ተነሡ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ሁሉ ፡ ሰበኩበት ፡፡ ሉተርም ፡ በሣይማ

ኖቱ ፡ አርፎ ፡ የርሳቸውን ፡ ቍጣ ፡ ጠበቀ ፡ እንዴህ ፡ ሲል ።
እኔ ፡ የማድርገው ፡ ስራ ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ፈቃድና ፡ ምክር ፡
አይሁን ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምክር ፡ እንጅ ። ማን ፡ ይ
ችላልና ፡ ይህነን ፡ ስራ ፡ ይከለክል ፡ ዘንድ ፡ ከእግዚአብሔ
ር ፡ ቢሆን ። ወይስ ፡ ማን ፡ ይችላል ፡ ያበጀው ፡ ዘንድ ፡ ከእ
ግዚአብሔር ፡ ባይሆን ። የኔም ፡ የላንትም ፡ የሁላችንም ፡
ፈቃድ ፡ አይሁን ፡ የተቀደሰ ፡ ፈቃድህ ፡ ይሁን ፡ እንጅ ፡ አባ
ታችን ፡ ሆይ ፡ በሰማይ ፡ ያለህ ።

የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ሉተር ፡ ወደ ፡ ሀይደልበርግ ፡ ተጸራ ፡ ከ
ዚያ ፡ ባንዲት ፡ ጉባኤ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ይፈተን ፡ ዘን
ድ ። አያሌ ፡ ጕበዞችም ፡ ተማሮች ፡ ከዚያ ፡ የሰሙት ፡
ትምህርቱን ፡ ተቀበሉ ፡ በኋላም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ በ
ማሳደስ ፡ ስራ ፡ ረዱት ። ከርሳቸውም ፡ ቡከርና ፡ ብረንፅ ።
አሁንም ፡ ይህ ፡ መጋደል ፡ ሲበዛ ፡ የሉተርም ፡ ጸላቶች ፡
ሳያርፉ ፡ ጳጳስ ፡ ሌዎን ፡ ሉተርን ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ አስጸራ
ው ፡ ከዚያ ፡ ይፈረድበት ፡ ዘንድ ። ነገር ፡ ግን ፡ ያገሩ ፡ ጌታ
ው ፡ ፍሪድሪኽ ፡ ጠቢብ ፡ ከጳጳስ ፡ ተንኰል ፡ ፈርቶ ፡ የጳጳ
ስን ፡ መለክተኛ ፡ ወደ ፡ ንምሳ ፡ አስመጣ ፡ እርሱም ፡ ካ
የታን ፡ የተባለ ። ሉተርንም ፡ ወደርሱ ፡ ላከ ፡ ወደ ፡ አው
ግስቡርግ ። ነገር ፡ ግን ፡ ካየታን ፡ ዕቡይና ፡ ደንቆሮ ፡ ሰው ፡ ሁ
ኖ ፡ ከሉተር ፡ ጋራ ፡ አልተማጐተም ። እንዲያው ፡ ሊክድ ፡
ፈለገው ፡ እንጅ ። እርሱ ፡ አውቀዋልና ፡ ከሉተር ፡ ጋራ ፡
ቢከራከር ፡ ሉተር ፡ ቢያሸንፈው ፡ ነበር ። አሁንም ፡ ሉተር
ን ፡ ሊይዝ ፡ ወደ ፡ ሮምም ፡ በግድ ፡ ሊወስደው ፡ ፈለገ ፡ ዷሮ ፡
ጳውሎስ ፡ በደማስቆ ፡ እንደ ፡ ደነ ፡ ደቀ ፡ መዛሙርት ፡ በከ
ፈር ፡ ካገር ፡ መካቡብያ ፡ አውርደው ፡ እንደ ፡ አደኑት ፡ እን
ዲህም ፡ ያውግስቡርግ ፡ ሹም ፡ የሉተር ፡ ወዳጅ ፡ አንዲት ፡
የከተማ ፡ ታናሽ ፡ ደጅ ፡ ከፍቶ ፡ ሰደደው ፡ በስውር ። ሉተ
ርም ፡ ሸሽቶ ፡ ወደ ፡ ዊተንበርግ ፡ ተመለሰ ። ካየታንም ፡ ይ
ህነን ፡ በሰማ ፡ ጊዜ ፡ ተቈጥቶ ፡ ወደ ፡ ፍሪድሪኽ ፡ ጠቢብ ፡
ጻፈ ፡ ሉተርን ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ እንዲሰድ ፡ ብሎ ። ያ ፡ ግን ፡ ጻ
ድቅ ፡ ሰው ፡ ነበረ ፡ የሉተርም ፡ ወዳጅ ። ስለዚህ ፡ የእግዚ
አብሔርን ፡ ሰው ፡ ለጸላቶቹ ፡ ፈቃድ ፡ አሳልፎ ፡ አልሰጠ

ም ፡፡ አሁንም ፡ ሌዎን ፡ ሉተርን ፡ ገና ፡ በቸርነት ፡ ወደ ፡ ሮ
ም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይመልስ ፡ ዘንድ ፡ ወደደ ፡ ጽፈትን ፡
ቢሰድ ፡ ሉተር ፡ ስለ ፡ ተማጉተው ፡ የፍትሐትን ፡ ነገር ፡ ያጸ
ናበት ፡፡ ደግሞም ፡ ብላቴንጌታው ፡ ስሙን ፡ ሚልቲጽ ፡ የ
ሚሉት ፡ ሉተርን ፡ ዕርቅ ፡ እንዲሻ ፡ አለው ፡፡ ሉተርም ፡ እ
ሺ ፡ አለ ፡ ጸላቶቹ ፡ ዝም ፡ ቢሉ ፡ እርሱ ፡ ደግሞ ፡ ዝም ፡ ብሎ ፡
ነበር ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ጸላቶቹ ፡ ዝም ፡ አላሉም ፡፡ አንድ ፡ መ
ምህርም ፡ ኤክ ፡ የሚሉት ፡ በለይጵጺግ ፡ ነበረ ፡ ዕቡይ ፡ ሰ
ው ፡፡ ያ ፡ በዊተንበርግ ፡ የተነሣችን ፡ አዲስም ፡ የተባለችን ፡
ትምርት ፡ በመጀመርያ ፡ መልካም ፡ ተቀበላት ፡ አሁን ፡ ግ
ን ፡ ይመጉትበት ፡ ዘንድ ፡ ፈለገ ፡፡ በመምህራንም ፡ መኻከ
ል ፡ በግልጽ ፡ መመጉት ፡ ስለ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነገር ፡ ልማድ ፡ ነ
በረ ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ልማድ ፡ ለወንጌል ፡ አገለገለ ፡፡ ኤ
ክም ፡ ካንድ ፡ በዊተንበርግ ፡ ካስተማረት ፡ መምህራን ፡ ካ
ርልስታድ ፡ ከሚሉት ፡ ጋራ ፡ መከራከር ፡ ፈለገ ፡ ስለዚህ
ም ፡ ሉተርና ፡ ካርልስታድ ፡ ሁለታቸው ፡ ባንድ ፡ ወደ ፡ ለይ
ጵጺግ ፡ ሔዱ ፡፡ ከዚያም ፡ ተመጓጉቱ ፡ ስለ ፡ አውጉስቲኑ
ስ ፡ ትምህርት ፡ ስለ ፡ ጸጋ ፡ ስለ ፡ ሰውም ፡ አርነት ፡፡ ኤክ ፡
ግን ፡ መመጉቱን ፡ እጅግ ፡ በሉተር ፡ ላይ ፡ አደረገ ፡፡ ሉተር
ም ፡ አሁን ፡ ከወንጌልና ፡ ከታሪክ ፡ የክርስቲያንን ፡ ትምህ
ርት ፡ አጸንቶ ፡ ኤክን ፡ አሸነፈ ፡፡ በዚህ ፡ ክርክርም ፡ መክ
ንያት ፡ ሉተር ፡ ደግሞ ፡ መጽሐፈ ፡ ቅዱስንና ፡ ታሪክን ፡ እ
ጅግ ፡ በመመርመር ፡ በውቀቱ ፡ ጸና ፡ አደገም ፡ የሮምንም ፡
ጨለማ ፡ አየ ፡ በቀደም ፡ ካየው ፡ ይልቅ ፡፡

ካሁንም ፡ ጀምሮ ፡ ፊልጶስ ፡ ሜላንኽቶን ፡ እጅግ ፡ የ
ተማረ ፡ ሰው ፡ የነበረ ፡ ከሉተር ፡ ጋራ ፡ በዊተንበርግ ፡ አስ
ተማረ ፡፡ ሁለታቸውም ፡ ወንድሞች ፡ ሆኑ ፡ እንደ ፡ ደዊት
ና ፡ እንደ ፡ ዮናታን ፡፡ ሜላንኽቶንም ፡ በሉተር ፡ ሃይማኖት ፡
በረታ ፡ ሉተርም ፡ ከሜላንኽቶን ፡ ዕውቀት ፡ ተማረ ፡፡ ከ
ለይጵጺግ ፡ መመጉት ፡ በኋላ ፡ ስለ ፡ ፍትሐት ፡ ስለ ፡ ሃይማ
ኖትም ፡ ስለ ፡ ሥርዓትም ፡ የሆነ ፡ ክርክር ፡ በዛ ፡፡

የዚያን ፡ ጊዜም ፡ ኤክ ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ ወደ ፡ ጳጳስ ፡ ሔደ ፡
በሉተር ፡ ላይ ፡ ሥልጣንን ፡ ከጳጳስ ፡ ይቀበል ፡ ዘንድ ፡፡ ጳጳ

ስንም ፡ በሉተር ፡ ላይ ፡ አስቍጥቶ ፡ ጉባኤ ፡ ተሰበሰበች ፡ በሉተር ፡ የፈረደ ፡ ፵፩ ቃላት ፡ ከመጻሕፍቱ ፡ ያወጡ ፡ ስሕተት ፡ ሁነው ፡ የቈጠረ ፡፡ ደሮ ፡ እልያ ፡ ቃላት ፡ ምንና ፡ ምን ፡ እንደሆኑ ፡ አላሉም ፡፡ ጳጳስም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ በሉተር ፡ ላይ ፡ ፈረደ ፡፡ ሉተር ፡ በ፲ ቀን ፡ መጻሕፍቱን ፡ ሁሉን ፡ ባይሰድ ፡ በሳት ፡ ይነደሉ ፡ ሰውነቱንም ፡ ለንጉሥ ፡ ፍርድ ፡ አሳልፈን ፡ እንሰጠዋልን ፡ ንጉሥ ፡ ስለ ፡ ኑፋቄው ፡ ይቀሥፈው ፡ ዘንድ ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ አያሌ ፡ መጻሕፍት ፡ ጨምሮ ፡ አወጣ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የነበረ ፡ ታላቅ ፡ ስሕተት ፡ ሁሉ ፡ የሚገለጽባቸው ፡፡ አንዲቱ ፡ መጽሐፍ ፡ ስምዋ ፡ ስለ ፡ ባቢሎን ፡ ምርኮ ፡ የተባለች ፡፡ በርሱም ፡ ገለጸ ፡ እሥራኤል ፡ አስቀድሞ ፡ በባቢሎን ፡ እንደ ፡ ተማረከ ፡ እንደዚህም ፡ አሁን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሮም ፡ በነቡከድነዛር ፡ እርሱም ፡ ጳጳስ ፡ ማለት ፡ የሚሆን ፡ ተማረከች ፡ ብሎ ፡፡

ኤክም ፡ ወደ ፡ ንምሳ ፡ ሲመለስ ፡ የጳጳስን ፡ ጽፈትና ፡ መግዛት ፡ በሉተር ፡ ላይ ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይዞ ፡ ባያሌ ፡ አገር ፡ የሉተርን ፡ መጻሕፍት ፡ አነደደ ፡፡ በብዙ ፡ አገር ፡ ግን ፡ በኤክ ፡ ተላገጹ ፡፡ ብዙ ፡ ሰዎችም ፡ ሉተርን ፡ የወደዱ ፡ ኤክን ፡ መግደል ፡ ፈለጉ ፡ እንደዚህም ፡ በለይጵጺግ ፡ በኤክ ፡ አገር ፡ ሆኑ ፡ ኤክ ፡ በግልጽ ፡ መዞር ፡ እንዳይቻለው ፡ ሰው ፡ እንዳይቀደው ፡፡

ሉተርም ፡ አሁን ፡ ለጳጳስ ፡ ከመገዛት ፡ ተለይቶ ፡ ጳጳስ ፡ አውጥቶታልና ፡ የጳጳስን ፡ ጽፈትና ፡ መግዛት ፡ ከጳጳሳት ፡ ቃኖኖች ፡ ጋራ ፡ ወሰደ ፡ በዊተንበርግም ፡ ጉብያ ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ከታላላቆቹ ፡ ከመምህራንና ፡ ከደቀ ፡ መዛሙርት ፡ ጋራ ፡ በተሰበሰቡ ፡ ጊዜ ፡ ታላቅ ፡ እሳትን ፡ አደረገ ፡ እለዚያንም ፡ መጸሕፍት ፡ ሁሉ ፡ ወደ ፡ እሳት ፡ ጣላቸው ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጉባኤ ፡ ስለ ፡ አሳዘንህ ፡ የዘላለም ፡ እሳት ፡ ይብላህ ፡፡

አሁንም ፡ የጳጳስ ፡ ቍጣ ፡ በዛ ፡፡ አዲስ ፡ ንጉሥን ፡ ካርል ፡ ፭ እጅግ ፡ ነዘነዘ ፡ መግዛቱን ፡ ይፈጽም ፡ ዘንድ ፡ በንምሳ ፡ መንግሥት ፡ ሁሉ ፡፡ ንጉሥም ፡ በወረሰው ፡ አገር ፡ የጳጳስን ፡ ነገር ፡ ፈጸመ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ጋዞቻቸው ፡ የሉተር ፡ ወዳጆች ፡ የነ

በረባቸው ፡ አገሮች ፡ በሰክስንና ፡ በሌላ ፡ አገር ፡ አልቻለው
ም ፡፡ አሁንም ፡ ካርል ፡ ፭ ፡ ባመት ፡ ፲፭፻፳፩ ፡ የመንግሥቱን ፡ ጉ
ባኤ ፡ ሰበሰበ ፡ ዎርምስ ፡ በሚልዋት ፡ አገር ፡ ሉተርም ፡ ወ
ዲያ ፡ ይመጣ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘው ፡ ከዚያ ፡ ይፈረድበት ፡ ዘን
ድ ፡፡ የሉተርም ፡ ወዳጆች ፡ እንዲይሔድ ፡ በመከሩት ፡ ጊ
ዜ ፡ እንደ ፡ ሁስ ፡ እንዲይሆንበት ፡ ብለው ፡ ሉተር ፡ መለ
ሰላቸው ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ በዎርምስም ፡ ሰይጣናት ፡ ቢመ
ሉ ፡ እንደ ፡ ጡብ ፡ በቤቶችዋ ፡ ሰገነት ፡ ላይ ፡ እኔ ፡ ደግሞ ፡
እሔዳለሁ ፡፡ ሉተርም ፡ ወደ ፡ ዎርምስ ፡ ሔደ ፡ ከዚያ
ም ፡ በጉባኤ ፡ ሁሉ ፡ የጉባኤ ፡ ጻፊ ፡ ጠየቀው ፡ ስለ ፡ አያ
ሌ ፡ ከዚያ ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ መጻሕፍት ፡ የርሱ ፡ መጻሕፍ
ት ፡ እንደ ፡ ሆኑ ፡ እርሱም ፡ እንደ ፡ ጻፋቸው ፡፡ ደግሞ
ም ፡ እንዲወድ ፡ ይክዳቸው ፡ ዘንድ ፡፡ ቢክድም ፡ ምን
ድር ፡ ነው ፡ ከተጻፈ ፡ ነገሩ ፡ የሚክድው ፡፡ ሉተርም ፡ መጻ
ሕፍቱን ፡ አስታወቀ ፡ ስለ ፡ መካድም ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡፡ ከ
እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ መስክረው ፡ እንደ ፡ ተሳትሁ ፡ በደገ
ልጹልኝ ፡ እኔ ፡ አልክድም ፡ ባውቀቴ ፡ ላይም ፡ አልበድ
ልም ፡፡ እነሆ ፡ ከዚህ ፡ ቆሚያለሁ ፡ ሌላ ፡ ማድረግም ፡ አ
ልችልም ፡ እግዚአብሔር ፡ ይርዳኝ ፡፡ አሜን ፡፡

ጸላቶቹም ፡ አሁን ፡ ይሸሩት ፡ ዘንድ ፡ እሹ ፡፡ ጳጳስም ፡
መግዘቱን ፡ አስቸኰለ ፡፡ መለክተኛውም ፡ ንጉሥን ፡ እሺ ፡
አሰኘው ፡ ሉተርን ፡ እንዲህ ፡ ይገዝተው ፡ ዘንድ ፡ካያሌ ፡ ቀ
ን ፡ ደህንነት ፡ በኋላ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሥልጣን ፡ እንደለው ፡ ሉ
ተርን ፡ አገኝቶ ፡ ይገድለው ፡ ዘንድ ፡፡ ሉተር ፡ እንኪያስ ፡ ከ
ዎርምስ ፡ ተነሥቶ ፡ ወደ ፡ ዊትንበርግ ፡ ሊመለስ ፡ ሔደ ፡፡ በ
መንገዱም ፡ ሲሆን ፡ አያሌ ፡ ፈረሰኞች ፡ ድንገት ፡ ወደቁበ
ት ፡ ከመንገድ ፡ አግድመው ፡ ሲመጡ ፡ ነጥቀው ፡ ከርሳቸው ፡
ጋራ ፡ ቶሎ ፡ ወሰዱት ፡ ዋርትቡርግም ፡ ወደ ፡ ተባለች ፡ አም
ባ ፡ ላይ ፡ የፍሪድሪኽ ፡ የጠቢብ ፡ ገንዘብ ፡ ወደ ፡ ነበረች ፡ አ
ኖሩት ፡፡ ይህ ፡ የፍሪድሪኽ ፡ ጠቢብ ፡ ማድረግ ፡ ነበረ ፡ ሉተርን ፡
ከጸላቶቹ ፡ እጅ ፡ ያስጠላው ፡ ዘንድ ፡ ብሎ ፡፡ በዋርትቡርግ
ም ፡ በሆነ ፡ ጊዜ ፡ ሉተር ፡ መሻቱን ፡ ሁሉን ፡ አገኘ ፡ ካርነት ፡ በ
ቀር ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ዝምብሎ ፡ አልተቀመጠም ፡፡ ከዚያ ፡ የእ

ግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ከዕብራይሥጥና ፡ ከዮናኒ ፡ ቋንቋ ፡ ወደ ፡ ንምሳዊ ፡ ቋንቋ ፡ አስተረጐመ ። እንደህም ፡ የእግዚ አብሔር ፡ ቃል ፡ በቀደም ፡ ጥቂት ፡ ይታወቅ ፡ የነበረ ፡ በንግ ደ ፡ ቋንቋ ፡ ተጽፎዋልና ፡ አሁን ፡ ወደ ፡ ንምሳ ፡ ሕዝብ ፡ ሁ ሉ ፡ እጅ ፡ ደረሰ ፡ የወደዱትም ፡ ከንምሳ ፡ ሕዝብ ፡ ተቻላቸ ው ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ትምህርት ፡ ይመረምሩ ፡ ዘንድ ፡ ለዘላለም ፡ መድኃኒታቸውም ፡ ይድኑ ፡ ዘንድ ። አሁንም ፡ ያ ፡ ብልሃት ፡ እግዚአብሔር ፡ ለሰው ፡ የሰጠው ፡ መጽሐፍ ን ፡ በማኅተም ፡ ያተሙ ፡ ዘንድ ፡ እጅግ ፡ ጠቀመ ። ባያሌ ፡ ቀን ፡ ብዙ ፡ ሽሕ ፡ መጻሕፍት ፡ ታትመው ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ሁ ሉ ፡ ሒደዋልና ። መጽሐፍ ፡ ቅዱስም ፡ ተተርጐሞ ፡ ታተመ ፡ በጥቂት ፡ ቀንም ፡ ወደ ፡ ንምሳ ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡ ደረሰ ፡ የብ ዙ ፡ ሰውም ፡ ልብ ፡ መለሰ ፡ ከጨለማ ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ ከ ሰይጣንም ፡ መግዛት ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ። ከዚህ ፡ በቀር ም ፡ ሉተር ፡ አያሌ ፡ ሌሎች ፡ መጻሕፍትን ፡ ጻፈ ፡ በዋርት ቡርግ ፡ ሲሆን ። ፩፤ አመት ፡ ተ፲፤ ወርም ፡ ከዚያ ፡ ከተቀመ ጠ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ዊተንበርግ ፡ ተመለሰ ።

የመመለሱም ፡ መክንያት ፡ ይህ ፡ ነበረ ። አያሌ ፡ ቀሳው ስት ፡ ከወደጆቹ ፡ የማምለክን ፡ ሥርዓት ፡ ለወጡ ፡ ጥበብ ፡ ሲያጡ ። እንደህም ፡ ወደ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ ገብተ ው ፡ ሥእልን ፡ ሁሉን ፡ አፈረሱ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ያመል ኩ ፡ ዘንድ ፡ በመንፈስና ፡ በውነት ፡ ብለው ። እንደህም ፡ በማድረጋቸው ፡ በሃይማኖት ፡ የደከሙትን ፡ ልብ ፡ አሳናከ ሉ ። ስለዚህ ፡ ሉተር ፡ ተመለሰ ፡ ሁከትን ፡ ያስቀመጥ ፡ ዘንድ ።

ሉተርም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከጳጳስ ፡ ጉባኤ ፡ ተለይቶ ፡ የቀደ መውን ፡ ከጳጳስ ፡ የተሰራውን ፡ ሥርዓት ፡ ለመጠበቅ ፡ አ ልታሠረም ። ስለዚህም ፡ እርሱ ፡ ከሌሎች ፡ መምህራን ፡ ከወንጌል ፡ ወገኖች ፡ ጋራ ፡ ሥርዓትን ፡ አደረገ ፡ ለቀሳውስት ና ፡ ለመነኵስት ፡ ከብሕትና ፡ እንደ ፡ ተፈቱ ፡ እንደ ፡ እግዚ አብሔር ፡ ሥርዓት ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ተደረገ ፡ ያንዲ ት ፡ ምሽት ፡ ባል ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ለሕዝብም ፡ ምሳሌች ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ በሁሉ ። ለሕዝብም ፡ ሥርዓትን ፡ አደረጉ ፡

በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለማምለካቸው ፡፡ ከሌላ ፡ ነገርም ፡ ይልቅ ፡ ያሽከሮችን ፡ ማስተማር ፡ ጠበቁ ፡፡ ሉተር ፡ ላሽከሮች ፡ ሁሉ ፡ ታናሽ ፡ መጽሐፍን ፡ ጻፈላቸው ፡ ከቴኪስሞስ ፡ የተባለ ፡፡ በርሱም ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ታላቅ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ተጻፈ ፡ ለቀሰውስትም ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ በልባቸው ፡ አኖረላቸው ፡ ዐሽከሮችንና ፡ የክርስቲያንን ፡ ሕዝብ ፡ ሁሉ ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ስብከትም ፡ በማስተማርም ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይወስድዋቸው ፡ ዘንድ ፡፡

የዚያን ፡ ጊዜም ፡ በሄልዌትያ ፡ ምድር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በወንጌል ፡ ታደሰች ፡፡ ከዚያም ፡ ፪ ፡ ሰዎች ፡ እግዚአብሔር ፡ መንፈሱን ፡ የሰጣቸው ፡ ከጳጳስ ፡ ስሕተት ፡ የተነሣ ፡ የተሰወረውን ፡ ወንጌል ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ አወጡት ፡፡ እርሳቸውም ፡ ጽዊንግሊና ፡ ኤኮላምጳድዩስ ፡ ነበሩ ፡፡ ጽዊንግሊም ፡ በጹሪኽ ፡ ኤኮላምጳዲዩስም ፡ በባሲል ፡ አስተማረ ፡፡ እርሳቸውም ፡ ከሉተርና ፡ ከሜላንኽቶን ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ነበረ ፡ በትምርታቸው ፡ በቍርባን ፡ ትምርት ፡ ግን ፡ ተለዩ ፡፡ ሉተር ፡ ሲል ፡፡ የጌታችን ፡ ገላና ፡ ደም ፡ በተቀደሰ ፡ እንጀራና ፡ ፀጅ ፡ በውነት ፡ ይሰጣልና ፡ ይቀበሉታል ፡ በምልክትም ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡፡ ጽዊንግሊ ፡ አለ ፡፡ ክርስቶስ ፡ የቍርባንን ፡ ሥርዓት ፡ ሲያደርግልን ፡ ማስታሰብያውን ፡ ሰራለት ፡ እኛ ፡ ሁለግዜ ፡ ፍቅረን ፡ እናስብ ፡ ዘንድ ፡ ገላው ፡ ስለኛ ፡ እንደ ፡ ተሰበረ ፡ ደሙም ፡ ስለኛ ፡ እንደ ፡ ፈሰሰ ፡፡ ክርስቶስም ፡ ሲል ፡፡ ይህ ፡ ሥጋዬ ፡ ነው ፡፡ ይህም ፡ ደሜ ፡ ነው ፡ ማለቱ ፡፡ የሥጋዬና ፡ የደሜ ፡ ምልክት ፡ ይህ ፡ ነው ፡፡

የዚያን ፡ ጊዜም ፡ አያሌ ፡ ከንምሳ ፡ ጋዞች ፡ የወንጌልን ፡ ብርሃን ፡ ተቀበሉ ፡ እርሳቸውም ፡ የሰክሰን ፡ ጋዝ ፡ መራጭ ፡፡ የብራንድንቡርግም ፡ መርክግራፍ ፡ ማለት ፡ የንምሳ ፡ ወሰን ፡ ጠባቂ ፡፡ የሀሰንም ፡ ለንድግራፍ ፡ ጋዝ ፡ ፊልጶስ ፡፡ ብዙም ፡ ከንምሳ ፡ ከተሞች ፡፡ እርሳቸውም ፡ አሁን ፡ አንድነት ፡ አደረጉ ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡ አንደች ፡ ክፉ ፡ ነገር ፡ ከጸላቶቻቸው ፡ ቢደርስባቸው ፡ ደህንነታቸውን ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡፡

ባመትም ፡ ፲፭፳፱፡ የመንግሥት ፡ ጉባኤ ፡ ደግሞ ፡ ተሰበሰበች ፡ ከዚያም ፡ የሮም ፡ ወገን ፡ በረቱ ፡ በወንጌል ፡ ወገን ፡ ላይ ፡፡ ትእዛዝንም ፡ አደረጉ ፡ የዎርምስን ፡ ትእዛዝ ፡ ደጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ የሉተርንም ፡ መጻሕፍት ፡ ሁሉ ፡ በሳት ፡ ያጥፉ ፡ ዘንድ ፡ የጳጳስም ፡ ሥርዓት ፡ ከቶ ፡ እንደይሻር ፡ ማንምም ፡ እንደይከለክል ፡ ደህነን ፡ ሥርዓት ፡ ከመጠበቅ ፡ ቁስም ፡ በስብከቱ ፡ እንደይከራከር ፡ በጳጳስ ፡ ነገር ፡፡

ደር ፡ ግን ፡ የወንጌልን ፡ ትምህርት ፡ ከሉተር ፡ የተቀበሉ ፡ ጋዦች ፡ በዚህ ፡ ላይ ፡ ተከራከረው ፡ ተጋደሉ ፡ ስለዚህም ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ጵሮተስታንቶች ፡ ማለት ፡ ተጋደዮች ፡ ደባላሉ ፡፡ ደህም ፡ ስም ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ ደገባል ፡ በምድር ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ደህና ፡ ማገልገል ፡ ከሚከለክለው ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ፡ ስትጋደል ፡፡

ባመትም ፡ ፲፭፴፡፡ ቄሣር ፡ ካርል ፡ ፭፡ ከመንግሥቱ ፡ ታላላቆች ፡ ከ፪፫፡፡ የሚበዙ ፡ ታላቅ ፡ ጉባኤን ፡ ሰበሰበ ፡ ጵሮተስታንቶን ፡ ያገዴ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለመመለስ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ በዚያች ፡ ጉባኤ ፡ በ፳፭፡ ሰኔ ፡ የጵሮተስታንቶች ፡ ጋዦች ፡ የከተሞቻቸውም ፡ መለክተኞች ፡ መምህራናቸውም ፡ ለቄሣር ፡ ካርል ፡ በመንግሥቱ ፡ ፊት ፡ ትምህርታቸውን ፡ አስታወቁት ፡ ሜላንኽቶንና ፡ ሉተር ፡ እንደ ፡ ጻፉት ፡ እንደህ ፡ ሲሉ ፡፡

የጵሮተስታንቶች ፡ ትምህርት ፡
በአውግስቡርግ ፡ በተሰበሰበች ፡ ጉባኤ ፡
በንምሳ ፡ ቄሣር ፡ በካርል ፡ ፭፡ በመንግሥቱም ፡ ፊት ፡
ያስታወቁት ፡፡

ባመት ፡ ፲፭፴፡፡ በ፳፭፡ ሰኔ ፡፡

፩፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡፡

በመጀመርያ ፡ አብረን ፡ እናስተምራለን ፡ እንደ ፡ ኒቅያ ፡ ሲኖደስ ፡ አንድ ፡ አምላካዊ ፡ ባሕሪ ፡ እንደለው ፡ አምላክ ፡ የተባለ ፡ በውነትም ፡ አምላክ ፡ የሚሆን ፡፡ በዚህ

ም ፡ ባንድ ፡ አምላካዊ ፡ ባሕሪ ፡ ሶስት ፡ አካላት ፡ እንደ ሉ ፡ ያንድ ፡ ኃይል ፡ ያንድ ፡ ዘላለምናም ። እርሳቸውም ፡ እግዚአብሔር ፡ አብ ፡ እግዚአብሔር ፡ ወልድም ፡ እ ግዚአብሔር ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ። ሶስታቸውም ፡ ሁ ሉ ፡ አንድ ፡ አምላካዊ ፡ ባሕሪ ፡ የዘላለም ። ያለ ፡ ክፍል ም ። ያለ ፡ መጨረሻም ። ኃይሉም ፡ ጥበቡም ፡ በጐነቱ ም ፡ ያልተወሰነ ። አንድ ፡ ፈጣሪ ፡ አንድ ፡ ጠባቂም ፡ ለሚ ታይ ፡ ለማይታይም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ።

አካልም ፡ ስንል ፡ ማለታችን ፡ የሌላ ፡ ክፍል ፡ ወይስ ፡ በሌላ ፡ ያለ ፡ መጨመርያ ፡ አይደለም ። መሆኑ ፡ ለራሱ ፡ ያለው ፡ እንጂ ፡ አባቶችም ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ ይህነን ፡ ቃል ፡ እንደደረጉ ።

ስለዚህም ፡ እንጥላለን ፡ ይህችን ፡ ትምህርት ፡ የሚ ጸልዋትን ፡ መናፍቃን ፡ ሁሉን ። እርሳቸውም ፡ ማኒኬ ዮች ፡ በ፪፡ አማልክት ፡ ያስተማሩ ፡ አንድም ፡ በጎ ፡ አን ድም ፡ ክፉ ። ደግሞም ፡ የበለንቲኒያኖስን ፡ ያርዮስ ንም ፡ የኤውኖሚዮስንም ፡ የሙሀመድንም ፡ ወገ ን ፡ እርሳቸውንም ፡ የሚመስሉትን ፡ ሁሉን ። ደግሞም ፡ የሳሞሰታን ፡ የቀደመውን ፡ ያዲስንም ፡ ወገኑን ። ባን ድ ፡ አካል ፡ የሚያስተምሩን ፡ በልያም ፡ ፪፡ በቃልና ፡ በመ ንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የሚጠራጠሩን ፡ እንደዚህ ፡ ሲሉ ። ልዩ ፡ አካ ላት ፡ አይደሉም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ቃል ፡ የተሰማው ፡ ቃልና ፡ ድ ምጽ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ ብለው ። መንፈስ ፡ ቅዱስንም ፡ የተ ፈጠረውን ፡ ኃይል ፡ በፍጥረት ፡ ይሉታል ።

፪። ስለ ፡ ሚወረስ ፡ ኃጢአት ።

ደግሞም ፡ በኛ ፡ ዘንድ ፡ ያስተምራሉ ፡ እንደዚህ ፡ ሲሉ ። ካደም ፡ መውደቅ ፡ ወዲህ ፡ ሥጋ ፡ ሁኖ ፡ የተወለደ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በኃጢአት ፡ ይረገዛል ፡ ይወለደልም ። የዚህም ፡ ማለት ፡ ይህ ፡ ነው ። ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከናቱ ፡ ሆ ድ ፡ ጀምሮ ፡ የክፉ ፡ ፈቃድና ፡ መሻት ፡ ይመላበታል ፡ የእ

ግዚአብሔር ፡ እውነተኛ ፡ ፍርሃት ፡ በእግዚአብሔርም ፡ እ ውነተኛ ፡ ሃይማኖት ፡ ከፍጥረቱ ፡ ይሆንለት ፡ ዘንድ ፡ እን ደይቻል ፡፡ ይህም ፡ ሕማም ፡ ሰው ፡ የሚወለድበት ፡ የሚ ወርሰውም ፡ ኀጢአት ፡ አይነተኛ ፡ ኀጢአት ፡ ነው ፡፡ ሰውን ም ፡ ሁሉን ፡ ለዘላለም ፡ በሚኖር ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቍ ጣ ፡ ያስኰንናል ፡ በጥምቀትና ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ሁለተ ኛ ፡ ባይወለድ ፡፡

ስለዚህም ፡ የጴላግዮስ ፡ ወገንንና ፡ ሌሎችን ፡ እንጥ ላለን ፡ የሚወረስውን ፡ ኀጢአት ፡ ኀጢአት ፡ ሁኖ ፡ የ ማይቈጥሩትን ፡ ሥጋውን ፡ በሥጋዊ ፡ ኀይል ፡ ይቀድሱ ፡ ዘ ንድ ፡፡ እንደዚህ ፡ አስተምረው ፡ የክርስቶስን ፡ ሕማምና ፡ ምግባሩን ፡ ያስነውራሉና ፡፡

፫፤ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ ጌታችን ፡፡

እንደሁም ፡ እንላለን ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ ሰው ፡ ሆነ ፡ ከንጽሕት ፡ ድንግል ፡ ከማርያም ፡ ተወልደ ፡፡ ሁለቱ ም ፡ ጠባያቱ ፡ ያምላክና ፡ የሰው ፡ ጠባይዕ ፡ ባንድ ፡ አካ ል ፡ ያልተለዩ ፡ እንደሁ ፡ ተዋሀዱ ፡ አንድ ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡፡ እውነተኛ ፡ አምላክና ፡ እውነተኛ ፡ ሰው ፡ የ ሆነ ፡፡ በውነትም ፡ የተወለደ ፡ ታመመም ፡ ተሰቀለም ፡ ሞ ተም ፡ ተቀበረም ፡ ስለ ፡ ሚወረስ ፡ ኀጢአት ፡ ብቻ ፡ አይደለ ም ፡ ስለ ፡ ሌላ ፡ ኀጢአትም ፡ ሁሉ ፡ እንጂ ፡፡ የእግዚአብ ሔርንም ፡ ቍጣ ፡ ያስታርቅ ፡ ዘንድ ፡፡

ደግሞም ፡ ክርስቶስ ፡ ወረደ ፡ ወደ ፡ ገሃነም ፡ በሦስተኛ ፡ ቀንም ፡ በውነት ፡ ከሙታን ፡ ተነሣ ፡ ወደ ፡ ሰማይም ፡ ወ ጣ ፡፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቀኝም ፡ ይቀመጣል ፡ በፍጥረ ት ፡ ሁሉም ፡ ላይ ፡ ለዘላለም ፡ ይገዛል ፡፡ የሚያምኑበትን ም ፡ ሁሉ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ይቀድሳቸዋል ፡ ያነጻቸው ማል ፡ ሕይወትንም ፡ ልዩን ፡ ልዩንም ፡ ስጥወታን ፡ በጎ ፡ ነ ገርንም ፡ ይከፍልላቸዋል ፡ ከሰይጣንና ፡ ከኀጢአትም ፡ ይ ወብቃቸዋል ፡፡

ደግሞም ፡ እርሱ ፡ ክርስቶስ ፡ ጌታችን ፡ በመጨረሻ ፡ በግ

ልጽ፡ ይመለሳል፡ በሕያዋንና፡ በሙታን፡ ይፈርድ፡ ዘንድ፡ በሐዋርያት፡ ስምቦሉን፡ እንደ፡ ተባለ፡፡

፬፡ ስለ፡ መጸደቅ፡፡

ደግሞም፡ በኛ፡ ዘንድ፡ እንዲህ፡ ብለው፡ ያስተምራሉ፡ የኀጢአታችን፡ ስርየትና፡ መጸደቃችን፡ በእግዚአብሔር፡ ፊት፡ እንደ ይሆንልን፡ በምግባራችን፡ ወይስ፡ በስራችን፡ ወይስ፡ በመክፈላችን፡፡ ነገር፡ ግን፡ የኀጢአትን፡ ስርየት፡ እንቀበላለን፡ በእግዚአብሔርም፡ ፊት፡ እንጸደቃለን፡ ከእግዚአብሔር፡ ጸጋ፡ የተነሣ፡ ስለ፡ ክርስቶስም፡ በሃይማኖትም፡ ክርስቶስ፡ ስለኛ፡ መከራ፡ እንደ፡ ተቀበለ፡ በርሱም፡ መክንያት፡ ኀጢአት፡ እንዲሰረይልን፡ ጽድቅንም፡ የዘላለምንም፡ ሕይወት፡ እንድንቀበል፡ ብናምን፡፡ ይህችን፡ ሃይማኖት፡ እግዚአብሔር፡ ጽድቅ፡ ሁና፡ ይላታል፡ ይቈጥራትማል፡ ቅዱስ፡ ጳውሎስ፡ እንዲል፡ በሮሜ፡ መልእክት፡ ምዕራፍ፡ ፫፡፡ ፬፡፡

፭፡ ስለ፡ ስብከት፡ ሹመት፡፡

እንዲህ፡ ያላትንም፡ ሃይማኖት፡ እናገኝ፡ ዘንድ፡ ብሎ፡ እግዚአብሔር፡ የመስበክን፡ ሹመት፡ ሰጠ፡ ወንጌልንና፡ ምሥጢራትንም፡ ሰጠ፡ በዚህ፡ ሁሉ፡ መንፈስ፡ ቅዱስን፡ እንቀበል፡ ዘንድ፡፡ መንፈስ፡ ቅዱስም፡ በሚወደው፡ ስፍራ፡ በሚወደውም፡ ጊዜ፡ በሚሰሙት፡ ሰዎች፡ ሃይማኖትን፡ ይሰራል፡ ወንጌል፡ ሲያስተምራቸው፡ የታረቀ፡ እግዚአብሔር፡ እንደለን፡ በምግባራችን፡ አይደለም፡ በክርስቶስ፡ ምግባር፡ እንጅ፡ እኛ፡ ብናምን፡ ብቻ፡፡

የመናፈቃንም፡ ከወንጌል፡ ከሚሰማ፡ ቃል፡ በቀር፡ መንፈስ፡ ቅዱስን፡ እንድናገኝ፡ በራሳችን፡ ማስናደት፡ በማ

ሰባችንና ፡ በስራችንም ፡ ብለው ፡ የሚያስተምሯባት ፡ ት ምህርታቸው ፡ ትወገዛለች ፡፡

፯፡ ስለ ፡ በጎ ፡ ስራ ፡፡

ደግሞም ፡ እንላለን ፡ እንዲህ ፡ ላለች ፡ ሃይማኖት ፡ በ ጎ ፡ ፍሬንና ፡ በጎ ፡ ስራን ፡ ማፍራት ፡ እንደ ፡ ገባት ፡ እግ ዚአብሔር ፡ ያዘዘውንም ፡ በጎ ፡ ስራ ፡ ሁሉ ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ እናደርገው ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ገባን ፡ እ ንዲህም ፡ ባለ ፡ ስራ ፡ እንታመን ፡ ዘንድ ፡ አይደለም ፡ ወይስ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጸጋ ፡ በርሱ ፡ እንገብር ፡ ዘ ንድ ፡፡ የኃጢአትን ፡ ስርየትና ፡ ጽድቅ ፡ በክርስቶስ ፡ ባለ ች ፡ ሃይማኖት ፡ ብቻ ፡ ተቀብለናልና ፡፡ ክርስቶስም ፡ ባለቤ ቱ ፡ ይለናል ፡ ሉቃስ ፡ ፲፯፡ ፲፡፡ ይህንን ፡ ሁሉን ፡ ባደረጋችሁ ፡ ጊዜ ፡ በሉ ፡፡ እኛ ፡ የማንጠቅም ፡ ባሮች ፡ ነነ ፡፡ እንዲህም ፡ አባቶች ፡ አስተማሩ ፡፡ አምብሮስዩስ ፡ ብልዋልና ፡፡ በእግዚ አብሔር ፡ ዘንድ ፡ እንዲህ ፡ ተወሰነ ፡ በክርስቶስ ፡ የሚያም ን ፡ እንዲድን ፡ ኃጢአቱም ፡ እንዲሰረይለት ፡ በስራ ፡ አይ ደለም ፡ በሃይማኖት ፡ ብቻ ፡ እንጅ ፡ ያለ ፡ ምግባር ፡፡

፯፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡፡

ደግሞም ፡ ያስተምራሉ ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡ ሁልጊዜ ፡ አ ንዲት ፡ ቅድስት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አለች ፡ ትኖርማለ ች ፡ እርስዋም ፡ የምእምናን ፡ ሁሉ ፡ ጉባኤ ፡ በርሳቸ ው ፡ ዘንድ ፡ ጽሩ ፡ ወንጌል ፡ የሚሰበክባቸው ፡ የተቀ ደሱም ፡ ምሥጢራት ፡ እንደ ፡ ወንጌል ፡ ትእዛዝ ፡ የ ሚገለገሉባቸው ፡፡

ይህ ፡ ነገር ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ላይነተኛ ፡ አንድነትዋ ፡ ይበቃልና ፡ በርስዋ ፡ ወንጌልን ፡ እንደ ፡ ጽሩ ፡ ማለቱ ፡ ባን ድ ፡ ልብ ፡ እንደ ፡ ሰበኩት ፡ ምሥጢራትንም ፡ እግዚአብሔ ር ፡ በቃሉ ፡ እንደዘዘው ፡ እንዲያገለግልዋቸው ፡፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አንድነትም ፡ በስፍራ ፡ ሁሉ ፡ አንዲት ፡ ከ

ቶም ፡ የማትለይ ፡ ከሰውም ፡ የተሰራች ፡ ሥርዓት ፡ እንድትገኝ ፡ አይሻም ፡፡ እንደህም ፡ ጳውሎስ ፡ ደላል ፡ ኤፌሳን ፡ ፬፤ ፬፡፡ አንድ ፡ ገላ ፡ አንድ ፡ መንፈስም ፡ እንደ ፡ ተጸራችሁ ፡ ለመጸራታችሁ ፡ በሚገባው ፡ ባንድ ፡ ተስፈ ፡፡ አንድ ፡ ጌታ ፡ አንዲት ፡ ሃይማኖትም ፡ አንዲት ፡ ጥምቀትም ፡፡

፰፡፡ ስለ ፡ ግብዞች ፡፡ በስምም ፡ ብቻ ፡ ክርስቲያን፡ ስላሉ ፡፡

ደግሞም ፡ እንደህ ፡ እንላለን ፡፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በውነት ፡ ሌላ ፡ ሳትሆን ፡ የምእምናንና ፡ የቅዱሳን ፡ ሁሉ ፡ ጉባኤ ፡ እንጅ ፡ ደህም ፡ ሳደቀር ፡ በዚች ፡ ሕደወት ፡ ብዙ ፡ ሐሰውት ፡ ክርስቲያናትና ፡ ግብዞች ፡ ተገኝተዋልና ፡ ደግሞ ፡ የተገለጹ ፡ ኃጥአን ፡ በቅዱሳን ፡ መኻከል ፡ ሲኖሩ ፡ ምሥጢራት ፡ ግን ፡ ኃደለኞች ፡ ደኖራሉ ፡ የሚያገለግልዋቸው ፡ ቀሳውስት ፡ እንኳ ፡ ቅዱሳን ፡ ባደደሉ ፤ ክርስቶስ ፡ ባለቤቱ ፡ እንደለ ፡ ስለ ፡ ፈሪሳውያን ፡ ማቴዎስ ፡ ፳፫፤ ፪፡፡ ስለዚህም ፡ የደናቱስ ፡ የሌሎችም ፡ ትምህርት ፡ ሁሉ ፡ እንደህ ፡ ያልሆነች ፡ ትጣላለች ፡፡

፱፡፡ ስለ ፡ ጥምቀት ፡፡

ስለ ፡ ጥምቀትም ፡ ያስተምራሉ ፡ እንደ ህ ፡ ብለው ፡፡ ጥምቀት ፡ ትገባለች ፡ ጸጋም ፡ በርስዋ ፡ ለመቀበል ፡ ደገለጻል ፡ ሕፃናትንም ፡ ማጥመቅ ፡ ደገባል ፡ እርሳቸውንም ፡ በጥምቀት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ አሳልፈን ፡ እንሰጣቸዋለን ፡ ደስም ፡ እናሰኘውበታለን ፡፡ ስለዚህም ፡ የሕፃናት ፡ ጥምቀት ፡ አደገባም ፡ የሚሉ ፡ ሰዎች ፡ መናፈቃን ፡ ሁነው ፡ ደቈጠራሉ ፡፡

፲፡ ስለ ፡ ቍርባን ፡፡

ስለ ፡ ጌታችን ፡ እራት ፡ እንደህ ፡ ብለው ፡ ያስተምራሉ ፡

የክርስቶስ ፡ እውነተኛ ፡ ገላና ፡ ደም ፡ በኅብስትና ፡ በወይን ፡ ፃጅ ፡ መልክ ፡ በቍርባን ፡ በውነት ፡ አለ ፡ በዚያም ፡ ይቈረባል ፡ እኛም ፡ እንቀበለውበታለን ፡፡ ከዚህም ፡ ጋራ ፡ የምትጸላ ፡ ትምህርት ፡ እንጥላለን ፡፡

፲፩፡፡ ስለ ፡ መናዘዝ ፡፡

ስለ ፡ መናዘዝም ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ያስተምራሉ ፡ በቤት ፡ ክርስቲያን ፡ ያለ ፡ ለብቻው ፡ መናዘዝና ፡ መፈታት ፡ እንጠብቀው ፡ ዘንድ ፡ እንደተወውም ፡ እንዲገባ ፡ እንጅ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ በመናዘዝ ፡ መበደልንና ፡ ኀጢአትን ፡ ሁሉን ፡ መንገርና ፡ መቍጠር ፡ አይፈለግም ፡ ማንም ፡ አይችለውምና ፡፡ መዝሙር ፡ ፲፱፡ ፲፫፡፡ ማን ፡ ይችላል ፡ መበደሉን ፡ ሁሉን ፡ ያውቅ ፡ ዘንድ ፡፡

፲፪፡፡ ስለ ፡ ንስሓ ፡፡

ስለ ፡ ንስሓም ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡ ያስተምራሉ ፡፡ ከጥምቀታቸው ፡ በኋላ ፡ ኀጢአት ፡ ያደረጉ ፡ ሁሉ ፡ ሁሉግዜ ፡ ንስሓ ፡ ቢገቡ ፡ የኃጢአትን ፡ ስርየት ፡ ያገኛሉ ፡ ፈትሐትም ፡ አይከለከልባቸውም ፡ ከቤት ፡ ክርስቲያን ፡፡ እውነተኛ ፡ ንስሓም ፡ ሌላ ፡ የለም ፡ በውነት ፡ በኃጢአቱ ፡ ማዘንና ፡ መፈራት ፡ እንጅ ፡ ከዚህም ፡ ጋራ ፡ በወንጌል ፡ ፈትሐት ፡ መታመን ፡ ኃጢአት ፡ እንደ ፡ ተሰረየች ፡ ጸጋም ፡ በክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ተሰጠች ፡፡ ይች ፡ ሃይማኖት ፡ ልብን ፡ ታጸናለችና ፡ ታጸግባለች ፡ በኋላም ፡ መሻል ፡ ይከተል ፡ ኃጢአትንም ፡ መተወት ፡፡ ይህ ፡ የንስሓ ፡ ፍሬ ፡ ነውና ፡ ዮሐንስ ፡ እንዲል ፡ ማቴዎስ ፡ ፫፡ ፰፡፡ የንስሓውን ፡ እውነተኛ ፡ ፍሬ ፡ ሰሩ ፡፡

የልያንም ፡ ትምህርት ፡ እንጥላለን ፡ እንዲህ ፡ የሚሉ ፡፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ቅዱሳን ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ ተመልሰው ፡ መውደቅ ፡ እንዳይችሉ ፡፡ ደግሞም ፡ የኖዋትያኖችን ፡ ትምህርት ፡ እንጥላለን ፡ ከተጠመቁ ፡ በኋላ ፡ ኃጢአት ፡ ያደረጉ ፡ ከፍት

ሐት ፡ የሚከለክሉባት ፡፡ እልያንም ፡ አንሰማም ፡ የሚያ ስተምሩ ፡ በሃይማኖት ፡ የኃጢአትን ፡ ስርየት ፡ እንደናገኝ ፡ በምግባራችን ፡ እንጅ ፡፡

፲፫፡ ምሥጢራትን ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ፡፡

ምሥጢራትን ፡ ስለ ፡ መጠበቅ ፡ ያስተምራሉ ፡ እንደሆ ፡ ሲሉ ፡፡ ምሥጢራት ፡ ክርስቲያን ፡ በግልጽ ፡ የሚታወቁ ባቸው ፡ ምልክቶች ፡ ብቻ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ አልተሰሩም ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ስለኛ ፡ ያሉት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ፈቃድ ፡ ምል ክቶችና ፡ ምስክሮች ፡ ይሆኑልን ፡ ዘንድ ፡ ሃይማኖታችነን ም ፡ ያስነሡ ፡ ዘንድ ፡ ያጸንዋትም ፡ ዘንድ ፡፡ ስለዚህም ፡ ሃይማኖትን ፡ ይፈልጋሉ ፡ ሰውም ፡ በሃይማኖት ፡ ሲቀበላ ቸው ፡ እንጅ ፡ ሃይማኖቱንም ፡ ሲያጸናባቸው ፡ እንዲገባ ቸው ፡ አይደረጉም ፡፡

፲፬፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስለ ፡ መግዛት ፡፡

በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስለ ፡ መግዛት ፡ እንደሆ ፡ ሲሉ ፡ ያስተ ምራሉ ፡፡ ለማንም ፡ አይገባም ፡ በግልጽ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲ ያን ፡ እንዲያስተምር ፡ እንዲሰብክም ፡ ምሥጢራትንም ፡ እንዲያገለግል ፡ በሥርዓት ፡ ካልተጸራ ፡፡

፲፭፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዓት ፡፡

የኛ ፡ መምህራን ፡ እንደሆ ፡ ሲሉ ፡ ያስተምራሉ ፡ ከሰው ፡ ከተሰራች ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዓት ፡ ያለ ፡ ኃጢአት ፡ መጠበቅ ፡ የሚችሉትን ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ ለ ዕርቅም ፡ ለበጎ ፡ ሥርዓትም ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚጠቅ ም ፡ እንደ ፡ አያሌ ፡ በዓላት ፡ ይህነንም ፡ የሚመስለውን ፡ ነ ገር ፡፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ግን ፡ የስተምራሉ ፡ የሰውን ፡ ልብ ፡ ከ ቶ ፡ እንዳያከብዱበት ፡ እንደሆ ፡ ያለ ፡ ነገር ፡ ለነፍስ ፡ መ ድኃኒት ፡ እንዲፈለግ ፡ ብለው ፡፡

ደግሞም ፡ ይላሉ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ለማስታረቅ ፡ ጸጋ ውንም ፡ ለመግበር ፡ ከሰው ፡ የተሰራ ፡ ልማድና ፡ ትእዛዝ ፡ ሁሉ ፡ ከወንጌል ፡ ጋራ ፡ እግዚአብሔር ፡ በክርስቶስ ፡ ስላለ ች ፡ ሃይማኖት ፡ ከገለጸውም ፡ ነገሩ ፡ ጋራ ፡ እንዲጸላ ፡፡ ስ ለዚህም ፡ የምንኰስና ፡ ስለት ፡ ሌላውም ፡ ካባቶች ፡ ወደ ኛ ፡ የመጣ ፡ ትእዛዝ ፡ ስለ ፡ መብልና ፡ ስለ ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ ጊ ዜም ፡ ልዩነት ፡ ሰው ፡ በርሱ ፡ ጸጋ ፡ ገብሮ ፡ የኃጢአትንም ፡ ዋጋ ፡ በርሱ ፡ ከፍሎ ፡ የሚመስል ፡ አይጠቅምም ፡ ከወን ጌልም ፡ ጋራ ፡ ይጻላል ፡፡

፲፮፡፡ ስለ ፡ ዓለም ፡ ሹመትና ፡ መግዛት ፡፡

ስለ ፡ ዓለም ፡ ሹመትና ፡ መግዛት ፡ እንዲህ ፡ ብለው ፡ ያስ ተምራሉ ፡ ባለም ፡ ያሉ ፡ ሥልጣናት ፡ ሁሉ ፡ በሥርዓትም ፡ የተሰሩ ፡ ሹመቶችና ፡ ሕጋጋት ፡ ሁሉ ፡ በጎ ፡ ሥርዓቶች ፡ እ ንዲሆኑ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተፈጠሩ ፡ የተሰሩም ፡፡ በክር ስቲያንም ፡ ኃጢአት ፡ እንደይቈጠር ፡ እርሱ ፡ ሹምና ፡ መ ኰንን ፡ ወይስ ፡ ፈራጅ ፡ ቢሆን ፡ እንደ ፡ ንጉሥ ፡ እንደ ፡ ሌላ ፡ ሹመትም ፡ ቢፈርድ ፡ ቢያጸድቅም ፡ ሕግ ፡ አፍራሾችንም ፡ በሰይፍ ፡ ቢቀሥፍ ፡ በቅንም ፡ ጾርን ፡ ቢያደርግ ፡ ቢሸምት ም ፡ ቢለውጥም ፡ ቢከራከርም ፡ በመኰንን ፡ ፍርድም ፡ ቢ ምል ፡ ገንዘብም ፡ ቢሆንለት ፡ ምሽቱንም ፡ ቢያገባ ፡ እን ዲህም ፡ ያለውን ፡ ነገር ፡ ቢያደርግ ፡፡

ስለዚህም ፡ የመናፈቃንን ፡ ትምህርት ፡ እንጥላለን ፡ ይ ህ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እንዲያው ፡ ኃጢአት ፡ ነው ፡ የሚሉ ፡፡ የለ ዚያም ፡ ኑፋቄ ፡ ትወገዛለች ፡ የክርስቲያንን ፡ ፍጻሜ ፡ የ ሚቈጥረት ፡ ሰው ፡ በሥጋው ፡ ቤቱንና ፡ ምድሩን ፡ ምሽቱ ንም ፡ ልጆቹንም ፡ በፈቃዱ ፡ ቢተው ፡ ያንንም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ን ፡ ባያደርግ ፡፡ አይነተኛዪቱ ፡ ፍጻሜ ፡ ግን ፡ ይህች ፡ ናት ፡፡ የእግዚአብሔር ፡ እውነተኛ ፡ ፍርሃት ፡ እውነተኛ ም ፡ ሃይማኖት ፡ በእግዚአብሔር ፡፡ ወንጌል ፡ የሚያ ፡ የጊዜም ፡ ባሕሪና ፡ ጽድቅ ፡ አያስተምርምና ፡ የውሥጥ ፡ እንጀ ፡ የዘላለምም ፡ የልብም ፡ ባሕሪና ፡ ጽድቅ ፡፡ ያለም

ንም ፡ መግዛትና ፡ መሾም ፡ ወይስ ፡ መጋባትን ፡ አይሸር ም ፡ ያዘናል ፡ እንጂ ፡፡ ይህነን ፡ ነገር ፡ ሁሉን ፡ እንደ ፡ እግዚ አብሔር ፡ እንደ ፡ አይነተኛ ፡ ሥርዓቱ ፡ እንድንጠብቀው ፡ በዚያም ፡ መቆም ፡ ሁሉ ፡ የክርስቲያንን ፡ ፍቅር ፡ በውነት ም ፡ በጎ ፡ ያለውን ፡ ስራ ፡ ሁሉ ፡ ሊየመጸራቱ ፡ ይገልጸው ፡ ዘንድ ፡፡ ስለዚህም ፡ ለክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ ይገባል ፡ ለመ ኰንኑ ፡ እንዲገዛ ፡ ለትእዛዛቱም ፡ ለሕጋጋቱም ፡ ያለ ፡ ኃጢ አት ፡ ይደረግ ፡ ዘንድ ፡ በሚቾል ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እንዲታዘ ዝ ፡፡ ያለ ፡ ኃጢአት ፡ ግን ፡ የመኰንን ፡ ትእዛዝ ፡ መፈጸ ም ፡ ባይቻል ፡ ለእግዚአብሔር ፡ እንድንታዘዝ ፡ ይገባናል ፡ ለሰው ፡ ከመታዘዝ ፡ ይልቅ ፡፡ የሐዋርያት ፡ ስራ ፡ ፭፡ ፳፱።

፲፯። ስለ ፡ ኋለኛ ፡ ቀን ፡ ስለ ፡ ዓለምም ፡ ፍጻሜ ፡፡

ደግሞም ፡ ያስተምራሉ ፡ ጌታችን ፡ የሡስ ፡ ክርስቶስ ፡ በ ኋለኛ ፡ ቀን ፡ እንዲመጣ ፡ ይፈርድ ፡ ዘንድ ፡ ሙታንንም ፡ ሁሉን ፡ ያስነሣል ፡፡ ምእምናንንና ፡ ምሩጻንንም ፡ የዘላ ለምን ፡ ሕይወትና ፡ ደስታ ፡ ይሰጣቸዋል ፡፡ ክፉ ፡ ሰዎችን ፡ ግን ፡ ሰይጣናትንም ፡ ወደ ፡ ገሃናምና ፡ ወደ ፡ ዘላለም ፡ ኵ ነኔ ፡ ይኰናቸዋል ፡፡ ስለዚህም ፡ የመናፈቃንን ፡ ትምርት ፡ ይጥላሉ ፡ የሚሉ ፡ የሰይጣናትና ፡ የርጉማን ፡ ሰዎች ፡ ሥ ቃይና ፡ መቅሠፍት ፡ ለዘላለም ፡ እንደይሆንላቸው ፡፡ ደግ ሞም ፡ የልያን ፡ ትምርት ፡ እንደ ፡ አይሁድ ፡ ከሙታን ፡ ት ንሣኤ ፡ ወዲህ ፡ ቅዱሳንና ፡ ጻድቃን ፡ አንዲት ፡ ዓለማዊት ፡ መንግሥት ፡ እንድትሆንላቸው ፡ በምድር ፡ ክፎችንም ፡ ሁ ሉን ፡ እንዲያጠፉ ፡ ብለው ፡ የሚያስተምሩትን ፡ ትምህር ት ፡ ይጥላሉ ፡፡

፲፰። ስለ ፡ አርነት ፡ ፈቃድ ፡፡

ስለ ፡ አርነት ፡ ፈቃድ ፡ እንደህ ፡ ሲሉ ፡ ያስተምራሉ ፡፡ ሰ ው ፡ ያርነት ፡ ፈቃድ ፡ በክፍል ፡ አለው ፡ በሜደ ፡ ባለማዊ ፡ ነ ገርም ፡ በደህና ፡ አካሔድ ፡ ይመላለስ ፡ ዘንድ ፡ አእምሮው

ም ፡ በሚያስተውለውን ፡ ነገር ፡ ይመርጽ ፡ ዘንድ ። ነገር ፡ ግ ን ፡ ሰው ፡ ያለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ጸጋና ፡ ረዴት ፡ ያለ ፡ መን ፈስ ፡ ቅዱስም ፡ መስራት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ ያሰኝ ፡ ዘ ንድ ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ከለልቡ ፡ ይፈራ ፡ ዘንድ ፡ ከለልቡ ም ፡ ያምን ፡ ዘንድ ፡ ወይስ ፡ የተወለደበትን ፡ ክፉ ፡ መመ ኞቱን ፡ ከልቡ ፡ ያወጣ ፡ ዘንድ ፡ አይቻለውም ። እንደዬህ ፡ ያ ለ ፡ ነገር ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ብቻ ፡ ይሆናል ፡ እንጅ ፡ እግዚ አብሔር ፡ በቃሉ ፡ በሚሰጠው ። ጳውሎስ ፡ ብልዋልና ፡ ፩፤ ቆሮንቶስ ፡ ፪፤ ፲፬፤፤ ነፍሳዊ ፡ ሰው ፡ አይቀበልም ፡ የእግዚአ ብሔርን ፡ መንፈስ ፡ ነገር ።

ሰውም ፡ ሊያውቅ ፡ ብለን ፡ እኛ ፡ እንደዬህ ፡ ስንል ፡ አዲስን ፡ ነገር ፡ እንደናስተምር ፡ እነሆ ፡ ያውጉስቲኑስ ፡ ቃል ፡ ስለ ፡ አር ነት ፡ ፈቃድ ፡ በሂጶግናስቲኮን ፡ በ፫፤ መጽሐፉ ፡ እንደዬህ ፡ ሲ ል ። እኛ ፡ እናምናለን ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ያርነት ፡ ፈቃድ ፡ እ ንደለው ። ለሁሉ ፡ ከፍጥረታቸው ፡ ከልደታቸውም ፡ አእ ምሮና ፡ ልቡና ፡ አለ ። ለእግዚአብሔርስ ፡ እንደችን ፡ ያደር ጉ ፡ ዘንድ ፡ እንደ፡ችሉ ፡ አይደለም ፡ ወይስ ፡ እግዚአብሔር ን ፡ ከለልባቸው ፡ ለመውደድና ፡ ለመፍራት ። ነገር ፡ ግን ፡ በ ሚደዊ ፡ ለዚችም ፡ ሕይወት ፡ በሚደርስ ፡ ነገር ፡ አርነት ፡ አ ላቸው ፡ በጎን ፡ ወይስ ፡ ክፉን ፡ ለመምረጽ ። በጎም ፡ ማለ ቴ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ይላል ፡ አውጉስቲኑስ ። የሰው ፡ ጠባይዕ ፡ የምትችለው ፡ እንደዚህ ። በርሻ ፡ መስራት ፡ ወይስ ፡ አለ መስራት ። መብላትና ፡ መጠጥም ፡ ወደ ፡ ወዳጅም ፡ መ ሔድ ፡ ወይስ ፡ አለመሔድ ። ል...ንም ፡ መልበስ ፡ ወይ ስ ፡ መግፈፍ ። መሥራትንም ። ቤትንም ፡ መጋባት ። ስራው ንም ፡ መስራት ። እንዴሁም ፡ ያለውን ፡ የሚጠቅመውን ፡ በ ጎም ፡ የሚሆንን ፡ ነገር ፡ ማድረግ ። ይህም ፡ ሁሉ ፡ ከእግዚ አብሔር ፡ በቀር ፡ አይሆንም ፡ አይቆምም ። ሁሉ ፡ ከርሱ ፡ ዘንድ ፡ በርሱም ፡ ኑርዋል ፡ እንጅ ። ደሮ ፡ ግን ፡ ሰው ፡ ከ መምረጹ ፡ ኃጢአትን ፡ ማድረግ ፡ ይችላል ፡ እንደዬህ ። ለ ጣዖታት ፡ መስገድ ፡ መግደልም ፡ ሌላ ፡ ክፉ ፡ ነገርም ።

ም ፡ ቅጋረኛች ፡ ልቦችን ፡ በስራቸው ፡ ትምርት ፡ አደከሙ ፡
እንጂ ፡፡ እጅግም ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ስራ ፡ ሆነ ፡፡ አያሌን ፡ ሰዎች ፡
የልባቸው ፡ ጭንቀት ፡ ወደ ፡ ገደሞች ፡ አስኰበላላቸው ፡ ተ
ስፋ ፡ ሲያድርጉ ፡ ከዚያ ፡ በምንኵስና ፡ ጸጋውን ፡ ይሰሩ ፡ ዘ
ንድ ፡ ብለው ፡፡ አያሌም ፡ ሌላውን ፡ ስራውን ፡ አወጡ ፡ በ
ርሱ ፡ ጸጋውን ፡ ይሰሩ ፡ ዘንድ ፡ የኃጢአትንም ፡ ዕዳ ፡ ይከ
ፍሉበት ፡ ዘንድ ፡፡ ከርሳቸውም ፡ ብዙ ፡ አገኙ ፡ ሰው ፡ እን
ዴህ ፡ አድርጎ ፡ ወደ ፡ ዕርቅ ፡ እንደይደርስ ፡፡ ስለዚህም ፡ የ
ግድ ፡ ነበረ ፡ ይህነን ፡ የሃይማኖትን ፡ ትምርት ፡ በክርስቶስ ፡
እንዲያስተምሩ ፡ እጅግም ፡ እንዲጋደሉበት ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡
ያውቅ ፡ ዘንድ ፡ በሃይማኖት ፡ ብቻ ፡ ያለ ፡ ምግባር ፡ የእግ
ዚአብሔርን ፡ ጸጋ ፡ እንድናገኝ ፡፡

ደግሞም ፡ ያስተምራሉ ፡ ይህ ፡ ሃይማኖት ፡ ሰይጣናትና ፡
ክፉአን ፡ ሰዎችም ፡ ካላቸው ፡ ሃይማኖት ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ እ
ንደይሆን ፡፡ እልያም ፡ ደግመው ፡ ታሪክን ፡ ክርስቶስ ፡ እን
ደ ፡ ታመመ ፡ ከሙታንም ፡ እንደ ፡ ተነሣ ፡ ተቀብለዋልና ፡፡
እኛ ፡ ግን ፡ ስለ ፡ አይነተኛ ፡ ሃይማኖት ፡ እንናገራለን ፡ የሚ
ያምን ፡ እኛ ፡ በክርስቶስ ፡ ጸጋንና ፡ የኃጢአትን ፡ ሰርየት ፡
እንድንቀበል ፡፡ ይህም ፡ ሃይማኖት ፡ ያውቃል ፡ የታረቀው
ን ፡ አምላክ ፡ በክርስቶስ ፡ እንደለው ፡ ወደርሱም ፡ ይጸራ
ል ፡፡ ያለ ፡ እግዚአብሔርም ፡ እንደ ፡ አራማውያን ፡ አይኖር
ም ፡፡ ሰይጣናትና ፡ ክፉች ፡ ሰዎች ፡ በዚህ ፡ ነገር ፡ በኃጢአ
ት ፡ ስርየት ፡ አያምኑምና ፡ እግዚአብሔርን ፡ ይጸላሉ ፡ ወደ
ርሱም ፡ በውነት ፡ መጽራት ፡ አይችሉም ፡ የበጎ ፡ ነገርም ፡
ተስፋ ፡ ያደርጉት ፡ ዘንድ ፡ አይሆንላቸውም ፡፡ እንዲሁም ፡
መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ይናገራል ፡፡ ሰይጣና
ት ፡ ግን ፡ ክፉት ፡ ሰዎችም ፡ ያላቸው ፡ ዕውቀት ፡ በመጽሐ
ፍ ፡ ቅዱስ ፡ ሃይማኖት ፡ አይባልም ፡፡ እንዲህ ፡ ይላልና ፡ በብ
ራውያን ፡ ፲፩፡ ፩፡፡ ሃይማኖት ፡ ታሪክን ፡ ማወቅ ፡ አይደለም ፡
በእግዚአብሔር ፡ መታመን ፡ እንጂ ፡ የርሱንም ፡ ተስፋ ፡
መቀበል ፡፡ አውጉስቲኑስም ፡ ያሳስብናል ፡ የሃይማኖትን ፡
ቃል ፡ ሲል ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ እንዲህ ፡ እናስታውለው ፡
ዘንድ ፡ ማለቱ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መታመን ፡ እንዲሆ

ን ፡ እርሱ ፡ እንዲማርን ፡ ታሪክን ፡ ማወቅ ፡ ግን ፡ ሰይጣናት ፡ ደግመው ፡ እንዲያውቁት ፡ እንደ ደደለ ::

ደግሞም ፡ ያስተምራሉ ፡ በጎ ፡ ስራ ፡ መስራት ፡ በግድ ፡ እንዲፈለግ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሰው ፡ እንደይታመንበት ፡ ጸጋን ፡ በርሱ ፡ ደገብር ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንጅ :: እግዚአብሔርን ፡ ያመሰግንበት ፡ ዘንድ :: ሃይማኖትም ፡ ሁለግዜ ፡ ጸጋውን ፡ የኃጢአትንም ፡ ስርየት ፡ ብቻ ፡ ይዛል :: መንፈስ ፡ ቅዱ ስም ፡ በሃይማኖት ፡ ተሰጥትዋልና ፡ ልብን ፡ በጎን ፡ ስራን ፡ ለመስራት ፡ ያሰናድዋል :: ይህ ፡ ግን ፡ ሳይሆን ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ በልብ ፡ ሳይኖር ፡ ለልብ ፡ ኃይል ፡ የለውም ፡ ደግሞም ፡ ከሰይጣን ፡ ሥልጣን ፡ በታች ፡ ነው ፡ እርሱም ፡ የተቸገረውን ፡ የሰውን ፡ ጠባይዕ ፡ ወደ ፡ ብዙ ፡ ኃጢአት ፡ ደወስደል ፡ ካለም ፡ ጠቢባን ፡ እንድናውቅ ፡ በጎ ፡ ያለ ፡ ነውርም ፡ ይመላለሱ ፡ ዘንድ ፡ የፈለጉ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ አልሆነላቸውም ፡ በግልጽ ፡ በብዙም ፡ በታላቅም ፡ ኃጢአት ፡ ወደቁ :: እንደህም ፡ ለሰው ፡ ይሆናል ፡ ያለ ፡ አደነተኛ ፡ ሃይማኖት ፡ ያለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ቢኖር ፡ ራሱንም ፡ ባለቤቱ ፡ በሰውነቱ ፡ ኃይል ፡ መግዛት ፡ ቢሻ :: ስለዚህም ፡ የሃይማኖት ፡ ትምርት ፡ አይሰደበ ፡ በጎ ፡ ስራ ፡ እንዲከለክል ፡ ተብሎ ፡ ያከብረት ፡ እንጅ ፡ በጎ ፡ ስራ ፡ መስራት ፡ አስተምርዋልና ፡ ረዴትንም ፡ ሰጥትዋልና ፡ በጎ ፡ ስራን ፡ እንሰራ ፡ ዘንድ :: ያለ ፡ ሃይማኖትና ፡ ያለ ፡ ክርስቶስ ፡ የሰው ፡ ጠባይዕና ፡ ችሎት ፡ እጅግ ፡ ደደክማል ፡ በጎ ፡ ስራ ፡ ከመስራት ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ከመጽራት ፡ በመከራም ፡ ከመታገሥ ፡ ባልንጅራውንም ፡ ከመውደድ ፡ የታዘዘውንም ፡ ሹመት ፡ ከመፈጸም ፡ ከመታዘዝም ፡ ከክፋ ፡ መመኞትም ፡ ከመሸሽ :: እንደህ ፡ ያለ ፡ ታላቅ ፡ በውነትም ፡ በጎ ፡ ሰራ ፡ አይደረግም ፡ ከክርስቶስ ፡ ረዴት ፡ በቀር ፡ እርሱ ፡ እንዲል ፡ በዮሐንስ ፡ ወንጌል ፡ ፲፭፡ ፭። ያለኔ ፡ አንዳችን ፡ ማድረግ ፡ አትችሉም :: የክርስቶስንም ፡ ረዴት ፡ አንቀበልም ፡ በሃይማኖት ፡ እንጅ ::

፳፩፤ ወደ ፡ ቅዱሳንም ፡ ስለ ፡ መጽራት ።

ለቅዱሳን ፡ ስለ ፡ ማገልገል ፡ ወገኖቻችን ፡ እንዴህ ፡ ብለው ፡ ያስተምራሉ ፡ ቅዱሳንን ፡ እንድናስብ ፡ ሃይማኖታችነን ፡ እናጽና ፡ ዘንድ ፡ አይተን ፡ ለርሳቸው ፡ ጸጋ ፡ እንደ ፡ ሆነላቸው ፡ በሃይማኖትም ፡ እንደ ፡ ተረዳቸው ፡ ደግሞም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በየመጸራቱ ፡ እርሳቸውን ፡ ምሳሎች ፡ ሊያድርጋቸው ፡ ላካሔደ ። እንዴህም ፡ ቄሣር ፡ ይችላሉ ፡ የዳዊትን ፡ ምሳሌ ፡ ይከተሉ ፡ ዘንድ ፡ ጾርን ፡ አድርገው ፡ በቱርኮች ፡ ላይ ። ሁለታቸው ፡ ነገሥታት ፡ ናቸውና ፡ የመንግሥታቸውን ፡ ሰዎች ፡ መጠበቅ ፡ ለሚገባቸው ። ነገር ፡ ግን ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ቅዱሳን ፡ መጽራት ፡ ከቅዱሳንም ፡ ዘንድ ፡ ረዴትን ፡ መሻት ፡ አልታዘዘም ። አንድ ፡ አስታራቂና ፡ መኻከለኛ ፡ ብቻ ፡ ተሹምዋልና ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በሰው ፡ መኻከል ፡ እርሱም ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ፩፤ ጢሞቴዎስ ፡ ፪፤ ፭። እርሱም ፡ ብቻውን ፡ ምድኅናችን ፡ ለብቻው ፡ የካህናት ፡ አለቃችን ፡ የጸጋ ፡ ዙፋናችንም ፡ ጸራቅሌቶሳችንም ፡ ነው ፡ ሮሜ ፡ ፰፤ ፴፬። እርሱም ፡ ብቻ ፡ ተስፋ ፡ አስደረገልነ ፡ ጸሎታችንን ፡ ይሰማ ፡ ዘንድ ። ይህም ፡ ከሁሉ ፡ የሚበልጥ ፡ ማምለክ ፡ ሁኖ ፡ በእግዚአብሔር ፡ መጽሐፍ ፡ ይቈጠራል ፡ ይህነን ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ በመከራ ፡ ሁሉ ፡ በመሻትም ፡ በጕደይም ፡ ሁሉ ፡ ከለልባችን ፡ እንሻው ፡ ዘንድ ፡ እንጸራበትም ፡ ዘንድ ። የዮሐንስ ፡ ፩፤ መልእክት ፡ ፪፤ ፩።

፳፪፤ ስለ ፡ ቊርባን ፡ በሁለት ፡ መልኩ ።

በኛ ፡ ዘንድ ፡ ቊርባንን ፡ በ፪፤ መልኩ ፡ ለሕዝብም ፡ ይሰጣሉ ። ይህ ፡ የክርስቶስ ፡ ጥሬ ፡ ትእዛዝ ፡ ነውና ፡ ማቴዎስ ፡ ፳፮፤ ፳፯። እንዴህ ፡ ሲል ። ከዚህ ፡ ጠጡ ፡ ሁላችሁ ። እንዴህ ፡ ብሎ ፡ ክርስቶስ ፡ በቁም ፡ ነገር ፡ ስለ ፡ ጽዋዕ ፡ አዘዘ ፡ ሁላቸው ፡ ከርሱ ፡ ይጠጡ ፡ ዘንድ ። ሰውም ፡ ከቶ ፡ እንደይጠራጠር ፡ ስለዚህ ፡ ጽዋዕ ፡ ለቀሳውስት ፡ ብቻ ፡ እንደይሆን ፡ ብሎ ፡ ጳውሎስ ፡ ፩፤ ቆሮንቶስ ፡ ፲፩፤ ፲፯፤ ይገልጸዋል ፡ የቆሮንቶስ ፡ ጉባኤ ፡ ሁለቱን ፡ እንደ ፡ ተቀበለች ። እ

ንደህም : ያለ : ማድረግ : እጅግ : ዘመን : በቤተ : ክርስቲ
ያን : ኖረ : ከታሪክ : ካባቶችም : መጻሕፍት : እንደ ገለጽ ::
ቂጵርያኖስም : ብዙ : ጊዜ : በመጻሕፍቱ : ይላል : ጽዋዕ :
በዘመኑ : ለሕዝብ : ሁሉ : እንደ : ተሰጠ :: እንደሁም : ሄ
ሮኒሙስ : ይላል : የሚያቍርቡ : ቀሳውስት : ለሕዝብ : የ
ክርስቶስን : ደም : እንደ ሰጡ :: ጳጳስ : ግላስዩስም : ባ
ለቤቱ : ያዛል : ቍርባን : እንደ ይከፈል :: ቃኖንም : ከቶ :
አይገኝም : ሕዝብ : አንድ : ክፍልን : ብቻ : ይቀበሉ : ዘን
ድ : የሚያዝ :: ጊዜና : ሰውም : አይታወቅም : መቼ : ወ
ይስ : በማን : ይህች : ልማድ : ሕዝብ : በቍርባን : ፩፤ ክፍ
ልን : ብቻ : እርሱም : እንጀራውን : እንደ ቀበሉ : የሚያ
ዝ :: ነገር : ግን : ይህ : ተገለጸ : ይህች : ልማድ : በእግዚአ
ብሔር : ትእዛዝና : በቀደሙ : ቃኖኖች : ላይ : እንደ ሆን : እ
ንደ ይገባም ::

ስለዚህም : እንደ : ክርስቶስ : ሥርዓት : ቍርባንን : መ
ቀበል : የፈለጉትን : ልብ : እናከብድ : ዘንድ : በጌታችን
ም : በክርስቶስ : ሥርዓት : ላይ : እንደ ቍርቡ : እናገደቸ
ው : ዘንድ : አልተገባነም ::

፷፫፡፡ ስለ : ቀሳውስት : መጋባት ::

በሰው : ሁሉ : እጅግ : ታላቅ : መክሰስ : ነበረ : በታላቆች
ና : በታናሾች : ንጽሕናውን : ይጠብቁ : ዘንድ : ባልቻላቸው :
በቀሳውስት : ዝሙት :: እንደህም : ያለ : የሚያስፈራ : ኃ
ጢአታቸው : መብለጥ : አይችልም : ነበረ :: ከዚህ : ታላ
ቅ : ኃጢአትም : ከዝሙትና : ከምንዝር : ከርሱም : ከተነ
ሣ : ማሰናከል : ይሸሹ : ዘንድ : ብለው : አያሌ : ከቀሳው
ስታችን : በመጋባት : ሕግ : ተጋቡ : መክንያትንም : ስለዚ
ህ : ይገልጻሉ : ወደ : መጋባት : እንደ : ተገደ : በልባቸው :
በግድ :: መጽሐፍ : ቅዱስ : በቁም : ነገር : ሲል :: እግዚአ
ብሔር : መጋባትን : እንደ ደረገ : ርክስናውን : ሊከለክልበ
ት : ጳውሎስ : እንደ ል : ፩፤ ቆሮንቶስ : ፯፤ ፪፤ ፱፤ ሰው : ከ
ምንዝር : ሁሉ : ሊሸሽ : ለእ ያንዳንደ : ምሽቱ : ትሁንለ

ት ፡ ብሎ ፡፡ መጋባትም ፡ ከመቃጠል ፡ ይሻላል ፡፡ እግዚአ
ብሔርም ፡ ወንድንና ፡ ሴትን ፡ ፈጠረ ፡ በመጋባት ፡ አንድ ፡
ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡፡ ባረካቸውም ፡ አላቸውም ፡፡ ብዙ ፡ ተበዙ
ም ፡፡ ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፡ ፩፡፡ አሁንም ፡ ሰው ፡ ቢያስብ ፡ ም
ናልባት ፡ ሥልጣንና ፡ ኀይል ፡ እንደለው ፡ ያለ ፡ ልዩ ፡ መጽ
ሬትና ፡ ኀይል ፡ ከእግዚአብሔር ፡ በፈቃዱና ፡ በስለቱ ፡ ብ
ቻ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ የነገሥታት ፡ ንጉሥን ፡ ፍጥረት ፡ ይ
ለውጥ ፡ ዘንድ ፡ የተሻለውንም ፡ ያደርገው ፡ ዘንድ ፡ ይህ ፡
እንደ ይሆን ፡ ታሪክ ፡ ገለጸ ፡ መርኩስ ፡ በዝቶበታልና ፡ ቤተ ፡
ክርስቲያንም ፡ በቀሳውስትዋ ፡ ዝሙት ፡ እጅግ ፡ ተነወረች ፡፡

አሁንም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃልና ፡ ትእዛዝ ፡ በሰው ፡
ትእዛዝና ፡ ስለት ፡ ሁሉ ፡ ከቶ ፡ መለወጥ ፡ አይችልምና ፡
በዚህና ፡ በሌላ ፡ መክንያት ፡ ቀሳውስትና ፡ ሌሎች ፡ የተቀደ
ሱ ፡ ሰዎች ፡ ምሽቶችን ፡ አጋቡ ፡፡

ደግሞም ፡ ይገለጻል ፡ ከታሪክና ፡ ካባቶች ፡ መጻሕፍት ፡
በድሮ ፡ ሥርዓት ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለቀሳ
ውስትና ፡ ለዲያቆናት ፡ ምሽቶች ፡ እንደ ፡ ነበሩላቸው ፡፡ ስ
ለዚህም ፡ ጳውሎስ ፡ ይላል ፡፡ ኤጲስቆጶስ ፡ ያለ ፡ ነውር ፡
ይሁን ፡ ያንዲት ፡ ሴት ፡ ባል ፡፡ ፩፡ ጢሞቴዎስ ፡ ፫፡ ፪፡፡ ደግ
ሞም ፡ በንምሳ ፡ አሁን ፡ ፬፻፡፡ አመት ፡ ብቻ ፡ ነው ፡ ቀሳወ
ስትን ፡ ለብቸኝነት ፡ እንደ ፡ አገዱ ፡ ከመጋባትም ፡ እንደ ፡ ከ
ለከልዋቸው ፡፡ እርሳቸውም ፡ ሁሉ ፡ የዚያን ፡ ጊዜ ፡ በዚህ ፡
ትእዛዝ ፡ እጅግ ፡ ተከራከሩ ፡ ሁከትም ፡ ሆነ ፡፡ ጳጳስም ፡
የዚያን ፡ ጊዜ ፡ የሚመጣውን ፡ መጋባት ፡ ብቻ ፡ አልከለከ
ለም ፡ ያለውን ፡ መጋባት ፡ ደግሞ ፡ አፈረሰባቸው ፡ እንጅ ፡፡

ደህም ፡ ማድረጉ ፡ ከሕግ ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ፡ ተጻላ ፡ በእግዚ
አብሔርና ፡ በሰው ፡ ዘንድ ፡፡ ከዚህም ፡ በግድ ፡ ከተደረገ ፡
ከቀሳውስት ፡ አለመጋባት ፡ ከቶ ፡ በጎ ፡ ነገር ፡ አልወጣም ፡
ክፉ ፡ እንጅ ፡፡ ደግሞም ፡ ጲዮስ ፡ ፪፡ እርሱ ፡ አዋቂ ፡ ሰው ፡
የነበረ ፡ እጅግ ፡ ጊዜ ፡ እንዲህ ፡ አለ ፡፡ አንዳንድ ፡ መክንያ
ት ፡ ለቀሳውስት ፡ አለመጋባት ፡ አለ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እጅግ ፡ ብ
ዙ ፡ መክንያት ፡ አለ ፡ ለመጋባታቸው ፡፡

ስለዚህም ፡ እኛ ፡ ለርሰዎ ፡ ለንጉሣችን ፡ ተስፋ ፡ እናደ

ርጋለን ፡ ይህነን ፡ እንዲያስቡ ፡ ለቀሳውስትም ፡ ሥልጣን ፡ እንዲሰጡ ፡ ምሽትን ፡ ያገቡ ፡ ዘንድ ፡፡ ለማንም ፡ አይጐዳምና ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ለሁሉም ፡ እጅግ ፡ ይጠቅማል ፡ እንጅ ፡ በዚህ ፡ ነገርም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ ብንከተል ፡፡ እርሱ ፡ ክስለት ፡ ሁሉ ፡ ይበልጣልና ፡፡ ሰውም ፡ ላለመጋባት ፡ እንኳ ፡ ስለት ፡ ካደረገ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ አይለወጥበትም ፡፡

፳፬፡፡ ስለ ፡ ቍርባን ፡፡

ጸላቶቻችን ፡ እኛ ፡ ቍርባንን ፡ እንደ ፡ ሻርነ ፡ ቢያጣሉነ ፡ ሐሰት ፡ ይናገራሉ ፡፡ የታወቀ ፡ ነውና ፡ ቍርባን ፡ በኛ ፡ ዘንድ ፡ እጅግ ፡ እንደ ፡ ክበረ ፡ ጸላቶቻችን ፡ ከሚያከብሩት ፡ ይልቅ ፡፡ መምህራኖችን ፡ ሕዝባችንን ፡ እጅግ ፡ ያስተምራሉና ፡ የምሥጢሩን ፡ ትምህርት ፡ ስለ ፡ ምንድርም ፡ እንደ ፡ ተሰራ ፡ ምንድርም ፡ ይገባል ፡ እናደርግ ፡ ዘንድ ፡ በነ ፡ ልንቀበለው ፡ ብለው ፡ የፈራውን ፡ ልብ ፡ ለማጽናት ፡፡ እንደዚሁም ፡ ሕዝብ ፡ ወደ ፡ ቍርባን ፡ ይመጣሉ ፡፡

መምህራኖችንም ፡ በቍርባን ፡ የገባውን ፡ ስሕተት ፡ ይጸይፋሉ ፡፡ ድግሞም ፡ የቍርባን ፡ ማድረግ ፡ በኛ ፡ ዘንድ ፡ አልተለወጠም ፡ በዚህ ፡ ብቻ ፡ እንጅ ፡ አስቀድሞ ፡ በለቲና ፡ ቋንቋ ፡ ከተቀደሰ ፡ አሁን ፡ በንምሳዊ ፡ ይቀደሳል ፡፡ ማምለክ ፡ ሁሉ ፡ ለዚህ ፡ ነውና ፡ ሕዝብ ፡ የክርስቶስን ፡ ዕውቀት ፡ ይማርበት ፡ ዘንድ ፡፡

ቍርባን ፡ ግን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ማድረጉ ፡ ከዚህ ፡ ዘመን ፡ አስቀድሞ ፡ ለክፉ ፡ ስለ ፡ ተደረገ ፡ ገቢያ ፡ እስኪሆንበት ፡ ቀሳውስትም ፡ በብር ፡ እስኪቀድሱት ፡ ድረስ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ እንዲህ ፡ ያለውን ፡ ኃጢአት ፡ መምህራኖችን ፡ ገሠጹ ፡ የጳውሎስን ፡ ነገር ፡ ሲያሳስቡ ፡ ፩፡ ቆሮንቶስ ፡ ፲፩፡ ፳፱፡ ሲል ፡፡ ሰው ፡ ሳይገባው ፡ ቢበላ ፡ ቢጠጣም ፡ ቍርባንን ፡ ለራሱ ፡ ኵነኔ ፡ ይበላል ፡ ይጠጣልም ፡ የጌታን ፡ ገላ ፡ አይለይምና ፡፡ ከዚህ ፡ ኵነኔ ፡ ፈርተን ፡ ለቍርባን ፡ የማይገባ ፡ ነገር ፡ ሻርነ ፡ ከመካከላችን ፡ የተሻየጠውን ፡ ቍርባን ፡

በስውርም ፡ ለብቻው ፡ ያለውን ፡ ቍርባን ፡ ስለ ፡ ብርና ፡ በግ ድ ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ የተደረገ ፡፡

ደግሞም ፡ ያችን ፡ ታላቂቱን ፡ ስሕተት ፡ ጸየፉ ፡ የሮም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ስታስተምር ፡ ክርስቶስ ፡ ጌታችን ፡ በሞ ቱ ፡ ስለ ፡ ሚወረስ ፡ ኃጢአት ፡ ብቻ ፡ ቤዛ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ቍ ርባንንም ፡ እንደ ፡ ደረገ ፡ ስለ ፡ ቀረ ፡ ኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ እንደህ ም ፡ ቍርባንን ፡ ምሥዋዕትን ፡ እንደ ፡ ደረገው ፡ ለሕያዋንና ፡ ለሙታን ፡ ኃጢአታቸውን ፡ ያስወግድበት ፡ ዘንድ ፡ እግዚአ ብሔርንም ፡ ያስታርቅ ፡ ዘንድ ፡፡ ከዚህ ፡ ትምርትም ፡ ክርክ ር ፡ ተነሣ ፡ እጅግ ፡ ሲመጉቱ ፡ አንድ ፡ ቍርባን ፡ ለብዙ ፡ ሰ ዎች ፡ ሲያቀርቡ ፡ መገባረ ፡ እንዲያህል ፡ ለእያንዳንዱ ፡ ለብቻው ፡ ከሚደረግ ፡ ቍርባን ፡ ጋራ ፡ ወይስ ፡ አያህልም ፡ ብለው ፡፡ አያህልምም ፡ ሲሉ ፡ እጅግ ፡ ቍርባኖች ፡ ተነሡ ፡ ቍጥር ፡ የሌላቸው ፡፡ ሰው ፡ እንደህ ፡ በማድረግ ፡ ፈቃዱን ፡ ሁሉን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ያገኝ ፡ ዘንድ ፡ በክርስቶስም ፡ ያ ለ ፡ ሃይማኖት ፡ እውነተኛ ፡ ማምለክም ፡ ተረስትዋል ፡፡

ስለዚህም ፡ መምህራኖችን ፡ እንደ ፡ ተገባቸው ፡ አስተማ ሩ ፡ ስለ ፡ ቍርባን ፡ ስለ ፡ በጎ ፡ ማቍረቡ ፡፡ ምሥዋዕትም ፡ ስለ ፡ ሚወረስ ፡ ኃጢአትና ፡ ስለ ፡ ሌላ ፡ ኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ ከ ቶ ፡ እንደ ፡ ደገኝ ፡ ካንድ ፡ ምሥዋዕት ፡ በቀር ፡ ክርስቶስ ፡ የ ሠዋው ፡ እርሱ ፡ በሞተ ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ ቤዛ ፡ ሁኖ ፡፡ እጅግ ፡ ድንቅና ፡ አዲስ ፡ ስንፍና ፡ ነው ፡ በቤተ ፡ ክር ስቲያን ፡ ማስተማር ፡ የክርስቶስ ፡ ሞት ፡ ስለ ፡ ሚወረስ ፡ ኃጢአት ፡ ብቻ ፡ ቤዛ ፡ እንዲሆን ፡ ስለ ፡ ሌላ ፡ ኃጢአትም ፡ አይደለም ፡፡ ስለዚህም ፡ ተስፋ ፡ እናደርጋለን ፡ ሰው ፡ ሁ ሉ ፡ እንዲያስታውል ፡ እንደህ ፡ ያለውን ፡ ስሕተት ፡ በከን ቱ ፡ እንደ ፡ ልጸየፍነው ፡፡ ደግሞም ፡ ጳውሎስ ፡ ሲል ፡፡ ሮሜ ፡ ፫ ፡ ፳፰ ፡፡ ጸጋ ፡ እንድናገኝ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ በሃይማ ኖት ፡ በስራም ፡ አይደለም ፡ ይህ ፡ የቍርባን ፡ ክፉ ፡ ማቍረ ብ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ይጻላል ፡ ሰው ፡ መስሎታልና ፡ በዚህ ፡ መ ቍረብ ፡ ጸጋውን ፡ ያገኝ ፡ ዘንድ ፡፡ እንደህ ፡ ነበረና ፡ ቄስ ፡ ለ ራሱ ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ለሕያዋንና ፡ ለሙታን ፡ ሁሉ ፡ ኃ ጢአትን ፡ ያስወገደበት ፡ ጸጋውንም ፡ ያደረገበት ፡ ይመስለ

ው ፡ ነበረ ። ደግሞም ፡ ቍርባን ፡ ስለ ፡ ኀጢአት ፡ መሥዋዕ ትን ፡ እናደርግበት ፡ ዘንድ ፡ አልተሰራም ፡ ክርስቶስ ፡ ይህነ ን ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ለወትሮ ፡ ተፈጽምዋልና ፡ ሃይማኖታችንን ፡ ለማስነሣትና ፡ ልባችንን ፡ ለማጽናት ፡ እንጂ ። ቍርባን ፡ ያሳስብናልና ፡ ክርስቶስ ፡ የጸጋውን ፡ የኀጢአት ፡ ስርየትን ም ፡ ተስፋ ፡ እንደስደረገልነ ። ስለዚህም ፡ ይቾ ፡ ምሥጢር ፡ ሃይማኖትን ፡ ትፈልጋለች ፡ ያለ ፡ ሃይማኖትም ፡ መቍረብ ፡ ከንቱ ፡ ነው ።

እንኪያስ ፡ ቍርባን ፡ መሥዋዕት ፡ አይደለምና ፡ ለሌሎ ች ፡ ሕያዋን ፡ ወይስ ፡ ሙታን ፡ ኀጢአታቸውን ፡ ያስወግድ ፡ ዘንድ ። ነገር ፡ ግን ፡ ያንድነት ፡ እራት ፡ ቄስና ፡ ሌሎች ፡ ለራሳ ቸው ፡ የሚቍረቡበት ፡ በኾ ፡ ዘንድ ፡ እንደዪህ ፡ ይደረጋል ፡ በ ባላትና ፡ በሌላ ፡ ጊዜ ፡ የሚቍረቡ ፡ ቢገኙ ፡ ቍርባን ፡ እንደ ቀደስ ። እንደዪህም ፡ እኛ ፡ እናደርጋለን ፡ በቅድም ፡ እንደ ፡ አደረጉ ፡ ከጳውሎስም ፡ ካፈ ፡ ወርቅም ፡ ከሌላ ፡ መጽሐፍ ም ፡ እንደ ገለጹ ።

፳፪። ስለ ፡ መናዘዝ ።

መናዘዝ ፡ በቀኅውስታችን ፡ አልተኻረም ። ይህነን ፡ ልማ ድ ፡ ጠብቀናለና ፡ ቍርባንን ፡ በፊት ፡ ላልተሰሙ ፡ ላልተፈቱ ም ፡ እንዳንሰጠው ። በርሱም ፡ ሕዝብ ፡ ይህና ፡ ትምርትን ፡ ይሰማሉ ፡ የፍትሐት ፡ ነገር ፡ ቄስ ፡ በክርስቶስ ፡ ትእዛዝና ፡ ሥልጣን ፡ ኀጢአቱን ፡ ለሚያስታውቀው ፡ በክርስቶስም ፡ ለሚያምን ፡ ሲል ። ኀጢአትህ ፡ ቀረ ። ይህ ፡ የምስራች ፡ ማ ጽናቱ ፡ እንዴት ፡ ታላቅ ፡ እንዲሆን ፡ የተገኘ ፡ የቄስ ፡ እርሱ ፡ ሰው ፡ ሁኖ ፡ ቃሉ ፡ አይደለምና ፡ ብሎ ፡ የእግዚአብሔር ፡ እ ንጅ ፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡ ኀጢአትን ፡ ይቀር ፡ ማለት ፡ የሚችል ። ፀርሱ ፡ ፈንታ ፡ በርሱም ፡ ትእዛዝ ፡ ተናግርዋልና ።

ስለዚህ ፡ ትእዛዝም ፡ መምህራኖችን ፡ ሕዝባችንን ፡ እጅ ግ ፡ ያስተምራሉ ፡ በሰው ፡ ነገር ፡ እንዲያምኑ ፡ ብለው ፡ በእ ግዚአብሔር ፡ ነገር ፡ እንጅ ፡ እንዳይጠራጠሩም ። ስለዚህ ፡ ነገርም ፡ ቀሳውስት ፡ አስቀድመው ፡ ባንዲት ፡ ቃል ፡ አላስታ

ማረም፡በመናዘዝ፡እጅግ፡በተናገረ፡ጊዜ፡የሕዝብን፡ል
ብ፡ ሠቀዩ፡ ኀጢአትን፡ በማስቍጠር፡ በመክፈልም፡ከን
ስሓም፡በመፍታትም፡በመንገድም፡ወደ፡ቅዱስ፡ስፍራ፡
ይህነንም፡በሚመስል፡ነገር። ከጸላቶቻችንም፡ ብዙ፡አ
ሉ፡ባለቤታቸው፡የሚሉ፡የመምህራኖችን፡ትምህርት፡
በዚህ፡ነገር፡ከሌላ፡እንዲሻል።

ስለ፡መናዘዝም፡መምህራኖችን፡እንዲህ፡ብለው፡ያስ
ተምራሉ፡ ሰውን፡እንዲያገዱ፡ ኀጢአቱን፡ ሁሉን፡ በስ
ም፡ ለመንገር፡ ይህ፡ ማንም፡ አይችልምና። ዳዊት፡ እን
ዲል። ማን፡ይችላል፡ይቈጥር፡ዘንድ፡ስንት፡ጊዜ፡እን
ዲበድል። የተሰወረብኝንም፡ ኀጢአት፡ ይቅር፡በልልኝ፡
መዝሙር፡ ፲፱፡ ፲፫። የሬሚያስም፡ ይላል፡ በመጽሐፉ፡
፲፯፡ ፱። የሰው፡ልብ፡ይደፍራል፡ተስፋውንም፡ይጥላል።
ማን፡ይችላል፡ያጠልቀው፡ዘንድ። የሰው፡ጠባይዕ፡እን
ንዲህ፡በኀጢአት፡ሁሉ፡መላ፡ሁሉን፡ማየትና፡ማወቅ፡
እንዲይችል። ከምንቈጥረውም፡ ኀጢአት፡ ብቻ፡ ብንፈ
ታ፡ባይጠቅምን፡ከሁሉ፡ባንፈታ፡ካንድ፡በውነት፡አልተ
ፈታነምና። ስለዚህም፡ገድ፡የለም፡ሰው፡ኀጢአቱን፡በ
መናዘዝ፡እንዲቈጥር። እንዲሁም፡አባቶች፡አስተማሩ፡
ስለ፡መናዘዝ፡እንደ፡አፈ፡ወርቅ፡ሌሎችም።

፷፯። ስለ፡መብል፡ልዩነት።

የቀደሙ፡ መምህራን፡አስተማሩ፡ሰበኩም፡ ጻፉም፡
የመብልን፡ልዩነት፡ከሰውም፡የተሰራውን፡ትእዛዝና፡
ልማድ፡መጠበቅ፡እንዲጠቅም፡ብለው፡ሰው፡በርሱ፡
ጸጋውን፡ይሰራበት፡ዘንድ፡የኀጢአትንም፡ዕዳ፡ይከፍ
ልበት፡ዘንድ። ስለዚህም፡ዕለት፡ዕለት፡አዲስ፡ጾም፡
የማምለክም፡አዲስ፡ነገር፡አዲስ፡ሥርዓትም፡ይህነን
ም፡የሚመስለው፡ነገር፡ተነሣ፡ መምህራንም፡ ብርቱ፡
ነበረበት፡እንዲህ፡ያለ፡ነገር፡ለማምለክ፡እንዲገባ፡ሰ
ውም፡ በመጠበቀው፡ ጸጋ፡ እንዲሰራ፡ ባለመጠበቀው
ም፡ታላቅ፡ኀጢአት፡እንዲሆን። ከዚህም፡እጅግ፡ታላ

ቅ ፡ ስሕተት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተነሣች ። የክርስቶስ ፡ ጸ
ጋ ፡ የሃይማኖትም ፡ ትምህርት ፡ ተጕድቶበታልና ፡ በወንጌ
ልም ፡ ከሁሉ ፡ የሚበልጥ ፡ ነገር ፡ እርሱ ፡ ነውና ፡ ስለ ፡ ጸ
ጋ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ ምግባሩም ፡ ስለ ፡ ሃይማኖትም ፡
የትምርት ፡ መሠረት ፡ ይጐደል ፡ እርሱ ፡ ቢጐደ ። ስለዚህ
ም ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ እጅግ ፡ ብርቱ ፡ ጻፈ ፡ በሙሴ ፡ በክ
ህነት ፡ ሕጉ ፡ ላይ ፡ በሰውም ፡ በተሰራ ፡ ካባቶች ፡ ወደኛ ፡
አልፎ ፡ በመጣ ፡ ልማድ ፡ ላይ ። እኛ ፡ እንማር ፡ ዘንድ ፡ በ
እግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ ቅዱሳን ፡ እንደንሆን ፡ በስራችን ፡ በ
ሃይማኖት ፡ በክርስቶስ ፡ እንጅ ፡ ጸጋውን ፡ ተቀብለን ፡ በክ
ርስቶስ ፡ መክንያት ። ይህች ፡ የጳውሎስ ፡ ትምርት ፡ ለመ
ጥፋት ፡ ቀረበች ፡ ሲያስተምሩ ፡ ሰው ፡ የእግዚአብሔርን ፡
ምህረት ፡ ሊሰራ ፡ በትእዛዛት ፡ በመጾምም ፡ መብልንም ፡
ልብስንም ፡ በመለየት ፡ የሚቀርም ። እንደህ ፡ ያለ ፡ የሰ
ው ፡ ሥርዓት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ትእዛዝ ፡ አስጨለም ፡
የሰው ፡ ሥርዓት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ትእዛዝ ፡ እጅግ ፡ የም
ትበልጥ ፡ ተቈጥራለችና ። ይህም ፡ ብቻ ፡ የክርስቲያን ፡ አ
ካሔድ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ አስተማሩ ፡ በዓልን ፡ እንደህ ፡ የሚ
ያከብር ፡ በግልጽም ፡ እንደህ ፡ የሚጸልይ ፡ እንደህም ፡ የ
ሚጾም ፡ እንደህም ፡ የሚለብስ ፡ ደህናና ፡ ደግ ፡ ክርስቲያ
ን ፡ ተባለ ። ሌላ ፡ የሚገባ ፡ የታዘዘም ፡ በጎ ፡ ስራ ፡ ግን ፡ ዓ
ለማዊ ፡ ሥጋዊም ፡ ነገር ፡ ሁኖ ፡ ተቈጠረ ። ሰው ፡ ኢያንዳ
ንዱ ፡ በየመጸራቱ ፡ የሚገባውን ፡ ነገር ፡ ቢሰራ ፡ ባለቤቱ ፡
ቢደክም ፡ ምሽቱንና ፡ ልጆቹን ፡ ይመግብ ፡ ዘንድ ፡ እግዚአ
ብሔርንም ፡ ለመፍራትና ፡ ለመውደድ ፡ ያሳድጋቸው ፡ ዘ
ንድ ፡ እመቤትም ፡ ልጆችን ፡ ወልዳ ፡ መልካም ፡ ብትጠ
ብቃቸው ፡ መኰንንም ፡ አገሩንና ፡ ሰዎቹን ፡ ቢገዛ ። እንደ
ህም ፡ የሚመስል ፡ ስራ ፡ ዓለማዊና ፡ ያልተፈጸመ ፡ የማይ
ጠቅምም ፡ ስራ ፡ ተባለ ፡ ካባቶች ፡ ወደኛ ፡ የወረደ ፡ የሰ
ው ፡ ትእዛዝ ፡ ብቻ ፡ የተመሰገነውን ፡ ስም ፡ ተቀበለ ፡ ቅዱ
ስና ፡ ፍጹም ፡ ስራ ፡ ተብሎ ። ስለዚህም ፡ ልክና ፡ ጨርስ ፡
አልታወቀም ፡ እንደህ ፡ ያለችውን ፡ ሥርዓት ፡ ለማድረግ ።

እንደህ ፡ ያለችም ፡ ሥርዓት ፡ የሰውን ፡ ልብ ፡ እጅግ ፡ ለ

ማስቸገር ፡ ሆነ ፡ ሁሉን ፡ ይጠብቁ ፡ ዘንድ ፡ ሰዎች ፡ አይችሉም ፡ ነበረና ፡ ደግሞም ፡ የታዘዘ ፡ ማምለክ ፡ ሁኖ ፡ መሰላቸው ፡፡ ጌርሶንም ፡ ይላል ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ተስፋቸውን ፡ ሁሉን ፡ እንደ ፡ ጣሉት ፡ እያሌም ፡ ነፍሳቸውን ፡ እንደ ፡ ገደሉ ፡ የክርስቶስን ፡ የጸጋውን ፡ ማጽናናት ፡ አልሰሙምና ፡ እጅግ ፡ ሁከትም ፡ እጅግም ፡ መጉደት ፡ በሥጋና ፡ በነፍስ ፡ በዚህ ፡ መክንያት ፡ ሆነ ፡፡

ስለዚህም ፡ መምህራኖችን ፡ በድፍረት ፡ አይደለም ፡ ወይስ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ሥልጣናት ፡ በመናቅ ፡ ስለዚህ ፡ ነገር ፡ ያስተማሩ ፡፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ታላቅ ፡ ጉደይ ፡ ነበረ ፡ እንጅ ፡ ስለዚህ ፡ ስሕተት ፡ ሁሉ ፡ ከለዚህ ፡ ሥርዓቶችም ፡ ስለ ፡ ተነሣ ፡ ጥፋት ፡ ያስተምሩ ፡ ዘንድ ፡፡ ወንጌል ፡ በግድ ፡ ይፈልገዋልና ፡ የሃይማኖት ፡ ነገር ፡ ወትሮ ፡ በሁሉ ፡ ላይ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይሰበክና ፡ ይማር ፡ ዘንድ ፡፡ ይህነን ፡ ትምርት ፡ ግን ፡ ሰው ፡ አያስተውልም ፡ በኀይሉ ፡ በስራውም ፡ ጸጋውን ፡ ይሰራ ፡ ዘንድ ፡ ቢመስለው ፡፡ እንዲሁም ፡ አስተማሩበት ፡ ሲሉ ፡፡ የሰውን ፡ ሥርዓት ፡ በመጠበቅ ፡ ሰው ፡ አይችልም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ምህረት ፡ መስራት ፡ ወይስ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ማስታረቅ ፡ ወይስ ፡ የኃጢአትን ፡ ዕዳ ፡ መክፈል ፡፡ ስለዚህም ፡ ይህ ፡ ነገር ፡ በግድ ፡ የሚፈለግ ፡ ማምለክ ፡ ሁኖ ፡ አይቈጠር ፡፡ መክንያትም ፡ ማቴዎስ ፡ ፲፭፡ ፫፡ ፱፡ ይገኛል ፡፡ ክርስቶስ ፡ ፈሪሳውያንን ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡፡ ለምን ፡ እላንተ ፡ ትላለፋላችሁ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ወጋችሁ ፡፡ በከንቱ ፡ ያመልኩኛል ፡ የሰውን ፡ ሥርዓት ፡ ትምህርት ፡ ኢያስተማሩ ፡፡ ደግሞም ፡ ሕዝብን ፡ ጸራ ፡ እንዲህም ፡ አለ ፡፡ ስሙ ፡ አስተውሉም ፡፡ ወደፉ ፡ የሚገባ ፡ ሰውን ፡ የሚያረክስ ፡ አይደለም ፡ ካፉ ፡ የሚወጣ ፡ እንጅ ፡፡ ደግሞም ፡ ጳውሎስ ፡ ይላል ፡፡ የእግዚአብሔር ፡ መንግሥት ፡ መብልና ፡ መጠጥ ፡ አይደለም ፡፡ ሮሜ ፡ ፲፬፡ ፲፯፡፡ ደግሞም ፡ በቈሎሳይስ ፡ ፪፡ ፲፯፡፡ ሰው ፡ አይፈረድባችሁ ፡ በመብልና ፡ በመጠጥ ፡ በዓልንም ፡ በመቍጠር ፡ በሰንበትም ፡፡ በ፩፡ ጢሞቴዎስም ፡ ፬፡ ፩፡ ፫፡፡ እንደሁ ፡ ያለ ፡ ትእዛዝ ፡ ሰው ፡ መብልንና ፡ መጋባትን ፡ ቢከለክል ፡

የሰይጣን ፡ ትምህርት ፡ ይባላል ፡ ከወንጌል ፡ ጋራ ፡ ይጸላ
ልና ::

ጸላቶቻችን ፡ ግን ፡ መምህራኖችን ፡ የሥጋውን ፡ ማድከ
ምና ፡ ተግሣጽ ፡ እንዲከለክሉ ፡ ቢሉ ፡ እወነት ፡ አይሉ
ም :: መምህራኖችን ፡ እግዚአብሔር ፡ ለምእምናን ፡ ለመ
ሾከም ፡ ስለ ፡ ሰጣቸው ፡ መስቀል ፡ እርሱም ፡ መከራና ፡ ጭ
ንቀት ፡ ስለሚሆን ፡ ያስተምሩናል ፡ በደስታም ፡ እንድንቀበ
ለው ፡ ይመክሩናል :: እርሱም ፡ በውነት ፡ ተግሣጽ ፡ ነው ፡
ለመድኀኒታችን :: ደግሞም ፡ ይላሉ ፡ ለክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡
እንዲገባ ፡ በሥጋው ፡ ይገዛ ፡ ዘንድ ፡ ስራውን ፡ በማብዛት ፡
በመብልም ፡ ልክ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ለኀጢአት ፡ መክንያት ፡
እንደይሰጥ ፡ ጸጋውን ፡ ለመስራት ፡ ግን ፡ አይደለም :: ይህ ፡
መግዛትና ፡ ሥርዓት ፡ በሥጋ ፡ ላይ ፡ አንደንድ ፡ ቀን ፡ ብቻ ፡
አይሁን ፡ ወትር ፡ እንጅ :: ስለዚህም ፡ ክርስቶስ ፡ ይላል ፡
ሉቃስ ፡ ፳፩፡ ፴፬፡፡ በነፍሳችሁ ፡ ተጠንቀቁ ፡ እንደይከብዲ ፡
ሆደችሁን ፡ በመምላት :: ስለዚህም ፡ ወትሮ ፡ እንጾማለ
ን ፡ ማለት ፡ ልባችነን ፡ አናከብድም ፡ በመብላት ፡ ብዛትና ፡
በስካር ፡ ሥጋችን ፡ ሁለግዜ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለማገልገ
ል ፡ የተሰናደ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ :: የምንጥል ፡ እንኪያ ፡ እ
ርሱ ፡ ጾም ፡ አይደለም ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ሰው ፡ ጾምን ፡ እንደ ፡
ሕግ ፡ ቢያድርገው ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ ጊዜ ፡ ለልዩ ፡ ልዩ ፡ መብል
ም ፡ ሰውን ፡ ለማጽደቅ ፡ የሚቈጠር :: እርሱም ፡ ከወንጌ
ል ፡ ጋራ ፡ ይጻላል ::

በኛ ፡ ዘንድም ፡ ሥርዓት ፡ አለን ፡ ደግሞ :: ደሮ ፡ ከርሱ ፡ ጽ
ድቅን ፡ እንፈልግበትም ፡ ሕግም ፡ አናደርግበትም ፡ ቤተ ፡ ክ
ርስቲያንን ፡ ለመስራት ፡ ብቻ ፡ እንጠብቀዋለን ፡ እንጅ ::

፺፯፡፡ ስለ ፡ ምንኵስና ፡ ስለት ::

ስለ ፡ ምንክስና ፡ ስንናገር ፡ ማሰብ ፡ ይፈልጋል ፡ አስቀድ
ሞ ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ በምንኵስና ፡ በገደሞችም :: በርሱም ፡
እጅግ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ጋራ ፡ የሚጸላ ፡ ነገር ፡ ነበ
ረ :: ባውጉስቲኑስ ፡ ዘመንም ፡ በገደሞች ፡ የገቡ ፡ ሰዎች ፡

እንደ ፡ ፈቃደቸው ፡ ነበረ ፡፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ተግሣጽና ፡ ትምህ ርት ፡ በከፋ ፡ ጊዜ ፡ የገደም ፡ ስለት ፡ ተደረገ ፡ በርሱም ፡ ተ ግሣጽ ፡ ሊመለስ ፡ ነበረ ፡ በግድ ፡ በማሠርያም ፡፡

ከዚህ ፡ ጋራም ፡ ብዙ ፡ ሌላ ፡ ነገር ፡ ተነሣ ፡ ሰዎችም ፡ እን ደ፡ህ ፡ ላለው ፡ ግዞት ፡ የውቀት ፡ ዕድሜያቸው ፡ ሳይደርስ ፡ ለ ምንክስና ፡ ታሠሩ ፡፡ ይህ ፡ ነገርም ፡ በሴቶች ፡ ገደሞች ፡ አ ስጨነቀ ፡ ከወንዶች ፡ ገደሞች ፡ ይልቅ ፡ ለሴቶች ፡ ኀዘን ፡ ሲ ገባቸው ፡ በድካማቸው ፡ መክንያት ፡፡ ይህ ፡ ነገርም ፡ ይህ ፡ ስለት ፡ ማድረግም ፡ ብዙ ፡ ሰዎችን ፡ አስቀድሞ ፡ አሳዘነ ፡ ብዙ ፡ ሰዎችንም ፡ አሰናከለ ፡፡ የምንኵስናም ፡ ስለት ፡ እ ንደ ፡ ጥምቀት ፡ ስለት ፡ ተቈጠረ ፡፡ መነክሶችም ፡ ተስፋ ፡ አ ደረጉበት ፡ ለኃጢአት ፡ ስርየት ፡ ለመጸደቃቸውም ፡ በእግዚ አብሔር ፡ ፊት ፡ ትርፍንም ፡ ያገኙበት ፡ መሰላቸው ፡፡ ምን ኵስናም ፡ ተመሰገነች ፡ ከሌላ ፡ ክርስቲያን ፡ መሆን ፡ ሁሉ ፡ ይልቅ ፡ ከክህነት ፡ ከመፍረድም ፡ ከመንግሥትም ፡ እርሱ ንም ፡ ከሚመስል ፡ ይልቅ ፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ነገርና ፡ ትእዛዝ ፡ ከተደረገ ፡ ሁሉ ፡ ይልቅ ፡፡ ይህም ፡ ሁሉ ፡ ከወን ጌል ፡ የሚበልጥ ፡ ተቈጠረ ፡ ከወንጌልም ፡ ጋራ ፡ ተጻለ ፡፡

አስቀድሞም ፡ ገደሞች ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስና ፡ የሌላ ፡ ዕ ውቀት ፡ ማስተማርያች ፡ ነበሩ ፡ ሊማሩም ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ገደሞች ፡ ሔዱ ፡፡ አሁን ፡ ግን ፡ ይጸድቁ ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ቅዱ ሳንም ፡ ይከብሩ ፡ ዘንድ ፡፡

እንዴት ፡ ግን ፡ ይላሉ ፡ መምህራኖችን ፡፡ ትምርታቸው ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፡፡ ምንኵስናን ፡ ትተው ፡ ወደ ፡ መጋባት ፡ የ ሚገቡ ፡ የብችነት ፡ ስጥወታ ፡ አልተቀበሉምና ፡ በኀ ፡ ያድ ርጋሉ ፡ ሥልጣንና ፡ ትእዛዝም ፡ አላቸው ፡ ምሽትን ፡ ያገ ቡ ፡ ዘንድ ፡፡ የምንኵስናም ፡ ስለት ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ሥ ርዓት ፡ አይሽርም ፡፡ የእግዚአብሔርም ፡ ትእዛዝ ፡ እንደዚህ ፡ ነው ፡፡ ስለ ፡ ምንዝር ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ መሽቱ ፡ ትሁንለት ፡፡ ለሴቲቱም ፡ ሁሉ ፡ ባል ፡ ይሁንላት ፡፡ ፩፡ ቆሮንቶስ ፡ ፯፡ ፪፡፡ እንደዚህም ፡ ይላል ፡ እግዚአብሔር ፡ በኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፡ ፪፡ ፲፰፡፡ መልካም ፡ አይደለም ፡ ሰው ፡ ብቻውን ፡ ይሆን ፡ ዘ ንድ ፡፡ የምትረደውን ፡ እርሱንም ፡ የምትከተል ፡ ባልንጀ

ራ ፡ ልፈጥርለት ፡፡ ይህነን ፡ እግዚአብሔር ፡ ያዘዘውን ፡ ት እዛዝ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በስለቱ ፡ ይሽር ፡ ዘንድ ፡ አይችልም ፡፡ እግዚአብሔር ፡ አንድ ፡ ሥጋ ፡ ይሆኑ ፡ ዘንድ ፡ ያደረጋቸው ፡ ወንድና ፡ ሴት ፡ ሰው ፡ ይለያቸው ፡ ዘንድ ፡ ወይስ ፡ አንድነ ታቸውን ፡ ይከለክል ፡ ዘንድ ፡ ቢወድ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፈቃድና ፡ ሥርዓት ፡ መከልከል ፡ ይፈልጋል ፡፡

ከዚህም ፡ በቀር ፡ አንድ ፡ ታላቅ ፡ መክንያት ፡ አለን ፡ የ ምንኩስና ፡ ስለት ፡ የሚፈታበት ፡ እርሱም ፡ ይህ ፡ ነው ፡፡ የእግዚአብሔር ፡ ሥርዓት ፡ ስለ ፡ ዘላለም ፡ መድኃኒታች ን ፡ የተሰራ ፡ እንደይፈርስ ፡ ሰው ፡ በሰራው ፡ በቅድስና ፡ መ ልክ ፡ እንደ ፡ ምንኩስና ፡፡ የእግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ለወትሮ ፡ ለዘላለም ፡ ፈጽምትን ፡ ጽድቅና ፡ መድኃ ኒት ፡ ሰራልነ ፡ ሰው ፡ በሃይማኖት ፡ ብቻ ፡ የሚቀበለው ፡ ቢ ያምን ፡ እግዚአብሔር ፡ በልጁ ፡ መክንያት ፡ በጸጋ ፡ ልጆቹ ፡ እንሆን ፡ ዘንድ ፡ እንዲቀበልን ፡፡ አሁንስ ፡ ሞነክሶች ፡ በም ንኩስናቸው ፡ የመላእክትም ፡ ማምለክ ፡ የሚመስል ፡ ማ ምለካቸው ፡ እንዲጸደቁ ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ጸጋ ፡ እን ዲያገኙ ፡ ይመስላቸዋል ፡፡ ይህ ፡ ግን ፡ ምንድር ፡ ነው ፡ የክ ርስቶስን ፡ ምስጋና ፡ ማሳነስ ፡ እንጅ ፡ የጸጋውንም ፡ ዋጋ ፡ የሃይማኖትንም ፡ ጽድቅ ፡ መካድ ፡፡

ከዚህ ፡ ይገለጻል ፡ እንደይህ ፡ ያለ ፡ ስለት ፡ የማይገባ ፡ ሐ ሰውትም ፡ ማምለክ ፡ እንዲሆን ፡ እግዚአብሔርንም ፡ እ ንዲያሳዝን ፡ ሰውም ፡ ለመጠበቀው ፡ እንዳይታሠር ፡፡

፳፰፡ ስለ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ሥልጣን ፡፡

ስለ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ሥልጣን ፡ አስቀድሞ ፡ እጅግ ፡ ተጻ ፈ ፡ ብዙ ፡ ጻፎችም ፡ የኤጲስቆጶሳትን ፡ ሥልጣን ፡ ካለ ም ፡ ኃይል ፡ ጋራ ፡ ይበለቁ ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ያለም ፡ ጋዦች ፡ እስኪሆኑ ፡ ድረስ ፡፡ ከዚህም ፡ መደብለቅ ፡ እጅግ ፡ ሁከት ና ፡ መናወጽ ፡ ተነሣ ፡፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ክርስቶስ ፡ የሰጣቸ ውን ፡ ሥልጣን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ለመስራት ፡ አላደረ ጉም ፡ ራሳቸውን ፡ ለማክበር ፡ እንጅ ፡ የሰውን ፡ ልብ ፡ ሲ

ያኮብደ : ከክርስቶስ : ትእዛዝ : ጋራ : በሚጸላ : ትእዛዛ
ቸው :: ቁሣርችንና : ነገሥታትንም : እንኳ : እንደ : ፈቃደ
ቸው : ይሾሙ : ይሽሩም : ዘንድ : ሲደፍሩ :: ይህንንም :
ድፍረታቸው : ብዙ : ደህናች : መምህራን : በየጊዜያቸ
ው : ጸየፉት : እርሳቸው : ግን : አልሰሙም :: ስለዚህም :
መምህራናችን : እግዚአብሔርን : ለማክበር : የሰውንም :
ልብ : ለማጽናናት : አሁን : ተገደ : የመንፈሳዊንና : የሥጋ
ዊን : ነገር : ሥልጣን : ይለዩ : ዘንድ : ሲያስተምሩ : ለሁለ
ታቸው : ኢየብቻቸው : ስለ : እግዚአብሔር : ትእዛዝ : ከ
ለልብ : ማክበር : እንደገባቸው : ከሁሉ : እንዲበልጥ : እ
ንደ : እግዚአብሔር : ስጦታ : በምድር : ላይ ::

እንደህም : ነው : የመምህራናችን : ትምርት :: የመክ
ፈቻ : ሥልጣን : እርሱም : የኤጲስቆጶሳት : ሥልጣን : ወ
ንጌል : እንደለ : ከእግዚአብሔር : የተሰጠ : ሥልጣንና :
ትእዛዝ : ነው : ወንጌልን : ለመስበክ : የኃጢአትን : ስርየ
ት : እግዚአብሔር : ለሁሉ : መስጠት : የሚወደው : ለመ
ግለጽ : ምሥጢራትንም : ለመክፈል :: ክርስቶስ : ሐዋርያ
ቱን : እንደህ : ብልዋልና : ዮሐንስ : ፳፡ ፳፩። ሰላም : ለላን
ት : ይሁን :: አብ : እንደ : ላከኝ : እንደሁም : እኔ : እልካ
ችኋለሁ :: ይህንም : ብሎ : እፍ : አለባቸው : አላቸው
ም :: መንፈስ : ቅዱስን : ተቀበሉ :: ኃጢአቱንም : የምት
ተውለት : ቀረችለት : የምትይዙበትም : ተያዘችበት :: ይ
ህ : ሥልጣን : ሰማይን : መክፈትና : መዝጋት : ግን : ሌላ :
የለም : የእግዚአብሔር : ቃል : ማስተማርና : መስበክ : እ
ንጅ : ምሥጢራትንም : ማገልገል :: በርሱም : ሥጋዊ : ገ
ንዘብ : አይሰጥበትምና : ነገር : ግን : መንፈሳዊ : የዘላለ
ም : ጽድቅ : መንፈስ : ቅዱስም : የዘላለምም : ሕይወት ::
ደህ : ገንዘብ : አይገኝምም : በመስበክ : ቍመት : እንጅ ::
በምሥጢራትም : ቅዱስ : ጳውሎስ : እንደል :: ወንጌል :
የእግዚአብሔር : ኃይል : እንዲሆን : የሚያምኑትን : ሁሉ
ን : ያድን : ዘንድ :: ሮሜ : ፩፡ ፲፮። ደህ : የኤጲስቆጶሳት :
የቤት : ክርስቲያንም : ሥልጣን : ሁኖ : ያለምን : ሥልጣ
ን : የመኰንንንም : መግዛት : ከቶ : አይከለክልም :: የመ

ኰንን ፡ ሹመት ፡ ልዩ ፡ ነውና ፡ የወንጌልም ፡ ሹመት ፡ ል
ዩ ፡ ነው ። እሊህ ፡ ፪ም ፡ ኢየብቻቸው ፡ ደኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ይ
ገባል ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ፡ ል ። መንግሥቴ ፡ የዚህ ፡ ዓለም ፡ አ
ይደለችም ። የዮሐንስ ፡ ወንጌል ፡ ፲፰፡ ፴፮። ሉቃስ ፡ ፲፪፡
፲፬። ፊልጵስዩስ ፡ ፫፡ ፳። ፪፡ ቆሮንቶስ ፡ ፲፡ ፬።

ስለዚህም ፡ መምህራኖችን ፡ እሊህን ፡ ፪፡ የቤተ ፡ ክርስ
ቲያንን ፡ ሹመትና ፡ የመንግሥትን ፡ ሹመት ፡ ይለያሉ ፡ ያ
ስከብርዋቸውማሉ ። ለኤጲስቆጶሳት ፡ ግን ፡ ያለም ፡ ሹ
መት ፡ ደግሞ ፡ ቢጨመርላቸው ፡ ይህ ፡ መጨመርያ ፡ ከእግ
ዚአብሔር ፡ ሥልጣን ፡ አይደለም ፡ ከነገሥታት ፡ እንጂ ፡
ለወንጌል ፡ ሹመታቸውም ፡ ከቶ ፡ አይደርስም ።

የኤጲስቆጶሳትና ፡ የቀሳውስት ፡ ሹመት ፡ በእግዚአብ
ሔር ፡ ትእዛዝ ፡ ይህ ፡ ነው ፡ ወንጌልን ፡ መስበክ ፡ የኀጢአ
ትንም ፡ ስርየት ፡ መግለጽ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ላይ ፡ የሚሰ
ሩትን ፡ ከጉባኤ ፡ መቍረጥ ፡ ባለም ፡ ኃይልም ፡ አይደለ
ም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንጂ ። እንዲሁም ፡ ለማድ
ረጋቸው ፡ ክርስቶስ ፡ እንዳዘዘ ፡ ቢያደርጉ ፡ መታዘዝ ፡ ይ
ገባላቸዋል ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሉቃስ ፡ ፲፡ ፲፮። ያለ ፡ ክ
ርስቶስ ፡ ትእዛዝ ፡ ግን ፡ አንዳችን ፡ ቢያዙ ፡ መታዘዝ ፡ ኃ
ጢአት ፡ ይሆናል ። ማቴዎስ ፡ ፯፡ ፲፰። ገላትያን ፡ ፩፡ ፰። ፪፡
ቆሮንቶስ ፡ ፲፫፡ ፰፡ ፲።

እንጂግ ፡ ክርክርም ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ ማምለክ ፡ ኤጲስቆጶሳ
ት ፡ ሥልጣን ፡ እንዳላቸው ፡ በማምለክ ፡ የሚወደትን ፡
ይለውጡ ፡ ወይስ ፡ ይጨምሩ ፡ ዘንድ ፡ ወይስ ፡ ይቍርጡ ፡ ዘ
ንድ ፡ ሥልጣን ፡ እንዳላቸው ፡ ወይስ ፡ አይደለም ። መም
ህራኖችንም ፡ እንዲህ ፡ ይላሉ ። ሰው ፡ ሁሉ ፡ ሥልጣን ፡ እ
ንደ ፡ ሌለው ፡ አንዳችን ፡ ለማድረግ ፡ ወይስ ፡ ለማዘዝ ፡ የ
እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ የሚከለክል ። ወይስ ፡ እግዚአብሔ
ር ፡ የከለከለውን ፡ ነገር ፡ ያዙ ፡ ዘንድ ፡ ለመድኃኒታችን ፡
እንደ ፡ ሚገባው ። የሐዋርያት ፡ ስራ ፡ ፲፰፡ ፲። ፪፡ ቆሮንቶስ ፡
፲፫፡ ፲። ይህነን ፡ ግን ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ ባይጠብቁ ፡ ወንጌል ፡
ይጐዳል ፡ ኃጢአትም ፡ ይበዛል ።

የቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ማምለክ ፡ ሁሉ ፡ እግዚአብሔር

ን ፡ ለማመስገን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንንም ፡ ልብ ፡ ለመስራት ፡ ነውና ፡ ሥርዓት ፡ ይፈለግለታል ፡ ይህ ፡ ምስጋና ፡ ይህም ፡ መስራት ፡ እንደ ፡ ይከለከል ። በዚህም ፡ ይገለጻል ፡ ኤጲስቆጶሳት ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ጌቶች ፡ እንደ ፡ ይደሉ ፡ ወይስ ፡ ምእምናን ፡ የርሳቸው ፡ ባሮች ። አንድ ፡ ጌታ ፡ ነውና ፡ እርሱም ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በደሙ ፡ የተበዛነ ፡ ከባርነት ፡ ሁሉ ፡ እርሱም ፡ ሁላችንን ፡ ይልናል ። አላንት ፡ በታላቅ ፡ ዋጋ ፡ ተገዛችሁ ፡ ለሰው ፡ ባሮች ፡ አትሁኑ ። ደሮ ፡ ኤጲስቆጶሳትና ፡ ቀሳውስት ፡ ዲያቆናትም ፡ የወንድሞቻቸው ፡ የደስታቸው ፡ ረ፯ች ፡ ናቸው ።

ቅዱስ ፡ ጴጥሮስም ፡ ኤጲስቆጶሳትን ፡ ይከለክላል ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ላይ ፡ እንደ ፡ ይገዙ ፡ እርስዋ ፡ የክርስቶስ ፡ መንጋ ፡ የምትሆን ፡ ይጠብቅዋት ፡ ዘንድ ፡ ለደህንነታቸው ፡ ያዘቸዋል ፡ እን፯ ። ፩፡ ጴጥሮስ ፡ ፫፡ ፲።

እኛም ፡ አሁን ፡ ሥልጣናታቸውን ፡ እንሽር ፡ ዘንድ ፡ አንሻም ፡ እንለምናቸዋለን ፡ እን፯ ፡ የሰውን ፡ ልብ ፡ ለኃጢአት ፡ እንደ ፡ ያገዱ ። ይህነን ፡ ግን ፡ ትተው ፡ ልመናችንን ፡ ቢንቁ ፡ ከኩነኔ ፡ ይፍሩ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቢቋጠርባቸው ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መክንያት ፡ እንደ ፡ ሰጡ ፡ ለመለየት ፡ እርሳቸው ፡ ሊከለክሉት ፡ የነበሩ ።

እሌህን ፡ ፳፰፡ ቃላት ፡ ጻፍነ ፡ ሃይማኖታችንን ፡ ትምህርታችንንም ፡ እንገልጽባቸው ፡ ዘንድ ። ማንም ፡ በዚህ ፡ የሚጠራጠር ፡ ቢገኝ ፡ መጨመርያውንም ፡ ትምርት ፡ የሚፈልግ ፡ ከለልባችን ፡ እሺ ፡ እንላለን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እናስተምረው ፡ ዘንድ ።

እኛ ፡ የጌታችን ፡ የቄሣር ፡ ሎላልት ፡
የዮሐንስ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ምህረት ፡
የሰክሰን ፡ ጋዢ ፡ መሪጭ ።
ጌዎርጊስ ፡ የብረንደንቡርግ ፡ ጋዢ ።

ኤርንስት ፡ የሊነቡርግ ፡ ጋዢ ፡፡
ፊልጶስ ፡ የሀስን ፡ ጋዢ ፡፡
ዮሐንስ ፡ ፍሪድሪኽ ፡ የሰክስን ፡ ሀርጾግ ፡፡
ፍራንሲስኩስ ፡ የሊነቡርግ ፡ ሀርጾግ ፡፡
ቮልፍገንግ ፡ የኣንሀልት ፡ ጋዢ ፡፡
አልብረኽት ፡ የመንስፈልድ ፡ ግራፍ ፡፡
የኒርንበርግ ፡ ከተማ ፡ መለክተኞች ፡፡
የሬውትሊንግን ፡ ከተማ ፡፡

ይህች ፡ የጵሮተስታንቶች ፡ ትምህርት ፡ ናት ፡ በወንጌል ፡ እንደ ፡ ተመሠረተች ፡ እንደ ፡ ተመሰከረችበትም ፡፡ የንምሳ ፡ ቄሣር ፡ ካርል ፡ ፭፤ ግን ፡ አልተቀበላትም ፡ ለመንግሥቱ ፡ ሁሉ ፡፡ ስለዚህም ፡ ብዙ ፡ ጋዦች ፡ ከምድራቸው ፡ ጋራ ፡ ከሮም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወጡ ፡፡

የሮም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ሲኖደስን ፡ ሰበሰበች ፡ በትሪኤንት ፡ ከጳጳስ ፡ በታች ፡ ካመተ ፡ ፲፭፻፵፭፤ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፲፭፻፷፫፤ ድረስ ፡፡ በዚች ፡ ሲኖደስም ፡ የሮም ፡ ጸላትነት ፡ ጸናች ፡ በጵሮተስታንቶች ፡ ላይ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ የነበረውንም ፡ ትምርታቸውን ፡ ወገዙ ፡፡ እንደዚህም ፡ መለየት ፡ ሆነ ፡ በሮም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያንና ፡ በጵሮተስታንቶች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መካከል ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡፡

ሉተርም ፡ ባመት ፡ ፲፭፻፵፮፤ ሞተ ፡ ነፍሱን ፡ አደራ ፡ ሰጥቶ ፡ በእግዚአብሔር ፡ እጅ ፡፡ የወንጌል ፡ ትምርት ፡ ግን ፡ ከጨለማ ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ እንደ ፡ ወጣች ፡ በርሱና ፡ በወደጆቹ ፡ በንምሳ ፡ መንግሥት ፡ ወደ ፡ ሌላ ፡ አገርም ፡ ወጣች ፡፡

በሄልዌትያም ፡ ጽዊንግሊ ፡ ሞተ ፡ ባመት ፡ ፲፭፻፴፩፤ እርሱም ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ዮሐንስ ፡ ካልቢኑስ ፡ ተነሣ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስና ፡ በኃይል ፡ የተጀመረውን ፡ ስራ ፡ በሄልዌትያ ፡ አድርጎ ፡ ከፋሬልና ፡ ከቤዛ ፡ ጋራ ፡፡ ብርሃናቸውም ፡ ወደ ፡ ሩቅ ፡ አገር ፡ አበራ ፡፡

በእንግልጣርም ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መታደስ ፡ ከንጉሥ ፡ ከሀንሪ ፡ ፰፡ በታች ፡ ጀመረ ፡ ባመት ፡ ፲፭፳፯፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ በተተረጐመ ፡ ጊዜ ፡ በቲንደልና ፡ በፍሪስ ፡፡ ቲንደልም ፡ በወንጌል ፡ካስተማረ ፡ በኋላ ፡ ባመት ፡ ፲፭፴፮፡ ተይዞ ፡ ተነደደ ፡፡ ባመትም ፡ ፲፭፴፬፡ ንጉሥ ፡ የሮም ፡ ጳጳስን ፡ መግዛት ፡ በመንግሥቱ ፡ ሻረ ፡፡ ሰዎቹንም ፡ ሁሉን ፡ አዘዘ ፡ ለጳጳስ ፡ ሥልጣን ፡ በሌላ ፡ አገርም ፡ ላለው ፡ ሥልጣን ፡ ሁሉ ፡ እንዳይታዘዙ ፡ ለርሱ ፡ ለንጉሥ ፡ ሥልጣን ፡ እንጂ ፡ እርሱም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ የመንግሥቱ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያኑም ፡ አለቃ ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡፡ ሀንሪ ፡ ግን ፡ ባንዳንድ ፡ ነገር ፡ የወንጌልን ፡ ነገር ፡ ካለም ፡ ነገር ፡ ጋሪ ፡ ደብልቆ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መሻት ፡ አልተፈጸመበትም ፡፡ ክረንመር ፡ ሪድሌም ፡ ለቲመርም ፡ ክሮምወልም ፡ ሌሎችም ፡ ለወንጌል ፡ በኃይላቸው ፡ አገለገሉ ፡፡

በሀንሪ ፡ ፰ም ፡ ልጅ ፡ በኤድወርድ ፡ ፮፡ ዘመን ፡ የወንጌል ፡ ትምርት ፡ አደገች ፡ ጸናችም ፡፡ እርሱ ፡ ግን ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ እቱ ፡ ማርያም ፡ ተከተለቸው ፡ በመንግሥት ፡፡ እርስዋም ፡ የወንጌል ፡ ጸላት ፡ ሁና ፡ ጽሩ ፡ ትምህርቱን ፡ በግድ ፡ ትሽረው ፡ ዘንድ ፡ ፈለገች ፡፡ ስለዚህም ፡ ብዙ ፡ ደህና ፡ መምህራን ፡ ስለ ፡ ወንጌል ፡ በሳት ፡ በንጬትም ፡ በሰይፍም ፡ በግዞትም ፡ሞቱ ፡፡ ብዙም ፡ካገራቸው ፡ ተሳደው ፡ ወደ ፡ ንምሳ ፡ ወደ ፡ ሄልቬትያም ፡ ሸሹ ፡፡ ይህችም ፡ ስደት ፡ ካመት ፡ ፲፭፶፫፡ እስከ ፡ ፲፭፶፰፡ ድረስ ፡ ነበረች ፡፡

ማርያምም ፡ ባመት ፡ ፲፭፶፰፡ በሞተች ፡ ጊዜ ፡ እትዋ ፡ ኤልሳቤጥ ፡ ነገሠች ፡፡ እርስዋም ፡ የወንጌል ፡ ወዳጅ ፡ ሁና ፡ ለወንጌል ፡ ትምህርት ፡ በመንግሥትዋ ፡ ሁሉ ፡ መግዛት ፡ ሰጠቸው ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ማምለክ ፡ በወንጌል ፡ ያቅኑት ፡ ዘንድ ፡ አዘዘች ፡፡ ይህም ፡ ባመት ፡ ፲፭፷፪፡ ሆነ ፡፡ የዚያን ፡ ጊዜም ፡ እሌህ ፡ ፴፱፡ ቃላት ፡ ተጻፉ ፡ የንግልጣር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ የሚናገሩ ፡፡

የእንግሊዝ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሃይማኖት ዋ ፡ ትምህርት ፡ በ፴፱፡ ቃላት ፡ ይህች ፡ ናት ፡፡

፩፡፡ ስለ ፡ ቅድስት ፡ ሥላሴ ፡፡

አንድ ፡ ሕያውና ፡ እውነተኛ ፡ አምላክ ፡ ብቻ ፡ አለ ፡፡ እርሱም ፡ ለዘላለም ፡ የሚኖር ፡፡ ሥጋም ፡ ክፍልም ፡ ሕማማትም ፡ የሌለው ፡፡ ኃይሉም ፡ ጥበቡም ፡ ቸርነቱም ፡ ያልተወሰነ ፡፡ የሚታይም ፡ የማይታይም ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ፈጣሪና ፡ ጠባቂ ፡፡ በዚች ፡ መለኮትም ፡ አንድነት ፡ ሦስት ፡ አካላት ፡ አሉ ፡፡ እርሳቸውም ፡ አብ ፡ ወልድም ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስም ፡፡

፪፡፡ ስለ ፡ ቃል ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ልጅ ፡ እርሱም ፡ እውነተኛ ፡ ሰው ፡ የሆነ ፡፡

ልጅ ፡ የአብ ፡ ቃል ፡ የሚሆን ፡ ከአብም ፡ ከዘላለም ፡ የተወለደ ፡፡ እርሱም ፡ እውነተኛ ፡ የዘላለምም ፡ አምላክ ፡፡ ከአብም ፡ ጋራ ፡ ያንድ ፡ ባሕሪ ፡ ሁኖ ፡ በተመሰገነች ፡ ድንግል ፡ በማኅፀንዋ ፡ ሲሆን ፡ ከባሕሪዋ ፡ የሰውን ፡ ጠባይዕ ፡ ተቀበለ ፡፡ እንደሁም ፡ ሁለት ፡ ምሉኣንና ፡ ፍጹማን ፡ ጠባያት ፡ እርሳቸውም ፡ መለኮትና ፡ ሰውነት ፡ ባንድ ፡ አካል ፡ ተዋሀዱ ፡ ከቶ ፡ የማይለዩ ፡፡ አንድ ፡ ክርስቶስ ፡ የሆነ ፡፡ እርሱም ፡ እውነተኛ ፡ አምላክ ፡ እውነተኛም ፡ ሰው ፡ ነው ፡፡ እርሱም ፡ በውነት ፡ መከራ ፡ ተቀበለ ፡፡ ተሰቀለም ፡፡ ሞተም ፡፡ ተቀበረም ፡፡ አባቱን ፡ ያስታርቅልን ፡ ዘንድ ፡፡ መሥዋዕትም ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ሚወረስ ፡ ዕዳችን ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ሚያደርገውም ፡ ኃጢአት ፡ ሁሉ ፡ እንጂ ፡፡

፫፡፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ መውረድ ፡ ወደ ፡ ሲዖል ፡፡

ክርስቶስ ፡ ስለኛ ፡ እንደ ፡ ሞተ ፡ እንደ ፡ ተቀበረም ፡ እንደሁም ፡ ወደ ፡ ሲዖል ፡ እንደ ፡ ወረደ ፡ እናምናለን ፡፡

፬፡፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ትንሣኤ ፡፡

ክርስቶስ ፡ በውነት ፡ ከሞት ፡ ተነሣ ፡፡ ተመልሶም ፡ ገላ
ውን ፡ ካፅንት ፡ ለሰው ፡ ጠባይዕም ፡ ፍጻሜ ፡ ከሚገባ ፡ ነገ
ር ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ፡ ወሰደ ፡ እንደሁም ፡ ወደ ፡ ሰማይ ፡ ወጣ ፡፡
ከዚያም ፡ ይቀመጣል ፡ በሰው ፡ ሁሉ ፡ ይፈርድ ፡ ዘንድ ፡ እ
ስኪመለስ ፡ ድረስ ፡ በኋለኛ ፡ ቀን ፡፡

፭፡፡ ስለ ፡ መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡፡

መንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ከአብ ፡ የሚወጣ ፡ ያንድ ፡ ባሕሪ ፡ ም
ስጋናም ፡ ክብርም ፡ ነው ፡ ከአብና ፡ ከልጅ ፡ ጋራ ፡ እውነተ
ኛም ፡ የዘላለምም ፡ አምላክ ፡፡

፮፡፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ለመድኃኒታችን ፡ ይበቃል ፡፡

ለመድኃኒታችን ፡ የሚገባ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ በመጽሐፍ ፡ ቅ
ዱስ ፡ ይገኛል ፡፡ ስለዚህም ፡ በርሱ ፡ ያልተገኘ ፡ ወይስ ፡ እ
ውነቱ ፡ ከርሱ ፡ የማይገለጽ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ሃይማኖ
ት ፡ ነገር ፡ አንቀበለውም ፡፡ ለዘላለም ፡ መድኃኒትም ፡ አ
ይፈለግም ፡፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ግን ፡ የምንላቸው ፡ መ
ጻሕፍት ፡ እልያ ፡ መጻሕፍት ፡ ናቸው ፡ የቃኖን ፡ የሚሉ
ት ፡ የብሉይና ፡ ያዲስ ፡ ኪዳን ፡ መጻሕፍት ፡ በሥልጣናቸ
ው ፡ ከቶ ፡ ያልተጠራጠሩ ፡

የቃኖንም ፡ መጻሕፍት ፡ ስምና ፡ ቍጥር ፡ ይህ ፡ ነው ፡፡

፩፤ የብሉይ ፡ ኪዳን ፡ መጻሕፍት ፡፡

፩፤ ኦሪት ፡ ዘፍጥረት ፡፡
፪፤ ኦሪት ፡ ዘፀአት ፡፡
፫፤ ኦሪት ፡ ዘሌዋውያን ፡፡
፬፤ ኦሪት ፡ ዘኍልቍ ፡፡
፭፤ ኦሪት ፡ ዘዳግም ፡፡
፮፤ መጽሐፈ ፡ ኢያሱ ፡ ወልደ ፡ ነዌ ፡፡
፯፤ መጽሐፈ ፡ መሳፍንት ፡፡

፰፡ መጽሐፈ ፡ ሩት ።
፱፡ መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ቀዳማዊ ።
፲፡ መጽሐፈ ፡ ሳሙኤል ፡ ካልእ ።
፲፩፡ መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ቀዳማዊ ።
፲፪፡ መጽሐፈ ፡ ነገሥት ፡ ካልእ ፡
፲፫፡ መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ቀዳማዊ ።
፲፬፡ መጽሐፈ ፡ ዜና ፡ መዋዕል ፡ ካልእ ።
፲፭፡ መጽሐፈ ፡ ዕዝራ ።
፲፮፡ መጽሐፈ ፡ ነህምያ ።
፲፯፡ መጽሐፈ ፡ አስቴር ።
፲፰፡ መጽሐፈ ፡ ኢዮብ ።
፲፱፡ መጽሐፈ ፡ መዝሙራት ፡ ዘዳዊት ።
፳፡ መጽሐፈ ፡ ምሳሌ ።
፳፩፡ መጽሐፈ ፡ መክብብ ።
፳፪፡ መጽሐፈ ፡ መኃልየ ፡ መኃልይ ።
፳፫፡ ትንቢተ ፡ ኢሳይያስ ።
፳፬፡ ትንቢተ ፡ ኤርምያስ ።
፳፭፡ ሰቆቃወ ፡ ኤርምያስ ።
፳፮፡ ትንቢተ ፡ ሕዝቅኤል ።
፳፯፡ ትንቢተ ፡ ዳንኤል ።
፳፰፡ ትንቢተ ፡ ሆሴዕ ።
፳፱፡ ትንቢተ ፡ ኢዮኤል ።
፴፡ ትንቢተ ፡ ዓሞጽ ።
፴፩፡ ትንቢተ ፡ ኦብድያ ።
፴፪፡ ትንቢተ ፡ ዮና ።
፴፫፡ ትንቢተ ፡ ሚክያስ ።
፴፬፡ ትንቢተ ፡ ናሆም ።
፴፭፡ ትንቢተ ፡ አንባቆም ።
፴፮፡ ትንቢተ ፡ ሰፎንያስ ።
፴፯፡ ትንቢተ ፡ ሐጌ ።
፴፰፡ ትንቢተ ፡ ዘካርያስ ።
፴፱፡ ትንቢተ ፡ መልክያስ ።

፪፡ ያዲስ ፡ ኪዳን ፡ መጻሕፍት ፡፡

፩፡ የማቴዎስ ፡ ወንጌል ፡፡
፪፡ የማርቆስ ፡ ወንጌል ፡፡
፫፡ የሉቃስ ፡ ወንጌል ፡፡
፬፡ የዮሐንስ ፡ ወንጌል ፡፡
፭፡ የሐዋርያት ፡ ስራ ፡፡
፮፡ የጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ ሮሜ ፡ ሰዎች ፡፡
፯፡ የጳውሎስ ፡ መጀመርያ ፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ ቆርንቶስ ፡ ሰዎች ፡፡
፰፡ የጳውሎስ ፡ ሁለተኛ ፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ ቆርንቶስ ፡ ሰዎች ፡፡
፱፡ የጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ ገላትያን ፡ ሰዎች ፡፡
፲፡ የጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ ኤፌሶን ፡ ሰዎች ፡፡
፲፩፡ የጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ ፊልጵስዩስ ፡ ሰዎች ፡፡
፲፪፡ የጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ ቆለሳይስ ፡ ሰዎች ፡፡
፲፫፡ የጳውሎስ ፡ መጀመርያ ፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ ተሰሎኒቄ ፡ ሰዎች ፡፡
፲፬፡ የጳውሎስ ፡ ሁለተኛ ፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ ተሰሎኒቄ ፡ ሰዎች ፡፡
፲፭፡ የጳውሎስ ፡ መጀመርያ ፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ ጢሞቴዎስ ፡፡
፲፮፡ የጳውሎስ ፡ ሁለተኛ ፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ ጢሞቴዎስ ፡፡
፲፯፡ የጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ ቲቶስ ፡፡
፲፰፡ የጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ ፊልሞን ፡፡
፲፱፡ የጳውሎስ ፡ መልእክት ፡ ወደ ፡ ዕብራውያን ፡፡
፳፡ የያዕቆብ ፡ ከቶሊካዊት ፡ መልእክት ፡፡
፳፩፡ የጴጥሮስ ፡ መጀመርያ ፡ መልእክት ፡ ከቶሊካዊት ፡፡
፳፪፡ የጴጥሮስ ፡ ሁለተኛ ፡ መልእክት ፡ ከቶሊካዊት ፡፡
፳፫፡ የዮሐንስ ፡ መጀመርያ ፡ መልእክት ፡ ከቶሊካዊት ፡፡
፳፬፡ የዮሐንስ ፡ ሁለተኛ ፡ መልእክት ፡፡
፳፭፡ የዮሐንስ ፡ ሶስተኛ ፡ መልእክት ፡፡

፳፮፤ የይሁዳ ፡ መልእክት ፡ ከቶሊካዊት ::
፳፯፤ የዮሐንስ ፡ ራእይ ::
አጶክርፋውያን ፡ ወይስ ፡ የተሰወሩ ፡ መጻሕፍት ፡ የሚል ዋቸው ፡ እንደ ፡ ቃኖን ፡ መጻሕፍት ፡ አንቀበልዋቸውም ::

፯፡፡ ስለ ፡ ብሉይ ፡ ኪዳን ::

የብሉይ ፡ ኪዳን ፡ ካዲስ ፡ ጋራ ፡ አይጻላም :: በሁለታቸው ፡ በብሉይና ፡ ባዲስ ፡ የዘላለም ፡ ሕይወት ፡ ለሰው ፡ ለ መቀበል ፡ ተሰጥታለችና ፡ በክርስቶስ ፡ እርሱ ፡ ብቻውን ፡ መኻከለኛ ፡ የሚሆን ፡ በእግዚአብሔርና ፡ በሰው ፡ መኻከ ል ፡ እውነተኛ ፡ አምላክና ፡ ሰው ፡ ሁንዋልና :: ስለዚህ ፡ ያ ባቶች ፡ አለቆች ፡ ስለሚያልፍ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ተስፋ ፡ እንደ ደረጉ ፡ የሚሉትን ፡ ሰዎች ፡ አንሰማም ::

ከእግዚአብሔርስ ፡ በሙሴ ፡ የተሰጠች ፡ የሌዋውያን ፡ ሕግ ፡ ስለ ፡ ምድራዊ ፡ ማምለክ ፡ ባዘዘች ፡ ነገር ፡ ክርስቲያ ንን ፡ ሰዎች ፡ በውነት ፡ አትገዛም :: ያገርም ፡ ትእዛዛት ዋ ፡ በመንግሥት ፡ ሁሉ ፡ በግድ ፡ መቀበል ፡ ከቶ ፡ አይገባ ም :: ይህ ፡ ግን ፡ ሳይቀር ፡ የሰውን ፡ ፈቃድ ፡ በእግዚአብሔ ር ፡ ለሚገዙ ፡ ትእዛዛት ፡ ከመታዘዝ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከቶ ፡ አልተፈታም ::

፰፡፡ ስለ ፡ ሦስት ፡ የሃይማኖት ፡ ምሳሎች ፡ ወይስ ፡ ስምቦሎች ::

እሊያ ፡ ፫፤ የሃይማኖት ፡ ምሳሎች :: የኒቅያ ፡ ምሳሌ :: ያታናስዮስም ፡ ምሳሌ :: የሐዋርያትም ፡ ምሳሌ ፡ እንቀበ ላለን ፡ እናምንባቸውማለን ፡ እውነታቸው ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ይገለጻልና ::

፱፤ ስለ ፡ ሚወረስ ፡ ኃጢአት ::

የሚወረስ ፡ ኃጢአት ፡ እርሱ ፡ አደምን ፡ መከተል ፡ አይደ

ለም ፡ የጸላግዩስ ፡ ወገን ፡ በክንቱ ፡ እንደ ፡ ተጫወቱ ። እርሱ ፡ የሰው ፡ ሁሉ ፡ የጠባዩ ፡ የባሕርዩም ፡ ጉድለና ፡ ጥፋት ፡ እንጀ ፡ በልደቱ ፡ ካደም ፡ የተቀበለው ። በዚህ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ከመጀመርያ ፡ ጽድቅ ፡ እጅግ ፡ ራቀ ፡ በሰውነቱም ፡ ለክፋ ፡ ይዘነብላል ። ሥጋው ፡ ሁለግዜ ፡ ተመኝትዋልና ፡ በመንፈስ ፡ ላይ ። በመክንያቱም ፡ ወደዚህ ፡ ዓለም ፡ ለሚወለድ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቍጣ ፡ የዘላለምም ፡ ኵነኔ ፡ ይገባዋል ። ይህም ፡ የሰውነታችን ፡ ሕማም ፡ ሁለተኛም ፡ በተወለዱ ፡ ሰዎች ፡ እንኳ ፡ ይቀራል ፡ በርሱም ፡ ይሆናል ፡ በዮናኒ ፡ ቋንቋ ፡ ፍሮኔማ ፡ ሰርቀስ ፡ *φρόνημα σαρκὸς* የተባለ ፡ ሥጋዊ ፡ ልብ ፡ እርሱም ፡ ሥጋዊ ፡ ማሰብ ፡ መመኛትም ፡ ፈቃድም ፡ የሚሆን ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ሕግ ፡ እንደይገዛ ። በክርስቶስስ ፡ በውነት ፡ በሚያምኑ ፡ ፍርድና ፡ ኵነኔ ፡ የለባቸውም ። ይህ ፡ ግን ፡ ሳይቀር ፡ ሐዋርያ ፡ ደግሞ ፡ የምኞ ፡ መናፈቅና ፡ መመኛት ፡ እንዲያው ፡ የኀጢአት ፡ ወገን ፡ እንዲሆን ፡ ያስታውቀናል ።

፲፤ ስለ ፡ አርነት ፡ ፈቃድ ።

የሰው ፡ መሆን ፡ ከአደም ፡ ኃጢአት ፡ በኋላ ፡ እንዴህ ፡ ነው ፡ በሰውነቱ ፡ ኃይል ፡ በበጎ ፡ ስራውም ፡ እንደይችል ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይመለስ ፡ ዘንድ ፡ ነፍሱንም ፡ ለሃይማኖት ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ለመጽራት ፡ ያዘጋጅ ፡ ዘንድ ። ስለዚህም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ በክርስቶስ ፡ በጎ ፡ ፈቃድን ፡ በልባችን ፡ ሰርቶት ፡ ሳይቀድምልን ፡ ይህነንም ፡ በጎ ፡ ፈቃድን ፡ ካገኘነ ፡ በኋላ ፡ ሳይረደን ፡ ለኛ ፡ ኃይል ፡ የለነም ፡ በጎን ፡ እግዚአብሔርንም ፡ ደስ ፡ የሚያሰኘውን ፡ ስራ ፡ ለመስራት ።

፲፩፤ ስለ ፡ ሰው ፡ መጸደቅ ።

እኛ ፡ ጻድቃን ፡ ሁነ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡ እንቈጠራለን ፡ በሃይማኖት ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ ጌ

ታችን ፡ ስለ ፡ መድኀኒታችንም ፡ ስለ ፡ ምግባሩ ፡፡ ስለ ፡ ምግባራችንም ፡ አይደለም ፡፡ ይህችም ፡ ትምርት ፡ በሃይማኖት ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ መጸደቃችን ፡ ማጽናት ፡ ይመላባታል ፡ ጳውሎስ ፡ እጅግ ፡ ጽሩ ፡ እንደገለጸው ፡ በመልእክቱ ፡ ወደ ፡ ሮሚ ፡ ሰዎች ፡፡

፲፪፤ ስለ ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡፡

በጎ ፡ ሥራ ፡ የሃይማኖት ፡ ፍሬ ፡ ሁኖ ፡ መጸደቃችንንም ፡ ተከትሎ ፡ ኀጢአታችንን ፡ ይሽር ፡ ዘንድ ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ፍርድ ፡ ይታገሥ ፡ ዘንድ ፡ አይችልም ፡፡ በክርስቶስ ፡ ግን ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ ያሰኘዋል ፡ እርሱም ፡ ይቀበለዋል ፡፡ እውነተኛውም ፡ ሕያውም ፡ ሃይማኖት ፡ ያለ ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ አይገኝም ፡ ይታወቅበታል ፡ እንጀ ፡ ዛፍ ፡ ሁሉግዜ ፡ እንዲታወቅ ፡ በፍሬው ፡፡

፲፫፤ ሰው ፡ ሳይጸድቅ ፡ ስለሚያደርገው ፡ ሥራ ፡፡

የክርስቶስን ፡ ጸጋ ፡ የመንፈሱንም ፡ መቀበል ፡ የሚቀድም ፡ ሥራ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ደስ ፡ አያሰኝም ፡፡ ከሃይማኖት ፡ በየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ አይነሣምና ፡ ሰውንም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ጸጋ ፡ ለመቀበል ፡ አያዘጋጀውም ፡፡ እንደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ፈቃድም ፡ አልተሰራምና ፡ የኀጢአት ፡ ወገን ፡ እንኳ ፡ እንዲሆን ፡ አንጠራጠርም ፡፡

፲፬፤ ስለ ፡ ትሩፋት ፡ ሥራ ፡፡

በሰው ፡ ፈቃድ ፡ የተሰራ ፡ እግዚአብሔር ፡ በሕጉ ፡ ካዘዘው ፡ በቀር ፡ በላየውም ፡ በጎ ፡ ሥራ ፡ የትሩፋትም ፡ ሥራ ፡ የሚሉት ፡ እንዲገኝ ፡ ብሎ ፡ የሚያስተምር ፡ ሰው ፡ ያለ ፡ ትዕቢትና ፡ ዐመፃ ፡ እንዲህ ፡ ማስተማር ፡ አይችልም ፡፡ ማለቱ ፡ እንዲህ ፡ ነውና ፡፡ ለሰው ፡ የሚገባውን ፡ እግዚአብሔርም ፡ ያዘዘውን ፡ ያድርገው ፡ ዘንድ ፡ ብቻ ፡ አያደርገ

ም ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሚገባው ፡ የሚበዛ ፡ ያደር ጋል ፡ እንጂ ፡፡ ክርስቶስ ፡ ግን ፡ ይላል ፡፡ የታዘዛችሁበትን ፡ ሁሉ ፡ ብታደርጉ ፡ በሉ ፡፡ እኛ ፡ የማንጠቅም ፡ ባሮች ፡ ነን ፡፡

፲፮፤ ክርስቶስ ፡ ብቻ ፡ ያለ ፡ ኀጢአት ፡ ነበረ ፡፡

ክርስቶስ ፡ በውነት ፡ በፍጥረታችን ፡ በነገር ፡ ሁሉ ፡ እኛ ን ፡ የመሰለ ፡ ሆነ ፡ ከኀጢአት ፡ በቀር ፡፡ ከኀጢአት ፡ ግን ፡ እርሱ ፡ በጣም ፡ ንጹሕ ፡ ነበረ ፡ በሥጋው ፡ በመንፈሱም ፡፡ እርሱ ፡ ያለ ፡ እንጂ ፡ የሚኖር ፡ በግ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ሰውነ ቱንም ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ምሥዋዕት ፡ ሁኖ ፡ ያቀርብ ፡ ዘንድ ፡ በዚህም ፡ ምሥዋዕት ፡ ያለምን ፡ ኀጢአት ፡ ያስወግድ ፡ ዘ ንድ ፡ መጣ ፡፡ ኀጢአትም ፡ ቅዱስ ፡ ዮሐንስ ፡ እንዲል ፡ በር ሱ ፡ አልነበረም ፡፡ እኛ ፡ ሁላችን ፡ ግን ፡ የቀረነ ፡ ጥምቀታች ንና ፡ በክርስቶስ ፡ ሁለተኛ ፡ ልደታችንም ፡ እንኳ ፡ ሳይቀር ፡ በብዙ ፡ ነገር ፡ እንበድላለን ፡፡ ኀጢአትም ፡ የለብንም ፡ ብ ንል ፡ ራሳችንን ፡ እናስታለን ፡ እውነትም ፡ የለብነም ፡፡

፲፯፤ ከ ጥ ም ቀ ት ፡ በ ኋ ላ ፡ ስ ለ ፡ ሚ ደ ረ ግ ፡ ኀ ጢ አ ት ፡፡

ከጥምቀት ፡ በኋላ ፡ በሰው ፡ ፈቃድ ፡ የሚሰራ ፡ የሞት ፡ ኀጢአት ፡ ሁሉ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ላይ ፡ ወይስ ፡ ስርየ ት ፡ የማይገኝለት ፡ አይደለም ፡፡ ስለዚህም ፡ ከተጠመቁ ፡ በኋላ ፡ በኀጢአት ፡ የሚወድቁ ፡ ሁሉ ፡ ከንስሓ ፡ አይከለከ ሉ ፡፡ መንፈስ ፡ ቅዱስን ፡ ከተቀበልነ ፡ በኋላ ፡ እንኳ ፡ እን ችላለን ፡ ከተሰጠነ ፡ ጸጋ ፡ እንርቅ ፡ ዘንድ ፡ በኀጢአትም ፡ እንወድቅ ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ጸጋ ፡ ተመልሰን ፡ እንነሣ ፡ ዘንድ ፡ ሕይወታችንንም ፡ የተሻለውን ፡ እናደርገ ው ፡ ዘንድ ፡፡ ስለዚህም ፡ በምድራዊት ፡ ሕይወታቸው ፡ ኃ ጢአትን ፡ ማድረግ ፡ እንዳይችላቸው ፡ የሚሉ ፡ ወይስ ፡ በ ወነት ፡ ንስሓ ፡ የሚገቡትን ፡ ከኀጢአት ፡ ስርየት ፡ ስፍራ ፡ የሚከለክሉ ፡ ትምህርታቸው ፡ ትወገዛለች ፡፡

፲፯፡፡ ስለ፡እግዚአብሔር፡ስለ፡ድሮ፡መለየቱና፡መምረጹ፡፡

ለሕይወት፡አስቀድሞ፡መለየት፡እርሱ፡የእግዚአብሔር፡የዘላለም፡ፈቃዱ፡ነው፡ያለም፡መሠረት፡ሳይሰራ፡ጽኑ፡የፈቀደበት፡በተሰወረ፡ምክሩ፡ከሰው፡ወገን፡ሁሉ፡በክርስቶስ፡የመረጻቸውን፡ሁሉን፡ከመርገምና፡ከፍርድ፡ያድናቸው፡ዘንድ፡፡ ለምስጋናም፡እንደ፡ተሰራ፡እቃ፡በክርስቶስ፡ወደ፡ዘላለም፡መድኃኒት፡ያደርሳቸው፡ዘንድ፡፡ እንጊዲህ፡እርሳቸው፡እግዚአብሔር፡እንዲህ፡የከበረውን፡ስጦታውን፡የሰጣቸው፡እንደ፡እግዚአብሔር፡ፈቃድ፡በጊዜው፡በልባቸው፡በመንፈሱ፡ይጸራሉ፡፡ እርሳቸውም፡በጸጋው፡መጽራቱን፡ይከተላሉ፡፡ እርሳቸውም፡እንዲያው፡ይጸደቃሉ፡፡ እርሳቸውንም፡እግዚአብሔር፡የጸጋ፡ልጆቹን፡ያደርጋቸዋል፡፡ እርሳቸውም፡እንደ፡አንደኛ፡ልጁ፡እንደ፡የሱስ፡ክርስቶስ፡ምሳሌ፡ይሆናሉ፡፡ እርሳቸውም፡በፍርሃቱ፡በበጎ፡ስራ፡ይመላለሳሉ፡፡ እርሳቸውም፡በመጨረሻቸው፡በእግዚአብሔር፡ምህረት፡ወደ፡ዘላለም፡ደህንነት፡ይደርሳሉ፡፡

መልካም፡ማሰብ፡ስለ፡እግዚአብሔር፡ስለ፡ድሮ፡መለየቱ፡ስለ፡መመረጻችንም፡በክርስቶስ፡የጻፈጠ፡ያመረም፡የማይናገርም፡ማጽናት፡ይመላበታል፡ለበጎ፡ሰዎች፡በልባቸው፡የክርስቶስን፡የመንፈሱን፡መስራት፡ለሚያውቁ፡የሥጋቸውን፡ስራ፡ምድራዊን፡ብልታቸውን፡ገድሎ፡ነፍሳቸውንም፡ወደ፡ላይ፡ወደ፡ሰማያዊ፡ነገር፡ወስደ፡፡ ይች፡ትምርት፡ሃይማኖታቸውን፡በዘላለም፡መድኃኒታቸው፡በክርስቶስ፡የሚቀበሉ፡እጅግ፡ታቆማቸዋለች፡ታጸናቸውማለች፡፡ እግዚአብሔርንም፡መውደዳቸውን፡እጅግ፡ታቃጥላለች፡፡ በሥጋዊ፡ሰዎች፡ግን፡የክርስቶስ፡መንፈስ፡በሌላቸው፡የመሰናከል፡ዕንቅፋት፡ነው፡ይህ፡ፍርድ፡የእግዚአብሔር፡መለየት፡በፊታቸው፡ቢሆን፡፡ ሰይጣን፡ይህነን፡መክንያት፡ያደርግባቸዋል፡ተስፋቸውን፡እንዲጥሉ፡ወይስ፡እንዴህ፡ከማድረጋቸው፡ወደልተኘለ፡ወደ፡ርኩስ፡አካሔዳቸው፡ጥፋት፡ይወስዳቸዋል፡፡

ደግሞም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ተስፋ ፡ በቅዱስ ፡ መጽሐፍ ፡ እንደ ፡ ተገለጸች ፡ እንቀበለው ፡ ዘንድ ፡ ይገባናል ፡ በመግባራችንም ፡ ያነን ፡ በቁም ፡ ነገር ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ የተገለጸውን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ፈቃድ ፡ እንከተል ፡ ዘንድ ፡፡

፲፰፡ የዘላለም ፡ መድኃኒት ፡ በክርስቶስ ፡ ስም ፡ ብቻ ፡ ትገኛለች ፡፡

ሰው ፡ ሁሉ ፡ በሚያምነው ፡ በሚያስታውቀውም ፡ ሕግ ፡ ወይስ ፡ መለየት ፡ ያችን ፡ ሕግ ፡ የፍጥረትንም ፡ ብርሃኑን ፡ ብቻ ፡ ቢከተል ፡ ይድናል ፡ የሚሉ ፡ የርሳቸው ፡ ትምርት ፡ ርግምት ፡ ሁና ፡ ትቈጠር ፡፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ የየሱስ ፡ ክርስቶስን ፡ ስም ፡ ብቻ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ይድንበት ፡ ዘንድ ፡ ይገልጸልናልና ፡፡

፲፱፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡፡

የክርስቶስ ፡ የምትታይ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የሚያምኑ ፡ ሰዎች ፡ ጉባኤ ፡ ናት ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጽሩ ፡ ቃል ፡ የሚሰበክባት ፡፡ ምሥጢራትንም ፡ እንዲገባቸው ፡ የሚያገለግሉባት ፡ እንደ ፡ ክርስቶስ ፡ ሥርዓት ፡ እንደዚህ ፡ ወደዚ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ሚደርስ ፡፡

የየሩሳሌም ፡ የስክንድርያም ፡ ያንጾኪያም ፡ አብያተ ክርስቲያናት ፡ እንደ ፡ ሳቱ ፡ እንደዚህ ፡ የሮምም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሳተች ፡ በማምለካቸው ፡ ሥርዓት ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ በሃይማኖት ፡ ትምህርታቸውም ፡ እንጂ ፡፡

፳፡ ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥልጣን ፡፡

ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥልጣን ፡ አላት ፡ የማምለክን ፡ ሥርዓት ፡ ትቈርጥ ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ ሃይማኖት ፡ ነገርም ፡ ክርክር ፡ ቢሆን ፡ ታስቀምጠው ፡ ዘንድ ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አይገባም ፡ በእግዚአብሔር ፡ በተጻፈ ፡ ቃሉ ፡ ላ

ደ ፡ አንደኛችን ፡ ታዝ ፡ ዘንድ ፡ ወይስ ፡ ምናቸውን ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ስፍራ ፡ እንዲህ ፡ ለማስተርጐም ፡ ከሌላ ፡ ስፍራ ፡ ጋራ ፡ እንዲጸላ ፡፡ ስለዚህም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ምስክርና ፡ ጠባቂ ፡ ሁና ፡ አንደኛችን ፡ ላታዝ ፡ ክርሱ ፡ ጋራ ፡ የሚጸላውን ፡፡ ሰውንም ፡ ላትፈልግ ፡ ባንደኛ ፡ ያምን ፡ ዘንድ ፡ ስለ ፡ መድኀኒቱ ፡ በግድ ፡ ይገባል ፡ ብላ ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ በቀር ፡፡

፷፩፤ ስለ ፡ ኦይኩሜኒኮች ፡ ሲኖዶች ፡፡

ኦይኩሜኒኮችን ፡ ሲኖዶች ፡ መሰብሰብ ፡ አይገባም ፡ ያለ ፡ መኳንንት ፡ ፈቃድና ፡ ትእዛዝ ፡፡ ተሰብስበውም ፡ ይስቱ ፡ ዘንድ ፡ ይችላሉ ፡ አንዳንድ ፡ ጊዜም ፡ በውነት ፡ ሳቱ ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ እንኳ ፡ በተቈረጠ ፡ ነገር ፡፡ የተሰበሰቡ ፡ እርሳቸው ፡ ሰዎች ፡ ናቸውና ፡ ሁላቸውም ፡ ኢያንዳንዳቸው ፡ ለእግዚአብሔር ፡ መንፈስና ፡ ለቃሉ ፡ አይገዙም ፡፡ ስለዚህም ፡ እርሳቸው ፡ ለመድኀኒታችን ፡ እንዲገባ ፡ የሚያዙት ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ኀይልና ፡ ሥልጣን ፡ የለውም ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ባይሆን ፡፡

፷፪፤ ስለ ፡ አያሌ ፡ ነገር ፡ ሰው ፡ ያወጣው ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስም ፡ ጋራ ፡ የሚጸላ ፡፡

የሮማውያን ፡ ትምህርት ፡ ስለ ፡ ነፍስ ፡ ንብረት ፡ ከሞት ፡ በኋላ ፡፡ ስለ ፡ ኀጢአት ፡ ስርየት ፡ በከንቱ ፡ ስራ ፡ በብርም ፡፡ ስለ ፡ ሥእልም ፡፡ ከክርስቶስና ፡ ከቅዱሳንም ፡ ስለ ፡ ተረፈ ፡ ነገር ፡ እንደ ፡ አፅንት ፡ ልብስም ፡ እንጨትም ፡ መሬትም ፡ ስለ ፡ መሰገዷቸውም ፡ ስለ ፡ መጸራታቸውም ፡፡ ወደ ፡ ቅዱሳንም ፡ ስለ ፡ መጽራት ፡፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ከሰው ፡ ልብ ፡ ብቻ ፡ ተነሣ ፡፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃልም ፡ አይገኝም ፡ ከርሱ ፡ ጋራ ፡ ይጸላል ፡ እንጂ ፡፡

፷፫። በጉባኤ ፡ ስለ ፡ ማገልገል ፡፡

ለሰው ፡ ሁሉ ፡ በግልጽ ፡ በጉባኤ ፡ ይሰብክ ፡ ዘንድ ፡ ምሥጢራትንም ፡ ያገለግል ፡ ዘንድ ፡ አይገባውም ፡ ለዚህ ፡ ማገልገል ፡ ካልተጸራ ፡ ካልተላከም ፡፡ እልያንም ፡ ብቻ ፡ በሥርዓት ፡ እንደ ፡ ተጸረ ፡ እንደ ፡ ተላኩም ፡ እንቈጥራለን ፡ ለዚህ ፡ ማገልገል ፡ በግልጽ ፡ በጉባኤ ፡ ሰራተኞችን ፡ ወደ ፡ ጌታችን ፡ ወይን ፡ ይጸሩ ፡ ይሰዱም ፡ ዘንድ ፡ ሥልጣን ፡ ከተቀበሉ ፡ ሰዎች ፡ የተመረጹ ፡ የተጸሩም ፡፡

፷፬። ቄስ ፡ በጉባኤ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በሚሰማው ፡ ቋንቋ ፡ ይናገር ፡፡

ቄስ ፡ በግልጽ ፡ በጉባኤ ፡ ቢጸልይ ፡ ምሥጢራትንም ፡ ቢያገለግል ፡ ጉባኤ ፡ በማይሰማው ፡ ቋንቋ ፡ ተናግሮ ፡ ይህ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ከመጀመርያም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ወግ ፡ ጋራ ፡ ይጸላል ፡፡

፷፭። ስለ ፡ ምሥጢራት ፡፡

በክርስቶስ ፡ የተሰረ ፡ ምሥጢራት ፡ እርሳቸው ፡ ክርስቲያን ፡ ሰዎች ፡ የሚታወቁባቸው ፡ ምልክቶች ፡ ብቻ ፡ አይደሉም ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ስለ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸጋ ፡ ስለ ፡ ፍቅሩም ፡ ወደኛ ፡ እውነተኞች ፡ ምስክሮች ፡ ኃይለኞችም ፡ ምልክቶች ፡ ናቸው ፡፡ እግዚአብሔር ፡ በርሳቸው ፡ በማይታይ ፡ መንገድ ፡ በልባችን ፡ ሰርትዋልና ፡፡ በርሱም ፡ ያለ ፡ ሃይማኖታችንን ፡ ያሐይውበቻዋል ፡ ያጸናባቸውማል ፡፡ ክርስቶስም ፡ ጌታችን ፡ በወንጌል ፡ የሰራቸው ፡ ምሥጢራት ፡ ሁለት ፡ ናቸው ፡፡ እርሳቸውም ፡ ጥምቀትና ፡ የጌታ ፡ እራት ፡፡

እልያ ፡ ፯ም ፡ ሮማውያን ፡ ደግሞ ፡ ምሥጢራት ፡ የሚልዋቸው ፡ እርሳቸውም ፡ የጥምቀት ፡ ማጽናት ፡፡ ንስሐም ፡፡ የቀሳውስትም ፡ እጅ ፡ መጫን ፡፡ መጋባትም ፡፡ ኋለኛ ፡ መቅባትም ፡ ሁሉ ፡ የወንጌል ፡ ምሥጢራት ፡ ሁነው ፡ አይቈጠሩ ፡፡ ክርሳቸው ፡ ተከፍለው ፡ የሐዋርያትን ፡ አካ

ሔድ ፡ በኵል ፡ ከመከተላቸው ፡ ተነሥተዋልና ፡ ተከፍለው ምም ፡ የሕይወት ፡ ንብረት ፡ ናቸው ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ያዘዘም ፡ ያላዘዘም ፡ ምሥጢራትን ፡ ግን ፡ እንደ ፡ ጥምቀትና ፡ የጌታችን ፡ እራት ፡ አይመስሉም ፡፡ የሚታይ ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ የተሰራ ፡ ምልክት ፡ ከማይታይ ፡ ጸጋው ፡ ጋራ ፡ የለባቸውምና ፡፡

ምሥጢራትን ፡ እንደሚገባ ፡ እንደ ፡ ክርስቶስ ፡ ሥርዓት ፡ ብንቀበላቸው ፡ ብናገለግላቸውም ፡ ይባረኩልናል ፡፡ እንደይገባ ፡ ግን ፡ የሚቀበልዋቸው ፡ ለራሳቸው ፡ ፍርድ ፡ ያደርጊቸዋል ፡ ቅዱስ ፡ ጳውሎስ ፡ እንደሚል ፡፡

፳፯፡፡ የቀሳውስት ፡ ክፋት ፡ የምሥጢርን ፡ ኃይል ፡ አይከለክልም ፡፡

በምትታይ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በውነት ፡ ክፉ ፡ ሁለጊዜ ፡ ከበጎ ፡ ጋራ ፡ ተደብልቆ ፡ ይገኛል ፡ ጊዜም ፡ አለ ፡ ለክፉ ፡ እጅግ ፡ ሥልጣን ፡ እንደለ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃልና ፡ ምሥጢራትንም ፡ በማገልገል ፡፡ ክፉ ፡ አገልጋዮች ፡ ግን ፡ በስማቸው ፡ አያገለግሉምና ፡ በክርስቶስ ፡ ስም ፡ እንጅ ፡ በትእዛዙም ፡ በሥልጣኑም ፡ ማገልገላቸውን ፡ መቀበል ፡ እንችላለን ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ካፋቸው ፡ ብንሰማ ፡ ምሥጢራቱንም ፡ ከርሳቸው ፡ ስንቀበል ፡፡ የክርስቶስም ፡ የሥርዓቱ ፡ ኃይል ፡ ባገልጋዮቱ ፡ ዐመፃ ፡ አይጠፋም ፡፡ የእግዚአብሔርም ፡ ስጥወታ ፡ አያንስም ፡ በሃይማኖትና ፡ በቅን ፡ ምሥጢራትን ፡ ከጇቸው ፡ በሚቀበሉ ፡፡ ለምሥጢር ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ ሥርዓትና ፡ ትእዛዝ ፡ ኃይል ፡ አለው ፡ በሰው ፡ ክፋት ፡ የማይጠፋ ፡፡

ያስ ፡ ሳይቅር ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተግሣጽ ፡ ይገባል ፡ ስለ ፡ ክፎች ፡ አገልጋዮች ፡ ይመረምሩ ፡ ዘንድ ፡፡ እርሳቸውም ፡ መበደላቸውን ፡ በሚያውቁ ፡ ሰዎች ፡ ይታጣሉ ፡ ዘንድ ፡ መበደላቸውም ፡ እውነት ፡ ሁኖ ፡ በተገኘ ፡ ጊዜ ፡ በቅን ፡ ፍርድ ፡ ከሹመታቸው ፡ ይሻሩ ፡ ዘንድ ፡፡

፳፪። ስለ ፡ ጥምቀት ::

ጥምቀት ፡ የሃይማኖት ፡ ማስታወቅ ፡ የመለየትም ፡ ምልክት ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ ክርስቲያን ፡ ካልተጠመቀ ፡ ሰው ፡ የሚለይበት ፡ የሁለተኛ ፡ ልደታችንም ፡ ምልክት ፡ ነው ፡ እንጂ :: ጥምቀትን ፡ የሚቀበሉ ፡ በርሱ ፡ በምትታይ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይተከላሉ ፡ ለኀጢአትም ፡ ስርየት ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ልጅነታችን ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ የተሰጠች ፡ ተስፋ ፡ ላይን ፡ ትመለከትበታለች ፡ ታተማለችም :: ሃይማኖትም ፡ ይጸናበታል :: የእግዚአብሔርም ፡ ጸጋ ፡ በጽሎት ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይበዛል ::

የሕፃናትን ፡ ጥምቀት ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ እንጠብቃለን ፡ ከክርስቶስ ፡ ሥርዓት ፡ ጋራ ፡ አይጸላምና ::

፳፫። ስለ ፡ ጌታችን ፡ እራት ::

የጌታችን ፡ እራት ፡ ክርስቲያን ፡ እርሱ ፡ በርሳቸው ፡ ሊሆንላቸው ፡ ለሚገባ ፡ ፍቅር ፡ ምልክት ፡ ብቻ ፡ አይደለም ፡ በክርስቶስ ፡ ሞት ፡ የሆነ ፡ የመድኀኒታችን ፡ ምሥጢር ፡ ነው ፡ እንጂ :: በቅንና ፡ በሃይማኖት ፡ እንደሚገባም ፡ ለሚቀበሉት ፡ የምንቈርሰው ፡ እንጀራ ፡ የክርስቶስ ፡ የሥጋው ፡ አንድነት ፡ ነው ፡ የበረከቱም ፡ ጽዋ ፡ የክርስቶስ ፡ የደሙ ፡ አንድነት ፡ ነው ::

የንጀራና ፡ የወይን ፡ ፃጅ ፡ ባሕሪ ፡ በጌታችን ፡ እራት ፡ እንዲለወጥ ፡ ባሕርያቸው ፡ ተሸርቶ ፡ የክርስቶስ ፡ ሥጋና ፡ ደም ፡ እንዲሆኑ ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ አይገለጽም ፡ ይህችም ፡ ትምርት ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ከቁም ፡ ነገሩ ፡ ጋራ ፡ ትጸላለች :: ያምሥጢርንም ፡ ነገር ፡ ታጠፋለች :: ብዙም ፡ አሰተኛ ፡ ሃይማኖት ፡ ከርሱ ፡ ተነሣ ::

የክርስቶስን ፡ ሥጋ ፡ በራቱ ፡ በሰማያዊ ፡ በመንፈሳዊም ፡ መንገድ ፡ ብቻ ፡ እንሰጣለን ፡ እንቀበለውማለን ፡ እንበላውማለን :: የክርስቶስንም ፡ ሥጋ ፡ በራቱ ፡ የምንቀበልበት ፡ የምንበላበት ፡ መያዣ ፡ የነፍስ ፡ አፍ ፡ እርሱ ፡ ሃይማኖት ፡ ነው ::

፴፱፤ ዐመፀኞች ፡ በጌታችን ፡ እራት ፡ የክርስቶስን ፡ ሥጋ ፡ አይበሉም ::

ዐመፀኞች ፡ ሕያው ፡ ሃይማኖትም ፡ የሌላቸው ፡ የክርስቶስ ፡ የሥጋውንና ፡ የደሙን ፡ ምሥጢር ፡ በሥጋና ፡ ለማየት ፡ ባፋቸው ፡ ሲቀበሉት ፡ ሲበሉትም ፡ ሲጠጡትም ፡ ክርስቶስን ፡ በውነት ፡ አይቀበሉትም :: የዚህ ፡ የከበረ ፡ ምሥጢር ፡ መብልና ፡ መጠጥ ፡ ለፍርዳቸው ፡ ይሆንባቸዋል ፡ እንጂ ::

፵፡፡ ስለ ፡ ሁለት ፡ መልኩ ::

የጌታው ፡ ጽዋ ፡ ከሕዝብ ፡ መከለከል ፡ አይገባም :: በክርስቶስ ፡ ሥርዓትና ፡ ትእዛዝ ፡ ቀሳውስት ፡ ታዘዋልና ፡ የጌታውን ፡ የራቱን ፡ ሁለት ፡ ክፍል ፡ ለክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ ይሰጡ ፡ ዘንድ ::

፵፩፤ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ በመስቀል ፡ ስለ ፡ ተፈጸመ ፡ ስለ ፡ አንድ ፡ ምሥዋዕቱ ::

እርሱ ፡ የክርስቶስ ፡ ምሥዋዕት ፡ በመስቀል ፡ ላይ ፡ ሁኖ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ የፈጸመው ፡ እርሱ ፡ ፍጹም ፡ ማደን ፡ ማስታረቅም ፡ ካሳም ፡ ሆነ ፡ ስለ ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ ኃጢአት ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ሚወለድበት ፡ ስለ ፡ ሚያደርገውም :: ስለ ፡ ኃጢአትም ፡ ሌላ ፡ ካሳ ፡ የለም ፡ እርሱ ፡ ብቻ ፡ እንጂ ::

ስለዚህም ፡ የቍርባን ፡ ምሥዋዕት ፡ ሮማውያን ፡ ስለሚናገሩ ፡ ቄስ ፡ በርሱ ፡ ክርስቶስን ፡ ምሥዋዕት ፡ ሁኖ ፡ እንዲያቀርብበት ፡ ስለ ፡ ሕያዋንና ፡ ስለ ፡ ሙታን ፡ ኃጢአታቸውና ፡ መቅሠፍታቸው ፡ ይፈታላቸው ፡ ዘንድ ፡ ብለው ፡ ስድብና ፡ አሰት ፡ ነበረ ::

፵፪፤ ስለ ፡ ቀሳውስት ፡ መጋባት ::

ጳጳሳት ፡ ቀሳውስትም ፡ ዲያቆናትም ፡ በብቸኝነት ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ወይስ ፡ ስለቱን ፡ ያደርጉ ፡ ዘንድ ፡ ወይስ ፡ ከመጋባት ፡ ይከለከሉ ፡ ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ አልታዘ

ዙም ፡፡ ስለዚህ ፡ እርሳቸው ፡ ቢወዱ ፡ እንደ ፡ ሌሎች ፡ ክር ስቲያናት ፡ ለመግባት ፡ ይግቡ ፡ ለበጎ ፡ አካሔዳቸው ፡ እንዲ ጠቅም ፡ ቢመስላቸው ፡፡

፷፫ ስለ ፡ ተገዘቱ ፡ ሰዎች ፡፡

በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በግልጽ ፡ በቅን ፡ ፍርድዋ ፡ በሥርዓ ትም ፡ ከቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ አንድነት ፡ የተቈረጠውን ፡ የ ተገዘተውንም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የምእምናን ፡ ጉባኤ ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ አረማዊ ፡ እንደ ፡ አጣሪም ፡ ይቍጠረት ፡ ንስሓ ፡ በ መግባት ፡ በግልጽ ፡ እስኪታረቅ ፡ ድረስ ፡ ሥልጣንም ፡ ባ ለው ፡ ፈራጅ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ መልሳ ፡ እስክትቀበለ ው ፡ ድረስ ፡፡

፷፬ ስለ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሥርዓት ፡፡

የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የማምለክዋ ፡ ሥርዓት ፡ በስፍራ ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ በጣምም ፡ በሁሉ ፡ ይሰማ ማ ፡ ዘንድ ፡ በግድ ፡ አይፈለግም ፡፡ በዘመን ፡ ሁሉ ፡ ልዩ ፡ ልዩ ፡ ነበረና ፡፡ ምድርም ፡ ዘመንም ፡ የሰውም ፡ ልማድ ፡ እ ንደ ፡ ለዩ ፡ ይህ ፡ ደግሞ ፡ ይለወጥ ፡ አንዳች ፡ ባይሰራ ፡ በእግ ዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ላይ ፡ የሚሆን ፡፡ ማንም ፡ በራሱ ፡ ፍር ድ ፡ በማሰብና ፡ በፈቃዱ ፡ በግልጽም ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ጋራ ፡ የማይጸላውን ፡ ሥርዓት ፡ በ ሥልጣንም ፡ የተሰራውን ፡ የተቀበሉትንም ፡ የሚያፈርሰ ው ፡ በግልጽ ፡ ይገሠጽ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ሥርዓት ፡ በ ድልዋልና ፡ የመኰንንም ፡ ሥልጣን ፡ ጐድትዋል ፡፡ የደከ ሙትንም ፡ የወንድሞቹን ፡ ልብ ፡ አሳዘነ ፡፡ ሌላ ፡ ሰው ፡ ከ መከተሉ ፡ ይፈራ ፡ ዘንድ ፡፡

በያገሩም ፡ በየሕዝብም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በሰው ፡ ብ ቻ ፡ የተሰራውን ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንን ፡ ሥርዓት ፡ ትሰራ ፡ ትለውጥም ፡ ትሽርም ፡ ዘንድ ፡ ሥልጣን ፡ አላት ፡፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ ለመስራት ፡ እስኪሆን ፡ ድረስ ፡፡

፻፭፡ ስለ ፡ ስብከት ፡ መጽሐፍ ::

በዚህ ፡ ቃል ፡ የስብከት ፡ ሁለት ፡ መጻሕፍት ፡ በኤድዋርድ ፡ ፯፡ በንጉሥ ፡ በኤልሳቤትም ፡ በንግሥት ፡ ዘምን ፡ የተጻፉ ፡ ይነበቡ ፡ ዘንድ ፡ ይመክራል ::

፻፮፡ ስለ ፡ ጳጳሳትና ፡ ስለ ፡ ቀሳውስት ፡ ቅደሴ ::

የዚህ ፡ ሥርዓት ፡ በጳጳሳትና ፡ በቀሳውስት ፡ ቅደሴ ፡ መጽሐፍ ፡ ይገኛል ::

፻፯፡ ስለ ፡ አገር ፡ መኳንንት ::

ንጉሥ ፡ ጌታችን ፡ መጀመርያ ፡ ከሁሉም ፡ የሚበልጥ ፡ ሥልጣን ፡ አለው ፡ በዚህ ፡ በንግልጣር ፡ ምድር ፡ በሌላ ፡ መግዛቱም ፡ ሁሉ :: የቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ያገርም ፡ መግዛት ፡ ሁሉ ፡ በነገር ፡ ሁሉ ፡ ለርሱ ፡ ነው :: በሌላ ፡ አገርም ፡ ላለ ፡ መኰንን ፡ በዚህች ፡ መንግሥት ፡ ሥልጣን ፡ የለውም :: በዚህ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ለነገሥታታችን ፡ አይገባም ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ይሰብኩ ፡ ዘንድ ፡ ወይስ ፡ ምሥጢራትን ፡ ያገለግሉ ፡ ዘንድ :: ይህች ፡ ሥልጣን ፡ እንጀ ፡ እግዚአብሔርን ፡ የፈሩት ፡ መኳንንት ፡ ወትሮ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የተቀበሉት ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ እንደለ ፡ መንግሥታቸውን ፡ በየክፍልዋ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ዘንድ ፡ እንደ ፡ ታመኑባት :: ለመቅደስና ፡ ላገር ፡ ግለው ፡ ይገዙ ፡ ዘንድ ፡ ዐመፀኞችንም ፡ ክፉ ፡ አድራጎችንም ፡ ባገር ፡ ሰይፍ ፡ ይከለክሉ ፡ ዘንድ :: የሮም ፡ ጳጳስም ፡ በንግልጣር ፡ መንግሥት ፡ መግዛት ፡ ወይስ ፡ ሥልጣን ፡ የለውም ፡ ከቶ ::

የመንግሥት ፡ ሕግ ፡ ክርስቲያንን ፡ ስለ ፡ ታላቅ ፡ መበደል ፡ በሞት ፡ መቅሠፍ ፡ ይችላል ::

ለክርስቲያን ፡ ይገባል ፡ በመኰንን ፡ ትእዛዝ ፡ ጋሻ ፡ ጦርን ፡ ይወስድ ፡ ዘንድ ፡ በዘምቻም ፡ ያገለግል ፡ ዘንድ ፡ የመንግሥት ፡ ጕዳይ ፡ ሲፈልገው ::

፴፰፡ ስለ ፡ ገንዘብ ::

የክርስቲያን ፡ ሰው ፡ ባለጠግነትና ፡ ገንዘብ ፡ ቅኑና ፡ መግዛት ፡ የጉባኤ ፡ አይደለም ፡ አያሌ ፡ መናፈቃን ፡ እንደ ፡ ሐለሙ ። ይህ ፡ ግን ፡ ሳይቀር ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ ይገባል ፡ እግዚአብሔር ፡ ከሰጠው ፡ ገንዘብና ፡ መግዛት ፡ ለድኆች ፡ ለበጎ ፡ መክንያትም ፡ ሁሉ ፡ እንደ ፡ ችሎቱ ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ።

፴፱፡ ስለ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰው ፡ መሐላ ።

በከንቱ ፡ ከሚደረግ ፡ ከቃሊልም ፡ መማል ፡ ክርስቲያን ፡ ሁሉ ፡ ተከለከለ ፡ በጌታችን ፡ በየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ በሐዋርያውም ፡ በያዕቆብ ፡ ቃል ። ነገር ፡ ግን ፡ የክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ ሰውን ፡ ከመማል ፡ ሁሉ ፡ እንዲያው ፡ አይከለክልም ፡ መኰንን ፡ ቢፈልገው ፡ በሃይማኖትና፤ በፍቅርም ፡ መክንያት ፡ ነቢይ ፡ እንዲያዘው ፡ ቢሆን ፡ በቅን ፡ በፍርድም ፡ በውነትም ።

ከዚህ ፡ ይጨርሳሉ ፡ የእንግሊዝ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡
፴፱፡ ቃላት ።

ከዚህ ፡ ይገለጻል ፡ የጵሮተስታንቶች ፡ ትምህርት ፡ በንምኅና ፡ በንግልጣር ፡ በታላቅ ፡ ነገር ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ እንዲሆን ። መሠረትንም ፡ ሁሉን ፡ እንዲጥሉ ፡ ከመጽሐፈ ፡ ቅዱስ ፡ ዘንድ ፡ ያልተነሣ ። እርሳቸውም ፡ አዲስ ፡ ጉባኤን ፡ አላደረጉም ፡ ካለች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በትምርትና ፡ በሥርዓት ፡ በማምለክም ፡ የገባውን ፡ ስሕተት ፡ ብቻ ፡ ያወጡ ፡ ዘንድ ፡ ተገደሉ ፡ እንጂ ።

የመጀመርያ ፡ መምህራናቸው ፡ ግን ፡ በሞቱ ፡ ጊዜ ፡ ታላቅ ፡ ክርክር ፡ ወጣ ፡ ስለ ፡ ታናሽ ፡ ነገር ። እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ የታደሰች ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የበላኞችን ፡ እንደትከተል ፡ ብሎ ፡ መከራ ፡ ሰደደላት ። የእግዚአብሔርም ፡ ጸላቶች ፡ ተነሡባት ፡ ፴፡ አመትም ፡ ጾር ፡ ሆነ ፡ በጵሮተስታንቶች ፡ ላይ ፡ በንምሳ ፡ እጅግ ፡ እስኪጨንቁ ፡ ድረስ ። በፈረ

ንስም ፡ የሮም ፡ ጸላትናት ፡ እጅግ ፡ ተቃጠለች ፡ በወንጌል ፡
ወገን ፡ ላይ ፡፡ ባመት ፡ ፲፭፻፸፪፡ ባንዲት ፡ ሌሊት ፡ የንጉሥ ፡
ሰርግ ፡ ሲሆን ፡ ብዙ ፡ አእላፈ ፡ ሰዎች ፡ ከጵሮተስታንቶች ፡
ወገን ፡ ተገደሉ ፡ ስለዚህም ፡ ይህች ፡ ሰርግ ፡ የደም ፡ ሰርግ ፡
ተባለች ፡፡

የ፳፡ አመት ፡ ጶርም ፡ ጵሮተስታንቶችን ፡ እጅግ ፡ ካስጨ
ነቀ ፡ ባኋላ ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ጸሩ ፡ እግዚአብሔርም ፡
የጉስታቡስ ፡ አደልፈ ፡ የስዌደን ፡ ንጉሥ ፡ ልብ ፡ አስነሣ ፡
እርሱም ፡ ወደ ፡ ንምሳ ፡ መጥቶ ፡ በጸላቶች ፡ ላይ ፡ ወደቀ ፡
አሸነፋቸውም ፡ ወንድሞቹንም ፡ በወንጌል ፡ አርነት ፡ አ
ወጣቸው ፡፡

የዚያን ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ ሁለተኛ ፡ ክርክር ፡ ተነሣ ፡ በጵሮተስ
ታንቶች ፡ መኻከል ፡ ስለ ፡ ትምርት ፡ ፊደል ፡ መንፈሳቸው ፡
ሲደክም ፡፡ እግዚአብሔርም ፡ ስለዚህ ፡ አያሌን ፡ ቅዱሳን ፡
ሰዎች ፡ አስነሣ ፡ ወደ ፡ ንስሐ ፡ የጸርዋቸው ፡ የቤተ ፡ ክርስቲ
ያንንም ፡ ኃጢአት ፡ ጉደደዋንም ፡ የገሠጹ ፡፡ ባካሔዳቸው
ም ፡ በትምህርታቸውም ፡ ለወንድሞቻቸው ፡ የሰበኩ ፡፡ በ
ስብከታቸውም ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ከኃጢአታቸው ፡ ወደ ፡ እግ
ዚአብሔር ፡ ተመለሱ ፡፡ ከለዚያ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ሰዎ
ች ፡ አያሌ ፡ እሌህ ፡ ናቸው ፡፡ አርንድ ፡ ስጴነርም ፡ ፍራ
ንክም ፡ በክስትርም ፡ ቡንያንም ፡ ደድሪጅም ፡ ጺንጸ
ንደርፍም ፡ ሌተንም ፡ ሀርቤም ፡ ዌስሌም ፡ ዊትፊልድ
ም ፡ ሌሎችም ፡፡

እሌህ ፡ ግን ፡ በወንጌል ፡ ኃይል ፡ እጅግ ፡ ባበሩ ፡ ጊዜ ፡ የ
ጨለማ ፡ ኃይል ፡ ተነሣባቸው ፡ ብርቱም ፡ ሆነች ፡፡ የመስቀል ፡
ትምህርት ፡ ለብዙ ፡ ሰዎች ፡ ስንፍና ፡ ሆነች ፡ ወንጌልም ፡ በ
ሰደፍ ፡ መጠበቅ ፡ አይሆንለትምና ፡ በመንፈስ ፡ ሰደፍ ፡ እን
ጅ ፡ የሰው ፡ ፀመፃ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ትዕግሥት ፡ በዛ ፡፡ ዐ
መፀኞችም ፡ ካለም ፡ ብልሃተኞች ፡ ወገን ፡ ሁነዋልና ፡ አያ
ሌ ፡ መምህራን ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተሳቱ ፡ አባቶቻቸው
ም ፡ የተጋደሉላትን ፡ ትምህርት ፡ ካዱ ፡ ከሕዝብም ፡ ብዙ ፡
ሰዎች ፡ ተከተልዋቸው ፡፡ ክርስቶስንም ፡ በውነት ፡ ከለልባ
ቸው ፡ የወደደት ፡ ሰዎች ፡ ጥቂት ፡ ሆኑ ፡፡ ተሰደቡም ፡፡

በእግዚአብሔር ፡ ላይም ፡ ከተነሣ ፡ ዐመፃ ፡ በእግዚአብ ሔር ፡ ሥርዓትም ፡ ላይ ፡ ዐመፃ ፡ ተከተለ ፡፡ የፈረንሲስ ፡ መንግሥት ፡ የወንጌልን ፡ ከሉተር ፡ ከከልዊንም ፡ የወጣችን ፡ ብርሃን ፡ አሳደደች ፡ በሮምም ፡ ጨለማ ፡ በኃጢአታቸውም ፡ ይኖሩ ፡ ዘንድ ፡ ወደዱ ፡፡ ስለዚህም ፡ እግዚአብሔር ፡ በልባቸው ፡ አሳብ ፡ አሳልፎ ፡ ሰጣቸው ፡ በጣም ፡ እስኪያብዱ ፡ ድረስ ፡ እስኪሉም ፡ ድረስ ፡፡ ማን ፡ ነው ፡ አምላካችን ፡ ቃሉን ፡ እንሰማ ፡ ዘንድ ፡፡ ንጉሣቸውን ፡ ሉድዊግ ፡ ፲፮፡ ገደሉ ፡ ባመት ፡ ፲፯፻፺፪፡ ክርስቶስንም ፡ ክደው ፡ ለሰው ፡ አእምሮ ፡ መቅደስን ፡ ሰሩ ፡ ጋለሞትንም ፡ የሰው ፡ አእምሮ ፡ ምሳሌ ፡ ናት ፡ ብልዋልና ፡ ወደ ፡ መቅደስ ፡ አግብተው ፡ በመሠውያ ፡ ላይ ፡ አቆምዋት ፡ አመለክዋትም ፡፡ አርነትና ፡ አንድነት ፡ ማለታቸው ፡ ነበረ ፡፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ አንድ ፡ እንዲሆን ፡ የታናሽና ፡ የታላቅ ፡ መለየትም ፡ እንዲጨርስ ፡ ሥርዓትን ፡ ሁሉን ፡ አፈረሱ ፡ የሰውን ፡ ንብረት ፡ ሁሉ ፡ ያስተካክሉ ፡ ዘንድ ፡፡ ሰውም ፡ ሁሉ ፡ ለራሱ ፡ ንጉሥ ፡ እንዲሆን ፡ መስሎት ፡ ለፈቃዱ ፡ ያልተገዛውን ፡ ባልንጀራውን ፡ አሳደደ ፡ እጅግ ፡ ደምም ፡ በፈራንስ ፡ ፈሰሰ ፡፡ ከራሳቸውም ፡ ያወጥዋቸው ፡ ሹማምታቸው ፡ እንደ ፡ ሰይጣናት ፡ ገዙባቸው ፡፡ እርሳቸውም ፡ አያሌ ፡ ወራት ፡ ከሠቀደዋቸው ፡ በኋላ ፡ በሰይፈቸው ፡ ወደቁ ፡፡ እንደዚህም ፡ ሲሆን ፡ ከጻድቃን ፡ ቍጥር ፡ አያሌ ፡ ነበሩ ፡ ያሰቡ ፡ ከዚህ ፡ ጨለማ ፡ ከዚህም ፡ ዐመፃ ፡ ምናልባት ፡ ሐሳዊ ፡ መሢሕ ፡ እንደነሣ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ እግዚአብሔር ፡ በዘላለም ፡ ምክሩ ፡ ፈቀደ ፡ በዚህ ፡ ዘመን ፡ ብርሃኑን ፡ መልሶ ፡ ያወጣ ፡ ዘንድ ፡ የቤተ ፡ ክርስቲያንም ፡ ወሰን ፡ ይዘርጋ ፡ ዘንድ ፡፡ ክርስቲያንም ፡ የተባለች ፡ ሕዝብ ፡ ክርስቶስን ፡ በካደች ፡ ጊዜ ፡ የክርስቶስ ፡ ዕውቀት ፡ ወደ ፡ ሌሎች ፡ አሕዛብ ፡ ደረሰች ፡ እርሳቸውም ፡ በስሙ ፡ ደኑ ፡፡

የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡

ታሪክ ፡

ስምንተኛ ፡ ክፍል ።

የቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ የመዘረጋትዋ ፡ ዘመን ።

ከ፲፯፻፳፡ ጀምሮ ፡ እስከ ፡ ፲፰፻፵፬፡ ድረስ ።

በዚህ ፡ ዘመን ፡ እግዚአብሔር ፡ እጅግ ፡ አደረገ ፡ ቤተ ፡ ክ
ርስቲያኑን ፡ ይዘርጋ ፡ ዘንድ ። ፊተኛ ፡ መጀመርያው ፡ አስ
ቀድሞ ፡ ተደረገ ፡ ነገር ፡ ገን ፡ እጅግ ፡ አልሆነበትም ።
የሮም ፡ ወገን ፡ በስምና ፡ በቍጥር ፡ እጅግ ፡ አደረጉ ።
እርሳቸው ፡ የጳጳስን ፡ መግዛት ፡ በጪንና ፡ በህንድ ፡ በ
ያጳንም ፡ በአሜሪካም ፡ አወጡ ፡ ነገር ፡ ግን ፡ የወንጌል ፡
ነገር ፡ የክርስቶስም ፡ ምስጋና ፡ ጥቂት ፡ ሆነበት ። የሮም ፡
ወገንም ፡ ወደ ፡ ሃበሻ ፡ ሲመጡ ፡ በቅላውዴዎስና ፡ በ
ሶስኔዎስ ፡ ዘመን ፡ ጾርን ፡ አስነሡ ፡ በግፍ ፡ ስለ ፡ ማይጠ
ቅምም ፡ ነገር ። በምሥር ፡ ጳጳስ ፡ ፈንታ ፡ የሮምን ፡ ጳጳስ ፡
ሲያደርጉ ፡ የፈሲካውንም ፡ ጊዜ ፡ ሲለውጡ ፡ የቅዳሜን
ም ፡ ማክበር ፡ ሲያጠፉ ፡ እንደዚህ ፡ ያለውንም ፡ ዝምብሎ
ን ፡ ነገር ፡ ሲያደርጉ ፡ ሰውንም ፡ በሰው ፡ ነገር ፡ ማስተማ
ር ፡ ሲፈልጉ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃልም ፡ አይደለም ። ስለ
ዚህም ፡ ስራቸው ፡ አልተባረከም ፡ ከእግዚአብሔርም ፡ አ
ልነበረምና ፡ አልጸናም ።
ከወንጌል ፡ ወገንም ፡ ከጵሮተስታንቶች ፡ ሃይማኖት
ን ፡ የዘረጉ ፡ እሌህ ፡ ናቸው ። ኤልዮትና ፡ ብሬነርድ ፡ በ
ኢንዲያኖች ፡ መካከል ፡ በሰሜን ፡ አሜሪካ ። ዮሐንስ ፡
ኤጌደም ፡ በግሬንላንድ ። ከሃሌም ፡ የተላኩ ፡ እርሳቸ
ውም ፡ ጺገንባልግ ፡ ሽዋርጽም ፡ ሌሎችም ፡ በህንድ ።
በጺንጽንደርፍም ፡ የተሰራች ፡ ጉባኤ ፡ የወንጌል ፡ ወ
ንድሞች ፡ ጉባኤ ፡ የተባለች ፡ በብዙ ፡ ስፍራ ፡ ወንጌል
ን ፡ ላሕዛብ ፡ ሰበኩ ። ይህች ፡ ጉባኤም ፡ የክርስቶስ ፡ ፍቅ
ር ፡ ምሳሌ ፡ ሆነች ። የክርስቶስ ፡ ፍቅር ፡ በብዙ ፡ ሰዎች ፡
ልብ ፡ በበረደ ፡ ጊዜ ፡ እርሳቸው ፡ አገራቸውን ፡ ትተው ፡ ወ
ደ ፡ ግሬንላንድ ፡ በምድር ፡ በሰሜን ፡ ዳርቻ ፡ ወደምትኖር ፡
ሔዱ ፡ ክርስቶስንም ፡ ለአያን ፡ አሕዛብ ፡ አስታወቁት ። ደ
ግሞም ፡ በምዕራብ ፡ ኢንዲያ ፡ ደሴቶች ፡ በነበሩ ፡ በተናቁ ፡

ባሮች ፡ መኻከል ፡ አስተማሩ ፡ በጅግ ፡ መከራም ፡ የብዙ ፡ ባሮችንም ፡ ልብ ፡ በውነት ፡ ለክርስቶስ ፡ አስገዙ ፡፡

ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ ሁሉ ፡ ጥቂት ፡ ሆነ ፡ በዚህ ፡ ዘመንም ፡ ከ፲፯፻፺፭፡ ወዲህ ፡ ወደ ፡ ተሰራ ፡ አይደርስም ፡፡ በዚያችም ፡ አመት ፡ በ፲፯፻፺፭፡ አንዲት ፡ ታላቅ ፡ ጉባኤ ፡ ተሰበሰበች ፡ በሎንደን ፡ በንግልጣር ፡ ከተማ ፡፡ እርሳቸውም ፡ እውነተኞች ፡ ክርስቲያኖች ፡ ከቀሳውስትና ፡ ከሕዝብ ፡ ነበሩ ፡ አብረው ፡ ይህነን ፡ ፈቃዳቸውን ፡ ያስታወቁ ፡ በኃይላቸው ፡ ሁሉ ፡ ይጋደሉ ፡ ዘንድ ፡ የክርስቶስን ፡ መንግሥት ፡ በምድር ፡ ሁሉ ፡ ለመዘረጋት ፡፡ ስለዚህም ፡ ይህችን ፡ ሥርዓት ፡ አደረጉ ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ በመኻከላቸው ፡ በፍቅር ፡ በሳምንት ፡ በወርም ፡ ባመትም ፡ ሁሉ ፡ ኢያንዳንዱ ፡ እንደ ፡ ችሎቱ ፡ ከገንዘቡ ፡ ብርን ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፡ ከሌሎችም ፡ ከክርስቶስ ፡ ወዳጆች ፡ ይለቅም ፡ ዘንድ ፡፡ ከጉባኤያቸውም ፡ ይህና ፡ ሰዎችን ፡ መረጹ ፡ ይህነን ፡ መስጠታቸውን ፡ የሚለቅሙ ፡ የሚጠብቁትም ፡ በርሱም ፡ የወንጌልን ፡ መልክተኞች ፡ አሳድገው ፡ አስተምረውም ፡ የሚሰዱበት ፡ የክርስቶስን ፡ ዕውቀት ፡ ወደ ፡ ማያውቁት ፡ አሕዛብ ፡ ይወስዱት ፡ ዘንድ ፡፡ ይችም ፡ ጉባኤ ፡ የሎንደን ፡ ሚስዮን ፡ ጉባኤ ፡ ተባለች ፡ የወንጌልን ፡ መልክተኞች ፡ ወደ ፡ አሕዛብ ፡ የምትሰድ ፡፡ ሚስዮን ፡ ማለት ፡ መስደድ ፡ ነውና ፡፡ እርሳቸውም ፡ በዚያ ፡ አመት ፡ ታላቅ ፡ መርከብ ፡ ይዘው ፡ ፴፡ መለክተኞችን ፡ ሰደዱ ፡ ኦታሀይቲ ፡ ወደ ፡ ሚልዋት ፡ ወደ ፡ ሩቅ ፡ ደሴት ፡፡ ከዚያም ፡ ጥቂት ፡ ወራት ፡ በኋላ ፡ ፲፬፡ መለክተኞችን ፡ ጨመሩላቸው ፡፡ ከርሳቸውም ፡ ተከፍለው ፡ ሞቱ ፡ ስለ ፡ ወንጌል ፡፡ ተከፍለውም ፡ ተበተኑ ፡፡ ተከፍለውም ፡ ደከሙ ፡ ወደ ፡ እንግልጣርም ፡ ተመለሱ ፡፡ ጥቂቶችም ፡ ኖሩ ፡ ተጋደሉም ፡ አስተማሩም ፡ በጅግ ፡ መከራ ፡ በጅግ ፡ ጭንቀትም ፡ የኦታሀይቲ ፡ ንጉሥ ፡ ጾማሬ ፡ ክርስቲያን ፡ እስኪሆን ፡ ድረስ ፡፡ ፳፭፡ አመትም ፡ በኦታሀይቲ ፡ ከተቀመጡ ፡ በኋላ ፡ ሃይማኖታቸው ፡ አሸነፈች ፡ ኦታሀይቲም ፡ ከብዙ ፡ ሌሎች ፡ ደሴቶች ፡ ጋራ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ ተቀበሉ ፡ ጣዖታታቸውንም ፡ ወደ ፡ እሳት ፡

ጨመሯ : መቅደሳቸውንም : አፈረሱ : ተጠመቁም : ክርስ
ቲያንም : ሆኑ ::

ባመትም : ፲፯፱ ሌላ : ታላቅ : ጉባኤ : በሎንደን : ተሰበ
ሰበች : እንደ : ሎንደን : ጉባኤ : እርስዋም : የእንግልጣ
ር : ቤተ : ክርስቲያን : የሚስዮንዋ : ጉባኤ :: እሊህ :
ጉባእዮችም : የሚስዮን : ወይስ : የመስደድ : ጉባእዮች :
ተባሉ : መምህራንን : ስለ : ሰደዱ : ወደ : አሕዛብ : የክር
ስቲያንን : ሃይማኖት : ያስተምሯ : ዘንድ :: የንግልጣር : ቤ
ተ : ክርስቲያን : ሚስዮን : ጉባኤ : መለክተኞቻቸውን : ሰ
ደዱ : ወደ : ዓለም : ሁሉ :: ከሌላ : ይልቅ : ወደ : አፍሪ
ቃ :: ደግሞም : ወደ : ህንድ :: ወደ : ህንድ : ደሴቶች
ም : ወደ : አሜሪካም :: ወደ : አውስትራልያም :: ወ
ደ : ቱርክ : መንግሥትም : ወደ : ምሥርም : ወደ : ሃ
በሻም : ሰደዱ :: የዚች : ጉባኤም : ሚስዮን : ወደ : አፍ
ሪቃ : እንዴህ : ነው :: ባፍሪቃ : ምዕራብ : የሻንክላ : ወገ
ን : ትኖራለች : ባለማወቅ : በመንፈሳዊት : ጨለማም : ከ
ሌላ : ሰው : ወገን : ይልቅ :: ስለዚህም : ብዙ : ሰዎች : አ
ሉ : የሚሉ :: ሻንክሎች : ሰዎች : አይደሉም : የንስሳ : ወ
ገን : እንጂ :: ይህ : ማለት : ግን : ታላቅ : ኃጢአት : ነው ::
በርሳቸው : ላይም : የካም : መርገም : በጣም : ተፈጸመ :
ለባርነት : የተረገመበት :: አሁን : ፸፱ አመት : ነውና : ባ
መት : ሁሉ : ከለዚያ : ብዙ : ሰዎች : እንደ : ተሼጡ : ለብ
ርቱ : ባርነት :: የፈረንጆች : መርከቦች : ሁለግዜ : መጥተ
ው : በጥቂት : ዋጋ : እጅግ : ሻንክሎችን : ገዙ : ወደ : አሜሪ
ካም : ወሰድዋቸው : ከዚያም : ለብርቱ : ስራ : ተሼጡ :
ሌላ : ሰዎች : ላልወደዱት :: ብዙ : ደህና : ክርስቲያኖች :
ነበሩ : እጅግ : ጊዜ : ደህነን : ነገር : የጻዩፉ : እንዴህ : ብለ
ው :: ሰው : ሁሉ : የሴም : የካምም : የያፌትም : ልጆች :
ካንድ : ሰው : ከአደም : መጥተው : ወንድሞች : ናቸው :
ሁላቸውም : እንደ : እግዚአብሔር : መልክ : ተፈጠሩ ::
ሁላቸውም : በአደም : መበደል : ኃጢአተኞች : ሆኑ :: ክ
ርስቶስ : ግን : ስለ : ሁላቸው : ሰማይን : ትቶ : መከራ : ተ
ቀበለ : ሞትም : ተነሣም : ወደ : ሰማይም : ወጣ :: የእግ

ዚአብሔር ፡ ልጅም ፡ የሰው ፡ ልጅ ፡ ሆነ ፡ የሰው ፡ ልጆች ፡ ሁሉ ፡ በርሱ ፡ ይድኑ ፡ ዘንድ ፡፡ ስለዚህም ፡ ለክርስቲያን ፡ አደገባም ፡ ወንድሙን ፡ እንደ ፡ ሚሸመት ፡ ነገር ፡ ይቈጥር ፡ ዘንድ ፡ ባርያውንም ፡ ያደርገው ፡ ዘንድ ፡ ወንድሙ ፡ ነውና ፡ የርሱም ፡ እኩል ፡ በእግዚአብሔር ፡ ፊት ፡፡

እንደዩህ ፡ ያለ ፡ መናገራቸው ፡ በጥቂት ፡ በጥቂት ፡ ወደ ፡ ብዙ ፡ ሰዎች ፡ ልብ ፡ ገባ ፡ የባሮችም ፡ ገብያ ፡ ለማጥፋት ፡ ተማካከሩ ፡፡ ብዙ ፡ ባሮችን ፡ ፈቱ ፡ ሴራ ፡ ሌዎናም ፡ ወደ ፡ ሚሉት ፡ ምድር ፡ ባፍሪቃ ፡ ምዕራብ ፡ ወሰድዋቸው ፡ ከዚያ ፡ ከተሞችንና ፡ መንደሮችን ፡ ለርሳቸው ፡ መኖርያቸው ፡ ሁነው ፡ ይሠሩ ፡ ዘንድ ፡፡ የንግልጣርም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሚስዮን ፡ ጉባኤ ፡ መለክተኞቻቸውን ፡ ሰደደላቸው ፡ በወንጌል ፡ ያስተምርዋቸው ፡ ዘንድ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ስራቸውን ፡ በታላቅ ፡ በረከቱ ፡ ባረከው ፡፡ እልያም ፡ ሻንክሎች ፡ ወደ ፡ እርነት ፡ ወጥተው ፡ ከጨለማ ፡ ወደ ፡ ብርሃን ፡ ደረሱ ፡፡ ከርሳቸውም ፡ ብዙ ፡ ደህና ፡ ክርስቲያን ፡ ሆኑ ፡፡ ሁላቸውም ፡ አሁን ፡ በጎ ፡ ስራ ፡ ይለምደሉ ፡ ብልሃትንም ፡ ይማራሉ ፡፡ በንግልጣር ፡ መንግሥትም ፡ ሁሉ ፡ የክርስቲያን ፡ ፍቅር ፡ አሁን ፡ በባርነት ፡ ሁሉ ፡ አሸነፈ ፡፡ ባመት ፡ ፲፰፴፬ ፡ አሁን ፡ ፯ ፡ አመት ፡ የሚሆን ፡ በእንግሊዝ ፡ መንግሥት ፡ ሁሉ ፡ የነበሩ ፡ ባሮች ፡ ተፈቱ ፡ የክርስቲያንን ፡ እርነት ፡ ያውቁ ፡ ይቀበሉም ፡ ዘንድ ፡፡ የቀደሙም ፡ ጌቶቻቸው ፡ እንዳይጐዱበት ፡ የመንግሥት ፡ ጉባኤ ፡ በንጉሥ ፡ ፈቃድ ፡ ፳ ፡ ሚልዮን ፡ ቀርሽ ፡ ለባሮች ፡ ጌቶች ፡ ሁሉ ፡ ሰጡ ፡፡ አንድ ፡ ሚልዮንም ፡ ፲፻ ፲፻ ፡ ወይስ ፡ ፻ ፻፻ ፡ ነው ፡፡

የንግልጣርም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሚስዮን ፡ ጉባኤ ፡ አንድ ፡ ታላቅ ፡ ሚስዮን ፡ ወደ ፡ ህንድ ፡ ነው ፡፡ ከዚያም ፡ እግዚአብሔር ፡ የፍቅር ፡ ስራቸውን ፡ እጅግ ፡ ባረከላቸው ፡፡ ብዙ ፡ አረማውያን ፡ ጣዖታታቸውን ፡ ትተው ፡ ሃይማኖትን ፡ ተቀበሉ ፡ ብዙ ፡ ሽህም ፡ ከህንድ ፡ አሽከሮች ፡ በወንጌል ፡ ማስተማርዮች ፡ ይማራሉ ፡፡

እንደሁም ፡ ኔውሴላንድ ፡ በተባላች ፡ ደሴት ፡ ሆነ ፡፡ ከጥቂት ፡ አመት ፡ አስቀድሞ ፡ የኔውሴላንድ ፡ ሰዎች ፡ ሰዎ

ን ፡ ባዮች ፡ ነበሩ ፡ አሁን ፡ ግን ፡ ባልንጀሪቸውን ፡ እንደ ፡ ነፍሳቸው ፡ ይወዱ ፡ ዘንድ ፡ ከወንጌል ፡ ተማሩ ፡ በጉባኤያችን ፡ መልክተኞች ፡ በስብከታቸው ፡፡

የዚች ፡ ጉባኤም ፡ ከሌሎች ፡ ጉባኤዎች ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ታላቅ ፡ ተግባር ፡ ይህ ፡ ነው ፡፡ እግዚአብሔር ፡ ቢወድ ፡ በምሥራቅ ፡ የተበተኑትን ፡ በሰውም ፡ ትምርት ፡ የተጨለሙትን ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ እርሳቸውም ፡ የሩም ፡ የሶርያም ፡ የአርመንም ፡ የግብጽም ፡ የሃበሻም ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ በወንጌል ፡ ታበሪቸው ፡ ዘንድ ፡፡ ስለዚህም ፡ የወንጌል ፡ መልክተኞች ፡ በምሥራቅ ፡ ሁሉ ፡ ተልከው ፡ ዞሩ ፡ የእግዚአብሔርንም ፡ ቃል ፡ በትነው ፡ ሰጡ ፡ በሁላቸው ፡ መኻከል ፡፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ይቀበላሉ ፡ካንዲት ፡ ታላቅ ፡ ጉባኤ ፡ የእንግሊዝና ፡ የንግደ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጉባኤ ፡ በሎንደን ፡ የሚልዋት ፡ በሎንደን ፡ የተሰበሰበች ፡፡ ይህች ፡ ጉባኤም ፡ ባመት ፡ ፲፰፻፬ ተነሣች ፡ በፊትም ፡ ታናሽ ፡ ነበረች ፡፡ በእግዚአብሔር ፡ በረከት ፡ ግን ፡ አድጋ ፡ በምድር ፡ ሁሉ ፡ ተዘረጋች ፡፡ በዚችም ፡ ጉባኤ ፡ እውነተኞች ፡ ክርስቲያናት ፡ ከመለያየት ፡ ሁሉ ፡ ካብያተ ፡ ክርስቲያናትም ፡ ሁሉ ፡ መኻከል ፡ ያንድ ፡ ልብ ፡ ሆኑ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ በምድር ፡ ቋንቋ ፡ ሁሉ ፡ ለሰው ፡ ሁሉ ፡ ያደርሱ ፡ ዘንድ ፡፡ ይህችም ፡ ጉባኤ ፡ ከተነሣች ፡ በኋላ ፡ ብዙ ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጉባኤዎች ፡ ተነሡ ፡ ታላቆችና ፡ ታናሾች ፡ በክርስቲያን ፡ አገር ፡ ሁሉ ፡፡ ሁላቸውም ፡ ያንድ ፡ ልብ ፡ ናቸው ፡ ለሁላቸውም ፡ ዕረፍት ፡ የላቸውም ፡ ከቶ ፡ እግዚአብሔር ፡ የፈጠረው ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ መጽሐፍ ፡ እስኪያገኝ ፡ ድረስ ፡፡ በለዚህ ፡ ጉባኤዎችም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ አሁን ፡ በ፪፻ ቋንቋዎች ፡ ተተረጐመ ፡፡ የሚስዮንም ፡ ጉባኤዎች ፡ እርሳቸው ፡ ደግመው ፡ የበዙ ፡ በንግልጣር ፡ በንምሳም ፡ በፍራንስም ፡ በአሜሪካም ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስን ፡ ከመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ ጉባኤዎች ፡ ይቀበሉታል ፡ በመልክተኞቻቸውም ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ ሁሉ ፡ ይሰዱታል ፡፡

በምሥራቅም ፡ የተበተኑ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ በሃይማኖታቸው ፡ ደከሙ ፡፡ ሁላቸውም ፡ በስላሞችና ፡ ባረማ

ውያን ፡ መኻከል ፡ ኑረው ፡ አይችሉም ፡ ብርሃንንና ፡ ኃይል
ን ፡ ያገኙ ፡ ዘንድ ፡ ወደ ፡ እውነተኛ ፡ አንድነትም ፡ ይደርሱ ፡
ዘንድ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ እንጂ ፡፡ እርሱ ፡ የሰው ፡ መ
ድኃኒት ፡ ነውና ፡ ሌላ ፡ የለም ፡፡ ስለዚህ ፡ የሚስዮን ፡ ጉባኤ
ዮች ፡ ወደለዚያ ፡ አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ መልክተኞቻቸ
ውን ፡ ሰደዱ ፡ ወንጌልን ፡ ይሰጥዋቸው ፡ ዘንድ ፡፡ ክርሳቸ
ውም ፡ አያሌ ፡ ተቀበልዋቸው ፡ አያሌ ፡ ግን ፡ ባለማወቃቸ
ው ፡ አልተቀበልዋቸውም ፡ ለደህንነታቸው ፡ የሚጠቅመው
ን ፡ ነገር ፡ አላወቁምና ፡፡

እንደሁም ፡ የእንግልጣር ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሚስዮን ፡
ጉባኤ ፡ መልክተኞቻቸውን ፡ ወደ ፡ ምሥራቅ ፡ ሁሉ ፡ በሰደ
ዱ ፡ ጊዜ ፡ ለሃበሻ ፡ ደግሞ ፡ አሰቡ ፡ የወንጌልን ፡ ብርሃን ፡
በመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡ በመልክተኞቻቸው ፡ እጅ ፡ የሰዱላቸ
ው ፡ ዘንድ ፡፡

ፍቅራቸው ፡ ለሃበሻ ፡ እጅግ ፡ ታላቅ ፡ ነው ፡፡ እርሳቸው ፡
ከውነተኞች ፡ ክርስቲያናት ፡ ሁሉ ፡ ጋራ ፡ እግዚአብሔርን ፡
ያመሰግናሉ ፡ የሃበሻውን ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በስላሞችና ፡
ባረማውያን ፡ መኻከል ፡ እስካሁን ፡ ድረስ ፡ ከስላምና ፡ ካ
ረማውያን ፡ ኃይል ፡ በታች ፡ እንደልወደቀች ፡ እንደ ፡ ቀሩ ፡
አብያተ ፡ ክርስቲያናት ፡ በምሥራቅ ፡ እንደሉ ፡ ሁሉ ፡ ጠብ
ቋታልና ፡፡ ነገር ፡ ግን ፡ ይህ ፡ አይበቃም ፡፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን
ና ፡ ለመንግሥት ፡ ደህንነት ፡ ይህ ፡ ይፈለጋል ፡ የሃበሻ ፡ ሰ
ው ፡ ሁሉ ፡ የእግዚአብሔርን ፡ ቃል ፡ እንዲያውቅ ፡ መ
ልካምም ፡ እንዲያስታውለው ፡ በልቡም ፡ እንዲቀ
በለው ፡ ፍሬውንም ፡ በበጎ ፡ ስራ ፡ የእግዚአብሔርን
ም ፡ ትእዛዝ ፡ በመከተል ፡ እንዲገልጽ ፡፡ እንደህ ፡ ይላ
ልና ፡ ሰሎሞን ፡፡ ጽድቅ ፡ ሕዝብን ፡ ከፍ ፡ ያደርጋል ፡፡ ኃጢ
አት ፡ ግን ፡ የሰው ፡ ጥፋት ፡ ነው ፡፡ ስለዚህም ፡ የወንጌል ፡
መልክተኞች ፡ ከጉባኤያቸው ፡ ተልከው ፡ መጽሐፍ ፡ ቅዱስ
ንም ፡ ይዘው ፡ መጡ ፡ ለሚፈልገውም ፡ ሰው ፡ ሁሉ ፡ ይሰጡ
ታል ፡፡ ከመጀመርያ ፡ መምጣታቸው ፡ ጀምረው ፡ እስካሁ
ን ፡ ድረስ ፡ ለሃበሻ ፡ ሰዎች ፡ የሰጡት ፡ የመጽሐፍ ፡ ቅዱስ ፡
ቍጥር ፡ ፬፲፱፡፡ ያህላል ፡ አንዳንድ ፡ በጥቂት ፡ ዋጋ ፡ የቀረም ፡

ሁሉ ፡ እንደ ያው ፡ ሰጥተው ፡ ክርስቶስ ፡ እንደ ል ። እንደ ያው ፡ ተቀበላችሁ ፡ እንደ ያውም ፡ ስጡ ። ጳውሎስም ፡ እ ንደ ል ። እኛ ፡ ገንዘባችሁን ፡ አንሻም ፡ ነፍሳችሁን ፡ እንጅ ፡ ለክርስቶስ ።

ጉደያቸውም ፡ በዚህ ፡ አገር ፡ ሌላ ፡ የለም ፡ የጳውሎስ ፡ ጉደይ ፡ እንጅ ፡ ወደ ፡ ሮም ፡ ለመምጣት ፡ ስለ ፡ ተናፈቀ ፡ እ ንደ ህ ፡ ሲል ። እላንተን ፡ ማየት ፡ እወደለሁ ፡ እሰጣችሁ ፡ ዘንድ ፡ የመንፈስ ፡ ቅደ ስን ፡ ጸጋ ፡ ትጸናችሁ ፡ ዘንድ ። ሮ ሜ ፡ ፩፡ ፲፩። የወንጌልም ፡ መለክተኞች ፡ ስለዚህ ፡ ያለም ን ፡ ደስታ ፡ ትተው ፡ ከወደድዋቸውም ፡ ሰዎች ፡ ተለይተው ፡ ወደ ፡ ዚህ ፡ አገር ፡ መጡ ። መከራንም ፡ ድካምንም ፡ በሰ ው ፡ አለማወቅም ፡ ጸላትነትን ፡ ተቀበሉ ፡ ስለ ፡ ክርስቶስ ፡ እርሱን ፡ ብቻውን ፡ ስለ ፡ ተከተሉ ፡ የርሱንም ፡ ቃል ፡ ብቻ ፡ ስለ ፡ ሰሙ ። ሃይማኖታቸውም ፡ አዲስ ፡ አይደለች ም ። መርማሪውም ፡ ከእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ጋራ ፡ እንድ ትገጠም ፡ ያገኛል ። ሃይማኖታቸው ፡ የሐዋርያት ፡ የኒ ቅያም ፡ ሃይማኖት ፡ ነው ። የጵሮተስታንቶችም ፡ ሃይ ማኖት ፡ በ፷፰፡ ቃላት ፡ እንደ ፡ አስታወቁት ፡ በአውግ ስቡርግ ፡ በላይ ፡ እንደሳየነ ። የእንግልጣርም ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሃይማኖት ፡ በ፴፱፡ ቃላት ፡ በቅድም ፡ እን ደ ፡ ገለጽነው ። ሁሉ ፡ አንድ ፡ ነውና ። ሌላ ፡ መሠረት ም ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ተምርት ፡ ይመሠርት ፡ ዘን ድ ፡ ማንም ፡ አይችልም ፡ ከተመሠረተው ፡ በቀር ። እ ርሱም ፡ የሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው ። ጳውሎስ ፡ እንደ ል ፡ ፩፡ ቆሮንቶስ ፡ ፫፡ ፲፩።

ለርሱም ፡ ለጌታችንና ፡ ለመድኃኒታችን ፡ ተሰቀሎና ፡ ሙ ቶ ፡ ከፍ ፡ ላለ ፡ በፍጥረት ፡ ሁሉ ፡ ላይ ፡ ንስሓውንና ፡ የኃ ጢአትን ፡ ስርየት ፡ ለወገኑ ፡ ሁሉ ፡ ይሰጥ ፡ ዘንድ ፡ በሃይማ ኖት ፡ ክብርና ፡ ምስጋና ፡ ይሁንለት ፡ ከአብና ፡ ከመንፈስ ፡ ቅደ ስ ፡ ጋራ ፡ ለዘላለም ። አሜን ።

PJ9272 .I78
Regni Dei in terris historia Amharice
Princeton Theological Seminary–Speer Library
1 1012 00079 7441